# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ ዓ.ም (2000)

ኢትዮጵያ ኢዮ፯ቹን ወደ እግዚአብሔር ማ[illegible]

ዕጣ ሆይ አንተ ዘመናትን ታቀዳጀሀ

ዋጋ
ETB 100
Euro 20

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## መታሰቢያነቱ

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ለኢትዮጵያውያን ነፃነት ለእውነተኛ ሃይማኖት ሰማዕትነት በፋሽስት ኢጣልያ ለተቀበሉት ለሰማእተ ጽድቅ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳስ እና ላለፉት ፷፤ ዓ.ም. ዓመታት ለቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ልዕልና መከራ የተቀበሉ በሰማእትነት ላለፉትና በሐዋርያዊ አገልግሎት መንፈሳዊ ፍሬ ላፈሩ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና ምዕመናት የ፷፤ ዓ.ም. በዐል መታሰቢያ እንዲሆን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቅዷል

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Right Resaved





## የመጽሐፉ አዘጋጆች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
አስተዳደርና መንግሥት በየዘመናቱ
በብፁዕ አቡነ ገሪማ (ዶ/ር)
የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊ
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት
ቢሮ ዋና ጸሐፊ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽንና
የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

የመጽሐፉን መግቢያ
1. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዐተ አምልኮ
2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት
3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅርሶች
በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት
የቅ/ፓትርያርክ ረዳት ሊቀ ጳጳስ

1. የክርስትና እምነትና ሥርዓተ አምልኮ በኢትዮጵያ
2. የሰማዕትነት ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
በሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ

የአጽዋማት ሥርዓትና በዐላት አከባበር
በሊቀ ሥዩማን ራድ አስረስ

በትምህርትና በማኅበራዊ አገልግሎት የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያበረከተችው አስተዋጽኦ
በዶክተር አግደው ረዴ

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር
መምህር ያሬድ ፈንታ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ጸዋትወ ዜማ
በንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ

የቅኔ ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን
በመጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ



www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፉ አዘጋጆች

የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ታሪክ በኢትዮጵያ
በዶክተር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል

የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ታሪክ
በሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት
በመልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን

## ለመጀመሪያ ጊዜ በ ፳፤ (2000) ዓ.ም ታተመ


የመጽሐፍ ሽፋን ዲዛይን
ገጽ ትንብርና
ፎቶ ግራፍ ኤዲቲንግ
አቶ ያዕቆብ ታደሰ
ወ/ት ፍሬ ሕይወት ግርማ

ህትመትና ዲዛይን ክትትል
መ/ር ዘለዓለም ነጋሽ
መ/ር ሱራፌል ወንድሙ

ኮምፒውተር ጽሑፍ
ወ/ሮ ዘለቃሽ ማሞ

ይህ ታላቅ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት ትብብር ያደረጉ
አባ ክንፈ ሚካኤል ኪዳነ እና አቶ ወዳጀ መሰለ በቅድስት ቤተክርስቲያን ስም ምስጋና እናቀርባለን፡፡






# ማውጫ


የብሁዕ ወቅዱስ መልእክት ገጽ

መግቢያ 1

ምዕራፍ 1 የክርስትና እምነትና ሥርዓተ አምልኮ በኢትዮጵያ ---------- 15

ክፍል 1 ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ---------- 15

ክፍል 2 ከ1ኛው እስከ 4ኛው ክፍለ ዘመን ---------- 15

ክፍል 3 ከ5ኛው እስከ 9ኛው ክፍለ ዘመን ---------- 17

ክፍል 4 ከ10 እስከ 15ኛው መቶ ዓመት ---------- 18

ክፍል 5 ከ16ኛው እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ---------- 22

ምዕራፍ 2 የአጽዋማት ሥርዓትና በዐላት አከባበር ---------- 31

ክፍል 1 አጽዋማት ---------- 31

ክፍል 2 በዐላት ---------- 38

ምዕራፍ 3 በትምህርትና በማኅበራዊ አገልግሎት
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ያበረከተችው አስተዋጽኦ፡ ---------- 54

ክፍል 1 የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ወቅታዊ ግምገማ ---------- 55

ክፍል 2 በአዲስ አበባ በተመረጡ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት
ማኅበራዊና ተቋማዊ ልማት ላይ የተደረገ ጥናት ---------- 67

ምዕራፍ 4 የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ---------- 83

ክፍል 1 የሁለት ሺሕ ዓመተ ምሕረት ምሥጢር ---------- 84

ክፍል 2 ሐሳበ ዘመን ---------- 86

ክፍል 3 ዘመነ አበው ---------- 92

ክፍል 4 ምሥጢረ ሐሳባተ ሠለስቱ ---------- 93




www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

ገጽ


ምዕራፍ 5 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ጸዋትወ ዜማ------ 95

ክፍል 1 የዜማ አጀማመር---------- 95

ክፍል 2 የቅዱስ ያሬድ ታሪክና አነሣሥ---------- 97

ክፍል 3 የቅዱስ ያሬድ ዜማ ይዘት---------- 104

ክፍል 4 የቅዱስ ያሬድ ዜማ ትምህርት ቤት---------- 107

ክፍል 5 የቅዱስ ያሬድ መጻሕፍተ ዜማ አከፋፈል---------- 109

ክፍል 6 የዜማ ምልክቶች አመጣጥ---------- 112

ክፍል 7 የቅዱስ ያሬድ ዜማ ---------- 128

ምዕራፍ 6 የቅኔ ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን---------- 129

ክፍል 1 የቅኔ ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ---------- 129

ክፍል 2 የቅኔ ትርጉምና ገጸ ባሕርያት---------- 130

ክፍል 3 የቅኔ ትምህርት አጀማመርና ሂደት---------- 131

ክፍል 4 የቅኔ ትምህርት መሥራቾችና የመጀመሪያዎች የቅኔ ጉባኤ ቤቶች---------- 135

ክፍል 5 22ቱ አርእስተ ቅኔ---------- 138

ክፍል 6 የቅኔ ትምህርት ጠቃሚነት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት---------- 142

ክፍል 7 የጠቅላላው ቅኔያት ይትበሀልና ዓይነት ከጸዋትወ ዜማ ጋርም ያላቸው ቁርኝት---------- 146

ክፍል 8 የቅኔ ትምህርት ቤት ምንጩ እንዳይደርቅ ወደፊት ምን መደረግ አለበት-------- 150

ምዕራፍ 7 የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ታሪክ በኢትዮጵያ ---------- 156

ክፍል 1 በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የአይሁድ ሥርዓት ተጽእኖ---------- 156

ክፍል 2 መጽሐፍ ቅዱስ በግእዝ ቋንቋ የተተረጐመው መቼ ነበር---------- 158

ክፍል 3 መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ "ግእዝ" የተረጉሙ ሰዎች---------- 160

ክፍል 4 የሰብዓ ሊቃናት /Septuagint/ ትርጉም ምንድን ነው? ---------- 166






# ማውጫ

ገጽ


ክፍል 5 መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ ለመተርጉም ጥቅም ላይ የዋሉ ትርጉሞች---------- 168

ክፍል 6 የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መሻሻል---------- 170

ክፍል 7 የኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት ሕትመት---------- 172

ክፍል 8 የኢትዮጵያ የብራና ቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙባቸው ቦታዎች----- 173

ምዕራፍ 8 የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን---------- 174

ክፍል 1 የትርጓሜ አስፈላጊነት---------- 174

ክፍል 2 የአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት---------- 176

ክፍል 3 የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ---------- 180

ክፍል 4 የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ ምንጮች---------- 182

ክፍል 5 የአንድምታ ትርጓሜ ዕድገትና መተላለፍ ትውፊታዊ ታሪክ---------- 186

ክፍል 6 የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ በአማርኛ---------- 187

ክፍል 7 የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ጥንተ ዘመን---------- 189

ክፍል 8 የአንድምታ ትርጓሜ ይዘቶች---------- 192

ክፍል 9 የአንድምታ ትርጓሜ ት/ቤቶች---------- 194

ክፍል 10 የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ምንጮች---------- 197

ክፍል 11 የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ስልት---------- 202

ክፍል 12 የአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ---------- 207

ምዕራፍ 9 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ታሪክ--------- 210

ክፍል 1 ቅድስና---------- 210




www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

ገጽ


ክፍል 2 ኢትዮጵያውያን ቅዱሳንና ቅዱሳት---211

ክፍል 3 ብሔረ ሙላዳቸው ከውጪ ሆኖ ቅድስናን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያገኙ ቅዱሳን---224

ምዕራፍ 10 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት---228

ክፍል 1 የብሕትውና አጀማመር---229

ክፍል 2 ወጣኒ---234

ክፍል 3 የምንኩስና ሥርዐት በኢትዮጵያ---237

ክፍል 4 የመነኮሳት ልብስ ከዓለማውያን ለምን ተለየ---247

ክፍል 5 የቅዱሳት ሴቶች ታሪክ---252

ክፍል 6 ገዳማቱ ለኢትዮጵያ ያበረከቱት አስተዋጽኦ---255

ምዕራፍ 11 የሰማዕትነት ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን---257

ክፍል 1 ሰማዕታተ ናግራን---265

ክፍል 2 ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በዘመነ ዮዲት---268

ክፍል 3 ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በዘመነ ግራኝ መሐመድ---269

ክፍል 4 ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በዘመነ ሱስንዮስ---275

ክፍል 5 የሰማዕታት ዘመን በደርቡሽ---281

ክፍል 6 የሰማዕትነት ዘመን በኢጣሊያ ፋሺስት---284

ክፍል 7 የሰማዕትነት ዘመን በዘመነ ደርግ---287

ክፍል 8 ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በሃያኛው መቶ ዓመት---291




# ማውጫ

ገጽ


ምዕራፍ 12 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት---293

ክፍል 1 የውጭ ግንኙነት ቅድመ ክርስትና---293

ክፍል 2 የውጭ ግንኙነት በዘመነ ክርስትና---294

ክፍል 3 የውጭ ግንኙነት በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን---298

ክፍል 4 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኦርዬንታል ኦርቶዶክስ እኅት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላት ግንኙነት---301

ክፍል 5 ከኦርዬንታልና በኢስተርን ኦርቶዶክስ አብያ ክርስቲያናት መካከል የተደረገ ግንኙነት---302

ክፍል 6 በመሪዎች ደረጃ በሚደረግ የጉብኝት ልውውጥ አማካይነት የተካሄደ የውጭ ግንኙነት---303

ክፍል 7 የውጭ ግንኙነት በአምስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ክህነት---306

ክፍል 8 የነፃ ትምህርት እድል---323

ምዕራፍ 13 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መንግሥት በየዘመናቱ---324

ክፍል 1 ከ1ኛው መቶ ዓመት እስከ 16ኛው መቶ ዓመት መነሻ ድረስ---324

ክፍል 2 ከ16ኛው መቶ ዓመት መሻ እስከ 19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ---330

ክፍል 3 ከ19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ እስከ 20ኛው መ ዓመት 1967 ዓ.ም. መነሻ ድረስ---334

ምዕራፍ 14 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶች---354




www.ethiopianorthodox.org

አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ም[illegible]

# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

‹‹ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት፤››
‹ከዚህ ዘመን፤ ከዚህ ዕለትና ሰዓት ያደረሰን አምላክ ይክበር ይመስገን፤›

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ የሁለት ሺህ ዓመተ ምሕረትን ፍጻሜና የሦስት ሺሕ ዓመተ ምሕረት መባቻን በሀገርና በዓለም ደረጃ በማክበር ላይ ናት፡፡ ነቢዩ ዳዊት ‹‹ሰብሕም ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ›› ‹እግዚአብሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑት› ሲል እንደተናገረው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሁለት ሺሕ ዓመተ ምሕረትን የምታከብረው ከዚህ ለአደረሳት አምላክ አዲስ ምስጋናን በማቅረብ ነው ፡፡ በዐሉ የሚከበረው በሀገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ቢሆንም በተለይ በአዲስ አበባ በዐሉ የሚከበረው የውጭ አህጉር ልዩ ልዩ እንግዶች የአብያተ ክርስቲናት መሪዎችና የዓለም አቀፍ ድርጅት ኃላፊዎች በሚገኙበት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ደስታ ይሰማታል ፡፡

አስቀድሞ እንደተገለጠው ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ የምታከብረው የሁለት ሺህ ዓመት መጨረሻንና የሦስት ሺህ ዓመት መባቻን ነው፤ ሌላው የክርስትና ዓለም ይህን በዐል ያከበረው ቀደም ብሎ መሆኑ ይታወሳል ፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው የክርስትና ዓለም በተለየ ጊዜ የምታከብረው የራስዋ የሆነ የዘመን አቁጣጠር መንገድ ስለአላት ነው ፡፡ ይህም የዘመን አቁጣጠር መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ነው ፡፡ በተለይ መጽሐፈ ሄኖክና መጽሐፈ ኩፋሌ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አቁጣጠር ዋና መነሻዎች ናቸው ፡፡ ከዚህም ጋር ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ጥንታዊው የዘመን አቁጣጠር ከአሁኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አቁጣጠር ጋር ተመሳሳይነት አለው ፡፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዘመን፣ የዓመት፣ የወርና የዕለት አቁጣጠር ስልት አያንዳንዱ ወር 30 ቀናት ያሉት ሲሆን ከዓመቱ 12 ወራት በተጨማሪ እንደ 13ኛ ወር የሚቆጠር ጳጉሜን አለ ፡፡ ጳጉሜን አምስትና ስድስት ቀናት ያሉት ክፍለ ጊዜ ነው ፡፡

ቤተ ክርስቲያን የሁለት ሺህ ዓመተ ምሕረት በዐልን በምታከብርበት በዚህ አጋጣሚ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መቸና እንዴት እንደገባ? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቼ እንደተመሠረተች፣ የክርስትና እምነት ለኢትዮጵያ ያበረከተውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት፣ ቤተ ክርስቲኒቱ በአሁኑ ጊዜ የደረሰችበትን ደረጃ መዘከር ግድ ይሆናል ፡፡

ሀ/ የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ መችና እንዴት እንደገባ

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ኢትዮጵያ በብሉይ ኪዳን እምነት አምልኮተ እግዚአአብሔር የሚፈጸምባት ሀገር ነበረች ፡፡ የብሉይ ኪዳን እምነት ወደ ሀገሪቱ የገባውም ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺህ ዓመት አካባቢ ንግሥተ ሳባ በኢየሩሳሌም ጉብኝት አድርጋና ከንጉሥ ሰሎሞን ጋርም ኅብረ ከተመሰሰች በኋላ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱ ጅውዶ ክርስቲያን ማለት ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን የተሸጋገረ ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን ትባላለች፡፡

የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በመጀመሪያው መቶ ዓመተ ምሕረት በንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ሐዋርያነት ነው፡፡ ቤሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 እንደተገለጠው ጃንደረባው በኦሪቱ ሥርዓት መሠረት ወደ ኢየሩሳሌም ሔዶ የፋሲካን በዐል አክብሮ ሲመለስ ወንጌላዊው ፊልጶስ አስተምሮና አሳምኖ ተጥምቆ ክርስቲያን ስለአደረገው ጃንደረባው ወደ ሀገሩ ሲመለስ የክርስትናን ዜና ለሀገሩ ሕዝብ በማብሰር መጀመሪያው የክርስትና እምነት ሐዋርያ ሁኗል፡፡ ከዚያም ቅዱስ ማቴዎስ፣ ቅዱስ ናትናኤል፣ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ቅዱስ ቶማስ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመዘለቅ ወንጌልን እንደሰበኩ እንደ እነ ሩፋኖስና ፍራሞጥስ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሓፊዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል ፡፡

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በመጀመሪያው መቶ ዓመተ ምሕረት ቢሆንም ቤተ ክርስቲያኒቱ ተመንበረ ጵጵስና ደረጃ ተደራጅታ ህልውናን የጀመረችው ግን በዐራተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ነው ፡፡ መጀመሪያው የቤተ ክርስቲያኒቱ ጳጳስም በኋላ አባ ሰላማ ከሞቱ ብርሃን የተባለው ቅዱስ ፍሬምናጦስ ሆኖ ጵጵስናን የተሾመውም በእስክንድርያው ቅዱስ ፓትርያርክ አትናትዮስ ነው ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## ለ. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ያበረከተችው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት

መንፈሳዊ አገልግሎትን በሚመለከት ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተመሠረተች በኋላ በፈጸመችው ሐዋርያዊ አገልግሎት በአሪት እምነት አምልኮተ እግዚአብሔርን ይፈጽም የነበረው ሕዝብ የክርስትና እምነትን ተቀብሎ ክርስቲያን ሆኗል ። ክርስቲያን የሆነው ሕዝብ በክርስትና እምነት አምልኮቱን ለመፈጸም የሚችልባቸው አብያተ ክርስቲያናት በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲታነጹ?አገልጋዮች ካህናትን ለማፍራት የሚቻልባቸው ትምህርት ቤቶች በሀገሪቱ እንዲስፋፉ ተደርጓል ።

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸምባቸውና ትምህርተ ክርስትና የሚሰጥባቸው አያሌ መጻሕፍት ተዘጋጅተው ለአገልግሎት ቀርበዋል ። ቤተ ክርስቲያኒቱ በኢትዮጵያውያን ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ቅዱስ ፓትርያርክ ከምትገለገልበት ደረጃ ደርሳለች፣ መንፈሳውያን አባቶች በጽሙናና በተባሕትዎ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት የሚያደርሱባቸው፣ በትምህርት ቤትና በቤተ መዘክርነት የሚያገለግሉ ገዳማት በብዛት ተመሥርተዋል ። መንፈሳዊው አገልግሎትም በአገር አቀፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም እንዲስፋፋ ተደርጎአል ።

ማኅበራዊ አገልግሎቱን በሚመለከትም ቤተ ክርስቲያን በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶችን በመክፈትና የኅብረተሰቡ ልጆች እንዲማሩ በማድረግ ለአያሌ ዘመናት ለሀገሪቱ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ባለቤት ሆና አገልግላለች ። የፍትሕ መጻሕፍትንም በማዘጋጀትና በመተርጐም በሀገሪቱ ዳኝነት ሕጋዊ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጋለች፣ ሕዝቡ ከመሃይምነት እንዲላቀቅ ፊደልና መመሪያ መጽሐፍ በብራና እየጻፈች ኅብረተሰቡን ስታስተምር ኖራለች፣ ሥዕልንና ቅርጻቅርጽን በማዘጋጀት ሥነ ጥበብና ኪነ ጥበብ እንዲስፋፉ አድርጋለች ። የሀገሪቱ ቅርሳቅርስ ቤተ መዘክር በመሆንም ቅርሶች ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ስታደርግ ቆይታለች። ዛሬም የኤች አይ ቪ. ኤድስ በሽታ ከተከሠተበት ጊዜ ጀምሮ ሕዝቡን ከዚህ ቀላፊ በሽታ ለመታደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ መርሐ ግብርን ዘርግታ የሕይወት ማዳን ተልእኮዋን በመፈጸም ላይ ትገኛለች ።

## ሐ/ ቤተ ክርስቲያኒቱ በአሁኑ ጊዜ የደረሰችበት የዕድገት ደረጃ

ቤተ ክርስቲያኒቱ ለበርካታ ዘመናት በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የበላይ አባትነት ስትመራ ቆይታ ነበር ። ከ1921 ዓ.ም. ጀምሮ ግን በራስዋ ጳጳሳት፣ ከዚያም በ1951 ዓ.ም. ጀምሮ በራስዋ ቅዱስ ፓትርያርክ በመመራት ራስዋን በራስዋ የምታስተዳድር ቤተ ክርስቲያን ሆናለች ። ከቆዩት የቤተ ክርስቲያኒቱ ነባር ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ የራስዋን ኮሌጆችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን፣ የካህናት ማሠልጠኛዎችን በማቋቋም ዘመናውያት ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ሕዝበ ክርስቲያኑ ብቁዓን አገልጋዮች ካህናትን መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርትን እንዲያገኝ በማድረግ ላይ ትገኛለች።

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ቤተ ክርስቲያኒቱ ሐምሳ ዐራት አህጉረ ስብከት ሐምሳ ዘጠኝ ሊቃነ ጳጳሳት፣ 500,000 ካህናት፣ 40,000 የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ገዳማት፣ 45 ሚሊዮን ተከታዮች ምእመናን ያሏት ቤተ ክርስቲያን ሆናለች። ቤተ ክርስቲያኒቱን በበላይነት የሚመራ በቅዱስ ፓትርያርክ የሚመራ የራስዋ ቅዱስ ሲኖዶስ አላት።

እኔም በአሁኑ ጊዜ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሆኜ በመመረጤ የቤተ ክርስቲያኒቱ የውጭ ግንኙነት በበለጠ እንዲጠናከር በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን ጥረት በማድረግ ላይ እገኛለሁ።

## የቤተ ክርስቲያኒቱ የወደፊት ራእይ፣

ቤተ ክርስቲያኒቱ እስካሁን ስታካሒደው የቆየችው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ወደፊት ተጠናክሮ በስፋት እንዲቀጥል፣ እስካሁን በሁለት ሺህ ዓመት ካስመዘገበችው የበለጠ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በሦስተኛው ሺህ ማስመዝገብ ከቤተ ክርስቲያኒቱና ከቅዱስ ሲኖዶሱ የሚጠበቅ ይሆናል ።



መንግሥት ለሀገር ግንባታና ለድኅነት ቅነሣ፣ የኤች አይ ቪ. ኤድስን ስርጭት ለመግታት ለሰላም ለፍትሕና ርትዕ መስፈን የቀየሰው ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ቤተ ክርስቲያኒቱም የበኩሏን አስተዋፅኦ ለማድረግ ቃል ትገባለች ።

በክርስቶስ ልደት የተበሰረው ሰላም በዓለም ላይ ሙሉ በሙሉ ገና ተግባራዊ ስላልሆነ በዓለም ላይ ሰላም እንዲሰፍን የሰላም ሐዋርያ በመሆን የምታካሒደውን አገልግሎት ትቀጥላለች ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በራሷ ሊቃውንት አተረጓጐም ስልት መጽሐፍ ቅዱስን አዘጋጅታ በመታተም ላይ ሲሆን ወደፊትም የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስን በማሳተም ለአገልግሎት ለማቅረብ ተዘጋጅታለች።

የሁለት ሺሕ ዓመተ ምሕረት ፍጻሜን ምክንያት በማድረግ የታተመው ይህ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሁለት ሺሕ የታሪክ ገዞ ያደረገችውን ሁሉ ለማዘከርና ለትውልድ ለማስተላለፍ በቂ ምስክር እንደሚሆን እናምናለን።

እግዚአብሔር አምላክ ሦስተኛውን ሺሕ ዓመተ ምሕረት የሥራና የውጤት፣ የበረከትና የሰላም ዘመን እንዲያደርግልን እንጸልያለን።

እግዚአብሔር አምላካችን
ለሀገራችንና ለዓለሙ ሁሉ ሰላሙን ይስጥልን

አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአዲስአበባ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ



www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በጥንታውያን የታሪክ ሠነዶችና በሥነ ፍጥረት ጥናት፣ በዓባይ ሸለቆ ዙሪያና በቀይ ባሕር አካባቢ ከታወቁት ታሪካውያን አህጉርና ሕዝብ ጎን፣ ተገቢ ቦታቸውን ይዘው የሚገኙ ናቸው፡፡

በሥነ ፍጥረት መረጃዎች፣ በመልክዐ ምድር አቀማመጥ ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ ከግብፅ በስተደቡብ ኩታ ገጠም ሆኖ በዘርና በቀለሙ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርስ ቀለምን፣ ትውልድን የሚያመለክት መጠሪያ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ሁለት የጽርዕ ቃላት ተዋጣጥመውና ተያይዘው ጥቁር ወይንም ጠይም ማለት የአንድነት ቃል ተጠቃልሎ በአካባቢው ለሚኖረው ሕዝብ የመጠሪያ ስም በመሆን ያገለግላል፣ ሀገሪቱንም ኢትዮጵያ ያሰኘው የኋሪዎቹ ደምግባት ነው የሚለው ሐሳብም በብዙዎች ዘንድ የተደገፈ ነው፡፡

የብሉይ ኪዳን አበው ነቢያት ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳይገቡ ኢትዮጵያና ኩሽ በማለት ኢትዮጵያን በየትንቢታቸው ያዘከራሉ፣ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በሁለት መቶ ሰማንያ ዐራት ዓመት ሰብአ ሊቃናት ብሉይ ኪዳኑን ከዕብራይስጥ ወደነገረ ዮናኒ ሲተረጉሙ በዕብራይስጡ ኩሽ ይባል የነበረውን ሁሉ ኢትዮጵያ ብለው ተርጉመውታል፣ ብሉይ ኪዳንን መጻፍ የተጀመረውም ከልደተ ክርስቶስ በፊት መሆኑ የሚነገር ሲሆን፣ ኢትዮጵያም ብሉይ ኪዳኑን የተቀበለችው ከልደተ ክርስቶስ በፊት በአንድ ሺህ ዓመት አካባቢ ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ "ኩሽ" ወይንም "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ከዓርባ ጊዜያት በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ንባብ ተመልክቷል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ "ኩሽ" ወይንም "ኢትዮጵያ" የሚለው ክልልም በየጊዜው የመስፋትና የመጥበብ ሁኔታ ያጋጠመው ቢሆንም የምድረ ኢትዮጵያ ማዕከል አክሱም ጽዮን እንደነበረች የሃይማኖት መጻሕፍት ታሪክ ያስረዳሉ፡፡

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2:13 "የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል" ይላል፤ በዕብራይስጡ "ኩሽ" የሚለው ቃል ሦስት ትርጉሞች ይኖሩታል፤

- በአንደኛ ትርጉሙ ከካም ልጆች መካከል አንዱ የሆነውን ኩሽን ያመለክታል፡፡ /ዘፍ.10:6/

- በሁለተኛ ትርጉሙ የዚህ ሰው ልጅ ነገድ የሆነው ሁሉ፣ "ኩሽ" ወይንም "ኩሻውያን" ተብለው እንደሚጠሩ ያሳያል፤ በዚህ ትርጉሙ መልክ ጠይም ለሆነው ሕዝብ እንደመጠሪያ የተሰጠ ስያሜ መሆኑ ይታወቃል፤ ይሁንና መልክ ጠይም የሆነው ሕዝብ ሁሉ የኩሽ ዘር ነው ማለትም አይቻልም፤(አይደለም)

- በሦስተኛ ትርጉሙ መልክ ጠይም የሆነው ሕዝብ የሚኖርበት መጠሪያ ስም መጠሪያ ከግብፅ ደቡብ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ያለው አካባቢ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ እንደሚታየው "ኩሽ" የሚለው ቃል ሁለተኛ ትርጉሙ ዘርዐ ትውልድን የሚያመለክት ሲሆን፤ በሦስተኛው ትርጉም ይህ ዓይነት ዘርዐ ትውልድ የሚኖርበት አካባቢ የመጠሪያ ስም ሆኖ መገኘቱ ነው፤ ይህም ኢትዮጵያ መሆኗን ያረጋግጣል፡፡

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ከልደተ ክርስቶስ በፊት በአንድ ሺህ ዓመት "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ገዐ እግዚአብሔር" ‹ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች› ይላል /መዝ.67:31/



www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያ የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠረ እግዚአብሔር መኖሩን በሕገ ልቡና ዐውቃ፣ አምና፣ ተረድታ፣ በቅዳሴ በውዳሴ አምልኮቷን ስትፈጽም መኖርዋ እሙን ነው፤ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን "ኢትዮጵያ ታብጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" በማለት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት የዘመረው፤ ወደኋላም ወደፊትም የሠራና የሚሠራ ሆኖ የተነገረ ትንቢት ነው፤ ማለት በዘመነ አበው፤ በዘመነ መሳፍንት፣ በዘመነ ነገሥት፣ በዘመነ ካህናት በዘመነ ሥጋዊ እስከ ዓለም ፍጻሜ ለነበሩት፣ ላሉት ለሚኖሩት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የተዘመረ መዝሙረ ዳዊት ነው፡፡

ከልደተ ክርስቶስ በፊት በስምንት መቶ ዓመት አካባቢ የነበረው ግጥም ገጣሚው ግሪኩ ሆሜር በግሪክ ሥነ-ጽሑፉ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመ ነበር፤ ሆሜር ስለ ኢትዮጵያውያንና ስለሚኖሩበት አካባቢ በሥነ-ጽሑፍ ገልጿል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ የትኛውን አካባቢ እንደያዘች አመልክቷል፤

ከሆሜር በኋላም ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከ400-300 ዓመት የነበረው የታወቀው ታሪክ ጸሐፊ ሄሮዶቶስ በሥነ ጽሑፉ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ሀገር ከግብፅ ደቡብ መስስ የሚገኝና ቀይ ባሕርንም ተከትሎ የሚዘልቅ አካባቢ እንደነበርና የእነዚህንም ኢትዮጵያውያን የኑሮ ዘዴ ሲገልፅ "የዕድሜ ባለጸጎች ጀግኖች፣ ደኖች፣ ርኃሩኆች፣ እንግዳ ተቀባዮች" እንደነበሩ ያመለክታል፡፡

ግሪኮች፣ የኢትዮጵያውያን ግዛት ብለው የሚጠሩትን፣ ግብፆችም በዘኩላቸው የደቡብ ኩሽ የሚሉትን፣ በድሮ ዘመን የፖለቲካ አነጋገር፣ ክልል ባለመኖሩና ባለመታወቁ ክልሉን ወይም ወሰኑን በትክክል ማወቁና መለየቱ የሚያስቸግር ይመስላል፡፡

በድሮ ዘመን ሁሉም የየራሱን አካባቢ ይዞታ፣ ስፋትና ርዝመት በግምት እንጂ በመስፈሪያ ለኩቶ የሚያውቅ እንዳልነበረ ከነበረው አሠራርና ዕውቀት መረዳት ይቻላል፣ ቢሆንም ታላቁ የመልክዐ ምድር ምርምር ሊቅ የነበረው አስትራቦ የኢትዮጵያ ድንበሮች በሰሜን ግብፅ፣ በደቡብ የሕንድ ውቅያኖስ መሆኑን ገልጿል፡፡

አስትራቦ ስለ ዓባይ ወንዝም ሲጽፍ ይህ ወንዝም ከኢትዮጵያ ተነሥቶ ወደሰሜን የሚፈስ፣ የሚመነጨውም ከአንድ ትልቅ ተራራ ሥር መሆኑን ገልጿል፡፡

በሌላም በኩል ሄሮዶቶስ የተባለው ሊቅ የዓባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ ከአንድ ትልቅ ተራራ መዳፈያ እንደሚመነጭና ርዝመቱም ከመነሻው እስከ መዳረሻው ዐሥራ ሁለት ሺህ ማይልስ እንደሚደርስ በመግለጽ አስትራቦ የተናገረውን ደግሞታል፡፡

ክብረ ነገሥት ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በየምዕራፉ የሚገኝ ቢሆንም ምድያም ተብላ የምትጠራ ኢትዮጵያ የሆነች ሌላ ሀገር አለች እንጂ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኘው የአሁኗ ኢትዮጵያ አይደለችም የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት ቅዱሳን አበው፣ ነቢያት ሐዋርያት፣ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የጻፉት ስለምድያም ሳይሆን የጥቁር ሕዝብ ሀገር ስለሆነችው ስለእኛይቱ ኢትዮጵያ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

እንግዲህ ኢትዮጵያ በዚህ ሁሉ ገጽታ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ የረዥምም ዘመን ታሪክ ያላት ሀገር ናት፡፡

"ኢትዮጵያ ታብጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" እንደተባለው ሁሉ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታውቅ የኖረችበት ጊዜ የሌለ መሆኑ ቢታወቅም ንግሥተ ሳባ በታሪክ የሰማችውን የሰሎሞንን ጥበብ ለማየትና በዘመኑ የነበረውን የሀገሪቱን ሁኔታ ለማስተዋወቅ የብሉይ ኪዳኑን እምነት፣ ትምህርትና ጥበብ ከመሠረቱ ለመረዳት ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገችው ጉዞ በተፈጠረው መልካም አጋጣሚ ግንኙነት ምክንያት የብሉይ ኪዳኑ ሥርዓትና ጽላተ ሙሴ ወደሀገራችን ገብተዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የብሉይ ኪዳን እምነት፣ ትምህርትና ሥርዓተ አምልኮት የሚፈጸምባት የጽላተ ሙሴ መንበር ሆና ትኖራለች፡፡ /1ኛ ነገሥ.10፡1-9/





በሕገ ልቡና እግዚአብሔርን ስታመልክ ኑራ፣ የበሉይ ኪዳኑን ሥርዓትና አምልኮት የተቀበለችው ኢትዮጵያ፣ አምልኮተ እግዚአብሔርን ስትፈጽም የኖረችው በብሉይ ኪዳኑ በአሪት ዘፀአትና በአሪት ዘሌዋውያን በታዘዘውና በተዘጋጁት ነዋያተ ቅዱሳት በዜተ ክርስቲያናችን ይሠራባቸዋል፣ ለምሳሌ የታቦተ ጽዮን ሕግና ሥርዐት አፈጻጸም፣ የበዐላት አከባበር፣ ግዝረት፣ የቀዳሚት ሰንበት አከባበር፣ በክበር፣ በጸናጽል እግዚአብሔርን ማመስገንና ወዘተ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያውያን መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም ይሔዱ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቧል፡፡ "ከኢትዮጵያ ወንዝ ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ልጆቼ ቍርባኔን ያመጡልኛል" ተብሎ በትንቢተ ሶፎንያስ ተጽፏል፡፡ /ሶፎ.3፡10/ ይህ የምሥዋዕት አቀራረብ ትውፊትን የሚመለከት ስለሆነ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖታቸው ሕግ ዕጣኑን፣ ለመሥዋዕትነት አገልግሎት የሚሆኑትን በሕጉ በታዘዘው መሠረት ወደ እግዚአብሔር ቤት ያቀርቡ ነበር፣ ዛሬም ይህ ዓይነቱ የመሥዋዕት አቀራረብ በሐዲስ ኪዳን ሥርዓተ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይለወጥ እንጂ ኢትዮጵያ ከብሉይ ኪዳን የወረሰቻቸው መታወቂያዋ ናቸው፡፡

በጥንቱ ዘመን በዳዊትና በሰሎሞን በሌሎችም ቅዱሳን አበው ነቢያት፣ ነገሥታት የታወቀችው ኢትዮጵያ አሁንም ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ከብሉይ ኪዳን በወረሰቻቸው ባህሎችና ሥርዐቶች ጥንታዊነቷ ጎልቶ ይታያል፡፡ ከዚህም ጋር በድሮውም ሆነ በአሁኑ ጊዜ የሕዝቡ መንፈሳዊ ስሜት፣ ባህልና ልማድ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ያሳያል፡፡

እንግዲህ ኢትዮጵያ ከልደተ ክርስቶስ በፊት የነበራት የአምነት ዕውቅና ከላይ ጠቅለል ባለ መልኩ በተገለፀው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ ይህ ሁሉ ሥርዐተ አምልኮት ይፈጸም የነበረው የአምልኮ ጣዖት ታሪክ ባልተገለጣት የካህናት ክተማ እየተባለች ትጠራ በነበረችው በአኩሱም ጽዮንና በሌሎችም ምኩራቦች መሆኑን የታሪክ ሠነዶች ያስረዳሉ፡፡

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት የሆነው አውሳብዮስ ዘቂሣርያ በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት የታወቀችው ኢትዮጵያ በሐዲስ ኪዳንም የታወቀች ሀገረ እግዚአብሔር መሆኗን የሕንደኬዋ ጃንደረባ መጠመቋንና ጥምቀተ ክርስትናን ተቀብሎ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ መመለሱን ይገልጻል፤ ከምድረ አስራኤል ውጭ ከሆኑት ሕዝብ፣ አሕዛብ መካከል በወንጌላዊው ፊልጶስ እጅ ተጠምቀ ምሥጢረ ጥምቀትን የተቀበለው ለመላው ዓለም የመጀመሪያው የክርስትና ሃይማኖት ፍሬ የሆነው ጥምቀተ ክርስትናን ተቀብሎ ወደበታው አኩሱም ጽዮን የተመለሰው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ለመላው ዓለም የሰው ልጅ ሕይወትን ለመስጠት ስለመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ፤

በዚሁ መሠረት አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ሔዶ በተመለሰው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አማካይነት የክርስትናው እምነት በአንደኛው መቶ ዓመት ማለትም በሠላሳ ዐራት ዓመተ ምሕረት ወደ ሀገራችን እንደገባ በማያሻማ ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡ /የሐዋ.8፡26-40/

ከዚህ አንጻር ኤጲስ ቆጶስ ተሾሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ ህልውና ታውቆ ተባርኮና ተቀድሶ በዐራተኛው ምዕት ዓመት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸምና ማስፈጸም ተጀመረ፡፡

ኢትዮጵያ፣ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከአዳም እስከ ሙሴ ደብረ ሲና በሕገ ልቡና፣ በይቀጥላልም በሙሴ ሕግ፣ ከጊዜ በኋላም አዲስ ኪዳኑን በመቀበል፣ በመማር ማስተማር በአነዚህ ሦስት ዓበይት ሕግጋት በቅደም ተከተል ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት፣ በመቀደስ፣ ቃሉን በመስማት፣ አምልኮቱንም በሕገ እግዚአብሔር ስትመራ የኖረች የሃይማኖት ሀገር ስትሆን የዕድገቷም አሳማኝ አቋም በዚሁ ንጉሥነትና መጠን የተገነባ ሆኖ ከአንዱ ወደቀጣዩ ትውልድ ሲወርድና ሲወራረድ መጥቶ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሶ ይታያል፡፡

ከዐራተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ዓመት የነበረው ጊዜ አርኪ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተፈጸመበት ወቅት የመሆኑን ያህል ቅዱሳት መጻሕፍት ከዕርዕና ከመሳሰሉት ጥንታውያን የሥልጣኔ ቋንቋዎች ወደ ግዕዙ ብሔራዊ ቋንቋ የተተረጐሙበት፣ ገዳማዊ ሕይወት የተመሠረተበት፣ የቤተ ክርስቲያናችን ውዳሴ፣ የቅዳሴ፣ የዝማሬ፣ በአጠቃላይም የዜማ ስልቶች በፈቃደ እግዚአብሔር በኢትዮጵያዊው አባት ቅዱስ ያሬድ የተደረሰበት የሥነ ጽሑፍ ውበት የታየበት ወቅት ሲሆን፣ ይህ ሁሉ ትምህርት፣ ተአምር



www.ethiopianorthodox.org

የሆነው በኢትዮጵያ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

በሰባተኛው መቶ ዓመት ሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ በሰለሙ ዓረቦች በመወረሩና ይህም ሁኔታ ከጊዜ በኋላ በቀይ ባሕር አካባቢ ቀይ ባሕርን ተከትሎ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ እየሰፋ በመምጣቱ የአኩሱም ጽዮን ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያኗ ከክርስትናው ዓለም ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተቋረጠ፡፡

በዘጠነኛውና በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዓመት በዮዲት ወይንም በጉዲትና በግራኝ መሐመድ የጥፋት ዘመናት እጅግ የበዛ የሕዝበ ክርስቲያን ሕይወት ጠፍቷል፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቅዱሳት መጻሕፍትና ቅርሳቅርሶች ተደምስሰዋል፣ በሁለቱም ጊዜያት የጥፋቱን ገፈት የቀመሰችው አኩሱም ጽዮን ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን አሁን ካለችበት ደረጃ የደረሰችው ያጋጠማትን አስከፊ ጊዜ አሳልፋ ሰማዕትነቱን ተቀብላ እንደ ሆነ የሃይማኖት ታሪክ መጻሕፍት ያስረዳሉ፡፡

ከዐሥረኛው እስከ ዐሥራ አምስተኛው መቶ ዓመት ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጉዲት ዘመነ መንግሥት የተደመሰሰውን ታሪኳን ከአኩሱም ጽዮን ጀምራ እንደገና መልሳ በማደስ በአሠራራቸውም በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት የታነፁበት፣ ስብከተ ወንጌል በመላ ሀገሪቱ የተስፋፋበት፣ ገዳማዊ ሕይወት በበለጠ የታደሰበት፣ ሥነ ጽሑፍ የዳበረበት ቅዱሳት መጻሕፍት ከዓረቢኛ ወደ ግዕዝ ቋንቋ በበዛት የተተረጐመበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህም ዘመን ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ከዐራተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ዓመት እንደነበረው የተሻለ ጊዜ የነበረ መሆኑ ይተረካል፡፡ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም በተለያየ መልኩ ጥንታዊና ታሪካዊ የሆነች ሀገር ናት፡፡ ስለ ሀገራችንም የታሪክ እና ጥንታዊነት ለመረዳት ነገር ግን ከመሠረቱ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡

## ሀ. ነገደ ካም /ነገደ ኩሽ/

ኩሽ የኖኅ የልጅ ልጅ የካም ልጅ ነው፡፡ ለካም ዐራት ልጆች ነበሩት፣ እነዚህም ኩሳ /ኩሽ/፣ ሚስራይ፣ ፋይ፣ ከነዓን ይባሉ ነበር፡፡

ኩሳም /ኩሽ/ አምስት ልጆች ወለደ፡፡ እነዚህም ሰባ፣ ኤዋልጥ፣ ሰብታ /አቢስ/፣ ሬጌም፣ ሰበቅታ ናቸው፡፡

ሬጌም ሳባንና ዮዳዳን ይወልዳል፡፡ እነዚህም በእስያ ደቡብ ሲኖሩ በኋላ ወደ ክፍላቸው ወደ አፍሪቃ እየተሻገሩ መጥተው ከኢትዮጵያ ጀምሮ እስከ ምስር /ግብፅ/ ወሰን ያለውን አገር እያቀኑና እያለሙ፣ ከተማም እየሠሩ ኖረዋል፡፡ ዋና ከተማቸውም መርገፌ ይባል ነበር፡፡ በኋላ ግን በዘመን ብዛት ጥቂት በጥቂት እያሉ እስከ አክሱም ወጥተው በአክሱም አጠገብ ሳባ የሚባለውን ከተማ ሠርተው ይኖሩ ነበር፡፡ የኩሽ ልጆች ከእስያ ወደ ኢትዮጵያ ያደረጉት ጉዞ ክክርስቶስ ልደት በፊት 3000 ዓመት አካባቢ እንደሆነ ይገመታል፡፡

እንግዲህ በዘመን ብዛት እየበዙ ሲሄዱ መንግሥት አቋቋሙ፡፡ በኢትዮጵያ የነገሡትን የነገደ ካምን ነገሥታት ስምና ቍጥር ስንመለከት ከካም ከሦስተኛው ትውልድ ከሰብታህ ይጀምራል፡፡ ሰብታህ /ሳቤታ / ክክርስቶስ ልደት በፊት ከ2545-2513፣ 30 ዓመት ነግሠዋል፡፡ ከሰበታህ እስከ ጲኦሪ 1ኛ /ከ2000-1985/ ከነገደ ካም በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት 22 ሲሆኑ ዘመኑም 560 ይሆናል፡፡

## ለ. ነገደ ሴም /ነገደ ዮቅጣን/

ኖኅ ሴምን ይወልዳል፣ ሴም ኤቦርን፣ ኤቦር ዮቅጣንን ይወልዳል፡፡ ዮቅጣንም 13 ልጆች ነበሩት፣ ስለዚህም ነገደ ዮቅጣን የሴም ልጆች ናቸው፡፡ /1ዜና.መዋዕ.1፡17-20/ ሳባ የዮቅጣን 10ኛ ልጅ ነው፡፡ /1ኛ ዜና መዋ.1፡20-21/

የነገደ ዮቅጣን መኖሪያ በእስያ ምድር ነበር፡፡ /ዘፍ.10/ ከ13ቱ የዮቅጣን ልጆች አምስቱ ሳባ፣ ኦፊል፣ አፊር፣ አቤማኤል፣ ዐዊላ፣ ቦታ ስለጠበባቸው ከወንድሞቻቸው ተለይተው የእስያ ደቡብ ወደሆነው ወደ የመን መጡ፡፡



ከ ... ከ ... ከ ...

በጂኦግራፊ አቀማመጥም ኢትዮጵያ ከንብዕ ደቡብ መሆኑዋ በቅዱስ መጽሐፍ ተነግሮዋል፡፡ /ሕዝ.29፡10፣ ዮዲ.1፡10/
ሱዳንንና ግብፅን ሲያጠጡ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ወንዞች ዐባይና ተከዜ በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቁ ናቸው፡፡ /ኢሳ.18፡1፣ ኤር.3፡10/

የኢትዮጵያ በማዕድን የከበረች አገር እንደመሆንዋ አልማዙዋና ወርቋም በዓለም ተደናቂ ነበር፡፡ /ኢዮ .28፣19/ ሕዝቡዋም በንግድ ሥራ በዓለም የታወቁ ነበሩ፣ በንግዳቸውም በልጽገውና ተደስተው ይኖሩ ነበር፡፡ /ኢሳ.43፡3/

የኢትዮጵያ ግዛት እጅግ በጣም ሰፊ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል፡፡ በዜና መዋዕል ካልዕ እንደተተረከው ኢትዮጵያውያን ዜራህ /ዝሪ/ በሚባለው ንጉሣቸው እየተመሩ ዘምተው ምድረ ይሁዳን ከያዙ በኋላ በንጉሥ አሣ ድል ሆነዋል፡፡ /2ዜና መዋ.14፡9-15፣16፡8/

ኢትዮጵያውያን ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር በነይላቸው ተመክተው በሚሠሩት ሥራ ነቢያት ይገሥፁአቸው ነበር፡፡ /ሶፎ.2፡12/

የታሪክ ምሁራን በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የማያቋርጥ ፍቅርና ግንኙነት ሲገልጡ ደግሞ "ኢትዮጵያ እጆቹዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" እያሉ በግልፅ ተናግረዋል፡፡ /መዝ .68፡3/

ከዚህ ሌላ እንደ ባጅ ያሉ ታዋቂዎች ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያ ያለ ሃይማኖት የኖረችበት የታሪክ ዘመን እንደሌለ ጽፈዋል፡፡ ይህም ያገር ውስጥ ታሪክ ጸሐፊዎች ከሚሰጡት የምስክርነት ቃል ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት ስለነበራት ሃይማኖት ስንናገር አቅኒዎቹዋን የሕይወት ታሪክ በመመርመር ነው፡፡ ኢትዮጵያን ያቀኑ ሰዎች የመምለኪ እግዚአብሔር የኖህ የልጅ ልጆች የአያታቸውን አምላክ አንድ እግዚብሔርን ያመልኩ እንደነበር በቅድሚያ ተናግረናል፡፡ ግን እምነቱ በትምህርት የተደገፈ ስለአልሆነና ኑሮውም የብሉይ ኪዳን ሕግና አምልኮተ እግዚአብሔር ከተሰበከባት ከምድረ ይሁዳ ውጭ ስለሆነ አንድ አንድ የአምልኮ ባዕድ ልማዶች ሠርገው ሳይገቡ አልቀሩም፡፡

ለምሳሌ ከጌታ ልደት በፊት 1000 ዓመት አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ለዘንዶ ይገብሩ፣ ዘንዶ ያመልኩ እንደነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት ተጽፎዋል፡፡ ይኸው ታሪክ ነገሥት እንደሚለው በኢትዮጵያ ሲመለክ የኖረውን ዘንዶ የገደለው የንግሥተ ሳባ አባት አንጋቦስ የተባለው ሰው ነው፡፡

በጣዖት ማምለክና የአሕዛብን ልማድ በማደጎ መውሰድ ከምድረ እስራኤል ውጭ ይቅርና በምድረ እስራኤል የተለመደ ነበር፡፡ ለልዑል እግዚአብሔር መመስገኛ ቤተ መቅደስን ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው ሰሎሞንም እንኳ ለግብፃዊት ሚስቱ መስገጃ ቤተ ጣዖት አሠርቶ ነበር፡፡ እሱም ፅቁባቱ አብዛኞቹ አሕዛብ ስለነበሩ እነሱ እየጐተቱት ለጣዖታት በመስገዱ ከእግዚአብሔር ተጣልቶ መንግሥቱ እሁለት ተከፍሎዋል፡፡ ይህን የመሰለ አድራጎት በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ተነግሮዋል፡፡ ነገር ግን የእስራኤል እምነት የሚነገረው በአንድ አምላክ ማመናቸው ነው፡፡ በኢትዮጵያም እንዲሁ ነው፡፡

## ሙ. አኩስም በሕገ ኦሪት

የሰው ልጅ በሕገ ልቡና ለ3844 ዓመታት ያህል ከኖረ በኋላ በእነዚህ ዓመታት በተፈጥሮ ዕውቀቱ ተጠቅሞ ከአምልኮ ጣዖት ሊወጣ ስላልቻለ እግዚአብሔር አምላክ በደብረ ሲና ተገልጦ ለዕውቀቱ አጋዥ ረዳት ይሆነው ዘንድ ሕገ ኦሪትን በነቢዩ ሙሴ አማካይነት ለሕዝበ እስራኤል ሠራ፡፡ /ዘፀአ.ም.19 ቁጥር 15-16/

ምንም እንኳ ሙሴ እስከ ተገኘበት ዘመን ድረስ በአዳምና በልጆቹ በእነ ኖኅ፣ በእነ አብርሃም፣ በእነ መልከ ጼዴቅ በሕገ ልቡና ይመለክ የነበረው የአንድ አምላክ እምነት በካምና በሴም ዘሮች አማካይነት በኢትዮጵያ ያለማቋረጥ ሲፈጸም እንደኖረ ቢታወቅም፣ የኦሪት እምነት በሀገራችን በይፋ ተቀባይነትን ያገኘው ከንግሥተ ሳባ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነው፡፡





በኢትዮጵያ ያለማቋረጥ ሲፈጸም እንደኖረ ቢታወቅም፣ የኦሪት እምነት በሀገራችን በይፋ ተቀባይነትን ያገኘው ከንግሥተ ሳባ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነው፡፡

## ንግሥተ ሳባ

ከኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ በሃይማኖታ እጅግ የላቀች እንደነበረች በብዙ የተሪክ ጸሐፊዎች የሚነገርላት ንግሥተ ሳባ /1013-982 ዓ.ዓ/ ኢትዮጵያንና የመንን በአንድነት ትገዛ ነበር፡፡ ይህች ንግሥት በክብረ ነገሥት "ማክዳ" በመጽሐፈ ነገሥት ንግሥተ ሳባ ትባላለች፡፡ /1ኛ ነገሥት ም.10 ክፍ 1 እስከ መጨረሻ/፡፡ በወንጌል ግን ንግሥተ ዐዜብ ተብላ ትጠራለች /ማቴ 12፡42/፡፡ ሳባ በአኩስም አጠገብ ያለ ቦታ ስም ሲሆን ዐዜብ በደቡብና ምዕራብ መካከል ያለ አቅጣጫ ነው፡፡ ይህም ስም የተሰጣት ከኢየሩሳሌም በዐዜብ በኩል የሚገኙ ኢትዮጵያንና የመንን ትገዛ ስለነበር ነው፡፡

ንግሥተ ሳባ ክክርስቶስ ልደት በፊት ባሉት ዘመናት ከነበሩት ነገሥታት በሃይማኖትም ሆነ በሥልጣኔ ዋነኛዋ እንደነበረች ይታወቃል፡፡ ንግሥት ማክዳ፣ ንግሥተ ሳባ በሚል ስመ መንግሥት በአያቶቿ ዙፋን ተቀምጣ፣ ለሰላሳ አንድ ዓመታት አስተዳድራለች፡፡ በክብረ ነገሥት እንደተገለፀው በመልኳ፣ በደም ግባቷ እጅግ ያማረች፣ በጥበብና በማስተዋል የተሞላች ነበረች፡፡ እሷም እግዚአብሔር በሰጣት ክብር፣ ብልጥግና፣ ወርቅና ብር በከበሩ ልብሶች፣ በግመሎች በባሪያዎች፣ በነጋዴዎችም እጅግ የበለፀገች ነበረች፡፡



ግዛትዋም እጅግ ሰፊ ነበር፡፡ በደቡባዊ ምሥራቅ እስከ ማዳጋስካር፣ በስተሰሜንና በስተምዕራብ እስከ ግብጽና እስከ ጥብያ ጻርቻ በስተደቡብ ዛሬ ቢክቶሪያ ኒያንዛ እስከተባለው ባሕር ነበር፡፡ ነጭ ዓባይ ኒያንዛ ከሚባለው ባሕር ወጥቶ ካርቱም ላይ ከጣና ባሕር ከሚወጣው ከጥቁር ዓባይ ጋር ተገናኝቶ የሱዳንንና የግብጽን አገሮች ያጠጣሉ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺህ ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ከነበሩ ገናና ነገሥታት በምትወለደው በንግሥተ ሳባ ዘመን ከኢየሩሳሌምና ከዐረብ፣ ከግብፅና ከሕንድም አገሮች ብዙ ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ ይመላለሱ ነበር፡፡ እነዚህ ነጋዴዎች ከኢትዮጵያ የሚገኘውን ልዩ ልዩ ዕንቁና አልማዝ ወርቅና ሽቱም እየገዙ በየሀገራቸው ስለወሰዱ በዚህ ሁሉ ምክንያት የኢትዮጵያና የንግሥተ ሳባ ዝና በዓለም ሁሉ ተሰማ፡፡ ንግሥተ ሳባ ጠንካራ ንግሥት በመሆኗ የንግድ መስመሩ እስከ ምስር፣ ኢየሩሳሌምና ሕንድ የሚዘልቀው የንግድ ድርጅቷ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር አድርጋለች፡፡ የንግድ እንቅስቃሴውነም የተመቻቸ ለማድረግ የሚረዷት ሰባ ሦስት መርከቦችና አምስት መቶ ሃያ የግመል መንጋ ነበራት፡፡ እነኝህም በታማኝ ሹሟ በታምሪን ኃላፊነት ሥር ነበሩ፡፡

በንግሥተ ሳባ ዘመን የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን በሕገ ኦሪት ለታቦተ ጽዮን ማረፊያ የሚሆን መቅደስ ማሠራት ጀምሮ ነበር፡፡ እሱም በተለያዩ ሀገሮች ለሚኖሩ ነጋዴች ለመቅደሱ ሠራ ሊጠቅሙ የሚችሉ ብርቅና ድንቅ ነገሮችን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያመጡ፣ ዋጋቸውንም በወርቅና በብር እንደሚከፍል አሳወቀ፡፡ በዚህ ጊዜ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም እየተመላለሰ ይነግድ የነበረው ታምሪን የተባለው ነጋዴ ቀይ ወርቅ ፣ ዘጲ እና ሌሎችንም የከበሩ ዕቃዎችን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ ለሰሎሞን ካስረከበ በኋላ ሲመለስ የሰሎሞንን ቤተ መንግሥት ሥነ ሥርዓት ጥበቡንና ክብሩን ሁሉ ለንግሥተ ሳባ ነገራት፡፡

ንግሥተ ሳባም በጆሮዋ የሰማችውን በዓይኗ አይታ ለማረጋገጥ በብዙ ወታደርና ደንገጡር ታጅባ ለሰሎሞን የሚርበውን ልዩ ልዩ ስጦታ በክብት አስጭና በታምሪን መሪነት ወደ ኢየሩሳለም ወረደች፡፡ /መጽ.ነገ.ቀዳ.10፡1-12፣ ዜና መዋ.ካልዕ 9፡1፣ ማቴ.2፡42/፡፡ በደረሰችም ጊዜ ንጉሡ ሰሎሞን በክብርና በደስታ ተቀበላት፡፡ እርሷም ከኢትዮጵያ ይዛለት የሔደችውን መቶ ሀያ መክሊት ወርቅ፣ እጅግም ብዙ ሽቱ፣ የከበረ ዕንቁ ሰጠችው፡፡ ሰሎሞንም የተለየ ማረፊያ ቦታ መርጦ ለራሷና ለሰዎቿ ሰጣት፡፡

የሳባ ንግሥት ወደ ሰሎሞን የሔደችው ጥበቡን ለማወቅ ነውና በልብዋ ያለውን ሁሉ አጫወተችው፡፡ እሱም የጠየቀችውን እንቆቅልሽ ሁሉ ፈታላት፡፡ ከእርሱ የተሰወረ ነገር አልነበረም፡፡ እርሷም አስተዋይና ጥበበኛ እንደመሆኗ የሰሎሞንን ጥበብ ሁሉ ሠርቶትም የነበረውን ቤተ መንግሥት የቤተ መንግሥቱን ሥርዓትና በእግዚአብሔር ቤት የሚያሳርገውን መሥዋዕት ካየች በኋላ እንዲህ አለችው፡፡ "ስለ ነገርህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው፡፡... አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ለዘለዓለም ወዶታልና እውነትን ትፈርድ ዘንድ ንጉሥ አድርጎ ሾመህ" /መጽ.ነገ.ቀዳ.10፡6-9/፡፡

እዚህ ላይ የተጠቀሰው የንግሥተ ሳባ አነጋገር ወደ ሰሎሞን ከመምጣቷ በፊት ገና ከልጅነቷ ጀምራ ኢትዮጵያውያን ቀደምቶቿ በሕገ ልቡና ያመልኩት በነበረው በአንዱ አምላክ በእግዚአብሔር ታምን እንደነበረ በግልፅ የሚያስረዳ ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ የእስራኤልን አምላክ ስም ጠርታ አታመሰግንም ነበርና፡፡ ይሁንና በኢየሩሳሌም ስድስት ወር በቆየችበት ጊዜ ሕገ ኦሪትን በመስማትና በመማር እምነቷን የበለጠ እንዳጠናከረች እሙን ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያናችንና በሀገር የታሪክ ሠነዶች ተጠቅሶ እንደሚገኘው ንግሥተ ሳባ ኢየሩሳሌም በቆየችበት ጊዜ ንጉሥ ሰሎሞን እና እርሷ ስለ ጥበብ ሲጠያየቁ ባደረጉት መቀራረብ ፀነሰች፡፡ ከዚህ በኋላ "ልጅህ መሆኑን የምትረዳበት ምልክት ስጠኝ" ብላ ከሰሎሞን የጣቱን ወርቅ ተቀብላ በቱሉ ወደ አገርዋ ተመለሰች፡፡ የኤርትራን ባሕር ተሻግራ በሐማሴን አውራጃ "ማይበላ" ከሚባለው ቦታ ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች፡፡ ስሙንም ዕብነ መለክ /የጥበበኛ ልጅ/ ብላ ሰየመችው፡፡ ይህም ከጊዜ በኋላ ተለውጦ ምኒልክ ተባለ፡፡ ከዚያም ጉዞዋን ቀጥላ ከመናገሻ ከተማዋ ከአኩስም ስትደርስ ደማቅ አቀባበል ተደረገላት፡፡

ሰሎሞን ከንግሥተ ሳባ ለመውለድ የወሰነው በሚወለደው ልጅ አማካይነት የአይሁድ እምነት በኢትዮጵያም እንደሚሰበክና እንደሚስፋፋ አስቀድሞ ስለተገለጠለት ነበር፡፡ ስለዚህ ከላይ እንደተመለከትነው ንግሥተ ሳባ ኢየሩሳሌም ሔዳ የአንድ አምላክን እምነት አጠናክራ ከተመለሰች በኋላ እውነተኛውን አምላክ በመልዐት ማምለክ ቀጠለች፡፡ ዜጎቿም ይህንኑ እምነት አጠንክረው እንዲይዙ አደረገች፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኦሪት እምነት እስከ ዘመነ ክርስትና ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ሃይማኖት ሆኖ ኖረ፡፡





ቀዳማዊ ምኒልክ በተወለደ በ22 ዓመቱ አባቱን ሰሎሞንን ለመገናኘት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደ፡፡ እዚያም እንደደረሰ እናቱ የሰጠችውን ቀለበት ለሰሎሞን አቀረበ፡፡ ሰሎሞንም በደስታ ተቀበለው፡፡ በተሰበቱና በመልኩ ልጁ መሆኑን ስለተረዳ ስሞ ባረከው፡፡ ሦስት ዓመት በኢየሩሳሌም በቆየበት ወቅት በሊቀ ካህናቱ በሳዶቅ መምህርነት ሕገ ኦሪትን፣ ሥርዓተ መንግሥትን የዕብራይስጥን ቋንቋ ተማረ፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ እናቱ ወደ ንግሥተ ሳባ ሲመለስ በፈቃደ እግዚብሔር በሳዶቅ የበኩር ልጅ በአዛርያስ አማካይነት ታቦተ ጽዮንን ይዞ መጣ፡፡ በዚህም ጊዜ በኢትዮጵያ የኦሪትን እምነት እንዲያስፋፋና የመንግሥቱንም ተግባር ለማካሔድ እንዲረዳ ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የተውጣጡ አሥራ ሁለት ሺህ የበኩር ወንድ ልጆችና ሌዋውያን ካህናት አብረው መጥተዋል፡፡

በዚህ አኳኋን ወደ ኢትዮጵያ የመጣችው ታቦተ ጽዮንን አኩስም ከተማ ውስጥ ቀደም ሲል የተሰየ ድንኳን፣ ቆየት ብሎ ደግሞ ቤተ መቅደስ ተሠርቶላት ኖረች፡፡ የምትገለገለውም በሥልጣነ ክህነት ተወስኖ በሚኖር ካህን ነው፡፡ ማንም ሰው እንዲያያት አይፈቀድለትም፡፡

ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተ ጽዮንን ይዞ በሰላም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አኩስም በደረሰ ጊዜ እናቱ ንግሥተ ሳባና የአገሩ ሕዝብ በእልልታና በደስታ ተቀበሉት፡፡ ወዲያውም ንግሥቲቱ ዙፋኑዋን፣ ሥልጣነ መንግሥቷን ለምኒልክ አስረክባ አነገሠችው፡፡ አዋጅም አስነገረችለት፡፡

ከጥቂት ዘመናት በስተቀር ለሦስት ሺህ ዓመታት ያለማቋረጥ እስከቅርብ ድረስ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ የተገኙ ነገሥታት ሥርወ መንግሥት በመሆን የመጀመሪያው ቀዳማዊ ምኒልክ ነው፡፡ እርሱም ለ25 ዓመታት /982-957ዓ.ዓ./ ከነገሠ በኋላ በተወለደ በ58 ዓመቱ ዐረፈና ከአኩስም ከተማ በስተምዕራብ በኩል በሚገኘው ቦታ በእናቱ መቃብር አጠገብ ተቀበረ፡፡ ይህም ቦታ ሳባ ቤተ መንግሥት በመባል የሚታወቅ ነው፡፡

ቀዳማዊ ምኒልክ ከኢየሩሳሌም ያመጣት ታቦተ ጽዮን በኢትዮጵያ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ቅድስተ ቅዱሳን በሆነችው በአኩስም ጽዮን ቤተ መቅደስ በጥንቃቄ ተጠብቃ ትገኛለች፡፡

ይህም ከፍተኛ ክብር ኢትዮጵያን የሃይማኖት የመንግሥት የሕግና የሥርዓት ምንጭ አድርጓታል፡፡ የጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በዛሬው ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙት ከ35 ሺህ በላይ ለሆኑ አብያተ ክርስቲያናት የቀዳሚነት ሥፍራን ይሰጣታል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ቀደም ብሎ ንግሥተ ሳባ ያመጣችው የኦሪት እምነት በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ መሠረት ሊይዝና ሊስፋፋ ችሏል፡፡ ከጥንታዊው የኦሪት እምነታችን የተወረሱና አሁንም ከሚሠራባቸው ትሩፍችና ባህሎች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 1ኛ. የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠራር፣

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጀምሮ በሰቀላ መልክ /በባሲሊካ/ ቅርፅ እየተሠሩ ካሉ ዘመናውያን አብያተ ክርስቲያናት በቀር በቀድሞ ጊዜና አሁንም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየተሠሩ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት አንደ ኦሪቱ ቤተ መቅደስ ቅኔ ማሕሌት፣ ቅድስትና መቅደስ በተባሉ ሦስት ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው፡፡ "ቅኔ ማሕሌት" መዘምራን ማሕሌት የሚቆሙበት ሲሆን፣ "ቅድስት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሥጋ ወደሙን ስምእመናን የሚያቀርቡበት ክፍል ነው፡፡ "መቅደስ" መንበረ ታቦቱ የሚገኝበት፣ ጳጳሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት ብቻ የሚገቡበት ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት ነው፡፡ ከበሮው፣ ጸናጽሉ ወዘተ ከኦሪቱ ሥርዓት ተያይዞ የመጣ እንደሆ ይታመናል፡፡

## 2ኛ. የትዳሜ አከባበር

ሰባተኛው ቀን ቅዳሜ እንዲከበር የታዘዘው በኦሪት ሲሆን /ዘፀ.20፣20/ ከዚያ ተያይዞ በመጣ ሥርዓትና በኋላም በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በተወሰነው መሠረት በሀገራችን በኢትዮጵያ ቅዳሜ



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ በዚህ ጽሑፍ ከመነሻው እስከ መደምደሚያው የተጠቀሱ የታሪክና የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረችው አኵስም ከተቆረቆረችበት ጊዜ ጀምሮ የሃይማኖትና የሥልጣኔ ምንጭ ሆና የኖረች መሆኗን በግልፅ ስለሚያስረዱ አኵስማውያን ጣዖት አምላኪዎች ነበሩ የሚሉ ከዚህ ሐቅ ሊማሩና አባባላቸውን ሊያስተካክሉ ይገባል እንላለን፡፡

## ሠ. ኢትዮጵያ ድሕረ ልደተ ክርስቶስ

ክክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ኢየሩሳሌም በሕገ ኦሪት አምልኮተ እግዚአብሔርን ሲፈጽም የኖረ ሕዝብ ቅድስት ሀገር እንደሆነች ሁሉ ክክርስቶስ ልደት በኋላም በመጀመሪያው ስብከተ ሐዋርያት የክርስትና እምነትን ለመቀበል የታደለው የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪቃዊ ክርስቲያን ቅድስት ሀገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን በመቀበል ሁለተኛዋ ኢየሩሳሌም ለመሆን የበቃው በአክሱም ማዕከልነት ነው፡፡ ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ ለሚገኘው አምልኮተ እግዚአብሔር መነሻው አክሱም ነው፡፡ በአክሱም መነሻነት የክርስትና እምነት እንዴት እንደተጀመረና እንደተስፋፋ ከሚከተለው ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡

### 1. አክሱም ከ1ኛው እስከ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

የክርስትና እምነት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አክሱም የገባው በሐዕዋ ለሕንደኬ የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪቃዊ ክርስቲያን አማካይነት ነው፡፡

ሐዕዋ ለሕንደኬ በትውልዱ አክሱማዊ የሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መሠረት ነው፤ ኢትዮጵያ የክርስትናን እምነት የተቀበለችው በመጀመሪያው ምዕት ዓመት በ34 ዓ.ም. ወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የኢትዮጵያን ንግሥት የሕንደኬን ጃንደረባ ስለ ክርስቶስ አስተምሮና አሳምኖ ባጠመቀው ጊዜ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረው ይህ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሕዕው ወይም ጃንደረባ ተብሎ ይጠራ እንደነበር ታውቋል፡፡

ጃንደረባው ወደ ክርስትና እምነት የተመለሰው ከአረማዊነት ሳይሆን በቀጥታ ከብሉይ ኪዳን እምነት ነበር፡፡ ይህንም መረዳት የሚቻለው በራሱ ቋንቋ በግእዝ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ በመገኘቱ ነው፡፡

ጃንደረባው የብሉይ ኪዳን እምነት ተከታይ ብቻ አልነበረም፡፡ እንደ ሕጉ የእምነቱንም ሥርዐት የሚፈጽም ሰው ነበር፡፡ "በዓመት ሦስት ጊዜ በበዐለ ናእት፣ በበዐለ ሐምሣ፣ በበዐለ መፀለት ወንዶች ልጆችህ ሁሉ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት እርሱ በመረጠው ስፍራ ይታዩ፣ በእግዚአብሔርም ፊት ባዶ እጃቸውን አይታዩ" /ዘዳ.16፡16/ በተባለው ትእዛዝ መሠረት ጃንደረባው ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም እየሔደ ለእግዚአብሔር ሔዶ ሥርዐተ አምልኮቱን ፈጽሞ ወደ ሀገሩ በሚመለስበት ጊዜ ይህን ታላቅ ጸጋ ሊያገኝ ችሏል፡፡

የኢትዮጵያዊው ጃንደረባና የቅዱስ ፊልጶስ ታሪክ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ታሪኩም ባጭሩ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡ "የእግዚብሔር መልአክ ፊልጶስን ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው መንገድ ሒድ አለው፡፡ እርሱም ተነሥቶ ሔደ፡፡ እነሆም ኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬ አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፡፡ ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡ ያነብበውም የነበረው ክፍል ይህ ነበር፡፡ እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም፣ በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፣ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፣ ትውልዱንስ ማን ይናገራል? /ኢሳ.53፡7/ ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወደሰረገላው ቀረበና የምታነብበው ታስተውለዋለህን? አለው፡፡ ጃንደረባውም "የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?" አለው፡፡ ከዚህ በኋላ በጃንደረባው ጋባዥነት ፊልጶስ በሠረገላው ላይ ተቀመጠ፣ ፊልጶስም አፉን ከፈተ፣ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ጌታችን ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት፡፡ በመንገድም ሲሔዱ ውሃ ወደአለበት ቦታ ደረሱ፣ ጃንደረባውም እነሆ ውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው ? አለው፡፡ ፊልጶስም በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው፤ ጃንደረባውም ‹ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ› አለ፡፡ ሠረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፣ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሃው ወረዱ፣ አጠመቀውም፣ ... ጃንደረባውም ደስ ብሎት መንገዱን ሔደ" /የሐ.8፡26-40/







ይህ በንብረ መንፈስ ቅዱስ የተመሠረተው፣ አስደሳችና እውነተኛ የክርስትና እምነት ታሪክ ኢትዮጵያ በዘመነ አኵስም ከምሥራቃውያንና ከምዕራባውያን ከሌሎች የአፍሪቃ ሀገሮች ቀድማ ከአይሁድ ቀጥላ ክርስትናን በመጀመሪያው ምእት ዓመት መቀበልዋን ያረጋግጣል፡፡ ትውፊትና ታሪክ እንደሚያስረዱትም ቅዱስ ፊልጶስ ያጠመቀው ጃንደረባ በሐዋርያት ዘመን ክርስትናን ወንጌልን ለኢትዮጵያ መስበኩ ተምኗል፡፡

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት እየተባለ የሚጠራው አውሳብዮስ ጃንደረባው ከተጠመቀ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ወንጌልን ስለመስበኩ የሚከተለውን ጽፎአል፡፡

"መልእክተ አድህኖ በየቀኑ ሩቅ ወደሆኑት ሀገሮች ሁሉ እየተስፋፋ ሳለ ፈቃደ እግዚአብሔር በሴትዋ ንግሥት ሕንደኬ/ ትመራ ከነበረችው ሀገር ከኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች አንዱን አመጣ ይህ ሰው ከእስራኤላውያን ቀጥሎ ከወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ የመለኮታዊውን ቃል መሥጢር ለመቀበል ቀዳማዊ ነበር፣ ከዓለም ምእመናን ቀዳምያት /የመጀመርያ ፍሬ/ ነበር፣ ይህ ሰው /ጃንደረባው/ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሕይወት ሰጭ የሆነውን የክርስቶስን በሰዎች መካከል መመላለስ የምታሳውቀውን ወንጌል ለመስበክ የመጀመሪያው ሰው እንደሆነ ታምኗል፡፡ "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለው ስለ ኢትዮጵያውያን እውነተኛ እምነትና አምልኮት የተነገረው ትንቢት በእርሱም ምክንያት ተግባራዊ ተጸሞን አግኝቷል፡፡
/አውሳብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ 13/

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም ጃንደረባው ወደ ሀገሩ ተመልሶ ለወገኖቹ ወንጌልን እንደሰበከና ክርስትናን እንዳስተዋወቀ ስለ ጃንደረባው በደረሱት ድርሰት ገልጠዋል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

"በርስትህ በኢትዮጵያ
በአቅራቢዋ በኖብያ፣ በአሎድያ፣
ዳግመኛም እስከ ናፕታና ሶባ ድረስ
ክርስትናን ለመስበክ የዘርህ የሕንደኬና የሕዝብዋ ሹም ሆይ
በአፍሪካ ችግር እንዳይኖር ጠብቃት እያልህ ወደጌታህ ጸልይ"



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ አረፍተ ነገር መሠረት ጃንደረባው ለኢትዮጵያ የክርስትና ሰባኪ ብቻ ሳይሆን ስለ አፍሪቃ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የምልጃ ጸሎት ማቅረብ የሚችል ቅዱስ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተጨማሪም እነዚሁ ብሔራውያን ሊቃውንት፡- ኢትዮጵያውያን የቅዱስ ፊልጶስን ትምህርት ከብልሁ ጃንደረባ ሰምተው ለድንግል ማርያም ልጅ ይሰግዳሉ..." በማለት ይገልጣሉ፡፡

ይህ አገላለጥ ጃንደረባው በመንፈስ ቅዱስ ከተላከለት አስተማሪው ከቅዱስ ፊልጶስ የተማረውን ትምህርት ለኢትዮጵያውያን በማስተማሩ ዳዊት በመዝሙሩ 71፡9 "ኢትዮጵያውያን በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ" ሲል የተናገረው ትንቢት እንደተፈጸመ ያሳያል፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" ብሎ እምነቱን በመግለጡና በማረጋገጡ "ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በሚያምን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፡፡ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል" /ዮሐ.4፡15/ የሚለው አምላካዊ ተስፋ የተፈጸመለት እውነተኛ አማኝ ነበር፡፡

ጀንደረባው የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በምታጠምቅበት ጊዜ ትጠቀምበት ለነበረው ሥርዐተ ተአምኖ ጀማሪ መሆኑ ይነገርለታል ሥርዐቱም የሚከተለው ነው፡፡ አጥማቂው ካህን፡- "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምናለህን?"
ተጠማቂው ምእመን፡- "አዎ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ"
ይህ ሥርዐት ከወንጌላዊው ፊልጶስና ከጃንደረባው ንግግር ስለሚተባበር ከዚሁ እንደተወሰደ ይታመናል፡፡ /የሐዋ.8፡37/

ወንጌላዊው ፊልጶስና ጃንደረባው በምን ቋንቋ እንደተነጋገሩ የግብረ ሐዋርያት አንባቢዎች ሁሉ ለማወቅ እንደሚፈልጉ ግልጥ ነው፡፡ ድርጊቱ የተፈጸመው በ34 ዓ.ም. በተከበረው በበዓለ ሃምሳ ሰሞን እንደሆነ በሐዲስ ኪዳን ተገልጧል፡፡ ስለዚህ ወንጌላዊው ፊልጶስ በበዐለ ሐምሳ ዕለት ከቅዱሳን ሐዋርያት ጋር ስለነበር በመንፈስ ቅዱስ በሀገሩ ሁሉ ቋንቋ የመናገር ስጦታን መቀበሉ የታመነ ነው፡፡ ስለሆነም ጃንደረባው በራሱ ቋንቋ በግእዝ መጽሐፈ ኢሳይያስን በሚያነብበት ጊዜ ፊልጶስ ሊሰማውና ሊያነጋግረው ችሏል፡፡ ስለዚህ ፊልጶስና ጃንደረባው የተነጋገሩበት ቋንቋ የኢትዮጵያ ቋንቋ ግእዝ ነበር፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ኢትዮጵያዊው የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ከሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ጋር ሲገናኝ መጽሐፈ ኢሳይያስን እያነበበ መገኘቱ የብሉይ ኪዳን አማኝ እንደነበረ ያስረዳል፤ ይህም የሚያመለክተው ክክርስትና በፊትም የኢትዮጵያውያን እምነት አምልኮተ እግዚአብሔር እንጂ አምልኮተ ጣዖት አለመሆኑን ነው፡፡ ስለዚህም በኢትዮጵያ ጣዖት ይመለክ ነበር፣ የሚለው አነጋገር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ብሔራዊ እምነት አምልኮተ እግዚአብሔር ሆኖ ስለ አንዳንድ ግለሰቦች ሕይወት ይታይ የነበረው አምልኮተ ጣዖት መሰል ድርጊት በኢትዮጵያ ጣዖት ይመለክ ነበር ለማለት የሚያስችል አይሆንም፡፡

ከዚያም በመቀጠል ፡- ከቅዱሳን ሐዋርያት መካከል ቅዱስ ማቴዎስ፣ ቅዱስ ናትናኤል፣ ቅዱስ በርተሎሜዎስ እንዲሁም ቅዱስ ቶማስ በኖብያና በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ቅዱስ ወንጌልን እንደሰበኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እነ ሩፊኖስና እነ ሶቅራጥስ መስክረዋል፡፡ በተለይ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በሕንድ በኩል አድርጎ ወደ ኖብያ ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ በመምጣት ቅዱስ ወንጌልን እንደሰበከና በዚያው አካባቢም በሰማዕትነት እንዳረፈ ጽፈዋል፡፡

በዘመናችን የሚገኙ አንዳንድ ዕውቅ ሰዎችም የፊተኛውን ታሪክ መሠረት እያደረጉ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ገብቶ እንዳስተማረ ያምናሉ፡፡ አያይዘውም ኢትዮጵያን መንበረ ማቴዎስ በማለት ይጠሯታል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው የክርስትና እምነትና ጥምቀት ክሥተት በአኩስምና በአካባቢዋም በሚኖሩ የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች በሚገባ ተቀባይነትን አግኝቶ እየተስፋፋ ፍሬምናቦስና ወንድሙ ኤዲሲዮስ ወደ አኩስም እስከመጡበት ድረስ ቆይቷል፡፡ ከዚህም በመቀጠል በመላዋ ኢትዮጵያ ተስፋፍቷል፡፡





# ምዕራፍ 1

## የክርስትና እምነትና ሥርዐተ አምልኮ በኢትዮጵያ

## ክፍል 1

## ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ

"ነገሥተ ሳባ ወዐረብ ጋዳ ያመጽኡ"
"የሳባና የዐረብ ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባሉ" /መዝ.71,10/

ነቢዩ ዳዊት "ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላኦቲሂ ሐመደ ይቀምሑ፤ ነገሥተ ተርሴስ ወደሴያት አምጋ ያበውኡ፤ ነገሥተ ሳባ ወዐረብ ጋዳ ያመጽኡ፤ ወይሰግዱ ሎቱ ኩሉሙ ነገሥተ ምድር ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይሰግዳሉ፤ ጠላቶቹም ዐመድ ይቅማሉ፤ የጠርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታ ያመጣሉ፤ የሳባና የዐረብ ነገሥታትም እጅ መንሻ ያቀርባሉ፤ ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል" ብሎ /መዝ .71 9-10/በተናገረው ትንቢት መሠረት ሄሮድስ በነገሠበት ዘመን የይሁዳ ክፍል በምትሆን በቤተልሔም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ጥበበኞች ሰዎች ከምሥራቅ መጡ ----" ወደ ቤት ገብተው ሕጻኑን ከእናቱ ጋር አይተው ከፈረስ ከሠረገላ ወርደው ሰገዱለት፤ ሳጥናቸውን ከፍተው ኮረጆዋቸውን ፈትተው ወርቁን ዕጣኑንና ከርቤውን ግብር አገቡለት" /ማቴ.2 1-11/ ብሎ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ እንደጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ተወልዶ ሳለ ወርቅ ዕጣን ከርቤ ከገበሩለት ሦስት ነገሥታት አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ባዜን እንደነበረ ይተረካል፡፡

ነቢዩ ኢሳይያስ "የግመሎች ብዛት፣ የምድያምና የጌፌር ግመሎች ይሸፍኑሻል፤ ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ፤ ወርቅንና ዕጣንን ያመጣሉ፤ የእግዚአብሔርንም ምስጋና ያወራሉ" /ኢሳ.60.6/ ብሎ በትንቢት እንደተናገረው የወርቅ እጅ መንሻ ያቀረበው ኢትዮጵያዊው ንጉሥ እንደነበር ይነገራል፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያ ክርስቶስን ያወቀችውና መባ በማቅረብ ልደቱን ያከበረችው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀዳማዊት ቤተ ክርስቲያን መባሉዋ በትክክል ነው፡፡

## ክፍል 2

## ከ1ኛ - 4ኛ ክፍለ ዘመን

"ነዋ ማይ ወመኑ ይከልአኒ ተጠምቆ "
"እነሆ ውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማን ነው" /የሐ.ሥ.8፡36/

ጌታችም መልአክ ፊልጶስን ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደሆነ መንገድ ሂድ አለው፤ ተነሥቶም ሔደ፤ እነሆም "ህንደኬ" የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አካባቢና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቡዋም ሁሉ የሰለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ሠግዶ ነበር፤ ሲመለስም በሠረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፤ መንፈስም ፊልጶስን ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው፤ ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማ፤ "በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" አለው፤ እርሱም "የተረጐመልኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?" አለው፤ ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመነው፤ ያነበበውም የነበረ የመጽሐፉ ክፍል ይህ ነበረ፡-

www.ethiopianorthodox.org

እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም፣ በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፣ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል"

ጃንደረባውም ለፊልጶስ መልሶ እባክህ ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለሌላ አለው፣ ፊልጶስም መናገር ጀመረ፣ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት። በመንገድም ሲሔዱ ወደ ውኃ ደረሱ፣ ጃንደረባውም እነሆ ውሀ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው? አለው። ፊልጶስም "በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል" አለው፣ መልሶም "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ። ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፣ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሀ ወረዱ፣ አጠመቀውም፣ ከውሀውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፣ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና" /የሐ.ሥ.8፡26-39/ በማለት መንገዱ እንደተረከው የክርስትና እምነትና ጥምቀት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ34 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ንግሥት በሕንደኬ ጃንደረባ በባዕከ አማካይነት ነው።

ያጠመቀውም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወንጌላዊው ፊልጶስ ነው፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ" የሚለውን የእምነት ፎርሙላ በመናገር የጀመረና ለዓለም ያበረከተ ኢትዮጵያዊው ባዕከ ነው። አይሁድና ተንባሎት እስከ ዛሬ ድረስ "ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ" መሆኑን ለማመን አቅቶዋቸው የተቸገሩበትንና ዓለምን የሚያስቸግሩበትን ክህደትና ኑፋቄ ሳይከተል "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አውቆና አምኖ በማሳመን ለወገኖቹ ትክክለኛውን እምነት ስለ ሰበከ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እስከዛሬ ድረስ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ታምናለች፣ ትሰብካለች፣ ታሳምናለች።

በዘመነ ሐዋርያት የክርስትና እምነትን በመቀበል የመጀመሪያው የወንጌል አዝመራ የሆነው ባዕከ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእምነትና ሥርዐተ አምልኮ ሕንፃ የመሠረት ድንጋይ ነው። ለሐዲስ ኪዳን ኢትዮጵያም ዓለም ዐቀፍ እውቅና ያገኘ የቤተ ክርስቲያናችን መሥራች ነው። ባዕከ በዚህ ሃይማኖታዊ ጉዞው የሕገ ኦሪትንና የሕገ ወንጌልን ጽድቅ በአንድ ጉዞ በመፈጸም የራሱንና የአገሩን ስም በቅዱስ መጽሐፍ ለማስጠራት በቅቶአል።

ባዕከ ወደ አገሩ ተመልሶ ከቅዱስ ፊልጶስ ስለ ክርስቶስ የሰማውንና የተረዳውን ለወገኖቹ ኢትዮጵያውያን እንደ አስተማረ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሓፊ አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ጽፎአል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችውም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ፊልጶስ የክርስትና አባቷ ስለሆነ በስሙ ቤተ ክርስቲያን አንፃ ጽላት ቀርፃ ታከብረዋለች። በጸሎቱና በአማላጅነቱም ትታመናለች፣ ከቅዱሳን ሐዋርያት መካከል ቅዱስ ማቴያስ፣ ቅዱስ ናትናኤል፣ ቅዱስ በርተሎሜዎስ፣ ቅዱስ ቶማስ በኑብያና1 በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ወንጌልን እንደ ሰበኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እነሩፊኖስና እነ ሶቅራጥስ መስክረዋል።

በ4ኛው መቶ ዓመት "ቅዱስና ያለ ተንኰል የሚኖር ነውርም የሌለበት ከንጊአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል" /ዕብ.7፣26/ ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነት እንደተናገረው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሾማቸው ከሐዋርያት ሐረገ ክህነት ተያይዞ የመጣ የሐዋርያት ተከታይ የሆነ ሊቀ ካህናት ማግኘት ይገባኛል ብላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ እንዲያስመጣላት ቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማን ወደ አስክንድርያ ላከች። ቅዱስ አትናቴዎስ የአስክንድርያ ፓትርያርክም ራሱት ሾሞ ላከው።

ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በመጀመሪያው ምዕት ዓመት ይሁን እንጂ በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስ መንበር የተሰጣት በአራተኛው ምዕት ዓመት በ330 ዓ.ም. ነው። ከ ኢትዮጵያ ተልኮ ሔዶ ከአስክንድርያው ፓትርያርክ ከቅዱስ አትናቴዎስ ዘንድ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሾሞ በመጣው በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መምህርነት በአብርሃና በአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ጊዜ የክርስትና ሃይማኖት በዐዋጅ ተሰብኩዋል።

[1] ሱዳን





ቅዱስ አባ ሰላማ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መንበረ ጵጵስናውን አክሱም ላይ አድርጎ በሀገራችን የወንጌልን ብርሃን በሰፊው ስለገለጠ ከሣቱ ብርሃን ተባለ። በዚሁ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የታወቀች ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ለመሆን መብቃቷን ታሪክ ያስረዳል።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ በምልዓት መፈጸም ጀመሩ። ቅዱስ ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ግዛት በሙሉ የወንጌልን ትምህርት ለማዳረስ የሚረዱት ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾመ። ይልቁንም በዚያ ጊዜ ሊቀ ካህናት የነበረውን አንበረምን ሕዝበ ቀድስ ብሎ ኤጲስ ቆጶስነት ሾመው በሕዝበ ቀድስም ስብከት የናባና የሳባ፣ የናግራንና የትግራይ፣ የአማራና የአንጎት፣ የቀጣ፣ የዘበግዱር ሕዝብ በክርስቶስ አምነውና ተጠምቀው ክርስቲያኖች ሆኑ[2]። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከዕርዕ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መለሰ። የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ የለወጠውና አዲሱንም ከገራ ወደቀኝ የመጻፍና የማንበብ ዘዴ የፈጠረ እሱ ነው። ይልቁንም ድምፁን በመከተል 6ቱን የፊደል ድምፆች የጨመረ አባ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን እንደሆነ ታሪክ ይናገራል።[3]

ከቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ሢመተ ጵጵስና ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመንበረ ጵጵስና ደረጃ ታወቀች። ከዚያም ጊዜ አንሥቶ እስከ 20ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከግብጻውያን ብቻ ጳጳሳት እየተሾሙ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ቈይተዋል። ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያውያን መካከል ጳጵሳ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጳጳስ፣ አቡነ ፊልጶስ ኤጲስ ቆጶስ ሆነው እንደተሾሙ ታሪክ ይናገራል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጥንታዊት የአስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሥርዐተ እምነት አንድነትና የአኀትማማችነት ኅብረት ስለነበራት ግብፃውያን ጳጳሳት ሥልጣነ ክህነት በመስጠት ብቻ ተወስነው የቀረው የአስተዳደሩና የውስጥ አመራሩ ይዞታ ግን በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ይካሄድ እንደነበር ታሪክ የማይክደው ሐቅ ነው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ፣ በሥርዐተ ትምህርትና በባህል ራሱን የቻለ አቋም የነበራትና ያላት መሆኑ የታወቀ ነው።

## ክፍል 3

## ከ5ኛ - 9ኛ ክፍለ ዘመን

በ5ኛው መቶ ዓመት /479ዓ.ም. አካባቢ/ የሮማ ግዛት ከነበሩ ልዩ ልዩ አገሮች ዘጠኝ ቅዱሳን ወደ አገራችን መጥተዋል፣ እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ዋናው ምክንያት የሚከተለው ነው፣ የአስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በኬልቄዶን ጉባኤ የአንድ ባሕርይን እምነት በመደገፉ ምክንያት በንጉሡ በመርቅያንና በንግሥቲቱ በብርክልያ ትእዛዝ በደቤተ ጋንግራ ውስጥ ታሥሮ በመሰቃየት ከአረፈ በኋላ እነዚህ ቅዱሳን የአንድ ባሕርይን እምነት በመከተላቸውና በማስተማራቸው ምክንያት ሁለት ባሕርይን የሚከተሉትን መለካውያንን የሚደግፈው የሮማ ንጉሥ መርቅያን ከፍ ያለ ሥቃይ ስለ አደረሰባቸው በእምነት መሰሎቻቸው የሆኑ ክርስቲያኖች ወደሚኖሩባት ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጥተዋል፣ ብዙም ሥራዎች አከናውነዋል፣ ከሠሩአቸውም ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ፡-

- ሥርዐተ ምንኩስናን መመሥረትና ማስፋፋት፣
- ገዳማዊ ሕይወትንና ምናኔን ማስተማር፣
- በቅዱስ አባ ሰላማ ጊዜ ያልተተረጐሙትን መጻሕፍት መተርጐም፣
- ገዳማትን በአየበታው ማቋቋም፣
- በከሣቱ ብርሃን ሰላማ ጊዜ የተቋቋመችውን ቤተ ክርስቲያን ማጠናከር የመሳሰሉት ናቸው።

ከዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት በኋላ የአክሱም ቤተ መንግሥትና መላው የኢትዮጵያ ግዛት በክርስትና ሃይማኖት ትምህርትና ስብከት ተዳርሶ ነበር።[4]

[2] ተክለ ተክለ ሃይማኖት
ገ.ደ. ያሳተመው ስንክሳር ገጽ 427-430
የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም - ዛጌ ከተክለ ጻድቅ መኮሪያ፣ ገጽ 217፣ ምዕራፍ 22
[3] የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም - ዘጌ ገጽ 111-112፣ ምዕራፍ 12
[4] የኢትዮጵያ ታክ አክሱም - ዛጌ ከተ.ጻ.መ የተጻፈ ገጽ 246 -253፣ የቤተ ክርስቲያን ታክ ከሱሌ መልአኩ የተጻፈ ገጽ 125- 126



www.ethiopianorthodox.org

ተሰዓቱ ቅዱሳን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ጥንካሬ ከፍተኛ ተልዕኮን ፈጽመው ስለዐረፉ ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን ብላ ታከብራቸዋለች፤ በስማቸው ገዳም ገድማ፣ ጽላት ቀርፃ፣ ቤተ ክርስቲያን አንፃ፣ ስንክሳራቸውንና ገድላቸውን ጽፋ መታሰቢያቸውንና በዓላቸውን ታከብራለች፤ በጸሎታቸውና በአማላጅነታቸው ታምናለች፡፡

ከዚህ በኋላ በስድስተኛው መቶ ዓመት መካከል /550 ዓ.ም./ አካባቢ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ አንድ አዲስ ምዕራፍ ተከፍቷል፡፡ ይኸውም የታላቁ ሊቅ የቅዱስ ያሬድ መነሣት ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያናችን ስትገለገልባቸው የኖረችውንና አሁንም የምትገለገልባቸውን፤ ስብሐተ እግዚአብሔር የምታደርስባቸውን አምስቱን ጸዋትወ ዜማዎችን የመጻሕፍት ብሉያትንና ሐዲሳትን ትርጉም በሙተንተን ከአማረ ጣዕመ ዜማና ጥልቅ ምሥጢር ጋር ደርሷል፡፡ 5 ጸዋትወ ዜማ የሚባሉትም ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ መዋሥዕትና ቅዳሴ ናቸው፡፡

ስለዚህም ቅዱስ ያሬድ እስከአሁን ድረስ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት የቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ዜማ ደራሲ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ቅዱስ ያሬድን ከቅዱሳን እንደ አንዱ በመቍጠር በስሙ ቤተ ክርስቲያን አንጻለች፣ ታቦት ቀርጻለች፡፡ ገድልና ስንክሳር ጽፋለች፡፡

ከ6ኛው - 9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክርስትናው እምነት የበለጠ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የመጣበት ጊዜ ስለነበረ ይህ ዘመን አያሌ ገዳማት የተመሠረቱበትና የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶችም የተስፋፉበት ወርቃማ ዘመን ነበረ፡፡ በሀገራቸው ሰላምን አጥተው የተሰደዱና የሰለሙ ዐረቦችን ኢትዮጵያ በሰብአዊነት ተቀብላ ያስተናገደችበትም ይኸው ዘመን ነው፡፡

በሰባተኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ የሰለሙ ዐረቦች በአገራቸው በተነሣው እስልምና ምክንያት በተፈጠረው ብጥብጥ በትውልድ አገራቸው መኖር ስለአቃታቸው በስደት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ዐረቦች በኢትዮጵያ በሰላም እንደሚኖሩ የሰሙ ቋረሽ የተባሉ ወገኖች ልዩ ልዩ ገጽ በረከት አስይዘው ከአብዲሳ አቡ ራቢያ ጋር ሌሎች ሁለት መልእክተኞችን ወደ ኢትዮጵያ ላኩ፤ የመልእክታቸውም ዓላማ ስደተኞችን ወደ መካ ለመመለስ ነበረ፤ መልእክተኞቹም በጊዜው ወደነበረው "አርማህ" ወደተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ ቀርበው የታዘዙትን እጅ መንሻ በማቅረብ እነዚህ ሸሽተው የመጡት ዐረቦች ከሐዲያኑ ናቸውና አስረክበን ብለው ጠየቁት፡፡ ንጉሥ አርማህም ስደተኞቹን አሳልፎ ስለአልሰጠ የክርስቲያን ደሴት ወደሆነችው ኢትዮጵያ እስልምና ገባ፡፡

ከ7ኛው እስከ 10ኛው መቶ ዓመት የእስልምና እምነት ተከታዮች ሰሜን አፍሪቃንና አስያን በከፊል እስከ ሕንድ ውቅያኖስ በመውረራቸውና ይህም ሁኔታ እስከ ቀይ ባሕር ደርሶ ስለነበር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያና ከሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ጋር የነበራት ግንኙነት ተቋርጦ ነበር፡፡

የጨለማ ዘመን ያስከተለው ችግር ከፍ ያለ ነው፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዕለት ወደ ዕለት ሥነ ሥርዐቷ እያማረና እየተሻሻለ፣ የሊቃውንቱዋ ቍጥር እየበዛ በመሔድ ላይ ሳለ በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን /842 ዓ.ም./ አካባቢ ጉዲት የተባለችው አይሁዳዊት ተነሥታ አብያተ ክርስቲያናትን አፈረሰች፤ ካህናትን አስፈጀች፤ መጻሕፍትንም አቃጠለች፤[5] ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የዛጌ መንግሥት እስከተነሣበት እስከ 10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የጨለማ ዘመን ስለነበረ ቤተ ክርስቲያናችን የነበረችበትን ሁኔታ ለመተረክ አስቸጋሪ ነው፡፡

## ክፍል 4

## ከ10ኛ - 15ኛ ክፍለ ዘመን

ከጉዲት በኋላ እስከ ዓፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ቤተ መንግሥቱ ከአኩስም ወደ ላስታ ተዛውሮ ስለነበር በላስታ የነገሡትም ነገሥታት ቅዱሳን ስለነበሩ በዘመናቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብርሃን ወጥቶላታል፡፡

4 የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም ዛጌ /ከተጻመደተጻፈ/





በቅዱስ ሐርቤ /ገብረ ማርያም/ ዘመነ መነግሥት /1131 ዓ.ም./ ቤተ ክርስቲያን በጣም ብርቱና አያሌ ሊቃውንት ያሏት ስለነበረች አሁን በዘመናችን ተፈጽሞ ያየነውን ራስን ችሎ በራስ መተዳደርን በመፈለግ ከሊቃውንቷ መካከል መርጣ ጳጳስ ለመሾም የጋለ ምኞት ስለነበራት ይኸው አሳቡዋ ይፈጸም ዘንድ ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ አቅርባ እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡ ይልቁንም በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት /1180 - 1220 ዓ.ም. ከፍ ያለ ክብርና ደረጃ እንደነበራት ቅዱስ ላሊበላ ያሠራቸው ዐሥሩ አብያተ ክርስቲያናት ምስክሮች ሊሆኑን ይችላሉ፡፡



እነዚህ ከድንጋዮች ተፈልፍለው የተሠሩት የላሊበላ ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት ከ12ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ የቤተ ክ ርስቲያኒቱ ዕድገትና መስፋፋት ከከፍተኛ ደረጃ ደርሶ እንደነበረ ምስክርነት ይሰጣሉ፡፡

በቅዱስ ላሊበላ ከቋጥኝ ፍልፍል የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት በመላው ኢትዮጵያ እስከ 23 ይደርሳሉ፡፡ 12ኛው እስከ 15ኛው ምዕት ዓመት የነበረው ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በብዛት የተነሡበት በዮዲት ጊዜ የፈረሱት አብያተ ክርስቲያናት የተጠገኑበትና የታደሱበት ዘመን ነበር፡፡

ታላቁ ጻድቅ ፍሬኑ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ የመጡትና በስማቸው የሚጠሩትን የገዳሳትንና የምድረ ከብድን ገዳማት የመሠረቱት በዚሁ ወቅት ነው፡፡

የዛጌ ዘመነ መንግሥት ተፈጽሞ መንግሥት ወደ ዋንቱ ወደ ሰሎሞን ዘር ሲመለስ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያናችን ከመንግሥት ልታገኝ የሚገባትን መብትና ሥልጣን ሁበትና ርስት እንዲታገኝ አድርገዋል፡፡ አባታችን ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ13ኛው መቶ ዓመት /1262 ዓ.ም. አካባቢ/ ዝነኛ ሐዋርያ ነበሩ፡፡ ከዚህም የተነሣ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል፡፡[6] ይልቁንም ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ይደረግ የነበረው የጳጳስ መምጣት ሳቢ ወሰነ ጊዜ በልዩ ልዩ ምክንያት ተቋርጦ ስለነበር በፈቃደ እግዚአብሔር ከፍተኛ መንፈሳዊ አባት / ጳጳስ ሆነው በመሾም የምእመናኑን መንፈሳዊ ፍላጎት ሲፈጽሙ ኖረዋል፡፡[7]

6 የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ይኩኖ አምላክ - ዓፄ ገብነ ድንግል /ከተጻመደተጻፈ/ ገጽ 8 ምዕራፍ 1
7 ተክለ ሃይማኖት



www.ethiopianorthodox.org





ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሀገራችን ጻድቃን መካከል ታላቅ ሐዋርያ ናቸው። በዘመናቸው ወሥራ ሁለት ንጉራ አድ /ሰባክያነ ወንጌል/ ሾመው አህጉረ ስብከት አካፍለው በመላ ኢትዮጵያ ወንጌል እንዲሰበክ፣ ምእመናን እንዲበዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ ክርስትና እንዲስፋፋ አድርገዋል። ራሳቸውም መንበራቸውን ደብረ ሊባኖስ አድርገው በመላ ኢትዮጵያ ዞረው አስተምረዋል። በዚህም መሠረት በስማቸው የተገደሙ ሦስት ገዳማት አሉዋቸው። በተወለዱበት በደብረ ጽላልሽ ዞረሬ፣ ገድል በፈጸሙበትና ዐጽማቸው በዐረፈበት በደብረ ሊባኖስ፣ በደብረ ዐስቦ ግራርያ በአስተማሩበት በደብረ መንክራት /ወላይታ/ ያሉት ገዳማት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳማት ናቸው።[8]

በአጠቃላይ በ12ኛውና በ14ኛው መቶ ዓመታት በወንጌል ስብከት መስፋፋት ረገድ የታላላቅ ደራስያንና ሰባክያን ትንሣኤ የታየበት ዐረፍተ ዘመን በመሆኑ ዘመነ ተሐድሶ እንደነበር በታሪክ ተጽፎዋል።

በደራሲነታቸው የታወቁት ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ሌሎችም አያሌ ቅዱሳን ሊቃውንት የተነሡት በዚህ ክፍለ ዘመን ነበር።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ደብረ እግዚአብሔር በተባለው በሐይቅ አስጢፋኖስ ገዳም በቅዱስ ያሬድ ወንበር ተቀምጠው የድጓ ምስክርነት ይሰጡ ነበር። ከአስተምህሮ ድጓ አወጣጥተው በሰዓት፣ በዕለት፣ በሳምንት፣ በወራት እንዲዘመር መድበው ጾመ ድጓን ማዘጋጀታቸው በታሪክ ተጽፎዋል። ድጓውንም ዮሐንስ፣ አስተምሕሮ፣ ፋሲካ ብለው በሦስት ክፍል የከፈሉ ርሳቸው እንደሆኑ ይነገራል። ከዚህም ሌላ የሌሊትና የመንፈቀ ሰዓታት አርጋኖን፣ መጽሐፈ ምሥጢር፣ ርቱዐ ሃይማኖት የተባለ ሃይማኖተ አበው ደርሰዋል። ሌሎችንም አያሌ የጸሎትና የአኩቴት፣ የቅዳሴና የውዳሴ መጻሕፍት አዘጋጅተዋል። የርሳቸው ደቀመዛሙርት የነበሩ አባ ጽጌ ድንግል ማሕሌተ ጽጌንና ሰቆቃወ ድንግልን፣ አባ ዐርከ ድንግል ዐርኬን፣ አባ መዝሙረ ድንግል በስማቸው የተጠራውን መዝሙረ ድንግል የተባሉትን የማሕሌትና የጸሎት መጻሕፍት ጽፈዋል። /ትውፊት/

## የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም



[8] ገጽ ክርስ[illegible] ታሪክ ከፊሉ መልአኩ የተጻፈ ገጽ 130 - 131



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ዘመን ስብከተ ወንጌል በመላ ኢትዮጵያ የተዳረሰበት፣ ገዳማዊ ሕይወት የተጠናከረበት፣ መንፈሳውያት መጻሕፍት ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐሙበትና በብሔራውያን ሊቃውንት ብዙ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የተጻፉበት ክፍለ ዘመን ነበር። በ14ኛው መቶ ዘመን በዓፄ ዳዊት ቀዳማዊ ዘመነ መንግሥት ከኢየሩሳሌም ምእመናንና ካህናት በስጦታ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተላኩት ጌታችን ሲስቀል የቀኝ እጁ ያረፈበት ግማደ መስቀልና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳት መስከረም 10 ቀን ኢትዮጵያ ገብተዋል።

በ15ኛው መቶ ዘመን በኢትዮጵያ ንጉሥ በዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዐዋጅና ትእዛዝ ልዩ ልዩ የጣዖታት አምልኮት እንዲቀር ተደርጓል። እንዲሁም በሐዋርያት ሲኖዶስ መሠረት ምእመናን ቀዳሚትንና እሑድን ፅኩል በማክበር በእነዚሁ ቀኖች በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ የክርስትና ትምህርት እንዲማሩ ካህናትና ዲያቆናትም ተገተው እንዲያስተምሩ ሥርዐት ተሠርቶ ነበር። በዓጼ ዘርዐ ያዕቆብ ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል። በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ገዳማትም መተዳደሪያ ደንብ /ሕግ/ አዘጋጅተው ልከዋል። ደቂቀ እስጢፋ /የእስጢፋ ተከታዮች/ በአለቃቸውና በመምህራቸው በሥርዐ እስጢፋ መሪነት ይሰጡት በነበረው ትምህርት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ክርክር ተነሥቶ መለያየት ተፈጥሮ ነበር።

## ክፍል 5

## ከ16ኛ - 20ኛ ክፍለ ዘመን መጨረሻ

በዚህ ክፍለ ዘመን በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ምዕራፍ ይዞ የሚገኘው የግራኝ መሐመድ መነሣት ነው። ግራኝ መሐመድ የተነሣው በ16ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ /1539 ዓ.ም. አካባቢ/ ነው። ግራኝ መሐመድ ተነሥቶ ወረራውን እንደጀመረ ወዲያውኑ አብያተ ክርስቲያናትን አፈረሰ፣ መጻሕፍትን አቃጠለ፣ ካህናቱንና ምእመናኑን አሳረደ። በጦር ኀይል አያስገደደ ሐረርን፣ ባሌንና ሲዳሞን፣ አርሲንና ደብብ ሸዋን፣ ጅማንና ስልጤን፣ ወሎንና ምሥራቅ ሸዋን፣ አልፎ አልፎም በጐንደር፣ በጐጃምና በትግራይ ብዙ ምእመናንን አሰለመ።

የጐዲትና የግራኝ ዘመን በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ዘመነ ሰማዕታት ይባላል። የግራኝ ኀይል በኢትዮጵያውያንና በፖርቱጋል ወታደሮች ኀብረት እንደተደመሰሰ /1543ዓ.ም./ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ኢየሱሳውያን የተባሉት የካቶሊክ ሚሲዮኖች ኢትዮጵያን ካቶሊክ ለማድረግ ብዙ ጊዜ ሞክረዋል። ነገር ግን ሳይችሉ ቀርተዋል።





ካቶሊካውያን በሀገራችን ለብዙዎች ኢትዮጵያውያን ደም መፍሰስ ምክንያት ሆነዋል። በተለይም በዓፄ ሱስንዮስና በዓፄ ዘድንግል ዘመን /1632 -1665 ዓ.ም. አካባቢ/ የአውሮፖ ካቶሊካውያን ኢትዮጵያን ካቶሊክ ለማድረግ ያደረጉትን ሙከራና ደም እስኪፋሰስ ድረስ የብጥብጥ መነሻና ምክንያት ሆነው እንደነበር፡-

1ኛ "ትቤ አክሱም መኑ አንተ" የሚለው ከአቶ አስረስ የኔ ሰው የተደረሰው መጽሐፍ፣
2ኛ " የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ልብነ ድንግል - ዓፄ ቴዎድሮስ ከአቶ ተክለ ጻድቅ መኮሪያ የተጻፈው ታሪክ፣
3ኛ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳሳትየተዘጋጀው እነዚህ የታሪክ መጻሕፍት በሰፊው ያስረዳሉ።

17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡት ጸጋዎችና ቅባቶች እነዚሁት ካቶሊኮችን ተጠግተው የተነሡ ናቸው ። በደንብ የተሙቁትና የተዳከሙት በዓፄ ቴዎድሮስ ዐዋጅ ነው።[9] ዓፄ ቴዎድሮስ በሃይማኖታቸው ጠንካራ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ነበሩ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የውጭና የውስጥ ኀይላት በአየጊዜው እየተነሡ ሊያዳክሙዋት ቢሞክሩም የሚደርስባትን መከራና ፈተና ሁሉ ኀይልዋ በሆነው በክርስቶስ ድል እያደረገች ኖራለች።

እንዲሁም ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፍጻሜ ላይ ይጀምርና በግዕዝ ብቻ ሳይሆን በአማርኛም ጭምር ሥነ ጽሑፍት እያበበ የቅኔ ማዕበልና ሞገድ የጐረፈበት፣ አያሌ የቅኔና የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃውንት የበዙበት ጊዜ ሲሆን የሥዕልና የቅርፃ ቅርፅ ሞያም የተሰፋፋበት ዘመን ነበር። የአቋቋም ዜማና ወረብ የተፈጠረው ከግራኝ በፊት ቢሆንም የተስፋፋውና የተጠናከረው በዚህ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ነው። በ19 ኛው ምእት ዓመት መጀመርያ ላይ አባ አብርሃም የተባሉ ኦርቶዶክሳዊ መነኮስ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ ተረጉመ።

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ዓፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ዓፄ ዮሐንስ 4ኛ ሲነግሡ አርሳቸው እንደ ዓፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን በሃይማኖት አንድ ለማድረግ ይመኙ ስለነበር ከውጭ በሚመጡ ሚሲዮኖች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጉ ነበር።[10] ወንጌልን በሰፊው ለማስተማር እንዲያመች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሱዋ ልጆች እንድትመራ አስበው ከእርሳቸው በፊት በንጉሥ ሐርቤ ተጠይቆ ሳይፈጸም የቀረውን ጥያቄ እንደገና በማንሣት ዓፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ አስከክንድርያን ጳጳሳት ሲኖዶስ ጠይቀው ነበር። ነገር ግን ስለአልተፈቀደላቸው 4 ግብፃውያን ጳጳሳት ሾመው እንዲልኩላቸው የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ጠየቁ። ፓትርያርኩም አቡነ ዮሐንስን፣ አቡነ ጴጥሮስን፣ አቡነ ሉቃስንና አቡነ ማቴዎስን ሾመው ላኩላቸው።

ዓፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግሥታቸው ለኢትዮጵያ ከአደረጓቸው ውለታዎች አንዱ ሀገሪቱ በሚሲዮናውያን ስብከት እንዳትከፋፈል ያደረጉት ጥረት ነው። በዘመነ መንግሥታቸው የግብፅና የሊብያ፣ የሱዳንና የሀገራቸውየኢትዮጵያ እስላሞች ግንባር ፈጥረው "ደርቡሽ" በሚል ስም አንድ ሆነው ሦስት ጊዜ ዘምተው ተዋግተዋቸው ሁለት ጊዜ ዓፄ ዮሐንስ ድል አድርገው ከአባረሩዋቸው በኋላ በሦስተኛው እንደገና ተመልሰው በጐንደርና በትግራይ ያሉትን ሊቃውንት አርደው አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥለው ብዙ ግፍ ማድረሳቸውን ስለሰሙ መተማ ላይ ጦርነት ገጥመው በሰማዕትነት ዐርፈዋል። ከዚህ ቀጥሎ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ምዕራፍ ይዞት የሚገኘው ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን ችላ ተተዳደር ዘንድ ከሊቃውንቶቿ መካከል መርጣ ጳጳስ ለመሾም ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ጥያቄና ትግል ነው።

ይህም ጥያቄ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና ምእመናን ሲጠና ቆይቶ ኢትዮጵያውያን ምሁራን እስከ ፓትርያርክነት ያለውን ማዕርገ ሢመት ከማግኘት የሚያግዳቸው ምንም ምክንያት ባለመኖሩ በ1921 ዓ.ም. ዐራት ኢትዮጵያውያን ቀሞሳት ተመርጠው ካይሮ ላይ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ 19ኛ እጅ ተቀብተው ተሾሙ።

9 የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ቴዎድሮስ - ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ /ተ/ጻ/መ/ ገጽ 7 - 8/ ምዕራፍ 3

10 የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ቴዎድሮስ - ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ /ተ/ጻ/መ/ ገጽ 63 - 64/



www.ethiopianorthodox.org

ይህም ጥያቄ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና ምእመናን ሲጠና ቆይቶ ኢትዮጵያውያን ምሁራን እስከ ፓትርያርክነት ያለውን ማዕርገ ሢመት ከማግኘት የሚያግዳቸው ምንም ምክንያት ባለመኖሩ በ1921 ዓ. ም. ዐራት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት ተመርጠው ካይሮ ላይ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ 19ኛ እጅ ተቀብተው ተሾሙ፡፡

ይህም የሆነው በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት በንጉሥ ተፈሪ መኮንን አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት ግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም. ነው፡፡ ስማቸውም ቀጥሎ ያለው ነው፡-

1. አቡነ አብርሃም የጐጃምና የጐንደር ጳጳስ፣
2. አቡነ ይስሐቅ የትግራይና የስሜን ጳጳስ፣
3. አቡነ ጴጥሮስ /ሰማዕቱ/ የወሎና የላስታ ጳጳስ፣
4. አቡነ ሚካኤል /ሰማዕቱ/ የኢሉባቦርና የምዕራብ ኢትዮጵያ ጳጳስ ናቸው፡፡

በ1928 ዓ.ም. በግፈኛው ፋሺሽት ኢትዮጵያ ስትወረር ሞሶሎኒ በ1929 ዓ.ም. በለብያ ዋና ከተማ በትሪፖሊ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማፈራረስና ክርስቲያኖችንም ለመፍጀት መነሣቱን የሚገልጥ ዐዋጅ ነገረ በዐዋጁም መሠረት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ቅርሶች ተቃጠሉ፣ ንዋያተ ቅድሳትና መጻሕፍት ተዘረፉ፣ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ መነኮሳትና ዲያቆናት መዘምራንና ምእመናን ተገደሉ፡፡ቀደም ብሎ በ1928 ዓ.ም. የሞሶሎኒ ጦር ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ የኢትዮጵያን ምእመናን ወደሳቱን ጐተራ ለማስገባት ለርግማ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ የአዝመራ ጊዜ የሆነላት መስሏት ነበር፡፡

በዚህም ተስፋ መሠረት የኢጣሊያ ጳጳሳት፣ ካርዲናሎች፣ ፓፓውም ለመሶሎኒ ብዙ የጦር መሣሪያ ርዳታ አድርገዋል፡፡ ምእመናኑም በአየቤተ ክርስቲያኑ ለሞሶሎኒ የጦር መሣሪያ መግዣ የሚውል ገንዘብ ወደ ሙዳየ ምጽዋት እንዲያስገቡ በየሰበካው ቂስ ይታዘዙ ነበር፡፡

ሞሶሎኒ ዐዋጁን በሥራ ለማዋል ከርግማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተደረገለት ርዳታ የራያንና የሶማሌን አስላሞች አስነስቶ የብዙ ክርስቲያኖች ደም አፈሰሰ፣ በሴት፣ በሕጻንና በሽማግሌ ሳይቀር የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዐባል በሆነ ሁሉ ላይ ግፍ ተፈጸመ፣ ብዙ ገዳማትንና አድባራትን አፈራረሰ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ጠላት እየተከላከለች ያቈየቻቸውን የታሪክና የእምነት ቅርሶች ዘርፎ ወስዶ ለቫቲካን አስረከበ፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በአስታትስቲክስ ክፍል እንደተመዘገበው 2000 አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጥለው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፡፡ በእየገዳማቱ አያሌ መነኮሳትና ካህናት ለሀገራቸው፣ ለሃይማኖታቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው መሥዋዕት ሆነዋል፡፡

ከጳጳሳቱም አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል በግፈኛው ፋሺሽት ተገድለዋል፡፡ የቀሩት ሁለት ጳጳሳት ብቻ ስለሆኑ በጣሊያን ጊዜ በርከት ያሉ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት በብፁዕ አቡነ አብርሃምና በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተሾመዋል፡፡





በዚህ በ19ኛውና በ20ኛው መቶ ዘመን ፕሮቴስታንቶች እንደአሸን በብዛት ወደ ኤትዮጵያ ገብተው አረማውያንን እያስተማሩ ያጠምቃሉ ተብለው ሲጠበቁ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ዐባላት ወደ እነሱ እምነት በመለወጥ የሚያካሂዱት ዘመቻና የበግ /ምእመናን/ ስርቆት በቀላል የሚገመት አይደለም፡፡

የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለመከፋፈል፣ ዐባላትዋንም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማነበር ድንጋጌ ውጭ ለመቀሰጥ ከአልሆነ በቀር የአንድነት ወንጌል በእነሱ ይሰበካል ማለት አይቻልም፡፡ የጉግና የዘር ልዩነት፣ የፍቅርና የመከባበር ዕጦት የተከሠተው በፕሮቴስታንት ስብከት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠላት ሁለቱን ታላላቅ አባቶች ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስንና ብፁዕ አቡነ ሚካኤልን ቢገድልባትም ከጠላት ወረራ በኋላ እንደገና በ1940 ዓ.ም. ሐምሌ 18 ቀን ካይሮ ላይ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው አምስት ጳጳሳት ተሾሙ ስማቸውም ቀጥሎ ያለው ነው፡፡

1. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የሸዋ ጳጳስ
2. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የጐንደር ጳጳስ
3. ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐረር ጳጳስ
4. ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የወሎጋ ጳጳስ
5. ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የሲዳሞ ጳጳስ

በ1943 ዓ.ም. ጥር 6 ቀን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ፡፡ በዚህ አ[illegible] ቀስ በቀስ በ1951 ዓ.ም. ሰኔ 21 ቀን የአመቤታችን ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን በሚከበርበት ዕለት ካ[illegible] ላይ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው በመሾም 17 ኤጲስ ቆጳሳትንና ሊ[illegible] ጳጳሳትን ሾሙ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የስብከተ ወንጌል ማ?በር አቋቍመው ከቅድስት ሥላሴ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤትና ከቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት ተመርቀው በሰለጠኑ መምህራን በመታገዝ ስብከተ ወንጌልን በመላ ኢትዮጵያ አዳረሱ። በመንግሥት ሬዲዮ ጭምር ስብከተ ወንጌል ለሕዝበ ኢትዮጵያ እንዲተላለፍም አደረጉ፤ ከዚህም ሌላ በዘመናቸው ቤና ቤተ ክርስቲያንና ተክለ ሃይማኖት የተባሉ ጋዜጦች አቋቍመው በጋዜጣና በመጽሔት ጭምር የሃይማኖተ ወንጌል ትምህርት ይሰጥ ነበር፤ "ፈለገ ሕይወት" የተሰኘ የትምህርት መምሪያም አቋቍመው ብሔራዊውንና መንፈሳዊውን የአብነት ትምህርት አስፋፉ። የሰንበት ት/ቤትም ተቋቋመ በተለይ ለስብከተ ወንጌሉ ማስፋፊያ የሚሆን የገቢ ምንጭ ለማግኘት የሚከራዩ አያሌ ሕንጻዎችንና ቪላ ቤቶችን አሠሩ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቤተ ክርስቲያኑዋን በሊቀ ጳጳስና 9 ዓመት በፓትርያርክነት 12 ዓመት ከመሩ በኋላ ጥቅምት 2 ቀን 1963 ዓ.ም. ስለ አረፉ፤ እንደራሴያቸው የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ.ም. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደችበት ቀን ሁለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው በአዲስ አበባ መንበረ ጳጳሳት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በኢትዮጵያ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ተሾሙ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም በዘመናቸው የስብከተ ወንጌል ድርጅት የሰበካ ጉባኤ አቋቍመው የቤተ ክርስቲያኑዋን አስተዳደር አቃኑ፤ ስብከተ ወንጌልን አስፋፉ፤ የሰንበት ት/ቤትንም አደራጁ፤ ይልቁንም በደርግ መንግሥት ቤተ ክርስቲያናችን ሀብቷንና ንብረቷን ስትቀማ በምዓኔ ሀብት የደረሰላትና ከመዘጋት ያዳናት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ያቋቋሙት የሰበካ ጉባኤ ነው። በዘመናቸው የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን፤ የካህናት ማሠልጠኛዎች ተቋቍመዋል። ቅዱስነታቸው ዘጠኝ ኤጲስ ቆጳሳት ሾመዋል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቤተ ክርስቲያኑዋን በእንደራሴነት 10 ዓመት፤ በፓትርያርክነት 5 ዓመት በድምሩ 15 ዓመት ከመሩ በኋላ በ1968 ዓ.ም. የካቲት 9 ቀን የደርግ መንግሥት ያለ ፍትሕ በግፍዕ ስለአሠራቸው የወላይታ ሐዋርያ የነበሩት አባ መልአከ ወልደ ሚካኤል ሰኔ 30 ቀን 1968 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ምእመናንና ካህናት ተመርጠው ሐምሌ 11 ቀን 1968 ዓ.ም. አሑድ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የኤጲስ ቆጳስነት ሥርዐተ ሢመት ተፈጽሞላቸው ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተባሉ። ነሐሴ 23 ቀን 1968 ዓ.ም. እሑድ የኢትዮጵያ ሦስተኛ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ፤

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ከተሾሙ በኋላ በተከታታይ ሁለት የሰባኤ ዓመታት 49 ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት ሾመዋል። በደርግ የተወረሱትን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅን የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕንፃዎችንና ቪላ ቤቶች አስመልሰዋል፤ የከሣቴ ብርሃን አባ ሰላማን ኮሌጅ አቋቍመዋል፤ የቅዱስ ጳውሎስን ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ወደ ኮሌጅ ደረጃ ከፍ አድርገዋል፤ የቅድስት ሥላሴን መንፈሳዊ ኮሌጅ ዩንቨርሲቲ ለማድረግ የሕንፃውን መሠረት ድንጋይ ባርከው ተክለዋል።

የሕንጻውም ሥራ ተጀምሮዋል። የምስካየ ኅዙናን መድኀኔዓለም መንፈሳዊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና ኮሌጅ ተከፍቷል። በቅዱስ ያሬድ ስም በአዲስ አበባ በቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲሠራ የመሠረት ድንጋይ አኑረዋል። በደብረ ኀይል ቅዱስ ራጉኤል፤ በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል፤ በመንበረ ጳጳሳት ቅድስት ሥላሴ፤ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳውያንና ዘመናውያን 1ኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተሠርተው ሥራቸውን ጀምረዋል። የአብነት ትምህርት ማስመስከሪያዎች የተጐት ብሔራውያን ዩኒቨርሲቲዎችና ት/ቤቶች ከፍተኛ በጀት ተመድቦላቸው ተጠናክረዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሦስተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ከተሾሙ በኋላ በተከታታይ ዓመታት 28 ኤጲስ ቆጳሳትንና ሊቃነ ጳጳሳትን ሾመዋል። የቤተ ክርስቲያኒቱን ሐዋርያት በመላ ኢትዮጵያ በዓመት ሁለት ጊዜ እየላኩና እያዘመቱ የሰበካ ጉባኤ ስብከተ ወንጌል፤ የሰንበት ት/ቤት ብሔራዊውና መንፈሳዊው የአብነት ት/ቤት እንዲጠናከር፤ ልማት እንዲለማ፤ የካህናት ማሠልጠኛዎች እንዲደራጁ ከሁሉም የበለጠ ጥረት አድርገው ተሳክቶላቸዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያኑዋን 12 ዓመት በፓትርያርክነት መርተው ግንቦት 28 ቀን 80 ዓ.ም. ስለአረፉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ነሐሴ 29 ቀን 1980 ዓ.ም. አራተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ። አቡነ መርቆሬዎስ 6 ኤጲስ ቆጳሳት ሾመዋል። አቡነ መርቆሬዎስ ሦስት ዓመት ቤተ ክርስቲያኑዋን ከመሩ በኋላ ነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓ.ም. በሕማም ምክንያት ሥልጣናቸውን ለቅዱስ ሲኖዶስ ስለአስረከቡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓ.ም. 5ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው በመንበረ ጳጳሳት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተሾሙ።

www.ethiopianorthodox.org

በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ት/ቤት ለማቋቋም የመሠረት ድንጋይ እየተቀመጠ ነው። በቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተከፍቶአል።

በቅዱስነታቸው ዘመን በመንበረ ፓትርያርክ ሕንጻ መንበረ ፓትርያርክን ጨምሮ ሰባት ሕንጻዎች ተገንብተዋል። በተለይ በኤድስ ቫይረስ በሽታ ?ብረተሰቡ ስለተጐዳ በማስተማሩም ሆነ በማጽናናቱ፣ በመንከባከቡም ሆነ በመርዳቱ መርሐ ግብር ፈጥና የደረሰችለት ይቺ ቤተ ክርስቲያን ናት።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ግንባር ቀደም ሐዋርያነት በተከታዮቻቸው ሊቃነ ጳጳሳት ሊቃውንትና መምህራን አስተማሪነት በአየሀገረ ስብከቱ በመዘዋወር ጥልቅ ትምህርት ስለተሰጠ የኤድስ ቫይረስ በሽታ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ጋብ ብሏል።

በቅዱስነታቸው አመራር ሰጪነት በአየሀገረ ስብከቱ አዳዲስ ገዳማት ተቋቁመዋል። የቀድሞዎቹም ተጠናክረዋል። በአዲስ አበባ በሌሎችም የክልልና የዞን ከተሞች በገጠርም ሳይቀር ብዛት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት በዘመናዊ ፕላንና ሕንፃ ተሠርተው ተመርቀዋል፤ በመሠራት ላይ ያሉም አሉ። አዳዲስ አህጉረ ስብከትና አብያተ ክርስቲያናትም በሀገር ውስጥና በውጭ አገር ተተክለዋል።

የአረጋውያን መጦሪያና የሕጻናት ማሳደጊያ ድርጅቶችም በጠንካራ ሁኔታ ተቋቁመው በአየሀገረ ስብከቱ ያሉ ብዙ የሙት ልጆች ያድጉበታል። ይማሩበታል። በድርሰትና በመጻሕፍትም ሕትመት በኩል አዳዲስ መጻሕፍት በሊቃውንት ጉባኤ ተዘጋጅተውና ታትመው ለማስተማሪያ ውለዋል፤ ብዙ መጻሕፍትም ከግዕዝ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው ታትመዋል፤ ከሁሉም በላይ 81 ቍጥር ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በሊቃውንት ከግዕዝ፣ ከዕርዕ፣ ከዕብራይስጥ ቋንቋዎች ተገናዝቦና ትርጉሙ ተስተካክሎ ታትሞዋል። በልማትም በኩል ብዙ ሥራ ተሠርቶዋል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን አማካይነት ውሀ ለሌላቸው ብዙ የውሃ ጉድጓድና የመስኖ ውሀ አስገኝታለች፣ የንብ ርባታ፣ የከብት ርባታ፣ የሽመና ሥራ የሳጅ አንዱስትሪዎች በማቋቋም ?ብረተሰቡን ትረዳለች፤ በበሽታ፣ በጦርነት፣ በጉርፍ ማጥለቅለቅ አደጋ ለደረሰባቸው ሁሉ በመልሶ ማቋቋሙ ርዳታ ግንባር ቀደም ናት።

በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያናችን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ክህነት የምትሰጠው መንፈሳዊና ማ?በራዊ አገልግሎት ከምንጊዜውም የላቀ ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ስደተኞችን በተመለከተ በሰጡት ዓለም ዐቀፍ አገልግሎት ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን የናንሰን መዳልያ ሽልማት አግኝተዋል። በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን በውጭው ዓለም 8፣ በሀገር ውስጥ 40 በድምሩ 48 አህጉረ ስብከት፣ እነዚህን አህጉረ ስብከት የሚመሩ 60 ሊቃነ ጳጳሳት አሉዋት።

ወደፊት ቤተ ክርስቲያናችን በሀገሪቱ ዙኖች ልክ ሊቃነ ጳጳሳትንና በወረዳዎቹ ልክ ቆሞሳትን በመሪነት ለመመደብ ዕቅድ እንዳላት ታውቋል።

በእነዚህ አህጉረ ስብከት ሥር የሚተዳደሩ 40ሺሕ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት፣ 500,000 ካህናት፣ 45 ሚሊዮን ምእመናን አሉአት። ቤተ ክርስቲያኒቱ ይህን ያህል የሃይማኖት መሪዎች፣ የካህናትና ምእመናን የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ብዛት ያላት ታላቅ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መሆንዋ ታውቆ በአሁኑ ጊዜ ያሉት መሪዋ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያን ምክር ቤት ?ሬዝደንት ሆነዋል። በቅዱስነታቸው ዘመነ ፓትርያርክነት በ?? ፍጻሜና በ?? ዋዜማ ላይ ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ሃይማኖታቸው በሰማዕትነት ለተሠዉት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የቅዱስነት መዓርግ ሰጥቶአል





ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታምነውና የምታስተምረው የክርስትና እምነትና ሥርዐተ አምልኮ ቀጥሎ ያለው ነው።

1. ሀልዎተ እግዚአብሔር /የእግዚአብሔር መኖር/

ስሙና የስሙ ትርጉም
ፈጣሪነቱ
ጌትነቱ /የባሕርይ/
አምላክነቱ
ንጉሥነቱ /የባሕርይ/
ሁሉን የያዘ፣ ሁሉን የጨበጠ መሆኑ
ሁሉን የጀመረ፣ ሁሉንም የጨረሰ መሆኑ
ዘለዓለማዊነቱ
ሁሉን ቻይነቱ
በዓለም ምልዓቱ
ሁሉን ዐዋቂነቱ /የባሕርይ/
ጥበበኛነቱ /የባሕርይ/
ሕያውነቱ
ኀያልነቱ /የባሕርይ/
ረቂቅነቱ /የማይታይ መሆኑ/
መሐሪነቱ /ሁሉን ይቅር ባይ/
ቅዱስነቱ /የባሕርይ/
በእውነት የሚገዛና የሚፈርድ መሆኑ /ፈታሒ በጽድቅ ኰናኒ በርትዕ/
የሰው ወዳጅ መሆኑ /መፍቀሬ ሰብእ/
ትዕግሥተኛነቱ
መምህርነቱ /የባሕርይ/
ብርሃንነቱ /የባሕርይ/
አዳኝነቱ
መጋቢነቱ
ጧባቂነቱ
ረዳትነቱ
ባለጸጋነቱ /የባሕርይ/
አባትነቱ /የባሕርይ/
ይህን የመሰለው የባሕርይ ግብሩ እየተተነተነ

2 ሥነ ፍጥረት ከእሑድ እስከ ዐርብ ሰማይንና በሰማይ የሚኖሩትን፣ ምድርንና በምድር የሚኖሩትን ባሕርንና በባሕር የሚኖሩትን ፍጥረታት ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር መሆኑን በመንገር የፍጥረቱን ሥርዐት በመተንተን ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች።

3 5 አዕማደ ምሥጢር

- ምሥጢረ ሥላሴ /የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር/
- ምሥጢረ ሥጋዌ /ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ሰው እንደሆነ/
- ምሥጢረ ጥምቀት /ውሀው ተለውጦ ማየ ገቦ የሚሆንበት ምሥጢር/
- ምሥጢረ ቍርባን /?ብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፣ ደመ ወልደ እግዚአብሔር የሚሆንበት ምሥጢረ ሃይማኖት/
- ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን /ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚነሡበት ምሥጢር በትንተናበየደረጃው ትምህርት ይሰጣል፣ ይታመናል።

www.ethiopianorthodox.org

4. ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፡-
   - ምሥጢረ ጥምቀት ከነሥርዐቱ
   - ምሥጢረ ሜሮን ከነሥርዐቱ
   - ምሥጢረ ቍርባን ከነሥርዐቱ
   - ምሥጢረ ንስሐ ከነሥርዐቱ
   - ምሥጢረ ተክሊል ከነሥርዐቱ
   - ምሥጢረ ክህነት ከነሥርዐቱ
   - ምሥጢረ ቀንዲል ከነሥርዐቱ በየደረጃው በትንተና ትምህርት ይሰጣል፡፡ ይታመናል፤ በተግባር ይፈጸማል፡፡

5. ነገረ ማርያም፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ታሪክና ክብር፣ ንጽሕናና ቅድስና፣ ድንግልናና ምርጫ፣ ተራዳኢነትና አማላጅነት በሰፊው በትምህርት ይሰጣል፤ ይታመናል፡፡

6. ክብረ ቅዱሳን፡-
   - ክብረ መላእክት /የመላእክት ክብር፣ ተራዳኢነትና አማላጅነት/
   - ክብረ ነቢያት /የነቢያት ትንቢትና ክብር/
   - ክብረ ሐዋርያት /የሐዋርያት ክብር ትምህርት፣ ተራዳኢነትና አማላጅነት/
   - ክብረ ሰማዕታት /የሰማዕታት ታሪክና ክብር፣ ተጋድሎና ቃል ኪዳን/
   - ክብረ ጻድቃን /የጻድቃን ታሪክና ክብር ቃል ኪዳንና አማላጅነት/

7. ቤተ ክርስቲያን እንዲት መሆኑዋ፣ ቅድስት መሆንዋ፣ ከሁሉ በላይ የሐዋርያት ጉባኤ መሆንዋ በትንተና ትምህርት ይሰጣል ይታመናል፤ ስለ ሥርዐቷም በተግባር ይነገራል፣

8. ስለ ጽላትና ታቦት ከእነ ሥርዐቱ ትምህርት ይሰጣል፡፡ ይታመናል፡፡

9. ስለ ሥዕል ያለው ሥርዐት ይነገራል፤ ይታመናል፡፡

10. ስለ መስቀል ያለው ሥርዐት ትምህርት ይሰጣል፤ ይታመናል፡፡





# ምዕራፍ 2

## የአጽዋማት ሥርዓትና የበዓላት አከባበር

### 1. አጽዋማት፡-

### ክፍል 1

ጾም ለተወሰነ ሰዓት ከሁሉም ምግብ መከልከል ሁሉንም ምግብ መተው ነው፣ ለተወሰኑ ቀናት ማለት የጾሙ ቀናት እስኪያልፍ ድረስ ከተወሰኑ ምግቦች መከልከል የተወሰኑ ምግቦችን መተው ነው፣ ይኸውም ጥሉላትን ፈጽሞ መተው ሰውነትን ከመብልና ከመጠጥ መከልከል መጠበቅ ነው፡፡ ጾም ከጥሉላት መከልከል ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆችን ከሚጐዳ ነገር ሁሉ መከልከልንና ለሌሎች መልካም ሥራ መሥራትንም ይጨምራል፡፡

በማንኛውም የሃይማኖት ሥርዓት ጾም አለ፤ የአፈጻጸሙ ሥርዓት ግን የተለያየ ሁኖ ይታያል፤ ለምሳሌ ያህልም ዕብራውያን ሲጾሙ ውለው ማታ ጥሉላት ይመገባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የክርስትናው እምነት ተከታይ እንደእኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ሲጾሙ ውለው ሰዓት ሲደርስ እህልና ውሃ ብቻ ይቀምሳሉ እንጂ የጾሙ ወር ወይም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ጥሉላት ፈጽሞ ክልክል ነው፤

የአጽዋማት ሥርዓት ሲባል ጾም እንዴት እንደሚገባና እንዴት እንደሚወጣ፣ እንዴትና ለምን እንደሚጾም ለይቶ ማወቅና እንደ ሥርዓቱ መፈጸምን የሚያመለክት ነው፤

የጾምን አላማና ጥቅም በሚመለከት የሸዋ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው "የበዓላትና የአጽዋማት ቀኖና" በሚል ርእስ እንደሚከተለው ገልጠውታል፡፡ "ጾም /ጦም/ ማለት ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል መወሰን ማለት ነው፡፡ ወይም ለሰውነት የሚያምረውንና የሚያስጐመጅውን ነገር መተው ማለት ነው፡፡ ጾም ከሃይማኖት ጋር ዘለዓለማዊ ዝምድና ስላለው ሃይማኖት ባለበት ቦታ ሁሉ ጾም አለ፡፡ ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ጾም ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ወራት እህልና ውሃ በአፋቸው አይገባም ነበር፡፡ /ዘፀ፡34፡28/ በጎጢአት ብዛት የታዘዘው የእግዚአብሔር መዓት የሚመለሰው ሕዝቡ በጾም ሲለምኑትና ሲማልዱት ነበር፡፡ /ዮናስ 2፣7-10/

"በሐዲስ ኪዳንም ጾም ሰው ሠራሽ ሕግ ሳይሆን ራሱ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሥራ መጀመሪያ አድርጎ የሠራው ሕግ ነው፡፡(ማቴ 4፣2፤ ሉቃ.4፣2) ይህም ብቻ ሳይሆን በቁራኝነት አብሮ የሚኖር መንፈሰ ርኩስ ሰይጣን እንኳ በጾም የሚወገድ መሆኑን መድኀኒታችን ተናግሮአል፡፡ (ማቴ 17፣21፤ ማር.9፣2) ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ የታዘዙ ሐዋርያትም በየጊዜው ከመንፈስ ቅዱስ ትእዛዝ የሚቀበሉት በጾምና በጸሎት ላይ እንዳሉ ነበር፡፡ (የሐ.ሥራ 13፣2) ለስብከተ ወንጌል የሚያገለግሉ ዲያቆናትና ቀሳውስትም የሚሾሙት በጾምና በጸሎት ነበር፡፡ (የሐ.ሥራ 13፣3፤ 4፣23 ) እነቆርኔሌዎስ ያላሰቡትን ያዩና ያገኙ በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ማልደው ነው፡፡ (የሐ.ሥራ 10፣30)

"የጾም ሃይማኖታዊ ትርጉም ፈጣሪን መለመኛ ከኀጢአት ቍራኛ መላቀቂያ መሣሪያ ስለሆነ በጾም ወራት ላምሮት ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመንፈሳዊ ኀይል ተቃራኒ የሆነ ሥጋዊ ፍትወትን የሚያበረታቱ የእልኮል መጠጦችን፣ ሥጋንና ቅቤን፣ ወተትንና እንቁላልን ማራቅ ታዟል፡፡ ከመባልዕትና ከሌላው ደስታ ሁሉ ጋር ባልና ሚስት በምንጣፍ በአልጋ አይገናኙም፡፡ (1ቆሮ.7፣5) ጾም ከትምህርተ ሐዋርያትና በሊቃውንትም ዘንድ ሲሰበክ ኑሯል፡፡ ?ነዳያንን ለመመገብ የሚጾም ንዑድ ነው፤ ክቡር ነው፡፡? እንደተባለ ጦመኛው ለምሳው ወይም ለራቱ ያለውን ወጭ ነዳያን እንዲረዱበት ለድኩማን መርጃ ድርጅት ወይም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለሚገኙ ነዳያን መስጠት ጾሙን የበለጠ ክርስቲያናዊ ያደርገዋል፡፡

"ጾም የታሪክ ድርጊቶችን እያስታወሱ ከኀጢአት ለመንጻት ስለራሱ የታሰበውን ለነዳያን በመስጠት የሚጾም መሆኑን ተረድተናል፡፡ ጾም ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም፤ ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም ይጾማል፤ ‹ለሚያሳድዱህ ጹምላቸው› እንደተባለ (ዲድ፡1፣3፤) በደዌ ዳኛ በአልጋ ቍራኛ የተያዙትን፣ ችግርኮና በስደት ያሉትንም በጾም ወራት ማስታወስና መጸለይ ይገባል፡፡ በጾም ወራት ከመባልዕት ብቻ ሳይሆን ዐይን ክፉ ከማየት፣ አንደበት ክፉ ከመናገር፣ ጆሮ ክፉ ከመስማት መቆጠብ ያስፈልጋል ተጽፎአል፡፡ "ይጹም ዐይን፣ ይጹም ልሳን፣ እዝንኒ ይጹም እምሰሚዐ ኀሡም በተፋቅሮ" ( ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፩ )

በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ባህልና ትውፊት ውስጥ ያሉ የምዕራብም ሆኑ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከሐዋርያት የወረሱት የጾም ሕግና ሥርዐት አላቸው፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ከመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ ስለሆነች ይህ የጾም ሕግና ሥርዓት አላት፡፡

በሕጓም መሠረት ሰባት የጾም ወራት አሏት፡፡
እነርሱም፡-

1. ዐቢይ ጾም፣
2. ጾመ ሐዋርያት፣
3. ጾመ ፍልሰታ፣
4. ጾመ ሐዋርያት፣
5. ጾመ ገሃድ፣
6. ጾመ ነነዌ፣
7. ጾመ ድኅነት ናቸው፡፡

ከእነርሱም የመጀመሪያው ጾም፣ ዐቢይ ጾም ወይም ሁዳዴ ጌታ ከተጠመቀ በኋላ የጦመው የአርባ ቀን ጦም ነው፡፡ (ማቴ፡4፣1) ምእመናን ጌታቸው ያደረገውን ምሳሌ ተከትለው ይጦሙታል፡፡ ዐቢይ ጾም ስምንት ሳምንታት (55 ቀኖች) አሉት፡፡ ከእነዚህም ቀኖች ውስጥ ሰባት ቅዳሜ ስምንት እሑድ ይገኛሉ፡፡ ዐሥራ አምስት ቀን ማለት ነው፡፡ ከጥሉላት እንጂ ከእህልና ከውሃ ስለማይጦም የጦሙ ወራት አርባ ቀን ብቻ ነው፡፡ ይህም በጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን የነበረ ሥርዐት ነው፡፡ ለምሳሌ በ 384 ገደማ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ከአስፓኝ ወደ ኢየሩሳሌም ረዥም ጉዞ የሄደችው (Egeria) ኤጌሪያ የተባለችው ሴት የተሳላሚ ጉዞ በሚለው መጽሐፏ (Peregrinatioed Loca sancta) እንደገመገችና የጥንት ክርስቲያኖችም በዚህ አቁጣጠር ሲቈጥሩ ማየታን ጽፋለች፤ የቆጵሮሱ ኤጲስ ቆጶስ ኤጲፋንዮስም በዚህ አቁጣጠር ይቈጥር ነበር ፡፡ (ፒ.ጂ.42 ገፅ 828) ሌሎች ደግሞ የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ሳምንት ለይተው ይቈጥራሉ፡፡ ለምሳሌም የመጀመሪያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል ይባላል፡፡ ሕርቃል /ኤራቅሊዮስ/ የቢዛንታይን ንጉሥ ነበር፡፡ (714 ዓ.ም.) ይህ ሳምንት በስሙ የተጠራበት ምክንያት አለው፤ በዘመኑ ፋርሶች ኢየሩሳሌምን ወርረው የጌታን መስቀል ማርከው ወስደው ነበር፡፡ እርሱ ወደፋርስ ዘምቶ መስቀሉን ከእነርሱ ነጥቆ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶአል፡፡ በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች ደስ ብሎአቸው ለስሙ መታሰቢያ ይህን የጾም ሳምንት በቀኖና ውስጥ አስገቡለት እየተባለ ይነገራል፡፡ ግሪኮች ግን ጾመ ሕርቃል የሚባለውን ነገር አያውቁም፤ በዚህ ሳምንት ከእንቁላል፣ ከአይብና ከዓሣ በቀር ሥጋ አይበላም ክልክል ነው፡፡ ጾም መሆኑንም ይናገራሉ፤ ከላይ የተጠቀሱትን መባልዕት መብላታቸውም በተድላ በደስታ የሰነበተ ስውነታቸው ወዲያው በጾም ሲደርቅ በሽታ እንዳያመጣባቸው ለጥንቃቄ ነው ይላሉ፡፡ የሳምንቱንም ስም "የአይብ ሳምንት ወይም ነጭ ጾም " ይሉታል፡፡

የመጨረሻው ሳምንት ሕማማት ነው፤ ሐዋርያት የጌታችን መከራ መስቀል እያሰቡ የጦሙት ነው ይላሉ፤ ያም ሆነ ይህ ሁሉም ከዐቢይ ጾም ጋር እንደ መርገፍና እንደ እጀታ ስለተያያዘ ከዐቢይ ጾም ይቈጠራል፡፡ ዐቢይ ጾም መባሉም የጌታ ጾም ስለሆነ፣ ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎች (አርእስተ ኃጣውእ ) ድል የተነሱበት፣ ድል የሚነሱበት ስለሆነ ነው፤ በሕዝቡም ዘንድ ሁዳዴ ይባላል፡፡ ሁዳዴ ማለት የመንግሥት መሬት የመንግሥት ርስት ማለት ነው፡፡ የመንግሥት ሁዳድ በሚታረስበት ጊዜ፣ አዝመራው በሚሰበሰብበት ጊዜ ልጅ አዋቂ ሳይባል የመንግሥቱ ዜጋ ሁሉ ለሥራ ታጥቆ እንደሚነሣ፤ ይህንም የጌታን ጾም የጌታን ሁዳድ የክርስቶስ ዜጎች የሆኑ ምእመናን ሁሉ ይጾሙታል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችንን መዝሙር ንባቡን ከዜማው አስማምቶና አጠናቅሮ የተናገረው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጾመ ድኅው በሁዳዴ ለሚገኙት እሑዶች ሁሉ የተለየ መዝሙር ስለሠራላቸው እያንዳንዱ እሑድ በመዝሙሩ ስም ይጠራል፡፡

"የመጀመሪያው እሑድ፡-
ዘወረደ ይባላል፡፡ በመጽሐፉ መጀመሪያ አምላክ ከሰማይ መውረዱን፣ ሰው መሆኑንና መስቀሉን ስለሚያወሳ ነው፡፡ ሙሴኒም ይሉታል፡፡ ምናልባት ስለሙሴ ሕግና ጾመ ሙሴን ስለሚያነሣ ይሆናል፡፡





"የሁለተኛው እሑድ፡-
ቅድስት ይባላል፡፡ ስለ ዕለተ ሰንበት ቅድስና ስለሚያወሳ ይሆናል፡፡

"የሦስተኛው እሑድ፡-
ምኩራብ ይባላል፡፡ በዚህ ሰንበት ጌታ በመዋዕለ ትምህርቱ በምኩራብ ገብቶ ማስተማሩ ይነገራል፡፡

"ዐራተኛው እሑድ፡-
መዋዕ ነው፡፡ ድውያንን መፈወሱን፣ ዕውራንን ማብራቱን፣ የሚያነሣ መዝሙር ይዘመርበታል፡፡

"አምስተኛው እሑድ፡-
ደብረ ዘይት ይባላል፡፡ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሁኖ ያስተማረው የዳግም ምጽአትን ነገር የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመርበታል፡፡

"ስድስተኛው እሑድ፡-
ገብርኄር ይባላል፡፡ የጌታውን ብር ተቀብሎ ያተረፈበት፣ በጌታውም ፊት ምስጋናን ያገኘው ሰው ታሪክ ይዘመርበታል፡፡

"ሰባተኛው እሑድ፡-
ኒቆዲሞስ ነው፡፡ በሌሊት ወደ ጌታ እየመጣ ይማር የነበረውን የኒቆዲሞስን ታሪክ የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመርበታል፡፡

"ስምንተኛው እሑድ፡-
ሆሣዕና ነው፡፡ ጌታ በአሕያ ውርንጭላ ሆኖ ሆሣዕና በአርያም እየተባለ ወደ ቤተ መቅደስ የገባበት ዕለት መታሰቢያ ነው፡፡ ከሠርክ ሆሣዕና እስከ ትንሣኤ ያለው ሰባት ቀን ሕማማት ይባላል፡፡ በእነዚህ ቀኖች ውስጥ ብዙ አዝማደ መባልዕት አይበሉም፡፡ ስግደት ይሰገዳል፡፡ የጌታን መከራና ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት፣ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከድርሳናት ተወጣጥተው በግብረ ሕማማት ይነበባሉ፡፡ አዳም ከፈጣሪው ተጣልቶ የኖረውን የጨለማና የመከራ ዘመን በማስታወስ መንበረ ታቦቱ በጥቁር ልብስ ይሸፈናል፡፡ ልብሰ ተክህኖውም ጥቋቁር ነው፡፡

"ሐሙስ፡-
ጸሎተ ሐሙስ ይባላል፡፡ ጌታ በፍጹም ትሕትና የደቀመዛሙርቱን እግር ያጠበበትና ከእነርሱም ጋር ግብር ያገባበት ምሥጢረ ቍርባንን ያሳየበት ዕለት ነው፡፡ "ፈረንጆች" ዕለቱን "Monday፣ Thursday ወይም " the last supper" ይሉታል፡፡ በዚህ ዕለት በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዐት የግብረ ሕማማቱ መጽሐፍ እንደሚያዘው ቅዳሴ ይቀደሳል፡፡ ከቅዳሴው ቀደም ብሎ ቋሱ ውሀውን በብርት አድርጎ በጌታ አምሳል የምእመናንን እግር ያጥባል፡፡ ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ምእመናኑ ወደየቤታቸው ሄደው ለበዓሉ የተዘጋጀውን ዳቦና ጉልባን ይበላሉ፡፡ ለትንሣኤ የተዘጋጀውም ጠላ የሚቀመሰውም የዚያ ዕለት ነው፡፡ ስለ ሕፅበተ እግር ካነሣን ዘንድ በሌሎች አኀት አብያተ ክርስቲያናት የሚታጠቡት በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አምሳል አሥራ ሁለት ሰዎች ናቸው፡፡ በእኛ ግን በቤተ ክርስቲያናት ያሉ ሁሉ ሴትም ሆነ ወንድ ይታጠባሉ፡፡ ነገር ግን አሠራራችን ምሳሌ ስለሚያጥረው እኛም እንደነርሱ አሥራ ሁለት ሰዎችን ብናጥብ የሐዋርያት ምሳሌ ነው፡፡
ከጸሎተ ሐሙስ በበነጋው ዓርብ የስቅለቱ መታሰቢያ ዕለት አኅበር ተሠርቶ ለስቅለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሲነበቡ ይዋላል፡፡ ስግደቱም ከሰሞኑ ሁሉ የበለጠ ነው፡፡ ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን ወደ ቋሱ እየቀረበ በሰሙነ ሕማማት ውስጥ የሠራውን ኀጢአት ይናዘዛል፡፡ ቋሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ተጨማሪ ስግደት ይሰጣል፡፡ በአሥራ ሁለት ሰዓት ሠርሖተ ሕዝብ ይሆናል፡፡ ሁለት ቀን የሚያከፍሉ እህል ውሃ ሳይቀምሱ ያድራሉ፡፡ የማያከፍሉ ግን ከሐሙስ የተረፈውን ጉልባንና ዳቦ ይላክኩታል፡፡



www.ethiopianorthodox.org

"ቅዳሜ ጠዋት ምእመናኑና ካህናቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሰበሰባሉ፡፡ የጠዋቱ ጸሎት ሲፈጸም ‹ገብረ ሰላመ በመስቀሉ› ክርስቶስ በመስቀሉ ሰላምን መሠረተ፡፡ ሰላምን ፈጠረ፡፡ የምሥራች እየተባለ በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰበ ሁሉ ቁጠማ ይሰጣል፡፡ የምሥራች ምልክት ነው፡፡ ምእመናኑም እየሰነጠቁ በራሳቸው ያስሩታል፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ላልመጡትም ካህናት በየበኩላቸው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፣ መስቀልና ቃጭል ይዘው፣ ቁጠማውን የምሥራች እያሉ ይሰጣሉ፡፡ ምእመናኑም ገንዘብ ያለው፣ ገንዘብ ይሰጣል፡፡ ገንዘብ የሌለው ደግሞ ለጧፍ የሚሆን "ማግ" ልቃቂት ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከማዕዶት እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉትን ዕለታት ተከፋፍለው ይዘው ለሰበካቸው ካህናት ምግብ እያዘጋጁ ያመጣሉ፡፡ በጉንደርና በላስታ ሁሉም በአንድ ላይ በደጀ ሰላም ይመገባሉ፡፡ ወይንም ምእመኑ ካህናቱን በቤቱ ይጋብዛል፡፡ በአዲስ አበባና በሸዋ ግን ወደየንስሐ አባታቸው ቤት ምግብ እያዘጋጁ ይወስዳሉ፡፡ የአክፋይ ይሉታል፡፡ በዚያ ግን ገብረ ሰላመ ነው የሚባለው፡፡ ይህች ቅዳሜ፡- "ሰንበት ዓባይ" ትባላለች የፈተኛዪቱ ቅዳሜ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ከሥራው ያረፈባት ዕለት እንደሆነች፣ ይህች ደግሞ የሦስት ዓመት ከሦስት ወር የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ፈጽሞ በከርሠ መቃብር ዐርፎ የዋለባት ዕለት ናት፡፡ ሁለተኛም ይህች ዕለት ‹ስዑር ቅዳሜ› ትባላለች፡፡ ስዑር መባሏም በዓመት አንድ ቀን ስለምትጾም ነው፡፡ በባላገር ግን ‹ስዑር› ያለውን ይዘው ሰሞኑን ምንም ሳይሠሩ ሰንብተው በዚህ ዕለት ይሠራሉ፡፡ "ቅዳሜ ሹር" እንዲሉ ቁጠማው የምሥራች ምልክት መሆኑ ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ዓለም በንፍር ውሀ በተጥለቀለቀ ጊዜ፣ የኖ? መርከብ ማረፊያ አጥታ ስትንሳፈፍ የውሀውን ሁኔታ ለመረዳት ኖ? ርግብን በመርከቡ መስኮት አሾልክ ይለቃታል፡፡ እርስዋም ቁማጠ ባፏ ይዛለት ትመለሳለች፡፡ ኖ? በዚህ ቁጠማ የውሀውን መድረቅ ተረድቶ ተደሰተ፡፡ መርከቡንም ለማሳረፍ ተዘጋጀ፡፡ ቁጠማ ለጥፋት ውሀ መድረቅ የምሥራች መንገሪያ እንደሆነ፣ አሁንም በክርስቶስ ሞት ማየ ሥራዊ፣ ማየ ድምሳሴ ነጢአት፣ ሞተ ነፍስ ከሰው ልጆች ተወገደ፣ የምሥራች ሲባባሉ ምእመናን ቁጠማ ይዘው፣ ቁጠማ አስረው ይታያሉ፡፡ በዚህች ዕለት በአንዳንድ ቦታ ቅዳሴ ይቀደሳል፡፡ በአንዳንድ ቦታ አይቀደስም፡፡ የሚቀድሱት የሚሰጡት መልስ ካማ የተፈጸመው ዓርብ ነው፡፡ ቅዳሴ መኖሩን የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጻፈው የዕለቱ "ክብር ይእቲ" ለማወቅ ይቻላል ይላሉ፡፡ አይቀደስም የሚሉት ደግሞ ምንም እንኳ የምንቀበለው ሥጋ፣ ነፍስ የተለየው፣ መለኮት የተዋሐደው ቢሆንም በትንሣኤ ድል ማድረጉን ከማየታችን በፊት መሥዋዕት አንሠዋም፡፡ ያሬድ የሠራው "ክብር ይእቲ" ቀድሱ የሚል ትእዛዝ የለውም ቅኔ ነው ይላሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በቅዳም ስዑር ቅዳሴ እንዳይቀደስ በቅዱስ ሲኖዶስ ተወስኖአል፡፡

## ለ. ከዐቢይ ጾም ቀጥሎ ሁለተኛው ጾም የሐዋርያት ጾም ነው፡፡ የሰኔ ጾም ይባላል፡፡

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ከመሄዳቸው በፊት የጾሙት ነው፡፡ ምእመናንም እነርሱን ምሳሌ አድርገው ከጸራቅሊጦስ በበነጋው ጀምረው ይጾሙታል፡፡ ይህ ጾም በሕዝቡ ዘንድ የወታደር ጾም ይባላል፡፡ ለስብከተ ወንጌል ዘመቻ የተዘጋጁ ሐዋርያት በጾሙት ተምሳሌት፣ በድሮ ዘመን ወታደሮች ለዘመቻ ሲነሡ ወይም ከዘመቻ ሲመለሱ በተሳተ በተገደፈ ይቅር በለን ለማለት በቀኖና ይጾሙት ነበር ማለት ነው፡፡ ይህ ጾም በመባጃ ሐመር ከፍና ዝቅ ስለሚል የተወሰነ ቀን የለውም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከእርባ ይበልጣል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከሠላሳ ያንሳል፡፡

## ሐ. ሦስተኛው ጾም የፍልሰታ ጾም ነው፡፡ (ጾመ ማርያም) ይባላል፡፡

የፍልሰታ ጾም ከነሐሴ አንድ እስከ አሥራ አምስት ያለው ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን እንደሚተረከው እመቤታችን ያረፈችው በጥር ሃያ አንድ ቀን ነው፡፡ (በሐምሳ ዓ.ም. ገደማ) ሐዋርያት በድኗን ሲቀብሩ ወደ ጌቴሰማኒ ይዘዋት ሲሄዱ አይሁድ በታተኗቸው፡፡ በዚህ ጊዜ መላእክት የእመቤታችንን አስከሬን ወስደው በገነት አኑረውታል፡፡ በስምንተኛው ወር በነሐሴ አስከሬኗን እንደገና ከጌታ ተቀብለው በጸሎትና በምሕላ ቀበሩአት፡፡ በዚህ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ አልነበረም፡፡ በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደ ልጅዋ ተነሥታ ስታርግ፣ ቶማስ ከሀገረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ያገኛታል፡፡ በዚህ ጊዜ ትንሣኤዋን ሌሎች ሐዋርያት አይተው፣ ለእርሱ የቀረበት መስሎት ተናደ፣ ‹ፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ› በፊት የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ፡፡ አሁን ደግሞ የእንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ፡፡ አሁን ደግሞ የእንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀርቼ ነው ብሎ ከደመናው ሊወረወር ታጣው፡፡ በዚህ ጊዜ እመቤታችን ቶማስን አጽናናችው፡፡ ከእርሱ በቀር ትንሣኤዋን ሌላ አንዳላየ ነገረችው፡፡ ለምስክር እንዲሆነውም ሰበኗን ሰጥታው ዐረገች፡፡ ቶማስ ሐዋርያት ወደአሉበት ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ እመቤታችንን እኮ ቀበርናት ብለው ነገሩት፡፡ እርሱም አውቆ፣ ‹ምሥጢሩን ደብቆ ‹ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር?› አላቸው ለማሳየት መቃብር ሲከፍቱ አሣቸ፡፡ በዚህ ጊዜ እመቤታችን ተነሥታ ዐርጋለች ብሎ ሁኔታውን ተረከላቸው፡፡ ለምስክር ይሁንህ ብላ የሰጠችውንም ሰበኗን አሳያቸው፡፡ ሰበኗን ቆራርጠው ለበረከት ተከፋፍለው ወደየሀገረ ስብከታቸው ተበታትነዋል፡፡ በዓመቱ ቶማስ ትንሣኤሽን አይቶ እንዴት እኛ ይቅርብን ብለው ከነሐሴ አንድ ቀን ጀምረው ሰባኤ ዝኩ፡፡ በነሐሴ አሥራ ዐራት ቀን ጌታ እመቤታችንን አምጥቶ እንድትገለጥላቸው አደረገ፡፡ በነሐሴ አሥራ ስድስት ቀን ዕርገቷን አከበሩ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችንን በረከት ለማግኘት ትጾማለች፡፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ጾም በተለይ ሕዋናቱ ያክብሩታል፡፡ በዚህ የአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ የማይጾምና የማይቈርብ የለም፡፡ ብዙ ሰዎች ቤታቸውን እየዘጉ በመቃብር ቤት ሰባኤ ገብተው በጾምና በጸሎት ይሰነብታሉ፡፡

በፍልሰታ ጾም ጊዜ በጠቅላላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለው ሁኔታ ሕዝቡ፣ ልጅ አዋቂ ሳይል የሚያሳየው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ለእመቤታችን የፍቅር ሀገርዋ መሆኑዋን ያመለክታል፡፡ (በሌሎች የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ጾሙ የተከበረ ነው፡፡ ታሪኩ ግን የእመቤታችን ዕረፍታም ትንሣኤዋም በነሐሴ ወር ነው ይላሉ፡፡

## መ. አራተኛው ጾም ጾመ ነቢያት ይባላል፡፡

ከነዳር አሥራ አምስት እስከ ታሕሣሥ ሃያ ስምንት ቀን ያለው ነው፡፡ የጾሙ ወራት አርባ አራት ቀን ነው፡፡ ልደት በታኅሣሥ ሃያ ስምንት ቀን በሚውልበት በዘመነ ዮሐንስ ቅበላው ኅዳር አሥራ ዐራት ነው፡፡ ጾሙ በአሥራ አምስት ይጀመራል፡፡ በሌላው ግን ቅበላው በኅዳር አሥራ አምስት ነው፡፡ ጾሙ በአሥራ ስድስት ይጀመራል፡፡ ይህን ጾም የምንጾመው ነቢያት በየዘመናቸው ስለመሢሕ መምጣት በናፍቆት ይጾሙ ይጸልዩ ስለነበረ፣ የእነርሱን አርአያ ተከትለን የክርስቶስን ልደት ከማክበራችን ቀደም ብለን ይህን ጾም እንድንጾም በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ተሠርቷል፡፡ ይህ ጾም እንደመጨረሻው በመግቢያውም ሊታውንትን የሚያከራክር አንድ አቍባበር አለው፡፡

በአጀማመሩ ላይ /ስንክሥ መንፈቀ ኅዳር/ ስለሚል አንዳንዶቹ ሊታውንት የዚህ ጾም መጀመሪያው አሥራ ስድስተኛው ቀን ነው፡፡ ይኸውም በዘመነ ማቴያስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ ነው፡፡ በዘመነ ዮሐንስ ግን ልደት ወደኋላ መጥቶ በሃያ ስምንት ቀን ስለሚውል ጾሙ በአሥራ አምስት ይጀመራል ይላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ‹አድልዉ ለጾም ነውና› በአራቱም ዓመት ጾሙ አሥራ አምስትን አይለቅም ይላሉ፡፡ በጉቦር ከአደረጉት ግን የሚያከራክርና የሚያጣላ አልነበረም፡፡

## ሠ. አምስተኛው ጾም ገሐድ ነው፡፡ ገሐድ ማለት ለውጥ፣ ልዋጭ ማለት ነው፡፡

ፍቸው ከዘይቤው ጋር አይገናኝም፡፡ ወይም እንደ ዘይቤው "ግልጥ" ማለት ነው፡፡ ይፋ ማለት በገሐድ እንዲሉ በገልጥ በይፋ ሲሉ ገሐድ የጥምቀት ብቻ ነው፡፡ ጥምቀት ረቡዕና ዓርብ በሚውልበት ጊዜ በኋላው የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስ የፍስክ ቀንነታቸው ወደጾምነት ተለውጦ ይጾማሉ፡፡ በእነርሱ ለውጥ ጥምቀት የሚውሉባቸው የጾም ቀናት ( ረቡዕና ዓርብ) የፍስክ ቀን ሁነው ይከበራሉ፡፡ ገሐድ የረቡዕና የዓርብ ለውጥ ነው ብለናል፡፡ ነገር ግን በሌላም ቀን ቢውል የጥምቀት ዋዜማ ይጾማል፡፡ ጥምቀት እሑድ ቢውል ቅዳሜ ጥሉላት አይበላም፡፡ ሰኞ ቢውል እሑድ ጥሉላት አይበላም፡፡ እህልና ውሀ ግን አይጠምም፡፡ አንዳንዶቹ ግን ጥምቀት ሰኞ ሲውል ከቅዳሜና ከእሑድ አዋጥተው ይጾማሉ፡፡ (ከቅዳሜ ስድስት ከእሑድ ሦስት) ጥሉላት በሁለቱም ቀኖች አይቀመስም ይላሉ፡፡ ነገር ግን ገሐድ አንድ ስለሆነ ("ሰላም ዕበል ለዕለተ ጾም ዋሕድ፣ ዘስሙ ገሐድ") ስንክሣር ጥር ዐሥር ቀን፡፡ ሰኞ ሲውል ቅዳሜ ከጥሉላት መጾም በአትል የገባ ልማድ ነው፡፡ ገሐድ ለጥምቀት ብቻ ነው፡፡ በልማድ ግን፣ የልደትንም ዋዜማ ገሐድ እንለዋለን፡፡ ነገር ግን ልደት የሚውልባቸው ረቡዕ ወይም ዓርብ የፍስክ ቀን ሁነው



www.ethiopianorthodox.org

እንዲከበሩ ቢታዘዝም (ፍ፡መ፡) በዋዜማ የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስ ከጾመ ነቢያት ጋር የተያያዙ ስለሆኑ መጾማቸው የግድ ነው፡፡ የማይጾሙ ሰዎች ግን መላውን ጾመ ነቢያት ሲበሉ ቆይተው ዋዜማውን ብቻ ገሐድ ነው ብለው ይጾማሉ፡፡" ሲሉ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አትተዋል፤ ነገር ግን የገሃድ ጾም "ጾመ ድራረ ልደት ወድራረ ጥምቀት ተብሎ በአንቀጸ ጾም የተገለጠ መሆኑን በዚህ ጽሑፍ መደምደሚያ እናሳያለን፡፡

## ረ. ስድስተኛው የነነዌ ጾም ነው፡፡ ይህ ጾም የሦስት ቀን ጾም ነው፡፡

ሰኞ፣ ማክሰኞ ረቡዕ በመባል ሐመር ከፍና ዝቅ ስለሚል ቁጥሩ ከአጽዋማት አዋድያት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በጥር አንዳንድ ጊዜ በየካቲት ይሆናል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን ጾም የወሰኑት የነነዌ ሰዎች በጾምና በጸሎት ከመዐት፣ ከጥፋት እንደዳኑ ምእመናኑም በጾምና በጸሎት ከፈጣሪያቸው ምሕረትና በረከት እንዲያገኙ በማለት ነው፡፡ (ስለሙሉ ታሪኩ ትንቢተ ዮናስን ይመለከቷል ብሉይ ኪዳን)

## ሰ. ሰባተኛውና የመጨረሻው ጾም (ጾመ ድኅነት) ረቡዕና ዓርብ ነው፡፡

ረቡዕና ዓርብ ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ እሑድ ከሚገኙት ረቡዕና ዓርብ በቀር ዓመት እስከ ዓመት ይጾማሉ፡፡ የሚጾመብት ምክንያት አላቸው፡፡

### ሀ. ረቡዕ፡-

የአይሁድ ሽንገላ ወይም ሲንሃጽሪየም ጌታን ዓርብ ዕለት ለመስቀል የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላለፈው ረቡዕ ዕለት ነው ይባላል፡፡ መድኃኔዓለም ለሰው ልጆች ሲል የተወሰነበትን የሞት ውሳኔ ሁልጊዜ በማስታወስ ክርስቲያኖች በዚህ ዕለት እንዲጾሙ ታዘዋል፡፡

### ለ. ዓርብ፡-

እንደሚታወቀው ጌታ የተሰቀለበትና የሞተበት ብዙ ዘመን ሲጠበቅ የነበረ ተስፋ የተፈጸመበት ቅዱስ ዕለት ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን በጾምና በጸሎት እንዲከበር ታዘዋል፡፡ /ፍ.መ/ እነዚህን አጽዋማት ከሰባት ዓመት በላይ ያለ ክርስቲያን ሁሉ እንዲጾማቸው ታዘዋል፡፡ ቅዳሴ የሚቀደሰውም ከእሑድና ከቅዳሜ በቀር በጾም ወራት ከሆነ በዘጠኝ ሰዓት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሌሎች ሳይገባቸው እንደሚሉን ቍርባን ጾም ያስገድፋል ተብሎ አይደለም፡፡ ጌታ ነፍሱን ከሥጋው የለየበትን ሰዓት ተከትሎ የተሠራ ሕግ ነው፡፡ የምንቀበለው ሥጋ ነፍስ የተለየው፣ መለኮት የተዋሐደው ነው፡፡ ካህ ተፈጽሞ ሥጋው ደሙ በይፋ የተሰጠን ጌታ ነፍሱን ከሥጋው ሲለይ ነውና፡፡ በጥንቱ ሥርዐት ግን ካሬም በገዳማትና በታላላቅ አድባራት ይህን ሰዓት በማክበር ከእሑድ ቅዳሜና ከበዓለ ሐምሳ በቀር መሥዋዕት ዘሠርክ ነው፡፡ (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአባ ጎርጎርዮስ ሲቀ ጳጳስ ሰኔ 1974 ዓ.ም. ገጽ 145-156)
ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አባ ጎርጎርዮስ ፡-

### 1.ጾመ ገሐድ፡-

ለጥምቀት እንጂ ለልደት ገሐድ የለውም፡፡ ምክንያቱም ከጾመ ነቢያት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በሚል አትተዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጸ ጾም ገሐድ "ጾመ ድራረ ልደት ወጥምቀት" "የልደትና የጥምቀት ጾም ዋዜማ" ተብሎ ተገልጦአል፡፡ "ሰላም ዕብል ለጾመ ዕለት ዋሕድ ዘስሙ ገሐድ " የሚለውም ጾመ ሁለት ቀን ቢሆንም እንደ አንድ ተቈጥሮ ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ ሁኖ መቈጠሩን የሚያመለክት ነው የሚሉ አሉ፡፡ ስለጾመ ነቢያት አጀማመርም ስንክሣር መንፈቀ ጎዳር በማለቱ ምክንያት አንዳንዶቹ በማቴዎስ፣ በማርቆስ በሉቃስ ልደት በሃያ ዘጠኝ በሚውልበት ጊዜ ጾመ በአሥራ ስድስት ይጀመራል፡፡ በዮሐንስ ልደት ወድኋላ መጥቶ በሃያ ስምንት በሚከበርበት ጊዜ፣ ጾመ ነቢያት በአሥራ አምስት ይጀመራል የሚለው ሊታውንቱን ሲያጋግር የቆየ መሆኑን ተመልክቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥቅምት 17 እና 21 ቀን 1980 ዓ.ም. በአደረገው ስብሰባ ጾመ ነቢያት በአራቱም ዘመናት ማለት በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስና በዮሐንስ ሁልጊዜም ጎዳር 15 ቀን እንዲጀመር፣ የልደት በዓል አከባበርም እንደተለመደው በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ ታኅሣሥ ሃያ ዘጠኝ ቀን እንዲሆን፣ በዮሐንስ ታኅሣሥ ሃያ ስምንት ቀን እንዲከበር ዕለቱ ማክሰኞ ወይም ሐሙስ ቢውል በማግስቱ ሃያ ዘጠኝ ረቡዕ ወይም ዓርብ ቢሆን እንደሚጾምና ውሉም እንደሚቀደስ ወስኖአል፡፡ ውሳኔውንም የቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ሁሉ ሊያከብሩት ይገባል፡፡





ከዚህ ሌላ ስለ አጽዋማት ጉዳይ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡ ግንቦት 7 ቀን 1961 ዓ.ም. በተደረገው ቅዱስ ሲኖዶስ ስለአጽዋማትና በዓላት አከባበር መመሪያ የሚሆነውን ጽሑፍ፡-

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ፣
ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፣
ብፁዕ አቡነ አብርሃም

ክቡር ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት "ጾምስ ጸባሕተ ሥጋ ውእቱ በከመ ምጽዋት ጸባሕተ ንዋይ ይእቲ እንደተባለው ምጽዋት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የገንዘብ ግብር እንደመሆኑ፣ ጾምም ምእመናን ሥጋቸውን ለነፍሳቸው ለማስገዛት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የሰውነት አገልግሎት መሥዋዕት ነውና ምሥጢሩን አውቀው ቢጾሙት ይጠቅማል፡፡

ስለዚህ ለሐዲስ ኪዳን መሠረቱ ብሉይ ኪዳን እንደሆነ፣ ለሐዲስ ኪዳንም አጽዋማት መሠረታቸው አጽዋማተ ብሉይ ናቸው፡፡ የብሉዩን አጽዋማት ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከእርሱም ቀጥሎ የተነሡ ነቢያት ጾመዋል፡፡ በዘመነ ሐዲስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢያትንና ኦሪትን ልሽር አልመጣሁም የሚለውን አዋጅ አጽንቶ አርባ ቀን ጹሞአል፡፡ ሐዋርያትና ሠለስቱ ምእትም የጌታችን ጾም መሠረት በማድረግ ጹመዋል፡፡

እነዚህም ፡-

ሀ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው አርባ ጾም፣
ለ. ረቡዕና ዓርብ፣
ሐ. የልደት ገሐድ፣
መ. የጥምቀት ገሐድ፣
ሠ. ጾመ ነነዌ
ረ. ጾመ ፍልሰታ እነዚህ የተለመዱ አጽዋማት ናቸው፡፡

እነዚህም አጽዋማት በሆስፒታል በጽኑዕ ደዌ ለሚገ ኙ ሕሙማን ሐኪም መድኃኒት አዘላቸው ለሚታከሙ፣ በመምህረ ንስሓቸው አማካይነት ሐኪም ያዘዘላቸውን እየተመገቡ ሊታከሙ ይችላሉ፡፡

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን ስለ አጽዋማት ማሻሻያ ልታወጣ ያሰበችበት ምክንያት ዘመን ያመጣውን ችግር ለማቃለል ቢሆንም እነዚህን አጽዋማት ለመጾም ቦታና ጊዜ ለማይፈቅድላቸው፡-

1. ወሰን ለመጠበቅ በየጠረፉ ለሚገኙ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት፣
2. በአየር፣ በባሕርና በየብስ ለሚጓዙ መንገደኞች፣
3. በየፋብሪካው በሥራ ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች፣
4. ከፍተኛ ጥናት በሚጠይቅ የትምህርት ገበታ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ከጥሉላት ምግብ በቀር ጠዋት ቍርስ ቢበሉ ሻይና ቡና ቢጠጡ ይፈቀዳል፡፡

በዚህም መሠረት በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙ ሊቃነ ጳጳሳት ከባድ ሥራ ለሚሠሩ ሠራተኞች ችግሩን ለያዩ በአስተያየት ማሻሻያ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት አጽዋማት ሌላ፡-

ሀ. ጾመነቢያት /የታህሣሥ ጾም/
ለ. ጾመ ሐዋርያት /የሰኔ ጾም/ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ አጽዋማት እንደ ዐበይት አጽዋማት ስለማይቈጠሩ የጾመ መታሰቢያነት እንዳይረሣ ያህል የነቢያትና የሐዋርያት ጾም ለሕዝቡ ሲባል ካልጾሙ ፋሲካ፣ ካላዘኑ ደስታ የለምና በየአጽዋማቱ መጨረሻ አምስት አምስት ቀን በመጾም የክርስቶስ ልደትና የሐዋርያት በዓል እንዲከበር" ቢደረግ የሚል አስተያየት ቀርቦ ነበር፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ሲኖዶስ ይህን አስተያየት ተመልክቶ ጉዳዩ ካህናቱን ብቻ ሳይሆን ሕዝበ ክርስቲያኑንም በተጥታ የሚመለከት በመሆኑ፣ ይኸው ተጠንቶ የቀረበው ሐሳብ በጋዜጦች፣ በራዲዮና በቴሌቭዥን ከተገለጠ በኋላ ሕዝቡ ይተችበት የመጨረሻውም ውሳኔ የሚደረገው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መምህራንና ካህናት ምእመናኑም አውቀውት አስተያየታቸውና አሳባቸውን ከገለጡበት በኋላ ይሆናል በማለት ተስማምቶ እንደነበር የሚገልጥ ጥናት አለ። (አዲስ ሕይወት ቁጥር 5 ገጽ 32-33 )

ይህ የአጽዋማት ጉዳይ እስከ ዛሬም ድረስ በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ እያነጋገረ ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ ያለፉትን ጥናቶች በመመልከትና የጊዜውንም ትውልድ አመለካከት በማጥናት ተገቢውን የማሻሻያ ውሳኔ ሊሰጥበት እንደሚገባ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል።

# ክፍል 2

## 1. በዓላት

በዓልን የማክበር ሥርዓት የተሠራው በሰው ፈቃድና ትእዛዝ የተሰጠ ሰው ሠራሽ ሥርዓት አይደለም። በእግዚአብሔር ቃል፣ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ የተሰጠ አምላካዊ ሥርዓት ነው፤ ፈጣሪ ኩሉ እግዚአብሔር ከአሐድ እስከ ዓርብ በአሉት ስድስት ዕለታት የመፍጠር ሥራውን ከጨረሰ በኋላ በሰባተኛው ቀን አረፈ፤ የመፍጠር ሥራውን ተወ፤ ሕገ አሪትንም ለሙሴ በሰጠ ጊዜ ይህን ሰባተኛውን ዕለት ሰዎች ሁሉ እንዲያከብሩት አዝዞአል። (ዘፀ.20፣8-11) ይህን መሠረት በማድረግ በተኖና ቤተ ክርስቲያን የተደነገጉ የጌታ ዐበይት በዓላት አሉ። እነርሱም "የጌታ ቀን" የምትባለው ዕለተ እሑድና በዓለ ትስብእት፣ በዓለ ልደት፣ በዓለ ጥምቀት፣ በዓለ ደብረ ታቦር፣ በዓለ ሆሣዕና፣ በዓለ ስቅለት፣ በዓለ ትንሣኤ፣ በዓለ ዕርገትና በዓለ ጰራቅሊጦስ ናቸው፤ ስለ እነዚህና ስለ ሌሎችም በዓላት አከባበር በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ?ብረተሰብአ ዘንድ አከራካሪ፣ በቤተ ክርስቲያን ዘኩልም ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለመስጠት አስቸጋሪ መስሎ እንደሚታይ ገልጠው ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በተባለው መጽሐፋቸው እንደሚከተለው አብራርተው ገልጠዋል።

"በዓላት በልማድ የሚከበሩ ወይም ቁጭ ብሎ መዋልን የወደደ ሰነፍ የፈጠራቸው አይደሉም። ምንጫቸው ሃይማኖት ነው። ከነዚህም ቀዳሚዉ ‹ቀዳም ሰንበት› ናት። የዚች ዕለት ክብር ከአስርቱ ቃላተ ኦሪት በአንዱ ታዝዞአል። ‹የእግዚአብሔር የአምላክህን ሰንበት አክብር› ተብሎ አይሁድ ዕለተ ሰንበትን እንዲያከብሩ የታዘዙት እግዚአብሔር ከሐሩድ እስከ አርብ ሲፈጥር ሰንብቶ ስላረፈ /ሥራ ስላልሠራባት ነው/ ስለ ቀዳም ሰንበት ክብር የአይሁድ ሊቃውንት ብዙ አይነት አተረጓጐም ነበራቸው። ‹አክብር› የሚለውንም ቃል ለእግዚአብሔር እንደሚስማማ አድርገው ለመተርጐም ያላዩት መዝገበ ቃላት የለም። ካህናቱም ሆኑ ሕዝቡ በዚች ዕለተ ሰንበት ስር መማስ ቅጠል መበጠስ ይቅርና የዘረጉትን አያጥፉም፣ ያጠፉትንም አይዘረጉም፣ የዝጉትን አይከፍቱም፣ የከፈቱትን አይዘጉም ነበር። ዜና አይሁድን የጻፈው ፈሪስ አይሁዳዊ የነበረው ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ‹አይሁድ በዕለተ ሰንበት ወደ ሽንት ቤት እንኳን አይሄዱም ነበር› ይላል። ከዚህም ጋር ቤት ቢቃጠል፣ ሰው ቢሞት፣ ጦር ቢመጣ በዕለተ ሰንበት ከሆነ መንተሳተስ ክልክል ነው። ለምሳሌ በመቃብያን ታሪክ እንደሚታወቀው ሰላሳ ሺህ አይሁዳውያን በወራሪ ጦር በአንድ ቀን ያለቁት በዚች በዕለተ ሰንበት ነበር። 1966 ዓ.ም. (በፈረንጆች 1973) ዩም ኪፑር የዳስ በዓል ማለት ነው። ግብጻውያን ያጠቋቸው በበዓሉ ምክንያት ተዘልለው ሳሉ ነው። አይሁድ ብዙ በዓላት አሏቸው። የበዓላቸውም ሕገ ማንኛውንም ሥራ ከመሥራት መወገድ ነው። በሌላው ዓለም ያሉ አረማውያን ደግሞ የራሳቸው በዓላትና የአከባበር ሥርዓቶች አሏቸው። አማልክቶቻቸው ብዙ እንደመሆናቸው መጠን ብዙ በዓላትና የተለያዩ የአከባበር ሥርዓቶች አሏቸው። ለምሳሌ 12 አማልክት የነበሯቸው ዕርዓውያን በዝያው ልክ በዓላት ነበሯቸው አከባበራቸውም እንደ አምልኮታቸው ከፍርሃት የመነጨ እንጂ መጽሐፋዊ ወይም ምሥጢራዊ ስላልሆነ ስለ ሥርዓቱ ብዙ አያስበብትም። በሚኖሩበት አካባቢ አንድ ለውጥ ሲያዩ ብቻ ቱሎ ብለው መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። ነፋስ ሲነፍስ፣ የነፋስ አምላክ /ኢዎሎስ/ ተቆጥቶ ነው። የዐሐይ መቀት ሲያይል የዐሐይ አምላክ /አጵሎስ/ ተቆጥቶ ነው። ባህር ስትታወክ የባሕር አምላክ ፖሊዳን ተቆጥቶ ነው በማለት ካህናተ ጣዖት በዓል ያዘጋጁ መስዋዕት ይሰው ነበር። የበዓል አከባበራቸው ሥራ የማይከለክል ነበር። የቆመውን ቢቆርጡ የተጋደመውን ቢፈልጡ በዓል እንደሻሩ አይቆጥሩትም ነበር። እነዚህ ማለት አይሁድና አረማውያን ወደ ክርስትና በገቡ ጊዜ የቆየውን ልማዳቸውን ለመተው አስቸጋሪ ነገር ገጥሟቸው ነበር።





የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ሐዋርያት ይህ ልማድ መሰናክል እንዳይሆን ሁሉንም እንደዓመሉ ተቀብሏቸው። ከአይሁድ ወደ ክርስትና የተመለሱት የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ በባህላቸው ያደርጉት የነበረውን ከማድረግ አልተከለከሉም። ለምሳሌ በአይሁድነት ሳሉ ቅዳሜን ብቻ ያከብሩ ነበር፤ ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ግን ቅዳሜንም እሑድንም ያከብራሉ። ግዝረትን የመሳሰለውም የብሉይ ኪዳን ትውፊት ከቤተ አይሁድ በተመለሱት ክርስቲያኖች ዘንድ እስከአሁን ይሠራበታል። ከአረማዊነት የተመለሱት ደግሞ እንደዚሁ የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ልማደ አረማውያንን አልተውም። የቅዳሜን በዓልነት አያውቁም፤ ግዝረት የላቸውም።

ሊቃውንቱና መምህራኑ የሕዝቡን የረዥም ዘመን ፍቅረ ጣዖት ለማስተው ስለአቃታቸው በጣዖት ተሠይሞ ይከበር የነበረውን ሁሉ በቅዱሳን ስም እየለወጡ ያከብሩታል። ለምሳሌ በጣዖታዊነት በነበሩበት ጊዜ ‹ፖሲዶን› የሚባለው ጣዖት የባሕር አምላክ ነው ይባል ነበረ። በክርስትና ዘመናቸው ግን ሊቃውንቱ ‹ኒኮላዎስ› የሚባለውን ቅዱስ የባሕር ጠባቂ ብለው በየዓመቱ ያከብሩታል። የመርከበኞች በዓል ነው። ‹ኦሪስ› ወይም ‹ማርስ› የጦር አምላክ ተብሎ ሲመለክ የኖረ ጣዖት ነው፤ በእርሱ ምትክ ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስን የወታደሮች ጠባቂ ብለው በየዓመቱ ያከብሩታል።

በጠቅላላው አረማውያን ለእያንዳንዱ ድርጊት /ፍጥረት/ አምላክ መድበውለት ስለነበር ዛሬ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚከበሩት ቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት የአንዳንድ ነገር ጠባቂዎች እየተባሉ ተሠይመዋል። በአረማውያን የበዓል አከባበር ‹ኢታንሥእ እደዊከ ወእገረከ› የሚል ትእዛዝ ስላልነበረ፤ አሁንም ከአረማዊነት የተመለሱ ክርስቲያኖች በዓል የሚያከብሩት ሥራ ፈትቶ ተቀምጦ በመዋል አይደለም። ለምሳሌ በዓሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ እንደሆነ የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቅዳሴ ይቀደሳል። የሰበኩው ሕዝብ ይልቁንም በስመ የተሠየሙት ምእመናን ያስቀድሳሉ፤ ቅዱስ ቍርባንም ይቀበላሉ፤ ከጸሎተ ቅዳሴው ፍጻሜ በኋላም በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የተሠየሙ ሁሉ ከቤታቸው ተተምጠው ወጥቶ ዘመድ የሆነ ሁሉ ‹የከርሞ ሰው ይበልህ› እያለ የሚያመጣላቸውን ስጦታ በያይነቱ ሲቀበሉ ይውላሉ።

"የመንግሥት በዓላት ‹ብሔራዊና ሃይማኖታዊ› በዓላት እንደ ልደት፣ ጥምቀት፣ ትንሣኤ በሚከበሩበት ጊዜ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመዘጋታቸው በቀር እያንዳንዱ ግለሰብአ በቤቱ ለዕለቱ ምግብ የሚሆነውን የግል ሥራ ቢሠራ ለራሱ ካልደከመው በቀር ከጐረቤትም ሐሜት አያስከትልበትም፤ እርሱም ለራሱ በዓል እንደ ሻረ አድርጎ አይቁጥረውም።" ስለ በዓላት አጀማመርና የተለያዩ ሥርዓቶች ከዚህ በላይ እንደ አርእስት አንሥተናል፤ የሀገራችንስ የበዓል አከባበር እንዴት ነው?

"በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበዓላት ቀኖና የራሱ የሆነ መልክ አለው ከሁሉ በፊት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሜንና እሑድን እንደ አንድ ቀን አድርጋ /አስተካክላ/ ታከብራለች። የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን የታዘዘ ሲሆን እሑድ ደግሞ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣባት ‹የጌታ ቀን› ተብላ ከሐዲስ ኪዳን የከበረች ናት፤ (ራእ፡ 1፣10)

"በእነዚህ በሁለት ቀኖች ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያናችን የክርስቲያኖች አከባበር እንደ አይሁድ ሰውን የሚጫን እንዳይሆን ብታስተምርም ‹ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያጽርዑ ተገብሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ፣ አላ ይትገብሩ ከመ ክርስቲያን ወኢትትዐቀቡ ሰንበተ ከመ አይሁድ› ክርስቲያኖች በዕለተ ሰንበት እንደ አይሁድ ሥራ ይፈቱ ዘንድ አይገባቸውም፤ ነገር ግን እንደ ክርስቲያን ይሥሩ፤ ሰንበትን እንደ አይሁድ አትጠናቀቁ፡፡(ፍት.ነ. አንቀጽ 19) ‹ወዕረፍትሰ አኰ በሰኪብ ከመ ዘሐመ በደዌ፤ አላ በትጋህ መዓልተ ወሌሊተ ከመ ንኩን ፍቁራኒሃ ሰዋቲ ዕለት› ዕረፍታችን በጽኑዕ ደዌ እንደታመመ ሰው አይደለም፤ ነገር ግን የዚች ዕለት ወዳጆችዋ እንሆን ዘንድ በመዓልትና በሌሊት በመትጋት ያሳርፉ፡፡ (ቅዳ.አትና)

ሕዝቡ ከብሉይ ኪዳን በወረሰው ትውፊት መሠረት በዕለተ ሰንበት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በዓላት ማናቸውንም ሥራ ቢሠን አይሠራም። ሌላው ቀርቶ ቅዳሜና እሑድ የተቀዳ ውሃ፣ የተወቀጠ ቡና የማይጠጡ፣ ወንዝ የማይሻገሩ ክርስቲያኖች አሉ። በሌሎችም በዓላት እንደ ሰንበት አይጸናም እንጂ ሥራ መማስ፣ ቅጠል መበጠስ፣ መጽሐፍ መጻፍ፣ መደጉስ፣ ልብስ ማጠብ ሁሉ በዓል እንደመሻር

www.ethiopianorthodox.org

ይቁጠራል፡፡ ይህ ሁሉ ከሕዝቡ ልማድ ጋር የተያያዘ ስለሆነ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የተደነገገ አይደለም፡፡ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የጌታ በዓላት ዘጠኝ ናቸው፡፡ እነዚህም ‹ዐበይት በዓላት› (ታላላቅ በዓላት) ይባላሉ፤

"1ኛ ብሥራት፡-

መጋቢት 29 ቀን ነው፤ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም የአምላክን ከእርሷ መወለድ ያበሠረበት ቀን ነው፡፡ በመንጐፈ ደይን ወድቆ ለነበረው የሰው ዘር ታላቅ የምሥራች ነውና የምሥራች ቀን ብሥራት ተብሎአል፡፡

"2ኛ ልደት፡-

በትንቢተ ነቢያት የተነገረለት የሰውን ልጆች በጥንተ ተፈጥሮ የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ አሁን ደግሞ በሐዲስ ተፈጥሮ ለመፍጠር ማለት ሰውን ለማዳን ሰው ሁኖ የተወለደበት ዕለት ነው፡፡ በዓለ ልደት በየዓመቱ የሚከበረው ታኅሣሥ 29 ቀን ነው፤ በዘመነ ዮሐንስ ግን የሉቃስ ጳጉሜን ስድስት ቀን ስለምትሆን ልደት ታኅሣሥ 28 ቀን ይሆናል፡፡ ይህም የተጀመረው በአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል፡፡ (1298ዓ.ም.) የልደት በዓል ከጾም ጋር የተያየዘ ስለሆነ ገሃድ የለውም፡፡ የማይጾሙ ሰዎች ግን ዋዜማውን ብቻ ገሃድ ብለው ይጾሙታል፡፡ በዘመነ ዮሐንስ ልደት ማክሰኞ ወይም ሐሙስ በ28 ቀን ቢውል 29 ረቡዕ ወይም ዓርብ ይጾማል" ነገር ግን ይህ ጉዳይ በየጊዜው ያከራክር ስለነበረ በ1980 ዓ.ም. ጥቅምት 17 እና 21 ቀን በቅዱስ ሲኖዶስ እንደተወሰነ ስለ አጽዋማት በተሰጠው ሐተታ እንደተገለጠ ማስተዋል ይገባል፡፡

"3ኛ ጥምቀት፡-

ክርስቶስ በተወለደ በ30 ዓመቱ የማዳን ሥራውን በጥምቀቱ ጀምሮአል፡፡ ጌታ የተጠመቀው በፈለገ ዮርዳኖስ ነው፡፡ ያጠመቀውም ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ነው፡፡ በተጠመቀም ጊዜ አብ በደመና ሆኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መስክሮለታል፡፡ መንፈስ ቅዱስም በፀዓዳ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጦአል፡፡ ይህ በዓል በሚከበርበት ጊዜ በዋዜማው ታቦታቱ ከየቤተ ክርስቲያናቸው ወጥተው በወንዝ ዳር (በሰው ሠራሽ የውሃ ግድብም ቢሆን) በዳስ በድንኳን ያድራሉ፡፡ ሌሊት ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደረስ አድሮ ሥርዐተ ቅዳሴውም ይፈጸማል፡፡ ሲነጋ በወንዙ ዳር (በግድቡ) ጸሎተ አኰቴት ተደርሶ አራቱም ወንጌላት ከተነበቡ በኋላ ውሃው ተባርኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል፡፡ የጠበሉን መረጨት አይተው በቀድሞ ዘመን ወደ ሀገራችን መጥተው የነበሩ ኢየሱሳውያን ‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ታጠምቃለች› ብለው አጥላልተው ጽፈዋል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ይህን የምትፈጽመው ጌታችን ለእኛ ብሎ ያሳየውን ትሕትና ለመመስከር የጌታን በረከተ ጥምቀት ለምእመናን ለማሳተፍ እንጂ የተጠመቁትን ምእመናን እየመላለሰች በየዓመቱ አታጠምቅም፡፡ ጥምቀት አሐቲ መሆንዋን ታውቃለች፡፡ ርግጥ ያልተጠመቁ አረማውያንና ሌሎችም የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ጊዜ እየመጡ በክርስቶስ አምነው ይጠመቃሉ፡፡ በዓለ ጥምቀት የሚከበረው ጥር 11 ቀን ነው፡፡ ጥምቀት ረቡዕ ቢውል ገሃዱ ማክሰኞ፣ ዓርብ ቢውል ገሃዱ ሐሙስ ለውጥ ሆኖ ይጾማል፡፡ በዓለ ጥምቀት የሚውልባቸው ረቡዕና ዓርብ አይጾሙምና፡፡ በበዓለ ጥምቀት የታቦታቱ ወደ ወንዝ መውረድ ጌታ በአደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመሄዱ ምሳሌ ነው፡፡



"4ኛ ደብረ ታቦር፡-

ጌታ በማስተማር በነበረበት ጊዜ በደብረ ታቦር ላይ ብርሃነ መለኮቱን ክብረ መንግሥቱን የገለጠበት ዕለት ነው፡፡ (ማቴ፡17፣1-9) ይህ በዓል በየዓመቱ ነሐሴ 13 ቀን ይከበራል፡፡ ይህ በዓል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በምእመናን ዘንድ የተለየ ስም አለው፤ በምእመናኑ ዘንድ ቡሄ ይባላል፤ ቡሄ ማለትም (መላጣ ገላጣ) ማለት ነው፡፡ በሀገራችን



www.ethiopianorthodox.org

ክረምቱ፣ አፈናው ተዋግዶ የብርሃን ወገግታ የሚታየው በዚሁ በዓል አካባቢ ስለሆነ ‹ብሄ› ያሉት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። ድርጊቱ በተፈጸመበት በፍልስጥኤም ግን የደመና መልክ የማይታይበት ፍጹም የበጋ ወራት ነው። በሀገራችን ይህ በዓል ከመድረሱ በፊት ቀደም አድርገው ጅራፍ ሲገምዱና ሲያጮሁ (ሲያጥኑ) ይሰነብታሉ። እናቶችም ለዚህ በዓል የሚሆን ዳቦ ለመጋገር (የሚከበረው በዳቦ ነውና) ሲያጥቡ ሲፈትጉ ይሰነብታሉ፤ በዓሉ እንደ ነገ ሲሆን እንደዛሬ በዋዜማው (ነሐሴ 12 ቀን) የሰፈር ሕፃናት በየሰፈሩ እየዞሩ ‹ብሄ ብሄ እያሉ ይጨፍራሉ፤ የሚገጥሙትም ግጥም አላቸው፡፡› ‹ብሄ ና ብሄ በሉ፣ ብሄ መጣ፣ ያ መላጣ፣ ቅቤ ቅቤት እንዳይነጣ› እዚህ ላይ ‹ብሄ› ያሉት ዳቦውን ነው። በዚህ ጊዜ እናቶች ካዘጋጁት ዳቦ እያነው ይሰጧቸዋል። ሄደው ዳቦአቸውን እየገመጡ ሲጋረፉ ይውላሉ፤ ለግርፊያ ተምሳሌት ባይገኝለትም የጅራፉ መጮህ የድምፀ መለኮት፣ጅራፉ ሲጮህ ማስደንገጡ የሐዋርያትን (የጴጥሮስን የያዕቆብንና የዮሐንስን) በድምፀ መለኮት መደንገጣቸውንና መውደቃቸውን ያስታውሳል። በአንዳንድ ቀበሌዎች የብሄ ዕለት ማታ ችቦ ያበራሉ።

### የደብረ ታቦር ተራራ

በደብረ ታቦር ለታየው ብርሃን መለኮት ምሳሌ ነው። በዚያውም ላይ በኢትዮጵያችን የፀአተ ክረምት ዋዜማ ስለሆነ ብሄን ብርሃን ቢሉት ይስማማዋል። ‹ብሄ ከዋለ የለ ክረምት›፣ ደሮ ከጮኘ የለም ሌሊት› እንዲሉ። የብሄ ዕለት ለዘመድ ለአዝማድ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በልጆቹ ልክ ዳቦ ይሰጣል። በተጨማሪም ለክርስትና ልጅ፣ ለውት ልጅ፣ ለአማች፣ ለምራት፣ የቅርብ ዕውቂያ ለአለውም ሁሉ የብሄ ዳቦ ይሰጣል። በተማሪ ቤት ደግሞ ደብረ ታቦር የተማሪዎች በዓል ነው። ተማሪዎች ቀደም አድርገው ‹ስለ ደብረ ታቦር› እያሉ እህሉን ጌሾውን ብቅሉን ይለምናሉ፡፡ሕዝቡምባሕሉን ስለሚያውቅ በገፍ ይሰጣቸዋል። የደብረ ታቦር ዕለት ጠላውን ጠምቀው፣ ቆሎውን ቆልተው፣ ዳቦውን ጋግረው ሲያስቀድሱ የመጡትን ምእመናን ሁሉ ከቅዳሴ በኋላ ይጋብዛሉ። ይህ እስከአሁን ድረስ በትምህርት ቤቶች (መንፈሳዊያን ት/ቤቶች) እየተሠራበት ያለ ነባር ትውፊት ነው።

### "5ኛ ሆሣዕና፡-

ከትንሣኤ አንድ ሳምንት ቀድሞ በሚውለው እሑድ የሚከበር ነው። ታሪኩ በወንጌል ተጽፎአል፡፡ (ማቴ.21፣1-11) በዓሉን በዚህ ዕለት እንዲሆን የወሰኑት ግን ሊቃውንት ናቸው። ሆሣዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነው። በዚያች ዕለት ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ‹ሆሣዕና› አያሉ ስለአመሰገኑት ዕለቱ በጌታ ስም ተጠርቶአል። አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች ደግሞ ሆሣዕናም ይሉታል ‹የፀበርት እሑድም› ይሉታል። ፀበርት እየተባረከ ለ ሕ ዝ ብ ይታደላል። ሕዝቡም ፀበርቱን እየተቀበለ እንደ መስቀል አድርጎ እየሠራ በየቤቱ ይሰቅለዋል። እንደ ጣት ቀለበት አድርጎ እየሠራ በጣቱ ይሰካዋል። ከቅዳሴ በኋላ በቤተ ክርስቲያን በራቱም መዓዝናት አራቱ ወንጌላት ይነበባሉ።

ከሠርክ ሆሣዕና ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ያሉት ዕለታት የዓመተ ፍዳ መታሰቢያ (ሰሙነ ሕማማት) ስለሆኑ ጸሎተ ፍትሐት፣ ጸሎተ አስተስርዮ አይፈጸምም። ጸሎተ ፍትሐትና ጸሎተ አስተስርዮ የሚደረገው በዚሁ የሆሣዕና በዓል ዕለት ነው። በአክሱምና በሌሎችም አንዳንድ ቦታዎች ታሪኩን እንዳለ ለመግለጥ አህያ ጭነው በዚያ ላይ ሰው አስቀምጠው ሥርዓተ ዑደት ይፈጸማል።

### "6ኛ ስቅለት፡-

የስቅለት በዓል ለዓለም ቤዛ ሊሆን መድኃኒዓለም ክርስቶስ የተሰቀለበት ዕለት ነው። የስቅለት በዐል ብዙ ዘርፍ አለው። ከላይ እንደተገለጠው ከሠርክ ሆሣዕና ጀምሮ ያሉት ዕለታት የዐመተ ፍዳ መታሰቢያ ናቸው። በነዚህ ቀኖች ውስጥ ብዙ አዝማደ መባዕልት አይበሉም። ስግደት ይሰገዳል። የጌታን መከራ ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ክቡዳሳት መ ጻ ሕ ፍ ት ና ከድርሳናት ሲነበቡ ይሰነብታሉ። ሐሙስ ጸሎተ ሐሙስ ይባላል። ጌታ በፍጹም ትሕትና የሐዋርያቱ ሙሉ ያጠበበት ከሐዋርያት ጋር ገበር የገባበትና ምሥጢረ ቁርባንን ያሳየበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት ቂሱ ውሀውን በብርት አድርጎ በጌታ አምሳል የምእመናን እግር ያጥባል። ጸሎተ ትዳሩው ከተፈጸመ በኋላ ምእመናኑ ወደየቤታቸው ሄደው ዳቦና ጉልባን ይበላሉ። ለትንሣኤ የተዘጋጀው ጠላ የሚቀመሰውም የዚያ ዕለት ነው። በበነጋው የስቅለት ዐርብ የስቅለቱ መታሰቢያ አንበር ተሠርቶ ሰቀቀለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሲነበቡና ሲሰገድ ይዋላል። ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን ወደቂሱ እየቀረበ ስግደት እንዲሰጠው ይጠይቃል። ቂሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ተጨማሪ ቀን ሲሰገደው ከዋለው ሌላ ስግደት ይሰጠዋል። ጥብጣቢው የተግሳጽ ምሳሌ ነው። አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሠርሆተ ሕዝብ ይሠናል።

በቤተ ክርስቲያናችን ልማድ እመቤታችን ያዕቆብና ዮሐንስ የጌታን ትንሣኤ ሳናይ እህል ውሀ እንቀምስም ብለው እስከ ትንሣኤ ቆይተዋል ይባላል። በሀገራችንም ብዙ ሰዎች ሐሙስ ማታ የቀመሱ እሑድ የትንሣኤ ዕለት ብቻ ነው እህል ውሀ የሚቀምሱት። ያልተቻላቸው ግን ዓርብ ማታ ትንሽ ቀምሰው እስከ ትንሣኤ ይሰነብታሉ። የሁለት ቀን ማክፈሉ እንኳ ቢከብድ ቅዳሜን ማክፈል ጥሩ ሥርዐት ነው። ቅዳሴው በመንፈቀ ሌሊት ስለሆነ በልቶ ማስቀደስና በልቶ መቁረብ እንዳይሆን።

### "7ኛ ትንሣኤ፡-

የትንሣኤ በዓል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ ከሞተ በኋላ ተቀበረ። በሦስተኛው ቀን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ከሙታን ተለይቶ የተነሣበት ዕለት፣ ትንሣኤ ትባላለች። ትንሣኤ ለክርስቲያኖች የድል ቀን የነፃነት ቀን ናት። የትንሣኤ በዓል በቤተ ክርስቲያናችን ከሌሎች በዐላት ሁሉ በጣም በደመቀ አኳኋን ይከበራል። መንፈሳዊ ተመስጦም አለበት። ከአምሳ አራት ቀን የጾም ገዛ በኋላ የምትመጣ ስለሆነች ትንሣኤን ሁሉም ይናፍቋታል። ይልቁንም በአክፍሎት የሠነበቱ ሁሉ ዕረፍተ ሥጋን ለማግኘት ትንሣኤን በናፍቆት ይጠባበቋታል። ቅዳሜ ማታ ለአሁድ አጥቢያ ሕፃኑ፣ ሽማግሌው፣ ወጣቱ፣ ባልቱቱ በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ይሰበሰባሉ። ሥርዐተ ጸሎት ይጀመራል። ለትንሣኤ በዓል በቀኖና ቤተ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን የተመዘገበው ጸዋትው ከተፈጸመ በኋላ በመንፈቀ ሌሊት ጸሎተ ቅዳሴው ይጀመራል። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል። የትንሣኤ ማዕድ ባዕድ ዘመድ ወዳጅ ጠላት የማይለይበት የጋራ ማዕድ ነው። የትንሣኤ ዕለት ምንም ቢሆን ያለው በልቶ ያጣው ጦም አያድርም። በከተማ እንጃ እንጂ በባላገር እያንዳንዱ ምእመን የተቻለውን ያህል ተማሪ እየወሰደ የትንሣኤን ማዕድ አብሮ ይመገባል። በትንሣኤ ሳምንት በደብዳቤም በስልክም የሚሰጠው ሰላምታ "እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ" ነው። ምላሹም "እንኳን አብሮ አደረሰን" ይላል። (ጽርዓውያን ከትንሣኤ እስከ ዕርገት አርባውን ቀን ሰላምታ የሚሰጣጡት፡- አንዱ "ክርስቶስ ተነሣ" ሲል ሌላው መላሹ "በእውነት ተነሣ" ይላል።) ከእሑድ ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉት ዕለታት እንደ አንድ ቀን ነው የሚጠሩት መዝሙሩም ጸሎቱም አይለወጥም። ምዕራባውያን ከትንሣኤ ይልቅ ልደትን በደመቀ አኳኋን ያከብራሉ። ይኸውም ስለ ሁለት ምክንያት ነው። አንዱ እንደ ክርስቲያኖች ሁሉ ክርስቶስ የተወለደበትን ዕለት ለማክበር ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ አሮጌውን ዓመት ሸኝተው አዲሱን ዓመት የሚቀበሉት በልደት ሳምንት ስለሆነ ተደራራቢ በዓል አድርገው ነው። በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ግን የበዓላት ሁሉ ርእስ ትንሣኤ እንደመሆኑ መጠን በጣም ይከበራል። በምሥጢርም ቢሆን የክርስቶስ አምላክነት በደብልጥ ጎልቶ የታወቀው በትንሣኤው ስለሆነ ከልደት አብልጠው ያከብሩታል።

"8ኛ ዕርገት፡-

ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ለሐዋርያት እየተገለጠ ታይቷቸዋል። ትምህርትም አስተምሯቸዋል። በተነሣ በዐርባኛው ቀን ቀደም አድርጐ እንደነገራቸው ለሐዋርያት አሁንም የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ነግሮ ወደሰማይ የወጣበት ቀን ነው። ይህ በዓል በቤተ ክርስቲያን በጸሎት በማሕሌት ይከበራል። በሕዝቡ ዘንድ ግን ልዩ መሰናዶ የለውም።





"9ኛ ጰራቅሊጦስ፡-

ጌታ በዐረገ በአሥረኛው፤ በተነሣ በሐምሳኛው ቀን ለሐዋርያት በነገራቸው የተስፋ ቃል መሠረት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው። በዓለ ጰራቅሊጦስ ባለው "ጰንጠቆስጤ" የሚል ይገኛል። ጰንጠቆስጤ ቃሉ የግሪክ ነው። "ፔንዲኮስቴ" አምሳ፣ አምሳኛ ማለት ነው። በብሉያትና በሐዲሳት በሌሎች መጻሕፍት ሁሉ ከዕብራይስጥና ከዕርዕ ሳይለወጡ የገቡ ብዙ ጥሬ ቃላት አሉ። "ለምሳሌ ፡- ኬፋ፤ ፋሲካ፤ ኤሎሄ፤ ሳማ፤ ሰበቅታኒ፤"-- ከዕብራይስጥ "ጰንጠቆስጤ፤ ጰራቅሊጦስ ጴጥሮስ ክርስቶስ፤ ንብቲራ" -- ከዕርዕ የተወረሡ ጥሬ ቃላት ናቸው። ጰራቅሊጦስ ማለት በጉን የሚቆም፤ የሚረዳ፤ የሚያዕናና ማለት ነው። ይህ በዓል በብሉይ ኪዳን የእሸት በዓል ነበር። (በዓለ ስዊት) እስራኤል የነፃነት በዐላቸውን ከሚያከብሩበት ከበዓለ ፋሲካ (በዓለ ፍስሕ) ጀምረው አምሳውን ቀን በዓል አድርገው ይሰነብታሉ። በአምሳኛዉቱ ቀን በዓለ ሰዊትን (የእሸት በዓላቸውን) ያከብራሉ። በሀገራቸው ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው ወቅት በሀገራችን ከመስከረም እስከ ህዳር እንዳለው የእሸት ወራት (የፀደይ ወራት) ነውና። የእሸት በዓላቸውን የሚያከብሩት በኦሪት ዘሌዋውያን በምዕራፍ 23:10-17 በታዘዙት መሠረት ማንኛውም እስራኤላዊ ገበሬ ከዘራው ሁሉ በያይነቱ እሸቱን ቆርጦ ተሸክሞ ወደ ምኩራቡ ይመጣል። በቤተ መቅደስ የሚያገለግለው ካህን ተቀብሎ ባርኮ ጸልዮ የሚጠበሰው እየተጠበሰ የሚታሸው እየታሸ በማህበር አንድነት ይበላል። ይህም " ቀዳምያት ይባላል።" የመጀመሪያው ማለት ነው። ከማንኛውም በረከት የመጀመሪያውን ወደ እግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ለእግዚአብሔር መስጠት እንዳለበት ታሣቢና። በዓለ ፋሲካን ለማክበር ከዝርወት ተሰብስበው የሰነበቱ አይሁድ ሁሉ ወደየመጡበት የሚመለሱት ይህን በዓለ ስዊትን ካከበሩ በኋላ ነው። ይህን ሁሉ የገለጥነው በጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በተሰጠበት ዕለት የነበረው ለታሪካችን መገናኛ እንዲሆን ነው። ከዝርወት የተሰበሰቡና በዚያውም የሚኖሩ አይሁድ ብዙውን ጊዜ በዓል የሚያከብሩ በደብረ ጽዮን ነው። ይመጣል ብለው የሚጠብቁት መሲሕም በደብረ ጽዮን ይገኛል ነው የሚሉት።ኦ እንግዲህ በዚህች በደብረ ጽዮን በዓለ ስዊትን ለማክበር ተሰብስበው እንዳሉ ሐዋርያት ደግሞ በዚሁ በደብረ ጽዮን በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር። (ይህን ቤት ቲቶ ኢየሩሳሌምን ሲያጠፋ አላፈረሰውም ይባላል።)

ጌታ በዐረገ በአሥረኛው ቀን ሧት መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጠ። ጌታ የነገራቸው የተስፋ ቃል ሁሉ ተፈጸመ። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የሞቱና የትንሣኤው ምስክሮች ሆኑ። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በእርሱ ላይ ሲያድር ለቤተ ክርስቲያን ገዘ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ። ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው "መንፈስ ቅዱስ ባይወርድላት ኑሮ የቤተ ክርስቲያን ህልውና ከሞኖና ቀጭጮ ይቀር ነበር። ስለዚህም በሚገባ አነጋገር ይህች ዕለት የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን ትባላለች" ይላል። ብዙ ሊታውንት ይህችን ዕለት የበዓላት ሁሉ እመቤት ይሏታል። የጰራቅሊጦስ በዓል በክርስቲያን ዓለም ሁሉ ከትንሣኤው በአምሳኛው ቀን ይከበራል። በሀገራችንም እንደዚሁ ነው። የትንሣኤው ቀለም (በቤተ ክርስቲያን) የሚፈጸመው የጰራቅሊጦስ ዕለት ነው።

ዘጠኙ ዐበይት በዓላትና የአመጣጣቸው እንዲሁም የአከባበራቸው ሥነ ሥርዓት ከዚህ በላይ እንዳየነው ነው። ከነዚህ ውስጥ የሆሣዕና የስቅለት የትንሣኤ የዕርገትና የጰራቅሊጦስ በዓላት ዐዋድያት ሰሰሆኑ በቀን አቆጣጠር መባቻ ሐመርን ተከትለው ወደላይ ወደታች ይላሉ። ዕለታቸው ግን አይፋለስም። ሆሣዕና ትንሣኤ ጰራቅሊጦስ እሑድን ስቅለት ዐርብን ዕርገት ሐሙስን አይለቅም። ሌሎቹ ፅንሰተ ልደት ደብረ ታቦር ጥምቀት ግን አዋድያት አይደሉም። ዕለታቸው ግን የተፋለሰ ነው። ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት ሌላ ዘጠኝ ንኡሳት በዓላት አሉ። እነርሱም፡-

1. መስቀል
2. ስብከት
3. ብርሃን
4. ናዛዊ
5. ግዝረት

www.ethiopianorthodox.org

6. ልደተ ስምዖን
7. ታና ዘገሊላ
8. ደብረ ዘይት
9. የመጋቢት መስቀል (መጋቢት 10 ቀን) ናቸው፡፡

## ሀ/ የመስቀል በዐል፡-

የሚከበረው መስከረም 17 ቀን ነው፡፡ ይህም በዐል በክርስቲያኑ ዓለም ሁሉ ይከበራል፡፡ ታሪኩም በመጠነኑ እነሆ፡- ጌታ በመስቀል ላይ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ሕሙማን መስቀሉን እየዳሰሱ በመስቀሉ እየታሹ ይፈወሱ ነበር፡፡ በዚህም ተአምራት እየተሳቡ ብዙዎች ክርስቲያን ሆኑ፡፡ ይህንን ያዩ አይሁድ መስቀሉን በአንድ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ጣሉት፡፡ በየቀኑ የአካባቢው ኗሪ ሁሉ ቆሻሻ ስለሚጥልበት ያ ቦታ እንደ ጉብታ ሆነ፡፡ ምንም እንኳ ባይችሉ ክርስቲያኖቹ ኢየሩሳሌምን ጨርሰው ሉቀው ስለወጡ የከተማዋም መልክ ፈጽሞ ስለተለወጠ መስቀሉ የተደፈነበት ቦታ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ከሦስት መቶ ዓመት በላይ ተዳፍኖ ቆይቷል፡፡ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (327) የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት አሌኒ ይህን ታሪክ ትሰማ ነበርና አስቆፍራ ለማውጣት ጉዞዋን ወደ እየሩሳሌም ቀጠለች፡፡ እዚያም ደርሳ ጉብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍር መስቀሉ ያለበትን አላገኘችውም፡፡ ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቅላት አላገኘችም፡፡ በመጨረሻ ግን የመስቀሉ መውጣት የእግዚአብሔር ፈቃዱ ነበርና አንድ አረጋዊ ስሙ ኪሪያኮስ የሚባል (ኪራኮስ ድጓ ) የእሌኒን መቸገር አይቶ እንደሚከተለው ይመክራታል፡፡ ‹አንችም በከንቱ አትድከሚ ሰውም አታድክሚ እንጨት አስብስበሽ ከምረሽ ዕጣን አፍስሽበት በአሳትም አያይዥው የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ አትጣጫውን አይተሽ አስቆፍረው በዚህ ምልክት ታገኝዋለሽ አላት› አሷም ያላትን ሁሉ አደረገች፡፡ ‹ዘዕጣን አንዐረ ሰገደ ጢስ ድጓ› የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ያህል አሳየ ያን ምልክት ይዛ አውጥታዋለች፡፡ ‹ብኃልኃታ ዘደፈኑ አይሁድ ዮም ተረክበ ዕፀ መስቀል› (ድጓ) ይህን በዓል በመላው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ያከብሩታል፡፡ በሀገራችንም እንደ አጋጣሚ ሆኖ የመስቀል በዓል ከጥቢ ወራት መግቢያ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የተለየ ድምቀት አለው፡፡



የመስቀል በዓል በመስቀል አደባባይ

በመስከረም 16 ባላገሩ በቀበሌው የከተማው ሕዝብ ማዘጋጃ ቤት ባዘጋጀለት ቦታ ከየቤቱ ችቦውን እንጨቱን እያመጣ ይደምራሉ፡፡ ካህናቱም በደመራው ፊትለፊት ጸሎት አድርሰው /መስቀል አብርሀ በከዋክብት አሠርገህ ሰማየ እምኩሉሰ ወሐየ አርአየ/ እያሉ ደመራውን ይዞራሉ፡፡ ቀጥሎም ሕዝቡ " እዮሀ አበባየ መስከረም ጠባዬ/ እያሉ በደመራው ዙርያ ይጨፍራሉ፡፡ ግጥሙ የወራት እንጂ የመስቀል





ባይሆንም ቀምነገሩ የመስቀልን ክብር አይለቅም፡፡ ማታ ሕዝቡ ችቦውን በየደጁ እያበራ ደስታውን ሲገልጽ ያመሻል፡፡ በ17 ጧት ደመራውን ይለኩማል፡፡ አመድ እስኪሆን ድረስ ይቃጠላል፡፡ ደመራው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ ሕዝቡ አመዱንና ትርኒሹን እየተሻማ ወደእየቤቱ ይዞ ይሔዳል፡፡ ለሰውም ሆነ ለከብት መድኃኒት ነው፡፡

በአዲስ አበባና በአካባቢው ግን ደመራውን የሚያቃጥሉት ወዲያው ጸሎቱ እንደአበቃ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጠው ይህ በዓል በሀገራችን በጥቢ ወራት ማለት አበቦች በሚፈነዱበት ወራት ስለሆነ በአንዳንድ አኃጋዊ የአንቁጣጣሽ በዓል ይባላል፡፡ እዚህ ላይ አንቁጣጣሽ የሚሉት ሕፃናቱ ልዩ ልዩ ተለማት ያሏቸውን አበቦች ለቅመው አንድ ላይ በሰርዶ አስረው ከደመራው ዕለት ጀምረው ለጐረቤቶቻቸውና ለአገኙት ሁሉ ይሰጣሉ፡፡ ሰዎችም የሀገር ትውፊት ነውና አበባውን እየተቀበሉ ገንዘብ ይሰጧቸዋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በየቤቱ እየዞሩ ወንዶችም ሴቶችም ለየራሳቸው የሀገር ባህል ግጥም እየገጠሙ ይጨፍራሉ፡፡ ባለቤቶችም እንደ ሽልማት እያደረጉ ገንዘብና ሌላም ነገር ይሰጧቸዋል፡፡ አንድ ላይ አጠራቅመው ድግስ ደግሰው ይመገባሉ፡፡ በገራኝ ወረራ ብዙ ባህሎች ሲደመሰሱ የመስቀል በዓል ግን እንኳን በክርስቲያኖቹ ተገደው በሰለሙት ኢትዮጵያውያን ዘንድ አልተረሳም፡፡ ለምሳሌ በሀገራችን ብዙ አስላሞች የመስቀልን በዓል ከክርስቲያኑ ጋር እንደ ክርስቲያኑ አድርገው ያክብራሉ፡፡ እንግዲህ ከቀን በኋላ በወራሪ ኃይል ተገደው አስልምናንን ቢቀበሉ ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ክርስቲያናዊ ባህል ሳያውቁ ያክብሩታል ማለት ነው፡፡ ባህል የሰውን ምንጭ የሰውን ከየት መጣ ቁልጭ አድርጐ የሚያሳይ መጽሔት ነውና፡፡ ከዚህም ጋር አንዳንዶች አስላሞች በአንገታቸው መስቀል ያስራሉ፡፡ መስቀል የክርስቲያኖች ምልክት መሆኑን አያውቁትም፡፡ ይህም መሠረታቸው ክርስቲያን መሆኑን ያሳያል፡፡

## ለ/ ስብከት፣

## ሐ/ ብርሃን፣

## መ/ ኖላዊ፡-

እነዚህ ሦስት በዓላት ከልደት በፊት የሚውሉ ሦስት ኢሑዶች ናቸው፡፡ ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው በትንቢት ይጠባበቁት የነበረው መሲሕ የዓለም ብርሃን የነፍሳት ጠባቂ ነው ለማለት በቤተ ክርስቲያናችን የመዝሙርና የጸሎት ሥርዓት ከልደቱ ቀደም ብሎ ያሉት ሦስት ኢሑዶች ስብከት፣ ብርሃን፣ ኖላዊ ተብለው ተሰይመዋል፡፡ አከባበራቸውም በቤተ ክርስቲያን ቀለም እንጅ ልዩ ሥርዓት የላቸውም፡፡

## ሠ/ ግዝረት፡-

ይህ በዓል የሚውለው ጥር ስድስት ቀን ነው፡፡ በሙሴ ሕግ እንደተጻፈ ሕፃን ሲወለድ በስምንት ቀኑ ይገረዛል፡፡ ይህን የሙሴን ሥርዓት ለመፈጸም ጌታ ከተወለደ በስምንት ቀኑ ተገርዟል፡፡ የተወለደው ታህሣሥ 29 ቀን ሲሆን ስምንተኛ ቀን የሚውለው በጥር ስድስት ቀን ነው፡፡ ይህ ቀን ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሲከበር ይኖራል፡፡

## ረ/ ልደተ ስምዖን፡-

ይህ በዓል ጌታ በተወለደ በአርባ ቀኑ የሚከበር ነው፡፡ ጌታ ሥርዓተ ኦሪትን ትንቢተ ነቢያትን ሊፈጽም እንጂ ሊያፈርስ ስላልመጣ ሕገ ኦሪትን ፈጽሟል፡፡ ለሙሴ ሕግን የሰጠ ሲሆን የሙሴን ሕግ ፈጽሟል፡፡ ከላይ እንዳየነው በስምንት ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ገብቶአል፡፡ አሁን ደግሞ በተጻፈው መሠረት (ዘፀ:13፣2፡፡ ዘሌዋ.12፡፡) የሙሴን ሕግ ለመፈጸም ሁለት ዋናስ ወይም ሁለት የርግብ ጫጨቶች መስዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ወሰዱት፡፡ በዚያም የእሥራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ የነበረ ስምዖን የሚባል ሰው ነበር፡፡ እሱም መሲሕን ሳያይ እንደማይሞት ከመንፈስ ቅዱስ ተረድቶት ነበር፡፡



www.ethiopianorthodox.org

በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ መሠረት ይህ ስምዖን በ284 ክፈታ ልደት በፊት በበጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት መጻሕፍተ ብሉያት ከዕብራይስጥ ወደ ዕርዕ በተመለሱ ጊዜ ከመላሾቹ ከሰባው ሊቃውንት አንዱ እሱ ነበር፡፡ እንደአጋማሚም ለእርሱ የደረሰው የኢሳይያስ መጽሐፍ ነበር፡፡ "ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ" ከሚለው ሲደርስ ድንግል ትወልዳለች ብሎ መተርጐሙን ተቀባይ የማያገኝ አሳፋሪ ነገር መስሎት "ድንግል ትወልዳለች" የሚለውን ንባብ "ወለት ትፀንሳለች" ብሎ መለሰው፡፡ ተመልሶ እንደገና ቢያይ "ድንግል ትወልዳለች" የሚል ተጽፎ አገኘ፡፡ ሁለተኛም ፍቆ "ወለት ትወልዳለች" ብሎ ጻፈ እንደገና ቢያይ "ድንግል ትወልዳለች" የሚል ንባብ አየ፡፡ በሦስተኛው እፍታለሁ ሲል የእግዚአብሔር መንፈስ ተገልጦ ተው አትፋቀው ይህን የተጠራጠርከውን ሳታየው አትሞትም አለው፡፡ ጌታ በአናቱ እቅፍ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ እሱም በእግዚአብሔር ፈቃድ መጥቶ እዚያ ተቀምጦ ነበር፡፡ ጌታን ከእመቤታችን ተቀብሎ ታቅፎ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ ሁለት ከቁጥር 29-32 ያለውን ጸለየ፡፡ ወደ ቤተ መቅደስ የገባበትና በስምዖን እቅፍ የታየበት ዕለት በቤተ ክርስቲያን ይከበራል፡፡ ስምዖን ጌታን በታቀፈ ጊዜ ከእርጅናው መታደሱ ስለሚነገር በዓሉ የጌታ ሁኖ ሳለ ልደተ ስምዖን እያልን እንጠራዋለን፡፡ ሌሎቹ "የጌታ ወደ ቤተ መቅደስ መቅረብ" ይሉታል፡፡

## ሰ/ ቃና ዘገሊላ ፡-

ቃና በገሊላ ክፍል የምትገኝ ቀበሌ ናት፡፡ በዚህች ቀበሌ ውስጥ ጌታ ከሠርግ በዓል ላይ ተገኝቶ ነበር፡፡ (ዮሐ.2፡1-12) ታሪኩን ከላይ በተጠቀሰው የወንጌል ምንባብ ውስጥ ይመለከቷል፡፡ የጌታ የመጀመሪያው ተአምር የተገለጠበት ድርጊት ስለሆነ እናከብረዋለን፡፡ ይህ በዓል የሚውለው በየካቲት 23 ቀን ነበር፤ ጌታ ዕለቱን ተጠምቶ ዕለቱን ወደ ገዳመ ሪሐ ሄዷል፡፡ ከተመለሰ በኋላ በሦስተኛው ቀን ወደ ሠርግ ቤት ተጠርቶ በየካቲት 23 ውሀውን የወይን ጠጅ በማድረግ የመጀመሪያውን ተአምር አሳይቷል፡፡ አሁን ግን በዐልና በዐልን ለማገናኘት ሲባል ጥር 12 ቀን የጥምቀት በዐል በዋለ በነጋው እናከብረዋለን፡፡

## ሸ/ ደብረ ዘይት፡-

ደብረ ዘይት ወይራ የሞላበት ተራራ ማለት ነው፡፡ የሚገኘውም በኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ ጥቂት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ነው፡፡ ጌታ ቀን በቤተ መቅደስ ሲያስተምር (ማቴ. 24) ደቀመዛሙርቱ የምጽአቱን ጉዳይ አንስተው ጠይቀውት ምልክቱን ገልጦ ነግሯቸዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድም የዐቢይ ጾምን እኩሌታ እሑድ የጌታ ዳግም ምጽአት መታሰቢያ አድርጐ መዝሙሩን በዳግም ምጽአት ጸፈል፡፡ ዕለቱም ደብረ ዘይት ይባላል፡፡





ምጽዐተ ክርስቶስ

## ቀ/ የመጋቢት መስቀል፡-

ይህ በዐል የሚከበረው መጋቢት አሥር ቀን ነው፡፡ በአንዳንድ የሀገራችን ሰዎች ዘንድ ዕለቷ በመስከረም ማስቀፈር ጀምራ መስቀሉ የወጣው መጋቢት አሥር ቀን ነው ይላሉ፡፡ ነገር ግን ይህን አተራረክ ለመቀበል በቂ ምስክር የለም፡፡ በዓለምም ዙሪያ መስቀሉ የወጣበት ዕለት የሚከበረው መስከረም 17 ብቻ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ መጋቢት አሥር ቀን ከንኡሳን በዓላት ዘጠነኛው ነው፡፡ ዘጠኙን ዐበይት በዐላትና ዘጠኙን ንኡሳት በዐላት [illegible] ለመረዳት ይቻላል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ከነዚህ ሌላ የእመቤታችን በዐላት፡- ልደታ፣ በአታ፣ ፍልሰታና አስተርእዮ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሲከበሩ የኖሩ ናቸው፡፡ ሌሎቹ በመቅድመ ተአምር የተጨመሩት 33ቱ በዓላተ ማርያምና በየወሩ በ21 የሚከበረው የእመቤታችን በዐል፣ በ29 የሚከበረው በዐለ እግዚእ፣ በ12 የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል ሌሎችም በዐላት የተጨመሩት በዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል፡፡ ከዚያም አያይዞ ሕዝቡ የቅዱሳንንና የመላእክትን በዐላት በየወሩ ማክበር ጀመረ፡፡ ለምሳሌ ቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳን ሰማዕታት፣ ጻድቃንም በዓመት አንድ ጊዜ እንዲከበሩ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ያለ ነው በእኛ ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ባለበት ሰበካ በትውልድ የመጣ ልማድ ሆኖ በቤተሰቡ ሁሉ ይከበራል፡፡ አያት ቅድመ አያቱ የጊዮርጊስን በዐል ያከብር እንደሆነ ልጁ፣ የልጅ ልጁ ያያቱ ታቦት ነው እያለ በየወሩ ተቀምጦ ይውላል፡፡

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በቀኖናዋ ሰፍራ ቆጥራ ያስተማረችው የጌታ፣ የእመቤታችን፣ የሐዋርያት፣ የመላእክትና የቅዱሳን በዐላት የተወሰኑ ሆነው ሳለ፣ ሕዝቡ በገዛ ፈቃዱ ምክንያት እየፈጠረ ዛሬም በዐል ነው ነገም በዐል ነው ብሎ ተቀምጦ ቢውል ቤተ ክርስቲያንን አያስወቅስም፡፡ እንደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም የዓመት ስንክሳር አላት፡፡ ይኸውም በየዓመቱ የሚከበረውን "ቅዱስ ጻድቅ" የሕይወት ታሪክና አሟሟት በዝርዝር የያዘ መዝገብ ነው፡፡ በዚሁ በስንክሳሩ መሠረት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም በዐላትን ያከብራሉ፡፡ አሁን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት በዐላትን መቀነስ ወይም ጨርሶ መሠረዝ ሳይሆን የአከባበሩን ዓይነት ማስተካከል ነው ወይም በግልጥ አነጋገር የበዐል ሥራ መፍጠር አለባት፡፡ ሥራ ፈትቶ መዋል በዐል ማክበር አለመሆኑን ተስ በቀስ ለምእመናኗ ማስረዳት አለባት፣ ምእመናን በዐሉንም አክብረው ሥራቸውንም ሠርተው ለመዋል ይችላሉና፡፡ "የነበረውን በአዋጅ መለወጥ ግን ትምህርቷን ያዛባዋል፡፡ በዐል ማክበር እንደ በኵተኛ ተኾቶ በመዋል አለመሆኑንም የቤተ ክርስቲያን አባቶች አስረድተዋል፡፡ ( የአትናቴዎስ ቅዳሴ) "ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያዕርዑ ተገብሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ፤ አላ ይትገብሩ ከመ ክርስቲያን፡፡ ወኢትትዐቀቡ ሰንበተ ከመ አይሁድ" (ፍትሐ ነገሥት 19)

የዓመት በዐላት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚከበሩት በዐዳት ነው፡፡ ለበዐሉ የተዘጋጀው መዝሙር እየተዘመረ ካህናቱ ታቦቱን ከመንበሩ አንሥተው ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ ከዞሩ በኋላ ሠርሠተ ሕዝብ ይሆናል፡፡ ይህ የሚሆነው ሧት በሚቀደስባቸው ዕለታት ነው፡፡ ውሎ ቅዳሴ ከሆነ ግን ታቦቱ ከዐዳት ሲመለስ ጸሎተ ቅዳሴ ይጀመራል፤ ጸሎተ ቅዳሴው ሲፈጸም ሠርሠተ ሕዝብ ይሆናል፡፡

ከነዚህ ከጠቀስናቸው በዐላት ሌላ በክርስቲያኑ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላ ብሔራዊ ደረጃ የሚከበር በዐል ቅዱስ ዮሐንስ (የዘመን መለወጫ) ነው፡፡ በኢትዮጵያችን ሁልጊዜ አዲስ ዓመት የሚጀመረው በመስከረም ነው፡፡ የጥንት ሮማውያን አዲስ ዓመት የሚያከብሩ በመጋቢት ወር ነበር፡፡ መስከረም ለመጋቢት ሰባተኛ ወር ነው፡፡ "ሴፕቴምበር ይሉታል" "ሴፕቴምበር (Septem)" ሰባት ከሚለው ቃል የተወረሰ ነው፡፡ ከጢባርዮስ ቄሣር በኋላ የተነሡ አያሌ የሮም ነገሥታት በዚህ ወር ተሰይመውበታል፡፡ ይህንኑ ወር የአንድትትዮን ወር ይሉታል፡፡ ( Indico) ከሚለው የላቲን ቃል የወጣ ነው፡፡ (Indicto-onis) አዋጅ መንገሪያ ትእዛዝ ማስተላለፊያ ውሳኔ መወሰኛ ማለት ነው፡፡ "የበጀት ዓመት" እንዲሉ ለነገሥታት የሚሰጠው ግብር፣ ለሃይማኖት አባቶች የሚቀርበው ገጸ በረከት ተሰብስቦ መፈጸም ያለበት በዚህ ወር ነው፡፡ በሀገራቸው የበጋው ወራት ፍጻሜ የክረምቱ ተጋባት በመስከረም ነውና፣ "አንደ ሀገራችን ግንቦትና ሰኔ" ይህንኑ ወር በየአሥራ አምስት ዓመት የአንድትትዮን በዓል እያሉ ያከብሩት ነበር፡፡

ሕገ መንግሥት የሚታደስበት፣ ውል የሚፈርስበት የሚታደስበት በዓል ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ግን እስራኤል ነፃ ከወጡበት ከመጋቢት ወር ጀምረው ቆጥረው በሰባተኛው ወር አዲስ ዓመት እንዲያከብሩ ከፈጣሪያቸው ታዘዋል፡፡ (ዘሌዋ.23፣24 ዘኍልቁ 29:1) አዲሱን ዓመታቸውን በዚህ ወር የሚያከብሩ ከእግዚአብሔር ታዘው ስለሆነ ይህ ዐውደ ዓመት ለእስራኤል ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊም ስሜት አለው፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓውደ ዓመት ብዙ ሃይማኖታዊ ድርጅቶችን ይፈጽመዋል፡፡

ሌቀ ካህናቱ ኤፉዱን ለብሶ የሐር መነሳንሱን ይዞ የዓመቱን በዐላትና አጽዋማት ለሕዝቡ የሚያውጀው በዚህ ቀን ነው፡፡ በክርስትና ዓለም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ የብሉይ ኪዳን ትእዛዝ ተቀብላ አዲስ ዓመት በመስከረም ወር መጀመሪያ እያከበረች ብዙ ዘመን ኑራለች፡፡ በኋላ ግን ከአንድ ሺህ ሰባ ሦስት እስከ አንድ ሺህ ሰማንያ አምስት የነበረው የሮማ ፓፓ ጎርጎርዮስ ሰባተኛ የአዲስ





ዓመት መጀመሪያ ከልደት እንዲያያዝ ለማድረግ በጥር ወር ይሁን ብሎ ወሰነ፡፡ በዚህ ውሳኔ የካቶሊክ ግዛት የነበረው ምዕራቡ ዓለም በሙሉ ሲስማማ ምሥራቁ የክርስቲያን ዓለም ግን መስከረምን አልለቀቀም፡፡ በፖለቲካና በንግድ ተጽእኖ ምክንያት መንግሥታት በአቶጣጠር ወደ ምዕራቡ ዓለም ሲሳቡም በምሥራቅ ያለች ቤተ ክርስቲያን አዲሱን ዓመት የምታከብረው አሁንም በመስከረም ነው፡፡ ለምሳሌ "ሩሲያ፣ ግሪክ፣ ሩማንያ" ሌሎችም ይህን የቤተ ክርስቲያን አዲስ ዓመት ይሉታል፡፡

በሀገራችን ግን ከጥንቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነቁጥ ሳይለወጥ የመንግሥቱም የቤተ ክርስቲያንም አዲስ ዓመት የሚጀመረው በመስከረም ነው፡፡ ይኸውም ለኢትዮጵያ ክብር ነው፡፡ ሁሉ መስከረም" ማለት ድነረ ክረምት እንደ ማለት ነው፡፡ በሀገራችን የክረምቱ የጨለማው ወራት ተፈጽሞ የበጋው የጥቢው ብርሃን የሚፈነጥቅበት ወር ነው፡፡ ስለዚህ በሀገራችን አዲሱ ዓመት ሁለት ዓይነት የአከባበር ጠባይ አለው፡፡ (ብሔራዊና ሃይማኖታዊ) ነገር ግን አንዱ ከሌላው የተራራቀ አይደለም፡፡ ብሔራዊ ያልነው ሕዝቡ ክርስቲያኑም ሆነ ሌላው በብሔራዊ ስሜቱ የሀገር ልብስ ለብሶ ብሔራዊ ዘፈን እየዘፈነ አርዶ ጠምቆ፣ ሲበላ ሲጠጣ፣ ሲገባበዝ ሲጠያየቅ ይውላል፡፡ በሃይማኖታዊ ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እየሄደ ለዚህ ያደረሰኝና አምላኬ ተመስገን፣ የክርሞ ሰው በለኝ፣ ተርፎ ለሚቀረው ዕድሜ አትንፈገኝ ብሎ ፈጣሪውን ይለምናል፡፡ ካህናቱም በቤተ ክርስቲያን ለበዓሉ የሚገባውን ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሳሉ፣ ኂሳም መምህሩ ወይም መሪጌታው ካፓ ላንቃ ለብሶ መስቀሉን ይዞ በዓመቱ የሚውሉትን አጽዋማትና በዓላት ያውጃል፡፡ ባሕረ ሐሳብ ያወጣል ቀጥሎም ፍሬያተ ምድር ዕጣኑ ጧፉ ዘቢቡ ስንዴው በመሶብ ወርቅ እየቀረበ ይባረካል፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት እያንዳንዱ ወንጌላዊ (ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ) አንዳንድ የመጠበሪያ ዓመት አለው፡፡ ይህም በየአራተኛው ዓመት መጨረሻ ለመጀመሪያው ይደርሰዋል፡፡ (patron) ይሉታል በፈረንጆች ጠባቂ ማለት ነው በኛም ይህንኑ ይመስላል፡፡ "በዮሐንስ እረስ በማቴዎስ እረስ" እንዲሉ የሕዝናቱ የአከባበር ትውፊት እንደ መስቀል ነው፡፡ ያንን ይመለከታል፡፡

ከዚህ ሌላ ሕዝቡ ከጳጉሜን ጀምሮ እስከ መስከረም አንድ የወንዝ ውሀ ወዳለበት እየሄደ ጠበል ነው እያለ በሌሊት ይነከራል፡፡ ይህም የቆየ ባህል ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች የአምልኮ ባዕድ ጠባይ ያለበት እየመሰላቸው ድርጊቱን ይነቅፋሉ፡፡ ነገር ግን የአምልኮ ባዕድ መርዝ እንዳይቀላቀልበት ሕዝቡን ማስተማር እንጂ በውሀ መጠቀሙ ነውር አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን የምእመናንን ሕይወት ዘወትር በትምህርት ካልቃኘችው ማንኛውም መንፈሳዊ ተግባር በአምልኮ ባዕድ መበረዙ አይቀርምና በመስቀልና በዘመን መለወጫ በዐል ዕለት ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው ዶሮዎች፣ ፍየሎችና በጎች ለዕርቦ እየተባሉ እያንዳንዱ ሰው በራሱና በቤተሰቡ ልማድ የሚፈጽመው እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተገኘ አይደለም" (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባ ጎርጎርዮስ የሸጋ ሊቀ ጳጳስ ገጽ 124-144)

በአሁኑ ጊዜ የበዓላት ቀን በዛ የሥራ ቀን አነሣ በዚህም ምክንያት ሕዝቡ ሥራ ፈትቶ እየዋለ ለድህነት ተዳረገ፣ ለዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ናት የሚል ትችት ይሰማል፡፡ እውነቱ ሲታይ ግን በቤተ ክርስቲያን ቀኖና በሳምንትና በዓመት እንዲከበሩ የታዘዙ በዓላት ፡-

ሀ/ በሳምንት ቅዳሜና እሑድ
ለ/ የጌታ ዘጠኙ ዐበይት በዓላት
ሐ/ የእመቤታችን በዓላት ግንቦት 1 ቀን ልደትዋ ፣ ኅዳር 21 ቀን ጽዮን፣ ጥር 21 ቀን ዕረፍትዋ፣ ነሐሴ 16 ቀን ፍልሰትዋ ከነዚህ ሌላ ታኅሣሥ 3 ቀን በአታ ውስተ ቤተ መቅደስ፡፡ የካቲት 16 ቀን የምሕረት ቃል ኪዳን የተቀበለችበት በበዓላቱ ስም ቤተ ክርስቲያን በታነጸበት በጸሎተ ማኅሌትና በቅዳሴ እንዲከበሩ ፤
መ/ የመላእክት በዓላት ፡-

ኅዳር 12 እና ሰኔ 12 ቀን በዓለ ሚካኤል

ታኅሣሥ 19 ቀን በዓለ ገብርኤል

www.ethiopianorthodox.org



ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል

- የሌሎች መላእክት በዓል በስማቸው ቤተ ክርስቲያን በታነጸበት

- የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታትም እንዲሁ በዕረፍታቸው ቀን በዓመት አንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናቸው በታነጸበት በማ?ሌት፣ በቅዳሴ እንዲከበር የጌታ የእመቤታችንና የቅዱስ ሚካኤል የወር በዓላት በማ?ሌትና በቅዳሴ እንዲከበር እንጂ ሕዝቡ ሥራ ፈትቶ እንዲውል የቤተ ክርስቲያን ቀኖና እንደማያዝዝ ገልጦ ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ አጽዋማትና ስለ በዓላት የማሻሻያ ውሳኔ እንዲያስተላልፍ ግንቦት 7 ቀን 1961 ዓ.ም. ጥናት ቀርቦ ነበር፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስም "ውሳኔ የሚሰጠው ጥናቱ በጋዜጦች፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ከተገለጠ በኋላ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መምህራንና ካህናት ምእመናኑም አውቀውት አስተያየታቸውንና አሳባቸውን ከሰጡበት በኋላ ይሆናል" በማለት እንደ አሳደረው ተመዝግቦአል፡፡ (ሐዲስ ሕይወት ቁጥር 5 ግንቦት 1 ቀን 1967 ዓ.ም.)

በሌላ በኩልም በሰኔ ወር 1996 ዓ.ም. የበዓላትን አከባበር አስመልክቶ በሊቃውንት ጉባኤ የቀረበ ጥናት

"1ኛ በየሳምንቱ በወል የሚከበሩ ቅዳሜና እሑድ
"2ኛ በየወሩ በወል የሚከበሩ

ሀ. ወር በገባ በ12ኛው ቀን በዓለ ሚካኤል /በዓለ መላእክት/
ለ. ወር በገባ በ21ኛው ቀን በዓለ ማርያም /በዓለ ቅዱሳን/
ሐ. ወር በገባ በ29ኛው ቀን በዓለ እግዚአብሔር ናቸው፡፡

"3ኛ በዓመት አንድ ቀን ብቻ የሚከበሩ የጌታ ተሰዐቱ ዐበይት በዓላት እነርሱም፡-



ሀ. በዓለ ጽንሰት /ትስብእት/ መጋቢት 29 ቀን
ለ. በዓለ ልደት ታኅሣሥ 29 ቀን
ሐ. በዓለ ጥምቀት ጥር 11 ቀን
መ. በዓለ ሆሣዕና ዐቢይ ጾም በገባ በስምንተኛው እሑድ ቀን
ሠ. በዓለ ስቅለት ከሆሣዕና እሑድ ቀጥሎ በአለው ዐርብ ቀን
ረ. በዓለ ትንሣኤ ከስቅለት ዐርብ ቀጥሎ በሚውለው እሑድ ቀን
ሰ. በዓለ ዕርገት በዓለ ትንሣኤ በተከበረ በ40ኛው ዕለት ሐሙስ ቀን
ሸ. በዓለ ጰራቅሊጦስ በዓለ ትንሣኤ በተከበረ በ50ኛው ዕለት እሑድ ቀን
ቀ. በዓለ ደብረ ታቦር ነሐሴ 13 ቀን ናቸው

"4ኛ በዓመት አንድ ቀን ብቻ በወል የሚከበሩ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በዓላት፡-

ሀ. ልደታ ግንቦት 1 ቀን
ለ. በዓለ በኣታ ውስተ ቤተ መቅደስ ታ?ሣሥ 3 ቀን
ሐ. በዓለ ጽዮን በኢትዮጵያ ጎዳር 21 ቀን
መ. በዓለ አስተርእዮታ ጥር 21 ቀን
ሠ. በዓለ ኪዳነ ምሕረት የካቲትና ነሐሴ 16 ቀን ናቸው፡፡

"5ኛ በዓመት አንድ ቀን ብቻ በወል የሚከበሩ የመላእክት በዓላት፡-

ሀ. በዓለ ቅዱስ ሚካኤል ጎዳር 12 እና ሰኔ 12 ቀን
ለ. በዓለ ቅዱስ ገብርኤል ታኅሣሥ 19 ቀን ናቸው፡፡
ሐ. የሌሎች ቅዱሳን መላእክት ቅዱሳን ሐዋርያት፣ ቅዱሳን ሰማዕታትና ጻድቃን ዓመታውያን በዓላት ግን በየስማቸው ቤተ ክርስቲያን በታነጸበት ቦታ በአጥቢያ ክልል በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ይከበራል፡፡

"6ኛ የቅዱሳን መላእክት፣ የቅዱሳን ሐዋርያት፣ የቅዱሳን ሰማዕታትና የጻድቃን ወርኃውያን በዓላት በየአጥቢያቸው በማኅሌትና በቅዳሴ ብቻ ይታሰባሉ፡፡" ይላል፡፡

ዛሬ ቅዱስ ሲኖዶስ እነዚህ ጥናቶችና የጊዜውን ትውልድ ሃይማኖታዊ አመለካከት ተመልክቶ ስለ አጽዋማትም ሆነ ስለ በዓላት አከባበር የማሻሻያውን ውሳኔ ማስተላለፍና ሥርዓት መሥራት ይችላል፡፡

21 አንቀጾች በአሉት በሐዋርያት ሲኖዶስ በ30ኛው ትእዛዝ "ከሚገባው ሥራ ያጉደልነው ቢኖር ለሠላችንም የእግዚአብሔር መንፈስ አሰንና እናንተ በሚገባ ፍረዱ" እንዲሁም በ35ኛው ትእዛዝ ከእኛ ምንም ያስቀረነው ቢኖር ኤጲስ ቆጳሱ ያሳስብ፡፡" በ47ኛው ትእዛዝም "የተወደዳችሁ ምእመናን ሆይ ከእኛ ምንም የቀረ ቢኖር እርሱንም ለሚገባው ሰው እግዚአብሔር ይገለጥለት፣ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሁከትና ወደ ወደብ ትደርስ ዘንድ" የሚለው የኋላ አባቶች የማሻሻያ ሥርዓት ለመሥራት የሚችሉ መሆናቸን የሚያመለክት የማሻሻያ ቀኖና ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በዚያን ጊዜ በነበሩት አባቶች እያደረ ሥራ ያሠራቸውና ይመራቸው እንደነበረ በየጊዜው በሚነሡ ብዙዓን አባቶች እያደረ እንደሚያሠራቸውና እንደሚመራቸው ይታመናል፡፡ የዚያን ጊዜው የዛሬ፣ የነዚያም አምላክ የእነዚህ አምላክ ነውና፡፡

"ከተጋብኦትነ ይኩን በከመ ተጋብኦቶሙ ለአርዳኢከ፤ አንተ ዘአሙንቱ፣ ወአንተ ዘለነ፣ አንተ ዘአሚሃ ወአንተ ዘይእዜ፣ ዚአከ ሰማያት ወዚአከ ምድር" መሰብሰባችን እንደ ደቀ መዛሙርትህ መሰብሰብ ይሁን፣ የእነርሱ አንተ ነህ የእኛም አንተ ነህ የዚያን ጊዜው አንተ ነህ የዛሬውም አንተ ነህ ሰማያት የአንተ ናቸው ምድርም የአንተ ናት" (ቅዱሠሰስቱ ምእት ም:4፣32-34) እንዲል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 3

## በትምህርትና በማኅበራዊ አገልግሎት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያበረከተችው አስተዋጽኦ

የዚህ ጽሑፍ አጭር ዓላማ በጥናትና በተከታታይነት ሳይቋረጥ የቆየውንና ያለውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትምህርትና የማኅበራዊ አገልግሎት አስተዋጽኦን በመገምገም የተበረከተውን ድርሻ እስከ ሁለተኛው ምዕት ዓመት ያለውን በመዳሰስ ለአንባቢ ለማቅረብ ነው፡፡

ስለ ቤተክርስቲያን ትምህርት ታሪካዊ አመጣጥ፣ ሥርዓት ትምህርት፣ እንዲሁም አገልግሎት መረጃችን በመሰብሰብና በመተንተን ግልጽ የሆኑ ማስረጃች ተገኝተዋል፡፡ አቢያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት እ.አ.አ ከ1896 ከመቋቋሙ በፊትና ከዚያም በኋላ ከፍተኛ የትምህርት አገልግሎት ለሕዝብ የሚሰጡ ተቋማት አሏቸው፡፡

እነዚህም ለሕዝብ ጠቀሜታ ያለው ትምህርት የሚሰጡ ብቸኛ ተቋማት ነበሩ፡፡ አሁንም ናቸው፡፡ ሥርዓታቸውና ይዘታቸውም ከቤተ ክርስቲያኒቷ ተልእኮ ጋር የተቆራኙ እንደነበሩ ብዙ ማስረጃች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሥርዓተ ትምህርቱ፣ የትምህርት ዓይነትና የሚፈጀው ጊዜ፣ ለትምህርት ጥራትና ጥልቀት ወሳኝነት እንዳለው የጽሑፉ ትንታኔ ያስረዳል፡፡

ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን፣ የግሪክ ኦርቶዶክስ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የትምህርቶችን ይዘት በማነጻጸር ግንኙነቶችንና ልዩነቶችን ጽሑፉ በሚገባ ያስረዳል፡፡

የመጀመሪያው የጹሑፍ ክፍል የሰነድ መረጃችን መነሻ በማድረግ ዝርዝር ግኝት ያቀረበ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ በአዲስ አበባ 3 አካባቢች ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በትምህርትና በማሕበራዊ አገልግሎት መስክ የምትሰጠውን ድጋፍ አጉልቶ ለማሳየት የተደረገ የጥናት ውጤት ቀርቧል፡፡ ይህ የጥናት ውጤት ቤተ ክርስቲያኒቷ በትምህርትና በማሕበራዊ አገልግሎት ረገድ አሁንም ዘመናዊ አቅጣጫ ይዛ በመራመድ ላይ መሆኗን ለማስረዳት የተሞከረ ጥረት ነው፡፡

የዚህን የሁለተኛውን ክፍል ጥናት በዋናው ተመራማሪ አቀነባባሪነት ያካሔዱት ሊቀ ጎሩያን ጌታቸው ፣ጎዴ ሲሆኑ ለጽሑፉ ጥራትና ጥልቀት አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ የጽሑፉ ሁለተኛው ክፍልም በተ ክርስቲያኒቱ ሕዝብን አጋር በማድረግ የትምህርት፣ የጤና፣ የማኅበራዊ አገልግሎትና የልማት አቅጣጫ መንደፍን ያረጋግጣል፡፡ ለዚህም ገለፃና ግኝት ሊቀ ጎሩያን ጌታቸው ፣ጎዴን እናመሰግናቸዋለን፡፡

የ፳፤ ዓመት በዓል አከባበር በሚከናወንበት ወቅት ይህ ጽሑፍ በመዘጋጀቱ

/ሀ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ማዕከል ሆና መገኘቷና ከኢትዮጵያ ማሕበራዊ ግንኙነት ጋር ጠንካራና የማያቋርጥ ስንሰለት እንዳላት፡

/ለ/ ቅርስንና ታሪክን እንዲሁም ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ ቀዳሚት ብሔራዊትና ሃይማኖታዊት ተቋም እንደሆነች

/ሐ/ አቢያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በዓለምና በአፍሪቃ ውስጥ በተደራጀ መልክ የዕውቀትና የአስተሳሰብ የአመለካከትና የክህሎት መረጃ ማዕከላት እንደሆኑ ማስረጃ ይሰጣል፡፡



# ክፍል 1

## ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት ወቅታዊ ግምገማ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ረዥም ታሪክ አለው፡፡ ከ4000 ዓመታት በፊት የሳባውያን ፊደላት በጥቅም ላይ መዋል ከጀመሩ አንስቶ የኢትዮጵያ የትምህርት አስተሰሰብ እንደመጣ ይታመናል፡፡ /ዶሬስ. ጄ 1962/፡፡ ከዚያም የግዕዝ ቋንቋና ፊደል ዳብሮ የመማሪያና የመገናኛ አገልግሎት በተሰጠበት ዘመን የጥንት ትምህርት መሠረት እንደተጣለ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ /A-2/

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለፉት 2000 ዓመታት ውስጥ ትምህርትን በማደበር፣ በማስፋፋትና በማስራጨት ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች፡፡

የአሁኑ የቤተ ክርስቲያን የትምህርት ሥርዓት የክርስትና ሃይማኖት በይፋ ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ከ፳ኛው ክፍለ ዘመን እንደ ጀመረ የታሪክ ጸሐፊች ያወሳሉ፡፡ /A-3/

አንድ አንድ የታሪክ ባለሙያች የቅዱስ ያሬድ ዜማ የተጀመረበትን የ6ኛውን ክፍለ ዘመን ወርቃማው ጊዜ ብለው ይዘክሩታል፡፡ እንዲሁም በ1300 - 1500 ክፍለ ዘመናት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለወንዶች ልጆችና ኋላም ለሴቶች ጭምር ትምህርት በሰፊው ይሰጥ እንደነበረ መረጃች ያጠናክሩታል፡፡

በዚህ ዘመን ወንዶች በብዛት መምህራንና ፡አገልጋዮች ሲሆኑ ሴቶች በአንድ አንድ ቦታዎች የመምህርነት ደረጃ እንዳገኙ ይታወቃል፡፡

መሠረታዊው የትምህርቱ ይዘት ንባብና የቃል ትምህርት እንዲሁም የተወሰነ ክቅዱሳት መጽሐፍት ተሰይተው የወጡ ትምህርቶች ለወጣቶች ይሰጡ ነበር፡፡ ከፊደል ንባብ ቀጥሎ መልእክተ ዮሐንስ ቀዳማዊ ከዚያም ክፍ ሲል በንባብ ቤት ዳዊት መድገም የትምህርቱ መሠረት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

እነዚህና ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች በግዕዝ ቋንቋ ይሰጡ ነበር፡፡ /A-6/

በግዕዝ የተጻፉ ዋና መረጃ ጽሑፎች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ የሃይማኖት ጽሑፎች ናቸው፡፡ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፖንክረስት እጥንተው በዘረዘሩት መሠረት በብሪቲሽ ሙዚየም ውስጥ እ.አ.አ ከ1877 ዓ.ም. በፊት 12 የመጽሐፍ ቅዱስ አንድምታ፣ 23 ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን የጸሎት፣ የግብረ-ገብ ትምህርት መስጫ መጻሕፍት እንዲሁም 39 የሃይማኖትና ነገረ መለኮት /ቲዎሎጂ/ መጽሐፎች ይገኛሉ፡፡

በሀገርም ሆነ በውጭ መጻሕፍት መገኘታቸው ከጥንት ጀምሮ ትምህርት በኢትዮጵያ ሥር የሰደደ መሆኑን ያመለክታል፡፡ /A-6/

በኢትዮጵያ መንበረ ፖትሪያርክ የትምህርት መምሪያ የተቀነባበረው መሠረታዊ መረጃ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ጊዜ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን አንድ ትምህርት ቤት አሠርቶ አገልግሎት እንደሚሰጥ ነው፡፡ /A-7/

አሁን ያሉትን የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና ደብሮችን ስንመለከት በድምሩ ቢያንስ 35=250 ይሆናሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ 21=150 የሚሆኑት የተጠናከረና ዕውቅና ያገኙ ትምህርት ቤቶች አሏቸው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ተቋማት ለሕብረተሰቡ የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በእያንዳንዱ ደብር ቁጥሩ አነስተኛ የማይባል /50-60/ ተማሪች ቢገኙም ትምህርቱን ለማጠናቀቅና ምሁራንነት ለማግኘት የተመደበው ጊዜ ብዙና አታካች ነው፡፡ እንዲሁም የትምህርት ቁሳቁስ የመጻሕፍት መረጃዎች ለተማሪችና ለአስተማሪች መቀመጫ በቂ እንዳልሆኑ ለመረዳት አያዳግትም፡፡ የትምህርቱም ትኩረት በቃል የሚተላለፍ ሲሆን የተነገውን አስተሳሰብ በተራ ለሌላው ማስተላለፍ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የተመረጡ ተማሪች ወደ ከፍተኛ የቤተክርስቲያን ትምህርት ለመሸጋገርና ዕውቀታቸው የሳተ እንዲሆን ይቻል ዘንድ ከ8-15 ዓመት አብነት ተብለው በሚጠሩ ትምህርት ቤቶች ከቆዩ በኋላ ስለችሎታቸው ምስክርነት ያገኛሉ፡፡

እነዚህ የአብነት ትምህርት ቤቶች በሚከተሉት ከፍተኛ ያትምህርት እርከኖች ይከፈላሉ፡፡

ሀ/ ዜማ ቤት

ለ/ ቅኔ ቤት

ሐ/ መጻሕፍት ቤት

ማተሚያ ቤቶች ሳይቋቋሙና ደራሲያን ባልበዙባቸው ዘመናት የማስተማሩ ዘዴ ከብዙ መቶ ዓመቶች በፊት ይደረጉ የነበሩትን የወረሰ ነው፡፡ የመማር ማስተማሩ ዘዴ በመካከለኛው ዘመን በአውሮፖ በየገዳማቱ መነኮሳት ይሰጡት ከነበረው ትምህርት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ጥንታዊያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች የሚሰጡት የትምህርት ዓይነትና ዘዴ ልዩ ባሕርይና ጠባይ የሥነ-ሥርዓትና የሥነ-ቋንቋ ስልት ስለአለው አስተሳሰብን በግዕዝና በአማርኛ መግለፅ ነው፡፡

ተማሪዎች የትምህርት ጥማቸውን ለማርካት ብዙ እንቅፋቶችና የኑሮ ጋሬጣዎች እየገጠማቸው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ሩቅ ቦታ ይጓዙ ነበር፡፡ የዚህ ዓይነት የትምህርት ጥረት ዋና ዓላማም ዕውቀትን ለማዳበር፣ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለመስጠት፣ በቤተክርስቲያን ተከብሮ መምህር ለመሆን፣ ጎብረተሰብንና አካባቢን ለማገልገል ሲሆን እነዚህን ክህሎቶች ለማግኘት ወደ አብነት ትምህርት ቤቶች መግባት ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የትምህርትና ሥልጠና መምሪያ አቀነባብሮ ባስቀመጠው መረጃ መሠረት በአሁኑ ጊዜ 5389 መምህራንና 125000 ተማሪች በቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት አንዞች ውስጥ 396 ተማሪች በ29 የአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ለእነዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መጠለያ፣ ምግብ የመምህራን ደሞዝ ትችላለች፡፡ የአብነት ት/ቤቶች በተለይ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ጎልተው ይታያሉ፡፡

ሠንጠረዥ አንድ፡ የአብነት ት/ቤቶች ብዛት በሀገረ ስብከት ደረጃ

| ሀገረ ስብከት | የአብነት ትምህርተ ቤቶች ብዛት |
|---|---|
| አዲስ አበባ | 2 |
| አርሲ | 1 |
| ጎጃም | 5 |
| ጎንደር | 6 |
| ሸዋ | 6 |
| ትግራይ | 4 |
| ወሎ | 5 |
| ድምር | 29 |

ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የትምህርትና ሥልጠና መምሪያ፡ 1994





ከላይ ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ረዥም ጉዞ ውስጥ ቤተክርስቲያን በሥነ-ጽሑፍና እንዲሁም ሁለገብ በሆነ መልኩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረገችና እያደረገች እንዳለ ያስረዳል፡፡

ይህንን ጉዳይ በቅርብ ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ ዘመናዊ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተለይም ዳኞችን አስልጥኖ በማቅረብ የቤተመንግሥትን ከፍተኛ ሹማምንት ለይቶ አዳብሮ በመመልመል፣ አስፈጻሚችን እንዲሁም በመላ ሀገሪቱ የመንግሥት አገልጋዮችንና ከፍተኛ ክህሎትና ብልሀት ያላቸውን አስተዳዳሪች ስታቀርብ ኖራለች፡፡ እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የሀገሪቱን ቅዱሳት መጻሕፍትና ባህላዊ ቅርስ በመጠበቅ ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከመንግሥት ጋር በመሆን ቅርስን ስትጠብቅ መቆየትዋ በተደጋጋሚ የተነገረ ቢሆንም በሥነ-መንግሥት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥም ከፍተኛ ቦታ እንዳላት የታወቀ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ላለፉት ዘመናት የብሔራዊ አንድነት ምልክት እንደነበረችም ታሪክ ያወሳል፡፡

ምንም እንኳን ከምዕራባውያን ጋር የነበራት ግንኙነት ውሱን ቢሆንም በ15ኛው ክፍለ ዘመን አየሰሳዊያን /ጀስዩትስ/ የተባሉ የፓርቸጊዝ ሚሲዮናውያን መጥተው መጠነኛ ትውውቅ አድርገው ተመልሰዋል፡፡

በየዘመኑ የውጭ ጠላቶች ኢትዮጵያንና፣ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ዓላማ ሲያጨናገፉ ቆይተዋል፡፡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የፓርቸጊዝ ወታደሮች መጥተው የተወሰነ ድጋፍ ባይሰጡ ኖሮ የኢትዮጵያ ቅርስም ሆነ የትምህርት ተቋማት በግራኝ መሐመድ ወድመው ነበር፡፡ እንዲሁም 1927/28 ዓ.ም ፋሺስት ኢጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር የክርስቲያን ተቋማትን በማውደም በዘመኑ የነበሩ አቡነ ጴጥሮስንና ሌሎች የቤተክርስቲያን አገልጋዮችንም በግፍ ገድሏል፡፡ በተለይ አያሌ ግድያ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች የደብረ ሊባኖስ ገዳምና ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በ1966 ዓ.ም የፊኑዳውን አብዮት ተከትሎ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ጨምሮ ብዙ ካህናት በግፍ ተገድለዋል፡፡ ከነዚህ ዘመናት ወዲህ ስለቤተክርስቲያን ትምህርትና ውድ ስለሆነው የቤተክርስቲያን ቅርስ ለመነጋገርና በከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተገቢው ምርምርና ጥናት ሊካሄድ አልቻለም፡፡

ይሁን እንጂ በምእመናን ጠንካራ እምነትና በአገልጋዮችም ያላሰለሰ ጥንካሬ የክርስቲያን እምነትና ትምህርት ወደኋላ ከመሄድ ይልቅ ወደፊት እየገሰገሰ ራሱን ከዘመናዊ ትምህርትና አስተሳሰብ ጋር ለማስተሳሰር ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

ሆኖም ባለጸጋና በኩራት የምንናገርለት ቅርሳችን የትምህርት ውጤት ስለሆነ ከዘመናዊ የትምህርት ሥርዓት ጋር መዋሐድ ይኖርበታል፡፡ በሌሎች ሀገሮች የቤተክርስቲያን ትምህርት የሥጋዊውን ትምህርት አቅር ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ለመድረስ ችሏል፡፡ በኢትዮጵያችን ግን በተለይ በ1938 - 1940 ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ እንዲጠናከር በመንግሥት ሲወሰን የቤተክርስቲያንን ትምህርት መነሻ ከማድረግ ይልቅ የምዕራቡን ትምህርት መነሻ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህ ረገድ አዲሱ ትውልድ የምዕራቡን የትምህርት ዘይቤ እያጎላና አብነት እያረጋገጠ ሲሄድ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርት ግን ከመደበኛው ትምህርት ጋር ሊወዳደር አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል በሀገሪቱ ውስጥ ለብዙ ሺ ዘመናት የተጠራቀመው ዕውቀት በተፈጥሮ ሕግጋት መሠረት እያደገ መምጣት ሲገባው በተቀነባበረ የውጭ ሴራ ምክንያት ጥንታዊው የኢትዮጵያ ትምህርት የዘመናዊ ትምህርት አካል ባለመሆኑ ዘመናዊ ትምህርትም በኢትዮጵያውያን አዕምሮ ሰርቶ ሳይገባና መሠረት ሳይያዝ እንደተንሳፈፈ ይገኛል ይህ ሁኔታ የተወሰኑ መስኮች ለምሳሌ እንደዘመኑ ህክምና ምህንድስናና ልዩ ልዩ ዘዴችን አያካትትም፡፡ይህን ሁኔታ የገመገሙ የትምህርት ባለሙያች ጉዳዩ በከፍተኛ ደረጃ እያሳሰባቸው ይገኛል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የቤተክርስቲያን ትምህርት ልማትንና የእርሻ ሳይንስን በማዳበር፣ የሕክምና ትምህርትን በማስፋፋት እንዲሁም ማኅበራዊ አገልግሎትን በመስጠት ከፍተኛ አጋር ለመሆን ይችላል። ቤተክርስቲያኒ ፍላጐቷን እውን ለማድረግ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ትይዩ ሥጋዊ ትምህርትን በመስጠት በለውጥ ሂደት ውስጥ ካለው ዓለም ጋር እኩል ግንዛቤ እንዲኖራት ባላት የተጠራቀመ ልምድ እና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ ትምህርትን ለማስፋፋት ጥረት አድርጋለች። በ1937 ዓ.ም. ሥጋዊውንና መንፈሳዊውን ትምህርት ያጣመረ ትምህርት የሚሰጡ ተቋማትን በማደራጀት በተለይ የቅድስት ሥላሴ ትምህርት ቤት ተከፍቷል፤ ይህ ትምህርት ቤት በደርግ ዘመን ተዘግቶ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በድግሪና በዲፕሎማ ትምህርት እየሰጠ ይገኛል።

በቀድሞቹ ዘመን ትምህርት ቤቱ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥባቸው ልዩ ልዩ ክፍሎች ስለነበሩት የመንፈስ አባቶችን ብቻ ሳይሆን የሚሊታሪ ባለሙያዎችን፣ የአየር ኃይል አብራሪዎችን፣ መሐንዲሶችን፣ ሐኪሞችን፣ የሕግ ሊቆችን፣ አስተዳዳሪችንም አፍርቷል።

በመንፈሳዊ አባቶች አንጻር ደግሞ፣ ፖትርያርኮችን፣ ሊቃነ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን፣ ሰባኪያንና ተመራማሪችን አስልጥኖ በማስመረቅ ትምህርት ቤቱ አሁን ባለበት ኮሌጅ ደረጃ ተመቻችቶ ይገኛል።

የኮሌጁ ዓላማ በግልፅ በጽሁፍ እንደተቀመጠው ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት ከአንድ ኮሌጅ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ተሸጋግሮ የዩኒቨርስቲ ስም የሚያገኝበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ከዚህም ኮሌጅ ሰላ በመቀሌ የፍሬምናጦስ ከሳቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅና በአዲስ አበባ ኮልፌ ሰዋሰው ብርሃን ያሉት ከፍተኛ ተቋማት የመስፋፋት እድላቸው ሰፊ ነው። በሌሎችም በየሀገረ ስብከቱ አንድ አንድ እራሱን የቻለ ኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ለማቋማቋም ምኞትና ዕቅድ አለ።

## 1.2. የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የጊዜ ሰሌዳ ቀመር

ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተክርስቲያን ትምህርት የሚፈጀውን የጊዜ ሁኔታ በየወቅቱ አንስቶ እንደተወያየበት መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህ ረገድ የአብነት ትምህርት ቤቶችን በተመለከተ ዝርዝር ጥናት እንዲከናወን ተደርጎ ልዩ ልዩ አማራጭ ሐሳቦች ቀርበዋል። እነዚህም አማራጮች በዝርዝር ሲታዩ የድርጊት ፕሮግራምና ሥርዓተ ትምህርት እንደሚያስፈልግና የማሻሻያ ሐሳቦችንም ጠቁመዋል።

ሠንጠረዥ ሁለት ለአብነት ትምህርት ቤቶች የጊዜ ማሻሻያና ቅድመ ሁኔታችን የሚያመለክት

| ተቁ | መስክ | ቅድመ ሁኔታና ተጨማሪ ትምህርቶች | መመመረቂያ /መመሻሸሪ | ድረ ያምረቃ | ጠቅላላ የትክክሎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ብለይ ኪዳን | ቅኔ እና ጸዋተወ ዜማ | 3 | 5 | 8 |
| 2 | አዲስ ኪዳን | ---------- | 3 | 4 | 7 |
| 3 | መፍኑተ ሊቃ ኦሪሃት | ---------- | 3 | 4 | 7 |
| 4 | መፍኑተ መነኮሳት | ---------- | 3 | 4 | 7 |
| 5 | ቅኔ | ቅኔ እስከ ዘራፊነት ዜማ እስከ አቋቋም | 4 | 1 | 4 |
| 6 | ድጓ | ቅኔና ጸዋተወ ዜማ ዝማሬ መዋስዕት እና አቋቋም | 2 | - | 2 |
| 7 | አቋቋም | ቅኔና ጸዋተወ ዜማና ዝማሬና መዋስዕት አቋቋም | 2 | - | 2 |
| 8 | ዝማሬ መዋስዕት | ቅኔ ናጸዋተወ ዜማና ዝማሬ መዋስዕት አቋቋም | 1 | - | 1 |
| 9 | ቅዳሴ | ቅኔና ዜማ እስከ አቋቋም | 2 | - | 2 |

ምንጭ፡ የትምህርትና ስልጠና መምሪያነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋዶ ቤተክርስቲያን መንበረ ፖትሪያሪክ 1995





ከላይ በሠንጠረዡ እንደታየው የትምህርቱ መጠንና ዓይነት እንዲሁም ጥልቀት የሚለካው በአስተማሪዎች ጥራት፣ በሥርዓተ ትምህርቱ ይዘት እንዲሁም ሥርዓተ ትምህርቱን ለማጠናቀቅ በሚፈጀው ጊዜ ነው። አንዱን የትምህርት ዓይነትና ደረጃ ተማሪው ሲፈጽም ወደ ሌላው ለመሸጋገር እንዲረዳው ይፋ የሆኑ መስኪያች ያስፈልጉታል። ስለዚህ የትምህርት ሥርዓት ተነድፎ የትምህርት አቅጣጫና ዘዴ አብሮ መታየት ይኖርበታል።

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ሁሉንም ማሟላት ባይቻልም የወደፊቱ የቤተክርስቲያን አቅጣጫ ከቤተክርስቲያኒቱ የትምህርት ሥርዓት ውጭ ካሉ ትምህርት ቤቶች ጋር ትይዩ መሆን ይኖርበታል ወይም ልቆ መገኘት አለበት። ይህም የትምህርት ሥርዓት አቅጣጫ ብዙ ተማሪችን እና ወላጆችን የሚስብ ስለሚሆን ለወደፊቱ በየደረጃው የሚፈለጉ መረችን በዓይነትና በጥራት በማስመረት በተለያዩ ማህበራዊና መንፈሳዊ ዘርፎች አስተዋፅኦ ለማበረከት ያስችላል።

ብዙ የትምህርት ባለሙያች በጋራ የደረሰበት ግንዛቤ እንደሚያመለክተን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ከዘመናዊ ትምህርት ጋር አጣምሮ ትምህርት ቤቶችንም ዘመናዊ ማድረግ ከተቻለ እስከ አሁን እንደተደረገው ሁሉ በውጭ ሴራ ምክንያት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርት ሊቀጭጭ እንደማይችል ነው። ይህም የትምህርት ባለሙያች ግኝት በአንገዝ የተደገፈ ነው። አገዙ እንደሚያስረዳው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ከ40 ሚሊዮን ያላነሱ ሲሆን የእነዚህ ተከታዮች የትምህርት ጥላጐት በቀላሉ የማይገመት በመሆኑ ነው።

የዘመናዊ ሥጋዊ ትምህርትንና የቤተክርስቲያንን ባህላዊ ትምህርት ሚዛን ለማስተካከል እና እንዲሁም የዘመናዊ የማኅበራዊ ኑሮ ፍላጐትና የቤተክርስቲያኒቱን የወደፊት አቅጣጫ ለማጣጣም አዲስ የትምህርት ምዕራፍ ቤተክርስቲያኒ መተለም አለባት። እነዚሁ የትምህርት ባለሙያች እንደሚያሳስቡት ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ ትምህርም ለመሸጋገር ይቻል ዘንድ ወይም ባህላዊ ትምህርትን ከዘመናዊ ትምህርት ጋር ለማዋሐድ ግንዛቤ፣ የአማርኛና የሌሎች ነባር ቋንቋዎች መዳበር አስፈላጊ እንደሆነ ያምናሉ።

አንድ ተማሪ ብዙ ዘመን የፈጀበትን የትምህርት ችሎታውን አስመስክሮ ወደ ትውልድ አገሩ ከተመለሰ በኋላ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ሳለ እንደ ችሎታው መጠን በመያውና በግብረገብነቱ ተመርጦ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት የተለያዩ የማዕረግ ስሞች ይሰጡታል።

## 1.3. የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማበብ

ከ35 ዓመታት በፊት የሰንበት ትምህርት ቤቶች በቃለ አዋዲ ተመስርተዋል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በ1971 ዓ.ም. በደርግ በጭካኔ ከመገደላቸው በፊት ለቤተክርስቲያኒቱ የሩቅ ራእይ መፍቻ እንዲሆኑ ያቋቋሙት ነው። ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት እነዚህ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ቅስቀሳና ትምህርት ለወጣቶች በመስጠት ላይ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ 2,706,000 አባላት ያሏቸው 8610 የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ይታወቃል።

በተቋም ደረጃ 35ሺ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ሲኖሩ 4 ሚሊዮን ወጣቶች በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚገለገሉ ይታወቃል። ይህ 4 ሚሊዮን የሚሆነው በወጣትነት ያለው ሕዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ጋር ግንኙነት እንዳለው መረጃዎች ያመለክታሉ። የሰንበት ትምህርት ቤቶች በጥቅሉ ከመቶ 68 የሚሆነውን በወጣትነት ዕድሜ ክልል ያለውን የሀገሪቱን አካል ያስተምራሉ። በአማካይ ግን በእያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ 315 ወጣቶች እንዳሉ ያመለክታል። ይህም በአስተተኛ ስሌት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

የሰንበት ት/ቤቶች አውታራቸውን ዘርግተው ፕሮግራማቸውን የሚያከናውኑት ከሥራ ሰዓት ውጪ ቅዳሜና እሁድ ነው፡፡ በስልጠናም በኩል ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጅተው ትምህርት ይሰጣሉ፡፡

የሥርዓተ ትምህርቱ ይዘት ስለቤተሰብ፣ ስለማህበራዊ ኑሮ፣ ስለወጣቶች ደህንነት፣ ስለዜግነት፣ ስለግብረገብነት፣ ስለሥነ-ተዋልዶ፣ በአጠቃላይ ስለአካባቢ ጤና ጥበቃ፣ ስለቤተክርስቲያን ሕግጋት፣ ስለወጣቶች መሪነት ትምህርት ይሰጣሉ፡፡ እንዲሁም ክርክርና ስነ-ጽሁፍ በማዘጋጀት ውድድርም ያደርጋሉ፡፡ በድራማ፣ በአካል እንቅስቃሴና በመዝሙር ወጣቱን ትውልድ ወደ ግብረገብነትና ወደ ቤተክርስቲያን በማግባባት ያስጠጉታል፡፡ እርስ በእርሳቸው ለመግባባትና ሥራቸውን ቀልጣፋ ለማድረግ መጽሐፎችንና ጋዜጦችን በማተምና በማሰራጨት ወጣት ላልሆነውም የጎብረተሰቡ አካል መረጃ እንዲደርስ ያደርጋሉ፡፡ ይህም እንቅስቃሴ ለወደፊት ለሚጠብቃቸው ኃላፊነት ዝግጁ ያደርጋቸዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የሰንበት ት/ቤቶች ወጣቶችን በማደራጀት በዛፍ ተከላ፣ በቅርስ ጥበቃ ታሪካዊ ቦታችንና ገዳማትን በመገብኘት ወጣቶችን በአእምሮ፣ በመንፈስ በአካልና በማኅበራዊ ዕድገት ያደብሯቸዋል፡፡ በክረምት ወራትም ከመደበኛው ትምህርት ጋር የተያያዘ ጥረትና ድጋፍ ማታም ሆነ ቀን እየሰጡ ደካማ ተማሪችን ይረዳሉ፡፡ ለድሆችና አረጋውያንም የገንዘብና የግብረ-ገብ ድጋፍ በየአብያተ ክርስቲያኑ እየዞሩ ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም አልፎ የእያንዳንዱን ቤተክርስቲያን የአስተዳደር ሂደት ለመርዳት በበጎ ፈቃደኝነት በኮሚቴ እየገቡ በተናጠልና በቡድን ድጋፍና የጉልበት ሥራ ያበረክታሉ፡፡ /A-8/

የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪች ከአንድ ወደ ሌላ ደረጃ በመሸጋገር ሰባክያንን፣ መምህራንና ዘማርያንን እየሰዩ ልምምድ እንዲያገኙ በማድረግ ለቤተክርስቲያን በጉፈቀደኛ አገልጋዮችን ያቀርባሉ፡፡

የሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሰጡት የትምህርት ዓይነትና ስርዓተ ትምህርቱም በጠቅላይ ቤተክህነት በተቋቋመው የሊቃውንት ጉባኤና በየሀገረ ስብከቱ በተሰየሙት የሊቃውንት ኮሚቴዎች እየታየ ይገመገማል፡፡ ይህ አዲስ የተዘጋጀው የሰንበት ትምህርት ቤቶች አቅጣጫና በትኩስ ኃይል የሚታገዘው እንቅስቃሴ የቤተክርስቲያንን ጥረት የሚደግፍ ስለመሆኑ አጠያያቂ አይሆንም፡፡

የወጣቱም ተሳትፎ እየሰፋና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በልዩ ልዩ ሙያ የሰለጠኑ ሰዎችን ቤተክርስቲያን ትሻለች፡፡ የወደፊቱ አቅጣጫም በየረድፉ የተማሩ ባለሙያዎችን የማቅረብ ሥራ ከፍተኛ የፋይናንስና የሰው ኃይልንም ይጠይቃል፡፡

ይህ አወንታ በየሀገረ ስብከቱ የአብያተ ክርስቲያናትና የገዳማት ብዛት እንዲሁም በመምጣቱም ጭምር የቤተክርስቲያንን አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልገው ሕዝብ ብዛት እየጨመረ መምጣቱ ልዩ ስልት የሚጠይቅና አገልግሎቱም ማህበራዊ ነክ የሆኑ ስትራቴጅዎችን መንደፍ የሚፈልግ ነው፡፡

የወደፊቱም አቅጣጫ ቤተክርስቲያኒቱ በመንፈሳዊ፣ በትምህርትና በማኅበራዊ አገልግሎት ላይ ያተኮረና ለምእመናንም በቂ የሆነ ጥቅም የሚያስገኝ ይሆናል፡፡

## ሠንጠረዥ ሦስት የተመረጡ ዓመታትን መነሻ በማድረግ በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ብዛት

| ተ.ቁ | ሀገረ ስብከት | አብያተ ክርስቲያናት ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 1960 | 1974 | 1993 |
| 1 | አዲስ አበባ | 40 | 113 | 226 |
| 2 | ሸዋ በድምሩ | 2547 | 3547 | 7094 |
| 3 | ትግራይ | 2272 | 2972 | 5944 |
| 4 | ወሎ | 1643 | 2643 | 5280 |
| 5 | ጎንደር | 2527 | 2927 | 5854 |
| 6 | ጐጃም | 2887 | 3111 | 6222 |





| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7 | ሀረር | 100 | 580 | 1160 |
| 8 | ሲዳማ | 166 | 210 | 420 |
| 9 | አርሲ | 292 | 300 | 600 |
| 10 | ወለጋ | 380 | 400 | 800 |
| 11 | ኢሲ.ባቦር | 160 | 201 | 402 |
| 12 | ከፋ | 206 | 306 | 612 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 127 | 227 | 454 |
| 14 | ባሌ | 71 | 91 | 182 |
| | ጠቅላላ ድምር | 14463 | 19643 | 35250 |

ምንጭ፡ ከመንበረ ፖትሪያርክ መዝገብ ቤት በጽ/ አቅራቢው የተቀነባበረ /1994/95/

ከላይ ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው የአብያተ ክርስቲያናት ብዛት በየዓመቱ እየጨመረ ስለሚሄድ የቤተክርስቲያን የትምህርት አገልግሎት እየሰፋ መሄዱን ነው፡፡ የተወሰኑ ናሙናችን ወስደን ስናመዛዝን ሦስት የስሌት ዓይነቶች ይገኛሉ፡፡

ሀ/ በአንድ ቤተ ክርስቲያን 20 ተማሪች ቢገኙ

ለ/ በአንድ ቤተ ክርስቲያን 10 ተማሪች ቢገኙ

ሐ/ በአንድ ቤተ ክርስቲያን 5 ተማሪች ቢገኙ

በ35250 አብያተ ክርስቲያናት ምን ያህል ተማሪች እንዳሉ መገመት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሃያ ተማሪች ቢገኙ በ35250 አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ /35250 X 20/ 705 ሺ ተማሪች አሉ ማለት ነው፡፡ ይህ አኃዝ በአነስተኛ ቢታሰብ እንጂ የተጋነነ አይደለም፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በልዩ ልዩ መልኩ የትምህርትና የማኅበራዊ አገልግሎት ቢያንስ ለአንድ ሚሊዮን ሕዝብ ትሰጣለች፡፡ ይህም በቀጥታ ከሚሰጠው ከሃይማኖት አገልግሎት ተጨማሪ ነው፡፡

ስለዚህ ትንተና እንደ መዝጊያ የሚያገለግለው ፍሬ ሃሳብ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ባላት የረዥም ዘመን ታሪክ ውስጥ ትምህርትን እንደ ዋና አድርጋ በመያዝ የትምህርትን መዋቅር በማስፋፋት ቅርስና ታሪክ በብቸኝነት ስትጠብቅ በመቆየቷ በዓለም ውስጥ በተለይም በአፍሪቃ የተለየ ቦታ አላት፡፡

## ፲.፬. ለቤተክርስቲያን ትምህርት የጉልት ሥርዓት ያበረከተው አስተዋፅኦ

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከዚያም አልፎ እስከ አፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ የጉልት ሥርዓት ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ የውጭም ሆኑ የውስጥ ታሪክ ጸሐፊች አጉልተው ያሳያሉ፡፡

ጉልት ማለት መሳፍንቱ መሳፍንቱ እና ነገሥታቱ ካላቸው ንብረትና የመሬት ይዞታ ለቤተክርስቲያን ሙገሳ የትምህርት ማስፋፊያ እንዲውል በትክክል የሚሰጡት ሥርዓት ነው፡፡ በዘመኑ ይህ ሥርዓት በዘጎ ሀገራት ነበር እንጂ በሌላ አይተረጐምም ነበር፡፡ ምክንያቱም በጀርመን በፈረንሳይ በእንግሊዝና በሩሲያ የዚህ ዓይነት ሥርዓት ስለነበረና ቤተ ክርስቲያኖችም በዚህ ይጠቀሙ ስለነበር ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርትና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለማስፋፋት ነገሥታቱና መኳንንቱ ንብረታቸውን ለማውረስ /ማለትም፤ መሬት ተንቀሳቃሽና ተንቀሳቃሽ ያልሆነውን ሀብታቸውን ለቤተክርስቲያን በማስተላለፍ እንዲሁም ብርትና ውድ የሆኑ የማዕድናት ውጤት የሆኑ የክብር ጌጣጌጦችን ፣ ወርቅ፣ አልማዝና ዕንቁ መስቀሎችንና ሥነ ዕሑፎችን ለቤተክርስቲያን በማውረስና የቤተክርስቲያን ሀብቶች እንዲሆኑ በመናዘዝ በሕይወት እያሉም ሆነ ነፍስና ሥጋቸው ከተለየ በኋላ በቤተክርስቲያን በኩል የእግዚአብሔር ወዳጆችና ልጆች እንደሆኑ ያረጋግጡ ነበር፡፡

በአንፃሩ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የትምህርት፣ የጤና እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአመሠኙ የሚደገፉት በምእመናኑ ሀብትና ጉልበት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከ1966 ዓ.ም. ወዲህ መሬትና ንብረት በአብዮታዊ ውሳኔ የሶሻሊስት መንግሥት በመውረሱ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የገቢ ምንጭ ታግቶ ችግር ላይ ወድቆ ስለነበር ነው፡፡

የሚከተለው ማስረጃ እንደሚያሳየው ከ4ኛው ክፈለ ዘመን እስከ 17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከመንግሥት ጋር አንድም ሁለትም ሆና በሕጋዊ መንገድ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የባህላዊ ሚና ትጫወት ስለነበረ ነገሥታቱና መኳንንቱ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ውጭ ፋይዳ ያለው ውሳኔ አያደርጉም ነበር፡፡

የጉልቱ ሥርዓት በዚህ የተነሣ ቤተክርስቲያንን ሲያጠናክር ኖሯል፡፡ /A-12/



ከላይ የተዘረዘሩት ስጦታ አድራጊችና ተቀባዮች በዘመኑ በሀገረስብከት ደረጃ ሲታዩ ብዙ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በአንድ ት/ቤት የተማሪች ቁጥር የማይታወቅ ቢሆንም የመምህራን ቁጥር ግን በቂ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ መረጃ ቀደም ሲል የተቀነባበረ በመሆኑ በልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገር የተደረጉ ጥረቶችን ሙሉ በሙሉ ባያንፀባርቅም ለዚያን ጊዜ ጥረቶች ማስረጃ ይሆናል ብለን እናምናለን፡፡ በተመሳሳይ ዘመናትና ከዚያ በኋላም በእንግሊዝ አገር ኦክስፎርድ፣ ካምብሪጅ፣ ቅዱስ አንድርያስ ዩኒቨርስቲዎች በነገሥታት መሬት በጉልት መልክ የተሰጡ ናቸው፡፡



በጀርመን በስዊድን በኢጣሊያንና በፈረንሳይ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎችም በሙሉ በጉልት መልክ ነገሥታቶቹ የሰጧቸውና ተከታዩ ትውልድ ያዳበሯቸው ናቸው፡፡ እንዲሁም በህንድ ሀገር ቀደም ሲል አዩር ቬዲክ (Ayur Vedick) ዩኒቨርስቲዎች በሀገሪቱ መሪች ድጋፍ መሬት እየተሰጣቸው ተቋቁመው ዛሬ ወደ ላቀ ደረጃ ደርሰዋል፡፡

ወደ 19ኛው ክፍለ ዘመን በምንጠጋበት ጊዜም በአሜሪካ የሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ፣ የየል ዩኒቨርስቲ፣ ፕሪስቶን ዩኒቨርስቲ፣ ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ፣ በርክሰይ ዩኒቨርስቲ፣ ስታንፎርድ ዩኒቨርስቲና ዊልያምስ ኮሌጅ የአካባቢ መሪዎች ለቤተክርስቲያን በሰጡት መሬትና ሀብት ተቋቁመው ወደ ላቀ ደረጃ የደረሱ ናቸው፡፡ እንዲሁም በጉልት ሥርዓት የተመሠረቱ ዩኒቨርስቲችና ኮሌጆች በብዛት ስለነበሩ ዛሬ ሥጋዊና መንፈሳዊ ትምህርት አጣምረው ወደ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ (Land Grant Colleges and Universities) አሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው መንግሥት ለቤተክርስቲያን ትምህርት እንዲሆን መሬትና ገንዘብ ይሰጣል እንጂ የቤተክርስቲያንን መሬትና ንብረት መውረስ በታሪክ እንደሌለ ነው፡፡ የዚህን ዓይነት የመንግሥትና የሕዝብ ድጋፍ ቤተክርስቲያን ካገኘች በየሀገረ ስብከቱ ያሉ ተቋማት የማይስፋፉበት ምክንያት የለም፡፡ በየሀገረ ስብከቱ ያሉ እነዚህ ተቋማት አገልግሎታቸው ለሕዝብም ለመንግሥትም ስለሆነ የሁሉንም ድጋፍ ይሻሉ፡፡

## 1.5. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የትምህርት ሥርዓት ከሌሎች ጥንታውያን የሮማን፣ የግሪክና የአይሁድ ሥርዓተ ትምህርቶች ጋር ያለው ተመሳሳይነትና ልዩነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጥንታዊትና ታሪካዊት በመሆኗ እንዲሁም መሠረትዋ የተጣለው ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲሆን ሀገርዋም የምትታወቅና በቅዱሳት መጻሕፍትም በተደጋጋሚ ስሟ የሚጠራ ስለሆነ ከርሷ እኩል ከነበሩ የክርስቲያንና የአይሁድ ጥንታዊ የትምህርት ሥርዓቶች ጋር ማነጻጸሩ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህም ንጽጽር ለአሁኑ ትውልድ ማሳሰቢያና ማነቃቂያ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡

ግሪክ፣ የሮማንና የአይሁድ የትምህርት ዘይቤዎች በሃይማኖት ደረጃ ተጀምረው ወደ ከፍተኛ የሳይንስና የማኅበራዊ ዕውቀት ማማኛ ተቋማት እንዲሆኑ ስለተደረገ የምዕራብ አገሮች የትምህርት ፍልስፍና ከእነዚህ ሦስት ምንጮች ተገኝቶ ልዩ ልዩ ቅርፅ በማውጣት ለህዝቦቻቸው ሕዝብና ለመላው ዓለም ጥቅም እየሰጡ ነው፡፡ በአንጻሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተመስርቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የቆየው የኢትዮጵያ የሃይማኖት የትምህርት ሥርዓት ግን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክስርስቲያን ብቻ በኃላፊነት ስለተተወ ከላይ የተጠቀሱት የምዕራባዊያን የትምህርት ፍልስፍና ዘዴ እንደ አውሮፖ አቆጣጣር ከ1945 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሀገራችን በመምጣት ባህላዊው ትምህርት በተወሰነ ደረጃ ብቻ እንዲታወቅ አድርገውታል፡፡ ይሁን እንጂ በ16ኛው ክፍለ ዘመን እና ከዚያ በፊት ያሉትን የትምህርት ፍልስፍናዎች፣ ዓላማዎች፣ ይዘቶች የማስተማር ዘዴችን ስንመለከት በግሪክ፣ በሮማውያን እንዲሁም በኢትዮጵያውን አልፎም በአይሁድ ሥርዓቶች ተካተው የነበሩ የትምህርት ዓይነቶች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

በዚያን ጊዜ የነበሩ የትምህርት ዓይነቶችም የዜጐችን ሕይወትና አመለካከት ሲያስተከክሉ ኖረዋል፡፡ የእነዚህ የሀገሪቱ የትምህርት ምንጭ ዓይነቶች አጉልተው ያሳዩት የነበረው፡-

ሀ/ ቤተሰብ የማኅበራዊ መሠረት መሆኑን፡፡ ትምህርትም ከቤተሰብ እንደሚጀምር አጉልተው ያስረዳሉ፡፡

ለ/ ከቤተሰብ በመረከብ ቤተክርስቲያንና የእምነት ተቋማት ወጣቶችን ማንበብ፣ መጻፍ፣ ሙዚቃ ማስተማር፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ማዳበርና መንፈሳዊ አመለካከታቸው እንዳይዛባ በምሁራን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይሰጡ ነበር፡፡

ይህ ከላይ የተጠቀሰውን ታሪካዊ ሐተታ የሚከተለው ሠንጠረዥ በአጭሩ ያስረዳል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ሠንጠረዥ አምስት፡ የጋራ የሆኑ የቤተክርስቲያን የትምህርት ዓይነቶች ከ1886 ዓ.ም በፊት

| ተ.ቁ | ትምህርቱን የሚሰጠው ሃይማኖት | የትምህርት ዓይነቶች | የትምህርት መስጫ/ቦታ |
|---|---|---|---|
| 1 | የላቲን ካቶሊክ ቤተርክስቲያን | - የላቲን ቋንቋ<br>- ራስን መግታት/አሴቲትዝም<br>- ሥነ ሥርዓት<br>- ቅዱሳተ መጽሐፍት<br>- ቅኔ<br>- ሙዚቃ<br>- ሕክምና<br>- ንባብ<br>- ቅዳሴ<br>- ሥነ ከዋክብት<br>- ግብረገብ | - ገዳማት<br>- አብያተ ክርስቲያናት<br>- የግል መኖሪያ ቤቶች<br>- ቤተመንግሥት<br>- የመኳንንት ችሎት |
| 2 | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን | - የግዕዝ ቋንቋ<br>- ቅዱሳት መጻሕፍት<br>- ቅኔ /poetry/<br>- ዜማ<br>- የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ<br>- የቤተክርስቲያን ሕግ<br>- መጽሐፈ መነኮሳት<br>- አቡሻሕር /astronomy/<br>- ፍትሐ ነገሥት<br>- ራስን መግታት/አሴቲትዝም<br>- ግብረ ገብነት<br>- ስዕል<br>- ግብርና<br>- አደጥበብ /የእንጨት፣ ሽማ፣ ቀርከሐ/<br>- ባህላዊ መድኃኒት/ሕክምና<br>- ንባብ<br>- ቅዳሴ | - ገዳማት<br>- አብያተ ክርስቲያናት<br>- ቤተመንግሥት<br>- የማሳፍንትና መኳንት ችሎት<br>- የግል ቤት |
| 3 | የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን | - ዜግነት<br>- መጽሐፍ ቅዱስ<br>- ግጥም<br>- የግሪክ ቋንቋ<br>- ሙዚቃ<br>- ራስን መግታት<br>- ግብረገብነት<br>- ሥነ ከዋክብት<br>- ስፖርት<br>- ሕክምና<br>- ታሪክ<br>- ፍልስፍና<br>- ሂሳብ | - ገዳማት<br>- አብያተ ክርስቲያናት<br>- ቤተ መንግሥት<br>- ግልፅ ቦታዎች<br>- የህዝብ መሰብሰብያ ቦታዎች<br>- ቤተሰብ |
| | | - የቤተሰብ ሕይወት<br>- ብሉይ ኪዳን | - ቤተሰብ<br>- ምኩራብ |
| 4 | የአይሁድ | - ታሪክ<br>- ሕግ<br>- ሥነ ከዋክብት<br>- ሂሳብ<br>- ሕክምና | |

www.ethiopianorthodox.org



ከላይ ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው የክርስቲያንና የአይሁድ የትምህርት ዘይቤዎች በአብዛኛው ተመሣሣይ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያውያንን ብቻ ለይተን ከሌሎቹ ጋር ስናመዛዝን የጥንቱ ሥርዓት እንደሚያዝዘው የትምህርቶች ዓይነት በመጠንም ሆነ በስፋትና በጥልቀት ዝምድና ያላቸው ቢመስልም ይዘታቸው የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌም ያህል በሥነ መለኮት የሃይማኖት ሥርዓትን ይዞ ትምህርቱ ሲሰጥ ከእያንዳንዳቸው እምነትና ታሪክ ጋር የተጣመረ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

አልውድ የተባለ ደራሲ የትምህርትን ታሪክ በሚገባ ሲተነትን ከላይ የተዘረዘሩትን የትምህርት ዓይነቶች ከዓረብኛ ተናጋሪች ለይቶ እነዚህ የዘመኑ ስልጣኔ ምንጮች ናቸው ይላል፡፡ ይህን ያለበት ምክንያት በሁሉም መስክ ተመሳሳይነት እንዳላቸው በማወቁ ነው፡፡

ሮራልይን የተባለ ደራሲ ደግሞ የጥንት የቤተክርስቲያን ትምህርት፡ በሚለው መጽሐፍ በምዕራፍ 2 እና 3 ላይ እንዳተተው ከላይ የተዘረዘሩት ትምህርቶች ከክርስቶስ የማስተማር ዘዴ ጋር የተገናዘቡ እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ ክርስቶስ መምህር ነበር፡፡ ሐዋርያትም ተማሪዎችና መምህራን ነበሩ፡፡ የክርስቲያን ትምህርትም የማስተማሪያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ሐዋርያትና ሌሎች ወጣቶች በእነዚህ ጽሑፎች ተምረው ሕዝብን በመስበክ አስተማሩ፣ የማስተማሪያ ቦታቸውም ምኩራቦች፣ አብያተ ክርስቲያናትና የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ናቸው ይላል፡፡

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርት የቤተክርስቲያን መሠረትና መሥራች ከሆነው ከክርስቶስ ጋር የተቆራኘ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን መረጃ በማየት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በትምህርትና በማኅበራዊ አገልግሎት ረገድ የምትሰጠው አገልግሎትም ምን ያህል ከሌሎች ጥንታዊያን የክርስቶስ ተቋሞች ጋር አንድነትና ልዩነት አላት? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ያስችላል፡፡

## 1.6 ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተደረገው ትንተና፡-

ሀ. ስለቤተክርስቲያን ትምህርት መግለጫ አግኝተናል

ለ. ስለአብነት ት/ቤቶች ጠቀሜታና ወደፊት ያላቸውን መልካም እድገት አዝማሚያ በመረጃ በተደገፈ ገለፃ አድርገናል፡፡

ሐ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የትምህርትና የማኅበራዊ አገልግሎት እየሰፋ መምጣቱንና በየሀገረ ስብከቱ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና አገልግሎታቸው በአይነት፣ በስፋትና በጥልቀት መስፋፋት ይችሉ ዘንድ የሕዝብ ድጋፍና አጋርነት እንዲኖራቸው ማስፈለጉን ጽሑፉ ዘርዝሯል፡፡

መ. በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያ የረዥም ዘመን ታሪክ መንግሥት በተለይም ነገሥታት፣ መኳንንትና መሳፍንት እንዲሁም ሀብትና ጉልበት ያለው ሁሉ ለቤተክርስቲያን ትምህርት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉን በመረጃ የታገዘ ገለፃ ቀርቧል፡፡ የጉልት ሥርዓት፣ በዘመኑ ቤተክርስቲያንና ቤተመንግሥት አንድም ሁለትም ስለነበሩ ታሪክን ትምህርትን እና ቅርስን በመጠበቅ በተደጋጋፊነት ያሳዩትን ባሕርይ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሠ. ከ18ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በአውሮፓም ሆነ በኢትዮጵያ ይሰጥ የነበረው የትምህርት ዓይነትና ይዘት ተመሣሣይ ሲሆን በአውሮፓ በሃይማኖት ተመስርቶ ከሃይማኖት ጋር ይሄድ የነበረው ትምህርት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ በኢትዮጵያ ግን የጥንቱ ቤተክርስቲያን ትምህርት ብቻውን ከቤተክርስቲያን ጋር ይገኛል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በበኩሏ በየአደባራቱና በየአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የትምህርት ተቋማትን በመክፈት ለሕዝብ ከመሠረተ ትምህርት ጀምሮ ትምህርትን ለማዳረስ ጥረት እያደረገች ነው፡፡

በከፍተኛ ደረጃም የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ የቅዱስ ጳውሎስ ሰዋስወ ብርሃን ኮሌጅ፣ ከተቱ ብርሃን መቀሌ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ የዝዋይና ሌሎች ትምህርት ቤቶች በጥሩ ሁኔታ እየተንቀሳቀሱ ስለሆነ እድገታቸው የማይገታ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

ወጣቶችን በማደራጀት በኩል የሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ በቀላሉ አይገመትም፡፡ የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪች ማኅበር በልዩ ልዩ ተቋማት ውስጥ ወጣቶችን ሲያስተምር ቆይቷል፡፡ ተምሮ ማስተማር ማህበር ለኢትዮጵያ ወጣቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው፡፡ ካለፉት 20 ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ጥሩ አገልግሎት እየሰጠ ያለው የማኅበረ ቅዱሳን ማኅበር በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ለቤተክርስቲያኒቱ አጋር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በጤናና በማኅበራዊ አገልግሎት ረገድ ቤተክርስቲያኒቱ ከመንግሥትና ከሕዝብ ጋር በመስለፍ ስለ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሽታ መከላከልና ምክር በመስጠት የተለያየ አሰራር ስልት ቀይሳ በቅንጅት በአገር አቀፍ እየተንቀሳቀቀች ትገኛለች፡፡

ሕጻናትና አረጋውያንንም በማስተማርና በመንከባከብ ረገድ በማዕከላዊ ደረጃ አንድ ከፍተኛ መዋቅር ዘርግታ ከውጭና ከውስጥ የሚገኝን ሀብትና ገንዘብ በማስተባበር በየክልሎች ሐጻናትንና አረጋውያንን የሚንከባከብ ኘሮግራም ዘርግታ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን በመርዳት ላይ ትገኛለች፡፡ ወደፊትም ልዩ ልዩ ሆስፒታሎችንና ክሊኒኮችን በማቋቋምና የጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን አገልግሎት ለመስጠት እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች፡፡

ከዚህ የመጀመሪያው ምዕራፍ የሚቀጥለው ጽሑፍ በአዲስ አበባ አካባቢ የተደረጉ ጥናቶችና የተገኙ ውጤቶችን የተመለከተ ይሆናል፡፡ ጥናቱ ያተኮረው በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል፣ በራጉኤልና በምስካዘ ኅዙናን መድኃኔዓለም አካባቢ በትምህርት፣ በማህበራዊ አገልግሎት እና እንዲሁም ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ማኅበራት ላይ ነው፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን ለማንዛቤ ይረዳ ዘንድ ለአንባቢያን ቀርቧል፡፡

ማኅደረ ስብሐት ቅድስት ፅዮን ጤና ሳይንስ ኮሌጅ





# ክፍል 2

## በአዲስ አበባ በተመረጡ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበራዊና ተቋማዊ ልማት ላይ የተደረገ ጥናት

2.1. ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ታሪካዊ መረጃ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን /ኢ.ኦ.ተ.ቤ/ ጥንታውያን ከሆኑና ኦርዮንታል ኦርቶዶክስ በመባል ከሚታወቁት፣ የኬልቄዶንን ጉባኤ ካልተቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ናት፡፡ እነዚህም የግብፅ ኦርቶዶክስ፣ የሶርያ፣ የአርመንና የሕንድ ማኅበር ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡

### ሀ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጭር ቅኝት /C-52/

ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንጮች እንደምንረዳው የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት የአይሁድ እምነት ገብቶ ለረጅም ዘመናት ቆይቷል፡፡ ከመረጃ ምንጮችም አንዱ «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለችን» የሚለው ጥቅስ ነው፡፡ /መዝ 67:31/

ስለ ኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያውያን የሚናገሩ ሌሎች መረጃዎች በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም በብሉይ ኪዳን ዘመን ኢትዮጵያውያን የእስራኤል አምላክ የሆነውን አንድ እግዚአብሔርን ያመልኩ እንደነበረ ያስረዳል፡፡ /B-19/

ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥተ ሳባ የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት ወደ ኢየሩሳሌም መሄዷና የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ኢትዮጵያ ከ982 ቅደመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ የብሉይ ኪዳንን እምነት ተቀብላ እንደ ነበር በግልጽ ያሳያሉ፡፡ /1ኛ ነገሥት 10:1-9//B-20/1

የብሉይ ኪዳን እምነት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከኢየሩሳሌም ውጭ መስራጨት እንደ ጀመረ ለክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ መግባት አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

በሦሳሳ አራት /34/ ዓመተ ምሕት ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ የነበረውና በወንጌላዊው ፊልጶስ የተጠመቀው የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ የገንዘብ ሚኒስትር ክርስትናን ለኢትዮጵያ አስተዋወቀ /የሐ.ሥ. 8:26-40/፡፡ ይሁንና በመንበረ ጵጵስና ደረጃ የቤተ ክርስቲያን መመሥረትና ሥጋ ወደሙን ማቀበል የተጀመረው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ይኸውም ፍሬምናጦስ በእስክንድርያው ፖትርያርክ አትናቴዎስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ የተሾመበት 330 ዓመተ ምሕረት ነበር፡፡ ፍሬምናጦስም ተሾሞ ወዲያው እንደመባ ወንጌልን መስበክ ሲጀምር ወደ ክርስትና ሃይማኖት የመለሳቸው የመጀመሪያቹ አማኞች ያንጊዜ መንበረ መንግሥታቸውን በአክሱም አድርገው ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ የነበሩት አብርሃ ወአጽብሐ ነበሩ፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእስክንድርያን ቤተክርስቲያን ፈለግ በመከተል የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የኦርቶዶክስ እምነት ማዕከል ሆነች፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኬልቄዶንን ጉባኤ ከማይቀበሉት የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አንዳ አንደመሆኗ፡-

1) የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቱንና ሥራውን ተቀብላ በጥብቅ ትከታተላለች

/C-52/ Taddesse Tamrat. Church and State in Ethiopia. pp 136-49. also pp 279
/B-19/ Tegew Hable Sellassie. Ancient and Medieval Ethiopia History. 1972 pp 95-96
/B-20/ The Queen of the South (the Queen of Kings/ Translated by Migiyel F Brooks /1995 pp 19-20

www.ethiopianorthodox.org

2) በሐዋርያትም ሥራና ትምህርት ጸንታ ኖራለች! ትኖራለችም፡፡

3) ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያደረጓቸውን የሦስቱን ጉባኤያት ውሳኔዎች ትቀበላለች፡፡ እነዚህም ጉባኤያት በ325 ዓ.ም የተደረገው የኒቅያ ጉባኤ፣ በ381 ዓ.ም. የተካሄደው የቁስጥንጥንያ ጉባኤና በ431 ዓ.ም. የተደረገው የኤፌሶን ጉባኤ ናቸው፡፡ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ትምህርተ ሃይማኖት እነዚህ ሦስቱ ጉባኤያት ባሳለፉቸው ውሳኔች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ /B-21/

በአራተኛውና በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመናት መካከል ያለው ጊዜ በቅዱስ ሰላማና /ፍሬምናጦስ/ በዘጠኙ ቅዱሳን ርዳታ ብሉያትና ሐዲሳት በግዕዝ ቋንቋ የተተረጐሙበት፣ ገዳማት የተመሠረቱበት ጊዜ ነበር፡፡ ቅዱስ ያሬድም ቤተክርስቲያኒቱን እስከ አሁን ድስ ከሌላው ሁሉ ለየት አድርጎ የሚያሳይአትን ጸዋትወ ዜማን የደረሰውና ያዘጋጀው በዚህ ጊዜ ውስጥ ነበር፡፡ ሆኖም በሰባተኛውና በስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእስልምና ሃይማኖት በቀይ ባሕር አካባቢ እየተስፋፋ መምጣቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቀረው የክርስትና ዓለም ጋር የነበራትን ግንኙነት እያደከመው መጣ፡፡ በዘጠኝኛው መቶ ክፍለ ዘመንም የአይሁድ እምነት ተከታይ የነበረችው የፈላሾች ንግሥት ዩዲት ተነስታ በአክሱምና በሌሎችም ቦታዎች በመስፋፋት ላይ በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ጥፋት ብታደርስም በ11ኛውና በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ሥራ ከፍተኛ እርምጃ ሲደረግ ችሏል፡፡ ከፍልፋል ድንጋይ የተሠሩት የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት የተገኙት በዚህ ዘመን ነበር2፡፡

በ1270 ዓ.ም. በጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ታላቅ ጥረት ሥልጣነ ክህኒ ሥርወ መንግሥት ወደ ሰሎሞን ሥርወ መንግሥት የተላለፈ ሲሆን ጻድቁ አባት ስላደረጉት ጥረትም ከሀገሪቱ ገዢ ሲሶው /1/3/ ለቤተክርስቲያኒቱ እንዲሰጥ ተደርጎ ነበር፡፡ ከዚህም በኋላ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጠንካራ የሃይማኖት እንቅስቃሴ ተደርጎ የነበረ ሲሆንም ከ1434 - 1468 ነገሠው የነበሩት አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ለቤተ ክርስቲያኒቲ ሥርዓት መሻሻሎችን አድርገዋል፡፡ /B-22/

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው ሩብ ውስጥ ግራኝ መሐመድ ተነስቶ እጅግ በጣም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያወድም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችንም አጥፍቷል፡፡ በዚህም ጊዜ ከመከራው ጽናት የተነሣ አንዳንድ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና እምነት ቢገቡም ብዙቆ የኢ.ኦ.ተ.ቤ አማኞች ግን መከራውን በጽናት ተቋቁመው በኦርቶዶክስ እምነታቸው እንደ ጸኑ ኑረዋል፡፡ ይሁንና በኃይሉ እግዚአብሔር ርዳታ ያንጊዜ ከፖርቹጋል መንግሥት ተልከዉ በመጡ ወታደሮች ድጋፍ ከ15 ዓመታት ጥፋት ቢኋላ ግራኝ መሐመድ ድል ሆኗል፡፡ /C-45/ ፡፡

ከዚህ ድል ቢኋላም በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ሱስንዮስ አማካይነት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ተሞክሮ የነበረው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እምነትም እንደተሞከረው ሳይሆን ቀርቶ በብዙ መሥዋዕትነት የኢ.ኦ.ተ.ቤ እምነትና ሥርዓት ጸንቶ ሊኖር ችሏል፡፡

በ18ኛውና በ19ኛው ምዕት ዓመታትም የሀገራችን አንድነት በመሳፍንት አገዛዝ የመከፋፈል ሁኔታ ባጋጠመው ጊዜ የኢ.ኦ.ተ.ቤ የሀገሪቱ አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር የሚያስችል ታላቅ ድርሻ አበርክታለች፡፡ ይህም ሁኔታ ቤተክርስቲያኒቱ በሕዝቡ ዘንድ የአንድነትና የኑነት ምልክት ሆና እንድትታይ አድርጓታል፡፡ አፄ ቴድሮስ በ1855 ዓ.ም. መንግሥታዊ ሥልጣን በጨበጡ ጊዜ ሀገሪቱን አንድ ለማድረግ ያነሣሣቸው ዋናው ምክንያት በቤተ ክርስቲያኒቲ ተይዞ የቆየው የአንድነት መንፈስ ነው፡፡ /B-22/

2 /B-21/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና ውጭ ግንኙነት /1996/ ገጽ 7-8

/B-22/ AYmro Wondimage grehu and Joachim, Motova, the Ethiopian Orthodox Church (1970) p.8

(C-45) Me Cabe, Jodeph, A Candid History of Jesuit, London, E.nosh, 1913

(B.22)op.cit





በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን /1920 - 1967 መጀመሪያ/ የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ከግብጽ ቤተክርስቲያን ተጥናዊ አገዛዝ ተላቃ ነፃነቷን እንድታገኝ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ከ1921 ዓ.ም. ጀምሮ የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ከሊቃውንቶቿ መካከል እየመረጠች ጳጳሳትን እንድትሾምና በእነሱ አመራር እንድትተዳደር ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያውም ኢትዮጵያዊ ፖትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ1951 ዓ.ም. ለመሾም በቅተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የኢ.ኦ.ተ.ቤ በ5ኛው ፖትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አመራር በቅዱስ ሲኖዶስ እየተዳደረች ትገኛለች፡፡ በዚህም አመራር የቤተክርስቲያኒቱ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሀገርም በጣም በመስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፖትርያርክ ርእሰ ሊቀነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወአጼጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የነበሩም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝደንት የቤተክርስቲያኒቲ አገልግሎት በትምህርትና በሥልጠና ለማሥራመድና ለማጠናከር ከፍተኛ ቁርጠኝነት የተመሳው ርምጃ አሳይተዋል፡፡

## ለ/ ቤተክርስቲያኒቱ ለማኅበራዊ አገልግሎት ያላት አሳቢነት

የቤተክርስቲያን መሥራች የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ በሦስት የሕይወት ጉዳዮች ላይ ያተኮር ነበር፡፡ እነዚህም ወንጌልን በተለያዩ ምሳሌች ማስተማር፣ በሽተኞችን መፈወስና በአስደናቂ ተአምራቶቹ ሙታንን ማስነሣት ነበሩ፡፡ ከምሳሌቹም አንዱ በፍዳሎችና በበጎች መስሎ የተናገረው የጻድቃንና የኃጥአን ምሳሌ ነበር፡፡ /ማቴ 25:31-46/ እናም በዚህ ምሳሌ በፍርድ ቀን ሰዎች ለሰዎች ችግር በሚያሳዩት ድርጊት መሠረት ፍርድ እንደሚያገኙ አስተምሯል፡፡ ይኸውም የሰበሰቡት ሀብትና ዕውቀት፣ ያላቸው ዝና እና ያጠራቀሙት ንብረት ምንም አይረዳቸውም፡፡ የሚረዳቸው ለተራበ በማብላት፣ ለተጠማ በማጠጣት፣ ለታረዘ በማልበስ፣ እንግዶችን በመቀበል እስረኞችን በመጐብኘት የሚፈጽሙት መልካም ሥራቸው ነው፡፡ /B-23/

እነዚህ ነገሮች ማንኛውንም ኅብረተሰብ የሚያሳስቡ ቢሆኑም ማናቸውም ሰው ሊፈጽማቸው የሚችሉ ቀላል ተግባራት ናቸው፡፡ ብዙ ገንዘብ አይጠይቁም፣ ዘወትር ለምናገኛቸው ሰዎች ቀላል ሰብአዊ ርዳታችን መስጠት ነው፡፡ እንደምሳሌው እነዚህን ነገሮች የሚፈጽሙ በበጎች ይመሰላሉ፡፡ የተራቡትን የተጠሙትን እንግዶችን የታረዘትን የታመሙትን እና የታሰሩትን የማይረዱ በፍየሎች ይመሰላሉ፣ በፍርድ ቀንም ዘለአለማዊ ቅጣት ይፈረድባቸዋል፡፡

በዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ላይ በመመሠረት የኢ.ኦ.ተ.ቤ በኅብረተሰባችን መካከል ለሚኖሩ ደሆች በጣሙን ታሰባለች፡፡ በስብከቷ፣ በቅዳሴዋ፣ በጽሎቷ3፣ ተከታዮቿ ለሰው ልጆች ሁሉ ደኅች ሩኅሩኆችና ለጋሶች እንዲሆኑ ደግማ ደጋግማ ታስተምራለች፡፡ ቤት የሌላቸው፣ የተራቡት፣ የታረዘት፣ ስደተኞች፣ በአጠቃላይ ችግረኞች በእያንዳንዱ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደጃፍ ይገኛሉ፡፡ የቤተ ክርስቲየኗን አስተምህሮ የሚያከብሩና የሚታዘዙ ምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ በየቤተክርስቲያናቸው ደጃፍ ለሚገኟቸው ለነዚህ ችግረኞች በተቻለ መጠን ሳንቲም፣ ምግብ፣ ልብስ ወዘተ ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ቤተክርስቲያኒቱ ለችግረኞች ከሥነ ልቡናዊ፣ አእምሮአዊና ማኅበራዊ ጭንቀት መተንፈሻ የሚያገኙበት የመጽናናት ምንጭ ሆናለች፣ ደሆችም ተስፋ ሳይቆርጡ እንዲኖሩ ታበረታታለች፡፡

ሐ/ ማኅበራዊ፣ ተቋማዊ በእነዚህም አማካይነት ሙዐለ ሕፃናትንም እንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችንም ከሌ ችን በማሻሻም ኅብረተሰቡን በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ የምስክየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ የታውቀው የተምሮ ማስተማር ማዘር በዚህ ገዳም የተሸሸመ ነው፡፡ (ኮ-24)ልማትና አገ ግሎት የማያቋርጥ ጥያቄ

ባለንበት ዘመን ኃላቀርነትን ድል ለማድረግ፣ ድኅነትን ለመቀነስ ብርቱ ጥረት እየተደረገ ባለበት በኢ ዮጵያ ማኅበረሰብ ውስጥ ለማኅበራዊ፣ ተቋማዊና አገልግሎቶች ልማት አስፈላጊነት ያለው ጥያቄ ከነ ት ዓመት በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ ኃላቀርነትን ለማሸነፍና ድኅነትን ለመቀነስ እየተደረገ ያለውን ጥረ በመጠኑም እንኳን ቢሆን ለማገዝ እንዲቻል በአዲስ አበባና በክልሎች የሚገኙ አንዳንድ የኢ.ኦ.ተ.ቤ. ሰበ አብያተ ክርስቲያናት ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትንና የወጣቶች ማኅበራትን አቋ መዋል፡፡ እነዚህም ተቋማት በተቻለ መጠን ኅብረተሰቡን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ በጥናቱ ዋና ክፍል በዘ ዘር እንደተገለጠው የዚህ ጽሑፍ ትኩረት በአዲስ አበባ በሚገኙ በሦስት አብያተ ክርስቲያናት የልማት እንቅስቃሴና አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የቤተክርስቲየኒቷ ተከታዮች ቁጥር ከዓመት ዓመት እየጨመረ ስለሚሄድ ያሉት ተቋማት እየተጣበቡ ናቸው፡፡ የሰንበት ት/ቤቶች በብዙ ሰበካ አብያተ ክርስቲያናት ተቋቁመዋል፣ እየተቋቋሙም ነው፡፡ እንደዕድር፣ ሰንበቴና ጽዋ ማኅበራት ያሉ ተቋማት ተመስርተዋል፣ እየተመሠረቱም ነው፡፡ የእየንዳንዱ ሰበካ ቤተክርስቲያን የበላይ ኃላፊ የሆኑት ሰበካ መንፈሳውያን ጉብኤያት ከአባሎቻቸው መካከል እየመረጠ የልማት ማኅበራትንና ኮሚቴዎችን አቋቁመዋል በማቋቋምም ላይ ናቸው፡፡ በእነዚህም አማካይነት መዐዘ ሕፃናትን፣ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣ ክሊኒኮችን በማቋቋም ጎብረተሰቡን በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ የታወቀው የተምሮ ማስተማር ማኅበር በዚህ ገዳም የተቋቋመ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በእያንዳንዱ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ምእመናን እየብለበለቡ እንደሰንበቴና ጽዋ ማኅበራት ያሉ ድርጅቶችን ይመሰርታሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል የየካ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ምእመናን እያንዳንዱ ከ300-500 አባላት ያሏቸው አሥራ አምስት ሰንበቴ ማኅበራትን አቋቁመዋል፡፡ ሰንበቴ ማኅበር በየቤተክርስቲያናቸው ቅጽረ ግቢ በሰሩት አዳራሽ በወር አንድ ጊዜ የሚሰበስቡ አባላት ያሉት የሃይማኖት ማኅበር ነው፡፡ ይህ ማኅበር ሁለት ዋና ዋና ዓላማች አሉት ፡፡ የመጀመሪያው ዓላማ አባላቱ አንድ ዳቦ በመቁረስና አንድ ጽዋ በመቅመስ በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት አንድ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ዳቦውና ጽዋው በየተራ የሚዘጋጅ ነው፡፡

ሁለተኛው ዓላማ ለእያንዳንዱ የሰንበቴ ማኅበር አባል የመቃብር ቦታ ለማስገኘት ነው፡፡ /ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ላመኑ ሕያዋንም ሙታንም መስባሰቢያ ናትና/ አንድ የሰንበቴው ማኅበር አባል ወይም ከቤተሰቡ መካከል አንዱ ሲሞት በዚያ በሰንበቴ ማኅበሩ የመቃብር ቦታ ይቀበራል፡፡ የመቃብር ቦታዎች የሚሰጡት በቤተክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ ሲሆን በሚሰጠው ቦታ ላይ የሚመለከተው ሰንበቴ ማኅበር መሰብሰቢያ አዳራሽና ፋካዎችን ይሠራል፡፡ በፋካዎችም አባላት ወይም ቤተሰቦቻቸው /ልጆች አባትና እናት ብቻ/ ይቀበሩባቸዋል፡፡ አስተዋጽኦን በተመለከተ እያንዳንዱ አባል የመግቢያና ወርሐዊ ክፍያን ይከፍላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በየካ ሚካኤል የደብረ መንክራት አቡነ ተክለሃይማኖት ሰንበቴ ማኅበር በ1990 ዓ.ም. እንደ ገና ሲደራጅ አባል የሆነ ሰው ለመግቢያ 700 ብር የከፈለ ሲሆን በየወሩ ብር 10 ወርሐዊ መዋጮ ይከፍላል፡፡ የዚህ ሰንበቴ ማኅበር አዳራሽ ባለአንድ ፎቅ ሲሆን የተሠራው ከአባላት በተሰበሰበ መዋጮ ነው፡፡

የጽዋ ማኅበራት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ጓደኞች የሚመሠርቷቸው ማኅበራት ናቸው፡፡ አብዚህ ለምሳሌ ማኅበራቱን የሚያቋቁሟቸው በእግዚአብሔር ስም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በቅድስት ድንግል ማርያም ወይም በቅዱሳን ስም ነው፡፡ ማኅበሩ የሚጠራበት ቅዱስ በዓል በሚውልበት ቀን አባላቱ ተሰብስበው የተዘጋጀውን ምግብና ጽዋ አብረው ይመገባሉ፡፡ ምግቡና መጠጡን የሚዘጋጀውም በየተራ ጽዋ እየተመራ በባለተራው አባል ነው፡፡ በየወሩ አባላቱ የሚሰበሰቡት በተወሰነ ሰዓት በባለተራው ቤት ሲሆን ስብሰባው በመካከላቸው ያለውን ክርስቲያናዊ የፍቅርና የመግባባት ስንስለት ያጠናክረዋል፡፡

እነዚህ ማኅበራት ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ጠቀሜታም አላቸው፡፡ አባላቱ በደስታም ሆነ በኀዘን ጊዜ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የጉልበት አስተዋጽኦ በማድረግ እርስበርስ ይረዳዳሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ መረዳዳት የተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮችን ያቃልላል፡፡ ጽዋ ማኅበራት ለማኅበራዊ ኑሮና ግጭቶችን ለመከላከል ጠቃሚዎች በመሆናቸው ማንነትን ይጠብቃሉ፡፡ ማኅበራዊ ስምምነትንም ከፍ ከፍ ያደርጋሉ፡፡ /B-26/5

2.2. የቤተ ክርስቲያኒቱን ያለፈ፣ የአሁንና የወደፊት ሚና ወይም ተግባር ማጥናት ስለማስፈለጉ

2.2.1. ሃይማኖታዊ አገልግሎት

3 (B-23) William Barclay. The Faily Study bilole series. The Gospel of matthews Vol.2 (1958) pp. 358-360



ሁሉም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጸሎትና የሥርዓተ ጸሎት ዓይነቶች በምሥጢራተ ቤተ ክርስትያን አከባበር ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ ምሥጢራት ጌታችን ኢዩሱስ ክርስቶስ ከመያዙ በፊት በነበረው ምሽት ሐዋርያት በተገኙበት የመሠረተው ዘለዓለማዊ ሥርዓት ነው፡፡ ሥጋ ወደሙ የሚከበረው ለሚቀበሉት ለነህናትና ለምእመናን ታስቦ ነው፡፡ ከተቀባዮችም መካከል በዕለቱ የተጠመቁ ሕፃናት፣ ወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች፣ ጋብቻቸውን የሚያከብሩ መሽሮች በንጽሕና ለመኖር የወሰኑ ባሎችና ሚስቶች፣ ሕሙማን፣ ሽማግሌዎች ይገኙበታል፡፡ ስለሆነም ፈጣሪን እያመሰገኑ ሥጋ ወደሙን ለእነዚህ ሁሉ ማቀበል ታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎት ነው፡፡

2.2.2. ማኅበራዊ አገልግሎት

የቤተ ክርስቲያኒቷ መሠረታዊ ተልእኮ ለሰው ልጆች መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን መስጠት ነው፡፡ ለዚህም ነው የኢ.ኦ.ተ.ቤ ለዘመናት ያለምንም የሃይማኖት፣ የዘር፣ የጾታ ልዩነት ከሕዝቦች ሁሉ ጋር ተቀራርባ በመሥራት ሰብአዊ ተግባራትን የምትፈጽመው፡፡ የ ኢ.ኦ.ተ.ቤ ለማኅበራዊና የኢኮኖሚ ልማት መስፋፋት የራሷን ልዩ አስተዋፅኦ በማድረግ የሀገሪቱን ልማት የምትደግፍ ብሔራዊት ቤተክርስቲያን ናት፡፡

ለዚህም የተቀደሰ ሥራ በልማት ኮሚሽኗ በኩል ከመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፣ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት፣ ከኦርቶዶክሳውያንና ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ድህነትን፣ ድንቁርናንና በሽታን በመዋጋት ረገድ ተባብራ ትሠራለች፡

ሀገራችን በድርቅ በተመታችባቸው ጊዜያት ሁሉ ከችግረኞች ጋር በቅርበት በመሥራት በኢትዮጵያ የተለያዩ ክፍሎች በረሃብና በድርቅ የተጐዱ ወገኖችን በመርዳት የራሷን ብርቱ ጥረት አድርጋለች፡፡ አሁንም በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽኗ በኩል በዕለት ደራሽና በመልሶ ማቋቋም ዘርፍ ባደረገቻቸው እንቅስቃሴች ጤና ጣቢያችን፣ መንገዶችን፣ ድልድዮ ችንና ት/ቤቶችን ሠርታለች፡፡ በተፈጠሮ አደጋዎች ለተጐዱ ወገኖች የውሃ ጉድጓዶች እንዲቆፈሩላቸው አድርጋለች፡፡

የቤተክርስቲያኒቷ ማኅበራዊ አገልግሎት ጐልቶ የሚታይበት ሌላው መስመር ለሙት ልጆች ማሳደጊያችን ለአረጋውያን መሪያችን በማቋቋምና በመንከባከብ ረገድ ነው፡፡ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት በሕፃናት ማሳደጊያቹ ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስና ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል፣ በመደረግም ላይ ይገኛል፡፡ በእነዚህ ሕፃናት ማሳደጊያች ተንከባካቢነት ካደጉና ከተማሩ ወጣቶች መካከል ብዙች መልካም ዜጋችና የመንግሥት ሰራተኞች ለመሆን በቅተዋል፡፡

2.2.3. ትምህርታዊ አገልግሎት

የትምህርት ታሪክ፣ ሃይማኖታዊ ተቋማት የትምህርታዊ ሥነ ጽሑፍ ሥርዓት ምንጮች እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ ይህም ሥርዓት በኢትዮጵያ የግዕዝ ፊደላትን ከመቅረጽና ከማሳደግ ይጀምራል፡፡ የታሪክ ቅርሶች ጥናትና ሊታውንት እንደሚያረጋግጡት በኢትዮጵያ ጽሕፈት የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺህ ዓመት በፊት ጀምሮ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጽሕፈት መሠረት የሆኑት የፊደላት አጠቃቀም ሥራ ላይ የዋለው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት መስፋፋት ከጀመረበት አንስቶ ነው፡፡

ከአክሱም ዘመነ መንግሥት በፊት የሳብያንና የአግአዝያን ፊደላት በአንድነት ጽሑፍ ላይ ውለው ነበር፡፡ ሆኖም የግዕዝ ቋንቋና ፊደላት በአክሱም ዘመነ መንግሥት የበላይነትን ሲያገኙ በሐልቶችና በሌሎች ነገሮች የሚጻፉ ጽሑፎች በግዕዝ ቋንቋና ፊደላት በመጠቀም የትምህርት ሥርዓቷን ማሳደግ ችላለች /B-19/፡፡

[illegible] ...ilee of miskaye Hizunan Medhanealem Monastery, thr Journal of the church issued for the Jubilee [illegible] ...ኒኤል የደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ 1190
[illegible] ...አካባቢው ተወላጆች መረዳጃ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ /በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣ/

www.ethiopianorthodox.org

የኢ.ኦ.ተ.ቤ ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ በሕዝቦቿ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ትምህርታዊ ሕይወት ውስጥ ታላቅ ድርሻ ስታበረክት ኖራለች፡፡ የቤተ ክርስትያኗ አገልግሎት በዋናነት ጉልቶ የሚታየው በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አከባበር ነው፡፡ በትልልቅ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት የቅዳሴ አገልግሎት ዘወትር ይካሄዳል፡፡ በዚህ አገልግሎት ዋናው ክፍል የምሥጢራት አከባበር ነው፡፡

የአሁኑ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ባለፈው ሁኔታ በጥልቀት ተቀርጿል፡፡ የጥንቱ ትምህርት መለያ በሕርዮን ያገኘው ልዩ ከሆነው ከሀገሪቱ ክርስቲያናዊ ውርስ ነው፡፡ ክርስትና በተስፋፋባቸው በኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢች ቤተክርስቲያኒቷ ዋናውን የኢትዮጵያን ጥንታዊ ባህል መሥርታለች፡፡ ከዚህም የተነሳ ለብዙ መቶ ዓመታት ጥንታውያን ትምህርት ቤቶችን ማቋቋምና ማስፋፋት ችላለች፡፡[6]

ተማሪዎች በትምህርት ላይ

የቤተ ክርስቲያን የትምህርት ሥርዓት የኢትዮጵያን ጥንታዊት ትምህርት ጠብቆ ለማቆየት አገልግሏል፡፡ ለትውልድም ሊተላለፍ የቻለው በዚህ ሥርዓት አማካይነት ነው፡፡
የቤተ ክርስቲያን የትምህርት ሥርዓት የሚከተሉት ዋና ክፍሎች አሉት

እነዚህም፡-

1. ንባብ ቤት = Nebab Bet
2. ቅዳሴ ቤት = Qedasse Bet
3. ዜማ ቤት = Zema Bet
4. ቅኔ ቤት = Qene Bet
5. መጽሐፍ ቤት = Metsehaf Bet

1. ንባብ ቤት፡-

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥበት የመጀመሪያው ደረጃ ንባብ ቤት ነው፡፡ ንባብ ቤት በሁሉም አብያተ ክርስቲያናትና በገዳማት፣ በብዙ መንደሮችና በአንዳንድ ወገኖች ግቢ እንኳን ሳይቀር የሚገኝ ነው፡፡ ይህም በአንድ አስተማሪ የሚከፈት ት/ቤት ነው፡፡ የንባብ ቤት የመጀመሪያው ተግባር ሕፃናት የሃይማኖት መጻሕፍትን እንዲያነቡ ለማስቻል ነው፡፡ በንባብ ቤት እፃናት ፊደላትን ተምረው ሲያጠናቅቁ ጥሩ አንባቢች እንዲሆኑ መልመጃ ይሰጣቸዋል፡፡ እንዲሁም መዝሙረ ዳዊትን ጨምሮ እንዳንድ ቀላል የሃይማኖት መጻሕፍትን እንዲማሩ ይደረጋል፡፡





2. ቅዳሴ ቤት፡-

ይህ ትምህርት ቤት ዲያቆናትና ቀሳውስት የቅዳሴን ዜማ በጥልቀት የሚማሩበት ት/ቤት ነው፡፡ የቅዳሴ ትምህርት ሰደድኩሳና ደብር ዓባይ በሚል ሁለት የዜማ ዓይነት ተከፍሎ የሚሰጥ ነው፡፡

3. ዜማ ቤት፡-

የቤተ ክርስቲያን መዚቃ በሰፊው የሚሰጥበት ት/ቤት ዜማ ቤት በመባል ይታወቃል፡፡ ዜማ ማለት የቤተክርስቲያን መዚቃ ማለት ነው፡፡ በታወቀው የዜማ ደራሲ በቅዱስ ያ ሬ ድ እንደተደረሰ የሚነገርላቸው የተለያዩ የዜማ ዓይነቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም አንዱና ዋናው ድጓ ነው፡፡

4. ቅኔ ቤት፡-

በዚህ ትምህርት ቤት ተማሪች በግዕዝ ቋንቋ ግጥሞችን እንዲገጥሙ ትምህርት ይሰጣቸዋል፡፡ ቅኔ፣ የዜማና የግጥም ምጣኔ ያለው በእንግሊዝኛ ናፖይትሪን ከተሰኘው ቃል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ በቅኔ ቤት ተማሪዎች የሚማሩት የቅኔ ግጥም መግጠም ብቻ ሳይሆን የግዕዝ ቋንቋን ከሰዋሰዋዊ ሕግጋቱ ጋር ነው፡፡ በመሆኑም ቅኔ ማጥናት ወይም መማር የግዕዝን ሥነ ጽሑፍ ለመረዳት ዋና ቁልፍ ነው፡፡

5. መጽሐፍ ቤት፡-

ይህ ትምህርት ቤት የብሉይና የሐዲስ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መ ነ ኮ ሳ ት ትርጓሜ የሚጠናበት ት/ቤት ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ተማሪች የቤተክርስቲያንን ትውፊት፣ ዶግማ፣ ታሪክና ሕገ ቤተክርስቲያንን በእያንዳንዱ ትርጓሜ አማካይነት ይማራሉ(B-30)፡፡ የቤተ ክርስቲያን ት/ቤቶች ጠቀሜታና አስፈላጊነት እንደሚከተለው
እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የቤተ ክርስቲያን ት/ቤቶች በሀገሪቱ ውስጥ ለሥጋዊም ሆነ ለመንፈሳዊ ትምህርት ብቸኞች የትምህርት አጀንሲዎች ሆነው ኖረዋል፡፡ ቀሳውስትና የሀገሪቱ ሚኒስትሮች የእነዚህ ት/ቤቶች ውጤቶች ነበሩ፡፡ የሕግ ባለሙያች፣ ዳኞች፣ ወታደራዊ መኮንኖች፣ ጸሐፊች ወዘተ ሥልጠና የሚያገኙት በእነዚህ ት/ቤቶች ወይም በገዳማት ነበርን /B-21/፡፡ ከጥቅሱ የምንረዳው የቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ለሃይማኖታዊ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለማኅበራዊ፣ ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊና ባሕላዊ አገልግሎቶችም አስፈላጊዎች እንደሆኑ ነው፡፡

## 2.2.4. የኢትዮጵያን ባህላዊ ቅርስ /ውርስ/ ማሳደግና መጠበቅ

ክርስትና በኢትዮጵያ ያለው ንጹሕ ሃይማኖታዊ ይዘት ብቻ ሳይሆን በብሔራዊ ሕይወትም ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ቤተክርስቲያኗ ሃይማኖታዊ ተቋም ብቻ ሳትሆን፣ ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ የሕዝቦች ባሕላዊና ሥነ መንግሥታዊና ማኅበራዊ ሕይወትም ተጠብቆ ያለባት ናት፡፡ /C-46/ ፡፡ ይህ አባባል በብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መጻሕፍት ተጠቅሶ እናገኘዋለን ይህም የሚያሳየው ቤተክርስቲያኗ የኢትዮጵያ ባህል ጠባቂም መሆኗን ነው፡፡ ይህች ቤተክርስቲያን ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርስ በመጠበቅና በማሳደግ ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች

ከላይ እንደተጠቀሰው የኢ.ኦ.ተ.ቤ የኢትዮጵያ ታሪክ ምንጭ መሆኗ ታምኖበታል፡፡ እንደዚህም በመሆኑ ለሥነ ጽሑፍ ዕድገትና ለታሪካዊ ድርጊቶች አመዘጋገብ ይውል ዘንድ ለግእዝ ጽሑፍ መልክና ቅርጽ የሰጠችው ይህችው ሃይማኖታዊት ተቋም ናት፡፡ ይህም ቤተክርስቲያን ለሀገር ለመንግሥትና በአጠቃላይ ለሕዝቡ አንድነትና ሰላም ምንያህል አስተዋፅኦ እንዳደረገች ያሳያል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሊፈጸሙ የቻሉት የዓለም አብዛኛው ሕዝብ በአእምሮአዊ ጨለማ ውስጥ ባለበት ጊዜ ነበር፡፡ በዓለም ወረቀት ላይ ሰፍሮ ከነበረበት ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከፍዮልና በግ ቆዳ የሚዘጋጀውን የብራና ፊደላትና ከፍዐ-ምንት ደረጃ እያደረሰችና ሀገራዊ የሆነ ቀለምና ብዕርም በማዘጋጀት ትምህርትን እያስፋፋችና ሥነጽሑፍንም እያሳደገች ነበር፡፡

www.ethiopianorthodox.org

እነዚህ የቤተክርስቲያኒቷ ታሪካዊና ባህላዊ አስተዋፅኦዎች ሁሉ፣ በትምህርት፣ በማኅበራዊ አገልግሎትና ሕዝቡ ትክክለኛ ሕይወትን ይመራ ዘንድ በውስጡ የሥነ ምግባር እሴቶችን በማስረፅ ላበረከተቸው ድርሻ በክርስቲያኖችም ሆነ ክርስቲያን ባልሆኑ ሁሉ ዕውቅና ልታገኝ፣ ከሕዝቡም አክብሮ ሊሰጣት ይገባል።

## 3. የጥናቱ አቀራረብ አንድምታ

እስከአሁን ድረስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ታሪክ ባጭሩ ለማኅበረሰቡ ያላት አሳቢነት፣ እያደገ የመጣውን የማኅበራዊነ የተቋማት ዕድገትና የአገልግሎት ጥያቄ፣ ያለፈው፣ የአሁኑና የወደፊቱ የቤተክርስቲያኒቱ ሚና ወይም ተግባር በሚገባ ተገልጿል። ገለፃው ቤተክርስቲያኒቱ ለአጥቢያ ሕዝብ በአጠቃላይ፣ ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በተለይ በሃይማኖት፣ በማኅበራዊና በትምህርታዊ አገልግሎቶች ያደረገችውን አስተዋጽኦና የተጫወተችውን ሚና በማያሻማ ሁኔታ ያስቀመጠ ነው። የሀገሪቱን ባህላዊ ቅርሶች በማሳደግና በመጠበቅ ረገድ ያደረገችውም አስተዋጽኦና ሚና በመጠኑ ተገልጿል።

ከእነዚህ ውይይቶችና ገለጻዎች ይህች ታሪካዊት ቤተክርስቲያን በረጅም ታሪኳ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ትምህርታዊና ባህላዊ ፍላጎቶች በማሟላት ረገድ በተቀ ሁኔታ ማገልገሏንና ጥቅም ማስገኘቷን ማንም ሰው መረዳት ይችላል። ከዚህ ከያዝነው ሁለ ኛ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በፊት ለአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዓመታት ቤተክርስቲያኒቱ የትምህርት ሚኒስቴር ነበረች።

የትምህርቱም ሥርዓት ከላይ እንደተገለፀው ዳኞችን፣ የሕግ ሰዎችን፣ አስተዳዳሪዎችን እና በባህላዊ መድኃኒቶች ሕዝቡን ሲያገለግሉ የኖሩትን የሕክምና ሰዎችን አፍርቷል። የነገሥታት ሕግ በመባል የሚታወቀውና ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕግ መሠረት የሆነው ፍትሐ ነገሥት የተተረጐመውና በተግባርም ላይ የዋለው በፍትሐ አደባባይ በሚሁሉ በቤተክርስቲያኒቷ ሊቃውንት ነበር።

ስለዚህ የኢ.ኦ.ተ.ቤ ካበረከተቻቸው ከእነዚህ አስተዋፅኦዎችና ተግባራት አንፃር ጥናቱ የታቀደውና የተመረጡ የኦርቶዶክሳውያን ሰበካ አብያተ ክርስቲያናትን ወቅታዊ ሁኔታ ለመዳሰስ ነው።

### 3.1. የጥናቱ መጠንና ወሰን

የጥናቱ መጠን በማኅበራዊና ተቋማዊ ዕድገት መሠረትነት የተመረጡ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን ይይዛል። እነዚህ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ከአዲስ አበባ የተመረጡት ለሕዝብ እየሰጧቸው ካሉ ጠቃሚና ተፈላጊ አገልግሎቶች ትምህርት ለመቅሰም ነው።

እነዚህም፡-

1) ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን /ገዳም/

2) መንበረ ጽባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

3) ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ናቸው።

### 3.2. የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም አጭር ታሪካዊ መሠረት

ባለፉት ዘመናት የኢትዮጵያ መሪዎች የመጀመሪያው ተግባራቸው ሃይማኖታቸውን መጠበቅ ነበር። በ1893 አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ገዳማት አስተዳዳሪ ለነበሩት ለመምህር ፈቃደ እግዚአ አንድ መመሪያ ሰጡ። ይኸውም የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ጽላት በቅድስት ሀገር ለነበረው የጴር ስሊጣን ገዳም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይውል ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወስዱት የሚገልጽ መመሪያ ነበር።



ጽላቱም ወደ ኢየሩሳሌም ተወስዶ የፋሽስት ኢጣሊያ ኃይሎች ኢትዮጵያን እስከወረሩበት እስከ 1928 ዓ.ም. በዚያ አገልግሎት ላይ ውሎ ነበር። ከወራሪው ቢኋላ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ እንግሊዝ አገር በስደት በሄዱና ከንጉሣውያን ቤተሰቦች ጋር እዚያ በቆዩበት ጊዜ በኢየሩሳሌም ያለው የመድኃኔዓለም ጽላት ከአስፈላጊ ንዋየ ቅድሳትና ከአምስት መነኮሳት ጋር ወደ እንግሊዝ ሀገር ተላከ። የላኩትም ያንጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩት እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ሲሆኑ ዓላማውም እንደተጠቀሰው በአምስቱ ዓመታት የጣሊያን ወረራ ወቅት /1928 -1933/ በለንደን ይገኙ ለነበሩት ንጉሣውያን ቤተሰቦች መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጥባት ነበር።



ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም

ወራሪዎች የኢጣሊያ ኃይሎችን አርበኞች በኃያሉ እግዚአብሔር ርዳታ ድል አድርገው በ1933 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ካስወጧቸውና አፄ ኃይለ ሥላሴም ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ ቢኋላ ታቦተ ሕጉም ከለንደን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተደረገ። እንደመጣም በቤተ መንግሥት የጸሎት ቤት ውስጥ እንዲቀመጥ ሆነ። በ1934 ዓ.ም. የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ከስደት ለተመለሱት የመንፈስ ማጽናኛ እንዲሆን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይባል በነበረው አሁን የኩቲት 12 በተባለው ሆስፒታል ቅጽረ ግቢ ተሠርቶ የመድኃኔዓለም ጽላትም በዚያ እንዲያርፍ ተደረገ። ከዚያ ቢኋላ የንጉሡ የግል አማካሪ በነበሩት በአባ ሐና ጀማ ኃላፊነት አዳዲስ ዲያቆናትና መነኮሳት ተቀጠሩ። እነሱም በዘመነ ስደት በለንደን ይደረግ እንደነበረው ጸሎተ ቅዳሴውንና ሌላውንም አገልግሎት በአማርኛ ማካሄድ ጀመሩ።

ከአምስት ዓመታት ቢኋላ የልዑል ራስ መኮንን ይዞታ የነበረ ከተፈረሰ መኮንን ትምህርት ቤት አዋሳኝ የሆነ ቦታ ተመርጦ ለአዲስ የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ሥራ ንጉሡ ግንቦት 5 ቀን 1948 ዓ.ም የመሠረቱ ድንጋይ አስቀመጡ። የአዲሱ ቤተክርስቲያን ሥራም በ1950 ዓ.ም ተፈጽሞ በተጀመረ በሁለት ዓመቱ ግንቦት 5 ቀን 1950 ዓ.ም. ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሣውያን ቤተሰቦች ብፁዕ አቡነ ባስልዮስና ሌሎችም ጳጳሳት ሚኒስቴሮችና ጥሪ የተደረገላቸው የክብር እንግዶች በተገኙበት ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። በዚህ ዓይነት የተቋቋመው የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በየጊዜው ባቋቋሟቸው የትምህርት የጠና የወጣቶች ተቋማት ኅብረተሰቡን በአግባቡ በማገልገል ላይ ይገኛል።

### ሀ. የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ትምህር ቤት መሸሸምና ዕድገት

ይህ ትምህርት ቤት የተቋቋመው በ1974 ዓ.ም. ነው። ት/ቤቱ የተሠራበትም ቦታ ከመጀመሪያው ጀምሮ የቤተክርስቲያኑ ይዞታ ነበር። ቀደም ሲል የእንጨት ሥራ ይካሄዱበት የነበረ ቦታ ሲሆን ነገር ግን ለትምህርት ቅድሚያ በመስጠትና ኅብረተሰቡን በተለያየ መንገድ ለማገልገል በመንፃት የገዳሙ አስተዳደር መኖሪያ ክፍሎችን በአዲስ መልክ በማደራጀት መማሪያ ክፍሎች እንዲሆኑ መወሰኑ ሕዝብ በቤተክርስቲያኑ ስም ከፈተ።

www.ethiopianorthodox.org

የትምህርት ቤቱ ዓላማ የትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን ሥርዓተ ትምህርት በመከተል ከሃይማኖትና የግብረገብ ትምህርት ጋር በማቀናጀት መደበኛ ትምህርት ለመስጠት ነበር፡፡ በ1986 ዓ.ም. በታተመው የቤተክርስቲያኑ መጽሔት በግልጽ እንዳስፈረው ትምህርት ቤቱ የመዐስ ሕፃናት ሥራውን ገጀመረው አርባ ሕፃናትን በመቀበል ነበር፡፡ ጊዜው እየቀጠለ ሲሄድ ግን ት/ቤቱ የትምህርቱን ጥራት እያሻሻለና እያሳደገ በመምጣቱ ዝናው ቤብረተሰቡ ስለታወቀ ብዙ ተማሪ ወደዚህ ገዳም ት/ቤት መጉረፍ ጀመረ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የመማሪያ ክፍሎችን ቁጥር መጨመር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ባለሁለት ፎቅ ሕንጻ በማሠራት ት/ቤቱ ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ት/ቤት በሥርዓተ ትምህርቱ መንፈሳዊውንና ዓለማዊውን ትምህርት አጣምሮ በአንድነት ቤብቃት ለመስጠት ከቀድሞው የቅድስት ሥላሴ ት/ቤት ቀጣሉ የመጀመሪያው ትምህርት ቤት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተፈላጊነት ስለነበረው ተጠቃሚው ኅብረተሰብ እና የተማሪች ቁጥር በአያሌው እየጨመረ ሊሄድ ችሏል፡፡

ስለሆነም እያደገ የመጣውን የማኅበረሰቡን ፍላጎት ለማሟላት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሕንጻ ማሠሪያ በርክት ያለ ገንዘብ በማስፈለጉ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለጀርመን ፕሮቴስታንት ማዕከላዊ የልማት ድርጅት የገንዘብ እርዳታ ጥያቄ ቀረበ፡፡ ድርጅቱም ጥያቄውን በቀና መንፈስ ተቀብሎ ብር 3751000 ስለሰጠ በዚህ ገንዘብ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተሠራ፡፡ ስለዚህ ገዳሙ በአሁኑ ጊዜ ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ መስናዲ ድረስ ከሁለት ሺህ ለማያንሱ ተማሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ከትምህርቱ ጥራትም የተነሳ ተማሪች በሁሉም ብሔራዊ ፈተናዎች ከፍተኛ ውጤት እያመጡ ከደረጃ ወደ ደረጃ እያለፉ ስለመጡ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ት/ቤት በተገልጋዩ ኅብረተሰብ ዘንድ በአዲስ አበባ ከሚገኙ እውቅ ት/ቤቶች እንደ አንዱ ለመቆጠር በቅቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ትምህርት ቤቱ በአሁኑ ጊዜ ለኅብረተሰቡ እየሰጠ ያለው ትምህርት ገዳሙን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም የሚያኮራና የሚያስመሰግን ሆኗል፡፡

## ለ. ተምሮ ማስተማር ሰንበት ት/ቤት

የምስካየ ኅዙናን ቤተክርስቲያን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት የተፈፈ መክንን እና የእቴጌ መነን ት/ቤት ተማሪችን ብዛት መሳብ ችሏል፡፡ በየሳምንቱ እሑድ ተማሪች ብዛት ወደ ቤተክርስቲያን እየመጡ በመንፈሳዊ አገልግሎቱ ተሳታፊ ከሆኑ በኋላ ብዙቹ በቤተክርስቲያን አንዳንድ ሥራዎች በፈቃደኝነት መሳተፍ ጀመሩ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተማሪዎችና በገዳሙ መካከል አንድነትን መፍጠር የሚችልና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሚሰጥበት ሰንበት ት/ቤት እንዲቋቋም ወላጆች በመጠየቃቸው «ተምሮ ማስተማር» የተባለው ታዋቂው ሰንበት ት/ቤት በ1956ዓ.ም ተመሰረተ፡፡

የተምሮ ማስተማር ማኅበር ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ለማኅበሩ አባላትና ለኅብረተሰቡ አስፈላጊ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል፡፡ ለአባላቱ የሚሰጠውን አገልግሎት በተመለከተ በየሳምንቱ እሁድ ከአራት ሰዓት ጀምሮ በማኅበሩ አማካይነት እየተጋበዙ የሚመጡ ምሁራን የሃይማኖት ትምህርት እየተሰጠ መሳጭ ትውልድ የክርስትና ሃይማኖትን በአግባቡ እንዲያውቅና እንዲረዳ እየተደረገ ነው፡፡ የትምህርቱ ፕሮግራም ከ1956ዓ.ም ጀምሮ እስከአሁን እየቀጠለ በመሆኑ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወላጆች ወንዶችም ሴቶችም የትምህርቱ አገልግሎት ተጠቃሚች ሆነዋል፡፡

ይህ አንጋፋ ማኅበር ለኅብረተሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት በተመለከተም

1. የመዚቃ ቡድን አቋቁሞ ቡድኑ ያሬዳዊ ዜማን በማጥናት በቤተክርስቲያኑ አገልግሎት ቤተሰይ በቅዳሴ ጊዜ ተሰጥዎ እንዲቀበሉ ከማድረጉም ሌላ ጋብቻቸውን በቤተክርስቲያን የሚፈጽሙ ሙሽሮችን በመዝሙር፣ በከበሮና በሽብሸባ በማጀብ ጥሩ መንፈሳዊ አገልግሎት ስለሚሰጥ ብዙ ሙሽሮች ጋብቻቸውን በዚሁ ቤተክርስቲያን እንዲፈጽሙ መስሕብ ሆኗል፡፡
2. የድራማና የሥነጽሑፍ ቡድን በማቋቋም ቡድኑ የተለያዩ ድራማችን በማዘጋጀትና ቤታሳላት በኅላት ለአካባቢው ኅብረተሰብ በማሳየት ሥነ ጽሑፎችንም በማቅረብ ሃይማኖታዊና ማኅበረሰባዊ እውቀትን በማስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡
3. የልማት ኮሚቴ በማቋቋምና በኮሚቴው አማካይነት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለዕርዳታ



ሰጪ ክፍሎች እንዲቀርብ በማድረግ ባገኘው ገቢ በገዳሙ ግቢ ውስጥ የእንጨት ሥራ ድርጅት አቋቁሞ ለገዳሙም ለኅብረተሰቡም አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

4. የማኅበሩ አባላት የቤተክርስቲያኒቱን የሞራል እሴቶች ጠብቀው ሕይወታቸውን ግብረገብነት ባልተለየው መንገድ እንዲመሩ የሚከታተል የዲስፕሊን ኮሚቴ አቋቁሟል፡፡ አንዳንድ የማኅበሩ አባላት የግብረገብነት ችግር ሲገጥማቸው ወደ ዲስፕሊን ኮሚቴው ቀርበው መንፈሳዊና ሥነ-ልቦናዊ ምክር በመቀበል በዚህ ረገድ ላጋጠማቸው ችግር መፍትሔ በማግኘት የክርስቲያንን ኅብረተሰብ የሞራል ደረጃ ጠብቀው በማስጠበቅ አርአያነት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ የምስካየ ኅዙናን ቤተክርስቲያን የተምሮ ማስተማር ሰንበት ት/ቤት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ወጣቶች እንቅስቃሴ በትምህርትም ሆነ በሥራ መስክ ግምባር ቀደም ማኅበር ነው፡፡

ማኅበሩ ብዙ ገጽታ ያላቸው አዳዲስ መርሐ ግብሮች በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያኗ ለሀገሪቱ በሞራል የተገነባ አስተማማኝ ተክታይ ትውልድ እንዲኖራት የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል፣ በማበርከት ላይም ይገኛል፡፡

## ሐ. ቤተ ሆሣዕና ክሊኒክና ላቦራቶሪ

የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ለኅብረተሰቡ አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ተቋማት አንዱ ቤተ ሆሣዕና በመባል የሚታወቀው ክሊኒክ ነው፡፡ ይህ ክሊኒክ በ1991ዓ.ም ተከፍቶ ለገዳሙ ካህናት፣ ለትምህርት ቤቱ ተማሪዎችና ለመምህራን፣ በተለይም በሰበካው አካባቢ ለሚገኙ የማኅበረሰብ አባላት የሕክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ክሊኒኩ የሚከተሉት ክፍሎች አሉት፡፡

1. የሕፃናት ሕክምና ክፍል
2. የቀዶ ጥገና ክፍል
3. የጓይን ክፍል
4. የማሕፀን ሕክምና ክፍል
5. አጠቃላይ ላቦራቶሪ

ክሊኒኩ ከተቋቋመ ወዲህ ከአስር ሺህ በላይ ለሆኑ በሽተኞች በሙሉ ወይም በቅናሽ ዋጋ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ የሥራው ርምጃ የሚያበረታታና ፈጣን እድገትን የሚያሳይ ሆኗል፡፡ የገዳሙ አስተዳደርም ባደረገው ጥረት እንደ አልትራ ሳውንድ ያሉ አዳዲስ መሣሪያች በእርዳታ ተገኝተው ሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን በወሊድች አስተሳሰብ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ይቻል ዘንድ ተጨማሪ መሣሪያች ያስፈልጋሉ፡፡ በምስካየ ኅዙናን ገዳም የታየው ምሳሌያዊ የሥራ ተነሣሽነት በአዲስ አበባና በክልሎች ባሉ አብያተክርስቲያናት እንደምሳሌ ተወስዶ በመደገም ላይ ይገኛል፡፡ የቤተክርስቲያኑ ሥራ ለኅብረተሰብ ችግር ፈጣና ምላሽ መስጠት የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በትምህርትና በጤና መስክ ማኅበራዊ አገልግሎት ስለመስጠት በምንነጋገርበት ጊዜ ጌታችን መድኃኔዓለምን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ያደረገውን ማስታወስ ይገባናል፡፡ በአንድ በኩል ሕዝቡን ስለመንከባከብ እግዚያብሔር ሲያስተምር በሌላ በኩል ደግሞ በተአምራታዊ ሥራው ሕመማንን ይፈውስ ነበር፡፡ አያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፈጸማቸው ለእነዚህ ሁለት የአገልግሎት መስኮች ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በዚህ ረገድ ጥሩ ምሳሌ ሆኗል (ገጽ - 32)

## ፲.፲. የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልና አመሠራረቱ

አሁንተቤ በማኅበራዊ አገልግሎት እያደረገች ላለው አስተዋጽኦ ሌላው ምሳሌ በቅድስት ሥላሴ ካቴደራል ተግባራት እየታየ ነው፡፡ ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን በ1883 ዓ.ም የተሠራው በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ነበር፡፡ ንጉሡ ቤተክርስቲያኑን አሁን ባለበት ቦታ ያሠሩት አንድ ባሕታዊ በነገሯቸው መሠረት ነው ይባላል፡፡ ባሕታዊው በሕልማቸው ሦስት ነጫጭ ርግቦች በዚያን ቦታ ላይ ሲያርፉ በማየታቸው ርግቦቹ ሥላሴን የሚያመለክቱ እንደሆነ በማመን የሥላሴን ቤተክርስቲያን በዚያ ቦታ ላይ እንሠሩ ለንጉሡ ነግረዋቸዋል፡፡ ቤተክርስቲያኑ ከተሠራ በኋላም ባሕታዊው ለንጉሡ በሥላሴ ስም የተቀረፀ ጽላት አስመጥተው እንዲያስገቡ ስለነገሩዋቸው ንጉሡ ይህንኑ ፈፅመዋል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

በዚህም ምክንያት አዲስ የተሠራው ቤተክርስቲያን «መካነ ሥላሴ» ተብሎ ተጠራ፡፡ (መካነ ሥላሴ ማለት የሥላሴ ቦታ ማለት ነው)9



መንበረ ጳጳሳት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

መካነ ሥላሴ ቤተክርስቲያን በተሻለ ሁኔታ ተጠብቆ እንዲያኖር አፄ ኃይለ ሥላሴ የሚከተሉትን ወበይት ተግባራት አከናውነዋል፡፡

ሀ. በ1910 ዓ.ም የቤተክርስቲያኑ ዙሪያ በመስቀል ተከልሎ እንዲከበር አደረጉ፣
ለ. በ1920 ዓ.ም መስከረም 27 ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን በዚህ ቤተ መቅደስ ትበዐ መንግሥት ተቀብተው የንጉሥነት ዘውድ በመድፋት ንጉሥ ተባሉ፡፡
ሐ. አሁን ያለው ካቴድራል በሐዋርያት መስቀል አምሳል እንዲሠራ ታኅሣሥ 15 ቀን 1924 ዓ.ም የመሠረት ድንጋይ አኖሩ፡፡

ከዚያ በኋላ ሥራው ቀጥሎ እያለ ሀገሩ በ1928 ዓ.ም በፋሽስት ኢጣሊያ ኃይሎች በመወረሯ የቤተክርስቲያኑ ሥራ ተቋረጠ፡፡ ነገር ግን ለአምላክ ምስጋና ይግባውና ወራሪው ኃይል በ1933 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ሲባረር ሥራው ቀጥሎ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ በ1936 ዓ.ም በታላቅ ሥነ ሥርዐት ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ፡፡ ስሙም «ከመካነ ሥላሴ» ወደ «መንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ተሰወጠ»፡፡

የቤተክርስቲያኑ አለቃም አዲስ ማዕረግ ተሰጥቷቸው ሊቀ ሥልጣናት ተባሉ፤ ትርጉሙም የሥልጣናት አለቃ ማለት ነው፡፡ ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ተብለው የተሰየሙት የመጀመሪያው አለቃ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሁለተኛ ፓትርያርክ የሆኑት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ነበሩ፡፡ ይህ ቤተክርስቲያን በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ትእዛዝ ከ1957 - 1960 በነበረው ጊዜ እንደገና እንዲሠራና እንዲስፋፋ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ወለሉ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ 36 ሜትር ከስሜን ወደ ደቡብ 26 ሜትር ከፍታው 35 ሜትር ሆኗል፡፡ መስፋፋቱ ብዙ ሕዝብ እንዲያስተናግድ አስችሏል፡፡ የአመሠራረት ታሪኩ ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለፀው ካቴድራል የሚከተሉትን ተቋማት መሥርቶ ኅብረተሰቡን በሚገባ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

9(B 32) Golden Jubille of Miskaye Hizan Medhanealem Monastery (1986)pp.10-20





### 3.3.2. የካቴድራሉ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

ከካቴድራሉ ጽ/ቤት የተገኙ መረጃች እንደሚገልፁት የመንበረ ፀባኦት ቅድስ ሥላሴ ካቴድራል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የተጀመረው መስከረም 14 ቀን 1955 ዓ.ም በማታው ክፍለ ጊዜ ነበር፡፡ ዓላማውም የጥንቱ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የ2ኛው ደረጃ ት/ቤት ስለተዘጋ የካቴድራሉን አገልጋዮች ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ሳይርቁ በዘመናዊ ትምህርት ለማስልጠን ታስቦ መሆኑን ታሪኩ ያስረዳል፡፡

ይሁንና በዓመቱ ማለት በ1956 ዓ.ም የት/ቤቱን ዓላማ በማሻሻል በቀኑም ክፍለ ጊዜ ትምህርት እንዲሰጥ በመደረጉ የክፍሉ ደረጃ ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል እንዲያድግ ተደረገ ከዚህ በኋላ በየዓመቱ ክፍሉ እያደገ ሄዶ በ1958 ዓ.ም 6ኛ ክፍልን በብሔራዊ ደረጃ ሲያስፈትን ተማሪቹ ከፍተኛ ውጤት በማግኘታቸው ት/ቤቱ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ ታዋቂነትን አገኘ፡፡ ይህም እውቅና የተማሪውን ቁጥር እያሳደገው መጣ፡፡ በ1961 ዓ.ም ደግሞ የ8ኛ ክፍልን ብሔራዊ ፈተና የወሰዱ ተማሪቶም እንዲሁ የላቀ ውጤት በማምጣታቸው የአካባቢው ኅብረተሰብ በውጤቱ በመርካቱ የገንዘብ አስተዋፅኦ እያደረገ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ክፍ እንዲል በማገዙ ት/ቤቱ እየተጠናከረ ሊመጣ ችሏል፡፡

### 3.3.3. ሁለተኛ ደረጃ፡-

ትምህርት ቤቱ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ባደገበት ጊዜ ካቴድራሉ በፈቃደኝነት በነፃ የሚያገለግሉ የውጭ ሀገር መምህራንን 3 ከአሜሪካ፣ 2 ከዴንማርክና 1 ከእንግሊዝ ሀገር አስመጣ፡፡ የእነዚህ መምህራን መምጣት ት/ቤቱ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት እንዲጠናከር አድርጓል፡፡

ካቴድራሉ ለካህናት ማሰልጠኛ ብሎ የጀመረው ት/ቤት ወደ ዘመናዊ ት/ቤት በመለወጥ ብቻ አልተወሰነም፡፡ አራት ሚሊዮን ያህል ብር ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ ያማረ የተዋበ ባለሁለት ፎቅ ሕንፃ በማሠራት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ሊቀነ ጳጳሳትና ሌሎች የክብር እንግዶች በተገኙበት ጥቅምት 20 ቀን 1997ዓ.ም አስመርቋል፡፡ አሁን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በዚህ ሕንፃ ውስጥ የሚሰጥ ሲሆን ኅብረተሰቡ በትምህርት አሰጣጡ ደስተኛ ስለሆነ በሁለቱም ክፍሎች ልጆቹን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡ በሁለቱም ክፍሎች ከአንድ ሺህ አምስት መቶ (1500) ያላነሰ ተማሪ ይገኛል ስለሆነም ካቴድራሉ በዚህ ት/ቤት አማካይነት እጅግ ጠቃሚ ማኅበራዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

### 3.3.4 የወጣቶች ማኅበራት

ቀደም ሲል ከተጠቀሰው ከካቴድራሉ ምረቃ በኋላ እንደ ሰንበት ት/ቤት ተማሪች በካቴድራሉ የሃይማኖት ትምህርት ይከታተሉ የነበሩ ወጣቶች የሥላሴ ማኅበር ተብሎ የሚጠራ አንድ ማኅበር መሠረቱ፤ ይህ ማኅበር ለወንዶች ብቻ የተቋቋመ ነበር፡፡ ይሁንና ከጥቂት ዓመታት በኋላ የካቴድራሉ አስተዳደር ወጣት ልጃገረዶችም የራሳቸውን ማኅበር መመሥረት እንዳለባቸው አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው ለጸሎትና ለአምልኮ ወደ ካቴድራሉ የሚመጡ ልጃገረዶችን ሰብስቦ እነርሱም የራሳቸውን ማኅበር እንዲያቋቁሙ አበረታታቸው፡፡ በመሆኑም «ማኅበረ ክርስቶስ» በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ማኅበር መሠረቱ፡፡

የእነዚህ ማኅበራት አባላት የተሻለ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ትምህርት ማግኘት ሲጀምሩ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት እየወደዱ በመምጣታቸው በተለይም ልጃገረዶች የቤተክርስቲያንን ዜማ በማጥናት በቤተክርስቲያን ውስጥ ከቍርባን በኋላ መዘመር ጀመሩ፡፡ ይህም እንደአዲስ ክስተት ታይቶ በክህናቱና በምእመናኑ ዘንድ የሚወደድ ሆኖ ተገኘ፡፡

የእነዚህ ማኅበራት አላማቸም የሚከተሉት ነበሩ፡ -

1. የክርስትና ሃይማኖትን መሠረታዊ ዓላማች መማርና ማስተማር
2. ሰብአዊ ተግባራትን ማከሄድ
3. የክርስቲያንን ብሔራዊ ባህል መጠበቅ

www.ethiopianorthodox.org

4. ወጣት ልጃገረዶች ያለፍርሃት አገልግሎት መስጠት እንዲችሉና ለንብረተሰቡ አገልግሎት የሚያስፈልገውን የሥራ አመራር ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ናቸው

ከላይ እንደተጠቀሰው በቅዳሴ ጊዜ የወጣት ልጃገረዶች ተሰጥዎ መቀበልና ከቅዳሴም በኋላም ልዩ ልዩ ጣዕመ ዜማችን ማሰማታቸው እንደአዲስ ነገር በመታየቱ ተግባሩ በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶች ተቀስሟል፡፡ በመሆኑም የካቴድራሉ ሰንበት ት/ቤት ለንብረተሰቡ ወጣት ክፍል ጠቃሚ የሆኑ ተግባራትን በማስተዋወቅ ረገድ በጣም ከፍ ያለ ድርሻ አበርክቷል፡፡

### 3.3.5 ከፍተኛ ክሊኒክ

የካቴድራሉ ክሊኒክ በቅርቡ የተሠራ ሲሆን የተሠራውም ከካቴድራሉ በተመደበ ገንዘብና የቤተክርስቲያኑ ልጅ ከሆኑት ከክብርት ወ/ሮ እስከዳር ገብረሕይወት በተለገሰ ከፍተኛ የገንዘብ አስተዋፅኦ ነው፡፡ ይህ ክሊኒክ በአሁኑ ጊዜ ለባለሙያዎች ተከራይቶ ለካቴድራሉ ገቢ የሚሰጋኝ ከመሆኑም ሌላ ለአካባቢው ተገብረተሰብ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው (B-33)፡፡

### 3.4 ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን

የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያንን ያሠሩት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባለተቤት የነበሩት እቴጌ መነን እነደሆኑ ታሪኩ ያስረዳል፡፡ ታሪኩ እንደሚያስረዳው ፋሽስት ኢጣሊያ በ1928ዓ.ም ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ እቴጌ መነን በስደት ወደ ውጭ አገር ከመሄዳቸው በፊት በሕይወት ላሉ ኢትዮጵያውያን ከጣሊያን ወረራ ነፃነታን ካገኘች ወደ ሀገር ቤት ሲመለሱ የቅዱስ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን እንደሚያሳንፁ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብተው ነበር፡፡

ኢትዮጵያ ነፃ እንደወጣች እቴጌ መነን ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ዛሬ የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ያለበትን ቦታ መርካቶ ውስጥ አፈላልገው አገኙና ያዙ፡፡ በዚህ መሠረት ግንቦት አንድ ቀን 1944 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ንጉሣዊያን ቤተሰብ፣ ሚኒስትሮችና ጥሪ የተደረገላቸው የነብር እንግዶች በተገኙበት በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ (በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ) መሪነት የደብረ አሚን ተክለሃይማኖትና የእንጦጦ ራጉኤል ካህናት ሥርዐተ ጸሎት ካደረሱ በኋላ ግርማዊነታቸው በዚያ እቴጌ መነን በያዙት ቦታ መርካቶ ውስጥ የመሠረት ድንጋይ አኖሩ፡፡ ሥራውም ወድያው ተጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ በመጠናቀቁ መስከረም አንድ ቀን 1948 ዓ.ም ግርማዊ ጃንሆይና ግርማዊት እቴጌ በተገኙበት ሥርዐተ ጸሎት በአዲሱ ቤተክርስቲያን በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ተመርቶና ተካሂዶ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ፡፡ በመሆኑም በዚህ ቀን የቅዱስ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን የማሠራት የእቴጌ መነን የረጅም ጊዜ ምኞት እውን ሲሆን ቻለ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ስማቸው በጸሎት ይዘከራል፡፡

### 3.4.1 የቤተክርስቲያኑ የልማት ተግባራት

ከቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን የልማት ተግባራት አንዱ የደርግ መንግሥት ወርሶት በነበረው፣ በኋላ ግን በ1984 ዓ.ም በኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ለቤተክርስቲያኑ በተመለሰው ቦታ ላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመሥራት እቅድ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በዚያን ጊዜ የቤተክርስቲያኑ አለቃ የነበሩት መልአከ ኃይል ታሪ ጸድቅ እውነቱ (አሁን ብፁዕ አቡነ አብርሃም) አመራር ሰጪነት የት/ቤቱ ሥራ በግንቦት 1988 ዓ.ም ተጀምሮ በብር 5940500 ወጪ ተሠርቶ በ1991 ዓ.ም በመጠናቀቁ ሐምሌ 6 ቀን ተመረቀ፡፡ ባለሦስት ፎቅ የሆነው ይህ የት/ቤት ሕንፃ በቤተክርስቲያኑ በምዕራባዊ ክፍል በኩል የተሠራ ሲሆን 64 ስኩዌር ሜትር ስፋትና 71 ክፍሎች አሉት፡፡ ከ71 ክፍሎች ውስጥ 15ቱ የሕንፃውን ወጪ ለመሸፈን ሲባል በሰትነት የተከራዩ ሲሆኑ የቀሩት ማለትም ከ1ኛ ፎቅ ጀምሮ ያሉት መማሪያ ክፍሎች የአስተዳደር ቢሮች ሆነዋል፡፡

ትምህርት ቤቱ በ1992 ዓ.ም በ20 ክፍሎች ዝግጅነት ሲከፈት ከ1 - 8ኛ ክፍል ድረስ 771 ተማሪዎች ተቀብሎ 23 መምህራንና 24 የቢሮ ሠራተኞችን ቀጥሮ ሥራውን ጀመረ፡፡ አንድ ጊዜ ከተከፈተ በኋላ ከዓመት ዓመት እየተጠናከረ በመሄድ ትኩረቱን በትምህርት ጥረት ላይ አደረገ፡፡ ይህም ትኩረት ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ወጤት እያመጡ በብዛት አለፉ፡፡ በዚህም ምክንያት ት/ቤቱ በአዲስ አበባ የትምህርት ቢሮና በተገልጋዩ ማህበረሰብ ዘንድ ታዋቂ ሆነ፡፡ በመሆኑም በአጭር ጊዜ ውስጥ ት/ቤቱ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ተሸጋግሮ በ10ኛ ክፍል ማትሪክ ሲያስፈትን በመስናዶ ደረጃ ደግሞ ከ11-12 ክፍል ያሉ ተማሪዎችን በማስተማር በመስናዶ ፈተና ብዙኆ ተማሪዎች ከ2-4 ነጥብ እያመጡ ዩኒቨርስቲ በመግባት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ አንደኛ ደረጃውም ሆነ ሁለተኛ ደረጃው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ታዋቂ ከሆኑት ጥቂት ትምህርት ቤቶች መካከል የማጠቀስ ሆናል፡፡

ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክ/ን 2ና ደጬጋ ት/ቤት

ስለዚህ ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ኅብረተሰቡን በሚገባ በማገልገሉ ኅብረተሰቡም በምላሹ ቤተክርስቲያኑን በሃይማኖታዊ አገልግሎቱ ብቻ ሳይሆን በትምህርታዊ አገልግሎቱም እያደነቀው ይገኛል፡፡ ቤተክርስቲያኑ በዚህ አድናቆት የበለጠ ተበረታትቶ ሁለተኛ ደረጃውን የሚያስፋፋና ኮሌጅም ለመክፈት የሚያስችል ባለ7 ፎቅ ተጨማሪ ሕንፃ ሠርቷል፡፡ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ምን ምን አገልግሎት እየሰጠና በዚህ አገልግሎት ኅብረተሰቡን ምን ያህል እየጠቀመ እንደሆነ ለማወቅ የሚፈልግ የቤተክርስቲያኑን ዙሪያ እየተዘዋወረ ማየት ያስፈልገዋል፡፡

### 3.4.2. የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያ ሰንበት ትምህርት ቤት አመሠራረትና እድገት

የቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት በቤተክርስቲያኑ ድጋፍ ሰጪነት ዲያቆናትን ጨምሮ 50 በሚሆኑ ወጣቶች በ1959 ዓ.ም ተመሠረተ፡፡ ከተመሠረተ ጀምሮም ሰንበት ት/ቤቱ በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን ከእነዚህም፡-

1. ሰንበት ት/ቤቱ በሚሰጠው የሃይማኖትና የሥነ-ምግባር ትምህርት ተኰትኩተው ካደጉት ወጣቶች መካከል ጥቂቶቹ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት በተለያዩ ፕሮፌሽናል የሥራ መስኮች ሲሰማሩ በዘቹ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ አጠናቀውና ቤተሰብ መሥርተው ጥሩ ክርስቲያናዊ ሕይወት በመምራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሌሎችም ቤተ ክርስቲያኑን በምንኩስናና በቅስና እያገለገሉ ናቸው፡፡ሌሎችም ቤተ ክርስቲያኑን በምንኩስናና በቅስና እያገለገሉ ናቸው፡፡
2. አባላቱ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል የታመመኑትን መጠየቅ፣ በአቅማቸው መሠረት የተቸገሩን መርዳት ሲሆን በሥራ እንቅስቃሴ በኩልም መዝሙራትን በማጥናት መዘመር፣ በተለያዩ ሥነ-ጽሑፎች አማካይነት ሃይማኖታዊና የሥነ ምግባር ትምህርት ለምእመናን መስጠት ናቸው፡፡ የተለያዩ የእጅ ሥራዎችንም በመሥራት እየሸጡ ባገኙት ገቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሠርተዋል፣ በዚህም አዳራሽ ሃይማኖታዊ ትምህርትን ጨምሮ የተለያዩ ተግባራትን ያካሂዱበታል፡፡ ሰንበት ት/ቤቱ በአዲስ አበባ ለሚገኘው የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የገንዘብ አስተዋጽኦ እንዳደረገ
3. በሰበካ ጉባኤው ሥራ አመራር ኮሚቴና ቤተክርስቲያኑ አስተዳደር በመታገዝ ሰንበት ት/ቤቱ በ1988 ዓ.ም ለወጣቶችና ለምእመናኑ የስድስት ወር የሃይማኖት ትምህርት ኮርስ አዘጋጅቶ ከሰጠ በኋላ በመጨረሻ ለተሳታፊዎች የምስክር ወረቀት ሰጥቷል በሥራ ክንውኑ ተገልጿል፡፡
4. ሦስ የፋይናንስ ምንጮች ድራማ ማሳየትና ሌሎች ማኅበራዊ ተግባራትን ማከሄድ ነው፡፡ እናም [illegible] ባደረገው ጥረት ብር 4600 ማግኘት ችሏል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

### 3.6. የጥናቱ ውጤት /ማጠቃለያ/

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ፣ በመዝሙር፣ በሥነጥበብ፣ በሥነ ሕንፃ፣ በቅርፃ ቅርፅና በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሥልጣኔ አቅጣጫዎች ሁሉ ከፍ ያለ ድርሻ አበርክታለች። ሁሉም የውጭ ኦር ቶዶክስ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት የቤተክርስቲያኒቱን ባህላዊ ቅርሶች ማለትም የአክሱምን ታሪካዊ ቅርሶችና የታቦተ ጽዮንን ማረፊያ ቤተ መቅደስ አስደናቂዎችን የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትንና በክርስቲያን ነገሥታት የተሠሩትን የጎንደርን አብያተ መንግሥት፣ በጣና ሐይቅና በሌሎችም ቦታዎች የሚገኙ ጥንታውያን ገዳማትን ለመጐብኘት ነው።

ይሁንና የቤተክርስቲያኒቱ ሚናና አስተዋጽኦ ባለፈው ጊዜ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ዛሬም ቢሆን አገልግሎቷና ተቋማቷ ይፈለጋሉ። ተከታዮቿ ሙሉ ሕዋናትን፣ ትምህርት ቤቶችንና ኮሌጆችን፣ ዩኒቨርስቲቶችን፣ የጤና ተቋማትን ፣ የወጣቶችንና የጎልማሶች ምእመናን ማንበራትን በተለይም ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናትን እንድትሠራላቸው በየጊዜው የሚጠይቋት አገልግሎቷ ተፈላጊ በመሆኑ ነው።

እነዚህን ጥያቄዎች አቅም በፈቀደ መጠን ማሟላት ይቻል ዘንድ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት፣ የየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስናችና የወረዳ አብያተ ክርስቲያናት ሀገራችን ድህነትን ድንቍርናንና በሽታን ለማስወገድ የምታደርገውን ጥረት ለማገዝ የልማት ተቋማትን እንዲገነቡ፣ መሠረተ ልማቶችን እንዲዘረጉ ጠቅላይ ቤተክህነት በየጊዜው ያበረታታቸዋል።

ከአዲስ አበባ የተመረጡ ሦስቱ አብያተ ክርስቲያናት ማለት ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም፣ መንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እና ደብረ ኀይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ለአባሎቻቸው ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ቀና መልስ በመስጠት የትምህርት የጤናና ሌሎች ተቋማትንም በመገንባት ማኅበራዊ አገልግሎታቸውን በአጥጋቢ ሁኔታ በመወጣት ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ ሌሎች አኀጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከእነዚህ ከሦስቱ ትምህርት ቀስመው ተመሳሳይና ከዚህም የበለጠ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መመከሪያና መማማሪያ መድረኮች ሊዘጋጁ ይገባል እንላለን።



# ምዕራፍ 4

## የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር

## ሁለት ሺህ ዓመተ ምሕረት ምሥጢር

የሐሳበ ዘመን ምንጭና መሠረት የሔኖክና የኩፋሌ መጻሕፍት ናቸው። ምክንያቱም ዓለም በተፈጠረባቸው ሰባቱ ዕለት ዑደት መሠረት ፀሥራ ሁለቱ ወሮች እያንዳንዳቸው በ30 ቀን፣ አራቱ ወቅቶች እያንዳንዳቸው በ91 ቀን፣ አንዱ ዓመትም በ364 ቀን ተወስኖ ተጽፎ የሚገኘው በእነዚህ መጻሕፍት ስለሆነ ነው። ወይከውን ዓመት ጥንቁቀ መዋዕለ ሠለስተ ምእተ ስሳ ወረቡዐ- ማለት ዓመቱም ጠንቅቆ ቢቆጥሩት ሦስት መቶ ስሳ አራት ቀን ይሆናል እንዲል (ሔኖክ 21፣ 49፤ ኩፋሌ 7፣30)።

ሳኅመኛም ሔኖክ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሰባት ሺሕ ዓመት ያለውን ዘመን በ0ሥር ሰንበታት ቀምሮ በስምንተኛው ሰንበት ትንቢቱን ከመድኀን ሱባዔውን ከትውልድ አስማምቶ ክርስቶስ የሚወለድበትን ዘመን ለይቶ ትንቢት ተናግሯል። ሱባዔም ቈጥሮአል። በዘመነ ሐዲስም አራቱ ወንጌላውያን ትንቢት የተነገረለት፣ ሱባዔ የተቈጠረለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነሆ ተወለደ ብለው ጽፈዋል። (ሉቃ.2፣ 7፤ ማቴ.1፣25)

ሐዋርያትም ጌታችን ያደረገውን ተአምራት ያስተማረውን ትምህርት እያስተማሩ ለመላው ዓለም የሥሥራት ተናግረዋል። ጌታችን እንደ ጾመም ምእመኑን ሁሉ ጾምን እንዲጾሙ፣ ምግባር ትሩፋትም እንዲሠሩ ሥርዓት ሠርተዋል። ቀጥሎም የአስክንድርያ ሲቀ ጳጳሳት የነበረው ቅዱስ ድሜጥሮስ ሐዋርያት ያስተማሩትን ትምህርት በመከተል የአጽዋማትንና የበዓላትን ቀኖና የሚያስረዳ መጽሐፈ ሐሳብን አቃንቶ ጻፈ። የተጥሩን መጽሐፍ አቃንቶ ጻፈ የተባለበት ምክንያት እንዲህ ነው።

ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እርሱ እስከነበረበት ዘመን ድረስ የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ የጌታችንን ጾም አርባው ቀን ከጥምቀት ማግስት ጀምረው እስከ የካቲት 21 ቀን በየዓመቱ ይጾሙ ነበር። ከዚህ በኋላ 31 ቀን ቈጥተው ሰሙነ ሕማማትን ይጾሙ የትንሣኤንም በዓል ያከብሩ ነበር። እንዲህ ማድረጋቸውም ቀድሞ በዘመነ ክርስቶስ በወሮች መካከል ካሉት የዕለታት ቍጥር ውስጥ አጽዋማትና በዓላት የተጀመሩበትን ቀን መነሻ ሰፈልጉ ነው። እንደዛሬው ልማድ የታወቁ ዕለታትን ሳይለዩ በሰንበት ሆነ፣ በሥራ ቀን አጽዋማትን ይጾሙ በዓላትን ያከብሩ ነበርና ቅዱስ ድሜጥሮስ ይህን የጾም ሥርዓት አቃንቶ ለመጻፍ እጅግ ይተጋ ነበር።

ስለዚህም በሠርቀ ሌሊትና በሠርቀ መዓልት ለሚውሉት አጽዋማትና በዓላት አቈጣጠር ስሌት አዕማደ ሃሳኑትን አበቅቴና መጥቅዕን እርሱ እስካለበት ዘመን ድረስ ለማውጣት ብዙ ጥረት አደረገ። የአውጣጡ ሥርዓትም እንዲህ ነው።

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እርሱ እስከነበረበት ዘመን ድረስ ያለውን ዓመተ ዓለም ቈጥሮና በንኡስ ቀመር ቀምሮ ከተፈፈሰው ዓመተ አበቅቴም አንዱን አትቶ /ቀንሶ/ ወንበርን አገኘ። ከወንበርም አበቅቴንና መጥቅዕን አወጣ። ቀጥሎም በዓለ መጥቅዕ የሚውልበትን ቀን ከዕለታት መካከል ፈልጎ ካገኘ በኋላ የዕለተ መጥቅዕን ቅውሳነ ዘመጥቅዑ ላይ ደምሮ መባጃ ሐመርን አገኘ። በመባጃ ሐመርም ጾመ ነነዌ የሚውልበትን ቀን ለይቶ አወቀ። ጾመ ነነዌ በተገኘበት መባጃ ሐመር ላይም ተውሳካትን እየደመረ አጽዋማትና በዓላት ሁሉ የሚውሉበትን ቀን አገኘ። ከዚህ በኋላ የጾመ ነነዌ፣ የጌታችን ጾም፣ የጾመ ሐዋርያት መግቢያ ከሰኞ አንሣይ ሥርዓትን ሠራ። እንዲሁም የበዓላት ቀን ማለት የደብረ ዘይት፣ የሆሣዕና፣ የትንሣኤ፣ የበዓለ ሠሙነ ቀን ከአሑድ ለዘሰዓሰሙ እንዳይወጣ፣ ስቅለት ከዓርብ፣ ርክበ ካህናትና ጾመ ድኅነት ከረቡዕ፣ ሐሙስ ከአሑሙስ ለዘሰዓሰም እንዳይወጣ ወሰነ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም የሰሙነ ሕማማትን ጾም፣ የትንሣኤን በዓል ከአርባው የጌታችን ጾም ጋር ተያይዘው እንዲጾሙና እንዲከበሩ ወሰነ፡፡ ዳግመኛም አጽዋማትና በዓላት ከተወሰነላቸው ቀመር ወደታች እንዳይወርዱ፣ ወደ ላይም እንዳይወጡ የማይናወጽ ሕግን ሠራላቸው፡፡ እንዲህ ባያደርግ ኑሮ ይህ ደገኛው ሥርዓቱ ፈርሶ እንደቀድሞው ልማድ አጽዋማቱና በዓላቱ በማንኛውም ቀን በዋሉ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ የአይሁድ አጽዋማትና በዓላት ከክርስቲያኖች አጽዋማትና በዓላት ጋር ለዘለዓለሙ እንዳይገናኙ የቀመርን ሥርዓት ሠራ፡፡ በመጨረሻም ቅዱስ ድሜጥሮስ ከአበቅቱና ከመጥቅዕ ጀምሮ እስከ ጥንተ ዮንና ሌሎችንም የቀመር ስልቶች ሁሉ ጽፎ፣ የአጽዋማትና የበዓላትን ኢይወርዳቸውና ኢየዓርጋቸውን በአንድ ዐቢይ ቀመር ወስኖ በዘመኑ ለነበሩ ሊቃነ ጳጳሳት ሁሉ ላከላቸው፡፡ እነርሱም ተቀብለው ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋር አንድ ሆኖ ስላገኙት ደስ ብሎአቸው አስተምረውበታል፡፡ ቍጥርም ቢሳሳት በአስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ይስተካከል በሚለው ሐሳብ ተስማምተዋል፡፡

ወአዘዙ ኵሉ ዘስሕተ አበቅቱ ወሐሳበ ይትመራሕ በሊቀ ጳጳሳት ዘአስክንድርያ" እንዲል፡፡ ይህንም መጽሐፈ ሐሳብ ቢቻል ክርስቲያን ሁሉ ባይቻል ግን ካህን ሁሉ ሊማረው ይገባል፡፡ ካህን ወመነኮስ ዘኢየአምር መጽሐፈ ሐሳብ ይትውን ከመ ፈሰገ ዘአልቦ ማይ፣ ወከመ ሀገር ዘአልቦ ሰብእ እንዲል፡፡

የዚህ መጽሐፍ ደግነቱ የሚታወቀውም በዐራቱ ማዕዘን ያሉ ምእመናን ሁሉ እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው በአተ ጾምን በአንድ ሰኞ ጀምረው በዓለ ትንሣኤን በአንድ እሑድ ስለሚያከብሩ ነው፡፡

# ክፍል 1

## የሁለት ሺሕ ዓመተ ምሕረት ምሥጢር

ዓለም ለሁለት ሺሕ ዓመት ወንጌልን ሰምታለች፡፡ "ወይሰብኩ ዝ ወንጌለ መንግሥት ውስተ ኵሉ ዓለም ከመ ይኩን ሰምዐ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ ወይእተ አሚረ ይብጽሕ ኀልቀት" ማለት ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፡፡ ለአሕዛብ ሁሉ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ ያን ጊዜ ፍጻሜ ይመጣል እንዳለ (ማቴ.24፣14)፡፡ የኢየሩሳሌም ጥፋትም የዓለም ፍጻሜ ምሳሌ ስለሆነ ጌታችን ለአይሁድ ከተናገረው የመከራ ትንቢት ወድኋኛው ዘመን ወደ ዓለም ፍጻሜም የሚያመለክት ነው፡፡ (ማቴ.24፣ 21-23) ይሁን እንጂ ሙሉ ፍጻሜ የሚሆነው በዓለሙ መጨረሻ መሆኑን ጌታችን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡-

ምሳሌዋን ከበለስ እወቁ ጫፍዋ ያቈጠቈጠ ቅጠልዋም የለመለመ እንደሆነ መከር እንደተቀረበ ታውቃላችሁ፡፡ እንዲሁም ደግሞ እናንተም ይህን ሁሉ ባያችሁ ጊዜ በደጅ እንደተቀረበ እወቁ፡፡ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስም ይህች ትውልድ እንዳታልፍ እውነት እላችኋለሁ፡፡" (ማቴ.24፣32-34)

ማሕሌታይ ያሬድም ይህን የጌታችን ቃል ሲተረጉም እንዲህ ይላል፡- "በለስ ዘይቤ፣ ቤተ እስራኤል እሙንቱ ወዐጸደ ወይኑ ክርስቶስ ውእቱ ዬ፣ ዬ፣ ዬ ወእመ በጽሐ ዕድሜሁ ይፈንዎሙ ለመላእክት በታሕ ቀርን" ማለት፡- በለስ የተባሉት የእስራኤል ቤተሰዎች ናቸው፡፡ የወይኑ ተክልም ክርስቶስ ነው፡፡ ወዮ ወዮው ይብላኝ የሰቆቃና የልቅሶ ቃል ነው፡፡ ዘመኑ በደረሰ ጊዜም መላእክቱን ከመለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፡፡ ተብሎ ምዕራፍ በተባለው መጽሐፍ ተተርጉሟል፡፡ ይህ ትውልድ አያልፍም ማለትም እነዮሐንስ ወንጌላዊ የኢየሩሳሌምን ጥፋት ካዩ በኋላ 30 ዓመት ኑረዋልና፡፡ ትውልዱ አያልፍም የተባለው በከፊል ተፈጽሟል፡፡ ሙሉ ፍጻሜ የሚሆነው ግን በዓለሙ መጨረሻ ነው፡፡ የሐሳብ ዘመን መምህራንም ጌታችን ያስተማረውን ትምህርት ዐብነት በማድረግ፡- ከአዳም እስከ 14 ቀመረ ድሜጥሮስ ባለው የዘመናት ቁጥር የወልደ ዕጓለመሕያውን መምጣት የምንጠራጠርበት ጊዜ ይሆናል ይላሉ፡፡ በዘንትሐዘብ ምጽአተ ወልደ ዕጓለመሕያው በዐሠርቱ ወአርባዕቱ አትማር በድሜጥሮስ እንዲል (መርሐ ፅውር)፡፡





ስሌቱም እንዲህ ነው፡-

14ቱ ቀመረ ድሜጥሮስ (14X532)=7448 ዓመተ ዓለም ነው፡፡ ከዚሁም ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው 5500 ዓመት ሲቀነስ 1948 ዓ.ም. ይተርፋል፡፡

በበለስ የተመሰለችው የእስራኤል መንግሥት በ1948 ዓ.ም. እንደ ተቋቋመች የታወቀ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ያለው ትውልድ ሳያልፍ ደግሞ ምጽአት እንደሚሆን ከጌታችን ቃል ተረድተናል፡፡ (ማቴ.24፣34) የአንድ ትውልድ ዕድሜም 70 ነው ቢበዛም 80 ዓመት ነው፡፡ (መዝ.89፣10)

ስለዚህ ይህን ሁሉ ባያችሁ ጊዜ በደጅ እንደቀረበ እወቁ ማለት ከደጅ የቆመ ፈጥኖ እንዲገባ ፈጥኖ ይደረጋልና፡፡ ተዘጋጅታችሁ ተቀመጡ ማለት ነው፡፡ (ሙቴ.24፣33)

አሁን እኛ ያለንበት ሁለተኛው ሺሕ ዓመት ለሰው ልጅ ሁሉ ሕይወት የሚጠቅም ይህን የመሰለ ታላቅ ቁም ነገር ያለበት ምሥጢራዊ ታሪክ የያዘ ነው፡፡ ዳግመኛም የዘለዓለማዊው እግዚአብሔር አብ ልጅ የሆነው ሥሙው ቃል የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ከሌሎች በዓላት ይልቅ ይበልጥ በዚህ ሁለት ሺሕኛው ዓመት በታላቅ ሥርዓተ አምልኮ በክርስቲያኖች ዘንድ ስለሚከበር ነው፡፡

ከዳግማይ አዳም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ ቁጥሩን ሁለት ሺሕኛ ዓመት ለማክበር ስንሣ ከቀዳማይ አዳም ጀምሮ የነበሩት በሺሕ የሚቈጠሩ ዓመታት መነሻና መድረሻ የሚሆኑም ሦስት የዐሐይ ጥንታት አሉ፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዓለም የተፈጠረበት ዕለተ አሑድ ጥንተ ዕለት ወይም ሐሳበ ሰማይ ወምድር ይባላል፣
- ቀመር የተጀመረበት ዕለተ ሠሉስ ጥንተ ቀመር ይባላል፣
- ብርሃናት የተፈጠሩበት ዕለተ ረቡዕ፣ ጥንተ ዮን፣ አበቅቱ ፀሐይ ወይም ሐሳበ ፀሐይ ይባላል፡፡ ጥንት ማለትም መነሻ፣ መጀመሪያ ማለት ነው፡፡

ይህ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ማለት እስከ ሁለት ሺሕ ዓመተ ሥጋዊ ያለው ዘመን ሲቈጠር በዐሐዲ 7ሺሕ 5መቶ ዓመት፣ በጨረቃ 7ሺሕ 7መቶ 29 ዓመት 7 ወር ከ27 ቀን ነው፡፡

ከ7ቱ ሺሕ 5መቶ ዓመተ ፀሐይ 5መቶው የ8ኛው ሺሕ ግማሽ ነውና እርሱን ሺሕ እስኪሞላ ድረስ አቈይቶ የሐሳበ ዘመን መምህራን በዓውደ ፀሐይና በሰባዔ እየቈጠሩና እየቀመሩ ከ7ቱ ሺሕ ዓመት የእያንዳንዱን ሺሕ ዓመት መነሻና መድረሻ ቀን ለይተውና አውቀው ከዚያ ያደረሳቸውን አምላክ በማመስገን የእያንዳንዱን ሺሕ ዓመት ፍጻሜ በጸሎትና በምሕላ ያስቡት ነበር፡፡ ከቀዳማይ አዳም ጀምሮ የእያንዳንዱ ሺሕ ዓመት መነሻና መድረሻ የሚሆኑ ዕለታት ሲዘረዝሩም እንዲህ ነው፡፡

1ኛው ሺሕ ከጥንተ ቀመር ከማክሰኞ ተነሥቶ በዕለተ ዓርብ ተፈጽሟል፡፡ 2ኛው ሺሕ ከዕለተ ቀዳም ተነሥቶ በዕለተ ሠሉስ ተፈጽሟል፡፡ 3ኛው ሺሕ ከዕለተ ረቡዕ ተነሥቶ በዕለተ ቀዳም ተፈጽሟል፡፡ 4ኛው ሺሕ ከዕለተ አሑድ ተነሥቶ በዕለተ ረቡዕ ተፈጽሟል፡፡ 5ኛው ሺሕ ከዕለተ ሐሙስ ተነስቶ በዕለተ አሑድ ተፈጽሟል፡፡ 6ኛው ሺሕ ከዕለተ ሰኑይ ተነሥቶ በዕለተ ሐሙስ ተፈጽሟል፡፡ 7ኛው ሺሕ ከዕለተ ዓርብ ተነሥቶ በዕለተ ሰኑይ ተፈጽሟል፡፡ ይህ የ7 ሺሕ ዓመት ዑደት በጥንተ ቀመር በዕለተ ሠሉስ ተጀምሮ በ7ኛው ጥንተ በዕለተ ሰኑይ መፈጸሙን መምህራኑ በነበራቸው የሐሳበ ዘመን ስሌት ችሎታ አስልተው አውቀውና ተረድተው ለመጭው ትውልድ መዝግበው ያቈዩት ነው፡፡ አሁን እኛ ያለንበት 8ኛው ሺሕ ዓመት ደግሞ ከጥንተ ቀመር ከማክሰኞ ተነሥቶ ለወደፊቱ በዕለተ ዓርብ ገና ይፈጸማል፡፡ ከጥንተ ፍጥረት እስከ ዛሬም ምጽአት ላሉት ዓመታት ሁሉ ሥርዓታቸው ይህ ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ቀደምት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እያንዳንዱ ሺሕ ዓመት ከሚፈጸምበት ዕለት ላደረሳቸው አምላክ ምስጋና ያቀርቡ እንደነበር እኛም በዕለተ ሠሉስ ከጀመረው ከ8ኛው ሺሕ 5መቶውን ፈጽመን ወደ 6ኛው መቶ ዓመት መባቻ ላሽጋገረን ለፈጣሪያችን ምስጋና እያቀረብን ተከታዮቹን ዓመታት የሰላምና የጤንነት ዘመን እንዲያደርግልን ከወትር መጸለይና ምህላንም ማድረስ ይገባል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል 2

## ሐሳበ ዘመን:-

የሐሳበ ዘመን ትምህርት ባሕረ ሐሳብ ይባላል። ባሕረ ሐሳብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት አንዱ ክፍል ነው። በአሁኑ ጊዜ ሥርዓተ ትምህርቱ በዐራት ጉባኤያት ተመድቧል። ያውም እንዲህ ነው።

ጉባኤ 1 መጻሕፍተ ብሉያት
ጉባኤ 2 መጻሕፍተ ሐዲሳት
ጉባኤ 3 መጻሕፍተ ሊቃውንት
ጉባኤ 4 መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው።

በጥንት ዘመን ግን የቅኔና የባሕረ ሐሳብ ትምህርት 5ኛ ጉባኤ እንደነበር አበው መምህራን ይናገራሉ። ጥንታዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት በተባለ መጽሐፍም የባሕረ ሐሳብ ትምህርት 5 ኛ ጉባኤ እንደነበር ተጽፎ ይገኛል። (ገጽ 216)

ባሕረ ሐሳብ የሚለው ቃል ሐሰበ ቁጠረ ከሚለው ግስ የወጣ ዘመድ ዘር ነው። ስለዚህ ባሕረ ሐሳብ ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ወይም ዓመተ ዓለም ማለት ነው። ሐሳበ ባሕር ቢል ግን የዘመን ቁጥር ማለት ነው። ባሕረ ሐሳብ መባሉም የባሕር አዝዋሪቱ፣ መንገዱ፣ ጥልቀቱና ስፋቱ ረዥምና ሰፊ እንደሆነ የባሕረ ሐሳብ ትምህርትም መንገዱና ስፋቱ ልዩ ልዩ በሆነ የአቅማራትና የሰባዕያት ምሥጢር የተዘጋጀ ስለሆነ ነው።

የባሕረ ሐሳብ ትምህርት መርሐ ዕውርና አቡሻህር የተባሉ ሁለት ታላላቅ የቁጥር አርእስቶችን አጠቃልሎ የያዘ ነው። አቡሻህር የተባለው መጽሐፍ መዛአ ዐሐይን፣ ምሕዋረ ከዋክብትን፣ የጨረቃ ብርሃን ምልዐትንና ሕጸጽን የሚያስተምር ነው። መጽሐፉ በደራሲው ስም ተሰይሟል። መርሐ ዕውር የተባለው መጽሐፍ ደግሞ የአቅማራትን ምሥጢር የአጽዋማትንና የበዓላትን ሥርዓት የሚያስረዳ ነው።

የትምህርቱ ምንጭ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር የሚመሳሰል መሆኑ ቢታወቅም እንኳ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሐሳበ ዘመን ሊቃውንት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ምሁራን ከጻፉዋቸው የቁጥር መጻሕፍት ጋር አያገናዘቡና ልዩ ልዩ ትርጓሜንም እየሰጡ ትምህርቱን ያስፋፉት እንጂ የውጭ ውርስ አይደለም። ከውጭ ለማስረጃነት የሚጠቀሰው የባሕረ ሐሳብ መጽሐፍ ወደ ግእዝ ቋንቋ የተተረጐመውም የደብረ ሊባኖስ መምህር በነበሩት በእጨጌ ፅንባቶም ትእዛዝ ነው። የተረጐሙትም አባ ሰሊጵ ዘደብረ ሊባኖስና የደብረ ብሥራት መምህር አበሞ ናቸው ይባላል። ይህን መጽሐፍ የተረጐሙት እነርሱ መሆናቸውን ለማስረዳትም "ዘደብረ ሊባኖስ ሰሊጵ ወዘደብረ ብሥራት አበሞ ለአቡሻህር ተመሰልዎ መጽሐፈ ሐሳብ በተርጉሞ፡፡" ማለት፡- የደብረ ሊባኖስ መምህር አባ ሰሊጵና የደብረ ብሥራት ሊቅ አበሞ የቁጥር መጽሐፍን በመተርጐም አቡሻህርን መሰሉ ተብሎ ሙያቸውን የሚገልጽ ቅኔ ተደርሶላቸዋል።

የቁጥር መጽሐፉን ባሕረ ሐሳብ፣ መርሐ ዕውር ብለው ሰይመው፣ እያንዳንዱ አራት ዓመትም በዐራቱ ወንጌላውያን ስም እንዲጠራ ወስነው አዲስ ሥርዓት የሠሩትም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ናቸው። መርሐ ዕውር ማለት ከድንቁርና ጨለማ ወደ ዕውቀት ብርሃን መርቶ የሚያደርስ ማለት ነው። በባሕረ ሐሳብ ትምህርት ያለው የዘመናት ቁጥርም አንድ ብሎ የሚቆጠረው የአዳምን ዕድሜ መነሻ በማድረግ ነው።

## የአዳም ተስፋ:-

እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮና በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ የንጉሥነትን፣ የክህነትንና የነቢይነትን ማዕርግ ሰጥቶ ንጉሠ ምድር ሥዩመ እግዚአብሔር ተብሎ በቤተ መንግሥቱ በገነት እንዲኖር ፈቅዶለት ነበር። እርሱ ግን ምድራዊ መንግሥት አንሶት ሰማያዊ መንግሥትን ለተመኘ ከክብሩ ተዋርዶ ከገነት ወጣ።



ነገር ግን አዳም በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ ንስሐ ስለገባና ካህን እንደመሆኑ መጠንም መሥዋዕት አቅርቦ እግዚአብሔርን ስለለመነ እግዚአብሔር መሥዋዕቱን ተቀብሎ ልመናውን ሰምቶ እርሱንና ዘሩን ለማዳን እንደሚመጣ ተስፋ ሰጠው። የተስፋውም ቃል እንዲህ ነው። "ወይቤ እግዚአብሔር ለአዳም አነ ሠራዕኩ ላዕለ ዝንቱ ምድር መዓልታተ ወዓመታተ ከመ ተሀሉ አንተ ውስቴታ ወታንሶሱ እስከ እሙንቱ ዓመታት ወመዓልታት እፈኑ ቃልየ ዘፈጠረተከ ወተዐጸውካ፣ ወይእቲ ዘአውዕአተከ እምገነት፣ ወሶበሂ ወደቀ እንሥአተከ ወይእቲ ካዕበ ዘታድኅነከ በተፍጻሜተ ኃምስቱ ዕለት ወመንፈቀ ወሶበ ሰምዐ አዳም ዘንተ ቃለ እም እግዚአብሔር ኃምስተ ዕለተ ወመንፈቀ ኢያእመረ ትርጓሜሃ..... ወእግዚአብሔር በምሕረቱ ላዕለ አዳም እርእያሁ ወአምላሊሁ ተርጉሞን ሎቱ እስመ ውእቶን ኀምሳ ምእት ወኃምስቱ ምእት ዓመታት ከመ ይመጽእ ወያድኅኖ ሎቱ ወለዘርዐ" ማለት ፡- መዓልታትንና ዓመታትን በዚህ ምድር ላይ ሠራሁልህ ይኸውም እነርሱ እስኪፈጸሙ ድረስ በምድር ላይ ትኖርና ትመላለስ ዘንድ ነው። የፈጠረችህና የተላለፍካት ከገነት ያወጣችህና በወደቅህም ጊዜ ያነሳችህ ዳግመኛም አምስት ቀን ተኩል ሲፈጸም የምታድንህ ቃሌን እልክልሃለሁ ብሎ እግዚአብሔር ለአዳም ነገረው። አዳምም አምስት ቀን ተኩል የሚለውን ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ በሰማ ጊዜ የእነዚህን ታላላቅ ነገሮች ትርጓሜ ሊያስተውል አልቻለም። ስለዚህም እግዚአብሔር አምስት ቀን ተኩል ማለት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት መሆናቸውን ገልጾ አርእያውና አምላያው ለሆነው ለአዳም በቸርነቱ ተረጐመለት። ያንጊዜም እርሱንና ዘሩን ለማዳን እንደሚመጣ ተስፋ ሰጠው ። (ትውፊ ዘመን ገጽ 147)

አዳምም ይህን ተስፋ ለልጆቹ ነገረ አስተማረም። ልጆቹም ተስፋው የሚፈጸምበትን ጊዜ ለማወቅ እኩሉ በፀሐይ፣ እኩሉ በጨረቃ፣ እኩሉ በከዋክብት ዘመናትን ይቆጥሩ ትንቢትን ይናገሩ ጀመር። ከእነርሱም መካከል ሱባዔውን የቁጠሩ ትንቢቱን የተናገሩ ሔኖክ፣ ሱቱኤል፣ ዕዝራ፣ ኤርምያስና ዳንኤል ናቸው።

## ሰንበተ ሔኖክ-

ሔኖክ ዘመናትን የቆጠረባቸው ትንቢትን የተናገረባቸው ሰንበታት ዐሥር ናቸው። ወርኢኩ ዐሥረ ሰንበታተ እምሰብዓቱ ማኅተመ ዓለም፡- ማለት ከሰባቱ ማኅተመ ዓለም ዐሥር ሰንበታትን አየሁ እንዲል እንጂ ማኅተም አንድ ሺሕ ዓመት ነው። ሰባቱ ማኅተምም ሰባት ሺሕ ዓመት ይሆናል ብለው መተርጐማን ያትታሉ።

ሦስተኛም ሔኖክ የትውልዱን ታሪክ ሲናገር እኔ በመጀመሪያይቱ ሰንበት ሰባተኛ ትውልድ ሆኜ ተወለድሁ ይላል። ይህም ከአዳም ጀምሮ እስከ እርሱ ድረስ ያለውን የትውልድ ሐረግ ቁጥሮ ነው። የሔኖክ ሱባዔ የሚቆጠረው በትውልድ ነው የሚባለውም ስለዚህ ነው።

ሔኖክ ኦሪትና ነቢያት የተናገሩትን ትንቢት የሚፈጽም የእግዚአብሔር ልጅ ከዐሥሩ ሰንበታት በስምንተኛው ሰንበት ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ አስቀድሞ ትንቢት ተናግሯል። ወእምድኅረዝ ትከውን ሳምንተ ሰንበት እንተ ጽድቅ፣ ወይትወሀብ ላቲ ሰይፍ ከመ ይትገበር ኩነኔ ጽድቅ ..... ወይትሐነጽ ቤተ ንጉሥ ዐቢይ ለስብሐት እስከ ለዓለም፡- (ሔኖክ 35፣1-19) ስምንተኛይቱ ሰንበት ጽድቅና ኩነኔ የሚታወቅባት ሱባዔ ናት። ሰይፍም ለርስዋ ይሰጣታል ታላቁ ንጉሥ የሚመሰገንባት ይሠራል። ምስጋናውም ዘለዓለማዊ ነው ብሏል። ምሥጢሩም እንዲህ ነው።

ለርስዋ ሰይፍ ይሰጣታል፡- ማለት ጽድቅና ኩነኔ የሚታወቅባት ወንጌል ያንጊዜ በዓለም ሁሉ ትሰበካለች ማለት ነው።

የታላቁ ንጉሥ ቤት ይሠራል፡- ማለት ታላቁ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሰገንባት ቤተ ክርስቲያን ትሠራለች ማለት ነው።

ምስጋናውም ዘለዓለማዊ ነው ማለት፡- ወንዶችና ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰብስበው ስለሕጉ ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር እያሉ ዘወትር ያመሰግናሉ ማለት ነው። በጠቅላላው ስምንተኛ ሰንበት [illegible] ዘመነ ክርስትና ናት ብለው መተርጉማን ያትታሉ።

www.ethiopianorthodox.org

የሔኖክ ሰንበታት ምሥጢርን ለመረዳት በሰባት በሰባት መቶ ዓመታት ተመድበው ከአንድ እስከ ፀሥር ክፍል የሚቆጠሩትን ሰንበታት ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ መላው የሔኖክ ሰንበት ሲደመር 7 ሺህ ዓመት ይሆናል፡፡ ሰንበት ማለት በዚሁ ገጽ ሱባዔ ማለት ነው፡፡ የሔኖክ ሱባዔ የሚቆጠረው በአበው ዕድሜ ነው ነቢያት ሱባዔያቸውን የሚቆጥሩት በዕለት፣ በዓመትና በትውልድ ነው፡፡ ስለዚህም የሔኖክ ሱባዔ ሱባዔ ትውልድ ይባላል፡፡ (ሔኖክ 35፣2፣ክፍል 91)

## ሱባዔ ኤርምያስ፡-

ኤርምያስ ከባቢሎን እንደተመለሰ በፈረሰው ቤተ መቅደስ ውስጥ ገብቶ ሲጸልይ ሳለ እንደሞተ ሆኖ ከቆየ በኋላ በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ ፈጣሪያችንን በአንድ ቃል አመስግኖ የአብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን አመስግኑ ከዚህ በኋላ ሰው ሊሆን ሥጋ ሊለብስ ወደዚህ ዓለም ሊመጣ የቀረው ዘመን 333 ሱባዔ ዕለት ነውና እርሱ ወደዚህ ዓለም ይመጣል፡፡ ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትንም ይመርጣል ብሎ ትንቢት ተናገረ፡፡

ኤርምያስ ሱባዔውን የጀመረበት ትንቢቱን የተናገረበት ራእዩን ያየበት ዘመን ዓለም በተፈጠረ 115 ሺህ 54 ዓመት ነው፡፡ የኤርምያስ ሱባዔ የሚቆጠረው በዕለት ነው፡፡ አንዱ ሱባዔ 490 ዕለት ነው፡፡ መላው ሱባዔ (490X33) = 163,170 ዕለት ይሆናል፡፡ ይህ ወደ ዓመት ሲለወጥ 446 ይሆናል፡፡ ቀሪው 1 ዓመት ከ15 ቀን ነው፡፡ ይህ በትርፍ ይያዛል እንጂ አይቆጠርም፡፡ ትንቢቱ ከተነገረበት ዓመት እስከ ክርስቶስ ልደት ያለው ጊዜ 446 ዓመት መሆኑ በዚህ ይታወቃል፡፡

| | |
|---|---|
| ኤርምያስ ሱባዔውን የቆጠረበት ዘመን ..... | 5054 ዓመት |
| ትንቢቱ ከተነገረበት ዓመት እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ..... | 446 ዓመት |
| ድምር ..... | 5500 ዓመት ይሆናል፡፡ |

ስለዚህ በተነገረው ትንቢት በተቆጠረው ሱባዔ መሠረት 5500 ዓመት ሲፈጸም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለዱ በዚህ ይታወቃል፡፡ (ተረፈ ኤርምያስ 11፣37:38,42-48,52፣53)

## ሰንበተ ዳንኤል

ዳግመኛም ስለጌታችን ሰው መሆን ጊዜ ወስኖ ሱባዔ ቍጥር የተናገረው ዳንኤል ነው፡፡ የዳንኤል ሱባዔ የሚቆጠረው በዓመት ነው፡፡ ዳንኤል "ሰባው ዘመን በተፈጸመ ጊዜ እንዘንጋ ዘኢ" ተብሎ በኤርምያስ የተነገረውን ትንቢት እያስታወሰ ሲጸልይ መልአኩ ገብርኤል በሰው አምሳል ተገለጸ፡-

እግዚአብሔር ልመናህን ሰምቷልና እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ፡፡ አሁንም ነገሩን መርምር ራእዩንም አስተውል ኃጢአት የሚሠረይበትና ቅዱስ ቅዱሳን ጌታችን የባሕርይ ክብሩን ገንዘብ የሚያደርግበት ሰባው ሱባዔ ሊደርስ ሊፈጸም ነው ብለህ ወገኖችህን ቅጠራቸው ብሎታል፡፡ (ዳን.9፣22-25, ኤር.29፣10)፡፡
ሰባ ሱባዔ አራት መቶ ዘጠና ዓመት ነው፡፡ ይህ ከማጠቡት እስከ ስቅለት ያለውን ጊዜ ያመለክታል፡፡ (ተር. ሕዝ.4፣6) ሰባው ሱባዔ በሦስት ክፍል ይከፈላል፡፡ መጀመሪያው ክፍል ሰባት ሱባዔ ነው፡፡ ይህ አርባ ዘጠኝ ዓመት ነው፡፡ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የተሠራበት ጊዜ ነው፡፡

ሁለተኛው ክፍል ስድሳ ሁለት ሱባዔ ነው፡፡ ይህ አራት መቶ ሰላሳ አራት ዓመት ይሆናል፡፡ ይህም የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከታደሰበት ጊዜ ጀምሮ ጌታችን ሰው ሆኖ ማስተማር እስከጀመረበት ያለው ጊዜ ነው፡፡ ሰባቱ ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ሲደመር ስድሳ ዘጠኝ ሱባዔ ይሆናል፡፡ ይህ አራት መቶ ሰማንያ ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡ ጌታችን የተጠመቀበት ጊዜን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጌታችን ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌል አመኑ እያለ ያስተምር ጀመር፡፡ ዘመኑ ተፈጸመ ማለት የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን የተቆጠረው ሱባዔ መድረሱን ያመለክታል፡፡ (ማር.1፣14 ዳን.9፣25)





ሦስተኛው ክፍል አንድ ሱባዔ ነው፡፡ ይህም ሰባት ዓመት ነው፡፡ በዚህም እርሱ ጌታ ከብዙ ሰዎች ጋር ለአንድ ሱባዔ ጽኑ ቃል ኪዳን ያደርጋል፡፡ በሱባዔው እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል ተብሎ የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም ጌታችን የሰው ልጆችን ለማዳን በዚሁ ጊዜ የሞትን ጽዋ ተቀብሎ በአሪት መሥዋዕት ምትክ ራሱን መሥዋዕት ስላደረገ ነው፡፡ (ዳን.9፣27) ሰባው ሱባዔ ከሚጠት እስከ ስቅለት ያለውን ጊዜ ያመለክታል የተባለውም ስለዚህ ነው፡፡ (ትርጓሜ ሕዝቅኤል 4 ፣6 ገጽ 56)

## ሐሳበ ዕዝራ ሱቱኤል፡-

ዕዝራ ሱቱኤል በ5000 ዓመተ ዓለም የነበረ ነቢይ ነው፡፡ እርሱም በናቡከደነፆር ዘመነ መንግሥት የተቃጠሉትን መጻሕፍት ለመተካት አምስት ጸሓፊዎችን መድቦ በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመራ ንባቡን በቃሉ በማስረዳት 94 መጻሕፍትን አጽፎአል፡፡ (ዕዝ.14፣44-46)

በእነዚህ መጻሕፍት የተገለጹትን ምሥጢር መሠረት በማድረግ ስለ ኀልፈተ ዓለም የገለጸው ትምህርትም እንዲህ ነው፡፡ የዚህ ዓለም የሕጻንነቱ ወራት አልፎአል ዘመኑም አርጅቷል፡፡ የሚያልፍበት ዘመንም ከዐሥር የተከፈለ ነው፡፡ አሁን ከዐሥረኛው ክፍል ደርሷል፡፡ የተረፈውም የዐሥሩ ክፍል እኩሌታ ነው ሲል አስረድቷል፡፡ (ዕዝ.13፣10-13) ምሥጢሩም እንዲህ ነው፡፡

ከዐሥረኛው ክፍል ደርሷል ማለት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እርሱ እስከነበረበት ጊዜ ያለውን ዘመን 5000 ዓመት መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተረፈውም የዐሥሩ ክፍል እኩሌታ ነው ማለት እርሱ ከነበረበት ጊዜ ወዲህ ያለው ዘመን 2500 መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የሐሳበ ዕዝራ አቆጣጠር ከፍጥረት እስከ ኀልፈተ ዓለም ያለው ዘመን ጠቅላላ ድምር (5000+2500)=7500 ዓመት መሆኑን ያስረዳል ብለው የብሉይና የቁጥር መምህራን ይተረጉማሉ፡፡

ይህም ከቀዳማይ አዳም ጀምሮ አሁን እኛ እስከደረስንበት እስከ ሁለተኛው ሺህ ዓመተ ሥጋዊ ያለውን የዘመናት ቁጥር በእጎዝ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ በዚህ ዘመን ብዙ ምልክቶች እየታዩና እየተነገሩም ናቸውና ትንቢቱን በቸልተኝነት ልንመለከተው አይገባም፡፡

በጠቅላላው የባሕረ ሐሳብ ትምህርት በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረው ትንቢት የተቈጠረው ሱባዔ የሚፈጸምበትን ጊዜና ዘመን እየለየ የሚያስረዳና የሚያመለክት የጊዜ መስተዋት ነው፡፡ እንዲህ መሆኑ ለማስረዳትም የብሉይና የሐሳበ ዘመን መምህራን ዘመኑን በስልሳ ሰንበተ ወንጌላውያን እየሰፈሩና እየቈጠሩ ከአሪትና ከነቢያትም ብዙ ምስክር እየሰጡ ትውልዱን ከዘመን፣ ትንቢቱን ከመድኀን እያስማሙና እየተረጐሙ ባለፈው ዘመን የሆነውንና የሚሆነውን በዝርዝር አስተምረዋል፡፡ ያስተምራሉም፡፡

የሰንበተ ወንጌላውያንን ምሥጢር ያወቀና የተረዳ የመልከዐ ኢየሱስ ደራሲም ድንረ ተፈጸመ ሱባዔ ሰንበታት ስባ (ፀ) በምጽአትከ ተነትመ አበሳ፡- ማለት ስባ ሰንበታት ከተፈጸሙ በኋላ በዳግም ምጽአትህ በደልና ኃጢአት ሁሉ ይደመሰሳል ብሎ የሰንበታትንና የዘመናትን ረቂቅ ምሥጢር አስረድቷል፡፡ 60 ሰንበታት ማለትም (60 x133)=7980 ዓመት ማለት ነው፡፡ ይህም ከሱቱኤል ዕዝራ ሐሳብ የተለየ የዘመናት አቈጣጠር ሥርዓት ነው፡፡ ምክንያቱም የሱቱኤል ዕዝራ ሐሳብ የዳግም ምጽአትን ጊዜ ሲያስርበው የመልከዐ ኢየሱስ ደራሲ ሐሳብ ግን ዘመኑን ያርቀዋልና ነው፡፡ ይህም ሕጽጹን ትቶ ወይም ሕጽጹን መልቶ መቀጠር የቅዱሳት መጻሕፍት ልማድ ነው ብሎ የተለያዩትን ሁለቱን የዘመናት ቍጥሮች ማስተረቅ የሚቻል መስሎ ይታያል፡፡ (ዘፍ.15፣13፣ ዘዳ.12፣40፣ገላ.3፣17)

ዘመን ማለት በኀሊና ሲመረመር የጊዜንና የዕድሜን መጠንና ልክ የሚወስን መሆኑን መጽሐፈ አበ ክህር ያስረዳል፡፡ ይህ ዘመን የሚባለው የጊዜ ዕድሜ በስያሜው አጠራር መሠረት ኀላፊ ጊዜ፣ ያሁንና የትንቢት ጊዜ ተብሎ በሦስት ክፍለ ጊዜያት ይከፈላል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ወፍካሬሁሰ ለዘመን በውስተ ልብ አርአያ ወሰን ውስቱ ለጊዜ ዕድሜ ወዝንቱሰ ጊዜ ዕድሜ ዘስመ ዘመን ይትከፈል አመንገለ ስሙ ኀበ ሠለስቱ ክፍል ኀበ ዘኀለፈ ዘመን፣ ወኀበ ዘይመጽእ፣ ወኀበ ዘሀሎሃ እንዲል (አቡ.አን 1) ። ከፍጥረት እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ ያለው ዘመን ሁሉ በእነዚህ ሦስት ጊዜያት ሰፈርና ሲቁጠር ይኖራል። ያለፈውንና የሚመጣውን ዘመን ቁጥሮና ሰፍሮ መረዳትና ማስረዳት እንደሚገ ሲያስረዳም አሪት ዘዳግም ምዕራፍ 4 ቁጥር 32 እንዲህ ይላል። ተሰአሉ ዘቀዲሙ መዋዕለ ዘኮ እምቅድሜክሙ እምአመ ፈጠሮ እግዚአብሔር ለዕጓለ አመሕያው ዲበ ምድር እምአጽናፈ ሰማይ እስ አጽናፈ ሰማይ ለአመ ኮነ ከመ ዝንቱ ነገር፡- ማለት እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ ከፈጠረው ጀምሮ ከሰማይ ዳር እስከ ዳርቻዋ ድረስ ከቶ እንዲህ ያለ ታላቅ ነገር ወይም እንደርሱ ያለ ተሰምቶ እንደሆ ከአናንተ በፊት የነበረውን የቀደመውን ዘመን ጠይቃችሁ ተረዱ ማለት ነው።

እንዲሁም ነቢዩ ዳዊት የቀድሞውን ዘመንና ዓመተ ዓለምን እያሰብሁና እየተናገርሁ ከልቤ ጋ ተጨዋወትሁ። ነፍሴንም አነቃቃት ነበር አያለ ያለፈውን ዘመን በማስታወስ ይጸልይ ነበር። ወኀለይኩ መዋዕለ ትካት፣ ተዘከርኩ ዓመተ ዓለም ወአንብበኩ፣ ሌሊተ ተዛዋዕኩ ምስለ ልብየ፣ ወአንቃሕኩዋ ለነፍስ እንዲል (መዝ.76፣5) የሐሳበ ዘመን መምህራንም የዘመን ወይም የጊዜን አቁጣጠር ሥርዓት ዓመተ ዓለ ብለው የሰየሙት ይህን መሠረት በማድረግ ነው።

## ኢዮቤላትና ሱባዕያት፡-

ከፍጥረት እስከ ፀአተ አሥራኤል ድረስ የነበረው ዘመን ሁሉ በኢዮቤልዩና በሱባዔ የተቈጠረ ነው ። የእያንዳንዱ ዓመት ቀን የተቆጠረውም 364 ቀን ባለው የፀሐይ ዓመት ነው። ዓመቱ በሱባዔ ሲቀመ 52 ሱባዔ ይሆናል። የሱባዕያቱ ሥርዓትም በልዩ ልዩ ክፍል የተመደበ ነው። ያውም ሰባተኛው ዕለት ፣ ሰባተኛው ዓመት፣ ኀምሳኛው የኢዮቤልዩ ዓመት ነው።

## ሰባተኛው ዕለት

ሰባተኛው ዕለት ማለት ከሳምንቱ ዕለታት ሰባተኛ የሆነው ቀዳም ሰንበት ነው። አርሱም ከመደበኛ ሥራ የሚታረፍበት በእግዚአብሔር የተመረጠ የዕረፍት ቀን ነው። በእግዚአብሔርና በአሥራኤል ልጆ መካከልም ዘለዓለማዊ የታል ኪዳን ምልክት ሆኖ ጸንቶ ይኖራል። (ዘፀ.31፣16-17)

በየሳምንቱ ሦስ አራት ሰዓት ሙሉ ሰንበትን የማክበር ታሪክም የአሥራኤል ሕዝብ ከግብጽ ከወ በኋላ በሁለተኛው ወር በሲና ምድረ በዳ ተጀመረ (ዘፀ.16፣1፣23፣1)። በየዓመቱ ከሚመላለሱት ኀምሳ ሁለት ሱባዔያት ወይም ሳምንታት ኀምሳ ሁለቱ ቀን የቀዳሚት ሰንበት በዓል ነው። (ዘፍ.2፣1-3፣ ዘፀ.20 ፣8-11) ።

## ሰባተኛው ዓመት፡-

በየሰባቱ ዓመት ስሚመላለሰው ሰባተኛው ዓመትና በየአርባ ዘጠኝ ዓመት ስሚመላለሰው ኢዮቤልዩ መሠረታቸው በየሳምንቱ የሚመላለሰው ሰባተኛው ቀን ነው። በአንድ ዓመት የሚከበረው ኀምሳ ሁለት የዕረፍት ሰንበትም በሰባተኛው ዓመት ሦስት መቶ ስድሳ አራት የዕረፍት ሰንበት ይሆናል። በዚህ ሰባተኛ ዓመት የሰንበት ቀን ብዛት 364 ቀን ስለሆነ መላው ዓመት ይከበራል። ይህም ዓመተ እድገት ወይም ንሥ ሰንበት ይባላል። (ዘሌ.25፣1-7)። ሰባተኛው ዓመት በሙሉ የሚከበርበት ምክንያትም ሰባተኛው ቀን እስከ ሰባተኛው ዓመት 364 የዕረፍት ቀን ሆኖ አንድ ሙሉ ዓመት በመሆኑ ስለርሱ ክብር ተብሎ ነው።

በዚህ ዓመት መሬቱ አይታረስም፣ አይዘራም፣ ባለዕዳም ዕዳውን እንዲከፍል አይገደድም፣ የወይን ዘለላም አይቈረጥም። የአሥራኤል ወገን ሁሉ በነጻነት ወደ ርስቱ ይመለሳል። ከእግዚአብሔር ዘንድ የምሕረት አዋጅ የታወጀበት ዓመት ነውና (ዘዳ.15፣1-2)

የአሥራኤል ልጆች ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡበት ዓመት ጀምሮ ስድስት ዓመት ቈጥረው ሰባተኛው ዓመት ለምድሪቱ የዕረፍትዋ ጊዜ ነውና መላውን ዓመት ያከብሩታል። ይህም የዕረፍት ሰንበት በሰባተኛው

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ (2000) ዓ.ም

በሰባተኛው ዓመት እርሻ የማይታረስ፣ አህል የማይዘራ፣ ወይንም የማይቈረጥ ከሆነ ምን እንበላለን፣ ምንስ እንጠጣለን ብለው እንዳይጨነቁም በስድስተኛው ዓመት በረከቱን በላያችሁ አዝዛለሁ። ምድሪቱም የሦስት ዓመት ፍሬን ታፈራለች። በስምንተኛውም ዓመት ትዘራላችሁ። ፍሬው እስኪገባ እስከ ዘጠነኛው ዓመት ድረስም ከአሮጌው አህል ትበላላችሁ ብሎ ተስፋ ሰጥቷቸዋል። አክብሩ ሰንበታትየ ወሐሩ በሕግየ ትብልው ከራሜ ከራሜ እምበረከትየ እምፍሬ ተግባርየ ይቤ እግዚአብሔር ፡- ማለት ሰንበቶቼን አክብሩ፣ በሕጌም ጸንታችሁ ኑሩ። እንዲህ ካደረጋችሁ ከቸርነቴ ባሕርይ ከሚገኝ በረከት የከረመና የኖረ፣ ያምናና የታች ዓምና የወዲያኛው የብዙ ዓመት አህልን ትበላላችሁ ብሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ነግሮታል። (ዘሌ .25፣18-22 ይኑ)

## የኢዮቤልዩ ዓመት፡-

ኢዮቤልዩ ማለት እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ከአርባ ዘጠኝ ዓመት በኋላ የሚያከብሩት ኀምሳኛ ዓመት ነው። ከሰባት ሰባተኛው ሱባዔ ዓመትም ሰባት የዕረፍት ሰንበት ዓመት ይገኛል። በኀምሳኛው ዓመት ኢዮቤልዩ ወይም ዐቢይ ሱባዔ ተብሎ የሚከበረውም የዕረፍቱ ሰንበት ሙሉ ሰባት ዓመት ስለሆነ ነው።

ወትጐልቍ ለከ ሰብዓተ ዕረፍተ ዘሰብዓቱ ዓመት ዘምስብዓት፣ ወእምዝ ትሬሲ ለከ ሰብዓተ ሰናብተ ዘዘ ፯ወ፯ ዓመት እንዲል (ዘሌ.25፣8፣ ትቤ አክሱም ገጽ 88) በሰባተኛው ዓመት አንድ ሙሉ ዓመት የሆነው ሰባተኛ ቀን በአርባ ዘጠኝ ዓመት ደግሞ ሰባት ሙሉ ዓመት ስለሆነ ስለሰንበታቱ ክብር በኀምሳኛው ዓመት ኢዮቤልዩ ወይም ዐቢይ ሱባዔ ተብሎ ይከበራል።

የኢዮቤልዩ ዓመትም ሥርዓቱ እንደ ሰባተኛው ዓመት የነጻነትና የምስጋና ዓመት ነው። እስራኤል ሃያማኖታቸውን የሚያጸኑበት፣ ምድሪቱም መላውን ዓመት የምታርፍበት የተቀደሰ ዓመት ነው። የበዓሉ አከባበር ሥርዓትም በሰባተኛው ወር በዐሥረኛው ቀን በበዓለ ስርየት በመለከት ድምፅ በአዋጅ ይጀመራል።

በእያንዳንዱ የኀምሳ ዓመት ዑደት ከሚመላለሰው ከአርባ ስምንተኛው ዓመት የሚገኝ ምርትም ከስድስተኛው ዓመት እንደሚገኘው ምርት ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ማለት እስከ ኀምሳ አንደኛው ዓመት በናጹም እምነት ጸንተው በዓሉን እያከበሩ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በቂ ምግብ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማክበር ቃል ኪዳኑን መጠበቅ በረከትን ያስገኛልና ነው። (ዘሌ.25፣8-12) የኢዮቤልዩ ዓመት የሚከበርበት የኀምሳኛው ዓመት መባቻም ዕለተ እሑድ ነው። ስለዚህ ዕለተ እሑድ በብሉይ ዘመን ትከበር እንደነበር በዚህ ይታወቃል።

## የኢዮቤልዩ አምሳል፡-

በሕግና በትእዛዝ በምትከበር ቀዳሚት ሰንበት ባሉ ዐሥራ ሁለት ሰዓተ ሌሊትና ዐሥራ ሁለት ሰዓተ መዓልት ላይ ጌታችን የተቀበረባት እንዲት የዓርብ ምሽት ሰዓት ስትደመር 25 ሰዓታት ይሆናሉ። ዳግመኛም ከሰንበት ምሽት ጀምሮ በምትቈጠር፣ ጌታችን በተነሣባት እሑድ ሰንበት ያሉ ዐሥራ ሁለት ሰዓተ ሌሊትና ዐሥራ ሁለት ሰዓተ መዓልት ሲደመሩ 24 ሰዓታት ይሆናሉ። የሁለቱ ሰናብት ሰዓታትና አንዲት የዓርብ ምሽት ሲደመሩ 49 ሰዓታት ይሆናሉ። እነዚህም የኢዮቤልዩ ሰንበታት አርአያና አምሳል ናቸው። ስለዚህ ሌዋውያን የኀምሳኛውን ዓመት መባቻ ዕለተ እሑድን ኢዮቤልዩ ብለው ያከብሩ እንደነበር የዘመነ ሐዲስ ካህናትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣባት ዕለተ እሑድ አርባ ዘጠኝን ሰዓ ኢዮቤልዩ ብለው ያከብራሉ። ክርስቲያኖችንም ሁሉ በዓሉን እንዲያከብሩ ያስተምራሉ።

ሃምሳኛም የወዘወዛችሁትን ነዶ ካመጣችሁበት ቀን በኋላ ከሰንበት ማግስት ፍጹም ሰባት ጊዜ ሰባት ቈጥ ። እስከ ሰባተኛው ሰንበት ማግስት ድረስም ኀምሳ ቀን ይሆናል። በዚሁ ቀንም አዲሱን የአህል ቈርባ ለእግዚአብሔር አቅርቡ ይላል (ዘሌ.23፣15-16) ከዚህም በሰንበት ማግስት አዲስ የአህል ቈርባን የቀረበበት ቀን እሑድ ነው። ይህ ቀን ሌዋውያን ቀዳምያቱንና በኩራቱን የሚቀበሉበት መሥዋዕትም የሚያቀርቡበት ስለሆነ በዓለ ሰዊት ብለው ያከብሩታል።

www.ethiopianorthodox.org

ዘመነ ሐዲስ ካህናትም ኦሪት ለወንጌል አምላል መርገፍ ናትና ጌታችን ከተነሣበት ዕለት ጀምረው እስከ ሰባተኛው ሰንበት ማግስት ኀምሳ ቈጥረው በበዓለ ሰዊት አምላል በዓለ ጰራቅሊጦስን ያከብራሉ፡፡ ሌዋውያን ቀዳምያቱንና በኩራቱን እንደተቀበሉ ሐዋርያትም በዚሁ ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው አዲሲቱን ወንጌላዊቱን ቤተ ክርስቲያን መሥርተዋል፡፡

# ክፍል 3

## ዘመነ አበው

ከአዳም እስከ ሙሴ ያለው ዘመን ዘመነ አበው ይባላል፡፡ የሐሳበ ዘመን መምህራን ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ ዘመነ አበውን፣ ሰባዔያትንና ሰንበታትን መርምረውና አጥንተው ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ ያለውን የዘመናት ቁጥር ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፡፡

| | |
|---|---|
| ከአዳም እስከ ርዱተ አይን ..... | 2256 ዓመት |
| ከርዱተ አይን እስከ ሙሴ ..... | 1588 ዓመት |
| ከሙሴ እስከ ሰሎሞን ..... | 593 ዓመት |
| ከሰሎሞን እስከ ክርስቶስ ..... | 1063 ዓመት |
| ድምር ..... | 5500 ዓመት ነው፡፡ |

አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዓመትን መሠረት በማድረግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተፀነሰበትን፣ የተወለደበትን፣ የተጠመቀበትን፣ የተሰቀለበትንና ከሙታን ተለይቶ የተነሣበትን ጥንተ ዕለት ቀጥለን እንጽፋለን፡፡

### ጥንተ ትስብእት፡-

ጥንተ ትስብእት ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተፀነሰበት ቀን ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ5500 ዓመት እሑድ መጋቢት 29 ቀን ጌታችን የተፀነሰበት ዕለት መሆኑን በቀመር እየቈጠረችና እየቀመረች ታስተምራለች፡፡

### ጥንተ ልደት፡-

ጥንተ ልደት ማለት ጌታችን የተወለደበት ቀን ማለት ነው፡፡ ዓለም በተፈጠረ በ5501 ዓመት በ1 ዓመተ ሥጋዊ ወይም ዓመተ ምሕረት በዘመነ ማቴዎስ ማክሰኞ ታህሣሥ 29 ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈቀ ሌሊት ተወለደ፡፡ ያንጊዜ ወንጌላዊው ማቴዎስ የመስከረም መባቻ ረቡዕ፣ ጥንተዮን አንድ ነበር፡፡

### ጥንተ ጥምቀት፡-

ጥንተ ጥምቀት ማለት ጌታችን የተጠመቀበት ዕለት ማለት ነው፡፡ ዓለም በተፈጠረ በ5531 ዓመተ ዓለም በ31 ዓመተ ሥጋዊ ወይም ዓመተ ምሕረት በዘመነ ሉቃስ ማክሰኞ ጥር 11 ቀን ጌታችን በመንፈቀ ሌሊት ተጠመቀ፡፡ ያን ጊዜ ጥንተዮን 3 ነበር፡፡

### ጥንተ ስቅለት፡-

ጥንተ ስቅለት ማለት ጌታችን የተሰቀለበት ቀን ማለት ነው፡፡ ዓለም በተፈጠረ በ5534 ዓመተ ዓለም በ34 ዓመተ ሥጋዊ ወይም ዓመተ ምሕረት በዘመነ ማርቆስ በ7 ጥንተዮን ዓርብ መጋቢት 27 ቀን ጌታችን ተሰቀለ፡፡ በተሰቀለ በ3ኛው ቀን እሑድ መጋቢት 29 ቀን በመንፈቀ ሌሊት ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፡፡ በተነሣ በ40 ቀን ግንቦት በባተ በ8ኛው ቀን ኀምስ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ በዐረገ በ10ኛው ቀን በተነሣ በ50ኛው ቀን ግንቦት በባተ በ18ኛው ቀን እሑድ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው፡፡ ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ጌታችን የማስተማር ሥራውን ከመጀመሩ በፊት እንደጾመ እነርሱም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በአንድነት ጾመው የማስተማር ሥራቸውን ጀምረዋል፡፡ የጾሙትንም ጾም ክርስቲያኖች ሁሉ ይጾሙት ዘንድ አዘዋል፡፡ ወበእንተዝ ንኤዝዘክሙ ትግበሩ በከመ ዝበርነ ንሕነ አምድኅረ ዐርገ እግዚእነ ውስተ ሰማይ እንዲል (ዲድስ.ክን.29)

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን ሐዋርያት የሠሩትን ጾም ምእመናን ሁሉ በየዓመቱ ይጾሙት ዘንድ ታስተምራለች፡፡ የዓመት በዓላቸውንም ሐምሌ 5 ቀን ታከብራለች፡፡





# ክፍል 4

## ምሥጢረ ሐሳባት ሠለስቱ፡-

በኢትዮጵያ የሐሳበ ዘመን ሊቃውንት የታወቁ ሦስት የሐሳበ ዘመን ዐበይት ክፍላት አሉ፡፡ እነርሱም ሐሳበ ድሜጥሮስ፣ ሐሳበ ቢዘንና ሐሳበ ጉንዳጉንዲ ይባላሉ፡፡ ሊቃውንቱ በእነዚህ ዐበይት ክፍላት ዘመናትን የሚቈጥሩበትና የሚቀምሩበት ልዩ ልዩ የቀመር ስልት አላቸው፡፡ ያውም እንዲህ ነው፡-

### ሐሳበ ድሜጥሮስ

ሐሳበ ድሜጥሮስ እሑድንና ሰኞን ወደኋላ ትቶ ማክሰኞን ጥንተ ቀመርና ርእሰ አንቀጽ ወንጌላዊን ማቴዎስ አድርጎ ቀመሩ ከተጀመረበት ቀን አንሥቶ እስከዛሬ ያለውን ዘመን ይቈጥራል፡፡ ሐሳበ ድሜጥሮስ ማክሰኞን ጥንተ ቀመር ያደረገበት ምክንያት ያንጊዜ የሚያዝያ መባቻ ማክሰኞ ዘመኑ ዘመነ አልዐ ስለነበር ነው፡፡ ትምህርቱ የተገኘው ከአስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ይታወቃል፡፡

### ሐሳበ ቢዘን፡-

ሐሳበ ቢዘን ዐሥራ ሁለቱን ንኡስ ቀመር ወደኋላ ትቶ እሑድን ርእሰ አንቀጽና ጥንተ ቀመር ወንጌላዊን ማቴዎስ አድርጎ ቀመሩን ከጀመረበት ቀን አንሥቶ እስከዛሬ ድረስ ያለውን ዘመን ይቈጥራል፡፡ ሐሳበ ቢዘን እሑድን ጥንተ ቀመር ያደረገበት ምክንያት ዓለም የተፈጠረበትና የሰባቱ ዕለታትም ጥንትና መነሻ፣ መጀመሪያም ስለሆነ ነው ብለው የቢዘን ሊቃውንት ያትታሉ፡፡ ትምህርቱም በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍለ ሀገር በሚገኝ ደብረ ቢዘን በተባለው ገዳም ይኖሩ ከነበሩ የሐሳበ ዘመን ሊቃውንት የመነጨ ነው፡፡

### ሐሳበ ጉንዳጉንዲ፡-

ሐሳበ ጉንዳጉንዲ ሃያ አራቱን ንኡስ ቀመር ወደኋላ ትቶ ዓርብን ርእሰ አንቀጽና ጥንተ ቀመር፣ ወንጌላዊን ማቴዎስ አድርጎ ቀመሩን ከጀመረበት ዕለት አንሥቶ እስከዛሬ ድረስ ያለውን ዘመን ይቈጥራል፡፡ ሐሳበ ጉንዳጉንዲ ጥንተ ቀመሩን ዓርብ ያደረገበት ምክንያት አዳም የተፈጠረበት ቀን ስለሆነና መጽሐፍ ቅዱስም የአበውን ዕድሜ ሲቈጥር ከአዳም ጀምሮ የሚቈጥር መሆኑን ስለተረዳ ነው፡፡ ትምህርቱም በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ምሥራቅ ክፍለ ሀገር በአጋሜ አውራጃ በሚገኝ ጉንዳጉንዲ ከተባለ ገዳም ይኖሩ ከነበሩ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የመነጨ ነው፡፡

### ዓመተ ዓለም፡-

ዓመተ ዓለም ከሐሳበ ድሜጥሮስ ጥንተ ቀመር ከማክሰኞ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ያለው ዘመን ሲቈጠር 7500 ዓመት ይሆናል፡፡ ከሐሳበ ቢዘን ጥንተ ቀመር ከእሑድ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ (7500-228)=7272 ዓመት ይሆናል፡፡ ከሐሳበ ጉንዳጉንዲ ጥንተ ቀመር ከዓርብ ጀምሮ ሲቈጠርም (7500-456)=7044 ዓመት ይሆናል፡፡ የእነዚህ ሦስት ዐበይት ሐሳባት ዓመተ ዓለም የእያንዳንዳቸው የዓመት ቁጥር የመብዛትና የማነስ ውጤት ቢያሳይም እንኳ ከእያንዳንዳቸው የሚተርፈው ዓመተ አበቅቴና ወንበር፣ የሚገኘው አበቅቴና መጥቅዕ ተመሳሳይ ስለሆነ ውጤታቸው አንድ ነው፡፡ የቀመርን ሥርዓት አያፈርስም፡፡

### ግጠ ተሰይ፡-

የዘመኑን አበቅቴና መጥቅዕ ለማወቅ 7500 ዓመተ ዓለም በ532 ዐቢይ ቀመር፣ በ19 ንኡስ ቀመር ሲቀመር 14 ዐቢይ ቀመር፣ 2 ንኡስ ቀመር ሆኖ 14 ዓመተ አበቅቴ ይተርፋል፡፡ ከ14 ዓመት 1 ሲቀነስ 13 ይተርፋል፡፡ ይህ ወንበር ይባላል፡፡ 13 ወንበር በ11 ጥንተ አበቅቴ ተባዝቶ ሰ30 ሲካፈል 4 ወር ሆኖ 23 ቀን ይተርፋል፡፡ ይህ አበቅቴ ይባላል፡፡ ዳግመኛም 13 ወንበር በ19 ጥንተ መጥቅዕ ተባዝቶ ሰ30 ሲካፈል 8 ወር ሆኖ 7 ቀን ይተርፋል፡፡ ይህ መጥቅዕ ይባላል፡፡ ስለዚህ የ2 ሺሕ ዓመተ ሥጋዊ ወይም ዓመተ ምሕረት ወንጌላዊ ዮሐንስ፣ አበቅቴ 23፣ መጥቅዕ 7 ይሆናል፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም "ለእመ ፈቀድከ ታእምር አበቅቱ ወርኅ እም ዓመተ ሥጋዊ ትዊስክ ዘልፈ 9 ዓመተ ዘይተርፍ እም ዓመተ ዓለም ላዕለ ዓመተ ሥጋዊ ማለት አበቅቱ ወርኅን ከዓመተ ሥጋዊ ለማውጣት ብትፈልግ ከዓመተ ዓለም የሚተርፈውን 9 ዓመት በዓመተ ሥጋዊ ላይ ሁልጊዜ ትጨምራለህ" ተብሎ በመጽሐፈ አቡሻህር በአንተጽ 26 እንደተጻፈው በ2000 ዓመተ ሥጋዊ ላይ 9 ዓመት ሲደመር 2009 ዓመት ይሆናል፡፡ ከዚህም ስለተጀመረ ተቈጠረ ስላልተፈጸመ ታተተ ተብሎ አንድ ዓመት ሲቀነስ 2008 ዓመት ይሆናል፡፡ ይህ በዐቢይና ንኡስ ቀመር ቢቀመር ከላይ እንደተጻፈው ተመሳሳይ የሆነ ወንበር አበቅቱና መጥቅዕ ይገኛል፡፡ በዚያም ሆነ በዚህ ዘመኑ ሲቀመር ውጤቱ አንድ ነው ልዩነት የለውም፡፡

## አጽዋማትና በዓላት፡-

በ2 ሺሕ ዓመተ ሥጋዊ ወይም ዓመተ ምሕረት መስከረም ረቡዕ፣ ጥምቀት ዓርብ ይብታል፡፡ ጥቅምት በባተ በ7ኛው ቀን ኀሙስ በዓለ መጥቅዕ ይውላል፡፡ የኀሙስ ተውሳክ 3፣ በ7 መጥቅዕ ላይ ሲደመር 10 ይሆናል፡፡ ይህ መባጃ ሐመር ይባላል፡፡ ስለዚህ የካቲት ቅዳሜ በባተ በ10ኛው ቀን፣ ሰኞ ጾመ ነነዌ ይገባል፡፡

ዐቢይ ጾም ሰኞ የካቲት 24 ቀን ይገባል፡፡
ደብረ ዘይት እሑድ መጋቢት 21 ቀን ይውላል፡፡
ሆሣዕና እሑድ ሚያዝያ 12 ቀን ይውላል፡፡
ስቅለት ዓርብ ሚያዝያ 17 ቀን ይውላል፡፡
ትንሣኤ እሑድ ሚያዝያ 19 ቀን ይውላል፡፡
ርክበ ካህናት ረቡዕ ግንቦት 13 ቀን ይውላል፡፡
ዕርገት ሐሙስ ግንቦት 28 ቀን ይውላል፡፡
ጰራቅሊጦስ እሑድ ሰኔ 8 ቀን ይውላል፡፡
ጾመ ሐዋርያት ሰኞ ሰኔ 9 ቀን ይገባል፡፡
ጾመ ድኅነት ረቡዕ ሰኔ 11 ቀን ይገባል፡፡

ብለው የሐሳበ ዘመን መምህራን የዓመቱ አጽዋማትና በዓላት የሚገቡበትን የሚውሉበትን ቀን ካስረዱ በኋላ የአሥርቆትን ሥርዓት ያስማሉ፡፡ ያውም እንዲህ ነው፡፡

ሃሌ ሉያ ከጌታችንና ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕማና ትእዛዝ የተገኘውን የዘመናትና የዓመታት ቁጥር፣ የሌሊትና የመዓልት ወሮች መባቻ አቈጣጠር ሥርዓት በምንዘክርበትና በምናስብበት በዛሬው ቀን፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን፡፡ አሁን ካለንበት ከወንጌላዊው ዮሐንስ ዘመን እንዳደረሰን፣ ወደ ዜናዊው ማቴዎስ ዘመን በሰላም እንዲያደርሰን እግዚአብሔርን እንለምናለን፡፡

ዘንድሮ ዓመተ ዓለም በፀሐይ 7 ሺሕ 500 ዓመት፣ በጨረቃ 7 ሺሕ 727 ዓመት 7 ወር ከ27 ቀን ነው፡፡ ከዚሁም 5 ሺሕ 500ው ዓመት፣ ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኩነኔ ዘመነ ብሉይ ይባላል፡፡ 2ቱ ሺሕ ደግሞ ዓመተ ምሕረት ዓመተ ሥጋዊ ዘመነ ሐዲስ ይባላል፡፡ መላው ዓመተ ዓለም መዋዕለ ዓለም ይባላል ብለው ዛሬ በዚች ዕለተ ረቡዕ ከመስከረም ወር መባቻ እንዳደረሰን እንዲሁም ወደ ጥቅምት ወር መባቻ በሰላም እንዲያደርሰን ፈጣሪያችንን እንለምነዋለን፡፡

ዛሬ በዚሁ ቀን ሠርቀ ሌሊት 25፣ ሠርቀ ወርኅ 29፣ ሠርቀ መዓልት 1፣ አበቅቴ ፀሐይ 1፣ አበቅቴ ወርኅ 23 ነው፡፡ ፀሐይም በዚሁ ቀን በሕልመልሜሌክ የምኅብና ወራት፣ በክረምት ከታላላቆቹ መዓርጋት በ1ኛው መዓርግ በሚዛን ማኅፈድ በአራተኛው ደጃፍ ሲያበራ ይውላል፣ ብለው አሥርቆቱን ከፈጸሙ በኋላ፣ የነበረው ወንጌላዊ አለፈ፡፡ የሚመጣው ወንጌላዊ ተተካ፣ በማለት የአሥርቆቱን ሥርዓት በጸሎት ይፈጽማሉ፡፡



# ምዕራፍ 5

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ፀዋትወ ዜማ

## ክፍል 1

### የዜማ አጀማመር

ዜማ ማለት ጣዕም፣ ለዛና ስልት ባለው ተከታታይ ቅንቀና የሚያስሙት ድምፅ ማለት ነው፤ ወይም በልዩ ልዩ ሥነ ድምፅ ተቀነባብሮ፣ ተደራጅቶና ተስማምቶ ልዩ ስሜትና ተመስጦ ሊሰጥ በሚችል መልኩ የሚያስሙት ቅንቀና ነው፡፡ ዜማ የተጀመረው በጥንተ ፍጥረት በመላእክት አንደበት ነው፤ መላእክት እንደተፈጠሩ ወዲያውኑ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን በጣዕመ ዜማ አመስግነዋል ኢዮ.38፣6፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ እግዚአብሔር ሰውንና መላእክትን መፍጠሩ ስሙን አመስግነው ክብሩን እንዲወርሱ ነውና በጣዕመ ዜማ ማመስገንን በባህርያቸው ውስጥ እንደ አንድ መሠረታዊ ፍላጎት አድርጎ ፈጥሮላቸዋል፤ ከዚህም የተነሣ ዜማን የመውደድ ዝንባሌ ተፈጥሮአዊ ሆኖ ይገኛል፤ ዜማን የመውደድ ዝንባሌ በመላእክትና በሰዎች ይበልጥ ጐልቶ ይታይ እንጂ ሕይወት ባላቸው በሌሎች ፍጡራንም በብዛት የሚታይ ነው፤ ለምሳሌ "አዕዋፍ ዘሠናይ ዜማሆሙ" ተብሎ የተመሠከረለትን የአዕዋፍ ዜማ መጥቀስ ይቻላል፤ እንግዲህ ይህንን ሁሉ ስንመለከት የስጦታ ሁሉ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ፍጡራንን በባህርያቸው በዜማ የማመስገን ፍላጎትና ዝንባሌ እንዲኖራቸው አድርጎ በመፍጠሩ የዜማ መገኛውና ምንጩ እርሱ ራሱ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ በጣዕመ ዜማ ማመስገን በሰማያውያን ፍጡራን ዘንድ የማያቋርጥ መደበኛ ሥራ ነው፤ ራእ.4፣9፣ ኢሳ.6፣2-4፡፡

እንደዚሁም ዜማ በተፈጥሮ የተገኘ ተወዳጅ ስጦታ እንደመሆኑ መጠን ሁሌም የመንፈስ ምግብ ነውና ሰዎች ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ ሲጠቀሙበት ኖሮዋል፤ ዘፍ.4፣21፤ ከዚህም የተነሣ ጣዕሙ፣ ይዘቱና ስልቱ ይለያይ እንደሆነ ነው እንጂ ሰዎች ከተፈጠሩበት ጊዜ አንሥቶ ከጣዕመ ዜማ የተለዩበት ጊዜ የለም፤ በመሆኑም በየትኛውም ክፍለ ዓለም የሚገኝ ሕዝብ የራሱ የሆነ ዜማ አለው፡፡

በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ ዜማ በአምስት ዓይነት ተከፍሎ ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል፤ እነዚህም፡-

ሀ. እግዚአብሔር የሚመሰገንበት መንፈሳዊ ዜማ /ማኅሌት/
ለ. ሕዝብ በደስታ ጊዜ የሚጠቀምበት የደስታ ዜማ /ዘፈን/
ሐ. ሕዝብ በኃዘን ጊዜ የሚጠቀምበት የኃዘን ዜማ /ልቅሶ/
መ. ነዳያን በችግር ጊዜ የሚለምኑበት የልመና ዜማ /ልመና/
ሠ. በሠልፍ ጊዜ ለመቀስቀሻ የሚጠቀሙበት የፉከራ ዜማ /ቀረርቶ/ ናቸው፡፡

ዜማ ለእነዚህ ሁሉ የጋራ መጠርያቸው ነው፤ ሆኖም የዜማዎቹ ድምፀ ቃና፣ ሥነ ቃልና እንቅስቃሴ የአንዱ ከሌላው የተለያዩ ናቸው፡፡

እንግዲህ ስለ ዜማ አጀማመርና አመጣጥ በአጭሩ ይህን ያህል ካልን በኋላ የዚህ ጽሑፍ ዋና ርእስ ወደሆነው "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ፀዋትወ ዜማ" ወደሚለው ዝርዝር ገለጻ እንገባለን፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ፀዋትወ ዜማ

## 1. ቅድመ ክርስትና የነበረ ዜማ

የኢትዮጵያ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የተለዩበት ጊዜ የለም፤ በመሆኑም ዜማ ተፈጥሮአዊ ስጦታ እንደመሆኑ መጠን በተፈጥሮ ያገኙትና የራሳቸው የሆነ የእግዚአብሔር ማመስገኛ ጣዕመ ዜማ አልነበራቸውም ማለት አይቻልም፡፡

ኦሪት ገና ወደኢትየጵያ ከመግባቱ በፊት ስብሐተ እግዚአብሔር፣ አምልኮተ እግዚአብሔርና ፈሪሃ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እንደነበረ ይታወቃል፤ አምልኮት ካለ ምስጋና አለ፤ ምስጋናም ካለ ዜማም አብሮ አለ፤ ከዚህ ሁኔታ ስንመለከት ከሕገ ኦሪት መምጣት በፊት በኢትዮጵያ በዜማ ማመስገን ነበረ ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህም በኋላ በኢትዮጵያ ዘመነ አበው አልፎ ዘመነ ኦሪት ሲተካና በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ታቦተ ጽዮንና ሌዋውያን ሲመጡ የመዝሙራት መጻሕፍት አብረው ስለመጡ የዜማው መልክ በመሣርያ፣ በዓይነትና በአጠቃቀም ተጨማሪ መልክ መያዙ አልቀረም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ /መዝ.150፣1-5፣ ዜና መዋ.ቀዳ.15፣16፤ 16፣4-37/ እንደሚያስረዳው በዳዊትና በሰሎሞን ጊዜ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በክበሮ፣ በጸናጽል፣ በመሰንቆ፣ በበገና፣ በዕንዚራ፣ በቀንደ መለከት፣ በዕልልታና በሆታ እግዚአብሔር በዜማ ይመሰገን እንደነበረ ነው፡፡

ይህ ዓይነቱ ምስጋናና የምስጋና መሣርያ በዋነኛነት ይጠቀሙ የነበሩ የታቦተ ጽዮን አገልጋዮች የነበሩ ሌዋውያን ካህናት መሆናቸውንም መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል /ዕዝ.3፡10/፡፡

በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ስትመጣ ሌዋውያንም አብረው ስለመጡ ዜማቸው፤ ማኅሌታቸውና የማኅሌት መሣርያቸው ሁሉ በዚያን ጊዜ አብሮ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶአል፤ አገሪቱም ይህንን የዜማ ስልት ከነመሣርያው እስከ ዘመነ ክርስትና ስትገለገልበት ቆይታለች፤ የዚህ ዓይነቱ ጣዕመ ዜማ አገልጋዮችም ታቦተ ጽዮን በምትኖርበት ድንኳን ውስጥ ከዓመት እስከ ዓመት ያለማቋረጥ የሚያገለግሉ ስለነበሩ "ካህናተ ደብተራ" ይባላሉ፤ ትርጓሜውም ታቦተ ጽዮን በምትኖርበት ድንኳን ውስጥ የሚያገለግሉ ካህናት ማለት ነው፤ ይህ ስም ከጥንት ጀምሮ የቁየ የመዓርግ ወይም የሙያ ስም ነው፤ ስያሜው እስከ ቅርብ ጊዜ ትልቅ የመዓርግ ስም ሆኖ ለቤተ ክርስቲያን ሊታውንት ይሰጥ ስለነበረ ሊታውንቱ ደብተራ አገሌ እየተባሉ ይጠሩበት ነበር፡፡

እነዚህ በዘመነ ኦሪት የመጡ የዜማ መሣርያዎች፣ አለባበሶችና የመዝሙር አጠቃቀም ስልቶች ዛሬም ድረስ ቤተ ክርስቲያን ስትገለገልባቸው ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ ከዜማ መሣርያዎች መካከል፡- ክበሮ፣ ጸናጽል፣ መለከት፣ መሰንቆ፣ በገና ወዘተ ይገኙበታል መዝ.150፣1-5፤

ከአለባበስም ረጅም ቀሚስ፣ ጥምጥም፣ መጐናጸፊያ /ጋቢ/ እና ካባ ወዘተ ይገኙባቸዋል ዘሌ.8፣7-9 ፡፡ ከመዝሙር ስልት ደግሞ የቅዱስ ያሬድ የምዕራፍ ዜማ ምዕዛል ስልት ይገኝበታል ዕዝ.3፣11፡፡

## 2. ዜማ በክርስትና ምሥረታ ጊዜ፡-

ኢትዮጵያ በዐራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመርያ አካባቢ የክርስትና ሃይማኖትን በብሔራዊ ደረጃ ስትቀበል ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸምያ የሚሆን ክርስቲያናዊ ዜማ ነበራት፤ ይህ ዜማ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንደሚታየው ለአገልግሎት ማስፈጸሚያ ያህል በመጠኑ ያገለግል የነበረ ዜማ እንጂ እንደ አሁኑ ጥልቀት፣ ምጥቀትና ርቀት ያለው፣ የተደራጀና የተቀነባበረ ዜማ አልነበረም፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

ከ330 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አምስት መቶ ዐርባ ዓ.ም. በዚሁ ዜማ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሲሰጡ፣ እግዚአብሔርም ሲመሰገን ኖሮአል፤ ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ግን እግዚአብሔር ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ሰዎች በፊቱ ይሰግዳሉ /መዝ.71፣9/ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች /መዝ.67፣31/ ሲል በዳዊት አንደበት የመለከረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖትና አምልኮተ እግዚአብሔር በልዩ ጣዕመ ዜማ እንዲታጀብ በመፈለጉ ከአኵስም ጽዮን ካህናተ ደብተራ መካከል አንዱን ካህን ለታላቅ ሰማያዊ ጣዕመ ዜማ መገለጥ መረጠ "ቅዱስ ያሬድ"

# ክፍል 2

## 1. የቅዱስ ያሬድ ታሪክና አነሣሥ

የቅዱስ ያሬድ ሐረገ ትውልድ ከካህናተ አኵስም ወገን ነው፤ አባቱ አብዩድ ወይም ይስሐቅ ይባላል፤ /አንዳንድ መጻሕፍት አዳም ይባላል ይላሉ/ እናቱም ክርስቲና ወይም ታውክልያ ትባላለች፤ ቅዱስ ያሬድ በአምስት መቶ አምስት ዓመተ ምሕረት በአኵስም ከተማ ተወለደ፤ እግዚአብሔር ሥራውን ሊሠራበት የመረጠው ቅዱስ ሰው ነውና ለወደፊት በእርሱ አማካይነት የሚሠራውን ሥራ ለመግለጽ ስለፈለገ በወላጆቹ አድሮ ከአዳም ስድስተኛ ትውልድ በሆነው በስድስተኛው ሰው በመላልኤል ልጅ በያሬድ ስም " ያሬድ" ተብሎ እንዲጠራ አደረገ ዘፍ፡5.15፡፡

ያሬድ ማለት ርደት፣ ወሪድ ማለትም መውረድ ማለት ነው፤ በቀዳማዊው ያሬድ ጊዜ ደቂቀ ሴት ከደብር ቅዱስ ወደ ደቂቀ ቃየል ወደ ምድረ ፍዳ ስለወረዱ ያንን ለማስታወስ አባቱ መላልኤል ያሬድ ብሎታል፤ "ወጸውዐ ስሞ ያሬድሃ እስመ በመዋዕሊሁ ወረዱ መላእክተ እግዚአብሔር ውስተ ምድር እለ ተሰምዩ ትጉሃነ" መጽ.ሕፃሌ 5፡21-22፤ ትርጓሜውም ስሙን ያሬድ ብሎ ጠራው በእርሱ ዘመን ትጉሃን ተብለው የሚጠሩ የእግዚአብሔር መላእክት /ደቂቀ ሴት/ ከደብር ቅዱስ ወደ ምድረ ፍዳ ወርደዋልና ማለት ነው፡፡

በኢትዮጵያም ዳግማዊ ያሬድ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተነሥቶ ለማያዊውን ልዩ ጣዕመ ዜማ ወደ ኢትዮጵያ የሚያወርድ ነውና ይህንን ለመግለጽ እግዚአብሔር በአባቱና በእናቱ አድሮ ያሬድ እንዲባል አድርጎአል፤ ምሥጢሩ ልዩ ጣዕመ ዜማን ከሰማይ የሚያወርድ መሆኑን ያሳያል፡፡

ቅዱስ ያሬድ አባቱ አብዩድ በሕጻንነቱ ስለሞተበት እናቱ ታውክልያ በሃይማኖት ኵትኵታ በፈሪሀ እግዚአብሔር አሳደገችው፤ ሕጻኑ ያሬድ በሰባት ዓመቱ ትምህርት እንዲማር የአኵስም ቤተ ጉባኤ /ቤተ ቀጢን/ መምህር ወደ ነበረው ወደ ጌዴዎን ወሰደችውና ትምህርት መማሩን ቀጠለ፤ ጌዴዎን የታውክልያ ወንድም ስለነበረ የሕጻኑ ያሬድ አጎት ነበረና በቅርብ እየተከታተለ ያስተምረው ነበረ፤ ሆኖም ትምህርት አልገፋ ብሎት ብዙ ዓመታት ተጕላላ፤ በዚህም ምክንያት ከዕለታት በአንድ ቀን አጎቱ ወይም መምህሩ ጌዴዎን ተናዶ ክፉኛ ገረፈው፤ ሕጻኑ ያሬድም በዚህ ተበሳጭቶና ተስፋ ቈርጦ ከአኵስም ከተማ ወጥቶ ወደ እናቱ መንደር ወደ መደባይ ወለል /ከአኵስም ወደ ሰሜን አቅጣጫ/ ሲጓዝ ማይ ክሬዋሕ "ማይ ኪራሕ" ከምትባል የውሀ ምንጭ ዳር ተቀምጦ ሲያዝንና ሲያለቅስ እግዚአብሔር አንድ የሚያጽናና ምልክት አሳየው፡፡

ይኸውም ክሬዋሕ /በትግርኛ ክራውሕ/ ከሚባል ዛፍ ሥር በውሀው ምንጭ ዳር ተቀምጦ ወደ ዛፍዋ ሲመለከት አንድ ትል የዛፍዋን ፍሬ ለመመገብ ሽቶ ወደላይ እየወጣና እየወደቀ ተደጋጋሚ ሙከራ ሲያደርግ ከቁየ በኋላ በሰባተኛው ጊዜ ወጥቶ ፍሬዋን ሲመገብ ተመለከተ፤ ተመራማሪው ተማሪ ያሬድ ከዚህ ትል ጥረትና ስኬት ትምህርት ወስዶ እኔምኮ ተስፋ ሳልቈርጥ ብዙ ጥረት ካደረግሁ እንደዚህ ሊሳካልኝ ይችላል ብሎ በተስፋ ተጽናንቶ እንደገና ወደ መምህሩ በመመለስ ትምህርቱን ለመቀጠል ወሰነ፤ ከዚህ በኋላ ወደመደባይ ወለል የነበረውን ጉዞ ሠርዞ መልስ ወደ አኵስም ከተማ ወደ መምህር ጌዴዎን ጉባኤ ቤት ሆነ፤ መምህሩ ጌዴዎንም ተቀብሎ ማስተማሩን ቀጠለ፤ በዚህ ጊዜ ሕጻኑ ያሬድ ለብዙ ጊዜ አልገፋ ያለውን ትምህርት በአጭር ጊዜ ውስጥ የግብረ ዲቁና ትምህርቱን አጠናቆ የታላቁ የአኵስም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ጥሩ አገልጋይ ዲያቆን ሆነ፤ ትምህርቱንም በስፋት ስለቀጠለበት የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ተርጓሚና ሊቅ ሆነ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር አንድ ትልቅ የሆነ ሥራን ለመሥራት በፈለገ ጊዜ ለሥራው መገለጫ በሆኑ ሰዎች ላይ መጠነኛ ፈተና ማሳየት ልማዱ ነው፤ ለማራ፣ ለኤልሳቤጥና ለቅድስት ሐና እንዲሁም ዕውር ሆኖ ለተወለደው ሰው ያደረገውን ሁኔታ ይህንን ያረጋግጣል፤ ይኸውም ለማራ ይስሐቅን ያህል ልጅ፣ ለኤልሳቤጥ ዮሐንስን ያህል ልጅ፣ ለሐናም ድንግል ማርያምን ታህል ልጅ ለመስጠት በፈለገ ጊዜ በመጀመርያ በመካንነት ብዙ ጊዜ እንዲቆዩ አድርጓል፤ የኋላ ኋላ ግን ሙቀት፣ ልምላሜና አበባ ቢለያቸውም በከሃሊነቱ ልጆችን ወልደው እንዲታቀፉ አድርጎአቸዋል ዘፍጥ.18፣10-14፤ ሳሙ/ቀዳ.1፣2-8፤ ሉቃስ 1፣9፡፡

ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰውም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ካደረገ በኋላ በከሃሊነቱ የዓይን ብርሃንን ሰጥቶታል፤ ይህም ለምን ዕውር ሆኖ እንደተወለደ በደቀ መዛሙርቱ ለቀረበለት ጥያቄ ጌታችን ሲመልስ የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው ሲል ገልጾአል፤ ዮሐ.9፣1-4፡፡

እንደዚህም ሁሉ የቅዱስ ያሬድ ትምህርት አልገባ ብሎት ለብዙ ጊዜ መጉላላት ነሽም፤ ገላጭም፤ ሰጭም እርሱ መሆኑን ለመግለጽ የተጠቀመበት ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል፤ ይህ ብቻም አይደለም ቅዱስ ያሬድ ከመጀመርያ ጀምሮ በጣም ዐዋቂና ትምህርት ተቀባይ ተማሪ ቢሆን ኖሮ ሰዎች የተገለጸለት ዜማንም ካለው የቋየ ዕውቀት እንደተገኘ አድርገው ይገምቱ ነበር፤ ነገር ግን የፈደል ቁጠራን ብዙ ዓመታት የወሰደበት ቅዱስ ያሬድ እንደገና እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከፍተኛ ሊቅና የዜማ ደራሲ ሆኖ መገኘት የእግዚአብሔር ከሃሊነትና ሰጭነት በተጨባጭ የሚያስረዳና የቅዱስ ያሬድ ዜማም በሥጋዊ እውቀት የተገኘ ሳይሆን በእግዚአብሔር ገላጭነት የተገኘ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

## 2. ቅዱስ ያሬድ መምህረ ብሉይ ወሐዲስ

ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔር አእምሮ መጻሕፍትን ከገለጸለት ጊዜ ጀምሮ በዲቁና መዓርግ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለ ትምህርቱን ስለቀጠለ የብሉይና የሐዲስ መምህር ሆኖ በመምህሩ በጌዴዎን ወንበር ተተካ፤ በዚህም መሠረት በትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ብዙ ሊታውንትን አፍርቶአል፤ ቅዱስ ያሬድ በምሥጢረ መጻሕፍት ትርጓሜ ብቻ ሳይሆን በሥነ ጽሑፍም የላቀ ዕውቀት የነበረው ታላቅ ሊቅ ነውና ከቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን በፊት የነበረው ጥንታዊ የግእዝ ፊደል አጠቃቀምና አጻጻፍ ከአባ ሰላማ ከሣቱ ብርሃን በኋላ ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉት የፊደል አናባቢዎች ተጨምረውለት በመሻሻሉ፣ አጻጻፉም ከቀኝ ወደ ግራ የነበረው ቀርቶ ከግራ ወደቀኝ በመደረጉ፣ በአልፍ ይጀምር የነበረው ፊደል በሀውት እንዲጀመር በመወሰኑ፣ ሕዝቡ አጻጻፉንም ሆነ ቋንቋውን ለመለማመድ ተቸግሮ ነበር፤ ነገር ግን ቅዱስ ያሬድ አዲሱን የግእዝ ቋንቋ አጠቃቀም በጽሑፍና በትምህርት ስላስፋፋው፣ በመጨረሻም በዜማ ድርሰቱ ስላዳበረውና የዜማ ትምህርት ደግሞ በመጽሐፍ ብቻ የሚማሩት ሳይሆን በቃል ጭምር የሚያዝ ስለሆነ ካህናቱ አዲሱን የግእዝ ቋንቋ በፍጥነት እንዲያውቁት አድርጎአቸዋል፡፡

በቅዱስ ያሬድ ዘመን ከተለያዩ የሮምና የታናሽ እስያ አገሮች የተውጣጡ ተስዐቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አኩስም ከተማ ውስጥ ቤተ ቀጢን በተባለው ጉባኤ ቤት ሲኖሩ የቅዱስ ያሬድ ትምህርት ቤት ለግእዝ ቋንቋ ዕውቀታቸው ዋና ምንጭ ነበረ፤ ተስዐቱ ቅዱሳን ከዚህ ከተራቀቀውና በግእዝ ቋንቋ ችሎታ በጣም ከታወቀው የቅዱስ ያሬድ ትምህርት ቤት በቀሰሙት የግእዝ ቋንቋ ዕውቀት አንዳንድ ያልተመለሱ መጻሕፍትን ለመተርጉምና ሥርዓተ ገዳምን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ችለዋል፤ ከዚህም የተነሣ በቅዱስ ያሬድና በተስዐቱ ቅዱሳን መካከል በጣም የቀረበ ግንኙነት ነበረ፡፡

## 3. ለቅዱስ ያሬድ ሰማያዊ ዜማ ተገለጸለት

ቅዱስ ያሬድ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ እያስተማረ ብዙ ጊዜ ከቁየ በኋላ እግዚአብሔር ሰማያዊውን ዜማ ሊገልጽለት ስለፈለገ ጎዳር 5 ቀን ጠዋት ከገነተ ኤዶሞ እርሱ ወዳለበት ሦስት አዕዋፍን ላከለት፤ ወፎቹም በአንድ ዛፍ ላይ ተቀምጠው በሰው አንደበት ያነጋግሩት ጀመር፤ እንዲህ እያሉ "ያሬድ ሆይ? አንተ ብዕዕ ነህ፤ አንተን የተሸከመች ሆድም ብፅዕት ናት" እርሱም ወደ እነርሱ እየተመለከተ እናንተ በሰው አንደበት የምትናገሩ አዕዋፍ ከየት መጣችሁ? ማንስ ላካችሁ? ሲል ወፎቹን ጠየቃቸው፤ ከሦስቱ ወፎች አንዷ እኛ ከኤዶም ገነት ወደ አንተ ተልከን የመጣን ነን፤ ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ሰማያዊ ማኅሌትን ትማር ዘንድ ልንነግርህ መጣን አለችው፤ ከዚህ በኋላ አዕዋፉ ከዓይኑ ተሠወሩ፤ ያሬድም በተመስጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተነጠቀ፤ በዚያም ፈጣሪ ፍጥረታት እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ የሚያመሰግኑ መላእክት በመንበሩ ዙርያ ሆነው ተወዳጅና ልዩ ጣዕም ባለው የዜማ ድምፅ ሲያመሰግኑ፣ ሲዘምሩና ሲያሸበሽቡ አየ፤ ከጣዕመ ዜማው የተነሣ ወደ እነርሱ ዘሎ ለመግባት ወደደ፤ በዚህ ጊዜ እዝቢያ አዕዋፍ ወደ እርሱ መጡ፤ ከእነርሱም አንዷ ወፍ ያሬድ ሆይ የሰማኸውን ዜማ አስተውለሃልን? ብላ ጠየቀችው፤ እርሱም አላስተዋልኩም ብሎ መለሰላት፤ እርሷም እንግዲያውስ እኔ እነግርሃለሁና አዲሱን የእግዚብሔር ስም እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ስም ጥራ አለችው፤ ቅዱስ ያሬድም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ስም በጠራ ጊዜ የሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ዜማ ተገለጸለት፤ ወዲያውም ቅዱስ ያሬድ በግእዝ፣ በዕዝልና በዓራራይ ዜማውን ማዜም ጀመረ፤ ከዚህ በኋላ ቀድሞ ወደነበረበት ወደ ቤተ ቀጢን ተመለሰ፤ ከዚያም ሆኖ ፊቱን ታቦተ ጽዮን ወዳለችበት ወደምሥራቅ አዙሮ እጁንም ዘርግቶ እንዲህ ብሎ ሰማያዊውን ዜማ ለመጀመርያ ጊዜ በአኮስም ዐውደ ምሕረት አሰማ፤ እንዲህ ሲል "ሃሌ ሉያ ለአብ፣ ሃሌ ሉያ ለወልድ፣ ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአየ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ" ይህም ማለት ለአብ ምስጋና ይገባል፣ ለወልድም ምስጋና ይገባል፣ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል፣ የጽዮን መጀመርያዋ የሆነ እግዚአብሔር ሰማይን ፈጠረ ዳግመኛም የድንኳኑን ሥራ እንዴት አድርጎ መሥራት እንዳለበት ለሙሴ አሳየው ማለት ነው ዘጸ.25፣8-10፤ ዘጸ:26፣30 ይህ ሁሉ የተፈጸመው ጎዳር 6 ቀን ነበረ፤ ከሰማይ እንደተመለሰ ለመጀመርያ ጊዜ ጣዕመ ዜማውን ያሰማበት ቦታም "ሙራደ ቃል" ተባለ እስከዛሬም ድረስ ሙራደ ቃል እየተባለ ይጠራል፤ ይኸውም ዜማው ከሰማይ የወረደ መሆኑን የሚያረጋግጥ እውነተኛ ማስረጃ ነው፤ የዜማውም ስም አርያም ተባለ ይህም ከልዑል ሰማይ የተገኘ ዜማ መሆኑን ይገልጻል፤ ከዚህም በተጨማሪ ዜማውን ከሰማይ ከመላእክት ዘንድ የሰማው መሆኑን ራሱ ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ሲል ያረጋግጣል "ዋይ /ወይ/ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ቅዱሳን እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር መልዐ ሰማያተ ወምድረ ቅዱሳተ ስብሐቲከ" ትርጓሜውም "ወይ ዜማ" በሰማይ ሳለሁ ከቅዱሳን መላእክት የሰማሁት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ የክብርህ ምስጋና ሰማያትንና ምድርን መላ እያሉ ማለት ነው፤ ድጓ ዘአርባዕቱ እንስሳ /በ1988ዓ.ም. ከታተመው ገጽ 81 ሁለተኛው ዓምድ ላይ/ እንደዚሁም ዝማሬ በተባለው ድርሰቱ" ሰማየ በአብ ወበወልድ አርያመ ወበመንፈስ ቅዱስ ኀበ ዐረጉ ሰማዕኩ እመላእክት ዝማሬ በአድንኖ ወበአትሕቶ ቦ ዘያጽሕሱ ወቦ ዘይዜምሩ " ትርጓሜውም በአብ ወደ ሰማይ፣ በወልድ ወደ አርያም፣ በመንፈስ ቅዱስም በወጣሁ ጊዜ ከመላእክት ዘንድ ዝማሬን ሰማሁ የሚያሸበሽቡ አሉ የሚዘምሩም አሉ ማለት ነው፤ ዝማሬ ዘቅዱስ ያሬድ ግንቦት 11 ቀን ላይ /በተስፋ ገብረ ሥላሴ የታተመ ገጽ 114 /

ይህ የቅዱስ ያሬድ ወደ ሰማይ መነጠቅና ከዚያም የመላእክትን ዝማሬ ሰምቶ መመለስ ከቅዱስ ጳውሎስ አባባል ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ሁለተኛ መልእክቱ የተገለጠለትን ሰማያዊ ራእይ ሲገልጽ "እንዲህ ያለው ሰው ከዐሥራ ዐራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ..... ወደ ገነት ተነጠቀ ሰውም ሊናገረው የማይገባውንና የማይነገረውን ቃል ሰማ" 2ቆሮ.12፣1-5 በእግዚአብሔር ዘንድ ለትልቅ ነገር የተመረጡ ሰዎች ወደ ሰማይ እየተነጠቁ መወሰድና በዚያም ልዩ የሆነውን ራእይ ማየት የተለመደ መሆኑን የቅዱስ ጳውሎስ አባባል ያረጋግጣል፤ ቅዱስ ያሬድም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሰማይ መነጠቁ ከድሮም ጀምሮ የተለመደ የእግዚአብሔር አሠራር እንጂ አዲስ ነገር እንዳልሆነ በዚህ መረዳት ይቻላል፡፡

ቅዱስ ያሬድ ዜማ ማስማት የጀመረበት ቀን ጎዳር 6 ቀን ስለነበረ መሐሪው እግዚአብሔር በሕጻንነቱ ጊዜ የነበረኝን የትምህርት አለመቀበል ችግር አስወግዶ ለዚህን አበቃኝ ሲል "አስተምሕሮ" ብሎ ወቅቱን ሰየመው፤ አስተምሕሮ ማለት የምሕረት ወቅት ማለት ነው፤ በዚህ ቀን ቅዱስ ያሬድ በሙራደ ቃል ሆኖ የዜማ ድምፁን ከፍ አድርጎ ባሰማ ጊዜ ንጉሡ አጼ ገብረ መስቀል ከሠራዊታቸው፤ ንግሥቲቱ ከሎጋንጡሮቿ፤ መሳፍንቱ፤ መኳንንቱ፤ ሊቃውንቱና ካህናቱ፤ እንስሳቱና አዕዋፉ ሁሉ እሱ ወዳለበት ቦታ ተሰብስበው ከጣዕሙ የተነሣ መንፈስን የሚያድስ ልቡናን የሚያስደስትና አጥንትን የሚያለመልም አዲሱን ሰማያዊ ዜማ ረኃብ ጥማት ሳይሰማቸው በከፍተኛ ተመስጦና አድናቆት ሲሰሙ ዋሉ፤ ቅዱስ ያሬድም በግእዝ፣ በዕዝልና በአራራይ ዜማውን እያስማማ ፈጣሪው እግዚአብሔርን ማመስገኑ ቀጠለ፤ ሲያመሰግነውም የሃያ ሁለት ሥነ ፍጥረት ፈጣሪና መጋቢ መሆኑን ለመግለጽ በሃያ ሁለት አርእስተ ዜማ እያቀነባበረ ነበር፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስ ያሬድ ሐዋርያዊ አገልግሎት

## 1.ቅዱስ ያሬድና አቡነ አረጋዊ በደብረ ዳሞ ገዳም ላይ

የቅዱስ ያሬድ፣ የአቡነ አረጋዊና የአጼ ገብረ መስቀል ፍቅር ከልክ ያለፈና በጣም የጸና ነበረ፤ ጻድቁ አቡነ አረጋዊ ለሥርዓተ ምንኩስና አገልግሎት የሚሆንና ከከተማ ወጣ ያለ ምቹ ቦታ ሲፈልጉ ከአኩስም ከተማ ወደ ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ አካባቢ ለዚህ አገልግሎት የሚሆን ትልቅ ተራራ አገኙ "ደብረ ዳሞ "ይህ የደብረ ዳሞ ተራራ ዙርያው ሁሉ ገደል የሆነና ምንም መውጫ የሌለው ስለነበረ ወደላይ ለመውጣት አልቻሉም ነበረ፤ ኋላ ግን ሱባዔ ገብተው ፈጣሪያቸውን ስለተማጸኑ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት የታዘዘ ዘንዶ መጥቶ በጅራቱ ወገባቸውን አሥሮ ወደተራራው ላይ አወጣቸው፤ ከዚያም ሆነው የተራራውን ራስ ሲመለከቱ ለምናኔና ለሥርዓተ ምንኩስና በጣም የተስማማ ሆኖ ስላገኙት ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ገብረ መስቀልን በተራራው ላይ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩላቸው አስታወሱአቸው፤ አጼውም እስከዛሬ ድረስ ቆሞ የሚታየውን አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ለጻድቁ አስረከቡአቸው፤ ጻድቁ አቡነ አረጋዊም የእመቤታችንን ጽላት በማስገባት ቤተ ክርስቲያኑን ለማስመረቅ ስላሰቡ ቅዱስ ያሬድን ከአኩስም ጽዮን ጋብዘው የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን እንዲጐበኝላቸው አደረጉ፤ ቅዱስ ያሬድም በጻድቁ ጥሪ መሠረት በደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ተገኝቶ የቤተ ክርስቲያኑን ሥራ ማማር በእጅጉ ስላስደሰተው በማድነቅ እንዲህ ብሎ ዘመረ "ይሔውጽዋ መላእክት እንተ በሰማያት ይሔውጽዋ መላእክት እስመ ማኅ ደረ መለኮት ያድክዋ ያድክዋ ያድክዋ ወርኢኩ ሥነ ሕንጼሃ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምስአል ወምስጋድ ወምስተሥራየ ኃጢአት ይእቲ ቅድስት ደብተራ" ትርጓሜውም በሰማያት ያሉ መላእክት ይጐበኙታል፤ የመለኮት ማደርያ ናትና መላእክት ይጐበኙታል፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዞርኋት ዞርኋት ዞርኋት የሕንጻዋ ማማርም አየሁ፤ እሷ መጸለያ፣ መስገጃና የኃጢአት ማስተሥረያ ቅድስት ድንኳን ናት ማለት ነው፤ በእንደዚህ ያለ ደማቅ ሁኔታ አጼ ገብረ መስቀል፣ ቅዱስ ያሬድና አቡነ አረጋዊ የደብረ ዳሞን ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት አከበሩ፤ በዚህ ምክንያት መነሻነት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታቦቱ ዓመታዊ በዓል ንግሥ ሲከበር ሥርዓተ ዑደት ማድረስ የተለመደ ሆነ፡፡

ቅዱስ ያሬድ በዚሁ ገዳም ስምንት ቀን ያህል ከአቡነ አረጋዊ ጋር ቈይቶ ወደ አኩስም ተመለሰ፤ እንደተመለሰም ወደ አኩስም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ቅድስት ወብፅዕት ስብሐት ወዙርክት ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን ብሎ በመጀመር አንቀጸ ብርሃን የተባለውን ድርሰቱ ደረሰ፤ ይህንን ድርሰት በሚደርስበት ጊዜ እጁ በታቦተ ጽዮን ላይ ረቦ በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኘ ስለነበር ከመሬት አንድ ክንድ ያህል ከፍ ብሎ ይታይ ነበር፤ ይህ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት የሆነው አንቀጸ ብርሃን በቤተ ክርስቲያናችን ተወዳጅ ከሆነው የውዳሴ ማርያም ጸሎት ቀጥሎ ዘወትር የሚጸለይና በቃል የሚጠና ነው፤ በምሥጢሩ ጥልቀትና ምጥቀትም እጅግ የላቀ ነው፡፡

## 2. የጣና ሐይቅ ጉብኝት

አቡነ አረጋዊ፣ ቅዱስ ያሬድና አጼ ገብረ መስቀል በሥራው ሁሉ አይለያዩም ነበርና አገሩን ለማዳረስ ከአኩስም ተነሥተው በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመጓዝ ጣና ሐይቅ ደረሱ፤ በጣና ሐይቅ ውስጥ ዛሬ ጣና ቂርቆስ እየተባለ በሚጠራው ደሴት ላይ ብዙ ቀናትን አሳለፉ፤ ከዚያም ተነሥተው ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ሲጓዙ አንድ ተራራ አገኙ፤ ያም ተራራ አቡነ አረጋዊ ለሥርዓተ ገዳም ስለተመኙት ያላቸውን ምኞት ለንጉሠ ነገሥቱ ለአጼ ገብረ መስቀል ገለጹ፤ አጼውም እግዚአብሔር ከፈቀደ እዚህም እንደ ደብረ ዳሞ ያለ ቤተ ክርስቲያን ልሥራልዎ አሉአቸው፤ እርሳቸውም ወደ እግዚአብሔር ጸለዩና የታዘዘ መልአክ መጥቶ "ዙር አባ መንገለ ምሥራቅ" አላቸው ወደ ምሥራቅ ዙር ማለቱ ነው፡፡ እርሳቸውም መልአኩ እንዳመለከታቸው አጼ ገብረ መስቀልንና ቅዱስ ያሬድን አስከትለው ወደ ምሥራቅ በኩል ዞረው ሲመለከቱ በሐረግ ተንጠልጥለው መውጣት እንደሚችሉ ተረዱና በሐረጉ እየተንጠለጠሉ ወደ ተራራው ወጡ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተራራው ስም "ዙር አባ" ተብሎ ተሰየመ፤ አጼ ገብረ መስቀልም ለጻድቁ በገቡላቸው ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያኑን በሦስት ዓመት ሠርተው ጨረሱ፤ አቡነ አረጋዊም ሥርዓተ ገዳምን እያስተማሩ ቅዱስ ያሬድም ዝማሬ መዋሥዕትን እያስተማረ ሦስት ዓመት



ያህል ከቈዩ በኋላ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑን አክብረውና የእመቤታችንን ታቦት አስገብተው ወደ አኩስም ከተመለሱ፤ ቅዱስ ያሬድም ወደ አኩስም እንደተመለሰ ማይክሬዋሕ /ማይ ክራውሕ/ በተባለው ቦታ ውዳሴ ማርያምንና አሥራ አራት ቅዳሴያትን በዜማ አደረሰ፡፡

## የቅዱስ ያሬድ ምናኔ

ቅዱስ ያሬድና ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ገብረ መስቀል በሁሉም ነገር ሳይለያዩ በጽኑ ፍቅርና ስምምነት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ያደራጁ ነበር፤ ፍቅራቸው እንደ ዘሩባቤልና እንደ ዮሴዕ ያለ ጠንካራ ፍቅር ነበረ፤ በዚህም ሁኔታ ቅዱስ ያሬድ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ አጼ ገብረ መስቀል ሥርዓተ መንግሥትን የማደራጀት ሥራ ይሠሩ ነበርና በዚህ ጊዜ ሥርዓተ ዑደት ሠሪዕናን፣ ሥርዓተ ንግሥናንና ሥርዓተ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያንን አዘጋጁ፤ ከዚህም ጋር አጼ ገብረ መስቀል ለቅዱስ ያሬድ ዜማ የተለየ ፍቅር ነበራቸውና ከአደባባይ መልስ ሲሆን የዕረፍት ጊዜያቸውን በቤተ ቀጢን ከቅዱስ ያሬድ ጉባኤ ቤት እየተገኙ ጣዕመ ዜማውን ያዳምጡ ነበር፤ በዚህም መሠረት ከዕለታት በአንድ ቀን ቅዱስ ያሬድ በጣዕመ ዜማ ተመስጦ ዝማሜውን ሲያወርደው ንጉሡም እንደ እርሱ ተመስጠው ዓይን ዓይኑን እየተመለከቱ የብረት ስለት ያለውን የወርቅ ዘንግ ይዘው እንደ እርሱ እዘማለሁ ሲሉ ሳያዩ ዘንጉን በቅዱስ ያሬድ እግር ላይ ቸከሉት፤ ሁለቱም በተመስጦ ስለነበሩ የሆነውን ነገር ሁሉ አላዩም፤ ይሁን እንጂ የቅዱስ ያሬድ እግር ደም በደም ሆኖ እንደ ጉርፍ አካባቢውን ሲያጥለቀልቀው ይታይ ነበር፤ በዚህ ጊዜ በአካባቢው ያሉ ደቀመዛሙርት ይህንን አይተው ለንጉሡ ነገሯቸው፤ እርሳቸውም ደንግጠው ጦሩን አነሡትና በዚህ እጅግ አዝነው ደምህን ስላፈሰስሁ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ጠይቀኝ አሰጥሃለሁ ሲሉ ቃል ገቡለት፤ ቅዱስ ያሬድም የምለምንህ አንዲት ነገር ናት፤ እርሷን ፈጽምልኝ አለው፤ አጼ ገብረ መስቀልም የፈለግኸውን ለምን ፈቅጄልሃለሁ አሉት፤ እርሱም እስከአሁን እግዚአብሔር በፈቀደልኝና በገለጸልኝ መሠረት በዚህ ከተማ ከአንተ ጋር ቈይቼአለሁ፤ ብዙ ደቀመዛሙርትም ተክቼአለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የቀረኝን ዘመን በጸሎትና በብሕትውና ማሳለፍ እንድችል ከከተማው ራቅ ወዳለ ቦታ ሄጄ ፈጣሪየን ማገልገል እፈልጋለሁና ፈቃድህ ይሁንልኝ አለው፡፡

አጼ ገብረ መስቀልም ይህንን የቅዱስ ያሬድ ቃል ሰምተው አዘኑ፤ እንኳን ጣዕመ ዜማውን ሲሰሙ ቀርቶ መልኩን ባዩ ቍጥር በኃዜት ይሞሉ የነበሩት አጼ ገብረ መስቀል ከእንግዲህ ወዲህ ያሬድን ማየት ሊቀርባቸው ነው፤ ጣዕመ ዜማውን ከእርሱ መስማትም እንደዚሁ ሊቀር ነው፤ በመሆኑም በጣም ኃዘን ተሰማቸው፤ ሆኖም አንድ ጊዜ ቃል ስለገቡ ከመፍቀድ በቀር ሌላ አማራጭ አልነበራቸውምና ከፍተኛ ኃዘን እየተሰማቸው ፈቀዱለት፤ መላው ካህናተ አኩስም ጽዮንና ሕዝበ ክርስቲያኑ በአጠቃላይ በኃዘን ተዋጠ፤ ቅዱስ ያሬድም በተፈቀደለት መሠረት ጉዞውን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ወደ ስሜን ተራራዎች አደረገ፤ ካህናቱም እስከተከዜ ወንዝ ድረስ በልቅሶ ሸኙት፤ ተከዜ ወንዝ ላይ ካህናቱና ደቀመዛሙርቱ ሲለዩት በሚከተለው ዜማ መልካሙን ሁሉ ተመኝላቸው፤ "ሰላመ ነሣእነ ወሰላመ ኃደግነ ለክሙ እግዚአብሔር ምስለ ኩልክሙ፤ ወሰላመ እግዚአብሔር እንተ ኩሉ ባቲ ተሠሉ ወትረ ምስለ ኩልክሙ" ትርጓሜውም ሰላምን ተቀበልን፤ ለእናንተም ሰላምን ተውንላችሁ፤ የእግዚአብሔር ሰላም ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ ሁሉም የሚገኝባት የእግዚአብሔር ሰላም ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ትሁን ማለት ነው ጸመ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ ከዘወረደ ሐሙስና ከምኩራብ ሐሙስ፡፡

ከዚህ በኋላ ተሳስመው ተሰነባበቱ፤ እነርሱም ወደ አኩስም ተመለሱ፤ እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ስሜን ተራራዎች ሄደ፤ በዚያም አሁን በስሙ የታነጸው ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቦታ ላይ በምናኔ ተወስኖ ፈጣሪውን በብሕትውና እያገለገለ ኖረ፤ ደቀመዛሙርቱም ድጓውን እየጻፉ ከእርሱ ጋር ይኖሩ ነበር፤ ከብዙ ዓመታት በኋላ የአኩስም ጽዮን ካህናት ሊጠይቁት ወደ ስሜን ሄዱና ተገናኝተው በናፍቆት ሰላም ሲባባሉና ሲሳሳሙ የሚከተለውን ቃል በዜማ ዘመረ "አኃውየ ሰላም ለክሙ ወበሰላም እኤምንክሙ ዳኅናትኑ አብያተ ክርስቲያናት ወሚመ ጽዮንሃ ቅድስተ ትኤምንክሙ ትኤምንክሙ አምንክሙኒ ፍሥሐ ወሰላም" ትርጓሜውም ወንድሞቼ ሰላምታ ለእናንተ ይገባል በሰላምም እጅ እነሣላችኋለሁ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ደኅና ናቸውን? ቅድስት ጽዮንስ ደኅና ናትን? ሰላም ትላችኋለች ሰላም ትላችኋለች ሰላምታችሁም ደስታና ሰላም ነው ማለት ነው ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ ገጽ 144 ላይ በ1988 ዓ.ም. የታተመ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

እንደዚሁም ካህናቱ ከእርሱ ጋር ከቁዩ በኋላ ወደ አኮስም ሊመለሱ አስበው ለመስነባበት በቀረቡ ጊዜ አሁንም በተለመደው ጣዕመ ዜማ እንዲህ እያለ ተሰናበታቸው "አኃውየ ፍቁራንየ ሰላም ለክሙ ዝክሩኒ ወትረ በጸሎትክሙ እስመ ብዙኃ ትረድእ ጸሎተ ጻድቅ ስእለተ ጻድቅ አጥብዑ ቀዋመ በሃይማኖት ከመ በረከተ ትረሱ፤" ትርጓሜውም የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ሰላምታ ይገባችኋል ሁልጊዜ በጸሎታችሁ አስቡኝ የጻድቅ ጸሎት ብዙ ትረዳለችና በረከትን ትወርሱ ዘንድ በሃይማኖት ጸንታችሁ ቁሙ ማለት ነው ከምኮራብ ሐሙስ ጾመ ድጓ፡፡

እንደዚሁም አንድ ወንድሙ ሊጠይቀው ከአኮስም በመጣ ጊዜ እንዲህ እያለ በጣዕመ ዜማ ተቀበለው "ሰላም ለከ እጉየ ሰላም ለከ ፍቁርየ ዘሠምረት ነፍስየ በሰላመ እግዚአብሔር" ትርጓሜውም ወንድሜ! ሰላም ላንተ ይሁን፤ በእግዚብሔር ሰላም ነፍሴ እጅግ የወደደችህ ወዳጄ! ሰላም ላንተ ይሁን ማለት ነው ከዘወረደ ረቡዕ ጾመ ድጓ፡፡

በዚህ ሁኔታ በምናኔ ስሜን ውስጥ ደብረ ሐዊ ከተባለው ተራራና ጫካ ብዙ ዓመታትን ካሳለፈ በኋላ ግንቦት 11 ቀን ከዚህ ዓለም ተለየ ወይም ተሠወረ፤ በዚህ ዓለም የኖረበት ጠቅላላ ዕድሜው ሰባ አምስት ዓመት ነው፡፡

## የቅዱስ ያሬድ አርእስተ ዜማ

ቅዱስ ያሬድ የዜማውን ድርሰት በሃያ ሁለት አርእስተ ዜማ ደርሶታል፤ ይህንም ያደረገበት ምክንያት ፈጣሬ ፍጡራን የሆነ እግዚአብሔር አምላክ በሃያ ሁለት ሥነ ፍጥረት የሚመሰገን መሆኑን ለማስረዳት ነው፤ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት የሥነ ጥፍረት ቀጥር ሃያ ሁለት መሆኑ እዚህ ላይ ልብ ይሰዋል፡፡

የሥነ ፍጥረት ምሳሌ የሆኑት ሃያ ሁለት አርእስተ ዜማ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ዋዜማ
2. በሐምስት
3. እግዚአብሔር ነግሠ
4. ይትባረክ
5. ሠለስት
6. ሰላም
7. መዝሙር /አቡን
8. ዘአምላኪየ
9. ሚበዝኑ
10. አርባዕት
11. ብፁዕ ዘይሌቡ
12. መወድስ
13. ኮልክሙ
14. ዕዝል
15. ዘይእዜ
16. ማኅሌት
17. ስብሐተ ነግህ
18. እስመ ለዓለም
19. አርያም
20. ክብር ይእቲ
21. ዝማሬ
22. ዕጣነ ሞገር








መሐትው፣ አቡንና መዝሙር ቀጥራቸው አንድ ወገን ነው፤
የቅዱስ ያሬድ ዜማ ድርሰት በነዚህ አርእስት የተወሰነና የተቀመረ ነው፤

አጼ ገብረ መስቀል የዜማውን ጣዕም ከሰሙና ከተረዱ በኋላ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን መገልገያና ለሕዝቡ መባረኪያ የሰጣቸው መሆኑን በመገንዘብ ሊቃውንቱን ተቀበሉትና ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ ይሁን ብለው አዘዙአቸው፤ ነገር ግን ካህናቱና ሊቃውንቱ ምን ምልክት አይተን እንቀበለው ብለው መለሱላቸው፤ ከዚህ በኋላ ንጉሡ እንግዲያውስ ሱባዔ እንያዝና እርሱ ይግለጽልን ብለው ከታሕሣሥ አንድ ቀን ጀምሮ ሱባዔ እንዲያዝ አወጁ፤ በዚያን ጊዜ ታሕሣሥ አንድ ቀን ሰኞ ዕለት ውሉ ነበርና ከሰኞ እስከ እሑድ በየቀኑ የአኮስም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያንን እየዞሩ አራት መቶ እግዚአታና አርባ አንድ በእንተ ማርያም እያደረሱ ምህላውን አካሄዱ፤ በሰባተኛው ቀን እሑድ ዕለት ምህላውን ጨርሰው ሲያሳርጉ ጌታ በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ ሆኖ በአኮስም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ተገለጸላቸው፤ ከዚህም አያይዞ ቅዱስ ያሬድ " ዘ በመስቀሉ ተቀነወ ወበነቢያት ተሰብከ መላእክት ወሊቃነ መላእክት ሰብሕዎ ኪያሁ ንሰብክ መድኀኒ" ብሎ ነገረ መስቀሉን በማውሣት የወልድ ምሳሌ በሆነው በዕዝል ዘመረ፤ ትርጓሜውም በነቢያት ትንቢት የተነገረለትንና በመስቀሉ ላይ የተቸነከረውን ጌታ መላእክትና የመላእክት አለቆች አመሰገኑት፤ እኛም እርሱ መድኃኒት እንደሆነ እንናገራለን ማለት ነው፤ በዚህ በተገለጸው ራእይ መሠረት ዜማው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ መሆኑን አምነው ቤተ መንግሥቱ፣ ቤተ ክህነቱና ሕዝቡ በአንድነት ተቀበሉት፤ የአኮስም ጽዮን ካህናተ ደብተራ፣ ቀሳውስትና ዲያቆናቱም ወደ ቅዱስ ያሬድ ጉባኤ ቤት ገብተው ዜማውን በንቃትና በትጋት ይማሩት ጀመር፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከመባቻ እስከ ሰባት ቀን የአኮስም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያንን እየዞሩ አራት መቶ እግዚአታና አርባ አንድ በእንተ ማርያም ማድረስ የተለመደ ቀዋሚ ሥርዓት ሆኖ እስከዛሬም ይሠራበታል፤ በሌሎች ታላላቅ የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራትም ከመባቻ እስከ ሰባት ቀን አራት መቶ ምህላና አርባ አንድ በእንተ ማርያም ማድረስ ከዚህ የተወረሰ ነው፤ ይህም ቀን ስብክት ተብሎ ተሰየመ፤ ስብክት መባሉም የቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ ከእግዚአብሔር የተገኘ መሆኑን ጌታ በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ ሆኖ ለሕዝቡ በመታየት ስላረጋገጠና ቅዱስ ያሬድም ይህ የተሰቀለው ክርስቶስ ነቢያት በትንቢት የሰበኩት መሆኑን በመዝሙር ስለገለጸ ይህንኑና ትንቢተ ነቢያትን ለማስታወስ ነው፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ዜማው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መደበኛ መገልገያ ሆነ፤ ማኅሌቱና ቅዳሴው ሁሉ በቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ ተቀነባበረ፤ የአኮስም ጽዮን ቤተ ክርስቲያንም ሰማያዊ ዜማን ከዓመት እስከ ዓመት ያለመቋረጥ የሚዘመርባት በምድር ያለች ሁለተኛ ጽርሐ አርያም ሆነች፤ ቅዱስ ያሬድ ስሙ እንዳመለከተው ሰማያዊ ዜማን ወደ ምድር አወረደ፤ ስም በተግባር ተገለጠ፤ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ታደርሳለች" ተብሎ በእግዚአብሔር ቃል የተነገረውና የተመሰከረው ንጹሑ አምልኮቷ በሰማያዊ ዜማ ታጀበ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም ክፍለ ዓለም የማይገኘውን ዜማ ተቀዳጀች፤ በዚህም ዜማ ሃይማኖቷን ገነባች፡፡

በቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ እጅግ ተመስጦ የነበራቸውና በማንኛውም መልኩ ዜማው እንዲስፋፋ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ የነበሩት ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ገብረ መስቀልም ለቅዱስ ያሬድ ደቀመዛሙርት ሰፊ ድጋፍ ያደርጉ ነበረ፤ ይህንንም የቅዱስ ያሬድ መጽሐፈ ገድል እንዲህ ብሎ ይገልጸዋል "ወአንበሮሙ ወመስቀሊ ወይነ ዘያስተፈሥሕ ልቦሙ ይሁቦሙ በበጊዜሁ ወያለብሶሙ ልብሰ ሜላት ወአልባሰ ወርቅ" ትርጓሜውም ንጉሥ ገብረ መስቀል አስተማሪውንና ተማሪውን በታላቅ ክብር አስቀመጣቸው ወይም አኖራቸው፤ እንደዚሁም ያማረ ምግብንና ልብን የሚያስደስት የወይን መጠጥን በየጊዜው ይሰጣቸው ነበረ፤ የሐርና የወርቅ ልብስም ያለብሳቸው ነበረ ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ያሬድም በበኩሉ መስከረም ሃያ አምስት ቀን የአበባ በዓል ሲከበር "ተቀጸል ጽጌ ገብረ መስቀል ሐጸጌ" እያለ በመዘመር እቅፍ አበባን ያበረከትላቸው ነበር፤ ትርጓሜውም አጼ ገብረ መስቀል ሆይ ያማረ አበባን ይቀዳጁ ማለት ነው፤ ይህም በዓል ባህሉና ሥርዓቱ ተጠብቆ እስከ አጼ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ድረስ መስከረም 25 ቀን ሲከበር ኑሯል፤ ኋላ ግን አጼ ዘርአ ያዕቆብ ግማደ መስቀሉን መስከረም 10 ቀን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባታቸው ለዚህ መታሰቢያ እንዲሆን በማሰብ በዓሉ ከመስከረም 25 ወደ መስከረም 10 ቀን ተዛውሮ እንዲከበር አድርገዋል፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አጼ መስቀል እየተባለ እስከ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ በዓሉ መስከረም 10 ቀን ይከበር ነበር፤ ከዚያም በኋላ በደርግ ዘመነ መንግሥት ለ17 ዓመታት ብቻ በዓሉን የማክበር ሁኔታ ተቋርጦ ነበር፤ ይሁንና በዓሉ

www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን በዓል እንደመሆኑ መጠን እንደ ደምቡ በቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምሕረት እንዲከበር አምስተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወአጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ወፕሬዚደንት ዘዓለም አብያተ ክርስቲያናት እንደ ጥንቱ በቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምሕረት እንዲከበር ስላዘዙ እነሆ አሁን በየዓመቱ መስከረም 10 ቀን በታላቅ ክብር በዓሉ እየተከበረ ይገኛል፡፡

# ክፍል 3

## የቅዱስ ያሬድ ዜማ ይዘት

የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በይዘቱ የሥነ ፍጥረት ውበትን በማድነቅና የሥነ ፍጥረት አስገኝ የሆነው እግዚአብሔርን በማመስገን ላይ ያተኮረ ነው፤ ይህም ማለት በክረምት ወራት ዘሩን፣ ልምላሜውን፣ ዝናሙን፣ መብረቁን፣ ነጐድጓዱን በመጥቀስ፣ በወርኃ ጽጌ የአበባውን፣ የመከሩን፣ የምርቱንና የፍሬውን ሁኔታ በመጥቀስ፣ ከዚህም ጋር ትንቢተ ነቢያትን፣ የክርስቶስ ልደትን፣ ጥምቀትን፣ ጾምን፣ ስቅለትን፣ ትንሣኤን፣ ዕርገትንና ስብከተ ሐዋርያትን በአጠቃላይ ጌታ ለሰው ልጆች ሲል በዚህ ዓለም የፈጸመውን የማዳን ሥራ ሁሉ በመጥቀስ፣ እንደዚሁም የቅድስት ድንግል ማርያምን፣ የቅዱሳን መላእክትን፣ የነቢያትን፣ የሐዋርያትን፣ የጻድቃንና የሰማዕታትን ክብርና ቅድስና በማውሳት፣ በስማቸው መማጸንና መጸለይን የሚያስገኘውን ጥቅም የሚያስረዳ ታላቅ የሃይማኖት ዜማዊ ትምህርት ነው፤ ቅዱስ ያሬድ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጥቀስ ዜማውን ደርሶአል፡፡ ከእርሱ በፊት የነበሩና በእርሱ ዘመን የተጻፉ የቅዱሳን ገድላትና ድርሳናት ሁሉ በዜማ ድርሰቱ ተካተዋል፡፡

የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጣቀሰ ብቻ ሳይሆን የተረጐመም ነው፤ ለምሳሌ "ሥናኖ ለያዕቆብ ዘአፍቀረ" ተብሎ በመዝ.46፣4 የተጠቀሰውን "ወሥኑሰ ለያዕቆብ ዘይቤ ይእቲ ሥጋ እንተ ነሥአ መድኀኒ እማርያም" ማለትም የያዕቆብን ውበት ወይም ደም ግባት ወደደ የተባለው የዓለም መድኀኒ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም የነሣትን ሥጋ ሲያመለክት ነው በማለት ተርጉሞታል፤ በዚህ ዓይነት የተተረጐሙና የተብራሩ ብዙ የትርጓሜ ዓይነቶች በድርሰቱ ውስጥ ይገኛሉ፤ ከዚህም በተጨማሪ ድርሰቱ ምስጋናን፣ ጸሎትን፣ ምክርን፣ ታሪክን፣ ትምህርተ መለኮትንና የሥነ ምግባር ትምህርትን ይዘና አካቶ ይገኛል፡፡

የቅዱስ ያሬድ ድምፀ ዜማዎች በጥቅሉ ሦስት ዓይነት ናቸው፤ እነርሱም ግእዝ፣ ዕዝልና ዓራራይ ተብለው ይታወቃሉ፤ ይሁንና የዜማው ዓይነት ሦስት ቢሆንም በባህርዩ ሲታይ የአንዱ ዜማ ክፍል ከሌላው የዜማ ክፍል የተለየ ነው፤ ይህም ማለት የዜማው ቃና ከሦስቱ ድምፆች ማለትም ከግእዝ፣ ከዕዝልና ከዓራራይ ሳይወጣ በመርዘምና በማጠር አንዱ ክፍለ ዜማ ከሌላው ክፍለ ዜማ ይለያል ማለት ነው፤ ለምሳሌ ድኅ ከዝማሬ፣ ዝማሬ ከመዋሥእት፣ መዋሥእት ከቅዳሴ በአንድ ምልክት ወይም ምልክቱ አንድ ሆኖ ሳለ ባህርዩ ይለያያል ማለት ነው፤ ይህም በቅዱስ ያሬድ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሰጣት የእግዚአብሔር ጸጋ ምን ያህል ታላቅና ዓይነተ ብዙ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሌላው የቅዱስ ያሬድ ዜማ ከሌላው ድርሰት የሚለይበት ባህርይ የዜማው ጣዕምና ክብደት፣ የኃይለ ቃሉ ጥልቀትና ምጥቀት እንዲሁም የሥነ ቃሉ ውበትና ከሌሎች የዜማ ደራስያን የተለየና ከባድ ሆኖ መገኘቱ ነው፤ ለምሳሌ የኋላ ሊቃውንት ጥቂት የሆኑ የዜማ ድርሰቶችን በድጓው ውስጥ እንዲካተቱ አድርገዋል፤ እነዚህ የኋላ ሊቃውንት የደረሷቸው ድርሰቶች አዋልድ ተብለው ይጠራሉ፤ ወንበርም የላቸውም፤ ይሁንና የሊቃውንቱ ድርሰቶችና የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ሲመዛዘኑ የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ወይም ልዩነት ያላቸው ሆነው ይገኛሉ፤ የቅዱስ ያሬድ ዜማና ድርሰት ከሆነ ምንም ቢሆን የዜማ ክብደትና አመል ወይም የኃይለ ቃል ክብደትና የምሥጢር ጥልቀት አይጠፋበትምና በዚህ ባህርዩ ከሌሎች ድርሰቶች ተለይቶ የመታወቅ ባህርይ አለው፡፡





የቅዱስ ያሬድ ዜማ እንዲሁ ልቅ የሆነ ድርሰት ሳይሆን እያንዳንዱ የድጓ ርእስ የራሱ የሆነ መታወቂያ ቤት ያለው ነው፤ ይህም ማለት እያንዳንዱ የዜማ ርእስ የራሱ የሆነ የተለየ ስም፣ የተለየ ቤት፣ የተለየ ሃሌታና የተለየ አገልግሎት ያለው ነው እንደዚሁም በኃይለ ቃል፣ በምልአተ ንባብ፣ በዜማ ክብደትና በአመል የተለየ ባህርይ ያለው ነው፤ በመሆኑም በዚህ ሁሉ በዓለም ውስጥ ተመሳሳይ የማይገኝለት ልዩ ስልት ያለው ዜማ ሆኖ ይገኛል፤ ሌላ የዜማ ዐዋቂ ሰው ዝም ብሎ እንደመጣለት ከሚጮኽ በስተቀር ምን ዓይነት ዜማ እንደሚያዜም ማለትም ግእዝ፣ ዕዝል ወይም ዓራራይ ከሦስቱ የትኛው እንደሚያዜም እንኳን አያውቅም፤ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ግን ግእዙን ከዕዝሉ፣ ዕዝሉን ከዓራራዩ ሳይደበላለቁ ለይተው የሚያዜሙት ነው፤ የቅዱስ ያሬድ ዜማ አዋቂ የሆነ ሰው የሌላውን ዜማ ምን ዓይነት ዜማ እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ይችላል፤ ምክንያቱም ሰውም ሆነ እንስሳ ከሦስቱ የቅዱስ ያሬድ ድምፀ ዜማ ማለትም ከግእዝ፣ ከዕዝልና ከዓራራይ ውጭ ሌላ ዜማ ኖሮ መጮኽ አይችልምና ነው፤ " ኢየዐዱ እንስሳ ወሰብእ እምነ ሠላስ ዜማሁ" ማለትም እንስሳም ሆነ ሰው ከሦስቱ ዜማዎቹ ማለፍ አይችልም ይላልና ነው፡፡

## የቅዱስ ያሬድ ድምፀ ዜማ ዓይነቶች

ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ያዘጋጀው በሦስት ዓይነት ድምፀ ዜማ ነው፤ እነርሱም፡-

### ሀ. ስማቸው፡-

1. ግእዝ
2. ዕዝል
3. ዓራራይ ይባላሉ፡፡

እነዚህ ድምፆች በአምስቱ የዜማ ድርሰቶች ሁሉ ይገኛሉ፤ ከነዚህ ሦስት ድምፅ የወጣ ዜማ የለም " ሠለስቱ ዜማ ዘውእቱ ግእዝ ወዕዝል ወዓራራይ" ማለትም የዜማ ድምጾች ሦስት ናቸው፤ ይኸውም ግእዝ፣ ዕዝልና ዓራራይ ናቸው ማለት ነው፤ በሌላም በኩል ሰዎችም ሆኑ እንስሳት ከነዚህ ሦስት ድምፀ ዜማዎች መውጣት እንደማይችሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፤ "አልቦ እምቅድሜሁ ወአልቦ እምድኅሬሁ ማኅሌታይ ሰብእ ዘከማሁ ያሬድ ካህን ለክርስቶስ ሰበከ ትንሣኤሁ እያዐዱ እንስሳ ወሰብእ እምነ ሠላስ ዜማሁ" ትርጓሜውም ከእርሱ በፊትም ሆነ በኋላ እንደርሱ ያለ የማኅሌት ሊቅ የለም፤ ካህን ያሬድ የክርስቶስን ትንሣኤ አስተማረ፤ ሰውም ይሁን እንስሳ ከሦስቱ ዜማዎቹ አይወጣም ማለት ነው፤ እነዚህ ዜማዎች የአንዱ ድምፅ ከሌላኛው ድምፅ ያልተደበላለቀ፤ ወጥ የሆነና የየራሳቸው የሆነ ድምፅ ያላቸው ናቸው፤ በመሆኑም የዜማን ጠባይ በጥልቀት የተማሩና ያወቁ ሰዎች አንዱን ድምፅ ከሌላኛው ድምፅ ለመለየት ጊዜ አይወስድባቸውም፤ የሦስቱ ድምፅ በዜማ ብቻ ሳይሆን በንባብ ወይም በምዕዛል ጊዜም ተጠብቆ የሚባል ነው፤ ይህም ማለት የግእዝ ንባብ፣ ከዕዝል ንባብ፣ የዕዝል ንባብ ከዓራራይ ንባብ የተለየ ነው ማለት ነው፤ ይህ ሁኔታ በተለይም በምዕራፍና በቅዳሴ ላይ የሚታይ ነው፡፡

### ለ. ትርጉማቸው

1. ግእዝ፡-

ግእዝ የሚለው ቃል የተለያየ ትርጉም ያለው ቢሆንም የሌላውን ትተን በዜማ ስያሜ ላይ ያለውን ትርጉም እዚህ ማየቱ ተገቢ ነው፤ በመሠረቱ ግእዝ ብዙ ትርጉም ይኑረው እንጂ ምሥጢሩ ዞሮ ዞሮ አንድ ወይም መጀመሪያ ከሚለው ሐሳብ አይወጣም፤ በዚህም መሠረት በዜማ ስምነቱ ስንመለከት ግእዝ ማለት አንደኛ ወይም መጀመርያ ዜማ ማለት ነው፤ በባህርዩም ሲታይ በጣም ጠንካራና ኃይለኛ ነው፤ ከዚህም የተነሣ ሊቃውንቱ ደረቅ ዜማ ወዙ ወይም ለዛው በቀላሉ የማይያዝ ብለው ይገልጹታል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

2. ዕዝል፡-

ዕዝል የሚለው ቃል ታላይ ወይም ተደራቢ ማለት ነው፤ ይህም ማለት ከግእዝ ጋር ተደርቦ የሚተዘዘል ማለት ነው፤ ይኸውም በዓቢይ ስብሐተ ነግህ፣ በነቢያትና በሰሎሞን ምዕላል በስፋት ይታያል፤ እነዚህ ምዕላሎች ዕዝል ሲሆኑ ከምዕላሎቹ የመጀመርያዎቹ ሁለት መስመሮች በዕዝል ሲባሉ ቀጥለው ያሉ አምስት መሥመሮች ግን በግእዝ መተዘዘላቸው ከግእዝ ተደርቦ መባሉን ያረጋግጣሉ፤ ዕዝል በዜማ ባህርዩም ማኅዘኒ ወይም አስለቃሽ፣ አሳዛኝ ማለት ነው፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ ጌታ በተሰቀለበት በዕለተ ዓርብ የሚዜም ይህ ዕዝል የተባለው ዜማ ነው፤

3. ዓራራይ፡-

ዓራራይ ማለት የሚያራራ፣ ልዩ ጣዕም ያለውና ልብን የሚመስጥ ማለት ነው፤ በባህርዩም በጣም ተወዳጅ የሆነና የማይጠገብ ዜማ ነው፤ ይህ ዜማ በአምስቱ የዜማ ድርሰቶች ሁሉ ያለ ቢሆንም በተለይ በቅዳሴ ዜማ በዝቶ የሚታይ ነው፤ የቅዳሴ ዜማ ቢያንስ ሰባ እጁ የዓራራይ ዜማ ነው፡፡

## ሐ. ምሳሌያቸው፡-

የቅዱስ ያሬድ ድምፀ ዜማዎች የተለያየ ስምና ትርጉም ያላቸውን ያህል ምሳሌያቸውም እንደዚሁ የተለያየ ምሥጢር ያለው ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር አንድነትንና ሦስትነትን የሚገልጽ ነው፤ ከዚህ አንጻር ሲታዩ እያንዳንዳቸው የሚከተለውን ምሳሌና ምሥጢር ይሰጡናል፡፡

## ሀ. ግእዝ

ግእዝ የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ ነው፤ ግእዝ የመጀመርያው ዜማ ስም እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔርንም በሦስትነት ስሙ ስንጠራ በመጀመርያ አብ የሚለውን ስም መቅደሙን የሚያስረዳ ምሳሌ ነው፤ የግእዝ ዜማ በባህርዩ ጠንካራና ኃይለኛ እንደሆነ ሁሉ እግዚአብሔር አብም ለአዳም የገባውን መሐላ ወይም ቃል ኪዳን ለመፈጸም አምስተኛው ሺሕ ተፈጽሞ ስድስተኛው ሺሕ ሲጋመስ በጽኑ ቀጠሮውና በታማኝ ቃሉ፣ ኃይሉና ክንዱ ዕሥነውን እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መላኩን ምሥጢሩ ያሳያል፤ በሌላም በኩል በዓቢይ ጾም ውስጥ ያሉት የመጀመርያዎቹ አምስት ሳምንታት የእግዚአብሔር አብና የአምስት ሺሕ ዓመታት ምሳሌ ናቸው፤ በመሆኑም የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ እንደመሆናቸው መጠን ቅዱስ ያሬድ ጾመ ድጓውን የአብ ምሳሌ በሆነው በግእዝ እንዲቀም አድርጎታል፤ የአምስት ሺሕ ዘመን ምሳሌ እንደመሆናቸውም አምስት ሳምንታት ናቸው፤ የግእዝ ዜማ በባህርዩ ፕንተር ያለ ዜማ መሆኑ በአምስት ሺሕ ዓመታት ውስጥ ሰዎች በጽኑ መከራ ሥጋና መከራ ነፍስ የነበሩ መሆናቸውን ምስጢሩ ይጠቁማል፡፡

## ለ. ዕዝል

ዕዝል የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌ ነው፤ ይኸውም የዕዝል ዜማ ስም ኣዛይ፣ ታላይ ወይም ተደራቢ ማለት እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጾአል፣ ይህ ስም ቅድመ ዓለም ከብ የተደወለው እግዚአብሔር ወልደ ድኅረ ዓለም ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ሲወለድ ቅድስት ድንግል ማርያም ያዘለችው መሆኑን ምሥጢሩ ያሳያል፤ የዕዝል ዜማ ከግእዝ ቀጥሎ እንደሚጠራ ከእግዚአብሔር አብ ቀጥሎም እግዚአብሔር ወልደ የሚጠራ መሆኑን በምሳሌነቱ ይገልጻል፤ የዕዝል ዜማ በባህርዩ አሳዛኝና አስለቃሽ እንደሆነ እግዚአብሔር ወልድም ሰውን ለማዳን የተቀበለው መከራ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ መሆኑን ምሥጢሩ ይገልጻል፤ ይህ የዕዝል ዜማ በዓቢይ ጾም ውስጥ በስድስተኛው ሳምንት በሰሙነ ገብርኄር ይቆማል፤ ይህም እግዚአብሔር ወልድ በስድስተኛው ሺሕ አጋማሽ ሰው ሆኖ መከራ በመቀበል ዓለምን ያዳነ መሆኑን ለመግለጽ ቅዱስ ያሬድ ስድስተኛውን ሳምንት የወልድ ምሳሌ በሆነው በዕዝል እንዲቀም አድርጎታል፤ ከዚህም ሌላ ዕዝል የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ጌታ ታላላቅ የማዳን ሥራዎች በሠራባቸው ቀናትና ዘመናት ዕዝል እንጂ ግእዝ አይቀደስባቸውም፤ ለምሳሌ ከቀናት ትስብእት፣ ልደት፣ ጥምቀት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ ዕርገት ወዘተ ሲሆኑ ከዘመናት ደግሞ ንጉሡ ሰሎሞን ክርስቶስን በሙሽራና በአበባ፣ ምእመናንን





ወደዚህ ዓለም መጥቶ የዓለም ቤዛ በመሆን ሰውን እንደሚያድን ነቢያት የተናገሩትን ትንቢት የሚታሰብበት ዘመነ ስብከት፣ ክርስቶስ የተወለደበትንና የተጠመቀበትን የሚታወስበት ዘመነ ልደት፣ ዘመነ አስተርእዮና ዘመነ መርዓዊ፣ ክርስቶስ መከራ ተቀብሎ የሞተበት፣ የተነሣበት፣ ያረገበትና መንፈስ ቅዱስን ሐዋርያት የሰጠበት ዘመነ ትንሣኤና የጰራቅሊጦስ ሳምንት በዕዝል መቀደሳቸው ዕዝል የወልድ ምሳሌ በመሆኑና ለእኛ ሲል የተቀበለውን መከራ ለማስታወስ ነው፡፡

## ሐ. ዓራራይ

ዓራራይ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው፤ ይኸውም የዓራራይ ዜማ ርኅራሄ ያለው ወይም አራ?ራኂ የሆነ ልዩ ጣዕም ያለውና ልብን የሚመስጥ መሆኑ ከላይ ተገልጾአል፤ በመሆኑም የዓራራይ ስም ከዕዝል ቀጥሎ እንደሚጠራ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስምም ከእግዚአብሔር ወልድ ቀጥሎ የሚጠራ መሆኑን ይገልጻል፤ የዓራራይ ዜማ ባህርይ ጣዕም ያለው፣ ልብን የሚመስጥና አራኅራኂ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ረቂቁን መንፈስ ልያት ከመስጠት በተጨማሪ የመንግሥተ ሰማያት ርስት ዓረቦን /መያዣ/ በመስጠት በጣዕመ ጸጋ ላይ ሕይወትን የሚያድል፣ የምእመናንን ልብ በደስታ የሚሞላ፣ በርኅራኄው ኃጢአትን የሚያስተሠርይ መሆኑን ምሥጢሩ ያሳያል፤ ቅዱስ ያሬድ የዓራራይን ዜማ በዓቢይ ጾም ውስጥ ከዕዝል ቀጥሎ በሰሙነ ኒቆዲሞስ እንዲቀም አድርጎታል፤ ከዕዝል ቀጥሎ ዓራራይ መቆሙ ጌታ ቤዛ ዓለም ሆኖ በመስቀል መሥዋእትነት ከከፈለ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ከዚያም እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሡ ምእመናን መሰጠቱን ያሳያል፤ ዜማው አራኅራኂ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም የምእመናንን ኃጢአት ይቅር እያለ በርኅራሄ የሚጠብቃቸው መሆኑን ምሥጢሩ ይገልጻል፤ በሌላም በኩል ቅዱስ ያሬድ የዓራራይን ዜማ በሰሙነ ኒቆዲሞስ እንዲቀም ማድረጉ ጌታ "ከውሃና ከመንፈስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ዮሐ.3፤5" ሲል የነገረው ለኒቆዲሞስ ነውና ዓራራይ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መሆኑን ለመግለጽ የመንፈስ ልደትን በተረዳ በኒቆዲሞስ ሳምንት እንዲቀም ሆነ፡፡ ከዚህም ሌላ ግእዝ፣ ዕዝልና ዓራራይ አብ የወልድ ወላዲ፣ የመንፈስ ቅዱስ አሥራጺ መሆኑን፣ ወልድም ከአብ የተወለደ መሆኑንና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ብቻ የሠረፀ መሆኑን፣ በሚያስረዳ ሁኔታ ተጣምረው የሚዜሙበት ሁኔታ አለ፤ ይኸውም ግእዝ ከዕዝልና ከዓራራይ ተጣምሮ መገኘቱ አብ ወላዲና አሥራጺ መሆኑን ያሳያል፤ ለዚህም የደብረ ታቦሩ ሠለስት ወአመ ሰዱስ የሚለውና ዘበዳዊት የሚለው የቃና ዘገሊላ አርዓፅት ተጠቃሽ ናቸው፤ ዕዝልና ዓራራይ ግን በየትኛውም ስፍራ ተጣምረው ሲዜሙ አይገኙም፤ ይኸውም ወልድ ከአብ ብቻ ከሚወለድ፣ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ብቻ ከሚሠርጽ በቀር ከወልድ የማይሠርጽ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፤ በሌላ በኩል የሦስቱን አንድነትና እኩልነት ለመግለጽ የመሥዋዕት መለወጫ በሆነው አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ በሚለው የቅዳሴ ዜማ ሦስቱም ድምፀ ዜማዎች በውስጡ ተሰባጥረው ይገኛሉ፡፡

# ክፍል 4

## የቅዱስ ያሬድ ዜማ ትምህርት ቤት

ቅዱስ ያሬድ በብሉይና ሐዲስ ትርጓሜ መምህርነቱ ላይ አዲስ የሆነውን ሰማያዊ ዜማ በማስገኘቱና በማስተማሩ በጸጋ ላይ ጸጋ የተጐናጸፈ በመሆኑ በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ታላቅ ሊቅ ነው፤ ሌሎች በዓለማችን የተነሡ ሊቃውንት መተርጉማን፣ ወይም ደራስያን፣ ወይም ደግሞ የምድራዊ ዜማ አዋቂዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ቅዱስ ያሬድ ግን ከሌሎች የዓለም ሊቃውንት በተለየ መልኩ በተርጓሚነት ላይ ደራሲነት፣ በደራሲነት ላይ የሰማያዊ ዜማ ባለቤት፣ በዜማ ላይ ቅድስናና ብዕዕና ከምናኔና ከብቃት ጋራ ያጣመረ የዓለማችን ብቸኛ የቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሊቅ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ ያለ ዕረፍት ቀን ከሌሊት የሚያስተምር መምህር ስለነበረ በአጭር ጊዜ ውስጥ መላው የአኮስም ካህናተ ደብተራ የዜማ ሊቃውንት እንዲሆኑ አድርጎአል፤ ከነዚህም ውስጥ በጣም የታወቁና ከእርሱ በኋላ የዜማ ትምህርትን ወደ መላ ኢትዮጵያ ያስፋፉ ደቀመዛሙርት የሚከተሉት ነበሩ፤

እነርሱም፡-

ሀ. መንክራ

ለ. ሳዊራ

ሐ. ብስድራ

መ. እስክንድራ የተባሉት ናቸው፤

የቅዱስ ያሬድ ትምህርት ቤት የራሱ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ነበረው፤ ሥርዓቱም እንደሚከተለው ነበረ፡-

ቅዱስ ያሬድ የነግህ ጸሎቱን እንደፈጸመ በ3 ሰዓት ደወል ይደወላል፤ ከዚህ በኋላ ደቀመዛምርቱ በሙሉ በሚማሩበት በቤተ ቀጢን ቤተ ጉባኤ ይገኛሉ፤ ያን ጊዜ የተማሪዎቹ አለቃ የመማርያ መጻሕፍትን ያቀርባል፤ ቅዱስ ያሬድም ትምህርቱን በጸሎት ከፍቶ ይጀምርላቸዋል፤ ደቀመዛሙርቱም ዙርያውን ከበው ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ፤ ደቀመዛምርቱ መጻሕፍቶቻቸውን በአትሮንስ አስቀምጠው በየተራ እየጠየቁ እርሱም እያስረዳቸው በዚህ ዓይነት እስከ 7 ሰዓት ድረስ ሲማሩ ይውላሉ፡፡

7 ሰዓት ሲሆን ደወል ተደውሎ ትምህርቱ በጸሎት ይዘጋና እስከ 8 ዕረፍት ይሆናል፤ 8 ሰዓት ሲሆን ደወል ተደውሎ እንደገና መምህራቸው ቅዱስ ያሬድና ደቀመዛምርቱ በጉባኤ ቤቱ ይገኛሉ፤ ትምህርቱ በጸሎት ከተከፈተ በኋላ እስከ 11 ሰዓት ሲማሩ ይቈያሉ፤ 11 ሰዓት ሲሆን ደወል ተደውሎ ትምህርቱ በጸሎት ይዘጋል፡፡

በ12 ሰዓት ደወል ተደውሎ ውዳሴ ማርያምን፣ መሐረነ አብንና ክሥተትን በዜማ ያደርሳሉ፤ አያይዘውም የቃል ትምህርት ጸሎት ይጸልያሉ፤ ቃል ትምህርት የሚባሉት ውዳሴ ማርያም፣ መስተጋብእ፣ አርባዕት፣ አርያም፣ ሠለስትና ክሥተት ናቸው፤ ከጸሎቱ ፍጻሜ በኋላ የማታ ትምህርት እስከ 4 ሰዓት ከምሽቱ ይቀጥላል፤ አራት ሰዓት ሲሆን ትምህርቱ በጸሎት ይዘጋል፤ ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱ እራታቸውን ይበሉና ሲቀጽሉ ያመሻሉ፡፡

ከሌሊቱ 8 ሰዓት ሲሆን ደወል ተደውሎ መምህሩም ደቀመዛሙርቱም በጉባኤ ቤቱ ይገኙና ትምህርቱ በጸሎት ይከፈታል፤ እስከ ጠዋቱ 11 ሰዓት ሲማሩ ቈይተው በዚህ ጊዜ ትምህርቱ በጸሎት ይዘጋል፡፡

በ11 ሰዓት ቅዱስ ያሬድ ደቀመዛምርቱን አስከትሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ እስከ ሁለት ሰዓት ከቀኑ የዕለቱን ስብሐተ ነግህ ያደርሳል፤ 3 ሰዓት ሲሆን ደወል ተደውሎ የማስተማር ሥራውን እንደገና ይቀጥላል፤ በዚህ ሁኔታ ይካሄድ የነበረው የቅዱስ ያሬድ ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት እስከ ዘመናችን ድረስ በአንዳንድ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት ሥርዓቱ ተጠብቆ ሲፈጸም ይገኛል፤ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ደቀመዝሙር ከወንበር ወይም ከትምህርት የሚገታበት ጊዜ ቢኖር የልመና ጊዜ ብቻ ነው፤ ከዚህ በተረፈ ግን ሌትም ሆነ ቀን፣ ማታም ሆነ ጠዋት መማር ነው፤ ዕረፍት ተብሎ የሚታወቅ ነገር የለም፤ ይህንን ሥርዓተ ትምህርት ስንመለከት በቅዱስ ያሬድ የተገነባው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት የትምህርት ተኮር ሥርዓት ብቻ ሳይሆን የምናኔ፣ የተጋድሎ፣ የትሩፋትና የጸሎት ቤት ማእከልም ጭምር እንደነበረ እንገነዘባለን፡፡





## የቅዱስ ያሬድ ዜማ መስፋፋት

ቅዱስ ያሬድ ከተሠወረ በኋላ የሱ ዕውቅ ደቀመዛሙርት የነበሩት ፡-

1. መንክራ
2. ብስድራ
3. ሳዊራ
4. እስክንድራ ናቸው፤

እነዚህ ደቀመዛሙርት ከቅዱስ ያሬድ በኋላ በመምህራቸው እግር ተተክተው የቅዱስ ያሬድን ዜማ ማስተማር ቀጠሉ፤ እነዚህ ዐራቱ ደቀመዛሙርት በትጋትና በንቃት እያስተማሩ ብዙ ሊቃውንትን ስላፈሩ የአኮስም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ጽርሐ አርያም አስመስለዋት ነበር፤ በተለይም በመጀመርያ መንክራና እስክንድራ በቤተ ቀጢን ሆነው ዜማን፣ የመጻሕፍተ ብሉያትን እና የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ ጭምር ያስተምሩ ስለነበር ጉባኤ ቤታቸው በጣም የሰፋ ነበረ፤ እንደዚሁም ብስድራ እና ሳዊራ በአባ ገሪማ ገዳም መደራ ጉባኤ ቤት ውስጥ ሆነው ዜማን እያስተማሩ ብዙ ሊቃውንትን አፍርተዋል፤ ሳዊራ ከመደራ ሳይወጣ ዕድሜውን በዚያ ፈጸመ፡፡

መንክራም ከአኮስም ወጥቶ ደብረ ዳሞ ሄደ፤ ከዚያም ከመነነ በኋላ በዚያው ዜማን እያስተማረ ብዙ ደቀመዛሙርትን አበርክቶ ዕድሜውን ሁሉ በዚያው ፈጽሞ ደብረ ዳሞ ተቀበረ፡፡

እንደዚሁም ብስድራ ከመደራ ወደ ሐማሴን ሂዶ ድግሣ በሚባል ገዳም ውስጥ በምናኔ ተወሰነ፤ እዚያም ዜማ እያስተማረ ብዙ ዘመን ተቀመጠ፤ በመጨረሻም በዚያው አርፎ ተቀበረ፡፡

ብስድራ ካስተማራቸው ብዙ ደቀመዛሙርት አንዱ ፀሐየ ቅዱሳን ይባል ነበር፤ እርሱም ከመምህሩ ሞት በኋላ ሐማሴንን ለቆ ወደ ሸዋ በመሄድ አጼ ገብረ መስቀል ባሠሩት ጎሐ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጦ ዜማን እያስተማረ ከቆየ በኋላ ብዙ ደቀመዛሙርትን ተክቶ በዚያው አረፈ፡፡

እስክንድራ ግን በአኮስም ውስጥ የቤተ ቀጢን ጉባኤ ቤት መምህር ሆኖ እስከመጨረሻ ዕድሜው በዚያው ኖረ፡፡

ከዚህ በኋላ የዜማው ትምህርት በትግራይ ውስጥ በሚገኙ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት፣ በጣና ቂርቆስ፣ በጎሐ ጽዮን፣ በተድባበ ማርያም፣ በመርጡለ ማርያምና በዙር አባ ሁሉ ተዳረሰ፤ በሂደትም በአንደዚህ ያለ ሁኔታ የቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ በመላው ኢትየጵያ ተስፋፋ፤

# ክፍል 5

## 1. የቅዱስ ያሬድ መጻሕፍተ ዜማ አከፋፈል

ቅዱስ ያሬድ ራሱ የደረሳቸውና ድርሰታቸው የሌሎች ሊቃውንት ሆነው ዜማቸውን ብቻ እሱ የደረሳቸው መጻሕፍት በአጠቃላይ አምስት ናቸው፤

እነዚህም፡-

ሀ. ድጓ
ለ. ምዕራፍ

www.ethiopianorthodox.org

ሐ. ዝማሬ

መ. መዋሥእት

ሠ. ዐሥራ ዐራቱ ቅዳሴ ናቸው፡፡

ከነዚህም ውስጥ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥእት ድርሰታቸውም ሆነ ዜማቸው የራሱ ሲሆኑ ቅዳሴ ግን ድርሰቱ የሌሎች ሊቃውንት ሆኖ ዜማው የእርሱ ነው፡፡

## 2. የቅዱስ ያሬድ መጻሕፍተ ዜማ ስያሜ

ሀ. ድጓ፡-

ድጓ የሚለው ስም የዜማ መጽሐፍ ስም ነው፤ ይኸውም ራሱ ቅዱስ ያሬድ የደረሰውና ያዜመው መጽሐፍ ሲሆን በመጠኑ ከሌሎች ድርሰቶቹ በጣም ትልቅ ነው፤ አጻጻፉ ረቂቅ ስለሆነ ድጓ የሚል ስም ተሰጥቶታል፤ ይኸውም ደግደገ ከሣ ካለው ግስ የወጣ ዘር ሆኖ የጽሕፈቱን መክሳት ወይም ደቃቅ መሆን ያመለክታል፤ አንዳንዶቹ እንደሚሉትም ንባቡን አላልቶ ድጓ ማለት የቤተ ክርስቲያን ትጥቋ ማለት ነው፤ አከፋፈሉም በዐራት ትላልቅ ክፍሎች ይከፈላል፤ ይኸውም፡-

1ኛ/ ዮሐንስ
2ኛ/ አስተምሕሮ
3ኛ/ ጾመ ድጓና
4ኛ/ ፋሲካ ናቸው፡፡

1. ዮሐንስ፡-

ይህ ክፍል ከዮሐንስ /መስከረም 1/ እስከ ኅዳር 30 ቀን ድረስ ያለው ሲሆን ክፍሉ በዜማው ከባድነትና በቁጥሩ ብዛት ከሌሎች ክፍሎች የበለጠ ነው፡፡

2. አስተምሕሮ፡-

ይህ ሁለተኛው የድጓ ክፍል ስለ እግዚአብሔር መሐሪነትና ርኅራኄ በማውሳት ስለሚጀምር አስተምሕሮ ተብሎ ይታወቃል፤ ምድቡም ከታሕሣሥ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ፋሲካ ድረስ ባለው ጊዜ የሚዘመር ነው፡፡

3. ጾመ ድጓ፡-

ይህ ሦስተኛ የድጓ ክፍል ከአስተምሕሮ የድጓ ክፍል ሆኖ በተለይም በጾመ አርብዓ ወቅት በነግህ፣ በሠለስት፣ በቀትርና በሠርክ እንዲሁም እሑድና ቅዳሜ በሌሊት የሚዘመር ነው፤ በውስጡም የያዘው ፍሬ ሐሳብ የጾምን፣ የጸሎትን፣ የምጽዋትንና የፍቅርን ጠቃሚነት አጉልቶ የሚያስተምር ነው፡፡

4. ፋሲካ፡-

አራተኛው የድጓ ክፍል ከፋሲካ ጀምሮ እስከ ጳጉሜን መጨረሻ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚዘመር ነው፡፡

ለ. ምዕራፍ፡-

ይህ ሁለተኛው የቅዱስ ያሬድ የድርሰት መጽሐፍ ነው፤ ምዕራፍ የተባለበት ምክንያት በየመዝሙራቱ መሐል ሃሌታና ድጓ እያስገባ ለመዝሙሩ ማረፍያ ስለሚጨምት በዚህ ምክንያት ምዕራፍ



የሚል ስም ሊያገኝ ችሏል፤ ይህ የዜማ መጽሐፍ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል፤ ይኸውም፡-

ሀ. የዘወትር ምዕራፍ
ለ. የጾም ምዕራፍ

የዘወትር ምዕራፍ የሚባለው በዓመቱ ውስጥ ባሉት ቀናት፣ ሳምንታትና በዓላት ሁልጊዜ በአገልግሎት ላይ የሚውል ሲሆን የጾም ምዕራፍ የሚባለው ደግሞ በጾመ አርብዓ ብቻ ለአገልግሎት የሚውል ነው፤ ከዚህም በተጨማሪ በዐሥሩ ምህላት የሚባለው አርእስተ ምህላ በዚሁ ክፍል ይካተታል፤ የምዕራፍ ቅንብር ከመዝሙረ ዳዊት፣ ከድጓና ከጾመ ድጓ ጋር የተቀናጀ ነው፤ የትምህርት አሰጣጡም እንደ ድጓው ወይም እንደ ዝማሬ መዋሥእቱ መጽሐፍ ተዘርግቶ ሳይሆን በቃል የሚጠናና የሚወሰን ነው፤ ስለሆነም ምዕራፍን ለመማር 150 መዝሙረ ዳዊትን፣ ከነቢያት 15 ምዕራፎችንና 5 መኃልያተ ሰሎሞንን በቃል ሸምድዶ መያዝ ግድ ነው፡፡

ሐ. ዝማሬ፡-

የቃሉ ትርጓሜ ዘመረ አመሰገነ ካለው ግሥ የወጣ ዘር ነው፤ ፍቹም ምስጋና ማለት ነው፤ ይህ የዜማ መጽሐፍ ከቅዳሴ ጋራ የተቆራኘ አገልግሎት ያለው ነው፤ ይኸውም ሥርዓተ ቅዳሴው ተከናውኖ የቍርባን ምሥጢር ለምእመናን በሚሰጥበት ጊዜ የሚዘመር ነው፤ ይህ ሥርዓት ጌታ ለሐዋርያት የቍርባንን ምሥጢር ካሳየ በኋላ ሐዋርያት ወድያውኑ በዝማሬ ምስጋና ማቅረባቸውን መሠረት ያደረገ የምስጋና ሥርዓት ነው ማቴ.26፣30፤ ይህ የዜማ ክፍል አምስት ክፍሎች አሉት፤ እነሱም፡-

ሀ. ዝማሬ
ለ. ጽዋዕ
ሐ. መንፈስ
መ. አኰቴት
ሠ. ምሥጢር ይባላሉ፡፡

እነዚህ አምስቱ የዝማሬ ክፍሎች ከተቻለ በአንድ ቀን ይዘመራሉ፤ ካልተቻለም 3ቱ ማለትም ዝማሬ፣ ጽዋዕ እና መንፈስ ይዘመራሉ፤ ይህ ካልሆነም ከአምስቱ አንዱን መርጦ ይባላል፤ እነዚህ እያንዳንዳቸው በያዙት ኃይለ ቃል ተለይተው ይታወቃሉ፤ ይኸውም ዝማሬው ኅብስት የሚለውን ቃል የሚያስቀድም ከሆነ ዝማሬ ይባላል፤ ጽዋዕ የሚለውን ቃል የሚያስቀድም ከሆነም ጽዋዕ ይባላል፤ መንፈስ የሚለውን ቃል የሚያስቀድም ከሆነ ደግሞ መንፈስ ይባላል፤ አኰቴትና ምሥጢር የተባሉት ግን ሁሉንም የሚያጠቃልሉ ስለሆኑ በአርእስታቸው ብቻ ይታወቃሉ፡፡

መ. መዋሥእት፡-

የቃሉ ትርጓሜ አውሥአ መለሰ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ መመላለሻ ማለት ነው፤ ምክንያቱም አባባሉ በግራና በቀኝ እየተመላለሰ የሚባል ስለሆነ ነው፤ በሌላም በኩል ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የሚጸለይለት ጸሎት እሱ ስለሆነ የነፍስ መሸኛና የመንግሥተ ሰማያት መውረሻ ጸሎት ማለት ነው፡፡ የመዋሥእት ጸሎት በዕለተ ፍትሐት ብቻ ሳይሆን በበዓላትም የሚደርስ የዜማ ጸሎት ነው፤ ይህ የዜማ ጸሎት ሲደርስ የመዝሙረ ዳዊትን መጀመሪያና መጨረሻ መሥመር በመጠቀም እናቱንና ምልጣኑን በድምር አሥራ ሁለት ጊዜ በማመላለስ ይባላል፤ መዋሥእት ከሌሎች የቅዱስ ያሬድ ዜማዎች ልዩ የሚያደርገው ሁሉም መዋሥእቶች ምልጣን ያላቸው መሆናቸውን ነው፤ መዋሥእት ሆኖ ምልጣን የሌለው የለም፡፡

ሠ. ቅዳሴ፡-

ድርሰቱ የሌሎች ሊቃውንት ሆኖ ዜማው ግን ሙሉ በሙሉ የቅዱስ ያሬድ ነው፤ ይኸውም ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ ኤፍሬምን ከሶርያ አባ ሕርያቆስን ከብህንሳ በደመና ጠቅሳ ቅዱስ ያሬድ በጊዜውያስተምርበት ከነበረ ከአኮስም ከተማ ወደ ሰሜን አቅጣጫ 2 ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ወደሚገኘው ማይክሬዋሕ /ማይ ክራውሕ/ ድረስ አምጥታ አባ ሕርያቆስን ቅዳሴዎን አባ ኤፍሬምን ውዳሴዎን ንገሩትና በዜማ ያድርስላችሁ አለቻቸው፤ በዚህ ጊዜ እነሱ ዘሩን እየነገሩት በዜማ አድርሶላቸዋል፤ ከዚያም አያይዞ አሥራ ሦስቱን ቅዳሴ በዜማ አድርሷቸዋል፤ በመቀጠልም ኪዳኑን፣ ሊጦኑንና መስተብቍዑን ሁሉ በዜማ አድርሶታል፤ ዘይነግሥ የተባለው የመስተብቍዕ ተመሳሳይ ድርሰት ግን ዜማውንና ዘሩን እርሱ ራሱ ደርሶታል፤ ቅዳሴ የተባለው የዜማ መጽሐፍ በሦስት ይከፈላል፤ ይኸውም፡-

www.ethiopianorthodox.org

ለ. ፍሬ ቅዳሴ

ሐ. መስተብቍዓት ተብለው ይታወቃሉ፡፡

የቅዳሴ ዜማ ጠባይ ከድጓ ለየት ያለ ስለሆነ አብዛኛው ምልክት ከድጓ ጋር አይገናኝም፤ የቅዳሴ ዜማ እስከ ጸሎተ ወንጌል ያለው የግእዝና የዓራራይ ስብጥር ዜማ ብቻ ሲሆን ከጸሎተ ወንጌል ጀምሮ እስከመጨረሻ ያለው ግን ግእዝን፣ ፅዝልንና ዓራራይን ሁሉ ያጠቃለለ ነው፡፡

# ክፍል 6

## የዜማ ምልክቶች አመጣጥ፣

የቅዱስ ያሬድ ዜማ ከጥንት ጀምሮ የተለየና የራሱ የሆነ ቅርጽ ያለው የዜማ ምልክት አለው፤ የዜማው ዋና መደቦች የሆኑ ግእዝ፣ ፅዝልና ዓራራይ ዜማውን በድምፀ ቃና ሲለዩ ምልክቶቹም የየዜማ መደቡ ጣዕመ ቃና ሳያደባልቁ ግን ደግሞ የመልካቸውን ቅርጽ ሳይለውጡ በሦስቱ ምድብ ዜማዎች ይገኛሉ፤ ለምሳሌ ጭረት የተሰኘው የዜማ ምልክት በሦስቱ ምድብ ዜማ ይገኛል፤ ሆኖም በጣዕመ ዜማ ተለይቶ ከሚታወቅ በስተቀር በምልክት ቅርጹ አይለይም፤ ሌሎቹም እንደዚሁ የሆነ ባህርይ አላቸው፤ ስለሆነም በቅዱስ ያሬድ የተፈጠሩ የዜማ ምልክቶች ወይም ኖታዎች ቅርጻቸውን ሳይለውጡ ለሦስቱ ምድብ ዜማዎች ሁሉ አገልግሎት ይሰጣሉ ማለት ነው፤ እነዚህ የዜማ ምልክቶች በዐራት ይከፈላሉ፤ ይኸውም፡-

ሀ. ራሱ ቅዱስ ያሬድ ያስገኛቸውና የፊደል ቅርጽ የሌላቸው የዜማ ምልክቶች፣

ለ. የኋላ ሊቃውንት ከዜማው ዘር ለምልክትነት በመምረጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደረጓቸው የዜማ ምልክቶች፣

ሐ. በተለያዩ ጊዜያት አንዳንድ ታላላቅ ሥራዎችን የሠሩ ሰዎች ሥራቸው እንዲታወስ ተብሎ በስማቸው የተዘጋጁ የአማርኛ ምልክቶች፣

መ. መምህሩ ደቀመዛሙርቱን በሚያስተምርበት ጊዜ በአካባቢ ባለው ሁኔታ በቀላሉ እንዲረዱለት ሲፈልግ አንድን ዐረፍተ ነገር በዜማ አስማምቶ ለምልክት የተጠቀመበት ሁኔታ ስላለ በዚህ መሠረት ጥቅም ላይ የዋሉ የዜማ ምልክቶችና አንዳንድ ጊዜም ራሱ ተማሪው ዜማው በቀላሉ ሊገባው ሲፈልግ አንድ ቀላል የሆነ አባባል በዜማ አስማምቶ የሚጠቀምበት ጊዜ ስለነበረ በዚህ ምክንያት የተፈጠሩ ምልክቶች ናቸው፤ በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ምልክቶች ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን በዜማው ውስጥ በምልክትነት የምትገለገልባቸው ናቸው፡፡

ምልክት ማለት የአንድን ነገር አቅጣጫ አመልካች ወይም ጥቆማ ሰጭ ማለት ሲሆን ይችላል፤ ይህ ቃል ለዜማ ብቻ ሳይሆን ለሌላም ብዙ ነገር ሊያገለግል የሚችል ቃል ነው፤ ለዜማ አገልግሎት በምንጠቀምበት ጊዜ ግን ምልክት ሲባል ዜማውን እንዴት ማዜም እንዳለብን ሊመራን፤ ሊያስረዳን፤ሊያሳውቀንና ሊያረጋግጥልን የሚችል ጠቋሚ ነገር ማለት ነው፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ዜማውን ሲጠራጠር ወይም ዜማ ሲጠፋው መጽሐፉን ገልጦ ምልክቱን በማየት ያንን የተጠራጠረውን ወይም የጠፋውን ዜማ በምልክቱ ጠቋሚነት ያገኘዋል ማለት ነው፤ ያም ሆኖ ሊረዳው የሚችለው በትምህርቱ ያለፈና የዜማውንና የምልክቱን አጠቃቀም በሚገባ ያወቀ ሰው ሲሆን ነው አለበለዚያ ግን ዜማውን ሳይረዳ፤ የምልክቱን ማንነትና አጠቃቀም ሳያውቅ ምልክቱን በማየት ብቻ እሄድበታለሁ ለማለ የሚቻል
አይደለም፤ እንግዲህ ከዚህ መሠረተ ሐሳብ ስንነሣ ምልክቶች ለዜማው ትምህርት መስፋፋትና መጠበቅ ያላቸው አስተዋጽኦ በእጅጉ የላቀ መሆኑን ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡

በቅዱስ ያሬድ የተዘጋጁ የዜማ ምልክቶች ለአንድ ሺሕ አራት መቶ አምሣ ዓመታት ያህል ዜማውን በመጠበቅ ሂደት ዓቢይ አስተዋጽኦ አድርገዋል፤ የእነዚህ ምልክቶች አገልግሎት በትምህርቱ ሂደት ጊዜ የጠቋሚነት ሚና በመጫወትና ለዜማው መጠበቅ የጉላ አስተዋጽኦ በማድረግ ብቻ ሳይሆን በአላቸው ምሥጢራዊ ትርጓሜም ነገረ መስቀሉን በማሳሰብ ጭምር አገልግሎት ይሰጣሉ፤ ይህንንም እንደሚከተለው እናያለን፡፡



### 1. በቅዱስ ያሬድ የተዘጋጁ የዜማ ምልክቶች

የምልክቱ ስያሜ፣ ቅርጹ፣ የሚሰጠው አገልግሎትና ትርጓሜ እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

ሀ. የምልክቶች ስያሜ፡-

| ቁጥር | የምልክቱ ቅርጽ | ስም |
|---|---|---|
| 1 | | ድፋት |
| 2 | | ሂደት |
| 3 | | ቅናት |
| 4 | | ይዘት |
| 5 | | ቍርጥ |
| 6 | | ጭረት |
| 7 | | ርክርክ |
| 8 | | ደረት |
| 9 | | ድርስ |
| 10 | | አንብር ናቸው፤ |

ሚስጥረ ሥላሴ

በቅዱስ ያሬድ ጊዜ የነበሩና እርሱ ራሱ ያዘጋጃቸው የዜማ ምልክቶች ከዚህ በላይ ስማቸው፣ ቍጥራቸውና ምልክታቸው የተገለጹት ሲሆኑ በዜማ አጠቃቀም ጊዜ የሚሰጡት ጥቅም ደግሞ የሚከተለው ነው፡፡

ለ. የምልክቶች አጠቃቀም፡-

1. ድፋት፡- ድፋት ማለት ድምጽንና አንገትን ወደታች ርግጥ አድርጎ ወይም ደፍቶ ትንፋሽን ወደ ሆድ ውስጥ በመመለስ ማዜም ማለት ነው፡፡
2. ሂደት፡- ሂደት ማለት እንደ ሜዳ መንገድ፣ እንደ ቦይ ውሀ ወይም ሰተት ብሎ እንደሚሄድ ተጓዥ አንተም ሳታቆም ወይም ሳታቋርጥ ምንም ነገር ሳትይዝ ሰተት ብለህ ሂድ ወይም አዜም ማለት ነው፡፡
3. ቅናት፡- ቅናት ማለት በዜማው ቃል መጨረሻ ያለውን አንዱን የፊደል ሆሄ ይዘህ አንገትን ወደላይ በማቅናትና ድምፅን እንቅ በማድረግ አዜም ማለት ነው፡፡
4. ይዘት፡- ይዘት ማለት በዜማ አጠቃቀም ጊዜ በፍጥነት ከሚዜመው ዘር አንዱን የፊደል ሆሄ ያዝ በማድረግ አዜም ማለት ነው፡፡
5. ቍርጥ፡- ቍርጥ ማለት ዜማውን በምታዜምበት ጊዜ ድምፅን በመጠነ በመቀነስ፣ ትንፋሽን ወደታች በማመቅና እንደገናም ድምፅን በማጋነንና አገጭን ወደፊት ገፋ በማድረግ አዜም ማለት ነው
6. ጭረት፡- ጭረት ማለት በዘር መካከል ያለውን አንዱን የፊደል ሆሄ ወደጐን ጫር በማድረግ አዜም ማለት ነው፡፡
7. ርክርክ፡- ርክርክ ማለት ረጅም የሆነውን ዜማ በላዩ ላይ ርክርክን በመጨመር በረጅሙ አዜም

www.ethiopianorthodox.org

8. ደረት፡- ደረት ማለት ደረትን ከፍ በማድረግና አንዱን የፊደል ሆሄ ወደላይ ቁንጠጥ በማድረግ ማዜም ማለት ነው፡፡
9. ድርስ፡- ድርስ ማለት የቃል መጨረሻ የሆነውን አንዱን የፊደል ሆሄ ያዝ በማድረግና ድምፅን ወደ ኋላ በመሳብ ዜማውን እስከ መድረሻው ማዜም ማለት ነው፡፡
10. አንብር፡- አንብር ማለት የአንዱን ዘር የመጨረሻ ሆሄ ያለምንም ተጨማሪ ድምጽና ርክርክ በማስቀመጥ ወይም በማቆም አዜም ማለት ነው፡፡ እንግዲህ በዜማ አጠቃቀም ጊዜ ምልክቶች የሚሰጡት አገልግሎት ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሲሆን ምሥጢራዊ ትርጓሜአቸው ደግሞ የሚከተለው ነው፡፡

## ሐ. የምልክቶች ትርጓሜ፡-

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙ መንፈሳዊ አገልግሎቶች በአጠቃላይ ምሥጢራዊ ይዘታቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከክርስቶስ ነገረ መስቀል ጋር ያተያያዙ ናቸው፤ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የተመሠረተው በክርስቶስ መሥዋዕትነት እንደመሆኑ መጠን በውስጧ የሚካሄደው ማንኛውም ዓይነት መንፈሳዊ አገልግሎት በክርስቶስ ነገረ መስቀል ዙርያ የሚያጠነጥን ነው፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ነገረ መስቀል የማይገልጽ ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት አትቀበለውም፤ በመሆኑም እነዚህ የዜማ ምልክቶች በቅርጻቸውም ሆነ በስያሜያቸው የሚናገሩት ቢኖር የክርስቶስን ሕማማተ መስቀል ነው፤ በዚህም መሠረት ምሥጢራዊ ትርጓሜአቸው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

1. ድፋት፡- ድፋት በቅርጹ ስንመለከተው በላዩና በሁለት ጐኖቹ ዝግ ሆኖ በታቹ በኩል ክፍት የሆነ ጐንበስ ብሎ ወደታች የሚመለከትን ነገር ይመስላል በምሥጢራዊ ትርጓሜውም ከላይ ወደ ታች መውረድን ያመለክታል፤ ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ወደዚህ ዓለም መምጣቱንና ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡
2. ሃይት፡- ሃይት በቅርጹ ሲታይ ረዘም ያለና ወደጐን የተሠመረ መሥመር ሆኖ በስተግራ በኩል በላዩ ላይ ጀልባ መሰል ቅርጽ አለው፤ ወይም በባህር ላይ ለመጓዝ የሚንቀሳቀስን ጀልባ ይመስላል፤ ይህም የሚያሳየው መሄድን፣ መጓዝን፣ መራመድን ስለሆነ በምሥጢራዊ ይዘቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረና በባህርና በየብስ እየተመላለሰ ማስተማሩን፣ እንዲሁም አይሁድ አንድ ጊዜ ወደ ቀያፋ አንድ ጊዜ ወደ ሐና አንድ ጊዜ ወደ ጲላጦስ አንድ ጊዜ ወደ ሄሮድስ እየወሰዱ እንዲንገላታ ማድረጋቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡
3. ቅናት፡- ቅናት በቅርጽነቱ ቀጥ ያላለና ከቀኝ ወደግራ የተሠመረ ወልጋዳ መስመር ይመስላል፤ ይህም ቅን ያልሆነን ጠማማ ነገር የሚያመለክት ሆኖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአምላክነቱ በሽተኞችን መፈወሱ፣ ለምጻሞችን ማንጻቱ፣ ዕውራንን ማብራቱ፣ ሙታንን ማስነሣቱና ጐባጣና ለንክላ የሆኑትን ማቅናቱ ያስቀናቸው ካህናተ አይሁድ ጠማማ በሆነ አእምሮአቸው ተመቅኝተው እንዲሰቀል ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው፡፡
4. ይዘት፡- ይዘት በቅርጹ ስንመለከተው ምንም ተጨማሪ የሌለው አንድ ነጥብ ነው፤ ይህም ብዙ ተጨማሪ ነገር የሌለውንና አንድ ብቻ የሆነን ነገር የሚያመለክት ሲሆን ከጽድቅ በቀር ሌላ ኃጢአትና በደል ወይም ጥፋት የሌለበትንና አኃዜ ዓለም የሆነውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ ይዘው ለሞት መዳረጋቸውን የሚገልጽ ነው፡፡
5. ቀርጥ፡- ቀርጥ በቅርጹ ሲታይ ከላይ ወደታች ቀጥ ያለ መስመር ሆኖ በቀኝ ጐኑ በኩል ትንሽ ተቀጥላ ያለው ነው፤ ቅርጹ በአጠቃላይ የመጥረቢያ ዓይነት ቅርጽ አለው፤ ይህም አንድን ነገር ለመቀረጥ የተዘጋጀ መሣርያን ያመለክታል፤ በምሥጢሩም "እነሆ ምሣር በዛፎች ላይ ነው" ሉቃስ 3፣9 ተብሎ እንደተገለጸው ጌታ ንሥሐ በማይገቡ ኃጢአተኞች ላይ እውነተኛና ቀጥተኛ ፍርድ የሚፈርድ መሆኑን ያሳያል፤ ወይም ሣፍ ከግንዱ በምሣር ተቁርጦ እንደሚለይ አይሁድም ጌታችንን በመከራ መስቀል ነፍሱን ከሥጋው መለየታቸውን / መግደላቸውን/ ያሳያል፤ በሌላም በኩል እርሱ በፈቃዱ ራሱን ለመከራ አሳልፎ በመስጠት ነፍሱን ከሥጋው ለመለየት ቀርጥ ውሳኔ ማድረጉን ያመለክታል፡፡





6. ጭረት፡- ጭረት በቅርጽ ሲመለከቱት ከግራ ወደቀኝ ከዚያም እንደገና ወደግራ የተጣመመና ጐባጣ መሰል ነገር ሆኖ ይታያል፤ ይኸውም ራሰ ጐባጣ ወይም ራሰ ጠማማ የሆነ በትርን ያመለክታል፤ በዚህ ከዘራ መሰል በትር ወይም በትረ ሕሰት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገረፉን ያመለክታል፡፡
7. ርክርክ፡-ርክርክ በቅርጹ ሲታይ የሚንጠባጠቡ ነገሮችን ይመስላል፤ ይኸውም ጌታችን ሲገረፍና ሲሰቀል ከሰውነቱ የተንጠባጠበውን የደም ነጠብጣብና የላብ ነጠብጣብ የሚያመለክት ነው፡፡
8. ደረት፡- ደረት በቅርጹ ሲያዩት በታችና በሁለቱ የቀኝና የግራ ጐኑ የተዘጋ በላይ በኩል ግን ክፍት የሆነ የድፋት ተቃራኒ ቅርጽ ነው፤ ይህ ቅርጽ አንድ ተኝቶ የነበረን ሰው አፈፍ ብሎ ሲነሣ የሚያሳይ ቅርጽ ነው፤ ይኸውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ሞትን ድል አድርጎ በራሱ ሥልጣን ከመቃብር አፈፍ ብሎ በመነሣት ወደሰማየ ሰማያት ማረጉን ወይም መውጣቱን የሚያስረዳ ነው፡፡
9. ድርስ፡- ድርስ የሚባለው ምልክት የቃሉ የመጨረሻውን ፊደል ወይም "ስ" ብሎ በመጻፍ የሚቀመጥ የዜማ ምልክት ነው፤ ይህ የፊደል ሆሄ በቅርጽነቱ ሲታይ ራሱን ወደሰማይ ቀና አድርጎና በሁለት እግሩ በአስተማማኝ ሁኔታ ቀጥ ብሎ የቆመን ሰው ይመስላል፤ ይኸውም የተነገረው ትንቢትና የተቋጠረው ሱባኤ በመድረሱ ተዋርዶ፣ ተስፋ ቋርጦና የሚተማመንበትን ድ?ነት አጥቶ የነበረውን የሰው ልጅ የክርስቶስ መሥዋዕትነት ባስገኘለት ፍጹም ነጻነት ተስፋ ትንሣኤን ማግኘቱንና ደ?ንነቱ በአስተማማኝ ሁኔታ የተረጋገጠ መሆኑን የሚያመለክትነው
10. አንብር፡- አንብር የሚለው የዜማ ምልክት መጨረሻውን የፊደል ሆሄ "ር" ብሎ በማስቀመጥ የሚገለጽ የዜማ ምልክት ሲሆን በቅርጹም ሲታይ ወደ ላይ ወደግራና ወደታች ያለው መሥመር የገጠመ ሆኖ ወደ ቀኝ ያለው ብቻ ክፍት የሆነ ቅርጽ ነው ይኸውም ሁለት ምሥጢራትን የሚገልጽ ቅርጽ ነው፤ እነርሱም፡-
   ሀ. ጌታ የማዳን ሥራውን ሁሉ ጨርሶ ወደሰማይ ካረገ በኋላ በየማነ አብ ወይም በአብ ቀኝ መቀመጡን፣
   ለ. ሰዎች በግራ የተመሰለ ግብረ ኃጢአትን ትተው በቀኝ የተመሰለውን ግብረ ጽድቅ ብቻ በመሥራት ቢኖሩ በዕለተ ምጽአት በቀኙ በኩል እንደሚቀመጡ ያመለክታል፡፡

እንግዲህ የዐሥሩ ትእምርታተ ዜማ ቁጥር፣ ስም፣ አገልግሎትና ምሥጢር ከላይ እንደተገለጸው ሆኖ ምሳሌነታቸው ደግሞ የዐሠርቱ ቃላተ ኦሪት የዐሠርቱ ሕዋሳት ምሳሌ ናቸው፤ እነዚህን የጠበቀ በነፍሱም በሥጋውም እንደሚድን ሁሉ በእነዚህ ትእምርታተ ዜማ ወይም የዜማ ምልክቶች በመጠቀም ፈጣሪውን የሚያመሰግንም ፍጹም ዋጋውን ያገኛል ወይም ድኅነተ ሥጋና ድ?ነተ ነፍስን ያገኛል ማለት ነው፡፡

## 2. የኋላ ሊቃውንት ያወጧቸው የዘር ምልክቶች፣

እነዚህ የዘር ምልክቶች የዜማውን ክብደትና እንደዚሁም ዜማውን ለመወሰን የሚወስደውን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ተማሪው ትምህርቱን በአጭር ጊዜ እንዲወስን ለማድረግ መምህሩ ወይም ደቀመዝሙሩ ጥርጥር ላይ ሲወድቅና ዜማ ሲጠፋው በተመሳሳይ ዜማ እንዲያገኘው አስበው የፈጠሩት ተጨማሪ ዘዴ ነው፤ በዚህም ዘዴ በዜማ ትምህርት አሰጣጥና ጥበቃ ላይ ከፍተኛ የሆነ መሻሻል ታይቶአል፤ ሊቃውንቱ ይህንን ዘዴ ሲጠቀሙ አስቀድመው የዜማ ቃላትን ለምልክትነት በመምረጥ ተመሳሳይ የሆኑትን ሁሉ በአንድ የዘር ምልክት እንዲዜሙ አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ አጥመቀን የመሰለ የዜማ ዘር በሙሉ የአጥመቀ የመጨረሻ ሆሄ (ቀ) የሆነውን በላዩ ላይ በመጻፍ በእርሱ ምልክትነት እንዲዜም አድርገዋል፡፡

. ተ ዊ ር

ለምሳሌ "ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ" "ብነ" የሚለውን የዜማ ቃል እንደ አጥመቀ አድርገህ አዜም ማለት ነው፤ ሊቃውንቱ እንደዚህ የመሳሰሉ የዘር ምልክቶችን በመምረጥ የተጠቀሙባቸውና ዛሬም ድረስ ከቅዱስ ያሬድ የምልክት ዜማዎች ጋር ተሰባጥረው በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ የዋሉ ብዙ የዘር ምልክቶች በእምስቱም የቅዱስ ያሬድ ፀዋትወ ዜማዎች ይገኛሉ፤ የእነዚህ የዘር ምልክቶች ጥቅም እጅግ የላቀ በመሆኑ ሥራ ላይ ከዋሉበት ጊዜ ጀምሮ ለትምህርቱ ጥራትና መጠበቅ አመቺ ሁኔታን ፈጥረዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ አንዳንድ በጣም ከባድና የተለየ አመል ያላቸው ዜማዎች ካልሆኑ በስተቀር አንድ ደቀመዝሙር ዜማውን ሙሉ በሙሉ ባይዘልቀውም የዜማን ጠባይ በደምብ የለየና ምልክቶችን ያወቀ ከሆነ ከመቶ ቢያንስ ስድሳ ያህሉን ምልክቱን እያየ በራሱ ማዜም የሚችል ሆናአል፤ ሲጠፋውም ምልክቱን በማየት ማግኘት ችሎአል፤ ይህም ከፍተኛ የእድገት ለውጥ ነው፤ ይህ ዓይነቱ የዘር ምልክት በምልክትነት መጠቀም የተጀመረው መቼ እንደሆነ በትክክል አልታወቀም፤ ሆኖም ከቅዱስ ያሬድ በኋላ ብዙም ሳይቆይ እንደተጀመረና ካለው ጠቀሜታ አኳያ እየዳበረ መጥቶ በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ሊታወቅ ተችሎአል፡፡

በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ማለትም በ1535 ዓ.ም. ገደማ አዛዥር ጌራና አዛዥር ራጉኤል የተባሉ የተድባበ ማርያም የዜማ ሊቃውንት በዜማ የዘር ምልክት ማቀነባበር ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው ተገልጾአል፤ በዘመኑ የተጻፈው ታሪክ ነገሥት እንዲህ በማለት ያብራራል "ወበመዋዕሊሁ ለንጉሥ ገላውዴዎስ ተንሥኡ አዛዥር ጌራ ወአዛዥር ራጉኤል ካህናት ማእምራነ ዜማ ወወጠኑ አውጽኦ ምልክት ዘድጓ" ይላል ትርጓሜውም በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት አዛዥር ጌራና አዛዥር ራጉኤል የተባሉ የዜማ አዋቂዎች ካህናት የድጓን ምልክት ማዘጋጀት ጀመሩ ማለት ነው፡፡
የዘር ምልክት ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ከመዋሉ ጐን ለጐን እስከ ጎንደር ዘመነ መንግሥት ድረስ በአንዳንድ ባለታሪክ ሰዎች ምክንያት በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የገቡ የአማርኛ የዜማ ምልክቶችም በአሁኑ ጊዜ በምልክትነት እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ እነርሱም እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

## 3. የአማርኛ ምልክቶች፡

እነዚህ ምልክቶች የአማርኛ ቋንቋ እየገነነ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በብዛት ስለገቡ አማርኛ በሚል ቃል ቢጠቃለሉም ከዚያ በፊት በዘመነ አኩስምም እንደነበሩ አንዳንድ ስያሜዎች ያመለክታሉ፤ ለምሳሌ " መገርሐት" በመባል የሚታወቀው ሃሌታ የአጼ ገብረ መስቀል የፈረስ ስም እንደነበረና ሊቃውንቱ ለንጉሠ ነገሥቱ ከነበራቸው ፍቅርና አክብሮት የተነሣ ከሃሌታዎች ውስጥ አንዱን ሃሌታ በንጉሠ ነገሥቱ ፈረስ ስም እንዲጠራ ማድረጋቸውን ይነገራል፡፡ የአማርኛ ቃል ምልክት ሲሆን አንድ ጉልህ ታሪክ ከሠራ ሰው ጋር ወይም አንድ ትዝታ ካለው ገጠመኝ ጋር የተያያዘ ሆኖ ለወደፊት እንዳይረሳ የድጓው ተማሪ በምልክት እያስታወሰው እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡

ለምሳሌ የወናግ ሰገድ ጦር አዝማች የነበሩት አዝማች ዮናኤል የቱርክን ጋሻ በታላቅ ጀግንነት ተዋግተውና ራሱን በጉራዴ ቁርጠው በመግደል ድል አድራጊ በሆኑ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ለዚህ ጀግንነትህ ላደርግልህ የምትፈልገውን ጠይቅና እፈጽምልሃለሁ አሏቸው፤ አዝማቹም ስሜ በድጓ ውስጥ ምልክት ሆኖ እንዲገባ ያድርጉልኝ እንዳሏቸውና ንጉሡም ምልክት ሆኖ እንዲጻፍ ማድረጋቸውን ተገልጾአል፤ ይኸውም ምልክት በአጭር አጻጻፍ "የወሎሌ" ተብሎ እንዲገባ ተደርጎአል፤ ቃሉም "የወናግ ሎሌ ዮናኤል ጋሻን ገደለው በሾተል" ማለት ነው፤ በመሆኑም ስማቸውና ጀግንነታቸው በማያልፈው የድጓ ዜማ ውስጥ ለዘላለሙ ሲታወስ ይኖራል፤ እንግዲህ እንዲህ በመሳሰሉውና በሌላ ገጠመኝ የገቡ የአማርኛ ቃላት ምልክቶች እንደ አማራት ጎንደር ተከናንበሽ ኑሪ፣ ወይ አይሸሽ ወይ አይዋጋ፣ የመሳሰሉት በብዛት በምልክትነት ተጽፈው አገልግሎት ሲሰጡ ይገኛሉ፤ ከዚህም ሌላ መምህሩ ተማሪያቸውን በቅርብ በሚታይ ነገር እያሳዩና እያዜሙ የሚያስተምሩበት ጊዜ እንደነበረና ምልክት ሆኖ የሚቀርበት ሁኔታም እንዳለ በሚከተለው እናያለን፡፡

## 4. መምህራን ወይም ተማሪዎች ያወጧቸው ምልክቶች፣

ጥንታውያኑ መምህራን የሚያስተምሩት በዛፍ ሥር ሆነው ሁሉንም ነገር በቅርብ እየተመለከቱ ነው፤ ታዲያ መምህሩ ተማሪው ዜማውን አልይዝላቸው ሲል ተማሪውም አልያዝለት ሲለው በቀላሉ ትዝ እንዲለው በአካባቢው ያለን ነገር በቃላት በማቀነባበርና በዜማ በማዜም ማስታወስ የተለመደ ነገር ነበር፤ በዚህም መነሻነት የድጓ ምልክት ሆነው የገቡ ብዙ ይገኛሉ፤ ለምሳሌ አህያ ትርገጥህ፣ ስንዴ በማዶ ይመስላል በረዶ፣ አየ ጉና ትመስላለች መና፣ ቡበይ ላሜ እየበላሽ ልምላሜ የመሳሰሉት ሁሉ እዚህ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡





## የቅዱስ ያሬድ ዜማ ጉባኤ ቤቶች

በአሁኑ ጊዜ የተለያየ ስም ያላቸው የቅዱስ ያሬድ ዜማ ጉባኤ ቤቶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም የቤተ ልሔም ጉባኤ ቤት፣ የቆማ ፋሲለደስ ጉባኤ ቤት፣ የአጫብር ጉባኤ ቤት፣ የተጉለትና የወንጨሬ ጉባኤ ቤት በመባል ይታወቃሉ፤ እነዚህ ጉባኤ ቤቶች ለምን ስማቸው ተለያየ? የመለያየታቸው ምክንያትስ ምንድን ነው? ለምንስ በዙ? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሡ ይሆናል፤ ይህ ጥያቄ በኋላ የሚመለስ ሆኖ ለመሆኑ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ከእርሱ በኋላ ተከታዮቹ ሊቃውንት ዜማውን ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት ሊያሸጋግሩ ቻሉ የሚለውን የዋና ዋናዎቹን መምህራን ስም በመጥቀስ ለማየት እንሞክራለን፡፡

የቅዱስ ያሬድ ደቀመዛሙርት በአኩስም ጽዮን ቤተ ቀጢን፣ በአባ ገሪማ ገዳም መደራ፣ በሐማሴን ድግሣ ውስጥ፣ በደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ ገዳምና በሸዋ ጎሐ ጽዮን ደብር ውስጥ ጉባኤ በማስፋፋት እንዳስተማሩ፣ ከነሱም በኋላ በታላላቆቹ የመላ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትና አድባራት ጉባኤው ተስፋፍቶ ትምህርት ይሰጥ እንደነበረና አገልግሎቱም በመላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ይካሄድ እንደነበረ ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡

በዚህ ረጅም ጊዜ የነበሩ ብዙ ሊቃውንት መምህራንን አንድ በአንድ ማወቅ ባይቻልም ከዋና ዋናዎቹ አልፎ አልፎ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፤ ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተነሡና በጣም ስመ ጥር የነበሩ መምህራን የሚከተሉት ናቸው፤ ከነዚህም በቀጥታ የቅዱስ ያሬድ ደቀመዛሙርት የነበሩት፡-

ሀ. የአኩስም ጽዮን ቤተ ቀጢን ጉባኤ ቤት መምህር የነበረው ሊቁ እስክንድራ

ለ. የእንዳባ ገሪማ ገዳም መደራ ጉባኤ ቤት መምህር የነበረው ሊቁ ሳዊራ

ሐ. በደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ ገዳም ውስጥ ሆኖ ያስተምር የበረው ሊቁ መንክራና

መ. በሐማሴን ውስጥ ድግሣ በተባለው ታሪካዊ ደብር ያስተምር የነበረው ሊቁ ብስድራ ናቸው፡፡

ሐማሴን ውስጥ ከብስድራ የተማረ ፀሐየ ቅዱሳን የተባለ ሊቅ እንደነበረና የኋላ ኋላ ወደ ሸዋ ጎሐ ጽዮን መጥቶ በማስተማር ዜማውን በሸዋ ውስጥ በስፋት እንዳዳረሰው ታውቆአል፡፡
ከዚህም በኋላ ከታወቁት ሊቃውንት መካከል ከአኩስም ጽዮን መምህር ከእስክንድራ ቤተ ጉባኤ በተዋረድ የተማሩት ፡-

ሀ. ሠንድሮስ
ለ. በልዳዶስ
ሐ. ኬፋ
መ. ገብረ ክርስቶስ
ሠ. አባ ጌራ ይገኙባቸዋል፡፡

የመጨረሻው መምህር አባ ጌራ ከአኩስም ወደ አማራ አገር /ወሎ/ መጥቶ ሐይቅ በተባለው ደሴት አጠገብ በሚገኘውና ደብረ እግዚብሔር ተብሎ በሚጠራው ደብር ውስጥ ጉባኤ ዘርግቶ ብዙ ደቀመዛሙርትን አስተምሮአል፤ ካስተማራቸውም ደቀመዛሙርት አንዱ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ናቸው፤ እርሳቸውም ከጉዲት በኋላ ከተነሡት ሊቃውንት መካከል በጣም እውቅ ነበሩ፤ አባ ጊዮርጊስ አስተምሕሮ በተባለው የድጓ ክፍል ውስጥ ተጠቃሎ የነበረውን የወርኃ ጾም መዝሙር ለብቻው በማውጣት ጾመ ድጓ ተብሎ እንዲለይና ሁሉም እንዲማረው ያደረጉ ናቸው፤ ከዚህም ሌላ ሰዓታት የተባለውን የዜማ ጸሎት የደረሱ እርሳቸው ናቸው፡፡



www.ethiopianorthodox.org

አባ ጊዮርጊስ ልሳነ ፅፍረት የተባለውን ሊቅ አስተማሩ፤ ከዚህ በኋላ በግራኝ መሐመድ ጦርነት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መጻሕፍት ስለተቃጠሉባትና ድጓም በደረሰው ቃጠሎ ስለወደመ በቀላሉ ሊገኝ አልቻለም፤ በኋላ ግን አጼ ሠርፀ ድንግል ድጓ የሚገኝበትን ደብር ሲያፈላልጉ በበጌምድር ውስጥ ጉና ተራራ አጠገብ በምትገኘው በቅድስት ቤተልሔም ደብር የሊቁ ልሳነ ፅፍረት ድጓ ተገኘ፡፡

ከዚህም የተነሣ ንጉሡ ቤተልሔም የድጓ ማስመስከርያ እንድትሆን በመፍቀዳቸው እስከአሁን በዚሁ ትታወቃለች፤ የቅድስት ቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ እጅግ ማራኪና በልዩ ልዩ የሐረግ ቅርጽ ያጌጠች እንደዚሁም እጅግ በሚያስደንቁ ጥርብ ድንጋዮች የተገነባች በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ተመሳሳይ የማይገኝላት ፅዑብ ድንቅ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት፤ ይህች ቤተ ክርስቲያን ቅርፀ ሞላላ ወይም የአራት መዓዝን ሰቀላ ቅርጽ ያላት ስትሆን ግንብዋም ሆነ ጣራዋ በጥርብ ድንጋዮች ተዋቅሮ የተሠራ ነው፤ በውስጧ የሚገኙ እንጨቶችና ብረቶች በልዩ ልዩ ውስብስብ ሐረጎች የተሞሉና የተዋቡ ናቸው፤ ይህ ፅዑብ ድንቅ የሆነውን ቅርስ ለመጠበቅ ዙርያውን የክብ ቅርጽ ያለውና ከጭታ የተሠራ ግንብ ተሠርቶለት ቆርቆሮ ለብሶአል፡፡

የዚህ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አሠራር በአኩስም ከሚገኘው የአጼ ካሌብ ቤተ መንግሥት ሕንጻ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይነት ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ ጥንት በደቡብ ዓረብ ከተሠሩ ሕንጻዎች ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን በመግለጽ ቢያንስ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ የተሠራ ሊሆን እንደሚችል የደብሩን ሕንጻ የመረመሩ የውጭ አዋቂዎች አስተያየታቸውን ጽፈዋል፡፡

የአገሩ ተወላጆች ግን የቤተ ክርስቲያኑ ውስጠኛው ሕንጻ ማለትም የሰቀላ ቅርጽ ያለውና በሐረግ የተዋበውን ባለ አሥራ ሁለት ቤተ መቅደሱን ሕንጻ በቅዱሳን ነገሥታት በአብርሃ ወአጽብሐ የተሠራ መሆኑን ከአባቶቻቸው በትውፊት ያገኙትን ታሪክ በማውሳት ይናገራሉ፤ በክብ ቅርፅ ጥንታዊውን ግብረ ሕንጻ አማክሎ በጭቃ የተሠራውና ጣራው ቀደም ሲል በሣር ዛሬ ደግሞ በቆርቆሮ ተከድኖ የሚገኘውን ግን ቀደም ሲል አጼ ዳዊት ያሠሩት መሆኑንና እሱ ሲያረጅ ደግሞ እንደገና አጼ ዮሐንስ ራብጎይ ከመተማ ጦርነት በፊት ትንሽ ቀደም ብለው አሁን ያለውን የቅኔ ማ?ሌት ሕንጻ ሙሉ በሙሉ ማሳደሳቸውን በእርግጠኝነት ይናገራሉ፡፡

አጼ ዳዊት ይህንን የውጭ ግንብ የሠሩበት ምክንያት ይህ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ሕንጻ ለመጠበቅ ብለው እንደሆነ ነዋሪዎቹ ያስረዳሉ፤ ነገሩም ተቀባይነት ያለው ነው፡፡
ወደ ዋናው ነገራችን ስንመለስ ቤተ ልሔም የድጓ ምስክር ሆና ማስተማር ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ከነበሩት መምህራን በጣም የታወቁት የሚከተሉት ናቸው፤ እነርሱም፡-

1. መምህር ልሳነ ፅፍረት
2. መምህር ዘቃለ አብ
3. እጨጌ ቃለ ዓዋዲ
4. መምህር ተጠምቀ መድኀን
5. መምህር ሕንጸ ሃይማኖት
6. መምህር ወልደ መስኮት
7. መምህር ሠርፀ ማርያም
8. መምህር ክንፈ ሚካኤል
9. መምህር ገብረ እግዚአብሔር
10. አለቃ መርሻ
11. አለቃ አምሳሉ
12. ሊቀ ምሁራን ጥበቡ
13. ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገላውና
14. አሁን በማስተማር ላይ የሚገኙ ሊቀ ምሁራን ---------- ናቸው፡፡

የቤተ ልሔም ጉባኤ ቤት በዚህ ሁኔታ ምስክር ቤት በሚሆንበት ጊዜ የተለያዩ ጉባኤ ቤቶች በአኩስም፤ በደብረ ሊባኖስ፤ በበጌምድርና በጎጃም እንዲሁም በዋድላ ነበሩ፤ እነዚህ ጉባኤ ቤቶች በያሉበት ማስተማራቸውን ስለቀጠሉ ከጊዜ በኋላ መጠነኛ የሆነ የዜማ ልዩነት ፈጠሩ፤ በየራሳቸው ጉባኤ ቤት ስም





ሀ. በመምህራኑ የዜማ አጠቃቀም ማለትም አስረዝሞና አሳጥሮ በማዜም
ለ. የተፈጥሮ ድምጽ በሚያስከትለው መጠነኛ ልዩነት
ሐ. በቦታ መራራቅ ምክንያት የመምህራኑ አለመገናኘትና አለመወያየት የፈጠረው ክፍተት ወዘተ ለዜማው መጠነኛ ልዩነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፤ በመሆኑም አንዱን ከአንዱ ለመለየት በየቦታቸው ስም መጠራት ስለጀመሩ ዛሬ የተለያዩ ጉባኤ ቤቶች ሊኖሩ ችለዋል፤ እነዚህም ጉባኤ ቤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. የቤተ ልሔም ጉባኤ ቤት
ለ. የቆማ ፋሲለደስ ጉባኤ ቤት
ሐ. የአጫብር ጉባኤ ቤት

ካሉት መካከል የሚጠቀሱት ናቸው፤ ከነዚህም መካከል በአሁኑ ጊዜ በጣም ጎልቶ የሚገኘው የቤተ ልሔሙ ጉባኤ ቤት ነው፡፡

እንደዚሁም አጫብርና ቆማ የቤተ ልሔም ያህል ስፋት ያለው ጉባኤ ቤት ባይኖራቸውም በአካባቢያቸው በመጠኑም ቢሆን እያስተማሩ በማስመረቅ ያሉ ጉባኤ ቤቶች ናቸው፡፡

ከነዚህ ሌላ በትግራይ አኩስም ውስጥ አኩስሜ፤ በሸዋ በደብረ ሊባኖስና በአንኮበር ይካሄዱ የነበሩ ወንጨሬና ተጉለቴ፤ በሰሜን ወሎ ዋድላ ውስጥ ዋድሌ ተብለው የሚታወቁ ጉባኤ ቤቶች ነበሩ፤ ሆኖም ዛሬ የጥንቱን ዜማቸውን ትተው የቤተ ልሔም ዜማ የሚጠቀሙ ሆኗል፡፡

እነዚህ ጉባኤ ቤቶች ስማቸውና ቦታቸው የተለያየ ቢሆንም የዜማቸው ድምፀ ቃና አኩስሜውና ዋድሌው ከቆማ ፋሲለደስ፤ ተጉለቴውና ወንጨሬውም ከአጫብሩ ልዩነት አልነበራቸውም ይባላል፤ ከዚህም ጋር ቆሜና አጫብር በዜማ ተቀራራቢ ናቸው፤ ስለሆነም ጉባኤ ቤቱ ቢታጠፍም የዜማው ወዝ ግን አሁንም በቆሜና በአጫብሬ የዜማ ትምህርቱ እየተሰጠ ስለሆነ አልጠፉም ማለት ይቻላል፤ ፊት በምስክርነት የነበሩ የጉባኤ ቤት ቦታዎች፡-

ሀ. አኩስሜ የተባለው በአኩስም ጽዮን ውስጥ፤
ለ. ተጉለቴና ወንጨሬ የተባለው በደብረ ሊባኖስ ውስጥ፤
ሐ. ዋድሌ የሚባለው ዋድላ ውስጥ ይሰጡ የነበሩ ናቸው፤ አሁን በመጠኑም ቢሆን በማስተማር ላይ ያሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ቆሜ የተባለው በጌምድር ውስጥ በሚገኘውና ቆማ ፋሲለደስ በተባለው ደብር ውስጥ ዛሬም ይሰጣል፤
ለ. የአጫብር ዜማ የተባለው ምሥራቅ ጎጃም ውስጥ መርጡለ ማርያም አጠገብ በምትገኝ አጫብር ኪዳነ ምሕረት ገዳም ውስጥ ይሰጣል፡፡

ከድጓ ሌላ የዝማሬ መዋሥእት ምስክር ጉባኤ ቤት በዙር አባ ጽርሐ አርያም አቡነ አረጋዊ ገዳም ይሰጣል፤ በዚህ ጉባኤ ቤት ከቅዱስ ያሬድ ጀምሮ እስካሁን የነበሩት የዝማሬ መዋሥእት መምህራን ዝርዝር የሚከተለው ነው፡፡

| የመምህሩ ስም | የተማሪው ስም |
|---|---|
| 1. ቅዱስ ያሬድ | በኪሞስን |
| 2. መምህር በኪሞስ | ጴጥሮስን |
| 3. " ጴጥሮስ | ማቴዎስን |
| 4. " ማቴዎስ | ዘካርያስን |
| 5. " ዘካርያስ | ዮስጦስን |
| 6. " ዮስጦስ | አብርሃምን |
| 7. " አብርሃም | ፊላታዎስን |
| 8. " ፊላታዎስ | ናትናኤልን |

www.ethiopianorthodox.org

| የመምህሩ ስም | የተማሪው ስም |
|---|---|
| 9. " ናትናኤል | ጢሞቴዎስን |
| 10. " ጢሞቴዎስ | አትናቴዎስን |
| 11. " አትናቴዎስ | ቴዎድሮስን |
| 12. " ቴዎድሮስ | ዲዮስቆሮስን |
| 13. " ዲዮስቆሮስ | በኪሞስን |
| 14. " በኪሞስ | መርሐ ክርስቶስን |
| 15. " መርሐ ክርስቶስ | ዕንባቆምን |
| 16. " ዕንባቆም | ዳንኤልን |
| 17. " ዳንኤል | ሰፋኔ ክርስቶስን |
| 18. " ሰፋኔ ክርስቶስ | ሕዝቅኤልን |
| 19. " ሕዝቅኤል | ዘክርስቶስን |
| 20. " ዘክርስቶስ | ወልደ ያሬድን |
| 21. " ወልደ ያሬድ | ስብሐት ለአብን |
| 22. " ስብሐት ለአብ | ዘትረ ወንጌልን |
| 23. " ዘትረ ወንጌል | ወልደ ሐዋርያትን |
| 24. " ወልደ ሐዋርያት | ኢሳይያስን |
| 25. " ኢሳይያስ | ገብረ አልፋን |
| 26. " ገብረ አልፋ | ሰብለ ወንጌልን |
| 27. " ሰብለ ወንጌል | እለእስክንድሮስን |
| 28. " እለእስክንድሮስ | ዕዝራን |
| 29. " ዕዝራ | ተክለ ወልድን |
| 30. " ተክለ ወልድ | ተክለ ሐዋርያትን |
| 31. " ተክለ ሐዋርያት | ሥንየን |
| 32. " ጌታየ ሥንየ | ዘዮሐንስን |
| 33. " ዘዮሐንስ | ገብረ ሕይወትን |
| 34. " ገብረ ሕይወት | ሄኖክን |
| 35. " ሄኖክ | ወልደ ሚካኤልን |
| 36. " ወልደ ሚካኤል | ወልደ ጊዮርጊስን |
| 37. " ወልደ ጊዮርጊስ | ቢሰጠውን |
| 38. " ቢሰጠው | ኮከብን |
| 39. " ኮከብ | ቀለመ ወርቅን |
| 40. " ቀለመ ወርቅ | መርዓዊን |
| 41. " መርዓዊ | ቀፀላን |
| 42. " ቀፀላ | መራሒን |
| 43. " መራሒ | ማኅፀንቱን |
| 44. " ማኅፀንቱ | ጓንጉልን |

45. መምህር ጓንጉል በአሁኑ ጊዜ በዙር አባ ጽርሐ አርያም ገዳም ዝማሬ መዋሥእትን በማስተማርና ምስክርነት በመስጠት የሚገኙ ሲሆኑ ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃገና ሌሎች ብዙ መምህራንን ያስተማሩ ናቸው፡፡

ከድጓና ከዝማሬ መዋሥእት ቀጥሎ ያለው ሌላ ጉባኤ ቤት የቅዳሴ ምስክር ጉባኤ ቤት ነው፤ የቅዳሴ ዜማ ትምህርት ቀደም ሲል በዙር አባ ጽርሐ አርያም አቡነ አረጋዊ ገዳም ይካሄድ ነበረ፤ ኋላም ሰሜን ወሎ ውስጥ ሰለልኩላ በተባለው ደብር ትምህርቱ ይሰጥ ነበረ፤ ዛሬ ግን በሰሜን ምዕራብ ትግራይ ውስጥ ሽሬ አካባቢ በደብር ዓባይ አቡነ ሳሙኤል ገዳም በስፋት ትምህርቱ ይካሄዳል፤ ምስክርነቱም ይሰጣል፤ ሆኖም ሰለልኩላ ውስጥም የደብር ዓባይ ያህል ባይሆንም ጉባኤ ቤቱ አለ፤ ትምህርቱም ይሰጣል፤ ቅዳሴውም እንደ ድጓ ቤቱ የሰለልኩላውና የደብር ዓባዩ መጠነኛ የሆነ የዜማ ልዩነት አለው፤ የሰለልኩላው ብቻ ሳይሆን ራሱ የደብር ዓባዩም ሁለት ወገን የሆነ ጉባኤ ቤት አለው፤ ሁለቱም በጣዕመ ዜማ መጠነኛ ልዩነት አላቸው፤ በአሁኑ ጊዜ ተወዳጅነት ያለውና በብዙ ቦታ አገልግሎት እየሰጠ ያለው የደብር ዓባይ የቅዳሴ ዜማ ነው፡፡



## የቅዱስ ያሬድ ማኅሌት በአቋቋም

### 1. የጎንደር አቋቋም አመጣጥ

በዚህ ክፍል በስፋት የምናየው በመቋምያ፣ በክበሮ፣ በጸናጽል፣ በሽብሸባ፣ በጭብጨባና በዕልልታ እየታጀበ በደማቅ ሁኔታ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት የቅዱስ ያሬድ ዜማ ክፍል ነው፤ አቋቋም የራሱ የሆነ የተለየ ዘር ያለው አይደለም ዘሩም ሆነ ዜማው ከአምስቱ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች ሆኖ ከሌሎች ሊቃውንት ድርሰቶች /መልክዓት/ ጋር በማቀነባበር ለክበሮውና ለጸናጽሉ በሚስማማ አኳኋን በረጅሙ የሚዜም ዜማ ነው፤ የዚህ ዜማ መሪው ቁም ዜማ ነው፤ ማለትም ከቁም ዜማው ምልክትና ላህይ ሳይወጣ በእሱ ብቻ እየተመራ የሚሄድና እሱን ተከትሎ የሚባል ነው፤ በመሆኑም ያለ ክበሮ በዜማ ብቻ የሚባለው ቁም ዜማ ሲባል በክበሮ የሚባለው ደግሞ ማኅሌት ይባላል፤ ይኸውም ማኅሌት ከክበሮ ጋር ተቀናጅቶ የሚባል መሆኑን ይታወቅ ዘንድ "ኃለየት ማኅሌተ እኅተ ሙሴ በክበሮ" ሲል ይገኛል፤ ይህም ማለት የሙሴ እኅት ማርያም በክበሮ እየዘመረች ፈጣሪዋን አመስገነች ማለት ነው፤ ዘጸ 15፣20

ቅዱስ ያሬድ ቁም ዜማውን ከመላእክት እንደሰማ ሁሉ አሁን እየተጠቀምንበት የሚገኘው ማኅሌትንም ከእነሱ ሰምቶ የጀመረው እርሱ ነው፤ ስለሆነም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማኅሌቱና ቁም ዜማው ሳይለያዩ ሁለቱንም በአንድነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስትገለገልባቸው ኖራለች፤ ይሁንና ማኅሌቱ መሠረቱን ሳይለቅ ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለና አባባሉም እየሰፋ መጥቷል፤ ከዚህም የተነሣ ማኅሌት የሚለውን ስያሜ አቋቋም በሚል ስም እስከመተካት ደርሶአል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ትክክለኛ ስሙ ማኅሌት እንጂ አቋቋም አይደለም፤ ምክንያቱም ማኅሌት በመጽሐፍ የሚገኝና መላእክት የሚያመሰግኑበት ዜማ ሲሆን አቋቋም የሚለው ስም ግን በመጽሐፍ የሌለና በኋላ የወጣ ስም ነው፤ ስሙ ሲወጣ የቻለውም ማኅሌት የሚለውን ስም ለመተካት ሳይሆን የማኅሌቱን አባባል ለመግለጽ ነው፤ ቃሉም የሚገልፀው ይህንኑ አባባል ነው፤ በአጠቃላይ ማኅሌት የሚለውንና አቋቋም የሚለውን ስም ለይቶ ለማስቀመጥ ካስፈለገ ማኅሌት የሚባለው በክበሮና በጸናጽል እየታጀበ የሚዘመረው ልዩና ረጅም ጣዕመ ዜማ ሲሆን አቋቋም ደግሞ የዚሁ ማኅሌት አባባል ወይም አቋቋም እንዴት መከናወን እንዳለበት የሚገልጽ ሥርዓተ ቁመት ነው፤ ስሙም የወጣ የማ?ሌቱ አባባል በተቀነባበረበት በጎንደር ዘመነ መንግሥት እንደሆነና የማኅሌቱን የአባባል ቅንብር ለመግለጽ የወጣ ስም እንደሆነ ብዙዎች ይገምታሉ፤ የሆነ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ አቋቋም እየተባለ የሚጠራው ትምህርት ብዙ ክፍል ያለው ሆኖ ይገኛል፤ ማኅሌት ከግራኝ በፊት በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በስፋት አገልግሎት እየሰጠ ከቆየ በኋላ በተለይም አገልግሎቱንና እውቀቱን ይዘው የቆዩት አብያተ ክርስቲያናት በግራኝ መሐመድ ሙሉ በሙሉ ሲቃጠሉና መምህራኑም ሲገደሉ የተወሰኑ መምህራን ወደ ጣና ሐይቅ ደሴቶች በመግባት ትምህርቱን ለማቆየት ችለዋል፤ ከነዚህም መካከል ደብረ ሐዘሎ ተጠቃሽ ነው፤ በዚህ ገዳም ይኖሩ የነበሩ የአባ አንበስ ረድእ አባ መዝሙረ ቅዱሳን ለአቋቋም ትምህርት መስፋፋት አስተዋጽኦ ያደረጉ ምሁር ናቸው፤ እሳቸው የአንክበሩን ሊቅ መምህር ኤስድሮስን አስተማሩ፤ ኤስድሮስ በግራኝ ወረራ ዘመን ከሸዋ ወደ በጌምድር ተሰደው በጣና ቂርቆስ ገዳም አቋቋምን አስተማሩ፤ በመቀጠልም ወደ ጎንደር በመሄድ በጎንደሮች ጊዮርጊስ ደብር ሆነው አሞንዮስንና ድሜጥሮስን አስተማሩ፤ ድሜጥሮስ በጎንደር ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ሆነው መብረቅና ነጐድጓድ የተባሉትን ሊቃውንት አስተማሩ፤ አሞንዮስም መ/ር ተስፋ ማርያምን፣ መምህር ተስፋ ማርያም መምህር ገ/ማርያምን፣ መምህር ገብረ ማርያም መምህር መድምምን፣ መምህር መድምም አለቃ ገብረ ሐናን አስተማሩ፤ አለቃ ገብረ ሐና ከበኣታ ሊቃውንት ከነመምህር ሉዜ ገብሩ፣ ከነ መሪጌታ ኃሤትና ከመሪጌታ ገብረ ማርያም ጋር በመሆን የአቋቋምን ባህል መሠረት ያስያዙ ናቸው፡፡

እንደዚሁም የደብረ መድኃኒት ዓቢየ እግዚእ መምህራን የነበሩት መምህር አሜር እሸቱና መምህር መዝሙር ካሣ፣ የአባ ጃሌው ተክለ ሃይማኖት አለቃ የነበሩት መ/ር እልፍነህ ለአቋቋም ባህል መስፋፋት አስተዋጽኦ አድርገዋል፤ መምህር አሜር እሸቱ የላይ ቤት አቋቋምን ያስፋፉ መምህር ገብረ ዮሐንስን አስተማሩ፤ ከበኣታው መምህራንም መምህር ላቀውና መምህር ማህሰ ወልደ ተክሌ ተተኩ፤ እነዚህ ሦስቱ መምህራን ጎንደር በድርቡሽ ስትወረርና በዘመነ ዓፀባ የነበሩ ናቸው፤ በመሆኑም በጎንደር ላይ በደረሰው ጥፋት ብዙ ሊቃውንት ሲያልቁ እነዚህ ከመከራው ተርፈው የአቋቋም ትምህርት እንዳይጠፋ ወንበር ዘርግተው በማስተማር ባህሉ እንዳይጠፋ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ናቸው፤ መምህር ላቀው መምህር

www.ethiopianorthodox.org

ፈለቀን፣ መምህር ፈለቀ መምህር ክፍሌ ወልደ ጻድቅን፣ መምህር ክፍሌ ወልደ ጻድቅ መጋቤ አእላፍ ሄኖክ ወልደ ሚካኤልንና መምህር ሐረገ ወይን ገብረ ማርያምን፣ መጋቤ አእላፍ ሄኖክ ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃን፣ በአሁኑ ሰዓት የጎንደር ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በኣታ አቋቋም ምስክር ጉባኤ ቤት መምህር ሆነው በማስተማር የሚገኙት መጋቤ አእላፍ ክቡርንና ሌሎችን አስተማሩ።

በአሁኑ ጊዜ የጎንደር አቋቋም በዐራት መደብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል እነርሱም፡-

ሀ/ የታች ቤት አቋቋም
ለ/ የላይ ቤት አቋቋም
ሐ/ የሳንኒ ቤት አቋቋም
መ/ የእርቅ ቤት አቋቋም ናቸው።

ከነዚህም ውስጥ የታች ቤቱ አቋቋም ብቻ በትምህርት የሚሰጥና ወንበር ያለው ሲሆን ሌሎቹ በመጠየቅና በማዳመጥ ብቻ የሚታወቁ እንጂ ወንበር የላቸውም በትምህርትም አይሰጡም።

## የበዓላት ሥርዓተ ማኅሌት አመዳደብ

### 1. የክብረ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት፡-

ይህ ሥርዓተ ማኅሌት በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል እነርሱም፡-

ሀ/ ሥርዓተ ዋዜማ
ለ/ ሥርዓተ መልክዕ
ሐ/ ሥርዓተ አርያም ወይም ሥርዓተ ዓቢይ ስብሐ ነግህ ናቸው።

### 2. የእሑድ ሥርዓተ ማኅሌት፡-

የእሑድ ሥርዓተ ማኅሌት በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ/ ክብረ በዓልነት ያላቸው እሑዶች ከሆኑ፡-

- ሥርዓተ ዋዜማ
- ሥርዓተ መልክዕ
- ሥርዓተ መወድስ ይቆምባቸዋል።

ለ/ ክብረ በዓልነት የሌላቸው ሆነው ከወርኃ በዓል ተደርበው ከዋሉ ፡-

- ሥርዓተ መልክዕ
- ሥርዓተ መወድስ ይቆምባቸዋል።

ሐ/ ተራ እሑድ ከሆነ ደግሞ ሥርዓተ መወድስ ብቻ ይቆምበታል።

### 3. የወርኃ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት

የወርኃ በዓል ሥርዓተ ማኅሌት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ/ ሥርዓተ መልክዕ
ለ/ ሥርዓተ አርያም ወይም ሥርዓተ ዓቢይ ስብሐተ ነግህ

ከዚህ ሌላ ያለከበሮ የሚቆሙ የዘወትር ስብሐተ ነግህ፣ የዓቢይ ጾም ጾመ ድጓና ዐሥሩ ምህላት አሉ፤ እነዚህ ሁሉ ከጥንት ጀምሮ አገልግሎት የሚፈጸምባቸው ሥርዓቶች ናቸው።





### 2. የተክሌ አቋቋም አመጣጥ

ይህ አቋቋም የተሰየመው የአለቃ ገብረ ሐና ልጅ በነበረው በአለቃ ተክሌ ስም ነው፤ የተሰየመበትም ምክንያት አቋቋሙን ያስፋፉትና መሠረት ያስያዙት አለቃ ገብረ ሐና ለልጃቸው ለአለቃ ተክሌ ስላስተማሩትና እርሱም ይህንን አቋቋም ከእርሳቸው በኋላ በደብረ ታቦር ኢየሱስ ደብር ወንበር ዘርግቶ በስፋት በማስተማር ብዙ መምህራንን ያፈራ በመሆኑ ስሙ በእርሱ ስም ተሰይሞአል።

ይህ አቋቋም ከአለቃ ገብረ ሐና በፊት የጎንደሮች ጊዮርጊስ የቤት ባህል ነበረ፤ በተለይም በዝማሜነቱ በጣም ተወዳጅና የሚመስጥ ስለነበረ አለቃ ገብረ ሐና ከደብሩ በመገኘት ብዙ ጊዜ ካዳመጡ በኋላ የራሳቸውን ማስተካከያ አክለውበት በተለይም ዝማሜውን ልዩ ጣዕምና እንቅስቃሴ እንዲሁም ልዩ የዘንግ ውዝዋዜ እንዲኖረው በማድረግ አሳምረው አዘጋጅተውታል፤ ይህንን አቋቋም ያዘጋጁበት ቦታም በጎንደር ከተማ ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በኣታ አካባቢ ከቤተልሔሙ በስተሰሜን ምሥራቅ አጠገብ በነበረው ቤታቸው ሆነው ነበር፤ በዚህ ቤታቸው አጠገብ የሸምበቆ ተክል በብዛት ስለነበረ ነፋስ ሸምበቆውን ሲወዘውዘው እያዩ፣ ከዘንጋቸው ጋር አዋሕደው ውዝዋዜውን አዘጋጅተውታል፤ አለቃ ገብረ ሐና ዝግጅታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የደከሙበትን ሙያ በሥውር ለልጃቸው ለአለቃ ተክሌ በዚያው ቦታ አስተማሩ፤ ልጃቸው አለቃ ተክሌም ወደ ደብረ ታቦር ሄዱና በዚያው ወንበር ዘርግተው ማስተማር ቀጠሉ፤ ብዙ መምህራንም አስተማሩ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የደብረ ታቦር ኢየሱስ ደብር እስካሁን ድረስ የተክሌ አቋቋም ጉባኤ ምስክር ሆኖ ያገለግላል።

የተክሌ አቋቋም መምህራን ሐረግ አወራረድ፡-

| የመምህሩ ስም | የተማሪው ስም |
|---|---|
| አለቃ ገብረ ሐና | ተክሌ ገብረ ሐናን |
| አለቃ ተክሌ | መኮንንንና ሌሎችን |
| አለቃ መኮንን | ቀለመወርቅንና ሌሎችን |
| አለቃ ቀለመ ወርቅ | ማኅተምን |
| አለቃ ማኅተም | መርሻን |

ርእሰ መምህራን መርሻ በአሁኑ ጊዜ በደብረ ታቦር ኢየሱስ እያስተማሩ የሚገኙ ናቸው።

## የሥርዓተ ማኅሌት አፈጻጸምና ትርጉማዊ ገጽታው

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅሌት በሚቆምበት ጊዜ የሚያስፈልጉ ንዋያት አሉ፤ እነዚህ ንዋያት የየራሳቸው የሆነ ትርጉምና ምሳሌ ያላቸው ናቸው፤ አንድ ማኅሌታይ ካህን ደብተራ በመጀመርያ አሟልቶ መገኘት ያለበት የሚከተሉትን ነው።

### 1. ልብስ

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ቀኖና በቤተ ክርስቲያን የሚለበሰው ልብስና አለባበሱ ከሌላው አለባበስ የተለየ ነው፤ ይኸውም ልብሱ ንጹሕ መሆን አለበት፤ በቀለምም ነጭ መሆን አለበት ራእ7፣9-15፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንኛውም ሰው ነጭ ጋቢ መደረብ አለበት፤ አለባበሱም በተመለከተ ጋቢውን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ትከሻ በማስተላለፍ ትእምርተ መስቀልን መሥራት

www.ethiopianorthodox.org

አለበት፤ ወንድ ከሆነ ከአንገት እስከ ተረከዝ፤ ሴት ከሆነች ደግሞ ራስዋን ከናንባ እስከ እግር ተረከዝ መልበስ ይጠበቅባቸዋል 1ቆሮ 11፣4-17፤ ይህ ሥርዓት ምእመናንን ሁሉ የሚመለከት ነው፤ ማ?ሌታውያን ካህናተ ደብተራና ስዩማን ቀሳውስት ደግሞ ከላይ የተጠቀሰውን አለባበስ እንዳለ ሆኖ በራሳቸው ላይ ነጭ የሆነ መጠምጠምያ ይጠመጥማሉ፤ ረዘም ያለ ቀሚስና ጥቁር ካባም ይለብሳሉ፤ ዓመት በዓል ሲሆን ደግሞ በጋቢ ፈንታ ጥንግ ድርብ ሊለብሱ ይችላሉ ዘሌ:8፣7-9፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ የአለባበስ ሥርዓት ተሟልቶ ሊገኝ ይገባል፡፡

## 2. ንዋያተ ማኅሌት

የማኅሌት መሣርያዎች የሚከተሉት ናቸው፤ እነርሱም ፡-

### ሀ. ከበሮ፡-

ከበሮ ማለት ከብረወ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሆኖ ትርጓሜው መታ፣ ጐሰመ ማለት ነው፤ ቃሉ ከዚህ ግሥ የወጣ ዘር ሆኖ ምሥጢሩ እግዚአብሔር በምስጋና የሚከብርበት፣ የሚመሰገንበት፣ ኃይለ መለኮቱና ጽንዐ መንግሥቱ የሚታወጅበት ትእምርተ ክብር የሆነ ንዋይ ማለት ነው፤ በማ?ሌት ጊዜ ይህ መሣርያ ተሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

### ለ. ጸናጽል፡-

ጸናጽል ጸንአለ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ሆኖ ፍቹ አቃጨለ ማለት ነው፤ ቃሉ የዚህ ግሥ ዘር ሆኖ ምሥጢሩ አምላካችን ሆይ ጸሎታችንን ስማ ምስጋናችንንም ተቀበል ማለት ነው ይህም በማኅሌት ጊዜ ተሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

### ሐ. መቋምያ፡-

መቋምያ ቆመ ካለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሆኖ ፍቹ ቀጥ ብሎ መቆም ማለት ነው፤ ቃሉ ከዚህ ግሥ የወጣ ሆኖ ምሥጢሩ እግዚአብሔርን ደጅ መጽናትንና የመስቀሉን ኃይል ምርኩዝ ማድረግን ያሳያል፤ ይህም በማ?ሌት ጊዜ ድምፅ የሌለው አስፈላጊ መሣርያ ነው፤ የዚህ መሣርያ አገልግሎት ፡-

1. ለዝማሜ ትርክዛ፣
2. ለምርኩዝነት ወይም ለድጋፍ፣
3. ለአስረጋጭነት ነው፡፡

## ማኅሌትና ውሣጣዊ ይዘቱ

### በማኅሌት ጊዜ የተለያዩ ክፍሎች አሉ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. በመጀመሪያ ቀኖናው በሚያዘው መሠረት ልብሱን በሚገባ ለብሶ፣ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ፣ እግሩን በማስተካከል መቋምያውን ይዞ ቀጥ ብሎ መቆም ነው፤ ከዚህ በኋላ ጸሎት ተደርጎ በሚከተለው አኳኋን የቁመቱ ሂደት ይቀጥላል፤ ቁመቱ በሰባት ዓይነት የተከፈለ ነው፤ ይኸውም ፡-

1. ቁም ዜማ
2. ዝማሜ
3. ቁም
4. መረግድ
5. ጽፋት
6. አመላለስ
7. ወረብ ናቸው፡፡

አባባላቸውና ምሳሌያቸውም እንደሚከተለው እናያለን፡-





### ሀ. ቁም ዜማ ፡-

አንድ ዜማ አዋቂ የሆነ ሰው ድጓውን አንድ ጊዜ በዜማ ይቃኘዋል፤ ከዚህ በኋላ በጎብረት አንድ ጊዜ ይዘለቃል፤ የዚህ ምሳሌ ቀያፋ ሰው ሁሉ ከሚሞት አንዱን ሰው ብንገድል አይሻልምን? በማለት ሐሳብ ሲሰጥ በጉባኤው የነበሩ ሁሉ ትክክል ነው ብለው ጌታ እንዲገደል መስማማታቸውን ያመለክታል ዮሐ11፣49-53፡፡

### ለ. ዝማሜ፡-

ዝማሜ ቁም ዜማው በጎብረት ከተዘለቀ በኋላ የድጓው መጀመርያ ክፍል ይመራል፤ማለትም መሪ እየመራ ተመሪ እየተመራ ይባላል፤ ቀጥሎም ካህናተ ደብተራዎቹ በጎብረት መቋምያውን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ወደፊትና ወደኋላ እየወዘወዙ አልፎ አልፎም መሬቱን እየመቱ የሚባል ነው፤ የዚህ ምሳሌ መሪው የይሁዳ፣ ተመሪው የቀያፋ ምሳሌ ሆኖ ይሁዳ ኢየሱስ ካለበት ቦታ መርቼ እወስዳችኋለሁ ብሎ ለሊቀ ካህናቱ ለቀያፋ መንገሩንና ቀያፋም እሺ ብሎ መስማማቱን ያመለክታል፤ ሉቃ22፣3-6፡፡ ከምራት በኋላ ካህናተ ደብተራ በጎብረት መዝመማቸው ይሁዳ በተናገረው ነገር ተስማምተው ዱላ በመያዝና በመደንገት ጌታ ወደነበረበት ወደ ጌቴ ሴማኒ መሄዳቸውን ያመለክታል ማቴ26፣47፤ የመቋምያውን ውዝዋዜና አመታት ጌታን አንዱ ወደፊት ሌላኛው ወደኋላ አንዱ ወደ ቀኝ ሌላኛው ወደ ግራ እየገፋና እየገፈተሩ በያዙት ዱላም እየደበደቡ ማንገላታታቸውን ያመለክታል፤ የድጓው እናት ዝማሜ ከተዘለቀ በኋላ መሪ እየመራ ተመሪ እየተመራ ምልጣኑ እስከ ጫፉ ድረስ ይመራል፤ ጫፉ ላይ ሁለት ጊዜ በ?ብረት ይዘመማል፤ ቀጥሎ ግራና ቀኝ ይነግል፤ ምልጣኑም ተደጋግሞ ይዘመማል፤ የዚህም ምሳሌ ይሁዳ አይሁድን መርቶ ወስዶ ጌታን ካስያዛቸው በኋላ በየተራ ወደ ሐናና ወደ ቀያፋ ሲያመሳልሱት ማደራቸውን በዚህ ጊዜ ሁለት ሰዎች ሊቃነ ካህናቱን በመደገፍ በጌታ ላይ በሐሰት መመስከራቸውን እንደዚሁም ወታደሮች በየመንገዱ ደጋግመው ማንገላታታቸውን ያመለክታል ዮሐ18፣ 24፤ማቴ:26፣61-68፡፡

### ሐ. ቁም፡-

ይህ ክፍለ ማኅሌት በግራ እጅ መቋምያ በቀኝ እጅ ጸናጽል ተይዞ ቀጥ ብሎ በመቆምና ጸናጽሉን ላይና ታች እየጣሉና ከበሮ እየመቱ የሚባል ነው፤ የዚህም ምሳሌ አይሁድ ሲነጋ ጌታን ይዘው በጲላጦስ ፊት ለፍርድ ማቆማቸውን ይጠቁማል ማቴ27፣11፤ ጸናጽሉ አይሁድ ስቀለው ስቀለው እያሉ በጲላጦስ ፊት ወደላይ እየዘለሉ መንጨጫታቸውን፣ መቋምያው ንጉሥ ነህና በትረ መንግሥት ልትይዝ ይገባሃል እያሉ በትረ ሕሉን በማስያዝ መሳለቃቸውን፣ ድምፀ ከበሮው የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ክብርና መንግሥት ይገባሃል እያሉ አሰምተው በመጮሕ መዘባበታቸውን ያመለክታል ዮሐ19 ፣6፤ ማቴ27፣28-31፡፡

### መ.መረግድ፡-

ከቁም በኋላ ድጓው ፈጠን ባለና ሞቅ ባለ የከበሮ አመታት እየተደረገ፣ እንዲሁም መጠነኛ የሆነ የአካል እንቅስቃሴ ወደ ቀኝና ወደ ግራ እየተደረገ፣ ጸናጽሉም እንደ ከበሮው ፈጠን እያለ የሚባል ነው፤ የዚህም ምሳሌ ጲላጦስ ጌታ እንዲገረፍ በፍጥነት ውሳኔ መስጠቱን፣ ወታደሮቹም ወደ ቀኝና ወደ ግራ እየገፈተሩ ወደ መግረፍያ ቦታ መውሰዳቸውን፣ ሕዝቡም በችኮላ በሞት መወገድ አለበት እያለ ከፍተኛ ጩኸት መጮኹን፣ ግርፋቱም በኦሪት ከታዘዘው ሕግና ደምብ ውጭ እጽፍ ድርብ እያደረጉ ጌታን መግረፋቸውን ያሳያል፡፡

### ሠ. ጽፋት፡-

ቃሉ ጸፍዐ በጥፊ መታ ካለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሆኖ ትርጉሙ በጥፊ መማታት ማለት ነ ው ፤ ይህ ክፍለ ማ?ሌት ጸናጽሉም ሆነ ከበሮው በፍጥነት እየተመታ የሚባል ነው፤ የዚህም ምሳሌ ወታደሮቹ የጌታን ፊት በጨርቅ እየሸፈኑ ደጋግመው በጥፊ በመምታት ማን መታሕ እያሉ የፈጸሙበትን ግፍ ያመለክታል፡፡

### ረ. አመላለስ፡-

አመላለስ መቋምያውን በትከሻ ላይ በመሸከምና በማስረገጥ፣ በጭብጨባና በእልልታ፣ መጀመርያ ዝግታ ባለው አመታት ተመላልሶ ኋላ የሚሸበሽብ ነው፤ ይህም ጲላጦስ ቀስ ብሎ አይሁድን በማሳመን ጌታን ሊያድን ፈልጎ መላልሶ ምን አደረገ እያለ መጠየቁን ያሳያል፤ ኋላ በሽብሻቦ መባሉ ግን ጲላጦስ በመጨረሻ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት ብሎ አሳልፎ መስጠቱንና ሕዝቡና ወታደሩ ደስ ብሎአቸው ተቻኩለው በእርግጫ እየተማቱ መስቀሉን አሸክመው ሊሰቅሉት ወደ ቀራንዮ መውሰዳቸውን ያሳያል ዮሐ19፣17

www.ethiopianorthodox.org

### ሰ. ወረብ፡-

ወረብ ማለት ቅብብሎሽ፣ ድግግሞሽ ማለት ነው፤ ይህም በመቀባበልና ደጋግሞ በማመላለስ የሚባል መሆኑን ይገልጻል፤ የወረብ አባባል እንደ አመላለስ መቋምያን በትከሻ ላይ በመሸከም፣ በማስረገጥ፣ በጭብጨባና በእልልታ የሚባል ነው፤ በምሳሌነቱ ጌታ መስቀሉን ተሸክሞ ወደቀራንዮ ሲጓዝ፣ የገሊላ ሴቶች ያለማቋረጥ እያለቀሱ መከተላቸውን አይሁድ ግን አሁንም ደጋግመው በእርግጫ እየተማቱ ደስ ብሎአቸው ሊሰቅሉት መስቀሉን አሸክመው ወደ ቀራንዮ መሄዳቸውን ያመለክታል፤ ሉቃ23፤ 26-29፤ በሌላም በኩል የአመላለስና የወረብ አባባል ኃዘንና ደስታ የተቀላቀለበት ገጽታ ያለው ነው፤ ኃዘኑ የመስቀል ምሳሌ የሆነው መቋምያ መሸከም ሲሆን ደስታው ደግሞ ጭብጨባውና እልልታው ነው፤ ይህም የተፈጸመው ድርጊት አሳዛኝ ቢሆንም ድ?ነትን ያስገኘ በመሆኑ የምእመናን ደስታ መሆኑን ለመግለጽ የሚደረግ ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ሁሉ የማኅሌት ያሬድ አባባል ስንመለከት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀልን የሚያሳስብ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ይህንን የመሰለ ታላቅ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በከፍተኛ ተጋድሎ ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ እስካሁን ላደረሱልን የኢትዮጵያ ሊቃውንት አባቶቻችን ከፍተኛ የሆነ አድናቆትና ምስጋና ሊሰጣቸው ይገባል፤ የአሁኑ ትውልድም ለዘመናት ተጠብቆ የኖረውን ዜማና ባህል ዘመኑ በሚጠይቀው ሁናቴ ተንከባክቦ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡

## የሰዓታት ዜማና ደራሲው

የዚህ ዜማ ደራሲ በቅዱስ ያሬድ ዜማና በምሥጢረ መጻሕፍት ከፍተኛ እውቀት የነበራቸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተባሉ ሊቅ ናቸው፤ አባ ጊዮርጊስ የደረሱት ይህ የዜማ ድርሰት በየሰዓቱ የሚደርስ ጸሎት ስለሆነ ሰዓታት በሚል ስም ተሰይሞአል፤ ይህ የዜማ ጸሎት በመካከሉ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶችና የሌሎች ሊቃውንት ድርሰቶች ተሰባጥረው ይገኙበታል፤ ለምሳሌ ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች አስተብ ወእትነግእና አንተ በሰማይ ከሊቃውንትም መስተብቁዕና ሊጦን አሉበት፤ ጸሎቱ ከዓመት እስከ ዓመት የሚባል አንድ ወጥ እንጂ እንደ ድጓ የተለየ የየቀኑ፣ የየበዓሉና የየዘመኑ የሆነ የለውም፤ በመሆኑም ከቅዱስ ያሬድ ዜማ ድርሰት ጋር ሊመጣጠን እጅግ በጣም ትንሽ ነው፤ አባ ጊዮርጊስ የሰዓታትን ዜማ ደረሱ ሲባል ዘሩን ራሳቸው ደረሱት ማለት እንጂ ከቅዱስ ያሬድ የተለየ ሌላ ዜማ ፈጥረው ደረሱ ማለት አይደለም፤ ድርሰታቸውን በቅዱስ ያሬድ ዜማ በማዜም አቀነባበሩት ማለት ነው፤ ይህ የሰዓታት ዜማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ገዳማት ከዓመት እስከ ዓመት ይቆማል፤ በሌሎች አድባራትና አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በዓበይት በዓላትና በወርኃ ጾም ይቆማል፤ የሰዓታት ዜማ ትምህርት ከቅዳሴ ጋር አብሮ የሚሰጥ ነው፤ የጋስጫው አባ ጊዮርጊስ የቅዱስ ያሬድ ዜማ መምህር ከመሆናቸውም ሌላ ምሁረ መጻሕፍት ስለነበሩ ብዙ መጻሕፍትን ደርሰዋል፤ በመሆኑም ጾመ ድጓ የተባለውን የወርኃ ጾም ክፍለ ድጓ ከድጓው አውጥተው ለብቻ እንዲቀነባበርና ሁሉም እንዲማረው አድርገዋል፤ የቤተልሔሙ መራሒ መምህር ልሳነ ፅፍረትንና የቆማ ፋሲለደስ መምህር ዕንቈባሕርይን ያስተማሩም እርሳቸው ናቸው፤ በመሆኑም በዜማ ትምህርት ከቅዱስ ያሬድ ቀጥለው የሚታወቁ እርሳቸው ናቸው፡፡

# ክፍል 7

## የቅዱስ ያሬድ ዜማ የሰጠው ጥቅም

የቅዱስ ያሬድ ዜማ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰጠው ጥቅም እጅግ በጣም ብዙ ነው፤ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፤ እነርሱም፡-

### 1. በሥነ ጽሑፍና በቋንቋ እድገት

በሁሉም ዘንድ እንደሚታወቀው ቅዱስ ያሬድ ዜማውን የደረሰበት ወቅት የግእዝ ቋንቋ ወደ አዲስ የአጠቃቀም ስልት በተሸጋገረበት ማግሥት ነበር፤ ይኸውም ከጥንት ጀምሮ በግእዝ ፊደልና ቋንቋ ሲጻፍ፣ ሲነበብና ሲነገር የነበረው ጥንታዊው ግእዝ በዐራተኛው ክፍለ ዘመን አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር በመሆን ለነባሩ ፊደል ከግእዝ እስከ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org



ቋንቋውም ሆነ ሥነ ጽሑፉ በዚሁ ዓይነት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረጋቸው ይታወቃል፤ በመሆኑም አዲሱን የግእዝ ቋንቋ ለመለማመድ ምሁራኑም ሆኑ ተራው ሕዝብ ቅዱስ ያሬድ እስከተነሣበት ጊዜ መቸገራቸው አልቀረም፤ ይሁንና ቅዱስ ያሬድ ዜማውን የደረሰው በአዲሱ ወይም በተሻሻለው የግእዝ ቋንቋ ስለሆነ ሊቃውንቱና ካህናቱ ዜማውን ሲማሩ የግእዙንም ቋንቋ ይበልጥ እንዲለማመዱትና በጥራት እንዲያውቁት አስችሎአቸዋል፤ በዚህም የቅዱስ ያሬድ ዜማ ለሥነ ጽሑፍ፣ ለቋንቋ ማደግና መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

### 2. በነገረ መለኮት ትምህርት

ቅዱስ ያሬድ የዜማ ደራሲ ብቻ ሳይሆን የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ መምህርም እንደነበረ ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡ ስለሆነም በዜማ ድርሰቱ ውስጥ ብዙ የሃይማኖት ትምህርቶች ተካተው ይገኛሉ፤ ቅዱስ ያሬድ ከብዙ መጻሕፍት ስለሚጠቅስና መጻሕፍትም ደግሞ የሚያስረዱት የሃይማኖትን ትምህርት ስለሆነ የሃይማኖት ትምህርቱን በዜማ አቀነባብሮ መድረሱ በጣም ተወዳጅ ትምህርት እንዲሆን አድርጎታል ማለት ነው፤ ከዚህም ጋር የረቀቀውን በማኅሌትና የተሠወረውን በመግለጥ የመተርጐም ሁኔታ በድርሰቱ ውስጥ ስለሚታይ ድርሰቱ ብዙ ጥቅም የሚሰጥ ነው፤ ድጓ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት ከመጀመርያ ጀምሮ ምን ይመስል እንደነበረ ለመረዳት ለሚፈልግ ሁሉ እንደቀዋሚና ተጨባጭ ማስረጃ የሚያገለግል የሃይማኖት ምስክር መጽሐፍ ሆኖ የሚያገለግል ስለሆነ በትምህርተ ሃይማኖት አስረጅነቱም ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ሆኖ ይገኛል፤ በመሆኑም ሊቃውንቱ በትርጓሜ ጊዜ በአስረጅነት እየጠቀሱ ይጠቀሙበታል፡፡

### 3. በሥርዓተ ጸሎት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቀኖና መሠረት ከዓመት እስከ ዓመት ለሚከናወነው ማንኛውም ሥርዓተ ጸሎት ዋና መሪው የቅዱስ ያሬድ ዜማ ነው፤ ማ?ሌቱ፣ ቅዳሴው፣ ፍትሐቱ፣ ጥምቀተ ክርስትናው ወዘተ ሁሉ በዜማው መሪነት የሚከናወኑ ናቸው፤ የዘመናቱ አከፋፈልም ሆነ በየዘመናቱ መከናወን ያለባቸው የጸሎት ክንውኖች የሚመራው ይህ የዜማ መጽሐፍ ነው፤ ከዚህም በተጨማሪ ራሱ ድርሰቱ በዋነኛነት ጸሎትን በብዛት የያዘ ነው፤ ከዚህም ሌላ የሥነ ምግባር ትምህርት፣ የምስጋናና የንሥሐ ትምህርትን ያጠቃለለ በመሆኑ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል፡፡

### 4. በታሪክ ትምህርት

የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በታሪክ ትምህርትም የበለጸገ ድርሰት ነው፤ በመሆኑም ከታሪክ አንጻር ሲታይ ክእርሱ በፊት የተፈጸመና እርሱ በነበረበት ጊዜ የተከናወኑ ነገሮች በዜማ ድርሰቱ ውስጥ ተተርክው ይገኛሉ፤ ለምሳሌ እሱ በነበረበት ጊዜ ከፍተኛ ጭፍጨፋ የተፈጸመባቸው የናግራን ሰማዕታት ታሪክሁኔታውን በመዘርዘርና የዋና ዋናዎቹን ሰማዕታት ስም በመጥራት ይተርካል፤ እንደዚሁም የሌሎች ቅዱሳን ታሪክን መዝግቦ ይገኛል፤ በመሆኑም በታሪክ መዝገብነቱ ብዙ ጥቅም የሚሰጥ ነው፡፡

### 5. የቤተ ክርስቲያንን አንድነት በመጠበቅ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድነት በማጠናከርና በመጠበቅ ረገድ የቅዱስ ያሬድ ዜማ የመጀመርያውን ደረጃ ይይዛል፤ ይህም ማለት ዜማው አንድና ወጥ የሆነ ሥርዓትን በመዘርጋት የቤተ ክርስቲያኗ ሁለንተናዊ ሕይወት በአጠቃላይ በቅዱስ ያሬድ ዜማ አሥሮ ቋጥሮታል፤ ማንም ሰው ሊፈታው ወይም ሊበጥሰው የማይችል ጠንካራ አንድነት እንዲሆን አድርጎታል፤ አቅጣጫው አንድ ብቻ ነው እርሱም የቅዱስ ያሬድ ዜማ ነው፤ ዜማው በየትኛውም አካባቢ የምትኖር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት መዝሙር፣ አንድ ዓይነት ቅዳሴ፣ አንድ ዓይነት ሥርዓት በአንድ ቀን ማቅረብ እንድትችል አድርጎአል፤ መለያየትና መከፋፈል በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ፈጽሞ ሊታሰብ የማይችል እስኪሆን ድረስ ጥበቃውን አሳይቶአል፤ ስለሆነም የቤተ ክርስቲያኗን አንድነት በመጠበቅ ከፍተኛ ጥቅም አስገኝቶአል፡፡

### 6. የቅዱስ ያሬድን ዜማ ከሌላው ዜማ ለየት የሚያደርገው

በዓለማችን ያሉ የሃይማኖት ተቅዋማት የየራሳቸው የሆነ ዜማ እንዳላቸው ይታወቃል፤ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ድርሰት ግን ከዚህ ሁሉ ለየት ያለ ባህርይ ያለው ነው፤ ዕድሜ ልክ ቢያዜሙትም በየቀኑ ልብን በኃሤት እየሞላና

በተመስጦ እያከነፈ ሐሳብን ሁሉ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ጨልጦ ከሚወስድ በቀር ሲጠገብና ሲሰለች አይታይም፤ ይህ ሊሆን የቻለው ዜማው በዓለም ውስጥ ተመሳሳይ የማይገኝለት ልዩ ጣዕም ያለው ከመሆኑም በላይ በውስጡ እንደ ልብ እየተቀያየሩ የሚዜሙ ብዙ የተለያዩ ዜማዎች ማለትም የግእዝ ዜማ፣ የዕዝል ዜማ፣ የዓራራይ ዜማ ያሉት በመሆኑ ነው፤ እንደዚሁም ድጓው ከዝማሬው፣ ዝማሬው ከመዋሥእቱ፣ መዋሥእቱ ከምዕራፉ፣ ምዕራፉ ከቅዳሴው የተለየ ጣዕምና ሰዛ ያለው ስለሆነ ሁሌም እንደ አዲስ ነገር የሚያዜሙት እንጂ የሚጠገብ አልሆነም፤ ዜማው በጣም ትልቅ ድርሰት ስለሆነ በዚያው ልክ ብዙ የተለያዩ ጣዕመ ዜማዎችና የዜማ አመሎች ስለሚገኙበት ሁሌም አዲስ ነው፤ እንደዚሁም ለእያንዳንዱ ክብረ በዓልና ለየዘመናቱ የየራሳቸው የሆነ ዝማጅት ስላላቸው ከተመደበላቸው ቀን በቀር በሌላ ቀን አይባሉምና ጣዕመ ዜማው በዓመት አንድ ጊዜ ስለሚባል ሁሌ ሳይጠገብ እንደተናፈቀ እንዲኖር አድርጎታል፡፡የቅዱስ ያሬድ ዜማ በቅንብሩና በአዘገጃጀቱ፣ በኃይለ ቃሉና በምሥጢር ገላጭነቱ በጣም የረቀቀና የጠለቀ ስለሆነ እንዲሁ በቀላሉ የሚለመድና የሚያዝ አይደለም፤ ዜማውን በትክክል ለማወቅ ቢያንስ ከ0ሥር ዓመት በላይ ይፈጃል፤ ስለሆነም በቀላሉ መያዝ እንደማይቻል ሁሉ በቶሎ የመጠገብ ባህርይም የለውም፡፡

ይህ የቅዱስ ያሬድ ዜማ ካለው ልዩ ጣዕምና ተወዳጅነት የተነሣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ማንም ሳይገፋፋቸውና ሳያስገድዳቸው በራሳቸው ፍላጎት ብቻ ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው፣ ከእናት አባታቸውና ከሥጋ ዘመዶቻቸው እንዲሁም ከትውልድ ቀያቸው ወጥተው ራቅ ወዳለ ሌላ ቦታ በመሄድ ሙሉ ጊዜያቸውን በቅዱስ ያሬድ ዜማ ትምህርት ጥናት ላይ በማዋል ረጅም ጊዜ ወስደው ሙያውን መማራቸው፣ እንዲሁም በትምህርት ጊዜ የሚያጋጥማቸው ረኃብና እርዛት፣ በሽታና ብቸኝነት ሳይበግራቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ሊቃውንት ሆነው መገኘታቸው የዜማውን ምንነት በትክክል የሚያረጋግጥ ተጨባጭ ምስክር ነው፤ ይህን ሁሉ ስንመለከት እውነትም በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸና የተሰጠ ሀብት መሆኑን እንረዳለን፤ ሊቃውንቱ ሙሉ በሙሉ ተምረው ዜማውን በሚገባ ካወቁ በኋላም ሳይሰለቹትና ሳይጠግቡት ሞት እስኪለያቸው ድረስ መላ ዘመናቸው ያመሰግኑበታል እንጂ በቃን ደከመን አይሉም፡፡





# ምዕራፍ 6

## ክፍል 1

## የቅኔ ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ

የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የትምህርት ዓይነቶች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1. ፀዋትወ ዜማ
2. ፀዋትወ ቅኔ
3. ትርጓሜ መጻሕፍት
4. የቀጥር ወይም የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ናቸው፡፡

ለእያንዳንዳቸውም ልዩ ልዩ የትምህርት ዘርፍና ስያሜ አላቸው፡፡ ይኸውም በጥቅሉ ፀዋትወ ዜማ የሚባሉት፤ ምዕራፍ፣ ጾመ ድጓ፣ ድጓ፤ ዝማሬ መዋሥዕትና ቅዳሴ እንዲሁም አቋቋም የሚል ስያሜ የተሰጣቸው የፀዋትወ ዜማ ዝርዝር የትምህርት ዓይነቶች ናቸው፡፡
የቅኔ መንገድ በአራት ይከፈላል፡፡

ይኸውም፡-

1. የጥንቱ የቅኔ መንገድ
2. የዋድላ
3. የዋሽራና የጐንጅ
4. የጎንደር የቅኔ መንገድ ነው፡፡

ትርጓሜ መጻሕፍት ተብሎ ጠቅለል ባለ መልኩ የተሰየመው ከፍተኛ የትምህርት ዓይነት ደግሞ አራት ክፍሎች አሉት፤

በዝርዝር ሲተነተኑም፡-

1. የብሉያት ትርጓሜ
2. የሐዲሳት ትርጓሜ
3. የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ
4. መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው፡፡

እነሱም በጥቅል ስማቸው አራቱ ጉባኤያት ተብለው ይጠራሉ፡፡

የቅኔና የመጻሕፍት መምህራኑም የመዐርግ ስም የቅኔ መምህሩ መጋቤ ምሥጢር፣ የመጻሕፍተ ብሉያት መምህሩ መጋቤ ብሉይ፤ የመጻሕፍተ ሐዲሳት መምህሩ መጋቤ ሐዲስ የመጻሕፍተ ሊቃውንት መምህሩ ሊቀ ሊቃውንት ተብለው ይጠራሉ፡፡ አራቱንም ጉባኤያት በሙሉ የሚያውቁትና ጉባኤ ዘርግተው የሚያስተምሩት መምህራን ደግሞ አራት ዓይና፣ ወርቅ በምንቸት እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ እንደእነ ወርቅ በምንቸት ድንቆማረቆ፤ እንደ እነ አራት ዓይና ጉሹና እንደ እነ አራት ዓይና ኤስድሮስ ማለት ነው፡፡

### የትርጓሜ መጻሕፍት መሥራቾች

የታች ቤትና የላይ ቤት የትርጓሜ መጻሕፍት መሥራቾች ከዚህ ቀጥሎ ስማቸው በተራ ቁጥር የተቀመጠው ጥንታውያን የአብነት መምህራን ናቸው፡፡

እነሱም፡-

1. መምህር አብራንዮስ



www.ethiopianorthodox.org

2. መምህር ሥነ ክርስቶስ
3. መምህር ኤስድሮስ
4. አለቃ ወልደ አብ የሚባሉ ኢትዮጵያውያን የአብነት መምህራን ሲሆኑ በጥቅሉ የታች ቤት ትርጓሜ መምህራን ተብለው ይጠራሉ።

ቀደም ሲል ግን

1. ጌታው ዮናስ
2. ጌታው ሠርፀ ድንግል
3. ጌታው ወልደ ማርያም
4. ጌታው መዝሙረ ድንግል የሚባሉ ኢትዮጵያውያን የላይ ቤት ትርጓሜ መምህራን ነበሩ

እንግዲህ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ከቤተ ክርስቲያን የትምህርት ዓይነቶች በመጠኑም ቢሆን ለመግለጽና ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተፈለገው ከፍ ብሎ በርእሱ እንደ ተገለጸው የቅኔ ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ የሰጠውን ጠቀሜታና የተጫወተውን ሚና እንዲሁም ያለውን የፍልስፍና ገጽ ባሕርይ ለማስጨበጥና ለማስገንዘብ በመሆኑ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የቅኔን ትምህርት አመሠራረት፣ አካሄድና ጠቀሜታ ፈለግ ብቻ ተከትሎ የሚጓዝ ይሆናል።

በዚህም መሠረት፣

1. የቅኔ ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ ከመቼ ጀምሮ እያደገ እንደመጣ
2. የታወቁት የመጀመሪያዎቹ የቅኔ ጉባኤ ቤቶች በሀገራችን በኢትዮጵያ በየትኛው ክፍል እንደሚገኙና የትኞቹ እንደሆኑ
3. የቅኔ ሥነ ጥበብ ስልትና ዓይነት
4. የቅኔ ምርምር ለሰው ልጅ አእምሮ የሚሰጠው ስፋት
5. ቅኔ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን አገልግሎት፣ የእምነትና የአምልኮ ምሥጢር መግለጫ መሆኑን ደረጃ በደረጃ መግለጽና ማስረዳት እጅግ በጣም ጠቃሚና ተገቢም ነው።

ስለሆነም የቅኔን ትርጉምና ዓይነት፣ ይዘትና ስልት፣ ለሰው ልጆች የሚሰጠውን የአእምሮ ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሀገርና ለወገን የሚሰጠውን ጠቀሜታና የሚያበረክተውን አገልግሎት ከረዥሙ ባጭሩ፣ ከብዙው በጥቂቱ በቅደም ተከተል ማቅረብ የጥናታዊ ጽሑፉ ዋና ዓላማ ነው።

# ክፍል 2

## የቅኔ ትርጉምና ገጸ ባሕርያት

ቅኔ በልሳነ ግእዝ በጥሬው ቋንቋ ሲተረጎም ቀነየ ገዛ ከሚለው የግእዝ ቋንቋ ግሥ የተገኘ ጥሬ ዘር ነው። በሌላ ብሂልም ቀነየ ገዛ የሚለውን የግሥ አንቀጽ ያስገኘ ጥሬ ዘር ነው። ትርጓሜውም መገዛት ማለት ሲሆን የቃሉ ትክክለኛ ትርጉም ይኸው መሆኑንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ ምዕ. 5 ቁ. 1 ላይ ‹‹ቁሙ እንከ ወኢትሑሩ ውስተ አርዑተ ቅኔ›› ማለት ከአንግዲህ ወዲህ ወደ ባርነት ወይም ወደ መገዛት ቀንበር አትሂዱ በማለት አረጋግጦ ገልጾታል።

የቃሉ ትክክለኛ ትርጉም ይህ ከዚህ በላይ የሰፈረው ይሁን እንጂ (ሆኖ ሳለ) ፍጡራን በየጊዜው የፈጣሪያቸው ተገዥች መሆናቸውን ለመግለጽና እግዚአብሔር ቀብቶ ለሾማቸው ሰዎች፣ ለቅዱሳን መላእክትና ለጻድቃን በየጊዜው አዳዲስ ድርሰት እየደረሱ የሚያቀርቡት የምስጋና ቅኔም ትርጓሜውና ፍችው ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው፡ወይም ከዚሁ ጋር የተዛመደ በመሆኑ አጠቃላይ ስያሜው ቅኔ የሚለውን ስም እንዲያገኝ አድርጎታል።

ከዚህም ሌላ የውስጥና የውጭ ሕዋሳትን ለሕሊና አስገዝቶ በሰከነ መንፈስና በተመስጦ በተወሰነ ወይም ቁርጥ ባለ ሐሳብ ላይ የሚታሰብ ስለሆነ ቅኔ የሚለውን ስያሜ ሊያገኝ ችሏል። ይህም ይታወቅ



ዘንድ በተመስጦ ቅኔ በመቁጠር ላይ ያለና በቅኔ ምሥጢር ልቡ የተሰወረ ሰው ቅኔ በሚቈጥርበት ወይም በሚያስብበት ጊዜ በአጠገቡ ወይም በፊቱ የሚደርሰውን ወይም የሚደረገውን ነገር እያየ አያይም፤ እየሰማም አይሰማም።

ይህም በመሆኑ በቀድሞ ጊዜ ማለት በጎንደር ዘመነ መንግሥት ጊዜ የጎንደር ደብረ ቁስቋም አለቃ (አስተዳዳሪ) በእልፍኞቸው ውስጥ ምንጣፋቸውን አስነጥፈው፤ መጻሕፍታቸውን በፊታቸው ደርድረው ለበዓለ ቁስቋም የሚቀኙትን ቅኔ ሲያስቡና ሲቈጥሩ ወይም ሲያወጡና ሲያወርዱ ንጉሡ ዘው ብለው ሲገቡ ልባቸው ተመስጦ ሊያዩዋቸው ባለመቻላቸው ቀና ብለው ሳያዩዋቸው ቁጭ እንዳሉ ቀሩ። ንጉሡም ነገሩ ገርሟቸውና ደንቋቸው በእሳቸው አጠገብ አልፈው ከአልጋ ላይ ተቀምጠው ፍጻሜውን ለማየት ሁኔታቸውን ይመለከቱ ጀመር። በዚህ ረገድ ንጉሡ ብዙ ጊዜ ካጠፉ በኋላ የደብረ ቁስቋሙ አለቃ አእምሮአቸው ሲመለስ ንጉሡ ተቀምጠው ቢያዩ ደንግጠው በመነሣት ንጉሡን እጅ ነሱ፤ ንጉሡም ‹‹ምን ነው? ምን ሆነህ ነው? ብለው ቢጠይቋቸው ‹‹ጃንሆይ ቁስቋምን ያህል ደብር አምነው ሹመውኛል፤ ለበዓል የተሰበሰበው ሰው አለቃው ምን ይናገር ይሆን እያለ ዓይን ዓይኔን ሲያየኝ ያልሆነ ነገር ቢሰማ ደብሩን አዋርዳለሁ፣ ጃንሆይንም አሳማለሁ፤ እኔም አፍራለሁ ብዬ ቅኔ እቆጥር ነበረ›› አሉ ይባላል።

ይህም ልብ ብሎ ላስተዋለው ራሱን የቻለ ታላቅ ትምህርት ነው። ዛሬ ‹‹የሾመኝን ወይም ቤተ ክርስቲያኔን እንዳላሳማ፣ ራሴንም እንዳላስነውር›› በማለት ስለኖላዊነቱ መብቃትና አለመብቃት የሚያስብና የሚጨነቅ የደብር አለቃ ይገኝ ይሆን? አይገኝም እንጅ ከተገኘ መልካም ነው። በሌላ አተረጓጎም ቅኔ ማለት ተቀኜ፤ ሙሽ አወጣ፤ ግጥም ገጠመ፤ አራቆ ተናገረ፤ አዜመ፤ አንጎራጎረ፣ መራ ተብሎ ከሚተረጎመው ግሥ የተገኘ ጥሬ ዘር እንደ ሆነ የቅኔ ሊቃውንት ያስረዳሉ። በአጭሩ የቅኔ አጠቃላይ ትርጉሙ ሰው ከራሱ ከልቡናው አንቅቶ፣ አመንጭቶ ለፈጣሪው አዲስ ምስጋና ለማቅረብ በፈለገ ጊዜ ምሳሌ መስሎ፣ ከምሥጢር ምሥጢር አማርጦና አራቆ ቤት በመምታትና ግጥም በመገጠም በልቡ ውስጥ ያለውን ዕውቀትና የአእምሮውን ርቀት ወይም ምጥቀት የሚያሳውቅበት፣ የዕውቀቱን ደረጃ ለሌላው የሚገልጽበትና የሚያስረዳበት፣ የሚሰማውንም ልቡና የሚያነቃቃበት፣ የሚያራቅቅበትና የሚመስጥበት ድርሰት እንደ ሆነ የቅኔ ሊቃውንቱ ያስረዳሉ።

ይህም በመሆኑ ራሳቸው የቅኔ ሊቃውንቱ የካህን የዕውቀቱ መጠን ወይም ስፋትና ጥልቀት የሚታወቀውና የሚለካው በቅኔው እንደ ሆነ ይናገራሉ፤ በዚህ ረገድ እንደ ቅኔ ሊቃውንቱ አባባል ከሆነ ቅኔ የማያውቅ ካህን የክህነቱ መጠን የቱን ያህል እንደ ሆነ ሊታወቅ አይችልም ማለት ነው። የቅኔን ድርሰት ጊዜ አይወስነውም፣ በየጊዜው በዓለም ላይ ማለት በሰማይም ሆነ በምድር ከሚከሰቱ አዳዲስ ድርጊቶች ጋር በመገናዘብ ከሰው ልቡና ሲፈልቅና ሲመነጭ የሚኖር የማያቋርጥ ድርሰት ነው። ይሁን እንጂ ቅኔ ሲባል ምንም እንኳን እንደ መለኮት ጊዜና ቦታ ባይወሰንበትም ይዘቱና ሙያው ሳይለዋወጥ ከጊዜው ጋር እየተለዋወጡ የሚጓዙ ባሕርያት አሉት።

# ክፍል 3

## የቅኔ ትምህርት አጀማመርና ሂደት

የቅኔ ትምህርት አጀማመርና ታሪካዊ አመሠራረት በአግባቡ፣ በሥርዓቱ መቼና የት እንደ ተጀመረ፣ እነማን እንደ ጀመሩትም ስንጠይቅ የተጀመረው በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው። የጀመረውም የሰሜን ኢትዮጵያ ማለት የትግራይ ተወላጅ የሆነውና በዜማ ፈጣሪነቱ ዝናው በመላው ዓለም የታወቀው የወዋትወ ዜማ ደራሲ ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ሲሆን፣ እሱም ፀዋትወ ዜማን ሲደርስ አብሮ እንደ ደረሰው የቅኔ ሊቃውንቱ ይተርካሉ። የሚያቀርቡትም ማስረጃ ቅዱስ ያሬድ ምዕራፍ በተባለው ድርሰቱ የሠራው ምቅናይ ከቅኔ ጋር ተመሳስሎ መገኘቱን ነው።

በሌላ አተራረክም ከቅኔ ድርሰት የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰት መቅደሙ የማይካድና ቅኔ በቅዱስ ያሬድ መዝሙር አልፎ አልፎ እየገባ የሚዘመር ስለሆነ ዋዜማ፣ ሚበዝኑ፣ ይትባረክ፣ ዘይእዜ፣ መወድስ፣ ኮከክሙ፣ ክብር ይእቲ፣ ዕጣነ ሞገር የሚለውን ስም ከቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰት



www.ethiopianorthodox.org

በመውሰድ ይህንን አስጠግቶ የቅኔን ድርሰት ቅዱስ ያሬድ ከፀዋትወ ዜማ ድርሰቱ ጋር አብሮ እንደ ደረሰው ይተረካል እንጂ በእውነተኛው ታሪክ ግን የቅኔን ድርሰት የደረሰው ዮሐንስ ዘገብሎን የተባለ የሰሜን ወሎ የዋድላ ተወላጅ የቅኔ ሊቅ እንደ ሆነ የቅኔ ሊቃውንት በትክክል ያምናሉ፡፡

በሌላ በኩልም የቅኔን ድርሰት የደረሰው ደቀ አስጢፋ ወይም ተዋነይ የተባለው የጎጃም ተወላጅ የቅኔ ሊቅ ነው የሚሉ አሉ፡፡ የሁለቱም ትረካ ማስረጃ የዋድላ አገባብ፣ የጎጃም አገባብ፣ የዋድላ ቅኔ፣ የጎጃም ቅኔ እየተባለ እስከ አሁኑ ትውልድ ድረስ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየና ያለ ስለሆነ የሁለቱንም ወገን ታሪክ ከመቀበል በስተቀር ሌላ አማራጭ እንደ ሌለ ታላቁ ሊቅ መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀምበሬ ‹‹ዝክረ ሊቃውንት›› በተባለው የቅኔ መጽሐፋቸው አረጋግጠው አትተውታል፡፡

ታሪኩም ባጭሩ እንደዚህ ነው፤ እንደ ዋድሎች አባባል የቅኔን ድርሰት የጀመረው ቅዱስ ያሬድ ነው የሚለውን ታሪክ መሠረት በማድረግ በ1460 ዓ.ም ዮሐንስ ገብላዊ የተባለው የቅኔ ፈላስፋ የቅኔን ድርሰት መሥራት የሆነው ቅዱስ ያሬድ በዜማ ድርሰቱ የቅኔን መንገድ እንደ ጀመረ ተገንዝቦ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የቅኔን ድርሰት እንዲገልጽለት በወሎ ክፍለ ሀገር በአማራ ሳይንትና በቦረና መካከል በሚገኝ ልዩ ስሙ ደብረ ታቦር በሚባል ቦታ በወቅቱም የአዷ ይኩኖ አምላክ ከተማ በነበረው ስፍራ ሱባኤ ገባ፤ በዚህም ጊዜ የቅኔ ምሥጢሩ ከነቤቱ ወይም ከነስንኙ ተገልጾለት ከቅዱስ ያሬድ ቅኔ አዘል የዜማ ድርሰት ጋር አያይዞ እንደ ደረሰው ይተርካሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ዮሐንስ ገብላዊ ለአባ ወልደ ገብርኤል አስተማረ፣ አባ ወልደ ገብርኤልም ለሠምረ አብ አስተማረ፣ ሠመረ አብም ያስተምር የነበረው በ1460 ዓ.ም ገደማ በዐዜ በአደ ማርያም ዘመነ መንግሥት ስለ ነበረ ንጉሡ አዷ በአደ ማርያም ሠምረ አብን ‹‹አንተ ከአነ አባትህ በከንቱ ትደክማለህ እንጅ ያገኛችሁት ከማን ነው?›› ብለው ጠየቁት፤ ሠምረ አብም ንጉሡን በአደ ማርያምን ‹‹በዚህ ጉዳይ ላይ የሚጠራጠሩ ከሆነ እግዚአብሔር ቸር ነው ይገልጽልናል ሱባኤ እንግባ›› አላቸው፡፡ ንጉሡም ፈቃደኛ ሆነው ሱባኤ ቢገቡ ጉዳዩ የመንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ተገልጾላቸው

‹‹ድኅረ ተሰብረ አጽንኦ ለሰብእናነ ልሕኩት
ለብሐዊ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት››

የሚለውን ቅኔ እንደ ዘረፉ ይነገራል፡፡

ቀኑም ጥር 12 ቀን የቃና ዘገሊላ ዕለት ስለ ነበረ ቅኔው ጉባኤ ቃና ተብሎ እንደ ተሰየመ ይተረካል፡፡ ከዚህ በኋላ ሠምረ አብ ለልሔብ፣ ልሔብ ለኤልያብ፣ ኤልያብ ለድድቅ ወልደ ማርያምና ለተዋነይ አስተማረ፤ በዚህ ዘመን ግራኝ መሐመድ ተነሥቶ ሁከት ስለ ተፈጠረ ተዋነይ ጣና ውስጥ ደቀ አስጢፋ ከሚባል ደሴት ውስጥ ገብቶ ተቀመጠ፣ ከዚያም ሲወጣ አገባቡን አጥፍቶ ቅኔውን ብቻ ይዞ ወጣ፣ መምህሩ ኤልያብ በዚያ ጊዜ ሞቶ ስለ ነበረ ከወንድሙ ከድድቅ ወልደ ማርያም ለመጠየቅና ለመቀጸል ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ አገባቡን ትቶ ቅኔውን ብቻ እንዳስተማረና በዚህ ምክንያት በጎንጅ አገባብና ዕርባቅምር እንዳነሰ ይነገራል፡፡

ድድቅ ወልደ ማርያም ግን በወሎ ክፍለ ሀገር ዳውንት ውስጥ ልዩ ስሙ የጨረቃ ከሚባል ስፍራ ተቀምጦ ከቅኔ ሊቃውንት ሳይለይ በመኖሩ አገባቡንና ዕርባቅምሩን ይዞ በመገኘቱ የቅኔን ትምህርት በተሟላ መልኩ አስተምሯል፡፡

ከእርሱ በኋላም 6 መምህራን ድድቅ ድድቅ እየተባሉ በተከታታይ አስተምረዋል፣ ድድቅ ማለትም ጀግና ማለት ነው፤ እነሱም የምሥጢር ጀግኖች ስለሆኑ በተከታታይ ድድቅ ድድቅ እያሉ እንደ ጠሩአቸውና በ6ኛው ድድቅ ጊዜ የቅኔ ጉባኤ ሰፍቶ 7 አዋጅ፣ 7 ዕርባ ቀምር፣ 7 አገባብ እንደ ተነገረ በቅኔ ሊቃውንት ዘንድ ይተረካል፡፡

ከዚህም ሌላ አንዳንዶች እንደሚሉት ደግሞ በአዷ እስክንድር ዘመነ መንግሥት ተዋነይ ወደ ግሪክ ሄዶ 7 ያህል ቋንቋዎችን አጥንቶ እንደ መጣና ከ7ቱም ቋንቋዎች አንዱ ቅኔ እንደ ሆነ፣ ለንጉሡ ለአዷ እስክንድርና ለሌሎችም ሐዋሪያ መንክራ፤ ብሉር ለተባሉ ሰዎች እንደ አስተማራቸውና የቅኔን ትምህርት እነሱ እንዳስፋፉት ይተርካሉ፡፡ ነገር ግን …… የራስን ታሪክ ለሌላ አሳልፎ ለመስጠትና በአድላዊነት ተዋነይን ከቅኔው ፈጣሪ ከዮሐንስ ገብላዊ አልቆ ለማሳየት አጉል ጥረት የተደረገበት ተአማኒነት የሌለው





ታሪክ ከመሆኑ በስተቀር የኢትዮጵያ ቅኔና የውጪ ቅኔ በሰምና ወርቁም ሆነ በማንኛውም ይዘቱና ትርጉሙ እንዲሁም በአጠቃላይ ገጸ ባሕርዩ የሰማይንና የምድርን ያህል የተራራቀ ስለሆነ፤ ዮሐንስ ገብላዊና ተነዋናይ የተነሡበትም ዘመን ብዙ ርቀት ስለአለው ይህ ታሪክ በቅኔ ሊቃውንት ዘንድ በጭራሽ አይታመንበትም፡፡

ተዋነይ ወይም ደቀ አስጢፋ ወደ ጽርዕ ሄዶ አልተማረም፤ ከኢትዮጵያ ውጭም የኢትዮጵያውያን የቅኔ ዓይነት የለም ከተባለና ይህ ትረካ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ዮሐንስ ገብላዊ የቅኔን ድርሰት ከምን አምጥቶ ደረሰው ቢባል በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ ቅዱሳን መላእክት በተፈጠሩ ጊዜ ‹‹መኑ ፈጠረነ፤ እምአይቴ መጻእነ ማለት ማን ፈጠረን? ከወዴትስ መጣን?›› በማለት ጠይቀዋል፡፡ በዚህም ጊዜ መኑ፤ እምአይቴ በማለት ንዑስ አገባብ፣ ፈጠረነ፣ መጻእነ በማለት ዕርባታ እንደ ተገኘ በቅኔ ሊቃውንት ይታመናል፡፡

ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ ነቢያት በየጊዜው ከጻፏቸው መጻሕፍት አግኝቶ አገባቡን ዐቢይ አገባብ፣ ንዑስ አገባብ፣ ደቂቅ አገባብ በማለት መድቦታል፡፡ ዕርባታውንም ከሀ እስከ ፋ ድረስ ያለው ግሥ ሁሉ በ 2 ባሕርያት፣ በ3 ጠባይዓት፣ በ4 ፀዋትው፣ በ8 አርእስት፣ በ22 ሠራዊት እንዲረባ እንዲገሠሥ አድርጎ ወስኖታል፡፡ የቅኔንም መንገድ ማለት የሰምና የወርቅን፣ የአንጻርን፣ የዝምድን፣ የፍላፃን፣ የኀብርን፣ የሠረዝን፣ የሌላውንም ቅኔ ሙያ ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት ክብሉያትና ከሐዲሳት አግኝቶ እንደ ተናገረው የቅኔ ሊቃውንት ያስረዳሉ፡፡

## ከቅኔ መንገድና ስያሜዎች ጥቂቶቹ

ቅኔን የፈጠረው ቅዱስ ያሬድ ነው ቢባልም እንዲሁ እምነበ አልቦ ኀበቦ የፈጠረው አይደለም፡፡ የቅኔ ምንጭና መሠረት መጻሕፍተ ብሉያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት ወይም በጥቅሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው፡፡

ቅኔ በአጠቃላይ ቃሉ ቅኔ ይባል እንጅ ዓይነተኛ መጠሪያውም ሰምና ወርቅ ይሁን እንጅ አንድ በአንድ ሲተነተንና ሲዘረዘር ውስጠ ዘ ግልጸ ዘ ብሂል፤ ሰምረገፍ፣ ሰም ገፊ ዝምዝም ወርቅ፣ ወፍ እግር፣ ዓይነውሃ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝ፣ ድርብ አሰናካይ፣ ወዘተ. የመሳሰሉ በርካታ መንገዶችና ስያሜዎች አሉት፤ በአጠቃላይም በጥንታዊው ኀዋዊ ዋዜማ ቅኔ እንደ ተገለጸው አምስት መቶ የሚሆኑ የተለያዩ መንገዶችና ስያሜዎች እንዳሉት የቅኔ ሊቃውንት ይተርካሉ፡፡

የቅኔ መንገዶችና ስያሜዎችም ምንጮች ቅዱሳት መጻሕፍት በመሆናቸው ከበርካታ የቅኔ መንገዶችና ስያሜዎች መካከል ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን ማለት

- የሰምና የወርቅ፤
- የአንፃር፤
- የውስጠ ወይራ፤
- የሰረዝ፤
- የአፍራሽ፤
- የምርምር፣ የቅኔ መንገዶች ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገኙ ለአብነት ያህል ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን፡፡

ሰምና ወርቅ ቅኔ ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ እንዴት እንደ ተገኘ ለመረዳት የሚከተለውን የቅዱስ መጽሐፍ ምንባብ ልብ አድርጉ ይመለከታል፡፡

በመጻሕፍተ መሳፍንት ምዕራፍ 9 ከቍጥር 7-21 ባለው ምንባብ እንደ ተገለጸው የሮበዓም ልጅ አቢአታም 70ውን ወንድሞቹን ገድሎ እርሱን ለመግደል የሚፈልገውን አቤሜሌክን የሰቂማ ሰዎች ባነገሡት ጊዜ ከተራራ ላይ ቆሞ ‹‹እናንተ የሰቂማ ሰዎች ስሙኝ ስሙኝ›› በማለት ባስተላለፈው የምፀት መልእክት ‹‹ዕንጨቶች ተሰብስበው ሄደው ዘይትን እናንግሥሽ ንገሽልን ቢሏት እግዚአብሔር የሰጠኝን ቅብዕቴን ትቼ አልነግሥም›› አለቻቸው፡፡ እንዲሁም በለስን ሄደው ‹‹ነይ ንገሽልን እናንግሥሽ›› ቢሏት



www.ethiopianorthodox.org

‹‹ምጥቀቱንና የተባረከ ፍሬዱን ትቼ አልነግሥም›› አለቻቸው፤ እንደ ገናም ወደ ወይን ዛፍ ሄደው ‹‹ና ንገሥልን›› ቢሉት በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ አስደሳችነቱን ልተው ነውን? አይሆንም›› አላቸው፡፡

ቀጥሎም ዶግን ‹‹ነይ ንገሽልን›› ቢሏት በእውነት እኔን የምታነግሱኝ ከሆነ ‹‹ኑ ከእኔ በታች በጥላዬ ሥር ተጠግታችሁ ዕረፉ››፤ አለቻቸው፡፡ ‹‹ምናልባት እሳት ከዶግ ወጥታ ዛፉን ሁሉ ሳትበላው አትቀርም ›› ብሎ የሰሙን ትርጉም ነግሯቸዋል፡፡ የወርቁንም ትርጉም ከምድያም ጋር ተዋግቶ ያዳናችሁን የአባቱን የሮበዓምን 70ውን ልጆቹን የገደለውን አቤሜሌክን ማንገሣችሁ የሚገባ ከሆነ እናንተን በእርሱ ደስ ይበላችሁ፤ እርሱንም በእናንተ ደስ ይበለው፤ ሳይገባው አንግሣችሁት እንደሆነ ግን ከእርሱ የወጣች እሳት እናንተን፣ ከእናንተም የወጣች እሳት እሱን ታጥፋው ታቃጥለው ብሎ ተርጉሞላቸዋል፡፡

በሌላ በኩልም በ2ኛ ዜና መዋዕል 25:17 ታሪክ ተመዝግቦ እንደሚገኘው የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ ወደ እሥራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮአስ ‹‹ና ፊት ለፊት እንተያይ›› ብሎ ቢልክበት ‹‹አቃኒ ለእከት ኀበ ዕፀወ ቈድሮስ እንዘ ትብል ወለተከ ሀቦ ለወልድየ›› ማለት አይጥ ከዝሆን ዘንድ፣ ችፍርግም ከዋንዛ ዘንድ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጄ ስጠው ብላ ላከች ዝሆን ወይም ዋንዛ ወይም ዝግባ ቤቷን እንይ ብለው ሄደው አረጋግጠው አጠፏት›› በማለት የሰሙን ትርጉም ተናግሯል፡፡

የወርቁንም ትርጉም ኤዶሞያስን ስለወጋህ መኩራትህ ነውን? አርፈህ አትቀመጥምን? ከይሁዳ ጋር ትወድቅ ዘንድ ለምን መከራ ትሻለህ; በማለት አብራርቶታል፡፡ ቅዱስ ዳዊትም ‹‹እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር አምሳለ ዘእምትክት›› ማለት አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤ ከቀድሞ ጀምሮ ያለውንም ምሳሌ እናገራለሁ በማለት ምሳሌ መስሎ ቅኔ መቀኘት ከቅዱስ መጽሐፍ የመነጨ መሆኑን አስተምሯል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ‹‹ወዘአንበለ ምሳሌሳ ኢተናገሮሙ›› ባለው መሠረት ምሳሌ እየመሰለና ምሳሌውን እየተረጐመ እንዳስተማረ በማቴ.03:1-58 ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ‹‹ወትሴሰየነ እክለ ዐብዕነ፣ እለ ትሴሰዩ እክለ ሕማምሰ›› ማለት የዕንባ እንጀራን ትመገበናለህ፣ የመከራን እህል የምትመገቡ በማለት በመዝ.79:5፤ 126:2 ላይ የሰፈረውም የቅዱስ መጽሐፍ ምንባብ የሰምና ወርቅን መንገድ ቁልጭ አድርጐ ያስረዳናል፡፡

‹‹ወበከመ አንገሠቶ ኃጢአት ለሞት ከማሁ ታነግሥ ለጽድቅ ጸጋሁ ለእግዚአብሔር›› ማለት ኃጢአት ሞትን እንዳነገሠችው የእግዚአብሔር ጸጋም ጽድቅን ታነግሣለች፤ ተብሎ በሮሜ 5:21 የተጻፈውም ቃል አንጻር የቅኔ መንገድን የሚያመለክት ነው፤ በመዝሙረ ዳዊት 49 ቍጥር 19 ‹‹ወይወረደ ውስተኀለመ አበዊሁ›› ተብሎ የተነገረውም ቃል ውስጠ ወይራ የቅኔ መንገድ የተገኘበት ምንባብ ነው፡፡ ‹‹አከለክሙ በመንፈስ ሐሩ ወፍቶተ ሥጋክሙ ኢትግበሩ እጸመ ሥጋኒ ይፈቱ ዘኢይፈቱ መንፈሰ ወመንፈሰ ይፈቱ ዘኢይፈቱ ሥጋ›› ማለት ሥጋ መንፈስ የማይወደውን ይወዳልና ፈቃደ ሥጋችሁን አትሥሩ፤ መንፈስ ግን ሥጋ የማይወደውን ይወዳልና በመንፈስ ፈቃድ ኑሩ›› የሚለውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል የሠረዝ ቅኔ መንገድ መሠረትና መነሻ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በመዝ.4 ቍጥር 9 እንደሰፈረው ‹‹አድኀንከነ እምእለሮዱነ ወአስተኃፈርኮሙ ለኵሎሙ ጸላዕትነ፤ ይእዜሰ ገደፍከነ ወአስተኃፈርከነ ማለት ከከበቡን ሁሉ አዳነከን፣ ጠላቶቻችንንም ሁሉ አሳፈርካቸው ካለ በኋላ ይእዜሰ ገደፍከነ ወአስተኃፈርከነ ዛሬስ ጠላኸን፤ አሰፈርከንም ከሚለውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ አፍራሽ መንገድ እንደተገኘ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

እንዲሁም በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕራፍ14 ቍጥር 14 ተመዝግቦ የሚገኘው ‹‹እም አፈ በላኒ ወፅአ መበልዕ ወእምነ ጽኑዕ ወጽአ ጥዑም›› ማለት ከበላተኛ አፍ መብል፤ ከብርቱም ጥዑም ተገኘ የሚለውም የቅዱስ መጽሐፍ ገጸ ንባብ የሚያስገነዝበን ምርምርን ስለሆነ ምርምር የቅኔ መንገድም ከዚሁ ቃል እንደ ተገኘ የቅኔ ሊቃውንት ያምናሉ፡፡





## የራሱ የቅዱስ ያሬድ ቅኔ

በርእሰ ዓውደ ዓመት የቅዱስ ዮሐንስ በዓል ዕለት ቅዱስ ያሬድ ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ፣ እግዚአብሔር ነግሠ፣ እግዚኦ ጸራህኩ በሚለው የዜማ ድርሰቱ የራሱ የሆነ ቅኔ አለው፡፡

ይትባረክ በተሰኘው ድርሰቱ ላይም የደረሳቸው ቤት የሚመቱ ቅኔዎች አሉት

እነሱም፡-

- ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ መጥምቅ፣
  ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ሊቅ፣
- ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ሰንኮራስ፣
  ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ንጉሥ፣
- ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ድንግል፣
- ሶበ ርእዩ ለክርስቶስ ቃል የሚሉ ናቸው፡፡

ይህንንም ሊቃውንቱ ከላይ ከተጠቀሱት የቅኔ ዓይነቶች አንዱን ወስደው ዋዜማ ቅኔ ከመጨረሻው ማለት ከመጽፈያው ላይ አስገብተው ይቀኙበታል፡፡ ይህም የቅኔ መሠረቱ የቅዱስ ያሬድ ቅኔ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ቅኔ በሀገራችን በኢትዮጵያ ወይም በቤተ ክርስቲያናችን ራሱን የቻለ ትምህርት ቤት ያለው ከፍተኛ የትምህርት ዓይነት ነው፡፡ የቅኔ ትምህርት ደቀመዛሙርትን ተመራማሪዎች፣ ደራሲዎችና የምሥጢር ሰዎች ወይም ፈላስፎች የሚያደርግ ከሣቱ ብርሃን በመሆኑ በቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ክብርና ቦታ የተሰጠው ነው፡፡

ቅኔ ቀደም ብሎም የነበረ ጥንታዊ ዕውቀት መሆኑ ባይካድም በተለይ በብሔራዊ ደረጃ የታወቀውና የቤተ ክርስቲያን መገልገያ መሆን የጀመረው ከቅዱስ ያሬድ መነሣት ማለት ከስድስተኛው መቶ ዓመት ወዲህ መሆኑ ይነገራል፡፡ ለዚህ ታሪክ ትክክለኛ ማስረጃ ሆኖ የሚጠቀሰውም ቀደም ሲል እንደተገለጸው መጽሐፈ ድጓ በመባል የሚታወቀው ትልቁ የፀዋትወ ዜማ ድርሰት ነው፡፡

ይኸውም የፀዋትወ ዜማ ደራሲ የሆነው ቅዱስ ያሬድ በድጓ ድርሰቱ ሚበዝኑ፣ ዋዜማ፣ ሥላሴ፣ ዘይእዜ፣ መወድስ፣ ክብር ይእቲና ዕጣነ ሞገር በማለት በዚሁ ድርሰት ውስጥ የሠራው ከመሆኑም በላይ በተለይም እንደ አርያም ባለው የዜማ ድርሰቱ ቤት እየሠራና እየመታ ስለሚሄድ ነው፡፡

በኋላም በ1460 ዓ.ም የተነሣው ዮሐንስ ገብላዊ ከቅዱስ ያሬድ የድጓ ድርሰት ጋር አያይዞ ከድጓው ድርሰት ውስጥ አውጥቶ ራሱን የቻለ ድርሰትና ትምህርት ሆኖ እንዲቀጥል ያደረገው ሲሆን ዜማው ግን የጐት መንገድ ነበር፡፡ ከጉባኤ ቃና እስከ ዕጣነ ሞገር ያለው የቅኔ ዓይነት በአሁኑ ዓይነት የዜማ ስልትና ቅኝት የተወሰነው ግን በ1678 ዓ.ም በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይተረካል፡፡

# ክፍል 4

## የቅኔ ትምህርት መሥራቾችና የመጀመሪያዎቹ የቅኔ ጉባኤ ቤቶች

ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተነሡትም የቅኔ ትምህርት ምንጮች ወይም መሠረቶች የሚከተሉት ናቸው፣ ከፍ ብሎ እንደ ተጠቀሰው የመጀመሪያው የቅኔ ትምህርት መሥራች ዮሐንስ ገብላዊ ሲሆን ዮሐንስ ገብላዊ አባ ወልደ ገብርኤልን፣ አባ ወልደ ገብርኤልም ሠምረ ክርስቶስን ወይም ሠምረ አብን አስተማረ፣ ይህም የተፈጸመው በ1470 ዓ.ም በዐፄ በእደ ማርያም ዘመነ መንግሥት ነበር፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም -

ሠምረ አብ ልሒብን፤ልሒብ ኤልያብን፤ኤልያብ ድድቅ ወልደ ማርያምንና ተዋነይን
አስተማረ፡፡ ድድቅ ወልደ ማርያም የዋድላ ቅኔ መንገድ አብነት ሲሆን ተዋነይ ደግሞ የጎጃም
ቅኔ መንገድ አብነት ነው፡፡

እነዚህ ሊቃውንት ለዘመናዊ የቅኔ መንገድ መሥራቾች በመባል ስማቸው በቅኔ ታሪክ ለዘለዓለሙ ሲታወስ ይኖራል፡፡

ከእነዚህ ከላይ ስማቸው ከተጠቀሰው የቅኔ ሊቃውንት ማለት ከድድቅ ወልደ ማርያምና ከተዋነይ በኋላ በተለይ ዋድላ፣ ዋሽራና ጎንጅ የቅኔ ትምህርት አብነት መምህራን መፍለቂያ ቦታዎች ሆነው ይኖራሉ፡፡ በመላ ኢትዮጵያ በ44ው አህጉረ ስብከት ለሚገኙት በርካታ የቅኔ ጉባኤ ቤቶችም መሠረቶች እነዚህ ናቸው፡፡

ስለቅኔ ታሪካዊ አመጣጥና ትምህርት የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ጽፈውና መዝግበው ያቆዩን ከዚህ በላይ ተዘርዝሮ በቀረበው ትረካ ዓይነት ሲሆን ከዚያ በፊትም የቅኔ ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ ተፈልስፎ እስከ እነቅዱስ ያሬድ ዮሐንስ ገብላዊና ተዋነይ ወይም ደቀእስጢፋ መነሣት ድረስ ሲሠራበት እንደቆየ እነዮሐንስ አድማሱን የመሳለሉት ዓይናማዎች የዘመኑ ምሁራን ስለ ቅኔ ታሪካዊ አመጣጥ ለዩኒቨርሲቲ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ እንደሚከተለው ይተርካል፡፡

ቅኔ የተጀመረው በአገው ምድር ነው፣ ጀማሪውም ዘሱቱኤል የተባለ ምሁር ነው፣ ዘሱቱኤል ተብሎ በላኤ መጻሕፍት በሆነው በሱቱኤል እዝራ ስያሜ የሚጠራውም ከሱቱኤል እዝራ ጋር ተመጣጣኝ በሆነው ዕውቀቱና በሊቅነቱ ነው እንጂ የተጸውኦ ስሙ ወይም የመጠሪያ ስሙ አንድሪም ነው ይላሉ፡፡ ዘሱቱኤል ኦሪታዊ ነበር፣ ከኦሪት ያመጣል ይጠቅሳል፣ የነበረውም ከኢትዮጵያ ክርስትና ከመግባቱ በፊት ይሁን ወይም በኋላ እንደሆን በትክክል አልታወቀም፡፡ ምናልባት ኦሪታዊ ስለነበረ ቅድመ ክርስትና ይኖር ነበር የሚል ግምት ያስከትላል፣ ይህ ደግሞ ኦሪታዊም ቢሆን ከክርስትናው ደርሶ እንደሆነስ? የሚል ጥያቄን ማስከተሉ የማይቀር ነው፡፡

በኢትዮጵያ ቅኔን የጀመረ ዘሱቱኤል ከሆነ በትክክል ልናውቅ የምንችለው ዘሱቱኤል ከቅዱስ ያሬድ በፊት መነሣቱንና መኖሩን ብቻ ነው፡፡

የዘሱቱኤል ቅኔ ብዙ ነበር ግን ከዘመን ብዛት ተዘግቷል ወይም በቃል እንጅ በጽሑፍ ስለአልተያዘ ለትውልድ ሊተላለፍ አልቻለም፡፡

የዘሱቱኤል ከሚባሉት ቅኔያት ውስጥ የሚከተሉት ቀጠፋዎች ብቻ ቀርበዋል፡፡

እነሱም፡-

‹‹ማእከለ አራዊት ንኪልሕ ወአልቦ ዘይሰምአነ
እስመ አራዊት ይበዝኑ እምኔነ
‹‹መኑ ጠቢብ ወመለብው
ከመ እግዚአብሔር አገው›› የሚሉ ናቸው፡፡

ትርጓሜአቸውም ‹‹በአራዊት መካከል ብንጮኽ የሚሰማን የለም አራዊቱ ከእኛ ይበዛሉና፣ እንደ እግዚአብሔር አገው ያለ ብልሕና አስተዋይስ ማን ነው ክንዋኔዎች ማለት ነው፡፡ ይህም የሚይመለከተው አገው ልቡ ዘጠኝ

ስምንቱን አኑሮ በአንዱ አጫወተኝ›› ጋገር መሠረት አገው ሲባል እንደ እግዚብሔር ልቡ የማይታወቅ ወይም ልበሰፊ ነገር አላፊ መሆኑን ነው፡፡

ዘሱቱኤል ቅኔ በመጀመሪያ በአንድ ንባብ ነበር በኋላ ሊቃውንቱ ጉት አደረጉት፣ ቆይቶም ራሱ ዘሱቱኤል በዜማ ማስተማር ጀመረ ይባላል፡፡





ዘሱቱኤል ብዙ ደቀ መዛሙርት ነበሩት፣ ከደቀ መዛሙርቱ ሁሉ እጅግ የገነነውና ከመምህሩ ብልጫ የነበረው ዕዝራ የተባለው ነበር፡፡ በዚህም ዕዝራ ዘሱቱኤል ተባለ፡፡

ዕዝራ መምህሩ ዘሱቱኤል ካለፈ በኋላ በመምህሩ በዘሱቱኤል እግር ተተክቶ ማስተማሩን ቀጠለ፡፡ በዚህ መልኩ የመምህሩና የደቀ መዝሙሩ ስም እየተቀያየረ እስከ ሰባት ትውልድ ደርሷል፡፡ በሰባተኛው ትውልድ ላይ ጌዴዎን ቀዳማዊ የሚባል ባለቅኔ ተነሥቷል፡፡

ዘሱቱኤልን መነሻ በማድረግ ከሱ በኋላ የተነሡ ብዙኃን የቅኔ ኃያላንም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1 ዘሱቱኤል (አንድሪም)
2 ዕዝራ ዘሱቱኤል (የዘሱቱኤል ደቀመዝሙር) ሲሆኑ በዚሁ ስም እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ቆይቷል፡፡
3 ጌዴዎን ቀዳማዊ
4 ዜና አዳም
5 የማነ አበ
6 ሠርጉ ጥበብ
7 ህላዊ አብ
8 ሠረቀ ብርሃን ቀዳማዊ
9 ኤልያስ
10 ሠረገላ ጥበብ
11 ነደ እሳት
12 ጌዴዎን ካልአዊ
13 አብነት
14 ነአምን በአብ
15 አሚናዳብ
16 ዘዮሐንስ
17 በኩረ ልደት
18 አካለ ወልድ ቀዳማዊ ናቸው፡፡

ከአካለ ወልድ ቀዳማዊ በኋላ ዐሥራ አምስት ሊቃውንት ተበትነዋል ይባላል፡፡ ከእነሱም አንዱ ዮሐንስ ገብላዊ ወይም ዮሐንስ ዘገብላ የሚባለው የዋድላ ሰው ነው፡፡

19 ዮሐንስ ዘገብላ
20 ብርሃን ካልአዊ
21 ተወክል
22 ዘከማየ
23 ይኩን ኮሎ
24 ተክለ አብ

ከእነተዋነይ ተራው ሀ. ተዋነይ ለ. ተክለ አብ ሐ. ጽድቅ ነው፡፡

25 ተከሥተ ብርሃን፤
26 ከፈለነ
27 ከተማ
28 ፀምሩ
29 ጌዴዎን ሣልሳዊ
30 ስሙ (መምህር)
31 ፍቅሩ
32 ተክሌ ዘዋሽራ ናቸው፡፡

ተክሌ ዘዋሽራ የተማሩት ከመምህራቸው ከየኔታ ቀሰሙና ከአባታቸው ከየኔታ ፍቅሩ ነው፡፡ ከተክሌ ዘዋሽራ ከ50 መምህራን በላይ ተመርቀዋል፡፡

33 መምህር ገብረማርያም
34 ነቢየ ልዑል መንግሥቱ
35 ግጨው ገብሬ ሲሆኑ ስጊዜው ስማቸው ያልተመዘገበ ሌሎች አራት መምህራንም ነበሩ፡፡
36 [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

37 ነቢየ ልዑል ናቸው፡፡

ይህ ሐረገ መምህራን በዋሽራ በኩል የመጣው ዘርፍ ነው፣ ከተዋነይ ጀምሮ በጎንጅ የተነሡ የመምህራን ሐረግ ስጊዜው ባለመገኘቱ አልተመዘገበም፡፡ መምህራን በየቅኔ ቤቱ ጠልቀው የሚያስተምሩት ታሪኩን ሳይሆን ጥበቡን ወይም (እውቀቱን) ብቻ በመሆኑ የቅኔው ታሪክ ጥናት በጣም የቆረቆዘ ነው፡፡

የታወቁት የቅኔ መምህራን የሙገሳ (የቅፅል) ስም፡፡

እከየ ገብረ ማርያም ዋድሌ
ጐርደም ገብረ ማርያም ዋድሌ
ቅኔ ፈጣሪ ደሪ ትግራይ
አነበሳው ገብረ መስቀል ቤተ ዮሐንስ
ግጨው ወልደ ጊዮርጊስ ቤተ ሉር ዋድላ
ግጨው ገብረ ማርያም ዋሽራ
ማዕበል ደለለ ዋሽራ
ማዕበል ደለለ ዋሽራ
ማዕበል ፈንቱ ዋሽራ
ዕቡይ ካሣ ጐንጅ
ገሞራው ጌቱ ጐንደር
ገሞራው ፈንሐስ ጐጃም
ገሞራው ጥበቡ ጐጃም
ዝሆን ገብረ ኢየሱስ
ነበልባል ወይም ዕንቆቆው ፈረደ ጐጃም
አጋር ጥበቡ ጐጃም
ደመናው ገሠሠ ይሰማላ ጐጃም
ዝናሙ ገብረ ሥላሴ ደብረ ኤልያስ ጐጃም
ወርቅ በምንቸት ድንቆ ማርቆ ጎንደር
ዕውብ ጐበዙ ትግራይ
መትረጌስ ዐወቀ መቂት
ድድቅ ወልደ ማርያም ዳውንት ወሎ
ነብሮ ገብረ ሕይወት በጌምድር ሲሆኑ ሌሎችም የሙገሳ ስም የነበራቸው ስመ ጥር መምህራን እጅግ በጣም በርካታ ነበሩ፡፡

# ክፍል 5

## 22ቱ አርእስተ ቅኔ

የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ድጓ፣ ምዕራፍ፣ መዋሥዕት፣ ዝማሬ ተብለው በአራት የተከፈሉ ሲሆኑ አርእስተ ድጓ በበኩላቸው 22 ናቸው፡፡ በዚሁ አንፃር አርእስተ ቅኔም 22 ናቸው፡፡

እነሱም፣

1 ግእዝ ጉባኤ ቃና
2 ዕዝል ጉባኤ ቃና
3 ዘአምላኪየ
4 ሚበዝኑ
5 ዋዜማ





6 ዐጭር ዋዜማ
7 አጭር ዋዜማ
8 ሥላሴ
9 ዘይእዜ
0 አጭር ዘይእዜ
11 ማህልከ
12 መወድስ
13 ኩልክሙ
14 ዐጭር ኩልክሙ
15 ሕንዔሃ
16 ግእዝ ክብር ይእቲ
17 ዕዝል ክብር ይእቲ
18 ግእዝ ዕጣነ ሞገር
19 ዕዝል ዕጣነ ሞገር
20 ግእዝ ሀሠረ ንጉሥ
21 ዕዝል ዐሠረ ንጉሥ
22 የህንዔሃ ክብር ይእቲ

ተብለው የተሰየሙት ቅኔያት ሲሆኑ እነሱም ከ2-11 የሚደርስ ቤትና የየራሳቸው የሆነ ሐረግ ያላቸውና በቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች በመልክ በመልኩ እየገቡ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡ ስለ እያንዳንዳቸው ቅኔያት የቤት ዓመታትና አደራረስም አንድ አንዶቹ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች በይዘታቸው ከቅኔ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን መነሻ መሠረት በማድረግ ጥቂት የቅኔ ሊቃውንት የቅኔን ቤት ቅዱስ ያሬድ እንደ ደረሰው ይናገራሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የቅኔ ሊቃውንት ግን ሐዊራ፣ መንክራ ብሉር፣ እስከንድር ከተባሉት ደቀ መዛሙርት ጋር እንደ ደረሰውና በመልክ በመልኩ ወይም በሕግና በሥርዓት እንደ ሠራው በትክክል ያምናሉ፡፡

## ቅኔ የምርምርና የፍልስፍና መሠረት ነው

ቅኔ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜና ምሥጢር መፈተሻ፣ የአእምሮ ማደሻ፣ የዕውቀት ማጎልመሻ፣ የምርምር ዋሻ ነው፡፡ ቅኔን ከእነ አገባቡ በጥልቀትና በስፋት የተማረ ሰው ትርጓሜ መጻሕፍት እያገደውም፣ ወደ መጻሕፍት መምህራን ዘንድ ሳይሄድ መጻሕፍትን ራሱ ሊተረጉማቸውና ሊያመሠጥራቸው ይችላል፣ ወደ ትርጓሜ መጻሕፍት ቤት ቢገባም ጊዜ አይፈጅበትም፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርጓሜ መጻሕፍትን አጠናቅቆ ተምሮ ሊወጣ ይችላል፡፡

የቅኔ ዓይነትም እስከ 500 እንደሚደርስ እነ ሊቀ ሕሩያን ዘገየን የመሳሰሉት የቀድሞቹ ስመ ጥሩ የቅኔ ሊቃውንት በነበራቸው ከፍተኛ የቅኔ ሙያ ችሎታ በዘመናዊው የጊዜ አካኼድ ቀምረውና ወስነው ያዘጋጁት አኃዛዊ የሩቅ ሰሚ ዋዜማ ቅኔ በአኃዛዊ ገጸ ንባቡም ሆነ በሂደቱ ከ 2000 በዓል ወይም ከሚሊኒየሙ በዓል ጋር ተዛማጅና ተስማሚ ሆኖ ስለተገኘ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## አኃዛዊ የሩቅ ሰሚ ዋዜማ ቅኔ

ምሁረ ምሁራን ሰማኒቱ፤ ዐሥሩ ቃላተ በወስኮ ሐምስ ሃምሳ፡፡
ምዕተ 20 ወምዕተ ሰላሳ፡፡
መምህረ መምህራን ክብራት ዘትርጓሜ ሠላስ ስልሳ፡፡
ለዘዓዕይንታ ዐሥር ፍና ሐስሳ፡፡
እም አእምሮ ሰሎሞን ኢሄሳ፡፡

ትርጓሜውም በ250 ላይ 120ንና 130ን በመደመር በአጠቃላይ 500 የቅኔ መንገዶችን ከ80መምህራን የተማረ የበርካታ መምህራንና የብዙ ትርጓሜ መምህር ዓይኖቿ ማለት አመመለካከቶቿ ወይም ምርምሮቿ ዐሥር የሆኑላት ቅኔን ወይም የምርምር ጉዳናን ከዕውቀቱና ከምርምሩ ብዛት የተነሣ ጠቢቡ ሰሎሞን እንኳን ሊገመግማትና አቃቂር ሊያወጣላት አልቻለም ማለት ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

500 የቅኔ መንገዶች መኖራቸውን በዘመናዊው የጊዜ ቤት አካኼድ በአኃዝ ቀምሮና ወስኖ በአጭር ዐረፍተ ነገር 15 ቤት ወይም ስንኝ መጥኖ ያቀረበልን አንድ የቀድሞ የቅኔ ሊቅ ብቻውን ነው። በዚህ ቅኔ አንፃር ራሳችንን ስንገመግመው ግን እጅግ ልንገረም እንችላለን።

ይኸውም የሀገራችን የኢትዮጵያን የሁለት ሺህ ዘመን በዓል ለማክበር በዝግጅት ላይ በነበርንበት ወቅት ሚሊኒየም የሚለውን ፈረንጅኛ ቃል ወደ እኛ ወደ ግእዝ ቋንቋ እንድለውጠው ወይም ሌላ አጭር ቃል እንድንፈጥርለት ተጠይቀን በነበርንበት ጊዜ 2000 የሚለውን የግእዙን አኃዛዊ ቃል ለማግኘት ብዙ ሆነን ብዙ ተጨንቀን ነበር፤ ብዙም ተመካክረን ነበር፤ አልፈን ተርፈንም ለትልቁ ጉባኤ አቅርበነው ነበር። ፳፤ ተብሎ እንዲሰየም የተወሰነውም በዚያው በትልቁ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ነው።

ከዚህም ጋር የቀድሞቹን ሊቃውንተ ቅኔ የመሥ ርቀትና ምጥቀት ካስታወስን ዘንድ የኔታ ገብረ ሥላሴ ወይም በሙገሳ ስማቸው ዝናሙ ገብረ ሥላሌ የተባሉት ስመ ጥሩ የቅኔ ሊቅ የወላዲተ አምላክ የቅድስት ድንግል ማርያምንና የልጅዋን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዘመነ ልደት አስመልክተው የተቀኙትን አኃዛዊ መወድስ ቅኔ ከፍ ብለን ካቀረብነው አኃዛዊ ዋዜማ ቅኔ ጋር ተዛማጅ ሆኖ ስለአገኘነው በአኃዝ ለተደገፈው የሚሊኒየም ወይም ለ፳፤ በዓል ተስማሚ እንደሆነ በመገመት አቅርበነዋል።

## አኃዛዊ መወድስ ቅኔ

ቀዳሜ ጥዑም ስምኪ ወለተ ዳዊት፣ ራብዐ ራብዕ ፈደል ወሳድሰ ሳድሰ ዳግም።
እንዘ ለታስዕ ራብዕ ሣልሰ ዚአኪ ስም።
አምጣነ ራብዕ ለራብዕ፣ ፈደል ሳድሱ ውእቱ ተፍጻም።
ምሳሌ ክልኤሰራብዕ፤ ወምሳሌ ክልኤ ሳድስ እንከ ናቀውም።
እምዘመን ራብዐዊ በራብዐ ክፍሉ ለዐም።
ልደትኪ ወልደቱ ለፀሐየ ጽድቅኪ ማርያም።
አምጣነ ኃቤኪ መጽአ መልአከ ሰላም።
በሳድሰ ዐሥር ዓመዓት ወበሳደሰ ወርኀ እመሰከረም።
የሚል ነው።

ትርጓሜውም በሀ ለ ሐ መ የፊደላት መንገድ መ የተባለው ፊደል አራተኛ ፊደል ነው፣ ማ የተባለው ፊደል በበኩሉ የአራተኛው ፊደል አራተኛ ፊደል ሲሆን ም የተባለው ፊደል ደግሞ የአራተኛው ፊደል ስድስተኛ ፊደል ነው፤ የ የተባለው ፊደልም ዘጠናኛ ፊደል ነው፤

ስለዚህ የቅኔው ሊቅ የኔታ ገብረ ሥላሴ ማርያም የሚለውን የወላዲተ አምልክ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም በአኃዝ ተንትነው ከአራቱ ክፍላተ ዘመን ጋር አገናዝበው በመተርጉም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ፀሐየ ጽድቅ የተባለው ልጅዋ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመነ አበው፤ ዘመነ መሳፍንት፣ ዘመነ ነገሥት ተፈጽሞ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ ካህናት መወለዳቸውንና መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸምና ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲጀመር ከመስከረም ወር ጀምሮ በስድስተኛው ወር አምላክን እንደምትወልድ ያበሥራት ዘንድ ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መላኩን አመሥጥሮ የሚገልጽና የሚያስረዳ ነው።

ለቅኔ ፈጣሪዎቹና ለሚሊኒየሙ የተበረከቱ መወድስ ቅኔያት
በመጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

### 1ኛ መወድስ

ገብላዊ ዮሐንስ ወደቀ እስጢፋ፣ ለእጓልክሙ ቅኔ
አርኩ ለዕንባቆም።
ለእመአልቦቱ ማኅደር ኀበ ይነውም።
ወዘእንበለ አስብ ለእመተርፈ፤ ሐዲስ አኮ ወአኮ መ[illegible]



እስመ ያሬድ ፈጣሪሁ፤ ፈጠሮ እምጥንት
ዘእንበለ አስብ ወጥቅም።
ቀራንበተሂ ኢይሬአዩ አዕይንተ ገጽ ወፍጽም።
ወበውስተ ሀገር ነቢየ ጽድቅ ኢይክብር በዓለም።
በአንጻረ ዝንቱ ውእቱ በኢትዮጵያ አዳም፤
ቅኔ ዘይቴጎት ወቅኔ ዘይደክም።

ትርጓሜውም የቅኔ ፈጣሪዎች ዮሐንስ ገብላዊና ደቀ እስጢፋ ሆይ ልጃችሁ ቅኔ የሚያድርበት ቤት ባይኖረውና ያለደመወዝ ቤቀር አዲስ ነገር አይደለም፣ ሊያስደንቅም አይችልም፤ ጥንቱንም ቢሆን ፈጣሪው ቅዱስ ያሬድ ቤት አልሠራለትምና፣ ደመወዝም አልመደበለትምና። ዓይኖችም ቅንድብን ሊያዩ አይችሉም፣ እንደ መጽሐፉ ቃል ነቢይም በሀገሩ አይከብረም። በገዛ ሀገሩ በኢትዮጵያ የቅኔ መዋረድና መድከምም በዚሁ አንጻር ነው ማለት ነው።

### 2ኛ መወድስ

እስከ አመ ጳውሎስ አም ወእስከነ 20፣
ምዕት ዕድሜነ ይሰሐብ ከመጊሜ።
ከንቱ ውእቱ ወኢረከበ ትርጓሜ።
ለአዳም ወለማቱሳላ ትምክሕቶሙ ዕድሜ።
እስመ ደክሙ ወዐዕረፉ፣ ተውኔተ ሳምናይ።
ዘመን ዘእንበለ ይብጻሕ ለፍጻሜ።
እመሎሙሂ ኢከፈሎሙ አምላከ ብዙኅ ሱላሜ።
ይጽንሑ ወይርአዩ ዘመነ ተሠያሜ።
ጳውሎስ ይኩን ለዓለመ ዓለም ቀዋሜ።
እስመ አጽገበነ በጊዜሁ ከራሜ ወኢከራሜ።

ትርጓሜውም እስከ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ሢመትና እስከ ሁለት ሺህ ዘመን ድረስ ዕድሜአችን እንደ ጉም ይሳብ ወይም ይጉተት ዘንድ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ የሆነው የአባታችን አዳም ዕድሜና ዘጠኝ መቶ ስልሳ ዘጠኝ የሆነው የማቱሳላ ዕድሜ ቢመኩበትም ከንቱ ነው፣ ትርጉምም የለውም። አዳምና ማቱሳላ የ8ኛውን ሺህ ዘመን የጨዋታ ፍጻሜ ሳያዩ ደክሟቸው ዐርፈዋልና። የዘመናትና የፍቅር አምላክም የተሾመውን ዘመን ፍጻሜ ለማየት እነሱን ባያድላቸውም ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ እንዲያድላቸውና ረዥም ዕድሜ እንዲሰጥልን እንጸልያለን፤ በዘመናቸው አሮጌውንም አዲሱንም አጣጣበውናልና ማለት ነው።

የቅኔ ትምህርት ከፍተኛ ትምህርት በመሆኑ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን ራሳቸው የአንድምታን ትርጓሜ በሚተረጉሙበት ወይም መጻሕፍትን በሚያኬዱበት ጊዜ በአስረጅነት ይጠቅሱታል።

ይኸውም፡-

‹‹ምንትኑ መንግሥት ከመታንክፉ መንግሥተ
ለብሂለ ነግሠ ፍጻሜሁ አኮኑ ብሂለ ሞተ››

የሚለውን የቀድሞ ቅኔ በሊቁ በዮሐንስ አፈወርቅ ተግሳጽ አተረጓጐም ላይ እንዳለ ባለቅኔ በለው ይጠቅሱታል።

‹‹ኦስመ እንዘቦ ሕያወ እሞተ ሥጋ ግዙፍ
ሞተ ዮሴፍ አኃዊሁ ነገርዎ ለዮሴፍ››

የሚለውንም ጥንታዊ ቅኔ በግብረ ሐዋርያት ትርጓሜ ላይ እንዳለ ባለቅኔ ብለው ይጠቅሱታል። ቅኔ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ መክፈቻ ከመሆኑም በላይ የድርሰት መለማመጃም ቅኔ ነው። ሲጀመር ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸው እንደ መልካ መልክና እንደ ዐርኬ፤ እንደ ነግሥ ያሉ በግጥምና በስድ ንባብ የተደረሱ ድርሰቶች ሁሉ በቅኔ አዋቂዎች የተደረሱ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ቅኔ የአእምሮ ማጎልመሻ፣ የመንፈስ ማደሻ በመሆኑም ዘወትር እንግዳ ድርሰት የሚያመነጭ አእምሮ እየጎለመሰ፣ ዘወትር እንግዳ ድርሰት የሚሰማ መንፈስ እየታደሰ ይሄዳል፣ ይህም በመሆኑ ነው በቅዱስ ያሬድ ፀዋትወ ዜማ በየፈርጁ እየገባ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ድርሰት የሆነው፡፡ ቅኔ በየቀኑ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ አዲስ ምስጋና ነው፣ አዲስ ምስጋናነቱም እንዲሁ እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውሃ ፈሳሽ ሳይሆን ከቅዱሳት መጻሕፍት የተገኘ ነው፣ ልብ ወለድ ድርሰት አይደለም፡፡ ይህም ይታወቅ ዘንድ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ‹‹ሰብሕም ለእግዚብሔር ስብሐተ ሐዲሰ እስመ መንክር ግብረ እግዚብሔር፣ ሰብሕም ለእግዚብሔር ስብሐተ ሐዲሰ፣ ስብሓቲሁ በማኅበረ ጻድቃኑ ማለት የእግዚአብሔር ሥራው አስደናቂ ነው፡፡ አዲስ ምስጋና አመስግኑት፣ ምስጋናው በማኅበረ ጻድቃን ነውና፣ እግዚብሔርን አዲስ ምስጋና አመስግኑት በማለት ጽፏል፡፡

# ክፍል 6

## የቅኔ ትምህርት ጠቃሚነት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት

በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ 1ኛ ቆሮ 14:26 ላይ ‹‹ወይእዜኒ ሶበ ትትጋብኡ ኮልክሙ ብክሙ መዝሙር፣ ወብክሙ ትምህርት ዘክሠተ አበይኖ፣ ዘነገረ በሐውርት ወምድራሳት፣ ወኮሎ በዘትትሐነጹ ግበሩ ለበቁዔት›› ማለት በምትሰበሰቡት ጊዜ ሁሉ በየቋንቋችሁ መዝሙር፣ ትምህርትና ድርሰት አላችሁ፣ እሱንም አእምሮአችሁን በሚገነባና በሚጠቅማችሁ መንገድ አድርጉት በማለት መዝሙርም ሆነ ግጥም፣ የቅኔ ድርሰትም ሆነ ሌላው ስድ ንባብ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና እግዚአብሔርን ለማመስገን ጠቀሚ መሆኑን አስተምሮናል፡፡

የቀድሞዎቹ የቅኔ ሊቃውንት የቅኔን ትምህርት ቀደም ሲል በተገለጸው ዓይነት በአምስት መቶ የተለያዩ መንገዶች መድበውና ቀምረው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውል ከማድረጋቸውም አልፈው ተርፈው ‹‹በአንድ ደንጊያ ሁለት ወፍ›› እንዲሉ ግሡ ወይም አንቀጹ የራሱን ፍችና ትርጓሜ እንደ ያዘ በአጫፋሪ ወይም በመስተዋምር ፊደል በመጠቀም ወይም አንዱን ፊደል ከግሡ ውስጥ ለይቶ በማውጣት እያንዳንዳቸው ፊደላት ለየራሳቸው ፍቺና ትርጓሜ እንዲኖራቸው በማድረግና ለእያንዳንዱ ነባር ቃል ሁለት ፍች በመስጠት እንዲሁም ዓይነስውር በመሪ እየተጐተተ እንደሚሄድ፣ ወይም ዓይናማው ሰው ሌላውን ዓይናማ ሰው እንደሚጐትተው ምሥጢራዊና ኅብራዊ የሆኑ ጉት የቅኔ መንገዶችንም በጭውውት መልክ ፈጥረዋል፡፡

እነዚህንም ጉት የቅኔ መንገዶች ጥቂቶችን ለዓይነት ያህል ከዚህ ቀጥለን አቅርበናቸዋል፡፡

‹‹ጊዜ ተሰቅለ ወልድ ፒርልዩ የሚል ሲሆን ትርጓሜውም ጌታችን እግዚአብሔር ወልድ በተሰቀለ ጊዜ ፀሐይ ጨልማለች፣ ጨረቃም ደም ሆናለች በአጠቃላይ ትርጉሙም ቀኑ ጠፍቷል ማለትም ጨልሟል በቅኔ ቤት ፒርልዩ የሚለው ነባር ቃልም ትርጉሙ ቀን ጠፋ የሚባል እሾሃማ የቆላ እንጨት ነው፣ ባለ ጉት ቅኔውም ሌላ ረዥም ዐረፍተ ነገር ሳያባክን ጊዜ ተሰቅለ ወልድ ፒርልዩ ማለት ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ቀን ጠፋ በማለት የእንጨቱን ቃል ባጭሩ ኅብራዊ ለሆነው ጉት ቅኔ ተጠቅሞበታል፡፡

መዓልተ ወሌሊተ ኮነ ፍቍርየ ወሌ የሰው ስም ነው ሌተ ማለት ደግሞ ለእኔ ማለት ነው፣ ወሌን ለብቻ ሊተን ለብቻ ተጠቅሞ ወሌ ለእኔ ቀን አይቶ ወይም ቀን ቢወጣ ወዳጄ ሆነ ማለት ነው፡፡

### ሌላው ጉት ቅኔ ደግሞ

‹‹ትቤላ በቃል ተክለሃይማኖት ቢፅየ››
ባሕቱ በክንፍ የዐብየኒ ኪያየ››

የሚል ሲሆን ትርጓሜውም ባለ ጉት ቅኔው ትቤላ በሚለው የሴት አንቀጽ ተጠቀሞ ላ የምትባለው ፊደል ተክለሃይማኖት ባልንጀራዬ ነው፣ በክንፍ ግን ይበልጠኛል አለች ማለት ሲሆን ሲራቀቅም ላ ፊደል አንድ እግሯ ሰባራ ነው፣ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ከገድላቸው ጽናት የተነሣ አንድ እግራቸው ተሰብሮ እንደ ላ ፊደል ስለሆነ ሁለቱን አመሳስሎ በጉባኤ ቃና ቤት መተቶ ጉት ቅኔውን አቅርቧል፡፡



### ሦስተኛው ጉት ቅኔ ደግሞ

‹‹ሐወጸ ሮጌል ወወልደ ነጐድጓድ መዋቲ የሚል ሲሆን
ክሳድየ እሁብ ለዘይፈትሐ ለዛቲ
ትርጓሜውም ሮጌል ማለት መቃብር ማለት ነው፡፡

ወንጌላዊው ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ ሞቶ አልተቀበረም ሀ የመጀመሪያ ፊደል ነው፣ ጸ ደግሞ በስተመጨረሻ ያለ ፊደል ነው፣ ባለ ጉት ቅኔው ሀ-ወጸ ጉበኝ በሚለው ግሥ ተጠቅሞ ወ የተባለውን ፊደል የሀናጸ አጫፋሪ በማድረግ መቃብርና ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ የሀንና የጸን ፊደላት ያህል የተራራቁ ናቸው በማለት ጉት ቅኔውን አራቆ፣ አመሥጥሮ አቅርቧል፡፡

እነዚህን ሦስቱን የጉት ቅኔ መንገዶች ለማሳየት ያህል ወይም ለዓይነት አቀረብናቸው እንጅ የቀድሞቹ የቅኔ ሊቃውንት በጭውውታቸው ወቅት እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በመባባል በግእዝም ሆነ በአማርኛ አመሥጥረውና አራቅቀው የሚያቀርቧቸው የጉት ቅኔ ዓይነቶችና መነገዶች እጅግ በርካታዎች ናቸው፡፡

ሀገረ ቅኔ በሆነችው በኢትዮጵያ የቅኔ ትምህርት እጅግ በጣም የተከበረና የተወደደ ነው፡፡ ክቡርነቱና ተወዳጅነቱም በካህናት ወይም በቤተ ክርስቲያን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ባሉት ኢትዮጵያውያን ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ባለው ወቅት ቅኔ የሚያውቁት ካህናቱ ብቻ ሳይሆኑ ነገሥታቱ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱም ጭምር ነበሩ፡፡

ተማሪዎች በትምህርት ላይ

የቅኔ ትምህርትና ዕውቀት የፆታ ልዩነትንም አይጠይቅም ነበር፡፡ የቅኔ ሙያ የወንድ አንቀጽ፣ የሴት አንቀጽ የሚል የሰዋስው አነጋገር ልዩነት ቢኖረውም በጠቅላላው የቅኔ ትምህርት የወንድና የሴት የፆታ ልዩነት የለም፡፡

ይህም በመሆኑ ነው ቀደም ባለው ወቅት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እነ እማሆይ ገላነሽን፣ እነ እማሆይ ለኪይደሉንና እነ ወ/ሮ ሃይማኖትን የመሳሰሉት ስመ ጥር የሴት የቅኔ መምህራት የነበሩት፣ ዛሬም ቢሆን እንደ ቀድሞ አይብዛ እንጅ ለምልክት ያህል በጥቂት አድባራትና ገዳማት የሴት የቅኔ መምህራት አልታጡም፡፡

በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ ብዙ ነገሥታትና መሳፍንት ቅኔ ያውቁ ነበር፣ እንዲያውም የቅኔ የመጀመሪያ ገጽ የሆነችውን ጉባኤ ቃናን በሱባኤ የደረሷት ንጉሡ ዐፄ በእደማርያም እንደ ሆኑ ቀደም ሲል ማተታችን አይዘነጋም፡፡ እነ ዐፄ እስክንድርም የቅኔ ባለሞያዎች ወይም ቅኔ አዋቂዎች እንደ ነበሩ፣ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ከደቀ እስጢፋ ጋር የተመላለሱት ቅኔ በጉልህ ያስረዳል፡፡

ምንት እገብረከ ቁንዕለ ገዳም አንተ ቤተ አንበሳ በዊአ፡፡
ኢትሰምዕኑ ጥህረቶ በአፍአ፡፡
እንከሰ ዘለከ ተጋንዮትከ ጠፍአ፡፡
ኃድግሰ ዘለከ ብዕአ፡፡
አንበሳ በኃይሉ እምድኃረ ሞአ፡፡
ጽንሖ ለአሳት ከዊነከ ብርአ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ትርጓሜውም አንተ የዱር ቀበሮ ከአንበሳ ቤት ትገባ ዘንድ ማነው ያደፋፈረህ ወይም ማነው የልብ ልብ የሰጠህ? በውጭ ሆነህ ጩኸቱን አትሰማምን? ለእኔ መገዛትህና እኔን መለማመጥህ ቀርቷልና፣ ይልቁንም ይህንን ከንቱ ምኞትህንና ብዕዓትህን ትተህ ወይም አቁመህ ብዕር ሆነህ ማለት ገለባ ወይም ጭድ ሆነህ እሣትን ጠብቀው ማለት ነው፡፡ በአንበሳና በእሳት የተመሰለ ንጉሡ አፄ እስክንድር ሲሆን በጫካ ቀበሮና በብዕር ወይም በገለባና በጭድ የተመሰለው ደግሞ ደቀ አስጢፋ ነበር፡፡

የጎንደር መንግሥት ተፍጻሜተ ነገሥት የነበሩት ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስም አሽከሮቻቸው መንግሥታቸውን ለመገልበጥ በተነሱባቸው ጊዜና ግልበጣውን ባከሸፉባቸው ጊዜ የተቀኟቸውን ቅኔያት ቀጥለን እንመልከት፡፡

...ሳእር ወዕዕ እለ በዝናም ልሕቁ፣
ለዝናም ዘአልሐቆሙ ከመ ይክልእዎ ተላጸቁ

ትርጓሜውም ሳርና እንጨት በዝናም አድገው ግድግዳና ክዳን በመሆን አሳዳጊያቸው ዝናምን ከቤት እንዳይገባ ከለከሉት ማለት ነው፡፡ ይህ ሰሙ ሲሆን ወርቁ ደግሞ ራሳቸው ንጉሡ በዝናም፣ አሽከሮቻቸው በሳርና በእንጨት መመሰላቸው ነው፡፡

ቀጥሎም ግልበጣው ከከሸፈ በኋላ እኒሁ ንጉሥ በተቀኙት ቅኔ
ምሰለ ሳእር ሳእር እመ የኅብር
ሠረገላ አይከውን ሳዕር

ጥሬ ትርጓሜውም ሳር ከሳር ጋር ወይም ሳርና ሳር ቢተባበር ምሰሶ ሊሆን አይችልም ማለት ሲሆን ለወርቁ ደግሞ አሽከሮቻቸው ሲተባበሩ ቢውሉ አንድ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን ሊያክሉ አለመቻላቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ብዙ ራሶችን ደጅ አዝማዞችም ቅኔ አዋቂዎች ነበሩ፡፡ ለአስረጂ ያህል የራስ ወልደ ገብርኤልን የግእዝ መወድስ ቅኔ ከዚህ ቀጥለን አቅርበነዋል፡፡

## የግእዝ መወድስ ቅኔ

ሥነ ጽጌ-ረዳ ዓለም እንተ ትትነገፈ፣ ወተነልፈ ቅዕበተ ኀልፈተ ጽላሎት ወሕልም፡፡
እመነ አሐዱ አፋኪ. እስመ ይወጽኡ ዮም፡፡
ለፈ ቡራኬ ወለፈ መርገም፡፡
ወምንተ ይኤድም፣ ዘመነነኪ. ወሖረ ፍኖተ አስቁጥስ ገዳም፡፡
አንሰ አረማዊ እንዘ ክርስቲያን በስም፡፡
ወለለጽባሑ በኃጢአት እንዘ ጽንአ ኃይልየ አደክም፡፡
ዘመንየ ኮሎ ፈጸምኩ እንበለ ጸሎት ወጾም፡፡
መዓልተ በመብልዕ ወሌሊተ በንዋም፡፡

ትርጓሜውም ፈጥነሽ የምትረግፊ፣ እንደ ጥላና እንደ ሕልም የምታልፊ አንቺ የጽጌረዳ አበባ ዓለም ሆይ ከአንዱ አፍሽ በአንድ በኩል በረከት በአንድ በኩልም መርገም ይወጣል፡፡ ንቆሽ ወደ ገዳመ አስቁጥስ የሄደም ምንኛ ያማረ ነው፡፡ እኔም በስም ክርስቲያን ስሆን አረመኔ ነኝ፡፡ በበዕለተ የተፈጥሮ ኃይሌን በኃጢአት ሳደክም ቀን በመብልዕ ሌሊት በእንቅልፍ ዘመኔን ሁሉ ያለጾምና ያለጸሎት ፈጸምኩት ማለት ነው፡፡

## በሌላውም ሥላሴ ዜማ ቅኔአቸው

ዓለም እስከ ጊዜሃ፣ በሐብለ ዝንጋዔ ትስሕበነ፣ ወታወርደነ ካዕበ ኀበዘቀዳሚ መርገም፡፡
ለዘተወለድነ በሥጋ ወደም፡፡
ዘአአማራሰ ማእምር ለባዊ፣ ለኀልፈተ ዛቲ ዓለም ፡፡
ፍዳ ወይን ይስተይ ማየ ዝናም፡፡
ወሀየንተ ልብስ ይትከደን ቆጽለ አእዋም፡፡
አስመ ዛቲ ጽላሎት ወሕልም፡፡





ትርጓሜውም ይህቺ ዓለም እስከ ጊዜዋ ድረስ በማዘናጋት ገመድ ትጐትተናለች፣ የዚህችን ዓለም ሕልፈት አውቃለሁ የሚል አስተዋይ ነኝ ባይም በወይን ፈንታ የዝናም ውሃ ይጠጣ፣ በልብስም ፈንታ ቅጠል ይልበስ፣ ይህቺ ዓለም ጥላና ሕልም ናትና በማለት የምናኔን ትምህርት አስተምረዋል፡፡

## የባለቅኔዎች ድፍረትና ሐቀኝነት

ባለቅኔዎች ወይም የቅኔ ሰዎች ደፋሮችና ቆራጦች ናቸው፤ የሚያስፈራቸው ነገር የለም፣ ነገሥታትንም ቢሆን አይፈሩም፡፡ አንድ አንድ ጊዜማ እግዚአብሔርንም አሻቅበው ለማዘዝ፣ ለመተቸትና ለመውቀስ ይደፋፈራሉ፡፡

ከጥንታውያን ባለቅኔዎች አንዱ በቅኔው ፈጣሪው እግዚአብሔርን ለማዘዝ ሞክሯል፡፡

ይኸውም፡-

‹‹ኮንኖ ኃጥአን ኮሎሙ ኢይደልዎከ ምንተ፡፡
አፍቅሩ ጸላዕተኮሙ እንዘ ትብል አነተ፡፡

ማለት አንተ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብለህ እያስተማርክ በኃጥአን ላይ መፍረድ አይገባህም›› ብሎ ተቀኝቷል፡፡

## ሌላውም ባለቅኔ

‹‹አነተሰ ወዳዊት እመ ትትአረቄ፡፡
ዳዊት ወኦርዮ ነገረ ቤርሳቤሕ ኢያኅለቀ፡፡
አክኑ ልቃሎሙ ፍትሐ ኢፈደይኮሙ በሕቁ፡፡
ለዳዊት ከመ ጌጋዩ ወለኦርዮ በከመ ጽድቁ፡፡

ትርጓሜውም አንተና ዳዊት በንስሐ ብትታረቁ ዳዊትና ኦርዮ የቤርሳቤሕን ነገር ገና አልጨረሱም፣ ለዳዊት እንደ በደሉ፣ ለኦርዮም እንደ ጽድቁ መጠን እውነተኛ ፍረዳቸውን አልሰጠኻቸውምና›› በማለት እግዚአብሔርን አሻቅቦ ወቅሶታል፡፡

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢም በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተቀጸል ጽጌ ዕለት በንጉሡ ፊት በተቀኙት የአማርኛ መወድስ ቅኔ

‹‹ሃይማኖተ አበው ኢኮነት ለባሕቲትነ፣
ዳዕሙ ይእቲ ለነባር ወለመጢ፡፡
ባሕቱ ሀገር ለባሕቲቱ ለቢጢ፡፡
ወእምዝ ንስእለከ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘትሰመይ አጢ፡፡
ቃልከ በቃልከ፣ ኀበ ወጽአ ይግባዕ እንበለ አሐቲ ውላጢ፡፡
መራርሂ ሀገሪትነ እንዘ በተፈጥሮ ሆምጣጢ፡፡
እመ ኢያከበረቶ ለቃልከ እምኢቦአ ጸንጠቆስጢ፡፡
ወዘይመስሎ ለዝንቱ እመ ኢሰበከ ለውጢ፣
ጥምቀተ ዳግማዊ እምኢተጠመቀነ በሸንቁጢ፡፡

በማለት ንጉሡ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያን ፈቅደው ባቋቋመበት ጊዜ ‹‹ አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት ግን የግል ነው›› ብለው የተናገሩትን ቃል እንዲያነሱ በድፍረት ጠይቀዋቸዋል፤ ሀገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው›› የሚለውን የንጉሡን ቃልም ‹‹ሃይማኖት የጋራ ነው፣ ሀገር ግን የግል ነው›› በሚለው ቅኔያቸው በድፍረት አስተባብለውታል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ቀደም ሲል በዐዒ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ደግሞ የአንኮበሩ ሊቅ የሚጣቅ ዐማኑኤል ደብር አለቃ የደብር እልቅናቸው ለጠንቋይ ወይም ለመጽሐፍ ገላጭ ተሰጥቶባቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የአማርኛ ምርምር ቅኔ በግጥም መልክ በድፍረት አቅርበው እልቅናቸውን አስመልሰዋል፡፡

ይኸውም፡-

በባሕር ዝንጀሮ በገደል ላይ ዓሣ፡፡
መቅደስ ለዛር ፈረስ ነጋሪት ለአንካሳ፡፡
ጌታዬ መንግሥትህ ተበላሽቷል እሳ፡፡

የሚለውን ቅኔያዊ ግጥም በድፍረት አቅርበው እልቅናቸውን እንዳስመለሱ ይነገራል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያመለክተውና የሚያስገነዝበው የባለቅኔን ቆራጥነትና ድፍረት፣ና ግልጽነትና ሐቀኝነት እንዲሁም ባለቅኔ የተሰማውን ነገር ሁሉ ለነገ የማይል፣ የተደበቀውን ምሥጢርና ሐቅ የሆነውን ነገር ሁሉ ግልጥልጥ አድርጉ የሚናገር ወይም ይፋ የሚያወጣ መሆኑን ነው፡፡

# ክፍል 7

## የጠቅላላው ቅኔያት ይትበሀል ዓይነት ከጸዋትወ ዜማ ጋርም ያላቸው ቁርኝት

ከሁለት ቤት እስከ ዐሥራ አንድ ቤት እየመቱ የሚሄዱት ጠቅላላው ቅኔያት ለየራሳቸው የሚያሳዩትን ልዩ ልዩ ባሕርያት፣ ይትበሀልና ዓይነት፣ ከጸዋትወ ዜማ ጋር ያላቸውን ቁርኝትና የዜማ ስልት ከዚህ ቀጥለን ለማሳየት እንሞክራለን፡፡

**ጉባኤ ቃና** ጉባኤ ቃና ማለት የራሱ ምሥጢርና ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ ከዘአምላኪያ ጀምሮ እስከ ዕጣነ ሞገር ድረስ ባሉት በየአንዳንዳቸው ቅኔያት በመካከል፣ በመነሻና በመድረሻው ሁሉ እየገባ የሚያገለግል ስለሆነ የቅኔዎቹ ሁሉ ስብስብ ወይም ክምችት ማለት ነው፤ ወይም ሁለገብ ቅኔ ተብሎ ሊተረጉም የሚችል የመጀመሪያ ቅኔ ነው፡፡\

**ዘአምላኪያ** ዘአምላኪያ የሚለው የቅኔ ዓይነት "አምላኪያ አምላኪያ እገይስ ኀቤከ" ተብሎ በመዝሙረ ዳዊት 62 በሚጀመረው ያሬዳዊ መዝሙር እየገባ ስለሚያገለግል ወይም እግዚአብሔር ስለሚመሰገንበት ዘአምላኪያ ሊባል ችሏል፡፡

**ሚበዝኑ** ሚበዝኑ የሚለው የቅኔ ዓይነት በ3ኛው መዝሙረ ዳዊት እግዚኦ ሚበዝኑ በሚለው ላይ አገልግሎት የሚሰጥ ስለሆነ ሚበዝኑ ተብሎ ሊሰየም ችሏል፤ ወይም ተሰይሟል፡፡

**ዘይሌቡ** ዘይሌቡ የተሰኘው የቅኔ ዓይነት ደግሞ "ብፁዕ ዘይሌቡ በሚለው በ40ኛው መዝሙረ ዳዊት እየገባ አገልግሎት የሚሰጥ ስለሆነ ዘይሌቡ ተብሎ ሊሰየም ችሏል፡፡

**ዋዜማ** ዋዜማ የተባለው የቅኔ ዓይነትም አብዛኛውን ጊዜ በክብረ በዓላት ዋዜማና የዋዜማ ዓይነት ባላቸው መዝሙራት /ቀለማት/ እየገባ የሚደርስ ስለሆነ ዋዜማ ተብሏል፡፡

**ሥላሴ** ሥላሴ ቅኔ የተሰኘው የቅኔ ዓይነትም ይትባረክ በተባለው ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ በ3ኛው መስመር ላይ የእየገባ የሚደርስ ስለሆነ ሥላሴ የሚለውን ስያሜ ሊያገኝ ችሏል፡፡

**ዘይእዚ** ዘይእዚ የተባለው የቅኔ ዓይነትም በስብሐተ ነግህ አገልግሎት ጊዜ "ይእዚ ትስዕር" በሚለው ጸሎተ ስምዖን ላይ ስለሚገባ ወይም እየገባ ስለሚያገለግል ዘይእዚ ተብሏል፡፡

**ሣህልከ** ሣህልከ የተባለው የቅኔ ዓይነት በዕለተ እሑድ በመወድስ አደራረስ ጊዜ ከ50ኛው መዝሙረ ዳዊት በኋላ "ሣህልከ እግዚኦ" በሚል መነሻ ስለሚቀርብ ሣህልከ ተብሏል፡፡ ሣህልከ በተለይ ለሀገርና ለሀገር መሪ ብቻ የሚቀኙት ቅኔ ነው፡፡





**መወድስ** መወድስ የተባለው የቅኔ ዓይነትም "ፍታሕ ሊተ" በሚለው በ42ኛው መዝሙረ ዳዊትና መወድስ በተባለው የአደራረስ ሥርዓት ላይ የሚገባ በመሆኑ መወድስ የሚለውን ስያሜ ሊያኝ ችሏል፡፡

**ኩልክሙ** ኩልክሙ ቅኔ ደግሞ ኩልክሙ በተሰኘው በ46 መዝሙረ ዳዊት እየገባ ስለሚያገለግል ኩልክሙ ተብሎ በመዝሙሩ ስም ተሰይሟል፡፡

**ክብር ይእቲ** ክብር ይእቲ የተባለው የቅኔ ዓይነትም በዕርገተ ቍርባን ጊዜ በ149 መዝሙረ ዳዊት ቍጥር 9 ላይ "ክብር ይእቲ ዛቲ ለኩሉ ጻድቃኑ" የሚለው መዝሙር ከቅኔው ቀጥሎ ስለሚዘመር ቅኔውም ክብር ይእቲ ሊባል ችሏል፡፡

**ዕጣነ ሞገር** ዕጣነ ሞገር የተሰኘው የቅኔ ዓይነትም ከዕርገተ ዕጣንና ከዕርገተ ቍርባን በኋላ የሚደርስ ቅኔ በመሆኑ ዕጣነ ሞገር የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

## የጠቅላላው ቅኔያት መጠንና ስያሜ

**ጉባኤ ቃና** ጉባኤ ቃና ሁለት ቤት ነው፡፡ ሁለት ቤት መሆኑ የመለኮትና የትስብእት ምሳሌ ነው፤ አንድም የመርዓዊና የመርዓት፣ የጌታና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነው፡፡ አንድም የቃና ውኃ ፊት ውኃ ኋላ ወይን የመሆኑ ምሳሌ ነው፤ አንድም የመርዓዊ ወይንና የጌታ ወይን ወይም የውኃውና የወይኑ ምሳሌ ነው፡፡ ጉባኤ ቃና ከአረፍተ ወይም ከአረፍተተ ነገሩ ጋር አራት ይሆናል፤ የኪሩቤል ምሳሌ ነው፤ በኪሩቤል አድሮ የሚመሰገን ጌታ ከሠርግ ቤት ተጠርቶ ውኃውን ጠጅ የማድረጉ ምሳሌ ነው፡፡

**ዘአምላኪያ** ዘአምላኪያ ሦስት ቤት ነው፤ ዘአምላኪያ ማለት የጌታ ምስጋና ማለት ነው፤ የጌታ ምስጋና እንዲህ ነው ለማለት ዘአምላኪያ ተባለ፣ ዘአምላኪያ ሦስት ቤት መሆኑ የእግዚአብሔር የሦስትነቱ ምሳሌ ነው፣ በሌላ በኩልም በስብሐተ ነግህ አደራረስ ጊዜ በዘአምላኪያ እየገባ በመነገሩ ነው፡፡ ቀለሙ አለመለወጡ የጌታ የአንድነቱ ምሳሌ ነው፡፡ በዓበይት በዓላት ስብሐተ ነግህ ሲደርስ የሚደረሱት ጉባኤ ቃናና ዘአምላኪያ ናቸው፡፡ ሰኞ ማክሰኞ ሐሙስ ግን የሚደርሰው ዘአምላኪያ ነው፡፡

**ሚበዝኑ** ሚበዝኑ ሦስት ቤት ነው፡፡ ሦስት ቤት መሆኑም የጌታ የሦስትነቱ ምሳሌ ነው፡፡ ሚበዝኑ ከአነሐረጉ ስምንት ይሆናል፡፡ የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ምሳሌ ነው፡፡ ሚበዝኑ የተባለበትም ምክንያት በሦስተኛው መዝሙር እየገባ በመድረሱ ነው፡፡

**ዋዜማ** ዋዜማ ማለት በሠርክ የሚደርስ መሥዋዕተ ስብሐት ማለት ነው፡፡ ዋዜማ ቤቱ አምስት ነው፤ አምስት መሆኑ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ምሳሌ ነው፡፡ ዋዜማ ከእነ ሐረጉ አራት ነው፡፡ የአራቱ መላእክት አምሳል ነው፡፡ ጌታ በዕለተ ዓርብ በተሰቀለ ጊዜ ከጎኑ እንደ ለ ፈደል ሆኖ ጥሩ ውኃ፡፡ ጥሩ ደም ፈስሷል፡፡ ይህንንም ደም አራቱ መላእክት በጽዋዐ ብርሃን ተቀብለው በአራቱ ማዕዘን ረጭተውታል፡፡
አንድም ዋዜማ አምስት ቤት መሆኑ፡-

1. በዘንዚከር
2. አንቀጸ ብርሃን
3. ቅዱስ እግዚአብሔር /ኪዳን/
4. ድንግ ማለት ዋዜማው /ኢኀደጋ ለምድር/
5. ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ ከተባለ በኋላ የሚደረስ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላም በኩል አምስት ቤት መሆኑ ከአራቱ ባህርያተ ሥጋ፣ ከአምስተኛው ባሕርየ ነፍስ ለተፈጠርኩት ይህን ምሥጢር ገለጸልኝ ለማለት ነው፡፡ አንድም የአምስቱ ቅንዋተ መስቀል፣ የአምስቱ ማህፈዳት ምሳሌ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## ነዋ በበግዑ ተብሎ በሚመለጠነው ምልጣን የገባ ቅኔ

አመ ርእየ ወንጸረ፣ ነደ መላኮት ሰይፈ በእደ ሚካኤል መንፈስ
ሰናክሬም መጥምቀ ነዳዲ ዘአኮ ጽኑስ
ዘምስለ ሦርሶር ኢዮብ ኮናኔ ሕማም ነፍስ
ንዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ሰነኮሪስ
ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ንጉሥ

ሥላሴ ማለት ሦስተኛ እየሆነ የሚገባ ማለት ነው፡፡ ሥላሴ ስድስት ቤት መሆኑ በስድስቱ ይትባረክ መግባቱ ነው፡፡ ወይም በይትባረክ የመመራቱ ምሳሌ ነው፡፡ ስድስት ቤት መሆኑ የስድስቱ ቃላተ ወንጌል አምሳል ነው፡፡ ሥላሴ መባሉ በዋዜማ በስብሐተ ነግህ፣ በአርያም የመደረሱ አምሳል ነው፡፡
ዘይእዜ አምስት ቤት መሆኑ በስብሐተ ነግህ በአራት ምእራፍ፣ በአራት ጉባኤ ቃና፣ በአምስተኛው ራሱ መደረሱ ነው፡፡

መወድስ ስምንት ቤት ነው፤ ስምንት ቤት መሆኑ የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ምሳሌ ነው መወድስ የእሁድ ምስጋናም ማለት ነው፡፡

| | |
|---|---|
| መዝሙር | 1 |
| አምላኪየ | 2 |
| ሚበዝኑ | 3 |
| ቃልየ | 4 |
| ጸኒሐ | 5 |
| ብፁዕ ዘይሴቡ | 6 |
| ከመ ያፈቅር | 7 |

ፍታሕ ሲተ 8 በስምንተኛው መዝሙር ለመደረሱ አምሳል ነው፡፡ መወድስ 15 ጊዜ መጸፋቱ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ 15 ምእራፍ ይሆናል፡፡ የዚህ አምሳል ነው፡፡ አንድም ጌታን መስቀሉን አሸክመው እያጣደፉ ሲወስዱት 15 ጊዜ ወድቋል የዚህ አምሳል ነው፡፡

## ሣህልከ ቅኔ

ሣህልከ ቅኔ በንጉሡ ብቻ ወይም በሀገር ብቻ የሚቀኙት ነው፡፡ ሣህልከ ቅኔ 24 ጊዜ ይመላለሳል፡፡

1 ተሣህልከ
2 እግዚኦ ፀወነ ኮንከነ
3 እግዚኦ ኮነኔከ
4 ግነዩ
5 የበዓሉ ምስባክ
6 መዝሙር
7 ዘአምላኪየ
8 እግዚኦ ሚበዝኑ
9 ቃልየ
10 ጸኒሐ
11 ብፁዕ ዘይሴቡ
12 ከመ ያፈቅርን በመላው ቆጥሮ 24 ይሆናል፡፡ የዚህ ምሳሌ ነው፡፡ ቤቱ ሦስት መሆኑ ጌታ በሦስተኛው ቀን የመነሣቱ ምሳሌ ነው፡፡ አንድም የሦስቱ የትንሣኤ ድርሰቶች ምሳሌ ነው፡፡ ሦስቱ ድርሰቶች አርያም፣ መወድስ፣ ስብሐተ ነግህ ናቸው፡፡

ዕጣነ ሞገር ድጓ ሲሆን መሪ ተመሪ ይጮኹታል፡፡ ቅኔ ሲሆን ግን መሪ እየነገረ ተመሪ ብቻ ይጮኸዋል፡፡ መሪ ለተመሪ መንገሩ ክቡር ነገር ነው፡፡ ስብሐተ መላእክትን፣ ሞተ ለማዕታትን፣ ሞተ ጻድቃንን፣ ሞተ ክርስቶስን፣ ራሱ አውቆ ለሰው ማስረዳቱ ነው፡፡ እርሱ ክብር ይእቲን መናገሩ ማዜሙ





የክርስቶስን ሞት አስቦ አውቆ ለሰው ማስረዳቱ ነው፡፡ መሪው ክብር ይእቲን መናገሩ የክርስቶስን ሞት ተረድቶ ማልቀሱ ነው፡፡ ተቀባዮች የተረዷው ምሳሌ ናቸው፡፡ ክብር ይእቲ ለጌታ ብቻ ነው፡፡ ሲጨርስም ሃሌ ሉያ ማለቱ ሎቱ ስብሐት ማለት ነው፡፡ ዕጣነ ሞገር ማለት ማሳረጊያ ማለት ነው፡፡

## የቅኔ ዜማ

ቅኔ ስንኝ፣ ልክና ስፍር ወይም መጠን ያለው ሲሆን ዜማውም ቅዱስ ያሬድ በደረሰው የዜማ ግእዝ፣ አራራይና ዕዝል ተብሎ ይጠራል፡፡ ይኸውም በአደራረሱ ሥርዓትና በወቅት የተወሰነ ነው፡፡ ዘአምላኪየና ሥላሴ የተሰኙት ቅኔያት ምንጊዜም ዜማቸው ዕዝል ነው፤ ለውጥ የላቸውም፡፡ ዋዜማ የተሰኘው ቅኔ ደግሞ ዜማው ምንጊዜም አራራይ ነው፣ ለውጥ የለውም፡ ሚበዝኑና ዘይሴቡ፣ ዘይእዜና ሣህልከ፣ መወድሰና ኮልክሙ የተሰኙት ቅኔያት ደግሞ ዜማቸው ምንጊዜም ግእዝ ነው፡፡ ጉባኤ ቃና፣ ክብር ይእቲና ዕጣነ ሞገር የተሰኙት ቅኔያት እንደ ወቅቱ ሁኔታ በግእዝና በዕዝል ይዜማሉ፡፡

## የቅኔ ትምህርት አሰጣጥ

በቅድሚያ ተማሪው ግሥና ነባር ቃል በቃሉ እንዲያጠና ይደረጋል፣ ተማሪው በቃል ያጠናው ግሥ እየተነገረው መምህሩ ግሡን ያወርዳል፣ ወይም ያዘምታል፣ ግሥ የማውረዱ፣ ወይም የማዝመቱ መርሐ ግብር እንደተከናወነ መምህሩ ለተማሪዎቹ እንደየደረጃቸው ቅኔ ይዘርፍላቸዋል፤ የዘረፈውንም ቅኔ ይፈታላቸዋል፣ ምሥጢሩን ያራቅቅላቸዋል፣ ቅኔ ይቈጥሩበት ዘንድ እንደ ነገ የሚውለውንም በዓል ታሪክ ይተርክላቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነውም በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ነው፡፡

ከዚያም ተማሪዎቹ መምህሩ እንደየደረጃቸው የዘረፈላቸውንና የፈታላቸውን ቅኔ ይቀጽላሉ፣ እርስ በራሳቸውም ይቀጻጸላሉ፣ /ይማማራሉ/ የሚከብዳቸው ከሆነም ከለየው ተማሪ ጠጋ ብለው ይቀጽላሉ፣ ያጠናሉ፣ የለየው ተማሪ እንዲያስቀጽላቸውና እንዲያስጠናቸውም በመምህሩ ይታዘዛል፣ ለአያንዳንዳቸው ጀማሪ ተማሪዎችም አስቀጻይ ባልደረባ ይሰጣቸዋል፡፡ ባልደረባቸውን ለምኖ እስከ ማብላት ድረስ ማክበርና መንከባከብ ደግሞ የተማሪዎቹ ድርሻ ይሆናል፡፡

የተማሪ ማደሪያ ገጽ

በማግስቱ ተማሪዎቹ መምህሩ በዘረፈላቸውና በቀጸሉት ቅኔ መጠን እንደየደረጃቸው ሲቆጥሩ ይውሉና ወደማታ፣ የቀናቸውም ማለት ትጉሆቹና የገባቸው በእኩለ ቀንም ቢሆን ለመምህሩ አመቺ በሆነው ሰዓት የቁጠሩትን ለመምህሩ እየነገሩ ያሳርማሉ፡፡

በዚህ ዓይነት ደረጃ በደረጃ ተምረው በዓመት በሁለት ዓመት ፈጣኖቹም ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቤት ሞልተው ይቀኛሉ፡፡ ከዚያም ትንሽ ካበሰሉት በኋላ ወደ አገራቸው ይገባሉ፤ ለአገልግሎትም ይሰማራሉ፡፡ አንድ አንዶቹም በመቆየት እስከ ዘረፉ ይደርሳሉ፤ ከዘረፉ በፊትም ግልበጣ የሚባል ትምህርት አለ፡፡ መምህሩ የዘረፈውን ቅኔ ገልብጦ መቀኘት ማለት ነው፡፡ እንዲህ እያለ ከዘረፉም አልፈው በመምህርነት ተመርቀው፣ እንዲሁም ከሁለት ከሦስት መምህራን ሙያውን አስፋፍተውና አጠናክረው ወደ አገራቸው ገብተው ወይም እግዚአብሔር በፈቀደላቸው ቦታ ወንበር ዘርግተው ያስተምራሉ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ቅኔ ሥነ ቃል አይደለም ከሕዝባዊ ቅኔም የተለየ ነው፡፡

የቅኔ ትምህርት አሰጣጥ ከዚህ በላይ በመጠኑ በተዘረዘረው ዓይነት የመማር ማስተማሩ ጀምሮ በቃል ብቻ የሚሰጥ በመሆኑ የዘመኑ ምሁራን ሥነ ቃል ነው ብለው ፈርጀውታል፡፡ ነገር ግን ቅኔ መምህር፣ ት/ቤት፣ ደቀመዝሙር ስለአለው፣ በዓይነትና በመጠንም ተመጥኖ ደረጃ በደረጃ እንደየተማሪው አቅም ከጉባኤ ቃና ወደ ዘአምላኪያ፣ ከዘአምላኪያ፣ ወደሚበዝኑ፣ ከሚበዝኑ ወደ ዋዜማ፣ ከዋዜማ ወደ ሥላሴ፣ ከሥላሴ ወደ ዘይእዜ፣ ወደ መወድስ ከመወድስ ወደ ክብር ይእቲና ወደ ዕጣነ ሞገር እየተሸጋገረ የሚሰጥ ትምህርት ስለሆነ ሥነ ቃል ሊሆን አይችልም፡፡

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅኔ በትምህርት ስለሚሰጥና ለስንኙም ሥርዓትና መጠን ስለተበጀለት፣ እንዲሁም የዜማ ዓይነት ስለአለው ማንም ሰው ወደ ቅኔ ት/ቤት ሳይገባ ሊደርሰው፣ ሊገጥመው ወይም ሊቀኘው አይችልም፡፡ ይህም በመሆኑ ከሀገር ውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ በአጠቃላይም ከሌላው ሕዝባዊ ቅኔ ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡

# ክፍል 8

## የቅኔ ትምህርት ቤት ምንጩ እንዳይደርቅ ወደፊት ምን መደረግ አለበት?

የቅኔ ትምህርት ፈጣሪዎችና ባለቤቶች የሆኑትን እነ ቅዱስ ያሬድን፣ እነ ዮሐንስ ገብሳዊንና እነ ተዋነይን ሌሎችንም ያፈራቸው ሀገረ ቅኔ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በቅኔ ት/ቤት በኩል ያለውን ይዞታዋን ሲመለከቱት ከአንድ ትውልድ ዘመን በኋላ ‹‹ኢትዮጵያ በርካታ የቅኔ ፈጣሪዎችና የቅኔ ጉባኤ ቤቶች የነበሩባት ሀገረ ቅኔ ነበረች›› ተብሎ የሚተረክላት አገር እንዳትሆን ታላቅ ሥጋት አለ፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ የተዘረጋው ሥርዓተ መንግሥት ወቅቱ ያስከተለውን የኑሮ ጫና ተገንዝቦ ለመላው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ተመጣጣኝ ዋጋ በመክፈል ባደረገው ዕድገትና መሻሻል አንጻር ለጥቂት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሠራተኞችና ለየአህጉረ ስብከቱም ሠራተኞች ጭምር እንደየ ሙያቸውና እንደየ አገልግሎታቸው የደመወዝ እስኬል ተበጅቶላቸው ገባሕተ ነግህም ሆነ ገባሕተ ሠርክ በመጠኑም ቢሆን የሙያቸውንና የአልግሎታቸውን ዋጋ አግኝተዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ ጀምሮ በአህጉረ ስብከት ዋና ዋና ከተሞች የሚገኙት የአድባራትና የገዳማት አገልጋዮች ካህናትም በሙያቸውና በአገልግሎታቸው መጠን በቂ ደመወዝ እየተከፈላቸው ነው፡፡ አብዛኛዎቹም ከሙያና ከአገልግሎት ውጭ ‹‹ለዘረከቦ ይርከቦ›› በማለት የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት ያለ አግባብ እንደ ቅርጫ ሥጋ ሲቃረጡት ወይም ሲቀራመቱት ይስተዋላል፡፡ የአብነት መምህራኑ ግን የደመዝ እስኬል አልተበጀላቸውም፣ እነሱ ፊደል ያስቁጠሩአቸው የአንድ ተራ ቂስና ዲያቆን ደመወዝ ያህል ሊከፈላቸው ይቅርና የአንድ ደብር ዐቃቤት ያህል እንኳን ደመወዝ አይከፈላቸውም፡፡ ይህም በመሆኑ በአሁኑ የሥልጣኔ ወቅት እንደ ጥንቱ የሚያስለምን መንደር ባለመኖሩና በልመና ቀራኒ መተዳደሩም አስነዋሪና አሳፋሪ ተግባር መስሎ በመታየቱ ትንሽ እህል መቃመስ የሚቻለውም በአዲስ አበባ ከተማ መሆኑን በመስማታቸው ሁሉም የአብነት መምህራን እንደ ለመዱት በቀን አንድ ጊዜ እንኳን መመገብ አቅቷቸው አክፍሎቱ ስለጠናባቸው ትንሽ እህል መቃመስ የሚቻለውም በአዲስ አበባ ከተማ መሆኑን በመስማታቸው ጉባኤ ቤታቸውን እየዘጉ፣ ወንበራቸውን እያጠፉ ነፍሳቸውን ለማትረፍ ሲሉ ወደ ከተማ በመፍለስ ወይም በመጉረፍ ላይ ናቸው፡፡

በሥልጣኔውም ሆነ በኑሮ ውድነቱ ምክንያት ለተማሪዎቹ የሚያስለምን መንደር በመታጣቱና ለመምህራኑም ቀለብ የሚሰፍር ገበሬ በመጥፋቱ፣ የሰበካ ጉባኤ አስተዋጽኦም ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው ከከተማ ካህናት አልፎ ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ አገልጋዮች ካህናት ለመዝለቅ አቅሙ ስለ አልፈቀደለት ወይም ጉልበት ስለ አነሰው የገጠሪቱ ኢትዮጵያ የአብነት መምህራን ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰቱን በነፍስ ወከፍ ተያይዘውታል፡፡

የአሁኑዎቹ የአብነት መምህራን ረኃብ ከቀድሞዎቹ የባሰ ይሁን እንጂ የቀድሞዎቹ የአብነት መምህራንም ቢሆኑ አሁን ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበትን ስብሐተ እግዚአብሔር ለአሁኖቹ ካህናት ሊያስተላልፉ የቻሉት በረኃብ አለንጋ እየተገረፉ ያለደመወዝና ያለ አፈሪ ቤት ተመሪውና አስቀጣሪው



ለመሆኑ ቀደም ባለው ወቅት የነበሩት የአብነት መምህራንና ደቀ መዛሙርቶቻቸው በግእዝና በአማርኛ የተቀኟቸው አንድ አንድ ቅኔዎች ያስረዳሉ፡፡ ለማስረጃም ያህል ጥቂቶቹን ቅኔዎች ከዚህ ቀጥለን አቅርበናቸዋል፡፡

ዋድላ የቅኔ ምንጭ (መሠረት) መሆኑ ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ስመ ጥሩው የቅኔ አብነት የነበሩት ዋድሌው አለቃ ሲራክ ስለ አብነት መምህራን ደመወዝ ከሙያቸው ጋር ተመጣጣኝ አለመሆን በተቀኙት ቅኔ ቁጭታቸውን ሲገልጹ፤

አአዱግ ወበቅል እነዘ ያወጽኡ ስልሳ፡፡
ሲራክ አምላክ ዋድላ ተሰይጠ ለሰላሳ፡፡

ማለትም አህያና በቅሎ ስልሳ ስልሳ ብር ሲያወጡ ወይም ሲሸጡ የዋድላ አምላክ ሲራክ በሰላሳ ብር ተሸጠ በማለት ምፀትና አሽሙር ቅኔ ተቀኝተዋል፡፡

ይህ ቅኔ በአንድ በኩል ምፀት የተባለበት ምክንያት አለቃ ሲራክ በዕውቀታቸው ራሳቸውን በራሳቸው ከፍ ከፍ አድርገው የዋድላ አምላክ በማለታቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ያልተማረ ሰው በምሁራን ዘንድ ከእንሰሳት ተለይቶ ስለማይታይ አህያና በቅሎ በመጠቀሳቸው ነው አሽሙር ቅኔ የተባለው፡፡ በዚያም ሆነ በዚህ ቅኔው የሚያስረዳው ከጥንት ጀምሮ የአብነት መምህራንን ወጋ ማጣትና በችግር መቆራመድ ነው፡፡ በሌላ በኩልም የቅኔ ደቀመዛሙርት የደረሰባቸውን ረኃብና ችግር አስመልክተው በተለያየ ቦታና ጊዜ ባቀረቡአቸው ተመሳሳይ የግእዝና የአማርኛ ቅኔያት፣

አንዱ የቅኔ ደቀመዝሙር፡-

‹‹ረኃብሂ ገጸ ወጨፎ በገባ ጊዜ ከአንጀቴ፡፡
ንዑ ክዳናትየ እናቴ ወአባቴ፡፡
በማለት ሲቀኝ ሌላው የቅኔ ደቀ መዝሙር ደግሞ፤
‹‹መብልዕየሂ ዜና መብልዕ ዘያመጽኦ ነፋስ፣
ወልብስየ ከመዶርሀ እምላዕለ አብራክየ እለብስ፤››
በማለት ተቀኝቷል፡፡

ትርጓሜውም የዘወትር ምግቤ ነፋስ የሚያመጣው የሀብታም የምግብ ሽታ ነው፣ ልብሴንም እንደ ዶሮ ከጉልበቴ በላይ እለብሳለሁ ማለት ነው፡፡

አርቲስቱ ዓለማየሁ እሸቴም
‹‹ዋጎረቤት ምግብ እያሸተትሽ ኑሪ፤
ለመብላት መብት የለሽ መቼም አትጠሪ፤››
በማለት ይህንኑ ቅኔ ነው በጨዋታው ደግሞ የተቀኘው፡፡

ያም ሆነ ይህ ከዚህ በላይ የቀረቡት የግእዝና የአማርኛ ቅኔዎች የሚያስረዱን የጥንቶቹ የአብነት መምህራን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ያስተማሩትና የተማሩት፣ የጥንቶቹ የቆሎ ተማሪዎችም የተጸሉት በተለያየ ቦታና ጊዜ የደረሰባቸውን ረኃብና ልዩ ልዩ ችግር በሰፊ ትእግስት ተቋቁመው መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ የጥንቶቹ የአብነት መምህራንም ሆኑ የቆሎ ተማሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የተማሩትና ያስተማሩት ከዚህ በላይ የተገለጸውን ረኃብና ችግር በትዕግሥት ተቋቁመው ሲሆን፣ በጊዜው ለውጥ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ረኃቡና ችግሩ እጅግ በጣም የተባባሰ በመሆኑ መምህራኑ ጉባኤ ቤታቸውን እየዘጉ፣ ወንበራቸውን እያጠፉ፣ ደቀ መዛሙርቱም መምህራኑን ተከትለው ወይም እየከዱ ከገጠር ወደ ከተማ እየፈለሱ መምጣት ግድ ሆኖባቸዋል፡፡

ጥቂት የአብነት መምህራን ነፍሳቸውን ለማትረፍ የቻሉት በዚህ ዓይነት ዘዴ ሲሆን ‹‹ነፍሳችንን ለማትረፍ ብለን ከዓላማችን ውጭ በአታችንን አንለቅቅም፣ ጉባኤ ቤታችንን አንዘጋም፣ ወንበራችንንም አናጥፍም›› በማለት በየአሉበት ከእነ ደቀመዛሙርቶቻቸው በረኃብና በበሽታ ያለቁትን የአብነት መምህራንማ ቤት ይቁጠራቸው፡፡

ይሁን እንጅ ነፍሳቸውን ለማትረፍ ወደ ከተማ ከፈለሱትም የአብነት መምህራን ውስጥ ቢሆን የእጅ መንሻ ያላቸውና ወገን ያጋጠማቸው ወይም እጸድቅ ባይ የወተፋቸው ጥቂት መምህራን በአንድ አንድ ደብር ሲወተፉ አብዛኛዎቹ የአብነት መምህራን ግን የመንደር ሕዛናት ፊደል አስቆጣሪና የሀብታም ዘበኞች በመሆን፣ ብዙዎቹም በጎዳና ተዳዳሪነትና በልመና ተግባር ተሰማርተው የዕለት ምግባቸውንና የዓመት ልብሳቸውን ስለሚያገኙ ቤተ ክርስቲያንን የጎብረተሰቡ መዘባበቻ አድርገዋታል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

በእጅ መንሻም ይሁን በወገን እንዲሁም በእጸድቅ ባዮች በአንድ አንድ ደብሮች የመወተፍ ዕድል የገጠማቸውም የአብነት መምህራን ቢሆኑ በሙያቸው እንዳያስተምሩ የሚማር ተማሪ ስለአላገኙ፣ የጉልበት ሥራ እንዳይሠሩ የማምረቻ ድርጅት ወይም ተቋም ባለመኖሩ፣ እንዳይቀድሱና እንዳይሠልሱም አብዛኛዎቹ የአብነት መምህራን ሥልጣነ ክህነት ስለሌላቸውና በብሕትውና ወይም በስውር ድንግልና የሚኖሩ በመሆናቸው፣ ሥልጣነ ክህነት ያላቸውም ቢሆኑ ሥልጣነ ክህነታቸው እንዲገለጽባቸው የማይፈልጉ በመሆናቸው ከተራ ሰሞነኛ ጋር ተመድበው ሰዓታት ቋሚ በመሆንና በየመንደሩ እየሄዱ በጸሎተ ፍትሐት ተሳታፊነት የተመደበላቸውን ወርሐዊ ደመወዝ ማግኘት ግዴታቸው ሆኗል፡፡

ጥቂቶቹም ተማሪ አልባ ወንበር ዘርግተው የማስተማሪያ መጽሐፋቸውን ሲያገላብጡና የወንበራቸውን ዓይን ዓይን በማየት ብቻ ሲመሽ ሲነጋ ወሩ ይገባደድላቸውና የወር ደመወዛቸውን እየተሸማቀቁ ይወስዳሉ፡፡

በቅርቡም የአዲስ አበባ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ካህናት በጎጃም ሀገር በማስተማር ላይ የሚገኙትን ስመ ጥሩውን የቅኔ መምህር የኔታ ያሬድን አስመጥተው እንዲያስተምሩ በብር600.00/ ስድስት መቶ ብር/ ቢቀጥሩአቸው "ከእናንተ ብር600.00/ስድስት መቶ ብር/ 600 ደቀመዛሙርት ይሻሉኛል" በማለት ወደበአታቸው ተመልቀው ሄደዋል፡፡

እነዚህ ታላላቅ የአብነት መምህራን ከራሳቸው ጥቅም ልይቅ የቤተ ክርስቲያን ጥቅም በማስቀደምና በማብለጥ ይህ ዓይነቱን ትምህርት ሲያስተምሩ ቤተ ክርስቲያናችንን ምን ይሰማታል? ቅድስ ሲኖዶስንስ የሚሰማው ስሜት ምን ዓይነት ነው? የእነዚህን የሁለቱን ክቡራን መምህራን ያህል ማሰብ ያስኮንን ይሆን?

ከዚህ ላይ አንድ ሌላ ምሳሌ ቢቀርብ ለጽሑፉ ዓላማ አጋዥ ኃይል ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል፡፡ በዜና ቤተ ክርስቲያን ተመዝግቦ እንደሚገኘው በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ አቡነ ዮሴፍ የሚባሉ ታላቅ ጻድቅ ነበሩ፡፡ በዘመናቸው ዝንጀሮ ሰብሉን ወይም አዝመራውን እየጨረሰበት ገበሬው ዝንት ዓለም ባዶ እጁን ሲቀርና ከችግር ላይ ሲወድቅ ብዙ ጊዜ ተመለከቱና የገበሬውን ሰብል ወይም አዝመራ ዳግመኛ እንዳይነካ ዝንጀሮውን እንደአወገዙትና እስከ አሁንም ድረስ ቢሆን ዝንጀሮው የአካባቢውን ገበሬ ሰብል /አዝመራ/ ሳይነካ የጻድቁን ውግዘት አክብሮ እንደሚኖር ይነገራል፡፡

ታዲያ ይህን ታሪክ የተረዱ አንድ የጎጃም ቄስ በአንድ ወቅት የአገራቸው ገበሬዎች የአቦ ዕለት በሬ ጠምደው ሲያርሱ ያገኙአቸውና ውጉዝ ከመአርዮስ ብለው ያወግዙአቸዋል፡፡ ሆኖም ቢያወግዙ፣ ቢወግዙ ገበሬዎቹ ገሮ ዳባ ልበስ ብለው አልሰማቸው ይላሉ፡፡ በዚህም ጊዜ ቄሱ ተበሳጭተው "እናንተ ያገሬ የጎጃም ሰዎች ብታንሱ ብታንሱ ከላስታ ዝንጀሮ አነሳችሁን?" አሉ ይባላል፡፡

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከሁለቱ መምህራን ማለት ከየኔታ ገብረ ሥላሴና ከየኔታ ያሬድ ያነሰ አስተሳሰብ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታልን? አይገመትም፡፡ ካልተገመተም ለአብነት መምህራኑ ሁሉ በየአሉበት ከሙያቸውና ከአገልግሎታቸው ጋር የተመጣጣነ በጀት መመደብ ይዋል ይደር የማይባል አጣዳፊ ተግባሩ ይሆናል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ትምህርቱ "ምን እንበላለን ምንስ እንለብሳለን? " በማለት ስለምግባቸውና ስለ ልብሳቸው እጅግ ሲጨነቁ የነበሩትን ወገኖች ተመልክቶ "የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፣ ያልዘሩትን እየሰበሰቡ ይመገባሉ፤ ታዲያ እናንተ ከሰማይ ወፎች አትበልጡምን?" ብሎአቸዋል፡፡

በዚህም አንጻር በሰማይ ወፎች የተመሰሉት የኔታ ገብረ ሥላሴና የኔታ ያሬድ ሌሎችም የአብነት መምህራን ሲሆኑ "እናንተ ከሰማይ ወፎች አትበልጡምን?" የተባሉት ደግሞ ቤተ ክርስቲያንና ቅዱስ ሲኖዶስ መሆናቸውን ነው፡፡ ነከሆኑም ዘንድ ከሰማይ ወፎች የተሻሉ ሆነው መገኘት ሊኖርባቸው ነው፡፡ ወይም የየኔታ ገብረ ሥላሴንና የየኔታ ያሬድን ምርጫ ምርጫቸው ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ግዴታቸውም ነው፡፡





ከዚህ በኋላ መምህር ተሻለ ማታ ከቤታቸው ሲገቡ ባለቤታቸው በብስጭት አንቱዬ ቅኔ አያውቁም እንዴ? ብለው ይጠይቋቸዋል፤ መምህር ተሻለም ሲመልሱ የዝማሬ መዋሥዕቱንና የአቋቋሙን ትምህርት ጠንቅቄ ከተማርኩና በመምህርነት ከተመረቅሁ በኋላ የቅኔውን ትምህርት ሳልሞክረው በአንቺ ተጠመድኩኝ›› ይሏቸዋል፡፡

ባለቤታቸውም መልሰው ‹‹ይህን ሁሉ ትምህርት ተምረው በአንድ በቅኔ ትምህርት እጅ ሰበራ መሆን የለብዎትም፣ የእነ መሪጌታ ቦጋለና የባለቤታቸው መዘባበቻ መሆንም የሞት ሞት ነው፤ እኔን አያጡኝም፤ እጠብቀዎታለሁ፤ ይሂዱና ቅኔውን ተምረው ይምጡ›› ብለው እንደ ገና ወደ ቅኔ ቤት ሰደዋቸው ቅኔ ተቀኝተው ተመልሰዋል ይባላል፡፡

ቅዱስ መጽሐፍ ‹‹መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት›› የሚላት እንዲህ ያለችውን ሴት ነው፡፡ ባሎቻቸው ካህናት በትምህርታቸው ወገበ ነጭ የሆኑባቸው ሚስቶች የመምህር ተሻለን ባለቤት ጋሻ ቢያነሱ እንዴት መልካም ነበር? ባሎቻቸውም እንደ መሪጌታ ቦጋለ ባለቤት ዓይነት ያሉት ሴቶች መዘባበቻ ከመሆን ይድኑ ነበር፤ በይበልጥም ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ ይሆኑ ነበር፡፡

ታዲያ ለዚህ ሁሉ የዘለቄታ መፍትሔው ምን ይሆን? ዘላቂ መፍትሔውማ ጠቅላይ ቤተ ክህነትም ሆነ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት እንደ ቤተ ክህነቱ የጽ/ቤት ሠራተኞች ለአብነት መምህራኑም የደመወዝ እስኬል ወይም መስፈርት አበጅቶ ተተኪ ደቀ መዝሙር ሲያገኙ በሚችሉበት ሥፍራ በዚያው ባሉበት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንደ ሙያቸውና አገልግሎታቸው መጠን ደመወዝ እየተከፈላቸው የማስተማር ሥራቸውን እንዲቀጥሉና ወንበራቸው እንዳይታጠፍ፣ ጉባኤ ቤታቸውም እንዳይዘጋ ማድረግ ነው፡፡

ደቀ መዛሙርቱም በትምህርት ገበታ ላይ እስከ አሉ ድረስ ድጎማ እንዲያገኙ ማድረግና ትምህርታቸውን ጨርሰው ከወጡ በኋላም በመንፈሳዊ ኮሌጆችና በካህናት ማሠልጠኛዎች ጥቂት ሥልጠና በመስጠትና በተገቢ ደመወዝ በመቅጠር የአብነት ት/ቤቶች በይዘታቸው እንዲጠናከሩና ተከታይ እንዲያኙ ብሎም ብሩህ ተስፋ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

ከዚህ ላይ ሁለት ታላላቅ የአብነት መምህራን በመላ ኢትዮጵየ አህጉረ ስብከት ለሚገኙት የአብነት መምህራን በአጠቃላይም ለቤተ ክርስቲያናችን የሰጡትን ትምህርትና ያተረፉትን መልካም ምሳሌነት ብንጠቅሰው ስለ አብነት ት/ቤቶች መጠናከር ላቀረብነው ሐሳብ ተጨማሪ ድጋፍና ማጠናከሪያ ሊሆነን ይችላል፡፡

ይኸውም ቀደም ባለው ወቅት ማለት በሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመነ ክህነት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በጎጃም ክፍለ ሀገር በታላቁ ቦታ በደበረ ኤልያስ የቅኔ ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ የባጁትን ስመ ጥሩውንና ታላቁን የቅኔ መምህር የኔታ ገብረ ሥላሴን ወይም በሙገሳ ስማቸው ዝናሙ ገብረ ሥላሴን አስመጥተው በአዲስ አበባ ተቀምጠው እንዲያስተምሩ ቢጠይቋቸው "እኔን ለመጥቀም አስበው ነው? ወይስ በታውን? ቦታውን ለመጥቀም አስበው ከሆነ ደብረ ኤልያስን እንደ ሌሎቹ ደብሮች ከፍ ከፍ ቢያደርጉት፣ እኔን ለመጥቀም አስበው ከሆነም መልካም ፈቃድም ሆኖ በዚያው ባለሁበት ቢረዱኝ የተሻለ ይሆናል" በማለት አዲስ አበባ ለመቀመጥ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ተመልሰው እንደ ሄዱ ይነገራል፡፡

ሌላው ራሱ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የቅኔን ትምህርት ለማዳከምና ለማጥፋት የሚያደርገው ከፍተኛ ጥረት ወደፊት እንዳይቀጥል ወይም በአንድ ቅዕበት ላይ እንዲቆም ትኩረት ሊሰጠውና በጥልቀት ሊታሰብበት የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ ነው፡፡ ይኸውም የቅኔ ትምህርት ለትርጓሜ መጻሕፍትም ሆነ ለጸዋትወ ዜማ ትምህርት ሁሉ ከፍተኛ መተርጎሚያ መሣሪያ ሆኖ ሳለ አንድና ብዙ፣ ሴትና ወንድ፣ ቅርብና ሩቅ የማያውቁትን በአጠቃላይ ቅኔን ጠለቅ ብሎ ማወቁ ይቅርና በሰዋስው እንኳን ትንሽ መነጋገር የማይችሉትን ሊቀ ሊቃውንት፣ ሊቀ ሥልጣናት፣ ንዑረአድ፣ ጸባቲ፣ መልአከ ገነት፣ መልአከ ብርሃናት፣ ሊቀ ሥዩማን፣ መጋቤ አዕላፍ፣ ሊቀ አዕላፍ፣ ሊቀ፣ ርእሰ ደብር፣ ሊቀ ጠበብት፣ ቀኝ ጌታ፣ ግራ ጌታ እየተባሉ እንዲሾሙ በማድረግ ለቅኔ ትምህርት መዳከምና መጥፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለው ራሱ ቤተ ክህነት መሆኑንም ማወቅና መረዳት ተገቢ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

በዓለማዊው ዕውቀት ሳይማሩና የዶክትሬት ሥራ ሳይሠሩ ዶክተር መባል አይቻልም፣ የማስትሬትን ትምህርት ሳያጠናቅቁም ባለማስተርስ መሆን አይሞከርም፣ ከፕሮፌሰርነት ማዕርግ ሳይደርሱም ፕሮፌሰር ተብሎ መጠራት በየትም ዓለም የለም፣ እንበለ ቆብ መነኩሴ፣ እንበለ መለዮም ወታደር መስሎ መታየት ጨርሶ አይቻልም፣ ቀደም ባለው ወቅት በነበረው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም ቢሆን እንበለ ሙያ ለከፍተኛ ሹመት መብቃትና የመዓርግ ስም ማግኘት አይቻልም ነበር፣ ታዲያ ዛሬ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በምን ምክንያት ተጣሰ?፡፡

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅና ወደየካህናት ማሠልጠኛዎች እየቡ የሚሠለጥኑትና በዲግሪና በዲፕሎማ እየተመረቁ ለሐዋርያዊ ተልእኮ የሚሰማሩትም ደቀ መዛሙርት የፈተና ዓይነትና የመግቢያ መስፈርት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በተለይም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሁሉ መፍቻ ቁልፍ የሆነው የቅኔ ሙያ መሆን አለበት፡፡

ወቅታዊውን አገልግሎት ለመስጠት ዘመናዊውን ዕውቀት አውቆ መገኘት አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንበትም መስፈርቱ ወይም መመዘኛው በዘመናዊው ትምህርት ከፍተኛ የነጥብ ብልጫ ማግኘት ብቻ መሆን የለበትም፡፡

በእውነቱ የቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ የአብነት ትምህርቶችን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ከታሰበና ምንጫቸው እንዳይደርቅ ከተፈለገ መስፈርትነታቸው እስከ ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያናችን ሢመተ ጵጵስና ድረስ ዘላቂ ካልሆነ ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ተጠብቀው ለትውልደ ትውልድ ሊተላለፉ ይችላሉ ብሎ መገመት ዘበት ነው፤ ራሳችን ለማጥፋት እየተጣጣርን ሌላው አይደግፋቸውም ብሎ ማሰብም የበለጠ ሞኝነት ነው፡፡

በበጎ ምሳሌነቱ ወይም በበጎ ጎኑ ከዚህ ላይ ልንጠቅሰው የሚያስፈለግ አንድ ጥሩ ጅምር ወይም ድርጊት አለ፡፡ ይኸውም ቅዱስ ሲኖዶስ በቅርቡ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት በተወሰነ የዓመት በጀት በአንድ አንድ አህጉረ ስብከት በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት የንባብ ትምህርት ቤቶች ተከፍተው የየአካባቢው ልጆች በቋንቋቸው የአብነት ትምህርት እንዲማሩ መደረጉ ነው፡፡

ስለሆነም እነዚህ የንባብ ት/ቤቶች ወደ ፊት ተጠናክረውና ተበራክተው ከቀጠሉ ቤተ ክርስቲያናችን ለመንፈሳዊ ኮሌጆችና ለካህናት ማሠልጠኛዎች የምትመለምላቸውን ደቀ መዛሙርት ከእነዚህ የንባብ ት/ቤቶች ልትመለምል ትችላለች፤ ይህም ከሆነ ዘንድ ወደ ፊት ከአሁኑም ቀሽሎ የተሻሉ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ይቻላል ማለት ነው፡፡

ከዚህም ሌላ በቅርቡ ለአብነት መምህራኑ አልፎ አልፎ የተደረገውም ድጐማ የሚመሰገንና ሊቀጥል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ቅዱስ ያሬድ፣ ዮሐንስ፣ ገብላዊና ተዋነይ ወይም ደቀ አስጢፋ የቅኔ ፈጣሪዎች ናቸው በማለት ዘለዓለም ሲተረኩና ሲያስተርኩ መኖሩ ብቻ እርባና የለውም፤ ትረካውንማ ከእኛ በበለጠ ፈረንጆችም ይተርኩታል፣ አልፈው ተርፈውም በትምህርቱ እየተጠቀሙበት ነው፣ ከአማርኛ አልፈው ግእዝ የሚያውቁና ቅኔ የተቀኙ ፈረንጆችም አልታጡም፡፡ ‹‹ነቢይ በሀገሩ አይከብርም›› እንደተባለው በተፈጠረበት አገር ያልተከበረው የቅኔ ትምህርት በሀገረ ባዕድና በውጭ ዜጐች እየተከበረ ነው፡፡

እነዲልማን ጆርመናዊ ‹‹መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ›› የተባለውን የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን የስዋስው ግእዝ መጽሐፍ የደረሱት በልሳነ ግእዝ የተጻፉ 600 የብራና መጻሕፍትን አንብበው እንደሆነ ራሳቸው አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመጽሐፋቸው አስፍረውታል፡፡

መፍቀሪተ ግእዝ የሚል የቅጽል ስም የተሰጣቸው እንግሊዛዊቷ ዲያና ስፔንሰርም ከታላቁና ከስመ ጥሩ ከመምህር ይሒይስ ወርቁና ከመምህር ተስፋ ወርቅነህ እንዲሁም ከመምህር ጌራ ወርቅ ግእዝና የግእዝ ቅኔን ተምረው ቅኔን በሚገባ ከማወቃቸውም በላይ በንግግራቸው የቀድሞ ሊቃውንትን ቅኔ ሲጠቃቅሱ ይደነቁ ነበር፡



እኒሁ ሴት በአንድ ወቅት በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ተገኝተው የቀድሞዎቹን ሊቃውንት ቅኔ ጠቅሰው ሲናገሩ

‹‹ዮም ዕለተ ብዙኃ ብዕል፣
እስመ ብዕለ ቃል ኮነ ለሥጋ፣ ወብዕለ ሥጋ ለቃል›› የሚለውን ጥንታዊ የሊቃውንት ቅኔ ጠቅሰው አንዱን ቤት መትተው ሁለተኛውን ቤት ሳይመቱ ሙሉ ቢሉ ሊሞላላቸው የቻለ ደቀ መዝሙር ሊያገኙ አልቻሉም ነበር፡፡

በዚያም ሆነ በዚህ የቅኔ ትምህርት ታላቅ የፍልስፍና ትምህርት በመሆኑ የኢትዮጵያንና የሊቃውንቶቿን ከፍተኛ ዕውቀት በጥልቀት ለማወቅ በጥረት ላይ የሚገኙት ፈረንጆች እንኳን ወደውትና አክብረውት ሲያጠኑትና ሲከታተሉት እኛ በቸልተኝነት የምንመለከተውና ልናከብረው ያልቻልነው ‹‹በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ እኩል ይቁጠራል›› በተባለው መንገድ ይሆን? ከእጃችን ወጥቶ በሌላ እጅ ያለ ወርቅ እንዳይሆን አጥብቀን ልናስብበት ይገባናል፡፡

በዚህ ረገድ የቅኔ ፈጣሪዎችና ፈላስፋዎች የሆኑትን እነ ቅዱስ ያሬድን፣ እነ ዮሐንስ ገብላዊንና እነ ደቀ እስጢፋ፣ እነ ሐዊራ፣ እነ መንክራ፣ እነ ብሉርን፣ እነ ድድቅ ወልደ ማርያምን የወለደች ከዚያም ወዲህ እነ ተዋነይን፣ እነ ክፍለ ዮሐንስን፣ እነ ዘመደ ብርሃንንና ...እንዲሁም በነበራቸው ከፍተኛ የቅኔ ሙያ ልዩ ችሎታ በተሰጣቸው የቅጽል ስም ወይም የሙገስ ስም እነ ጌቴ ገሞራውን፤ እነ ማዕበል ወልደ ሕይወትን፤ እነ ማዕበል ፈንቴን፣ እነ ዕቡይ ካሣን፣ እነ ዶሪ የቅኔ ፈጣሪን፣ እነ ግጨው ገብሬንና ዕፁብ ኀበዝን የመሳሰሉትን ያፈራች ሀገረ ቅኔ ኢትዮጵያ በእነሱ እግር እንደ እነሱ ያሉ ሌሎችን ካልተካች የቅኔ ሙያዋ አፈ ታሪክ ብቻ ሆኖ መቅረቱ ነው፡፡

ግሪካዊው ፈላስፋ ፕላቶ እንደ ተናገረው ለአንዲት አገር ብልህ መሪ፣ ጀግና ሠራዊትና ግብረ ገብ ሕዝብ ያስፈልጓታል፣ እነዚህ ሦስት አካላት ከሌሉ ግን አስተማማኝ አገር ልትሆን አትችልም፣ እነዚህንም ሦስት አካላት ማፍራት የሚቻለው በትምህርት ነው፣

ስለዚህ የአንድ አገር ዓይነተኛ ቅርስ ትምህርት ስለሆነ ሀገራችን ኢትዮጵያ አያሌ ጀግኖች የቅኔ ፈላስፎችን ያፈራችበትንና የምትኮራበትን ይህ ዓይነቱን የቅኔ ትምህርት ቅርስ እንዳለ የመጠበቁና የማስፋፋቱ ብሎም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የማድረጉ ዐቢይ ጉዳይ በቤተ ክህነቱ ልዩ ትኩረት ሊሰጠውና የዘለቄታ መፍትሔ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

ስለቅኔና ለቅኔ ሰዎች የማስቡ ጉዳይ ለቤተ ክህነት ብቻ የሚተው አይደለም፡፡መንግሥትንም በእጅጉ ሊያሳስበው ይገባል፡፡ ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው ለአንዲት አገር ብልህ መሪ፣ ጀግና ሠራዊት፣ ግብረ ገብ ሕዝብ እንደሚያስፈልጓት ሁሉ የቅኔ ሰዎችና ደራስያንም በእጅጉ ያስፈልጓታል፡፡ ደራስያንና የቅኔ ሰዎች ከሌሉ የመሪዋን ብልህነት፣ የሠራዊቷን ጀግንነት፣ የሕዝቧን ግብረ ገብነት መግለጽ አይቻልም፤ አንደበቷ የታሰረ፣ ዓይነ ልቡናዋ የታወረ አገር ትሆናለች፡፡

የሀገር ታሪክ እንደሚነግረን ባለፉት ዘመናት አገራችን ትመራ የነበረው በአመዛኙ በቅኔ አዋቂዎችና በመጻሕፍት መተርጉማን ሕግ አውጭነትና አማካሪነት ነበር፡፡ ሕገ መንግሥቱ፣ ፍትሐ ብሔሩ፣ ወንጀለኛ መቅጫው የተዘጋጀው ምሁራኑ ቤተ ክርስቲያንና የቅኔ ሰዎች ከተረጎሙት ከፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ እንደሆነ የሚክድ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡

የቅኔ ትምህርት ቅርስነትና ከበሬታ ከሌሎቹ ብርቅና ድንቅ የሀገሪቱ ቅርሶች የላቀ ሊሆን ይገባዋል፤ ቅኔ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምድረ አፍሪካም ታላቅ ከበሬታ አለው፡፡ ከፍተኛ የቅኔ ፍቅር የነበራቸው አፍሪካዊው ፕሬዝዳንት ሴንጉር መንግሥታዊ ሥልጣናቸውን በቅኔ ለውጠው ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገው በመተው ወደ ቅኔ ቤት እንደ ሄዱና የደራሲነት ሥራቸውን እንደ መረጡ መዘንጋት አያሻም፡፡ ወደ ባሕር ማዶውም ስንሻገር እነዊሊያም ሼክስፒርን የመሳሰሉት የቅኔ ሰዎች የአንድ አገር ነጻነት ልዋጭ ሆነው እንደ ቀረቡ ልነረሳ አይገባንም፡፡

በአጠቃላይ ድቀተ ቅኔ ጉዳቱ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በይበልጥም ለሀገሪቱ በመሆኑ ከወደቀበት አገግሞ እንዲነሣና ቢቻል ካለፈው በበለጠ መልኩ ያለዚያም በነበረበት ሁኔታ ተጠብቆና እንክብካቤ ተደርጐለት ለትውልደ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ መንግሥታዊ ድጋፍ ያስፈልገዋል፤ ባለፈውም ተጠበቆ ሊቆይ ቻለው በቤተ ክህነቱ ብቻ ሳይሆን በቤተ መንግሥቱም ድጋፍ ጭምር ነውና፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 7

## የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ታሪክ በኢትዮጵያ

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በመጀመሪያዎቹ ስድስት መቶ ዓመታት መጽሐፍ ቅዱስ ከተተረጐመባቸው በጣም ጥቂት የዓለም ቋንቋዎች መካከል ሁለቱ የአፍሪካ ቋንቋዎች ናቸው፡፡ እነሱም የግብጽ ጥንታዊ ቋንቋ "ቅብጥ" እና የኢትዮጵያ ጥንታዊው ቋንቋ "ግእዝ"[1] ናቸው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን በግእዝ የመተርጐም ታሪክ ለመዳሰስ አንድ ሰው የሀገሪቱን ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ስረ መሠረት ቢያንስ በአጭሩ መመልከት አለበት፡፡ በአፍሪካ ቀንድና በቀይ ባሕር ምዕራባዊ ጐን ልዩ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ያላት ኢትዮጵያዊ ክብዙ ሺህ ዓመታት ጀምሮ በመካከለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ ሥልጣኔ መካከል እንደ ድልድይ ሆና ኖራለች፡፡ በረጅም ታሪካዊ ጉዞ ኢትዮጵያ ከደቡብ ዐረቢያ፣ ከግብጽና ከእስራኤል ሕዝቦች ጋር ቅርብ ግንኙነቶችን አዳብራ ነበር፡፡ ይሁንና ግንኙነቶቹ በአየርና በምጣኔ ሀብት ሁኔታዎች ተለውጠዋል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ቦታዎች፣ በተለይም ከደቡብ ዐረቢያ አያሌ ሕዝቦች ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመታት ጀምሮ በነበረው ረጅም ጊዜ ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ መፍለስ /መሰደድ/ ጀምረው ነበር፡፡ እነዚህ ስደተኞች ውስው አድረው ቋንቋቸውን፣ የአጻጻፍ ሥርዓታቸውንና ሌሎች ባህላዊና ሃይማኖታዊ ውርሶቻቸውን መጠቢያ ወዳገኙበት ወደ ኢትዮጵያ ማሰገባት ችለዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ ውርሶች ሁሉ በኋላ ጊዜ በኢትዮጵያ እየተለወጡና እየተሻሻሉ መጥተዋል፡፡[2]

# ክፍል 1

## በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ የአይሁድ ሥርዓት ተጽእኖ

በንግድ ተጀምሮ በፖለቲካ መስክ እያደገ የመጣው የኢትዮጵያና የእስራኤል ግንኙነት ከክርስቶስ ልደት በፊት በመጀመሪያው ሺህ ዓመት መግቢያ ላይ በንግሥተ ሳባና በንጉሥ ሰሎሞን ጊዜ ከፍ ካለ ደረጃ ደርሶ ነበር፡፡ ንግሥተ ሳባ ንጉሥ ሰሎሞንን እንደጉብኝት የሚያስረዳው ቀዳሚው የመጽሐፍ ቅዱስ የመረጃ ምንጭ 1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1 - 13 እና 2ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 9 ከቁጥር 1-12 ያለው ነው፡፡[3] ሆኖም የንግሥተ ሳባ ታሪክ በኢትዮጵያ[4] ፣ በደቡብ ዐረቢያ[5] እና በአይሁድ[6] የሥነ ጽሑፍ ትውፊት ስፊ ማብራሪያ ተሰጥቶታል፡፡ "በመካከለኛው ምሥራቅም በየትኛውም አካባቢ ከሚገኙና መልካም ከሆኑ አካባቢዎች የአንዱ ርእስ ሆኗል"፡፡[7]

ስለ ንግሥተ ሳባ ታሪክ ዋናው የኢትዮጵያ ምንጭ "ክብረ ነገሥት" ተብሎ የሚጠራው የኢትዮጵያን ብሔራዊ የረጅም ጊዜ ታሪክ የያዘና ዋናው የንጉሣዊ አገዛዝ አስተሳሰብ የመነጨበት መጽሐፍ ነው፡፡ " ክብረ ነገሥት" ንግሥተ ሳባ ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር ቅርብ ግንኙነት መሥርታና ከዚህም በማስከተል የአይሁድን ሃይማኖት ተቀብላ እንደነበር በሰፊው ይገልጻል፡፡ ከኢየሩሳሌም ስትመለስም ከሰሎሞን የወለደችው "ምኒልክ" የተባለው ልጅዋ የኢትዮጵያ ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት መሥራች እንደሆነ "ክብረ ነገሥት" ያስረዳል፡፡ በኢትዮጵያ የመጨረሻው ንጉሠ ነገሥት እስከነበሩት ቀዳሚዊ ኃይለ ሥላሴ ድረስ የነገሡ ነገሥታት ሁሉ ከቀዳሚዊ ምኒልክ ዘር ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ እንደሆኑ ጽኑ እምነት ነበራቸው፡፡ ይህም እምነት በተሻሻለው የ1955 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 2 ላይ እንደሚከተለው ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ "የንጉሠ ነገሥቱ ክብር ከኢየሩሳሌሙ ንጉሥ ከሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥተ ሳባ ልጅ ከቀዳሚዊ ምኒልክ ያለማቋረጥ ሲቀጥል ከመጣው ሐረግ ጋር ተያይዞ ለዘለዓለም ይኖራል፡፡"[8] በዚህም ላይ Proffessof E.Ullendoroff አስተያየት ሲሰጡ እንዲህ ብለዋል፡፡

"እዚህ ላይ ለዘብ ባሉ የሕግ ቃላት ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ምሥጢራዊ ግንኙነት ቀጥታ ዝርያ ያለው ነው የሚለውን የማያቋርጥ ጠንካራ አቋም እናገኛለን፡፡ ይህም የብሉይ ኪዳን ታሪክን ጸንቶ የመኖር ጠቀሜታና ስፊ ውጤቱን የሚያስታውስን ነው፡፡"[9]

1 ግእዝ የኢተዮጵያ የጥንት ቋንቋ ነው፡፡ ግእዝ ቋንቋ ራሱን የቻለ የጽሑፍ ቋንቋ የሆነበት ጊዜ በትክክል አይታወቅ፡፡ በሰሜን መሥራት ኢትዮጵያ ባለችው በማሜራት የተገኘው ከክፈ.ዘ2ጎ የ3ኛው መተ ክፍለ ዘመን ዘሐውልት ላይ የተረጸ ጽሑፍ ዘኢትዮጵያ ተጻሚው የግእዝ ጽሑፍ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ጸ/ር ሥርገው ሐዘለ ሥላሴ Ancient and Medieval History of Ethiopia በሚል ርእስ የጻፉትን ገጽ 12 ተመልከቱ፡፡

2 ሥርገው ሐዘለ ሥላሴ 1972 ገጽ 29-33

3 አንዳንድ ትናንሽ ነገር ግን አስፈላጊ ያልሆኑ ልዩነቶች ዘሁለቱ የቁሙራ ኪዳን ታሪኮች መካከል ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ልዩነቶች ለሰሎሞንና ለነባ አፈታሪክ እድገት አስፈላጊነታቸው ትንሽ የሆነ ነገር ግን ጽሑፍን ሰጋስተቀሳሾ ጽሁ ቀቱ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ E.Ullendorf, Ethiopia and the Bible (London, Oxford University Press 1968 p.132

4 ሥርገው ሐዘለ ሥላሴ 1972 ገጽ 36-38

5 A. W. Arbery, trans., The koran Interpreted (London, 1937) PP. 384-85; E. Ullendorf, 'Hebraic - Jewish Elements in Abyssinian Christianity', JES, 1965, pp. 29-35.





ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ስለ አንዳንድ ፈሪሳውያንና ጸሐፍት አለማመን ሲናገር ንግሥተ ሳባ የሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከሩቅ አገር መምጣቷን እንዲህ ሲል አመስግኗል፡፡ "ንግሥተ አዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፣ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፡፡"[10]

ክብረ ነገሥት ቀዳማዊ ምኒልክ ባደገ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ አባቱን ሰሎሞንን እንደ ጉብኝና አዚያም በቆየበት ጊዜ የአይሁድን ሃይማኖት ሥርዓት መንግሥቱ ጋር አማምሮ እንደተማረ በዝርዝር ይተርካል፡፡ ወደ ሀገሩ ሲመለስም ቀዳማዊ ምኒልክ በብዙ ካህናትና የሕግ መምህራን ታጅቦ መጥቷል፡፡ እነዚህ ካህናትና መምህራንም የአይሁድን ሃይማኖትና ባህል በአጠቃላይ፣ የሙሴን ሕግ በተለይ ለሀገሪቱ (አክሱም-ኢትዮጵያ) በሰፊው እንዳስተዋወቁ ይታመናል፡፡ በዚህ ጽሑፍ (ክብረ ነገሥት) ላይ ቀዳማዊ ምኒልክ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት በምሥጢር አምጥቶ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ዋና ከተማ በነበረችው በአክሱም እንዳስቀመጣት ተገልጿል፡፡ በዚህም ምክንያት ይህች የቃል ኪዳን ታቦት እስከአሁን በዚያ እንደምትገኝና በዚህም ምክንያት አክሱም የተቀደሰች ከተማ እንደሆነች በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ይታመናል፡፡[11]

ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር የነበሯት እነዚህ የቅርብ ግንኙነቶች፣ በተለይም በሃይማኖትና በባህል መስክ፣ ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በመላው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ ሥር ሰደው በኖሩ የአይሁድ መሰል ልማዶች ሊረጋገጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ልማዶች እንደ ቅዳሜ አከባበር፣ በምግብ አጠቃቀም ረገድ ንጹሕና ንጹሕ ባልሆኑ እንስሳት መካከል ያለው ልዩነት፣ ሥርዓታዊ ንጽሕና እና የግዝረት ሥርዓቶች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ የሰንበትን በጥብቅ መከበር አስመልክቶ W.C.Harris የተባሉት ደራሲ የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡ "በሬና አህያ አርፈው ይውላሉ፡፡ የእርሻ ሥራ ይቆማል፡፡ የቤት ጥቃቅን ሥራም አይሠራም፡፡ ቀኑን ሙሉ ሥራ አልባ መንፈስ ሰፍኖ ይውላል..."[12] ክርስትና በኢትዮጵያ ከተስበከ በኋላ ቅዳሜና እሁድ ሁለቱም በአኩል ደረጃ ሲከበሩና ሁለቱም በግዕዝ "ሰንበት" በሚል መጠሪያ ሲጠሩ ኖረዋል፡፡ የቀድሞው "ቀዳሚት ሰንበት"፣ የኋለኛው "ሰንበተ ክርስቲያን" ወይም በኦሮምኛ ቅዳሜት "ሰንበተ ጢና" ወይም " ሰንበተ ዱራ"፡ ተብሎ ሲጠራ ታላቁ እሁድ ሰንበት ደግሞ "ሰንበተ ጉዳ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ሥራን በተመለከተ ቅዳሜ እንዳይሠራ የሚከለክሉ ዝርዝር መመሪያዎች በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ባደረገው በዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ በተዘጋጀው በመጽሐፈ ብርሃን ተጽፈው ወጥተዋል፡፡ መጽሐፉ ስሜታዊ በሆነ መንገድ የሰንበትን አስፈላጊነት ያስረዳል፡፡[13]

በመጀመሪያዎቹ አምስቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከታዘዙ የምግብ መመሪያዎች ብዙዎቹ በኢትዮጵያ በተወሰነ ጥብቅነት ሲፈጸሙ ኖረዋል፡፡ Mansfield Parkins ሲጽፍ፣ "በምግብ አመራረጥ ከአቢሲኒያውያን የበለጠ ጠንቃቃ ሕዝብ የለም"[14] ማለቱ የተጋነነ አይደለም፡፡ ዘሌዋውያን ምዕራፍ 11 በሚያዘው የአመጋገብ መመሪያ መሠረት ሽሆናቸው ያልተሰነጠቀ እንደ ግመልና እንደ ጥንቸል ያሉ እና የማያመነዥኩ እንደ አሳማ ያሉ እንስሳት እንዳይበሉ ከተከለከሉ እንስሳት መካከል ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ዘንድ ያለማወላወል ከሚፈጸሙ የንጽሕና ሥርዓታት ጋር የተያያዙ መመሪያዎች ከብሉይ ኪዳን የተገኙ ናቸው፡፡[15]

6 Detailed accounts are given in the work of F. Josephus of the 1st century A. D, and in the Babylonian Talmud of the 3rd century A. D. F Josephus, Jewish Antiquities, ed. by J. Thackerapy & R. Malcus (Loeb Classical Library, London, 1961) vol. VIII pp. 165 - 175: The Babylonian Talmud, Seder Nezikan, trans.by A. Epstein (London, 1935) p.76. The Babylonian Talmud interprets the ac counts about the Queen of Sheba in 1 kings 10:1-10 in a metaphorical sense.

7 E.Ullendorff, Ethiopia and the Bible (London, 1968), p.132.

8 Revised Constitution of Ethiopia (Addis Ababa, 1955), p.3.

9 E. Ullendorff, Ethiopia and the Bible (London, 1968), p.139-140.

10 ማቴዎስ 12:42፣ ሉቃስ 11:32፡፡

11 ክብረ ነገሥት ምዕ48፣ E. Ullendorff, 1968 82-85,135,141-142 ሥርገው ሐዘለ ሥላሴ 1972 38

12 W.C.Harris, The Highlands of Ethiopia, vol.3(London,1844).

13 Betshaf Berhan. ed by Conti Rossini & L. Ricci in C. S. C. o., 1964/5.

14 M. Parkins, Life in Abyssinia (London, 1966 imperssion of the 2nd edition 1868) pp. 207-8.

15 ዘጸአት 19:15፣ ዘሌዋውያን ምዕ.12 እና 15፡፡ 1ሳሙ.21:4-6፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የግዝረት ልማድም በኢትዮጵያ በሰፊው በተግባር የሚገለጽ ነው። ይሁንና ይህ ልማድ የአይሁድ ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ጀምሮ የኢትዮጵያ አዋሳኝ የሆኑ አገሮችን ጨምሮ በዓለም ሕዝቦች መካከል የተስፋፋ በሆኑ የግዝረት ልማድ ከዚያ በፊት ጀምሮ የነበረ ነው ማለት ትክክለኛ ሊሆን ይችላል። ሆኖም በኢትዮጵያ ለመኖሩ ልዩ የብሉይ ኪዳን ተያያዥነት እንዳለው ማስረዳት ይቻላል። ከልደት በኋላ በ8ኛው ቀን የግዝረት አፈጻጸም በኢትዮጵያና በአይሁድ ብቻ የሚደረግ ነው።

ይህም ሐቅ ኢትዮጵያን ግዝረትን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በብሉይ ኪዳን ትእዛዛት ተጽእኖ ሥር እንደነበረች የሚያረጋግጥ ሐቅ ነው። ይሁን እንጂ ከወንድ ግርዛት በተጨማሪ ኢትዮጵያ እንደ አብዛኞቹ ጐረቤቶች ሀገሮች የሴት ግርዛትንም ስትፈጽም ኖራለች። ይህ ልማድ ግን በብሉይ ኪዳን የለም። ስለዚህ ኢትዮጵያ የግዝረትን ልማድ ከሁለቱም ማለት ከአይሁድ ሃይማኖትና ከጎረቤቶቿ እንደወረሰች ተአማኒነት ያለው ይመስላል።[16]

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሐዋርያት ድድስቅልያ በተቀመጠው መሠረት በሳምንት ሁለት ጊዜ ረቡዕ እና ዓርብ የሚጾም ሲሆን ረቡዕ የሚጾመው ጌታችን መጽሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ ለመያዝና ለመስቀል ምክር የፈጸሙበትን ዕለት ለማዘከር እንዲሁም ዓርብ የሚጾመውም ጌታችን ስለ ዓለም ድኅነት ሲል በመስቀል የተሰቀለበትን በማስታወስ ነው።[17]

እነዚህ ቀደም ያሉ የአይሁድ ተጽእኖዎች እና ሥር የሰደዱ የብሉይ ኪዳን ልማዶች በኢትዮጵያ መኖር ክርስትና ከመግባቱ በፊት የአይሁድን ሃይማኖት ቢያንስ የተወሰኑ ሰዎች ይከተሉ እንደበረ ያስረዳል። ይሁን እንጂ በክብረ ነገሥት እንደተጻፈው የአይሁድን ልማድ አጀማመር ከክርስቶስ ልደት በፊት በ10ኛው መቶ ዓመት ከነበረው ከንጉሥ ሰሎሞን ጊዜ ጋር ማያያዝ አስቸጋሪ ይሆናል። አንዳንድ ምሁራን ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የተጀመረው ግንኙነት በማከታተልም የአይሁድ ሃይማኖትና ባህል ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ6ኛው መቶ ዓመት ከባቢሎን ምርኮ ቀደም ብሎ እንደነበረ ያምናሉ። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ያሉ ፈላሻዎች "ከመጀመሪያዎቹ አምስቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውጪ ምንም ሃይማኖታዊ መመሪያዎችን አያውቁምና ነው።

በአይሁድ መምህራን የተዘጋጀውን የብሉይ ኪዳን መመሪያዎችን ባህላዊ የቃል ትርጉም (Mishnah) እና የአይሁድን የፍትሐ ብሔርና የሃይማኖት ሕግ የያዘውን የጽሑፍ ስብስብ ታልሙድን (Talmud) አያውቁም።"[18] ከሁሉም በላይ ከጴዋዊ በኋላ የተሠሩ በዓላትና አከባበራቸው በኢትዮጵያ በፈላሻዎችም ሆነ በክርስቲያኖች ወንድሞቻቸው ተከብረው አያውቁም።

ኢትዮጵያውያን ሐዲስ ኪዳን ከመቀበላቸው በፊት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፣ ወይም ቢያንስ ከጥቂት ክፍሎች ጋር ይተዋወቁ ነበር? ወይስ አልነበረም? የሚል ጥያቄ ማንሣት ይቻላል። ይህ ጥያቄ አስቸጋሪ ሲሆን በሚከተለው ክፍል ሐሳብ ተሰጥቶበታል።

# ክፍል 2

## መጽሐፍ ቅዱስ በግእዝ ቋንቋ የተተረጐመው መቼ ነበር?

መጽሐፍ ቅዱስ በግእዝ የተተረጐመው መቼ? በማን? እና ከምን ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች ነበር? የሚለው ጥያቄ እስከ አሁንም ድረስ አከራካሪ ጉዳይ ነው። ክክርስቶስ ልደት ወደ ኢትዮጵያ ዘልቀው የገቡ የአይሁድና የብሉይ ኪዳን ተጽእኖዎች እንዲሁም አመለካከቶች ብሉይ ኪዳን ወይም ቢያንስ የተወሰኑ ክፍሎች (መጽሐፎች) በተመሳሳይ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ እንደተተረጐሙ ሐሳብ ይሰጣሉ።ነገር ግን ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ መቼ እንደተተረጐመ በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በተጻፈው በመጽሐፈ ምሥጢር ውስጥ የተመዘገበ አንድ ታሪክ ስለ ብሉይና ሐዲስ ኪዳናት ትርጉም በግእዝ የሚከተለውን መግለጫ ይሰጣል።

16 ለዝርዝር አስተያየቶች E. Ullendorff, Ethiopia and the Bible, ገጽ 105 - 109 ተመልከት።
17 ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ተመልከት
18 ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ተመልከት





... ወመክብበ መጻሕፍቲሃሰ ዘብሉይ ተዐልዋ እምዕብራይስጢ ኀበ ግእዝ በመዋዕሊሃ ለንግሥተ አዜብ እንተ ሐወጸቶ ለሰሎሞን። ወበእንተዝ ኮነ ጽሩየ ፍካሬሆሙ ለመጻሕፍተ ነቢያት ዘውስተ ብሔረ አግዓዚ እስመ በሕገ አይሁድ ነበሩ እምቅድመ ልደተ ክርስቶስ። ወእመስኬ አዕለውዎ እምድኅረ ልደተ ክርስቶስ ሜጡ ለቃልያን ቃለ ጽዱቀ ውስተ ስምዐ ሐሰት። መከመሰ ተአልዋ መጻሕፍተ ነቢያት እምዕብራይስጢ ኀበ ግእዝ ትረክብ ትእምርቶ በውስጠ መጽሐፈ ነገሥት ዘይብል ትርጓሜ ነገረ ዕብራይስጢ ኀበ ግእዝ፣ ኤሎሄ ብሂል አምላክ።

አዶናይ ብሂል አግዚእ። ጸባኦት ብሂል አግዚእ። ጸባኦት ብሂል ዘኀይላት። ለመክብበ መጻሕፍቲሃሰ ዘሐዲስ ለምድርነ ኢትዮጵያ ተዐልዋ እምሮማይስጢ ኀበ ግዕዝ እምቅድመ ያስተርኢ ሃይማኖተ ንስጥሮስ ወእምቅድመ ይትፈጠር ሃይማኖተ ልዮን፣ ወእምቅድመ ይትጋብኡ ማኅበረ ክለባት ዘውእቶሙ ኤጲስ ቆጳሳት ዘኪልቄዶን። ወበእንተዝ ኮነ ፍካሬ መጻሕፍቲሃ ለብሔረ አግዓዚ ዘብሉይኒ ወዘሐዲስኒ ንጡፈ ከመ ወርቅ ወፍቱነ ከመ ብሩር።

"... የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በተመለከተ ሰሎሞንን በጐበኘችው በንግሥተ አዜብ ዘመን ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተተረጐሙ። በዚህም ምክንያት በብሔረ አግዓዚ (ኢትዮጵያ) የሚገኙ የነቢያት መጻሕፍት ትርጉም የጠራ ሆነ። ከልደተ ክርስቶስ በፊት ሕዝቡ ለአይሁድ ሃይማኖት ታማኝ ነበሩ። ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በተተረጐሙት ግን የክርስቶስ ሰዎች እውነተኛውን ቃል ወደ ሐሰት ለወጡ።

የነቢያት መጻሕፍት ግን ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ እንደተተረጐሙ በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ የተተረጐመ የሚል ትምህርት ታገኛለህ። በትምህርቱም ኤሎሄ ማለት አምላክ፣ አዶናይ ማለት ጌታ፣ ጸባኦት ማለት ኃያል ማለት ነው። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በተመለከተም ለሀገራችን ኢትዮጵያ የተተረጐሙት ከላቲን (ሮማይስጥ) ወደ ግእዝ ሲሆን፣ ይኸውም የሆነው የንስጥሮስ ሃይማኖት ከመከሠቱ (431 ዓ.ም.)፣ የልዮን ሃይማኖትም ከመፈጠሩ (451ዓ.ም.)[19]..."[20]

በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ብሉይ ኪዳን የተተረጐመው ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደሆነ ያረጋግጣሉ።[21] አንዳንድ የግዕዝ ምሁራን በዘመኑ የግዕዝ ቋንቋ ራሱን ችሎ የጽሑፉ ቋንቋ ከመሆን ደረጃ አልደረሰም።[22] የሚል አስተያየት ቢሰጡም በብሉይ ኪዳን ዘመን የተተረጐሙት ጥንታውያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት የምንረዳው ግን በዘመኑ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞ ጥንታዊነቱን እንደጠበቀ እስካሁን መኖሩን ነው።

ወንጌላዊው ፊልጶስ በጌታ ትእዛዝ ወደ ጋዛ በሚወስደው መንገድ ሄዶ የኢትዮጵያ ንግሥት ካንዳስ የገንዘብ ሚኒስትር /በጅሮንድ/ የነበረው ጃንደረባ በተገናኘው ጊዜ ጃንደረባው በሠረገላው ውስጥ ሆኖ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።[23] ይህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ መጽሐፉን ያነብ የነበረበት ቋንቋ የግዕዝ ቋንቋ ነበር። አንዳንድ ሊቃውንት ጃንደረባው ያነብ የነበረው በግሪክ ወይንም በአብራይስጥ ቋንቋ ነበር የሚል አስተያየት ቢኖራቸውም የእስራኤል ዘሮች እንደሆኑ የሚታመኑት ፈላሾች እንኳን ያሏቸው የሃይማኖት መጻሕፍት በሙሉ በግእዝ እንጂ በዕብራይስጥ ወይንም በግሪክ የተጻፉ አልነበሩም።

19 ቀናቱ በዚህ ጽሑፍ እዚጋጅ የገቡ ናቸው።
20 መጽሐፈ ምሥጢር የቤራና መጽሐፍ በመጋዘ ፓትርያርክ ፊተ መጻሕፍት የሚገኝ ገጽ 74 - 75 See E. Ullendorff, 1968, 31-32.
21 ሥርገው ሐፀፀ ሥላሴ 1972 ገጽ 44 እና 120።
22 ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ተመልከት
23 ግሕጥ.8:26-38. ኢሳ.53:7-8።
24 ሥርገው ሐፀፀ ሥላሴ 1972 ገጽ 44።
25 E. Ullendorff, 1968, p.10; ሥርገው ሐፀፀ ሥላሴ 1972ገ ገጽ 120።

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል 3

## የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ትርጉም ምንድን ነው?

የትርጉም ሥራ አስፈላጊነቱ ታምኖበት የተጀመረው ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ነው፡፡ በጥንታዊው ዓለም ጥቂት አገሮች ለሥነ ጽሑፍ ፊደላትን ለመፍጠር ከተሳካላቸው በኋላና የፍልስፍናና የሳይንስ ግንኙነቶቻቸውን ከመዘገቡ በኋላ፣ የተጻፉት ጽሑፎች ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው ቋንቋ መተርጐም ጀመሩ፡፡ የመጀመሪያው የትርጉም ሥራ ቅ.ል.ክ. በ3000 ዓመት ላይ ነው የተጀመረው፡፡ በትርጉም ታሪክ ውስጥ ስለ ሥነ ከዋክብት፣ ታሪክ፣ ፍልስፍና እና ስለ ሃይማኖት የተጻፉ መጻሕፍት ከፍ ያለ ቦታ ይዘዋል፡፡

ብዙ ቋንቋዎችና ብዙ ጐሳዎች ከነበሩበት ከባቢሎን ግዛት ጀምሮ አሁን እስከ አሉት የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ድረስ ለመደበኛ ግንኙነት መግባባት ትርጉም ፍጹም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ብዙ ባለሙያ ተርጓሚዎች የተለያዩ መጻሕፍትን ከአንድ ቋንቋ ወደሌላው በመተርጐም በሥራ ላይ ተጠምደዋል፡፡ ቅ.ል.ክ በ3ኛው ሺህ ዓመት የአሦር ንጉሥ የነበረው ሳርጎን (Sargon) ያገኛቸው የጦር ድሎች በግዛቱ ባሉ ብዙ ቋንቋዎች እንዲነገር አድርጎ ነበር፡፡ እንዲሁም ቅ.ል.ክ በ2100 በባቢሎን ግዛት ንጉሥ ሐሙራቢ (Hammurabi) ብዙ ጸሐፊዎች ነበሩት፡፡ እነዚህም የንጉሡን አዋጆች በግዛቱ ውስጥ ባሉ በርካታ ቋንቋዎች እየተተረጐሙ ሕዝቡ በሚገባ እንዲገዛለት ያደርጉ ነበር፡፡ ይህም በመጽሐፈ አስቴር 8፡9 ተገልጾ እናገኛቸዋለን፡-

"በዚያን ጊዜም ኒሳን በተባለው በመጀመሪያው ወር ከወሩም በሀያ ሦስተኛው ቀን የንጉሡ ጸሐፊዎች ተጠሩ፡፡ መርዶክዮስም ስለ አይሁድ እንዳዘዘው ሁሉ ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሃያ ሰባቱ አገሮች ላሉ ሹማምንትና አለቆች አካውንትም ለእያንዳንዱም አገር እንደጽሕፈቱ ለእያንዳንዱም ሕዝብ እንደ ቋንቋው ለአይሁድም እንደጽሕፈታቸውና እንደ ቋንቋቸው ተጻፈ፡፡"

በነህምያ ጊዜ (ቅ.ል.ክ በአምስተኛው መቶ በኋለኛው ክፍል) በአይሁድ ዘንድ ልዩ የትርጉም ቅጽ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ይህ ዓይነት ትርጉም የቃል (የስማ በለው ዓይነት) ትርጉም ነበር፤ ሆኖም ቀስ በቀስ አደገና በጽሑፍ ላይ ዋለ፡፡ ከዚህም ትርጉም (Targum) የተባለው ቃል ቀስ በቀስ ተገኘ፡፡ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ በሀገራቸውና በባቢሎን ይኖሩ የነበሩ አይሁድ የሚናገሩት አራማይክ (Aramaic) ነበር፡፡ ሕገ ኦሪት (አምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ) በምኩራቦች ውስጥ ለምእመናን የሚነበበው በዕብራይስጥ ነበር፡፡ ንባቡ በመጀመሪያ በዕብራይስጥ ቋንቋ በኋላም ሕዝቡ በዕብራይስጥ የተነበበውን መገንዘብ እንዲችሉ በአረማይክ ይተረጐም ነበር፡፡ እያንዳንዱ ተርጓሚ[26] ቃል በቃል ባጭሩ ወይም ራሱ በመሰለው አያስፋፋ ስለ ብሉይ ኪዳን ያለውን እውቀትና የቋንቋ ችሎታ በመጠቀም ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ አረማይክ ይተረጉም ነበር፡፡

ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ሕዝቡ የቅዱሳት መጻሕፍትን ንባብ ለመስማት "የውሃ በር" ከሚባለው ቦታ ፊት ለፊት ባለው አደባባይ ይሰበሰቡ እንደነበር ከነህምያ ም.8.ከቁጥር 1-8 እንረዳለን፡፡ የሕግ ምሁሩ ዕዝራ ቅዱሳት መጻሕፍትን በዕብራይስጥ ሲያነብ ሌዋውያኑ (ዕብራይስጥና አረማይክ ስለሚያውቁ) ሕዝቡ በዕብራይስጥ የተነበበውን እንዲረዱት በአረማይክ ቃል በቃል ይተረጉሙላቸው ነበር፡፡[27]

አሁን ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የተባለውን ትርጉም እንመልከት፡፡ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ወደ ግሪክኛ የተተረጎመ የመጀመሪያና በጣም ጥንታዊ የሆነ የትርጉም ነው፡፡ ምንም እንኳ በአፍሪካ ቋንቋ ሳይሆን በግሪክኛ ቢሆንም የመጀመሪያው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በአፍሪካ አህጉር እንደተደረገ ማወቁ ያስደንቃል፡፡

26 ተርጓሚ የሚለው ቃል ዕዕብራይስጥ "meturgema" ይባላል፡፡ ትርጉም የተባለውም ቃል የተገኘው ከዚሁ ነው፡፡
27 ነህምያ 8:8



ከላይ እንደገለጽነው ወደ ግሪክኛ የተመለሰው የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው ትርጉም " ሰብዓ ሊቃናት" (Septuagint) የተተረጐመው ቅ.ል.ክ ከ285-246 በዳግማዊ በጥሊሞስ ፊላደልፉስ (Ptolemy II Philadelphus) ዘመነ መንግሥት በግብጽ አገር በአስክንድርያ ነው፡፡ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የሚባለውም ስም 70 የሚል ትርጉም ከነበረው ከላቲን ቃል የተገኘ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሮማውያን ቁጥር LXX /70/ ምልክት ተሰጥቶታል፡፡ ይህም ሎጥር መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግሪክኛ ተርጉመዋል ተብለው የሚታመንባቸውን ሰባ ሁለት /72/ የአይሁድ ምሁራንን ያመለክታል፡፡

የግሪክ ግዛት የሆነችው የመቄዶንያው ንጉሥ ታላቁ አስክንድር ቅ.ል.ክ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያደረገው የግዛት መስፋፋት ግብፅን በመቂዶንያ ግዛት ሥር እንድትወድቅ አድርጓት ነበር፡፡ ከዚያም በአጭር ጊዜ ውስጥ ግሪክኛ ቋንቋ በመላው የግሪክ ግዛት የመግባቢያ ቋንቋ ሆነ፡፡ በአዲስ መልክ የተመሠረተችው የአስክንድርያ ከተማ በግሪክ ግዛት ውስጥ በተሰበሰቡ በተለያዩ ሕዝቦች መካከል ግሪክኛ የጽሑፍና የንግግር መግባቢያ ቋንቋ የተደረገባት ከተማ ሆነች፡፡ በብዙ የአስክንድርያ ነዋሪዎች መካከል የአይሁዶች ቁጥር ከፍ ያለ ነበር፡፡ ከአስክንድርያ ነዋሪ ሕዝቦች መካከል አንድ ሦስተኛው አይሁዶች እንደነበሩ ይታመናል፡፡[28] ሆኖም የአይሁድ ሕዝቦች ወደ ግብፅ በብዛት መግባት የጀመሩት ከታላቁ አስክንድር ድል ቀደም ብሎ ነበር፡፡ ግብፅ በተለይም አስክንድርያ ታላቁ አስክንድርን በተካው በበጥሊሞስ 1ኛ (Ptolemy I) አገዛዝ ወቅት የበዙ አይሁዶች መኖሪያ ሆና ነበር፡፡ ስለዚህም የአይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍት መኖር በአስክንድርያ ለሚኖሩ የግሪክ ሕዝቦች በቀላሉ የሚታወቅ ነበር፡፡ [29]

## የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) አመጣጥ

የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግሪክኛ ለመተርጎሙ ታሪክ ቀዳሚውና በጣም የታወቀው ምንጭ አራስቲያ (Aristea) ለወንድሙ ለፊሎክራጥስ (Phiolcrates) የጻፈው ደብዳቤ ነው፡፡ ይህ ደብዳቤ የግብፅ ንጉሥ ዳግማዊ በጥሊሞስ ፋላደልፉስ (Ptolemy II Philadelphus) (ቅ.ል.ክ 285-247) በአስክንድርያ ላቋቋመው አዲስ ቤተ መጻሕፍት ከተቻለ በዓለም ያሉ መጻሕፍትን ሁሉ ለማሰባሰብ ተመኝቶ እንደነበርና ብዙም እንደሰበሰበ ይገልጻል፡፡ በጣም ተፈላጊ የሆነው የአይሁድ የሕግጋት መጽሐፍ ቅጅ በቤተ መንግሥቱ ቤተ መጻሕፍት አለመኖሩን ዘግይቶ በመረዳቱ ደብዳቤ ጽፎ አራስቲያስ አራሱና ሌሎች ያሰብትን የመልእክተኞች ቡድን በኢየሩሳሌም ለሚገኘው ሊቀ ካህናት አልአዛር (Eleazar) ላከ፡፡ በዚህም መልእክቱ የአይሁድን ሕግ ቅጅና እሱን ወደ ግሪክኛ መተርጐም የሚችሉ ምሁራንን ወደ አስክንድርያ እንዲልክለት ጠየቀ፡፡ መልእክቱም የተሳካ ውጤት አስገኘ፡፡ ሊቀ ካህናቱ በንጉሡ ጥያቄ ተስማምቶ በሚገባ የተጌጠ የአይሁድን መጽሐፍ ቅዱስና ይህንንም ቅዱስ መጻሕፍ ጥሩ አድርገው የሚተረጉሙ ከአሥራ ሁለቱ ነገደ አስራኤል ከእያንዳንዱ 6፤ በአጠቃላይ 72 ሊቃውንትን ላከለት፡፡ በዚህም ምክንያት ትርጉሙ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint){LXX} የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡ ንጉሥ ዳግማዊ በጥሊሞስ እንደ መጀመሪያ እርምጃ አድርጎ ከመቶ ሺህ ለሚበልጡ አይሁዳውያን ምርኮኞች ነፃነት ሰጡ፡፡[30] ተርጓሚዎቹም እስክንድርያ በደረሱ ጊዜ በንጉሡ ክፍተኛ አቀባበል እንደተደረገላቸው ተገልጿል፡፡ ከዚያም ከአስክንድርያ አጠገብ ወደሚገኝ ምቹና ገለል ያለ አካባቢ ተወስደው የመኖሪያ ቦታ ተሰጣቸው፡፡[31] አንድ ሌላ ምንጭ ወደ ፋሮስ የሚባል ደሴት[32] እንደተወሰዱ ይናገራል፡፡ የትርጉሙም ሥራ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ ልክ በተርጓሚዎቹ ቁጥር በ72 ቀናት እንደተጠናቀቀ አንዳንድ ትውፊታዊ ምንጮች ይናገራሉ፡፡ ሰባ ሁለቱ ሊቃናት ሁለት ሁለቱ በአንድነት በሠላሳ ስድስት ቡድን ተከፍለው አንዱ ቡድን ከሌላው ጋር በማይገናኝበት ፍጹም የብቸኝነት ሁኔታ እንዲሠሩ መደረጋቸውንም ይናገራሉ፡፡ ለእያንዳንዱም ቡድን ጸሐፊ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ሕገ ኦሪትን በመንፈስ ቅዱስ ረድኤትና አነሳሽነት ስለተረጉሙ የ36ቱም ቡድን ረቂቅ በሁሉም መልኩ ፍጹም ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡[33] ሌሎች ተጨማሪ ታሪኮች እንደሚሉት እያንዳንዱ ተርጓሚ የራሱ ክፍል ተሰጥቶት የተረጉመ ሲሆን የሁሉም ትርጉም በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ስለተፈጸመ ትርጉማቸው ቃል በቃል ተመሳሳይነት ያለው ሆኗል፡፡[34]

28 Jerasimos Konidaris, General Church History (Athens 1957), p.66
29 Lancelot C.L.Brenton, The Septuagint with the Apocrypha: Greek and English (Handrickson Publisher, 1998).
30 ገ.ክ ከማሁ
31 Melvin K.H.Perers, "Septuagint" in The Anchor Bible Dictionary (?Doubleday) 1992, vol.5, 1096.
32 C. Brenton, (1998), p.ii
33 H. B. Swete, An Introduction to the Old Testament in Greek (abbridge, 1989), 9-12.
34 Brenton (1998), ii

www.ethiopianorthodox.org

ትርጉሙ የአይሁድ ካህናት ሽማግሌዎች ሕዝቡ በእስክንድርያ ተሰብስበው በተገኙበት ተነበበ፡፡ ከምንጩ ዕብራይስጡ ጋር ፍጹም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ሁሉም በአድናቆት ተቀበሉት፡፡[35] ንጉሡ ዳግማዊ በጥሊሞስም ስለ ዕብራውያን የሕግ መጽሐፍ በከፍተኛ ደረጃ ተደነቀ፡፡ ተደስቶም ትርጉሙን በቤተ መጻሕፍቱ አስቀመጠው፡፡ ተርጓሚዎቹም ከንጉሡ ብዙ ሽልማቶችን ለራሳቸውና ለኢየሩሳሌሙ ሊቀ ካህናት እንደተቀበሉ በጽሑፉ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ተርጓሚዎቹ ወደሀገራቸው ሲሄዱ ንጉሡ ወደ እስክንድርያ ተመልሰው እንዲመጡ ጋብዟቸው ነበር፡፡ [36]በአራስትያስ ደብዳቤ መሠረት በእስክንድርያ ውስጥ የነበሩ አይሁዳውያን በየምኩራባቸው እንዲጠቀሙበት የአዲሱ ትርጉም ቅጅዎች እንዲሰጣቸው ንጉሡን ጠይቀው ተሰጥቶአቸዋል፡፡ በመሆኑም ትርጉሙ ታዋቂነት አግኝቶ በእስክንድርያ በሚኖሩ አይሁዳውያን ማኅበረሰብ ዘንድ ታላቅ አድናቆትን አትርፏል፡፡ ትርጉሙ "ፈጽሞ የተጣራ ስለሆነ በመግደፍ፣ አቀማመጡን በማዘዋወር ወይም በመጨመር ማናቸውም ክፍል እንዲሰወር በሚያደርግ ሰው ላይ ርግማን እንዲያርፍበት በአይሁዳውያን ማኅበረሰብ በወቅቱ ተወስኖ ነበር፡፡[37]

የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ትርጉም በጥንቃቄ በመመርመር አንዳንድ ምሁራን በኦሪስትያስ ደብዳቤ እንደተገለጸው ትርጉሙ የተካሄደው በፍልስጥኤም አካባቢ በሚኖሩ አይሁዶች ሳይሆን በግብፅ ውስጥ በሚኖሩ አይሁዳውያን እንደሆነ ያስባሉ፡፡ የሚያቀርቡአቸውም ምክንያቶች (1ኛ) በትርጉሙ ውስጥ ግብፃዊ ምንጭነት እንዳለው በግልጽ የሚያሳዩ አገላለጾችና ቃላት እንዳሉበት ያትታሉ፤ (2ኛ) Vander Heeren አስተያየት ሲሰጥ "የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ዋና ቋንቋ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ተርጓሚዎቹ ስለ ዕብራይስጥ ቋንቋና ስለፍልስጥኤም መልክአ ምድር የተሟላ ዕውቀት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡ በአንጻሩ የሚያመለክተው ልዝብ ያልሆነውን የአስክንድርያን ፈለጊዊ አነጋገር ነው"[38] ብሏል፡፡ (3ኛ) በተመሳሳይም Sir Brenton በ285 ቅ.ል.ክ በዚያ ቋንቋ ትርጉም ለማካሄድ የሚያስችል በቂ የግሪክኛ ቋንቋ ዕውቀት የነበራቸው አይሁዳውያን በፍልስጥኤም መኖራቸውን ይጠራጠራል፡፡ (4ኛ) ሌሎች ምሁራን ደግሞ የሰብዓ ሊቃናትን ትርጉም ምንጭ በተመለከተ ሌላ መላምት በመፍጠር ብሉይ ኪዳንን ለግብፅ ንጉሥ (ለጳጥሊሞስ) የተረጐሙለት በፍልስጥኤም የነበሩ አይሁድ ሳይሆኑ፣ በእስክንድርያ የነበሩ አይሁድ ናቸው፡፡ ይህንንም ያደረጉት ለእነርሱ መነጋገሪያ ቋንቋቸው በሆነው በግሪክኛ የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ሲሉ ግምታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይሁንና ይህን መላምት ለመቀበል አንዳንድ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ (5ኛ) አንዳንድ ምሁራን በአጭር ጊዜ ውስጥ (35 ዓመታት) የእስክንድርያ አይሁዳውያን እንዲህ ያለ ትርጉም አስፈለጋቸው ብሎ ማሰብ አይቻልም በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአአምሮ መያዝ ያለበት በዚህ ጊዜ በእስክንድርያ ከኖሩበት ይልቅ ረዘም ላለ ጊዜያት በኖሩባቸው አገሮች ቋንቋዎች አይሁዶች ምንም ዓይነት ትርጉም እንዳለደረጉ ፍንጭ አለመገኘቱ ነው፡፡[39]

ስለሆነም በጣም አሳማኝ የሆነው መደምደሚያ ለግብፁ ንጉሥ ትርጉሙ ተፈጽሞለታል፤[40] የአይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍት ቅጅም በጥያቄው መሠረት ከተርጓሚያን ቡድን ጋር በኢየሩሳሌሙ ሊቀ ካህናት ለንጉሥ በጥሊሞስ ተልኮለታል የሚለው ይሆናል፡፡ እንዲሁም የግሪክኛ ቋንቋ ጥሩ እውቀት ያላቸው በእስክንድርያ ጥቂት አይሁዳውያን ከኢየሩሳሌም ከመጡት 72 ሊቃውንት ጋር በትርጉሙ ሥራ ተባብረዋል ማለትም ይቻላል፡፡ ከዚያ በኋላም በእስክንድርያ የሚኖሩ ግሪክኛ ተናጋሪዎች አይሁዶች ከመደበኛው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ የነበራቸው ዕውቀት እየቀነሰ በመሄዱ በሰብዓ ሊቃናቱ ትርጉም መጠቀማቸው አያጠርጥርም፡፡

35 A. Vander Heeren, "Septuagint Version" in the Catholic Encyclopedia, vol. XIII, 2.
36 Ibid., p.ii, peters, "Septuagint" in the Anchor Bible Dictionary, vol.5, p.1096.
37 Perers, "Septuagint" in the Anchor Bible Dictionary, vol.5,p.1096; C.L>Brenton, 1998, p.ii; Septuaginta edited by A. Rahlfs (Stutagart 1935), vol.I, XXIII.
38 A. Vander Heeren, "Septuagint Version" in The Catholic Encyclopedia, vol. XIII, p.3.
39 C.L.Brenton, Septuagint, p.ii.
40 Ibid., p.ii.



## የአይሁድ ቀኖና መጻሕፍት በሙሉ በሰብዓ ሊቃናት ተተርጉመዋል?

ከላይ እንደታየው በሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የትርጉም ውጤት ዙሪያ ያሉ ሁኔታዎች ብዙ አከራካሪዎች ናቸው፡፡ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የሚለው ቃል በአጠቃላይ የሚውለው 1ኛ. ለዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፤ 2ኛ. የዕብራይስጡ ምንጫቸው ለጠፉባቸው ወይም በከፊል ለተጠበቁ ተጨማሪ መጻሕፍትና 3ኛ. በመጀመሪያ በግሪክኛ ለተጻፉና በአንዳንዶች በዕብራይስጥ ለተጻፉ ነገር ግን በዕብራይስጥ ቀኖና ውስጥ ላልተካተቱ መጻሕፍት ነው፡፡ ይሁንና የታወቁ ነገር ግን የዕብራይስጥ አቻ የሌላቸው መጻሕፍት በተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንደ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) አይቆጠሩም፡፡ በተለምዶ አዋልድ ተብለው ነው የሚቆጠሩት፡፡

አንዳንድ ምሁራን የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም (Septuagint) የሚይዘው የመጀመሪያዎቹን አምስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (አምስቱ ብሔረ ኦሪት) ብቻ ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን የግሪክ አይሁዳውያን ቅዱሳት መጻሕፍትን ሁሉ ያጠቃልላል ይላሉ፡፡ ይሁንና በአሪስቲያስ ደብዳቤ የተገለጹት ድርጊቶች የሚያመለክቱት አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት (አምስቱ ብሔረ ኦሪትን) ብቻ ነው፡፡ [41] ብዙ ምሁራን የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ሁሉም መጻሕፍት ትርጉም በተመሳሳይ ጊዜ በተመሳሳይ ሕዝቦች የተፈጸመ አንድነት ያለው ትርጉም አይደለም፤ ነገር ግን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ተርጓሚዎች የተተረጉሙ ተከታታይ ትርጉሞችን የያዘ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ ሆኖም የመጨረሻዎቹ ክፍሎች ቅ.ል.ክ በ1ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ክፍል እንደተጠናቀቁ ምሁራኑ አረጋግጠዋል፡፡ ከአምስቱ የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍተ ኦሪት በቀር ሌሎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ትርጉሞች የተለያዩ ሰዎች ሥራዎች እንደሆኑ የሚታወቁት በአተረጓጐማቸው ነው፡፡ አተረጓጐማቸው በመጀመሪያ ደረጃ ከቃል በቃል እስከ ነፃ አተረጓጐም የሚዘዩ ሁኔታ ይታይባቸዋል፤ በ2ኛ ደረጃ ልዩነቱ በአተረጓጐም ስልት፣ ቅርጽና ዓይነት ሁሉ ይታያል፡፡ በመሆኑም የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ትርጉም ሦስት ዓይነት የአተረጓጐም ምልክቶችን ያሳያል፡፡ እነዚህም በምሁራን እንደታዩት አንዳንድ ጊዜ ፍጹም የቃሉን ትርጉም ብቻ የሚከተል ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በፍቺው ላይ የተመሠረተ ሆኖ ይገኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ነፃና በተርጓሚው አባባል ተተርጉሞ ይገኛል፡፡[42]

## ለሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የተሰጠ ምስክርነት

ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) በመጀመሪያ በከፍተኛ ክብር ተይዞ በእስክንድርያ በመኖሩ የአይሁድ ማኅበረሰብ መደበኛ እውቅና አግኝቷል፡፡ በእስክንድርያ የአይሁድ ማኅበረሰብ ከፍተኛ አባል፣ በግሪክ ቋንቋ፣ በፍልስፍናና በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ ዕውቀት የነበረው ፊሎ (philo) እና ቅ.ል.ክ በ1ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ የነበረው ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (Josephus)፣ እንደነዚህ ያሉ ጸሐፊዎች ሰብዓ ሊቃናትን (Septuagint) በአማራጭነት ይጠቀሙ ነበር፡፡ ፊሎ ((philo)) ለሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ከፍተኛ ግምት ስለነበረው፣ የሚከተለውን ገለጻ ሰጥቷል፡፡ "ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ከዋናው ምንጭ ከዕብራይስጥ የተተረጉመና ትክክለኛ መጽሐፍ ነው፡፡[43] እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ተርጓሚዎችን "እንደተርጓሚዎች ሳይሆን እንደ ነቢያትና የጌታ ካህናት አድርጎ" ይገምታቸው ነበር፡፡[44]

የኦሪስትያስ ደብዳቤና የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ታሪክ በብዙ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ድ.ል.ክ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩ የጥንቶቹ አብያተ ክርስቲያናት ጸሐፊዎች እውነተኛና ትክክለኛ ነው ተብሎ ተቀባይነትን አግኝቶ ቆይቷል፡፡ ጠርጥሊያኖስ (Tertullian)፣ ቅዱስ አውገስጢኖስ (St.Augustine) እና ሰማዕቱ ጀስቲን(Justin the Martyr) የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) 72 ተርጓሚዎች በአግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት እንደተረጐሙት አምነው ተቀብለውታል፡፡[45] ቅዱስ ኢሬኒዮስ St. Irenaeus እና ቀሌምንጦስ በእስክንድርያ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡፡ "ሲተረጐሙ እርስ በእርስ አልተማከሩም፡፡ በተለያዩ ክፍሎች በነበሩ ወይም በቡድን ሆነው ነው የተረጐሙት፡፡ ትርጉሞቻቸውም ሲወዳደሩ ከመተርጐሚያው መጽሐፍና ከእያንዳንዱ ጋር በስሜትም በአገላለጽም የሚስማሙና የማይለያዩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡[46]

41 Melvin K. H. Peters, "Septuagint" in The Anchor Bible Dictionary (Doubleday 1992), vol.5,p.1104.
42 Michael Jinbachian, "Bible Translation Throughout History and Today", unpublished paper, p.5; C.L.Brenton, 1998,p.ii.
43 Peter Borgen, "Philo of Alexandria" in the Anchor Bible dictionary, vol.5,p.336.
44 Michael Jinbachian, "Bible Translation...", p.7.

www.ethiopianorthodox.org

## ለመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) አስፈላጊነት

ሀ. ከላይ እንደአየነው ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) በጣም ጥንታዊ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ነው፡፡ ለዚህም ይህ ትርጉም በአሁኑ ጊዜ ለዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ማሶራቲክ ምንባብ (Masoretc Text) ተብሎ በዓለም ተቀባይነት ያገኘውን የዕብራይስጡን ቴክስት (ምንባብ) ለመረዳት ከፍተኛ ጥቅምና ተፈላጊነት አለው፡፡ "ማሶራቲክ ቴክስት" (Masoretc Text) የሚለው ስያሜ የሚያመለክተው አንድ ነጠላን መጽሐፍ ሳይሆን የብዙ መጻሕፍትን ስብስብና ሌሎች ምንጮችንም ነው፡፡ የእነዚህ መጻሕፍት ጥንተ ነገርና የመጨረሻ ቅርጻቸውም የተወሰነውና የተመሠረተው በመካከለኛው ዘመን ምናልባትም ድ.ል.ክ በ6ኛውና በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት መካከል ማሶራቶች በሚባሉ የአይሁድ ሊቃውንት ነው፡፡[47] ቅ.ል.ክ በ3ኛውና በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት እንዲሁም ድ.ል.ክ በመጀመሪያዎቹ አምስት መቶ ዓመታት መካከል የቴክስት ብልሽት፣ ግድፈት፣ ጭማሪ ወይም የቦታ ልውውጥ በዕብራይስጡ ቴክስት ውስጥ ተከስቷል ብለው ብዙ ምሁራን ያምናሉ፡፡ የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ትርጉም የተመሠረተባቸው መጻሕፍት በአንዳንድ ቦታዎች ከማሶራቲክ መጻሕፍት የተሻሉ ናቸው ከሚለው ከVander Heeren ጋር እንስማማለን፡፡[48]

ለ. ከመጀመሪያው አንስቶ የአስክንድርያ ግሪክኛ ተናጋሪዎች አይሁዶች ሰብዓ ሊቃናትን (Septuagint) ለምኩራባቸውና ለማስተማሪያነት በፍልስጥኤም የሚገኙት ረበናት መምህራን ሳይቀሩ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ እናም አይሁዳውያን ቀስ በቀስ ለሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የመጨረሻውን ከፍተኛ ሥልጣን (ዕውቅና) ሰጥተውታል፡፡[49] በኋላም ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ከአስክንድርያ ዘዝርወት ባሉ አይሁድ ሁሉ መካከል ተሰራጨ፡፡ በዚህ መንገድ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) አይሁዳዊነትን በማስፋፋትና በመጠበቅ ተግባር ከፍተኛ ጥቅም ያለው መሆኑ ተረጋገጠ፡፡[50] ከአባቶቻቸው አገር ርቀው በስደት ላይ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ የዕብራይስጥ ቋንቋ ዕውቀታቸው በጣም እየቀነሰ በመጣ ጊዜ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ለሕገ ኦሪትና ለሌሎች የአይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍት በታማኝነት እንዲቀጥሉ ረድቷቸዋል፡፡ እንደዚሁም አይሁዳውያን ያልሆኑ ሕዝቦችም ከአይሁድ መጻሕፍት ዕውቀት እንዲቀስሙና ስለ አንድ አምላክ እምነት ግንዛቤ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡[51]

ሐ. በተጨማሪም ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ለኋላኛው የክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮ መንገድ ጠራጊ ሆኗል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከክርስትና የመጀመሪያ ቀናት ጀምሮ ለአይሁዶች እንደሆነ ሁሉ ለክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንም ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ቅዱስ መጽሐፋቸው ስለሆነ ነው፡፡

ድ.ል.ክ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በአነስተኛ ቁጥርም ቢሆን በርሚውያን ግዛት የአይሁድ ሕዝብ ያልነበረበት ከተማ አይገኝም ነበር፡፡ ክርስቶስ በተወለደበት ጊዜ በምድረ አስራኤል ውስጥ ከነበሩት ይልቅ በውጭ የነበሩት አይሁድ አምስት ወይም ስድስት ጊዜ አጥፍ ይሆኑ እንደነበር ይገመታል፡፡[52] በዚህ የአይሁድ በዓለም ሁሉ መሰራጨት የአውነተኛው አምላክ ዕውቀትና የመሲሕ መምጣት ተስፋ በሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) አማካይነት በአሕዛብ ምድር ሁሉ በመጠኑም ቢሆን ይታወቅ ነበር፡፡ ይህም ለክርስትና መስፋፋት በአያሌው ረድቷል፡፡ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ተሠራጭቶ ስለነበር የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች እንደ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ አድርገው በቀላሉ ተቀብለውት ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በስብከቱ፣ ሐዋርያትም በትምህርታቸውና ሐዲስ ኪዳንን በጻፉበት ወቅት ከብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ሲጠቅሱ ዘወትር የሚጠቅሱት ከሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ነበር፡፡ ስለሆነም የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በጻፉበት ጊዜ ሰብዓ ሊቃናትን (Septuagint) በእውነተኛ ትርጉምነቱ ተጠቅመውበታል፡፡

45 Vander Heeren, op.Cit.3
46 Ibid.
47 Emanuel Tov, Textual Criticism of the Hebrew Bible (Fortress press, 1992), 22.
48 vander Heeren, op. cit., p.iii
49 C.L.Brenton, op. cit., p.iii
50 Septuagint, vol.I,p.XXIII.
Ibid. Wilston Walker, A History of the Christian Church (N?Ew York, 1959), 16. በአስክንድርያ የአይሁድ ሕዝብ ቁጥር የአመለካከት ሕዝቡ አንድ ሦስተኛ ነበሩ፡፡ J. Konidaris, General Church History (Athens 1957), p.66.





ክርስትና ቀስ በቀስ ከተስፋፋ በኋላ ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) አዲስ በተቋቋሙት ማኅበረ ክርስቲያን መካከል በሰፊው ተሰራጨ፡፡ እናም ብዙ ዓመታት ከማለፋቸው በፊት ይህ ትርጉም በአሕዛብ፣ እንዲሁም በአይሁድ እጅ ይገኝ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አይሁዳውያን ሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) በክርክር ወቅት በእነርሱ ላይ እንደመከራከሪያ ነጥብ እየሆነ በተግባር መዋሉን ባወቁ ጊዜ፣ ለሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ይሰጡት የነበረው አክብሮት ተቃራኒ ወደሆነ ስሜት ተለወጠ፡፡ በክርስቲያኖችና በአይሁድ መካከል በማካሄደው የዘወትር ንትርክ ክርስቲያኖች ከሰብዓ ሊቃናት(Septuagint) ራሳቸውን ለዩ፡፡ በዚህም ምክንያት ለሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) የነበረውን ዕውቅናና ሥልጣን ለማሳጣት የሚቻላቸውን ሁሉ አደረጉ፡፡ የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ትርጉም ትክክለኛ አይደለም እያሉም ይከራከሩ ጀመር፡፡

ይሁንና የአሕዛብ ክርስቲያኖች የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ትርጉም ትክክለኛና በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት የተተረጐመ መሆኑን አበክረው ይናገሩ ጀመር፡፡ እነርሱ እንዲያውም በአይሁድ በኩል የተከሰተው ክህደት እግዚአብሔርን እንደማቃለልና ለእነርሱ እውርነት እንደማስረጃ አድርገው ተመልክተውታል፡፡

ድ.ል.ክ በመጀመሪያዎቹ አንድ ሺህ ዓመታት ክርስትና በየቦታው ሲሰራጭ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) መሠረትነት ነበር፡፡ የሚተረጐሙት፡፡ ስለሆነም ብሉይ ኪዳን ወደ ቅብጥ፣ ግእዝ፣ የጥንቱ ላቲን፣ አረብኛ፣ አርመን፣ ጆርጂያና ወደ ጥንቱ ስላቮኒክ የተተረጐመው ከሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ነበር፡፡ በአሁኑም ጊዜ ሁሉም የምሥራቅና የኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ለቤተ ክርስቲያን አምልኮና ትምህርት እንደመደበኛ ቴክስት (መጽሐፍ) አድርገው የሚጠቀሙት ሰብዓ ሊቃናትንና (Septuagint) ከሱ የተገኙ ትርጉሞችን ነው፡፡

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግእዝ መቼ ተተረጐመ የሚለውን ጥያቄ እስቲ ለጥቂት ጊዜ እንመልከት፡፡ የኢትዮጵያን መጻሕፍት ብዙዎቹ በተቀመጡባቸው ሁኔታዎች ምክንያት የተተረጐሙባቸውን (የተጻፉባቸውን) ቀናት መወሰን ከባድ ችግር ይፈጥራል፤ ቢሆንም አሁን ያሉት ቀደምት የመጽሐፍ ቅዱስ በእጅ የተጻፉት (የብራና) መጻሕፍት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተጻፉ ብዙ ምሁራን ያምናሉ፡፡[53] በእርግጥ ይህን ማለት መጽሐፍ ቅዱስ እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በኢትዮጵያ ቋንቋ አልተተረጐመም ማለት አይደለም፡፡ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጨምሮ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በኢትዮጵያ ቢያንስ የክርስትናን ያህል ዕድሜ እንዳለው ይገመታል፡፡

ከ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የመጽሐፍ ቅዱስ የእጅ (የብራና) ጽሑፎች ለምን እንደሌሉን ጥሩ ምክንያቶች አሉ፡፡ 1ኛ. ከሁሉ አስቀድሞ በጥንታውያን ጽሑፎች ሳይንስ (Science of paleography) በመታገዝ የኢትዮጵያ የእጅ መጻሕፍት የተጻፉበትን አቅራቢያ ዘመን የሚወስን በቂ ምርምራዊ ጥናት አልተደረገም፡፡ 2ኛ. የአገሪቱ የአየር ጠባይ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ የኢትዮጵያ አየር ጠባይ በተለይም ባህሏ ባደገበትና ክርስትናም በተስፋፋበት በደጋማው ክፍል አየሩ በጣም ቀዝቃዛ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ የእጅ /የብራና/ መጻሕፍትን ለረጅም ዘመናት በደህና ሁኔታ ጠብቆ ማቆየት አይቻልም፡፡ 3ኛ. በመካከለኛው ዘመን ክርስትናን በሚቃወሙ ኃይሎች ሁለት ዐበይት ጦርነቶች ገጥመዋት ሀገሪቱ ተሰቃይታለች፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የብራና የጸሎት መጻሕፍትና ቅዱሳት መጻሕፍት ጨምሮ ጥንታውያን የባህል ቅርሶች በብዛት ወድመዋል፡፡ በ 9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበርስትና ተቃራኒ የሆነች "ጉዲት" ተብላ የምትጠራ ሴት በኃይል ሥልጣን ይዛ ለ40 ዓመታት ክርስቲያኖችን በጭካኔ አሳዳለች፡፡ በእርሷ አገዛዝ ዘመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በውስጣቸው ከነበሩ በዋጋ ከማይተመኑ መጻሕፍትና ንዋያተ ቅድሳት ጋር ተቃጥለዋል፡፡[54]

በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ አቲላ ተብሎ የሚጠራው የሙስሊም ጦረኛ ግራኝ መሐመድ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (1520-51) ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ብዙ ቅድሳት መጻሕፍትና የጸሎት መጻሕፍት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው ንዋያተ ቅድሳት ጋር በዚህ የጥፋት ኃይል ወድመዋል፡፡[55]

53 [illegible] ሐዲስ [illegible] 1972ዓ.ም 18
54 [illegible] Rossini, "La caduta della dinastia elavension amarica del Be'eta Nagast." RRAL. XXI (1923). pp.2-314; [illegible] ሐዲስ [illegible] ፹ 203, 225-36; Ibidem. The problems of Gudit". JE[illegible] vol.10.1(1972).pp.113-124; "Church and state in the Aksumite period". PICES. (Addis Ababa, 1966). 1ff.



www.ethiopianorthodox.org

የሆነ ሆኖ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በአንድ በተለየ ጊዜ የተደረገ አይመስልም፡፡ A.Dillman and E. Ullendorff እነደገለጹት "ከሁለትና ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ የወሰደ የቀስ በቀስ ሂደትና ብዙ ተርጓሚዎች የተሳተፉበት"[56] የረዥም ጊዜ ውጤት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ትርጉሙ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ2ኛው አጋሽ እንደተፈጸመ ምሁራን ተስማምተዋል፡፡[57] በሌላ በኩልም Ullendorff የተባለው ፕሮፌሰር R. H. Charles ን[58] ተከትሎ በትክክል ሲናገር "ከመጀመሪያዎቹ ትርጉሞች አንዱም ከ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ በኋላ እንዳልተፈጸመ ደህና ግምት መውሰድ እንደሚቻል" አስተያየቱን በትክክል ሰጥቷል፡፡[59] በA. Ralf አስተሳሰብ መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉም የጀመረው ወደ ኢትዮጵያ በገባበት በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ከሶርያ የመጣው የመጀመሪያው ሐዋርያ፣ በኋላ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ የሆነው አቡነ ፍሬምናጦስ ነው፡፡[60]

በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ የአክሱም መንግሥት ጠንካራ የክርስቲያን መንግሥት ሆኖ እንደነበር የተረጋገጠ ነው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በ451 ዓ.ም. ከተካሄደው ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ የጉባኤውን ውሳኔዎች ባለመቀበላቸው በመለካውያን በኃይል እንዲሰደዱ የተደረጉት የሶርያ መነኮሳት በኢትዮጵያ "ዘጠኙ ቅዱሳን" በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነሱም የመጽሐፍ ቅዱስን አብዛኛውን ክፍል ወደ ግእዝ እንደተረጐሙ ይታመናል፡፡[61]

# ክፍል 4

## መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ /ግእዝ/ የተረጐሙ ሰዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ መተርጐም ቢያንስ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ እንደወሰደ ስለሚታመን በትርጉሙ ሥራ ብዙ ተርጓሚዎች እንደተሳተፉበት አያጠራጥርም፣ ትርጉሞቹም የተለያዩ የቋንቋ ችሎታ በግልጽ የሚታይባቸው እንደሆኑ አጠራጣሪ አይደለም፡፡ ይህን ነጥብ በተመለከተ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስለ ኢትዮጵያ በመጻፍ ታዋቂ የሆነው የመጀመሪያው ሊቅ የነበረው ኢዮብ ሉዶልፍ Job Ludolf "በምንጩ ቋንቋ ያለ ተመሳሳይ ቃል በተለያየ ሁኔታ ተተርጉሟል፣ ይህም የተለያዩ ተርጓሚዎች መኖራቸውን ያመለክታል" በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡[62] E. Littmann የተባለውም ተመራማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት እያንዳንዱ በተለያዩ እውቀታቸው አንዱ ከሌላው በማይመሳሰል ልዩ ልዩ ተርጓሚዎች እንደተተረጐመ ሐሳብ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም Littmann ይህን አጠቃላይ አስተያየት ሲሰጥ የተወሰነ መጽሐፍ ወይም መጻሕፍት አልጠቀሰም ወይም አላመለከተም፡፡ አስተያየቱም አንዳንድ ትርጉሞች ቃል በቃል ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ አጠቃላዩን ስሜት የሚያንጸባርቁ እንደሆኑና፣ አንዳንድ ተርጓሚዎች ደግሞ ጥሩ የግሪክኛና የግእዝ ቋንቋ ዕውቀት እንዳላቸው ሲያሳይ፣ ሌሎች ግን በዚህ ረገድ ብዙ ጉድለቶችን አሳይተዋል የሚል ነው፡፡[63] እኔም በጥናቴ ወቅት የመጀመሪያዎቹን ሦስቱን ወንጌላት The Synoptic Gospels ለማጥናትና የአንዳንድ ቃላትን፣ ሐረጐችንና ጐን ለጐን የሚሄዱ አገላለጾችን አተረጓጐም ለማወዳደር ሞክሬአለሁ፡፡ የሚከተለውን ይመልከቱ

ሀ. Preaching baptism of repentance "የንስሓን ጥምቀት እየሰበከ" ማርቆስ 1.4፣ ሉቃስ 3.3 ፣ የሐዋርያት ሥራ 13.24 ይህ ሐረግ በማርቆስ፣ በሉቃስና በግብረ ሐዋርያት በተለያየ አባባል ተተርጉሟል፡፡ በማርቆስ "... ወይሰብክ ጥምቀተ ከመ ይነስሑ" "... ንስሓ ይገቡ ዘንድ ጥምቀትን ያስተምር ነበር፣" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ በሉቃስ "... ወሰበከ ጥምቀተ ለንስሓ "ለንስሐ ጥምቀትን ሰበከ" ተብሎ ሲተረጐም በሐዋርያት ሥራ "ወሰበከ ሎሙ ... ጥምቀተ ... ከመ ይነስሑ" "ንስሓ እንዲገቡ ጥምቀትን ሰበኳቸው" በሚል ተተርጉሟል፡፡

55 አቶ ተክለ ጻድቅ መኮሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮ (አዲስ አበባ 1965(E.C)pp.40-68; ሥርግው ሐዘል ሥላሴ 1972 ገጽ 18
56 E. Ullendorff, 1968,38; ሥርግው ሐዘል ሥላሴ 1972 pp 120
57 I Guidi, Storia della letteratura ethiopica, (Foma, 1932).pp 12 ff; AVOOBUS, Die Spurem eines aeterem athiopschem Evangelien Texts in Lichte der Literarischem menu, (Stockholm, 1954).pp.15-16; E.Cerulle, Stoma della Letteratura Ethiopica, (Milano, 1956), pp.23-25
58 Hasting's Dictionaties of the Bible, I, 791; E. Ullendorff, 1968, p.44.
59 E. Ullendorff, 1968, 44.
60 A. Ralfs, "Die Aethiopische Bibilibersetzung: in Septuagnasrudien, (Gottangen, 1965). p.673.
61 ሥርግው ሐዘል ሥላሴ 1972 ገጽ 115-121



ለ. For the forgiveness of sins ለኃጢአት ይቅርታ ማቴዎስ 26.28፣ ማርቆስ 1.4፣ ሉቃስ 3.3 እንደገና ይህ ሐረግ በሦስቱም ወንጌላት በሦስት በተለያዩ መንገዶች ተተርጉሟል፡፡ በማቴዎስ "ከመ ይትነደግ ኃጢአት" "ኃጢአት ይቅር ይባል ዘንድ" ተብሏል፡፡ በማርቆስ "ወይትነደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ" "ኃጢአታቸውም ይቅር እንዲባል" በሚል ሲተረጐም በሉቃስ "በዘይትነደግ ኃጢአት" "ኃጢአት ይቅር ይባል ዘንድ" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

ሐ. Confessing their sins "ኃጢአቶቻቸውን እየተናዘዙ" ማቴዎስ 3.6፣ ማርቆስ1.5፡፡ ማቴዎስ " እንዘ ይትአመኑ ኃጣውኢሆሙ" "ኃጢአቶቻቸውን እየተናዘዙ" ሲል ማርቆስ "እንዘ ይትአመኑ ኃጢአቶሙ" "ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ" ብሎታል፡፡ ልዩነት ኃጢአት የሚለው ቃል በብዙና በነጠላ ቁጥር መነገሩ ነው፡፡

መ. ገዳም ማቴዎስ 3.1፣ ማርቆስ1.3፣ ሉቃስ 1.80፣ 3.2፣ 4፣ ዮሐንስ 1.23፣ 3.14፣ 11.54 ይህ ቃል በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ወንጌላት በሁለት የተለያዩ መንገዶች ተተርጉሟል፡፡ ማቴዎስ"ገዳም" /ብቸኛ ቦታ/ ሲለው፣ ማርቆስ "ሐቅል" /ጫካ ወይም ሰው የማይኖርበት/ ብሎ ተርጉሞታል፡፡ የሉቃስ ወንጌል ተርጓሜ በዚህ ቃል ላይ አንድ ዓይነት አቋም የለውም፡፡ በአንድ ቦታ "ገዳም" ሲል /ሉቃ 1.80/፣ በሌላ ቦታ ደግሞ "ሐቅል" ብሏል ሉቃ 3.2፣4፡፡ በዮሐንስ ግን በሁሉም ቦታ ገዳም ተብሏል፡፡

ሠ. Wild honey "የዱር ማር" ማቴዎስ 3.4፣ ማርቆስ 1.6፣ የማቴዎስ ተርጓሚ ይህንን ቃል በግእዝ "መዓረ ገዳም" የዱር ማር ሲለው፣ የማርቆስ ተርጓሚ ግን "መዓረ ጸደና" የጣዝማ ማር ብሎታል፡፡

ረ. brood of vipers የእፉኝት ልጆች(RSV & NIV)**፣ እባቦች(GNB)፣ የእባቦች ጥርቅም(CEV)፡፡ ይህ ሐረግ በማቴዎስና በሉቃስ በተለያየ ሁኔታ ተተርጉሟል፡፡ የማቴዎስ ተርጓሚ በሦስት የተለያዩ ቦታዎች ማቴዎስ 3.7፣ 12.34፣ 23.33 "ትውልደ አራዊተ ምድር"፣ የእፉኝት ልጆች ብሎ ሲተረጉም፣ በሉቃስ ግን "ትውልደ ሰባድዕት" ተብሏል፡፡ ያው የእፉኝት ልጆች ማለት ነው፡፡ ልዩነቱ በግእዝ እነጋገር ነው፡፡

ሰ. ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ ማቴዎስ 3.8፣ ሉቃስ 3.8 ይህ ዐረፍተ ነገር በማቴዎስና በሉቃስ ትንሽ ልዩነት ያለው ሆኖ ተተርጉሟል፡፡ ልዩነቱም በማቴዎስ ግበሩኪ እንከ ሠናየ ፍሬ ዘይደልወክሙ ለንስሓ "ለንስሓ የሚገባ መልካም ፍሬ አድርጉ" የሚለው በሉቃስ "መልካም" የሚለው ቃል ቀርቶ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ" ማለቱ ነው፡፡

ሸ. "እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት ይችላል፡፡" ማቴ.3.9፣ ሉቃ 3.8 ይህ ዐረፍተ ነገር በማቴዎስና በሉቃስ በሁለቱም በተመሳሳይ መንገድ ተተርጉሟል፡፡ ይሁንና በሁለቱ የዐረፍተ ነገሮች አወቃቀር ልዩነት አለ፡፡ ይህም ልዩነት ምናልባት ሁለቱንም ወንጌላት የተረጐሙትን የተለያዩ ሰዎች ወይም የሰዎች ስብስቦች ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው፡፡ ማቴዎስ በግእዝ እንደሚከተለው አስቀምጦታል፡፡ "ይክል እግዚአብሔር እምእላንቱ አዕባን አንሥኦ ውሉደ ለአብርሃም፡፡" በአማርኛ ከላይ በአርእስቱ እንደጻፈው ነው፡፡ የሉቃስ አቀማመጥ ደግሞ እንደሚከተለው ነው፡፡ "ይክል እግዚአብሔር አንሥኦ ውሉደ ለአብርሃም እምእላንቱ አዕባን፡፡" በአማርኛ "ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል" ማለት ነው፡፡

ቀ. ዲያብሎስ፡- ይህ ቃል በማቴዎስ ስድስት ጊዜ ተጽፎአል፡፡ 4.1፣ 5.8፣11፣ 13.39፣ 25.41፡፡ በሁሉም ማስረጃዎች ከ25-41 በቀር ቃሉ "ዲያብሎስ" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ በ25.41 ግን "ሰይጣን" ተብሏል፡፡ ይኸውም ቃል በሉቃስ ወንጌል በአምስት ቦታ ይገኛል፡፡ 4.2፣3፣6፣13፣8.12 እናም በእነዚህ ሁሉ "ሰይጣን" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ እንደዚሁም የዮሐንስ ወንጌል ተርጓሚዎች በመጽሐፉ በሙሉ "በዲያብሎስ" ፈንታ "ሰይጣን" የሚለውን ቃል ተጠቅመዋል፡፡

62 H.Ludolf, Commentariusad Suam Historium Aethiopco, (Frankfort, 1691), Lib. Iii, Cap 4, 2-7.
63 I.Littmann, "Geschichte der Aethiopischen Litteratur: in Geschichte D. Chrislichen Litteratureen des Orients, 2nd ed. (Leipzig, 1909), pp.223-25. See comment on this in Ullendorff, 1968, 46.

www.ethiopianorthodox.org

 በ. *** በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ማቴ 3.3፣ ማር 1.3. ሉቃ 3.3-6፣ ይህ ሐረግ በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ወንጌላት በተለያየ ሁኔታ እንደተተረጐመ ማስተዋሉ ስሜትን የሚስብ ነው፡፡ በማቴዎስ በግእዝ ቋንቋ "ቃል ዘይወርሕ በገዳም፣" ይላል፣ "በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ" ማለት ነው፡፡ ማርቆስ የግእዙ ትርጉም የሚከተለው ነው፡፡ "ቃለ ዐዋዲ ዘይሰብክ በገዳም" የቃል በቃል ትርጉሙም "በምድረ በዳ የሚያስተምር /የሚሰብክ/ ሰው ድምፅ" ማለት ነው፡፡ በሉቃስ የተተረጐመው ደግሞ "ናሁ ቃለ ዐዋዲ በገዳም" የሚል ሲሆን በአማርኛም "እነሆ በምድረ በዳ ቃለ ዐዋዲ" የሚል ነው፡፡

በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን በሁለቱም ተነሣሪ አባባሎች፣ ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጎች በተለያዩ መጻሕፍት በተለያየ ሁኔታ የተተረጐሙባቸው በርካታ ምንባቦች አሉ፡፡ ይህም በግልጽ የሚያስገነዝበው ልዩ ልዩ መጻሕፍት በተለያዩ ተርጓሚዎች መተርጐማቸውን ነው፡፡ ይህም አባባል አንድ ተርጓሚ በመሳሳት ተመሳሳይ ቃልን ወይም አገላለጽን በተለያዩ መጻሕፍት በተለያየ መልክ ሊተረጉም እንደሚችል የሚኖረውን ሁኔታ ሊሸር የሚችል አይደለም፡፡ በአሁኑ ጊዜ እንኳ አልፎ አልፎ አንድ ዓይነት አቋም የሌላቸው ተርጓሚዎች አሉ፡፡ አንድን ተመሳሳይ ቃል ወይም አገላለጽ በተለያዩ መጻሕፍት በተለያየ ሁኔታ ሲተረጉሙ እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህ ሁኔታ በተሻሻሉና ቀደምትነት ባላቸው በዕብራይስጥና በግሪክ መጻሕፍት መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስን የግእዝ ትርጉም በቁም ነገር መርምሮ ሐሳዊ ሕትመት እንዲወጣ ማድረግ በጣም አስፈላጊነት አለው፡፡

# ክፍል 5

## መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ ለመተርጉም ጥቅም ላይ የዋሉ ትርጉሞች

መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት በግእዝ የተተረጐመው ከምን ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች ነው? ለሚለው አስቸጋሪ ጥያቄ ብዙ ጊዜ እየተነሣ በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ግምታዊ መልሶች ተሰጥተውታል፡፡ እንደ ኢዮብ ሉዶልፍ (Job Ludolf) እና ብዙ ሌሎች ምሁራን አስተያየት ብሉይ ኪዳን በግእዝ ቋንቋ የተተረጐመው ከሰብዓ ሊቃናት ትርጉም (Septuagint) ነው፡፡ ሐዲስ ኪዳንም እንደዚሁ ከግሪክኛ መጽሐፍ ተተርጉሟል፡፡[64] ይህም ሊሆን ይቻለው ግሪክኛ በአነዚያ ዘመናት የምሥራቃዊ ሮማ ግዛት መደበኛ ቋንቋ በመሆኑና በሶርያ፣ በታናሿ እስያና በግብጽ አብያተ ክርስቲያናት በሰፊው አገልግሎት ላይ ውሎ ስለነበር ነው፡፡ በአክሱም መንግሥትም ወቅት ግሪክኛ በአጠቃላይ ሁኔታ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ በሐውልቶች ላይ በተጻፉ መግለጫዎችና በገንዘቦች ላይ የተገኙት ጽሑፎች ማረጋገጫ ናቸው፡፡[65]

ከሶርያ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያን ፍሬምናጦስና ዘጠኙ ቅዱሳን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግእዝ ሲተረጉሙ በግሪክኛ መጽሐፍ እንደተጠቀሙ ብዙ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ የብሉይ ኪዳን ትርጉምን በተመለከተ ከላይ እንደተጠቀሰው ከሰበዓ ሊቃናት ተርጉም (Septuagint) መተርጐሙ አጠቃላይ ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡ ነገር ግን የየትኛውን ትርጉም ነው የተጠቀሙት የሰብዓ ሊቃናት (Septuagint) ትርጉም መጠነኛ ለውጦች የተደረጉባቸው ሁለት ቅጂዎች አሉ፡፡ እነዚህም በሶርያ ግዛት በሰፊው ሥራ ላይ ውሎ የነበረው ሉስያን ቅጂ (Lucian Recension) እና በግብጽ ይሠራበት የነበረው ሄሲቺያን (Hesychian Recension) የተባለው ቅጂ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዘመናት የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጥገኛ ሆና በመኖሯ የብሉይ ኪዳን የግእዝ ትርጉም በሄሲቺያን (Hesychian Recension) ቅጂ ላይ የተመሠረተ ለመሆኑ ብዙዎች ይገምታሉ፡፡ ሊትማን (Littmann) የተባለው ተመራማሪ ግን በዚህ አይስማማም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን ከሶርያ ስለመጡና አብዛኛውም ትርጉም በእነርሱ የተካሄደ እንደመሆኑ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ያን ጊዜ በሶርያ በሰፊው ሥራ ላይ ውሎ ከነበረው ከሉስያን ቅጂ (Lucian Recension) የተተረጐመ ስለመሆኑ ሊትማን (Littmann) አጥብቆ ያምናል፡፡[66] ይህ በጣም ምክንያታዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የቅርብ ግንኙነት ስለነበራት ነው፡፡

64 H. Ludolf, Historia Aethiopica, (Frankfort, 1681), Lib.iii, Cap. 4. 2-7
65 E. Ullendorf, 1968.41.
66 E. Littmann, 1909, 224ff.





ይሁንና ተርጓሚዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግእዝ በተረጐሙ ጊዜ የግሪክን መጽሐፍ ተጠቅመዋል ስንል ለትርጉማቸው የተጠቀሙት የግሪክ መጽሐፍን ብቻ ነው ማለታችን አይደለም፡፡ ከዚህ በተያያዘ አንድ ሰው ሉፍግሬን (Lofgren) በተባለው ተመራማሪ የሐሳብ መስመር ሊያስብ ይችላል፣ ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግእዝ ቋንቋ የተረጐሙ ከሶርያ የመጡት ዘጠኙ ቅዱሳን ከሆኑ፣ የሶርያን መጽሐፍ ቅዱስ ወይም የሉሲያን (Lucian Recension) ቅጂ ለምን እንዳልተጠቀሙ ለመግለጽ ያስቸግራል የሚለው ነው፡፡[67] ከሶርያ ቋንቋ በብድር የተወሰዱ እንደ ሃይማኖት፣ ገሃነም፣ ኦሪት፣ ጣዖት፣ ቍርባን፣ መሥዋዕት ወዘተ የመሳሰሉ ቃላት በግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መገኘትና ጥቅም ላይ መዋል የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ከሶርያ ቋንቋ ጋር የተለማመዱና ለትርጉማቸው ተግባርም የሶርያን መጽሐፍ ተጠቅመው ሊሆን ይችላል የሚል ጠንካራ ስሜት በአንዳንድ ምሁራን መካከል አስካሁን አለ፡፡[68] ይሁንና ይህ ሙሉ ለሙሉ ትክክል ላይሆን ይቻላል፡፡ እንደ እነዚህ ካሉ የብድር ቃላት አንዳንዶቹ ከአይሁድ አረማይክ (Aramaic) ቋንቋ የተገኙና በኢትዮጵያም ውስጥ ከክርስትና በፊት የነበረው የአይሁድ-አረማይክ (Jewish - Aramaic) ቋንቋ ቅሬት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡[69] ይህም አስተያየት ሲሰጥ የሶርያ የብድር ቃላት ሳይተው ነው፡፡ "ሃይማኖት" የሚለው ቃል ለምሳሌ እምነት በሚለው ስሜት ለክርስትና እምነት ሊወሰንና ለሶርያ ቋንቋ የተለየ ነው ተብሎ ሊታሰብ አይገባውም፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ይህ ቃልና ብዙ ሌሎች የአረማይክ ቃላት ከነድምፃቸውና አነጋገራቸው በግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ የውጭ አገር ቃላት ሳይሆን እንደ ግእዝ ቃላት ሆነው ተወስደዋል፡፡[70]

እንደ A. Voobus[71] F.C. Buritt[72] ያሉ ምሁራንን አስተያየት በመከተል Ullendorff በትክክል እንዲህ ብሏል፡፡ "በ5ኛውና በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሶርያ ሚስዮናውያን በመምጣታቸው የሶርያ ትርጉም ከግሪክ መጽሐፍ ጋር በመቀናጀት ተግባር ላይ ውሏል የሚለው አስተሳሰብ መረጃው በእርግጥ ያበረታታል፡፡"[73] ለግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መሠረትነት ሙሉ በሙሉ የግሪኩን ወይም ሙሉ በሙሉ የሶርያውን ትርጉም ተጠቅመዋል የሚሉትን ሰዎች ባለመቀበል ከፕሮፌሰር ጋር ዩሊንዶርፍ ጋር መስማማት አጥጋቢ ምክንያት ያለው ነው፡፡ "ታሪካዊ ሁኔታዎችና የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ሥነ ልሳናዊ ሐተታ ከሁለቱ ባንዱ ብቻ ተጠቅመዋል የሚለውን ዶግማዊ አመለካከት ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርጋሉ" በማለት ዩ-ሊንዶርፍ ይገልጻል፡፡[74] ለግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በዚህ ሁኔታ የግሪክና የሶርያ የሁለቱም ትርጉም በተለይም የግሪክ ተወዳዳሪ በሌለው በዋና መሠረትነት በተግባር ላይ ውሏል የሚለው መላምት በጣም አሳማኝነት ያለው ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ጥቂት የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን የባህል ሊቃውንት ብሉይ ኪዳን በቀጥታ ከዕብራይስጥ እንደተተረጐመ በአጽንኦት ይናገራሉ፡፡ ይሁንና ይህ የሚመስል አይደለም፡፡ ይህን የሚደግፍ አሳማኝ ማስረጃም አናገኝም፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ምሁራን አስቸጋሪ በሆኑ ጥቂት መጻሕፍትን በመተርጐም ወቅት ተርጓሚዎቹ የአይሁዳውያን ስደተኞችን ምክርና እርዳታ አግኝተዋል ይላሉ፡፡[75] በመሆኑም እንደነዚህ ባሉ ትርጉሞች ጥቂት የዕብራውያን ስሜቶች ተንጸባርቀዋል የሚል ሐሳብም ገልጸዋል፡፡ በአንዳንድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአንዳንድ ግለሰብ ጸሐፊዎችና አንባቢዎች ከዕብራይስጡ ጋር እንዲስማሙ አድርገዋል የሚል ሐሳብ ሊመሠርት ችሏል፡፡[76] ይህ ከዚህ በታች በገርዝር ተገልጧል፡፡ እንደዚህ ያሉ ማሻሻሎችም ቀደም ባለ ጊዜ ማለትም ከ4ኛው ምናልባትም እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ እንደተደረጉ አንዳንድ ምሁራን ያምናሉ፡፡[77] በዚህም ምክንያት የአንዳንድ የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ አከፋፈል የዕብራይስጡን የመጀመሪያ አከፋፈል ይከተላል ብለዋል፡፡

67 E. Ullendorf, 1968.50.57.
68 ሥዩመ ሐዲስ ሥላሴ 1972 120
69 E. Ullendorf, 2968. 39n. 6.
70 See the word hamanot in the Targum of ps. 33:4.
71 A. VOobus, Die Sperum eines alterem aethiopischem Evangelientextes in Liecht der literarischem monumente (Stockholm, 1951). p.8: Idem, Early Versions of the New Testament. (Stckholm, 1954). p. 250.
72 F. C. Burkitt, "Text and Versions" Enncyclopedia Biblica, iv (London, 1903), col. 5012.
73 E. Ullendorff, 1968, 56. የላይኛውን መጽሐፍ ገጽ 56 ይመልከቱ



www.ethiopianorthodox.org

በአራተኛውና በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መካከል መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግእዝ ሲተረጐም በሰባ ሊቃናት ትርጉም (Septuagint) ውስጥ ያሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ፣ ከአዋልድ መጻሕፍትም አብዛኞቹ ጭምር እንደተተረጐሙ ይታመናል። እንደዚሁም እንደ መጽሐፈ ሄኖክ፣ ኩፋሌ፣ ዕርገተ ኢሳይያስ፣ ባሮክ፣ መልእክተ ኤርምያስ፣ የሄርማስ መጽሐፈ ኖላዊ፣ የቀሌምንጦስ መልእክታት፣ ዲዲስቅልያና ትእዛዘ ሐዋርያት በ4ኛውና በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ መካከል ከግሪክኛው ተተርጉመዋል።[78] እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ትውፊት ቀኖናዊና ቀኖናዊ ባልሆኑ ወይም አዋልድ መጻሕፍት መካከል በግልጽ ልዩነት አለማድረጉን ማስተዋል ያስፈልጋል። ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የተጻፉና ቀኖናውያት ናቸው ተብለው በእኩል ደረጃ የሚታዩ ናቸው።

# ክፍል 6

## የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መሻሻል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነሐሴ 20 በሚነበበው ስንክሳር የሚገኝ አንድ ትውፊታዊ ማስረጃ አለ። ይህ ማስረጃ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጐመው አባ ሰላማ በሚባል ተርጓሚ ሊቀ ጳጳስ እንደሆነ ያስረዳል። የተተረጐመውም ከዐረብኛ ነው ይላል። መረጃውም እንደሚከተለው ይነበባል፡

በዛቲ ዕለት አእረፈ አባ ሰላማ መተርጉም ...
ሰላም ለከ ለዖመ ሃይማኖት ስርዋ፤
ትእዛዘተ ኦሪት ወወንጌል እንተ ዲቤከ ተክአዋ፤
ሰላማ ገዘርከ ከመ በጎቤነ ነዋ፤
በከናፍሪከ ምዑዛት እመኃላ ክርቤ ወዐልዋ፤
እምነ ዓረቢ ለግእዝ መጻሕፍት ተዐልዋ፡፡

"በዚች ዕለት /ነሐሴ 20/ ተርጓሚው አባ ሰላማ አረፈ" በማለት ታሪኩን ከጀመረ በኋላ መረጃውን በግጥም መልክ እንዲህ ሲል ይገልጻል፡፡

"የሃይማኖት ዛፍ ሥር ለሆንኸው ላንተ ሰላምታ ይገባል፤
የወንጌልና የኦሪት ትእዛዘት በአንተ ላይ ፈስሰዋል፤
ሰላማ ሆይ መታሰቢያህ በእኛ ዘንድ ይገኛል፤
ክርቤና ዐልዋ ከሚባሉ ሽቶዎች የበለጠ መዓዛ ባላቸው ከንፈሮችህ ኃይል
መጻሕፍት ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል፡፡"[78 80]

ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ስለተደረገው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም እዚህ ላይ የሰጠው መረጃ ወደ ግእዝ የተደረገውን የመጀመሪያውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በምንም ዓይነት አይመለከትም፡፡ የሚመለከተው በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተደረገውን የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማሻሻል ነው፡፡[81] ይህም የተደረገው "አባ ሰላማ" የሚል ቅጽል ተሰጥቷቸው ከነበሩት ከቅዱስ ፍሬምናጦስ ስም ጋር ስማቸው በተመሳሰለው በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩት ሁለተኛው አባ ሰላማ ሊቀ ጳጳስ አመራር ነው። እንዲያውም የእያንዳንዱ "ሰላማ" መለያ በቤተ ክርስቲያኒቷ ተወስኗል። የመጀመሪያው ፍሬምናጦስ "ሰላማ ከማቴ ብርሃን" የሚባሉ ሲሆኑ፣ የኋለኛው ግን "ሰላማ መተርጉም" በሚል ቅጽል ይለያሉ፡፡

የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ትርጉም ማሻሻል ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ አንድ ሰው ሊያነሣ ይችላል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ተርጓሚዎች መነሻ ወይም ምንጭ በሆነው ቋንቋ የሚገኙ አንዳንድ አስቸጋሪ ምንባቦችን በትክክል መተርጉም እንዳልቻሉና ውጤቱም ብዙ ያልተስተካከሉ ትርጉሞችን እንዳስከተለ ይታመናል፡፡ ከእነዚህም ጉድለቶች በተጨማሪ በኋላ ዘመን መሻሻል ባስፈለጋቸው ልዩ ልዩ የተሞሩ መጻሕፍት ውስጥ ከጊዜ ወደጊዜ ብዙ ስሕተቶች ገብተዋል፡፡ የአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የትርጉም መሻሻል በዐረብኛው ትርጉም ላይ የተመሠረተ መሆኑ ይታመናል፡፡

[78] የጳጉሜን መጽሐፍ ገጽ 37- 38 ይመለከቱ፡፡
74 A. Dillman. Biblia Veteris Testamenti Aethiopica, vol. ii, fasc. i., p.3.
75 E. Ullendorff, 1968,57
76 Zuurmond R., "Ethiopic Versions" in The Anchor Bible Dictionary, vol. 6, p. 908
77 "Lesynaxair Ethiopien" in Patrologia Orientalis, vol.ix, 4, p.359



ይሁንና በእነዚያ ዘመናት ከብዙ ምንጮች የተገኙ ብዙ የዐረብኛ ትርጉሞች ስለነበሩ የግእዙን ትርጉም መሻሻል ለማግኘት ከየትኞቹ የዐረብኛ ትርጉሞች እንደተሻሻለ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ብዙ ሊቃውንት እንደሚያምኑት ይህ ማሻሻል የተደረገው ፋዩም (Fayum) የተባለው አገር ሰው የነበሩት "ራባይ ሰአዲያ ጋኦን" (Rabbi Ds'adua Ga'on of Fayum) የተባሉት ሊቅ እንደተረጐሙት በሚገመተው የዐረብኛ ትርጉም ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ የእርሳቸውም ትርጉም ከምንጩ ከዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ጋር በቅርበት የተያያዘ መሆኑ ይታመናል፡፡[82] ይህም ሆኖ የኢትዮጵያው የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ የተሻሻለው ትርጉም ከሰአዲያ (Sa'adia) ትርጉም ጋር ምን ያህል ተመሳሳይ እንደሆነ በእርግጠኝነት ለመናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ዐረብኛ፣ ዕብራይስጥና ግዕዝ በጥሩ ሁኔታ የሚያውቅ /ቀ/ ምሁር /ራን/ የሰአዲያን (Sa'adia) ትርጉም ማጥናትና ከኢትዮጵያው ትርጉም ጋር ማነፃፀር ይኖርበታል፡፡ /ባቸዋል/፡፡

አንዳንድ ምሁራን የብሉይ ኪዳን ትርጉም መሻሻል በዕብራይስጡ መሠረት እንደሆነ ያምናሉ፡፡[83] ሆኖም ይህን አስተሳሰብ የሚደግፍ የተወሰነ ማስረጃ የለም፡፡ ይህ ጉዳይ ጥሩ የዕብራይስጥና የግእዝ ቋንቋ ዕውቀት ባላቸው ምሁራን በቁም ነገር ሊጠና የሚገባው ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በመንበረ ፓትርያርክ በግሪኩ ሰብዓ ሊቃናትና በግእዙ መሠረትነት መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ በምንተረጐምበት ጊዜ የግእዙን መጽሐፍ ቅዱስ ስንመረምር የግእዙ ብሉይ ኪዳን ከግሪኩ ሰብዓ ሊቃናት ይልቅ ከዕብራይስጡ ጋር በጣም የተተራረበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህም የግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራይስጡ መሠረትነት ወይም ከዕብራይስጡ መሠረትነት በተተረጐመው በሰአዲያ (Sa'adia) ትርጉም መሠረትነት እንደተሻሻለ ያላንዳች ጥርጥር ያስረዳል፡፡

አንዳንድ ሌሎች ምሁራን ደግሞ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የተደረጉ ሁለት የተለያዩ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ማሻሻያዎች እንዳሉ ይናገራሉ፡፡ የመጀመሪያው "ተራ /ቀላል መሻሻል" (Vulgar Revision) ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህም ከላይ በተጠቀሰው በሰአዲያ የዐረብኛ ትርጉም ላይ ተመሥርቶ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሻሻለው ነው የሚል ግምት አለ፡፡ ሌላው "በምሁራን የተሻሻለ" (Academic Revision) ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህም ምናልባት በምንጩ በዕብራይስጡ ላይ ተመሥርቶ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሻሻለ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡[84] ይህ መሻሻል ከመጀመሪያው ከዕብራይስጡ ማለት የማሶሬቲክ (Masoretic) ምንባብ ጋር ብዙ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይሁንና ዩሊንዶርፍ (Ullendorff) "የአካዳሚክ ትርጉም መሻሻል" (Academic Revision) የሚባለውን ባለመቀበል አስተያየቱን እንደሚከተለው ሰጥቷል፡፡ "በኋላኛው መካከለኛ ዘመን ሁኔታዎች ሰፊ ለሆነ የዕብራይስጥ ትርጉም ወይም እርማት የተመቻቹ አልነበሩም፡፡" በመሆኑም የ"አካዳሚክ ትርጉም መሻሻል የሚባለውን ለመቀበል የማይቻል መሆኑን" እንደተገነዘበ በማጠቃለያው ገልጿል፡፡ "የዕብራይስጥ ቋንቋ ተጽእኖ ወይም ተሰሚነት ከ4ኛው እስከ 7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ እንደምክንያት ይቆጠራል፡፡" በማለት ዩሌንዶርፍ ያስባል፡፡[85]

ሆኖም ከፍ ባለ ደረጃ በሚወደደው ትውፊት ላይ በመመሥረት የኢትዮጵያ ጥንታውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ብሉይ ኪዳን ሁለት ትርጉሞች እንዳሉት ይገልጻሉ፡፡ አንደኛው ከምንጩ ከዕብራይስጡ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከሰብዓ ሊቃናት ትርጉም (Septuagint) በቀጥታ እንደተተረጐመ ያስገነዝባሉ፡፡ ሆኖም በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስለተደረገው የትርጉም ማሻሻል አንዳችም አይናገሩም፡፡ አዲስ ኪዳንን በተመለከተ ግን የሰላማ ሐዲስ ኪዳንና የቀድሞው ሐዲስ ኪዳን የሚባሉ የሁለት ትርጉሞችን መኖር ይቀበላሉ፡፡[86] ሆኖም የሰላማ ሐዲስ ኪዳን በኢትዮጵያ በካህናቱና በምእመናኑ ዘንድ ታዋቂ አለመሆኑንና በአገልግሎት ላይም እየዋለ እንዳልሆነ መስተዋሉ አስፈላጊ ነው፡፡[87]

በሌላም በኩል የሶርያው ትርጉሞች ለመጀመሪያው የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በመሠረትነት አገልግለዋል የሚል አቋም ያለው ኤ ቮቡስ (A. Voobus) የተባለው ምሁር የ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የትርጉም መሻሻል በግሪክ የመጀመሪያው ትርጉም መሠረትነት እንደተካሄደ በእርግጠኝነት ይናገራል፡፡[88] ይሁን እንጂ የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ባህላዊን ሥነልሳናዊ ሁኔታዎች እንዲህ ያለውን አባባል የሚደግፉ አይመስልም፡፡ ስለዚህ የ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የትርጉም መሻሻል በአመዛኙ በሰአዲያ (Sa'adia) የዐረብኛ ትርጉም ላይ የተመሠረተ ይመስላል፡፡

[80] ... ገጽም ይኸውና ገጽም ይኸ መጽሐፍ የተተመገቡ የጽሑፉን ውፅት ለመጠቀት ነው፡፡
[81] ይኸ ... ከ14ኛው መቶ ዓመት (ዮ.ል.ክ) በኢትዮጵያ የሥጋ ጽሑፍ ትንሣኤ መጀመሪያ መሆኑ ይታወቃል፡፡
[82] The Catholic Encyclopedia, vol. v, 1913, p.570. See also Ullendorff, 1968, pp. 47-49.
[83] H. Hirschberg, Catalogue des mss. Ethiopiens dela Bibliotheque nationale, Paris, 1877, pp.9-11.
[84] Lundgren, O. Die athiopische ubersetzung des propheten Daniel, pans, 1927; xxiv ff.; Schafers, J. Die athiopische ubersetzung Jeremias, Freiburg, 1912; 178; The Achor Bible Dictionary, Vol.6,p.908.
[85] Ullendorff, 1968: 57.



www.ethiopianorthodox.org

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ምሁራን የመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም የቀኖና መጻሕፍትና ጥቂት የአዋልድ መጻሕፍት በዚህ ጊዜ እንዲሻሻሉ እንደተደረገ ገምተዋል፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ ጸሐፊዎቻቸው በሚገባ ሳይታወቁ በመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ሰዎች ስም የተጻፉ እንደ ኪዳነ አብርሃም፣ ሙሴ በሲና ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገው ንግግርና እንደ የሲቢል ጥበብ (Wisdom of Sybil) ያሉ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በ14ኛውና በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መካከል ከዐረብኛ ተተርጉመዋል፡፡[89] በተሻሻለው የትርጉም ክለሳ ወቀት ብዙ ተርጓሚዎች ተሳትፈው ስለነበር የተለያዩ መጻሕፍት የተሻሻሉት የትርጉም ክለሳዎች አኩልነት እንዳይኖራቸውና የተለያዩ እንዲሆኑ ምክንያት ሆነዋል፡፡

# ክፍል 7

## የኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት ኅትመት

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ኅትመት በ1513 ዓ.ም. በሮም ውስጥ በጄ.ፖትኪን (J. Potken) ተዘጋጅቶ የታተመው መዝሙረ ዳዊት (Psalterium Chaldaeum) ነበር፡፡ ይሁንና ይህ ሒሳዊ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ አልነበረም፡፡ ሒሳዊ በሆነ መንገድ የተዘጋጀው የዳዊት መጻሐፍ በያ. ሉዶልፍ (J. Ludolf) የተሠራውና "መዝሙር ዘዳዊት" በሚል ርእስ በ1701 ዓ.ም. የታተመው ነበር፡፡[90] ስለኢትዮጵያ በመጻፍ የታወቀው ሌላው ታላቅ ሰው አገስት ዲልማን (August Dilmnn) ስምንቱ ብሉረ አሪት፣ አንደኛና ሁለተኛ ሳሙኤልን፣ አንደኛና ሁለተኛ ነገሥትን፣ እንደዚሁም የብሉይ ኪዳንን አዋልድ በ1853 እና 1894 መካከል ሒሳዊ በሆነ መንገድ አዘጋጅቶ አሳትሟል፡፡ የተሟላ የኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳን ፍራንቺስኮ ዳ በሳኖ በተባለው የሮማ ካቶሊክ ምሁር ካህን ለመጀመሪያ ጊዜ በ4 ቅጾች /መጻሕፍት/ ተዘጋጅቶ ከ1922-26 ባለው ጊዜ ታትሟል፡፡[91] ይህም ከተለያዩ ምንባቦች ጋር በማነፃፀር ሒሳዊ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ እንዳልሆነ ተገልጿል፡፡[92] የዳባሳኖ ዋና ዓላማ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተግባራዊ ጠቀሜታ ያለው የተሟላ የግእዝ ብሉይ ኪዳን አሳትሞ ማውጣት ነበር እንጂ ሒሳዊ ኅትመት ማዘጋጀት አልነበረም፡፡

ሐዲስ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1548 በሮም ታተመ፡፡ "ኢዲቲኦ ፕሪንሴፕስ" (Editio Princeps) ተብሎ የተጠራው ይህ እትም በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ተጠብቀው በኖሩ ቀደምት የእጅ /የብራና/ ጽሑፎች ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ ይህም ፕትመት ኢየሩሳሌምን ጐብኝተው ወደ ሀገራቸው ይመለሱ የነበሩ ሦስት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ወደ ሮም ሄደው ስለነበር በእነርሱ የተዘጋጀ ነበር፡፡ እነርሱም ይህን የመጀመሪያ ሐዲስ ኪዳን ፕትመት ያዘጋጁባቸውን በእጅ የተጻፉ የግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት ይዘው ነበር ይባላል፡፡ ይህ ፕትመት በ1753 ዓ.ም. በዋልተን ፖሊግሎት እንደገና ተባዝቷል፡፡[93] በጣም የታወቀው የኢትዮጵያ ሐዲስ ኪዳን በቶማስ ቤል ፕላት (Thomas Bell Platt) በ1830 ለBritish and Foreign Bible Society) ታትሟል፡፡[94]

86 ይህ መረጃ የብሉይ ኪዳን ትርጉሞ ምሁር ፀሎት ፀሎይ ለደፈሩ ሥላሴ ዮሐንስ ፀዶል ምስጋል ጊዜ ተረጋግጧል፡፡
87 " " የሐዲስ ኪዳን ትርጉሞ ምሁር ፀሎት ፀሎን መቃርስ ተረጋግጧል፡፡
88 Voobus A. Early Versions of the New Testament, Stockholm, 1954, 247 ff cf. Ullendorff, 1968, 53.
89 Auurmond R. "Ethiopic Versions" in The Anchor Bible Dictionary, vol.6,p.808.
90 Ibid.: The Catholic Encyclopedia, vol.v,1913, p.570.
91 The Anchor Bible Dictionary, vol. 6, p. 809.
92 E. Ullendorff, 1968, p. 59.
93 Encyclopaedia Biblica, vol. iv, col. 5012. The Anchor Bible Dictionary, vol. 6, p. 809; E. Ullendorff, 1968, p.34.
94 Encyclopaedia Biblica vol. iv, col. 5012. The Anchor Bible Dictionary, vol. 6, p. 809.
95 E. Ullendorff, 1968, p.35.





# ክፍል 8

## የኢትዮጵያ የብራና ቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙባቸው ቦታዎች

በሚያማምሩ ብራናዎች የተጻፉ ቁጥራቸው የበዛ በእጅ የተጻፉ የግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ደብረ ሊባኖስ፣ ደብረ ቢዛን፣ ደብረ ዳሞ፣ ጉንዳጉንዲ፣ ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ በጣና ባሕር ደሴቶች ላይ ባሉና በመሳሰሉት ገዳማት ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መጻሕፍት አብዛኞቹ ያማሩ ምሳሌዎች፣ በጥሩ የሚያበራ ሁኔታና በሚያስደንቅ አጻጻፍ የተጻፉ ናቸው፡፡[95] በሽህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ መጻሕፍት በብዙ የአውሮፓ ብሔራውያን ዩንቨርሲቲዎች አብያተ መጻሕፍት የሚገኙ መሆኑን ሲያስታውሱት አስገራሚ ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት እንዴት አውሮፓ ደረሱ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመንና ከዚያም በፊት ጀምሮ ብዙ ተጓዦች፣ አሳሾችና ተመራማሪዎች ጐብኚዎችም በተደጋጋሚ በኢትዮጵያና በኤርትራ ተጉዘዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች በገንዘብ የማይተመን ዋጋ ያላቸውን እነዚህ በርካታ መጻሕፍትን አሰባስበው የያዙ ገዳማትንም ጎብኝተዋል፡፡ እነዚህ ሕዝቦች ከገዳማቱ ጥሩ ጥሩ የሆኑ መጻሕፍትን በእጃቸው የሚያስገቡበትን መንገድና ዘዴ ተጠቅመው ወደ አውሮፓ በመውሰድ ሸጠዋቸዋል ወይም ለልዩ ልዩ አብያተ መጻሕፍት ሰጥተዋቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የኢትዮጵያን ገዳማት በዋጋ ከማይተመን ሀብታቸው ሲያራቁት፣ የአውሮፓን አብያተ መጻሕፍት ግን አበልጽጓል፡፡ በጣም ብዙ ቁጥርና ሰፊ አገልግሎት ያላቸው የኢትዮጵያ የብራና ቅዱሳት መጻሕፍት፣ በዊንድሶር ካስትል ቤተ መጻሕፍት፣ በማንቸስተር በጆን ራይላንድ ቤተ መጻሕፍት፣ በበርሊን፣ በሌኒንግራድ ቤተ መጻሕፍት፣ በቪኤና ቤተ መጻሕፍት ወዘተ ይገኛሉ፡፡ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ በማይክሮፊልም የተቀረጹ ስብስቦች በሚንሶታ በኮሌጅቪል በሂል ገዳም ቤተ መጻሕፍት (Hill Monastic Manuscript Library) (HMML) ይገኛሉ፡፡ የገዳሙ ቤተ መጻሕፍት ኃላፊዎች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ የኢትዮጵያ ገዳማት መጻሕፍት ቤተ መጻሕፍት ተብሎ የተሰየመ በአዲስ አበባ አቋቁመው የተራቀቀ የማይክሮ ፊልም መሣሪያ ተከሉ፡፡ በጣም ብዙ መጽሐፍ ቅዱስ ነክ የሆኑና የቅዱሳንን የሕይወት ታሪክና ተጋድሎአቸውን የሚያወሱ መጻሕፍትን በሦስት ኮፒ ፊልም አንስተው አንዳንድ ቅጅ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፣ ለአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲና ለሂል ገዳም ቤተ መጻሕፍት ሰጥተዋል፡፡ ዶክተር ደብልዩ ኤፍ ማኮምበር (W. F. Macomber) እና ዶ/ር ጌታቸው ኃይሌ ስለ የኢትዮጵያ የብራና ቅዱሳት መጻሕፍት አስመስጋኝ ካታሎግ (Catalogue) /የመጻሕፍት ዝርዝር/ አዘጋጅተዋል፡፡[96]

96 Macomber, W. F. 1975 - 78 A Catalogue of Ethiopian Manuscripts, vols. 1 - 3, Collegeville, MN.: Getachew Haile. 1978 - 88. A Catalogue of Ethiopian Manuscripts, vols. 4 - 11, Collegeville, MN.

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 8

## የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡፡

## ክፍል 1

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአንድምታ ትምህርት ቤት ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማብራራት የሚያገለግሉ ሁለት ቃላት አሉ፡፡ እነርሱም ትርጓሜና ፍካሬ ናቸው፡፡ ነገር ግን የትኛው ለነጠላ ትርጓሜ፣ የትኛውም ለአንድምታ ትርጓሜ እንደሚጠቅም ውሳኔ የለም፡፡ ሁሉም በሁሉ ይነገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ የአማርኛው ቅዱስ መጽሐፍ ብዙ ጊዜ ትርጓሜን ሲጠቀም፣ የግእዙ ቅዱስ መጽሐፍ ፍካሬን ይጠቀማል፡፡ ስለዚህም የሚከተሉትን በግእዙና በአማርኛው መመልከት ይቻላል፡፡

| ግእዝ | አማርኛ |
|---|---|
| "... ኀጣእነ ዘይፈክር ለነ<br>" ዝንቱ ውእቱ ሕልምከ<br>ወፍካሬሁ እነግር ቅድመ ነጉሥ፡፡"<br>"ፍካሬ ዘጻድቃን ወዘኃጥኣን | "... የሚተረጉምልን አጣን፡፡" (ዘፍ. 40.8)<br>ሕልምህ ይህ ነው ትርጓሜውንም<br>በንጉሡ ፊት እናገራለሁ" (ዳን.2.36)<br>የጻድቃንና የኃጥአን<br>ትርጓሜ፡፡" (መዝ.1.አርእስት) |

ከዚህም የተነሣ ትርጓሜ በግእዝ አብዛኛውን ጊዜ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ለመመለስ ሲያገለግል ፍካሬ በግእዝ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ለመመለስ ሳይሆን ምሳሌ ቅኔ ሕልምና ሌላም ሕቡእ ለሆነ ነገር ሁሉ ማብራሪያ ነው፡፡

2. የትርጓሜ አስፈላጊነት

ሀ. ኮነጢአት በፊት ብሩህ የነበረው የሰው አእምሮ ኮነጢአት በኋላ ጨልሞአል፣ የእግዚብሔርን መልእክት በቀጥታ ከማስተዋል ተገቷል፡፡ ምሥጢረ ነገረ እግዚብሔርም ተሰውሮበታል፡፡

ለ. ሰዎች በብዙ መንገድ ይለያያሉ፣ ለምሳሌ ፡-
በሀገር፣ የአንዱ ሀገር ትምህርትና ባህል ልማድና ቋንቋ ወዘተ ከሌላው ሀገር ይለያል፡፡ በትምህርት፣ አንዱ ምሁር፣ ሌላው ኢምሁር ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ትርጓሜና ማብራራት ያስፈልጋሉ፡፡

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ የተነገረበትና የተጻፈበት ዘመን እጅግ ሩቅ ነው፣ ቦታው፣ ባህሉ፣ ሥርዐቱ፣ ኑሮው፣ ልማዱ፣ ቋንቋው፣ ዛሬ ካለንበት ዘመን የተለየ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተነገረላቸው ሕብረተ ሰብኦች በአስተሳሰብና በዕውቀት ከእግዚአብሔርም ጋር ከነበራቸው ቅርብነት አኳያ ከዛሬው ሕብረተሰብእ የተለዩ ነበሩ፡፡ ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ለዛሬው ኅብረተሰብእ አስፈላጊ ነው፡፡

መ.በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ የንግግር ዐይነቶች እንደ ሕልም፣ እንቆቅልሽ፣ ምሳሌያዊና ቅኔያዊ ስላሉት ሕልም፣ ራእይና ትንቢት ጥበብም ስላሉት ትርጓሜ አስፈላጊ ነው፡፡ (ዘፍ.40፣ መሳ.14፡18፤ መሳ.9.8-15፡፡ ዮሐ.10:9-18፡፡ ሉቃ.13.32 ዮሐ 2.19-21፡፡ 21፡18-19፡፡ ሮሜ.12፣20፡፡)



3. አንድምታ

አንድ የተባለው ቃል ሁለት ባዕዳን ፊደላት ምና ታ ታክለውበት አንድምታ የተሰኘውን ቃል ሊያስገኝ ችሏል፡፡ አንድምታ ለቅዱሳት መጻሕፍት ፍካሬ ወይም አብርሆት የተሰጠ ሥረይ /ተርም/ ነው፡፡ አንድ ማለት ሁለተኛ የሌለው ነጠላ ብቻ ሲሆን አንድም ከመስተጻምር ጋር በመሆኑ ሌላ አንድ የተጨመረበት ማለት ነው፡፡ በዚህ ዐይነት አንድምታ ማለት ሌላ ተጨማሪ ያለው አንድ ማለት ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከቅዱሳት መጻሕፍት አንዱን ቃል ወይም አረፍተ ነገር ከአንድ ጊዜ በላይ ሁለተኛ ሦስተኛ በማለት ፈንታ "አንድም" እያሉ እስከ ዐሥራ ሦስት ጊዜ (ራእ.6:2) ስለሚተረጉሙ "አንድምታ" ለትርጓሜ መጻሕፍት ስያሜ ሆኗል፡፡
አንድምታ የአማርኛ ቃል እንደመሆኑ መጠን ቅዱሳት መጻሕፍት በአማርኛ መብራራት ከጀመሩበት አንሥቶ ተግባራዊ ለመሆን በቅቷል፡፡ ከአማርኛ በፊት ግን መጻሕፍት በግእዝ ተነብበው በግእዝ ይተረጐሙ ስለነበረ እንደ አንድም የሚያገለግሉ ሌሎች የግእዝ ቃላት ነበሩ፡፡ እነዚህም ኋላ በቦታቸው ይታያሉ፡፡

አንድም በቃል ብቻ ይነገራል እንጂ በአንድምታ ትርጓሜ መጽሐፍ ውስጥ አይጻፈም፡፡ እርሱን የሚተካው "ቦ" የተባለው የግእዝ ቃል ይጻፋል፡፡ "ቦ" ደግሞ ከተጻፈ በኋላ አንድም ተብሎ ይነበባል እንጂ ቦ ተብሎ አይነበብም፡፡ ቦ ማለትም ሌላ ተጨማሪ ትርጓሜ አለ ማለት ሲሆን ከግእዝ የፍካሬ መንገድ የተወሰደ ነው፡፡ ይህንም በቦታው እናያለን፡፡

ዛሬ ግን በታተሙት የአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት ውስጥ በ "ቦ" ፈንታ አንድም የተባለው ቃል ራሱ በሙሉ ተጽፎ ይገኛል፡፡ (ቅዳ.ማር.ምዕ.1:7፡፡ ሮሜ 1:1፡፡)

4. የአንድምታ ትርጓሜ በቅዱሳት መጻሕፍት

ለአንድምታ ትርጓሜ ቅዱስ መጽሐፋዊ መሠረት አለው፡፡ ምክንያቱም በቅዱስ መጽሐፍ ለአንድ ቃል ወይም ዘርዕ ከአንድ በላይ ትርጓሜ እንዳለው ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉት ምሳሌያውያት ትርጓሜዎችን እንመልከት፡፡

ሀ. "እናንተ ከሕግ በታች ልትኖሩ የምትወዱ ሕጉን አትሰሙምን? እስኪ ንገሩኝ አንዱ ከባርያዩቱ፣ አንዱም ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደነበሩት ተጽፎአልና፡፡ ይህም ነገር ምሳሌ ነው፡፡ እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለት ኪዳኖች ናቸው፡፡ (ገላ.4:21-24) እዚህ ላይ ሁለቱ ሴቶች ሣራና አጋር በታሪክ የታወቁ ሰዎች መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለቱ ኪዳኖች ብሉይና ሐዲስ ተተርጉመዋል፡፡

ለ. እንደዚሁም በ1ቆሮ 10:1-5 "ሁሉም ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዐለት ጠጡ፡፡ ያም ዐለት ክርስቶስ ነበረ፡፡" ተብሎ ዐለቱ ከዐለትነቱ ሳይወጣ በክርስቶስ ተተርጉሞአል፡፡ ከዚህም ጋር በ1 ቆሮ ፡10:11 ላይ እስራኤል ከግብፅ በወጡ ጊዜ የደረሰባቸው ሁሉ " እንደ ምሳሌ ሆነባቸው" መባሉ ምሳሌያዊ አንድምታ ነው፡፡

ሐ. "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰረው" ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፎአል፡፡ (ዘዳግ.25:4) ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲተረጉም "እግዚአብሔር ስለ በሬ ይገደዋልን? ይህን ማለቱ ስለ እኛ አይደለምን? ብሏል፡፡ (1ቆሮ 9:9-12) ከዚህ በሬ በአንድምታ እንደ ወንጌል መልእክተኛ ሆኖ ተተርጉሞአል፡፡ ጌታችንም ለአንድምታ ትርጓሜ መሠረት የሚሆን ምሳሌን አሳይቶአል፡፡ ይኸውም መንግሥተ ሰማያትን በአንድ ምዕራፍ ውስጥ በተለያዩ ስድስት ነገሮች መስሎ ማስተማሩ ነው፡፡ (ማቴ.13:1-47) ተጨማሪ ማስረጃዎች ዮሐ.3:14-15፡፡ ራእ.1:8

www.ethiopianorthodox.org

5. የአንድምታ ትርጓሜ ዐይነት

እንደ ኢትዮጵያ ትርጓሜ ቤት ባህል የአንድምታ ትርጓሜ ዐይነት ፈደላዊና መሥጢራዊ(መንፈሳዊ) ነው፡፡ ማንኛውም የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ ወይም ቃል ከፈደላዊ ትርጓሜ በስተኋላ የተሰወረ ምሥጢራዊ ወይም መንፈሳዊ ትርጓሜ አለው፡፡ ይህም የተሰወረ ምሥጢር መገለጥ እንዳለበት በማመን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ማንኛውንም ንባብ በአንድምታ ለመተርጐም ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

"መጽሐፍ ይቀትል፣ ወመንፈስ የሐዩ፤ ንባብ (ፊደል) ይገድላል፣ ትርጓሜ ግን ያድናል፡፡" (2ቆሮ.3፡6) እንደተባለው የቅዱሳት መጻሕፍት ዘርዕ በአንድምታ መሥጢራዊ ትርጓሜ ካልተተረጐመ አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ ዘርዕ ሊኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- "እግዚአብሔር በክንፎቹ አዘላቸው፤ (ዘዳግ.33፡11) "ቀኝ ዐይንህ ብታስትህ አውጣት፣ ቀኝ እጅህ ወይም ቀኝ እግርህ ብታስትህ ቁርጠህ ጣላት፡፡" (ማቴ.5፡29-30) ወዘተ.ይመስሉ፡፡ እነዚህ ዘሮች በምሥጢራዊ ትርጓሜ ካልተተረጐሙ በቀር ፊደላዊ ትርጓሜያቸው ስሜት አይኖረውም፡፡

የአስክንድርያና አንጾኪያ ት/ቤቶች በእነዚህ ሁለት የትርጓሜ ዐይነቶች የታወቁ ናቸው፡፡ የአንጾኪያ ት/ቤት ፊደላዊ ወይም የቃል በቃል ትርጓሜን እንጂ መንፈሳዊ የአንድምታ ትርጓሜን አይደግፍም፡፡ የአስክንድርያ ት/ቤት ደግሞ በአንድምታ ትርጓሜ ላይ እንጂ በፊደላዊ ወይም በቃል በቃል ትርጓሜ ላይ አያተኩርም፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ት/ቤት ግን የሁለቱም ት/ቤቶች ትርጓሜ ስለሚነገርበት የማንኛውም ተቃዋሚ ሳይሆን ሁለቱንም አጣምሮ የያዘ ነው፡፡

# ክፍል 2

## የአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት፣

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአንድምታ ትምህርት ቤት ትውፊት በአንድምታ የሚተረጐሙ የብሉይና የሐዲስ ኪዳናት ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ሳይሆኑ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ የሆኑ ሌሎች መጻሕፍትም በአንድምታ ይተረጐማሉ፡፡ እነዚህም መጻሕፍት ዐለም አቀፍ የጋራ ቅዱሳን አበው የደረሷቸው ናቸው፡፡ በመሠረቱ በቅዱሳን አበው የተደረሱት መጻሕፍት ራሳቸው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተዘጋጁ ትርጓሜ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና የቅዱስ ቄርሎስ መጻሕፍት ቀጥተኛ ትርጓሜዎች መሆናቸው በይዘታቸው ይታወቃል፡፡ ሆኖም የቤተ ክርስቲያናችን የአማርኛ አንድምታ መምህራን በእነዚህና በሌሎችም መጻሕፍት ላይ ተጨማሪ አንድምታ በማከል እንዲብራሩ አድርገዋል፡፡ ነገር ግን የትምህርት መጻሕፍት እንጂ ከቀኖናውያን መጻሕፍት ጋር የሚቈጠሩ አይደለም፡፡ ባጠቃላይ የአንድምታ ትርጓሜ የሚካሄድባቸው መጻሕፍት ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

1.ብሉይ ኪዳን

- ስምንቱ ብሔረ ኤሮት (ከዘፍጥረት እስከ ሩት)
- አርባዕቱ ብሔረ ነገሥት (ከቀዳማዊ ሳሙኤል እስከ መጽሐፈ ነገሥት ፃልስ)
- ሁለት ዜና መዋዕል (ሕፁፃን)
- ሦስቱ መጻሕፍተ ዕዝራ
- መጽሐፈ ነህምያ
- ኩፋሌና ሄኖክ
- ጦቢት፣ ዮዲትና አስቴር
- ሦስቱ መጻሕፍተ መቃብያን፣
  - ሀ. መቃቢስ ዘሞአብ/
  - ለ. መቃቢስ ዘብንያም
  - ሐ. ዘአልአዛር
- መጽሐፈ ኢዮብ
- መዝሙረ ዳዊት
- አምስቱ መጻሕፍተ ሰሎሞን
- መጽሐፈ ሲራክ



- መጽሐፈ ኢሳይያስ
- መጽሐፈ ኤርምያስ
- መጽሐፈ ሕዝቅኤል
- መጽሐፈ ዳንኤል
- ዐሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት፡፡

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ላይ የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ የተዘጋጀ ሲሆን የመዝሙረ ዳዊት አንድምታ ትርጓሜ በ1950 ዓ.ም. በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ተዘጋጅቶ ታትሞአል፡፡ የአምስቱ መጻሕፍተ ሰሎሞንና የመጽሐፈ ሲራክ አንድምታ ትርጓሜ በአለቃ ኀይለ ሥላሴ፣ በብላታ መርሥዔ ኀዘን ወ/ቂርቆስና በመልአከ ገነት ክፍሌ ለሕትመት ተዘጋጅቶ በ1917 ዓ.ም. ታትሞአል፡፡ የመጽሐፈ ኢሳይያስና የመጽሐፈ ኤርምያስ አንድምታ ትርጓሜ በትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት በ1997 ዓ.ም.፣ የመጽሐፈ ዳንኤልና የዐሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት አንድምታ ትርጓሜ በ1998 ዓ.ም. እንደዚሁም የጦቢት፣ የዮዲት፣ የአስቴርና የኢዮብ መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ በ1998 ዓ.ም. በትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት ታትሞአል፡፡ እንደዚሁም የአምስቱ ብሔረ ኦሪት አንድምታ ትርጓሜ በትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት በ1999 ዓ.ም. ታትሞአል፡፡ የመጽሐፈ ሕዝቅኤል አንድምታ ትርጓሜም በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ተዘጋጅቶ በ1916 ዓ.ም. ታትሞአል፡፡ ዜና አይሁድ በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ግን እስከአሁን የተዘጋጀ የአንድምታ ትርጓሜ የለም፡፡ መምህራንም በጉባኤ አያሄዱትም፤

2.ሐዲስ ኪዳን

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከማቴዎስ እስከ ራእይ ያሉት 27 መጻሕፍት ሲሆኑ በሁሉም ላይ የአንድምታ ትርጓሜ ተዘጋጅቶአል፡፡ ሁሉም ታትመዋል፡፡

የአራቱ ወንጌላት አንድምታ ትርጓሜ በመምህር ወልደ ሩፋኤልና በአለቃ ገብረ መድኅን ተዘጋጅቶ በ1916 ዓ.ም. አዲስ አበባ ታትሞአል፡፡ ከግብረ ሐዋርያት እስከ ራእየ ዮሐንስ ያሉት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ "ሠለስቱ መጻሕፍት ሐዲሳት" በሚል ርእስ በሊቀ ሊቃውንት መሓሪ ትርፌ ተዘጋጅተው በ1951 ዓ.ም. ታትመዋል፡፡ ሦስቱ መጻሕፍት ፡-

1. ግብረ ሐዋርያት፣
2. ሰብዓቱ መልእክታት፣
3. ራእየ ዮሐንስ ናቸው፡፡ እንደዚሁም የቅዱስ ጳውሎስ የዐሥራ አራቱ መልእክታት አንድምታ ትርጓሜ በሊቀ ሊቃውንት መሓሪ ትርፌ ተዘጋጅቶ በ1948 ዓ.ም. አ/አ ታትሞአል፡፡

ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ ሁሉ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት አንድምታ ለመምህራንና ደቀመዛሙርት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ምክንያቱም፡-

1. የትርጓሜ ዘዴዎች አሉት፣
2. የአያንዳንዱን መልእክት ምክንያተ ተጽሕፎት ይዞአል፡፡
3. በመልእክታቱ ውስጥ ከሌላ መጽሐፍ የተጠቀሱ ጥቅሶች ሁሉ ፡-
   ሀ/ ከምን መጽሐፍ
   ለ/ ለምን
   ሐ/ የት እንደተጠቀሱ ያስረዳል፡፡

ከስምንቱ መጻሕፍት ሥርዐት በመጽሐፈ ኪዳን በክፍል አንድ ላይ ብቻ የአንድምታ ትርጓሜ የተዘጋጀ ሲሆን በሌሎቹ ላይ የተዘጋጀ የአንድምታ ትርጓሜ እስካሁን የለም፡፡

3. መጻሕፍተ መነኮሳት

መጻሕፍተ መነኮሳት የሚባሉት፡-

www.ethiopianorthodox.org

1. ማር ይስሐቅ ዘነነዌ፣
2. ፊልክስዮስ ዘመቡጋና
3. አረጋዊ መንፈሳዊ /ዮሐንስ ሳባ/ የጻፉአቸው ገዳማዊ ሕይወትን የሚናገሩ መጻሕፍት ናቸው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት በተለያዩ ዘመናት ወደ ግእዝ ተመልሰዋል፡፡

- መጽሐፈ ፊልክስዮስ በአጼ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግሥት (1327-1355) በካልእ ሰላማ ብርሃነ አዜብ (ብፁዕ አቡነ ሚካኤል) ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፡፡

- የማር ይስሐቅ መጽሐፍ በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት (1530-1549 ዓ.ም.) በሰሊክ ዘደብረ ሊባኖስ መነኮስ ዘተድባበ ማርያም ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፡፡ በእነዚህ ሦስት መጻሕፍት ላይ የአንድምታ ትርጓሜ ተሠርቶአል፡፡ ትርጓሜው ቃል በቃል ሲነገር ከቁየ በኋላ መጽሐፈ ማር ይስሐቅን አለቃ ደስታ እሸቴ መጽሐፈ ፊልክስዮስን አባ ገብረ ክርስቶስ፣ መጽሐፈ አረጋዊ መንፈሳዊን መምህር ደስታ (በኋላ ብፁዕ አቡነ አብርሃም) ለኅትመት በሚያበቃ ሁኔታ አዘጋጅተው በ1920 ዓ.ም. ታትሞአል፡፡

## 4. መጻሕፍተ ሊቃውንት

1. መጽሐፈ ቂርሎስ፣

ይህ መጽሐፍ የእስክንድርያውን የቅዱስ ቂርሎስንና በዘመኑ የነበሩትን የሊቃውንት ድርሳናት ይዞአል፡፡ እነዚህም ፡-

ሀ/ እስትንቡእ፣
ለ/ ጸላድዮስ /ተሰእሎ ወተሰጥዎ/
ሐ/ ተረፈ ቂርሎስ /የራሱ የቂርሎስና የሌሎች ሊቃውንት ስብሰባ/ ናቸው፡፡ መጽሐፉ በስድስተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፡፡ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ደጋግሞ ከቅዱስ ቂርሎስ መጽሐፍ በመጥቀስ ዘምሮአል፡፡ በቅዱስ ቂርሎስ መጽሐፍ ላይ የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ተዘጋጅቶአል፡፡ ነገር ግን እስካሁን አልታተመም፡፡

## 2. ሃይማኖተ አበው

ሃይማኖተ አበው ከስድሳ በላይ የሆኑ የጋራ አባቶች ሊቃውንት ትምህርተ ሃይማኖት፣ መልእክትና ምስክርነት ያለበት መጽሐፍ ነው፡፡ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ አባት ግን ከእነዚህ መካከል የለም፡፡ መጽሐፉ በአጼ እስክንድር ዘመነ መንግሥት (1470-1486 ዓ.ም.) ዐሥራተ ጽዮን በተባለ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፡፡ በዚሁ መጽሐፍ ላይ የተዘጋጀው የአንድምታ ትርጓሜ እስካሁን አልታተመም፡፡ ሊቃውንቱ በእጅ እየጻፉ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፍ ችሏል፡፡

## 3. ዮሐንስ አፈወርቅ

በኢትዮጵያ የሚታወቀው የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መጽሐፍ ድርሳንና ተግሣጽ ነው፡፡ ድርሳኑ ለዕብራውያን በተጻፈው መልእክት ላይ የተናገረው ስብከት ሲሆን ተግሣጹ በየጊዜው ያስተላለፈው ምክርና እዝናት ነው፡፡ እጨጌ ፅንባቆም በአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት (1500-1530 ዓ.ም.) ከዐረብኛ ወደ ግእዝ መልሶታል፡፡ መጽሐፉ ራሱ ትርጓሜ ሲሆን እንደገና የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ተደርጎበታል፡፡ በ1924 ዓ.ም. ለኅትመት በሚያበቃ ሁኔታ በሊቁ ገብረ ክርስቶስ ተዘጋጅቶ ታትሞአል፡፡

## 4. መጽሐፈ ቅዳሴ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እስከ 20 የሚደርሱ መጻሕፍተ ቅ[illegible]

www.ethiopianorthodox.org



የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ያላቸው ዐሥራ አራቱ መጻሕፍት ብቻ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ሥርዐተ ቅዳሴው፣ ቅዳሴ ሐዋርያትና ቅዳሴ እግዚእ በስድስተኛው ምእት ዓመት ከሱርስት ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል፡፡ ሌሎች ቅዳሴያት ግን በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተደርሰው በመጻሕፍቱ አርእስት በተጠሩት ቅዱሳን አበው የተሰየሙ መሆናቸውን ብዙዎች ሊቃውንት ያምኑበታል፡፡ ሌሎች ደግሞ በመጻሕፍቱ አርእስት ላይ በተጠቀሱት ቅዱሳን አበው እንደተደረሱና በየጊዜው እንደተተረጉሙ ያምናሉ፡፡ የዐሥራ አራቱ መጻሕፍተ ቅዳሴ የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ከኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት፣ ከሊጦንና መስተብቍዕ ጋር ለሕትመት እንዲበቃ ሆኖ በመምህር ገሪማ (ብፁዕ አቡነ ሚካኤል) ተዘጋጅቶ በ1918 ዓ.ም. አ.አ ታትሞአል፡፡

## 5. ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ማርያም በቅዱስ ኤፍሬም (306-373) የተደረሰ ሲሆን በቅዱስ ያሬድ (6ኛው ምእት) ወደ ግእዝ ተመልሶአል፡፡ የውዳሴ ማርያም የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ በተለያዩ ሊቃውንት ተዘጋጅቶ በተለያዩ ጊዜያት ታትሞአል፡፡ (1963 ዓ.ም)

## 6. ፍትሐ ነገሥት

"ፍትሐ ነገሥት" የተባለው መጽሐፍ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1426-1460ዓ.ም.) በዲያቆን ጴጥሮስ ወልደ ዐብደል ሰይድ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፡፡ የፍትሐ ነገሥት አንድምታ ትርጓሜ በአለቃ ገብረ መድኅን ለኅትመት በሚያበቃ መልኩ ተዘጋጅቶአል፡፡ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በ1958 ዓ.ም. የእጅ ጽሑፉን በፎቶ ኮፒ አባዝቶታል፡፡ በዚህም ምክንያት ለብዙዎች መምህራንና ደቀመዛሙርት ተዳርሶአል፡፡

## 7. አቡሻሕር

"አቡሻሕር" የሐሳበ ዘመን መጽሐፍ ነው፡፡ የሐሳበ ዘመን ትምህርትን ካዘጋጁ ሊቃውንት አንዱ ዮሐንስ አቡሻሕር ግብፃዊ ሲሆን መጽሐፉ በአዘጋጁ ስም ተሰይሞአል፡፡ የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የሐሳበ ዘመን አቋጣጠር ከዚህ ሊቅ ሐሳበ ዘመን ትምህርት ጋር ስለሚስማማ መጽሐፉ በሀገራችን ዝነኛ ነው፤ መምህራን ያስተምሩታል፤ ደቀመዛሙርትም ይማሩታል፡፡

የመጽሐፉ ምድብ ከሊቃውንት መጻሕፍት ጋር ነው፡፡ ሰሊክ ዘደብረ ሊባኖስ መነኮስ ዘተድባበ ማርያም በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት (1530-1549 ዓ.ም.) ከዐረብኛ ወደ ግእዝ መልሶታል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ላይ ለኅትመት እንዲበቃ ሆኖ የተሠራ የአንድምታ ትርጓሜ የለም፡፡

## 8. መቅድመ አርባዕቱ ወንጌላት ቅዱሳት

አሞንዮስ እስክንድርያዊ (175-242) አውሳብዮስ ቂሣርያዊ (260-340) እንደጻፉት የሚነገር የአርባዕቱ ወንጌላት መቅድም አለ፡፡ መቅድሙ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ መቼና በማን እንደተተረጉመ በውስጡ ባይገለጥም ካልእ ሰላማ መተርጉም እንደተረጉሙት በትውፊት ይነገራል፡፡

አሞንዮስና አውሳብዮስ ስለ አራቱ ወንጌላት ጸሓፊዎች ስምና አጭር ታሪክ፣ ስለ ወንጌላቱ አከፋፈል፣ ዓላማ፣ ይዘትና ጥቅም ኀብረትና መለያየት፣ የኀይለ ቃላት መጠንና አርእስት፣ በየዘመናቸው ጸፈዋል፡፡ የሁለቱ ሊቃውንት ሥራ በአንድነት ተገናዝቦ አንድ መጽሐፍ የሆነ ይመስላል፡፡ መጽሐፉ ወደ ግእዝ ከተተረጉመ በኋላ በብሔራውያን ሊቃውንት የአንድምታ ትርጓሜ ተዘጋጅቶለታል፡፡ ይህም ከወንጌላቱ በፊት ተጽፎ "መቅድመ ወንጌል" ሆኖ ይነበባል፣ ይተረጉማልም፡፡ ከቅዱስ መጽሐፍ ውጭ ቢሆንም ለሌላ ማስረጃ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ (ኤፍ.1) ነገር ግን ከአንድምታ ትርጓሜ ጋር እንጂ ከመደበኛው የወንጌል ዘር ጋር ሊጻፍና ሊጠረዝ አይገባም፡፡

# ክፍል 4

## የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ ምንጮች

የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ አራት ምንጮች እንዳሉት ከይዘቱ ይታወቃል፡፡ የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ "እንዲል" ይላል እንጂ ማን እንዳለ ብዙ ጊዜ አይገልጥም፡፡ የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ ግን " ይቤ እገሌ፣ እገሌ ተርጉመ ከመዝ ወከመዝ፤ እገሌ እንዲህ አለ፤ እገሌ እንዲህና እንዲህ ብሎ ተረጉመ፡፡ ስለሚል ምንጩ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት ከግእዙ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ አራት ዐይነት ምንጮች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህም ፡-

1. የቅብጥ፣ /ግብፅ/ ቤተ ክርስቲያን
2. የሶርያ ቤተ ክርስቲያን
3. የግሪክ ቤተ ክርስቲያን
4. የግእዝ ናቸው፡፡

የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት መጻሕፍት ላይ ያዘጋጁት የአንድምታ ትርጓሜ ወደ ግእዝ ተተርጉሞ በምንጭነት ይጠቀሳል፡፡ የሊቃውንቱም ስም ይወሳል፡፡ የአንዳንዶችም ሊቃውንት ትርጓሜ ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ የአማርኛ አንድምታ ሆኖአል፡፡ ለምሳሌ የቅዱሳን ቄርሎስና ዮሐንስ አፈወርቅ መጻሕፍት ቀድሞ የግእዝ በግእዝ አንድምታ ነበሩ፡፡ ኋላ ግን መሠረታዊው ዘር በሊቁ ከተተረጉመ በኋላ የሊቁ ትርጓሜ እንደገና በብሔራውያን ሊቃውንት በአማርኛ ተብራርቶአል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት አራቱ የግእዝ አንድምታ ምንጮች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 1. የሶርያና የቅብጥ ምንጭ

ሀ/ ትርጓሜ ኦሪት ዘዮሐንስ አፈወርቅ

ይህ ትርጓሜ በስምንቱ ብሔረ ኦሪት ላይ የተሠራ ነው፡፡ ግብፃዊው ኢብን ጠይብ ከግሪክ ወደ ዐረብኛ መልሶታል፤ ስለዚህም የኢብን ጠይብ ሥራ ወይም የኢብን ጠይብ ትርጓሜ በመባል ይታወቃል፡፡ ከኢብን ጠይብ ሥራ ላይም ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፡፡

ለ/ ትርጓሜ ዳንኤልና ትርጓሜ ደቂቅ ነቢያት፣

ይህ ትርጓሜ በአንኮሊጦስ ዘሮምና በጎርጎርዮስ ዘእንዚንያዙ የተዘጋጀ ነው፡፡ ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፡፡ በውስጡም የተጠቀሱትን ሊቃውንት በስም ያዘክራል፡፡

ሐ/ ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ ከዐረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጉመ፣

ይህ ትርጓሜ ወንጌል ሰፊ ሐተታና አብርሆት ያለው ነው፡፡ በአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ የሚነገረው ገለጣና ሐተታ ከዚህ ትርጓሜ ወንጌል የተወሰደ ነው፡፡

ይህ ትርጓሜ ወንጌል፡- የሳዊሮስ ዘአንጾኪያን፣ የቄርሎስ ዘእስክንድርያን፣ የአውሳብዮስን፣ የዮሐንስ አፈወርቅን፣ የቲቶስ ዘባስጥራን፣ የኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስን፣ የአቡሊድስ ዘሮምን /ቅድመ ተፈልጦ/ የጎርጎርዮስ ዘእንዚንያዙን፣ የቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያን፣ የባስልዮስ ዘቂሣርያን፣ የአትናቴዎስንና የዲድሞስ ዘዕውሩን፣ የቴዎፍሎስ ዘእስክንድርያን፣ የጢሞቴዎስ ዘአልቦ ጥሪትን፣ የኢሳይያስ ባሕታዊንና የስምዖን ዘዓምድን ትርጓሜ "ይቤ እገሌ" እገሌ እንዲህ አለ እያለ ያካተተና የያዘ ነው፡፡

መ/ የኢብን ጠይብ ትርጓሜ ወንጌላት አርባዕቱ፡፡

ይህ ትርጓሜ የአቡ ፈረጅ ትርጓሜ በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ ሰው ላይ ብዙ ክርክር ተነሥቶ ነበር፡፡ የክርክሩም ምክንያት በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ከቍጥር 18-25 ባለው የግእዝ በግእዝ ትርጓሜው ነው ፡፡



ሠ/ በግብረ ሕማማት ውስጥ የሚገኝ የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ፣

በግብረ ሕማማት ውስጥ ከኦሪትና ነቢያት ንባብ በኋላ የተነበበው በግእዝ ተብራርቶ ይገኛል፡፡ የትርጓሜው አካሄድም "ይተረጉማል" በሚለው መንገድ ነው፡፡ ትርጓሜው በብሔራውያን ሊቃውንት ከተዘጋጀው የኦሪትና የነቢያት ትርጓሜና ከላይ ከተጠቀሱት አራት ምንጮች የተወሰደ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በግብረ ሕማማት ውስጥ የሚገኘው የግእዝ ትርጓሜ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በ1996 ዓ.ም. ግብረ ሕማማቱ ሲታተም ታትሞአል፡፡

ረ/ ትርጓሜ መልእክታተ ጳውሎስ

በዐሥራ አራቱ የጳውሎስ መልእክታት ላይ በግእዝ የተዘጋጀው ትርጓሜ የቅርያቆስን፣ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን፣ የቅዱሳን አትናቴዎስንና የኤፍሬምን ትርጓሜ በብዛት ያካተተ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የዕብራውያን ትርጓሜ እንደገና በአማርኛ አንድምታ ተዘጋጅቶ በ1923 ዓ.ም. ታትሞአል፡፡ የመጀመሪያው ሊቅ በተረጉመው ላይ ሐተታ፣ ታሪክ፣ ምሳሌያትና የተለያዩ ማብራሪያ ተጨምረውበታል፡፡ ማስረጃ ጥቅሶችም ተጠቅሰውበታል፡፡ (ዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን 1 ገጽ 1-3፡፡ ድርሳን 3 ገጽ 48-49 ወዘይመስሉ፡፡)

### 2. የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ምንጭ /የዮናውያን ምንጭ/

ከመለያየት በፊት የነበሩ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አበው ሊቃውንት ከተረጉሙት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ የተመለሰ የግእዝ በግእዝ አንድምታ ትርጓሜ በቤተ ክርስቲያናችን ይገኛል፡፡ በአንድ ትርጓሜ ወንጌላት አርባዕቱ መጨረሻ ላይ በተጻፈ አስማተ መምህራኑ ትርጓሜ ላይ የሚከተለው ይነበባል፡፡

"እሉ እሙንቱ መምህራን ዮናናውያን እምቅድመ ተፈልጦ ያዕርፍ እግዚአብሔር ነፍሳቲሆሙ.... እግዚአብሔር ነፍሶቻቸውን ያሳርፍና ከመለያየት በፊት የነበሩ ዮናናውያን መምህራን እኒህ ናቸው፡፡" ይልና ትርጓሜያቸው ወደ ግእዝ የተወሰደላቸውን ዮናናውያን መምህራን ይዘረዝራል፡፡ (ትርጓሜ ወንጌል አርባዕቱ) ትርጓሜያቸው ወደ ግእዝ ተተርጉሞ ከሚጠቀሱ ሊቃውንት አበው ጥቂቶቹን እንመልከት፡፡

ሀ/ ትርጓሜ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣

ይህ አባት በመሓልየ መሓልይ ዘሰሎሞን ላይ የተረጉመው የአንድምታ ትርጓሜ ወደ ግእዝ ተተርጉሞአል፤፤ ተርጓሚውም ካልእ ሰላማ ብርሃነ አዜብ ነው፡፡ ይህ ትርጓሜ ለአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ መነሻ ምንጭ ሲሆን የመሓልየ መሓልይ መሠረታዊ ዘርን ጠንቅቆ የያዘ ነው፡፡ በአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ የሚገኙ በቅዱስ ያሬድ የዜማ ትምህርት የሌሉ፣ በልማድ ዕብራይስጥ የሚባሉ ነገር ግን ያይደሉ ዘሮች በግእዙ የአንድምታ ትርጓሜ ውስጥ አይገኙምና፡፡ (መሓል.2:16-17፡፡ 3.10፡፡ 4:13፡፡ 5:1፡፡ 6:1፡፡ 6:11፡፡ ወዘይመስሉ፡፡)

ለ/ ትርጓሜ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ

ቅዱስ ባስልዮስ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በበርካታዎች ላይ ትርጓሜ ሠርቶአል፡፡ በተለይ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ላይ ስለ ስድስቱ ዕለታት ፍጥረታት ያዘጋጀው ትርጓሜ ታዋቂና ዝነኛ ከመሆኑ የተነሣ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይጠቀሙበታል፡፡ በእኛም ቤተ ክርስቲያን ወደ ግእዝ ተተርጉሞ በአንዳንድ ገዳማት ይገኛል፡፡ ስሙም የባስልዮስ አክሊማሮስ በመባል ይታወቃል፡፡ በስድስቱ ዕለታት ስለ ተፈጠረው ሥነ ፍጥረት የሚናገር መጽሐፍ ማለት ነው፡፡ እንደዚሁም በምሳሌያት ስሎሞን ላይ ያዘጋጀው ትርጓሜ በመጽሐፈ ሃይማኖተ አበው ከመጠቀሱ ጋር ለብቻው በግእዝ ተጽፎ ይገኛል፡፡ (ሃይ .አበው ምዕ.32 ክፍል 3 ቍጥር 11-18)

www.ethiopianorthodox.org

### ሐ/ ትርጓሜ ዮሐንስ አፈወርቅ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዕብራውያን መልእክት ላይ ከጻፈው ትርጓሜ ሌላ በሌሎች የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይም ትርጓሜ ጽፎአል፡፡ ለምሳሌ፡- በማቴዎስ ወንጌል፣ በሮሜና በአንደኛ ቆሮንቶስ፣ በኤፌሶንና በፊልጵስዩስ፣ በቈላስይስ፣ በተሰሎንቄ፣ በጢሞቴዎስና በፊልሞና መልእክታት ላይ እንደ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ ዐይነት ሳይሆን እንደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ ዐይነት አዘጋጅቶአል፡፡ የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜው "ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ" በተሰኘ የግእዝ በግእዝ አንድምታ ውስጥ ከሌሎች አባቶች ትርጓሜ ጋር ይገኛል፡፡ (ትርጓሜ ወንጌላት ቅዱሳት ዘእምቃላተ ብዙኃን መምህራን ግእዝ በግእዝ) ከላይ በተጠቀሱት መልእክታት ላይ የጻፈው ትርጓሜም "ትርጓሜ ጳውሎስ ግእዝ በግእዝ ውስጥ በየምዕራፉ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ እንደ ዕብራውያን መልእክት ትርጓሜው ግን በሙሉ ወደ ግእዝ አልተተረጐመም፡፡

## 3. የግእዝ ትርጓሜ

የግእዝ ትርጓሜ ማለት በውጭ ሊቃውንት በውጭ ቋንቋ ሳይደረስ መሠረቱ ግእዝ የሆነና በብሔራውያን ሊቃውንት የተዘጋጀ ማለት ነው፡፡

### ሀ/ የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ትርጓሜ

ቀደም ያሉት ብሔራውያን ሊቃውንት በራሳቸው ተመርሖ ልቡና በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የግእዝ በግእዝ አንድምታ ትርጓሜዎችን አዘጋጅተው ሲያስተምሩ ኖረዋል፡፡ ከእነዚህም አንዱ የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ትርጓሜና የአንዳንድ አስቸጋሪ ቃላት ማብራሪያ ነው፡፡ ይህንም የመሰለ በመጽሐፈ ሕዝቅኤል ላይ የተሠራ ትርጓሜ አለ፡፡ (መምህረ ኦሪት ግእዝ በግእዝ)

### ለ/ ሁለተኛ የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ትርጓሜ፡፡

ይህ ትርጓሜ ኦሪት በግእዝ ተነብቦ በግእዝ የተብራራ ሲሆን ከዐረብኛ እንደ ተተረጐመ በዳሩ የተጻፈ ማስታወሻ አለ፡፡ መጽሐፉ ባጠቃላይ የተዘጋጀው ግን በ1603 ዓ.ም. በቁስ አጼ ምህርካ ድንግል እንደሆነ ተገልጦአል፡፡ ትርጓሜው ከመጀመሪያው የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ትርጓሜ በይዘቱና በምሥጢሩ ይሰፋል፡፡ በአንዳንድ የዚህ መጽሐፍ ቅጅ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ቤተ አይሁድ ተጠቅመውበታል፡፡ ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ሥጋዌን እንዲሁም ነገረ ማርያምን የሚተረጐመውን ክፍል ፍቀውት ይገኛል፡፡

### ሐ/ ትርጓሜ ሕዝቅኤል

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ካዘጋጁት ትርጓሜ ሕዝቅኤል ሌላ በብሔራውያን ሊቃውንት ግእዝ በግእዝ የተዘጋጀ ትርጓሜ ሕዝቅኤል አለ፡፡ የዚህ ትርጓሜ ማብራሪያ በጣም ዐጭር በመሆኑ "መጽሐፈ ሕዝቅኤል አልተተረጐመም" የሚሉ ብዙዎች ነበሩ፡፡ በኋላ ግን አለቃ ኪዳነ ወልድ ግእዝ በግእዝ የተተረጐመውን መሠረት አድርገው፣ ዘርዉንም ከሰብዓ ሊቃናቱ አውጥተው በዕብራይስጡ ሰውጠው የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ጽፈዋል፡፡ ግእዝ በግእዝ የሆነው የትርጓሜ ሕዝቅኤልም አካሄድ "ዘይቤ በሚለው መንገድ የተሰናዳ ነው፡፡

ለምሳሌ፡-
ሕዝ.ምዕ.47፡6-12
"ወሰደኒ ኀበ ድንጋገ ፈለግ" ዘይቤ ጥምቀት፣ ወበድንጋገ ፈለግ ብዙኀ ዕፀው..." ዘይቤ መጻሕፍት፡፡ "ወይፈውሶ ለማይ" ዘይቤ ጥምቀት ያጠፍኦ ለኀጢአት፡፡
"ወይመልዑ ዓሣት ውስቴቱ" ዘይቤ መሃይምናን፡፡
"ወይመጽኡ መስግራን" ዘይቤ ሐዋርያት፡፡



ትርጓሜው፡-
- ወደ ወንዙ ዳር ወሰደኝ ማለት ጥምቀት ነው፡፡
- በወንዙ ዳርም ብዙ እንጨቶች አሉ ማለት መጻሕፍት ናቸው፡፡
- ውሃውንም ይፈውሰው ነበር ማለት ጥምቀት ኀጢአትን ያስተሰርያል ማለት ነው፡፡
- በውስጡም ዓሣዎች ሞልተው ነበር ሲል ምእመናን ናቸው፡፡
- ዓሣ አጥማጆች ይመጡ ነበር ማለት ሐዋርያት ናቸው፡፡

በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ የአስቸጋሪ ቃላት መፍቻ አለው፡፡ (ትርጓሜ ሕዝቅኤል ግእዝ በግእዝ)

### መ/ ትርጓሜ ራእይ ዘዮሐንስ

ይህ ትርጓሜ በብሔራውያን ሊቃውንት ግእዝ በግእዝ የተዘጋጀ ሲሆን ከአማርኛው የአንድምታ ትርጓሜ ይልቅ በጣም የተብራራ ነው፡፡ መጽሐፉ በ57 ምቅዋም ተከፍሏል፤ ምቅዋም በዚህ መጽሐፍ እንደ ምዕራፍ ወይም እንደ ክፍል የሚያገለግል ነው፡፡

በዚህ ትርጓሜ መግቢያ ላይ ቅዱስ ሰላማ ከሣቱ በርሃን በግብፅ ጳጳስ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰ ጊዜ የራእየ ዮሐንስ መጽሐፍን ይዞ እንደመጣና ወደ ግእዝ እንደተረጐመ ተገልጦአል፡፡ መጽሐፉ ቦ አለ ይቤሉ (እንዲህ የሚሉም አሉ) ከማለት በቀር ራእየ ዮሐንስን ከተረጐሙ ቀደምት ሊቃውንት አይጠቅስም፡፡ ነገር ግን ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶችን ይጠቅሳል፡፡ ተርጓሚው ኢትዮጵያዊ ሊቅ እንደመሆኑ ቋንቋንና ፊደልን በሚመለከት ቦታ ላይ ግእዝን ያነሣሣል፡፡ /ትርጓሜ ራእይ 1፡8፡፡ 9፡11/ የአተረጓጐሙ መንገድም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ራእ.1፡ 13 እና 16
13. "ርኢኩ ሰብዐ መኃትወ ዘወርቅ፤ ወማእከለ መኃትው ይነብር ወልደ እጓለእመሕያው...
16. "ወውስተ እዴሁ ዘየማን ሰብዓቱ ከዋክብት..."
"ናሁ ተርጉመ ሎቱ መንፈስ ቅዱስ በዓለ ዝንቱ መጽሐፍ ከመ ሰብዐቱ መኃትው እሙንቱ አብያተ ክርስቲያናት፣ ወከዋክብትኒ እሙንቱ ኤጲስ ቆጶሳት እለ ሥሉጣን ዲቤሆሙ፡፡

" ወቦ እለ ይቤሉ መኳንንተ ይእቲ ሀገር፡፡ ወነቢሮቱኒ ለወልደ ዕጓለ እምሕያው ማእከለ ሰብዓቱ መኃትው ያጤይቅ ከመ ውእቱ ርእሰ ቤተ ክርስቲያን፡፡ ወእኂዞቱኒ ከዋክብተ በየማኑ በእንተ ሢመተ እዴሆሙ ለካህናት ውእቱ፣ ወያሌቡ ከመ እሙንቱ እጉዛን ታሕተ ሥልጣኑ፡፡ በከመ ይቤ ነቢይ እስመ ውስተ እዴሁ ኵሉ አጽናፈ ምድር፡፡

"ወቦ እለ ይቤሉ፡- ርእየ ጥዩቀ በአርኣያ ሰብዐቱ ከዋክብት ዐበይት ዘኮኑ እሙንቱ የአምርዎሙ ቅድመ እስመ ጽሑፍን ጥቀ ለዘከመዝ ግብር፡፡ ወእሉ እሙንቱ ከዋክብት ቀዳሚ አጣርድ ካልእ ዙሓል፣ ሣልስ መሸተሪ ራብዕ መረሕ፣ ኀምስ ዝሑራ፣ ሳድስ ፀሐይ ወሳብዕ ወርኃ፡፡ ወበእንተ ክብረ ሢመቶሙ ለእሉ ኤጲስ ቆጶሳት መሰሎሙ በዝንቱ አርኣያ፡፡"

ትርጓሜው፡-
13. "ሰባት የወርቅ መቅረዞችን አየሁ፣ በመቅረዞችም መካከል የሰው ልጅ ተቀምጦአል፡፡...
16. በቀኝ እጁም ሰባቱ ከዋክብት አሉ፡፡"

እነሆ የዚህ መጽሐፍ ባለቤት መንፈስ ቅዱስ ሰባቱ መቅረዞች አብያተ ክርስቲያናት እንደሆኑ ኮከቦችም በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸው ኤጲስ ቆጶሳት እንደሆኑ ተረጐመለት፡፡

"የዚያች ሀገር መኳንንት ናቸው ያሉም አሉ፡፡ የሰው ልጅም በመቅረዞች ላይ መቀመጡ የቤተ ክርስቲያን

www.ethiopianorthodox.org

ራስ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ኮከቦችንም በቀኝ እጁ መያዙ ስለ ካህናት ሹመት ነው፡፡ ነቢይ "የምድር ዳርቻ ሁሉ በእጁ ውስጥ ነው" እንዳለ ከሥልጣኑ በታች እንደሆኑም ያስረዳል፡፡ "እንዲህ የሚሉም አሉ፡- እነርሱ /ኤጲስ ቆጶሳቱ/ ያውቋቸው በነበሩ በሰባቱ ታላላቅ ከዋክብት ምሳሌ በእርግጥ አይቶአል፡፡ ሰዎቹ ለእንደዚህ ያለ ሥራ ይተጉ ነበርና፡፡ ከዋክብቱም እነዚህ ናቸው፡፡ አንደኛው አጣርድ፣ ሁለተኛው ዙሓል፣ ሦስተኛው መሸተራ፣ አራተኛው መረሕ፣ አምስተኛውም ዝሑራ፣ ስድስተኛው ፀሓይ፣ ሰባተኛውም ጨረቃ ነው፡፡ ስለ ኤጲስ ቆጶሳቱ የሥልጣን ክብር በዚህ ምሳሌ መስላቸው፡፡"(ትርጓሜ ራእይ ዘዮሐንስ ግእዝ በግእዝ)

### ሠ/ ብሂለ መተርጉም

በመጽሐፈ ግብረ ሕማማት ውስጥ ከኦሪትና ከነቢያት፣ ከመጽሐፈ ኢዮብና ከመጻሕፍተ ሰሎሞን እንዲሁም ከመጽሐፈ ሲራክ ንባብ በኋላ በተነበበው የግእዝ ዘርዕ ላይ የግእዝ በግእዝ አንድምታ ይገኛል፡፡ ይህ ትርጓሜ "ይቤ መተርጉም ተርጓሚው እንዲህ አለ" ተብሎ ስለ ተጻፈ "ብሂለ መተርጉም " እየተባለ ይጠራል፡፡ የተርጓሚው አባባል ማለት ነው፡፡ የዚህ ትርጓሜ አዘጋጁ ካልእ ሰላማ መተርጉመ መጻሕፍት ሲሆኑ አካሄዱ ከሌላው የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ ይለያል፡፡ ምሥጢራዊ ብሂሉንና ትንቢታዊ ፍካሬውን ከመግለጥ በቀር ሌላ ታሪካዊ ሐተታ የለውም፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንጂ ከሌሎች ሊቃውንትም ትርጓሜ አይጠቅስም፡፡ ቦ ዘይቤ በተባለው የትርጓሜ ግእዝ መንገድም ብዙ ጊዜ አይጠቀምም፡፡ ይሁን እንጂ መጨረሻውን መንፈሳዊ ምሥጢረ ትርጓሜ ይገልጣል፡፡ በመሆኑም ለአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ (ግብረ ሕማማት ገጽ 204-207 በ1942 ዓ.ም. የታተመ)

የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከእነዚህ ከተጠቀሱት የግእዝ አንድምታዎች ሌላ በርካታ የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ ሠርተዋል፡፡ በተውሶ ብቻ አልኖሩም፡፡ እንደዛሬ የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ እንደጸሎት አንድ ወጥ ከመሆኑ በፊት እያንዳንዱ ሊቅ በራሱ ተመርሖ ልቡናና አለብዎተ መንፈስ ቅዱስ የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ ያዘጋጅ ነበር እንጂ ሌላው ያሸከማቸውን ተሸክመው የኖሩ አልነበሩም፡፡ ከፍተኛ የጎሠሣና የፈጠራ ችሎታም ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ዛሬ እንደ አላዋቂ የሚያስቈጥር መሆኑን ስለ አላጤኑት ሥራቸውን ሁሉ በሌላ ስም ሰይመውታል፡፡

# ክፍል 5

## የአንድምታ ትርጓሜ ዕድገትና መተላለፍ ትውፊታዊ ታሪክ

የአንድምታ ትርጓሜ ከተመሠረተባቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጥቂቶቹ (አምስቱ ብሔረ ኦሪት) ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ0ሥረኛው ምእት ዓመት በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያና በተከታዩ ዘመን እንደሆነ በትውፊት ይነገራል፡፡ በእነዚህም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ላይ እንደዛሬው የአንድምታ ትርጓሜ ባይሆንም አጫጭር መግለጫና ማብራሪያ ይሰጥ እንደነበር አሁንም ትውፊታዊ ታሪክ ያስረዳል፡፡ መግለጫውና ማብራሪያውም ይሰጥ የነበረው ያንጊዜ ወደ ኢትዮጵያ በመጡት የአይሁድ መምህራን እንደሆነ ይነገራል፡፡

ቀጥሎም ከ350 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ስድስተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ አብዛኛው የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከዚያም በኋላ በየጊዜው የአበው ሊቃውንት መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል፡፡ ወደ ግእዝም ተተርጉመዋል፡፡ በቅዱስ ፍሬምናጦስ ዘመን ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ በተተረጉሙ ጊዜ ገብረ መስቀልና ተክለ ሃይማኖት የተባሉ ብሔራውያን ሊቃውንት በትርጉሙ ሥራ ተሳታፊዎች እንደነበሩ ገድለ አብርሀ ወአጽብሐ ያስረዳል፡፡ ከዚህ ዘመን ጀምሮ ከመለያየት በፊት የነበሩ የጋራ ቅዱሳን አባቶች ያዘጋጁአቸው የአንድምታ ትርጓሜዎች ወደ ግእዝ መተርጉም ጀምረዋል፡፡

በትውፊት እንደሚነገረው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ቀዳማዊ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያብራሩ ያስተምሩ ከነበሩት መምህራን መካከል ስመ ጥሩ ሊቃ

www.ethiopianorthodox.org



መምህራን በገድላትና ድርሳናት ተመዝግበዋል፡፡ እነርሱም አዛርያስ፣ ሳዶቅ፣ ሌዊ፣ አሮን፣ አልኣዛር፣ ሕዝበ ራእይ፣ ይዋሒ፣ አኪን፣ ስምዖን፣ እንበረም ናቸው፡፡ ይህ የስም ዝርዝር ከኢትዮጵያ ሊቃነ ካህናት የስም ዝርዝር ጋር ተመሳሳይነት አለው ምናልባት መምህራኑና ሊቃነ ካህናት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመምህርነት የሚያገለግሉት ሊቃነ ካህናቱ፣ በሊቀ ካህናትነትም የሚያገለግሉ መምህራኑ ናቸውና፡፡ እነዚህ መምህራን ኦሪቱን እየተረጐሙ ወደ ንጉሡ ይመጣ ለነበረው ሕዝብ ሊያስተምሩ ኖረዋል፡፡ በእንበረም ጊዜ ቅዱስ ፍሬምናጦስ መጣና እንበረምን ክርስቲያን ካህን አድርጎ ሾመው፡፡ ቀጥለው የተጠቀሱት የሐዲስ ኪዳን መምህራን ናቸው፡፡

እነዚህም፡-

ይታምር፣ አብዩድ፣ ጌዴዎን፣ ያሬድ፣ ሕዝበ ባርክ፣ ተክለ ቀዐት፣ ዐጽቀ ሌዊ፣ ሐርበ ኀሸ፣ ይግናህ መስቀል፣ ይቅና ዳዊት፣ ዘልዑል፣ ሚናስ፣ አባ ይድላ፣ ሕይወት ብነ በጽዮን፣ በኩረ ጽዮን፣ ሕዝበ ቀድስ፣ ብርሃነ መስቀል፣ ሕይወት ብነ፣ ሴት፣ ወረደ ምሕረት፣ ዘካርያስ፣ ዘርዐ ዮሐንስ፣ ተክለ ሃይማኖት ናቸው፡፡ ይህ የስም ዝርዝር ከሊቃነ ካህናቱ የስም ዝርዝር ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ምክንያታዊ ሐተታው ከላይ እንደተገለጠው ነው፡፡ በመቀጠልም እስከ ዕጨጌ ቃለ ዐዋዲ ድረስ ያሉትን መምህራን የስም ዝርዝር እናያለን፡፡ እነዚህም ፡-

ፊልጶስ፣ ሕዝቅያስ፣ ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስ፣ ዮሐንስ ከማ፣ እንድርያስ፣ መርሐ ክርስቶስ፣ ጴጥሮስ፣ እንባቆም፣ ያዕቆብ፣ ማትያስ፣ ዮሐንስ፣ ዘትረ ወንጌል፣ አብርሃም፣ ዘወንጌል፣ ዘሚካኤል፣ በትረ ጊዮርጊስ፣ ዘክርስቶስ የማነ አብ፣ ሕርያቆስ፣ ቃለ ዐዋዲ ናቸው፡፡ ይህም ዝርዝር ከደብረ ሊባኖስ ዕጨጌዎች ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ከዚህ በኋላ የመምህራኑ ስም ከአበው ምኔት መስመር ይለያል፡፡ እስከ ዕጨጌ ቃለ ዐዋዲ ድረስ የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ ግእዝ በግእዝ ነበረ፡፡ ዘመኑ (1674-1698) ምንም እንኳ የአማርኛ ቋንቋ የሕዝብ ቋንቋ የሆነበት ሕዝቡ ግእዝን ከመስማት የራቀበት ዘመን ቢሆንም መምህራኑ በቁየው ትውፊት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍትን በግእዝ እያብራሩ ያስተምሩ ነበር፡፡

# ክፍል 6

## የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ በአማርኛ፤

አማርኛ ከግእዝ ወጥቶ የሕዝብ ቋንቋ ወይም መነጋገሪያ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ሕዝቡ ግእዝን ከመስማት እየራቀ መጣ፡፡ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ከሣቴ ብርሃን ሰላማና ተከታዮቻቸው አበው እንዲሁም ብሔራውያን ሊቃውንት በዘመናቸው ለክርስቲያኑ ሕዝብ ያዘጋጁት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብሂላዊ ትርጓሜ እንደነበራቸው በግእዝ አንድምታ ክፍል ተገልጦአል፡፡ ይህም በግእዝ ተነብቦ በግእዝ የተብራራ ነበር፡፡ መምህራኑ ከእነ አቡነ ሰላማ ተያይዞ የመጣውን፣ በግእዝ የተተረጐመውን ጥንታዊ ትርጓሜ ራሳቸው እንደተማሩት በቤተ ክርስቲያን ለሕዝቡ ያስሙ ነበር፡፡ ነገር ግን ሕዝቡ አማርኛ መነጋገሪያ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ከግእዝ መራቁን ከአማርኛ በቀር ግእዝን ለመስማት መቸገሩን አልተገነዘቡም ነበር፡፡

ችግሩ በቀዳማዊ (ጻድቁ) ዮሐንስና (1659-1674) በአድያም ሰገድ ኢያሱ (1674-1698) አዝማነ መንግሥት ጐልቶ ስለታወቀ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ተጀመረ፤ አጼ አድያም ሰገድ ኢያሱ በ1674 ዓ.ም. በነገሡ ጊዜ በዐዋቆች ሊቃውንትና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የሚነገረውን ትምህርት ሳይሰማ በሚመለሰው ሕዝብ መካከል ስፊ መራራቅ በመኖሩ ከፍተኛ ትኩረት ተደረገበት፤ ለዚህም መፍትሔ እንዲሆን አፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ የተገኙበት ጉባኤ ተደርጎ አንድ ውሳኔ ተወሰነ፡፡ ውሳኔውም፡-

- በአንድምታ ትርጓሜ ሊነገሩና ሊመሰጠሩ የሚገባቸው መጻሕፍት በአራት መንበር (ጉባኤ) እንዲመደቡ፣
- የጉባኤ መጻሕፍት ሁሉ ንባባቸው በግእዝ ሆኖ ትርጓሜያቸው (ፍካርያቸው) በአማርኛ ንዲሆንና ለሕዝብ እንዲገለጡ፣

- ሊቃውንቱ የጉባኤ መጻሕፍቱን በግእዝ ቢያውቋቸውም አንድ ሊቅ ለአንድ ጉባኤ፣ ሌላውም ሊቅ ለሌላው ጉባኤ እንዲመደብ፣
- አራት ሊቃውንት የአራቱ ጉባኤያት (መናብርት) ባለቤቶች ሆነው ፍካሬያቸውን እንዲያዘጋጁ" የሚል ነበር፡፡

በዚህም መሠረት በአራት መንበር (ጉባኤ) የተመደቡት መጻሕፍት፡-

1. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት
2. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት
3. መጻሕፍተ ሊቃውንት (ምስለ አቡሻሕር)
4. መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው፡፡

የእነዚህንም የጉባኤ መጻሕፍት ብሂላዊ የአንድምታ ፍካሬ በአማርኛ ቋንቋ እንዲያዘጋጁ ሊቃነ መናብርትና መፈክራን ሆነው የተመረጡ አራት ሊቃውንት ነበሩ፡፡ እነርሱም፡-

1. ዕጨጌ ቃለ ዐዋዲ ለብሉይ ኪዳን መጻሕፍት
2. መምህር ሠርዌ ክርስቶስ ለሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት
3. መምህር ክፍለ ዮሐንስ ለመጻሕፍተ ሊቃውንት
4. ዐቃቤ ሰዓት አብራንዮስ ለመጽሐፈ መነኮሳት (ማር ይስሐቅ አንቀጽ 5 ገጽ 104 ዐምድ 1) ነበሩ፡፡ መሪዎችን መናገር ነው እንጂ ሌሎችም መምህራን ከተጠቀሱት ሊቃውንት ጋር በየወንበሩ ተመድበው በአማርኛ አንድምታ ፍካሬ ሥራ ተሳትፈዋል፡፡

አዬ አድያም ሰገድ ኢያሱም መምህራኑና ደቀመዛሙርቱ በሚያስተምሩበትና በሚማሩበት ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን መፍቅድ ሁሉ ያደርጉላቸው ነበር፡፡ መሳፍንቱና መኳንንቱም በሚያስተዳድሩት ሀገር የንጉሡን አርአያ በመከተል የጉባኤ መምህራንና ደቀመዛሙርት በአዲስ መልክ የተዘጋጀውን የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ እንዲያስተምሩ አደረጉ፡፡ ስለዚህም በጉንደር፣ በአክሱም፣ በጎንጃም፣ በሸዋ፣ በላስታና በቤተ አምሐራ (አማራ ሳይንት) በሚገኙ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት መምህራን ስላስተማሩ የአማርኛ አንድምታ ፍካሬ ሊስፋፋ ችሏል፡፡

የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ አጀማመር ከላይ ለመግለጥ እንደተሞከረው ሕዝቡ በማያስተውለው ግእዝ ይነገር የነበረው የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታ ትምህርት ለሕዝቡ ግልጥ እንዲሆን ለማድረግ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ ችግር ያለበት ሆኖ ይታያል፡፡ ምክንያቱም አራቱ ሊቃውንትና ተባባሪዎቻቸው መምህራን ካዘጋጁት የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ በቀር ማንም ሊቅ ሌላ ትርጓሜ አዘጋጅቶ እንዳያስተምር ሆኖአል፡፡

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የመጽሐፍ መምህር ወይም ሊቅ የሚባለው ሁሉ መምህሩ ቃል በቃል የነገሩትን ትርጓሜ በቃል ማጥናትና ያን መልሶ ለሌላው በቃል ማስጠናት እንጂ በራሱ ተመርሖ ልቡና የሚጨምረው የለም፡፡ ምሥጢር አመሥጥሮ፣ ማስረጃ ጨምሮ፣ የረዘመውን አሳጥሮ፣ ያጠረውን ዘርዝሮና ተንትኖ እንዲያስተምር አይፈቀድለትም፡፡ ይህም ሁኔታ የደቀ መዛሙርትን ስፍሐ አእምሮ ያጠባል፡፡

ነገር ግን የቅዱሳት መጻሕፍት በግእዝ ተነብበው በግእዝ ይተረጐሙ በነበረበት ጊዜ እያንዳንዱ ሊቅ የቀደመውን የግእዝ አንድምታ መሠረት በማድረግ በራሱ ግንዛቤ ሌላ የግእዝ ፍካሬ ያዘጋጅ እንደነበረ በአንድ በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ላይ በርካታ የተለያየ የግእዝ አንድምታ ትርጓሜ በየመምህራኑ እንጂ ይገኛል፡፡

የአንድምታ ትርጓሜ አንድ ጊዜ በአንድ ዐይነት መንገድ መወሰኑ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደ ቅዱስ ያሬድና ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘሰግላ በሊቅነታቸው አብነት ሆነው የሚጠቀሱ ሊቃውንት በብዛት እንዳይኖሩን አድርጓል፡፡ ከዚህም ጋር የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ (በተለይ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ) ዐጭርና በሰፊው ያልተብራራ ሆኖ ይታያል፡፡





በመሆኑም እንደ ቀደሙት አራት ሊቃነ መናብርት ያሉ ሊቃውንት ተለይመው በቁየው ፍካሬ ላይ አብርሆት ሊያክሉበት ያስፈልጋል፡፡

### በአራቱ ጉባኤያት የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ መምህራን ሐረግ

| የብ.ኪዳን መም. | የሐ.ኪ.መም. | የመ.ሊ.መም. | የመ.መነ.መም |
|---|---|---|---|
| ዕጨጌ ቃለ ዐዋዲ | ሠርዌ ክርስቶስ | ክፍለ ዮሐንስ | ዐቃቤ ሰዓት አብ ራንዮስ |
| አባ ስቡሐት ለአብ | ጸጌ ድንግል | ዕጨጌ ሄኖክ | መንፈቆ ወ/ተ/ሃይማኖት |
| መ.ኢስድሮስ | አባ ያዕቆብ | መ/ኢስድሮስ | መ/መሳ |
| መ.ዮሐውደ.ዮስ | በትረ ክርስቶስ | ዐቃቤ ሰዓት | ከብቴመ/ኢስድሮስ |
| መ.ገወሰን | አሊቃ ጓንጉል | ዚታኑስ ሣህሉ | ዮሐውደ.ዮስ |
| መ.ገተ/ሃይማኖት | መ.ኢስድሮስ | አሊቃ ውሂብ | የሩስ |
| አቶ አደራህ | ሥላ ክርስቶስ | መዘመር ካሣ | አቶ ተ/ሃይማኖት |
| አራት ዐይን ሻሹ | ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ | ..... | አቶቪር ሳሜህ |
| መ.ዝቢረ ኤልያስ | ወልደ አብ | ..... | መ/ሀሲብ |
| መ.ሰው አገኘሁ | ወልደ ሚካኤል | መ/አንግዳ ዘድንጂ | መ/ጽዝስ ወልድ |
| መ.ፈ.ሊታዎስ | አሊቃ ጐሩይ | አሊቃ ተከሩ ዘድንጐጫ | መ/ደስታ (ስብሃ አብርሃም) |
| ዶ/ር አየለ ዓለሙ | ዶ/ር አየለ ዓለሙ | ዶ/ር አየለ ዓለሙ | መ/ርጐሩይ ዘአሊያስ |
| መ/ከበት ገ/ሥላሴ ወወቀ | መ/ከበት ገ/ሥላሴ ዐወቀ | መ/ከበት ገ/ሥላሴ ዐወቀ | ዶ/ር አየለ ዓለሙ |
| | | | መ/ከበት ገ/ሥላሴ ዐወቀ |

ይህ በአራቱ ጉባኤያት በእያንዳንዱ መስመር የወረደ ሐረገ ትውልድ ነው፡፡ በተለይ የፍትሐ ነገሥትና የመጻሕፍተ መነኮሳት መምህራን የትምህርት ሐረገ ትውልድ በየመጽሐፉ መቅድም ስለተጻፈ ከዚያ መረዳት ይቻላል፡፡

# ክፍል 7

## የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ጥንተ ዘመን

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ የተጀመረው በ17ኛው ምእት ዓመት መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም ጋር የውስጥ ማስረጃዎች የታሪኩን እውነታ ያረጋግጣሉ፡፡ በአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ የሚነገረው ቋንቋ፣ በስም የተጠቀሱ የነገሥታት ታሪክ፣ የኢትዮጵያ መልክአ ምድርና በስም የተጠቀሱ መምህራን የአንድምታውን ጥንተ ዘመን አካባቢ በማመልከት ረገድ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

### ሀ/ ቋንቋ

በአንድምታ ትርጓሜ የሚገኘው የቃላትና የአረፍተ ነገር፣ የስምና (የባለቤት) የግሥ ባጠቃላይ የአገባብ ወይም የሰዋስው አጠቃቀም ከዛሬው አማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም የተለየ ሆኖ ይታያል፡፡ የአንድምታ ትርጓሜ መምህራኑ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተሰበሰቡ እንደመሆናቸው የእየአካባቢያቸው የአነጋገር ዘይቤ በትርጓሜው ውስጥ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የብሉይ ኪዳን የአንድምታ መምህራን በብዛት በጎጃምና በጎንደር መምህራን ይነገር ስለነበር፣ ጥንታዊው የጎጃምና የጎንደር የአነጋገር ስልት በብሉይ ኪዳን አንድምታ ውስጥ ጎልቶ ይገኛል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተለው ተጠቅሶአል፡፡



www.ethiopianorthodox.org

1. "... ዛሬስ አያ የያዕቆብ ልጆች ጠገቡና የጋለሞታዋ ቤት ወዴት ነው ; እያሉ ይዞራሉ ሆነ ይበሉን ;..." (ማቴ.1፡3፡፡)
2. "ያይወልድሽን አባት ያዕቆብን አቡነ ማለትሽ ሐሰትሽ፡፡" (ዮሐ.4፡18)
3. "... ከአባታችን ከአብርሃም አንተ ትበልጣለህን; እርስ እንኳ የሞተ..." (ዮሐ.8፡52)
4. "... እኛታ ዕውራን;" (ዮሐ.9፡51)
5. "... ተአምራትስ ይህታ..." (የሐዋ.6፡8)
6. "ቃለ እግዚአብሔር ሳልየከስ እሞታለሁ; ብለህ መሥዋዕት ትሠዋለህ፡፡" (የዳዊት ትርጓሜ መግቢያ)
7. "... ግንባሩን እንደመቱት ውሻ አይግባኙን ወጥቶ ሄዶአል፡፡" (ቅዱ.ባስ.ገጽ 351)
8. "... የራስ ዐምዶ የእኅትዎ ልጅ፣ የልጅ ልጅዎም ቢሉ መባአ ጽዮን (ዐሥራተ ጽዮን) ሃይማኖተ አበውን ከዐረብ ወደ ግእዝ መልሶታል፡፡ "የራስ ዐምዶ የእኅታቸው ልጅ" በማለት ፈንታ በሌሉበት በቅርብ እንዳሉ ተደርጎ ተነግሮአል፡፡

ከአንድ እስከ ስምንት የተጠቀሱት የአንድምታ ትርጓሜ የአማርኛ አነጋገር ባሁኑ ጊዜ በገጠርም ሆነ በከተማ በጥቅም ላይ እንዳሉ አይታይም፡፡ ነገር ግን በአንድምታ ት/ቤት የቀደሙ መምህራን እንዳስቀመጧቸው ይገኛሉ፡፡ ዛሬም መምህራኑ ያስተምሩአቸዋል፣ ደቀመዛሙርቱም ይማሯቸዋል፡፡ የአማርኛ አንድምታ ይህ ዐይነት ንግግር በነበረበት ዘመን መዘጋጀቱን መረዳት ይቻላል፡፡

## ለ/ ነገሥታት

በአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ ነገሥታት በብዙ ቦታ ተጠቅሰዋል፡፡ ይኸውም በምሳሌነትና በዘመናቸው ስለተፈጸመው ድርጊት ነው፡፡ ከተጠቀሱት ነገሥታት መካከል ብዙዎቹ ከ1553ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ ያሉት ሲሆኑ ከቀደሙት ነገሥታትም በአንጻርና በምሳሌ የተጠቀሱ አሉ፡፡ ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አብርሀና አጽብሐ (የሮሜ መልእክት) መግቢያ ታሪክ ገጽ11
- ይኩኖ አምላክ (ዮሐንስ አ.ወ.ድ.364 ገጽ ዐምድ 2፡፡)
- አጼ ዘድንግል፣ ርጉም ተክለ ሃይማኖት፣ አጼ ዮስጦስ፣ አጼ ቴዎፍሎስ፡፡ (ዮሐ አ.ወ.ተ 110-111 ዓምድ 1) በእነዚህ ነገሥታት በተለይ በአራቱ ነገሥታት ዘመን የአማርኛ አንድምታ ሥራ ተሠርቶ እንደነበረ ይታያል፡፡ አብርሀ አጽብሐና ይኩኖ አምላክ ግን እንደ ማስረጃ ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡

## ሐ/ የኢትዮጵያ ታሪክ

የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ በርካታ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ ያመለክታል፡፡ ታሪካቸው በአንድምታ ከተጠቀሰላቸው ሰዎች አንዳንዶች በአንድምታ ትርጓሜ ሥራ ጊዜና በኋላ የነበሩ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም የአማርኛ አንድምታ በጽሑፍ መቅረብ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ሊቃውንቱ በየጊዜው በትርጓሜያቸው ላይ ማስረጃ ይጨምሩ ነበር፡፡ የሚከተሉት ለአብነት ተጠቅሰዋል፡፡

- ቆብ አስጥል ኅይሌ፣ ጥቁር ከብቱ (ዳን.3፡4፡፡ ፍ.ነገ. 581፡፡ ቅዳሴ ገጽ 62፡፡) እነዚህ ሰዎች ሳይሸሙ የተሸሙ በዕውቀታቸው ለሚከበሩ ሰዎች ምሳሌ ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡





- ዐቃቤ ሰዓት አብራንዮስ (ማር.ይስ.ገጽ 104) በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ ቀድሞ ያልነበረ ቃል በመጨመራቸው ምክንያት "ይህን ቃል የጨመሩ ዐቃቤ ሰዓት አብራንዮስ ናቸው" እየተባሉ ይጠቀሳሉ፡፡
- ቂስ አጼ ምህርካ ድንግል (ማቴ.23፡5) በዘፈረ ልብሳቸው ላይ "ኢየሱስ ናዝራዊ" የሚል ጥቅስ ስለጻፉ ተጠቅሰዋል፡፡
- አባ መልክአ ክርስቶስ (ማቴ.25፡28) የተማሩትን ያላስተማሩ ገብር ሀካይ በመሆናቸው ተጠቅሰዋል፡፡
- ራስ ወልደ ልዑል (ዮሐ.አ.ወ.ተ264) የባለ መድኀኒትን ትእዛዝ ባለመቀበላቸው ምክንያት የሕይወት ኅልፈት እንደደረሰባቸው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህና ሌሎችም ሰዎች ሁሉ የነበሩበት ዘመንና የተወለዱበት አካባቢ ባይጠቀስም በጉንደር ዘመነ መንግሥት እንደነበረ ግልጥ ነው፡፡

## መ/ ኢትዮጵያውያን መምህራን

በአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ የአንድምታ መምህራን ሁሉም ባይሆኑ አንዳንዶቹ አልፎ አልፎ ይጠቀሳሉ፡፡ የሚጠቀሱበትም ምክንያት በተለመደው አንድምታ ላይ የሰጡት ተጨማሪ አስተያየት "የመምህር እገሌ ትርጓሜ፣ መምህር እገሌ እንዲህ ብለዋል" እየተባለ ስለሚጠቀስላቸው ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከሚጠቀሱ ክቡራኑ ስም መምህራን መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- መምህር ኤስድሮስ ሉቃ.2፡26፡፡ ዮሐ.5፡8፡፡
- ዐቃቤ ሰዓት ከብቱ ሮሜ.9፡3፡፡
- ዐቃቤ ሰዓት አበሞ ራእይ 1፡3
- መልአከ ገነት ተክለ ሃይማኖት ዮሐ.አ.ወ.ተግ.ገጽ 20፣117-118
- አቶ አደራህ ኢሳ.34፡8 "ዮሐ.አፈ.ወ.ድ 93፣ተግሣጽ 117-118፡፡
- አዛዥ ላሜህ ሃይ አበ እለ እስክንድሮስ
- መምህር ክፍለ ጊዮርጊስ ሕዝ.42፡4፡፡
- ሰንዱን ዮሐ.አ.ወ.ድ 379
- መምህር ዐምደ ሚካኤል ማቴ.24፣36፡፡
- የሣራት ወልደ ማርያም (እነሴ ጎጃም) ፍ.ነገ.263፡፡

የሌሎችም መምህራን የእነ አብሳዲ ትርጓሜ ተጠቅሶአል፡፡ ገላ.4፡15፡፡ የአቦ ባርያ ሃይ አበ ባስልዮስ፡፡ ስዲ ጳውሎስ መዝ.9፡16፡፡ 10.1፡፡ 57፡4፡፡ ቲቶ.1፡12፡፡ አንክሮጦስ ኢሳ.48.16፡፡ ስዲ ጳውሎስ የሚጠቀሰው ለጉብኝት ወደ ሀገራችን የመጣ የውጭ ሀገር ሰው ሲሆን የመዝሙረ ዳዊትን ዘርዕ ከዕብራይስጡ ለማስተካከል ይሞክርና ከመምህራኑ ጋር ይነጋገር ስለነበር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ለቀደሙትና ለኋለኞች መምህራን የአንድምታ ትርጓሜ ዕውቅና ተሰጥቷል፡፡ (ማቴ.25፡31) መምህር ወልደ ሥላሴ የያዕቆብ ዘሥሩግን የሕይወት ታሪክ ከኢየሩሳሌም ወደ ሶርያ ሄደው ማምጣታቸው ሁልጊዜ መተረኩም ለሊቃውንቱ የትርጓሜ ሥራ ዕውቅና መሰጠት እነርሱንም ለቀጣይ ትውልድ ማስተዋወቅ ነው፡፡ ቅዳሴ ዘያዕቆብ ገጽ 433 ዐምድ 1፡፡

## ሠ/ የኢትዮጵያ መልክዐ ምድራዊ ጥቅስ

በአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት ውስጥ ለሚገኙ አንዳንድ ሀገሮች የኢትዮጵያ ቦታዎች የርቀትና የአቀማመጥ፣ የግዛትና የወሰን ምሳሌና ማስረጃ በመሆን ቀርበዋል፡፡ የቦታዎች በአንድምታ ውስጥ መጠቀስ የተጠቀሰለትን ቦታ በምሳሌነት የሚያስረዱ ከመሆናቸውም በላይ ተርጓሚዎች ከተጠቀሱት አካባቢ የመጡ መሆናቸውንም ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ተርጓሚዎቹ የአንድምታ ትርጓሜን በየት እንደሠሩ፣ በየትም እንዳስተማሩ ይገልጣል፡፡ አብዛኛዎቹ ተጠቃሾች ቦታዎች በጎንደርና በጎጃም፣ በስሜንና ትግራይ ውስጥ የሚገኙ ናቸውና፡፡ በአንድምታ ትርጓሜ ውስጥ ከሚጠቀሱ ቦታዎች ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

- ጎንደር ኢሳ.39:2፡፡ ቅዳሴ ገጽ 17፡፡ ስሜን በጌምድር ማቴ.2:12፡፡
- ጎጃም፣ አሬንጎ፣ ይባባ፣ ዐባይ ሕዝ.26:2፡፡ ማቴ.2:12፡፡
- ትግራይ ምሳ.9:12፤ ማቴ.2:12፡፡
- ዝዋ (ጎጃም) አድዋ (ትግራይ) 1ቆሮ.ታሪ.ገጽ 173፡፡
- ወሎ ሃይማኖተ አበው ዘአለ እስክንድሮስ
- ሸዋ ኢዮብ 28.1፡፡ እናርያ ኢዮብ 16:1፡፡
- ይፋት ኤር.14:3፡፡ (በ1996 ዓ.ም. የታተመው የተባለውን ሀገር አይጠቅስም)
- በጎንደር ከተማ የሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ማቴ.1:5፡፡ ወዘይ ...
- ወንዞችና ሐይቆች ዳጋ/ ምጽሌ፣ ዝዋይ መቅድመ ራእይ፣ ሠለስቱ ሐዲሳት ገጽ 393
- አገው ዮሐ.አ.ወ.ተግ.22፡፡ ጋፋት ዮሐ.አ.ወ.ድ 124 ወዘይመስሎ...

# ክፍል 8

## የአማርኛ አንድምታ ይዘቶች

የአማርኛ አንድምታ ይዘቶች ሦስት ናቸው፤ እነዚህም፡-

1. የግእዝ ዘርዕ፣
2. ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጓሜ፣
3. አንድምታዊ ሐተታ ናቸው፡፡

### (ሀ) የአንድምታ ትርጓሜ የተመሠረተበት የግእዝ ዘርዕ፣

የትርጓሜ ሊቃውንት ከእየ መምህሮቻቸው በተረከቡት ትውፊት መሠረት ስለ ግእዝ ዘርዕ የየራሳቸው ልዩ አመለካከት አላቸው፡፡ እነዚህም ፡-

- የተለያዩ ንባባት፣
- የዳር ማብራርያ፣ /ምልክት/
- አማራጭ ርእስ፣
- የዘርዕ እርማት፣
- ምቅዋም /ጉባኤ፣ ምዕራፍ/ ናቸው፡፡

### (ሀ) የተለያዩ ንባባት

የተለያዩ ንባባት የሚባሉት ከመደበኛው ንባብ ወይም ዘርዕ በተጨማሪ የሚጠቀሱ ወይም እንደ ሥርዋጽ የሚገቡ ናቸው፡፡ ይህም "እንዲህ ባለው እንዲህ ይላል እየተባለ የሚነገረው ሐተታ ነው፡፡ ይህንም ለመግለጥ የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡

- "ዮሴፍሰ ፈኃረሃ ለማርያም እስመ ጻድቅ ውእቱ ኢፈቀደ ይክሥታ፡፡" "ፈኃረሃ" ባለው ዐቃቢሃ፣ ተለኣኪሃ ይላል፡፡ (ማቴ.1:19፡፡)
- "አ ዮሴፍ ወልደ ዳዊት ኢትፍራህ ነሢአታ ለማርያም..." "ነሢአታ" ባለው አዕርጎታ አውፅአታ፣ ዐቂቦታ፣ ተልእኮታ ይላል፡፡ (ማቴ.1:20)

-"ወኮሎንኬ ትውልድ እምአብርሃም እስከ ክርስቶስ አርብዓ ወክልኤቱ፡፡" አርብዓ ወክልኤቱ ባለው አርብዓ ወሠለስቱ አርብዓ ወአርባዕቱ፣ አርብዓ ወንምስቱ ይላል፡፡ ይህም ከተባለ በኋላ ቁጥሮች የተጨመሩበት ምክንያት ይብራራል፡፡ (ማቴ.1:18)

ይህ ዐይነቱ ሐተታ አንዳንድ ጊዜ የዘርዑን ትክክለኛነት በሌላ ጊዜ ደግሞ ዘርዑ ትክክል አለመሆኑን ለመግለጥ ይነገራል፡፡

www.ethiopianorthodox.org



### ለ. የዳር ማብራርያ /ምልክት/

ይህ ማብራርያ ወይም ምልክት በግእዙ መጽሐፍ ግልየት፣ እንደዚሁም በመጽሐፉ ሲራክ ላይ የሚደረግ ምልክት ነው፡፡ ምልክቱ በአንጻሩ ያለው ዘርዕ ምን እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል 5.18 በዳሩ ላይ /በሲራኩ/ "ሮ" ወይም "ሎ" ተጽፎ ይገኛል፡፡ "ሮ" ወንጌል በመንግሥተ ሮም መሠራትዋን፣ "ሎ" ደግሞ ወንጌል ሉዓላዊት መሆንዋን ያመለክታል፡፡ ተጨማሪ መረጃ ኢሳ.6:1፤ 14.28 ላይ ያለውን የዳር ምልክት በጉባኤ ቤት መጽሐፍ መመልከት ይቻላል፡፡

### ሐ. አማራጭ ርእስ፣

የአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት የተለያየ አማራጭ ርእስ አላቸው፡፡ ይህም መጻሕፍቱ አንድ ጊዜ በዕብራይስጡ ርእስ፣ በሌላ ጊዜም በግሪኩ ርእስ መጠራታቸውን ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ቆሐልት (ዕብ) ለመጽሐፈ መክብብ የተሰጠ ርእስ ነው፡፡
- አክሳሳፎስ (ግሪ) የመጽሐፈ ጥበብ ርእስ ነው፡፡
-ድርያሚን (ላቲን) የዜና መዋዕል ርእስ ነው፡፡
- ሕፁዋን የዜና መዋዕል ርእስ ነው፡፡

### መ. የዘርዕ እርማት፤

ኢትዮጵያውያን የብሉይና የሐዲስ ሊቃውንት የአንድምታ ትርጓሜ የሚያስተምሩባቸውን መጻሕፍት ዘርዕ ያርማሉ፡፡ እርማቱንም በግልየታቸውና ጠርዛቸው ላይ ያስቀምጣሉ፡፡ ከዚህም ጋር የግእዙ ዘርዕ ከተነበበ በኋላ ወደ አማርኛ ከመተርጐሙና ምሥጢራዊ ትርጓሜው ከመገለጡ በፊት በግእዙ ዘርዕ ላይ ሰዋስዋዊ ስሕተት ነው የሚሉትን "እንዲህ ሲል ነው" ብለው ያርማሉ፡፡ ወይም ትክክል ነው በተባለው ቃል ይተካሉ፡፡ ምሳሌ፡-

- "ፈቀደ እግዚእ ያግእዞ ለአዳም ኀዙነ ወትኩዘ ልብ፡፡" ኀዙነ ልብ፣ ወትኩዘ ልብ ሲል ነው፡፡ (ኤፍ.2:1)
- "ብእሲ ላዕለ ብእሲ ገብሩ ኀሣሮሙ" ብእሲ ወብእሲ ገብሩ ኀሣሮሙ ሲል ነው፡፡ (ሮሜ.1:27) በዚህ ዐይነት ብዙ የዘርዕ እርማት በጉባኤ ቤት መጻሕፍት ሁሉ ጠርዝና ጠርዝ፣ ግልየትና ሐውልት ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡

### ሠ. ምቅዋም

ሊቃውንቱ በጉባኤ ቤት ትርጓሜ የሚያስተምሩባቸው የጥንታውያን መጻሕፍት አከፋፈል በክፍልና በምዕራፍ፣ በጉባኤና በምዕራፍ፣ እንዲሁም በምቅዋም ነው፡፡ ምቅዋም የምዕራፍ ምትክ ነው፡፡ ምዕራፍ ክፍልና ምቅዋም የመጽሐፉ ዘርዕ መክፈያ ሲሆኑ ጉባኤ የትርጓሜ ማረፊያ ነው፡፡ ስለሆነም ጉባኤ የተባለው መክፈያ በመተርጉማን መጻሕፍት ብቻ ነው፡፡ ጉባኤ ከምዕራፍ ጋር የሚገናኝበት ጊዜ አለ፡፡ (ኢሳ.6:1፣ 7:1፤10፣1፤) ምቅዋም በአሁኑ ጊዜ በብዙ መጻሕፍት ላይ አይገኝም፡፡ ሆኖም ለአብነት ያህል በመጽሐፈ ቁርሎስና በዮሐንስ ራእይ የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ላይ ይገኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምዕራፍ እንደ ዘርዕ በአንድምታ ይተረጉማል፡፡ ለምሳሌ፡

"ኦሪት ዘልደት ምዕራፍ ፴ወ፰፤"
"የኦሪት ዘልደት ሠላሳ ስምንተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡፡ ቦ ምዕራፈ አሐዱ ሠላሳ ወስምንቱ ይላል፡፡ ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት የአንደኛው የኦሪት ዘልደት ሠላሳ ስምንተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡፡ (የጸሐፊው የኦሪት አንድምታ ምዕ.38.1)

## 2. ከግእዝ ወደ አማርኛ ትርጓሜ /መተርጉም/

በመጀመሪያ የግእዙ ዘርዕ በግእዝ ይነበባል፡፡ በመቀጠልም ከአማራጭ ትርጓሜ ጋር ወደ አማርኛ በነጠላ [illegible]

ለምሳሌ፡- "ወተወለዶ እግዚእ ኢየሱስ መጽኡ ሰብአ ሰገል፤ ጌታ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ፣ ተወልዶ ሳለ፣ከተወለደ በኋላ ሰብአ ሰገል መጡ፡፡" (ማቴ.2፡1) በአጠቃላይ በአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት ጊዜ የአንድ መጽሐፍ ዘርዕ በሁለት ቋንቋዎች በግእዝና በአማርኛ ይነበባል፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት ከዚህ ለመራቅ ከግእዙ ንባብ በኋላ ቀጥታ ወደ ምሥጢራዊው ትርጓሜ ይሻገራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ኢሳ.1፡9፡፡ 24.1፡፡ ሚክ.4፡6-7 ወዘይ

### 3. አንድምታዊ ሐተታ

ከሦስቱ የአማርኛ አንድምታ ይዘቶች ዋናው ይህ ሦስተኛው ነው፡፡ ይህም ምሥጢርን፣ ሐተታን፣ ታሪክን፣ ጥቅስንና ሌላውን ሁሉ ያካትታል"፡ የአንድምታው ሐተታ ብዙ ጊዜ "ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ፣ ለምን እንዲህ አለ? ቢሉ በሚል የጥያቄ መንገድ ይቀረፃል፡፡ መልስም ይሰጣል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የአንድምታው ሐተታ "ግድፈተ ጸሓፊ ነው" በሚል መልስ ይደመደማል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሰውን መመልከት ይቻላል፡፡ ኤር.52፡23፡፡ ማቴ.1፡8 እና 17፡፡ ነገር ግን ግድፈተ ጸሓፊ ነው ሲባል በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የጻፉ ነቢዩ ኤርምያስና ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ግድፈት አድርገዋል ማለት አይደለም፡፡ ምንአልባት የገልባጩ ግድፈት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ሊቃውንቱ ከገልባጩ የተገደፈ ነው የሚሉትን ቃል ይጽፋታል፣ ያነቡታል፣ ይተረጉሙታልም፡፡

# ክፍል 9

## የአንድምታ ትርጓሜ ት/ቤቶች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ዐይነት የአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት ቤቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህም ፡-

1ኛ/ ላይ ቤት

2ኛ/ ታች ቤት ናቸው፡፡

እነዚህ ሁለት ዐይነት ትምህርት ቤቶች በአንድ ጊዜ የተቋቋሙ ሳይሆኑ በተለያየ ጊዜ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ መጀመሪያው የላይ ቤት አንድምታ በመባል የሚታወቀው ትርጓሜ የሚነገርበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ከጊዜ በኋላ ደግሞ የታች ቤት አንድምታ የተባለው ትርጓሜ የሚሰጥበት ትምህርት ቤት ተቋቁሞአል፡፡ በትውፊት እንደሚነገረው የታች ቤት አንድምታ ትርጓሜ የተዘጋጀው በመምህር አራት ዐይን ኤስድሮስ (1716 ዓ.ም.) መሆኑ ታውቋል፡፡ መምህር ኤስድሮስ ከብዙኃን መምህራን የተማሩ ከመሆናቸውም በላይ በየገዳማቱ በተለይም በጣና ደሴቶች በሚገኙ ገዳማት እየተዘዋወሩ ሦስት መቶ መጻሕፍትን አንብበው (አስነብበው) የቅዱሳት አምላካውያት መጻሕፍትንና የሊቃውንትን መጻሕፍት ትርጓሜ በሚገባ ካደላደሉ በኋላ በጐንደር ልደታ ለማርያም ሰፊ ገባኤ ዘረጉ፡፡ ያንጊዜም ብዙኃን ደቀመዛሙርትን እነ ጌታው ገላውዴዎስንና ሥነ ክርስቶስን፣ ሌሎችንም አስተማሩ፡፡

መምህር ኤስድሮስም የመጻሕፍትን አንድምታ ትርጓሜ ካሻሻሉ በኋላ የተሻሻለውን የትርጓሜ መንገድ እንዲያጠኑ ደቀመዛሙርቶቻቸውን ቢጠይቋቸው ብዙኃኑ ፈቃደኞች ሲሆኑ ጌታ ዮናስ የተባሉት ደቀ መዝሙራቸውና ሌሎች ግን "ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት፡- እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም" ማለት እርስዎ ልዩ ትርጓሜ ከመጨመርዎ በፊት አስተምረውናል በማለት በመምህር ኤስድሮስ ተሻሻለ የተባለውን የአንድምታ ትርጓሜ ለመማር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በመምህር ኤስድሮስ የተሻሻለው አዲሱ ትርጓሜ "የታች ቤት ትርጓሜ" ሲባል ከእርሳቸው በፊት የነበረውና እነ ጌታ ዮናስ በቀጣይነት ያስተማሩት ጥንታዊው ትርጓሜ የላይ ቤት ትርጓሜ እየተባለ መጠራት ጀመረ፡፡ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች አመሠራረት ምክንያትም ይህ ነው፡፡ የታች ቤት አንድምታ ትርጓሜ ትምህርት በብዛት የሚነገረው በጎንደር ነው፡፡ የላይ ቤት አንድምታ ትርጓሜ ደግሞ በጎጃም በስፋት ሲነገር ኖሯል፡፡ አሁንም ይነገራል፡፡ ይሁን እንጂ ዛሬ በጎጃም የሚነገር የላይ ቤት አንድምታ ብቻ ሳይሆን ሁለቱም የላይ ቤትና የታች ቤት አንድምታ ትርጓሜዎች ይነገራሉ፡፡

ከመምህር ኤስድሮስ በኋላ በታች ቤት አንድምታ ትርጓሜ ላይ እንደገና አንዳንድ መሻሻል ተደርጓል፡፡ ይህንም ያደረጉ አለቃ ወልደ አብ የተባሉት ሊቅ ናቸው፡፡ አለቃ ወልደ አብ በትውልዳቸው የሸዋ ሰው ናቸው፡፡ አለቃ ወልደ አብ 600 መጻሕፍትን ካነበቡ በኋላ በመምህር ኤስድሮስ በተሻሻለው ትርጓሜ ላይ አዳዲስ የራሳቸውን አስተያየት ጨምረው በስፋት ስላስተማሩ "የትርጓሜ አባት" እየተባሉ ይጠራሉ፡፡



በመሆኑም በታች ቤት አንድምታ ትምህርት ቤት ታዋቂና ስመ ጥር በክብር ተጠቃሽም ሊቅ ናቸው፡፡ በላይ ቤትና በታች ቤት የአንድምታ ትርጓሜ መካከል ያለው ልዩነት የአብርሆትና የሐተታ ማብዛትና ማሳጠር፣ ታሪክና ምሳሌን በብዛት በማቅረብና በማሳነስ እንዲሁም በቋንቋ አጠቃቀም እንደሆነ ይታያል፡፡ ለምሳሌ በአራቱ ወንጌላት የአንድምታ ትርጓሜ መግቢያ ላይ የሚነገር ረዥም ሐተታ አለ፡፡ በሐተታው ውስጥ "ጌታ የወንጌል ጸሓፊዎችን ከፍ ብሎ አምስት፣ ዝቅ ብሎም ሦስት ለምን አላደረጋቸውም? ለምን አራት አደረጋቸው?" ተብሎ ከተጠየቀ በኋላ በታች ቤት መምህራን ዘንድ አራትነት ያላቸው ዐሥራ አራት ነገሮች ለጥያቄው መልስ ሆነው ተሰጥተዋል፡፡ የላይ ቤት መምህራን ግን በታች ቤት መምህራን የሚቀርበውን ይህን ሁሉ የአራት ቍጥር ምሳሌያዊ ሐተታ አይጠቀሙበትም፡፡

ከዚህም የተነሣ የታች ቤቱ መምህር አራት የሆኑ ነገሮችን ሁሉ በምሳሌነት ሲጠቀሙ የሰሙት የላይ ቤቱ መምህር ባለቤታቸውን ጠርተው "እነዚያን አራት አሞሌ ጨዎች የታች ቤት መምህራን እንዳይወስዱብኝ ደብቂልኝ" አሉ ይባላል፡፡

በዚህ መሠረት ብዙ ጊዜ የላይ ቤት አንድምታ ትርጓሜ እንደሚረዝም ቢነገርም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የታች ቤቱ ትርጓሜ ይረዝማል፣ የላይ ቤቱም ያጥራል፡፡

ከዚህም ሌላ የታች ቤት መምህራን ለአንዳንድ ተአምራት ምሳሌያዊ ትርጓሜን ሲሰጡ የላይ ቤት መምህራን ከዚህ ነጻ ናቸው፡፡ (ማቴ.8፡14-16) ታሪክና ሐተታን በተመለከተም በውዳሴ ማርያም 3፣2 እና 10፣7:6 እና 8 ወዘተ ያለው ረዥም ሐተታ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ያለውን ልዩነት አጉልቶ ያሳያል፡፡

በላይ ቤት የትርጓሜ ሐተታ መብዛት ምክንያት ነገሩን ግልጥ ለማድረግ እንደሆነ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉት ጥቂት ሐተታዎች በንጽጽር ቀርበዋል፡

| | የላይ ቤት አንድምታ | | የታች ቤት አንድምታ |
|---|---|---|---|
| 1 | "...ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ከብልየት ታደሱ፣ በአእምሮ ጐለመሱ፡፡ ብልየት ድንቁርና ነው፤ አንድ ቋንቋ ብቻ መናገር ነው፤ መታደስ ዕውቀት ነው፤ በሰባ ሁለት ቋንቋዎች መናገር ነው፡፡" (የትርጓሜ ወንጌል መግቢያ ታሪክ) | 1 | "...ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ከብልየት ታደሱ፣ በአእምሮ ጐለመሱ፤ ምሥጢር ተረጐሙ፤ አንድ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ ሰባ አንድ ቋንቋ ተጨመረላቸው፡፡ (የትርጓሜ ወንጌል መግቢያ ታሪክ) |
| 2 | "...እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም በልብ የመከረውን፣ ድኅረ ዓለም በነቢያት ያናገረውን ለመፈጸም ሥጋ ሆነ፡፡ (የትርጓሜ ወንጌል መግቢያ ታሪክ) | 2 | "...እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም በልብ የመከረውን፣ በነቢያት ያናገረውን ለመፈጸም ሥጋ ሆነ፡፡" (የትርጓሜ ወንጌል መግቢያ ታሪክ) |
| 3 | "መልአኩ ገብርኤል ... በስድስተኛው ወር ተላከ... ስለምን በስድስተኛው ወር ተላከ? ቢሉ፡-<br>በስድስተኛው ቀን የተፈጠረ አዳም በድሎ ነበርና እርሱን ለማዳን ወልድ እንደመጣ ለማጠየቅ ነው፡፡<br>ስለምን በዚያ ወራት ተላከ? ቢሉ<br>በዚያ ወራት የተፈጠረ ፍጥረት በዚያ ወራት በተፈጠረ አዳም በደል ምክንያት ተጐድቶ ነበርና እርሱን ለማዳን ወልድ እንደመጣ ለማጠየቅ ነው፡፡ አንድም በስድስተኛው ሽህ ተላከ፡፡ ጌታ ሰው መሆኑ ስድስተኛው ሺህ ሲጀመር ነውና፡፡...<br>ስለምን ገብርኤል ተላከ? ቢሉ<br>መላላክ የለመደ ነውና ወደ ዘካርያስና ወደ ኤልሳቤጥ የተላከ እርሱ ነውና፡፡ ገብርኤል ማለት አምላክ ወሳብእ ማለት ነው፡፡... አምላክ ሰው፣ ሰውም አምላክ የሚሆንበት ጊዜ ደረሰ ለማለት ነው፡፡ (የላይ ቤት የሉቃስ ወንጌል ትርጓሜ) | 3 | "ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር ገብርኤል የሚባል መልአክ ከእግዚአብሔር ታገዘ መጣ፡፡ ሳድስ ወርኃ ጌታ በስድስተኛው ወር ሰው መሆኑን ያሳያል፡፡ እንኳን በወር በዕለት ይመስለዋል፡፡ (የታች ቤት የሉቃስ ወንጌል ትርጓሜ)<br><br>በላይ ቤትና በታች ቤት ይህና ይህን የመሰለ ልዩነት ያለ ከመሆኑ የተነሣ የታች ቤት መምህራን የላይ ቤቱን አንድምታ ትርጓሜ እንደ ምንጭና ማስረጃ አድርገው ሲጠቅሱ የላይ ቤት መምህራን ግን ከመተቸት በቀር የታች ቤት ትርጓሜን አይጠቅሱም፡፡ (መቅድመ ወንጌል 1916 ዓ.ም. ገጽ 12 ዐምድ 2፣ እንዲሁም ገጽ 17 ዐምድ 2፡፡) |

www.ethiopianorthodox.org

## የላይ ቤት አንድምታ ትርጓሜ መምህራን፤

የአንድምታ ትርጓሜ የላይ ቤትና የታች ቤት ትርጓሜ ተብሎ ከተከፈለ በኋላ መምህራኑ የላይ ቤትና የታች ቤት መምህራን እየተባሉ መጠራት ጀምረዋል፡፡ በመሠረቱ ከኤስድሮስ በፊት የነበሩት መምህራን ሁሉ የአንድ ዐይነት ትርጓሜ መምህራን ነበሩ፡፡ የመምህር አስድሮስን ተጨማሪ አንዳንድ ጊዜም ተቀናሽ ትርጓሜን የተቀበሉ መምህራን የታች ቤት ትርጓሜ መምህራን ሲባሉ ያልተቀበሉት ደግሞ የላይ ቤት ትርጓሜ መምህራን መባላቸው ቀደም ተብሎ ተገልጦአል፡፡
ከላይ ቤት መምህራን ጥቂቶች በመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ባልታተመ ማስታወሻ መጽሐፍ ላይ ስለተገኙ እንደሚከተለው ተጽፈዋል፡፡

"በቃላቸው እውነተኞች የሆኑ አባቶቻችን እንደነገሩን የመንፈሳውያን አባቶች መምህራን ትውልድን እንጽፋለን፡፡

"ክቡር አባታችን ሠርጸ ድንግል ዘየሣራት ወደ ዐዋቂዎች ሊቃውንት ወደ ግብፅ ሀገር ወርዶ ስምንት ዓመት ተቀመጠ፡፡ ዐሥራ ሁለት ዓመት ተቀመጠ የሚሉም አሉ፡፡ በዚያም የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜን ተምሮ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡ በትምህርትም ብዙኃን መምህራንን ወለደ፡፡

"ከእነርሱም መካከል የሣራቱዎች /የሣራት ሰዎች/ አባ መቃርስ፣ አባ ትርሲትና ተክለ ማ?በር የተባለው የአነቄይ ሰው ገላውዴዎስ፣ አባ ጳውሊ፣ ሠርጸ ክኒሳ የተባለው አባ ዝክሪና ድባይ ናቸው፡፡ እነዚህም ስሞቻቸውን የምናውቃቸው ናቸው፡፡

"አባ ትርሲትም በብሉይ ኪዳን ትርጓሜ አምኃ ጊዮርጊስ ዘየሣራትን፣ በትምህርት ወለደ፡፡ አምኃ ጊዮርጊስም ተዝካሮን ወለደ፣ ተዝካሮም የአንባ ማርያሙን አቤቶ ጸጋ ክርስቶስንና የዲማውን አባ መዝሙረ ድንግልን ወለዳቸው፡፡

"አቤቶ ጸጋ ክርስቶስም አቤቶ ዘኢየሱስን ወለደ፡፡ አቤቶ ዘኢየሱስም የደብሳኑን ዘወልደ ማርያምን ወለደ፡፡

"አባ መዝሙረ ድንግል ዐቃቤ ሰዓት አበሞን ወለደ፤ ዐቃቤ ሰዓት አበሞም የወይናሙን አባ አብራንዮስንና የጎንጃን አባ አካለ መስቀልን ወለደ፡፡ ዳግመኛም በትምህርት ጸጋ ከአቤቶ ዘኢየሱስ ተወለደ፡፡

"አባ አካለ መስቀልም የጎንጃን አባ ዘማርያምን ወለደ፡፡ የወይናሙ አባ አብራንዮስም ሠናየ ጥበብ አቤቶ አቤሴሎሞን ወለደ፡፡ እነዚህ ሁሉ የብሉይ ኪዳን መምህራን ናቸው፡፡

"አባ ዝክሪ በሐዲስ ኪዳን ትምህርት የጽላሎውን አባ መዝገበ ሥላሴን ወለደ፡፡ አባ መዝገበ ሥላሴም የጎንጃን አባ ዲዮስቆሮስን ወለደ፡፡ አባ ዲዮስቆሮስም የየሣራቱን አባ አስጢፋኖስን፣ የጎንጃን መምህር አባ ዐምደ ሃይማኖትን፣ አባ ጸጋ ክርስቶስን፣ የቆማውን አባ የማነ አብንና የቤገምድሩን ሐዋርያ መስቀልን ወለዳቸው፡፡

"አባ ሐዋርያ መስቀልም አቤቶሁን ደመ ክርስቶስን ወለደ፡፡ አቤቶሁን ደመ ክርስቶስም አቤቶ ሚካኤልን ወለደ፡፡ አቤቶ ሚካኤልም ዐቃቤ ሰዓት አፈ ክርስቶስን፣ የድርድራውን ወልደ ዮናንና የአረሁናውን አባ ቆዝሞስን ወለዳቸው አባ ቆዝሞስም ካልእ ቆዝሞስንና አቤቶ ሚካኤልን ወለዳቸው፡፡ እኒህም የሐዲስ ኪዳን መምህራን ናቸው፡፡"

የትምህርታቸው ጸጋ ከእኛ ጋር ይኑር
አሜን፡፡

(ያልተተመ የክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ መዝገብ)



ከእነዚህም ሌላ ስመ-ጥር የነበሩት የብሉይ ኪዳን አንድምታ መምህራን እነ ጌታ ገላውዴወስ፣ መልአከ ገነት ወሰን፣ መልአከ ገነት ተክለ ሃይማኖት፣ አቶ አደራህ፣ አራት ዐይና ጎሹ፣ መምህር ገብረ ኤልያስ፣ መምህር ሰው አገኘሁ፣ መምህር ፈላታዎስ፣ መምህር ጌታሁን (ትልቁ) የላይ ቤት የብሉይ ኪዳን አንድምታን ከታች ቤቱ የብሉይ አንድምታ ጋር በማነጻጸር ያስተምሩ እንደነበር ይተረክላቸዋል፡፡ እኒህ ሊቃውንት የላይ ቤቱ አባባል እንዳይቀር "የላይ ቤት አብነት ወይም የላይ ቤት አማርኛ ወይም የላይ ቤት ትርጓሜ እንዲህ ይላል በማለት ያብራሩ ነበር ተብሎ ይነገርላቸዋል፡፡ የታች ቤት መምህራንም የራሳቸውን ቤት ትርጓሜ ከጨረሱ በኋላ የላይ ቤቱን አባባል ለመስማት ወደ ላይ ቤት መምህራን ይሄዱ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ እስካሁን ድረስ የላይ ቤት ትርጓሜ በታች ቤት መምህራን መጠቀሱ አልቀረም፡፡

# ክፍል 10

## የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ምንጮች

መምህር ኤስድሮስ በደሴተ ጣና ከሚገኙ መጻሕፍት ሦስት መቶ መጻሕፍትን አንብበውና ጥናት አድርገው ከዚያ በፊት ያስተምሩት በነበረው የአንድምታ ትርጓሜ ላይ ማሻሻልና ተጨማሪ ማብራራት እንዳደረጉ በትውፊት ይነገራል፡፡ ከዚህም ጋር "መምህር ኤስድሮስ እንዲህ ብለዋል፡፡" እየተባለ የሊቁ ተጨማሪ አብርሆት ይጠቀሳል፡፡ (ዮሐ.5፡8) እንደዚሁም አለቃ ወልደ አብ ከመምህራቸው ከመምህር ኤስድሮስ በላይ ስድስት መቶ መጻሕፍትን በማንበብ የአማርኛ አንድምታን ፍካሬ ማቃናታቸው አሁንም በጉባኤ ቤት ይተረካል፡፡ እነዚህ ሁለት ታላላቅ ሊቃውንት ያነበቧቸው መጻሕፍት ምን ዐይነት በማንና መቼ የተደረሱ፣ ከምን ቋንቋ የተተረጐሙ መጻሕፍት እንደሆኑ ባይጠቀስም ለአንድምታ ትርጓሜ የሚጠቅሙ መሆናቸው ግልጥ ነው፡፡ በተለይ አለቃ ወልደ አብ ዐረብኛ ቋንቋ ያውቁ እንደነበረ ስለሚነገርላቸው የአስክንድርያና የአንጾኪያ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት በዐረብኛ የጻፉአቸውንና ግብጻውያን የኢትዮጵያ ጳጳሳት ያመጡአቸውን የትርጓሜ መጻሕፍት ማንበባቸው የማይቀር ነው፡፡ ይህም እውነታ በአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ "በዐረቡ እንዲህ ይላል" እየተባለ የሚጠቀሰው ባህለ ትርጓሜ የአለቃ ወልደ አብ ሥራ መሆኑ ይነገራል፡፡ (ማቴ.1፡3፤17፡9፡፡ ዮሐ.1፡41 እና 42፡፡ ራእ .9፡11 የአራቱ ወንጌላት መግቢያ ታሪክ 1988 ዓ.ም.ገጽ 52.)

ብዙ ጊዜ "....." እንዲል በማለት በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ ያለ ባለቤት የሚጠቀሱ ጥቅሶች ሁሉ መምህር ኤስድሮስና አለቃ ወልደ አብ፣ ሌሎችም ተከታዮቻቸው ሊቃውንት መጻሕፍትን አንብበውና ጥናት አድርገው ያስቀመጡአቸው ናቸው፡፡ ሊቃውንቱ የትርጓሜ ምንጮች የሚገኙበትን ቦታ አስመጥቀሳቸው የደቀመዛሙርት የመጠየቅና የመመራመር ፍላጎት እንዲሰፋ ለማድረግና ተመራምረው ይድረሱበት ለማለት እንደሆነ የትርጓሜ መምህራን ራሳቸው ይናገራሉ፡፡ በሌላም በኩል ራሳቸው መምህራኑ ብቻ ተጠያቂ እንዲሆኑ ፈልገው የትርጓሜ ምንጮችን እንደማይናገሩ ሐሜት አለ፡፡ ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ አንዳንድ ዐይናማ ሊቃውንት የትርጓሜ ምንጮችን ለደቀ መዛሙርታቸው በቃል መናገር፣ በጽሑፍም ማስፈር ጀምረዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ በአሁኑ ጊዜ የትርጓሜ ምንጮች እየታወቁና እየተለመዱ መጥተዋል፡፡

በስም የተጠቀሱትና ያልተጠቀሱት ምንጮችን በዚህ ጽሑፍ ለመግለጥ ተሞክሮአል፡፡ ከአንድምታ ትርጓሜ ስብስብ ውጭ በስም በተጠቀሱ ምንጮች ላይ ብዙ ጊዜ የአማርኛ ሐተታ ይቀርባል፡፡ የግእዝ ዘሮችም የቃላት ትርጓሜን ለማብራራት ወይም የተለያዩ ዘሮችን (ንባቦችን) ለመግለጥ ይገባሉ፡፡ (የሐዋ .1፡2፤ 7፤9፤ ሮሜ.1፡25) እንደዚሁም ለአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ የሚጠቀሱ የተለመዱ ጥቅሶች አሉ፡፡ (ዳን.2.46፡፡ ቅዳሴ 272፤275)

ሀ. የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ማስረጃ (ምንጭ)

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የግእዝ በግእዝ አንድምታ ትርጓሜ ለአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ አተራረጽ እጅግ ጠቅሞአል፡፡ ከሌሎች የትርጓሜ ምንጮች ሁሉ የዚህ ምንጭነት የበለጠ ሆኖ ይታያል፡፡ ለምሳሌ የማቴዎስ ወንጌል 2.3 አንድምታ ትርጓሜ ስብአ ሰገል 12 ነገሥታት ነበሩ በሚለው የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ወንጌልና ሦስት ናቸው በሚለው ተአምረ ኢየሱስ መካከል ያለውን ግልጥ የሆነ ልዩነት

www.ethiopianorthodox.org

ይጠቅስና መፍትሔ ሲሰጥ ዐሥራ ሁለት ሆነው ከወጡ በኋላ ዘጠኙ ወደ ቤቱልሔም ሳይደርሱ ተመልሰዋል በማለት የትርጓሜ ወንጌልን ዐሳብ ያጸናል፡፡ የግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ኦሪትም ዛሬ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ መምህራን ለሚተረጉሙት የኦሪት አንድምታ ትርጓሜ ምንጭነቱ የታወቀ ነው፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት 1.3 ላይ "ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጸልል መልዕልተ ማይ" ተብሎ ከተነበበ በኋላ የሚቀጥለው ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ "ይህንም መሻፍቃን የተባለው ሊቅ ለውሆች ሕይወት የሚሰጥ፣ ውሆችን የሚያነጻ ነፋስ ነው ብሎ ተርጉሞታል፡፡"

ትርጓሜ ኦሪትም "በጥምቀት ጊዜ የሚሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው፡፡" ይላል፡፡ ሳዊሮስም " ደመ ድንግልናን ከእመቤታችን የከፈለ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው" ይላል፡፡ ባስልዮስም "እንደ ኤርምያስና ዮሐንስ ላሉት በማ?ፀን የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው ብሏል" እየተባለ ለሚታተው የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ሁሉ ምንጩ ግእዝ በግእዝ የኦሪት ትርጓሜ ነው፡፡

ሌሎችም ትርጓሜ ወንጌልንና ትርጓሜ ኦሪትን የሚያሳዩ ግልጽ ጥቅሶች በብሉይና ሐዲስ ኪዳናት እንዲሁም በሊቃውንት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ አሉ፡፡ (ዮሐ.13.15፡፡ ፍ.ነ 163፤ ዘዳግ .32:8፡፡ ዘፍ.37.34፡፡)

በማቴዎስ ወንጌል 1.16 ላይ "ክልኤቱ ሊቃውንት አመሩ ፈቃደ ዮሴፍ ወሠለስቱ ሊቃውንት አመሩ ፈቃደ ሥላሴ" በመባል ሁለቱ ሊቃውንት የዮሴፍን ፈቃድ አመለከቱ፤ ሦስቱ ሊቃውንት ደግሞ የሥላሴን ፈቃድ አመለከቱ" ተብሎ ያለ ስም የተጠቀሱትን አምስት ሊቃውንት መተርጉማኑ ስማቸውን ገልጠው ይናገራሉ፡፡ "ሁለት ሊቃውንት የተባሉ ያዕቆብ ዘሥሩግና ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ ናቸው፡፡ ሦስቱ ሊቃውንትም ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ አትናቴዎስና ያዕቆብ ዘሮሃ ናቸው" ይላሉ፡፡ መተርጉማኑ የሊቃውንቱን የስም ዝርዝር የወሰዱት ከግእዝ ትርጓሜ ወንጌል ነው፡፡

ይህን የመሰለ ያለ ስም ወይም ስም ሳይጠቀስ የተወሰደ ትርጓሜ ወንጌልም በየክፍለ ትርጓሜው በብዙ ቦታዎች ይገኛል፡፡ ለምሳሌ፡-

- የሰብአ ሰገል ብዛት ማቴ.2:3፣
- አብርሃም ሶርያዊ ማቴ.17:19፣
- ትርጓሜ ቤተልሔም ማቴ.2:1፣
- ትውልደ አራዊተ ምድር ማቴ.3:7፣
- ሐተታ ዐቀብተ መቃብር ማቴ.28:15 ወዘይመስሎ፡፡

## ለ. ሃይማኖታዊ ታሪክ፣ (ተአምር፣ ገድልና ዜና ቅዱሳን ገዳማዊ ታሪክ)

ብሔራውያን ሊቃውንት የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜን በአዘጋጁ ጊዜ ብዙ ምንጮችን መጠቀማቸው የትርጓሜ ሥራቸው ያሳያል፡፡ የቅዱሳንን ገዳማዊ ሕይወት፣ ገድልና ተአምር ምሳሌና ማስረጃ ማብራርያም አያደረጉ በትርጓሜያቸው አስገብተዋል፡፡ እነዚህ ምንጮች በስምም ያለ ስምም ተጠቅሰዋል፡፡

- ስንክሳር መዝ.109:4፤ ሚክ.5:6፤ ሉቃ.2:21፤ ዮሐ.4:11፤ ማር.ይስ.አንቀጽ 4 ምዕ.5 ገጽ 85፡፡ ውዳ.ማር.1:7፡፡ ማር.ይስ.ምዕ.6 ገጽ 59፡፡
- ዜና አበው ፡- ሮሜ.12:15፡፡ ማር.ይስ.229-330፡፡
- መጽሐፈ ገነት ሮሜ.5:5፡፡

በስም የተጠቀሱ ምንጮች ወይም ማስረጃዎች ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉት ናቸው፡፡



- ተአምረ ኢየሱስ፡- ማቴ.2:3፤ 25:13፤ ዮሐ.20:30፤ ዮሐ.አፈ.ወር.ድ 420፤ ቅዳ...255፡፡
- ተአምረ ማርያም፡- መዝ.44:7፡፡ ዮሐ.አፈ.ወር.ተግ.27፡፡
- ነገረ ማርያም፡- ሉቃ.1:27፤ ቅዳ---247፤ ራእ.5:13፡፡
- ገድለ ፊቅጦርና ገድለ ሲኖዳ፡- ማቴ 24.14
- ገድለ ዮሐንስ መጥምቅ፡- ማቴ 14.11፡፡
- ገድለ ተክለ ሃይማኖት ፈልክስዮስ ፡- ተስ.109 ገጽ 145
- ገድለ ሐዋርያት ማር.ይስ.አንቀጽ 18 ገጽ 175 ዐምድ 1፡፡
- መጽሐፈ ሐዊ፡- መዝ.29:6፡፡
- አክሲማሮስ፡- ዘፍ.2:17፡፡ ሕዝ.16:3፡፡
- ግብረ ሕማማት፡- ቅዳሴ ገጽ 156፡፡
- መጽሐፈ ሳዊሮስ፡- ሉቃ.4:18፡፡ ከዚህ ላይ ሳዊሮስ በስም ሳይሆን "ሊቁ" በመባል ብቻ ተጠቅሶአል፡፡ "መንፈስ እግዚአብሔር ላዕሌየ ... የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፡፡ " ይህንም ሊቁ "መንፈስ ዘህላዊየ -- በባሕርዬ ያለ መንፈስ ነው" ብሎ ወስዶታል ተብሎ የተጠቀሰው ሊቅ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዕብ.2:15፡፡ 11:19፡፡
- አንኮራጦስ ዘኤጲፋንዮስ፡- ሕዝ.44:2፡፡ ማቴ.2:11፡፡
- ዕርገተ ኢሳይያስ፡- ሲራ.1:9፡፡ 24:8፡፡
- ራእየ ኢሳይያስ፡- ዮሐ.አ.ወ.ድ.338፤ ዮሐ.አ.ተ.74፡፡
- ራእየ ኤልሳዕ፡- ማቴ.10:1፡፡
- ድርሳነ መድኀኔዓለም ፡- ማቴ.27:28
- ግብረ ያዕቆብ ዘስሩግ፡- ዘፍ.22:10፡፡
- ድርሳነ ሚካኤል፡- ፍ.ነ.291

### ሐ/ የታሪክና የሕግ መጻሕፍት

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜን ሲያዘጋጁ ያልጠሰቁለት ምንጭ የለም፡፡ ሃይማኖት ነክ የሆኑትን መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን የዓለም ታሪክ መጻሕፍትንም ተጠቅመዋል፡፡ በተለይም በአኃት አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት ተደርሰው ወደ ግእዝ የተተረጉሙ መጻሕፍትን ለትርጓሜ ሥራቸው በብዛት ይጠቅሳሉ፡፡ ለምሳሌ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ፡- ዘሌዋ.23:44፤ ዘዳግ.32.8፤ ኢሳ.40.31፤ 1ጴጥ 3.7፡፡ ቅዳሴ ገጽ 37፡፡ ዮሐ.አፈ.ወር.ተግ 340፡፡
- ዮሐንስ መደብር፡- ሕዝ.16:1፡፡ ሉቃ13.5፡፡

www.ethiopianorthodox.org

- ዜና እስክንድር፡- ሕዝ.38.4፡፡ መዝ.66፡1፡፡ 1ቆሮ.3፡19፡፡ ዮሐ.አፈ.ወር.ድ 99፡፡

- ፈውስ መንፈሳዊ፡- ቅዳሴ (ሥርዐት) 42

## 2. ጸሎትና የመዝሙር መጻሕፍት

እነ መምህር ኤስድሮስና እነ አለቃ ወልደ አብ ብዙ መጻሕፍትን አንብበው የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜን አዘጋጁ ሲባል በብሔራውያን ሊቃውንት በማእዝ የተደረሱና የአምልኮት አገልግሎት መፈጸሚያ የሆኑ የመዝሙርና የጸሎት መጻሕፍትን ሁሉ በማንበብ ነው፡፡ መልክዓት፣ ሰዓታት፣ አርኪ.ዎች፣ ማ?ሌተ ጽጌ፣ የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት እንደዚሁም የሊቃውንቱ ቅኔያት ለአንድምታ ትርጓሜ ምንጭና ማስረጃ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- መልክአ ኢየሱስ ፡- ሕዝ.22፣15
- ሰዓታት ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፡- ኢሳ.19፡2፣

- ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ፡- ኢሳ.19፡1፡፡ ሉቃ.1፡40፣ ፍ.ነገ.135፣ ፍ.ነገ.495፣ ቅዳሴ (ሥርዐት) 42፣ 86፡263፡፡

- ማኅሌተ ጽጌ፡- ቅዳሴ ማር.ምዕ.1 ቁ.1.ገጽ 413፣ ምዕ.2፡ቁ.27 ገጽ 429፡፡

- አንቀጸ ብርሃን፡- ኢሳ.6.2፡፡

- አርኪ፡- 1ቆሮ.6፡3፡፡ ኤፍ.1፡7፣ ፊልክስዩስ ተስ.23 ገጽ 44፡፡

## 3. ቅኔ ሊቃውንት

የታላላቅ ሊቃውንት ቅኔዎች ለአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ምንጭ ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡ የትርጓሜ አዘጋጂዎች ከእነርሱ በፊት የነበሩ ሊቃውንት የደረሱአቸውን ቅኔዎች ለምንጭነት ተጠቅመዋል፡፡ ከቅኔዎቹ ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

"እስመ እንዘቦ ሕያወ እሞተ ሥጋ ግዙፍ፣

-"ሞተ ዮሴፍ አኃዊሁ ነገርዎ ለዮሴፍ" ግብ.ሐዋ.7.12 ገጽ 63 ዐምድ 1፡፡
ከግዙፍ ሥጋ ሞት ሕያው ሳለ
"የዮሴፍን ሞት ለዮሴፍ ወንድሞቹ ነገረውታልና" ግብ.ሐዋ.7.12 ገጽ 63 ዐምድ 1፡፡

-"ዐጽመ ነቢየ ቤቴል ድኅነ ምስለ ዐጽመ ባዕድ፣
እንዘ ነፍሱ ትውዒ በነድ፡፡
የቤቴል ነቢይ ዐጽም ከሌላው ዐጽም ጋር ዳነ፡፡
ነፍሱ በእሳት እየተቃጠለች፡፡" ፊልክስ ክፍል 3 ተስእሎ 31 ገጽ 58፡፡
አረጋዊ መን.ድር.25 ገጽ፡139፡፡

- ምንትኑ መንግሥት ከመ ታንክሩ መንግሥተ፣
ለብሂለ ነገሠ ፍጻሜሁ አኮኑ ብሂለ ሞተ፡፡
መንግሥትን ታደንቁ ዘንድ መንግሥት ምንድን ነው?
ነገሠ የማለት ፍጻሜው ሞተ ማለት ነውና" (ዮሐ.አፈ.ወር.ተግ.ገጽ 111)



## 4. ሥነ ፍጥረታዊ ታሪክ

በዚህ ምድብ ለአንድምታ ትርጓሜ በምንጭነት የሚጠቀሰው ፊሳሎጎስ ነው፡፡ ይህም የፍጥረትን ጠባይዕ የሚናገር የፈላስፋ መጽሐፍ ነው፡፡ በተለይም ነገረ እንስሳትንና ነገረ አራዊትን የሚናገር ነው፡፡ ሊቃውንቱ የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ይህን መጽሐፍ እንደተጠቀሙ በብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ማቴ.8፡17፡፡ 10፡16፡፡ ሮሜ.4፡13፡፡ ውዳሜር 6፡2፣ 7፡1፡፡ ፍ.ነገ.163፡፡ በፊሳሎጎስ የሚጠቀሱ አራዊትና አዕዋፍ በትርጓሜ ውስጥ ተደጋግመው ይነገራሉ፡፡

-አንበሳ፡- ራእይ 5.5፣

- ዘአሐዱ ቀርኑ (ባለ አንድ ቀንዱ) መዝ.21፡21፣

- አፍዖት፡- ማቴ.3፡7፣

- ያፈ ፊንክስ፡- መሳ.5፡4፣ ኢሳ.40፡31፣ ኤር.8፡7፣ ቅዳሴ አትና.323፡፡

## 5. ባህለ ጠቢባን

የአንድምታ ትርጓሜ ሊቃውንት "ዐይነ ርግብ" እየተባሉ እንደሚጠሩ ከትርጓሜ ቤት ትውፊት እንረዳለን፡፡ የርግብ ዐይኗ ሁለንተናው እንደሚያይ የመተርጉማኑ ዐይነ ልቡናቸው ምሥጢረ ሰማይ ወምድር፣ ዐይነ ሥጋቸውም ብዙ መጽሐፈ ጥበብ ያያል፡፡ በመሆኑም የአንድምታ ትርጓሜያቸውን ከብዙ መጻሕፍት ንባብ ቀስመው አዘጋጅተዋል፡፡ በዝግጅታቸውም የጠቢባንን አባባል ተጠቅመዋል፡፡ ይህንም መጽሐፈ ፈላስፋ ከተባለው መጽሐፍ እየጠቀሱ ማስረጃ ማድረጋቸው በትርጓሜያቸው ይገኛል፡፡ 1ቆሮ.15 ፡33፣ ዮሐ.አፈ.ወ.ድ 33 ገጽ 433፡፡ ሃይ አበ ትርጓሜ ሱኑት ዘአስክንድርያ፡፡

## 6. ሥነ ጥበብ

በአንድምታ ትርጓሜ ውስጥ ባለቤቱ በስም ያልተጠቀሰ በርካታ ሥነ-ጥበባዊ ሐተታ ይገኛል፡፡ አንዳንዱም ምንም እንኳ በስም ባይጠቀስ ከሄኖክ ሥነ-ጥበባዊ ሐተታ ጋር ዝምድና አለው፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉት ሥነ ጥበባውያን ገለጣዎች ቀርበዋል፡፡

- ዕፀ መድኀኒት ፡- መዝ.93፡11፣ ኤር.1፡11፡፡
ሥነ ከዋክብት፡- መዝ.146፡4፣ 148፡3፡፡ ይሁዳ 13፣
ሲራክ 36፡8፣ ፍ.ነገ.440 - 441፣ 457 - 458፣ 567፡፡ ቅዳሴ ማርያም ገጽ 259 - 260፡፡

## 7 .ፍካሬ ረበናት

በኋላ የተነሡ ብሔራውያን ሊቃውንት ከቀደሙት ሊቃውንት ይልቅ የውጭ ቋንቋ የመማርና ብዙ መጻሕፍትን የማንበብ ዕድል ስለገጠማቸው የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜን በሚያዘጋጁበት ጊዜ በተለይም መጽሐፈ ሕዝቅኤልን በሚተረጉሙበት ጊዜ ከአይሁድ ረበናት ፍካሬ ጠቅሰዋል፡፡ ሚድራሽን ለትርጓሜ ሥራቸው ምንጭ አድርገዋል፡፡ ሕዝ.17፡1፣ 24፡8፣ 26፡1፣ 37፡2፣ 39፡11፣ 41፡8፣ 42፡4፣ 45፡2፡፡ ይህ ምንጭ የሚገኘው በመጀመሪያው የመጽሐፈ ሕዝቅኤል ትርጓሜ ሳይሆን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍለ ጊዮርጊስ ባዘጋጁት በሁለተኛው የመጽሐፈ ሕዝቅኤል ትርጓሜ ውስጥ ነው፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ዕብራይስጥ ያውቁ ስለነበር ታልሙድን በማንበብ የረበናትን ፍካሬ ለትርጓሜያቸው ማስረጃ አድርገዋል፡፡ ይህም እጅግ ያስከብራቸዋል፡፡ እነ መምህር ኤስድሮስ ብዙ መጻሕፍትን አንብበው የአንድምታ ትርጓሜን እንደአሻሻሉ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም እንዲሁ አድርገዋል፡፡ (ትርጓሜ ሕዝ.ከኪዳነ ወልድ 1916 ዓ.ም.)

www.ethiopianorthodox.org

## 8. የዕለት ማስታወሻ

የአማርኛ አንድምታ ሊቃውንት መጻሕፍትን በማንበብ ለትርጓሜ ሥራቸው ምንጭና ማስረጃ የሚሆኑ ነገራትን እንዳገኙ ሁሉ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ከሚያገኙአቸው ሰዎች ጋርም በመወያየት ወይም በትውፊት ሲተላለፍ የመጣውን ብሂል በማስታወስ የአንድምታ ትርጓሜን አዳብረዋል፡፡ አበ-ነገሩን ሳይጠቅሱ ነገሩን ብቻ ጠቅሰዋል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ተቀምጦአል፡፡

"... ፈረንጅ ‹ብአሴ ጻድቀ ዘአነግረክሙ› ያለው ማኅደር ነው፡፡ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ ያለው ኅዳሪ ነው፡፡" ይላል ግን ‹ይውግርዎ› ባለው ይረታል" (ዮሐ.8፡58) ይህ ትችት ከሌላ እምነት ተከታይ የውጭ ሀገር ሰው ጋር በመወያየት ጊዜ የተገኘ ወይም የውጭ ሰው ከጻፈው መጽሐፍ የተወሰደ ይመስላል፡፡ ከዚህም ሌላ በሮሜ መልእክት 16፡22 ላይ "ጠርጤዎስ" ስለተባለው ሰው ሲያትቱ "ጠርጤዎስ" ድሃ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለትሕትና ራሱን ጠርጤዎስ አለ፡፡ አንድም ያልታወቀ ሰው ነው፡፡... ካሉ በኋላ "በቀድሞ ዘመን ወደ ሀገራችን መጥቶ የነበረ ፈረንጅ እሲሀን ሁሉ (በሮሜ 16 የተጠቀሱትን ሁሉ ) አውቃቸዋለሁ፤ ይህን ሰው ግን (ጠርጤዎስን) አላውቀውም ብሏል፡፡" በማለት ያትታሉ፡፡ ይህም ለአንድምታ ሥራ የሊቃውንቱን ከፍተኛ ግንዛቤ ያመለክታል፡፡

# ክፍል 11

## የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ስልት

በሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ ተዘጋጅቶ በታተመው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት አንድምታ ትርጓሜ መቅድም ላይ የተጻፉ 13 የትርጓሜ ስልቶች አሉ፡፡ እነዚህን ስልቶች በመጽሐፉ መቅድም ገጽ 1-3 መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ከእነዚህም ጋር ሌሎች ተጨማሪዎች ስልቶች አሉ፤ እነርሱም ከዚህ በመቀጠል ተጠቁመዋል፡፡

### ሀ/ የሰዋስውና የቃል አገባብ፣

1. ሁለት ዐይነት ፍች ላለው የግእዝ ቃል በአማርኛ አማራጭ ትርጉም መስጠት ለምሳሌ "ወርኅ" ጨረቃ ወይም ወር ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡ (ሄኖ.80፡1 ወይም 26:36፡፡ ሲራ.43:7-8)
2. ተመሳሳይ ድምፅ ላላቸው የግእዝ ቃላት በአማርኛ አማራጭ ትርጉም መስጠት፤ ለምሳሌ "ረኃዩ ኮሉ" በአሌፍ ሲጻፍ ሁሉን የምታይ ተብሎ ይተረጐማል፡፡ "ረዓዩ ኮሉ ተብሎ በዐይን ሲጻፍ ደግሞ ሁሉን የምትጠብቅ የሚል ትርጊሜን ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ይህ ትርጓሜ የፊደሉን ድምፅ ለይተው ለማያውቁ እንጂ ለማለዩ አሻሚ አይሆንም፡፡ ( አረጋ .መን.መልእክት 42 ገጽ 316 ዐምድ 2) "ስአሊ ለነ" እንደዚሁም "ስማዕ ሰማይ" የሚለው ንባብ በዚህ ዐይነት ይተረጐማል፡፡ (ውዳሜር ኢሳ.1:2፡፡)
3. ለአንድ የግእዝ ቃል በተለያየ አነባበብ አማራጭ ትርጉም መስጠት፣ ምሳሌ፡- "እመ ቦ ዘሰምዐኒ፣ ወአርኅወኒ እበውእ ሶቤሃ ወአዐርፍ ምስሌሁ፡፡- የሚሰማኝና የሚከፍትልኝ ቢኖር ወዲያውኑ እገባለሁ ከእርሱ ጋርም አርፋለሁ፡፡ ሁለተኛው አማራጭ ትርጓሜ "የሚስማም የሚከፍትም ቢኖር ወዲያውኑ እገባለሁ፡፡ ከእርሱም ጋር አርፋለሁ፡፡" ማለት ነው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ከሰምዐና አርኅወ ግሦች መጨረሻ ያለውን ፊደል "ኒ" አንድ ጊዜ በዝርዝር በሁለተኛ ጊዜ በአገባብ ስለተተረጐመ ነው፡፡ (ራእ.3:20)
4. ቃላትን በማናበብ ወይም ባለማናበብ አማራጭ ትርጉም መስጠት፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፤ "መስቴ መኮንን" የሚፈርድ መጠጥ ነሙ፡፡ ይህ ሳይናበብ ነው፡፡ ሁለተኛው አማራጭ "መስቴ - መኮንን" የፈራጁ መጠጥ ነው፡፡ ይህ በመናበብ ነው፡፡ (ትም.ኅቡ.ቅዱ.ገጽ 10፣ዐምድ 2፡፡) ይህን የመሰለ ትርጓሜ ሃይ.አበ. ቁር. ምዕ.78 ቁ.28 ዕዝራ ሱቱኤል 7:2 ላይ መመልከት ይቻላል፡፡



5. "ማኅሸ" ቀጣዩ ንባብ አዲስ አረፍተ ነገር ማኅሸ ተብሎ ለመጀመሪያው ንባብ አማራጭ ትርጉም መስጠት፤ ወይም አንድን ዘርዕ ወይም ንባብ ወደኋላም ወደፊትም ካለው አሳብ ጋር ለማስማማት ሲፈለግ ወደፊት ያለውን ዘርዕ ማኅሸ ማድረግ ነው፡፡ (ምሳሌ ሮሜ.1 ፡32፡፡) ቅዳሴ ትም.ኅቡ 1 ገጽ 4 ሕዝ.39:8
6. አንድን የግእዝ ቃል በተለያየ የአማርኛ ቃል መተርጉም (ምሳሌ፣ ዮሐንስ አፈ.ወር ተግሣጽ 29 ገጽ 340 ዐምድ 1፡፡ ሕዝ.47:10)
7. የቃላትን መንፈሳዊ ትርጓሜ ሳይሆን መዝገበ ቃላዊ ፍች መግለጥ፣ ለምሳሌ ፍርሀት፣ ድንጋጤ፣ ረዐድ የተሰኙት ቃላት እንደ አግባባቸው በሚከተለው መንገድ ተብራርተዋል፡፡

- ፍርሀት የአእምሮ፣ ድንጋጤ የናላ፣ ረዐድ የጉልበት ነው፡፡(መዝ.47:5፡፡ ኤር.1:17፡፡ ሱቃ.1:12፡፡) ይህም መንገድ በአንድ ቋንቋ ተመሳሳይነት ያላቸው የሚመስሉ ግን ልዩነት ያላቸውን ቃላት ሊያስተረጉም የሚችል ነው፡፡ ገብረ (ሠራ)፣ ለሐኰ (ሠራ)፣ ፈጠረ (ፈጠረ) ማለት ሲሆን ገብረና ለሐኰ እምነበ ቦ ናቸው፡፡ ፈጠረ ግን እምነበ አልቦ ነው፡፡ (ዘፍ.1.፣7፤17፤2:7) ግእዙ ግን ገብረን እምነበ አልቦ ሲሆን ለሚባው ፍጥረት ያደርገዋል፡፡ (ዘፍ.1:1)፡፡ በመሆኑም ከዕብራይስጡ ይለያል፡፡

## ለ. የአገላለጥ አንድምታ

በአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ውስጥ አንድ ዘርዕ በፊደላዊ ትርጓሜ ሳይሆን በተለያየ ምሳሌያዊ ታሪካዊና ትንቢታዊ ትርጓሜ እስከ 13 ጊዜ ድረስ ይተረጐማል፡፡ ይህም የአገላለጥ ወይም ገላጭ ትርጓሜ ይባላል፡፡ በሌላም በኩል አወራረድ ይባላል፡፡ ለዚህም አንዳንድ ምሳሌዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

1. "በተመረጠች ቀን ሰማሁህ፤
   በመዳን ቀንም ረዳሁህ፡፡" (ኢሳ.49:8)
   የተመረጠች ቀንና የመዳን ቀን፡-
   - ሀ. እስራኤል ከግብፅ የወጡበት ቀን፣
   - ለ. በደብረ ሲና ሕግ የተሠራባት ቀን፣
   - ሐ.እስራኤል ከባቢሎን ምርኮ የወጡባት ቀን፣
   - መ.የተመረጠች ቀን ጌታ የተፀነሰባት ቀን፣
     የመዳን ቀን ጌታ የተወለደባት ቀን፡፡
   - ሠ. የተመረጠች ቀን ዕለተ ልደት፣
     የመዳን ቀን ዕለተ ስቅለት
   - ረ. የተመረጠች ቀን ዕለተ ስቅለት
     የመዳን ቀን ዕለተ ትንሣኤ፡፡
   - ሰ. የመዳን ቀን ከዕለተ ዐርብ እስከ ዕለተ ምጽአት፣
   - ቀ. የተመረጠች ቀንና የመዳን ቀን ዕለተ ንስሓ ናት፡፡
2. "ቀላይ ቀላይን ትጠራዋለች" (መዝ.41.7)
   - ሀ. ኤርትራና ዮርዳኖስ ፣
   - ለ. አሶርና ባቢሎን፣
   - ሐ. ፋርስና ሜዶን፣
   - መ. ነቢያትና ሐዋርያት
3. በተነበበው ዘርዕ ውስጥ አንዝ ከተገኘ የአንዙን መጠን ለመመላት ብዙ አኃዛዊ አገላለጥ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፈ ምሳሌ 9:1 እና በቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ምዕ.3 ቁጥር 11"ጥበብ ቤትዋን ሠራች፤

www.ethiopianorthodox.org

ሰባቱንም ምስሶችዋን አቆመች፡፡"
የሚለው ዘርዕ በሚከተለው የአገላለጥ ትርጓሜ ተተርጉሞአል፡፡ "ሰባቱ ምስሶዎች፡-

ሀ. ሰባቱ ዕለታት፣
ለ. ሰባቱ ሀብታተ መንፈስ ቅዱስ (ኢሳ.11.2)
ሐ. ሰባቱ መጻሕፍተ ቅዱሴ (አራቱ ወንጌላትና ሦስቱ ሐዲሳት ሃይ.አበ.ቁር.)
መ. ሰባቱ መጻሕፍተ ጉባኤ (ወንጌል፣ ሦስቱ ሐዲሳት፣ ሃይማኖተ አበው፣ ዲድስቅልያ፣ ቀሌምንጦስ፡፡)
ሠ. ሰባቱ መዓርጋተ ክህነት (ሦስቱ ዐበይት ፣ አራቱ ንኡሳን)
ረ. ሰባቱ ልኡካነ ቤተ ክርስቲያን (ሠራዒ ቂስ፣ ንፍቅ ቂስ፣ ሠራዒ ዲያቆን፣ ንፍቅ ዲያቆን፣ አንባቢ መዘምር፣ ዐዋቂ ኖኅት፡፡)
ሰ. ሰባቱ ሕዋሳት (ዐይን፣ ጆሮ፣ አፍ፣ አፍንጫ፣ እጅና እግር፣ ንኡስ መሌሊት፡፡)

በመጽሐፈ ሄኖክ 7.2 ወይም 24.3 ላይ "ሰባቱን ተራሮች አየሁ" የተባለው አንዛዊ ዘርዕ እንደሚከተለው ተገልጦአል፡፡ ሰባቱ ተራሮች፡-

1. ገነት
2. ደብር ቅዱስ
3. ሐመረ ኖኅ፣
4. ደብረ ሲና፣
5. ደብረ ዘይት፣
6. ደብረ ታቦር፣
7. ቀራንዮ ናቸው፡፡

የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ይህን በመሰለ የአገላለጥ ትርጓሜ የተሞላ በመሆኑ የትርጓሜ መጻሕፍትን በየአንቀጹ መመልከት ይቻላል፡፡ (ምሳ.1፡20-21፡፡ ኢሳ.1.9፡፡ 8፡1፡፡ ዘካ.8፡4፡፡ መክ.1፡15 ፡፡ኢሳ.4፡19፡፡) ይህ ዐይነቱ ስልት እንደ ስብከት ነጻ ትርጓሜ ነው፡፡ የአንዙ ትርጓሜም አንዳንድ ጊዜ ተመጣጣኝ አንዝ ሲፈለግለት በሌላ ጊዜ የተለያዩ ስም የገጠማቸውን ነገሮች በመደመር ይተረጐማል፡፡ ራእ.13፡18፡፡ በመሆኑም ሕግ የሌለው ሆኖ ይታያል፡፡ ለአንድ ዘርዕ የተሰጡ ትርጓሜዎች በአንድ ጊዜ የተዘጋጁ ሳይሆኑ በየጊዜው በተለያዩ ሊቃውንት የተተረጐሙ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ "ዕፀ ሕይወት" (ውዳ.ማር.5፡2) በቅዱሳን ባስልዮስና ማር ይስሐቅ ፍቅር ተብሎ ሲተረጐም በቅዱስ ኤፍሬም ሥጋውና ደሙ ተብሎ ተተርጐሟል፡፡

## 4. ኅብረ አምሳላዊ ትርጓሜ (አሊጎሪ)

የአማርኛ አንድምታ ትርጓሜ ከፊደላዊና ታሪካዊ ትርጓሜ የራቀ ባይሆንም በአብዛኛው በ?ብረ አምሳላዊ ትርጓሜ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአንድ ንባብ ድርጊት ወይም ሰው ወዘተ መሰሎ በ?ብረ አምሳላዊ ትርጓሜ በተተረጐመ ጊዜ መጀመሪያው አሳብ ያለ ዋጋ ወይም ያለ ጥቅም የሚቀር አይደለም፡፡ ለምሳሌ የኖኅ መርከብና በውስጥዋ የነበሩ ሰዎች ወደ መርከብዋ ያልገቡት ሰዎችም በመጀመሪያ ታሪካዊ ትርጓሜያቸው አንዳለ ሆኖ በሁለተኛ ጊዜ የሚከተለው ኅብረ አምሳላዊ ትርጓሜ አላቸው፡፡

ሀ/ መርከብ የሥልጣነ እግዚአብሔር፣ ኖኅና ቤተሰቡ የጻድቃነ ብሊት፣ በውጭ የነበሩት የኃኣነ ብሊት ምሳሌ ናቸው፡፡

ለ/ መርከብ የእመቤታችን፡፡ ኖኅ የጌታ፣ በቀኝ ያሉት በእመቤታችን ቃል ኪዳን ያመኑ፣ በግራ ያሉት በእመቤታችን ቃል ኪዳን ያላመኑ ምሳሌ፡፡

ሐ/ መርከብ የመስቀል፣ ኖኅ የጌታ፣ በቀኝ ያሉት የፊያታዊ ዘየማን፣ በግራ ያሉት የፊያታይ ዘአጋም ምሳሌ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

መ/ መርከብ የጥምቀት ምሳሌ ኖኅና ቤተሰቡ የጥሙቃን፣ ሦስት ክፍል መሆንዋ ጥምቀት በሥላሴ ስም ነውና፡፡

ሠ/ መርከብ የቤተ ክርስቲያን ኖኅና ቤተሰቡ የምእመናን ሦስት ክፍል መሆንዋ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ክፍል ናትና፡፡

ረ/ መርከብ የትንሣኤ ኖኅና ልጆቹ የሙታን ምሳሌ፣ ሦስት ክፍል መሆንዋ በኮረ ትንሣኤ ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን የመነሣቱ ምሳሌ ነው፡፡ (ዘፍጥ.8፡19-20፡፡)

ከዚህም ሌላ የአንድምታ ኅብረ አምሳላዊ ትርጓሜ "ለጊዜው" እና "ለፍጻሜው" በሚል ሥረይ ይብራራል፡፡ አንድ ፊደላዊ ወይም ታሪካዊ ትርጓሜ ከተተረጐመ በኋላ "ለጊዜው ተደርጎአል፣ ፍጻሜው ግን ምሳሌ ነው፡፡" ወይም "ለጊዜው ስለ እገሌ ቢሆን ፍጻሜው ስለ እገሌ ነው፡፡" ተብሎ ይብራራል፡፡ (ሕዝ.47፡1፣ ማቴ.8፡14፡፡ ማቴ.12፡42፡፡ ሉቃ.1፡33፡፡ ውዳ.ማር.1፡5፣6 ሕዝ.21፡19፡፡ 1ጴጥ.3፡21፡፡)

እንደዚሁም ኅብረ አምሳላዊ ትርጓሜ ደረቅ ሐዲስ፣ (ሰሙ ቀርቶ) (መዝ.109፡፡ ኢሳ.7፡14 እንደገናም "አምሳልና/ መርገፍ፣ ሰምና ወርቅ፣ ትንቢትና ፍጻሜ" እየተባለ ይገለጣል፡፡ (ሕዝ.33 9፡፡ 34፡2፡፡ 37፡ 25፡፡ 47፡5፡፡ ዕብ.7.1፡፡)

## 5. ተመክንዮታዊ ኅሠሣ፣

ምክንያቱ ያልተገለጠ ድርጊት ሲገኝ መተርጐማኑ ምክንያቱን ለመግለጥ "ለምን...?" የሚል ጥያቄ ያቀርቡና የተለያዩ ኅሠሣዎችን ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ በኦሪት ዘፀአት 2.5 እና የሐዋ.ሥ.7.21 "የፈርዖን ልጅ ተርሙት ወደ ባሕር ለምን ወርዳ ሙሴን አገኘችው ቢሉ?" በማለት ከጠየቁ በኋላ አራት ኅሠሣዎችን ያቀርባሉ፡-

ሀ. ኮብሽ የሚባል ደዌ ስለነበረባት ለመታጠብ፣
ለ. ዓሣ አንበሪ፣ አዞ ጉማሬ ታመልክ ነበርና ለማሚረት፣
ሐ. ነጋዴ ወዳጅ ነበራትና ለመገናኘት፣
መ. ለመዋኘት ሄዳ አግኝታዋለች፡፡

እንደዚሁም በመጽሐፈ ጥበብ 7.8 "የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት ሆና ቆመች" ይላል፡፡ መተርጉማኑ "እግዚአብሔር ለምን የጨው ሐውልት አደረጋት?" ብለው በመጠየቅ ሦስት ምክንያቶችን ያቀርባሉ፡፡ ሐዋርያው ናትናኤል በበለስ ስር ተቀምጦ ስለመታየቱም በተመሳሳይ ኅሠሣ አምስት ምክንያቶች ተሰጥተዋል፡፡ (ዮሐ.1፡48)፡፡

በዚህ ዐይነት ትርጓሜ ከተደረደሩት ምክንያቶች የትኛው ትክክለኛ እንደሆነ ለማወቅ ያስቸግራል፡፡ ምናልባት ማስረጃው ወይም ምንጩ አልተጠቀሰም እንጂ እያንዳንዱን ምክንያት የተለያዩ ሊቃውንት ተናግረው በኋላ አንድ አስተጋባኢ ሁሉንም ሰብስቦ በአንድነት ያስቀመጣቸው ይመስላል፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ ፊደላዊ ትርጉሙን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

## 6. የንባብና የምሥጢር ኅብረት

ይህ ዐይነቱ ስልት የሚያመለክተው የመጻሕፍትን በንባብና በምሥጢር መተባበር ነው፡፡ ለምሳሌ ማቴ.6፡11 "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፡፡" ከዚህ ንባብ በኋላ ቀጣዩ አብርሆት ይቀርባል፡፡ "በዚህም መጻሕፍት ተባብረዋል፡፡ ሀ/ ያዕቆብ በኦሪት (ዘፍ.28፡20-22፡፡) ለቅዱስ ጳውሎስ (1ጢሞ.6.8፡፡) ሐ. ሠለስቱ ምእት (ሃይ.አበ.ምዕ.21.1 ገጽ 58) መ. ማር ይስሐቅ ምዕ.12 ገጽ 21 ዐምድ 2፡፡ ይህንም የመሰለ ኅብረተ ንባብ ወምሥጢር ከሚከተሉት ጥቅሶች መመልከት ይቻላል፡፡ ሲራክ 5.13፡፡ መዝ.6፡5 ፡፡ ኤር.9.2፡፡ ሉቃ.12፡37፡፡ 2ጴጥ.3.2፡፡ ይህ ዐይነቱ ትርጓሜ ተዛማጅ ወይም ተጓዳኝ ጥቅስ ስለሚመስል ከፊደላዊና ታሪካዊ ትርጓሜ ይተባበራል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

### 7. ዕርቅ

ስለ አንድ ነገር በተለያዩ መጻሕፍትና በተለያዩ ሰዎች ወይም በአንድ ሰው በተለያየ አንቀጽ ላይ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ዐሳብ ያለ መስሎ ቢታይ መፍትሔው "ዕርቅ" ይባላል። "ከዚያ እንዲህ አለ፤ ከዚህም እንዲህ አለ፤ ይህ አይጣላምን? ተብሎ ይጠየቃል። ከዚያም "አይጣላም" የሚል መልስ ይሰጣል። በመቀጠልም የዕርቁ ነገር ይቀርባል። ሲራ.2.18። ሉቃ.2.21። 3.1። 9.28። የሐዋ.ሥ 22.9። 2ተሰ.2 :4። ራእ.11:2። ይህ ዐይነት ትርጓሜ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ ችግር ያለባቸውን ዘሮች ለፈታ ስለሚችል በተወሰኑ ንባቦች ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ተመሳሳይ ችግር ባለባቸው ንባባት ለደረግ የሚገባው የትርጓሜ ስልት መንገድ ነው።

### 8. ሐተታ

አንድ ዘርዕ ወይም ንባብ ተነብቦ ከተተረጐመ በኋላ በተጨማሪ በስፍሐትና በዝርዝር የሚደረገው አብርሆት "ሐተታ" ተብሎአል። ይህም የምርምር አንድምታ ትርጓሜ መንገድ ማለት ነው። ለምሳሌ፡- "ድንግል ሆይ ምድራዊ ኀብስትን የተመገብሽ አይደለም። በሰማያት የተጋገረ ሰማያዊ ኀብስትን እንጂ።

ሐተታ፡- "በሰማይ ስንዴ፣ አበዛና ምኅፃ ኑሮ አይደለም። በሰማያዊ መልአክ እጅ መምጣቱን ሲያይ እንዲህ አለ።" ቅዳ.ማር.5.3-4፤ ገጽ 241-242። ተጨማሪ ምሳሌዎች፡- ሮሜ.1:2። 1ቆሮ.7:12። ሮሜ .5:20። 2ቆሮ.5:1። ሥርዐተ ቅ.12:22 ገጽ 101።

### 9. አብነት

የተነበበውን የግእዝ ዘር በሌላ መልክ የሚተካ ዘርዕ ወይም ሌላ ንባብ ማለት ነው። ምሳሌ ፡- ማቴ 8:29 "እስመ ኮነ መኮንን ይሜህሮሙ። እንደ ንጉሥ ያስተምራቸው ነበርና። "እስመ ኮነ መኮንን ባለው ኮመ ዘሥልጣን ቦ" ይላል። አብነት። ተጨማሪ ምሳሌ ፡- መዝ.1:1። ቅዳ.ማር.5:58፤ ገጽ248።

### 10. ሥነ ቃል

ብሔራውያን ሊቃውንት የአንድምታ ትርጓሜን በአማርኛ ቋንቋ በሚያዘጋጁበት ጊዜ የትርጓሜ ሥራቸውን ግልጥና ብሩህ ለማድረግ ብዙ ብሔራዊ ዘዴን ተጠቅመዋል። መዝሙርና ቅኔን የዕለት ማስታወሻንም እንደተጠቀሙ ሁሉ በየዕለቱ በሕዝቡ ዘንድ የሚነገረውን ሥነ ቃል በትርጓሜያቸው በማስገባት ማብራርያ አድርገውታል።

ሥነ ቃል ለትርጓሜ ገላጭ ወይም ማብራርያ ከመሆኑም ሌላ የአንድምታውን ትርጓሜ ጥንተ ዘመን ያመለክታል። በተጨማሪም የአንድምታ ትርጓሜ በ?ትመት እስከወጣ ድረስ ሊቃውንቱ በየጊዜው በአንድምታው ትርጓሜ ላይ አዲስ ዐሳብ በመጨመር ማብራርያ ያደርጉ እንደነበር ያሳያል።

በአንድምታ ትርጓሜ ውስጥ በብዛት የሚነገረው ሥነ ቃል የአማርኛ አንድምታ በቅርጸቱና በይዘቱ ፍጹም ብሔራዊ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው።

ሥነ ቃል በሁሉም ብሔረ ሰብእ ዘንድ ያለ ሲሆን በአንድምታ ውስጥ የተጠቀሰው ሥነ ቃል በተወሰኑ አካባቢዎች የሚነገር ከመሆኑም ሌላ የአንድምታ ተርጓሚዎችን ስፍራ ይገልጣል። የሁሉቱ ትምህርት ቤቶች (ላይ ቤትና ታች ቤት) መምህራን ሁሉ ሥነ ቃልን ይጠቀሙ እንደነበር በሁሉም አንድምታ ውስጥ ይገኛል። ይኸውም በአራቱ የአንድምታ መጻሕፍት ሁሉ ውስጥ ነው።

ከሚጠቀሱት ሥነ ቃላት ጥቂቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ምእመናን "በቃል ያለ ይረሳል፣ በመጽሐፍ ያለ ይወረሳልና፡፡" ጻፍልን ስላሉት ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌሉን ጻፈላቸው። (የቅዱስ ወንጌል መግቢያ ታሪክ ገጽ 50)



- ኦርፍ የተባለችው የኑኃሚን ምራት "ከሞተ አቴቴ ምን አለኝ ከአማቴ" ብላ ከአማትዋ ከኑኃሚን ተለይታ ቀረች።
- ለሩት ዋርሳ መሆን የሚገባው ሰው "ከሁለት ዛፍ ያረፈች ወፍ ሁለት ክንፏን ትነደፍ፡፡" እንዲሉ ሁለት ቤተሰብ ማስተዳደር አልችልም ብሎ ዋርሳነቱን ተወ። (ማቴ 1:5)
- የጌታ ሥጋዊ ሐረገ ትውልድ በሦስት ክፍለ ዘመን ተመድቦ መጻፉ እንደ ሦስት ምስክር ነው። "ልማ በሥሉስ ጥፋ በሥሉስ፡፡" እንዲሉ። (ማቴ 1:17)
- የገደለ ይፈረድበታል እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቈጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። ኦሪትንም ወንጌልንም የሠራ እርሱ አይደለምን? ለምን እንዲህ አለ? ቢሉ ጌታ ሁን፣ እንደአሻህ ሁን" እንዲሉ ነው። (ማቴ.5:22)
- የእንጦጦ መምህር ቢናገር በዓመት፣ ያውም እሬት" (ውዳ.ማር.4:3)

ተጨማሪ ማስረጃዎች፡- ማቴ.12:38፤ ማቴ.20:22። ማቴ.24:34፤ ማቴ.25:33፤ 1ሳሙ.8:21፤ ዕብ.11 :20፤ ቅዳ.ማር.1:1፣ገጽ 413። ሉቃ.1:37። ወዘተ...።

### 11. ትች

ብዙ ጊዜ ትች የአነጋገር ነው። ምሥጢሩም አጽንዖታ ቃል ነው። ምሳሌ ዮሐ.4:2 "ወእግዚእነሰ ኢያጥመቀ፡፡ ጌታችን ግን አላ--ጠመቀም፡፡" ተጨማሪ ማስረጃ ቅዳሴ ማርያም ምዕ.6 ቁ.21 ገጽ 253 ወዘተ።

### 12. አንድ ወገን

በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን አንድ ወገን አድርጎ መተርጐም ነው። ኢሳ.53:1፤ 54:1። 1ቆሮ.9:18።

### 13. ማስጠበቅ ወይም ማቈየት

የተነበበውን ለጊዜው ማቈየትና በመሥጢር ሊቀድም የሚገባውን በፊት መተርጐም ነው። በመቀጠል የቈየውን ንባብ መተርጐም ነው። 2ቆሮ.1:15-16። ፍት.ነገ. አንቀጽ 2፣ ውዳ.19

# ክፍል 12

## የአንድምታ ትርጓሜ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ግእዝና የግእዝ ቅኔም በሚገባ ያወቁ ደቀመዛሙርት ወደ አንድምታ ትርጓሜ ቤት ይገባሉ። አብዛኛውን ጊዜ ደቀመዛመርቱ በወንጌል ወይም በመዝሙረ ዳዊት ወይም በውዳሴ ማርያም ይጀምራሉ። ነገር ግን ይህ ቀዋሚ ሕግ አይደለም። ትምህርቱ ሁልጊዜ በጥዋት ይሄዳል (ይሰጣል)። በጸሎት ይጀመራል። በጸሎትም ይፈጸማል።

መደበኛው ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ጉባኤ ማሄድ አለ። ጉባኤው ሦስት ዐይነት ነው። ይኸውም፡-

ሀ. ወንጌል፣
ለ. ግብር፣
ሐ/ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት እስከ ራእይ ነው።

ይህ የሐዲስ ኪዳን አንድምታ ትርጓሜ ብቻ በሚሰጥበት ት/ቤት ነው። የብሉይ ኪዳን አንድምታ ትርጓሜ ት/ቤት ግን ከመደበኛው ትምህርት በፊት አንድ ጉባኤ ይደርሳል። ይህም የመዝሙረ ዳዊት፣ የፀሥራ አምስቱ ነቢያትና የመሐልየ ሰሎሞን፣ የኢሳይያስ አንድምታ ትርጓሜ ነው። በሊቃውንትና በመጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ ቤት ግን ከጸሎት በኋላ በቀጥታ መደበኛው ትምህርት ይጀመራል።

www.ethiopianorthodox.org

መምህሩ በወንበር ወይም በመደብ ወይም ከፍ ባለ ነገር ላይ ይቀመጣል፡፡ ደቀመዛሙርቱ በዙርያው በመሬት ላይ አጎዛ አንጥፈው ይቀመጣሉ፡፡ ሁሉም ደቀመዛሙርት አንድ መጽሐፍ አይማሩም ሁለት ወይም ሦስት ወይም አራት ሆነው አንድ መጽሐፍ መማር ይጀምራሉ፡፡ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ መጽሐፉን በአትሮንስ ላይ ዘርግቶ በግእዝ ያነባል፡፡ መምህሩ ትርጓሜውን ያብራራል፡፡ ከዚያ በኋላ የመጀመሪያው ቡድን ደቀመዛሙርት ያዳመጡትን ለብቻቸው ሆነው ያጠናሉ፡፡ ሌላውም ቡድን በዚህ ዐይነት ይቀጥላል፡፡ አንድ ጉባኤ (ክፍለ ትምህርት) ሦስት ጊዜ በመምህሩ ይደጋገማል፡፡

የአንድምታ ትምህርት የሚሰጠው በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ነው፡፡ መምህሩ በቃል ይተረጉማል፤ ደቀመዛሙርትም በቃል ያጠናሉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፡-

- ደቀመዝሙሩ አንብቦአል እንጂ ተምሮአል ስለማይባል፣
- የአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት በመጀመሪያ ስላልተጻፉ፣
- አንዳንዴም መምህራኑ ማየት የተሳናቸው ስለሚሆኑ (እንደ መምህር ኤስድሮስ)
- ከዚህም ጋር ደቀመዝሙሩ በቃል በማጥናት ፈንታ ቢጽፍ ትርጓሜውን ሊያጠናው አይችልም ስለሚባል ነው፡፡ ዛሬም እንኳ ደቀመዝሙሩ ከመምህሩ እያዳመጠ በሚጽፍበት ጊዜ "ህየንተ ልቡ ኮኖ ወረቀቱ" ማለት ወረቀቱ በልቡ ፋንታ ሆነው" እየተባለ ነው፡፡ (መ/ገነት ገብረ ሥላሴ ዐወቀ)

ይሁን እንጂ ደቀመዝሙሩ በመጨረሻ የትርጓሜ ምልክት ሊጽፍ ይችላል፡፡ ምልክት ማለትም የግእዙን ዘርዕ በምሕዋር መጻፍ ለቀሪው ዘር አንድ ምልክት ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡-

1. በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ፡፡ የሚለውን ዘርዕ በአጭሩ "በቀዳሚ ሃ. ብሎ መጻፍ ነው፡፡ ሃ ሃድ አንብብ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ አንድምታው ይጻፋል፡፡
2. በቀዳሚ እ.ገ.ይ ወምድረ፡፡ ወምድረ እስከሚለው ድረስ አንብብ ማለት ነው፡፡ በመቀጠል የአንድምታው ትርጓሜ ይሰፍራል፡፡
3. ደቀመዝሙሩ የግእዝ መጽሐፍ ካለው በመጽሐፉ ግልየትና ሐውልት ላይ የአንድምታውን ትርጓሜ በምልክት ይጽፋል፡፡ ይህም ምልክት ነጥብ ነው፡፡ አንድምታው ሁለት ከሆነ ሁለት ".." ሦስት ከሆነ "..." አራትም ከሆነ "...." ዐሥር ከሆነ ዐሥር ነጥቦች ማስቀመጥ ነው፡፡ በነጥብም ፋንታ አጎዛ ማስቀመጥ የተለመደ ነው፡፡ አስቀድሞ የተተረከ ታሪክ፣ የታተተ ሐተታና የተጠቀሰ ጥቅስ ካለ እንዳለፈው ወይም አይለወጥም ተብሎ ይጻፋል፡፡ ይህ ሁሉ በወቅቱ የጽሕፈት መሣርያ ችግር ስለነበር ነው፡፡ ድካምንም ለመቀነስ ነው፡፡ ማንኛውም የአንድምታ ደቀመዝሙር ከቀደሙ አባቶች ሲወርድና ሲዋረድ የመጣውን የአንድምታ ትርጓሜ ቃል ሳይገድፍ ቅደም ተከተሉን ሳያዛንፍ ሳይጨምርና ሳያተርፍ በቃሉ አጥንቶ ምልክት ጽፎ ሲጨርስ ስመ ጥር ሊቅ ይባላል፡፡ የብሉዩ መጋቤ ብሉይ፣ የሐዲሱ መጋቤ ሐዲስ፣ የሊቃውንቱም ሊቀ ሊቃውንት ይባላል፡፡

የቅዱሳት መጻሕፍት አንድምታዊ ትርጓሜ ጎላፊና መጻኢ፣ እንደዚሁም የማያቋርጥ ወትራዊ እንደመሆኑ አይወሰንም፡፡ ሊቃውንት በየጊዜው እንደ ትንቢቱ ፍጻሜና እንደ ራእዩ ፍካሬ እንደ ምሳሌው አማናዊነት፣ እንደ ታሪኩ ባለቤት ትርጓሜን ሊጨምሩ፣ ዘይውን ሊፈጥሩ፣ በሁለትና በሦስት የታተውንም ከዚያ በላይ ሊያብራሩ ይችላሉ፡፡



ሆኖም የኢትዮጵያ ሊቃውንት በሁለት ሺሕ ዓመታት ውስጥ መጀመሪያ በግእዝ በግል፣ ሁለተኛ በአማርኛ በወል እንዴት እንዳዘጋጁ በዚህ ዐጭር ጽሑፍ በመጠኑ ለመግለጥ ተሞክሮአል፡፡

"እስከ ዝየ አብጽሐ ሉቃስ ሉቃስ እስከዚህ አደረሰ" ግብር 28:33 እንደተባለ የቀደሙን አባቶች የትምህርታቸው ጸጋ ይድረሰንና እስከ ሁለተኛው ሺሕ ዓመት መካተቻ ድረስ በቋንቋውና በስልቱ በቅርፀቱና በይዘቱ ፍጹም ብሔራዊ የሆነ የአንድምታ ትርጓሜን አድርሰዋል፡፡ ከሦስተኛው ሺሕ ዓመት መባቻ ጀምሮ ደግሞ እስከ መካተቻው ድረስ ደቂቅ ሊቃውንት እስከዛሬ የነበረውን ሊጠብቁ የጐደለ ቢኖር ሊመሉ፣ ያልተስተካከለም ቢኖር ሊያስተካክሉ እንደሚችሉ የትርጓሜው አንቀጽ ምንጊዜም ክፍት ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 9

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ታሪክ

ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ከመግለጻችን አስቀድሞ፤ ሀገረ እግዚአብሔር ስለሆነችው ኢትዮጵያ በመጠኑም ቢሆን ማውሳቱ አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም፡- « በስመ ኀዳሪ ይጼዋዕ ማኅደር፤ ወበስመ ማኅደር ይጼዋዕ ኀዳሪ» ተብሏልና ። ብሊሉም፤ በነዋሪው መኖሪያው፤ በመኖሪያውም ነዋሪው ይጠራል ማለት ሲሆን ፤ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት « ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ታነሳለች» በማለት የተነበየውን ትንቢት፤ የተናገረውን ትምህርት በጥልቀት ስንመረምር ልዑል እግዚአብሔር ከኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያም ከልዑል እግዚአብሔር እስከ ሕልቀተ ዓለም የማይነጣጠሉ መሆናቸውን የምናይበት ረቂቅ ምሥጢር ነው ። (መዝ. 67 . 31)

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሦስት ሺህ የበለጠ የነፃነት ዕድሜ የተቆ ጠረላት፤ በእርግጥም ሀገረ አምላክ ናት፤ በመሆኑም ሀገራዊ ባህል አላት፤ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንን መሠረት ያደረገ ከማንም ያልተከለሰና ያልተበረዘ ንጹህ እምነትና ሥርዓተ አምልኮት ያላት ሉዓላዊት ሀገር ናት። ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን እንደ ቅርጫ ሥጋ ሲቀራመቱ፤ እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን ነፃነቷንና አንድነቷን አክብራና አስከብራ የቆየችው፤ ለቅኝ ግዛትም አልመች ያለችው በሃይማኖቷና በነፃነት ታሪኳ እየተከሳከሰች ስለቆየችና ስለኖረች ለሌሎች አፍሪካውያን የነፃነት ምሳሌ ሆና ኖራለች። ሀገራችን ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ጠላት በየምዕት ዓመታቱ የተለያየ ችግርና ፈተና ቢገጥማትም የእምነትን ጋሻ አንግባ ፤ ሲወጋ እንጂ ሲወረወር የማይታየውን የጸሎት ጋሻ (እቡነ ዘበሰማያትን) ገትራ (ወድራ) የደረሰባትን ፈተና ሁሉ በትዕግስት አልፋ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምጋና ይድረስውና የሦስት ሺህ ዓመት ነፃነትን ፤ የሁለት ሺህ ዓመት ክርስትናን ለማሰብና ለማዘከር በመብቃቷ « ስብሐት ለእግዚአብሔር፤ ለዘአብጽሐነ እስከዛቲ ሰዓት» የሚለውን ስብሐተ እግዚአብሔር በማድረስ ነው ።

## ክፍል 1

### ቅድስና

ቅድስና በምንልበት ጊዜ ቅድስናን በሁለት ክፍሎ ማየት ተገቢ ይሆናል፤ ይኸውም፡-

ሀ. የባሕርይ ቅድስና ፤

ለ. የጸጋ ቅድስና ማለት ሲሆን የባሕርይ ቅድስና በምንልበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ብቻ የምንገልጸው ልዩ አገላለጽ ነው ። የጸጋ ቅድስና በምንልበት ጊዜ ደግሞ ለማያውቋን መላእክትና ምድራውያን ሰዎች ራሳቸውን ለቅድስና አዘጋጅተው ሲገኙ ቅድስናውን የሚያገኙት የቅድስና ባለቤት ከሆነው ከእግዚአብሔር የሚገኝ ልዩ ስጦታ ነው። በተለይ ምድራውያን ሰዎች በሃይማኖት ጸንተው፤ በበጎ ሥራ ተቃኝተው በቅን ልቡና እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ቅዱሳን ይሆናሉ፤ ቅዱሳንም ይባላሉ ። «እኔ አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ተብሏልና። (ዘሌ. 19 . 2)

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን በምንልበትም ጊዜ ብሔራውያን ቅዱሳንንና ከውጪ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ያበረከቱትን ከፍተኛ መንፈሳዊ አገልግሎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅድስናን ሰጥታ፤ በየስማቸው ቤተ ክርስቲያን አንጻ፤ ጽላት ቀርጻ፤ ገጾም ገድማ ያከበረቻቸውና የምታስከብራቸው ቅዱሳን በርካታዎች ሲሆኑ በዚህ ጽሑፍ አጠቃሎ መግለጽ ባይቻልም ለግንዛቤ ያህል የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቅዱሳን በማለት በሁለት ዐበይት ክፍሎች ከፍሎ መግለጽ ይቻላል

ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው ሐዋርያዊ አገልግሎታቸውን ፈጽመው ዘለዓለማዊ ዕረፍታቸውን በኢትዮጵያ ምድር በማድረጋቸው ብሔረ ሙላዳቸውን ለመግለጽ ያህል ታስቦ የተገለጸ ጽሑፍ መሆኑ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል።





የኢትዮጵያን የሁለት ሺህ ዘመን ቅዱሳን ታሪክ በዚህ ጽሑፍ አምልቶና አስፍቶ መግለጽ ባይቻልም ዝርዝር ታሪኩን ለታሪክ ጸሐፊች በመተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አስኝታ የሆኑትን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ዓበይት መምህራንን፤ እንደዚሁም በቤተ ክርስቲያናችን ስም በየአረፍተ ዘመናቱ መላ ሕይወታቸውን የሰው ዘር የሆነውን ሁሉ በሥራና በጸሎት በማገልገል ፤ እግዚአብሔርን በማመስገን ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡትንና እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነውን ገድል የፈጸሙትን ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን የጸታ ልዩነትን ሳታደርግ በገድላቸው ጽናትና በቱሩፋታቸው ብዛት «በውዕ እና ብዕዕት፤ ቅዱስና ቅድስት» ሊያሰኝ ከሚችል የብዕዕናና ቅድስና ማዕረግ የደረሱ መሆናቸውን በማረጋገጥና በስማቸውም ቤተ ክርስቲያን እንዲታነጽ፤ ገዳም እንዲገደም፤ ደብር እንዲደበር ፤ ገድልና ድርሳን እንዲጻፍላቸው፤ ወርኃዊና ዐመታዊ በዓላቸው እንዲታሰብና እንዲዘከር በማድረግ በቅዱስነት ያወቀቻቸውንና ያላወቀቻቸውን ኢትዮጵያውያንና ብሔረ ሙላዳቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆኑትን ቅዱሳንና ቅዱሳትን ስም ዝርዝር በከፊልም ቢሆን እንደሚከተለው ለመግለጽ እንሞክራለን።

## ክፍል 2

### ኢትዮጵያውያን ቅዱሳንና ቅዱሳት

1. ሕጽዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ፡-

ክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ወይም ኢትዮጵያና የክርስትና ሃይማኖት የተዋወቁት ሐዋርያው ቅዱስ ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት 8 . 26-40 ላይ እንደመዘገበው ጃንደረባው እንደ ብሉይ ኪዳኑ ሥርዓት ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ሥርዓተ አምልኮትን ፈጽሞ በፍኖተ ጋዛ ሐዋርያው ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ባጠመቀው ጊዜ ነው ። ዘመኑም ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ 34 ዓ.ም. ነው። «የቤተ ክርስቲያን አባት» እየተባለ የሚጠራው አውሳብዮስም የወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስን ግብረ ሐዋርያት መሠረት አድርጎ «ሕጽው ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆነ የኢትዮጵያ ሐዋርያ እሱ ነው » በማለት ጽፎአል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ገጽ 18 ላይ ይመለከቷል።

2. ቅዱሳን ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ

www.ethiopianorthodox.org

አብርሃና አጽብሐ የተሰኙት ቅዱሳን ነገሥታት (ወንድማማች) እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን ፍጹም በሆነ ስምምነት ለ15 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን በጋራ ከአስተዳደሩ በኋላ እንደ አበው ሐዋርያት እጣ ተጣጥለው አብርሃ በአክሱም፣ አጽብሐ በሸዋ መናገሻ ከተማውን ኤረር በማድረግ መንበረ መንግሥታቸውን ዘርግተው እየተመካከሩ ኢትዮጵያን በማስተዳደራቸው፣ ለሃገሪቱና ለቤተ ክርስቲያን ያደረጉትን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሁለቱ ወንድማማች ነገሥታት የቅድስና ማዕረግ ሰጥታቸዋለች፡፡ በስማቸውም ቤተ ክርስቲያን አንጾለች፡፡ ወርሐዊና ዓመታዊ በዓላቸውንም በየዓመቱ ጥቅምት 4 ቀን እንዲታሰብና እንዲከበርም አድርጋለች፡፡ (ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ ከመምህር ኃይለ ሥላሴ ዓለማለሁ 1989 ዓ.ም. አዲስ አበባ)

### 3. አፄ ካሌብ

ከአብርሃና አጽብሐ ቀጥሎ ከተነሡት ቅዱሳን ነገሥታት ክርስትናን በማስፋፋትና በመንከባከብ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረጉት (ከ485 - 515 ዓ.ም.) የነበሩት አፄ ካሌብ ናቸው፡፡ አፄ ካሌብ ስለ ክርስትና መስፋፋት፣ ስለ ክርስቲያኖች አንድነት ብዙ ተጋድሎን ከተጋደሉ፣ ከአሳለፉ በኋላ መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለአፄ ገብረ መስቀል አስረክበው፣ መንነው ልብሰ ምንኩስናን ለብሰው ከአክሱም ወደ ሰሜነ ምሥራቅ በሚገኘው በአባ ጳንጠሌን ገዳም በሚገኘው ዋሻ የምናኔ ሥራቸውን ቀጥለዋል ፡፡ ከዚህም ጋር ቤተ መንግሥታቸውን ለቀው በመነኑበት ሰዓት እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነውን ማለትም የነገሡበትን ዘውድ ወደ ጌታ መቃብር ጎልጎታ ልከው በምናኔ 12 ዓመታት ከተጋደሉ በኋላ በ 536 ዓ.ም. ግንቦት 20 ቀን አርፈዋል ፡፡ አፄ ካሌብ በምንኩስናና በምናኔ ሕይወት የቅዱሳንን አሰረ ጽድቅ ፈጽመው ያለፉ ደገኛ ንጉሥ ስለነበሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖዎራቸው ከቅዱሳን ነው፡፡ ( የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ 1974 ዓ.ም.)

### 4. አባ ዮሐኒ

አባ ዮሐኒ ብሔረ መላዳቸው በክልል ትግራይ፣ በተንቤን ፣ልዩ ስሙ ሀገረ ሰላም ከተባለው ቀበሌ ሲሆን የነበሩበትም ዘመን በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ በቆላ ተንቤን ደብረ አንግሃ (ዓሣ) ከተባለው በረሃ በጾምና በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ከነበሩት ከአባ አሞኒ ጋር እንደ ኖሩ፣ እድገታቸውም በእናት ጡት ሳይሆን ቱራ እያጠባቸ እንዳሳደጋቸው በገድለ አቡነ ዮሐኒ ተመዝግቧል፡፡ ገዳማቸውም ደብረ አንግሃ (ዓሣ) ተብሎ የተሰየመ ሲሆን ወርሐዊና ዓመታዊ በዓላቸውም ጎዳር 5 ቀን ይታሰባል፡፡

(ምንጭ ፡- 1. የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ከዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣
2. Journal Of Ethiopian Studies. Vol. 13 No.2 July 1975.) ከዶ/ር ክነፈርግብ ዘሰቀ

### 5. ቅዱስ ያሬድ

ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ505 ዓ.ም. የተነሣ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ነው፡፡ቅዱስ ያሬድ በዓለም በሚታወቅበት ሙያውና ዕውቀቱ በመንፈስ ቅዱስ የተታኘ የመንፈሳዊ ዜማ ደራሲ፣ የቅኔ ተመራማሪ ፣ ኪሩቤልን በሚያስመስለው ጣዕመ ዝማሬ የተወደደና ድምፀ መልካም ማሕሌታዊ ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድ ድጓ፣ ዝማሬ መዋሥዕትና ምዕራፍ የተሰኙ የዜማ መጻሕፍት አሉት፣ የብሉያት የሐዲሳትና የሊቃውንት መጻሕፍት ትርጓሜም ሊቅ ነው፡፡ ከእነዚህ ከብሉያት ከሐዲሳትና ከሊቃውንት መጻሕፍት ለጸሎትና ለማሕሌት የሚስማሙትን ቃላት እየመረጠ ምሥጢራትን ከትርጓሜ እያስማማ ዜማቸን በዐራቱ ክፍላተ ዘመን በመፀው፣ በሐጋይ፣ በጸደይና በክረምት በመክፈል የየወቅቱን የተፈጥሮ ሥነ ባሕርይ በአንክሮና በምሥ ጋና በሚገልጽ ጣዕም እንዲዘመሩና እንዲጸለዩ ያደረገ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ነው፡፡ ዜማውንም ግእዝ፣ ዕዝልና አራራይ በሚል በሦስት የዜማ ስልት ከፍሎ ዘምሮታል፡፡ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቱን ያዘጋጀው ከ 540 - 560 ዓ.ም. ባለው ዘመን ነው፡፡ ማሕሌታዊው ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያ ሰማናዊ ክፍሎች ለ11 ዓመታት እየተዘዋወረ ሲያስተምር፣ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግልና ሲያስገለግል ቆይቷል፡፡





በመጨረሻም በሰሜን ተራራዎች ሥር ካሉት ገዳማት በአንዱ ዋሻ ውስጥ ገብቶ በጾም፣ በጸሎት፣ በብሕትውና ዘመኑን አሳልፎአል ፡፡ ሊቁ ቅዱስ ያሬድ እስከ ዛሬ ጎልፈትና ውላጤ ያላገኘው በጣዕመ ዝማሬውና በምልክቱ ልዩ የሆነ የዜማ ድርሰቱን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያበረከተ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ሊቅ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዝክረ ስሙን በጥንቃቄ ጠብቃ፣ በስሙ ጽላት ቀርፃ፣ ቤተ ክርስቲያንን አንፃ፣ ገድሉን ጽፋ፣ በዓለ ዕረፍቱንም በየዓመቱ ግንቦት 11 ቀን ታከብራለች ፡፡



(ምንጭ፡- The Ethiopian Orthodox tewahedo Church Faith, order of worship and Ecumenical relations July 1996.)

### 6. ሀ. ቅድስ ይምርሃነ ክርስቶስ
ለ. ቅድስ ሐርቤ (ገ/ማርያም)
ሐ. ቅዱስ ላሊበላ
መ. ቅድስ ነአኩቶለአብ

እነዚህ ቅዱሳን፡- የነበሩበት ዘመን ከ11ኛው እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን ምስፍናን ከክህነት፣ ክህነትን ከምስፍና ጋር አስተባብረው በመያዝ ለክርስትና መስፋፋት፣ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት፣ ለአገር አንድነት የከፈሉት መሥዋዕትነት፣ ያቆዩት መንፈሳዊ ቅርስ በዐይን የሚታይ፣ በእጅ የሚዳሰስ ከመሆኑም በላይ ለሀገር ኢኮኖሚ የደም ሥርና የጀርባ አጥንት ሆነው የሚታዩት ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ሕያው ምስክሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም እናት ቤተ ክርስቲያን ከላይ ስማቸው ለተጠቀሰው መንፈሳዊያን ነገሥታት የቅድስና ማዕረግ ሰጥታ፣ ገድላቸውን ጽፋ፣ ለትውልደ ትውልድ አቆይታለች፡፡

(ምንጭ)፡- 1. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ መስከረም 1990 ዓ.ም.
2. ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፡ሐሴ 1978 ዓ.ም.
3. የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ከዶ/ር ሥርጌ ሐብለ ሥላሴ 1981 ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

## 7. አቡነ ኢየሱስ ሞአ

የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ብሔረ ሙላድ በአማራ ክልል፣ በጎንደር ጎርጎራ አካባቢ ልዩ ስሙ ዳህና ከሚባለው ቦታ፣ ፈረሃ እግዚአብሔር ከነበራቸው፣ በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው ከኖሩት ከአባታቸው ዘክርስቶስና ከእናታቸው ከእግዚእ ክብራ ግንቦት 26 ቀን 1196 ዓ.ም. የተወለዱ፤ ዕድሜያቸው ለትምሕርት በደረሰ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አጠናቀው ብሉያትንና ሐዲሳትን የተማሩ፤ ዕድሜያቸው 30 ዓመት ሲሞላ በገዳመ ደብረ ዳሞ ምንኩስናን የተቀበሉ፤ በስማቸው የሚጠራውን የ ሐይቅ ገዳም የመሠረቱ፤ በቅድስናቸው እንደ ከዋክብ የሚያበሩ፤ በትምህርታቸውና በድርሰታቸው ቤተ ክርስቲያንን በዕንቁ ያስጌጡ፤ ምእመናንን ወደ ሕይወት የሚወስዱ ጽምአ ነፍስን የሚያረኩ፣ በሁለት ወገን እንደተሳለ ሰይፍ ቅድስናን ከሊቅነት ጋር የተላበሱ፣ የእልፍ አእላፋት ቅዱሳን ማለትም፡- እነ አባ በጸሎተ ሚካኤልን፤ እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን፤ እነ አቡነ ሐፍተ አምላክን፤ እነ አቡነ አሮንን፤ እነ አቡነ ገብረ ናዝራዊን፤ እነ አቡነ ሕዝቅያስን ፤ እነ አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስን ፤ እነ አቡነ ዮሴፍን ፤ እነ አቡነ ገብረ እንድርያስን ፤ በጸሎቱ፣ በድርሰቱ፣ በትምህርቱ ካልዕ ቂርሎስ፤ ካልዕ ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለውን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን እና የመሳለሉትን የክርስትና ፋና ወጊ የሆኑትን ቅዱሳን ሁሉ ያስገኘ የአቡነ ኢየሱስ ሞአ የአንድነት ገዳም እንደነበር ሕያው ምስክር ነው።

ቤተ ክርስቲያንም በስማቸው ቤተ ክርስቲያን አንጻ ፣ጽላት ቀርጻ፣ ሥራቸውንና ቅድስናቸውን አክብራ ታስከብራለች።

ምንጭ ፡- የሐይቅ ቅዱስ አስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ትናትና እና ዛሬ ጎዳር 8 ቀን 1994 ዓ.ም.

## 8. አቡነ ተክለ ሃይማኖት (ዘደብረ ሊባኖስ)

ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት «ቀደስኩክ አምከርሠ እምከ» ተብሎ እንደተመረጠው ነቢዩ ኤርምያስ በፈቃደ አምላክ ፣ በብሥራተ መልአክ መጋቢት 24 ቀን ተጸንሰው ታኅሣሥ 24 ቀን በ1197 ዓ.ም. በዘረፈ ደብረ ጽላልሽ ተወልደው በ3 ኛው ቀን «እመአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ» (መዝ 10:1) ተብሎ እንደተነገረው አሐዱ አብ ቅዱስ ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ ፣ አሐዱ ውስቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው ስመ ሥላሴን በተአምራት አመስነኑ፡-

በ40ኛው ቀን በጥምቀት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ፍሥሐ ጽዮን ተብለው ተሰይመዋል። ከብዙ ትምህርትና አገልግሎት በኋላ በአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ለ 10 ዓመታት፤ በሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ገዳም ለ 11 ዓመታት ያህል፤ በደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ ገዳም ለ17 ዓመታት ያህል አበውን በመርዳትና ተአምራትን በማድረግ ከቆዩ በኋላ ፣በ1267 ዓ.ም. የደብረ ሊባኖስን ገዳም መሥርተዋል። በተለይም በመላ ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ ወንጌልን ሰብከዋል፤ ጣዖታትን አጥፍተዋል፤ የወንጌልን ብርሃን አብርተዋል። በመጨረሻም ከሚያልፈው ዓለመ ሥጋ ወደማያልፈው ዓለመ ነፍስ ነሐሴ 24 ቀን 1297 ዓ.ም. ዐርፈዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በስማቸው ገድል ጽፋ፣ ገዳም ገድማ፣ ጽላት ቀርፃ፣ የቅድስናን ማዕረግ ሰጥታ ስታከብራቸው ትኖራለች።

ምንጭ ፡- የኢትዮጵያ ብርሃን ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ ከብፁዕ አቡነ ማቴስ 1993 ዓ.ም.)





## 9. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተወለዱት በደቡብ ወሎ ሀገረ ሰብከት ልዩ ስሙ ቦረና በተለይም ሽግላ በምትባል ቦታ በ1358 ዓ.ም. ከአባታቸው ሕዝበጽዮን እና ከእናታቸው እምነ ጽዮን ተወለዱ። አባ ጊዮርጊስ ለአቅመ ትምህርት ሲደርሱ አባታቸው ሐይቅ እስጢፋኖስ ወደሚባለው ገዳም ወስደው፣ አባ ሰረቀ ብርሃን ለሚባሉ መምህር ሰጧቸው፤ አባ ጊዮርጊስ የቅዱስ ያሬድን ትምህርት በጥልቀት ከሚያውቁት ሊቃውንት አንዱ ናቸው ። የቅኔ ሰውም ነበሩ ። የአባ ጊዮርጊስን ሊቅነትና ጥበብ ለማረጋገጥ መጽሐፈ ሰዓታት የተባውን መጽሐፋቸውን መገንዘቡ በቂ ነው። አባ ጊዮርጊስ፣ አመስግነው በቃኝ የማይሉ ፣ ሲቀመጡ፣ ሲነሱ፣ ሲጓዙ ከማመስገን፣ አንደበታቸው የማያርፍ፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጸሎት፣ የትምህርት እና የእምነት መሠረት የሆኑትን፡-

1. መጽሐፈ አርጋኖንን፣
2. » ምስጢርን፣
3. » ሰዓታትን፣
4. » እንዚራ ስብሐትን፣
5. » ሕይወተ ማርያምን፣
6. ውዳሴ መስቀልን ፣
7. ተአምኖ ቅዱሳንን፣
8. ክብረ ቅዱሳንን፣
9. ጸሎት ዘበአተ ቤትን
10. ጸሎተ ማዕድን፣
11. መኣዛ ቅዳሴን፣
12. ኖኅተ ብርሃንን፣
13. ፍካሬ ሐዋርያትን፣
14. ውዳሴ ሐዋርያትን፣
15. ውዳሴ ስብሐትን፣
16. የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት፣ የመላእ ክትና የሊቃነ መላእትን ውዳሴ (ሰላምታ) የተባሉትን መጻሕፍት ደርሰው ያበረከቱ ኢትዮጵያዊ ሊቅና ጻድቅ ናቸው።

አባ ጊዮርጊስ ከብዙ መንፈሳዊ አገልግሎት በኋላ በ60 ዓመታቸው በ 1458 ዓ.ም. ሰኔ 7 ቀን በዕለተ እሑድ አርፈው አጽማቸውም በጋስጫ ገዳም (ደቡብ ወሎ) አርፏል። በዘመኑ የነበሩት የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ይሥሐቅ «ኢትዮጵያዊው ቂርሎስ አምደ ሃይማኖት» በማለት ስመ ቅጽል እንደ ሰጧቸው በታሪክ ተመዝግቧል። ቤተ ክርስቲያናችንም የቅድስናን ማዕረግ ሰጥታ፣ ቤተ ክርስቲያንን አንጻ፣ ገዳም ገድማ፣ በዓለ ዕረፍታቸውን በየወ ሩና በየዓመቱ ሰኔ 7 ቀን ታከብራለች።

(ምንጭ፡- ማዕደት መጽሔት ጥር 11 ቀን 1977 ዓ.ም. ቁጥር 16 ከመ/ብርሃናት ተስፋ ወርቅነህ)



www.ethiopianorthodox.org

## 10. ሳሙኤል ዘዋልድባ

የሳሙኤል ዘዋልዳባ፣ አባታቸው እስጢፋኖስ፣ እናታቸው ዓመተ ማርያም ይባላሉ። የተወለዱትም በ1289 ዓ.ም. በአክሱም ሲሆን፣ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ትምህርት ቤት ገብተው በጥቅሉ ብሉያትንና ሐዲሳትን፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተምረዋል። በብቃታቸውና በደግነታቸው፣ በትምህርታቸውም ከታወቁት ከታላቁ መምህር ከአቡነ መድኃኔነ እግዚእ ዘደብረ በንኰል ምንኩስናን መቀበላቸውን መጽሐፈ ገድላቸው ይተርካል። አቡነ ሳሙኤል ምንኩስናን ከተቀበሉ በኋላ ከአክሱም ወደ ማን-እንዳባ ከተባለው ገዳም ገብተው አገልግለዋል። በኋላም ከማን-እንዳባ ገዳም ወጥተው ለረጅም ጊዜ ወደተቀመጠበት፣ ብዙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆችን ወደ አፈሩበት፣ ታላቅ ክብርና ምሥጋና ወደአገኙበት፣ ታቦት እስኪቀረጽላቸ፣ ገድል እስኪጻ ፍላቸው ድረስ ብዙ ትሩፋትን ወደ ሠሩበት፣ በመጨረሻም ዕረፍታቸውና መቃብራቸው ወደሆነበት ወደ ገዳመ ዋሊ ገብተዋል አቡነ ሳሙኤል በአቡነ መድኃኔነ እግዚእ እጅ ምንኩስናን በተቀበሉበት ቀን ሰባቱ የኢትዮጵያ ከዋክብት ተብለው የተሰየሙት ስመ ጥሩቹ መነኮሳት፡-

1. ሳሙኤል ዘዋልድባ፣
2. ሳሙኤል ዘቆየጻ ፣
3. ሳሙኤል ዘጣሬጣ፣
4. ዮሐንስ ዘጉራንቋ ፣
5. ታዴዎስ ዘባልታርዋ፣
6. አባ ያስዮን ዘማን - እንዳባ ፣
7. ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤ፣ በመባል የሚታወቁት ናቸው።

አባ ሳሙኤል፣ በዋልድባ ገዳም ተቆጥሮ የማያልቅ ብዙ መንፈሳዊ ትሩፋትን ከሠሩ በኋላ ዕረፍታቸው ሲደርስ፣ ከፈጣሪያቸው ጋር በጸሎት ተገናኝተው፣ ብዙ የምሕረት ቃል ኪዳን ተቀብለዋል። ከዚያ ለገዳሙ አበምኔት የሚሆን በመነኮሳቱ ድምጽ አስመርጠው በአርሳቸው እግር ከተኩ በኋላ የዋልድባን መነኮሳት በሙሉ አሰባስበው ቡራኬና አባታዊ ምክር ሰጥተው በተወለዱ በሠባ ዓመታቸው፣ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታኅሣሥ 12 ቀን በእሄ ይሥሐቅ ዘመነ መንግሥት አርፈው ብዙ መንፈሳዊ ትሩፋት በሠሩበት በዋልድባ ገዳም ተቀብረዋል።

አባ ሳሙኤል በሞቱ በ 40ኛው ቀን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በፈቃደ እግዚአብሔር ከመቃብራቸው ዘንድ መጥተው ከጸለዩ በኋላ « ሳሙ ኤል ዘገዳመ ዋሊ፣ መነኮስ ፍጹም፣ ምዑዝ ምንኩስናሁ፣ ንጹሕ ድንግልናሁ ፣ አካለ አንበሳ ግሩመ ይሜጥን በእዴሁ» እያሉ በስማቸው ድርሰት ደርሰ ውላቸዋል።





በዚህ ስም ማለትም በተመሳሳይ ስም ይጠሩ የነበሩ የኢትዮጵያ ቅዱሳን፡-

1. አቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ሃሌሉያ
2. አቡነ ሳሙኤል ዘቆየጻ
3. አቡነ ሳሙኤል ዘጣሬጣ
4. አቡነ ሳሙኤል ዘወገግ
5. አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ የተሰኙት ቅዱሳን እንደነበሩ ማስታወስ አስፈላጊ ይሆናል።

(ምንጭ ፡- 1. የዋልድባ ገዳም ታሪክ ከበረውን ከበደ አዲስ አበበ ጥቅምት 21 ቀን 1983 ዓ.ም.
2. ባሕታዊያን በዋልድባ ገዳም ከትሳንት እስከ ዛሬ ከቆሞስ አባ ተክስተ ብርሃን ወልደ ሳሙኤል (ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል) 1997 ዓ.ም. አ)

## 11. አባ ገብረ ናዝራዊ

አባ ገብረ ናዝራዊ በ15ኛው ክፈለ ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ብላ ሰይማ መታሰቢያቸውንም ብየወሩና በየዓመቱ ጥር 29 ቀን እንደምታከብርላቸው ስለ እሳቸው የተጻ ፈው መጽሐፈ ስንክሳር በዋቢነት ይጠቀሳል ። መጽሐፈ ስንክሳሩ «ሰላም ለገብረ ናዝራዊ እንተ ነጸረ ወርእየ፣ ለእግዚአብሔር ገሃደ ስብሐተ ገጹ ውስተ ። በላዕለ ምጥማቃትኒ ሶበ ውእቱ ጸለየ ።እምሳለ መብረቅ ሰጢቆ ሰማየ፣ ብርሃነ ጸጋ ወረደ ከመይቀድስ ማየ።» ተብሎ ተደርሶላቸዋል።

ምንጭ ፡- 1. መጽሐፈ ስንክሳር ጥር 29 ቀን፣
2. የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ሚያዚያ 1982 ከዶ/ር ሥርግው ሐብለሥላሴ፣
3. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትላትናና ዛሬ መስከረም 1990 ዓ.ም. አዲስ አበባ
4. ባሕታውያን በዋደብ ገዳም ከትናንት እስከ ዛሬ ከቆሞስ አባ ተክስተ ወ/ሳሙኤል (ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል)

## 12. አቡነ ሐራ ድንግል

አቡነ ሐራ ድንግል፣ በደቡብ ጎንደር ከአባታቸው ከቁስ ገበዝ ዮሐንስ እና ከእናታቸው ከወለተ ጊዮርጊስ ጥቅምት 19 ቀን 1540 ዓ.ም. ተወለዱ። አቡነ ሐራ ድንግል ከንባብ እስከ ከፍተኛው መንፈሳዊ ትምህርት በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ተምረዋል። በዚሁ ገዳም ማዕረገ ምንኩስናን ተቀብለው ከጎኃም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጥተው አያሌ የምነና ሥራ ሠርተዋል። በኋላም ከደብረ ሊባኖስ ወደ ትውልድ ቦታቸው ተመልሰው በደቡብ ጎንደር፣ በፎገራ ወረዳ ደራ ከተባለው አካባቢ ቀስቀርያ በተባለች ኮረብታማ ቦታ በስማቸው የሚጠራውን ገዳም መሥርተዋል።አቡነ ሐራ ድንግል በመሠረቱት ገዳም ያለሙትን አትክልት ከየአቅጣጫው ለሚመጡ ምእ መናን እና በተለይም ችግርኞችን ይረዱ ነበር። በገዳሙ ውስጥ ባለችው የውኃ ምንጭ የተለያዩ ህሙማንን እያጠመቁና መዝገበ ጠበሉን እያጠጡ ልዩ ልዩ ደዌ ያለባቸውን ሕሙማን ይፈውሱ ነበር። አቡነ ሐራ ድንግል ሀብተ ፈውስ የተሰጣቸው ቅዱስ ሲሆኑ ብዙ መንፈሳዊ ሥራ ከሠሩና ብዙ ተጋድሎን ከተጋደሉ በኋላ ጥር 21 ቀን 1625 ዓ.ም. በ85 ዓመታቸው አርፈዋል። ቤተ ክርስቲያንም በስማቸው ጽላት ቀርጻ፣ ቤተ ክርስቲያን አንጻ፣ ገዳም መሥርታ፣ ገድላቸውን አጽፋ፣ አክብራ አስከብራቸዋለች።

(ምንጭ ፡- ገድለ አቡነ ሐራ ድንግል ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1997 ዓ.ም. አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org

## 13. አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ

በገድላቸውና በትሩፋታቸው የታወቁት ጻድቁ አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ የተወለዱት በዋድላ ደላንታ ዳውንት ልዩ ስሙ አስጋጅ ደብረ ሲና በተባለው ቦታ ነው ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ከተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው ከተማሩ በኋላ በሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ገዳም ሥርዓተ መንኩስናን ተቀብለው ለ11 ዓመታት ያህል ገዳሙን ካገለገሉ በኋላ «ወበጽሐ አድያመ ሼዋ ወመሐረ በህየ» ተብሎ በገድላቸው እንደተጻፈው የክርስቶስን ቸርነቱንና ሕግጋቱን የምትናገር ወንጌልን እየተዘዋወሩ አስተምረዋል፡፡ በዝቋላ ገዳም 40 ቀን በጾምና በጸሎት እንዲሁም በስግደት ቆይተው በአካባቢው ብዙ ምእመናንን ወደ ክርስትና መልሰዋል፡፡ ወንጌልን እየተዘዋወሩ አስተምረው ሚያዚያ 9 ቀን በዕለተ ዓርብ በአድያምሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት በ89 ዓመት ዕድሜያቸው አርፈው ብዙ ትሩፋት በሠሩበት በደብረ አሰጋጅ አርፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ቅድስናን ሰጥታ፤ በስማቸው ጽላት ቀርጻ ገዳም ገድማ ሲታሰቡና ሲዘከሩ እንዲኖሩ አድርጋለች፡፡

## 1.4. አባ ኂሩተ ክርስቶስ

አባ ኂሩተ አምላክ የነበሩበት ዘመን በ13ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ደቀ መዝሙር፤ የአፄ ይኩኖ አምላክ ወንድም፤ ቀጥራቸው ሰባቱ ከዋክብት ከተባሉት ከእነ አባ በትረ ማርያም፤ ከእነ አባ ያፍቅረነ እግዚእ፤ ከእነ አባ ታዴስ፤ ከእነ አባ ያስድ፤ ከእነ አባ ዘካርያስ፤ ከእነ አባ ዮሐንስ እንደነበር ታውቋል፡፡ ጻድቁ አባ ኂሩተ አምላክ ከሐይቅ የ አባ ኢየሱስ ሞአ ገዳም ብዙ ተጋድሎ ካደረጉ በኋላ ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ መጥተው ገዳሙን አቋቁመው መነነ ዕረፍታቸው በዚሁ ገዳም ነው፡፡ ይህ ገዳም የብዙቹ ቅዱሳን ነገሥታት የእነ አፄ ዳዊት፤ የእነ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ፤ የእነ አፄ በዕደ ማርያም፤ የእነ አፄ ሱስንዮስ፤ የእነ አፄ ፋሲል አጽም እንዳረፈ ተመዝግቧል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በስማቸው ጽላት ቀርጻ ገድል ጽፋ ቅድስናን ሰጥታ አክብራ አስከብራቸዋለች፡፡

(ምንጭ ፡- ማዕጾት ቍጥር 23 ሚያዚያ 1979 ዓ.ም. አዲስ አበባ) 15.

## 15. አቡነ ዜና ማርቆስ

አቡነ ዜና ማርቆስ በሰሜን ሸዋ በተጉለትና ሀረሬ ደብረ ጽላልሽ (ቡልጋ) አውራጃ ከታላቁ ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አጎት ከክህን ዘርአ ዮሐንስና ከእናታቸው ከቅድስት ማርያም ዘመዳ በ1262 ዓ.ም. ኅዳር 24 ቀን ተወለዱ፡፡ አቡነ ዜና ማርቆስ በአባታቸው ቤት ንባብና ዳዊት፤ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ እየተማሩ ካደጉ በኋላ በሀረሬ ደብረ ጽላልሽ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አገልግለዋል፡፡ በብሕትውና ሥራ ከቆዩ በኋላ አማራ ሳይንት ከነበሩት ከአቡነ ጌርሎስ ልብሰ ምንኩስናን ለብሰው የቅስና ማዕረግን ተቀብለው «ዜና ማርቆስ ሆይ! እንደ ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት በስብከትህና በትምህርትህ ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር አምነው ተጠምቀው ይድናሉ፤ የጣዖታትን ቤት ታፈርሳለህ፤ በመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትን ታንጻለህ፤ ኢትዮጵያ በሙሉ የቅድስና ሥራህን በታሪክ መዝገብ ትጽፍልሃለች» ብለው እንደባረኳቸው ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ሰባት ቤት ጉራጌ ሄደው ወንጌልን ሰብከዋል፡፡ ጣዖታትን አጥፍተዋል፤ ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቁምስናን ተቀብለው፤ አገር ከፍለው ሰጥተዋቸው፤ ትምህርተ ወንጌልን አዳርሰው ዛሬ ደብረ ብሥራት የተባለውን ገዳም ገድመው ለ130 ዘመን ቆይተው ታኅሣሥ 3 ቀን 1402 ዓ.ም. ደብረ ብሥራት ገዳም በክብር አርፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ቅድስናን ሰጥታ ጽላትን በስማቸው ቀርጻ ፤ ገድላቸውን ጽፋ አክብራ ታስከብራቸዋለች፡፡

(ምንጭ ፡- ማዕጾት ቍጥር 19 1978 ዓ.ም.)

## 16. አብርሃም ዘደብረ ጽዮን

የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ማለቂያ በ15ኛው ምዕት መጀመሪያ ላይ የኖሩ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ሲሆኑ በክልል ትግራይ ገረዓልታ ውስጥ ደብረ ጽዮን የሚባለውን ገዳም ያቋቋሙ ናቸው፡፡

(ምንጭ ፡- (Journal of Ethiopian studies , Vol.12 No. 2 1975 P.60 - 61)





## 17. አቡነ ፊሊጶስ

በኢትዮጵያ ፊልጶስ በሚል ስም የሚጠሩና በስማቸው ታቦት ተቀርጾላቸው፤ ቤተ ክርስቲያን ታንጾላቸው፤ በብዙ ቦታች የአንድነትን ገዳም ያቋቋሙ ብዙ ቅዱሳን አሉ፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከሾሙአቸው ከ 12ቱ ንዑራነአድ አንዱ አቡነ ፊልጶስ ሲሆኑ በጎንደር ክፍለ ሀገር ልዩ ስሙ ሰማዳ በመባል በሚታወቀው ቦታ ደብረ ዕንቁ የተባለው ገዳም የተመሠረተው በጻድቁ አቡነ ፊልጶስ ስም ነው ፡፡ የደብረ ቢዘኑን ገዳም የቆረቆሩት ደግሞ ከ1323-1406 ዓ.ም. የነበሩት አቡነ ፊልጶስ ናቸው፡፡ አቡነ ፊልጶስ የትውልድ ቦታቸው ክልል ትግራይ በተለይ አዲጉላገል በመባል በሚታወቀው መንደር ሲሆን አባታቸው ይርድአነ እግዚእ እናታቸው መግደላዊት ይባላሉ፡፡ አቡነ ፊልጶስ ወንጌል ሳልደረሳቸው አዳርሰው ደብረ ቢዘንን ገዳም አቋቁመው ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳንን ተቀብለው ነሐሴ 5 ቀን በ84 ዓመታቸው ከድካም ወደ ዕረፍት ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋግረዋል፡፡ በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ነሐሴ 5 ቀን በየዓመቱ ታስባቸዋለች በታላቅ ክብርም ታከብራቸዋለች፡፡

ምንጭ 1. ትንሣኤ መጽሔት ቍጥር 129 ነሐሴ 1980 ዓ.ም.
2. :- Journal of Ethiopian studies . Vol.13 No. 2

## 18. አቡነ ዮሴፍ ዘወለቃ

የጻድቁ አቡነ ዮሴፍ አባታቸው ዳግማዊ አፄ ዳዊት ሲሆኑ እናታቸው ጽዮን ሞገሳ ይባላሉ፡፡ የትምህርት አባታቸው አቡነ ዜና ማርቆስ ሲሆኑ የነበሩበትም ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በላስታ አውራጃ ግዳን ወረዳ ከሚባል ልዩ ቦታ በቅድስና ከታወቁት ከአባ ዘካርያስ ዘንድ የምንኩስናን ደንብና የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ተምረዋል፡፡ ወደ አክሱምና ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም በመሄድ ከቅዱሳን አበው በረከትን ተቀብለዋል ፡፡ ከዚያም በዋልድባ፤ በሰሜን ተራራ፤ በቅዱስ ያሬድ የጸሎት ቦታ፤ በጾምና በጸሎት ተወስነው ብዙ ዓመታን አሳልፈዋል፡፡ ወደ ደብረ ሲባኖስ ገዳም መጥተው ማዕረገ ምንኩስናን ተቀብለዋል፡፡ በመጨረሻም በአሁኑ ጊዜ በስማቸው ወደ ሚጠራው ቦታ መጥተው ብዙ መነኮሳትንና መናንያንን አሰባስበው የክርስትናን እምነትና የምንኩስናን ሥርዓት፤ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ በደንብ አስተምረው የአንድነት ገዳምን አቋቁመዋል፡፡ ለጸሎት ከቆሙባቸው ቦታዎች ሁሉ ጠበል ፈልቆላቸዋል፡፡ ጠበሉም እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ በሽተኞችን ሲፈውስ ይገኛል፡፡ ቦታውም በስማቸው አቡነ ዮሴፍ ተብሎ ይጠራል፡፡ ሌላው አስደናቂ ተአምር በገዳሙ ክልል የዝንጀሮና የጦጣ መንጋ ይገኛል፡፡ በጻድቁ ቃል ኪዳን የዝንጀሮም ሆነ የጦጣው መንጋ የገበሬውን አዝመራ እስከ አሁን ድረስ አይበላም፡፡ ገበሬውም ከአጨዳ የተረፈውን ቃርሚያ አይሰበስብም፡፡ ይህም ለጻድቁ የተሰጠ ቃል ኪዳን ነው ፡፡ ኪዳኑም ገበሬው ቃርሚያውን እንዳይሰበስብ፤ ዝንጀሮና ጦጣውም የገበሬውን አዝመራ እንዳይበላ የተሰጠ ቃል ኪዳን እንደሆነ በገድለ አቡነ ዮሴፍ ተመዝግቧል፡፡ ጻድቁ በጾምና በጸሎት ተወስነው ዕድሜያቸው 100 ዓመት ሲሆን በአፄ በዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ግንቦት 19 ቀን ዐርፈዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያንም የእኚህን ታላቅ ጻድቅ ቅድስና ሥራ ተመልክታና አጥንታ ቅዱስ የሚያሰኘውን ስም ሰጥታ ገድላቸውን ጽፋ በየዓመቱ ግንቦት 19 ቀን በዓለ ዕረፍታቸውን በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ታከብርላቸዋለች፡፡

ምንጭ፡- 1. ቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት በ1982 ዓ.ም. ከዶ/ር ሥርግው ሐብሌ ሥላሴ ፤
2. Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2 Juiy 1975
3. ትንሣኤ መጽሔት ቍጥር 92 1977 ዓ.ም. )

## 19. አቡነ አሮን ዘመቁት

አቡነ አሮን ዘመቁት የተባሉት ጻድቅ ከአባታቸው ከገብረ መስቀልና ከእናታቸው ከዓመተ ድንግል በአፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግሥት የተወለዱ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ናቸው ፡፡ የአባ በጸሎተ ሚካኤል ደቀ መዝሙርም እንደ ነበሩ ተመዝግቧል፡፡ ስለ አቡነ አሮን ቅድስና

www.ethiopianorthodox.org

ከሚናገሩት ታሪካውያን ነገሮች በምሳሌነት ሁለቱን ብቻ መጥቀስ ስማንዛቤ ይረዳል ብለ
እንገምታለን፡፡
እነሱም፡-

1. ባሕር ተሻግረው ሲሄዱ የጸሎት መጽሐፋቸው ማለትም ዳዊታቸው ከባሕር ውስ
ገብቶ ከቆየ በኋላ በመልአከ እግዚአብሔር አመልካችነት በሰባት ዓመቱ
በመቋሚያቸው እንዳወጡትና ምንም ጉዳት እንዳልደረሰበት፤

2. ከፍልፍል ድንጋይ የተሠራው አስደናቂ ገዳማቸው መሀሉ ከድርገት መውረጃው
ላይ ጣራው ክፍት ሆኖ ካህናቱ መጽሐፍ ሲያነቡ፤ ማንኛውንም መንፈሳዊ
አገልግሎት ሲያበረክቱ በጣራው የሚገባው ፀሐይ ስለሚያቃጥላቸው ዣንጥላ
ይዘረጋሉ፤ ፀሐይ ይገባል፡፡ በክረምት ግን የተፈለገውን ያህል ዝናም ቢዘንብ
ውሽንፍርና በረዶ ቢወርድ፤ ክፍት በሆነው ጣራ የዝናም ጠብታ አይገባም፡፡ ይህ
የጻድቁ ተአምር ነው ፡፡

ከዚህ ላይ ሊቁ አለቃ ለማ ኃይሉ «እነ ወዝናም፤ እንዘ ንጹሐን እምነውር ወእንዘ በቀ
አልብነ አሮን ለበዊእ ቤቱ በይነምንት ከልአነ ለእመ ዐረግነ ላዕለ ወእመ ታሕተ ወረድነ
ዘምስለ አቡነ አሮን ያስተሳልመኑ፡፡ አረጋዊ ኢተረክበ ለነ» ሲሉ የተቀኙት ዋዜማ ቅ
በዋቢነት ቀርቧል፡፡ የጻድቁ እረፍት መስከረም 5 ቀን በየወሩና በየዓመቱ የሚታሰብ ሲሆ
ቤተ ክርስቲያንም በስማቸው ቤተ ክርስቲያን አንጻ፤ ጽላት ቀርጻ፤ ገድል ጽፋ አክብ
ታስከብራቸዋለች፡፡ «የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል» ተብሏልና፡፡

## 20. አባ ዳንኤል-

የአባ ዳንኤል ብሔረ ሙላድ በሰሜን ሸዋ፤ በአንክበር አካባቢ ሲሆን የነበሩበትም ዘመን በአ
ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው ፤ የብሉያትና የሐዲሳት ሊቅ እንደነበሩም ይታወቃ
ምንኩስናቸውም በግሁሳን መናንያ እነንደሆነ ተመዝግቧል፡፡ ከዚያም እየተዘዋወሩ ወንጌ
ከሰበኩና ካስተማሩ በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር በክልል ትግራይ በቆላ ተንቤን የሚገኘው
«ወቅዋን ቅ/ገብርኤል ዘአባ ዳንኤል» የተሰኘውን ገዳም ገድመው በሰማንያ ዓመታቸ
ታኅሣሥ 19 ቀን እንዳረፉ ተመዝግቧል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ
ክርስቲያንም በዓለ ዕረፍታቸውን ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ ታኅሣሥ 19 ቀ
እንዲታሰቡ አድርጋለች ፡፡

ምንጭ፡- 1. Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2
2. ትንሣኤ መጽሔት 126 = 1980.

## 21. ጻድቁ አቡነ ክርስቶስ

አቡነ አካለ ክርስቶስ የነበሩበት ዘመን ከ1299-1314 በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት
ነው፡፡ አባታቸው ገላውዴስ፤ እናታቸው ወለተ አዳም ይባላሉ ፡፡ የትውልድ ቦታቸውም
ጉንደር ነው አያሉ የምናኔ ሥራ ከሠሩ በኋላ ደብረ ማህደ የተሰኘውን ገዳም ገድመው
ጥር14 ቀን አርፈዋል፡፡ በቃል ቃልኪዳናቸውም በዚህ ቦታ ልዩ ልዩ ተአምራት ይደረጋ
ቤተ ክርስቲያንም ቅድስናቸውን አክብራ ስታስከብራቸው ትኖራለች፡፡

ምንጭ፡- 1. Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2 Juiy 1975
2. ሐመር መጽሔት ፹ኛ. ዓመት ቁ. 2 1992

## 22. አቡነ ሀብተ ማርያም

ታላቁ ጻድቅ አቡነ ሀብተ ማርያም መካነ ትውልዳቸው በሰሜን ሸዋ በመንዝና ግሼ ል
ስሙ የራዊ በተባለ ቦታ ሲሆን አባታቸው ፍሬ ቡሩክ፤ እናታቸው ዮስቴና ይባላሉ ፡፡
የነበሩበትም ዘመን በአፄ በዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት ከ1468 - 1478 ዓ.ም ነው፡፡
በገድላቸው እንደተመዘገበው በእናታቸው ጀርባ «እግዚአ መሣሪ ክርስቶስ» እያሉ ይጸል
እንደነበር፤ ልዑል እግዚብሔርም «አንተን የተመረጠ ዕቃ አድርጌሃለውና ቃሌን ለተመረጠ
ሰዎች ተናገር» እያለ በራእይ ይነግራቸው እንደነበርና በተለያዩ ቅዱሳት መካናት
እየተዘዋወሩ መንፈሳዊ አገልግሎትታቸውንና ተጋድሎ[illegible] 26



ቀን በ1490 ዓ.ም እንዳረፉ ፤ በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ደብረ ሲዋኖስ አካባቢ ሰበይ
አቡነ ሀብተ ማርያም ገዳም ተብሎ እንደተገደመላቸው፤ ገድል እንደተጻፈላቸው፤ ጽላት
እንደ ተቀረጸላቸው ፤ መታሰቢያቸውም በየዓመቱ ኅዳር 26 ቀን እንዲከበርላቸው
ተወስኗል፡፡

ምንጭ፡- 1. Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2 Juiy 1975
2. ሐመር 4ኛ ዓመት ቁጥር 1989

## 23. ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ

ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ብሔረ ሙላዲ በሰሜን ሸዋ ቡልጋ ሲሆን የነበረችበትም ዘመን ከ
11-13 መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን ትውልዷ ከመሣፍንትና ከመኳንንት ወገን እንደነበር
ተመዝግቧል፡፡ በሕግና በሥርዓት ተድራ 12 ልጆችን ከወለደች በኋላ ወደ ጣና ደሴቶች ሄዳ
በምናኔ ብዙ ተጋድሎ ከተጋደለች በኋላ በደሴቶቹ ውስጥ አርፋለች፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ለክርስቶስ ሠምራ ቅድስናን ሰጥታ መታሰቢያዋ በየዓመቱ
ነሐሴ 24 ቀን ይታሰባል፡፡

ምንጭ፡- 1. የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ከዶ/ር ሥርግው ሐብተ ሥላሴ
2. Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2 Juiy 1975

## 24. ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ

ወለተ ጴጥሮስ ከአባቷ ከባሕር ስገድ እና ከእናቷ ክርስቶስ ዕበይ፤ በጎንደር ክፍለ ሀገር ስ
ማዳ ወረዳ ልዩ ስሙ በለስ ቅዱስ ሚካኤል በተባለው ቦታ በ1562 ዓ.ም. የተወለደች
ቅድስት ናት ፤ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ የምናኔ ሥራዋን የጀመረችው ስማዳ በተባለው ቦታ
በፈቃደ እግዚአብሔር አባ የሣነ ክርስቶስ ዘሬማ ፤አባ ተገዝረ ድንግል ዘጣና የተባሉት
ሁለት መናንያን መነኮሳት ባመለከሲት መሠረት፤ ወደጣና ደሴት ሄዳ የምናኔ ሥራዋን
ጀመረች፤ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ በየገዳማቱ እየተዘዋወረች ድኩማንን በመርዳት፤ ውሃ
በመቅዳት፤እንጨት በመስበር፤ እንጀራን በመጋገር፤ ብዙ ትሩፋትን ካደረገች በኋላ በ70
ዘመኗ በ1636 ዓ.ም. በክብር አርፋለች፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በስሟ ቤተ ክርስቲያን አንጻ፤
መታሰቢያዋ እንዲከበርና እንዲዘከር አድርጋለች፡፡

## 25. ሳሙኤል ዘደብረ ሃሌ ሉያ

አቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ሃሌ ሉያ መካነ ልደታቸው ተምቤን፤ ልዩ ስሙ መረታ ሲሆን፤
የአቡነ ዐቢያ እግዚእ የእሀት ልጅ ናቸው፡፡ አባታቸው ይርድአነ እግዚእ፤ እናታቸው
ትቀድሰነ ማርያም ይባላሉ፡፡ በ14 ዓመታቸው ልብሰ ምንኩስናን ተቀዳጅተው ሐዋርያዊ
ግዳጃቸውን የፈጸሙ ታላቅ አባት ናቸው፡፡ የነበሩበትም ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡
ደብረ ሃሌ ሉያ የተባለውም ገዳም መሥራች እሳቸው ናቸው፡፡ ዕለተ ዕረፍታቸውም ሐምሌ
26 ቀን በራሳቸው ገዳም ከመንበሩ ሥር አርፈው ስመ ገዝራቸው ሲታሰብና ሲዘከር
ይኖራል፡፡ «ገዝረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ» ተብሏልና

ምንጭ፡- 1. ቤና መዋዕል ዘብዙኅ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ነሐሴ 1978 ዓ.ም.
2. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያ ትናንትናና ዛሬ 1990 ዓ.ም.
3. Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2 Juiy 1975

## 26. አቡነ ቶማስ ዘሽሬ

እኝህ ጻድቅ ሀገራቸው በክልል ትግራይ በሽሬ ሀይዳ ከተባለው ልዩ ሥፍራ የተወለዱ ጻድቅ
ናቸው፡፡ በስማቸው የታነጸው ገዳም በጽምብላ ወረዳ፤ ከተከዜ አፋፍ ላይ የሚገኝ ሲሆን
የአንድነት ገዳም ነው ፡፡ በገዳሙ ውስጥ ሥጋ፤ ቅቤ አይበላም፡፡ ተብልቶም ከሦስት ቀናት
በፊት ወደ ገዳሙ አይገባም፤ ዕረፍታቸውም በየወሩ በጥቅምት 13 ቀን ይታሰባል፡፡

ምንጭ፡- 1. Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2 Juiy 1975

www.ethiopianorthodox.org

## 27. ሰባቱ ከዋክብት-

ሰባቱ ከዋክብት የሚባሉት በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት (1307 ዓ.ም.)

1. አቡነ በትረ ማርያም ዘዘጌ
2. አቡነ ዘዮሐንስ ዘክብራን
3. አቡነ ታዴዎስ ዘደብረ ማርያም
4. አቡነ ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉንቤ
5. አቡነ አሳይ ዘማን - እንዳባ
6. አቡነ ዘካርያስ ዘገሊላ
7. አቡነ ኖብ ዘጉርጉራ የተባሉት በጣና ሐይቅ የሚገኙ ትን ገዳማት የቆረቆሩና ያቋቋሙ፤ስብከተ ወንጌልን በአካባቢው ያስፋፉ፣ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ናቸው፡፡

ምንጭ፡- 1. የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ከዶ/ር ሥርግው ሐብሰ ሥላሴ

## 28. ኖላዊ ሐር

አቡነ ኖላዊ ሐር የተባሉት ጻድቅ ሀገራቸው በክልል ትግራይ ሽሬ ቤተ ቂርቆስ ሲሆን በምናኔ ዓለም የኖሩ ታላቅ ጻድቅ ናቸው፡፡ በሃይማኖት ምክንያት ብዙ ስቃይ እንደደረሰባቸው ይነገራል፡፡ በስማቸው የታነጸ ገዳም አላቸው፡፡ የሚገኘውም በጸአዳ አምባ ሕርያ ከተባለው ቦታ ይገኛል፤ በረሃማ ቦታ ነው፡፡ የነበሩበትም ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡

ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ 1990 ዓ.ም.

## 29. ክርስቶስ ቤዛነ፡-

አቡነ ክርስቶስ ቤዛነ የተባሉት ጻድቅ አገራቸው ተንቤን ተአሚና ከተባለው ቦታ ሲሆን በ442 ዓ.ም. የተወለዱ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አባት እንደሆኑ በገድለ ተክለ ሃይማኖት ገጽ 184 ላይ ተመዝግቧል ምክንያቱም ምንኩስናቸውም ከዘጠኙ ከዋክብት ቅዱሳን ከተባሉት ከእነ አቡነ አረጋዊ እንደነበርና በስማቸው የተገደመ ገዳም፤ በተምቤን ተአሚና ከተባለው ቦታ ይገኛል፡፡

ምንጭ፡- Journal of Ethiopian studies , Vol.13 No. 2 July 1975

## 30. መዝራዕተ ክርስቶስ :-

በሰሜኑ አህጉረ ስብከት ገዳማተ ኢትዮጵያን ተዘዋውረው ሠፊ ጥናት ያደረጉት አቶ ግርማ ኤልያስ እንደመዘገቡት የአቡነ መዝራዕተ ክርስቶስ እናት በተከታታይ አምስት ልጆችን ወልዳ ሁሉም እንደሞቱባት በዚህም ምክንያት «ፈጣሪዬ የሚያድግ ልጅ ቢሰጠኝና ለአንድ ቀንም ቢሆን ፊቱን አይቼ በሞትኩ» እያለች ትመኝ ነበር እግዚአብሔርም ኀዘኗን ሰምቶ መዝራዕተ ክርስቶስን እንደ ወለደች ጊዜውም የሃይማኖት ስደት የበዛበት ዘመነ ሱስንዮስ ስለነበረ ጨቅላ ልጇን ይዛ በፎገራ ወረዳ ቆራጣ ወለተ ጴጥሮስ ገዳም ገባች ሕጻኑ መዝራዕተ ክርስቶስ እድሜው ለትምሕርት እንደደረሰ አባ ስነ ክርስቶስ ከሚባሉ መነኮስ እየተማረ አደገ በመጨረሻም በኂሁ መነኮሰ ልብሰ ምንኩስናን ለብሶ በርካታ የትሩፋት ሥራዎችን ከሠራ በኋላ ወደ ክልል ትግራይ ተጉዞ በአድዋ አውራጃ የሃ አቡነ አፍጹ ገዳም ከተሳለሙ በኋላ ገዳሙን ከከበቡት ረዳጆም ተራሮች በአንደኛው ማይ ዱር ወደ ሚባለው ተራራ ወጣ ከዚያም አዲስ ገዳም መስርቶ ታቦተ ማርያምን አስገብቶ ሲኖር ከየአቅጣጫው መናንያን መነኮሳት ወደ እርሱ ተሰበሰቡ እስከ ዘጠና ሦስት ዓመቱ ድረስ ያንን ገዳም በአምኔትነት እያተስዳደረ ከኖረ

በኋላ ግንቦት 29 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ማይዱር በተባለው ገዳሙ እራሱ ባሠራት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ውስጥ አርፏል ገዳሙም እስከ ዛሬ ድረስ እንዳ አቡነ መዝራዕተ ክረስቶስ እየተባለ ሲጠራ ይኖራል ::

ምንጭ፡- 1. Journal of Ethiopian tudies , Vol.13 No. 2
2. ሐመር መጽሔት ፴ ዓመት ቁጥር 5





## 31. ቅዱስ ቀውስጦስ :-

ቅዱስ ቀውስጦስ የተወለዱት በአማራ ክልል፣ በሰሜን ሸዋ በወግዳና ቡልጋ አካባቢ ነው፡፡ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ታውቋል፡፡ የቅዱስ ቀውስጦስ አባት ገላውዴስ የተባለው ሲሆን እናታቸውም እምነ ጽዮን ይባላሉ፡፡ ገላውዴስና እምነ ጽዮን በሕገ እግዚአብሔር ተጋብተው ሲኖሩ በደቡብ ክልል በወላይታ ነግሦ የነበረው መተሎሚ በወራሪነት ወደ ሰሜን ሸዋ ዘምቶ ቡልጋንና አካባቢውን በሚዘርፍበት፣ ሰውንም በሚማርክበት ጊዜ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን እናት እግዚእሐረያን፣ ቅድስት እምነ ጽዮን ከወንድሟ ከመድኃኒነ እግዚእ ቤት ከፈጠጋር ማርኮ ከወሰዳቸው በኋላ እግዚእሐረያን ለራሱ ሚስት፣ እምነ ጽዮንን ለታላቅ ወንድሙ እንዲያገቡ ከወሰነ በኋላ ሁለቱ እኅትማማቾች ለአሥር ቀናት ያህል እህል ውኃ ሳይቀምሱ በጾም በጸሎት፣ በተጊሃ ስግዳት ወደ እግዚአብሔር በሐዘንና በለቅሶ ስላመለከቱ መላእክት ማለትም ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል በአክናፈ ረድኤት ከመተሎሚ ሠራዊት ነጥቀው እግዚእሐረያን ለጻጋዘአብ፣ እምነ ጽዮንን ለገላውዴስ ከአስረከቧቸው በኋላ ቅድስት እምነ ጽዮን ከምርኮ ከተመለሰች ከአምስት ወር በኋላ ሐምሌ ሰላሳ ቀን ጻድቁ ቀውስጦስን ጸንሳ ግንቦት 1 ቀን ወልዳለች፡፡

የቀውስጦስ የትምህርት አባት « ሕይወት ብነ በጽዮን » የተባሉት ሲሆኑ ትምህርተ ሃይማኖትን በሚገባ እንዳስተማሯቸው፤ ማዕረገ ዲቁናን ከአቡነ ጌርሎስ፤ ሥርዓተ ምክንኩስናን ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደተቀበሉ መጽሐፈ ገድለ ቀውስጦስ ይተርካል፡፡ እድገታቸውና ተጋድሏቸውም የዮሐንስ መጥምቅን ዕድገትና ተጋድሎ ይመልሳል፡፡ ዮሐንስ መጥምቅ የማኑ ማር ማለትም የቀባ ወይም የጣዝማ ማር እየተመገበ እንደኖረ ጻድቁ ቀውስጦስም ከእግዚአብሔር የታዘዘላቸውን የገድል ማር እየተመገቡ አድገዋል፡፡

ዮሐንስ መጥምቅ ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ያለ አግባብ ሲያገባ የወንድምህን የፊሊጶስን ሚስት ልታገባ አይገባህም ብሎ በማውገዙ በሰይፍ አንገቱን ተቆርጦ በሰማዕትነት እንዳረፈ፤ ጻድቁ ቀውስጦስም የወንድማቸው ልጅ አጼ አምደ ጽዮን የአባቱን ዕቅብት በማግባቱ የአባትህን ዕቅብት ልታገባ አይገባህም ብሎ ስላወገዙት ሰው እንዳያየው በድቅድቅ ጨለማ ወደ በዮ አፋፍ አስወስዶ በእንሳሮ አረህ ላይ ኮሶ አረህ በሚባለው ጫካ ውስጥ በሰይፍ አስመትቶ አስገድሏቸዋል፡፡ ልዩ ቦታውም የገዳይ መቀጫ ተብሎ በአካባቢው ሕዝብ ይታወቃል፡፡ በሀገረ ክፋ ከሰባ በላይ የሚሆኑ አድባራትና ገዳማትን እንዳሠሩ ገዘክረ ታሪካቸው ያወሳል፡፡

ምንጭ፡- ገድለ አቡነ ቀውስጦስ 1998 ዓ.ም. ( ያልታተመ )

## 32. ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ :-

ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ የትውልድ አገሯ በጎንደር ክፍለ ሀገር ፎገራ አካባቢ ሲሆን አባቷ ላባ፣ እናትዋ ደግሞ ወንጌላዊት ይባላሉ፤ የነበረችበትም ዘመን በ1595 ዓ.ም. እንደሆነ ተመዝግቧል፡፡

ዕድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ በትምህርት የሚኖሩ ባሕታዊ ከእግዚአብሔር ታዘው ከእናት አባቷ ቤት ተቀምጠው ፊደል እዳስቆ ጠሯት፣ ዳዊት እንዳስደገሟት፣ የብሉያትን እና የሐዲሳትን ትርጓሜ እንዳስተማሯት ስለ እሷ የተመዘገበው ዝክረ ታሪክ ይገልጻል፡፡ ወላጆቿም ለአቅመ ሔዋን እንደደረሰች ዘርዐ ክርስቶስ ለሚባል ሰው ዳሯት፡፡ ዘርዐ ክርስቶስም ጽኑዕ ዓላማ የነበረው ጻድቅ ሰው፣ በድንግልና ሕይወቱን ለመምራት የወሰነ ስለ ነበረ ሁለቱ ተጋቢዎች ተመካክረው ንጽሕናቸውን ጠብቀው ሳይገናኙ ለአርባ ዘመን ጽመዳነ ጸሎት ሆነው ቆይተዋል፡፡ በመጨረሻም በፈቃደ እግዚአብሔር በብሥራተ መልአክ ከግንባሩ ላይ የብርሃን መስቀል የታተመበት ልጅ በመውለዳቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ተአምራቱን እያደነቁ በገድል ላይ ገድል እየጨመሩ ኖረዋል፡፡ የነበሩበትም ዘመን ሱስንዮሳዊ ዘመን ስለነበረ ሰማዕትነትን ተቀብለዋል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ ታቦተ ኪዳነ ምሕረትን ይዛ፣ በርካታ ደናግል መናንያን አስከትላ፣ ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር ቆቦ ወረዳ በመሄድ ራማ ኪዳነ ምሕረት የምትባል ገዳም መሠረተች፡፡ በመጨረሻም «እመ ምዑዝ» በተባለው ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን አሳንጻ እንደ ጨረሰች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ይህች በስሟዛ የተሠራችው ቤተ ክርስቲያን እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ አትፈርስብሽም በዚህችም ቦታ ላይ ሴቶችም ወንዶችም አማኞች እንደ አሽን ይበዛሉ፣ በስምሽ የተማጸነውን፣ በቃል ኪዳንሽ የጸናውን መጽሐፈ ገድልሽን የጻፈውንና ያልጻፈውን፣ በስምሽ ለድሆች የሰጠውን፣ በዚህች ቦታ መንኖ የመነኰሰውን አረጋውያንን የረዳውን፣ ዝክርሽን የዘከረውን ቤተ ክርስቲያንሽን ያነጸውንና የሳነጸውን ሁሉ እስከ አሥር ትውልድ ምሬልሻለሁ » ሲል ቃኪዳ ገብቶላታል፡፡ ዘመኑም በአዲ ፋሲል ዘመን ማለትም በ1673 ዓ.ም. ነው፡፡ ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ በዚህ ቦታ ስትጋደልና ስታገለግል ለብዙ ዓመታት ኖራ አርፈለች፡፡ ቀብሯም ራሷ ካሠራችው ቤተ መቅደስ አጠገብ ነው፡፡ መታሰቢያዋም በየወሩና በየዓመቱ ይታሰባል፡፡ በጊዜ ዕረፍቷም ብዙ ተአምራት ተደርገዋል፡፡ ለ40 ቀናት ያህል በመቃብሯ ላይ አምደ ብርሃን እያበራ ቆይቷል

ምንጭ፡- «ሕብረ ብዙ » ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፣ የሰሜን ወሎና ዋግሕምራ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አዲስ አበባ 1998 ዓ.ም.

# ክፍል 3

## ብሔረ-ሙላዳቸው ከውጪ ሆኖ ቅድስናን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያገኙ ቅዱሳን አበው፡፡

### 1. ቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፡-

አባ ሰላማ በትውልዱ ጽርዓዊ፣ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የነበረ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ነው፡፡ የነበረበትም ዘመን ከ 330 - 352 እንደነበረ፣ በታሪክ ተመዝግቧል፡፡ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ «ዝንቱስ ብእሲ መምህርነ፣ ዘተፈነወ ውስተ ምድርነ ይክሥት ብርሃነ» ብርሃንን ይገልጥ ዘንድ ወደ ሀገራችን የተላከ ይህ ሰው መምህራችን ነው፣ በማለት በድጓው ያስነብበናል፡፡

በመሠረቱ እውነተኛው የዓለም ብርሃን ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ባይካድም በክርስቶስ አምነው የክርስቶስን የዓለም ብርሃንነት ለዓለም ያሳወቁ ሁሉ «ብርሃናተ ዓለም» ተብለዋል፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት ብርሃናተ ዓለም እንደሆኑ በወንጌል ተጽፏል፡፡/ማቴ 5 ፡ 14/ በዚህም አንጻር የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ ፍሬምናጦስ « ከሳቴ ብርሃን» ወይም ብርሃነ ኢትዮጵያ እየተባለ ይጠራል፡፡ስለ ክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ሦስት የተለያዩ ታሪኮች አሉ፡፡ 1ኛ. በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፣ 2. በሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ፣ 3ኛ. በቅዱስ ፍሬምናጦስ ጊዜ እንደገባ ይተረካል፡፡ ሁሉም እውነት እንደሆነ በታሪክ አዋቂች ተረጋግጧል፡፡ ግን ክርስትና የሀገሩ እምነት የሆነውና ከእነ ሙሉ ሥርዓቱ የተሰበከው በቅዱስ ፍሬምናጦስ ሐዋርያነት ጊዜ ነው፡፡





ፍሬምናጦስ ይባል የነበረው ጵጵስናን ሲቀበል በኢትዮጵያውያን ሰላማ በመባል ተሰይሟል፡፡ ይህ ስያሜ ሰላማ በክርስቶስ መስቀልና ሞት፣ እንዲሁም ትንሣኤ፣ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ስለተፈጸመው የዕርቅ ሥራ ለሕዝበ ኢትዮጵያ አብሳሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡

አቡነ ሰላማ የኦሪት ቀንበርና የአሕዛብ ልማድ አጨልሟት የነበረችው ኢትዮጵያን በብርሃነ ወንጌል ስለ አበራ፣ በብርሃነ ትምህርቱ የተደሰቱ ኢትዮጵያውያን «ሰላማ ከሣቴ ብርሃን» ሲሉ ሥራውን ጨምሮ የሚገልጥ የክብር ስም ሰጥተውታል፡፡

## በሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተፈጸሙ ዐበይት ድርጊቶች

### 1. መካሪ / አበነፍስ/ ፡-

በአቡነ ሰላማ ጊዜ በየቀበሌው አንዳንድ ካህን /ቄስ/ መካሪ መደረጉ ነው፡፡ ይህም አፈጻጸም መጻሕፍትን አንብቦ ለማይጠቀም ሕዝብ ቀርቶ ለአዋቂና ለተማረም የሚጠቅም መልካም ድርጊት ነበረ፡፡ ይሁን እንጂ በጊዜ ብዛት መካሪው ካህን /ቄስ/ ስለ ነፍስ ጉዳይ የአባት ያህል በመምከሩ አበ ነፍስ ማለትም የነፍስ አባት ተብሎ ይጠራ ጀመረ ፡፡ በኋላም ስለ ኃጢአት ኑዛዜ በመቀበል ንስሐን ስለሚሰጥ የንስሐ አባት ተብሏል፡፡ እስከ አሁንም ይህ አጠራር ተጠብቆ ይገኛል፡፡

### 2. አበ ልጅ / የክርስትና አባት/ ፡-

አበ ልጅ ማለት የሚጠመቀውን ተጠማቂ በእግዚአብሔር መንገድ እየመራ እንዲያሳድገውና እንዲያስተምረው፣ እንደዋስ ወይም እንደተያዥ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ፊት መቀበሉን የሚያረጋግጥ ምእመን ነው፡፡ ይህ ሥርዓት ከመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር አብሮ ተመሥርቷል፡፡

### 3. ቅዱሳት መጻሕፍት፡-

በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ከግሪክ /ከሰብዓ ሊቃውንት/ መጻሕፍት ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል፡፡ አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ ካበረከታቸው ታላላቅ ሥራዎች አንደኛው ቅዱሳት መጻሕፍትን መተርጐሙ ነው ፡፡

### 4. ቋንቋ ፡-

የጥንቱ ግዕዝ ዛሬ እንደምናነበው ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያለው ድምጽ በፊደሉ አልነበረም ዳሩ ግን ግእዙን ብቻ አናጋሪ አድርጎ ይነበብ ነበር፡፡ ለምሳሌ «ሐወለተ አክሰመ» ሐውልተ አክሰም ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጐም አስቸጋሪ ስለሆነበት አቡነ ሰላማ ከኢትዮጵያ ብሔራውያን ሊቃውንት ጋር ተመካክሮ በጥንታዊው የፊደል ቅርጽ መሠረት ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያለውን ትእምርተ ድምጽ /ዋየል/ አዘጋጀ፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሃይማኖት ቋንቋ ወይም መሠረት ከሆኑት ከአብራይስጥና ከግሪክ ቋንቋ ሳይቀር ተርጉሞ ጻፈ፡፡

### 5. የሃይማኖት ትምህርት፡-

ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ያመጣልን ትምህርተ ሃይማኖት በጌታችን በመድኃ ኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተው፣ በሐዋርያት የተሰበከው ፣ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ማለትም በ318 ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት የጸናው ትምህርተ ሃይማኖት ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

አቡነ ሰላማ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ ከመሆኑም ጋር ብዙ በረከቶችን ስላስገኘላት በዓመት ሁለት ጊዜ ሐምሌ 26 እና ታኅሣሥ 18 ቀን ቅዱስ አባት ብላ ታከብረዋለች፡፡ በስሙም ቤተ ክርስቲያን አንጻለች፡፡ በክልል ትግራይ በአቡነ ሰላማ ስም የታነጹ 3 አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ ከግቱ ብርሃን ሰላማ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀዳማዊ ሐዋርያ መሆኑ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም የታወቀ ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታላቅ መምህር «አባ ሰላማ ከሠተ ለነ ብርሃነ ዜናሁ ለምድኃኒነ» አባ ሰላማ ብርሃን የሆነ የመድኃኒታችንን ዜና ገለጠልን እያለች የወንጌል መልክተኝነቱንና ቅዱስነቱን ትመሰክራለች፡፡

ምንጭ፡- ትንግኤ መጽሔት ቁጥር 34 ሐምሌ 1972 ዓ.ም.

## 2. ተሰዓቱ ቅዱሳን ፡-

ተሰዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በ480 ዓ.ም. በመንግሥተ አልአሜዳ ዘመን ሲሆን የመጡበትም ዐቢይ ምክንያት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ያስተማረውንና የተሰዋለትን ቀጥተኛውን ትምህርተ ተዋሕዶ በመካከላቸውና በ451ዓ.ም የተደረገውን የኬልቄዶን ጉባኤ ባለመቀበላቸው ከቢዛንታይን መንግሥት በደረሰባቸው የከፋ ስቃይ ምክንያት ነው፡፡

እነዚህ ቅዱሳን ኢትዮጵያን እንደተወለዱባት አገር ቆጥረው ክርስትናን በሚገባ አስተምረው አስፋፍተዋል፡፡ እስከዛሬ ድረስ በስማቸው የሚጠሩትንና ሌሎችንም ገዳማት መሥርተዋል፡፡

የቤተ ክርስቲያኒቱን የግእዝ ቋንቋ በሚገባ አውቀው ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስትና ከጽርእ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መልሰዋል፤ ቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን በሚገባ ፈጽመው ስላረፉ ቅዱሳን ብላ ታከብራቸዋለች፡፡ ስማቸው፣ ገዳማቸውና የዕረፍት ቀናቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

| ስም | ገዳም | የዕረፍት ቀን |
|---|---|---|
| አባ አሌፍ | ብንዛን (አህስአ) | መጋቢት 11 ቀን |
| አባ አረጋዊ | ደብረ ዳሞ | ጥቅምት 14 ቀን |
| አባ አፍጼ | ዮሃ (የሐ) | ግንቦት 12 ቀን |
| አባ ሊቃኖስ | ደብረ ቆናጽል | ጎዳር 21 ቀን |
| አባ ገሪማ | መደራ | ሰኔ 17 ቀን |
| አባ ጉባ | ገርዓልታ | ግንቦት 29 ቀን |
| አባ ይምአታ | ገርርዓልታ | ጥቅምት 23 ቀን |
| አባ ጵንጠሌን | አኩሱም አጠገብ | ጥቅምት 6 ቀን |
| አባ ጽሕማ | ጼዴንያ | ጥቅምት 16 ቀን ነው፡፡ |





## 3. አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ግብጻዊ፡-

ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ዘመን በዘመነ ቅዱስ ላሊበላ ሲሆን፣ በምድረ ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ ወንጌልን በመስበክቸው፣ ክርስትናን በማስፋፋታቸው፣ አምልኮ ባእድን በማጥፋታቸው፣ልዩ ልዩ ተአምራን በማድረጋቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅድስናን ሰጥታ፣ ጽላት ቀርጻ ገዳማትን በስማቸው ገድማ፣ ገድላቸውን ጽፋ በየዓመቱ መጋቢት 5 ቀን የዕረፍታቸውን መታሰቢያ ታከብርላቸዋለች፡፡

ይሁን እንጂ እነ አባ ኢስጣቴዎስ ክፋሉ ባሕር፣ እነ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ እነ ቅዱስ መርቆሬዎስ፣ እነ ቅዱስ ፋሲለደስ፣ እነ ቅዱስ ቂርቆስ፣ እነ ቅድስት ኢየሉጣ ፣ እነ ቅድስት አርሴማ እና የመሳሰሉት፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የቅድስና ስምና ሥራ የተሰጣቸው ብዙዎች ስለሆኑ ወደፊት በስፋት የሚጻፍላቸው ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን ወላዲተ አምላክ ቅዱሳን እንደመሆኗ መጠን ወደ ፊት ልዑል እግዚአብሔር ቢፈቅድ ፡-

1. የእነ አቡነ ኢስጣቴዎስን ኢትዮጵያዊ፣ የነበሩበት ዘመን ከ1273 - 1352 ዓ.ም.
2. የእነ አቡነ አብርሃምን ኢትዮጵያዊ፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
3. የእነ አቡነ አኖሬዮስን፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
4 የእነ አቡነ አኖሬዮስ ዘይንእስን፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
5. የእነ አቡነ በጸሎተ ሚካኤልን፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
6. የእነ አቡነ ፊልሞናን፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
7. የእነ አቡነ ፊቅጦርን፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
8. የእነ አቡነ ሕንፃ ሃይማኖትን፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
9. የእነ አቡነ መድኃኒነ እግዚእን፣ የነበሩበት ዘመን በ14ኛው ክፍለ ዘመን
10. የእነ አቡነ መርሐ ኢየሱስን፣ የነበሩበት ዘመን ከ1407 - 1496 ዓ.ም.
11. የእነ አቡነ ሕፃን ሞዓን፣ የነበሩበት ዘመን በ15ኛው ክፍለ ዘመን
12. የእነ አቡነ ፍሬ ሚካኤልን፣ የነበሩበት ዘመን በ15ኛው ክፍለ ዘመን
13. የእነ አቡነ አናንያን ኢትዮጵያዊ፣ የነበሩበት ዘመን በ15ኛው ክፍለ ዘመን
14. የእነ አቡነ አብራጎስን ኢትዮጵያዊ፣ የነበሩበት ዘመን በ1718 ዓ.ም.

እና የመሳሰሉትን ገዳማውያን አርአስተ አበው ቅዱሳን ዜና ገድል፣ ወደ ፊት በቀጣይ የሚቀርብ ሆኖ ለአሁኑ ከዚህ ላይ ይቆየን፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 10

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት

### የምንኩስና መሠረቱ፣

እግዚአብሔር በዘመነ ብሉይ የተሠሩትን አሥሩን ሕግጋት እና በዘመነ ወንጌል ራሱ የሠራቸውን ስድስቱ ሕግጋት አጽንቶ አንድ ሕግ እንደሰጠ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታመነ ነው፡፡

ከመአስባንና ከደናግል ለመረጣቸው አሥራ ሁለት ሐዋርያትና ለሰባ ሁለቱ አርድእት የሥልጣን መዓርግ ሰጥቶ ለመአስባንና ንጹሓን ደናግል በመባል ተስተካክለው መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሱ ለመደረጉ፡፡

ሄኖክ በተባሕትዎ ጀማሪነት ለመአስባን፣ መልከ ጼዴቅና ኤልያስ በድንግልናዊ ሕይወት ጀማሪነት ለደናግል አብነት ወይም መሪ መሆናቸው እስከአሁን ተያይዞ ከመጣው ታሪክ እንረዳለን፡፡

ዮሐንስ መጥምቅም ሄኖክንና ኤልያስን አብነት በማድረግ፣ ሠላሳ ዘመን በገዳም ተወስኖ እህል ሳይበላ የግመል ጸጉር ለብሶ ወገቡን በጠፍር መታጠቂያ ታጥቆ የማርና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ በግብረ ተባሕትዎ ጸንቶ ኖሯል፡፡ (ማቴ.ም.3፣4፤ 10፣15፡፡)

ሥርዓተ ምንኩስና እንዲህ በመንፈስ እግዚአበሔር የተመራ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ "ቤቱን ወንድሙንና እህቱን አባቱንና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን ንብረቱን ትቶ በስሜ አምኖ ይከተለኝ የዚህን ሁሉ መቶኛ እጥፍ ያገኛል የዘለዓለም ድህነትም ያገኛል" ብሎ ስለ መዓርገ ምንኩስና ትክክለኛ ትርጉም ሰጥቶ የተናገረውን ቃል መሠረት በማድረግ ይኸውና በገዳማቱ በሺህ የሚቆጠሩ መናንያን መነኮሳት ይገኛሉ፡፡ (ሉቃ ም.9:82) በዘመነ ሊቃውንት የተገኘ ሥርዓተ ተባሕትዎ በዘመነ አበው (በነሄኖክና በነመልከ ጼዴቅ) ተያይዞ መምጣቱ የታወቀ ሲሆን እስከ አሁን የደረሰበት ደረጃ ሲታይ ከሐዋርያትና ከሰብዓ አርድእት ዘመነ ስብከት በኋላ እንደ ቀድሞ ሰዎች (እንደነ ኤልያስ) እንደኋላ ሰዎችም (እንደ ዮሐንስ መጥምቅ) ንጽሕናዬን ጠብቆ ከሴት ርቄ መኖር እፈቅዳለሁ ብሎ ሰውነቱን ለእግዚአበሔር አደራ በሰጠ አባ እንጦንስ ላይ ያደረገው ጸጋ ምንኩስና አሁንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትና መናንያን ከትውልድ ወደ ትውልድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲተላለፍ የቆየ ሲሆን ወደፊትም እስከ ምጽአተ ክርስቶስ ድረስ ጸንቶ የሚኖር ነው፡፡

ልብሰ ምንኩስናው ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ ሲሆን ቆቡ የአክሊለ ሦክ፣ ቀሚሱ የከለሜዳ፣ ቅናቱ የሐብል፣ ሥጋ ማርያም የማርያም ሥጋ፣ አስኬማ በሰውነቱ መስለን እንደተናገርነው ሰው የመሆኑ ምሳሌ ነው፡፡

እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ኩፋት ደፍተው፣ በሎታ ይዘው፣ ዝናር ታጥቀው ጫማ አዝበው እንደተነሡ መነኮሳትም እንዲህ ያለ ልብሰ ምንኩስና ለብሰው በምናኔ የዚህ ዓለም ፍላጐትን ምኞትን ድል ነስተው በሞት ከዚህ ዓለም ይለያሉ፡፡

በተለይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት የመነኮሳት ሕይወትና አኗኗር፣ ብዛትና አመጋገብ፣ አለባበስና የገዳማቱ ሥርዓት ከቅዱሳን አባቶች የወረስነውን ተጋድሎ ከዚህ ቀጥሎ በሰፊው እናያለን፡፡ ቸሩ አምላካችን እንኳን ለበዓለ ፳፤ ዓ.ም. በሰላም አደረሳችሁ አላለሁ፡፡





# ክፍል 1

## የብሕትውና አጀማመር

ነቢያት፣ሐዋርያት፣ ሊቃውንት፣ መነኮሳት፣ ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ በዱር በገደል፣በአሳት፣ በስለት፣ በረሀብ፣ በእርዛት፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በምናኔ የተንገላቱ መከራ የተቀበሉት ለእምነታቸው፣ ለምግባራቸው፣ ለባህላቸውና ለሥርዓታቸው፣ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ነው ለእምነታቸው፣ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት በማስተማርና በማስከበር ሁሉም የእግዚአብሔርን ስም ይጥራ፣ ሁሉም ከእግዚአብሔር የተገኘና በእግዚአብሔር የሚረዳ ነው በማለት ነው፡፡

እነ ኤልያስ፣ እነ ኤርምያስ፣ እነ ኢሳይያስ በድንግልና በብሕትውና በማስተማር፣ ነገሥታት ነን ባዮችን፣ ድሀ አትብድሉ፣ ፍርድ አታጓድሉ፣ ጣዖት አታምልኩ፣ በእግዚአብሔር እመኑ በማለት የሰውን ነጻነት የእግዚአብሔርን ቸርነት ለመመስከር የአመቻቸው ብቸኝነታቸው ነው፡፡ ያስተማሯቸውም ለሰው ሕይወት ለሀገር ደኅንነትና ነጻነት ነው፡፡

በሐዲስ ኪዳን የነበሩ አበው ሠለስቱ ምዕት ሃይማኖተ አበውን ለማፋለስ የመጀመሪያው ከሐዲ ከስምዖን መስረ ቀጥሎ የተነሣው አርዮስን እግዚአብሔር ወልድን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ለይቶ «ወልድ ፍጡር ነው» ብሎ ሲነሣ በ325 ዓ/ም አበው ሊቃውንት መጻሕፍትን ጠቅሰው ጉባኤ ዘርግተው «ቀዳሚሁ ቃል»ን ተርጉመው «ወቦቱ ኮሉ ኀነ ወዘአንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ» ብለው ረተው «ወነአምን በአሐዱ አምላክ ወልደ አብ ዋሕድ ዘሀልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም» በማለት የወልድን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ ሥልጣን ወይም የራሱ ሥልጣን አለመኖሩን፣ ሥራቸው ሥልጣናቸው፣ አንድ መሆኑን ያስረዱት አበው መነኮሳት ናቸው፡፡ የሠለስቱ ምዕት ሕይወት የምንኩስና ሕይወትን የሚጠይቅ ነበርና፡፡ ይህም በሁሉ ነገር ፈጥኖ ደራሽነታቸውን ያስረዳል፡፡

በ381 መቅዶንዮስ የተባለ መናፍቅ «መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር አንድነት የለውም» ብሎ የክህደት ትምህርትን ሲነዛ 200 አበው ሊቃወንት መነኮሳት መጽሐፍ ጠቅሰው ተከራክረው «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረፀ እምአብ» ብለው በጸሎተ ሃይማኖት የወሰኑ ያስተማሩ መነኮሳት ሊቃውንት ናቸው፡፡

ተምሮ ማስተር፣ በምግባር በዕውቀት ራስን አስመስሎ ማውጣት ሰውን መፍጠር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው እኔ በክርስቶስ ትምህርት ወልጃችኋለሁና እኔን ምሰሉኝ ያለው፡፡

ባሕታዊ ማለት ከዓለም የራቀ ብቸኛ ማለት እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡

ሥርዓተ ብሕትውና የተጀመረው የአዳም ሰባተኛ ትውልድ በሆነው በሄኖክ ነው፡፡ ይኸውም ይታወቅ ዘንድ የሄኖክ አባት ያሬድ መላእክት ወይም ውሉደ እግዚአብሔር የተባሉት የሴት ልጆች በሰይጣን ወተመደ ተይዘው ከእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ወጡና በማይገባ ፍትወት ተመስጠው ከደብር ቅዱስ ሊወርዱ እንደተነሡ በሰማ ጊዜ አስጠርቶ እንዲህ ያለውን ክፉ ሥራ አትሥሩ እያለ ተቈጥቷቸውና አስምሏቸው ነበር፡፡

ሄኖክም ሲመክራቸው እንዲህ ብሏል « እናንት የሴት ልጆች ወዮላችሁ ተዉ፣ የአባታችሁን መሐላ አታድርሱ፡፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተወ ያባቱን መሐላ ያፈረሰ፣ ከደብር ቅዱስ የወረደ፣ ከአዋልደ ሰዋል ጋር ኃጢአት የሠራ ተመልሶ ወደ ደብር ቅዱስ አይገባም ብሎ መክሯቸው ነበር፡፡

እነሱ ግን ምክሩን ጥሰው ፣ መሐላውን አፍርሰው ከደብር ቅዱስ ወርደው ከሰዋል ልጆች ጋራ የማይገባ ሥራ እየሠሩ ይዘፍኑ ይጨፍሩ ይሳለቁ የመጻደቁ ጀመር፡፡

ያሬድ በዚህ እያዘነ ከኖረ በኋላ፣ በሚሞትበት ጊዜ ልጁን ሄኖክን « ልጄ አንተስ

www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔርን ምስጋና አታቋርጥ፣ ዘወትር ጸልይ » ብሎታል፡፡

እሱም ያባቱን ትእዛዝ ተቀብሎ በዚሁ መሠረት አምስት ዓመት እግዚአብሔርን ካገለገለ በኋላ ከተወለደ ጀምሮ ሦስት መቶ ሰላሳ አምስት ዓመት ሲሆነው ሚስት አግብቶ ቤት ሠርቶ ልጅ ወልዶ መኖሩ መንፈሳዊ ስሜቱን የማያረካው መሆኑን ተረድቶ ፣ ከመብል ከመጠጥ ከመከልከሉም በላይ ሰው ወደሌለበት ወደ እግረ ገነት ሔዶ በተባሕትዎ ጸንቶ ኖረ፡፡

እንግዲህ ከላይ እንደተገለፀው ባሕታዊ ማለት ከዓለም ወጥቶ፣ ከሰው ተለይቶ ከፍትወተ ሥጋ የራቀ ብቸኛ ማለት ነው ያልንበትን ምክንያት አንባቢ ሊገምተውና ሊያመዛዝነው ይችላል፡፡

ሄኖክ በእግረ ገነት ስድስት ዓመት ከኖረ በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ገነት አሳርጎታል፡፡ (ዘፍ. ም.5 ቁ.24፣ ዕብ. ም.11 ቁ.5)

ስለዚህ ሚስት አግብቶ ቤት ሠርቶ ንብረት ትዳር መሥርቶ ልጅ ወልዶ እግዚአብሔርን አገለግላለሁ ማለት ከሰው ተለይቶ ከዚህ ዓለም ርቆ በተባሕትዎ ወይም በሥርዓተ ምነና አንድ ወገን ሆኖ እግዚአብሔርን ማገልገል የበለጠ መንፈሳዊነት መሆኑን ተረድቶ መኖር ማለት መሆኑን ከዚህ በላይ ሔኖክ የተናገርነውን ታሪክ ያስረዳል፡፡

ቴስብያዊ ኤልያስም የሄኖክን አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት አብነት አድርጐ በድንግልና ጸዋሚ ተሐራሚ ሆኖ እግዚአብሔርን እያገለገለ በሥልጣኑ ሰማይ ዝናም ለዘር ጠል ለመከር እንዳይሰጥ ምድርም የተከሉባትን እንዳታጸድቅ የዘሩባትን እንዳታበቅል እያወገዘ በመንፈሳዊ ግርማ ታፍሮ ተከብሮ ከኖረ በኋላ እንደሄኖክ በአፍራሰ እሳት በሠረገላ እሳት ወደ ሰማይ አርጓል፡፡ (2ነገ. ም.2÷11)

ሆኖም ለመአስባን ሥርዐተ ተባሕትዎ የጀመረላቸው ሄኖክ ለደናግል ሥርዐተ ድንግልናን ጀምሮ የሰጣቸው ኤልያስ መሆኑን ከዚህ ታሪክ እንረዳለን፡፡

መአስባንና ደናግል በሥርዓተ ተባሕትዎ ጸንተው ንጹሐን የመንፈስ ቅዱስ አርጋብ ሆነው ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ማረጋቸውን የሚያስረዳ ከዚህ በላይ የተናገርነውን የሄኖክና የኤልያስን ምሳሌነት ነው፡፡

ሄኖክና ኤልያስ በህብተ ልደት ሳይታደሉ ባሕታዊ ማለት እንዴት ይስማማል ቢባል ባሕታዊ ማለት ከዓለም የራቀ ማለት ከሆነ ከዓለም ርቀው የሠሩት የብቸኝነት ሥራቸው ባሕታውያን ያሰኛቸዋል ብለን እንመልሳለን፡፡

እንዲሁም የእግዚአብሔር አገልጋይ (ካህን) ሆኖ ጠጉሩን ሳይላጭ፣ ጥፍሩን ሳይቆርጥ ጠጅ ሳይጠጣ በስንዴ በወይን እያስታኮተ የኖረና ርእሰ ባሕታውያን የሆነ የመልከ ጼዴቅን ታሪክ ለዚሁ ደጋፊ እናደርገዋለን፡፡ (ዘፍ.ም.14÷8-23፣ ዕብ. 7 ÷1)

በዚያውስ ላይ የሄኖክና የኤልያስ ብሕትውና የዘመነ ሐዲስ ባሕታዊ እንደምን ያስረዳል? የሚል ቢኖር በዘመነ ብሉይ የሠራቸውን ?ሥሩን ሕግጋት በዘመነ ወንጌል በሠራቸው ስድስቱ ሕግጋት አጽንቶ አንድ ሕግ እንደሰጠ ሁሉ ከመአስባንና ከደናግል ለመረጣቸው ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትና ለሰባ ሁለቱ አርድእት መሠረትነት የሥልጣን መዓርግ ሰጥቶ መአስባንና ንጹሐን ደናግል በመባል ተሰተካክለው መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሱ አድርጓልና የሄኖክ ተባሕትዎ ጀማሪነት ለመአስባን የመልከ ጼዴቅና የኤልያስ ድንግልና ጀማሪነት ለደናግል አብነት ወይም መሪ መሆኑን እስከ አሁን ተያይዞ እንደመጣ እንረዳለን፡፡

ዮሐንስ መጥምቅም ሄኖክንና ኤልያስን አብነት በማድረግ፣ ሠላሳ ዘመን በገዳም ተወስኖ እህል ሳይበላ የግመል ጸጉር ለብሶ ወገቡን በጠፍር መታጠቂያ ታጥቆ የማርና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ በንብረ ተባሕትዎ ጸንቶ ኖሯል፡፡ (ማቴ.ም 3÷4፣ ሉቃ.ም. 10÷15)

ሥርዓተ ምንኩስና እንዲህ በመንፈሰ እግዚአብሔር የተመራ ሲሆን፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ





በመዋዕለ ስብከቱ « ቤቱ ወንድሙንና እህቱን አባቱንና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን ንብረቱን ትቶ በስሜ አምኖ የተከተለኝ የዚህን ሁሉ መቶኛ እጥፍ ያገኛል የዘለዓለም ድህነትም ያገኛል »ብሎ ስለ መዓርገ ምንኩስና ትክክለኛ ትርጉም ሰጥቶ የተናገረውን ቃል መሠረት በማድረግ ይኸውና በየገዳማቱ በሺህ የሚቆጠሩ መናንያን መነኮሳት ይገኛሉ፡፡ (ሉቃ.ም. 9÷62)

የሰው ህብቱ ልዩ ልዩ ስለሆነ ግን የተቻለው በድንግልና መንኩሶ እንደ ኤልያስ እግዚአብሔርን ያገለግላል ያልተቻለው እንደ ሄኖክ ቤት ሠርቶ ሚስት አግብቶ ሕፃናት ወልዶ ቀጥቶ አሳድጎ በዚህ ዓለም በተባሕትዎ ይኖራል፡፡

እንዲህ ማለት ከሐዋርያት እንደ አንዱ ሆኖ ወይም ሐዋርያትን አብነት አድርጎ ቤቱን ንብረቱን ሚስቱን ልጆቹን ይተውና የምናኔ ሥራ ይሠራል ማለት ነው፡፡

እንግዲህ የሚያስቀናው ዕድል የትኛው ነው? እንደ አባቶቻችን ሐዋርያት ቤቱን፣ ንብረቱን ሚስቱን ልጁን ትቶ ኑ ተከተሉኝ ያለውን ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል የመስቀሉን መሸከም የሚያመለክተው አስኬማን ተሸክሞ ቅዱስ ጴጥሮስን መምሰል ነው? ወይስ ሚስት አግብቶ የዕቃ ቤቱንም ቁልፍ ይዞ በዕቃ ቤቱ ያለውን ገንዘብ እየሠረቀ ለሚስቱ የሰጠ ይሁዳን መምሰል ነው የተሻለው?

እንደ አብርሃም እንደ ኢዮብ በዚህ ዓለም ገንዘባቸው ሰማያዊ ክብርን ዋጅተውበትና ከእግዚአብሔር ጋር ተወዳጅተውበት ያለፉ አንዳንድ ደጋግ ሰዎች ምንም ባይታጡም ቤት ንብረት ይዞ በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ሰዎች ይልቅ ራሱን ከዚህ ዓለም ለይቶ በእውነተኛ መንፈሳዊነት የተወሰነ ሰው ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በበለጠ ማገልገልና ማስደሰት እንደ ሚቻለው የታወቀ ነው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ ሲያስረዳ « እኔ ያለ ጎዝን ልትኖሩ እወዳለሁ ሚስት ያላገባ ሰው በሚያስደስተው ገንዘብ እግዚአብሔርን ያስበዋልና፡፡ ሚስት ያገባ ግን ሚስቱን በሚያስደስታት ገንዘብ የዚህ ዓለም ንብረት ያስባልና እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔርና የሰው ፈቃድ ተለያየ? » ብሎ የዚህ ዓለም ንብረት ለጽድቅ ሥራ እንቅፋት መሆኑን ገልጦ ተናግሯል (1ቆሮ. 7፣37)

እስከዚህ ድረስ የተዘረዘረው ቃለ ሐተታ ስሙ በበለጠ እግዚአብሔርን የሚያስደስትበትን ምግባረ ምንኩስና ለመግለጥ ነው እንጅ ጥንት አዳምና ሔዋን ወንድና ሴት ሁነው መፈጠራቸውን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል፡፡ ባልና ሚስት አንድ አካል ይሆናሉ፡፡ እንዲህ ከሆነ አንድ አካል እንጂ ሁለት አካል አይባሉም፡፡ እግዚአብሔር አንድ ያደረጋቸውን ሰው አይለያቸውም፡፡ ከዚህስ አስቀድሞ በኦሪት የተጻፈውን አልተመለከታችሁምን?» ብሎ ማስተማሩን በመዘንጋት አይደለም፡፡ ኦሪት ዘፍ.ም2.-24፡ ማቴ.ም. 19-4፡፡

## ስለ ልብሰ ምንኩስና ጥንታዊነትን የያዘ ምሳሌ

1 የብሉይ ሊቀ ካህናት በውስጥ እጀ ጠባብ በላይ እጀ ሰፊ፣ ከዚያ በላይ ደግሞ እንደ መብርህት ያለ ይደርብ ነበር፡፡ ይህንንም ለብሶ አፍአዊ መሥዋዕት ይሠዋና አፍአዊ ኃጢአትን ያስተሠርይ ነበር፡፡ መነኮሳትም እንዲህ ያለ ልብሰ ምንኩስና ለብሰው ውሳጣዊ መሥዋዕትን ይሠውና ውሳጣዊ ኃጢአትን ያስተሠርያሉ፡፡

2 እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ኩፋት ደፍተው፣ በሎታ ይዘው ፣ ዝናር ታጥቀው ጫማ አዝበው እንደ ተነሡ መነኮሳትም እንዲህ ያለ ልብሰ ምንኩስና ለብሰው በምናኔ ወይም በሞት ከዚህ ዓለም ይለያሉ፡፡

3 መነኮሳት ልብሰ ምንኩስና ለብሰው ረቂቅ ጠላታቸው ሰይጣንን ድል በነሡ ጊዜ ሥላሴ የብርሃን ካባ ላንቃ ያለብሷቸዋል፡፡

ይህም አንድ የበቃ መነኩሴ እንዳየው ነው፣ የበቃ መነኩሴ ሦስት የብርሃን ካባ ላንቃ ሲወርድ አይቶ መልአኩን ቢጠይቀው መልአኩም ከሦስቱ የብርሃን ልብስ አንዱ ባሕታዊ ዘበሕድአት፣ ሁለተኛው

www.ethiopianorthodox.org

ድውይ ዘበአኵቴት፣ ሦስተኛው ረድእ ዘበጥብአት የሚያገኙት ክብር ነው ብሎ አስረድቶታል።

ይኸውም በየዋህ ጳውሊ ቃል ተገልጧል። የዋህ ጳውሊና አባ እንጦንስ በፈቃደ እግዚአብሔር ተገናኝተው ነገረ እግዚአብሔርን እየተነጋገሩ ከሰነበቱ በኋላ የዋህ ጳውሊ በአባ እንጦንስ ራስ ላይ ቆብ አይቶ አባ እንጦንስን ይህን ከማን አገኘኸው ብሎ ጠየቀው።

አባ እንጦንስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰጠኝ አለና በፈጣሪው ፈቃድ እንዳገኘው ገለጠለት። በዚህ ጊዜ የዋህ ጳውሊ የጌታን ቸርነት እያደነቀ ሰውን በሕገ ልቡና ይጠቀም ብሎ ፈጠረው፣ በሕገ ልቡና መጠቀም ባይሆንለት ሕገ አሪትን ሠራለት፣ በዚያውም መጽደቅ ባይቻለው ፣ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሕገ ወንጌልን ሠራ፣ ሥጋውን ደሙን ሰጠ። ዛሬም ለሰው መጽደቂያ የሚሆን ይህን ምክንያተ ድኂን አመጣ? እያለ በተመስጠ እግዚአብሔርን አመሰገነ።

ወዲያውኑ አባ እንጦንስ ይህ መዓርገ ምንኩስና በእኔ ብቻ የሚቀር እንደሆነ ወይም ለሌሎች የሚተላለፍ እንደሆነ ወደ እግዚአብሔር አመልክትልኝ ብሎ ለመነው።

ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ወደ ፊት በጸጋ ምንኩስና የሚወለዱት ደጋግ ሰዎች በብቃት ተገልጠውለት ደስ ብሎት ገጹ ብሩህ ፈገግታ እያሳየ ስለ ወጣ ምን ተገለጠልህ ብሎ ጠየቀው።

የዋህ ጳውሊም ጽዕድዋን አርጋብ በጠፈር ሞልተው እንተ እየመራኻቸው ተከትለውህ ሲሄዱ አየሁኝ አለው።

ምድርናቸው? ብሎ ቢጠይቀው እኒህማ በቆብ የምትወልዳቸው(የምተካቸው) ንጹሐን መነኮሳት ናቸው ብሎታል።

ግብረ ምንኩስናም እንዲስፋፋ የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ አባ እንጦንስ በእንደዚሁ ያለ መንፈሳዊ ጸጋ ተቃኝቶ ሥርዓተ ምንኩስናን በበለጠ ለማደስና ርእሰ መነኮሳት ለመሆን በመመረጡ ለአባ መቃርስ አመነኰሳቸው አባ መቃርስ ለአባ ጳኩሚስ አባ ጳኩሚስ ለአባ ቴዎድሮስ አባ ቴዎድሮስ አባ አረጋዊን ሥርዓተ ምንኩስናን እያስተማሩ ትሩፋት እየሠሩ በምናኔ በገድል ተክተዋቸዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተሰዓቱ ቅዱሳን በአፄ አልአሜዳ ዘመነ መንግሥት 486 ዓ/ም ከመጡ ወዲህ አባ አረጋዊ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ አበ መነኮሳት ይባላሉ፡ ገዳምን ለመጀመሪያ ጊዜ የመሠረቱ አባት ናቸው። ከዚያ በመቀጠል ብዙ ቅዱሳን የነሱን ፈለግ በመከተል ሥርዓተ ምንኩስናንና ገዳማትን አስፋፍተዋል በኢትዮጵያ የአንድነትና የቁራት ገዳማት ከ4000 መቶ በላይ አሉ። የሚከተሉት ናቸው።

ከዚህ በኋላ በዚህ ቆብ እንጦንስ መቃርስን፣ መቃርስ ጳኩሚስን፣ ጳኩሚስ ጳላሞንን፣ ጳላሞን ቴዎሮስን፣ ቴዎሮስ ሮማዊ አረጋዊን ይወልዳሉ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ መነኮሳት እንደ ማር፣ እንደ ቅጠል በዝተው ተነሥተዋል። ይሩማሊስ ጳላድዮስ የሚባሉ ሁለት ሊቃውንት መነኮሳት ከግብፅ ተነሥተው አገር ላገር እየዞሩ የአበውን ዜና ያሉትን ከቃላቸው፣ የሞቱትን ከአርድዕቶቻቸው፣ እየጠየቁ ጽፈዋል። መጽሐፉንም ሲጽፉ ቃለ አበው፣ ዜና አበው፣ ካልዕ ዜና፣ ሣልስ ዜና፣ ራብዕ ዜና፣ እያለ ጽፈውታል። ሙሉ ታሪኩ ከፊልክስዮስ መቅድም የተወሰደ ስለሆነ ከዚያ መመልከት ይቻላል።

በዚህ መሠረት የተጀመረው የምንኩስና ሕይወት በጠቅላላ በኦርቶዶክስ አማኞች ዘንድ ትልቅ ደረጃን ይዞ ይገኛል። የአባ እንጦንስና የአባ ጳኩሚስ ፣ደኛ በ325 ዓ/ም የምንኩስናን ደንብና መመሪያ ሥርዓት ጻፈ። የምንኩስና ኑሮ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ማገልገል፣ ሕገ ምንኩስናን መጠበቅ፣ ከማናቸውም ዓለማዊ ኑሮ መከልከል፣ እንደሆነ አስገንዝበ። መነኮሳት የማይለዋወጥ ዘላቂ የሆነ ችግርን ፈተናን በመታገላቸው ብዙዓን ይባላሉ።

ምን እንልበስ? ምን እንብላ? በማለት ጊዜያቸውን አያባክኑም። ንጽሕናቸውና ጸሎታቸው ወሰን ወደሌለው ደስታ ይወስዳቸዋል፣ «ወረሰዮ ከመ ዕዳው ለዝ ዓለም» ይህን ዓለም እንደ ትቢያ እንደ ጉድፍ አይተውታልና። የተስፋቸው ሐብል እስከ ዘለዓለም ሳይበጠስ ጸንቶ ይኖራልና።

የምንኩስናን ኑሮ በጣም ያስፋፋው የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አትናቴዎስ ነው። የሴቶችንም ምንኩስናና ገዳም የጀመረች የአስፋፋች የአባ ጳኩሚስ እኅት ማርያም የምትባል ናት።

ከዚህ በኋላ ምንኩስና ከምስር ተነሥቶ ወደ ግሪክና ወደሮም፣ ወደሶርያና ወደሌሎች አገሮች ተስፋፋ፣ ተጠናከረ። በአንድነት መሥራት፣ በአንድነት መመገብ፣ ለሁለም አንድ ዓይነት እኩል መልበስ፣ ይህ የኔ ይህ የአንች ሳይባባሉ በሰላም በፍቅር በክብር መኖር ተለመደ። «ወአልቦ ጽኑስ እምውስጠቶሙ ወድመር ኩሉ ንዋዮሙ» በማለት ስለመጀመሪያቹ ክርስቲያኖች ኑሮ እንደተናገረ ሐዋርያው።(የሐዋ. ሥራ 4፣ 32)

የኋላ መነኮሳት ሊቃውንትም ለሕይወታቸው መመሪያ፣ ይሆናቸው ዘንድ ከብሉያት፣ ከሐዲሳት፣ ከሊቃወንት መጻሕፍት በተጨማሪ መጽሐፈ መነኮሳትን ጻፉ። መጽሐፉም በሦስት ይከፈላል። ሲከፈሉ፣

1ኛ/ ፊልክስዩስ
2ኛ/ ማር ይስሐቅ
3ኛ/ አረጋዊ መንፈሳዊ ተብለው ይጠራሉ። ይዘታቸውም
ፊልክስዩስ ዜናቸውን፣ ታሪካቸውን ይናገራል፣

በየገዳማቱ የሚኖሩ አበው መነኮሳት ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ፈቃዱን በመፈጸም የሚፈጽሙት ተጋድሎ እኛ እንድንጸና ያደርገናል ዛሬ ያለው የሚታየው ነገር፣ የሥጋ መሻቱ የዓይን አምሮቱ ኃላፊ ጠፊ መሆኑን ተገንዝቦ ክርስቶስን መከተል እግዚአብሔር አምላክ በየዘመኑ ሁሉ ለሚነሡ ሰዎች በፍቅር፣ በቅድስና መልካም የሆነውን ሁሉ በመሥራት በእምነት ጸንተው ስለሌላ ወንድም ቤዛ በመሆን ሰማዕትነትን በመቀበል አልፈው አስተምረውናል።

ገዳማዊ ሕይወት ምድራዊ ፍላጎትንና የሰይጣን ሽንገላን በመቃወም ሰማያዊ መንግሥትን የሚወርስበት ምስጢር ያለው በመሆኑ ፈተናውም የዛኑ ያህል ይከብዳል።

# ክፍል 2

## ወጣኒ

አንድ ሰው ሀሊናውን ለምኖና አነሳሥቶት ወደ ገዳም በሚገባበት ወቅት በገዳሙ ሕግ ከየትም ይምጣ ከየት ማንም ይሁን ማን እግሩን አጥበው ማረፊያ ሰጥተው ይቀበሉታል። እስከ ሰባት ቀንም ማንም አይጠይቀውም ለጠበል ከመጣ ሰባት ቀን ተጠምቆ ወደ መጣበት ይመለሳል፣ ለምንና ከሆነም ከሰባት ቀን በኋላ የገዳሙ መጋቢ ከየት መጣህ ለምንስ መጣህ ብሎ ይጠይቀዋል። ነገር ግን ሰባት ቀን ሙሉ ለምንም ይምጣ ለምን ምግቡና መኝታው ሁሉ ይሰጠዋል።



ለምንና ከሆነ ከመጣበት ቦታ ማለትም ገዳም ከሆነ ከገዳም ከትምህርት ቤት ከሆነ ስሙን በመግለጽ እንዲህ "ለ ቦታ መጣሁ ይላል ለምን? መጣህ? ሲሉት አባቶች እናንተን መስየ በዚህ ቅዱስ ገዳም ለመኖር መጣሁ ይላል፣ ወዲያውኑ መጋቢ ወደ በላይ ኃላፊዎች ያቀርበዋል አዲስ የመጣ መናኝ ነው ብሎ።

ከነሱ የሚነገረው ይህ ቃል ነው ወንድማችን በዓለማችን እንደ ገዳም ያለ ፈተና የሚበዛበት ቦታ የትም የለም ሰብአዊ ፈተና ተሰባስቦ የሚገኘው በገዳም ነው ስለሆነም አትችለውምና ወደ መጣህበት ብትመለስ ይሻልሃል ምክንያቱም (ብዙን ሕማሞሙ ለጻድቃን) ማለት የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው በተባለው መሠረት፣ በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ሰዎች በምናኔ ወደ ገዳም በገቡ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ፈተና የበለጠ ክብደት አለውና። ስማ ልጃችን አባቶች በዚህ ገዳም የሚኖሩት የዚህ ዓለም ትዝታ የሚያደርስባቸውንና ከዚሁ ከገዳሙ የሚቀበሉትን ፈተና ችለውና ታግሰው ነው።

አባቶች የሚዋጉት ከዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ከረቂቃን አጋንንትም ጋር ጭምር ከመዋጋት አቋርጠው አያውቁም ጦርነቱም እስከ ዕለተ ሞት ድረስ የሚያከትም አይደለም፣ በጠቅላላው በገዳም በመናንያን ላይ የሚደርሰው ፈተና እጅግ ብዙ ነው በውነቱ ወንድማችን ወደ መጣህበት ብትመለስ የተሻለ ነው ይሉታል።

የወጣኒው መልስ አባቶች እናንተን ያስቻለ መድኃኔዓለም ያስችለኝ እናንተን ለመምሰል ቆርጬ ስለመጣሁኝ አልመለስም-ይልቅስ ፈቃዳችሁ ይሁንልኝ ብሎ ይለምናቸዋል። እነርሱም መክረው በል ከዛሬ ጀምሮ ተቀብለነሃል ይሉታል።

ከዚች ሰዓት ጀምሮ ሥራ ይመደባል በገዳም ሥራ ክቡር ነው ከፈተና መታገስን ያለማጉረምረምና ያለመታከት መታዘዝን፣ በተለያዩ ሥራዎች በተለያዩ ገድሎች ሥጋን ማድከም ሕርመትን፣ ጾምን መለማመድ አለበት።

እነዚህን ሁሉ ለማድረግ የማይሆንለት ከሆነ ከወዲሁ ምርጫውን ማስተካከል አለበት በገዳሙ።

በተለያየ የሥራ ቦታ አትክልት በብዛት አሉት በነዚህ ቦታዎች የሚመደብ ሰው አትክልት መትከል፣ መኮትኮትና ውሀ ማጠጣት ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተግባራት ማከናወን በቦታው ከሚኖሩ መሰሎች ጋር በመስማማትና መቲረ ፈቃድን በማሳየት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ማገልገል ይጠበቅበታል።

በዚህ ጊዜ ጠባዩና ችሎታው አፍቅሮ ቢጽነቱ የሚመዘንበት ነው ልክ እንደ አባ ዮሐንስ ሐሊር ትዕግስትን ይጠይቃል።

አባ አሞይ የደረቀ እንጨት ተክሎ ለምልማ እስክ ታፈራ ድረስ ውኃ እንዲያጠጣት ለአባ ዮሐንስ አዘዘው አባ ዮሐንስም ያለማጉረምረም በትሕትና በመቲረ ፈቃድ በሥራ ሁለት ምዕራፍ ያህል ከሚርቅ ቦታ በቀን ሁለት ጊዜ ውኃ እያመላለሰ ያጠጣ ጀመር በሦስተኛው ዓመት ያች እንጨት ለምልማ አብባ ያማረ ፍሬ አፈራች።

አባ አሞይ በዮሐንስ ታዛዥነት እጅግ ተደሰተ ፍሬውን ለቅሞ ለገዳሙ ማኅበር እንካችሁ ይህ የታዛዥነት ፍሬ ነው እያለ ሰጣቸው።

የመነኮሳት ምግብ ዳቤ ወይም (መኮሬታ)፣ ቋርፍ (ወይም) ሥራሥር ተቆፍሮ የሚገኝን ንፍር፣ ቅጠላ ቅጠል፣ ቆሎ የመሳሰሉትና አትክልት እንደገዳሙ ሁኔታ ሥርዓት እህልም ቅጠላ ቅጠል በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ከቀኑ በ9 ሰዓት ወይም በ3 ቀን አንድ ጊዜ ብቻ የሚመገቡም አሉ። ለምሳሌ አትክልት የሚመገቡ መነኮሳት አትክልቱን ግማሹ ቀን ግማሹ ሌሊት በፈረቃ ነው ውኃ የሚያጠጡት ታድያ በዚህ እህልም ባለ በረኻና አራዊት በበዛበት ቦታ በሌሊት ተነሥቶ ባትሪን በመጠቀም ሙሉውን ሌሊት ሲያጠጡ ማደር በጣም ከባድ ነው አንዳንድ ጊዜ ባትሪ በሚያልቅበት ጨረቃም በሌለችበት ወቅት እየዳበሱ ጨለማውን ከተለያዩ ዘንዶችና ነብር አሳማ ጋር የሕይወት መሥዋእትነት በመክፈል የሚሰራበት ገዳም ነው።

ዮሐንስ በልቡናው ዘወትር እግዚአብሔርን ያስብ ነበር ለአንድ አፍታ ያህል እንኳ ከማሰብ አያቋርጥም ነበር ቅዱስ አራራ አትክልተኛው/ወንዘኛ/ ተብሎ ይጠራል ነገር ግን እንደገዳማቱ ህግና አኗኗር

www.ethiopianorthodox.org



አፉ ቃለ እግዚአብሔርን አያቋርጥም አንዳንድ ቦታ ላይ በጋራ የሚሠራበት ነው በሚያጠጡበት ጊዜ ድምጻቸውም አይሰማም በነገራችን ላይ ውኃ የሚያጠጡት በመሸከም አይደለም በመስኖ ነው፡፡

ወንዘኛው ወይም አትክልተኛ ሌሊት ሲያጠጣ ያደረ ጥዋት የሥራ ደወል በሚደወልበት ጊዜ ደከመኝ ሳይል ከማኅበር ጋር ወደ ሥራ ያመራል በተገባር ቤትም ይሁን እንጨት መሸከም የተገኘውን ሥራ ይሠራል፡፡

በወጣኒነት ጊዜ ጾር ሳይጠፋላቸው ዲያብሎስ በልዩ ልዩ ዓይነት ጾር እንዳይዋጋቸው ማለትም የትዕቢት ጾር ይህንን ሠርተናልና አክብሩ አመስግኑን ሳይሉ በጥብአት ዲያብሎስን ድል በማድረግ የምንኩስናን ሥርዓትና ጠባይ ሀ. ብለው ይማሩታል ራስን የመማዝት ጠባይ መላ ሕዋሳቱን ጠብቆ በልቡናው ተዘክሮተ እግዚአብሔር ሲይዝ ነው፡፡

በተለይ ለወጣኒ አፍአዊና ውሳጣዊ ሕዋሳትን መሰብሰብ የሚገባ መሆኑን አበው በደንብ ይመክራሉ፡፡

ሰው አብዝቶ ሕዋሳቱን በገፃ ቁጥር በልቡናው የሚመላለሱ ምክንያቶች ከውስጡ እየጠፉ ይሄዳሉ በአንድነት ገዳማት ከዕለት ምግብ ጀምሮ ምንም ዓይነት የግል ንብረት አይፈቀድም ልብስ እንኳ ለአንድ መናኝ በየስድስት ወሩ ግማሽ ጣቃ አቡጀዴ ይሰጠዋል እንጂ ሌላ የሚያገኘው የለውም፡፡

ቤትም ቢሆን በማኅበር ፈቃድ ይሰጠዋል መሥራት የሚችል ከሆነ ጉልበት ካለው ማኅበር ፈቅዶለት ማንኛውም ወጭ ተደርጎለት በጉልበትም ጭምር ሊሠራለት ይችላል ለዚሁ ሲያስብ የዓመት እረፍት ወስዶ ማለት ፈቃድ አግኝቶ መሆን አለበት፡፡

ሥራ ፈት ሆኖ መቀመጥም በገዳም በጥብቅ የተከለከለ ነው ያለበቂ ምክንያትና ያለመጋቢ ፈቃድ ከገዳሙ ወጥቶ መዘዋወርም አይፈቀድም፡፡ አመጋገብንም በተመለከተ የገዳሙ ቀኖና የሚፈቅደውን የምግብ ዓይነትና መጠን ተላልፎ መመገብ ክልክል ነው፡፡ በሥራ መለገም፣ ስሕተትን መደበቅ፣ በጠቅላላ የዓለማዊና ሥጋዊ ፍላጐት ተገዥ መሆን የገዳማዊ ሕይወት ገጽ ባሕርይ አይደለም፡፡

ከመገልገል ይልቅ ለማገልገል ፈጣን መሆን የገዳሙ ኑሮ ሌላው ግዴታ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ገዳተኑ የሥራ እንጂ የሰነፍ መጠሪያ ቦታ ያለመሆናቸው ግልጽ ነው፡፡



# ክፍል 3

## ሀ. የምንኩስና ሥርዐት በኢትዮጵያ መቼ፣ እንዴት እና በእነማን፣ እንደተመሠረተ

ወጣኒ ምንኩስናን ለመቀበል በገዳማትና በትምህርት ቤት የኖረ ድንግል ከሆነ ሦስት ዓመት በረድእነት ማገልገል አለበት ይኸውም ጠባዩና ችሎታው የሚመዘንበት አነጋገሩ ፣ አለባበሱ፣ አረማመዱ፣ ትሕትናን ፍቅረ ቢጽን፣ ሕዋሳትን መግዛት፣ በፈተና መታገስ ያለማጉረምረም ያለመታከት፣ መታዘዝን እነዚህን ሁሉ መለማመድ አለበት፡፡

በዓለም ከሚኖሩ በተለያየ ምክንያት ወደ ገዳሙ በምነና ሲመጡ ደግሞ አንድ ሰው ከምንኩስና በፊት ሰባት ዓመት በረድእነት ማገልገል አለበት ምክንያቱም ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋልና ነው፡

ምንኩስናን ለመቀበል የሚያስብ ሰው አስቀድሞ የምንኩስናን ሕይወት እንዴት ሊመርጥ እንደቻለ ራሱን መጠየቅ አለበት፡፡ በረድእነት ማገልገል አለበት ምክንያቱም ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋልና ነው፡

አንዳንድ ጊዜ ወደ ምንኩስና የሚመጣ ሰው ከባለ ቤቱ ተጣልቶ ሊሆን ይችላል ወይም ከልጆቹ ተቀያይሞ እንደሆነ አይታወቅምና አመጣጡ በጥንቃቄ ሊጤን ይገባል፡፡ ስለዚህ እየቆየ በሄደ ጊዜ ልጆቼ ታዩኝ ባለቤቴ ናፈቀችኝ ብሎ ወደዓለም ቢመለስ የምንኩስና ምንነትና ዓላማ፣ የመነኮሳቱን አኗኗር ሊከሰቱ የሚችሉ ፈተናዎች ለመቋቋም የሚያስችሉ መርሆች በስፋት ይረዳሉ፡፡

ወጣኒዎች ሦስት ዓመት ገባዕተ ሰርክ ሰባት ዓመት ካገለገሉ በኋላ በምልአተ ጉባኤ ማኅበር ፊት ተጥቀው ቁመው ምንኩስናን እንዲፈቀድላቸው ይጠይቃሉ ማኅበሩም እገሌ ይገባዋል እገሌ ይቆይ ማለት ውሳኔ ይሰጣል በአባቶች ፈቃድና ቡራኬ ምንኩስና ይፈቀድላቸዋል፡፡

ምንኩስና ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ዘመን በ 410 ዓ/ም፣ በአክሱም ዘመነ መንግሥት፣ በአፄ አልአሜዳ ዘመነ መንግሥት ነው፡፡

መጀመሪያ ይዘውት የመጡትም ተሰዓቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን ናቸው፡፡ የመጡበት ምክንያት ሁለት ታሪካዊ መነሻ እንዳለው ይነገራል፡፡

ዓፄ አልአሜዳ ቤተ ክርስቲያን በየቦታው ለማሠራት ሲል ሕዝቡን ያስተምሩልን ገዳማቱን ያመሥርቱልን ብለው እንዳስመጧቸው ይነገራል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በ451 ዓ/ም በኬልቄዶን ጉባኤ በተፈጸመው ስህተት ማለት የሮሙ ልዮን ከመለካውያን ከመርቅያን ከነብርክልያ ጋር በመሻረክ ነገሥታቱ ከማያገባቸው ጉባኤ ጣልቃ በመግባት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አባት በዲዮስቆሮስ ላይ የፈጸሙትን በደል በመመልከትና በማጤን ወደ ኢትዮጵያ በብዛት እንደመጡ ይነገራል፡፡

### ተሰዓቱ ቅዱሳን

የምንኩስናው አምጪትና የገዳማት መሥራቾች ከሆኑት አባቶቻችን መካከል ዋነኞቹ ዘጠኙ ቅዱሳን ናቸው፡፡ ስማቸው እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

1 አባ አሌፍ ዘቂሳርያ አሌፍ በግእዝ ፊደል አንደኛ መጀመሪያ የመጣ ማለት ነው

2 አባ ጽሕማ ዘአንጾኪያ፣ ጽሕማ ማለት ጢማም ማለት ነው

3 ዘሚካኤል (አባ አረጋዊ)፣ ሮም ቁስጥንጥንያ አረጋዊ ማለት ሽማግሌ ማለት ነው

www.ethiopianorthodox.org

4 አባ አፍጹ ታናሿ ሶርያ መናፍቃንን እየገሰጸና እየዘለፈ ስላስቸገራቸው አፈ ፅጹ ብለው ሰየሟቸው ይባላል
5 አባ ይስሐቅ (ገሪማ)፣ ሮም ቆስጥንጥንያ ገሪማ ማለት የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ሥራ የሚሠራ ማለት ነው
6 አባ ሊቃኖስ ዘቁስጥንጥንያ፣ ሊቃኖስ ማለት በጣም የተማረ ማለት ነው
7 አባ ጉባ ዘቂልቂያ፣ ዘቂልቂያ፣ ጉባ ማለት ተራራ የሚያህል በጣም የሚያስፈራ ማለት ነው
8 አባ ይምዓታ (የማታ) ዘቆስያ፣ ይምዓታ ማለት በኋላ፣ ማታ የመጣ ማለት ነው
9 አባ ጳንጠሌን ዘቁስጥንጥንያ፣ ጳንጠሌዎን ማለት በክሪክ ቋንቋ ሱርሱሪ ወይም ልብስ ማለት ነው፣

የጻድቁ አቡነ ገሪማ ሥዕል

እነኚህ ዘጠኙ ቅዱሳን የምንኩስናን ኑሮ በኢትዮጵያ መሠረቱ፡፡ በተለይ መጀመሪያ መጥተው ባረፉበት በትግራይ ሀገረ ስብከት በስማቸው የተሠሩት ገዳማት ይገኛሉ፡፡ ከብዙቹም አንዱ የአቡነ አረጋዊ ገዳም ደብረ ዳሞ ነው፡፡ ይህም ገዳም ታሪካዊና ዝነኛ ሲሆን በርከት ያሉ መናንያን የተገኙበት አውንም ያሉበት ገዳም ነው፡፡

በዚህም ታላቅ ገዳም አባቶች ከመላ ኢትዮጵያ እየመጡ ከአቡነ አረጋዊ ከዊነ ምንኩስናን፣ ሥርዓተ ገዳምን እያጠኑ፣ እየመነኮሱ እነሱም ብዙ ገዳማትን መሠረቱ፡፡ ከእነዚህም እነ ዮሐንስ ከማ፣ እነ ኢየሱስ ሞዓ ፣ እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ መድኃኔነ እግዚዕ ዘደብረ በንኮል ፣ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ ሳሙኤል ዘወገግ ፣ እንደ ማህበረ ሥላሴና ቶማስ ዘምድረ ሃይቅ የመሳሰሉት ቅዱሳን ይገኙበታል፡፡ የመሠረቷቸውም ገዳማት ዛሬም በጉልህ ይታወቃሉ፡፡ የአባ ኢየሱስ ሞዓ ገዳም በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በአምባሰል ወረዳ ሐይቅ ገዳም ይገኛል፣ በዚህም ገዳም ብዙ ቅዱሳን በመንፈስ ተወልደውበታል የመጀመሪያው ወንበር ሰጥቶ የሚል የቅጽል ስም አለው፡፡





ታዋቂውና ዝነኛው ደራሲ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ምሥጢር የተገለጸላቸው በዚሁ ቦታ ነው፡፡ እነ አቡነ ተክለሃይማኖት፣ እነ አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ፣ እነ በጸሎተ ሚካኤል እነ ሂሩተ አምላክ እና ለንግሥና መዓርግ የበቁት አፄ ይኩኖ አምላክም ከዚሁ ገዳም ተምረዋል፡፡ ይህ ገዳም የመጀመሪያ ታላቅ ትምህርት ቤት ነው፡፡ አንድ ሰው ምርጫውን የሚመርጠው፣ የሕይወቱንም መንገድ የሚወስነው ከተማረ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤት ገብቶ መማር የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ምርጫው፡፡ ከተማረ ካወቀ፣ ከተረዳ በኋላ የራሱ ምርጫ ይሆናል፡፡ ወደ ምንኩስና ሕይወት የሚሄዱትም መጀመሪያ በመማር የትሩፋት ሥራ በመሥራት ነው፡፡

የጻድቁ አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ

እንግዲህ የገዳም መሠረቱ፣ የኑሮ ሕይወቱ ከላይ እንደተገለጠው የትምህርት፣ የተአምራት፣ የፈውስ፣ የበረከት፣ የሰላም የአንድነት፣ የፍቅር ቦታ መሆኑ ነው፡፡ በአንድና በሁለት የተጀመረው ገዳም ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ1000 በላይ ገዳማት ይገኛሉ፡፡ የመነኮሳቱና የመነኮሳይያቱ እንዲሁም የባሕታውያኑ ብዛት ከመቶ ሺህ በላይ ይሆናል፡፡

## በቆብ የምንኩስና መዓርግ በመቀበል መወለድ

ይህ ክፍል በአርእስቱ እንደተገለጸው በቆብ የምንኩስና ልደት መቀበል ነው፡፡ ይህም ልደት በምንኩስና የሚወለዱት ልደት የሚያደርጉት ገቦ ነው፡፡ ምንኩስናም ማለት በንጽሕናና በድንግልና ሁኖ በጾም በጸሎት በስግደት በአጽንዖ በዓት በትህርምት በአገልግሎት ተወስኖ መኖር ነው፡፡ ከእነዚህ ገዳማውያን አበው በምንኩስና ሥርዓትና ቀኖና አስኬማ የተወለዱ አባቶች ጳጳሳት ሊቃነ ጳጳሳት ይገኛሉ፡፡

ለዐሐይ መከላከያ ከራሳቸው ላይ የሚደፉት ቆብ ነበራቸው ይባላል፡፡ ለሰው አጥፊ የሆነውን ነገር ሁሉ አይሠሩም፣ ለእንስሳት ሁሉ የሚራሩ የሚያዝኑ ነበሩ፡፡ ጸሐፍት ፈረሳውያን ሰዱቃውያን የተባሉ ሁሉ ከነቢያትም ወገን እነ ኤልያስና እነ ዮሐንስ መጥምቅ የአነርሱ ወገን ናቸው ይባላል፡፡ ዮሐንስ መጥምቅም ይከታተል የነበረው የእነሱን ሕግና ሥርዓት ነበር፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ

እነርሱም ራሳቸውን የማይላጩ፣ የሚያስክር መጠጥ የማይጠጡ፣ ከሁሉ ነገር የተከለከሉ፣ ናዝራውያን ነበሩ፡፡ ናዝራዊ ማለት ከክፉ ነገር ሁሉ የተከለከለ ማለት ነው፡፡ ቋንቋው የዕብራይስጥ ነው፡ ናዚር ወይም ናዛር ማለት ከክፉ ነገር ሁሉ የተከለከለ፣ ስእለት ወይም ብፅዓት ያደረገ፣ ሕይወቱን፣ ሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጠ፣ በሰውነቱም የተቀደሰና የተለየ ሰው ማለት ነው፡፡

እንደነ ሶምሶን እንደነ ሳሙኤል እና ዮሐንስ መጥምቅ መሳ.13:1 1ኛሳሙ.11፣26-28 ሉቃ. 1:15 ናዝራውያን ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በተወለደበትና ባደገበት ናዝሬት ኢየሱስ ናዝራዊ ይባላል ወይም ተብሎ ይጠራል ናዝራዊ መባሉ ናዝሬት በመኖሩ ነው፡፡

አዳምን ከነልጆቹ ከኮነኔና ከሞት እንዲያድነው ጽኑ ተስፋና ብፅዓት ሰጥቶ የነበረ ጌታችን መድኃኒታችን ናዝራዊ ተባለ «ወበአ ናዝሬተ ኀበ ተሀፅነ ከመ ይሰመይ ናዝራዊ ናዝራዊ ይባል ዘኀደ ናዝሬት ገብቶ አደረ» ማቴ 2:23 ለእኛም ተባሕትውንም ሆነ በገዳም መወሰን፣ መጾም፣ መጸለይን፣ መስገድን፣ በገዳም መኖርን፣ የአስተማረን መምህረ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ክርስትናን የመሠረተ እርሱ ነውና፡፡ «ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ቅዱስ ገዳመ ከመ ይትመከር እምዲያብሎስ»

«ወጾመ አርብዐ መዓልተ ወአርብዐ ሌሊተ ዐርባ መዓልትና ዐርባ ሌሊት ጾመ፡፡» ሠራዔ ሕግ ነውና ሥራውን በገዳም መሠረተ፡፡ በገዳም ምን መደረግ እንዳለበት አስተምሮና ሠርቶ ካሳየ በኋላ ለማስተማር በዓለሙ በሚገኙት ሁሉ አስተማሪ እንዲሆኑ ሐዋርያትን መረጠ፡፡ መጀመሪያ ጴጥሮስንና እንድርያስን ቀጥሎም ያዕቆብንና ዮሐንስን ጠራቸው፡፡ «ዓለሙን ተውት እኔን ተከተሉኝ» በማለት ጠራቸው ማቴ.4:1 ሉቃ. 4:1-2 ማር.1:12

ገዳመ ቆሮንቶስ

አባቱን እናቱን ዘመድ አዝማዱን እህት ወንድሙን ትቶ ያልተከተለኝ የኔ ደቀመዝሙር ሊሆን አይችልም አላቸው፡፡ እነሱም ሁሉንም ትተው ተከተሉት ማቴ. 4:22፣19:27 ቅዱስ ጴጥሮስም የጠየቀው ስለዚህ ነበር እንዲህ ሲል እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፡፡ «ምንተ እንከ ንረክብ የምናገኘው ጥቅም ምንድን ነው?» አለው ጌታም እንዲህ ሲል መለሰለት «አማን አማን አብለክሙ እሰ ተለውክሙኒ አመ ዳግም ልደት ትንትሙ ትነብሩ ዲበ ዐሠርቱ ወክልኤቱ መናብርት» አላቸው፡፡

ይህም ማለት በዳግም ምጽአት ፍርድ ሲሰጥ በክብር ሁናችሁ ታያላችሁ አላቸው፡፡ ደስታችሁ ዋጋችሁ ምናኔያችሁ ያስተማራችሁት ፍሬ በዚያን ጊዜ ይገለጣል አላቸው፡፡ የሐዋርያት ጥሪና ምርጫ ተልእኮ ዳም ገብቶ፣ በዓት አጽንቶ፣ መንኖ፣ ከዓለም ርቆ መኖር አልነበረም፡፡ ዓለሙ አስተማሪ መካሪ ሚፈልግበት ሰውንም ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኀጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ሚመሩበት ጊዜና ሰዓት (ዘመን) ስለነበር ከዓለሙ ተለይተው በዓለሙ ወስጥ እንዲኖሩ ወንጌልን ስንገበው እንዲዝዙ አደረጋቸው፡፡ ትእዛዙም በጣም ከባድ ነበር፣ «ኢትንሥኡ በትረ ወኢአሃዕነ፣ ወኢቁናማተ፣ በትርም አትያዙ፣ ጫማም አታድርጉ፣ የሥንቅ አቅማዳም አትያዙ፣ በእግዚአብሔር ኢመኑ፣ ሁሉም እንደ እናት እንደ አባት እየሆኑ ይቀበሏቸኋል፣ በሄዳችሁበትም ቦታ ሰላም የሚገባው ዘኢ አካባቢ ማን ነው ብላችሁ ጠይቁ፣ በዚያ ዕረፉ፣ ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት አትዘዋወሩ፡፡» «ይደልዎ ሰራዊ ለዘይትቀነይ፣ ላገለገለ የዕለት ምግቡ ይገባዋልና ሲል 12 ሐዋርያትን መርጦ ላካቸው፡፡» ማቴ10:1 ሉቃ. 9:10

የሐዋርያት ምናኔ ወንጌልን ለማዳረስ፣ በትምህርት በተአምራት በሰዎች ላይ ያለውን ጭንቀት ስጋትና ጥፋት ለማስወገድ፣ እንቅፋት እንዳይሆንባቸው ከዓለሙ እንዲለዩ አደረጋቸው፡፡ ለሚስት፣ ለልጆች፣ ለሀብት፣ ለንብረት ማሰብና መጨነቅ እንዳይኖር ምን ላብላቸው፣ ምን ላጠጣቸው፣ በምን ላስደስታቸው እንዳይሉ ነው ከዓለሙ ነጻ ያወጣቸው፡፡ ስለዚህ የጌታ ትምህርት የገባው ሐዋርያው እንዲህ ሲል ተናገረ «እስመ ዘኢያውስበ ይኄልዮ ለእግዚአብሔር በዘያሠምሮ ለእግዚአብሔር ወዘሰ አውስበ ይኄሊ ንብረተ ዝንቱ ዓለም በዘያሠምሮ ለብእሲቱ፣ ይህም ያላገባ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኘው ገንዘብ ደስ [illegible] ደስ የሚያሰኝበትን ገንዘብ ያስባልና» 1ኛ ቆሮ. 7:32

www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያት



ሐዋርያው «ንዋየ ኅሩየ ረስይከከ ከመ ትጹር ስምየ በውስተ አሕዛብ ስሜን በአሕዛብ ዘንድ እንድታስተምር ልዩ መሣሪያ አድርጌ መርጬሃለሁ» ባለው መሠረት «ወአንስ ሐሰ ሊተ ኢይዜነር ዘአንበለ በመስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ» እኔስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀል እንጂ በሌላ አልመካም «ወበኀኔየ ምውት ዓለም፣ ዓለም በእኔ ዘንድ የሞተ ነው» «ወአነሂ ምውት በኀበ ዓለም፣ እኔም በዓለም ዘንድ የሞትኩ ነኝ» በማለት የዓለም ጭንቀትና ጥበት የሌለበት መሆኑን ገለጠ፡፡ ገላ. 6፡14 የወንጌል ገበሬ የሆኑ ወንጌላውያን ዛሬም ያስፈልጋሉ፡፡ የት ይገኙ? መሳዮች ሞልተዋል፣ ሆነው የተገኙ ግን የሉም፡፡ ካሉም መልካም ከሌሉም እንዲኖሩ ማድረግ የቅዱስ ሲኖዶስ ድርሻ ነው፡፡ ከመንበሩ ላይ አለንና «ሚመክሙ እግዚአብሔር ጳጳሳተ ከመ ትርአዩ ቤተ ክርስቲያኑ ለክርስቶስ እንተ አጥረያ በደሙ» ወአተባ በዕፀ መስቀሉ ተብሎ ተጽፏል የሐ.ሥራ 20:28 ሐዋርያት ከዓለም የተለዩበትን ግዳጅ ተወጡ፡፡ በሮማ ከተማ ወንጌልን ሲመስክሩ በነኔሮን አንገታቸው ተቆረጠ፣ ደማቸው ፈሰሰ፣ አለአግባብ ተስቅለው ሞቱ እነ መጥምቁ ዮሐንስ ለዘፈን ተሸጡ፣ አንገታቸው ተቀረጠ፣ ሀሉም በየሀገረ ስብከታቸው የምናኔ ሥራቸውን ፈጸሙ «ሰማዕተ ኮኑ በሃይማኖት ወበዕንዐ ትዕግሥት» እንዲል፡፡

## ለ/ የመነኮሳቱም መመሪያ የገዳማቱ ሥርዐት

የምንኩስና ሕይወት በትሩፋት የበለጸገ ቢሆንም የሁሉም መነሻ የሚሆኑ መመሪያች አሉት፡፡ ከእነዚህም ዋና ዋናቹ፡-

1. ንጽሕና ቅድስና
2. ተአዝዞ(አሆ በሃሊትን) መታዘዝ፣ እሺ ማለት
3. መንኖ ጥሪትን (ለራስ ወይም ለግል የራሱ የሆነ የራሷ የሆነ ሀብት አለማስቀመጥ)
4. ለጾም፣ ለስግደት፣ ለጸሎት፣ ጠቅላላ ለትሩፋት ጽሙዳን መሆን፣ ለሁሉም ነገር በሰዓት መገልገል ናቸው፡፡



ለመመንኮስ አብዛኞቹ ገዳማት የሚሰጡት ጊዜ ለ3 ዓመታት ብቻ ነው፡፡ ሦስት ዓመት በገዳሙ ማኅበር በሚሰጠውና በሚሰጡት ሥራ ተሰማርተው ይሠራሉ፣ ፈተናውንም ይለምዳሉ፡፡ ከ3 ዓመታት በኋላ ይመነኮሳሉ፣ ማኅበሩን ይመስላሉ፡፡ ከምንኩስናም በኋላ ከመነኮሱበት ገዳም በፈቃዳቸው አይወጡም፣ ለሥራ ጉዳይ ማኅበሩ አዝዟቸው ለከፍተኛ ሥራ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ መርጦዋቸው ካልሆነ በቀር በዓታቸውን ለቀው አይሔዱም፣ ሊሔዱም አይገባቸውም፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት ነው ይህንን ቃል መመሪያ በማድረግ ሥራውን ይጀምራል የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ስቀሉ(ገላ. 5፡22) ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ ገዳማቱ የሚተዳደሩት መናንያኑ ሠርተው በሚያገኙት ገቢ ነው፡፡

ሥራ አለመፍታት ራሱ የምናኔ ሕይወት ሌላው ገጽታ ሲሆን ሥራ ፈትነት ደግሞ የዚህ ተቃራኒ የሆነ ኢገዳማዊ ጠባይ ስለሆነ በእርጅና ወይም በሕመም ምክንያት ለመሥራት የማይችል አቅመ ደካማ ካልሆነ በቀር በተረጅነት እንዲኖር አይፈቀድለትም፡፡ አቅመ ደካማ እንኳን ቢሆን ማኅበሩ ድካሙን አይቶ ከሥራ ነጻ እንዲሆን ካላደረገው በቀር እሱ ራሱ ደክሜያለሁ ፣ ልረፍ ብሎም አይጠይቅም፡፡



ከሁሉ በላይ በገዳማቱ ፍቅር በዝታ ትታያለች አፍቅሮ ቢጽ በዮሐንስ መልእክት በተነገረው ቃል «ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል እግዚአብሔርን ማንም አላየውም እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በኛ ፍጹም ይሆናል» (1ዮሐ ም. 4፡11) በሚለው ቃል መሠረት በአባቶች እንደበት ለወጣኒዎች ምክር ይሰጣቸዋል፡፡

ብፁዕ ቅዱስ በአሕዛብና በክርስቲያን መካከል ባለች ወሰን አገር ኤጲስ ቆጶስነት ተሾሞ ይኖራል፡፡ አሕዛብ ከክርስቲያኖችን በየገዳማቱ ሥርዓተ ምንኩስና የሚሰጠው በገዳሙ ፈቃድ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ በማኅበር ጸሎት በአበምኔቱ ብራኬ መስቀለ ሞት የተባለን አስኬማ ይሰጣቸዋል የአበ ምኔቱ ምክር እንደሚከተለው ነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የበረታችሁ ሁኑ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ካለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር በሰማያዊ ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡

ስለዚህ በክፉ ቀን ለመቃወም፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምታችሁ ቁሙ የክፉን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበት የእምነት ጋሻ አንሡ የመዳን ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው (ኤፌ. 5:12) ልብሰ ምንኩስና ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ በመሆኑ፣ ቆቡ የአክሊለ ሦክ፣ ቀሚሱ የክሳሜዳ፣ ቅናቱ የሐብል ሥጋ ማርያም የማርያም ሥጋ፣ «ወለነሰ መሰለነ በአስኬማሁ» ለአባ እንጦንስ የተሰጠውና በተባህትዎ ሥራው በአለባበሱም እስከ አሁን ለተነሡት መነኮሳት አብነታቸው ነው፡፡

ዛሬ የመነኮሳችሁ አባ አባ ለመባል አይደለም አባቶች ለመምሰል እንጂ ይህንን ገዳም ለኛ ያስረከቡን የላመ የጣመ ሳይቀምሱ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብሱ፣ ጨዋ ጥሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ድምፀ አራዊትን ማርማ ለሊትን ታግሰው፣ ከዓለማዊ ኑሮ ርቀው፣ ከሥጋዊ ግብርና ተድላ ደስታ ተጠብቀው በሥራ ተጠምደው ከሰው ሽክምነት ተላቅቀው፣ ራስን በራስ እየረዱ ዘወትር በጾምና በጸሎት፣ በገድልና በትሩፋት ተጠምደው እግዚአብሔርን በሙሉ ዘመናቸው በማመስገን ልክ እንደ አበው አባቶች መስለው ነው፡፡ ከዛሬ ጀምሮ የማኅበሩ አባላት ሁናችኋል ታድያ የአባቶች አባላትና አካላት ከኃጢአት የራቁ ጽድቅን የሚናፍቁ ሥጋዊ ፈቃዳትን የሚንቁ ለዘለዓለማዊ ሕይወት የተዘጋጁ እንደ አባቶች መሆን ያስፈልጋል ብለው ይመክራሉ፡፡



በገዳማት ከመነኮሰም ቢሆን የረድእነትና የአገልግሎት ተግባር እጥፍ ድርብ ድርብርብ ያደርገዋል እንጂ አይቀንሰውም ተፈቅዶለት ለጸሎት ወይም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ካልተመደበ በተር መንኩሼአለሁ ብሎ ቤት ዘግቶ መኖር አይችልም ከሁሉም የበለጠ የሚታመንበትና የሚጠበቅበት ሥራ ነው፡፡



በተለይ በሰብኤ ወቅት ከፍ ያለ አገልግሎት ይፈጽማል የሌሊቱ ጸሎት የሰርክ ጸሎት መሳተፍ የግድ ነው ይህንንም ሥራ ፈት በመሆን አይደለም ሥራን በማክበር ነው የሚፈጽሙት በአንድ አሳብ ተስማሙ አንድ ፍቅር አንድ ልብ አንድ አሳብ ይኑራችሁ፣ በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ ስእንኳ አታድርጉ ነገር ግን ባልንጀራውን ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር ስለኛ የባርያውን መልክ ይዞ በሰው ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ ለሞት ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ ታዘዘ፡፡ (ፊል. 2:7)፡፡

አባቶች ለኛ ያወረሱን መሪያቸው እግዚአብሔር መሣሪያቸው ጸሎት ሥራቸው ትሩፋት ፍሬአቸው ከን ጹሕ እምነትና ከሥነ ምግባር የተገኘ ገዳማዊ ሕይወት ነው፡፡

አንድ ከማኅበር ተለይቶ በዋሻ የሚኖር መነኩሴ ራእይ በማየቱ የበቃሁ ነኝ ብሎ በልቡ ይታብይ ነበር ምክንያቱም ማር ይስሐቅ ከሰው ተለይቶ የሚኖር መነኩሴ ከወኃ ይጠራል ያለውን ቃል በማሰብ በቅቸአለሁ እግዚአብሔር ይመስገን እነ አባ አገሌ ማኅበር እናገለግላለን ብለው እኔ በለጥጓቸው የሚል መዋፎ ስሜት በሀሊናው ተቀረፀ፡፡



በዋሻ የሚኖር መነኩሴ

ከዕለታት አንድ ቀን የሆነ ድምጽ ሰማ ድምፁም አልበቃህም የሚል ነበር ወደዋሻ ገብቶ አብዝቶ ይጾምና ይጸልይ ጀመር ለሦስት ጊዜ ያህል ስለተናገረው ተደናገጠ ቃሉም አልበቃህም ከበቃህ ከእሾህ ተኛ የሚል ነበር ባሕታዊው ሂዶ ከእሾህ ቢተኛ አልወጋውም እንደበቃ ተማመነ ነገርኩህ በቅቸአለሁ አለ እሾህ ያልኩህ እሾህ አይደለም ሂድ ተመለስ ወደ ማኅበር በረድእነት አገልግል ይለዋል ተመልሶ መጋቢ በመደበው ሥራ ጀመረ የተመደበበት ሥራ ሊቀ አበው ይባላል አረጋውያን በማም የሸመገሉትን ማገልገል ከመጠብ ማቅረብና እስከ ልብስ ማጠብ ድረስ ያለው ነው ታድያ አንዱ የትሂደህ ነው ሲል ሌላው ደግሞ እንዴት የተረገመ ነው መጀመሪያ እኔን አይታዘዝም እኔን ትቶ ከአባ አገሌ ይሄዳል እንዴ? ይላሉ ሌላው ደግሞ መጀመሪያ የመቁነን ወይ የድርጎውን ደወል በሚደወልበት ለኔ ነው ምግብ ማምጣት ያለብህ ሲሉት ጭራሽ አእምሮው ሀረበት ምክንያቱም አረጋውያኑ ለሱ የተመደቡ 10 ይሆናሉ በዚህ ጊዜ ያለመቅቀቱን ተገነዘበ፡፡ አንድ መነኩሴ የሚበቃው በትሩፋትና በአገልግሎት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል

www.ethiopianorthodox.org

ያየሰማው ቃል በዋሻ እያለ አልበቃህም ከበቃህ ከእሾኽ ተኛ ያለኝ ለካ የሰው አንደበትና ነገር ነው ብሎ አመነበት በገዳም አረጋውያን በሁለት ይከፈላሉ ከላይ የጠቀስናቸው በዓለማዊ ኑሮ የነበሩ ልጆች ወልደው አሳድገው ለቁም ነገር አብቅተው ከእንግዲህ ይብቃኝ ብለው ቤት ንብረታቸውን ጥለው ለጾምና ለጸሎት ለንስሐ ከገዳሙ ገብተው ከፍሁምነት ደርሰው እንደነ ሄኖክ ለመጠቀም በአፍራሰ እሳት በሰረገላ እሳት ወደ ሰማይ ለማረግ ነው 2ነገ. 2÷11::

ሌላው ደግሞ «አንሰ እፈቅድ ለክሙ ዘእንበለ ኃዘን ተሀልዉ» እኔ ያለ ኃዘን ልትኖሩ እወዳለሁ (እፈቅዳለሁ) ያላገባ እግዚአብሔርን ደስ የሚሰኝበት ገንዘብ ያስባል 1ቆሮ. 7፣2 ስለሆነም እግዚአብሔርን የሚያፈቅሩ ሕጉንና ትዛዙን አክብረው በንጽሕና ተጠብቀው የሚኖሩ ከመናንያኑ መካከል ከመንፈሳዊ ሕይወት ምልአት ደረጃ ላይ ሲደርሱ በማህበር ፈቃድና ቡራኬ ከገዳሙ አንድነት ሳይለዩ በልዩ ቦታ ተወስነው ለተባሕትዎና ለጸሎት ይመደባሉ ገና በሕፃንነታቸው ራሳቸው ለእግዚአብሔር ያስገዙ ባሕታውያን አባቶችም በሊቀ አበው ታዛዥነት ማንኛውም የሚፈልጉት ገዳሙ የሚፈቅደውን ምግብ ይቀርብላቸዋል::

ባሕታዊ

በአንዳንድ ገዳማት ከፍራፍሬና ከሥራ ሥር በቀር ሌላ ዓይነት ምግብ አይፈቀድም አብዛኛቹ ገዳማት ደግሞ አህል ይመገባሉ ሊቀ አበው ሰዓት ጠብቆ መጠየቅና ምግብ ማድረስ ብቻ ነው ሥራው::

ምግቡ፡ የሚያዘጋጀው ደግሞ መጋቢ ወይም (ተለሽ) ይባላል ሰዓት ጠብቆ ሁሉጊዜ ከሰዓት ሳያሳልፍ ማዘጋጀት አለበት ከቅዳሜና እሑድ በቀር ከዓመት እስከ ዓመት ከቀኑ በ9 ሰዓት ምግብ ይሰጣል ቅዳሜና እሑድ ግን ከሚቱ 3 ሰዓት መቁነን ወይም ድርጉ ይሰጣል:: ይህ ሲሆን(ለተለሽ) የሚረዱም አሉ አርድእት ይባላሉ መታዘዝ በተለያዩ ሥራዎች ትሕትና በተምላበት ሌሊት ቀን ሳይሉ፣ ፀሐይ ብርድ ሳያሰቅቃቸው እንደ ንብ እየተወናጨፉ ገዳሙን የሚያገለግሉ ከዋክብት ብዙ ናቸው::

«እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉ እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው ስለ ሥጋ ማ"ብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና መገዛትም ተስኖታል በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም:: ሮሜ. 8:5::





# ክፍል 4

## የመነኮሳት ልብስ ከዓለማውያን ልብስ ለምን ተለየ?

መነኮሳት «በምድር መላእክት፣ በሰማይ ሰዎች» ናቸው፣ ስለዚህ በዚህ አስተሳሰብ ከዓላማውያን እንደተለዩ ሁሉ በአለባበስም ከዓለማውያን ሰዎች ይለያሉ:

### የመነኮሳት ልብስ፣

ሀ- የማር መልክ ያለው፣
ለ- ብጫ ወይም ወይባ ዓይነት፣
ሐ- ጥቁር ነው::

መነኮሳት እንደነዚህ ዓይነት መልክ ያላቸው ልብሶች እንዲለብሱ ያስፈለገበት (ያዘዘው) የደነገገው ማን እንደሆነ ለማወቅ ሲጠየቅ እንደአተረጓጐሙ የተለያየ ምክንያት ይሰጠዋል::

1ኛ/ መነኮሳት ከዓለም የተለዩ፣ ዓለምን ንቀው፣ ንጽሕ ጠብቀው መኖርን ስለመረጡ በበረሀ ገዳማት ቆርቁረው እየተጋደሉ ፣ እየተፈተኑ በትሕርምት ጸንተው የሚኖሩ በሥጋ የሞቱ በመንፈስ የበረቱ ማለት ሲሆን በዓለማውያን ዘንድ የተናቀና የተጠላ ልብስ መልበስን መረጡ የሚሉ አሉ::

2ኛ/ ጥቁር ልብስ የገዳማውያን መነኮሳት ሲሆን ብጫው ግን የመናንያን(የግሁሣን) ልብስ ነው የሚሉም አሉ፣ በነገራችን ላይ እነዚህ አባቶች ገዳማውያን መነኮሳትና መናንያን (ግሑሳን) ብለን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን::

3ኛ/ ከፍ ብለን ለመጥቀስ እንደሞከርነው መነኮሳት ቦታ መርጠው በአንድነት፣ በፍቅር፣ በወንድማማችነት ሆነው ገዳም መሥርተው በማኅበር ተደራጅተው የሚኖሩበት ሲሆን ባሕታውያን (ግሑሳን) ደግሞ ከገዳም ማኅበራዊ ኑሮ ወጥተው ጭው ካለ በረሀገብተው የሰው ድምፅ ከማይሰማበት አራዊት አጋንንት ከሰለጠኑበት በዋሽ ወይም በጣሻ በቋጥኝ ወይም እግር ከማታስዘረጋ ጎጆ ተኩርትመው ፣ ወይም ቆመው አእምሮአቸውን ሰብስበው፣ ልባቸውን ወደ አንዱ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር አቅንተው ዘወትር በጾም በጸሎት ተወስነው የሚኖሩ ማለት ነው::

4ኛ/ ባሕታዊ ማለት ተባሕተወ፣ ብቸኛ ሆነ፣ ከሰው ተለይቶ ሰው ወደማይደርስበት ቦታ የሔደ ሥጋውን ክዶ ለነፍሱ ብቻ ያደረ ማለት ነው::

5ኛ/ ግሑስ ማለትም ትርጉሙ ከዚሁ ያልተለየ ሆኖ ፍሉስ፣ ፈላሲ፣ ምንም ምን የሌለው፣ ምን ምንም የማይፈልግ፣ ከምን ከምንም ግንኙነት ፍላጎት ሁሉ የተለየው ምላውንም፣ ራቱንም የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ያደረገ ማለት ነው:: ልብሱም ከላይ ከጠቀስናቸው የልብስ ዓይነቶች በጣም የተለየ ነው፣ ይኸውም ስሌን፣ ወይም አጽፍ ነው አጽፍ ማለትም ከለፋ ቆዳ የተሠራ ነው::

የመነኮሳቱ፣ የባሕታውያኑና የግሑሳኑ አኑዋኑዋርና አለባበስ በመጠኑም ቢሆን የጠቆምን ቢሆንም መነኮሳት ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ቀለሞች ያሉአቸው ልብስ እንዲለብሱ የተገደዱበት ምክንያት እንዳለም አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች ይናገራሉ::

ይኸውም ከታላቁ ባሕር በስተደቡብ ምዕራብ፣ ከአፍሪካ አህጉር በስተሰሜን ምዕራብ የሚገኘው የጹሮ ሰው ምስር፣ ያሁኑ ግብጽ ተብሎ በሚጠራው አገር ከ644 ዓ/ም በፊት በሀገሩ ላይ ጥቂት አረማውያን ቢኖሩም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች በብዛት እንደነበሩት ታውቋል::

www.ethiopianorthodox.org

በዚህም መሠረት የከፈሉትንና ያልከፈሉትን ለመለየት ሲሉ ብረት እያጋሉ በግምባራቸው ላይ ይተኩሱአቸው ጀመር፣ ከዚህም ሌላ የክርስትና እምነትህን ከደህ (ጥለህ) የእስልምና እምነት ያዝ እያሉ በግስገደድ በሰይፍና በግርፋት በብዛት ገደሉ እንዲሁም አብያተ ክርስቲያኖቻቸውን እያፈረሱ፣ ንዋየ ቅድሳቶቻቸውን መስጊድ ይሠሩባቸው እንደነበሩ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡፡

በዚህ ችግር ምክንያትም ክርስቲያኖች ምንም ጥቂት ቢሆኑም ከእስላሞቹ ጋር ጦርነት ገጠሙ በኃይል እግዚአብሔርም ብዙውን ጠላት ቢጠርጉትም ከመካከለኛው ምሥራቅ አረቦች እየመጡ ስለተረባረቡባቸው ተሸነፉ፡፡ ከዚህ በኋላማ እስላሞቹ በክርስቲያኖቹ ላይ እጅግ የከፋና የጸና መከራ ይፈጽሙባቸው ጀመር፡፡ በተለይም በ650 ዓ/ም ከሊፍ ኤልሙታዊክል የሚባል የእስልሞቹ መንግሥት በክርስቲያኖቹ ላይ የፈጸመው ግፍ ዘግናኝና አስቃቂ የሆነ ደንብ አወጥቶባቸው ነበር፡፡

ደንቦቹም

1ኛ/ የግብጽ ክርስቲያኖች ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የማር መልክ ያለው ልብስ እንዲለብሱ፣

2ኛ/ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ቤት ላይ

ሀ- ከዕንጨት የተሠራ የዝንጀሮ ቅርጽ ያለው
ለ- ከዕንጨት የተሠራ የሰይጣን ምስል የያዘ
ሐ- የውሻ መልክ ያለው የላአት ምስል በየአብያተ ክርስቲያናቱና በያንዳንዱ ክርስቲያን ቤት ላይ እንዲሰቀል፣

3ኛ/ በየክርስቲያን ቤቱና በየአብያተ ክርስቲያናቱ መስቀልና የመስቀል ምልክት እንዳይኖር፣ ቢኖር፣ ወይም ቢገኝ ደግሞ እጅግ ጽኑና አስከፊ ፍርድ እንደሚያስከተል ጽኑ ማስጠንቀቂያ በየቤቱ እንዲሰጥ አደረገ፡፡

ከዚህ በኋላ ተባርዮን የማያስቀር አምላክ የሁሉንም መብት የሚያስከብር የእስላሞቹ መሪ ተነሥቶ ክርቲያኖቹ በሰላምና በደስታ መኖር ጀመሩ፣ ነገር ግን ከሰላሙ ዘመን በኋላም ከሁሉ የከፋና ጨካኝ የሆነ ኤልሐኪም የሚባል መሪ ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያናቸውን እያፈረሰ የእስላም መስጊዶች ከማድረጉም በላይ፡፡

1ኛ/ የክርስትና ሃይማኖት መሪዎች ማለት መነኮሳትና ተሳውስት ልብሳቸው ጥቁር እንዲሆን፣

2ኛ/ ትልቅ ግንደ መስቀል አሠርቶ ተሸክመው በየመንደሩ እየዞሩ መከራ እንዲቀበሉ፣

3ኛ/ በሰው ሁሉ ዘንድ ውሾች ተብለው እንዲጠሩ፣ እንዲሰደቡና እንዲደበደቡ አደረገ፡፡

ምእመናን በዚህ ዓይነት ተጽእኖና የግፍ አገዛዝ እስከ 4400 ዓ/ም በእምነትና በትእግሥት ችለው ጸንተው ተሸክመው ሃይማኖታቸውን ጠብቀው ተቀመጡ፡፡

በመላዓለም የሰው መብት እየተጠበቀ መምጣቱ ሲታወቅ ግን መነኮሳቱ ጥቁር፣ የማር መልክ ያለውና ብጫ ልብስ መልበስ ጀመሩ፣ ለመከራቸው ማስታወሻ እንዲሆናቸውም በትልቁ ጉንደ መስቀል ምትክ ትንሽ የእጅ መስቀል እንዲይዙ ደነገጉ (ወሰኑት) መስቀል ለማሳለምም መነኮሳቱና ቀሳውስቱ ትልቁ ጉንደ መስቀል አሸክመው በየመንደሩ ሲያዞሩአቸው ምእመናኑ እየተከተሉ ጉንደመስቀሉን ይሳለሙት ነበርና ያ የመከራ ትዝታ እንዳይረሳ መስቀል ማሳለም ተጀመረ የሚሉ አሉ፡፡

ይህም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ« ዘኢደረ መስቀለ ሞተየ ኢይክል ይጸ መደኒ» መስቀሉንም የማይዝ፣ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም ባለው መሠረት እነሆ እነዚህ አባቶች ቃሉን ትእዛዙን እንደፈጸሙ ያሳስበናል፡፡ (ማቴ 3፣ 38 ማቴ 10፣ 24፡፡ ማር 8 :34፡፡ ሉቃ9÷23 14 ፡27)



ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘላለም ነው (2ኛቆሮ. 4÷:16)፡፡

አባቶች በሙዱጋ ሲኖሩ ዋዕየ ፀሐይን ችለው ብርዱንና ረሀቡን ታግሠው ለዚች ለምታልፈው ጊዜያዊት ዓለም ከምንም ሳያስቡ በሰው ዘንድ የተናቁ ከምንም የማይቆጠሩት ሰዎች በፈጣሪ ዘንድ ግን ከፀሐይ የበሩ ከወርቅና ከዕንቊ የከበሩና የጠሩ ናቸው፡፡

እንዳባት ሥላሴን፣ እንደናት ቅ/ማርያምን፣ እንደወንድም እንደ እኅት መላእክት አሉና፤ እንደ ርስት እንደጉልት የማታልፍ ርስተ መንግሥተ ሰማያት አለችና፡፡ የሚገባ ኃዘን የራስን ኃጢአት አይቶ ግፍዐ ሰማዕታትን ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን አስቦ ማዘን ነው፡፡ በዋልድባም የሱባዔ ትርጉሙ ይህ ነው፤ የራስን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን እንደ አዳም እንደ ቅ/ጴጥሮስ እንደ ዳዊት ነው፤ መልካቸው ሳይለወጥና ሳይሰቀቁ እንባቸው እንደ ሰን ውሃ ይወርድ ነበር፡፡

ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን አስቦ ማዘን እንደ ዮሐንስ ነው፤ የዕለተ ዓርብ መከራውን እያሰበ ሰብዓ ዘመን ቁጹረ ገጽ ሁኖ ኑሯል፤ ዛሬ በንስሓ የሚያለቅሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው፤ (እስመ እሙንቱ ይትፌ ሥሑ) ሱባዔ አባቶች በእውነትና በመጽጽት በእግዚአብሔር ፊት ልቡናቸውን ከፍተው ከአምላካቸው ጋር የሚገናኙበት ጊዜ ነው፡፡ በገዳማዊ ኑሮ ብቻ ራሳቸውን ከዓለም ፈጽሞ በማግለል በፈጽሙት ገድልና ትሩፋት የቃል ኪዳን ቅዱሳን ለመሆን የበቁ ቅዱሳን ናቸው፡፡

## ባሕታዊ ዘበሀድኦት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ «ጻድቃን ዓሉገዳማተ ዘዘብድሠ ጠሊ ወበሐሜለት» ጻድቃን ሁሉን እያጡ የበግና የፍየል ለምድ ለብሰው ዞሩ ዓለም አልተገባቸ-ውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በከርሠ ምድር ተቅበዘበዙ (ዕብ.11÷31-38)፡፡

በየክፍለ ዘመኑ የነበሩ አሁንም ያሉ፣ ከቤተሰብ ተለይተው ቤት ንብረታቸውን ጥለው፣ የዚህን ዓለም ተድላና ደስታ ንቀው በየገዳማቱ እየገቡ በጸምና በጸሎት ተወስነው በመኖርና እንዲሁም በየዋሻው የዱር ቅጠልና ውሀ ብቻ በመመገብ ለቁመተ ሥጋ ያህል በገዳም ተሰውረው የሚኖሩ ቅዱሳን አባቶች ባሕታውያን ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡

በኀቡእም ሆነ በግልጽ ፍጹም በሆነ ተባሕትዎ ለሚኖሩ ቅዱሳን አባቶች ገዳማት መጸሚያና መጸለያ እንዲሁም የዕድሜ ልክ ሱባዔ መያዣ ሆነው ለዘመናት እንደ ኖሩና አሁንም እንደ ሆኑ የአባቶች ገድለ ተባሕትዎ ያስረዳል፡፡

እንግዲህ ከብዙ ባሕታውያን አባቶች እንደምንረዳው ያንድ መናኔ ባሕታዊ ህልውና በጸምና በጸሎት ወስኖ፣ በሱባኤ ተጠምዶ ከዓመት እስከ ዓመት ከሚኖርባት ገዳም ወይም ዋሻ መንቀሳቀስ አይችልም፡፡ ውተግሕሥ እምነጽርታ ወዘክሮታ» በዓይን ከማየት በልብ ከማሰብ በጆሮ ከመስማት ፈጽመው ተከለከሉ ከሰው ተለይተው ጸባ ለብሰው ጸዋ ጥሰው ድንጋይ ተንተርሰው ጸብአ አጋንንትን፣ ግርማ ሌሊትን፣ ድምፀ ጋራዊትን፣ ችለው በብሕትውና የሚኖሩ አያሌ ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ጊዜያዊ ተድላና ደስታ ራሳቸውን ሰውረው በገዳም ይኖራሉ፡፡

እግዚአብሔርን የሚያፈቅሩ ሕጉና ትእዛዙን አክብረው፣ በንጽሕና ተጠብቀው፣ የሚኖሩ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምሥጢርን የሚያውቁ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ያስገዙ ባሕታውያን ፈቃደ ሥጋን በፍጹም ቆርጠ በመጣል መሪያቸው እግዚአብሔርን፣ መሣሪያቸው ጸሎትን፣ ሥራቸው ትሩፋትን ሠሪተ ሰማያትና በመንፈሳዊ ትጋት ይኖራሉ፡፡ ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘለዓለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለን፡፡(2ቆሮ.5÷1)

www.ethiopianorthodox.org

በገዳም የሚኖር ባሕታዊ

ባሕታውያን በትዕግሥት በኀቡእ ሁነው ከበዓት ሳይናወጡ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ተወስነው ከመኖር በቀር በማንኛውም የገዳሙ አስተዳዳር አይገቡም የባሕታውያን ግዴታዎች በቀን ስለ አርድእት ስለ ምእመናን ስለሀገርና ስለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ማድረስ አለባቸው፤ ይህ የገዳማቱ ሕግ ነው ግዴታም ነው፡፡

«ብፁዓን እለ ይርኀቡ ወይጸምዉ በእንተ ጽድቅ» አባቶች አብዝተንማ ከተመገብን ሰውነታችን ገትቶ ማኖር እንደምን ይቻለናል ብለው ከሚገበሉት ከሚጠጡት ከፍለው ሰጥተው የሚራቡ ንፁዳን ክቡራን ናቸው(ማቴ. 5÷6)፡፡

የሁሉም አብነቱ አባቶች ናቸው እንዲህ ያሉ የትሩፋት አበጋዞች በሰውነት ያለ አእምሮ ጠባይዕ ሥራ ሠርቶ ሊገለጽ ነው እንጅ ተሰውሮ ሊቀር አይደለም፤ ሰውነታቸው በወዲህም በወድያም ዓለም ክበረ «ወጻድቃንሰ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም» ሥራውን ሠርተው ክብሩን ይወርሱ ዘንድ ጻድቃንስ ሁልጊዜ በዘለዓለም ሕይወት ውስጥ ናቸው፡፡

የገዳማቱ በአርምሞ የሚኖሩ ባሕታውያን ብዙ ናቸው ማለትም ምንም ሳይናገሩ አፋቸው የሚከፈተው ለጸሎትና ለምስጋና ብቻ ነው፤ ጾጥታንና ዝምታን ገንዘብ በማድረግ ይታወቃሉ፡፡

«ወይበውዕ ሰብእ» አባቶች በሰው ልቡና ገብተው ምን እንዳሰብክና ምን እንደ ሠራህ ያውቃሉ፤ ልክ ዳዊት በኢዮአብ፣ ኢዮአብ፣ በዳዊት ልብ፣ ሳኦል በአበኔር፣ አበኔር በሳኦል ልቡና ምን እንዳለ እንዳወቁ ባሕታውያንም በሰው ልቡና ያለውን ያውቃሉ፡፡

የአባቶች መዓርግ እስከዚህ ነው፤ የሰውን ልቦና ይመረምራሉ፤ ያለፈውንም የሚመጣውንም በእግዚአብሔር ኃይልና ቸርነት ያውቃሉ፡፡ ለዚህም ነው አርድእቶች ወደ ገጠር ሲላኩ ከባሕታውያን አባቶች እግር ወድቀው ጸሎት የሚቀበሉት ከፈተና እንዲሰውራቸው ወደ አባቶች ሔደው እንዲጸልዩላቸው ሲጠይቁአቸው ኃይለ አጽራርንና ኃይለ አጋንንትን ያድክምላችሁ፤ ሰይጣን ያደረበት ሰውም አይግጠማችሁ፤ ወደ በአታችሁ በሰላምና በደህና ይመልሳችሁ ብለው [illegible]፡፡

www.ethiopianorthodox.org



ሌላው የሚያስገርመውና የሚያስደንቀው የመነኮሳት ሕይወት ነው፤ የመጽሐፉ ፍሬ ነገርም ይህ ነው፡፡ የልደተ አበው አቆጣጠርም በመጽሐፉ እንደተገለጸው የመጀመሪያው መነኮሴ ሁለተኛውን፤ ሁለተኛው ሦስተኛውን፤ ሦስተኛው አራተኛውን፤ እንዲህ እያለ ተበራከተ፡፡ ከሕገ ሥጋ ወደ ሕገ ነፍስ፤ ከወጣኒነት ወደ ማዕከላዊነት፤ ከማዕከላዊነት ወደ ፍጹምነት ይደርሳል ማለት ወደ ዐሥሩ መዓርጋት ይደርሳል፡፡ ዐሥሩ መዓርጋትም እነዚህ ናቸው፡

- ጽማዌ፡- መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ማየት፤ ነገር ግን የሚወጡበትንና የሚወርዱበትን አለማወቅ ነው፡፡
- ልባዌ፡- መላእክት የሚወጡበትንና የሚወርዱበትን ማወቅ ነው፡፡
- ጣዕመ ዝማሬ፡- ከዚህ መዓርግ ሲደርሱ ውዳሴ ከንቱ ይታወማቸዋል፡፡
- አንብዐ ንስሓ፡- እንደሰን ውኃ እንባቸው ሳያቋርጥ መፍሰስ ነው፡፡
- ኮነኔ፡- ሥጋን ለነፍስ ማስገዛት ነው፡፡
- ዑቃቤ፡- በዚያው ጸንቶ መኖር ነው፡፡
- ንጹሬ፡- ካሉበት ሁኖ መላእክትን በየከተማቸው ማየት ነው፡፡
- ሐሴት፡- እንደ እግረ ፀሐይ ከሁሉ መድረስ ነው፡፡
- ተሰጥሞ፡- በባሕረ ብርሃን መዋኘት ነው፡፡
- ፍቅረ ደቂቀ እጓለ እመሕያው፡- አማኒ መናፍቅ፤ ኃጥእ ጻድቅ፤ ባዕድ ዘመድ፤ ሳይሉ ሁሉን እንድ አድርጎ አስተካክሎ መውደድ ነው፡፡

እነዚህ መዓርጋት የሚገኙት ከሰው ለተለዩ፤ በዱር በገደል፤ ለሚኖሩ ቅዱሳን ነው፡፡ ሁሉን አስተካክሎ ማየት የሚቻለው ማንነው? ከዚህ መዓርግ የሚደርስ ሰውስ? እንደተጠቀሰው ከዐሥረኛው መዓርግ ሲደርሱ ሁሉን አስተካክለው ያያሉ፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ ለዚህ መዓርግ እንዲበቃ አይጠበቅበትም፡፡ የሚጠበቅበት ዋናው የእግዚአብሔር ሰው መሆን መቻሉ ነው፡፡ የፍጹምነ መነኮሳት ሕይወትም ይህን ያመለክላል፡፡

# ክፍል 5

## የቅዱሳት ሴቶች ታሪክ

1. ዓመተ ክርስቶስ ተጋዳሊት፣ ይህች እናት በተጋድሎ የጸናች እንደጻድቁ ተክለ ሃይማኖ በአግርዋ ቁማ 48 ዓመት የጸለየች ትልቅ እናት ስትሆን ስንክሳርና ገድለ ቅዱሳን አጥብቆ ሠርቶላታል፤ ገዳማዊት ተሐራሚት የሆነች ትልቅ እናት ስትሆን ስለ እሷ አ ዳንኤል አጥብቆ የተናገረላት በግንቦት 28 ቀን ዐርፋለች፤ የካቲት 8 ቀን የሚሉም አሉ ፡

2. ማርያም ክብራ ዘደብረ ሊባኖስ፤ ማርያም ክብራ በስንክሳር ላይ ስሟ ብቻ ተጠቅሶአል ሌላው ታሪኳ ግን አልተገለጠም፤ የደብረ ሊባኖስን የሴት ገዳም የቆረቆረችና የመሰረተች ፣ እጇ እንደፋና ያበራ የነበረች፣ እነ ክርስቶስ ሠምራም የእሷን ዝና ሰምተው የመነኑ በቀን በቀን ወደ ገዳሙ ከ35 የሴት መነኮሳይያት በላይ ይገቡ የነበሩ ሴቶች ከመነኮሱ በኋላ ወደ ሌላ ቦታ እንዳይሄዱ ያስወሰነች ደገኛ እናት ስትሆን በስሟ ገድል ተጽፎአል ታቦትም ተቀርጾላታል፤ በ70 ዓመቷ በሐምሌ 30 ቀን ዐርፋለች፡፡

3. ማርያም ዘደብረ ፅላልሽ፣ በዚህ ስም የተጠራችው እናት ፅላልሽ በተባለው ቦታ የተወለደች ስትሆን የሀገረ ገዥ ልጅ ናት ወደ ደብረ በግዕ ገዳም ገብታ በምናኔ የኖረች በአቡነ ዜና ማርቆስ እጅ ምንኩስናን የተቀበለች ሰይጣን በሰው አምሳል መጥ ሊያስታት ሲል በያዘችው በትረ መስቀል ስታማትብበት እንደ ጢስ ተኖ ጠፋ፤ ተጋድሎዋ የበዛ ትልቅ እናት ናት፣ ገድል አላት ፣ የታወቀች ጻድቅት እናት ስለሆነች ልጅነራባት የሚገባ ነው፡፡

4. ሰበነ ድንግል፣ ይህች እናት ሽዋ ስትሆን ፅዑብ ድንቅ የሚያሰኝ ገዳም በስሟ የተጠራ በጐንደር አላት፤ ሽዋ መንዝ ውስጥም እንደነበረች ይነገራል፤ ገድል አላት፣ ታቦትም እንዲቀረጽላት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተሰብስበው ወሰኑ፤ ስለዚህ የምንመካባት እናት ጻድቅት እናት ናት ፣ ዕረፍቷ በሰኔ 26 ቀን ነው፡፡

ጻድቁ ቅ/ክርስቶስ ሠምራ

5. ጻድቅቷና ተጓዋቂዋ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ሀገርዋ ቡልጋ ልዩ ስሙ ጊሬ ከተባለው ቦታ ተወለደች፤አባቷ ደርሱና ወይም ርሳኒ እናቷ እሌኒ ይባላሉ፤ ይህች ጻድቅት ሠምረ ጊዮርጊስ የተባለውን ክርስቲያን አግብታ 12 ልጆችን ወለደች ፤ ከነዚህም ውስጥ የታወቀው ዳግማዊ ቂርቆስ ተብሎ የተጠራው የ3 ዓመቱ ሕፃን ልጁ ነው በጣና ቂርቆስ ከባሩ ውስጥ ቁማ 12 ዓመት ጸልያለች በደብረ ሊባኖስ 7 ዓመት በስግደት በጾምና በጸሎት ኑራለች፤ በሽዋ፣ በጎጃም፣ በጣና ዙርያ ገዳም አላት፤ በነሐሴ 24 ቀን ዐርፋ በእርሷ ስም በተጠራው በራሷ ገዳም ተቀብራለች፡፡



6. ጻድቅት ፍቅርተ ክርስቶስ፣ እጅግ አስደናቂ ታሪክ ያላት ቅድስት ናት፤ በስሟ የተጠራ ገዳም አላት፤ በግራ መቂት በጥባት ወረዳ ቀበሌ የእማሙዝ ገዳም ይባላል፤ ይህን ገዳም የመሠረተችው ጻድቅትዋ ኢትዮጵያዊት ስትሆን የቤተ ክርስቲያኗ ሥራ ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን የተለየ ነው፤ ግድግዳው በሙሉ በስሟዛ (በሰንሰል) ነው የተሠራው፤ በምሥራቅ ሲዞሩ የምትወድቅና የዘመመች ትመስላለች ፤ በምዐራብ ሲዞሩም እንዲሁ በደቡብም ሲዞሩ እንዲሁ በሰሜንም ሲዞሩ እንዲሁ ነው የተጣመመች ትመስላለች፣ ቤተክርስቲያኒቱ ግን የማታረጅ ልዕልና ያላት ለጻድቅትዋ የተሰጠ በረከት ስለሆነ ያስደንቃል፤ ይህን የመሰለውን ታሪክ እየጣሉ ወደ አውሮፓ ተጉዘው ከመጡ በኋላ ኢትዮጵያዊነታቸውን ለመለወጥ የሚመክሩ ሰዎች ያሳዝናሉ፡፡

7. ቅድስት ለባሲተ ክርስቶስ፤ ይህች ጻድቅት ምንኩስናዋ የተመሰከረላት ትልቅ እናት ናት፣ በታሕታይ ተንቤን ውስጥ በስሟ የተሠራ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል፤ ዕረፍቷም በሰኔ 15 ቀን ሲሆን የራሷ ገድል አላትና ገድሏም አስደናቂ ታሪክን የያዘ ነው፡፡

8. ቅድስት መክብበ ድንግል፣ የዚች ጻድቅት እናት ስሟ በስንክሳር ተደጋግሞ ተነግሮአል፤ በቀደምቱ በተጋድሎ በጾም በስግደት የታወቀች እናትና በስሟም የተሠራ ቤተ ክርስቲያን በትግራይ ሽሬ ታይታይ አዲያቦ ይገኛል፡፡

9. ቅድስት እህተ ጴጥሮስ፣ ሀገርዋ ትግራይ ሲሆን በዳሞ ተራራ ሥር ተወለደች፤ ወደ ጎንደር መጥታ ከነወለተ ጴጥሮስ ጋር አብራ ከዐላውያን ጋር ስትከራከር ቆይታ ወደ ሞጊና ገዳም ሄዳ በገዳሙ ውስጥ ስትሰግድ ቆይታ ለማኅበረ ሥላሴና ለደብረ ጻሞ ገዳም በረታብና በችግር ጊዜ ወረርሽኝ ሆኖ ለመነኮሳቱ ስትረዳ የኖረች ደገኛ እናት ናት፤ በቀን 1500 ስግደት ትሰግድ ነበር 1000 (አንድ ሺህ) አቡነ ዘበሰማያትም ትደገም ነበር፡፡ በተወለደች በ 67 ዓመቷ ሐምሌ 7 ቀን ዐርፋለች፡፡

10. ወለተ ሰሜት ቅድስት ዜላሎ፣ ይህች ጻድቅት ሀገዋ ጉጃም ደብረ ወርቅ ሲሆን መንና ሄዳ ደብረ ጽላሎ ጉንጂ ገባች፣ ከዚህም በኋላ መላ ዘመንዋን በጾምና በጸሎት በስግደት አሳለፈችው ፤60 ዓመት ሙሉ ፀጉርዋን ያልተላጨች ፀጉርዋ መኝታና ልብስ ይሆናት ነበረ፤ ታሪኳን መጽሐፈ ስንክሳር አስፍቶ የሠራላት ዝናብን እንደ ኤልያስ ታዝዘው የነበረች ከፀጉርዋ በስተቀር ሌላ ልብስ የሌላት ደገኛ ቅድስት ናት፡፡ የራሷም ገድል አላት ፤ ታቦትም በስሟ አላት፣ ዕረፍቷም በግንቦት 20 ቀን ነው፡፡

11. ቅድስት ወሌ ማርያም፣ ቡርክትና ደግ ነበረች፡፡ የአጼ ወናግ ሰገድ እናት ነበረች፤ መንና ሄዳ በጣናባህር ገብታ ከባሕሩ ውስጥ ቁማ እጅግ አጥብቃ የጸለየች እናት ስትሆን ገድል አላት ስንክሳርም ሰርቶላታል ዕረፍቷም በግንቦት 3 ቀን ነው፡፡

12. ቅድስት ማርያም ክብራ ዘጽላሎ የዚች እናት ሀገርዋ ደብረ ፅላሎ ሲሆን ባሕታዊትና መናኝ ጻድቅት ናት ሕገ ምንኩስናን ከአቡነ ኢየሱስ ሞአ ተቀብላ ምናኔዋን ቀጠለች፤ ክብቃቷ ብዛት የተነሣ 10ሩም ጣቶቿ እንደፋና ያበሩላት ነበረ፤ በዚህም ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ማህቶት ትባላለች በተወለደች በ62 ዓመቷ ሐምሌ 30 ቀን ዐርፋለች፡፡

www.ethiopianorthodox.org

13. ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ፣ የትውልድ ሀገርዋ ጉንደር ስማዳ በለስ ሚካኤል ሲሆን አባቷ ባሕ
አሰገድ ሲሆን እናቷ ክርስቶስ አብየ ይባላሉ፣ እነ ዮሐንስ ዘድንግል የተባሉ ወንድሞች
ነበሩአት፣ ባለታሪክ የሆነች እናት ናት፣ የባሏም ስም መልክአ ክርስቶስ የበጌ ምድር ገዥ ነበ
፣ በስማዳ በለስ ሚካኤል ትኖር ነበር፣ ባለትዳርና የ3 ልጆች እናት ስትሆን መንና ሄዳ ጣና
ሐይቅ ገዳም ገባች፣ መንና ከገባችበት

ቅ/ወለተ ጴጥሮስ

ገዳም ባሏ ሄዶ አበምነቱን ከሶ ከገዳሙ አስወጣት አሷ ግን ተደብቃ ወደ ሌላ ሀገር መንና ገባች
፣ በዘመኗ የነበረው ጨካኝ ገዥ በሰይጣናዊ መንፈስ ተነሳስቶ ቁመቱ 275 ክንድ ከሆነ ገደል
ላይ እሱ ከአፋቱ ላይ ሁኖ ቢወረውራት መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ተቀብሎ ከንጹሓን መነኮሳት
ጋር ብሔረ ብፁዓን ወስዶ አስቀምጦአታል፣ በዚህም ስርዓትን ማስታኮትን ተምራ ተመልሳ ወደ
ጣና ገብታ በዚያ ስትጸልይ ልብሶቿ እንደመብራት ለገዳሙ ያበሩ ነበረ፣ ቅድስት ወለተ
ጴጥሮስን ያመነኮሳት አባት አቡነ ማርቆስ ግብጻዊ ይባላል፣ መንና ከሄደችም በኋላ ባሏ ወደ
ካቶሊክ እምነት እንዳይገባ ትስብክውና ታስተምረው ነበረ ይህች ጻድቅት የጉንደር ተወላጅ ነች
ካቶሊካውያን በጉንደር ከተማ በገመድ አስረው እየጉተቱ አሠቃዩአት መታገል በጀመረች በ30
ዓመት በትዳር ዓለም 26 ዓመት በምናኔ ዓለም 36 በጠቅላላ 80 ዓመት ሲሆናት በሕዳር 18
ቀን ዐርፋለች በሕዳር 16 ቀንም ይላሉ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ በጎንደር 2 በጉጃም 5 በደምሩ
7 ገዳማት በስሟ ተሠርተው ይገኛሉ በተለይ በጉጃም ስሟ የገነነ ከፍተኛ ገዳም አላት ጉብኝ
ዎችን የሚማርክ ገዳም የአንድነት አላት ታሪኳም በሴቶች ወንጌላዊት ሕይወት መጽሐፍና
በልሳነ ተዋሕዶ መጽሔት ቁጥር 37 ላይ ተዘግቦአል ወለተ ክርስቶስ ወለተ ጻውሎስ
እህተ ክርስቶስ የሚባሉ ጓደኞች ሴቶች ነበሩአት አብረው ነው በምናኔ ዓለም የኖሩት የወለተ
ክርስቶስ ዕረፍቷ በሕዳር 7 ቀን ነው፡፡

14. ፀበለ ማርያም ተሐራሚት ይህች እናት እጅግ የታወቀች በስንክሳሩም የተጠቀሰች ታላቅ
እመቤት ስትሆን ይህች ጻድቅት በገዳማዊትነት የታወቀች ትልቅ እናት ነበረች፡፡ እረፍቷም
በጥቅምት 24 ቀን ነው፡፡





# ክፍል 6

## ገዳማቱ ለኢትዮጵያውያን ያበረከቱትን አስተዋጽኦ

ሀ/ ገዳማት የጥበብ የዕውቀት የፍልስፍናም ምንጭ ናቸው፣ ቀደሚሃ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር በተባለው መሠረት በገዳም መጀመሪያ የሚያጠኑትና የሚማሩት የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት መጋቢነት አዳኝነት አዛኝነትና ርኅራሄ ነው በዚህ መሠረት ነው ገዳማት ዩኒቨርስቲ ናቸው የምንለው ለምሳሌ እንደ ደብረ ዓባይና ደብረ ሊባኖስ የመሳሰሉ የጉባኤ ቤቶች በጣም አስደናቂ ናቸው፣ ስለዚህ ገዳማት ለኢትዮጵያ ያበረከቱት ዕውቀት ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ ባህል፣ፍቅርና አንድነት ነው ከመነኮሳት የተገኘው ፣

ለ/ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሊቃውንት፣ መነኮሳት፣ ጻድቃን ለማዕታት በሙሉ በዱር በገደል፣በእሳት፣ በስለት፣ በረኃብ፣ በእርዛት፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በምናኔ የተንገላቱ መከራ የተቀበሉት ለእምነታቸው፣ ለምግባራቸው፣ ለባህላቸውና ለሥርዓታቸው፣ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ነው፣ መከራ የተቀበሉ ለእምነታቸው፣ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት በማስተማርና በማስከበር ሁሉም የእግዚአብሔርን ስም ይጥራ፣ ሁሉም ከእግዚአብሔር የተገኘና በእግዚአብሔር የሚረዳ ነው፣ በማለት ነው፡፡

ተምሮ ማስተማር፣ በምግባር በዕውቀት ራስን አስመስሎ ማውጣት ሰውን መፍጠር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው እኔ በክርስቶስ ትምህርት ወልጃችኋለሁና እኔን ምሰሉኝ ያለው፡፡

ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ዕድቱ የተገነባው የኢትዮጵያዊነት ክብርና መለዮ በሆኑ ገዳማት ነው እንላለን፡፡

ታሪክ መስታወት ነው፡፡ የረቀቀውን አጉልቶ የተረሳውን መዝግቦ ያሳያል እንደሚባለው የአንድ አገር ሕዝብ ታሪኩ፣ ጀግንነቱ፣ ታላቅነቱ፣ ባህሉና አኗኗሩ በሚገባ ሊታወቅ የሚችለው በሥነ ጽሑፍና በሥዕል ወይም በቅርጻቅርፅ ተሥሎና ተቀርጾ ለትውልደ ትውልድ በሚተላለፈው ሥዕላዊ መግለጫ እንደሆነ ማንም ሰው የሚረዳው ነው፡፡ እንዲሁም ተምሮ ማስተማር መነኮሳት በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አየተዟዟሩ ትውልድን አስተምረዋል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ኦሪት፣ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ በሕገ ወንጌል ያመነች ጥንታዊት ሀገር ከመሆኗም በላይ በዚያው ዘመን ርዝመትን መጠንም በሥነ ጽሑፍ የታወቀችና የሕዝቧ ሥልጣኔ ጥንታዊነቱ፣ ጀግንነቱ፣ እምነቱና ባህሉ ሌላውም ሁሉ እንዴት እንደሆነ ሊታወቅ የቻለው መጀመሪያ በሐውልቶች፣ በጠፍጣፋ ድንጋዮችና በሸክላ ዕቃች ላይ በኋላም በብራና ተጽፈውና ተሥለው ለትውልደ ትውልድ እየተላለፉ በመጡት የቅርጻቅርጽ፣ የጽሑፍና የሥዕል ቅርሶች ነው፡፡ ታሪክ ማኅደር እንደምንረዳው በሀገራችን ትልቁን ሚና ያበረከቱት ገዳማት ናቸው፡፡

ለምሳሌም ያህል በአክሱም ሐውልቶች ላይ በሳባውያን፣ በግሪክና በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ጽሑፎች ሃይማኖት እማኞች (ምስክሮች)ናቸው፡፡ ሆኖም የሥነ ጽሑፍ መሠረት የሆነው ፊደልና የሥነ ጽሑፍ ስልት ከጥንት የታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት በኢትዮጵያ ከተጀመረበት ዘመን አንሥቶ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ዓለም ገና በጨለማ ውስጥ በነበረበት የዕውቀት ብልጭታም ባልፈነጠቀበት ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መነኮሳት ከበግ፣ ከፍየልና ከልዩ ልዩ እንስሳት ቆዳ ብራና ፍቀው ልዩ ልዩ ብሕትመቶችን ቀምመው የሸምበቆ ብዕር ቀርጸው በጉልሕ ወይም በረቂቅ ለመጻፍ በሚያስችል ሁኔታ ከዘጋጀ ከፊደል በኋላ ከዘመናዊው የአሠራር ስልት በማያንስ ሁኔታ እየጠረዙና እየደጎሱ ለተጠቃሚው ሕዝብ በማቅረብ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ገዳማቱ ያደረጉት አስተዋፅኦ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ካለው በርካታ የታሪክ ቅርስ አኳያ ሲታይ ግን ዕውብና ድንቅ የሆኑትን የታሪክ አሻራዎች መቼ፣ በየገዳማቱ ለአገሪቱ የተደረገውን አስተዋፅኦ የአያሉ ጥንታዊና አስገራሚ ታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት የሆነችው አገራችን በየዘመኑ ታሪኳ ከውጭና ከውስጥ ይነሱ በነበሩት ጦርነቶች ምክንያት የጀመረችውን የስልጣኔና የእድገት ፈለግ ከመቋረጡም በላይ የነበረውም ቢሆን ተበታትኖና ተበላሽቶ በአብዛኛው ለጥፋት ተዳርጓል፡፡

በአገራችን ውስጥ ያሉትንና ወደ ሌሎች አገሮች የተሻገሩትን ቅርሶች በተመለከተ በርካታ ጽሑፎች የወጡና በመውጣት ላይ ያሉ ቢሆንም ከጊዜው ርቀትና በመረጃች መውደም፣ መጥፋት ወይም ተቆፍረው ያለመውጣት የተነሣ በምርምር በተገለፁትና በአፈ ታሪክ በሚነገሩት ታሪኮች መካከል የአበው መነኮሳት ያበረከቷቸው መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

በአገራችን ውስጥ ከ12ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በቀደምት ሊቃውንት የተጻፉ የብራና መጻሕፍትም ለዘመናዊው ታሪክ ምርምር ሥራ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ቀላል ባይሆንም ዓላማቸውና አጻጻፋቸው ሃይማኖታዊ እሴትን ለማዳበርና ለማበርከት በአባቶች የተፃፉ ናቸው፣ ስለዚህ የብራና መጻሕፍት በሃይማኖት መሪዎች ተከታዮች ከፍተኛ ክበሬታ አላቸው፡፡

ይህም የታሪክ ትምህርት በኅብረተሰቡ ዘንድ ሊኖረው የሚችል ጥቅም የጎላ ከማድረጉም በላይ ሕዝቡ ታሪካዊ ቅርሶቹን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ብቃት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡ ከዚህም በላይ አገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክና ነጻነት ያላት ጥንታዊት ሀገር መሆኗን አበክር ለማወቅ የሚጣጣረው ዜጋዋ ራሱ አይቶና አንበቦ ለመረዳት የሚኖረው ዕድል ሰፊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በቅርብ ጊዜ እየተደረጉ ያሉት ጥናቶችና ምርምሮች የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ጎልቶ እንዲወጣ እያበረከቱት ያሉት አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

ሌላው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ምን እንዳለና በቤተ ክርስቲያን ዙርያ ያሉት የታሪክ ቅርሶችን በሚመለከት ያለው እውነት ለአካባቢው ነዋሪቹ ሳይቀር ጥቅሙና እውቀቱ ከፍተኛ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ገዳማት ቅርስና ታሪክ፣ በውስጧ የያዘቻቸውን ቅርሶችና ሌሎች መስሕቦች፣ ኢትዮጵያ በሰው ልጅ ታሪካዊ ዕድገት ሂደት ውስጥ በጥንታዊ የሕንጻ ኤራር፣ ኅብረተሰባዊ አደረጃጀት፣ በስነ ጽሑፍ፣ በሥዕል የሃይማኖታዊ ትሩፋቶችና ሌሎች የሥልጣኔ አሻራዎች ያበረከተቸው አስተዋፅኦ የሚገባውን ያህል እንዲታወቅ አልተደረገም፡፡

ቱሪዝም ለአንድ ሀገር ግንባታ ከሚሰጠው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አንጻር ጠቢ አልባው ኢንዱስትሪ በመባል ይታወቃል፡፡ ይኸውም በዘመናችን በነዳጅ ዘይት ገቢ ባልተናነሰ ሁኔታ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ረገድ ያለው የጐላ አስተዋጽኦ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ጸጋ በአባቶች መነኮሳት ጥረትና መሥዋዕትነት የተገኘ ሀብት መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

ገዳማት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ማዕከል ብቻ ሳይሆኑ የምጣኔ ሀብታዊ ማኅበራዊ ሥነ ጥበባዊ የሥርዓተ መንግሥት የወጭ ግንኙነት ባጠቃላይ የታሪክ የሥልጣኔ እና የነገሥታት ገድሎች ዜና መዋዕሎች መረጃ ማዕከላት ናቸው፡፡

የቅርስ ባለቤትና የቅርስ ጠባቂዎች ምንም አይነት ጥቅም ባያገኙ ጥሬ ቆርጥመው ውሃ ተጐንጭተው ድንጋይ ተንተርሰው ለትውልድ ያስረከቡትን ቅርስና ታሪክ የአበው መነኮሳትና የገዳማት ውጤት ነው፡፡

ድንጋይ ተንተርሰው ለተውልድ ያስረከቡተን ቅርስና ታሪክ የአበው መነኮሳተና የገዳማተ ውጤተ ነው፡፡



# ምዕራፍ 11

## የሰማዕትነት ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

ሰማዕት የሚለው ስም "ሰምዐ" ሰማ፣ አደመጠ፣ አስተዋለ፣ ተቀበለ፣ መሰከረ፣ ምስክር ሆነ፣ ያየውን የሰማውን ተናገረ፣ አየሁ ሰማሁ አለ ከሚለው ግሥ የወጣ ቃል ነው፡፡ ሰማዕት ማለትም ምስክሮች፣ ሰማዕቶች፣ ሃይማኖታቸውን መስክረው በሰማዕትነት የሞቱና የሚሞቱ ማለት ነው፡፡ ኄኖክ "በምድር ላይ የሚፈስሰውን ደምና በምድር ላይ የሚደረገውን ግፍ አዩ" እንደአለው /ኄኖ 2፣28/ ነው፡፡ ሰማዕተ ሐሰት የዲያብሎስ ወገኖች ሲሆኑ ሰማዕተ ጽድቅ የእግዚአብሔር ወገኖች ናቸው፡፡ ሰማዕታት ሃይማኖታቸውን ላለመካድ በሰይፍ፣ በጦር፣ በአሳት፣ በመሳሰለው ስለሚሞቱና ለመንግሥተ እግዚአብሔር ደማቸውን ስለሚያፈስሱ አሸናፊዎች ናቸው፣ ስለዚህም "ሰማዕታት መዋዕያን" ይባላሉ፡፡(ቅዳ)

የሰማዕትነት ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቼ እንደነበረና ሰማዕታተ ኢትዮጵያ እነማን እንደሆኑ ከመግለጻችን በፊት በዘመነ አበው፣ በዘመነ ኦሪት፣ በዘመነ ሐዲስ የሰማዕትነት ጊዜና ሰማዕታት እንደነበሩ በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ማስታወስ የሚያስፈልግ ይሆናል፡፡ ሰማዕታት በዘመነ አበው፣ ሰማዕታት በዘመነ ኦሪት፣ ሰማዕታት በዘመነ ክርስቶስ፣ ሰማዕታት በዘመነ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት በዘመነ ሰማዕት፣ ሰማዕታት በዘመነ ሊቃውንት በዓለም ላይ ታሪካቸው ተመዝግቦአል፡፡

### ከዘመነ አበው ሰማዕታት

በዘመነ አበው የሰማዕታት መጀመሪያ የአዳምና የሔዋን 3ኛ ልጃቸው ዐቤል ነው፣ በወንድሙ በቃየል በቅንዓተ ብኢሲት በድንጋይ ተመትቶ በሰማዕትነት ሞቷል፡፡ (ዘፍ፣4,2-8፣ 1 መቃ:23,1-2፣ 28,2-5፣ ማቴ 23,35፣ ዕብ፣11,4፣ 1፣24፣ ስንክሳር ጥር 2፣ ሚያዝያ 6)

### ከዘመነ ኦሪት ሰማዕታት ጥቂቶቹ

ከዘመነ ኦሪት ሰማዕታት ናቡቴ፣ ነቢዩ ኢሳይያስ፣ ነቢዩ ኤርምያስ፣ ነቢዩ ሕዝቅኤል፣ 5ቱ የመቃቢስ ልጆች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ ናቡቴ፡- ናቡቴ የተባለው እስራኤላዊ አትክልተኛ በግፈኞቹ የእስራኤል ነገሥታት በአክዓብና በኤልዛቤል ትእዛዝ በድንጋይ ተወግሮ ሞቷል፡፡ (መጽ.ነገ.ቀዳ ም.20 ቁ.1-25 ስንክሳር ታኅሣሥ 1 ቀን)

ለ ነቢዩ ኢሳይያስ፡- ከዐበይት ነቢያት አንዱ ነቢዩ ኢሳይያስ በይሁዳ ንጉሥ በምናሴ ትእዛዝ በእግሮቹና በራሱ መካከል በመጋዝ ተሰንጥቆ በማሰዕትነት ሞቷል፡፡ (ካል.ነገ.21,16 ስንክሳር መስከረም 6)

ሐ ነቢዩ ኤርምያስ ፡- ከዐበይት ነቢያት አንዱ ነቢዩ ኤርምያስ አይሁድ ጣኦት እያመለኩ ስለአስቸገሩት ቢገሥፃቸው በጠላትነት ተነሡበት፡፡ ስለዚህም በአይሁድ በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት ሞቱዋል፡፡ (ተረፈ ባሮክ 5,54-62፣ስንክሳር ግንቦት 5 ቀን)

መ ነቢዩ ሕዝቅኤል፡- ነቢዩ ሕዝቅኤል እስራኤል በባሌሎን ሳሉ ጣኦት ሲያመልኩ አይቶ ቢገሥፃቸው አለቆቻቸው በጠላትነት ተነሥተው ገደሉት፡፡ (ስንክሳር ሚያዝያ 5 ቀን)

ሠ 5ቱ የመቃቢስ ልጆች፡- ከብንያም ነገድ የሆነው የመቃቢስ ልጆች 5 ናቸው፣ 5ቱም መቃብያን በሞዐባውያንና በከለዳውያን ንጉሥ በጺሩጻይዳን ትእዛዝ በእሳት ተቃጥለው በሰማዕትነት ሞተዋል፣ የሞቱትም 70 ለሆኑ ጣዖቶቹ ከአልሰገዳችሁና ከአልሠዋችሁ ብሎ ቢያዝዛቸው እንቢ ስለአሉትና ለጣዖቱም የተሠዋውን መሥዋዕት አንበላም በማለታቸው ነው፡፡
(መጽ.መቃ/ቀዳማዊ ም.3 ቁ.3,1-ፍጻሜ ስንክሳር ታኅሣሥ 25 ቀን)

www.ethiopianorthodox.org

(ፈ) አልአዛር ሚስቱና 7 ልጆቹ፡- ከሕገ ኦሪት መምህራን አንዱ አረጋዊው ሊቀ ካህናት አልአዛር ሚስቱ ሰሎሜና ልጆቹ አንኢም፣ አንጦኒሃስ፣ ያዝያ፣ አልአዛር፣ አስዮና፣ ሰሙናና፣ መርካሎስ በዘመዶቻቸው በ3 ካህናት በስምዖን፣ በአልፍሞስና፣ በመባልስ ቅንዓት ከዕርዉ ንጉሥ ከአንዋያክ ጋር ስለተጣሉና መሥዋዕተ ዕሪያ አንሠዋም ስለአሉ ሰባቱን ልጆች ገደላቸው፤ አልዓዛርንና ሚስቱን ግን በጋለ ብረት ምጣድ አስተኝቶ ጠብሶ ገደላቸው ። (ስንክሳር ነሐሴ 8 ቀን)

## ከዘመነ ሐዲስ ሰማዕታት ዋና ዋናዎቹ፣

ከዘመነ ሐዲስ ሕጻናተ ቤተ ልሔምና ዘካርያስ፣ እነ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ከሐዋርያትና አርድዕት፣ እነ ቅዱስ ጴጥሮስ እነ ቅዱስ ጳውሎስ እነ ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ እነ ቅዱስ ማርቆስ፣ የሐዋርያት ተከታዮች ከሆኑት እነ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ እነ ቅዱስ መርቆሬዎስ፣ እነ ቅዱስ ቂርቆስ በአጠቃላይ በእነ ዲዮቅልጥያኖስና መክስምያኖስ የተጨፈጨፉት የ3ኛውና የ4ኛው መቶ ዘመን ሰማዕታት ሁሉ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

### 1. ሕጻናተ ቤተልሔም ፡-

የ2 ዓመትና ከዚያም የሚያንሱ 14 ዕልፍ ከ4 ሺ (144000) የቤተልሔምና የአውራጃዎቿ ሕፃናት በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ሠይፍ ታርደዋል።
(ማቴ 2,16-17፤ ራእ.ዮሐ 14,1-5 ስንክሳር ጥር 3)

### 2. ዘካርያስ ወልደ በራክዩ፡-

የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ አባት ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ "ልጅህን ዮሐንስን ከአላመጣህና ከአልገደልሁት አንተን እገድልሃለሁ" ብሎ ታላቁ ሄሮድስ በ3 ዓ.ም አካባቢ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ በማዕጠንት አገልግሎት ላይ እያለ በሰይፍ አንገቱን አስቁርጦ አስገድሎታል።
(ማቴ 23,35-36፤ ስንክሳር መስከረም 8 ቀን)

### 3 መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ፡-

የሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ልጅ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በ30 ዓ.ም. አካባቢ በታላቁ ሄሮድስ ልጅ በገሊላ ንጉሥ በሄሮድስ አንቲጳስ ትእዛዝ አንገቱን በሰይፍ ተቁርጦ በሰማዕትነት ሞቷል።
(ማቴ14,1-12፤ማር፣6,14-29፤ስንክሳር መስከረም 2ቀን)

www.ethiopianorthodox.org



### 4. ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ፡

ከዘመነ ሐዲስ ሰማዕታት የመጀመሪያው ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስ ነው። ስለዚህም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት ይባላል። (ቅዳ) ቅዱስ እስጢፋኖስ በቅንዓተ አይሁድ በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት ሞቷል።(የሐ.ሥ፤ምዕ፤6-ም.7 ስንክሳር ጥር1)

### 5 ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ፡-

ከ12 ሐዋርያት አንዱ የዘብዴዎስ ልጅ የሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ወንድም ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ያስተማራቸውን ምእመናን መባና ምጽዋት ከገንዘባቸው እንዲሰጡ በማድረጉ በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ አግሪጳ (የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ) ትእዛዝ በሰይፍ አንገቱን ተቁርጦ በሰማዕትነት ሞቷል። (የሐ.ሥ 12,1-2፤ ስንክሳር ሚያዝያ 17 ቀን ገድ. ሐዋ.ም 20 ገጽ 156-160)

### 6. ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ፡-

ሐዋርያው ቅ/በርተሎሜዎስ በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ አግሪጳ ትእዛዝ አሸዋ በተመላበት የዝተት ከረጢት ተጨምሮ ወደ ባሕር ተጥሎ በስጥመተ ባሕር ሰማዕት ሆኑዋል። (ስንክሳር መስከረም 1 ቀን ገድ.ሐዋ. ም.10፤ ገጽ 100-107 ም.16፤ ገጽ 128-133)

### 7. ወንጌላዊው ቅ/ማቴዎስ፡-

የመጀመሪያውን ወንጌል የጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በሀገረ ካህናት ወንጌልን ሲያስተምር ብዙ አሕዛብ በማመናቸውና በመጠመቃቸው በካህናተ ጣኦት ሴራ አንገቱን በሰይፍ ተቁርጦ በሰማዕትነት ሞቷል። (ስንክሳር ጥቅምት 12) ገድ.ሐዋ.ም.12፤ ገጽ112-118

### 8 ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ፡-

የአፍራቅያ /አፍሪቃ/ ሐዋርያ ቅዱስ ፊልጶስ በአረማውያን ዐድማ ቍልቍል ተሰቅሎ በሰማዕትነት ሞቷል።(ስንክሳር ህዳር 18 ቀን ገድ.ሐዋ.ም."4፤ ገጽ 123-127)

### 9. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፡-

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በኔሮን ቄሣር ንጉሠ ሮም ትእዛዝ ቍልቍል ተሰቅሎ በሰማዕትነት ሞቷል። (ስንክሳር ሐምሌ 5 ቀን ገድለ ሐዋርያት የታተመው ገጽ 7-10)

### 10 ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡-

"ምርጥ ዕቃ" የተባለው የአሕዛብ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ በኔሮን ቄሣር ትእዛዝ አንገቱን በሰይፍ ተቁርጦ በሰማዕትነት ሞቷል።
(ስንክሳር ሐምሌ 5 ቀን ገድለ ሐዋርያት የታተመው ገጽ 17-18)

### 11. ሐዋርያው ቅዱስ አንድርያስ፡-

ሐዋርያው ቅዱስ አንድርያስ ዕጣው ልዳ ነበረችና ልዳ ገብቶ ሲያስተምር ጣኦት አምላኪዎች አረማውያን በዕንጨት ላይ ሰቅለው፤ በድንጋይ ወግረው ገድለውታል። (ስንክሳር ታኅሣሥ 4 ቀን ገድ.ሐዋ. ም16 134-142)

12. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዕልፍዮስ፡-

የዕልፍዮስ ልጅ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በብዙ አህጉር እየተዘዋወረ ወንጌልን ከአስተማረ በኋላ በኢየሩሳሌም በአይሁድ ምኩራብ ገብቶ በግልጥ ሃይማኖተ ክርስቶስን ሲያስተምር አይሁድ ከሮሙ ንጉሥ ከቀላውዴዎስ ቄሣር አጣልተው በንጉሡ ትእዛዝ በ ድ ን ጋ ይ ተወግሮ እንዲሞት አድርገውታል። (ስንክሳር የካቲት 10 ቀን ገድ.ሐዋ.ም 18 ገጽ 154)

13. ቅዱስ ማትያስ ሐዋርያ፡-

በይሁዳ አስቆሮታዊ ምትክ ሐዋርያነት የተሾመው ቅዱስ ማትያስ ሀገረ በላዕተ ሰብእ ገብቶ ሲያስተምር ሁለቱን ዐይኖቹን አውጥተው አሳውረውታል፤ ወኀኒ ቤት አስገብተውታል፤ ከቅዱስ እንድርያስም ጋር አንገታቸውን በገመድ አሥረው ለ3 ቀን ያህል በሀገሩ ጥጋጥግ ጐተቱዋቸው፤ደማስቆም ገብቶ ሲያስተምር በአልጋ አስተኝተው አሳት አነደዱበት፤ አሳቱ ግን ምንም አልነካውም
(ስንክሳር መጋቢት 8 ቀን ገድ.ሐዋ ም.9፤ገጽ 91-99 ም.19፤ገጽ154-155)

14. ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤል /ስምዖን/፡-

ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ቅዱስ ናትናኤል /ስምዖን/ በራንጥያ በምትባል ደሴት ገብቶ በማስተማር በሌሎችም አገሮች እየተዘዋወረ ብዙ ሰዎችን ከአጠመቀና ቤተ ክርስቲያንን ከአሳነፀ በኋላ ከሐድያን ብዙ ስቃይ አደረሱበት፤ በመጨረሻም በፅንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። ስንክሳር ግንቦት 15 ቀን

15. ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ /ዲዲሞስ/፡-

ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ቅዱስ ቶማስ /ዲዲሞስ/ በሕንድ አገር ገብቶብዙ ሰዎችን ስለአስተማረና ስለአጠመቀ የአገሩ ገዢና አረማውያን ተቃውመውት ቆዳውን ገፍፈው ሽልቻ አወጡት፤ በመጨረሻም በአቴና በጦር ወግተው ገደሉት።
ስንክሳር ግንቦት 26 ቀን ገድ.ሐዋ. ም.11 ገጽ 108 እስከ 111

16. ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ፡-

ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ሁለተኛውን ወንጌል የጻፈው የአስክንድርያ የመጀመሪያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ አስክንድርያ ገብቶ በማስተማር ከአንያኖስና ከቤተሰቡ ጀምሮ ብዙ ሰዎችን ስለአጠመቀ፤ በሀገረ በርቃና በ15ቱ አህጉርም አስተምሮ ብዙዎችን ክርስቲያን በማድረጉ የቀኑ አረማውያን በፈርዖን ትእዛዞና ፈቃድ የትንሣኤ ዕለት በዜተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው ገመድ በአንገቱ አስረው በእየአውራጃው በአሾህና በሱፋጭ ድንጋይ ላይ ሁለት ቀን ሙሉ ከጐተቱትና ደሙ በእየመንገዱ ሲፈስ ከዋለና ከአደረ በኋላ በሰማዕትነት ሞቷል፡፡ በድኑንም በአሳት ሊያቃጥሉ በነደደ አሳት ውስጥ ጨምረውት ነበር፤ ግን በተአምራት አልተቃጠለም፤ ደቀመዛሙርቱ ቀብረውታል።
(ስንክሳር ሚያዝያ 30 ቀን ገድ.ሐዋ.ም .21 ገጽ 161-164)





17. ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ፡-

ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ሦስተኛውን ወንጌል የጻፈው ቅዱስ ሉቃስ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ከተገደሉ በኋላ ሮም ገብቶ ወንጌልን ሲያስተምር በኔሮን ቄሣር ትእዛዝ በእርሱ ትምህርትና በሚያሳየው ተአምራት አምነው ክርስቲያን ከሆኑት አራት መቶ ሰባ ሰባት ሰዎች ጋር አንገቱን በሰይፍ ተቁርጦ በሰማዕትነት ሞቷል።
(ስንክሳር ጥቅምት 22 ቀን ገድ.ሐዋ.ም .13 ገጽ 119-122)

18. ቅዱስ ሐናንያ፡-

ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ቅዱስ ጳውሎስን ያጠመቀው ቅዱስ ሐናንያ በሐዋርያት አንበሮተ እድ የደማስቆ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሾሞ ብዙ ሰዎችን ክርስቲያን ስለአደረገና አምልኮተ ጣዖትንም ስለተቃወመ ሉቅያኖስ በተባለ ገዢ ትእዛዝ ደሙ በምድር ላይ እስከሚፈስስ ድረስ ተገርፎዋል፤ጕንበብረት ዱላ ተቀጥቅጡዋል፤ ደረቱን በጋለ ሽቦ አቃጥለውታል፤ በመጨረሻም ከከተማ አውጥተው በድንጋይ ወግረው ገድለውታል።
(ስንክሳር ጥቅምት 4 ቀን ሰኔ 27 ቀን)

19. ቅዱስ ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእ፡-

ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በአንድ ቤት አብረው ስለአደጉ የጌታ ወንድም እየተባለ የሚጠራው የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ያዕቆብ ድውያነ ነፍስን በትምህርት እየፈወሰ ብዙ ሰዎችን ስለአስተማረና ወደ ጥምቀተ ክርስትና ስለአስገባ፤ አይሁድ ቀንተው በሦስተኛ ደርብ ሆኖ ሲሰብክ ከደርቡ ላይ አውርደው ጽኑ ግ ር ፋ ት ገረፉት፤ ራሱንም በዱላ ደበደቡትና በሰማዕትነት ሞተ። (ስንክሳር ሐምሌ 18 ቀን)

20. ቅዱስ በርናባስ፡-

ከ72 አርድዕት አንዱ በርናባስ /ወልደ ኑግዜ/ ከቅዱስ ማርቆስ ጋር ቆጵሮስ ገብቶ / በማስተማር ብዙ ሰዎችን አሳምኖ ስለአጠመቀ አይሁድ ቀንተው ከገዢዎቹ አጣልተው ከባድ ግርፋት አስገርፈውታል፤ በእግር ብረትም አሰሩት፤ በድንጋይም ወግረው ገደሉት።
(ስንክሳር ታኅሣሥ 21)

21 ቅዱስ ይሁዳ ሐዋርያ ወልደ ዮሴፍ ፀራቢ፡-

ከ72ቱ አርድዕት አንዱ የእመቤታችን ጠባቂ የቅዱስ ዮሴፍ ልጅ ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ በብዙ አገሮች እየተዘዋወረና መልእክት እየጻፈ በማስተማር ብዙ ሰዎችን ከአጠመቀ በኋላ በመጨረሻ ሐራፒ በምትባል አገር ገብቶ በማስተማር ብዙ ሰዎችን ክ ር ስ ቲ ያ ን ሲያደርግ ሰምቶ የዚያች ሀገር ገዢ ይዞ ጽኑ ሥቃይ አሰቃየው፤ ችንካር ያለው ጫማ በእግሮቹ ውስጥ አስገብቶ አንድ ምዕራፍ ያህል አስሮጠው፤ ከዚያም ሰቀለውና በጦር ወጋው በዚህም በሰማዕትነት ሞተ፤ (ስንክሳር ሰኔ 25 ቀን ገድ.ሐዋ ም.7 ገጽ 84-90)

22. ቅዱስ ጢሞና፡-

ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ከ7 ዲያቆናትም አንዱ የሆነው ቅዱስ ጢሞና በሐዋርያት አንበሮተ እድ በብልቃ /ግሪክ/ ሀገር ምዕራብ በምትገኘው በሰብራ ሀገር ኤጲስ ቆጶስነት ተሾሞ

www.ethiopianorthodox.org

ከሮናናውያንና/ግሪኮች/ ከአይሁድ ብዙዎችን አስተምሮ አጥምቆዋል። የዚያች አገር ገዢ ይህን ሰምቶ በአሳት አቃጥሎ ገድሎታል። (ስንክሳር ጥቅምት 26)

23. ቅዱስ አጋቦስ፡-
ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ቅዱስ አጋቦስ ከአይሁድና ከግሪኮች ብዙ ሰዎችን አስተምሮ አጥምቆ ክርስቲያን በማድረጉ በቅንዓት የተመሉት አይሁድ በኢየሩሳሌም ብቻውን ስለ አገኙት ታላቅ ግርፋት ገርፈውታል፤ በአንገቱም ገመድ አስገብተው እስከ ከተማው ውጭ ጐትተው በድንጋይ ወግረው ገድለውታል።(ስንክሳር የካቲት 4 ቀን)

24. ቅዱስ አርስጥቦሎስ፡-
ከ72ቱ አርድዕት አንዱ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር ቅዱስ አርስጥቦሎስ ሐዋርያትን እየተከተለ በማስተማር ብዙ ሰዎችን ስለአጠመቀና ክርስቲያን ስለአደረገ በአብራጥያስም አገር ኤጲስ ቆጳስነት ተሾሞ ብዙዎችን ስለአሳመነ ከአይሁድና ከግሪኮች ብዙ ችግር ደርሶበታል። እየከሰሱ ወደ ገዢዎች በማቅረብ በድንጋይ እንዲወገር አድርገዋል፤ እግዚአብሔር ግን በተአምራት አድኖታል። (ስንክሳር መጋቢት 19 ቀን)

25. ቅዱስ መርቂሎስ /ጳውሎስ/፡-
ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ቅዱስ መርቂሎስ /ጳውሎስ/ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ረዳት ሆኖ ሮም ገብቶ ማስተማሩንና ብዙ ሰዎችን ማጥመቁን ኔሮን ቄሣር ሰምቶ ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ጳውሎስን ከአገደለ በኋላ ቅዱስ መርቂሎስን ተከቅዝቆ እንዲሰቀል እንዲሞት አድርጎታል። (ስንክሳር ሐምሌ 6 ቀን)

26. ቅዱስ አድሊጦስ፡-
ከ72ቱ አርድዕት አንዱ ቅዱስ አድሊጦስ መግኒን በሚባል አገር ገብቶ ብዙ ሰዎችን አስተምሮ ከአጠመቀ በኋላ አቴና ገብቶ ሲያስተምር አረማውያን በድንጋይ ወግረው ገደሉት፤ በድኑንም በአሳት አቃጠሉት። (ስንክሳር መስከረም 24 ቀን)

27. ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮም፡-
የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ቅዱስ ቀሌምንጦስ በሮም ብዙ አሕዛብን እያስተማረ በማጥመቁ ንጉሡ ጠልብሎስ ሰምቶ ክርስቶስን እንዲክድና የንጉሡን ጣዖት እንዲያመልክ ቢጠይቀው ስለተቃወመው ከባድ ብረት በአንገቱ አንጠልጥሎ በባሕር ውስጥ አሰጠመው። ስለዚህም በሰማዕትነት ሞተ።(ስንክሳር ?ዳር 29 ቀን ገድ.ሐ.የታተመው ገጽ 11-12)

28. ቅዱስ ጢሞቴዎስ፡-
በአባቱ ግሪካዊ በእናቱ አይሁዳዊ የሆነው በልስጥራን አገር የተወለደው የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር ቅዱስ ጢሞቴዎስ ወገኖቹን አይሁድንና ግሪኮችን አስተምሮ ክርስቲያኖችን በማብዛቱ ቀንተው ገድለውታል። (ስንክሳር ጥር 23 ቀን)

29. ቅዱስ አናሲሞስ፡-
የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር ቅዱስ አናሲሞስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሞተ በኋላየንጉሡ ወታደሮች አለታ ወደ አንዲት ደሴት ወስዶ ከአጋዘው በኋላ በዚያች ደሴት ያሉትን ሰዎች አስተምሮ ክርስቲያን ማድረጉን ስለሰማ ከባድ ግርፋት አስገርፎና ጭኖቹን አሰብሮ በግፍ አስገድሎታል። (ስንክሳር የካቲት 21 ቀን)

30. ቅዱስ ጊዮርጊስ፡-
በዐውደ ዱድያኖስ 7 ዓመት የተሰቃየው ቅዱስ ጊዮርጊስ በንጉሡ በዱድያኖስ ትእዛዝ በሰይፍ አንገቱን ተቁርጦ በሰማዕትነት ሞቱዋል። (ስንክሳር ሚያዝያ 23 ቀን)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፲ (2000) ዓ.ም

31. ቅዱስ ቴዎድሮስ፡-
የአንጾኪያው ሰው ቅዱስ ቴዎድሮስ በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ በ153 ረጃጅም የብረት ችንካሮች ተቸንክሮ በሰማዕትነት አርፎዋል። (ስንክሳር ጥር 12 ቀን)

32. ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ፡-
አንጌቤናዊው ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ አለእስክንድሮስ በተባለ ገዢ ትእዛዝ በፈላ ውሀ በነደደ እሳት በጋለ ብረት በመጥበስ ከዚያም በከፉ በልዩ ልዩ ጸዋትው መከራ ሲሰቃዩ ከቁዩ በኋላ በሰይፍ አንገታቸውን ተቁርጠው በሰማዕትነት አርፈዋል።
(ስንክሳር ጥር 15ና ሐምሌ 19 ቀን)

33.ቅዱስ ፋሲለደስ፡-
ቅዱስ ፋሲለደስ በዲዮቅልጥያኖስ መስፍን ትእዛዝ በሰይፍ አንገቱን ተቁርጦ በሰማዕትነት ሞቱዋል። (ስንክሳር መስከረም 11 ቀን)

www.ethiopianorthodox.org

34.ቅዱስ ገላውዴዎስ፡-

የሮሙ ንጉሥ የትማርያኖስ ወንድም ቅዱስ ገላውዴዎስ በጣዖት አላመልክም ለጣዖትም አልሰግድም ስለአለ፣ በዚህም ላይ ገላውዴዎስ የነገሥታት ዘር ስለሆነ መንግሥቱን ይቀማኛል ብሎ በመስጋት ዲዮቅልጥያኖስ በጦር ተወግቶ እንዲገደል አድርጎታል። (ስንክሳር ሰኔ 11 ቀን)

45. ቅዱስ ቴዎድሮስ ካልዕ፡-

በላዕላይ ግብፅ ሰጥብ በምትባል አገር የተወለደው የንጉሥ ዲዮቅልጥያኖስ ሊቀ ሠራዊት የነበረው ቅዱስ ቴዎድሮስ ንጉሡ ክርስቶስን ክዶ ጣዖት አቁሞ በመስገዱና በማሰገዱ ስለተቃወመው ከአስገረፈውና ከባድ ድብደባ ከአስደበደበው በኋላ አንገቱን በሰይፍ አስቈርጦት በሰማዕትነት ሞቷል። (ስንክሳር ሐምሌ 20 ቀን)

36. ቅዱስ መርቆሬዎስ፡-

መርቆሬዎስ ማለት ገብረ ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት ነው፤ ሀገሩ ሮሜ ነው፤ በዘመኑ ዳኪዎስ የሚባል የሮም ንጉሥ ነበር፤ ጣዖት አምላኪ ነው፤ መርቆሬዎስ የርሱ ወታደር ነበር፤ በርበር የተባሉ ጠላቶች ተነሥተውበት በጦርነት ድል አድርጎ አሳርፎት ነበር፤ በኋላ ግን ለጣዖት ካላጠንህ ብሎ በርጥብ የዘንባባ በትር አስገረፈው፤ ዳግመኛም በበሬ ቍርዝ አስገረፈው፤ ኋላም በአግር ብረት አሥሮ ወደ ቀጴጵቅያና ወደ አስያ ቂሣርያ መከራ እንዲያጸኑበት ላከው፤ብዙ መከራ ከአደረሱበት በኋላ አንገቱን በሰይፍ ቆርጠው ገደሉት፤ የተገደለውና በሰማዕትነት የሞተው በንጉሡ በዳኪዎስ ትእዛዝ ነው።(ስንክሳር ?ጳጉሜ 25 ቀን)

37. ቅዱስ ቶማስ ዘመርዓስ፡-

የመርዓስ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ቶማስ በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ በጨለማ ቤት 22 ዓመት አሥረውታል፤ ከሐዲዎች በየዓመቱ ወደታሠረበት እየገቡ ከሰውነቱ አንድ አንድ ብልት እየቈረጡ አካሉን ቈርጠው ጨረሱት፤ በመጨረሻ በአሳት የተሰበሰበ ግንድ አስመሰሉት፤ (ስንክሳር ጎጃር 9 ቀን ፣ ነሐሴ 24 ቀን)

38. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ፡-

የአርማንያ /አርመን/ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ሰማዕት ዘአንበሳ ደም ነው፤ ይኸውም የአርማንያ ንጉሥ ድርጣድስ ለጣዖት ከአልሰገድህና ከአልሠዋህ ብሎ ከአሠቃየው በኋላ ጥልቅ ወደሆነ ደረቅ ጉድጓድ ውስጥ ጨምሮ ዐሥራ አምስት ዓመት በጉድጓድ ውስጥ አሥሮት ኖሩዋል፤ በዚያም ከአሥር ቤት እያለ ሞቱዋል።(ስንክሳር ታኅሣሥ 15)

39. ቅዱስ ዲዮስቆሮስ፡-

25ኛው የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ "ሁለት ባሕርይ" የሚለውን የንስጥሮስንና የልዮንን ሃይማኖት ከአልተቀበልህ ተብሎ በርሙ ንጉሥ በመርቅያንና በዕቴጌይቱ በብርክልያ ትእዛዝ ተደብድቦ ጥርሱ ወልቆ ጠጉሩ ተነጭቶ በደሴተ ጋግራ ታሥሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ኖሩዋል። (ስንክሳር መስከረም 7 ቀን)

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዓለም ዐቀፍ ሰማዕታት ጥቂቶችና በጣም የታወቁት ብቻ ናቸው። ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እስከ 4ኛው መቶ ዓመት እስከታላቁ ቈስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ሥሉጥ የሌላቸው አያሌ ምእመናን በሰማዕትነት ሞተዋል።

በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት በግብፅ ብቻ ስምንት መቶ ሺ ክርስቲያኖች በሰማዕትነት ሞተዋል ይባላል። ከዚህም የተነሣ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የምትቈጥረው በዓመተ ሰማዕታት ነው።



# ክፍል 1

## ሰማዕታተ ናግራን

ክርስትና ወደ ዐረብ አገር የገባው በመጀመሪያው መቶ ዓመት አጋማሽ ነው። ገላ.1፣17

በመጀመሪያ በዐረብ አገር በናግራን ክርስትናን የመሠረተው ፋሚውም የሚባል የሶርያ ተወላጅ ነው ይባላል። ከዚያም በየጊዜው ከሮስጥንጥንያ ብዙ ቀሳውስት፣ ኤጲስ ቆጳሳት እየሔዱ ክርስትናን አስፋፉ፤ ከእነዚህም በጣም ታዋቂው ሐዋርያ አባ ጳውሎስ ይባላል።

ምንም እንኳ መምህራኖቻቸው ከሮስጥንጥንያና ከሶርያ የመጡ ቢሆኑም፣ የናግራን ክርስቲያኖች የአክሱምን መንግሥት እንደ በላይ ጠባቂና ደጋፊ መቍጠራቸው የታወቀ ነበር። ዳሩ ግን የደቡብ ዓረብ ይልቁንም ሀገረ ናግራን ለአክሱምና ለቍስጥንጥንያ መንግሥታት በሩቅ ስለሚገኝ የሮም የጦር መሪዎች አስባስያኖስና ጥጦስ በ70 ዓ.ም. ከኢየሩሳሌም አይሁድን በአሳደዱዋቸው ጊዜ ሀገረ ናግራንን ወርሰዋት ስለነበር እነዚሁ አይሁድና አረማውያኑ ተባብረው በጠብ ዐይን ክርስቲያኖቹን እያዩ በየጊዜው አጠቁዋቸው። ከማጥቃትም አልፈው ይፈጁዋቸው ጀመር። የናግራን ሰማዕታት በዓለም ዐቀፍ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሚታሰቡ ሰማዕታት ናቸው። የአይሁድ ንጉሥ ፊንሐስ ይባል ነበር፤ በሀገረ ናግራን ክርስቲያኖች የሚኖሩባት ታላቅ ከተማ ነበረች። በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፊንሐስ ሊያጠፋት መጣ፤ ቅጽሩዋ በደንብ የተቀጸረና በሠራዊት የተከበበ ስለነበረ ሊገባባት አልቻለም፤ ስለዚህም ተበሳጨ በውጭ ያገኛቸውን ዝቡራዎች ገደለ፤ ታናናሾቹንም ማርኮ ለባሮቹ ሰጣቸው። ፊንሐስም "እኔ ከእናንተ ጋር ጠብ አልፈልግም፤ ከሀገር ሰው አንዱን እንኳ ማጥፋት አልሻም በከተማዋም ውስጥ የደም ጠብታ አይፈስም፤ ነገር ግን የከተማዋን አሠራርዋን፣ አደባባዮቿን፣ ገበያዎቹዋን ማየት እሻለሁ" ብሎ እየማለ ለከተማው ባለሥልጣኖች ላከ፤ መልእክቱ ሄሮድሳዊ ሽንገላ ነበር እንጂ እውነት አልነበረም።

የሀገረ ናግራን ክርስቲያኖች አባታቸው ቅ/ኒሩት ይባል ነበር። አባት ኒሩትም "ይህን አይሁዳዊ አትመኑት፤ ሐሰተኛ ነውና፤ በሩንም አትክፈቱለት አላቸው። አባት ኒሩትንም አልሰሙትም፤ በሩን ከፈቱለትና ገባ፤

ይህ ፊንሐስ /ማዝሩቅ/ የሚባለው የሚሚያሪት /የመን/ ንጉሥ የአይሁድንና የአረመኔዎቹን ድጋፍ ይዞ ክርስቲያኖቹን አሳደደ፤ ገንዘባቸውን አዘረፈ፤ ሁለተኛም ነበልባሉ ወደ አየር እስከሚደርስ እሳትን አንድደው የሀገሪቱን ኤጲስ ቆጳስ አባ ጳውሎስን እንዲያመጡት አዘዘ፤ እሱ እንደ ሞተ በነገሩት ጊዜ ዐጽሙን ከመቃብር አውጥቶ አቃጠለው።

ከዚህም ሌላ ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ መነኮሳትን አንባቢዎችንና መዘምራንን ሰብስቦ እነሱንም በእሳት ውስጥ ጨመራቸው፤ ሥጥራቸውም 4027/አራት ሺህ ሃያ ሰባት/ ሰዎች ነበሩ፤ ይህንም ያደረገው ክርስቲያኖችን ለማስፈራራት ነበር።

ዳግመኛም የብረት ዛንጅር /አንገት ብረት/ በቅዱስ አባት ኒሩት አንገት ውስጥ እንዲያስገቡ አዘዘ፤ የሀገሩን መኳንንትና ታላላቅ ሰዎችን እንዲያሥሩዋቸው ክርስቶስን የማይክድ ሁሉ እንዲህ ተሰቃይቶ በክፉ አሟሟት ይሞታል የሚል ዐዋጅ ነጋሪ እየጮኸ በከተማው ውስጥ እንዲያዞራቸው አዘዘ።

ቅዱሳን ሕዝበ ክርስቲያንም በሰሙ ጊዜ እንዲህ አያሉ ጮሁ" እኛ የአመንበትንና በስሙ የተጠመቅንበትን ክርስቶስን አንክደውም፤" ይህ ርኅም አይሁዳዊም ሰምቶ ወንዶችንና ሴቶችን፣ ወጣቶችንና ሕፃናትን፣ ሽማግሌዎችንም ሁሉ እንዲገድሉ አዘዘና ገደሉዋቸው፤ ሥጥራቸውም 4252/አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ሁለት/ ሰዎች ነበሩ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም በኋላ የቅዱስ ኂሩትን ሚስት ቅድስት ድማህን ከሁለት ሴቶች ልጆቿ ጋር ያዟት፤ በንጉሡ ፊት አቀረቡዋትና ሃይማኖታቸውን እንዲክዱ ተጠየቁ፤ "ሃይማኖታችንን እንክደም" ስለአሉ የቅድስት ድማህን ሁለቱን ልጆቿን በሰይፍ ቁረጡዋቸውና ቅድስት ድማህም ፈጣሪዋን ለምናና አመስግና እስዋም እንደ ልጆቿ በሰይፍ ተቀላች፤ ሦስቱም በሰማዕትነት ተጋድሎዋቸውን ፈጸሙ፡፡

ከዚህም በኋላ ቅዱስ ኂሩትን ከወኀኒ ቤት ያመጡት ዘንድ አዘዘ፤ ከእርሱም ጋር 1040/አንድ ሺህ አርባ/ አስረኞች ሰዎች ነበሩ፡፡ ቅዱስ ኂሩትንም ሃይማኖቱን ይተው ዘንድ አስገደደው፤ ቅዱስ ኂሩትም ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን እያመለክሁት ስኖር 78/ሰባ ስምንት/ ዓመት ሆነኝ፤ እስከ 4 ትውልድ ለማየት ደርሻለሁ፡፡ ዛሬም ስለ ክበረ ስሙ ምስክር ሆኜ ስሞት እጅግ ደስ ይለኛል" አለው፤ ንጉሡም ወደ ወኀኒ ወስደው፤ በዚያ አንገቱን እንዲቁርጡት አዘዘ፤ ቅዱስ አባት ኂሩትም ይህን በሰማ ጊዜ ደስ አለው፤ የሮምና የኢትዮጵያ መንግሥት ያጸና ዘንድ የተረገመ የአይሁድን መንግሥት ያጠፋ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ ሕዝቡንም ባረካቸው፤ ከዚህ በኋላ ፊንሐስ የቅዱሳኑን ራሳቸውን ቁረጣቸው፡፡

በዚያም የአምስት ዓመት ልጅ ያላት አንዲት ክርስቲያን ሴት ነበረች፤ ከቅዱሳኑ ደም ወስዳ ተቀባች፤ ልጅዋንም ቀባችው፤ ወታደሮችም አይተው አስረው ወደ እሳት ጨመሩዋት፤ ልጅዋን ግን አይሁድ ወደ እነሱ ወስደው ወደ ንጉሡ አቀረቡት፤ ንጉሡም "እኔን ትወዳለህን? ወይስ ክርስቶስ የሚሉትን?" አለው፤ ሕጻኑም "እኔስ የአጼ ሥራ ነኝና ክርስቶስን እወደደዋለሁ፤ ይልቅስ ልቀቀኝ ወደ እናቴ ልሒድ " አለው፡፡ በክለክለውም ጊዜ እግሩን ነክሰው፤ አምልጦም ሮጦ ወደ እሳቱ ውስጥ ገባ፡፡

ሁለተኛም የዐሥር ወር ሕጻን እንደ ተሸከመች አንዲትን ሴት አመጡዋት፤ እናቲቱም ስለ ልጅዋ ስታዝን ልጁ ሰምቶ አይዞሽ እናቴ ክዛሬ በኋላ ይህን እሳት አናየውም አላት፤ በዚያ ጊዜ ከልጅዋ ጋር ወደ እሳት ተወረወረች፡፡

ሕዝበ ክርስቲያኑም ይህን አይተው ግማሾቹ ወደ እሳት ግማሾቹም ወደ ሰይፍ ተሸቀዳደሙ፡፡ በዐረቢያ በረሀ በናግራን ከተማ አይሁድ የፈጸሙት ግፍ የተሞላበት ጭፍጨፋ መላውን ዓለም ያሳዘነ ነው፡፡ የሮም ንጉሥ ዮስጢናስም ይህን ሰምቶ ወደ እስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ወደ አባ ጢሞቴዎስ መልእክት ላከ፤ በሀገረ ናግራን ከሚኖሩ የክርስቲያን ወገኖች ደማቸውን ይቀበል ዘንድ ለኢትዮጵያ ንጉሥ ለዐፄ ካሌብ መልእክት እንዲልክ ነው ንጉሡ ለሊቀ ጳጳሳቱ የላከበት፡፡ ክርስቲያን የነበሩትን የኢትዮጵያን ንጉሥ ካሌብን ለማሳመን የተመረጡት የግብፅ ፓትርያርክ አቡነ ጢሞቴዎስ የመልእክት አሳላፋቸው የክርስቲያኖችን ግፍና መከራ የሚያሳይ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ንጉሥ ዓፄ ካሌብም መልእክቱ በደረሳቸው ጊዜ ፈጥነው ተነሥተው ወደ አክሱም ጽዮን ገብተው ጸሎት አድርገው በዋሻ ከሚኖሩት ከጻድቁ አቡነ ጳንጠሌዎን በረከትን ተቀብለው ከ120,000/አንድ መቶ ሃያ ሺ/ በላይ ከሆኑ ሠራዊት ጋር በመርከብ ተሳፍረው ወደ ሀገረ ናግራን ሔዱ፤ ናግራንም በደረሱ ጊዜ የንጉሡን የፊንሐስን ከተማ ደመሰሱ፤ ሰውም እንስሳም ተመታ፤ ሸሹት ለማምለጥ የቻለ የለም፡፡

ከዚህ በኋላ የናግራንን ከተማ ሕንፃዎች አደሱ፤ የሰማዕታትንም መታሰቢያ ሐውልት በከተማው አቆሙ፡፡ ቀጥሎም ወደ ሮም ንጉሥ ወደ ዮስጢናስ፤ ወደ እስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ወደ አባ ጢሞቴዎስ የምሥራች ላኩ፤ እነሱም ሰምተው እጅግ በጣም ተደሰቱ፡፡ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት፡፡ (ስንክሳር ኅዳር 26 ቀን)

በ524 ዓ.ም. በናግራን የተደረገውን ዕልቂት በዘመኑ የነበሩ የዐረብ፤ የቀስጥንጥንያና የሶርያ ታሪክ ጸሐፊዎች፤ የመንግሥትና የቤተ ክህነት ደራሲዎች እነፕሮኮፒዎ፤ እነሰርጊዮስ በልዩ ልዩ ዓይነት እየከፋፈሉ በዝርዝር ጽፈውታል፡፡

በእነሱ አጻጻፍ ማዝሩቅ (ፊንሐስ) የሚባለው የሂሚያሪት /የመን/ ንጉሥ በክርስቲያኖቹ ላይ ጭፍጨፋ በፈጸመበት ጊዜ የክርስቲያኖቹ ጳጳስ አባ ቶማስ ወደ አክሱም መጥቶ ለአክሱሙ ንጉሥ በክርስቲያኖቹ ላይ የተደረገውን ግፍ አስመልክቶ በሐይዋና የሚመራ ጦር ይዞ ተመለሰ፤ በዚህ ጊዜ ማዝሩቅ /ፊንሐስ/ ከአክሱም የዜደውን የጦር ሠራዊት ብዛት በአየ ጊዜ ፈርቶ ዕርቅ አደረገ፤ በዕርቅ ብዙውን ሠራዊት ከመለሰ በኋላ ዕርቁን አፍርሶ ክርስቲያኖቹን እንዲጠብቅ በናግራንና በዛፋር የቀረውን 300 የሚያህል ወታደርና ክርስቲያኖቹን ፈጃቸው፡፡ በናግራን፤ በዛፋርና በሀድራሞት ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት አቃጠለ፤





የአክሱም ንጉሥ ዓፄ ካሌብም ይህን መርዶ በሰሙ ጊዜ ዛውንስ የሚባለውን የጦር አለቃቸውን አስከትለው የኤርትራን ባሕር በመርከብ ተሻግረው ዓረብ አገር ከገቡ በኋላ የማገሩትን /ፊንሐስ/ ጦር ፈጅተው ንጉሡን ገደሉ፤ በአገሩም ላይ አሱአር የሚባለውን አንግሠው እንደተመለሱ ጽፈዋል፡፡

የሁለቱም ታሪክ ጸሐፊዎች አተራረክ በተለያየ መንገድ ቢሆንም መደምደሚያውን የክርስቲያኖቹን ማለቅና የካሌብን መበቀል ከመግለጽ አይዘለሉም፡፡

የአነባጅና የአነ ኮንቲሮሲኒ አጻጻፍ እንደሚገልጸውም የአክሱሙ ንጉሥ ዓፄ ካሌብ ጦሩን ያዘመቱት ከቀስጥንጥንያው ንጉሥ ጋር ስምምነትና ምክክር አድርገው መሆኑን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ዓፄ ካሌብ በ525 ዓ.ም. የሂሚያሪቱን /የመን/ ንጉሥ ፊንሐስን ድል አድርገው ከገደሉት በኋላ ለዐረብ ግዛት አብርሃ የሚባለውን ሾመው መመለሳቸውን ይናገራሉ፡፡

በሞሪዬ የታሪክ መጽሐፍ ደግሞ ቀጥሎ ያለው ተጽፎዋል፡፡ ዓፄ ካሌብ /አለ አጽብሐ/ በአክሱም በነገሡበት ዘመን የቀስጥንጥንያው ንጉሥ የአናስታስ ዘመን ማለቂያ ላይ ሃይማኖቱ ይሁዲ የሆነው ዱናዋስ /ፊንሐስ/ የሚባል በሂሚያሪት /የመን/ ነገሠ፤ አሱም እንደ ነገሠ ከ518-519 ዓ.ም. 4250 ክርስቲያኖችን አረደ፡፡ ይህም ችላ ተብሎ ላለ በተከታታይ ዓመታት ከዚህ የበለጠ ግፍ በክርስቲያኖች ላይ ፈጸመ፡፡ በከተማው ውስጥ ብዙ መነኮሳትን፤ አያሌ ካህናትንና ምእመናንን ጨፈጨፈ፤ ሀብታቸውን ዘረፈ፤ ቤተ ክርስቲያናቸውን አቃጠለ፡፡

ጨካኙ ዱናዋስ /ፊንሐስ/ በዚሁ በናግራን ጉድጓድ አስቁፍሮ እሳት እያስነደደ ክርስቶስን እንክድም ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ ጉድጓዱ እያስጨመረና እያቃጠለ ፈጃቸው፡፡ በዚያም ቀን 20 ክርስቲያኖች ተፈጁ፡፡

ይህን ሁሉ ከአደረገ በኋላ የክርስቲያኖቹን መሪ የተከበረውን የ95 ዓመት ሽማግሌ አሬታስ /ኂሩት/ የሚባለውን ከእነዜተሰቡ አስመጥቶ "ክርስቶስን ካድ" ቢለው "እልክድም" ስለአለው እንገቱን በሰይፍ አስቁርጦ ገደለው፡፡

በዚህ ጊዜ በቀስጥንጥንያ ዙፋን አናስታስ ሞቶ በምትኩ ዮስቲኖስ ተቀምጦ ነበርና የዚህን ወራ ሲሰማ በጣም አዘነ፤ ስለዚህ ጉዳይ ለእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ለአስትሪዩስ /ከጢሞቴዎስ ቀጥሎ የተሾመ/ ደብዳቤ ጻፈ፡፡ ሊቀ ጳጳሳቱም ለአክሱም ንጉሥ ደብዳቤ ጻፍለት ብሎ መከረው፡፡ ከዚህ በኋላ ኖኖስስ ለሚባል መልእክተኛ ደብዳቤ አስይዞ ለአክሱሙ ንጉሥ ላከ፡፡

የአክሱሙ ንጉሥም መልእክቱን በአክብሮት ከተቀበለ በኋላ 70ሺ ጦር በደንብ አዘጋጅቶ በ524 ዓ.ም ወደ የመን ተጓዘ፤ እንደደረሰም 30ሺ ጦር ይዞ የአይሁድ ጦር ሠራዊት ከመርከብ ሲወርድ ጠብቆ ገጥሞ ጋፈጠው፡፡ የካሌብ ጦር ወዲያው አሸንፎ በታተናቸው፡፡

ከዚያም ካሌብ ወደየመን ከተማ ወደ ዛፋር ሔደው የከተማውን ጠባቂዎች አሸንፈው ከተማውን ያዙ፤ አይሁድ ንጉሥ በአልተቤትም በዚህ ጊዜ ተማረከች፡፡ ከዚያም በኋላ ከአይሁድ ንጉሥ ከዱናዋስ /ፊንሐስ ጋር ተገናኝተው ካሌብ ራሳቸው ፊንሐስን ወግተው ከፈረሱ ላይ ወደ ባሕር ገለበጡትና ሞተ፡፡

ይህም የሆነው በ525 ዓ.ም. ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ካሌብ ወደ ዛፋር ከተማ ተመልሰው የክርስቲያኖቹ ዕልቂት በተፈጸመ ጊዜ ደም በማፍሰስ አባሪ ተባባሪ የነበሩትን የፊንሐስን ሹሞች እያሲያዙ አስገደሉና በሀገረ ናግራን የተፈጁትን የምእመናን ደም በሚገባ ተበቀሉ፤ ክርስቲያኖችም ከስደት በየስፍራቸው ተመለሱ፡፡

ካሌብም ወደ እስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት የድሱን ዜና በደብዳቤ ገለጡ፤ ሊቀ ጳጳሳቱም ወደ ቀስጥንጥንያ ንጉሥ ልከው ስለ አዘሠሩ በሁሉም ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ፡፡ /የኢትዮጵያ ታሪክ ከኑብያ - አክሱም ተክለ ጻድቅ መኮሪያ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብፁዕ አቡነ ኅርኅርዮስ/



www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል 2

## ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በዘመነ ዮዲት

በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመንና በየጊዜውም ብዙ የእስራኤል ሕዝብ ካህናትም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሕዝቡን ሕገ ኦሪት እያስተማሩ በእውነተኛው አምላክ በእግዚአብሔር እንዲያምን አድርገውታል። በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥት ቅዱስ አባ ሰላማ /ፍሬምናጦስ/ ሢመተ ጵጵስናንና ሥርዐተ ክርስትናን ከአመጣ በኋላ ክርስትናው በአክሱምና በመላ ኢትዮጵያ እየተስፋፋ በመሔዱ ሁሉም ጕጉ ተቀብሎት ሲኖር የእስራኤል ወገኖች የሆኑት ክርስትናን አንቀበልም ብለው በዚያው በቀድሞው የኦሪት ሃይማኖት ሥርዐት ጸንተው ተቀመጡ። እነዚህም የሚኖሩት በሰሜን ኢትዮጵያ ነበር። ከአክሱም ፈልሰው በእነዚህ አካባቢዎች ስለሰፈሩ ፈላሻዎች ይባላሉ። ቍጥራቸው እየበዛ፣ ኀይላቸው እየበረታ ሲሔዱ ከመካከላቸው ጌሥዎን የሚባለውን አንደ ንጉሥ አድርገው ሾሙት። ስጌሥዎን በጣም ቆንጆ ልጅ ነበረችው፣ እሱዋም ዮዲት የምትባለው ነች።

በርስዋ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሥ ድግናዋን /ግዳጃን/ ነበር፣ ነገር ግን እሱ ስለሞተ አንበሳ ውድም የሚባለው ሕፃን ልጁ ነገሠ፣ የነገሠው ንጉሥ ሕፃን ስለሆነ ለማስተዳደር አለመቻሉን ዮዲት በዐወቀች ጊዜ በስሜንና በባስታ የሚኖሩትን ፈላሾች ወገኖቿን ይዛ ወደ አክሱም ዘመተች።

የአክሱም መሳፍንትም ሕፃኑን ንጉሣቸውን እንደያዙ ዮዲትን በመፍራት ከትግራይ ወደ ሸዋ ሸሹ። ከዚህ በኋላ በ842 ዓ.ም. ነገሥትና በአክሱምና በዙሪያው ያሉትን ሐውልቶች እያስፈረሰች አብያተ ክርስቲያናቱን ሁሉ አቃጠለች፣ ከነገሥታት የሚወለዱትን መሳፍንትና የክርስትና ሃይማኖት መሪዎች ካህናትን አሳረደች። በአጠቃላይ ክርስቲያኖችን አስጨፈጨፈች። በዚህ ጭካኔዋ ዮዲት የተባለው ስሟ ተለውጦ ጉዲት፣ አሳቶ ተባለች ይባላል።

አንበሳ ውድም ወደ ሸዋ ሸሽቶ በመጣ ጊዜ የሸዋ ሕዝብ በደስታ ተቀበለው። ከአክሱም ጸዮን ጀምሮ በሰሜን ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና መጻሕፍት ሲቃጠሉ ታቦታቱ ወደዙዋይ መጥተው በዝዋይ ደሴት ተቀምጠው ከአሳት ዳኑ።

ጉዲት /ዮዲት/ ይህን በሰማች ጊዜ በነገሠች በ23ኛው ዓመት ብዙ ወታደር ወደ ሸዋ ላከች። የተላኩትም ወታደሮች አንበሳ ውድምን መንዝ ላይ ጦርነት ገጠሙት።

አንበሳ ውድምም የመንዝን ባላገር ይዞ የዮዲትን ጦር ተዋግቶ መለሰው። ከዚህ በኋላ ራሱዋ ጉዲት የቀረውን ጦሩዋን እየመራች ወደ ሸዋ መጣች፣ አንበሳ ውድምም መምጣትዋን ሲሰማ ከመንዝ ወደ መራቤቴ ወረደ። እርስዋም ንጉሡን ለመከታተልና ለመያዝ ወይም ለመግደል ሞክራ ሳለ የመንዜ ገደላገደልነት ስለ አስቸገራት፣ በዚህም ላይ ንጉሡን የሚረዳው የሸዋ ሕዝብ በደፈጣም በፊት ለፊትም ጦርነት አደጋ እየጣለ አልበገር ስለ አላት ከሸዋ ወደ አክሱም ተመልሳ የተረፉትን አብያተ ክርስቲያናት እያቃጠለችና ክርስቲያኖችን እየፈጀች 17 ዓመት ያህል ኖራ በሙሉ 40 ዓመት ነግሣ ሞተች።

ከዚህ በኋላ አንበሳ ውድም ወደ አክሱም ተመልሶ በአባቶቹ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ሥልጣኑን በማደላደል የፈረሱትንና የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት እንደገና አቋቋመ። የተሰደዱትም ክርስቲያኖች በየቦታቸው ተመለሱ። (የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጌ ተክለ ጻድቅ መኮሪያ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትሪክ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ)



# ክፍል 3

## ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በዘመነ ግራኝ መሐመድ

በዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያንና የፖርቱጋልን ቤተ መንግሥት መላላክና መወዳጀት ያወቁትና በዚሁ የነገሡት በሕንድና በምጥዋ በቀይ ባሕር ዳር ዳር በግዛት ሚትና ማታ ከፖርቱጊዞች ጋር የሚዋጉት ቱርኮች ለግራኝ አሕመድ የበቃ አዳዲስ መሣሪያና ጥይት አስረክበት፣

ግራኝ አሕመድም በዐፄ ልብነ ድንግል ጦር ሠራዊት ውስጥ የማይገኘውን አዳዲስ መሣሪያ እንደ ልቡ በአገኘ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ለማድረግ ተዘጋጀ።

ሲመቸው የሚሸፍተው ሳይመቸው የሚገብረው የአዳልና የሐረር ሕዝብ መብርን በጠላ ጊዜ ተከላካይ ነበር እንጂ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የአጥቂነት ተግባር በሥራም በመንፈስም አላሳየም ነበር። በኋላ ግን ቱርክን የሚያህል ታላቅ መንግሥት ደጋፊ፣ ግራኝ አሕመድን የመሰለ አክራሪና አመፀኛ የጦር መሪ በአገኘ ጊዜ የሐረር፣ የሱማሌ፣ የአዳል ሕዝብ አልገብርም ማለትና በገዛ አገሩ መሸፈት ሳይበቃው ቀርቶ ወደ አጥቂነት ስፋራ ዞሮ ኢትዮጵያን ለመውረር የክርስቲያኑን መንግሥት ገልብጦ የአስላምን መንግሥት ለማቆም በአብያተ ክርስቲያናት ምትክ መስጊዶችን፣ በወንጌል ምትክ ቁርዓንን ለመተካት በዚሁ በግራኝ መሪነት ተዘጋጀ።

በቱርክ መንግሥት ዘመናዊ መሣሪያ የሚዋጋውን የግራኝን ሠራዊት በጦርና በጉራዴ መከላከል ስለአልተቻለ በኢትዮጵያ ምሥራቅና ሌብ፣ ደቡብና ዐዜብ የሚገኘው አገር ሁሉ በግራኝ አሕመድ ሥልጣንና አስተዳደር ውስጥ ገባ፣ በእጁ የወደቀውን ክርስቲያን ሁሉ በሰይፍ አያስፈራራ በግድ አስለመው፣ አንቢ ያለውንም አረደው። በመላ ኢትዮጵያ የነበረው ሕዝበ ክርስቲያን ብብዛት የሰለመው በዚያ ጊዜ በግራኝ ሰይፍ አስገዳጅነት ነው። የጋብቻም ሥርዐት የተበላሸው ከዚያ ወዲህ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ግራኝ አሕመድ ከግራኝ አሕመድ ጋር ጦርነት ከጀመሩ እንሥቶ ሕይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ ፀሥራ ሦስት ዓመት ሙሉ ከአገር ወደ አገር እየዞሩ ለሀገራቸው፣ ለመንግሥታቸውና ለሃይማኖታቸው ሲከላከሉ በየጦርነቱም ልጆቻቸው እነ ፊቅጦር፣ እነ ሚናስ፣ መኳንንቶቻቸው እነ ራስ ወሰንሰገድ፣ እነ ራስ ማዕጠንቱ፣ እነ ራስ ዳገልሀን፣ እነ ነራስ ዐምዱ፣ እነ ጸሐፌ ላሕም /የወረገኑ ሹም/ ሮቤል፣ እነ ዐቃቤ ሰዓት ነገደ ኢየሱስ፣ እነ አዝማች ዮሐንስ፣ እነ አዛዥ ተክለ ጊዮርጊስ፣ እነ ሮምሰገድ፣ እነ አስላም አሰግድ፣ እነ ጌጴዎን፣ እነ ግራጌታ ፅገራ .... ወዘተ ሲሞቱ፣ ሲማረኩ፣ ሲሰደዱ፣ የዚህ ሁሉ የጦርነትና የሞት፣ የመራብና የመጠማት፣ የመንከራተት አደጋ ከጊዜ ርዝመት ጋር ተስፋ አስቈርጦ መንፈሳቸውን አላላላውም። በዚህም የጠላያቸውን ብርታት፣ የጎሰናቸውን ጥብቅነት፣ የልባቸውን ቈራጥነት እንረዳለን። የፀሥራ ሦስት ዓመት ፅድሜ በአለው ጊዜ ውስጥ ከተድላ፣ ከደስታ፣ ከሞቀ ቤተ መንግሥት ተለይቶ በዱርና በበረሀ እየተዘዋወሩ ከንይለኛ ባላጋራ ጋር አስከሞት ድረስ ቈርጦ መከላከል በእውነትም እንደርሳቸው የመሰለ ቈራጥና ጉብዝ ካልሆነ በቀር ቅምጥልነትን፣ ደስታን የሚፈልግ መሪ ሁሉ የሚችለውና የሚሸከመው አይደለም።

በጉብዝና በኩል ጠንካራነታቸውን ስንመለከት ደግሞ ለአምልኮተ እግዚአብሔርና ለክርስትና ሃይማኖት ፍጹም ቀናዒና ተከላካይ መሆናቸውን ከግራኝ ጋር ስለጋብቻ የተመላለሱት ንግግር ያስረዳናል።

ግራኝ አሕመድ በጦር ኀይል አሸንፎ በሦስቱ ሩብ የኢትዮጵያ ግዛት ላይ ተስፋፍቶ ግዛቱን በመሠረተ ጊዜ "ከግራኝ ጋር መዋጋት ከእግዚአብሔር ጋር እንደመዋጋት ይቈጠራል፣ ይልቅስ ሴት ልጅዎን ይዳሩልኝና አንታረቅ...." ሲል የዕርቅ ድርድር አቅርቦላቸው ነበር። እርሳቸውም ለዚህ ጥያቄ "ለአንድ ክርስቲያን ለአልሆነና ሃይማኖቱ ለአልታወቀ ልጄን ሰጥቼ ከመታረቅ፣ በኀጢአታችን ምክንያት በሚቀጣን በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻለናል፣ እርሱም ምሕረቱ ለዘለዓለም ስለሆነ በፊቀደ ጊዜ ኀይለኞችን ደክሞ ለደካሞች ኀይል ይሰጣል..." የሚል መልስ ላከብት። በዚህም ፍጹም የክርስቲያንነትን መንገድ ተከታይ እንደሆኑ እንረዳለን" በማለት የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊ አቶ ተክለ ጻድቅ መኮሪያ በታሪክ መጽሐፋቸው ዐፄ ልብነ ድንግልን ያደንቋቸዋል።[3]

ዐፄ ልብነ ድንግል በ1533 ዓ.ም. ከሞቱ በኋላ ልጃቸው ገላውዴዎስ በኢትዮጵያ ነገሡ። በዚያው ዓመት 400/አራት መቶ/ የፖርቱጋል ወታደሮች ከህንድ ተነሥተው በቬርሙዴዝ እየተመሩ ምጥዋ ገቡ። የፖርቱጊዞቹም መምጣት በተሰማ ጊዜ በክርስቲያኖቹ ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ። ኀይላቸውም ተቀሰቀሰ።

የእስላሞቹ ኀይል ግን በዚህ ጊዜ ደከመ። ቀድሞ ዐፄ ልብነ ድንግልን እየከዱ በግዴታም በውዴታም ለግራኝ ገብተው የነበሩትም እየተመለሱ ለዕቴጌ ሰብለ ወንጌል መግባት ጀመሩ።

ከዚህም በኋላ በ1534 ዓ.ም. በመጋቢት ወር በተለይ አናሳ[4] በሚባለው ስፍራ ግራኝ አሕመድ በአንድ ወገን፣ ፖርቱጊዞችና የኦቴጌ ሠራዊት በሌላው ወገን ሆነው ጦርነት ገጠሙ። ፖርቱጊዞችም ይዘው የመጡትን መድፍ በእስላሞች ላይ በተኮሱ ጊዜ በእስላሞች ስፊር የመጀመሪያ ድንጋጤ ወረደ፣ በመጨረሻም ክርስቲያኖቹ በርሱ ላይ አነጣጥረው ሲተኩሱበትና በጥይት እግሩን ተመትቶ ሲቈስል፣ ፈረሱም በጥይት ተመትቶ ሁለቱም ወደቁ። ግራኝ እንዳይማረክ ጭፍሮቹ በቶሎ አንሥተው ወሰዱት። ግራኝም ለዘዚድ ሁልጣን[5] መሣሪያና ወታደር ላክልኝ ብሎ በድብቅ ላከበት።

ሁልጣን ዘዚድም ክርስቲያን የሆነው የፖርቱጋል መንግሥት ክርስቲያኑን የኢትዮጵያን መንግሥት መጠዳቱን ደኅና አድርጎ ያውቃልና ከየመን 2ሺ ቱርኮችና ዐረቦች ላከለት። እነርሱም ከመታዘዛቸው በላይ የፖርኩ ወርቅና ብር እንደአለፈው ሁሉ እናገኛለን በማለት መሣሪያ እየያዙ መጥተው ከግራኝ ጋር ተገናኙ። አራጌም ላይ ጦርነት ተደረገ። በጦርነቱም የፖርቱጊዞቹ መሪ ክርስቶፎሮስ ደጋግማ በጥይት ተመታና ቈስሎ ወደቀ። ቀኝለኛውን ዶም ክርስቶፎሮስን የሚወድዱት ጭፍሮቹ አነሡና አሸሹት። በኋላም ፖርቱጊዞቹ በአንድ ጫካ ውስጥ አስቀምጠው የዶም ክርስቶፎሮስ ደጋማን ቀስል ሲያስሩ እንዴት ሴት በአጠገባቸው ስለ ልፍ እስላሞች እርሱዋን አይተው ሲከታተሉ ወዲያው ክርስቶፎሮስን አግኝተው ስለማረኩት የሚያሳዝን ነገ[illegible] በክርስቲያኖቹ ደረሰባቸው።

ዐፄ ልብነ ድንግል ከግራኝ አሕመድ ጋር ጦርነት ከጀመሩ ከ፳ ዓመት ... ... ...

እስላሞቹ ቁስሉ የደከመውን ክርስቶፎሮስ ደጋማን ይዘው ሆሆ እያሉ ወስደው በግራኝ ፊት አቆሙት። ማናቸውንም ውርደት ፈጸመብት። እርሱ ግን በጫማ ጥፊ ሲደበድቡት፣ ሲተፉብትና ሲሰድቡት ሳይፈራና ሳይንቀጠቀጥ ዝም ብሎ በወታደርነትና በኩራት ዐይናቸ ይመለከታቸው ነበር። እንዲምሩትም ራሱን ዝቅ አድርጎ አልተለማመጣቸውም። ይልቁንም በጦርነት ቁስለው የነበሩትን የግራኝ አሕመድ ን አጐትና የወንድሙን ልጅ ሙስሳቸውን እንዲያነምና እንዲያስታምም ቢጠይቁት አላደርገውም ብሎ መለሰ ፡ ፖርቱጊዞችና ኢትዮጵያውያንም የመሸንበትን ቦታ አሳየን ቢሉት መልስ አልሰጠም። ግራኝም "እስላ ሁንና ልማርህ" ብሎት ነበር፤ ነገር ግን እንደ ክርስቶፎሮስ ያለ ቁራጥ ጀግና በፍርሃት ሃይማኖቱ ን መለወጥ አይሆንለትምና እንቢ አለ። እንዲያውም ግራኝ ጠጋ ብሎ ሃይማኖትህን በእስልምና ለውጣ ልማርህ ሲለው እንደታሠረ ምራቁን ተፋበት።

ከዚህ በኋላ በብዙ ዓይነት ዱላ እየደበደቡ፣ በፊቱም ላይ እየተፉ ከአሰቃዩት በኋላ በመጨረሻ ራሱ ግራኝ አሕመድ በመጥረቢያ ራሱን ቁረጠው። የተቁረጠውንም የዚህን የኾርማና ራስ ወደ ኮንስታንቲኖፕል (ሎስዋንዋንያ) ለቱርክ ሡልጣን ላኩለት። ለቱርክ ሡልጣን መላኩም ዋናው የርዳታው ደጋፊ በመሆኑ ግዳይ በመባል ደጋፊውን ለማስደሰት ነው፤ "ክርስቶፎሮስ ደጋማ ፈቃደኛ ሆኖ ከህንድ መምጣቱ፣ ከመጣ በኋላ ጦርነቱን በገዥግነት ለላከው መንግሥትና ለመጣበት የሃይማኖት ጉዳይ ሳያወላውል መዋጋቱ፣ ከዚህም በላይ ከምርኮ በኋላ በግራኝ ፊት በተፈጸመበት ልዩ ልዩ ሥቃይ ከማዛኑ በአለመራቁ፣ የወንድነቱ ጽናትና ጥብቅነት ለሰው ሁሉ ምሳሌነቱ የሚጠቅም ነው" በማለት ኢትዮጵያዊው ታሪክ ጸሐፊ አቶ ተክለ ጻድቅ መኮሪያ በታሪክ መጽሐፋቸው እጅግ ያደንቁታል።[6]

ግራኝ አህመድ ከሞተ በኋላ በዐፄ ልብነ ድንግል ጊዜ ከኢትዮጵያ ተልኮ ፖርቱጊዞችን ለርዳታ በአስመጣው በቤርሙዴዝና በዐፄ ገላውዴዎስ መካከል የፖለቲካና የሃይማኖት ጭቅጭቅ ተነሣ። ምክንያቱም ቬርሙዴዝ ከዐፄ ልብነ ድንግል ተልኮ ሮማ በደረሰ ጊዜ የሮማ ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ላይ በሃይማኖት በኩል ሥልጣን ያገኛል ሲል በራሱ አሳብ ወይም ከዐፄ ልብነ ድንግል ተልኮ ይሁን ይህንኑ ቃል ተናግሮ ነበር። እንደዚሁም ወደ ሊስቦን /የፖርቱጋል መናገሻ ከተማ/ በደረሰ ጊዜ የፖርቱጊዝ መንግሥት በአጋማሹ በኢትዮጵያ ላይ ገዢነት፣ በወደቦቹዋ በምጥዋና በኤርትራም ላይ ጥቅምን ያገኛል ብሎ ነበርና። አሁንም አባትዎ እንደሰጡት ተስፋ ከኢትዮጵያ ገሚሱ ለፖርቱጊዝ መንግሥት ይሰጣ የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን አቡን ከአስክንድርያ መምጣቱ ቀርቶ ከሮማ ይምጣ፤ እኔም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ አቡን ልሁን ብሎ ገና ግራኝ ሳይሞት ከዐፄ ገላውዴዎስ ጋር በተገናኘ ጊዜ አንሥቶሳቸው ምንም እንኳን በመጀመሪያ የእሺታ መልክ ቢያሳዩም በመጨረሻ ግን በፍጹም ይህ ሁሉቱ አሳብ አይቻልም ብለውት የነበረውን ግራኝ ከሞተ በኋላና ይልቁንም እንደተለመደ ግብጻዊ አቡን ለጳጳስነት ከአስክንድርያ በመጡ ጊዜ ክርክሩን እንደገና ቀሰቀሰ።

እርሳቸውም መጀመሪያ እንደሰጡት መልስ ወዳጅ ለወዳጁ እንደሚረዳዳ፣ እንደዚሁ ክርስቲያኑ የፖርቱጊዝ መንግሥት ለክርስቲያኒቱ ለኢትዮጵያ ርዳታ በአደረገበት ምክንያት የኢትዮጵያ መንግሥት ተዋሕዶ ሃይማኖቱን ወደ ካቶሊክነት ለማዛወር ከመንግሥቱም ግዛት ገሚሱን መሬት ቁርጦ ለመስጠት አይችልም" ብለው የመጨረሻውን መልስ ሰጡት።

ከሊቃውንቱም ወገን አባ ዝክሪና አባ ጳውሎስ፣ ንግሥት ሰብለ ወንጌልም ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ወደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ለመደባለት እንደማይቻል አጥብቀው ተከራከሩት።

እርሱም በዚህ ነገር ተቈጥቶ ስድብ እየጨመረ በጎይል ሲናገር የዕልፍኝ አሽከሮችና ፖርቱጊዞች ከንጉሡ ፊት ገትተው ወደ ውጭ አወጡት።

ንጉሡም ጓደኞቻቸው ሲሔዱ እርሳቸውንና ኢትዮጵያን መርጠው ለቀሩት ፖርቱጊዞች ከዚህ እንደሚከተለው ቸርነት አደረጉላቸው።

1. ከግራኝ አሕመድ የተማረከውን ወርቅና ሀብት ለቀሩትና ለተመለሱትም ዐደሉዋቸው፣
2. በግብርም ጊዜ በበዓልም ቀን በክፍታ ቦታ እንዲቀመጡ አደረጉ፣
3. ሰፋፊም መሬት ለየአንዳንዳቸው ሰጥተው በአለጉልት አደረጉዋቸው።

6 የኢታ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ም.12 ገጽ62





ከሔዱት በቀር የቀሩት ሁሉ በዚህ በተደረገላቸው ደግ ሥራ ደስ ተሰኝተው ከወይዘሮዎቻቸም እየመረጡ ሚስት አግብተው በደስታ ተቀመጡ። ይልቁንም አለቃቸው አርያስ ዲያዝ ከሞቱ በፊት ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ገብቶ ስሙ ማርቆስ ተብሎ እስከመጨረሻ ለንጉሡ አገልጋይና ወዳጅ ሆኖ ነበር። በመጨረሻውም ከንጉሡ ጦር ጋር ሆኖ ከሸፈቱ እስላሞች ጋር ሲዋጋ ሞተ። በርሱም ፋንታ አላይ ስሙ የተጠቀሰው ኦሪዮስ ሱዛ ተሾሞ እርሱም እንደሹመት አባቱ የንጉሡ ባለሟል ነበር።

ቤርሙዲዝ ቀድሞ ከሚቸ ከዐፄ ልብነ ድንግል እንደተሰጠው ተስፋ "እኔም ጳጳስ ልሁን፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ካቶሊካዊት ትሁን" ብሎ ንጉሡንም ዘለፋና ስድብ እየጨመረ በድፍረት እየተናገረ በአደረገው ክርክር ከዚያ ወዲህ ከተነሡ ታሪክ ጸሐፊዎች ውስጥ እነ ሱዳልፍ፣ እነ ብሩስ፣ እነባሴት የማይገባ ሥራ መሥራቱን እየገለጹ ነቅፈውታል፤ ዐፄ ገላውዴዎስንም የአገራቸውን ሙሉ ነፃነትና የቤተ ክርስቲያናቸውን ሃይማኖት ለመጠበቅ በሚገባ ተከራክረዋል" እያሉ ጽፈዋል።

ዣን ባቲስት ኩልቦ የሚባሉት የካቶሊክ ሚሲዮናዊ ግን "የአባታቸውን ቃል ኪዳን በመጠበቅ ፋንታ የአፈረሱት ዐፄ ገላውዴዎስ ይነቀፋሉ እንጂ ቤርሙዴዝ አይነቀፍም" ሲሉ ጽፈዋል።[7]

ዐፄ ገላውዴዎስ የግራኝን ጦር ድል አድርገው መንግሥታቸውን ከአደላደሉ በኋላ ሰው ሁሉ ወደ ሰላማዊ ሥራው እንዲመለስ አደረጉ፣ ወታደር የሆነው ወገን ግን የተረፈውን የግራኝን ጦር እንዲከታተል ትእዛዝ ሰጡ።

በግራኝም ጊዜ የፈረሱትና የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተመልሰው እንዲሠሩ ትእዛዝ ተሰጥቶ ነበር። በአማራ ሳይንትም የተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን በአማረ ጌጥ ራሳቸው አሠሩ።

## የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት፣

ቤርሙዲዝ ከዐፄ ገላውዴዎስ ተጣልቶ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ስለ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት የተደከመው ድካም በከንቱ እንዳይቀር በቤርሙዴዝ ፋንታ ጠባያቸውና ትምህርታቸው ከእርሱ የተሻሉ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የካቶሊክን ሃይማኖት እንዲያስፋፉ በማለት የፖርቱጋል ንጉሥና የሮማ ሊቀ ጳጳስ ርስበርሳቸው መመካከር ጀመሩ። ለአገባብም እንዲመች ሲሉ የሮማ ሊቀ ጳጳስ 3ኛ ጳውሎስ ወደ ኢትዮጵያ ሚሲዮናውያንን ከመላካቸው በፊት ሮማ ቅ/አስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ለኢትዮጵያ ቋንቋና የቤተ ክህነት ጉዳይ የአገሩ ባህልና ልማድ የሚጠናበት ትምህርት ቤት እንዲከፈት አድርገው ነበር፤ በዚህም ት/ቤት ብዙ የቤተ ክህነት ሰዎች እየተመረጡ ገብተው ያጠኑ ነበር።

ከእነሱም ውስጥ ዣን ኤኔዝ ባፊቶ አንድሬ፣ አቪዮዶ፣ ሚልኪዎሪ፣ ካርኔሮ የሚባሉ ከዐሥር ሌሎች ሚሲዮናውያን ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ወንጌልን እንዲሰብኩና እንደ ሊቀጳጳሱም አሳብ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አለቆች እንዲሆኑ በ3ኛ ጳውሎስ ተከታይ በዩልዮስ 3ኛ የሊቀ ጵጵስና ዘመን ተመረጡ።

ከእነዚሁም በመጀመሪያ ስሙ የተጠራውን ዣንኤኔዝን የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብለው በራሳቸው አሳብ ሾሙት፤ እንደዚሁ ቀጥለው ያሉት የመገፍመሪያው ፓትርያርክ ቢሞት እንደ እየማዕርጋቸው በሹመት እንዲከተሉት አድርገው የኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ ሰጥተው አስናበቱዋቸው፤ የእነሱም ክፍላቸው አየሱሳውያን /ጂሱዩት/ ከተባሉት ወገን ነው።

ሚሲዮናውያኑ ከሮማ ተነሥተው በ1548 ዓ.ም. በመጋቢት ወር ሕንድ ደረሱ፤ የሕንድም አገረ ገዥ ደብዳቤ ለዐፄ ገላውዴዎስ አስቀድሞ፣ ቀጥሎ ሚሲዮናውያኑን ከብዙ ገጸ በረከት ጋር ላካቸውና መጥተው ከንጉሡ ጋር ተገናኙ።

ንጉሡ ዐፄ ገላውዴዎስም የፖርቱጋል መንግሥት በቅርብ ጊዜ በአደረገው የወታደር ርዳታ ውለታ ምክንያት የመጡትን ኢየሱሳውያን በመልካም አቀባበል ተቀበሉዋቸው። ሲመጡም የመገፍመሪያው ፓትርያርክ ቀርቶ እንድርያስ አቢዶዶ ፓትርያርክ ሆኖ ነበር።

7 ፡ ስለቤና የሃይማኖት ታሪክ ከሞሰው መጽሐፋቸው 2ኛውን ቮሊም ከ128 እስከ 129 ገጽ ያለውን ተመልከት



www.ethiopianorthodox.org

ጥቂት ቀንም ውስው እንደ አደሩ በእንግዶቹና ከግብፅ በመጡት በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ዮሴፍ፣ እንደዚሁም በኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት መካከል የሃይማኖት ክርክር ተነሣ፡፡ እነዚያ የካቶሊክን ሃይማኖትና የሮማን ሊቀ ጳጳስ ሥልጣን በኢትዮጵያ ለማስገባት፣ እነዚህም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስን ሥልጣን በመከላከል ብዙ መጽሐፍ እየጠቀሱ ብዙ ቀን ሲከራከሩ ቆዩ፡፡

ንጉሡም የሁለቱ ወገኖች ጉዳይ በጉባኤ እንዲታይ አድርገው በጉባኤውም ራሳቸው ተቀምጠው ብብ ሳይቀሰቀስ ነገሩ በሰላም እንዲያልቅ ይጥሩ ነበር፡፡

በመጨረሻም በታላቁ ቁስጠንጢኖስ ጊዜ በኒቅያ ጉባኤ 318 ሊቃውንት ከወሰኑት ቀኖናና እምነት ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ግራም ቀኝም አንልም በማለት "ጸሎተ ሃይማኖትን..." አንብበው ከዚህ ከአባቶቻችን ሃይማኖት በፍጹም አንወጣም ብለው የመጨረሻውን ቍርጥ አሳብ ንጉሡም ሊቃውንቱም ለሚሰድናውያኑ ነገሩዋቸው፡፡ እነሱም "እያደር በስብከት እንገባለን" በማለት ለጊዜው የሃይማኖቱን ክርክር አቆሙና ስብከታቸውን ብቻ እንዲቀጥሉ አስፈቅደው ጉባኤው ተበተነ፡፡

ይሁን እንጂ ንጉሡ ምንም ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ባይለውጡም ለሚሰድኖቹ በዚያ ጊዜ በአደረጉት መልካም አስተያየትና አቀራረብ ከሊቀ ጳጳሱና ከቀሳውስቱ ወገን ሃይማኖታቸውን ወደ ካቶሊክነት ለውጠዋል እየተባሉ ከመታማት አልዳኑም፡፡ ታሪክ ነገሥቱም "ንጉሡ የፈረንጆቹን ሃይማኖት ወድዶ ነበር፤ ነገር ግን እንደ ግራኝ ጊዜ ያለ ሁከት እንዳይነሣበት ስለ ፈራ በእስክንድርያ ሃይማኖት ቆመ" ሲል ያወሳል፡፡[8]

ዐፄ ገላውዴዎስ ምንም እንኳን በመሠረቱ የፖርቱጋሎች ርዳታ ቢጨመርበትም የግራኝን ጦር አሸንፈው የተወረረውን አገር መልሰው አቋቋሙ፡፡ በግራኝ አሕመድ ጊዜ ከተቃጠሉት ውስጥ የተ ድባበ ማርያምንና የመካነ ሰማዕት፣ የደብረ ወርቅን አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸው አሠሩ፡፡

እንደዚሁም በሸዋ፣ በአማራ ሳይንት፣ በጐጃም፣ በበጌምድር፣ በትግራይ የተቃጠሉትን የደብረ ብርሃን ሥላሴን /ሸ/፣

- የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን
- የምስካለ ማርያምን፣
- የገነተ ጊዮርጊስን
- የደብረ ሕንፀታን
- የደብረ ድማህን /ጐጃም/፣
- የመካነ ሥላሴን፣
- የወልደ ነጐድጓድ
- የደብረ ኪሩቤልን፣
- የአትሮንስ ማርያምን /ወሎ/
- የኢንድርስ ማርያምን
- የታዕካ መንግሥትን፣
- የደብረ ጽርሐ ማርያምን፣
- የገነተ ማርያምን፣
- የአባ ጊዮርጊስ ዚጋስጫን /ወሎ/
- የደብረ ቤቱልን፣
- የእግዚአብሔር አብን፣
- የደብረ እስጢፋኖስን፣
- የመርጡለ ማርያምን /ጐጃም/
- የደብረ ዘይትን፣
- የናዝሬትን፣

8 ታሪክ ነገሥት ረኔ ባሴት ያሳተመው ገጽ 334





- የአምበር ቂርቆስን፣
- የገሊላን፣
- የአጥለሰን፣
- የደብረ መሊሕን፣
- የ?ለተ ማርያምን
- የጎሐ ጽዮንን /ሸዋ/
- የዋሻ ሚካኤልን /ሸዋ/

- የደብረ ክርቤን /ግሸን ወሎ/ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት እንዲሠሩ በየአለበት ትእዛዝ አስተላለፉ፡፡ ነገር ግን ከእነዚሁ ውስጥ ጥቂቶቹ ከእርሳቸው ዘመን ሲሠሩ የቀሩት በጐንደር ነገሥታት ዘመን በየጊዜው ተሠርተዋል፡፡

## የዐፄ ገላውዴስ በሰማዕትነት መሞት

የዐፄ ልብነ ድንግል ልጅ ንጉሥ ገላውዴዎስ በዘመኑ ግራኝ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠለ፣ ከንጉሡ ከዐፄ ልብነ ድንግል ጋር ተጣላ፣ ተዋጋ፣ ንጉሡም የሚዋጉለት ሠራዊት እስከሚሰበሰብ ድረስ ግራኝን መቋቋም ስለአልቻለ ወደ ሰሜን እያፈገፈገ ሔደ፣ ንጉሡም በመዋጋት ላይ ሳለ ድንገት ታሞ ሞተ፣ ይህም ወንጀለኛና ከሐዲ የኢትዮጵያን አውራጃዎች 15 ዓመት አጠፋ፣ ከኢትዮጵያም ሕዝብ ብዙዎቹን ማረከ፣ ከቦናት ሃይማኖትም አውጥቶ የአሱ ተከታዮች አደረጋቸው፡፡ በትምክህትም አነጋገር ከአሁኑ ጀምሮ አውራጃዎችን ሁሉ በቍጥጥሬ ሥር ስለአዋልሁ የሚቃወመኝ የለም አለ፡፡ የንጉሡ ልጅ ገላውዴዎስስም ከተከላካዩ የጦር አለቆቹ ጋር ተዋግቶ ግራኝን ድል አደረገው፣ ግራኝም ከብዙ ፈረሰኞችና ከቱርክ ወታደሮች ጋር ወደአርሲ ቀርቦ ንጉሡን ጦርነት ገጠመው፡፡ ንጉሡንም እግዚአብሔር ስለረዳው ግራኝን ገደለው፡፡ ግራኝን በመፍራት የተሰደዱት ሁሉ ተመለሱ፣ የተቃጠሉና የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትም እንደ ገና ታነፁ፣ ታነፁ፡፡

ከዚህ በኋላ ከእስላሞቹ አንዱ ከብዙ ጦረኞች ሠራዊት ጋር መጥቶ በመድኃኒታችን በዓለ ስቅለት ንጉሡ ከጥቂት ሰዎች ጋር ላለ ድንገት አገኘው፡፡ ቤተሰዎቹ፣ የጦር መኮንኖቹ እስከሚሰበሰቡ ድረስ ምሽግ እንገባለና ተደብቀን እንቀመጥ አሉት፡፡ ንጉሡ ግን የክርስቲያኖችን መማረክና የአብያተ ክርስቲያናትን ጥፋት አላይም ብሎ እንዚ አላቸውና በጦርነቱ መካከል ገባ፡፡ በውጊያውም ጠንክሮ ነበር፡፡ በኋላ ግን እስላሞቹ ከብበው በስደፍ መቱት፡፡ በብዙ ቦታም በጦር ወጉት፡፡ ከፈረሱም ላይ አስጥለው እንጉቱን ቁረጡትና በሰማዕትነት ሞተ፡፡ /ስንክሳር መጋቢት 27 ቀን/

# ክፍል 4

## ሰማዕታተ ኢትዮጵያ በዘመነ ሱስንዮስ

በዐፄ ገላውዴዎስ ጊዜ መጥተው የነበሩት የውጭ አገር ሚሲዮናውያን ትምህርት ቤት ከፍተን ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች ከፖርቱጊዞች ልጆች ጋር ደባልቀን እየአስተማርን ለቤተ መንግሥቱ አገልጋዮች የሚሆኑ ልጆ እናዘጋጅ ብለው አስቀድሞ ለዐፄ ያዕቆብ ኋላም ለዐፄ ዘድንግል አቀረቡላቸው፡፡

ዐፄ ዘድንግልም የት/ቤቱ ጉዳይ እስኪመከርበት ድረስ ይቁይ አሉና ከእነዚሁ ውስጥ መልእክተኛ ወደ ሮማ ጳጳስ ወደ ክሌማንት /ቀሌምንጦስ/ 7ኛና ወደ ኤስፓኙ ንጉሥ ወደ ፊልጶስ 3ኛ የወዳጅነት ደብዳቤ ጨምረ ው ላኩ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ዓላማቸውም የእጅ ሥራ የሚያስተምሩ ኤስፓኞችና ፖርቱጊዞች ወደ ኢትዮጵያ ለማስመጣት ነበር ሚሲዮኖቹም ይህንኑ ተስፋቸውን በንግግር ስለአጸኑላቸው ሚሲዮኖቹን ወዳጅ አድርገዋቸው ነበር በመጨረሻም ካቶሊኮችንና ኮፕቶችን እያከራከሩ አሳባቸውን ከካቶሊኮቹ ጋር አደረጉ ይባላል፡፡ በዚህም ጊዜ ንጉሡ ከጦር መሪው ከደጃዝማች ላዕከ ማርያም ጋር ተስማምተው ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ለውጠው ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ዞረዋል እየተባለ በቀሳውስቱም በሕዝቡም ዘንድ ተወራ፡፡ በዚህ ምክንያት በዚያ ዘመን የነበሩት ከአስክንድርያ የመጡት ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ "ለንጉሡ ለዘድንግል የሚታዘዘውን ገዝቻለሁ" ብለው መኳንንቱንም ሕዝቡንም አወገዙ፡፡ በዚህ ጊዜ የእናርያ ተወላጅ የሆነው ደጅ አዝማች ዘሥላሴ ራስ ዘሥላሴ ተብሎ የጐጃምን ሕዝብ ይዞ በንጉሡ ላይ ተነሣ/ ንጉሡም ወታደሮቻቸውን አስከትለው ሔደው ደምቢያ ውስጥ ባርጫ በሚባለው ስፍራ ከደጅ አዝማች ዘሥላሴ ጋራ ለጦርነት ተሰለፉ፡፡ በዚህም ጦርነት የቤተ ክህነትና የሃይማኖት ጽናት ያለው ክርስቲያን ሁሉ ከራስ ዘሥላሴ ጋር ሆነ፡፡

በዚያ ዘመን የነበሩ 700 የሚሆኑ ነፍጥ የያዙ ፖርቱጊዞችና ሚሲዮኖች ግን ከንጉሡ አሽከሮች ጋር ሆነው በዐፄ ዘድንግል ጐን ተሰልፈው በፊትም እንሞታለን እያሉ ያደፋፍሩዋቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የዐፄ ዘድንግል ሠራዊት በጦርነቱ ስለተሸነፈ ዐፄ ዘድንግል ከዋናው አዝማች ከራስ ዘሥላሴ በተተኮሰ ጥይት ተገደሉ፡፡ ከዘድንግል በኋላ ዐፄ ያዕቆብ ሁለተኛ ነግሠው ስለነበር ከሱስንዮስ ጋር ጦርነት ገጠሙና ሱስንዮስ ዐፄ ያዕቆብን በጦርነቱ ገደላቸው፡፡ ጳጳሱ አቡነ ጴጥሮስም ወታደሩን እያበረታቱ የሱስንዮስን ጦር እንዲመልስ ያስተምሩ ነበርና ከሱስንዮስ ወታደሮች አንዱ በጥይት ገደላቸው፡፡ ገላውዴዎስ የሚባለውን የዐፄ ያዕቆብን ልጅ ሱስንዮስ አሳንቆ ገደለው፡፡

ዐፄ ሱስንዮስ ከመንገሣቸው በፊት ጳጳስ ስለአስገደሉ የቤተ ክህነት ሰዎችና እውነተኞቹ ክርስቲያኖች ቂም ይዘውባቸው ስለነበር በነገሡ ጊዜ አልተደሰቱም፡፡ ዐፄ ሱስንዮስም በቤተ ክህነቱና በምእመኑ እንደተጠሉ ያውቁ ነበር፡፡ ሕዝቡም በቤተ ክህነቱ ስብከት እንደሚነሳባቸው ተጠራጠሩ፡፡ በሰሜንም ቱርኮች ኢትዮጵያን ለመውረር ተዘጋጅተው ስለነበር አነሱን ወገቸ ለመመለስ ቤተ ክህነቱ ሕዝቡ ካላበረከቱ ወይም ከውጭ መንግሥት የበቃ ርዳታ ከአላገኙ የማይቻል መሆኑን አመዘዘኑ፡፡ ከቤተ ክህነቱና ከክርስቲያኑ ሕዝብ ጋር ያላቸው ቅያሜ እየባሰ በሔደ ጊዜ በአጠገባቸው ያሉትን ሚሲዮኖችና የውጭ አገር ሰዎች ባለሙዋል አደረጉዋቸው ፤ ለካቶሊክ ሚሲዮኖቹም የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን የሚተክሉበትና የሚተዳደሩበት ሰፊ መሬት ከደንቢያ ሰጡቸዋው፡፡ ፖኤዝ የሚባለውን የካቶሊኮችን አለቃ ከፍሬሞና ወደ ደንቀዝ አስመጥተው በአጠገባቸው አስቀመጡት፤ ደንበኛ ሥርዐተ ንግግቸውን ለማክበር አኩስም ጽዮን ቤተ መቅደስ ውስጥ የዝምድናና የወታደር ጥየቃ ሲኖርበት እንደዚሁም "በሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አንተዳደራለን" የሚል ጽሕፈት ነበረበት፡፡

የአስፓኝ ነገሥታት በካቶሊክ ሃይማኖት ፍቅር የተቃጠሉ የሮማን ቤተ ክርስቲያንና ሊቃነ ጳጳሳቱን በጣም የሚያከብሩ ነበሩ፡፡ የሮማ ጳጳሳትም ከአነልዮንና ከአነ ጉርጎርዮስ ትልቁ ገርምሮ በአውሮፓ የካቶሊክ ነገሥታት ላይ አንድ አንድ ጊዜ እስከመሾም እስከ መሻር እየደረሱ ክብርና ሥልጣን ስለነበራቸው በማናቸውም ረገድ የአስፓኝ ነገሥታት በራሳቸውም ሥራ በሊቃነ ጳጳሳቱም ድጋፍ ገናናነታቸውን እንደያዙ ነበር፡፡ ዐፄ ሱስንዮስም ደብዳቤ የላኩት በፒር ፖኤዝ ጠቋሚነት ይህን ከተረዱ በኋላ ነው፡፡

## በካቶሊክ ሃይማኖት ምክንያት በክርስቲያኖች ላይ የደረሰው እልቂት

ወደ ሮማ ጳጳስና ወደ አስፓኝ ንጉሥ ተልኮ የነበረው ፖኤዝ ሌሎችንም ሰዎች ጨምሮ መልስ ይዞ ከአውሮፓ መጣ፡፡ እነሱም ከንጉሣቸውና ከጳጳሳቸው እንደ አውሮፓ ቍጥር በ1609 ዓ.ም. መጋቢት 15 ቀን የተጻፈውን ደብዳቤ አስረከቡ፤ በደብዳቤውም የሰፈረው ቃል "ከዚህ ቀደም የፖርቱጊዝ መንግሥት ከዐፄ ልብነ ድንግል ቃል ተቀብሎ ርዳታ ከላከላቸው በኋላ ልጃቸው ገላውዴዎስ የአባታቸውን ቃል ተቀብለው ስለአልፈጸሙ አሁንም ርስዎ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የካቶሊክን ሃይማኖት ተቀብላ የቤተ መንግሥቱም የቤተ ክህነቱም ሃይማኖት ካቶሊክ መሆኑ በግልጽ ከአልታወቀ በደብዳቤ የጠየቁትን ጉዳይ ለመፈጸም ያዳግታል፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሮማ ቤተ ክርስቲያን ከተደረበ ግን ማናቸውንም ርዳታ እናደርጋለን" የሚል ነበር፡፡



ንጉሡም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ጽፈው ፍቁረ እግዚእንና ከሚሲዮኖቹ አንዱን አንቲን ፈርደንዲዝን መልሰው ላኩዋቸው፡፡ እነዚህ መልእክተኞች መልሱን ከምምባታቸው በፊት ኢየሱሳውያን የሚባሉት እነዚሁ ሚሲዮኖች የንጉሡን ልብ ስለአገኙ በፍሬሞና /ትግሬ/ በጐርጐራ /ደምቢያ/ በሌላውም ከተማ ሁሉ እንደልባቸው የካቶሊክን ሃይማኖት በየጉባኤው በየገበያው በየመኳንንቱም ቤት እየሰበኩ በካቶሊክነት ያጠምቁ ገርመር፡፡ በዚህ ጊዜ ለኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖት የተቈረቈሩት ሕዝቡንና ካህናቱን እየቀሰቀሱ ንጉሡ ካቶሊክ ሆነዋል እያሉ በማውራት ለመሸፈት አቈበቈቡ፡፡

የሚሲዮኖቹ መሪ ፔርፖኤዝ በኋላ ደግሞ ከሮማ ሊቀ ጳጳስ ዘንድ ፓትርያርክ ተብሎ ከ18 ሚሲዮናውያን ጋር የመጣው ሜንዴንዝ አልፎንሶ የአዲሱ ሃይማኖት መሪ ሆነው የቀረባቸውን በካቶሊክነት ሲያጠምቁ፤ አዲስ ሕግና ሥርዐት ሲያበጁ፤ የነበረውንና ያለውን ተዋሕዶ ሃይማኖት ለመከላከል በየሥፍራው የተነሡት ደግሞ ብዙ ነበሩ፡፡ እነዚህም ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ስምዖን፤ የታወቁት መምህር አባ ዳዮስቆሮስ ከመሳፍንት የዐፄ ሱስንዮስ ወንድም ራስ የማነ ክርስቶስ፤ የልጃቸው የወይዘሮ መለኮታዊት ባል ራስዮልዮስ ዮናኤል የዳሞት ገዥ ጌጦዎን የፈላሾች ባላባት አቤቶ የማነ አብ፤ አቤቶ መልክ ክርስቶስ፤ አቤቶ ዘመንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡ ሌሎችም ብዙ ካህናትና ዲያቆናት ስለ ሃይማኖታችን እንሞታለን እያሉ በአንድነት ተነሣሥተው በዐፄ ሱስንዮስ ላይ ዐመፁ፡፡ ንጉሡም ሠራዊታቸውን ይዘው እነዚህኑ ለመውጋት ከደንቀዝ ወደ ደዳ ሄደው ተሰለፉ፡፡

በዚህም ጊዜ ጳጳሱ አቡነ ስምዖን ንጉሡ ሱስንዮስ የአስክንድርያንና የአባቶቻችንን የአነ ቅዱስ ማርቆስን ተዋሕዶ ሃይማኖት ለውጠው ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ገብተዋልና አሳቸውን ተከትሎ የሚወጋን "ውጉዝ ከመ አርዮስ" ብለው ገዙቱ፡፡ ይሁን እንጂ ግዝቱ ጦርነቱን ለማቆም አልቻለምና ከንጉሡ ወታደሮች ጋር ብዙ ሚሲዮኖችና የውጭ አገር ሰዎች ተጨምረው ከአንድ ፊትም ጳጳሱና ቀሳውስቱ ሆነው አርስበርሳቸው ተዋግተው ወታደሩን ያዋጉ ገርመር፡፡

በኦርቶዶክሳውያኑ ጦርነት ውስጥ አዝማች የነበሩት ዋናው ዮልዮስና አባ ዳዮስቆሮስ ከብዙ ወታደርና ካህናት ጋር በጥይትና በጦር ተመትተው ወደቁ፡፡ ጳጳሱም አቡነ ስምዖን እንደ ሹመት አባታቸው ከንደ አቡነ ጴጥሮስ መስቀላቸውን በእጃቸው ጨብጠው "እይሂቸሁ ለሃይማኖታችሁ ብትሞቱ ለማዕትነት ተቀበላላችሁ" እያሉና እያደፋፈሩ በጦርነቱ መካከል ገብተው ሲያዋጉ አንድ ወታደር በጦር ወግቶ ገደላቸው፡፡ ራስ የማነ ክርስቶስና ከርሱ ጋር በሱስንዮስ ወታደሮች የተማረኩት በዚያው አውራጃ እንዲታሠሩ ተደረጉ፡፡ ቅ/ወሰተ ጴጥሮስ ባለቤቷ የሱስንዮስ ደጋፊ ስለነበር እንደ ባለቤቱ ሃይማኖቱን ክሕለውጥም ብላ በሱስንዮስ ታሥራ ተሰቃይታለች፡፡ አቡነ ኖላዊነ ኄር የተባሉት ጳጵስ አንደ ወሰተ ጴጥሮስ ታሥረው፤ ፍቅርተ ክርስቶስም ታሥራ ሁሉም ድብደባና መከራ ተቀብለዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ሱስንዮስ ቤተሰቦቻቸውን አስከትለው በሚሲዮናዊው በፔር ፖኤዝ እጅ ተጠምቀው ካቶሊክነታቸውን በገሀድ አስታወቁ፡፡ በዚህም ቀን አርአያነታቸውን እየተከተሉ ብዙ ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው ወንድማቸው ራስ ሣህለ ክርስቶስም በካቶሊክነት ተጠመቁ፡፡

"ከአስክንድርያ ተዋሕዶ ሃይማኖት የተጠመቃችሁ ሁሉ በሮም ሃይማኖት ተጠመቁ፤ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያኑና በዓል አከባበሩም እንደ ሮማ ቤተ ክርስቲያን ይሁን" የሚል ትእዛዝም አወጡ፡፡

በዚህም ጊዜ በትግራይ፤ በላስታ፤ በበጌምድር፤ በጐጃም፤ በሸዋ ያሉ ሊቃውንት ደንቀዝ እየሔዱ "ሰማዕትነት አያምልጥህ" እየተባባሉ ፓትርያርክ ተብሎ ከሮማ ጳጳስ በተላከው በሜንዴዝ አልፎንሶ ትእዛዝ ተገፋፍተው ሞቱ፡፡ በዚሁ አያያዝ አባ አፈ ክርስቶስ የሚባሉ ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት በጥብቅ ይከራከሩ የነበሩት መላላቸው በንጉሡ ትእዛዝ ተቈረጠ፡፡

ዐፄ ሱስንዮስ ከሺህ ሦስት መቶ ዓመት ይበልጥ ዥምሮ በኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ ዘንድ ጸንቶ የኖረውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለውጦ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት የዞረበትና ሕዝቡም እንዲከተለው በጦርነት ለማስገደድ የሞከረበት ምክንያት በሰሜን ፈላሾች በዳሞትና በጐጃም ኦሮሞዎች፤ በሰሜን ቱርኮች፤ በሌላውም ሥፍራ የሚነሣባቸውን የውስጥና የውጭ ጠላታቸውን የሚያጠቁበት የወታደርና መሣሪያ ርዳታ ከአስፓኝ መንግሥት ማግኘት ስለአስፈለጋቸውና ከርዳታው በፊት የኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን ወደ ካቶሊክ መለወጡዋን በግልጽ አስቀድመን ካላወቅን ለመላክ አይቻልም ስለአሉዋቸው ነው፡፡

ነገር ግን ዐፄ ሱስንዮስ የጠየቁት ርዳታ አስቀድሞ በእጃቸው ሳይገባ በገሀድ በካቶሊክነት የራሳቸውን የቤተ ሰባቸው መለወጥ አልበቃ ብሎ ሕዝቡንና ካህናቱን በግድ ካቶሊክ እንዲሆኑ ቀድሞ በተዋሕዶ ሃይማኖት የተጠመቁት በቂ አይደለምና እንደገና በካቶሊኮቹ ቄሶች እጅ እንዲመጠቁ፣ ዐርብና ረቡዕም መጾሙ ቀርቶ ቀዳሚት እንዲጾም፣ የቀዳሚት ስንበትነትም እንዲሻር፣ የቅዳሴውና የሚሕሌቱም ሥርዐት ተለውጦ በ1 ጊዜ እንደ ካቶሊክ ሥርዐት እንዲሆን፣ ትእዛዛቸውን በዐዋጅ አወጡ፡፡ ዐዋጁንም የፊራ ሲፈጽም ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቀናተኛ የሆነው የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ወገንም እንቢ ብሎ ሲዋጋ ሲማረክ፣ ሲቀጣ፣ ሲታሠር፣ ሲገደል ሁለት ዓመት ቈየ፡፡

ስለዚህም አቶ ተክለ ጻድቅ መኮሪያ በጻፉት የኢትዮጵያ ታሪክ "ዐፄ ሱስንዮስ ካቶሊክ መሆናቸውን በግልጽ በአስታወቁበት ቀን ይቅርና በዚህ ሃይማኖት እንኳን ቢጠረጠሩ ሕዝቡ እንደሚሸፍት የታወቀ ነው" ብለዋል፡፡ (የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ገጽ 136 ምዕራፍ 28)
በአገው፣ በጉጃም፣ በትግራይ፣ በሸዋ በየመሪዎቻቸው ተነሡና ከሸ.ህ 611 ዓ.ም. ዝምሮ እስከ ሸ.ህ 618 ዓ.ም. ድረስ በየሀገሩ ዘረፋና ዕልቂት ሆነ፡፡ ንጉሡም ወታደሮቻቸውን ይዘው ሽቅብና ቁልቁል እየርገጡ ሲዋጉ ሲያዋጉ ትርፉ ከወዲያም ከወዲህም ያው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕልቂት ሆነ፡፡ የሃይማኖቱ ጦርነት ሊቆምና አገሩ ሰላም ሊሆን አልቻለም፡፡

## ፋሲል ይንገሥ፣ ሃይማኖት ይመለስ

በዚህ የሃይማኖት ጦርነት ምክንያት አገሩ ታውኮ ሳለ፣ በ1618 ዓ.ም. ልጃቸው ማርቆስና ሴት ልጃቸው ወ/ሮ መለኮታዊት በ1 ዓመት ሁለቱም ተከታትለው ስለሞቱ ካቶሊክ ከመሆናቸው የተገማ እግዚአብሔር መዓት እንደአወረደባቸው በሕዝቡ ተነገረ፡፡

ፋሲል /ፋሲለደስ/ የተባሉት ልጃቸው በዚህ የሃይማኖት ጦርነት ጊዜ በጣም ተቸግረው ነበር፡፡ ምንም እንኳ ከአባታቸው ጋር እየሆኑ ስለ ሃይማኖታቸው የሸፈቱትን ሰዎች ቢወጉም ከጦርነቱ ተመልሰው ወደቤታቸው ሲገቡ ግን የሞቱትን ሰዎች ሬሳና ቍስለኛ በማስመልከት "የአባቶቻችንን ሃይማኖት በመለወጣዎ ምክንያት ለምን የብዛ ሕዝብዎን እርስ በርሱ ያስተላልቁታል" እያሉ ከአባታቸው ጋር ይጨቃጨቁ ነበር፡፡ "አሁንም ተመልሻለሁ ይበሉ፣ ሕዝቡም ወደ ጥንቱ ሃይማኖቱ እንዲመለስ ዐዋጅ ይንገሩት" እያሉ ያዙበሉዋቸው ነበር" ብለው አቶ ተክለ ጻድቅ ጽፈዋል፡፡ (የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ም.29፣ ገጽ 138) በመጨረሻም ዐፄ ሱስንዮስ በነገሡ በ27ኛው ዓመት ታመው እንደበታቸው ተዚጋ፡፡

በዚህ ጊዜ ታሪክ ነገሥታቸው እንደሚለው ልጃቸው ፋሲል "እግዚአብሔር ይህን መዓት ያመጣባቸው ሃይማኖታቸውን በመለወጣቸውና የክርስቲያንን ደም በማፍሰሳቸው ይሆናል ሲሉ በየገዳማቱና በየአድባራቱ "በጸሎታችሁና በንስሐችሁ አባቴን አድኑልኝ፡ እኔም ያላችሁኝን አደርጋለሁ" እያሉ ብዙ መባ ላኩ፡፡ አባ ዐምደ ሥላሴ የሚባሉ ከሸዋ ሐይው መተማ አጠገብ በበረገው የማኅበረ ሥላሴ ገዳም አዲስ ቁርጥረው በዚያው የሚኖሩ የበቁ መነኮሴ ነበሩ፣ እርሳቸውም "አባትህን እኔ በእግዚአብሔር ፈቃድ እፈውሰዋለሁ" ብለው ወደ አቤቶ ፋሲል ላኩ፡፡ አቤቶ ፋሲልም "እሺ ያሉኝን አደርጋለሁና መኖተው አባቴን ይፈውሱልኝ" ብለው መልሱን ላኩባቸው፡፡

ከዚህ በኋላ አባ ዐምደ ሥላሴ ከገዳማቸው መነኮሳትን አስከትለው ወደ ደንቀዝ ሐዱ፡፡ በደረሱም ጊዜ አቤቶ ፋሲል በክብር ተቀብለው በመልእክት የተነጋገሩትን በቃል አጽድቀው መነኮሴው ሌሎች መነኮሳትን ጨምረው ቀን በልዩ ልዩ ጸሎት፣ ሌሊት በሰዓታት 3 ሰዋዊ እግዚአብሔርን ሰምነው አጥምቀው ስለአቈረቡዋቸው ዐፄ ሱስንዮስ የተዚጋ እንደበታቸው ተከፈተና "የእስክንድርያ ሃይማኖት ትመለስ፣ የሮም ሃይማኖት ትርከስ፣ ፋሲል ይንገሥ" ብለህ ዐዋጅ አናግር ብለው ለልጃቸው ለአቤቶ ፋሲል ተናገሩ፡፡

ዐፄ ሱስንዮስም ፈውስ ሊያገኙ የቻሉት በመነኮሴው ምክር ንስሐ ገብተው ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተመልሰው እንደሆነ በአንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ተወስ[illegible]

www.ethiopianorthodox.org



ይህም ዐዋጅ ከተነገረ በኋላ በየዋሻው በየበረሀው የተሰደዱት ሊቃውንትና ካህናት መጻሕፍቶቻቸውን ይዘው ወደየቤታቸው ተመልሰዋል፡፡

አባ ዐምደ ሥላሴም ዐፄ ፋሲል ከጣሙሳ 44 ጉልት ስለሰጡዋቸው ተመልሰው ማኅበረ ሥላሴን ገዳማቸውን አቀኑ፣ ማኅበረ ሥላሴም የተባለው የአባ ዐምደ ሥላሴ ገዳም ስለሆነ ነው፡፡ ዐፄ ሱስንዮስም በነገሡ በ28 ዓመታቸው በ1625 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር ስለአረፉ ልጃቸው ፋሲል ነገሡ፡፡

ሕዝቡም ካህናቱም በአባታቸው ጊዜ ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት መለወጥ ውስጡን መቁርቁራቸውን ያውቅ ነበርና ከዳር እስከ ዳር ንግግቸውን በደስታ ተቀበለው፡፡

ከዚህ በኋላ ሊቃውንቱ በዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ መሪነት "የብዙ ሕዝብ ደም ፈስሶአልና ከሮማዊው ጳጳስ ከአልፎንሶ ጋር ተከራክረን ስለደማቸው እንፋረዳለንና ዐዋጅ ይነገርልን" ብለው ለዐፄ ፋሲል ነገሩዋቸው፡፡ እሺ ብለው ዐዋጅ አናገሩላቸው፡፡ ሊቃውንቱም ከእየአገሩ ተሰበሰቡና ጐንደር ላይ ጉባኤ ተደረገ፡፡

በዚህ ጊዜ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ የተማሩ ሊቅ ነበሩና ለሊቃውንቱ አፈ ጉባኤ ሆነው ቆሙ፣ ሜንዶዝ አልፎንሶም ወገኖቹን አነ/ኢዝን ይዞ ቆመ፣ በመገመሪያ አልፎንሶ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስን "የአብ የባሕርይ ልጁ ታሞ፣ ሞቶ ዓለምን አዳነ" የሚል ንባብ ከብሉይና ከሐዲስ ማስረጃ ስጡኝ" ብሎ ጠየቃቸው፡፡ ዕጨጌም ጳውሎስ ወደ ሮሜ በጻፈው መልእክቱ "እግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት አዳነን" ይልብሃል ቢሉት መልስ አጥቶ ዝም አለ፡፡ ቀጥሎም ማሸነፊያ ያገኘሁ መስሎት "የእግዚአብሔር ፊቱ ወይቶ ነው? ብሎ ቢጠይቃቸው፣ በጉባኤው መብራት አስበርተው የዚህ መብራት ፊቱ ወይቶ ነው ?" እያሉ መልሰው ጠየቁት፣ ስለሆም መልስ አላገኘም፣ ዕጨጌም "የዚህ መብራት ፊት በዚህ ገጽ ነው አንደማይባል የእግዚአብሔርም ፊት በአራቱ ማዕዘን ነው" ብለው ረቱት፡፡ ይልቁንም "የእግዚአብሔር ፊቱ ከፊ ወደሚሠሩ ሰዎች ነው" የሚለውን መዝሙረ ዳዊት ጠቅሰው ፊታቸውን ወደ አልፎንሶ አዙረው በጥፊ መቱት ይላል ታሪኩ፡፡ ከዚህም አያይዞ አንዱ ሊቅ" ረከብናሁ ለበትር ዘያደክማ ለርሜ፣ ጽናብ በንባብ ወቅሩፀ በትርንሜ" ብሎ ሲቀኝ፣ ሊቃውንቱ "ንሴብሖ ለእግዚአብሔር" እያሉ በማሕሌት ያሬድ በአደባባይ አሸበሸቡ" ሲል ታሪክ ነገሥቱ ይናገራል፡፡

በሱስንዮስ ለተጨፈጨፉት ሰማዕታት ምክንያቶቹ ካቶሊኮች መሆናቸውን ገድለ አቡነ ሐራ እንደሚከተለው በስፋት ይገልጠዋል፡፡

" ወበ፲ ወ፪ ዓመት እምናኔሁ ለአቡነ ሐራ ድንግል መጽአት ሃይማኖተ ሮምያ ኀበ ምድረ ኢትዮጵያ ወበረት ፲ ዓመተ እንዘ ኢትትከሠት ለኵሉ ሰብእ እንዘለ ኀዳጣን ሰብእ እለ ያፈቅርዋ ወይብልዋ ሃይማኖትነ ይእቲ ዘታጸድቀነ እስመ ያሩ አዕይንቲሆሙ ወተጸለለ ልቦሙ ከመ ኢያብርሁ በብርሃነ አእምሮ ሰብሐቲሁ ለእግዚአብሔር፡፡ ወበ ፲ ዓመት ተከሥተት እምሥዋሪሃ፣ ወተነግረት በነገ ኵሎሙ ሰብእ በተአዘዘ ንጉሥ ዘአፍቀሪ ወፈተዋ፣ ወበትምህርተ ካህናተ ሮምያ እለ ይትአመኑ በብሂል ፪ ባሕርይ ፪ ግብር እምድኅረ ተዋሕደ ቃል በነሢአ ሥጋ ወነፍስ እምድንግል ወይክፍልዎ ለፀ አካል፣ ወለፀ ባሕርይ ነው ፪ እንዘ ይብሉ መለኮት ይትበር ግብረ መለኮት፣ ወትስብእት ይትበር ግብረ ትስብእት ... ወበውስቴ ጊዜ ፈለሰት ሃይማኖተ አስክንድርያ ቅድስት እንተ ተአምን ብሂል ፪ ውስቴ መለኮት ወትስብእት በተዋሕዶ ... ....

ወአመ ተከሥተት እንታክቲ ሃይማኖት እንተ ያመልክዋ ነገደ ልዮን፣ ያደ ዐዋዲ ውስተ ኵሉ ምድረ ኢ/ዮጵያ በትእዛዘ ንጉሥ እንዘ ይብል ተወከፉ ኵልክሙ ዛቲ ሃይማኖተ ዘአምጻእነ ለክሙ እምድረ ሮም ከመ ትርከቡ ሕይወተ ወመድኀኒተ ለሥጋክሙ ወነፍስክሙ፣ ወትነብሩ በሀገርክሙ እንዘለ ይትሐየድ ንግሥክሙ ወይትበርበር ቤትክሙ፣ ወይትሐትል ሕያውናክሙ በሞት፣ እመሰ ዐበይክሙ ዘንተ ትእዛዘ ዘተጸአ እምአፈ ንጉሥ ይትሐየድ ንዋይክሙ ወይትበረበር ቤትክሙ ወትመውቱ አንትሙ በኵናት፣ ወበመጥባሕት፡፡

ወአምድኅረ ዝንቱ ትእዛዘ ተሐውከት ኵላ ሀገር ወማሰነት ቦ ሰብእ እለ ተሰዱ ብሔረ ርሑቀ ለአ/ንግሥ ሃይማኖቶሙ ወቦ እለ ተቀትሉ በእንተ ሃይማኖቶሙ በኵናት ወበመጥባሕት፣ ወቦ እለ ሞቱ ወ[illegible] ሞት ወቦ እለ ቦኡ በዛቲ ሃይማኖት በእንተ ፍርሀተ ሞት፣ ወቦ እለ ቦኡ በእንተ ረኪበ ክብር ኀላፊ፣ [illegible] ቦቱ፣

አቡነስ ሐራ ድንግል ኮነ ዘያጸንዕ በሃይማኖት ኩሎ ሰብአ ዘይመጽኡ ኀቤሁ፣ ወዘይሰምዑ ምክረ ዚአሁ፣ ወይትዋህፎሙ ወያበውኦሙ ወያኀድሮሙ ውስተ ቤቱ ለኩሎሙ መነኮሳት ወካህናት ወምእመናን እለ ተሰዱ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት፡፡

ወበ፤ ወ፮ ዓመት እምዘ ፈለሰት ሃይማኖተ እስክንድርያ ቅድስት ተመይጠት ወኮነት ከመ ቀዳሚ በትእዛዘ ንጉሥ ዘስሙ ፋሲለደስ፡፡ ወፈለሰት ሃይማኖተ ሮምያ ወበዝኑቱ ሚጠተ ሃይማኖት ኮነ ትፍሥሕት በምልዐ ምድረ ኢትዮጵያ ወተመይጡ ኩሎሙ ስዱዳን እለ ተርፉ እምነ ሞት ወበኡ በበሀገሮሙ ወበበመካኖሙ ውነበ አቡነሂ ሐራ ድንግል ተጋብኡ ብዙኃን መነኮሳት እለነበሩ ዝርዋነ በኩሉ ገጸ መካን ወተዘይነዉ ተመይጦታ ለሃይማኖቶሙ፡፡

ወሠናየ ኮነ ዝ ነገር በቅድሜሆሙ እስመ ተመይጠት ሃይማኖት ብዙኃን ዘመን እምዘፈለሰት፡ ወሰብሕዎ ወአዕኰትዎ ለእግዚአብሔር ኩሎሙ ነቢሮሙ በፆ አፍ"

በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው ከገድሉ የተገኘው ታሪክ ትርጉሙ በአማርኛ ቋንቋ እንደሚከተለው ነው፡፡ "አቡነ ሐራ ድንግል ምናኔ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በ14ኛው ዓመት የሮምያ ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ምድር መጣች፣ የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ብርሃን እንዳያበሩ ዐይናቸው ታውሮዋልና ልባቸውም ተጋርዶዋልና ከሚወዳዋትና የምታጸድቀን ሃይማኖታችን ይቺ ናት ከሚሉዋት ከጥቂቶች ሰዎች በስተቀር ለሰዎች ሁሉ ስትገለጥ 10 ዓመት ኖረች፡፡

በ10ኛውም ዓመት ከተሠወረችበት ተገለጠች፣ በሚወዳትና በሚመኙት ንጉሥ /ሱስንዮስ/ ትእዛዝና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋንና ነፍስን በመንሣት ቃል ከተዋሐደ በኋላ ሁለት ባሕርይ፣ ሁለት ግብር በማለት በሚያምኑ የሮምያ ካህናት ትምህርት በሰዎች ሁሉ ዘንድ ተነገረች፡፡ ሮማውያን መለኮት የመለኮትን ሥራ ይሠራል፣ ትስብእትም የትስብእትን ሥራ ይሠራል እያሉ አንዱን አካልና አንዱን ባሕርይ ወደ ሁለት ይከፍሉታል፡፡

በዚያም ጊዜ መለኮትና ትስብእት በተዋሕዶ አንድ ነው ብላ የምታምን ቅድስት የእስክንድርያ ሃይማኖት ተሰደደች፡፡ የልዮን ወገኖች የሚያመልኩባት ያቺ የካቶሊክ ሃይማኖትም በተገለጠች ጊዜ ወገኖ ነጋሪ በንጉሡ /ሱስንዮስ/ ትእዛዝ በመላ ኢትዮጵያ ዞሮ ዐዋጅ ነገረ፣ እንዲህ እያለ፦

ለሥጋችሁና ለነፍሳችሁ ሕይወትና መድኀኒት ታገኙ ዘንድ ከሮም ምድር ያመጣነላችሁን ይቺን ሃይማኖት ሁላችሁም ተቀበሉ፣ ገንዘባችሁ ሳይቀማ፣ ቤታችሁ ሳይዘረፍ፣ ደኅንነታችሁም በሞት ሳይጠፋ በሀገራችሁ ትኖራላችሁ፡፡

ከንጉሥ አፍ የወጣውን ይህን ትእዛዝ እንቢ ከአላችሁ ግን ገንዘባችሁ ይቀማል፣ ቤታችሁ ይወረዘራል፣ እናንተም በጦርና በሰይፍ ትሞታላችሁ፡፡

ከዚህም ዐዋጅ በኋላ ሀገሪቱ በመላዋ ታወክች፣ ጠፋችም፣ ሃይማኖታቸውን ለማዳን ሩቅ አገር የተሰደዱ ሰዎች አሉ፡፡ ስለ ሃይማኖታቸውም በጉራጅና በጦር የተገደሉ አሉ፣ በሌላም ሞት የሞቱ አሉ፣ ሞትን በመፍራትም በዚች ሃይማኖት የገቡ አሉ፣ አላፊ ክብርንም ለማግኘት የገቡ አሉ፣ የሚጸድቁበት መስሎዋቸውም የገቡ አሉ፡፡ አባታችን ሐራ ድንግል ግን ወደ እርሱ የሚመጡትንና ምክሩን የሚሰሙትን ሰዎች ሁሉ በሃይማኖት ያጽናና ነበር፡፡ ስለ ቀናች ሃይማኖት የተሰደዱትን መነኮሳት፣ ካህናትና ምእመናን ሁሉ እየተቀበለ ወደቤቱ አስገብቶ ያሳድራቸው ነበር፡፡ ቅድስቲቱ የእስክንድርያ ሃይማኖትም ከተሰደደች አንሥቶ በ16ኛው ዓመት ስሙ ፋሲለደስ በተባለ ንጉሥ ትእዛዝ ተመልሳ እንደ ቀድሞዋ ሆነች፣

የሮምያ ሃይማኖትም ፈለሰች፡፡ በዚህም የሃይማኖት መመለስ በመላ የኢተዮጵያ ምድር ደስታ ሆነ፣ ከሞት የተረፉት ስደተኞች ሁሉ ተመለሱ፡፡ በአገራቸውና በየቦታቸውም ገቡ፣ በእየቦታው ሁሉ ተበትነው የነበሩት ብዙዎች መነኮሳት በአባታችን በሐራ ድንግል ዘንድ ተሰበሰቡና የሃይማኖታቸውን መመለስ ተጨዋወቱ፡፡ ይህም ነገር በፈታቸው መልካም ሆነ፡፡ በተሰደደች በብዙ ዘመን ሃይማኖት ተመልሳለችና ሁሉም አንድ ሆነው በአንድ አፍ እግዚአብሔርን አመሰገኑት፣ አከበሩትም፡፡"



# ክፍል 5

## የሰማዕትነት ዘመን በደርቡሽ

በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በ1880 ዓ.ም. አካባቢ በባሕረ ኢትዮጵያ በኩል የደርቡሾች አጥቂነት እየባሰ በመሔድ ላይ ይገኝ ነበር፡፡ ዋናው የንቅናቄው መሥራች ማህዲ አህመድ ከሞተ ወዲህ ተክታዩ ከሊፋ አብዱላሂ የማህዲን የግዛትና የአስልምናን ሃይማኖት የማስፋፋት ዓላማ በመከተል የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት የጦርነት ፍጥጫ ጀመረ፣ በ1878-79 ዓ.ም. ላይ ብዙ ጊዜ አፄ ዮሐንስ ደብረ ታቦር በመቀመጥ በመተማና በጋላባት የደርቡሾቹን ንቅናቄ በሩቁ ይቁጣጠሩ ነበር፡፡

በመተማ የደርቡሾቹ መገፋት በተሰማ ጊዜ የወሎ እስላሞች ሽፍትነት ስለተቀሰቀሰ ንጉሠ ነገሥቱ ከደብረ ታቦር ተነቃንቀው ወደእዚያ ሲያመሩ በጋላባትና በመተማ የነበሩት ደርቡሾች ምቹ ጊዜ ስለአጋጠማቸው ከወሰን አልፈው ደምቢያንና ጭልጋን ወረሩ፡፡ የደምቢያውም አስተዳዳሪ ሹም ዳኘና ፋንታ ከደርቡሾቹ ጋር በመዋጋት ሕይወታቸው ዐለፈ፡፡ ስመ ጥሩው ገዳም ማኅበረ ሥላሴ በዚህ ጊዜ ተቃጠለ፡፡ ብዙም ሰው አለቀ፡፡

በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ወሎ ውስጥ እንደነበሩ የጐጃሙን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ጦራቸውን ይዘው ሐይደው ደርቡሾችን እንዲከላከሉ አዘዙአቸው፡፡ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም እስከ 100,000/አንድ መቶ ሺ/ የሚደርሰውን የገዛ ጦራቸውን ይዘው በአገው ምድር አድርገው ወደ ደንቢያ ተጓዙ፡፡ ከዚያም አልፈው ጥር ወር በታበረከ አላህ በኤልኑር ዋድ ፋጋራ የሚመሩትን አንሳሮችን አሸነፉ፡፡[9]

ከዚያም አልፈው መተማ ደርሰው በመሐመድ ዋድአራብ የሚመሩትን ደርቡሾች አሸንፈው በደስታ ወደኋላቸው መለስ ብለው በደብረ ሲና ሰፈሩ፡፡[10]

የዚህን ሁሉ ወሬ ዋናው የደርቡሾች ጠቅላይ መሪ ከሊፋ አብዱላሂ ሲሰማ በበኩሉ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን የሚወጋ ጦር አዘጋጅቶ የበላይ መሪ ጣምዳን አቡ አንጋ የሚባለውን ሾመ፡፡ በርሱም ውስጥ አህመድ ዐሊ አብዱላሂ፣ ኢብራሂም ፣ አልዚኪ፣ ቱማል፣ አራቢ፣ ዳዙ፣ አላህ የሚባሉት የጦር አለቆች የነበሩበት ጦራቸውን ይዘው ይገኙ ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ በደንብ ከተዘጋጁ በኋላ በአቡ አንጋ እየተመሩ ከጋላባት ወደ ደንቢያ መጥተው ሣር ውሀ በሚባለው ቀበሌ ሠፈሩ፡፡ በዚህም ጊዜ ጥር 10 ቀን 1880 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ገሥግሠው መጥተው ደርቡሾቹን ሲገጥሙ እነዚያ ቀደም ብለው ምቹ ስፍራ ይዘው ይጠባበቁ ነበርና የመጀመሪያውን ግንባር ቀደም የኢትዮጵያ ጦር በቀላሉ አሸንፈው ደጅኑንም በድንገት ፈረስ እያባረሩ ይወጉ ጀመር፡፡ ከዚያ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦር ፈራርሶ የሚረሱትን ማርከው ጉንደርን አጠፉ ሊቃውንቱን ወልደ አብ፣ ወልደ ሚካኤልን ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ አረዱዋቸው፣ ሴሎችንም ሊቃውንትና መምህራንን፣ ካህናትንና ዲያቆናትን፣ ምእመናንና ምእመናትን በጥይት ቆሉዋቸው፡፡ በኋላም ሕምዳን አቡ አንጋ ወደአገሩ ተመልሶ እንደ ደንቡ ከማረከው ውስጥ ከአምስት አንዱን እጅ ሰራሱ አስቀርቶ የቀረውን ምርኮ ከነ ሰዉ ለከሊፋ አብዱላሂ አስረከበ፡፡

በዚህ የሃይማኖት ጦርነት ቍጥሩ በትክክል ያልታወቀ አያሌ ሕዝበ ክርስቲያን በሰማዕትነት ሞቱ፣ ከ44 የጉንደር አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ዐርባዎቹ መቃጠላቸው በልዩ ልዩ የታሪክ መጻሕፍት ተጠቅሰዋል፡፡[11] ከታወቁትም ዐርበኞች ደጃች ካሣ፣ ደጃች ይማም ካሣ፣ ፊት አውራሪ እሸቴ፣ ፊት አውራሪ ንጉሤ፣ ፊት አውራሪ ረታ፣ ፊት አውራሪ ይልማ፣ ጸሓፌ ትእዛዝ አለቃ እሸቴ፣ ቀኝ አዝማች ለማ፣ ባላገባራስ ጋርጠው፣ በጀግንነት እየተዋጉ በጦሩ ሜዳ ወድቀው መሞታቸውን ተክለ ሥላሴ አብራርተው ገልጸውታል፡፡

9 አ[illegible] የደርቡሽ አንድ የነገድ ክፍል ነው
10 ወ[illegible]ረ ጉንደር ነው ደብረ ሲና የሚገኘው፣ ከጉንደር ርቀቱ 38 ማይልስ ነው
11 ዮ[illegible] ገብረ ሥላሴ ዘውደ ጽሑፍ ገጽ 446፣ በማርከስ ሐርቅድ ጽሑፍ ገጽ 101

www.ethiopianorthodox.org

ጸሓፊው ከዚሁ አያይዘው ጽሑፋቸውን በመቀጠል አቡ አንጋ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መኳንንት ውስጥ የ12 ሰው ጭንቅላት ቁርጦ ለሱዳኑ /ደርቡሽ/ መሪ ለአሚር አብዱላሂ ስለባ ላከ፡፡ የቀረውን ምርኮ እየነዳ ጉንደር ገብቶ ቤተ ክርስቲያን ማቃጠሉን፣ ብዙ ክርስቲያን ማረዱን፣ የተረፈውን ምርኮኛ እየነዳ ወስዶ በዘረፋ ከአገኘው ከ30,000 (ሰላሳ ሺህ) ብር ጋር ወስዶ አምዱርማን ለነበረው አለቃው ለአብዱላሂ ማስረከቡን፣ ከሌፋ አብዱላሂም አቡ አንጋን አመስግኖ ከተማረኩት ሴት ወይዛዝርት ውስጥ ቆንጆዎቹን ለራሱ ዕቁባት አድርጎ አስቀርቶ የቀሩትን ጉንጫቸውን እያስተለተለ ባሪያ ሆነው መሸጣቸውን፣ ከተማረኩት ወይዛዝርት ውስጥ የራሳቸው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ምንትዋብ ዐዳል የምትባለው ባለቤቷ ደጃች ጀምበሬ ሲሞቱ እሷ ተማርካ ሳለ በእስላም እጅ አልበላም ብላ /አልሰልምም ብላ/ በችጋር እንደሞተች ዘርዝረው ጽፈዋል፡፡

በዚሁ ጊዜ ደርቡሽ ከመተማ ወደ ደንቢያ /ሣር ውሀ/ መጥቶ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ተዋግቶ ማሸነፉን፣ ጉንደርን ማቃጠሉንና ሰውንም መፃጅቱን አቶ ዐጽሜ ጽፈዋል፡፡ ንጉሥ ምኒልክ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን መሸነፍ ሲሰሙ ከቦሩ ሜዳ ወደ በጌምድር መገሥገሣቸውን ከዚያም ወደ ጉንደር ወርደው በአዘዞ ሠፍረው ከሠራዊታቸው ብዛት የተነሣ ሠራዊታቸውን በአንድ ጊዜ ማስሰፍ ስለአልቻሉ ሁለት ጊዜ አሰልፈው ያንደኛውን ሰልፍ ሁኔታ በአቅራቢያው የነበሩት ደርቡሾች በሰላዮቻቸው በኩል ተገንዝበው ማድነቃቸውን ዘርዝረዋል፡፡[12]

ዓፄ ዮሐንስ ንጉሥ ምኒልክ ወደሀገራቸው እንዲመለሱ ከአደረጉ በኋላ ከደርቡሾች መሪ ከአብዱላሂ ጋር በደርቡሽ ሹሞች በነሐምዳን አቡ አንጋ አማካይነት "እኛና እናንተ አፍሪካውያን ሁላችንም የካም ልጆች ወንድም አማች ነን፡፡ በዚህም ላይ ወሰነተኞችና ጐረ ሀገሮች ስለሆንን በአንድነት ሆነን ነጮቹን እንቃወም " የሚል ደብዳቤ በመጻፍ በዚህም በኩል አዲስ የፖለቲካ መስመር ከፍተው ነበር፣ አብዱላሂ ግን ይግረምዎት ብሎ መደምደሚያውን "እኛና እናንተ ኅብረት የምናገኘው የክርስትና ሃይማኖትዎን ለውጠው የእኔን ሃይማኖት እስልምናን ሲቀበሉ ብቻ ነው" የሚል መልስ ስለሰጠ በዚህ በኩል የመስማማቱ ነገር እንደዚሁ ውድቅ ሆነና ሁለቱም ለሚለየው ጦርነት ይዘጋጁ ጀመር፡፡ 13

በዚህም መሠረት ዓፄ ዮሐንስ ፈታቸውን ወደ መተማ አዙረው ደርቡሽን ለመከላከል ወደ ደምቢያ ሔዱ፡፡ ደምቢያ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ደርቡሾች ከተዋጉበት ሣር ውሀ ከሚባለው ስፍራ ደርሰው በጦርነቱ ውስጥ የሞቱትን የሕዝበ ክርስቲያኑን አጥንት አይተው በጣም አዘኑ ይባላል፡፡ እርሳቸውም ወደ መተማ ጉዞ ጀመሩ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግን በአለፈው የሣር ውሀ ጦርነት ሠራዊታቸው ስለተጐዳ በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ተሰናብተው ቀሩ፣ የጐጃሙ ጳጳስ አቡነ ሉቃስ ብቻ "ከንጉሠ ነገሥቱ አልለይም" ብለው አብረው ተጓዙ፡፡ አብሮ የዘመተውን የጦር ሠራዊት ቍጥር ብላቴን ጌታ ኀሩይ 150,000 /መቶ ሃምሣ ሺ/አግረኛና ከዚሁም 20,000 /ሃያ ሺ/ ፈረሰኛ ሲያደርጉት አለቃ ተክለ ሥላሴ 100,000/መቶ ሺ/ እግረኛና 20,000 /ሃያ ሺ/ ፈረሰኛ ላይ መድበውታል፡፡

የተከተሉዋቸው ዋና ዋና የጦርና የአስተዳደር መኳንንት ዕድሜያቸው ወደ ሰማንያ ዓመት የተጠጋ ነበር፣ ደጅአዝማቹና ፈትአውራሪው፣ ቀኝ አዝማቹና ግራ አዝማቹ እጅግ ብዙ ነበር፣ ከቤተ ክህነትም ወገን ከአቡነ ሉቃስ በቀር ጳጳሳቱ እነ አቡነ ጴጥሮስ፣ ዕጨጌው አባ ቴዎፍሎስ ታቦት አጅበው የሔዱ ብዙ ካህናትና ዲያቆናት ይገኛሉ፡፡ ከደርቡሽ ጦር በቀር ከወሎና ከወሎ አካባቢ ከዋጅራት፣ ከራያና አዘቦ የሔደው ወድዶ ዘማች አስላም በሼክ ጦልሃ ቤን ጃፋር መሪነት የቀረውም ከወዲህ ከኢትዮጵያ ሰሜንና ከባሕረ ኢትዮጵያ ከቦጎስና ከቢኒ አሚር በነአህመድአል ጅር በነዲግላል መሐመድ እየተመራ ወደ ደርቡሾቹ ተደባልቆ ጎይላቸውን አጠናክሮላቸዋል፡፡[14] ከማህዲ አነሣሥ ወዲህ ደርቡሾች የአስልምናን ሃይማኖት ለማስፋፋት የቱርክንና የግብጽን ግዛት የፈረንጆችን፣ በተለይ የእንግሊዞችን የበላይ ተቈጣጣሪነት ደምስሰው አስልምናን በክርስትና ለመተካት የተነሡበት፣ እንደ መሐመድ ተከታይ የቈጠሩት ማህዲ አህመድ የተናገረው ሁሉ የሚፈጸም፣ የእርሱንም እምነት ተከትሎ በተነሣው ተዋጊ ጦር ላይ የማንም ጎይል ተነሥቶ እንደማይመልሰው መረዳታቸውን አቡ አንጋ ለአፄ ዮሐንስ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ገልጾታል፡፡[15]

12 አቶ ወርሚ የአርሞ ታሪክ ገጽ 163-165፣ አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት ከተ.መ. ገጽ 457-465
13 G.S. the process of the Reunification of the Ethiopian Empire P.525-533
ኀሩይ ወልደ ሥላሴ ኢትዮጵያና መተማ የአፄ ዮሐንስ ታሪክ ገጽ 11
14 L. Italia in Africa P 239-240
አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት ከተ.ጸ.መ. ገጽ 538
15 አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት ከተ.ጸ.መ. ገጽ 532-533





በዚያ ጊዜ ኢትዮጵያውያንና ሱዳኖች ያደረጉት ጦርነት የሃይማኖት ጦርነት መሆኑ ይታወጎታል፡፡ አቶ ተክለ ጻድቅ መኮሪያ "ዓፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት" በተባለው ስለ ዓፄ ዮሐንስ ታሪክ በጻፉት መጽሐፋቸው የደርቡሽን ጦርነት በተመለከተ በጻፉት አስተያየት በእንግሊዞች ላይ ያላቸውን ትዝብት ቀጥሎ በአሉት መስመሮች እንዲህ ሲሉ ገልጠውታል፡፡

"በዚህ መካከል የሚያሳዝነው እንግሊዞች ወደ መቅደላ ዓፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት የመጡ ጊዜ ከአፄ ዮሐንስ /ያንጊዜ ደጅ አዝማች ካሣ/ የተደረገላቸውን አቀባበልና መስተንግዶ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ከልባቸው ንግሥት ቪክቶሪያን እንደ እናት፣ ጀኔራል ናፒየርን እንደ አባት ቈጥረው ሲመኩባቸው የነበረው ሁሉ ቀርቶ የአሁኑ የአፄ ዮሐንስና የደርቡሾች ጦርነት ዋና ሰበቡ የእንግሊዝ መንግሥት በአድሚራል ሔዊት አማካይነት ግብፅንና ኢትዮጵያን አዋውሎ ውሉን ለማክበር ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱ ለግብፆች ረድተው ከሱዳኖቹ ጋር በተዋጉበት ምክንያት መሆኑን እያወቀው በአሁኑ ጊዜ በመስዕ በኩል ጣሊያንን ጋብዞ ማስጠቃቱ ሳያንሰው በርሱ ሰበብ በተነሣው የደርቡሾች ጦርነትና የርሱንም ጀኔራሎች እነጉርዶን ከፈጅዋቸው ደርቡሾች ጋር ለመዋጋት ወደ መተማ ሲጓዙ አንዳች ርዳታ ሊያደርግላቸው አልፈለገም፡፡ ወታደርና የጦር መሣሪያ ባያቀብል እንኳን "በዚህ ዐይነት መክቱ፣ እንደዚህ አድርጋችሁ ብታጠቁ ታሸንፋላችሁ" ብሎ የሚመክር አንድ የጦርነት ልማድ ያለው እንደማርክሃም ያለ አንግሊዛዊ መኮንን ሊለግሣቸው አልቻለም፡፡

ካፒቴን ሐሪሰንና ሚስተር ጀራልድ ፓርታልን ልኮ "ለኢጣልያ መሬት ቈርጠው ይስጡ" የተባለውን አነጋገር ንጉሠ ነገሥቱ ሳይቀበሉ ከቀሩ ወዲህ ይኸው የእንግሊዝ መንግሥት አንድነቱንና ዝምድናውን ከኢጣልያ ጋር አጥብቆ እርሳቸውን ገሸሽ አድርጎ ትቷቸዋል፡፡

በመንግሥታት መካከል ጥቅምን መከተል እንጂ የሞራል ግዴታ በምንም ዐይነት ስለሌለ ሁኔታው ያሳዝናል፣ ስለዚህ የመንግሥት መሪ ሁሉ በሌላው መሪ መታመንን ትቶ ራሱ በራሱ ለራሱ የሚወጣበትን መንገድ ጠንክሮ ከማበጀት በቀር ሌላ መድኀን እንደሌለ ይህ የአሁኑ የእንግሊዞች አቅዋም ደኅና መማሪያ የሆነ የፊደል ሰሌዳ ነው፡፡

ማናቸውም ውል ወይም የቃል ኪዳን ወዳጅነት ቢደረግም ውሉ የሚሠምረው በመጀመሪያ ራስን አደርጅቶ መሆን አለበት፡፡ ያለዚያ ውሉ የጌታና የአገልጋይ መልክ ፈጥሮ ጸጸት ሊያስከትል ይችላል፡፡ የዓፄ ዮሐንስና የእንግሊዞች ውል ከዚህ ሁኔታ ላይ እንደወደቀ ይታያል፡፡"[16]

## ዓፄ ዮሐንስ በሰማዕትነት እንደ ሞቱ

ኢትዮጵያውያኑ "በብርቱ ጦርነት ከተከላከሉ በኋላ የከተማውን ቅጥር በአንድ ወገን ጥሰውት ገቡ፡፡ በከተማው ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ እየወጣ እንዲሸሽ ቤቱንና ቅጥሩን አቃጠሉት፡፡ በአንድ ወገንም ዘልቀው ግምጃ ቤቱን ያዙት፣ ያቡ አንጋንም አዕምሮ ለማቃጠል ቤቱን ሁሉ ይቀሰቅሱ ነበር፣ ይህንም ያስቡበት ምክንያት አቡ አንጋ ጉንደርን አጥፍቶ ሊቃውንቱን ሁሉ በአሳት አቃጥሎዋቸው ነበርና የዚያን ብድር ለመመለስ ነበር፡፡

"ነገር ግን ዓፄ ዮሐንስ ምንም ጠንክረው ቢዋጉ፣ ድል ማድረግ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይሆንምና ድል ለማድረግ ጥቂት ሲቀራቸው በጠመንጃ ቁሰሉና ወራው ያንጊዜውኑ በየሰልፉ ውስጥ ተሰማ፡፡ መኳንንቱም ወታደሩም ከቅጥሩ ውስጥ እየወጡ መሸሽ ጀመሩ፡፡"

"ዓፄ ዮሐንስ ከመቀሰላቸው የተነሣ ሰውነታቸው መድከሙን ስለተረዱት የወንድማቸውን የደጃች ጉግሣን ልጅ ራስ ጎይለ ማርያምን /ጠቅላይ የጦር አዝማቹን/ አልጋ ወራሽ ለማድረግ አስበው ጳጳሱንና ዕጨጌውን፣ ስጊዜው በአጠገባቸው የተገኙትንም ትልልቆች መኳንንት ሰብስበው ራስ ጎይለ ማርያምን ጥሩት ቢሉ በጦርነት ስለቁሰሉ ለመምጣት አይችሉም አሉዋቸው፡፡ እርሳቸው ግን አይችልም ያሉኝ ቢሞት ነው ብለው በጣም አዘኑ፡፡ ቀጥለው ወንድሙን ራስ መንገሻን ጥሩልኝ ብለው እኔ የሞትሁ እንደሆነ አልጋ ወራሽ ልጄ ራስ መንገሻ ነውና ለእርሱ ተገዙ ብለው የኑዛዜ ቃል ተናገሩና በማግሥቱ ዐረፉ፡፡"

16 አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት /ከተ.ጸ. መ/ ገጽ 539



www.ethiopianorthodox.org

ብላቴን ጌታ ኀሩይ ከዚሁ አያይዘው "መኪንንቱ የንጉሠ ነገሥቱን ሬሳ በሳጥን ውስጥ አግብተው ወደ አትባራ ወንዝ ፊታቸውን አዙረው መሸሻቸውን፣ ደርቡሾቹ እየተዋጉ የሞቱትን የኢትዮጵያን መኪንንት ሁሉ ራሳቸውን እየቁረጡ አምዱርማን ድረስ ለከሰፋ አብዱላሂ መላካቸውን፣ ቢሆንም ሐብሾች በማግሥቱ እሑድ እንደገና ተመልሰው አደጋ ይጥሉብናል እያሉ ሲፈሩ ማደራቸውን፣ ነገር ግን ሰላይ ልከው ስለነበረ፣ ሰላዩ ተመልሶ አበሾች ፊታቸውን ወደ አትባራ ወንዝ አዙረው ይሸሻሉ እንጂ አንድም መኮንን ተዳፍሮ ፊቱን ወደ እኛ ያዞረ የለም ብሎ ሪፖርት ስለአደረገ፣ የጦር አበጋዙ ዘኪ ቱማል ሠራዊቱን እንደገና በአዲስ ኀይል ሰብስቦ በድንገላ ፈረስና በጠያር ግመል አድርጎ እግር በእግር ተከታትሎ መጋቢት 3 ቀን ሰኞ የአፄ ዮሐንስን ሬሳ ይዘው የሚጓዙት መኪንንት በአትባራ ወንዝ ዳር ሠፍረው ሳሉ ደርሶ አደጋ ጥሎ እንደተዋጋቸው፣ የአፄ ዮሐንስ አሽከሮችና መኪንንቱም በድንኳኑ ዙሪያ ተሰልፈው እርስ በርሳቸው እየተፎካከሩ ጠንክረው መከላከላቸውን፣ "የጌታችንን ሬሳ አናስማርክም በማለት በድንኳኑ በር ላይ ትልቁ ራስ አርአያ /አጐታቸው/፣ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ገብረ ጻድቅ የዘበኞች አለቃ ደጃች ተድላ፣ ብላታ ገብረ ማርያም አዛዥ ወንድምሁነኝ፣ አዛዥ ላዕከ፣ ጽራግ ማሠራ ዘሚካኤል፣ መምህር ወልደ አረጋይ፣ መምህር ክንፈ ኪሩብ፣ ቁስ ገበገ ሰላማ በሰማዕትነት መሞታቸውን ዘርዝረው ጽፈዋል።[17]

# ክፍል 6

## የሰማዕትነት ዘመን በኢጣሊያ ፋሺሽት

በ1928 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በግፈኛው ፋሺሽት ተወረረች፤ መሶሎኒ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ ለመግዛት በአደረገው ዘመቻ እንደ ፈረንጆች አቈጣጠር በ1937 (በ1929) ዓ.ም. በሊብያ ዋና ከተማ በትሪፖሊ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለማፈራረስና ክርስቲያኖችንም ለመፍጀት መነሣቱን የሚገልጥ አዋጅ ነገረ። አዋጁም የሚከተለው ነበር፦ "የፋሺሽት ኢጣሊያን በሊብያና በኢትዮጵያ ለሚኖሩ እስላሞች የሰላም ዋስትና ለመስጠት አስቡዋል፤ ትክክለኛ ፍትሕና ብልጽግናም ለእስላሞች ያደርጋል። የነቢዩ መሐመድንም ሕግ ያከብራል፤ ከዚህም በላይ ለመላው ዓለም እስላሞች ያለውን ቅንና መልካም አስተሳሰብ ሊገልጥ ይወዳል።

ከዚህ ቀደም ብሎ በ1935 (በ1928) ዓ.ም. የሙሶሎኒ ጦር ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ የኢትዮጵያን ምእመናን ወደ ካቶሊክነት ጐተራ ለማስገባት ሰሮማ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ የአገመራ ጊዜ የሆነላት መስሎዋት ነበር። ስለዚህ የኢጣሊያ ጳጳሳት ካርዲናሎችና ፓፓውም ለሙሶሎኒ ብዙ የጦር መሣሪያ ርዳታ አድርገዋል። ምእመናኑም በየቤተ ክርስቲያኑ ለሙሶሎኒ የጦር መሣሪያ መግዣ የሚውል ብር ወደ ሙዳየ ምጽዋት እንዲያስገቡ በየሰበካው ቁስና መነኩሴ ይታዘዙ ነበር።[18] የኢጣሊያ ፋሺሽት ጦርነት ያደረገው በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም ከጦርነቱ ስፍራ በራቁት በሰላማዊ ሕዝብ ላይ በማስደንገጥ ለመግደልና ዘራቸውንም ለማጥፋት አደጋ እየጣለ ወጋቸው።

በአይሮፕላን ላይ መርዝ የተቀላቀለበት ውሀ የሚረጭ መኪና ተዘጋጅቶ ሰፊ በሆነው አገር ላይ ሞትን የሚያመጣ ረቂቅ ዝናም እንዲወርድበት ተደረገ። ከ9-15 ቍጥር ያላቸው አይሮፕላኖች እየተመላለሱ የመርዝ ዝናብ ሳያቋርጥ እንዲወርድ አደረጉ። ከጥር ወር መጨረሻ 1928 ዓ.ም. ጀምሮ በወታደሮች፣ በሴቶችና በልጆች፣ በከብቶችና በፈሳሽ ወንዞች፣ በኩራዎችና በከብት መሰማሪያዎች ቦታዎች ላይ ሳያቋርጥ ሞት የሚያመጣ ይህ የመርዝ ዝናብ ዘነበባቸው። ፍጡር የሆኑትን ሁሉ ለማጥፋት ውሀውንና ለከብት የሚሆነውን ሣር መርዝ ብቻ ለማድረግ የፋሺሽቶች የጦር ሹም አይሮፕላኖቹ ይህንኑ ሥራቸውን እየተመላለሱ እንዲሠሩ አደረጉ። ይህም በረቂቅነት የሚሠራ የጭካኔ ሥራ ጦርነት ከሚደረግበት ቦታ በራቁት ቦታዎች የሚገኙትን ሕዝብ አጠፋቸው።

17 ክንግሥተ ሳባ እስከ ፀድዋ ጦርነት ገጽ 154-156
አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት /ከተጻ. መ/ ገጽ 541-545
18 A. Bertola Regimedei Culti nell Africa Italiana "Bologana 1939" P.162
የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ /አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ/ ገጽ 87-88



በዚህም መርዝ ሰውም ከብትም አለቀ፤ ይህም የመርዝ ዝናብ የዘነበበትን ውሀ የጠጡ መርዙም የነካውን ምግብ የተመገቡ በታላቅ ስቃይ አለቁ። በዚህም መርዝ በብዙ ሺ የሚቈጠሩ ሰዎች ሞቱ። በተለይም የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. በግራዝያኒ ላይ በተወረወረው ቦምብ ምክንያት በአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ ከባድ ዕልቂት ደረሰ። በአካፋና በመጥረቢያ ተጨፈጨፈ። በጦር ሜዳ የተማረኩት ራስ ደስታ፣ ደጅ አዝማች በየነና ሌሎች በብዙ መቶ የሚቈጠሩ መኪንንት በግፍ ተገደሉ፤ ቍጥራቸው ከ150 የማይልሙ የጦር አይሮፕላኖች በላዩ እያንገዳገዱ የጋዝ ጭስና ቦምብ አዘነበበት፤ በዚህ ጦርነት በየግንባሩ በርካታ መኪንንት፣ የጦር አለቆችና ሠራዊት አልቀዋል። በቤተ ክርስቲያናችን በካህናትና በሴቶችም ላይ ግፍና ርኩሰት ተደረገ።

ጣሊያን በገባበት ሀገር ሁሉ ሕዝቡን እየሰበሰበ በመትረየስ ፈጀው። በብዙ ሺ የሚቈጠሩ በየተራራውና በየሜዳው በመርዝ ተቃጠሉ። ሙሶሎኒ አዋጁን በሥራ ላይ ለማዋል ክሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተደረገለት ርዳታ የራያንና የሶማሊያን እስላሞች አስነሥቶ የብዙ ክርስቲያኖችን ደም አስፈሰሰዋል። በሴት፣ በሕፃንና በሽማግሌም ሳይቀር የኢትዮጵያ ክርስቲያን በሆነ ሁሉ ላይ ግፍ ተፈጸመ። ብዙ ገዳማትንና አድባራትን አፈራረሰ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ወራሪና ዘራፊ እየተከላከለች የአቋየቻቸውን የታሪክና የሃይማኖት ቅርሶቿን ዘርፎ ወስዶ ለቫቲካን አስረከበ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአስታትስቲክስ ክፍል እንደ ተመዘገበው 2,000 አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጥለው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል።

በአርበኝነት ለሃይማኖታቸውና ለአገራቸው ክብር ሲሉ ከኢጣሊያ ጋር ፊት ለፊት ተዋግተው የሞቱትን ክርስቲያኖች ሳይጨምር በአድባራቱና በገዳማቱ፣ በደብረ ሊባኖስ፣ በላሊበላ፣ በአክሱም፣ በጐንደርና በዝቋላ ብዙ ባሕታውያንና ካህናት ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው መሥዋዕት ሆነዋል።

ከጳጳሳቱም ታሪካቸው ለኢትዮጵያ ክርስቲያን መመኪያ የሆነው አቡነ ጴጥሮስ (ቀዳማዊ) ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያና አቡነ ሚካኤል ጳጳስ ዘጉራ በግፈኛው ፋሺሽት በሰማዕትነት ሞተዋል። በ1997 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የሰማዕትነት ስምና ቅጽል፣ ክብርና ማዕርግ እንዲሰጣቸውና ሰማዕት መሆናቸው እንዲታወቅ ዐዋጅ ወጥቷል። ከዚህም በመነሣት የአቡነ ጴጥሮስ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን በአውሮፓና በኢትዮጵያ በመቋቋም ላይ ነው።

ከዚህ ላይ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስከፊና አሳፋሪ ሆኖ የሚታየው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመደምሰስ የሮማ ፓፓ ከሞሶሎኒ ጋር መተባበሩ ነው። ፓፓው የተቀደሰ ዘመቻ ነው ብለው መድፉንና ታንኩን ባርከዋል። በዚህ ሁሉ ድርጊታቸውም በዓለም ክርስቲያኖች ዘንድ ተነቅፈውበታል።

በጀርመን በአስራኤል ላይ ግፍ ሲፈጸም ከሂትለርና ከሞሶሎኒ ጋር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመተባበርዋ በአለፈው ቅርብ ዓመት የሞቱት ፓፓ አስራኤልን ይቅርታ ሲጠይቁ የንቀታቸው ብዛት የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ አልጠየቁም።

በጊዜው የነበሩት ፓፓ ከሞሶሎኒ ጋር ሆነው ምክር ይሰጡ የነበሩና ብዙ ካህናትንም ያስፈጁ የወታደር ልብስ ለብሰው የመጡ የሮማ ካቶሊክ ቄሶች በርሳቸው አመራር ሰፈኒነት የተላኩ እንደነበሩ ይተረካል። ይህ ሁሉ ተደምሮ ታሪካቸው መርዝ የተጨመረበት ወተት ሆነዋል።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ምክንያት ብዙ ነቀፋና ትችት ከጻፉባቸው መካከል ኢሊክ ሲንድሩም የሚባሉት የስዊድን ጋዜጠኛ ፓፓውን እንዴት እንደወቀሱዋቸው ከዚህ ቀጥሎ ቀርቡዋል፡፡

"ቅዱስ ሆይ? እኔ በሰሜን አገር የተወለድሁ አንድ ፕሮቴስታንት ነኝ፡፡ በአገራችንም በስዊድን በግንባራችን የምንደፋው በዕልፍኛችን ሆነን ከእግዚአብሔር ከአምላካችን ጋር ስንነጋገር ነው እንጂ ከሰው ጋራ ብንናገር ቆመን እንነጋገራለንና በእግርዎ ላይ ወድቄ ጫማዎን ስለማልስምዎ አይቄጡብኝ፣ ቅዱስ ሆይ? እኔ አንድ ምስኪን ኅጢአተኛ እርስዎ ግን የመድኃኒታችን ምትክ ነዎት፡፡ የማይሳሳቱም ነዎት፣ ይሁን እንጂ እኔ እነቅፍዎታለሁ፡፡ እርስዎ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዋና ነዎት፡፡ ካቶሊካዊት ማለትም የሁሉ ማለት ነው፡፡ ዛሬ እንግዲህ የርስዎ ቤተ ክርስቲያን በእውነት የሁሉ ቤተ ክርስቲያን ናት? እርስዎ ከሞሶሎኒ ጋር ሆነው ከሌላው ዓለም ጋር በጠብ አሉ፡፡ እርስዎና ከርስዎ በታች ያሉት ሌሎችም ጳጳሳት ኢትዮጵያ ለኢጣሊያ ቅኝ አገር እንድትሆን የሚገባ ነው ብለው ተናገሩ፣ እርስዎ መቼም የሐዋርያው የጴጥሮስ ተከታይ ነዎትና አይሳሳቱም፡፡ እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ ቃልዎን ሳይሰማ በኢጣሊያ ላይ "ሳንክሲዮ" ቢያደርግ መሳሳቱ ነው? ቅዱስ ሆይ? ኢጣሊያ የፍርድ ሥራ ትሠራለች ብለው ሰብከዋል፡፡

የመሲና የቢረንዴሌም ጳጳሳት ወርቃቸውን ሁሉ ለጦርነቱ ከሳራ እንደሰጡ ሰማን፡፡ እናንተ ጳጳሳት ይህን ስታደርጉ እግዚአብሔር ከኢጣሊያ ጋር ነው የማለት ይመስለኛል፡፡

እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ የኢጣሊያን ሥራ ቢቃወም የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቃወም ይሆን? ኢትዮጵያውያንስ አገራቸውን ሲጠብቁ በእግዚአብሔር ላይ ተነሥተው ይህን ርስዎ እንደ አሉ ኢጣሊያ የጽድቅ ውጊያ የምትዋጋ ከሆነ ሌላውም ዓለም ይህን የጽድቅ ጦርነት ቢቃወም መቼም ከእናንተ በቀር ሌላው ዓለም ሁሉ እግዚአብሔርን የካደ ይመስላል፡፡ እንግዲህ ርስዎ እንደሚሉት እግዚአብሔር አምላካችን የኢጣሊያ መንግሥት ቃሉን ሊያፈርስ፣ መሐላውንም ሊሰብር ፈቅዶዋል፡፡

እርስዎ እንደሚሉት የኢትዮጵያ ሰዎች አገራቸውን ለመጠበቅ ቢሰበሰቡ፣ የኢጣሊያ አይሮፕላን ጥርግ አድርጎ ቢያጠፋቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ነው፡፡ ሴቶችንና ሕፃናቱን በቦምብ ሲያጠፋ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ፡፡ ይህን ሁሉ ከአሁን በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ አላገኘንም ነበርና ርስዎ አሁን ስለአስተማሩን ትልቅ ነገር ነው፡፡ ይህን ሁሉ የምታስተምረን ቅድስቲቱ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡

በዱሮ ዘመን ግን ቤተ ክርስቲያን ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል ብላ ታስተምር ነበር፡፡ ቅዱስ ሆይ? የርስዎ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አይደለችም፣ የሁሉም አይደለችም፣ እግዚአብሔር መሐላን ማፍረስ ይወድዳል ብለው ቢያስተምሩን ውሸትዎ ነው ብለን እንመልስለዎታለን፡፡ ርስዎም የዓለም ሁሉ አባት ነኝ ሲሉ ሳሉ የመሶሎኒ ባሪያ ሆነዋል፡፡

በኢጣሊያ ላይ ሥጋዊ "ሳንኪሲዮ" እንደ ተደረገ እንደዚሁም በርስዎ ላይ መንፈሳዊ "ሳንኪስዮ" ማድረግ የግድ ነው፡፡ ርስዎ የሚያመልኩት አምላክ ጣዖት ነው እንጂ አምላክ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያ ርስዎ ለሚያመልኩት አምላክ ጸሎት ልታሳርግ አትችልም፡፡ ሌላው ዓለም እንደዚሁ ወደ ርስዎ አምላክ ሊጸልይ አይችልም፡፡ ርስዎ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰውየው ለመሶሎኒ የሚታዘዙ ሆነዋልና፡፡ ርስዎ መናገር በተገባዎ ጊዜ ዝም አሉ፣ ዝም ማለትም በተገባዎ ጊዜ ተናገሩ፡፡ አሁንም ከሌሎች ጳጳሳት ጋር የሞሶሎኒን ጫማ ስመዋል፡፡ የዓለምን ሰላም የሚያውከውን ወንበዴውን ቢያወግዙት ኖሮ ለቤተ ክርስቲያንዎ እንዴት ያለ ጥቅም በሆነ ነበር፡፡ ምንአልባት ርስዎም በታሠሩ ነበር፡፡ ምንአልባትም እንደ ዱሮ ዘመን ክርስቲያኖች ወደሰማዕትነት ሞት በደረሱ ነበር፡፡ ዓለምም ሁሉ ከእርስዎ ጋር በሆነ ነበር፡፡ ክርስቲያን ቢሆን አረመኔም ቢሆን ሰው ሁሉ ርስዎ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆኑ በተረዳ ነበር፡፡ አሁንም በቅርብ የገና በዓል ነው፡፡ ስግፍ ጦርነት ወርቃቸውን የሰጡ ጳጳሳትም እንግዲህ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን፣ በምድርም ላይ ሰላም ይሁን፣ ለሰውም በጎ ፈቃድ ይሁን ብለው ሊዘምሩ ናቸው፡፡ ይህንም ሲዘምሩ በደረታቸው የወርቅ መስቀል ሳያደርጉ አይቀርም፡፡ ነገር ግን በጀርባቸው ላይ የዕንጨት መስቀል ቢሸከሙ ይሻል ነበር፡፡

ቅዱስ ሆይ? በዓሉን ያስምርልዎ ብዬ ምኞቴን እገልጻለሁ"

ይህ የጭካኔ ድርጊት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል እንደ ትልቅ ገደል ሆኖ ያገለል፡

www.ethiopianorthodox.org



# ክፍል 7

## የሰማዕትነት ዘመን በዘመነ ደርግ

በ1966 ዓ.ም. ከየካቲት ወር ጀምሮ በኢትዮጵያ ሀገራችን የወታደር ዓመፅ ተጀመረ፣ በዚሁ ዓመት ክርስቲያን ባለሥልጣኖች እየታደኑ ይታሠሩ ጀመር፡፡ ከቤተ ክርስቲያናችን ባለሥልጣኖች የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ንዑረ አድ ኤርምያስ ከበደ ሰኔ 22 ቀን 1966 ዓ.ም. ታሠሩ፡፡

በተከታዩ ዓመት በ1967 ዓ.ም. በዘመን መለወጫ ማግሥት መስከረም 2 ቀን ራሱን ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ብሎ የሰየመው የጦርና የፖሊስ ሠራዊት መኰንኖች ስብስብ ንጉሠ ነገሥቱን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ከዙፋናቸው አውርዶ አራተኛ ክፍለ ጦር አሠራቸው፡፡ ደርግም ንጉሡን ከአወረደ በኋላ ርስ በርሱ እየተሿሿመ የመንግሥቱን ሥልጣን ያዘ፡፡ በዚሁ ዓመት ኅዳር 15 ቀን እየአደነ ከአሠራቸው መሳፍንትና መኳንንት፣ ሚኒስትሮችና ከፍተኛ የጦር መኰንኖች ውስጥ 60 ሰዎች ከእሥር ቤት አውጥቶ ገደለ፡፡

በዚሁ ዓመት በየካቲት 25 ቀን የገጠር መሬትን ደርግ ከባለርስቶች ሲቀማ የቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያ የነበረውን የሰሞን መሬትንም አብሮ ቀማ፣ በዚህም ብቻ ሳይበቃው ሐምሌ 19 ቀን 1967 ዓ.ም . የከተማ ቤትን ከባለንብረቶች ሲወርስ ቤተ ክርስቲያናችን በስእለት ገንዘብ ያሠራቻቸውን ታላላቅ ሕንጻዎችና አያሌ ቪላ ቤቶች በጥቅል ወረሰ፡፡ በወቅቱ የደርግ አቀንቃኞች የነበሩት የት/ሚኒስቴር ባለሥልጣኖችም ቤተ ክርስቲያኑዋ በሙዳየ ምፅዋት ያሠራቻቸውን መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት በጥምር ትሰጥባቸው የነበሩትን በአዲስ አበባና በየክፍለ ሀገሩ የነበሩትን 28 ት/ቤቶች በእጀ መናኛ ገብተው ወሰዱዋቸው፡፡ አሁንም አልተመለሱም፣

በ1968 ዓ.ም. መስከረም 17 ቀን የበዓለ መስቀል ዕለት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተቀብተው የተሾሙትን አዲሶቹን ኤጲስ ቆጳሳት ፡-

1. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስን
2. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስን
3. ብፁዕ አቡነ ጳውሎስን

/አሁን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ/ መስከረም 23 ቀን በተሾሙ በሳምንቱ አሥሮ አራተኛ ክፍለ ጦር ወሰዳቸው፡፡ ከእነሱም ጋር የካህናት አስተዳደር መምሪያ ሐላፊ የነበሩትን መጋቤ ካህናት ዘውዴ ወልደ ማርያምንና ሌሎች ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን አሠረ፡፡ በተከታታይም የሰበካ ጉባኤ መምሪያ ሐላፊውን ዶ/ር ሐዲስ የሻነውንና ሌሎች የቤተ ክህነት ሠራተኞችን አሠረ፡፡ የክርስትና ሃይማኖታችን ሕዝባዊ በዓላት ሆነው በዐዋጅ ይከበሩ የነበሩትን የማዕዶትን፣ የቃና ዘገሊላንና የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰታ በዓላትን ሻረ፡፡

በዚሁ ዓመት የካቲት 9 ቀን ቅዱስ ፓትርያርኩን አቡነ ቴዎፍሎስን ከመንበራቸው አውርዶ ወደ እሥር ቤት አስገባቸው። ለማረፊያ የተመረጠላቸው በታላቁ ቤተ መንግሥት በዙፋን አዳራሽ ሥር የሚገኝ ለወይን ጠጅ ማቀዝቀዣ የተዘጋጀው ዋሻ ነው። ክረምት ከበጋ እንደ በረዶ ይቀዘቅዛል። አካላቸው በብርድ ተኮማትሮዋል። በሙጭት እንፋሎት ደምስሮቻቸው ተግተርትረዋል። መንፈሳቸው ተጨንቋል። በቁጥጥር ሥር የዋሉት ሁሉ ንጹሕ አየር ለማግኘት በፀሐይ አካላቸውን ለማሞቅ፣ የተሳሰሩ እግሮቻቸውን ለማፍታታት በሽቦ በታጠረ 17 ሜትር በ25 ሜትር በሆነ ጠባብ ክልል ውስጥ ሲንከላወሱ ቆዩ።

በመጋቢት 3 ቀን 1968 ዓ.ም. ከእኩለ ቀን በኋላ ታላቁ መንፈሳዊ አባት ሁለት እጆቻቸው በአንድ ላይ በሰንሰለት ታስረው እየተገፈተሩ ያለመጫማያ በባዶ እግራቸው ሲሔዱ የተመለከቱትና በአሰቡት ክው ብለው የቀሩት እሥረኞች ሲጫወቱት ነገሩ ይዘገንናል።

የአደፈ ሹሮአማ ቀሚስ እንደለበሱ ከቀኝም ከግራም ከኋላም ሳንጃ የተሰካበት ጠበንጃ ተደግኖባቸው ወደዚያች የፖሊቲካ እስረኞች መቀየጃ ቅጥር ግቢ ሲገቡ መንፈሳዊ አባቱ "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" በማለት ግፍ ለሚፈጽሙባቸው የሚጸልዩ እንጂ የተበሳጨና የተሸበሩ አይመስሉም ነበር።

እስረኛው ከድንጋጤው ገና ሳይላቀቅ ምን እንደሚልና እንደሚያደርግ አሰላስሎ ሳይጨርስ ከቆመበት ሳይላወስ ነበር ወደ አንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ አስገብተው የቁሰፋባቸውና እግራቸውን በእግረ ሙቅ፣ እጃቸውን በሰንሰለት ጠፍረው ያሰሩዋቸው። መንፈሳዊው አባት የታሠሩባት ክፍል በማግሥቱ የአሳሪዎች ምልልስ ታየባት። ሹሞች በመፈራረቅ ጉቦኝዋት። ይህ ሁሉ ጋጋታ የተከሠተው በአንድ ክፍል ውስጥ እግር እጃቸው ከአልጋ እግር ጋር የታሠረው መንፈሳዊ አባት "ምግብ አልበላም" ብለው በመወሰናቸው ነበር፤ እኒያ ታላቅ አባት በዚያች መስኮት በሌላት ጠባብ ክፍል ምግብ ብቻ ሳይሆን ንጹሕ አየርም ሳያገኙ ሰባት ቀን ጠማቸውን ውሰው አደሩ።

የደረቀ ጉሮሮአቸውን በውሀ እየተጐመጠመጡ በመትፋት ብቻ ምግብ ሳይበሉ ውሀ ሳይጠጡ መጸሙን ቀጠሉ፤ ጠንካራነታቸውን አስመሰከሩ።

ከቅዱስ ፓትርያርኩ ቀደም ብሎ ለአገራቸው ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱት ክርስቲያን ባለሥልጣኖች እየተሰቀሙ ከመታሠራቸውና ከመገደላቸውም በላይ ጳጉሜን 3 ቀን 1966 ዓ.ም. ለአገር አንድነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት አዛውንት ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገ/ማርያም በሚንስትር ማዕርግ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩትን አልጋ ተሸክመው ወደ እሥር ቤት እንዲሔዱ በማድረግ ክብረ ኅሊናቸውን አቀስለዋል። መስከረም 15 ቀን 1967 ዓ.ም. የአክሱሙ አስተዳዳሪ ንቡረ እድ ገ/ሥላሴ ፀሐዩም ሲሾሙ ከንጉሡ የተሸለሙት የወርቅ ጫማ፣ ሙካሽ ካባ ላንቃና ቀሚስ በቤታቸው መገኘቱ ወንጀል ሆኖባቸው በሬዲዮ ስማቸው እንዲጠፋ ከተደረገ በኋላ ታስረዋል።

እንዲሁም የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ሚያዝያ 10 ቀን 1969 ዓ.ም. ታስረዋል። ነገር ከሥሩ፣ ውሀ ከጥሩ እንደሚባለው ስለ ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ መከራ መስቀል ስንጽፍ የነገሩን ሥር መሠረት ማስረዳት ያስፈልጋል።

ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስ መቻል፣ መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት፣ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ለመቀራረብና ለክርስቲያናዊ ተግባርና ልማት፣ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጽናት ይጥሩ የነበሩትን እኒህን መንፈሳዊ አባት ደርግ በየካቲት 9 ቀን 1968 ዓ.ም. ከመንበረ ፓትርያርክ በጨለማ አፍኖ ወሰዳቸው። በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ በአንድ ክፍል ውስጥ ብቻቸውን አሠራቸው። " ሲጠበቅ የቆየው ፍርድ" በሚል ርእስ መግለጫ አወጣባቸው። በዚህ መግለጫ የተዘረዘረው ውንጀላ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም. "ሰማዕቱ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ" በሚል ርእስ ቤተ ክርስቲያን በአወጣችው መጽሔት አንድ በአንድ ተስተባብሎዋል። በአንጻሩም ፓትርያርኩን ከመንበራቸው ለማውረድ ያበቁት ምክንያቶች የፓትርያርኩ አቋም ከደርግ ፖሊሲ ጋር የማይስማማ መሆኑና የቤተ ክርስቲያንንም መብት ለማስከበር ለወታደራዊ መንግሥት የጻፋዋቸው ደብዳቤዎች ጎይለ ቃል እንደነበሩ ማስረጃ በመጥቀስ በዚሁ መጽሔት ተገልጹዋል።[19]

19 የአስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግሥት ወይም ከአበራ ጀንበሬ ገፅ 145

20 የአስር ቤቱ አበሳ ከአበራ ጀንበሬ ገጽ 149



እኒህ አባት በእሥር ላይ በነበሩበት ጊዜ ከዕለታት አንድ ቀን ልብስ ከቤት እንዲላክላቸው ለቤተሰብ በጻፉት ደብዳቤ ላይ "አባ ቴዎፍሎስ" ብለው በመፈረማቸው "ስምህ አባ መልእክቱ" ስለሆነ አባ መልእክቱ ብለህ ፈርም" ሲል ሻምበል ስሜ ወልደ ጊዮርጊስ የተባለው የዘብ ሐላፊ ከዛቻ ጋር ሲጠይቃቸው "እኔ አሁን አባ ቴዎፍሎስ እንጂ አባ መልእክቱ አይደለሁም፣ አባ መልእክቱ ዱሮ ጳጳስ ከመሆኔ በፊት እጠራበት የነበረው የዓለም ስሜ ቢሆንም የፈለግኸውን ብታደርግም አባ መልእክቱ ብዬ አልፈርምም" በማለት በድፍረት መለሱለት።

ከዚህ በኋላ ፓትርያርክ ሆነው በተሾመበት ጊዜ የቆጵሮስ ፕሬዝዳንት ብፁዕ አባ መቃርዮስ የሸለሙዋቸውን ከወርቅ የተሠራ የእጅ መስቀል ቀምቶ ወሰደባቸው። በሚተኙበት ትንሽ ክፍል ውስጥ ሰቅለውት የነበረውንም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥዕል አውርዶ ወሰደው።[20]

ሐምሌ 3ና 5 ቀን እንዲሁም ሐምሌ 7 ቀን 71 ዓ.ም. 5 ያህል ከቅዱስነታቸው ጋር አብረው የታሠሩ ክርስቲያን የመንግሥት ባለሥልጣናት ከእስር ቤቱ ከተወሰዱ በኋላ በዚሁ በመጨረሻው ሐምሌ 7 ቀን ቀዳሚት ማታ እኒሁ ታላቅ አባት ተጠሩ፣ ከርሳቸው ጋር ከእስር ቤቱ በተጠሩት በሦስት መንፈሳውያን ልጆቻቸው ማለትም በአቶ ዮሐንስ ኪዳነ ማርያም፣ በደጅ አዝማች ካሣ ወ/ማርያምና በብ/ጄኔራል ሳሙኤል በየነ ታጅበው ጥቁር ቀሚሳቸውን ለብሰው ካባቸውን ደርበው፣ አክሊል እንደተቀዳጁ፣ አርዌ ብርት እንደያዙ፣ ነጠላ ጫማ እንደተጫሙ ቀሪዎቹን በመስቀላቸው በመባረክ መርቀው በግርማ ወጡ፣ ወደ ሞት ሲሔዱ ጽዋዐ ሰማዕታትን ለመቀበልና ሕይወታቸውን ለቆሙለት ዓላማ አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጁ እንጂ ምንም ዓይነት ሥጋት የሚታይባቸው አልነበሩም።

የቀሪዎቹ እስረኞች ጭንቀት ግን በዚያች ቀውጢ ሰዓት በእጅጉ ጨመረ፣ የመኖር ተስፋቸውም አከተመ። ጭንቀቱን በጣም የከበደ የአደረገው እያሰለሱ ስለሚወስዱ በነጋ በጠባ ቀጣዩ የእኔ ተራ ይሆን የሚለው ቀርጥን ያለማወቅ ነበር። ጭንቀቱን ሲያራዝሙም እሑድንና ሰኞን ምንም እስረኛ ሳይጠሩ ውሰውና አድረው ማክሰኞ ሐምሌ 10 ቀን 1971 ዓ.ም. ለምሽት መስተንግዶ ከመኪንንቱ አንዱን እስረኛ ጠሩ። ይህ በሁለት ቀን ልዩነት የተደረገ ጥሪ የሥጋቱን ትኩሳት በመለኪያው ላይ እንደ ዓይን ጥቅሻ ወደ ሰማይ ሰቀለው። ትካዜው ቀጠለ፣ መራበሹ ተባባሰ።

ፓትርያርኩንና ሌሎቹን ከሐምሌ 3-7 ቀን የወሰዱዋቸውን እስረኞች የት እንደአደረሳችኋቸው ግለጡልን በማለት ነበር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ፣ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፣ የሰብአዊ መብት አስከባሪዎች ድርጅቶች ደጋግመው የጠየቁት። ደርግ ግን የገዘሆን ጆሮ ይስጠኝ ብሎ ዝም ብሎ ነበር።

ይህም አባቶች፣ ዘመዶች በሞቱባቸው ቤተሰቦች ከፍተኛ ኀዘንን አሳደረ፣ ከፊሎቹ ያዘኑት የቤተሰባቸው አስተዳዳሪ የነበሩትን አባወራዎቻቸውን ደርግ በግፍ ስለገደለባቸው ሲሆን ከፊሎቹ ደግሞ የት እንደ አደረሱዋቸው ስንኳ ሳያውቁ በመቅረታቸው ነበር። የአጡዋቸውን መልሶ የማግኘት ተስፋ ባይኖራቸውም አዕማቸው የወደቀበትን ለማወቅ ከተጣለበት አውጥቶ በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ለመቅበር ባለመቻላቸው ኀዘናቸው ዕጥፍ ድርብ ሆኖ ነበር።

በይፋ ተላቅሶ ዕርም የማውጣት መብት ስንኳ ስለአልነበራቸው ኀዘኑ ከአንጀት የማይወጣ ሆኖባቸዋል። በደርግ በግፍ የተገደሉት የኢትዮጵያ ሰማዕታት አዕም የተጣለበትን ስፍራ በውል ማወቅ ሳይቻል ብርቱ ምሥጢር ሆኖ ለዘመናት ቆይቷል።

www.ethiopianorthodox.org

የአንዳንዶቹ ሰማዕታት ሬሳ በቤተሰቦቻቸው ክትትልና ፍለጋ በጉድፍ መጣያ ላይ እየተጣለ ትኩሱን ተገኝቷል። ለምሳሌ የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ የመጀመሪያው አዘጋጅ የነበሩት ብላታ ደምሴ ወርቅ አገኘሁ ከመኖሪያ ቤታቸው ታፍነው ከተወሰዱ በኋላ በቤተሰባቸው ፍለጋና ክትትል በሱማሌ ተራ ቆሻሻ መጣያ ላይ ተገድለው ተጥለው ሬሳቸው ተገኝቶ ተቀብረዋል።

ብዙ የክርስቲያን ልጆች የሆኑ ወጣቶችም ከወላጆቻቸው ጉያ እየተጐተቱ ተወስደው በእየአውራጃዉ ጉዳናውና በየሸለቆው እየተገደሉ ተጥለው የግማሾቹ ሬሳቸው እየተሸጠ ሲቀበሩ፣ የግማሾቹ ሬሳ የት እንደደረሰ ሳይታወቅ ቀርቷል።

ሆኖም ጊዜው ሲፈቅድ የተሰወረው ተገልጦዋል፣ የተደበቀው ይፋ ወጥቶዋል።ለሰማዕታቱ አዕም ፍለጋ ሁኔታዎች ተመቻቹ፣ ጠቋሚ ተገኘ።

በ1967 ዓ.ም. በጎዳር 14 ቀን ምሽት በአዲስ አበባ ወጎኒ ቤት ቅጥር ግቢ በጥይት ተደብድበው የተገደሉትን የቀድሞ ባለሥልጣኖች /ክርስቲያኖች/ አጃሞች በወጎኒ ቤቱ እስረኞች የተቀበሩበት ረግረግ ስፍራ በጠቋሚ ታወቀ። ጉድጓዱ ሲቆፈር የሚጎቹ አዕም አንዱ በሌላው ላይ እንደተደራረበ ተገኘ። ቁፋሮው በጥንቃቄ የተከናወነ ቢሆንም ኖራ አፍስሰውባቸው ስለነበር ከዐሥራ ሰባት ዓመታት በኋላ አፅሙ ሲወጣ አንደኛውን ከሌላው ለመለየት የሚያስችል ምልክት ለማግኘት አልተቻለም።

በየካቲት 9 ቀን 1984 ዓ.ም. ነበር የእነዚህ ሰማዕታት አዕም ከተጣለበት አልባሌ ስፍራ ወጥቶ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ገዳም ለጊዜው ከቁየ በኋላ በሐምሌ 20 ቀን 1984 ዓ.ም. በአፀደ ቤተ ክርስቲያኑ በተዘጋጀለት መካነ መቃብር በክብር ያረፈው። እንዲሁም ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሁለት ጠቋሚዎች ያሳዩት ስፍራ ትክክል ሳይመጣ ቀርቶ በሦስተኛ ሰው ጥቆማ መሬቱ ሲቆፈር ምንም የሳጥን ቅሬት ሳይኖር የተፈለገው አዕም ተገኘ። በራስ ቅልና በፊት ቅርፅ እንደዚሁም በእግር ቅልጥም የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው ተብሎ የታመነ አዕም በታላቁ ቤተ መንግሥት ከመንግሥቱ ኃይል ማርያም ጽ/ቤት ጋር በተያየዘ በልዩ ረዳቱ መሥሪያ ክፍል ሥር ከፎቁ የሽንት ፍሳሽ ከሚወርድበት ስፍራ በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ተቁፍሮ ወጣ። ከወጣም በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወት ሳሉ በእሠሩት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኘው መካነ መቃብር በክብር እስከሚያርፍ ድረስ አፅሙ ዕለቱኑ የካቲት 9 ቀን 1984 ዓ.ም. በታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው እንዲቁይ ተደረገ።

ሌላው ተዳፍኖ የቁየው ምሥጢር የፓትርያርኩ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና በ1971 ዓ.ም. በሐምሌ ወር አብረዋቸው የተወሰዱት መገደላቸው በይፋ ያልተገለጠው ስምንት እስረኞች ጉዳይ ነበር። የእነዚህን ሰዎች መገደል ወይንም በሕይወት መኖር ለማወቅ ቤተሰቦቻቸው፣ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የሰብአዊ መብት አስከባሪዎች ድርጅቶች ብዙ ዓመታት ወትውተዋል። የተዳፈነ ምሥጢር ነበርና ሊገልጽላቸው የደፈረ አልነበረም።

ከዐሥራ ሦስት ዓመታት በኋላ ነበር ስለአሟሟታቸው ሁኔታ አቶ ቀነዓ አብሳ ፍንጭ የሰጡትና ድርጊቱ ሲፈጸም የነበረ ሌላ ሰውም የመቃብሩን ስፍራ ያመለከተው። የዐይን ምስክሮቹ እንደገለጡት 33 ሰዎች ነበሩ ደርግ ለገዳይነት በአሠለጠናቸው ኮማንዶዎች በተለያየ ጊዜ እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ተገድለው በልዑል ራስ ዐሥራት ካሣ ግቢ ውስጥ የተጣሉት።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና ሌሎቹ እስረኞች ወደ ልዑል መኖሪያ ቤት እየተወሰዱ በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ በሰዋራ ስፍራ የተደበቁ ኮማንዶች በገመድ እያነቁ እንደገደሉዋቸውና ሕይወታቸው ሲያልፍ ሌሎች ሬሳቸውን ወስደው በአጥሩ ካብ ሥር በዕርድ መልክ በተቁፈረው ጉድጓድ ውስጥ ወርውረው እንደጣሉዋቸውና ቀባሪዎች አፈር እንደአለበሱዋቸው ነበር በዐይን ምስክር የተረጋገጠው።

አዕም ለማውጣት በዚያ ስፍራ ቁፋሮ ተጀምሮ ከአራት ቀኖች ያላለለ ማፈላለግ በኋላ ነበር የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው ፓትርያርክ አዕም በሚያዝያ 23 ቀን 1984 ዓ.ም. ተቁፍሮ ወጥቶ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው እንዲያርፍ የተደረገው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፲ (2000) ዓ.ም

በሐምሌ 3 ቀን 1984 ዓ.ም. ደግሞ አዕሙ ወደ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ ጸሎተ ፍትሐት ሲደረስበት አደረ።

በማግሥቱ ከውጭ አገር ለበዓሉ የመጡ የአብያተ ክርስቲያናት ልዑካን፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የልዩ ልዩ ሃይማኖት ማኅበሮች መሪዎችና ካህናት ብዙ ምእመናን በተገኙበት በዐውደ ምሕረቱ በተደረገው ልዩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ነበር የቅዱስነታቸው ትሩፋትና ገድል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተወካይ በብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ንግግር ከተገለጸ በኋላ "ቴዎፍሎስ ቅዱስ ሰማዕት" ተብለው እንዲጠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ መወሰኑ የታወጀውና በሥነ ሥርዐቱ ላይ የተገኙት ሁሉ "ይደልዎ" በማለት መንፈሳዊ አዋጁን የተቀበሉት።

የቅዱስነታቸው አዕም ዕለቱኑ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም. በክብር ያረፈው በጉሩ ሰፈር ራሳቸው በአሳነፁት በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአሠሩት መካነ መቃብር ነው።

# ክፍል 8

## ሰማዕታተ ኢትዮጵያ

## በሃያኛው መቶ ዓመት ግራኝ (አክራሪ እስላም)

በ1983 ዓ.ም. በግንቦት 20 ቀን የተፈጸመውን የመንግሥት ለውጥና በለውጡ ምክንያት የተፈጠረውን ግርግር መጠቀሚያ በማድረግ በሐረርጌና በአርሲ ያለው አክራሪ እስላም ከ1984-85 ዓ.ም. ድረስ ቁጥራቸው በደንብ ያልታወቀ አያሌ ካህናትንና ምእመናንን በአርባጉጉ አውራጃና በምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ በአሰቦት ገዳምና በአካባቢው ፈጅቷል። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንም አቃጥሎዋል።

1ኛ/ በአርሲ ሀገረ ስብከት በአርባጉጉ አውራጃ ከ670 /ስድስት መቶ ሰባ/ በላይ ካህናትና ክርስቲያኖች ታርደዋል፣ ግማሾቹ በእሳት ተቃጥለዋል፣ ግማሾቹ ደግሞ እየተቁራጉ ወደ ገደል ተወርውረዋል። እንዲሁም ቁጥራቸው ያልታወቀ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በከባድ መሣሪያ ተደብድበው ተቃጥለዋል፣ ቅርሳቸውም ተዘርፎዋል። 43,000/አርባ ሦስት ሺ/ ምእመናንም ተሰድደዋል።

2ኛ/ በምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት በተለይም በአሰቦት /ደብረ ወገግ/ አቡነ ሳሙኤል ገዳምና በአካባቢው ያሉ መነኮሳትና ምእመናን በብዛት አልቀዋል፣ የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናትም ተቃጥለዋል።

3ኛ/ በ1998 ዓ.ም. ጎዳር 8 እና 9 ቀን በአርሲ ሀገረ ስብከት በኩፋሌ ወረዳ በቁሬ ከተማና በአንሻ ሰበካ 6 ምእመናን ተገድለዋል፣ ከመቶ በላይ የሆኑ ክርስቲያኖች ቤታቸው ተቃጥሎ ተሰድደዋል፣ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ፈቃድና ትእዛዝ በ1916 ዓ.ም. በታላቁ ካህን በመምሬ ዳኜ ርዳቸው /በኋላ እባ ወልደ ጻድቅ/ ጽላቷ ከአዲስ አበባ ሔዶ በአንሻ ሰበካ የተተከለችው የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቃጥላለች።

ይቺ ቤተ ክርስቲያን በመቃጠሉዋ እመቤታችን ብዙ ተአምራት እንደአሳየች ከሞትና ከስደት የተረፉት ምእመናን ይናገራሉ። ቤተ ክርስቲያኑዋን ለማቃጠል በመጀመሪያ እሳት የለኮሱው አስላም አብዶ ሥጋውን እየቦጨቀ በመብላት ላይ እንደአለ ይነገራል፣ ከዚህም ሌላ ተባባሪዎች ሆነው ያቃጠሉዋት አስላሞች በአቃጠሉበት ዕለት በአየሳምንቱ በሞት እየተጠሩ ከዚህ ዓለም መለየታቸው ይሰማል።

www.ethiopianorthodox.org

4ኛ/ በ1999 ዓ.ም. መስከረም 16 ና ጥቅምት 5 ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዓመታዊ ክብረ በዓል የሚደረግበትን በጅማ አጋሮ አካባቢ የሚገኘውን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ቤተ ክርስቲያን ከብበው ማሕሌት በመቆም ላይ ያሉትን ካህናትና ምእመናን የቤተ ክርስቲያኑን መዝጊያ አክራሪዎች እስላሞች ሰብረው ገብተው ቤተ ክርስቲያኑን እሳት በመለኮስ በውስጡ ካሉት ካህናትና ምእምናን ጋር አቃጥለውታል። በቤተ ክርስቲያኑ በዐውደ ምሕረት ቆመው የሚያስቀድሱትንም በሰይፍና በገጀራ አንገታቸውን እየቀሉ ጭካኔና ግፍ በተመላ አገዳደል ገድለዋቸዋል። ግድያው የተፈጸመው በዚህ ብቻ ሳይሆን በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በዴዴሳ በጅማ ሀገረ ስብከት በማናቶባና በሌሎች ወረዳዎች ጭምር ነው። በዚህም ቦታ የተገደሉት ምእመናን 8 ሲሆኑ የተቃጠሉት 3 አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። የተቃጠሉት ቤቶችም ከ800 በላይ ናቸው። በአጠቃላይ በ98 እና በ99 ዓ.ም በወለጋ፣ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በአርሲ፣ በደቡብ ወሎ 12 አብያተ ክርስቲያናት በእስላሞች ተቃጥለዋል፡

እነዚህ አክራሪ እስላሞች ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለውጠው መስቀላቸውን አውልቀው እንዲሰልሙ በማስገደድና ይህን በማይፈጽሙት ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ግድያ በመፈጸም፣ ከሞት የተረፉትም ከቀያቸው እንዲሰደዱ አድርገዋል። በማስገደድም ብዙ ሙጥር ያላቸውን ክርስቲያኖች አስልመዋል። ይህንኑ መርዶ /ቤና/ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥቅምት 4 ቀን 99 ዓ.ም. ዕትም፣ ሪፖርተር ጋዜጣ መስከረም 28ና ጥቅምት 6 ቀን 99 ዓ.ም. ዕትም፣ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ጥቅምት ወር 99 ዓ.ም. ዕትም ኖኅተ ጥበብ ጋዜጣ በግበውታል።

በዚህም ነቢዩ ዳዊት "እስመ በእንቲአሁ ይቀትሉነ ኵሎ አሚረ፣ ወከነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ፣ በእሱ ምክንያት ሁልጊዜ ይገድሉናል፣ እንደሚታረዱ በጎችም ሆንን" ብሎ የተናገረው፣ በቅዳሴ ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስም "ሰማዕታት ከዐዉ ደሞሙ በእንቲአሁ፡- ሰማዕታት ስለርሱ ደማቸውን አፈሰሱ" ተብሎ የተጻፈው ተፈጸመ። (መዝ.43፣22)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



# ምዕራፍ 12

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት

የክርስትናው ዓለም በባህል፣ በቋንቋ፣ በአህጉር በተለያዩ ሕዝበ ክርስቲያን አንድነት ላይ የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙበት ሰፊ ዓለም ነው። በመሆኑም በዚህ ሰፊ ዓለም ላይ ተራርቀው በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የእርስ በእርስ ትውውቅና ትብብር ሊኖር የሚችለው ዓለም አቀፍ ግንኙነት ማድረግ ሲቻል ነው። የውጭ ግንኙነት የሚባለውም ይህ ዓይነቱ ዓለም-አቀፍ ግንኙነት ነው። በአሁኑ ጊዜ የዓለም ሕዝብ በየብስ፣ በባሕርና በአየር በሚደረግ ጉዞ እርስ በእርሱ እየተገናኘ ስለሆነ በዚያው አንፃር በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚደረገውም የውጭ ግንኙነት በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም በላቀ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ነው። በዚህም ግንኙነት አማካይነት የሚደረገው የእርስ በእርስ ተራድኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

ከዘመነ ክርስትና በፊትም በሕገ ኦሪት አምልኮተ እግዚአብሔርን በሚፈጽሙ ሕዝበ እግዚአብሔር መካከል በኢየሩሳሌም ማዕከልነት ዓለም-አቀፍ ግንኙነት ይካሄድ ነበር። ኢትዮጵያም ከክርስቶስ ልደት በፊት ሕገ ኦሪትን ተቀብሎ አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም የበቃ ሕዝብ ሀገር ስለሆነች ከኢየሩሳሌም ጋር ጥብቅ ግንኙነት ነበራት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል በቀጥታ የተሸጋገረ ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት ታሪክ ለመጻፍ ከዘመነ ብሉይ መነሳት አስፈላጊ ይሆናል።

## ክፍል 1

### የውጭ ግንኙነት ቅድመ ክርስትና

ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት በፊትም የራስዋ የሆነ ቤተ ክህነት ነበራት። ያም ቤተ ክህነት ከንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት በኋላ የተመሠረተ ተቋም ነበር። ይህም ጉብኝት በመጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ታሪክ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነበር። ንግሥተ ሳባ የሴምና የካም እምነት ተከታይ ሕዝብ ንግሥት ስለነበረች በጊዜዋ በነበረው የውጭ ግንኙነት አማካይነት ሌላዋ የነገደ ሴም ሀገር የሆነችውን የኢየሩሳሌምን ዝና ለመስማትና ለማወቅ የሀገር ርቀት አላገዳትም። በጅሮዋ የሰማችውን በዓይኗ ለማየት ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺህ ዓመት አካባቢ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገችው ጉዞና ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር ያደረገችው ውይይት መጽሐፍ ቅዱሳዊት ሀገር ኢትዮጵያን የብሉይ ኪዳን ሕዝብ ሀገር ለመሆን ያስቻለ ፍሬያማ የውጭ ግንኙነት እንደነበር በውጤቱ ማረጋገጥ ይቻላል። መጽሐፍ ቅዱሳዊት ኢትዮጵያ፡

1. ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት ዘመን የተሸጋገረችው
2. ሌዋውያን ካህናት መጻሕፍተ ኦሪትንና ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ የመጡትና ከዚያም አምልኮተ እግዚአብሔርን በኦሪቱ ሕግ መሠረት ለመፈጸም የተቻለው፣
3. ሕዝቧ ሥርዓተ ግዝረትን በመፈጸም የበረከተ አብርሃም ተሳታፊ ለመሆን የበቃውና በዚህም ሀገሪቱ የኢየሩሳሌም አቻ ሀገር ለመሆን የቻለችው ከንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት በኋላ እያደገ በመጣው የውጭ ግንኙነት ምክንያት እንደነበር የሀገሪቱ ታሪክ ያረጋግጣል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ሕዝብና መሪዎች ጻድቃነት (1ነገሥ.19፡9)፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገሪቱን ማዕድን ወደር-የለሽነት (ኢዮ.28፡19)፣ ግሪካዊው ፈላስፋ ሆሜር የሀገሪቱን ሕዝብ ውበት በማድነቅ መጻፋቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊት ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በውጪ ዓለም ዘንድ ለመታወቅ የሚያስችል ዓለም አቀፍ ግንኙነት የነበራት ሀገር መሆንዋን የሚያመለክት ነው። ከዚህ ዝክረ ታሪክ መረዳት የሚቻለው ሀገሪቱ በጊዜው ታደርገው በነበረው ሃይማኖተ ነክ ዓለም-አቀፍ ግንኙነት በንግዱና በፖለቲካው ዘርፍም የቱን ያህል ታዋቂነትን አንደአገኘች ነው። ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግማ የተጠቀሰች ሀገር መሆንዋም በዓለም ላይ መጽሐፍ ቅዱስን በሚቀበል ሕዝብ ዘንድ ዝናዋ የታወቀ ሀገር ለመሆን እንደበቃች ይታመናል። የንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም [illegible] የውጭ ግንኙነት የመጀመሪያ እንጂ የመጨረሻ አልነበረም።

www.ethiopianorthodox.org

በመሆኑም በዘመነ ብሉይ በተደረገው የንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳንን እምነት በመቀበል ሀገረ እግዚአብሔር ለመሆን እንደበቃች ሁሉ በኋላም በንግሥት ሕንደኬ ክፍተኛ ባለሥልጣን የኢየሩሳሌም ጉዞ ውጤት ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ የክርስትና እምነት ተቀባይ ሀገር ለመሆን በቅታለች፡፡

# ክፍል 2

## የውጭ ግንኙነት በዘመነ ክርስትና (ከመጀመሪያው እስከ ሐያኛው መቶ ክፍለ ዘመን)

### 2. ሀ. የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ የኢየሩሳሌም ጉዞና የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ መግባት፡

በኢየሩሳሌምና ከኢየሩሳሌም ውጭ የሚኖር የብሉይ ኪዳንን እምነት የተቀበለ ወንድ ልጅ ሁሉ በዓለ ናዕትን /የቂጣ በዓልን/፣ በዓለ ሠዊትን /የእሸት በዓልን/፣ በዓለ መጸለትን /የዳስ በዓልን/ ማክበር የእምነቱ ግዴታው ነበር፡፡ በዚህ ግዴታ መሠረት ሕገ ኦሪትን ከተቀበሉት ኢትዮጵያውያን መካከልም እሥራኤላውያን ከፋሲካ በዓል በኋላ ሰባት ሰባቱ ቋጥረው በሚያከብሩት "በዓለ ሠዊት" ላይ ተገኝተው የበዓሉ ተሳታፊ ለመሆን ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዙ ነበር፡፡ /ሶፎንያስ 3.10/፡፡ በዚህ ምክንያት በዓሉ በ34 ዓ.ም. በተከበረበት ጊዜ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በየሀገሩ ልሳን ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ በመደነቅ ከሰሙት ምእመናን መካከል ኢትዮጵያውያውንም እንደነበሩ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዓለ ሐምሳን አስመልክቶ በተናገረው ቃለ ስብከት መስክሯል፡፡ /ድርሳን በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሐዋ.ሥራ 2፡1-13/፡፡

የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ ባለሥልጣን የነበረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሕገ ኦሪቱ በሚያዝዘው መሠረት በ34 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ በዓሉን አክብሮ ሲመለስ በጋዛ መንገድ ከወንጌላዊው ፊልጶስ ጋር ተገናኘ፡፡ ጃንደረባው በሠረገላው ላይ ተቀምጦ የኢሳይያስን መጽሐፍ /ምዕራፍ ሐምሳ ሦስትን/ እያነበበ ሲሄድ እሱንና ወንጌላዊው ፊልጶስን መንፈስ ቅዱስ አገናኛቸው፡፡ የሚያነብበው ቃል ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀል የተነገረ ትንቢት መሆኑንም ተረጐመለት፡፡ በመቀጠልም ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ መሆኑንና /ዮሐ.1፡29/ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዓለምን ማዳኑን ተንትኖ ሰበከለት፡፡

በዚህ ዓይነት ፊልጶስ እያስተማረ፣ ጃንደረባው እየተማረ ውሃ ከአለበት ቦታ በደረሱ ጊዜ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተማረውን ትምህርት ከልብ ተረድቶ ስለአመነ "እነሆ ውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?" አለው፡፡

ፊልጶስም "በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዷል" አለው፡፡ እሱም "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ሠረገላው እንዲቆም አዘዘ፡፡ ቅዱስ ፊልጶስና ጃንደረባው አብረው ወደ ውኃው ወረዱ፡፡ ቅዱስ ፊልጶስ ጃንደረባውን አጠመቀው፡፡ ከውኃው ከወጣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ነጠቀው /ሰወረው/፡፡ ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ግን ደስ ብሎት ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡ የሐዋ.ሥራ 8፡26-40፡፡ ጃንደረባው የክርስትና እምነትን ተቀብሎ ወደ ሀገሩ እንደተመለሰም የክርስትና እምነትንና ሥርዓተ ጥምቀትን ለሀገሩ ሕዝቦች በመግለጹ የክርስትና እምነት ዜና በብዙዎች ጆሮ እንዲደርስና እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ታሪክ የሚጀምረው ከዚህ ጊዜ ነው፡፡ ይህንም እንደ አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች አረጋግጠዋል፡፡ /አውሳብዮስ ዘቂሣርያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ ቁጥር 1፡፡/ ሮማዊው ጆሮምም "መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ " በሚለው ጽሑፉ የጃንደረባውን ታሪክ በመተረክ አድናቆቱን ገልጧል፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞና ከዚያም በወንጌላዊው ፊልጶስ ስብከት የክርስትና እምነትን ተቀብሎ ወደ ሀገሩ መመለሱ ኢትዮጵያ የክርስትና ዜናን ለመስማትና ለመቀበል እንድትችል ያደረገ ፍሬያማ የውጭ ግንኙነት በመሆኑ ይህ የውጭ ግንኙነት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ይዞ ይገኛል፡፡



### 2. ለ. በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከእስክንድርያ ጋር የተደረገ የውጭ ግንኙነትና የኢትዮጵያ መንበረ ጵጵስና መመሥረት

ከዚህ በላይ እንደተተረከው የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን /34/ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያኒቱ በመንበረ ጵጵስና ደረጃ ተደራጅታ ተልዕዋን ለማከናወን የበቃችው ግን በኋላ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ የመጀመሪያው ጳጳስ ሁኖ የተሾመውም ጢሮሳዊው ፍሬምናጦስ ሲሆን ታሪኩም እንደሚከተለው ነው፡፡

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ኢዛና እና ሳይዛና የተባሉ ሁለት ወንድማማቾች በአንድነት ነግሠው ሀገሩን ይመሩ ነበር፡፡ የጢሮስ ከተማ ተወላጅ የነበረው መሮፕዮስ ዘመዱ የሆነውን ፍሬምናጦስንና ወንድሙን ኤዲስዮስን ወይም ሲድራኮስን አስከትሎ ሕንድን ለመጐብኘት በአዱሊስ ወደብ በኩል ሲያልፍ በድንገት ሽፍቶች አደጋ ጣሉባቸውና ፈላስፋው መሮፕዮስ ተገደለ፡፡ ፍሬምናጦስና ኤዲስዮስ ግን ከአደጋው ድነው ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት ተወሰዱ፡፡ በቤተ መንግሥቱ እንክብካቤ እየተደረገላቸው የሀገሩን ቋንቋና ባህል እያጠኑ ብዙ ጊዜ ኖሩ፡፡ ከዚያም በተለያየ የሥራ ዘርፍ ተመድበው ሲሠሩ የዘመነ ንጉሥ ታዜር ሞተ፡፡ ንጉሡ ሲሞት ሁለቱ ጢሮሳውያን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ቢፈልጉ ሊሄዱ እንደሚችሉ ጉጉዜ ሰጥቶ ነበር፡፡ ሆኖም የመንግሥቱን ኃላፊነት የተረከበችው ንግሥት አሕየዋ /ሶፊያ/ ልጅዋ ለሥልጣነ መንግሥት እስኪደርስ ድረስ እስዋን እየረዱ እንዲቆዩ ለመነቻቸው፡፡ ፍሬምናጦስ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተገኘ በመሆኑ የራሱን ዕውቀት በመጨመር በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተሰማው የክርስትና እምነት ዜና የበለጠ እንዲጠናከር በማድረግ የሚፈጽመው ተልዕኮ ቀላል አልነበረም፡፡ ከዚህም ጋር በየጊዜው እየተገናኘ ስለ ክርስትና እምነትና ሥርዓት ያነጋግረው ነበር፡፡ የክርስትና ዜና በሀገሪቱ ተስፋፍቶ መቆየቱን በመመልከት የእምነቱን ሕግ በምልዓት ለመፈጸም የሚቻለው ክህነትና ቁርባን ሲኖር መሆኑን ለንጉሡና ለሲቀ ካህናቱ በማስረዳት ይህ እንዲሟላ ግፊት ያደርግም ነበር፡፡ እነሱም ፍሬምናጦስን የእኛን ቋንቋና ባህል፣ የእነሱንም ቋንቋና ባህል የሚያውቅ ከአንተ በቀር ሌላ የለምና አንተ ወደ እስክንድርያ ሄደህ ክህነትንና ሥርዓተ ቁርባንን አምጣልን ብለው እሱን ወደ እስክንድርያ ላኩት፡፡

ጊዜው (325 ዓ.ም.) በኒቅያ ከተማ በተደረገው ዓለም-አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ አርዮስ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን የተለየበትና እንዲሁም በ328 ዓ.ም. ቅዱስ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሁኖ የተሾመበት ወቅት ነበር፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስ ከኢትዮጵያ ያመጣውን መልእክት ተቀብሎ ጉዳዩን ለማየት ጉባኤ አደረገ፡፡ የቀረበው ጉዳይ በቅዱስ አትናቴዎስ ሲቀ መንበርነት በጉባኤ ታይቶ የሀገሩን ቋንቋና የሕዝቡን ባህል የሚያውቅ ከፍሬምናጦስ በቀር ሌላ ሰው ስለሌለ ፍሬምናጦስ የኢትዮጵያ ጳጳስ ሁኖ እንዲሾም በጉባኤ ተወሰነ፡፡ በውሳኔው መሠረት ቅዱስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን "ኤጲስ ቆጶስ ዘአክሱም ወዘኩላ ኢትዮጵያ" ብሎ በአንብሮተ ዕድ ሹሞ ላከው፡፡ ፍሬምናጦስም በ330 ዓ.ም. የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ሁኖ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ፡፡

ከእስክንድርያ እንደተመለሰም ነገሥታቱን ኢዛናንና ሳይዛናን አስተምሮ አጠመቃቸው፡፡ "አብርሃ አጽብሓ" ብሎም በክርስትና ስም ጠራቸው፡፡ ከዚያም መንበረ ጵጵስናውን በአክሱም አድርጎ ሐዋርያዊ ተልዕኮውን በማስፋፋት የክህነትንና የቁርባንን ሥርዓት መፈጸም ጀመረ፡፡ በኢትዮጵያ ወንጌልን ለማስፋፋት የሚረዱትን ቀሳውስትና ዲያቆናት ሾመ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከጽርዕ /ግሪክ/ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መለሰ፡፡ በዚህ ምክንያት ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ፡፡ እሱም በፈጸመው ሐዋርያዊ ተግባር "ክፃቱ ብርሃን" ተብሎ ተሰየመ፡፡ ፍሬምናጦስ በእስክንድርያው ሲቀ ጳጳስ በቅዱስ አትናቴዎስ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ ከእስክንድርያ ጋር ያለው ግንኙነት ቀጣይነት ያለው ስለሆነ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ጊዜያችን ድረስ ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ከግብጽ ስታስመጣ ኑራለች፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን የበላይነት ነፃ ወጥታ በራስዋ ጳጳሳትና ፓትርያርክ የምትመራ ብትሆንም ከግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚደረገው የውጭ ግንኙነት አሁንም አልተቋረጠም፡፡ ያን ጊዜ የተደረገው ይህ የውጭ ግንኙነት የክርስትና እምነትን ሙሉ በሙሉ መቀበሏን ያረጋገጠችበት ስለሆነ የላቀ ግምት የሚሰጠው የውጭ ግንኙነት ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## 2. ሐ. በአርዮስ የክህደት ትምህርት ምክንያት የተደረገው የውጭ ግንኙነት

ቅዱስ አትናቴዎስ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ የተደረገው ዓለም-አቀፍ ጉባኤ አርዮስንና የክህደት ትምህርቱን አውግዞ ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ያጸደቀውን የኦርቶዶክስ እምነት በመጠበቅና በማስጠበቅ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ታላቅ አባት ነበር። ቅዱስ ፍሬምናጦስም ከሹመትና እምነት አባቱ ከቅዱስ አትናቴዎስ በተቀበለው ቃል ኪዳን መሠረት የአርዮስን የክህደት ትምህርት በመቃወም በኒቅያ የተወሰነውን እምነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ የሚያስተምር ጳጳስ ነበር። ሁኖም በዚያን ዘመን የኒቅያን ዓለም-አቀፍ ጉባኤ የጠራውና የአርዮስንም መወገዝ በቀጥታ የደገፈው ታላቁ ንጉሥ ቁስጠንጢኖስ በ337 ዓ.ም. ስለአረፈ መንበረ መንግሥቱን የወረሰው ልጁ ኮንስታንቲየስ 2ኛ አርዮስንና ትምህርቱን የሚደግፍ ስለነበረ ቅዱስ አትናቴዎስን ከአስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ አባርሮ የቀጳዶቅያ ሰው የነበረውን አርዮሳዊ ጊዮርጊስን በቅዱስ አትናቴዎስ መንበር አሾመው። እንደገናም በአክሱም መንበር የተቀመጠውን ቅዱስ ፍሬምናጦስን ለማባረርና ሌላ አርዮሳዊ ጳጳስ ለመተካት በነበረው ፅቅድ መሠረት ንጉሥ ኮንስታንቲየስ 2 ኛ ለኢትዮጵያ ነገሥታት ለአብርሃና አጽብሓ ደብዳቤ ጻፈ። በሕንድ ሀገር ሶትራ በተባለችው ከተማ የተወለደ ቴዎፍሎስ የተባለ ሕንዳዊ ቂስ ንጉሡ የጻፈውን ደብዳቤ ለአብርሃና አጽብሐ እንዲያደርስ ወደ ኢትዮጵያ ተላከ። ለነገሥታቱ የተጻፈውም ደብዳቤ ሙሉ ቃል እንዲህ የሚል ነበር።

"ቢክቶሪዮስ ኮንስታንቲዮስ ማክሲሞስ አውግስጦስ ለአብርሃና አጽብሐ /ኢዛናና ሳይዛና/፣ እግዚአብሔር የሰጠን ትምህርትና ማስተዋል ለሁሉም እውነትንና ጽድቅ ለሚፈልግ ሁሉ እንዲዳረስ ስመኝ በእናንተና በሮማውያንም ቤተ ክርስቲያን መካከል አንድነት እንዲኖር ይገባል። ከሹመቱ የተሻረው፣ ብዙ ክስም ቀርቦበት ሙመለስ ያቃተው አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን ልኂቃና አሁን በቶሎ ፍሬምናጦስን መልሳችሁ ለተከበረው ጳጳስ ለጊዮርጊስና በዚያም ላሉት ቀሳውስት ላኩትና የአርሱን ነገር እነሱ ይጨርሱት። የአባ አትናቴዎስን ሥራ ግን ከእናንተ በቀር አገር ሁሉ አውቆ አላስጠጋም ስላለው በእናንተ ዘንድ መጠጊያ ይፈልጋል። ፍሬምናጦስ ግን ከልቡ ጳጳስ ሲሆን ከፈለገ የሕይወቱን ታሪክ ለቀሳውስቱ ገልጦ የቤተ ክህነትን ሕግና ሥርዓት በደንብ ፈጻሚ መሆኑ ከተረጋገጠ በእነሱ ዘንድ ተመልሶ እንደገና ጳጳስ መሆን ይችላል። ያለዚያ ግን እንደለፍላፊው እንደ አትናቴዎስ ከሕግ የሚሸሽ ሁኖ ወደ አክሱም የመጣና ሹመቱን የያዘ እንደሆነ እናንተንም ቤተ ክርስቲያናችሁንም እንዳያበላሽና ሁከት እንዳይፈጥር ያስፈልጋል። እኔ ግን እንደሚመስለኝ ፍሬምናጦስ ወደ አስክንድርያ ተመልሶ በጣም ከተከበረው ጳጳስ ጊዮርጊስና ከፍ ካሉት ሊቃውንት ጋር ተገናኝቶ የቤተ ክህነትን ሕግና ትምህርት ከተረዳ በኋላ ወደ ጵጵስና ሥፍራው ሊመለስ ይችላል" የሚል ነበር። ነገሥታቱ አብርሃና አጽብሓ ግን ለኒቅያ ጉባኤ ውሳኔና ለቅዱስ አትናቴዎስ ትምህርት ያላቸውን ሙሉ ድጋፍ በመስጠት የኮንስታንቲዮስን አሳብ ሳይቀበሉት ቀርተዋል። መልእክቱን ይዞ ወደ አክሱም የመጣው ቴዎፍሎስም የተላከበት ጉዳይ ውጤት አልባ ስለሆነበት በመጣበት መንገድ ተመልሶ ሄዷል። በዚህ ጊዜ ቅዱስ አትናቴዎስ ከነበረበት የስደት ቦታ ሁኖ የኢትዮጵያ ነገሥታት አብርሃና አጽብሓ የወሰዱትን አስደናቂ አቋም ስለሰማ ለኢትዮጵያውያኑ ነገሥታት የምስጋና ደብዳቤ እንደጻፈ ይነገራል። በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከቁስጥንጥንያ ጋር የተደረገው ይህ የውጭ ግንኙነት በዚያን ጊዜው ዓለም ሳይቀር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነበራትን ታዋቂነት የሚያረጋግጥ በመሆኑ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው።

## 2.መ. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው ዓለም-አቀፍ ጉባኤያትና የዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት

2.መ.ሀ. ዓለም-አቀፍ ጉባኤያትን በሚመለከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው ሦስት ዓለም-አቀፍ ጉባኤያት አሉ። እነዚህም የኒቅያ (325)፣ የቍስጥንጥንያ (381)፣ የኤፌሶን /431/ ጉባኤያት ናቸው። እነዚህ ጉባኤያት ቤተ ክርስቲያን ከመከፋፈሏ በፊት የተካሄዱ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጉባኤያቱን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ትቀበላለች። በመሆኑም ቀደም ሲል ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፣ ቀጥሎም ቅዱስ ማቴዎስና ሌሎቹም ሐዋርያት ያስተማሩትን ትምህርት መሠረት በማድረግ በሦስቱ ጉባኤያት ማለት በኒቅያ፣ በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን የተወሰነውን የሃይማኖት ቀኖና ተቀብላ ስታስተምር ኑራለች።

ከእነዚህ ጉባኤያት በኋላ በ451 ዓ.ም. የተካሄደውን የቂልቄዶኑን ጉባኤ ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎቹም አኃት አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉትም። ምክንያቱም የመለኮትንና

www.ethiopianorthodox.org





ትስብእትን ተዋሕዶ በመለያየት ክርስቶስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ እንደአለው የሚያሳይ ውሳኔ የተላለፈበት ጉባኤ በመሆኑ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የተከሠተውን ልዩነት ለማስወገድ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በጐ ፈቃድና ፍላጐት ቢኖርም ወደቀድሞው አንድነት ለመመለስ ገና አልተቻለም።

## 2. መ. የተሰዐቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት

"ዘጠኙ ቅዱሳን" በመባል የሚታወቁት ቅዱሳን በጊዜው በነበረው ዓለም-አቀፍ ግንኙነት ስለ ኢትዮጵያ መልካም ዜና በመስማት በ480 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጡ። የመጡትም ክቊሣርያ፣ ከታናሿ እስያ፣ ከቊስጥንጥንያ፣ ከቊልቅያ፣ ከቆስያ፣ ከአንጾኪያ ነው። እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡበትም ምክንያት የተወገዘውን የኬልቄዶኑን ጉባኤና ውሳኔውን አንቀበልም በማለታቸው በቢዛንታይን ነገሥታት ሥቃይ ስለጸናባቸው ነው። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝበ ክርስቲያንም የቅዱሳኑ እምነት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነት ጋር አንድ ሁኖ ስለአገኙት በፍቅር ተቀበሏቸው። ስማቸውም አባ አሌፍ፣ አባ አረጋዊ፣ አባ አፍጺ፣ አባ ሊቃኖስ፣ አባ ገሪማ፣ አባ ጉባ፣ አባ ይምዓታ፣ አባ ጸንጠሌዎን፣ አባ ጽሕማ ይባላል። እነሱም በዓት አጽንተው፣ እስከዛሬ ድረስ በስማቸው የሚጠሩትን ገዳማት አቅንተው ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን፣ ሥርዓተ ገዳምንና ምንኩስናን እያስተማሩ ኑረዋል።

## 2. ሠ. በአጼ ካሌብ ዘመን የተደረገ የውጭ ግንኙነት

የክርስትና እምነት በደቡብ አረቢያ ሁሉ ቀደም ብሎ ተዳርሶ ስለነበር ከአጼ ካሌብ ዘመን በፊት ጀምሮ በደቡብ ዓረቢያና በክርስቲያን ኢትዮጵያ መካከል የቅርብ ግንኙነት ነበር። በ70 ዓ.ም. ጥቶስ ኢየሩሳሌምን በአጠፋ ጊዜ ተሰድደው ደቡብ ዓረቢያ የገቡ አይሁድ ፊንሐስ በተባለ አይሁዳዊ ሰው እየተመሩ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በሀገረ ናግራን የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ማሠቃየት ጀመሩ። ሥቃዩ የጸናባቸው ምእመናንም በቂስጥንጥንያ፣ በአስክንድርያና በኢትዮጵያ ለሚኖሩ የሃይማኖት ወንድሞቻቸው አሰሙ። ይህም የዕልቂት ዜና የክርስቲያን ኢትዮጵያን መንግሥትና ሕዝብ በጣም አሳዘነ።

የቂስጥንጥንያው ንጉሥ ዮስጢኖስም ዕልቂቱ ያሳዘነው መሆኑን ገልጦ ለአስክንድርያው ሊቀጳጳስ ለአባ ጢሞቴዎስ 3ኛ መልእክት ላከ። አባ ጢሞቴዎስም የኢትዮጵያ ንጉሥ አጼ ካሌብ የናግራን ክርስቲያኖችን እንዲታደግ መልእክት ላከ። አጼ ካሌብ መልእክቱ ሲደርሰው ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን በመረዳት "ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት" ብሎ ወደያመን ዘመተ። ከዚያም ግፈኛውን ፊንሐስን ከነሠራዊቱ ደምስሶ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን አስጠገነ፣ አዲስም አሳነጸ። በመጨረሻም ከፊንሐስ ሠይፍ የተረፉትን አጽናንቶና አረጋግቶ ከአሥር ሺህ ሠራዊት ጋር የሚጠብቃቸው አብርሃ የሚባል ብልህ ሰው ሹሞላቸው ወደ አክሱም ተመልሷል። የክርስቲያን ኢትዮጵያ መንግሥትና ቤተ ክህነት በጥምር ያደርጉት የነበረው የውጭ ግንኙነት ከ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የተቋረጠበት ጊዜ እንዳልነበር ግልጽ ነው።

ለምሳሌ፡-

(ሀ) በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጼ ዳዊት ከኢየሩሳሌሙ ፓትርያርክ አባ ዮሐንስ ጋር በአደረገው መጻጻፍ ፓትርያርኩ አባ ዮሐንስ ጌታ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀል ከአክሲለ ሦኮና ቅዱስ ሉቃስ ከሣላት የእመቤታችን ሥዕል ጋር ለአጼ ዳዊት ልኮለታል። ዛሬ በግሸን ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ግማደ መስቀል ያን ጊዜ የተላከው ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሕዝበ ክርስቲያን በያመቱ መስከረም 21 ቀን ወደ ግሸን የሚጉርፈውም ይህን ግማደ መስቀል ለመሳለም ነው።

(ለ) በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በፍሎሬንስ ኢጣልያ በተደረገ ዓለም-አቀፍ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት የሚኖር ኢትዮጵያዊ መነኮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ተገኝቶ ነበር። መልእክተኛው የተመረጠው በገዳሙ መነኮሳት ሲሆን ይህ የጉባኤ ተሳትፎ በዓለም-አቀፍ ደረጃ በታሪክ ሲዘከር ይኖራል።

(ሐ) በ19ኛው መቶ ዓመት አፄ ዮሐንስ አራት ጳጳሳትን ከግብፅ በማስመጣት ከዚያ በፊት በአንድ ጳጳስ ይሰጥ የነበረው አገልግሎት በስፋት እንዲቀጥል አድርገዋል፡፡ የእነዚህም ጳጳሳት ስም አቡነ ዮሐንስ፣ አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሉቃስ፣ አቡነ ማቴዎስ ይባላል፡፡ በዚህ ዓይነት የቤተ ክርስቲያኒቱ የውጭ ግንኙነት የተቋረጠበት ጊዜ ባይኖርም በይበልጥ እየሰፋና እያደገ የሄደው ግን በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡

# ክፍል 3

## የውጭ ግንኙነት በሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን

### 3. ሀ. ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ለማሾም የተደረገ የውጭ ግንኙነት

ቅዱስ ፍሬምናጦስ የኢትዮጵያ ጳጳስ ሁኖ ከተሾመበት ከ330 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1921 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትመራው አስቀድሞ እንደተገለጠው ከእስክንድርያ መንበረ ማርቆስ እየተሾመ በሚላክ ግብጻዊ ጳጳስ ነበር፡፡ ሁኖም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምኞቷና ጥረቷ ከራስዋ አበው ሊቃውንት መካከል ተመርጦ በሚሾም ጳጳስ መመራት ስለነበር ይህ ምኞትና ጥረት እያደገ ሄዶ በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የነገሠው ቅዱስ ሐርቢ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ለማሾም ለመጀመሪያ ጊዜ ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ገብርኤል በደብዳቤ ጥያቄ አቀረበ፡፡ ሁኖም ጥያቄው ተቀባይነትን በአለማግኘቱ በየጊዜው ከተነሡ አንዳንድ ነገሥታት ተመሳሳይ ጥያቄ መቅረቡ ባይቀርም እስከ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ ጉዳዩን ከፍጻሜ ለማድረስ አልተቻለም ነበር፡፡

በ1921 ዓ.ም. በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ (ያን ጊዜ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ባለሙሉ ሥልጣን አልጋ ወራሽ) ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ተመሳሳይ ጥያቄ ስለአቀረቡ ከብዙ ውጣውረድ በኋላ በዚሁ በተጠቀሰው ዓ.ም. አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ካይሮ ላይ በእስክንድርያው ፓትርያርክ ዮሐንስ 19ኛ ተቀብተው ተሾሙ፡፡ እነዚህም ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ ብፁዕ አቡነ አብርሃም፣ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ፣ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ነበሩ፡፡ በዚሁ ዓ.ም. ፓትርያርኩ ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት ስለመጡ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን "ሳዊሮስ" ብለው ጵጵስና ስለሾሙዋቸው የኢትዮጵያኑ ጳጳሳት ቁጥር አምስት ሆነ፡፡ በዚህም ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው ሊቃውንት መካከል ጳጳስ እንዳይሾሙ የሚያግደው የግብጻውያን ሰው-ሠራሽ ቀኖና ሊፈርስ ችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምኞትና ጥረት በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የበላይነት ነፃ ወጥታ በራስዋ ሊቀ ጳጳሳትና ፓትርያርክ ለመመራት እስከትችል ድረስ ጥረቷን ስለቀጠለች በ1943 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እጅ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት፣ በ1951ዓ.ም. ደግሞ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ እጅ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሁነው ተሾሙ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና በግብጽ ቤተ ክርስቲያን መካከል የነበረው የበላይነትና የበታችነት ግንኙነት ስለአከተመ በአሁኑ ጊዜ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት የሚያደርጉት በእኩልነት ደረጃ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በራስዋ ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትርያርክ መመራት ከጀመረች ወዲህ የውጭ ግንኙነቷ እየሰፋና እያደገ ስለመጣ በዚያው መጠን የበለጠ ዓለም-አቀፍ ዕውቅናን እያገኘች ነው፡፡ ይህን ግንኙነት የምታደርገውም፡-

- በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ
- በአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ
- ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት በሚያደርጉት የጋራ ጉባኤ
- በመሪዎች ደረጃ በሚደረግ የጉብኝት ልውውጥ አማካይነት ነው፡፡





### 3. ለ. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርን በሚመለከት

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ኢ.ኤ.አ በ1948 ዓ.ም. የተቋቋመ የአብያተ ክርስቲያናት ዓለም-አቀፍ ተቋም ነው፡፡ ማኅበሩ የተቋቋመው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አዳኝ መሆኑን በሚያምኑና በዚያም እምነት አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ የሚገባውን ክብርና ምስጋና በአንድ ቃል ለማቅረብ በተባበሩ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆን ማኅበሩ የተቋቋመበት የራሱ የሆነ አላማና ተግባር አለው፡፡ አላማና ተግባሩም ምሥጢረ ቍርባንን በአንድነት ለመፈጸም እስከሚቻል ድረስ አባል አብያተ ክርስቲያናት ስለ እምነት አንድነት የሚያደርጉትን ጥረት ማበረታታትና የክርስትናው ዓለም አንድነቱን በተግባር እንዲያሳይ ማብቃት ነው፡፡ በአባል አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሊኖር የሚገባውን የእርስ በእርስ ተራድኦ ማጠናከርም ሌላው የድርጅቱ ዓቢይ ተግባር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዚህ ድርጅት መሥራች አባል ስትሆን አሁንም በአባልነቷ እንደጸናች ትገኛለች፡፡

ቅዱስነታቸው በሮማንያ በተካሄደው የሰላም ጉባኤ ስብሰባ ላይ

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አላማውን ተግባራዊ የሚያደርገው በጠቅላላ ስብሰባ፣ በማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባና በሌሎችም የሥራ ክፍሎች ነው፡፡ ሕጉ ለአባል አብያተ ክርስቲያናት ተከታዮች ብዛት ክፍተኛ ግምት ስለሚሰጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እንደምእመናኗ ብዛት በስባት ዓመት አንድ ጊዜ በሚካሄደው ጠቅላላ ስብሰባ አሥራ ሁለት፣ በዓመት አንድ ጊዜ በሚደረገው የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ደግሞ ሁለት መቀመጫዎችን በመያዝ ስብሰባውን ትሳተፋለች፡፡ ዓለም አቀፍ ግንኙነቱንም ታጠናክራለች፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ድርጅቱ በ1948 ዓ.ም. በአምስተርዳም ከአደረገው መሥራች ጉባኤ ቀጥሎ በየሰባት ዓመት በኢባንስተን /አሜሪካ/ በ1954 /ኢ.ኤ.አ/፣ በኒውደልሂ /ሕንድ/ በ1961፣ በሎፕሳላ /ስዊድን/ በ1968፣ በናይሮቢ /ኬንያ/ በ1975፣ በባንክቦር (ካናዳ) በ1983፣ በካምቤራ (አውስትራልያ) በ1991፣ በሐራሬ /ዝምባብዌ/ በ1998፣ በፖርቶ አሌግሬ /ብራዚል/ በጠቅላላ ዘጠኝ ስብሰባዎችን አዘጋጅቷል። በእነዚህ ስብሰባዎች በተደረጉ ገንቢ ውይይቶች ምክንያት፡-

ሀ. በእርስ በእርስ ጥላቻ ፈንታ በአባል አብያተ ክርስቲያናት መካከል መልካም ግንኙነትን በመፍጠር በኩል ከፍተኛ እርምጃ ተደርጓል።

ለ. አባል አብያተ ክርስቲያናት የሐዋርያትን ትምህርት በመከተል የክርስትና እምነትን በጎብረት ለመመስከርና ከዚህ ደረጃ ለመድረስ የተጀመረውንም ጉዞ እስከመጨረሻው ድረስ በጎ ብረት ለመቀጠል ያላቸውን መልካም ፈቃድ አሳይተዋል።

ሐ. በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ሊኖር የሚገባውን የእርስ በእርስ ተራድኦ መርሐ-ግብር ተግባራዊ በማድረግ በኩል መልካም ውጤት ታይቷል። በዚህ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዕለት ደራሽ እርዳታ፣ በመልሶ ማቋቋምና የልማት ነክ መርሐ-ግብር እፊጸጸም በኩል ከድርጅቱ አባላት አብያተ ክርስቲያናት የተደረገላትና የሚደረግላት ተራድኦ ከፍተኛ ስለሆነ ምስጋና ታቀርባለች።

በ1963 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ አራተኛ ስብሰባን አስተናግዳለች።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ፖርቶ አሌግሬ-ብራዚል ላይ በ2006 በተደረገው የድርጅቱ 9ኛ ጉባኤ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፕሬዚዳንት ሁነው ስለተመረጡ ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ በአመራር ደረጃ ድርጅቱን ለማገልገል ተረኛ ሁናለች። ዝርዝር ሐተታው ወደፊት በቦታው ይገለጣል።

## 3.ሐ. የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤን በሚመለከት

የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የተመሠረተው እ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም. ሲሆን ዋና መሥሪያ ቤቱ የሚገኘውም ድርጅቱ በተመሠረተበት በናይሮቢ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የድርጅቱ መሥራች አባል ናት። ማኅበሩ የተመሠረተው እንደዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ሁሉ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል በመከተል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አዳኝ መሆኑን በሚያምኑና በዚያም እምነት አንድ አምላክ ለሆኑ ለአብ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ የሚገባውን ክብርና ምስጋና ማቅረብ የአምልኮታቸው ሥርዓት በሆነ የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ነው። የድርጅቱ ዋና አላማ፡-

- በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ወንጌል ስለ አብያተ ክርስቲያናት ሕይወት፣ አገልግሎት፣ ምስክርነትና አንድነት የሚያገዘውን ቃል ለመፈጸም፣
- የጋራ ጥናትና ምርምር ለማድረግ፣
- የጉብኝትና የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የቅርብ ግንኙነትና የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ለማበረታታት፣
- በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የባለሙያ ተራድኦ እንዲኖር ለማድረግ፣
- አብያተ ክርስቲያናት የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝ፣
- ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጋር በመተባበር ከዚህ በላይ የተገለጠውን ተልዕኮ ለማከናወን ነው።



ጉባኤው በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ አጠቃላይ ስብሰባ፣ በየዓመቱ አንድ ጊዜ ደግሞ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባ በማካሄድ የጋራ ውይይት ያደርጋል። ውሳኔዎችንም ያሳልፋል። የጉባኤው መሥራች አባል የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በየአምስት ዓመቱ አንድ ጊዜ በሚደረገው አጠቃላይ ስብሰባ አምስት፣ በየዓመቱ በሚደረገው የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባ አንድ መቀመጫ በመያዝ የበኩሏን ተሳትፎ ታደርጋለች። የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከማኅበሩ ሦስት ፕሬዝዳንቶች አንዱ ሁነው በመመረጥ በኃላፊነት አገልግለዋል። ለምሳሌ በ1961 ዓ.ም. በአቢጃን፣ አይቦሪኮስት የተካሄደውን አጠቃላይ ጉባኤ በፕሬዚዳንትነት የመሩት ቅዱስነታቸው ነበሩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ1990 ዓ.ም. ስባተኛውን የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አስተናግዳለች። ዝርዝር ሐተታው ወደፊት በቦታው ይገለጣል።

# ክፍል 4

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኦርዮንታል ኦርቶዶክስ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላት ግንኙነት

የኦርዮንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በመባል የሚታወቁት አብያተ ክርስቲያናት የአስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ የሶርያ /አንጾኪያ/ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት የመለኮትንና ትስብእትን ተዋሕዶ በማመን "አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ" ባሮች በመሆናቸውና "ሁለት ባሕርይ" የሚለውንም ትምህርት በመቃወም አንድ ስለሆኑ "አኃት አብያተ ክርስቲያናት" ይባላሉ፣ አንትማማኞች አብያተ ክርስቲያናት ማለት ነው። እነዚህ አምስት አብያተ ክርስቲያናት ሦስቱን ጉባኤያት ማለት የኒቅያን፣ የቊስጥንጥንያን፣ የኤፌሶንን ጉባኤያት ሲቀበሉ አራተኛውን የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ አይቀበሉም፣ ለጉባኤውም ዕውቅና አይሰጡም።

በዚህ ምክንያት "ነን ካልሴዶናውያን" ማለት "የኬልቄዶኑን ጉባኤ የማይቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት" በመባል ይጠራሉ። የኬልቄዶኑን ጉባኤ የማይቀበሉትም "ሁለት ባሕርይ" በሚል እምነት ቤተ ክርስቲያንን የከፋፈለ ጉባኤ በመሆኑ ነው።

የኦርዮንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በ431 ዓ.ም. ከተደረገው ከኤፌሶን ጉባኤ ወዲህ የመጀመሪያ የሆነ ጉባኤ በ1957 /በ1965 ኢ.ኤ.አ/ ዓ.ም. በአዲስ አበባ በመሪዎች ደረጃ አከያሂደዋል። የዘመኑ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ለአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች ጥሪ በማስተላለፍና ተሳታፊዎቹን በማስተባበር በኩል ታሪካዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ቤተ ክርስቲያናችን ጉባኤውን ያስተናገደችው በወቅቱ የሐረር ሊቀ ጳጳስና የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ እንደራሴ በነበሩት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ኃላፊነት ሲሆን ተሳታፊዎቹ መሪዎች ጉባኤውን በሰላም ጀምረው በሰላም ፈጽመዋል፣ በልዩ ልዩ አርእስተ ጉዳዮች ላይ በመነጋገርም ከጋራ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።



www.ethiopianorthodox.org

1. ዘመናዊው ዓለምና አብያተ ክርስቲያናት
2. በመንፈሳዊው ትምህርት ተባብሮ ስለመሥራት
3. በጎብረት ሐዋርያዊ አገልግሎትን ስለመፈጸም
4. ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ስለምናደርገው ግንኙነት
5. በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ቀዋሚ ግንኙነት እንዲኖር አንድ ድርጅት ስለማቋቋም
6. ስለ ዓለም ሰላምና ስለ ትክክለኛ ፍርድ የሚሉ ሲሆኑ በእነዚህ አርእስት ላይ የተጀመረው ውይይት ወደፊትም ቀጣይነት እንዲኖረው ተስማምተዋል። "በዚህና ወደፊትም በሚደረጉ ጉባኤያት አማካይነት አብያተ ክርስቲያናቶቻችን የኒቅያ፣ የቁስጥንጥንያና የኤፌሶን ጉባኤዎች በተካሄዱበት ዘመን የነበራቸውን የአንድነት መንፈስ አድሶ በአዲስ ኃይልና በአዲስ ሕይወት እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ዓለም የላከበትን አላማ ወደፊት ለማራመድ ያስችለናል ብለን እናምናለን በማለትም የወደፊት መልካም ራዕያቸውን ገልጸዋል። በዚሁ ስብሰሳ መጨረሻ ለግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ "የሃይማኖት ጋሻ" የሚል የክብር ስም ተሰጥቷል።

# ክፍል 5

## በኦርየንታልና በኢስተርን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተደረጉ ጉባኤያት

የኢስተርን /ምሥራቅ/ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስ በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ፣ ሁለት ፈቃድና ግብር" እንደአለው ሲገልጹ የኦርዬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን የቅዱስ ቄርሎስን ትምህርት አብነት በማድረግ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ከሆነ በኋላ ምንታዌ /ሁለትነት/ ስለጠፋ ክርስቶስ "አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ ፈቃድ፣ አንድ ግብር" ያለው አምላክ መሆኑን ስለሚያምኑ ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው የውጭ ግንኙነትና ውይይት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ በመምጣቱ ልዩነቱን ለማስወገድ በሁለቱ ወገን አብያተ ክርስቲያናት ምሁራን መካከል ሰባት ይፋ የሆኑና ያልሆኑ ጉባኤያት ተካሄደዋል። እነዚህም ፡-

1. በአርሁስ ዴንማርክ እ.ኤ.አ በ1964 ዓ.ም.
2. በብርስትል ኢንግላንድ በ1967 ዓ.ም.
3. በጀኔቫ-ስዊዘር ላንድ በ1970 ዓ.ም.
4. በአዲስ አበባ-ኢትዮጵያ በ1971 ዓ.ም.
5. በአባ- በሾይ ገደም- ግብጽ በ1989 ዓ.ም.
6. በቻምቤዚ-ስዊዘርላንድ በ1990 ዓ.ም.
7. በቻምቤዚ-"በ1993 ዓ.ም. የተካሄዱት ጉባኤያት ነበሩ። በእነዚህ ጉባኤያት ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞቿን በመላክ ተሳትፋለች።

በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ልዩነት የተፈጠረው ከኬልቄዶን ጉባኤ ወዲህ ስለሆነ ከላይ በተዘረዘሩት ጉባኤያት ሁሉ በኬልቄዶን ጉባኤ የተከሠተው ልዩነትና ውግዘት መነሻ ምክንያት በጥልቀት ተመርምሯል። በመጨረሻም በቻምቤዚ ከጎዳር 1-6 ቀን 1993 ዓ.ም. /እ.ኤ.አ/ በተደረገው ጉባኤ በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት የተከሠተው የሁለት ባሕርይና አንድ ባሕርይ ልዩነት የቃላት አገላለጥ እንጂ የምሥጢር ልዩነት አለመሆኑን ጉባኤው ተገንዝቧል። ከእነዚህ ጉባኤያት በፊት የኢስተርን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የኦርዬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን "የአውጣኬ ትምህርት ተከታዮች" የኦርዬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የኢስተርን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን " ንስጥሮሳውያን" በማለት እርስ በእርሳቸው ይተቻቹ ነበር። በእነዚህ ጉባኤያት ግን ንስጥሮስና አውጣኬ በሁለቱም ወገን የተወገዙ መናፍቃን መሆናቸው ስለተገለጠ የእርስ በእርስ ትችቱ እንዲቆም ስምምነት ተደርጓል። ከዚህም ጋር በእነዚህ ጉባኤያት በሁለቱም ወገን ላይ የተላለፉትን ውግዘቶች ለማንሣት ስለሚቻልበት ሁኔታ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። ስለ ውግዘቶቹ መነሣትም የውሳኔ አሳቦች ተርበዋል። እነዚህም የውሳኔ አሳቦች፡-

1. የሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ቤተሰቦች ውግዘቶችን እንዲያነሡ፣
2. የውግዘቶቹ መነሣት በሁሉም ወገን በአንድ ጊዜ እንዲፈጸም፣
3. ሁለቱም ወገን የውግዘቱን መነሣት እንዲያስታውቁ፣





4. ያለፈው ሲኖዶሳዊ ወይም የግል ውግዘት በሁለቱም ወገኖች እንደማይቀጥል እንዲያረጋግጡ፣
5. የሁለቱም ወገን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስም በቅዳሴ ጊዜ እንዲጠራ የሚሉ ነበሩ። ሁኖም ስምምነቱ በእያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት ተከታዮች ዘንድ ገና ያልተመከረበትና ስምምነትም ያልተደረገበት ስለሆነ ተግባራዊ አልሆነም።ያለፈው ውግዘት እንዲነሣና አንድነትም እንዲፈጠር የተደረገውን ስምምነት በሚመለከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የያዘችው አቋም ግን የሚከተለው ነው።

ሀ. በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት "አንድ አካል፣ ሁለት ባሕርይ በተዋሕዶ" የሚለው የኬልቄዶናውያኑ የእምነት አገላለጥ "አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ" ከሚለው የኦርዬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የእምነት አገላለጥ የተለየና ውግዘቱም "ሁለት ባሕርይ" በሚለው የእምነት አገላለጥ ምክንያት የተላለፈ ስለሆነ፣

ለ. ውግዘቱን በተመለከተ ከአባቶቻችን የተቀበልናቸው መጻሕፍት በትክክል የተጻፉና ለአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ስንገለገልባቸው የቆዩና አሁንም ያሉ ስለሆነ፣

ሐ. በጥንታውያኑ ኬልቄዶናውያን ላይ የተላለፈውን ውሳኔ ለማንሣት ቀኖናዊ ሥልጣን ስለሌለና ውግዘቱን ያስተላለፉትንም አባቶች ክብር ስለሚያቃልል በጥንታውያኑ ኬልቄዶናውያን ላይ የተላለፈውን ውግዘት ማንሣትና ያንጊዜ የተወገዙትን ዛሬ ቅዱሳን ብሎ መጥራት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኩል ድጋፍ እንደሌለው አቋም ተወስዷል።

የምሥጢረ ሥጋዌን ትምህርት ልዩነት በሚመለከት ኬልቄዶናውያኑ ወይም የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት "ሁለት ባሕርይ በተዋሕዶ" የሚሉት አዲስ የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት አገላለጽ "አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ" ከሚለው የኦርዬንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት አገላለጽ ጋር አንድ አይደለም። ስለሆነም "ሁለት ባሕርይ በተዋሕዶ" የሚለው ቃል "አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ" በሚለው ቃል ካልተተካ አንድነቱን ለመቀበል ዝግጁ አለመሆንዋን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሳውቃለች። ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ጋር እስከአሁን የነበረውን መልካም ግንኙነት ግን ወደፊትም ለመቀጠል ሙሉ ፈቃደኛ መሆንዋን አረጋግጣለች።

# ክፍል 6

## በመሪዎች ደረጃ በሚደረግ የጉብኝት ልውውጥ አማካይነት የተካሄደ የውጭ ግንኙነት

አብያተ ክርስቲያናት የውጭ ግንኙነት ከሚያደርጉባቸው መንገዶች አንዱና ዋናው የግል ጉብኝት ልውውጥ ነው። በተለይ በመሪዎች ደረጃ የሚደረገው ጉብኝት ለውጭ ግንኙነት መጠናከር የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ሐያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአብያተ ክርስቲያናት የውጭ ግንኙነት እየሰፋና እየተናከረ የመጣበት ክፍለ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም መልእክተኞቿን ለጉብኝት ወደ ውጭ በመላክና የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችንም ተቀብላ በማስተናገድ በኩል ስታደርገው የቆየችው የውጭ ግንኙነት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በተለይ ከመጀመሪያው ፓትርያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እስከ አምስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ክህነት ባለው ጊዜ በመሪዎች ደረጃ የተደረገው የውጭ ጉብኝት ልውውጥ እጅግ ብዙ ቢሆንም ዋና ዋናውና በቤተ ክህነት ቤተመዘክር ሠነድ ተመዝግቦ የሚገኘው ከዚህ እንደሚከተለው ተዘርዝሮ ቀርቧል።

6.1. በ1944 ዓ.ም. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግሪክ የገባበት አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶኛ ዓመት ሲከበር የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ወደ ግሪክ ሄደው የበዓሉ ተካፋይ ሁነዋል።

6.2. በ1948 ዓ.ም. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች ጉባኤ አምስተርዳም ላይ ሲካሄድ አሁንም በወቅቱ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የቤተ ክርስቲያኒቱን ልዑካን በመምራት በጉባኤው ተሳትፈዋል። ቤተ ክርስቲያናችን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሥራች አባል የምትባለውም ስለዚህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

6.3. በ1958 ዓ.ም. አሥራ ሁለት የአሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ልዑካን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ታላላቅ አድባራትንና ገዳማትን ከመጐብኘታቸውም በላይ ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ጋር ተነጋግረዋል፡፡

6.4. በ1960 ዓ.ም. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከሩስያ ፓትርያርክ አሌክሲ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ወደ ሩስያ ተጉዘው በሩስያ ቤተ ክርስቲያን የወርቅ ኢዮቤልዩ ላይ ተገኝተዋል፡፡ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የተላከውን የወርቅ አርዌ ብርትና ልዩ ልዩ ስጦታም ለፓትርያርክ አሌክሲ አበርክተዋል፡፡

6.5. በ1961 ዓ.ም. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ጋር የሮማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ጐብኝተዋል፡፡ ስለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነትም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ፓትርያርክ ዱስቲንያን ጋር ሰፋ ያለ ውይይት አድርገዋል፡፡

6.6. በ1961 ዓ.ም. በሮድስ ግሪክ በተደረገው በመጀመሪያው የመላው ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ልዑካን ተገኝተው ጉባኤውን ተሳትፈዋል፡፡

6.7. በ1961 ዓ.ም. የሮማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ጄስቲንያን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይፋ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በዓለ ጥምቀትንም በጃንሜዳ አክብረዋል፡፡ በመጨረሻም ግንኙነቱ እንዲቀጥል፣ የሊቃውንት፣ ደቀመዛሙርትና የሥነ ጽሑፍ ልውውጥ እንዲደረግ የጋራ መግለጫ ወጥቶ የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ተፈራርመዋል፡፡

6.8. በ1962 ዓ.ም. የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ መልእክተኛ ሜትሮፖሊታን ኒቆዲሞስ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ በኢትዮጵያና የብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርኩ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ እንግዳ በመሆን በኢትዮጵያ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ ሜትሮፖሊታን ኒቆዲሞስ በየጊዜው የተደጋገሙ ጉብኝት ማድረጋቸውም በታሪክ ማኅደር ተዘ[illegible]

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፪ (2000) ዓ.ም

6.11. በ1964 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥሪ ስለተደረገላቸው በግሪክ ይፋ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ ከአቴናና የመላዋ ግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ኤሮኒሞስ ጋርም በመገናኘት ስለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ተወያይተዋል፡፡ በመጨረሻም የነፃ ትምህርት ዕድልን፣ ስብከተ ወንጌልንና የጋራ መረዳዳትን በተመለከተ የጋራ መግለጫ ወጥቶ ሁለቱም መሪዎች ተፈራርመዋል፡፡ ቅዱስነታቸው ከግሪክ ጉብኝታቸው በኋላም ወደ ቊስጥንጥንያ አምርተው ከኢኩመኒካል ፓትርያርክ አቴና ጎራስ ጋር ተገናኝተው ስለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ተነጋግረዋል፡፡

6.12. በ1966 ዓ.ም. የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፒሜን ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንግዳ በመሆን ኢትዮጵያን ጐብኝተዋል፡፡ ስለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነትም መግለጫ ወጥቶ ሁለቱ መሪዎች ተፈራርመዋል፡፡

6.13. በ1966 ዓ.ም. በግብፅና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ጸንቶ በኖረው አንድነትና ግንኙነት መሠረት ብፁዕ ወቅዱስ ሣልሳይ ሲኖዳ የእስክንድርያ ፓፓና የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ በተደረገላቸው የክብር ጥሪ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለአምስት ቀናት ጉብኝት አድርገዋል፡፡ ለኢትዮጵያ ምእመናንም ቡራኬ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ዓመት ብፁዕ አባ መቃርዮስ የቆጵሮስ ሊቀ ጳጳሳትና ፕሬዚዳንት ከግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ኢትዮጵያን ጐብኝተዋል፡፡

6.14. በ1965 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዩ.ኤስ.አሜሪካ፣ በዌስት ኢንዲስና በደቡብ አሜሪካ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ ይህ ወቅት ቅዱስነታቸው በሀገር ውስጥ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለማፋጠን እንደ ልማት ኮሚሽን፣ ሰበካ ጉባኤ፣ ማይክሮ ፊልም ፕሮጀክት ወዘተ ... ለመሳሰሉት የሥራ ዘርፎች መሠረት የጣሉበትና የውጭ እርዳታም የሚፈለግበት ጊዜ ነበር፡፡ ከሀገር ውጭ ደግሞ ይህ ወቅት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ እያደገ መጥቶ ለአንድነት፣ ለሰላም፣ ለፍትሕ፣ ለእርስበእርስ መደጋገፊና ትብብር ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠበትና እነዚህንም አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ በአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች መካከል የጉብኝት ልውውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሁኖ የሚታይበት ጊዜም ነበር፡፡ እንደዚሁም ቅዱስነታቸው በሰሜን አሜሪካና በዌስት ኢንድስ ቀደም ብለው ያቋቋሟቸውን አብያተ ክርስቲያናት መጐብኘትና ማጠናከር ዋና ዕቅዳቸው አድርገው የተነሡበት ጊዜ ነበር፡፡ በመሆኑም ቅዱስነታቸው ይህን ጉብኝት ያደረጉት እነዚህን አላማዎች ለማሳካት ነበር፡፡

ይህን አላማ በመያዝ ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ተጉዘው ግንቦት 8 ቀን 1965 ዓ.ም. ሰሜን አሜሪካና ከዚያም ደቡብ አሜሪካ የገቡት ቅዱስነታቸው በዚያ የሚገኙ ታላላቅ ካቴድራሎችን፣ የታወቁ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፣ ታላላቅ ዩንቨርስቲዎችን በመጐብኘት ከከፍተኛ የሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎች፣ የዩንቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች ጋር በመገናኘት ተነጋግረዋል፣ በታላላቅ ካቴድራሎች ቀድሰው አቊርበዋል፡፡ ዓለም- አቀፍ የጸሎት ሥነ-ሥርዓቶችን መርተዋል፡፡ በሰጡት ስብከትና ትምህርት አያሌ ምእመናንን አጽናንተዋል፡፡

ከዚህም ጋር በታላላቅ ጉባኤዎች ላይ በአደረጉአቸው ንግግሮች የጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት በሚያምኑ አብያተ ክርስቲያናት መካከል መቀራረብ፣ መተባበርና አንድነትም እንዲፈጠር አስገንዝበዋል፡፡ የተቀበሏቸው መሪዎችም በአደረጓቸው ንግግሮችና በሰጧቸው ሽልማቶች ለቅዱስነታቸው ያላቸውን አክብሮትና አድናቆት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ጉብኝት በኋላ ቅዱስነታቸው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን በመጐብኘት ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

6.15 በ1970 ዓ.ም. ሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሞስኮ፣ በኢችሚያድዚንና በፖላንድ ይፋ ጉብኝት አድርገዋል። ከየአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች ጋርም በመገናኘት ስለ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነትም ውይይት አድርገዋል።

6.16 በ1972 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ጐብኝተዋል። ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ሊቀ ጳጳስ ሱራፌል ጋርም ስለ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነትና የአስኮላርሺፕ ጉዳይ ተነጋግረዋል።

6.17 በ1974 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከጀርመንና ከኦስትርያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ጀርመንን፣ ኦስትርያንና ሮምን ጐብኝተዋል፤ ከአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች ጋርም ስለ ተራድኦ ተነጋግረዋል።

6.18 በ1974 ዓ.ም. ሞስኮ ላይ በተካሄደው ዓለም-አቀፍ የሰላም ጉባኤ ላይ ሦስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተገኝተዋል።

# ክፍል 7

## የውጭ ግንኙነት በአምስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ክህነት

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ ክህነት የቤተ ክርስቲያናችን የውጭ ግንኙነት የበለጠ ስፋትና ጥንካሬ እያገኘ የሄደበት ወርቃማ ዘመን ነው። ይህንም ከሚከተለው ሰፊ ሐተታ መረዳት ይቻላል።

7.1 በ1985 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በጀኔብ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት፣ በአሜሪካ፣ በእንግላንድ፣ በቢየና ኦስትርያ፣ በቫቲካን-ሮም ጉብኝት አድርገዋል። በዚህም ጊዜ ከየአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች ጋር ስለዓለም ሰላምና ስለ ልማት ተራድኦ ተወያይተዋል። በተለይም ባቲካንን በጎበኙበት ወቅት በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት የሚገኙት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት፣ በሮም የሚገኘው የአኩስም ሐውልት ስለሚመለስበት ጉዳይ ከፖፕ ዮሐንስ ጳውሎስ ዳግማዊ ጋር ተወያይተዋል።

7.2 በ1986 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር ቅዱስነታቸው የቍስጥንጥንያው ዓለም-አቀፍ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በርተሎሜዎስ በአደረጉላቸው ጥሪ መሠረት በቍስጥንጥንያና በአቴንስ ጉብኝት አድርገዋል። በጉብኝቱም ወቅት የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በምሥራቅና በኦርዩንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተጀመረው የመቀራረብ ውይይት ስለሚቀጥልበት ሁኔታ ተነጋግረዋል። በዚሁ ዓመት በአስክንድርያና በአፍሪካ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፖርቴንዮስ የቅዱስነታቸው እንግዳ በመሆን ኢትዮጵያን ጐብኝተዋል።

7.3 በ1986 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከአርመን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ ባዝኪን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት አርመንን ጐብኝተዋል። ስለ ኦርዩንታል አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት መጠናከርም ተወያይተዋል። የታሪክ ቦታዎችንም ጐብኝተዋል።

7.4 በ1986 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው በኤሲሲ-ኢጣልያ "የእግዚአብሔር ወዳጆች፣ የሰላም ምስክሮች በሚል ርእስ በተዘጋጀው ጉባኤ ላይ ተገኝተው ንግግር አድርገዋል። በጉባኤው ላይ ከተገኙት ታላላቅ የሃይማኖትና የመንግሥታት መሪዎች ጋርም ተገናኝተው ስለ ዓለም ሰላም ተነጋግረዋል።

7.5 በ1986 ዓ.ም. የቍስጥንጥንያው ዓለም-አቀፍ ፓትርያርክ በርተሎሜዎስ የቅዱስነታቸው እንግዳ በመሆን በኢትዮጵያ ጉብኝት አድርገዋል። በዓለ ጥምቀትንም በጃንሜዳ አክብረዋል፣ ልዩ ልዩ የታሪክ ሥፍራዎችንም ገዳማትንም ጐብኝተዋል።

7.6 በ1986 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በካሪቢያን ሐዋርያዊ ጉብኝት አድርገዋል። የጎበኝዋቸውም ሀገሮች ጃማይካ /ኪንግስተን/፣ ባርቤዶስ/ብርጅ ታውን/፣ ጉያና/ጆርጅታውን /ትሪንዳድና ቶቤጉ /ፓርት ኦፍ እስፔይን/ ናቸው። ቅዱስነታቸው ከእነዚህ ሀገሮች እንደደረሱ በአሜሪካና በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ማትያስ፣ በካሪቢያን ደሴቶችና በላቲን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ፣ ኢትዮጵያውያን ካህናትና ምእመናን፣ የሀገሩ ተወላጆች የሆኑት የቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች፣ የመንግሥትና የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል። በጉብኝታቸው ወቅት ቅዱስነታቸው በዚያ ለሚገኙ ምእመናን አባታዊ ትምህርት ሰጥተዋል፣ ቀድሰው አቍርበዋል፣ ከመንግሥታትና የሃይማኖት ሪዎች ጋር ተገናኝተው ተነጋግረዋል፣ ልዩ ልዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተቋማትን ጐብኝተዋል፣ ጉብኝታቸውን ምክንያት በማድረግ በየሀገሩ በተደረጉ ልዩ ልዩ ስብሰባዎች ላይም በመገኘት ንግግር አድርገዋል።

www.ethiopianorthodox.org

7.7 በ1988 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው በሩስያና በዩክሬን ጉብኝት አድርገዋል፡፡በዚህ ጉብኝት ከሩስያው ፓትርያርክ ዳግማዊ አሌክሲ ጋር በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ጸንቶ የቆየው ግንኙነት ለወደፊትም ተጠናክሮ ስለሚቀጥልበት ሁኔታ ተነጋግረዋል፡፡ ገዳማትን፣ የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻ ፋብሪካንና የታሪክ ቦታዎችን ጐብኝተዋል፡፡

7.8 በ1989 ዓ.ም. ከመስከረም 24-ጥቅምት 6 ቀን ቅዱስነታቸው ወደ ኢየሩሳሌም ሐዋርያዊ ጉዞ አድርገዋል፡፡ ከዚያ በቆዩበትም ጊዜ የኢትዮጵያ ገዳማትን የውስጥ ይዞታ በመመልከት የገዳማቱ ይዞታ ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ከብፁዕ ሲቀ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና ከገዳማውያኑ ጋር ተወያይተዋል፣ መመሪያም ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የእሥራኤልና የፍልስጥኤም ግጭት ሰላማዊ መፍት ሔ ስለሚያገኝበት ሁኔታ ከእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ፕሬዚዳንትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር በየጽሕፈት ቤታቸው ተገናኝተው ተነጋግረዋል እንዲሁም በዚሁ ዓመት ከግንቦት 16-30 ቀን ቅዱስነታቸው በኢየሩሳሌም ጉብኝት አድርገዋል በጉብኝታቸውም ወቅት በኢየሩሳሌም የሚገኙት የኢትዮጵያ ገዳማትና ንብረቶች ጥንታዊ ይዞታቸውን ሳይለቁ መታደስ ያለባቸው እንዲታደሱና በጥንቃቄ እንዲጠበቁ መመሪያ ሰጥተዋል፡፡

ከዚያም በአላባር ምስክበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ገዳም ሊሠሩ ለታቀዱት የእንግዳ ማረፊያ፣ የአረጋውያን መጦሪያና የጤና ጣቢያ የመሠረት ድንጋይ ከማኖራቸውም በላይ ለዚሁ ከፍተኛ ሥራ መርጃ ይሆን ዘንድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም አንድ ሚሊዮን ብር እርዳታ ሰጥተዋል፡፡

7.9 በ1990 ዓ.ም. የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ የሆኑት የካንተበሪ ሊቀ ጳጳስ ዶ/ር ጆርጅ ኬሪ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በተደረገለቸው ጥሪ መሠረት በኢትዮጵያ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በዓለ ጥምቀትንም በጃንሜዳ ተገኝተው አክብረዋል፣ በጣና ሐይቅ የሚገኙትን ገዳማትና እንዲሁም የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተዋል፡፡ ከጉብኝታቸው በኋላ በአደረጉት ንግግር "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአምነቷና ሥርዓቷ ጽናት በዓለማችን ላይ ከሚገኙት አብያተክርስቲያናት መካከል መልካም ምሳሌነት ያላት ቤተ ክርስቲያን መሆንዋን በመስማት ብቻ ሳይሆን በማየት ለመረዳት ችያለሁ" ሲሉ አድናቆታቸውን ገልጸዋል፡፡

7.10 በ1990 ዓ.ም. 7ኛውን የመላው አፍሪካ ጠቅላላ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያናችን አስተናግዳለች፡፡ በዚህ አህጉራዊ ጉባኤ ከ143 አህጉር በተሳታፊነትና በተመልካችነት የተወከሉ ከ800 በላይ የሚሆኑ ልዑካን ተሳትፈዋል፡፡ ስብሰባው የተከፈተው በአዲስ አበባ አስታዲዮም በተደረገ ጸሎት ሲሆን በዚህ ሥርዓተ ጸሎት ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ የጉባኤው ተሳታፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ በርካታ የአዲስ አበባ ካህናትና ምእመናን ተገኝተዋል፡፡ ስብሰባው የተካሄደው "ተቸገርን ግን አልጠፋንም" በሚል ርእስ ነው፡፡ በአዲስ አበባ አስታዲዮም የተካሄደው የጸሎት ሥነ-ሥርዓት እንደተፈጸመ ጉባኤው በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን መሰብሰቢያ አዳራሽ ተከፍቷል፡፡ ጉባኤውን በንግግር የከፈቱት በቅደም-ተከተል ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንትና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳወሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ናቸው፡፡

ቅዱስነታቸው በአደረጉት የመክፈቻ ንግግር "ወደ እናት ሀገራችን ኢትዮጵያና ወደ ቤተ ክርስቲናችን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ስንቀበላችሁ ደስታ ይሰማናል" ከአሉ በኋላ " ገነትን ወደሚያጠጣው ሁለተኛው ወንዝ ወደፈለገ ግዮን ምድር፣ ወደ ንግሥተ ሳባና ወደ ንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ሀገር፣ ጽላተ ሙሴ ወደትምገኝበት፣ ወደቅዱስ ያሬድና ወደ ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ሀገር እንኳን ደህና መጣችሁ" ብለዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪካዊነት አስመልክተው ሲናገሩም "ቤተ ክርስቲያናችን ልዩና የምትደነቅ ናት፣ ልዩ ባሕርይዋ ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱም እምነቷና ሥርዓቷ በታላቅ ጥንቃቄ ብሉያትና ሐዲሳት የተጣመሩበት የተዋሕዶ ሃይማኖት መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ሐዋርያዊና ጥንታዊ መሆኑ ነው፡፡ እጅግ ጥዑምና ሕሊናን በአንቃዕድዎ ወደ አምላክ የሚስብ፣ ከዝማሬ መላእክት የሚነጻጸር የራስዋን ያሬዳዊ ዜማ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ደርሳ ለአያሌ ዘመናት ስትገለገልበት ቆይታለች፣ እየተገለገለችበትም ነው" በማለት አስገንዝበዋል፡፡

አፍሪካንና እንዲሁም የጉባኤውን ሂደት በሚመለከት በአደረጉት ንግግር "በአሁኑ ወቅት በአህጉራችን ያሉትንና በምዕራቡ ዓለም የፈለሱትን የአፍሪካ ሕዝቦች መንፈሳዊና ማኅበራዊ ችግሮች ለመፍታት በጐ ፈቃደኝነቱና ቍርጠኝነቱ ሊኖረን ይገባል፤ ይልቁንም በሽታን፣ ድህነትን፣ ጦርነትንና መፈናቀልን፣ ዘረኝነትንና የመንፈሳዊ ጸጋ እጦትን አበክረን መታገል ይኖርብናል፡፡

ይህ ታላቅ ጉባኤ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት እኒህንና ከተሳታፊዎች የሚቀርቡለትን ሌሎችንም አሳቦች አብላልቶና አቀናጅቶ በመጨረሻ አንድ ተጨባጭ አርምጃ እንደሚወስድ ጽኑዕ ተስፋ አለኝ፣ በአውነቱ የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ይህን ካልፈጸመ ተግባሩን በአጥጋቢ ሁኔታ አከናውኗል ብሎ ለመናገር ያስቸግራል... የሰው ልጅ ሕይወት የከበረና የተቀደሰ ስለሆነ በጭካኔ በከንቱ ሊጠፋ አይገባውም፣ ራሱ ፈጣሪ የሰጠንን ሕይወት የማጥፋት መብቱም የእኛ አይደለም፤ ዳር በማይበጅለት፣ ወሰን በማይከለልለት ዘለዓለማዊ ጥበቡና ፍቅሩ እርሱ አምላካችን ይርዳን" የሚል ሰፊ መልእክት ያለበት ታሪካዊ ንግግር ከአደረጉ በኋላ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና በአርባ ሚሊዮን ምእመናን ስም ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ልባዊ ደስታዬን በድጋሚ እገልጻለሁ" በማለት ንግግራቸውን አጠቃለዋል፡፡

ክቡር ፕሬዝደንት ነጋሶ ጊዳዳ በበኩላቸው ለጉባኤው በአደረጉት ንግግር "የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት የአፍሪካውያንን ባህል በመጠበቅና ሕዝቡን ከቅኝ ግዛት ለማላቀቅ በተደረገው ትግል ያበረከቱት አስተዋጽኦ የላቀ መሆኑን ጠቅሰው የአፍሪካን ሕዝቦች በሃያ አንደኛው ሙቶ ክፍለ ዘመን በተሻለ ማኅበራዊ ሥርዓት ለማኖር በሚደረገው እንቅስቃሴ አብያተ ክርስቲያናት በማኅበረ-ሰቦች ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ ተሰሚነት በመጠቀም ሕዝቡን ወደተሻለና ብሩህ ጐዳና የመምራት ታላቅ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል" ብለዋል፡፡ ቀጥሎም እርስ በእርስ መፈቃቀርና መቻቻል በሕዝቦች መካከል ሥር እንዲሰዱ የሃይማኖት መሪዎች የማስተማር ሞራላዊና መንፈሳዊ ኃላፊነት እንደአለባቸው በመጥቀስ ንግግራቸውን አጠቃለዋል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ማኅበሩን ለአሥር ዓመት ያህል በፕሬዚዳንትነት የመሩት የደቡብ አፍሪካው አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ዴዝሞን ቱቱ ስለ አፍሪካ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግርና መፍትሔ፣ ስለ አፍሪካ የተፈጥሮ ጸጋ ታላቅነት ሰፋ ያለ ንግግር አድርገዋል። በንግግራቸውም ስለ አህጉሩ ያላቸውን መልካም ራዕይ ሲገልጹ "በነገይቱ አፍሪካ ብሩህ ተስፋ ይታየኛል፣ ለዚህም ምክንያት አለኝ፣ ክርስቶስ የተሰደደው ወደዚህችው አፍሪካችን ምድር ነው፤ አፍሪካ የሥልጣኔና የሰው ልጅ ምንጭ ናት፤ ይህ የሚያሳየው እግዚብሔር አፍሪካን ምን ያህል እንደወደዳት ነው፤ አምላ ገነኖችንና ጨቋኞችን ከአፍሪካ ጫንቃ አሽቀንጥረን እንጣል፤ ያን ጊዜ አፍሪቃ ነፃ ትሆናለች" ብለዋል።

በመቀጠልም የመላው አፍሪካ አብያ ክርስቲያናት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ቄስ ዶ/ር ጆሴ ቢሎ ችፔንዳ ማኅበሩ በአለፉት ጊዜያት ስለአህጉሩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ስኬት የአበረከተውን አስተዋጽኦና ወደፊትም ሊያደርገው የአቀደውን ተመሳሳይ ተልዕኮ አፈጻጸም የሚገልጽ ሰፋ ያለ ዘገባ አቅርበው ውይይት ተካሂዷል። በመጨረሻም ስለ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ኑሮ ዕድገትና ጥንካሬ፣ ስለ ፍትሕና ርትዕ መስፈን፣ ድህነትንና በሽታን ለመቀነስና ብሎም ለማጥፋት የአፍሪካ ሕዝብ በሚያደርገው ትግል የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት የላቀ ድርሻ ማበርከት እንደአለባቸው በመስማማት ስብሰባው ተፈጽሟል።

7.11 በ1990 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም ጉብኝት አድርገዋል። በጉብኝታቸውም ወቅት የገዳማውያኑ አንድነትና ሰላም ተጠናክሮ ሊቀጥል ስለሚችልበት ሁኔታ ከማኅበሩ ጋር ከመወያየታቸውም በላይ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ባኮስ የተጠመቀበትን ቦታ ጐብኝተዋል። ወንዙን ባርከዋል። በጋዛ ሸለቆ አቅራቢያ የሚገኘው ይህ ቦታ የኢትዮጵያ ቅርስና ሀብት እንዲሆን ከእሥራኤል ባለሥልጣኖች ጋርም ተነጋግረው ተስፋ ተገኝቷል። በዚህ ጉብኝት ቅዱስነታቸው የዴርሁልጣንን ገዳም የባለቤትነት ይዞታ በተመለከተ ከእሥራኤል መንግሥት ባለሥልጣናት፣ የፓርላማ አባላትና የሃይማኖት መሪዎች ጋር ተነጋግረዋል። ምንጊዜም ቢሆን የዴርሁልጣን ገዳም ይዞታ ለድርድር የማይቀርብ መሆኑንም ገልጸዋል።

7.12 በ1990 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው በመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ ለመገኘት የመጡትን ተቀማጭነታቸው በአስክንድርያ የሆነውን በአፍሪካ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ ጴጥሮስን በመንበረ ፓትርያርኩ ተቀብለው አነጋግረዋል። ሁለቱ ፓትርያርኮች በተገናኙበት ወቅት በአሁኑ ጊዜ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስለሰላምና ስለሰው ልጆች ደኅንነት ከመቸውም በበለጠ የጋራ ጥረት ማድረግ እንደአለባቸው ተወያይተዋል። በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ስለአለው ግንኙነት መጠናከርም ተነጋግረዋል።



7.13 በ1990 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን የኢጣልያ ፕሬዝዳንት ክቡር አስካርሲዊጅ ሰካልፋሮን በመንበረ ፓትርያርኩ ተቀብለው አነጋግረዋል። በዚህም ወቅት ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ ስለምታበረክተው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ምልዓትና ስፋት ቅዱስነታቸው ለፕሬዝዳንቱ ገለጻ አድርገውላቸዋል። በወረራ የተወሰደው የአኩስም ሐውልት ለባለቤቷ ሀገር ለኢትዮጵያ እንዲመለስ የኢጣልያ መንግሥት በመፍቀዱም የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ አመስግነዋል ክቡር ፕሬዝዳንቱም ስለተደረገላቸው የሞቀና የደመቀ አቀባበል ምስጋና አቅርበዋል።

7.14 በ1991 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተፈጠረው ግጭት ሰላማዊ መፍትሔ ስለሚያገኝበት ሁኔታ በኤርትራ የሃይማኖት መሪዎችና በኢትዮጵያ የሃይማኖት መሪዎች መካከል የተጀመረውን ውይይት ለመቀጠል እንደኖ በኦስሎ ኖርዌይ፣ ሁለተኛ በፍራንክፈርት ጀርመን በተደረጉ ጉባኤዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ልዑካን በመምራት ተገኝተዋል። ጦርነት ለማንም ለምንም የማይበጅ የሰው ልጅ ቀሳፊ መሆኑን በመገንዘብ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ሰላም ይሰፍን ዘንድ ቅዱስነታቸው በጉባኤው ላይ የተማኅፅኖ ጥሪ አቅርበዋል።

7.15 በ1992 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከፍተኛ ልዑካንን በመምራት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኒዮርክ የተካሄደውን የሁለት ሺሕ ዓመት የዓለም የሃይማኖት መሪዎች ጉባኤ ተካፍለዋል። ጉባኤው በብዙ መቶ የሚቈጠሩ የዓለም የሃይማኖት መሪዎች የተሳተፉበት ሲሆን ርእሰ ጉዳዩም ሰላም ነበር። በዚህ ዐቢይ ጉባኤ ላይ ቅዱስነታቸው በአስተላለፉት መልእክት "በዚህ ዓለም ለግጭት መስፋፋትና ለሰላም እጦት ዋናው ምክንያት ሕገ እግዚአብሔርን አለማክበርና አለማመን፣ በሰው ልጆች መካከል ፍቅር አለመኖር ነው።

ይህ ሲጓደል ሰላም አይኖርም፣ በሰው ልጆች መካከል ግጭት ይበረክታል... የዘመኑ ሰው የሥልጣኔን ቁንጮ ጨበጥኩ ብሎ በሚመጻደቅበት በአሁኑ ወቅት በየዕለቱና በየሥፍራው አሰቃቂ ድርጊት ሲፈጸም ማየቱ ለማመን የሚያስቸግር ነው። በዚህ ወቅት እኛ የሃይማኖት አባቶች የጥረታችን ዋና ትኩረት መሆን ያለበት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅና ዓለም-አቀፍ የሞራል ዕሴት እንዲያንሠራራ ማድረግ ነው ከዚህም ጋር ሁሉም መንግሥታት ግጭትን ከመጫርና ከማባባስ እንዲታቀቡ በአጽንዖት እንጠይቃለን" ብለዋል፡

7.16 በ1993 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት ክቡር ሚስተር ክሊንተን በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ብፁዓን አባቶችን አስከትለው ኤድስን ስለመከላከል በዋሽንግተን በተደረገው ዓለም-አቀፍ ጉባኤ ላይ ተገኝተዋል። በስብሰባው ላይ በአስተላለፉት መልእክት " በኤድስ ለተያዘ ለአንድ ሰው የሥጋ ሞትን ከማሰብ ይልቅ ዘለዓለማዊ ሕይወትን አጣለሁ ብሎ እንደማሰብ ያለ አስደንጋጭ ነገር የለም፣ ቤተ ክርስቲያን ሕሙማንን በማጽናናት ሥርዬትን እንዲያገኙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ልታደርግ ትችላለች። ከዚህም ጋር ቤተ ክርስቲያን ሰፊ የሰው ኃይልና በሕዝቡም ዘንድ ተደማጭነት ስለአላት፣ እንዲሁም በአክብሮት ስለምትታይ የበሽታውን መስፋፋት በመግታት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ልታበረክት ትችላለች" ሲሉ ተናግረዋል።

www.ethiopianorthodox.org

7.17 ቅዱስነታቸው በዚሁ ዓመት "ኃላፊነት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት" በሚል ርእስ በጀርመን ዋና ከተማ በበርሊን በተደረገው ዓለም-አቀፍ ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል፡፡ በስብሰባው ላይ በአደረጉትም ንግግር "ኃላፊነት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የሚጠበቅብንን ተግባር በሙሉ ልብ ማከናወንና አለማከናወናችን የሚገለጽበት የሰው ልጅ የተግባር መመሪያ መሥፈርት ነው... ኃላፊነትን በብቃት ለመወጣት ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ፣ እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ መውደድ፣ ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ያስፈልጋል... በዓለም ላይ ለተንሠራፋው የሰው ልጅ ችግር ኃላፊነት ሊሰማን ይገባል... የቍሳዊ ነገሮች አምልኮና ፍላጐት በየጊዜው እየተስፋፋ መጥቷል፤ በአንጻሩም የሰው ልጅ መንፈስ ፍቅርን፣ ደግነትንና ርኃራኄን እየተጠማ ነው... የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር እየራቀ በመሄድ ላይ ይገኛል... የሰው ልጅ ህልውናና ተስፋ እግዚአብሔርንና ሰውን በማፍቀር ላይ የተመሠረተ ነው..." ሲሉ ገልጸዋል፡፡

7.18 ቅዱስነታቸው አሁንም በዚህ ዓመት ማለት በ1993 ዓ.ም. በግሪክ አቴንስ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በጉብኝ ታቸውም ወቅት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መሥሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው የግሪክ መንግሥት ባለሥልጣናትን አነጋግረው የተስፋ ቃል ተገብቶላቸዋል፡፡ በኢትዮጵያና በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በአለው ወዳጅነት ምክንያት ይሰጥ የነበረው የነፃ ትምህርት ዕድል እንዲቀጥል በጠየቁት መሠረት የግሪክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አወንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

7.19 በ1993 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በአደረጉላቸው ጥሪ መሠረት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ካራኪን ዳግማዊ የመላው አርማንያ ሕዝብ ካቶሊኮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ጎብኝተዋል፡፡ ለእንግዳው ካቶሊኮስ ክብር በመንበረ ጽባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከፍተኛ የአቀባበል ሥነ-ሥርዓት ተደርጓል፡፡ እንግዳው ካቶሊኮስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ አጠቃላይ የሰበካ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ተገኝተውም የቤተ ክርስቲያናችንን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተመልክተዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አቶ መለስ ዜናዊ ጋር ተገናኝተው ተነጋግረዋል፡፡ የሰበታ ቤተ ደናግል ጠባባት ገዳምን፣ የመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን፣ በጎፋ መካነ ጠባባት ገዳምን፣ የመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን፣ በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን የቀድሞውን ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን መካነ መቃብርና የደብሩን ቤተ መዘክር ጎብኝተዋል፡፡



በጨረሻም በሁለቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ለረጅም ዘመናት ጸንቶ የቆየው የትምህርተ መለኮት አንድነትና መንፈሳዊ ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል በሁለቱ መሪዎች መካከል ስምምነት ተደርጓል፡፡

7.20 በ1993 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና ሎችንም ከፍተኛ ልዑካን በማስከተል በደቡብ አፍሪካ ሐዋርያዊ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ የጉብኝቱ ዋና አላማም የቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች በሆኑት ደቡብ አፍሪካውያንና በደቡብ አፍሪካ በሚገኙት ኢትዮጵያውያን ምእመናን መካከል በመገኘት ሐዋርያዊ ተልዕኮ ለመፈጸም ነበር፡፡

ጆሐንስበርግ ሲደርሱ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ተጠባባቂ ጉዳይ ፈጻሚና የኤምባሲው ሠራተኞች፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአፍሪካ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ በደቡብ አፍሪካ የክፕት /ግብጽ/ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ፣ በጆሐንስበርግ የጽርሐ ጽዮን መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት፣ የሰንበት- ትምህርት ቤት ወጣቶች በአይሮፕላን ጣቢያው ተገኝተው ደማቅ አቀባበል ያደረጉላቸው ሲሆን ፖርት ኤልሳቤጥ ሲደርሱም የሀገሩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ የቤተ ክርስቲያናችን እምነት ተከታዮች የሆኑት የደቡብ አፍሪካ ተወላጆች፣ የአብያተ ክርስቲያናት ተጠሪዎች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል፡፡ ቅዱስነታቸው በደቡብ አፍሪካ ጉብኝታቸው ለምእመናን ቃለ ምዕዳን ሰጥተዋል፡፡ ቀድሰው አቍርበዋል፡፡ በተለይ በጆሐንስበርግ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ከ600,000.00/ከስድስት መቶ ሺህ ብር/ በላይ አውጥተው የገዙትና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሚያመች መልክ ያዘጋጁት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት ሥርዓት በቅዱስነታቸው ቡራኬ ተፈጽሟል፡፡ ሁሉም ሀገር የእግዚአብሔር ሀገር ስለሆነ በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ምእመናን ከሀገራቸው ውጭ በመኖራቸው ኀዘንና ትካዜ እንዳይሰማቸው አባታዊ አጽናኝ ምክር ሰጥተዋቸዋል፡፡ ከፍተኛ ገንዘብ አውጥተው ለቤተ ክርስቲያን የሚሆን ሕንፃ በመግዛታቸው መርቀዋቸዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ለተገዛበት ዕዳ የሚከፈል የ100,000.00/አንድ መቶ ሺህ ብር/ እርዳታም አድርገዋል፡፡ ደቡብ አፍሪካውያን ምእመናንን በሚመለከት እነዚህ አፍሪካውያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ጥረት የጀመሩት ከአንድ መቶ ዓመት በፊት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን የፈለጉትም ኢትዮጵያ በአድዋ ጦርነት በኢጣልያ ጦር ላይ ያገኘችውን ድል በማድነቅና እንዲሁም ከሌላው የክርስትና ዓለም በፊት በዘመነ ሐዋርያት የክርስትና እምነትን የተቀበለች አፍሪካዊት ሀገር በመሆንዋ ነው፡፡

በዚህ ምክንያት የዚህች ጥንታዊትና አፍሪካዊት ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን አባቶቻቸው የጀመሩት ጥረት ተግባራዊ ለመሆን የቻለው ግን ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ በልጆቻቸው ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እነዚህ አፍሪካውያን የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ከመሆናቸውም በላይ በፓትርያርክ ለመጐብኘት በመብቃታቸው የተሰማቸው ደስታ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህንም ከንግግራቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ደቡብ አፍሪካውያኑ ቅዱስነታቸውን ለመቀበል በተዘጋጀው ሥነ-ሥርዓት ላይ በአደረጉት ንግግር " ይህች የዛሬዋ ዕለት ደርሳ እናያታለን ብለን አላሰብንም ነበር፡፡ይህችን ዕለት ሲጠብቁ ሕይወታቸው ያለፈ ወገኖቻችን ብዙዎች ናቸው፡፡ በዓረፋበት ቦታ የዚህችን ዕለት ደስታ ይካፈላሉ፡፡ ዛሬ ያለነው ግን ያዩ ዓይኖቻችን የተመሰገኑ ናቸው፡፡ ቀደምት አባቶቻችን በትእግሥት እንጠብቅ ይሉ ነበር፡፡ ተስፋችን ተፈጸመ፡፡ የዘመርነው መዝሙር የቅዱስ አባታችንና የሌሎችንም ብፁዓን አበው መምጣት የሚመለከት ነው፡፡ ሕልማችን ዕውን ሁኗል፡፡ ደስታችን ተፈጽሟል፡፡ ላቅ ያለ ደስታ ተሰምቶናል...ቅዱስ አባታችን ከቀደሙ አበው በዕድሜ የበለጸጉ አረጋውያንን ይቀበሉ፣ ቤተ ክርስቲያናችንን እነሆ፣ ልጆቻችንም እነሆ፤ ቁልፉን ይረከቡ..." በማለት ጥልቅ ስሜታቸውን ገልጸዋል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስነታቸውም ባሰሙት ቃለ ምዕዳን "እናንት ደቡብ አፍሪካውያን ወንድሞቻችንን እኅቶቻችን፣ ቀደምት አባቶቻችሁ ሲጠብቁትና ሲናፍቁት የነበረው ተስፋ ለፍጻሜ ደርሶ ዓይን በዓይን ተያይተን ገጽ ለገጽ ለመገናኘት መብቃታችን ጸሎታችሁ ቅድመ እግዚአብሔር መድረሱን ያመለክታል... ዛሬ ለሁላችን ታላቅ ቀን ነው፡፡ ሁላችንም አንድ ቤተሰብ ሁነናል፡፡ እንደቀደሙት አባቶቻችን ብልሆችና ታማኞች ልንሆን ይገባል፡፡ ታሪክና ሃይማኖት ያለን ሕዝብ ነን፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የረጅም ዘመን ታሪክና ብዙ ተከታዮች አባላት ያሏት ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ከዚህ በኋላ ስትናፍቁትና በትዕግሥት ስትጠባበቁት የቆያችሁትን ኦርቶዶክሳዊ እምነት በንጹሕ ልብ በመቀበል በጥንቃቄ መጠበቅና በሥርዓቱ መያዝ ይኖርባችኋል" በማለት ተናግረዋል፡፡ የንዋያተ ቅድሳት ስጦታም አድርገዋል፡፡ በመጨረሻም ቅዱስነታቸው በፖርት ኤልዛቤጥ በሚገኘው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ቀድሰው አቍርበውና ትምህርት ሰጥተው ወደጆሐንስበርግ ተመልሰዋል፡፡ ከዚያም ለምእመናኑ በድጋሚ የማጠናከሪያ ቃለ ምዕዳንና ትምህርት ሰጥተው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል፡፡

እንዲሁም በዚሁ ዓመት ማለት በ1993 ዓ.ም. በ?ዳር ወር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን የናንሰን ሜዳይ ሽልማት አግኝተዋል፡፡ ቅዱስነታቸው ለዚህ ሽልማት የበቁት ስለ ስደተኞች መልካም አያያዝ በአደረጉት ጥረት ሲሆን ሽልማቱን የተቀበሉት በአፍሪካ አዳራሽ በተደረገ ደማቅ ሥነ-ሥርዓት ላይ ነው፡፡ ሽልማቱን በተቀበሉበት ወቅት ቅዱስነታቸው በአደረጉት ንግግር" ይህ ሽልማት ለሕዝባችን፣ ለሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ለሀገራችን የሃይማኖት ተቋማትና ለመላው አፍሪካ ታላቅ ክብር ነው፡፡ እኔም እንደሌሎች የሀገሬ ሰዎች ስምንት ዓመት በእሥር ቤት፣ አሥር ዓመት በስደት አሳልፌያለሁ፡፡ በደርግ ሥርዓት በስደት ላይ በነበርኩበት ወቅት ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን በስደት የነበሩትን ሰዎች ሕይወት ለማሻሻልና ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማድረግ አጥር ነበር... አሁንም የስደተኞችን ችግር ለማቃለል ሁሉም ጥረት ሊያደርግ ይገባል" ሲሉ ገልጸዋል፡፡



7.21 በ1994 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው በአሜሪካ ኒውዮርክ ምዕራባዊ ክፍል የሚገኘው ቲትዩትና በካሊፎርኒያ ሳንፍራንሲስኮ የሚገኘው የፓካርድ ፋውንዴሽን ዋና መ/ቤት በአደረጉላቸው ጥሪ መሠረት ከሰኔ 15-24 ቀን በተጠቀሱት ሀገሮች ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በዚህ ጉብኝታቸው ቅዱስነታቸው በቸታኒ ኢንስቲትዩት ለተሰበሰበ በብዙ ሺህ ለሚቆጠር ሕዝብ ንግግር ድርገዋል፡፡ በአደረጉትም ንግግር ስለዓለም ሰላም፣ ስለሕዝቦች አንድነት፣ ስለ ድህነት ቅነሳና በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የተስፋፋው የዘመኑ ቀሳፊ በሽታ ስለሚወገድበት ሁኔታ፣ ለኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትናና ድኅረ-ክርስትና ታሪክ በስፋት ገልጸዋል፡፡ በመቀጠልም በካሊፎርኒያ ሳንፍራንሲስኮ በሚገኘው የፓካርድ ፋውንዴሽን ዋናመሥሪያ ቤት ተገኝተው በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዘረጋችውን የልማት መርሐ-ግብርና ኅብረተሰቡን ከቀሳፊው የኤድስ በሽታ ለማዳን የምታደርገውን ጥረት በስፋት በማስረዳት ይህኑ ጥረት አጠናክሮ ለመቀጠል የድርጅቱ ተጨማሪ ርዳታ እንደሚያስፈልጋት በአጽንዖት አሳስበዋል፡፡ የፋውንዴሽኑ የሥራ ኃላፊዎችም ሥራው በትክክል ከተካሄደ ርዳታውን ለመቀጠልና ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር አብሮ ለመሥራት ያላቸውን በጐ ፈቃድ ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም ቅዱስነታቸው በአስታንፎርድ ዩኒበርሲቲና በበርክሌይ ዩኒበርሲቲ ተገኝተው ስለጉብኝታቸው ዋና አላማ ከሁለቱም ዩኒበርሲቲዎች ኃላፊዎች ጋር ተነጋግረዋል፡፡ ከዚያም በሳንፍራንሲስኮ ከሚገኙት ከሮም ቤተ ክርስቲያንና ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ተገናኝተው ስለዓለም ሰላምና ስለዘመኑ ቀሳፊ በሽታ የጋራ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ተወያይተዋል፡፡

7.22 እንዲሁም በዚህ ዓመት ቅዱስነታቸው የሳን ጂዲዮ ማኅበረ ሰብአ በአሲሲ ፓሰርሞ ጣሊያን በአዘጋጀው ዓመታዊ የሰላም ጉባኤ ላይ ተገኝተዋል፡፡ ሰላምን በመጠበቅ ረገድ የክርስቲያኖች ተባብሮ መሥራት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ለጉባኤው አስገንዝበዋል፡፡ ይህ ማኅበረ ሰብአ በሌሎች ሀገሮች ላይ በአዘጋጃቸው ሌሎች ስብሰባዎች ላይም ተገኝተዋል፡፡

7.23 በ1995 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር ቅዱስነታቸው ብፁዓን አባቶችን በማስከተል ወደቤይሩት ሊባኖስ በመጓዝ ሐዋርያዊ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በዚያ በሚገኘው የቤተ ሳይዳ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ክብረ በዓል ላይ በመገኘትም ከ35ሺህ በላይ ለሚሆን ሕዝብ ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት በአስር ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያትን በአባታዊ ምክር ከማጽናናታቸውም በላይ ለአስረኞቹ ዓለም-አቀፍ ትኩረት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው የሊባኖስ ባለሥልጣናትና የሃይማኖት መሪዎች ጋር ተነጋግረዋል፡፡ በጉብኝቱ ወቅት የሦርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዛካና የሲሲሲያ አርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊኮስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አራም ከሺሺያን የሞቀ ወንድማዊ አቀባበል ያደረጉላቸው ከመሆኑም በላይ ከእነዚህ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያለው ግንኙነት ስለሚጠናከርበት ሁኔታ ተወያይተዋል፡፡

7.24 በ1996 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በታኅሣሥ ወር በጅቡቲ ሐዋርያዊ ጉብኝት አድርገዋል፡፡ ጅቡቲ ሲደርሱም በጅቡቲ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ጉዳይ ፈጻሚ ከሀገሪቱ ርእሰ-ብሔርና ጠቅላይ ሚኒስትር ተወካዮች ጋር አቀባበል አድርገውላቸዋል፡፡ በጉብኝታቸው ወቅት ቅዱስነታቸው ከሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ዑመር ጊሌና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ዴለይታ መሐመድ ጋር ተገናኝተው ተነጋግረዋል፡፡ በጅቡቲ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤት ጽሕፈት ቤትንና የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ሕንፃን መርቀው ከፍተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን በመጐብኘት ትምህርትና ምክር ሰጥተዋል፡፡

www.ethiopianorthodox.org



ሀ. በዚሁ ዓመት በየካቲት ወር ቅዱስነታቸው በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ኤች.አይ. ቪ. ኤድስን ለመከላከልና ሕሙማኑንም ለመንከባከብ ቤተ ክርስቲያናችን ለአወጣቸው ፕሮጀክት የተፈቀደውን የአምስት ሚሊዮን ብር እርዳታ ስምምነት ከአሜሪካ ተወካዮች ጋር ተፈራርመዋል። የእርዳታው ገንዘብ በሽታው በከፍተኛ ደረጃ ለተስፋፋባቸው ክልሎች እንደሚደርስም አስረድተዋል። በዚህ የእርዳታ ስምምነት ላይ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ዓለም-አቀፍ የልማት ድርጅት ዳይሬክተር ሚስተር ዊሊያም ሃሚኒክ፣ ሚስተር ኮንስታንቴን የዓለም-አቀፍ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ድርጅት ዋና ዳይሬክተር፣ ጳጳሳትና የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ተገኝተዋል።

ለ. በዚሁ ዓመት በሚያዝያ ወር ቅዱስነታቸው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የአስክንድርያና የአፍሪካ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጴጥሮስን በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል። በንግግሩ ወቅት በኤች አይ ቪ ኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናትን ለመርዳት በጉ አድራጊዎች ሊተባበሩ እንደሚገባ አስረድተዋል። ለአንግዳው ፓትርያርክ በሰበታ ቤተ ደናግል ጠባባት ገዳም የምሳ ግብዣ ተደርጓል። አንግዳው ፓትርያርክ በገዳሙ ሥር እየተሬዱ በመማር ላይ የሚገኙትን ሕፃናትና የገዳሙን የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ጎብኝተዋል።

ሐ. በዚሁ ዓመት በግንቦት ወር ቅዱስነታቸው በአቴንስ ሐዋርያዊ ጉብኝት አድርገዋል። አቴንስ እንደደረሱ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተወካይ ሜትሮፖሊታን፣ በኢትዮጵያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ የአቴንስ የምክሐ ደናግል ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ አባላትና አገልጋዮች ካህናት፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች፣ የሀገሩ መንግሥት ተወካዮች የክብር አቀባበል አድርገውላቸዋል። በዚህ ጉብኝት ቅዱስነታቸው ለምእመናን ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል፤ ቀድሰው አቍርበዋል። አባታዊ መመሪያና ምዕዳን በመስጠት በኢትዮጵያውያኑ ምእመናን መካከል ተፈጥሮ የነበረው አለመግባባት ሰላማዊ መፍትሔ እንዲያገኝ አድርገዋል።





ከዚያም ድህነት ስለሚወገድበት፣ የቤተ ክርስቲያናችን ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዘክር አያያዝ ስለሚሻሻልበት፣ የግሪክኛ ቋንቋ ትምህርት አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ ኮሌጆች ሊመደቡ ስለሚችሉበት፣ የልማት እርዳታና የመልሶ ማቋቋም መርሐ ግብር ተጠናክሮ ሊቀጥል ስለሚችልበት ሁኔታ ከግሪክ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ከሒለንስቲክ ሲቢላይዜሽን ሚኒስትር፣ ከአቴንስና ከመላዋ ግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ከክርስቶዶሎስ ጋር ውይይት አድርገዋል። የቀረቡትን ጥያቄዎች በየፊርጁ ለማስተናገድ እንደሚቻልም ቃል ተገብቶላቸዋል። ቅዱስነታቸው ግሪክ በቆዩበት ወቅት ሐይድራና አጊና የተባሉትን ታሪካውያን ደሴቶች በመርከብ ተዘዋውረው ጉብኝተዋል። በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው አቀባበልና መስተንግዶ ለግሪክ መንግሥትና ለግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ምስጋና አቅርበዋል።

መ. ቅዱስነታቸው በነሐሴ ወር 96 ዓ.ም. ወደ ኢጣልያ ተጉዘው የቅዱስ ኢጂዲዮ ገዳም በአዘጋጀው ዓለም አቀፍ የሰላም ጉባኤ ላይ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ተገኝተዋል። የስብሰባው ዋና ርእስ "የሃይማኖት መሪዎች ለምእመናኖቻቸው ጠንካራ የሰላም መልእክት እንዲያስተላልፉ፣ በዓለም ሰላም እንዲሰፍን፣ ሰዎች ያለችግርና ሥቃይ መኖር እንዲችሉ ሁሉም ጎብረተሰብአ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ" የሚል ነበር። ቅዱስነታቸው በዚህ ጉባኤ ላይ "ሰላምና ክርስቲያናዊ አንድነት" በሚል ርእስ ንግግር አድርገዋል። በዚህም የሰላምንና የክርስቲያናዊ አንድነትን አስፈላጊነት በዝርዝር አስረድተዋል። ቅዱስነታቸው በሚላኖ በቆዩበት ወቅት ከዚያ በሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ቀድሰው አቍርበዋል፣ ትምህርትና ቃለ ምዕዳንም ሰጥተዋል። በዚያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምእመናን በጥገኝነት የሚገለገሉበት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያውያን ምእመናን እንዲሰጣቸው የሚላኖ ካርዲናልን ጠይቀው የይሁንታ መልስ አግኝተዋል።

7.25 በ1997 ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በተባበሩት ዓረብ ኤምሬት፣ በዱባይና በአቡዳቢ ሐዋርያዊ ጉብኝት አድርገዋል። ቅዱስነታቸው ከተከታዮቻቸው ጋር ዱባይ አውሮ?ላን ማረፊያ ሲደርሱ የአቡዳቢ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያንና የሻርጃ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች፣ የኢ.ፌ.ዴ. ቆንሲላ ጽ/ቤት ሠራተኞች፣ ካህናትና ምእመናን፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል። በዚያ ለሚኖሩ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመገልገያነት ከሰጡት በሻርጃ ከአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊና ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመገናኘት ውይይት አድርገዋል። ከዚያም ወደ ሻርጃ ሰዓሊተ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አምርተው ከቦታው ሲደርሱ ደማቅ አቀባበል ተደርጐላቸዋል። በዚህ ጉብኝት ቅዱስነታቸው በዚያ ለሚገኙ ምእመናን ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል። ቀድሰው አቍርበዋል። በየቤተ ክርስቲያናቸው ለኢትዮጵያውያን ምእመናን የመገልገያ ቦታ ከሰጡት ከግሪክ ኦርቶዶክስና ከሕንድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ኃላፊዎች ጋርም በመገናኘት ውይይት አድርገዋል። በውይይቱ ወቅት ለኢትዮጵያውያን ምእመናን ተጨማሪ የአገልግሎት ጊዜ እንዲሰጥ ለእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ኃላፊዎች ጥያቄ አቅርበው የእወንታ መልስ አግኝተዋል።

ሀ. በዚህ ዓመት ቅዱስነታቸው በታኅሣሥ ወር ሊቃነ ጳጳሳትን በማስከተል ወደ ናይሮቢ ኬንያ ሐዋርያዊ ጉዞ አድርገዋል። ከዚያ ሲደርሱ በኬንያ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አምባሳደርና የኤምባሲው ሠራተኞች፣ የናይሮቢ ደብረ መድኀኒት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና ካህናት፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ቅዱስነታቸው በዚህ ጉብኝት ለምእመናን ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል፤ ቀድሰው አቍርበዋል፤ በዘመናዊ ?ላን ሊሠራ ለታቀደው ለደብረ ሰላም መድኀኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠዋል። የሕንፃውን የመሠረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ በሰጡት ቃለ ቡራኬ "ቤተ ክርስቲያኑን የምንሠራው አብረን ነው፤ ልጆቼ በርቱልኝ፣ የጀመራችሁትን መንፈሳዊ ሥራ ፈጽማችሁ ለማየት ያብቃን፣ የስደተኞች ጉዳይና የበጉ አድራጊት ድርጅት ሠራተኞች የስደተኞች መጠለያ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት እንዲተጉ አደራ እላለሁ" በማለት አባታዊ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል። ቅዱስ ሲኖዶስ ለዚህ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ወጭ የተቸለውን ሁሉ እንደሚያደርጉም ቃል ገብተዋል።

www.ethiopianorthodox.org

ለ. በዚሁ ዓመት በየካቲት ወር 97 ዓ.ም. ለሦስተኛ ጊዜ በደቡብ አፍሪካ ቅዱስነታቸው ብፁዓን ጳጳሳትን አስከትለው ሐዋርያዊ ጉብኝት አድርገዋል። ቅዱስነታቸው ጆሐንስበርግ አውሮፓ ላን ጣቢያ እንደደረሱ በደቡብ አፍሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጉዳይ ፈጻሚ፣ በደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የፕሮቶኮል ኃላፊ፣ በጆሐንስበርግ የጽርሐ ጽዮን መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፣ ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ከዚያም ቅዱስነታቸው በጽርሐ ጽዮን መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ጸሎት ከአደረጉ በኋላ በዓውደ ምሕረቱ በተደረገው የአቀባበል ሥነ-ሥርዓት የደብሩ አስተዳዳሪ የእንኳን ደህና መጡ ንግግር አድርገዋል። የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችም ያሬዳዊ መዝሙር ዘምረዋል። የአቀባበሉ ሥነ-ሥርዓት እንደተፈጸመ ቅዱስነታቸው የቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ ቦታውን በከፍተኛ ወጭ ገዝቶ የአቋቋመውን ሙዓለ ሕፃናት የጐበኙ ሲሆን ስለድርጅቱ መቋቋም በም/ሊቀ መንበሩ ሰፊ ገለጻ ተደርጓል። ወደፊትም ለቤተ ክርስቲያኑ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ ገስት ሐውስ /የእንግዳ ማረፊያ/ የማሠራት ዕቅድ እንደአለም ተገልጿል። ቅዱስነታቸውም በአዩትና በሰሙት የተደሰቱ መሆናቸውን ገልጸው ይህ ሙዓለ ሕፃናት ለኢትዮጵያውያን ሕፃናት የመንፈስ ዕድገትን የሚያስገኝና የማንነት ሁኔታን የሚያስገነዝብ መሆኑ ታውቆ በበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል። ከዚያም የካቲት 12 ቀን ወደ ፓርት ኤልሳቤጥ ተጉዘው ከአውሮ?ላን ማረፊያው ሲደርሱ የሀገሩ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት አቀባበል አድርገውላቸዋል። በዚህ ጉብኝት ቅዱስነታቸው በዚያ ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች ደቡብ አፍሪካውያን ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል፣ ቀድሰው አቀርበዋል። 19 የሚሆኑ ደቡብ አፍሪካውያን መዓርገ ዲቁናና ቅስና ተቀብለዋል። ከዚያም ወደጆሐንስበርግ በመመለስ ቅዱስነታቸው በሰበካ ጉባኤው አባላት መካከል የነበረው አለመግባባት እንዲፈታ አድርገዋል። ስለወደፊቱ የሰበካ ጉባኤው ሥራ መቃናትም መመሪያ ሰጥተዋል።

ሐ. ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን በሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም. የዓለም መንግሥታት ታላላቅ መሪዎችና የሃይማኖት አባቶች በተገኙበት የመላው ካቶሊክ መሪ በሆኑት ዳግማዊ ጆን ፖል የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝተዋል። በዚህ ወቅት በሮም ከአንዳንድ የሃይማኖትና የሀገራት መሪዎች ጋር ተገናኝተው ስለ ሰላም ጉዳይ ተነጋግረዋል። በሮም በምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ቀድሰው አቀርበዋል፣ ትምህርትና ቡራኬም ሰጥተዋል።

መ.ቅዱስነታቸው በዓለም አብያ ክርስቲያናት ምክር ቤትና በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ግንኙነት ክፍል ከመስከረም 4-9 ቀን 97 ዓ.ም. በሃልተን ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ የተካሄደውን ጉባኤ በጸሎት ከፍተዋል። የጉባኤው ዋና አላማ "አፍሪካ የድህነት፣ የጦርነት፣ የልዩ ልዩ በሽታና የኋላ-ቀርነት አህጉር ከመሆንዋ በቀር ለዓለም ያበረከተችው በጎ ነገር የለም" የሚለውን አፍራሽ ገጽታ መለወጥ የሚያስችል ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ውርስ /ባህል/ ለዓለም ያበረከተች ክፍለ ዓለም መሆንዋን በማሳየት ላይ የተመሠረተ ነበር። ቅዱስነታቸው በዚህ ጉባኤ ላይ የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል። ያደረጉትም ንግግር አፍሪካ የጥንታዊው የዐባይ ሸለቆ ሥልጣኔ ማዕከል፣ የጥንታዊው ሰው መገኛ፣ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ታሪክ እንደሚያሳየው ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ የተሰበከባት፣ በዘመነ ሄሮድስ ለቅድስት ድንግል ማርያምና ለልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ መጠለያ የሆነችና የተባረከች፣ ለሰው ልጅ ሕይወት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው የባህላዊ ሃይማኖት ማዕከልና የላቀ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት መሆንዋን በግልጽ የሚያስረዳ በመሆኑ የጉባኤው አባላት በጋለ ጭብጨባ ተቀብለውታል።

7.26 በ1998 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በብራዚል ፖርቶ አሌግሬ ላይ በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር 9ኛ አጠቃላይ ስብሰባ ላይ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ሁነው ተመርጠዋል።





የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አስቀድሞ እንደተገለጠው በ1948 ዓ.ም. በአምስተርዳም ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በሰባትና በስምንት ዓመት ልዩነት ዘጠኝ ስብሰባዎችን አካሂዷል። እነዚህም በ1948 ዓ.ም. በአምሰተርዳም ከተደረገው መሥራች ጉባኤ ቀጥሎ እ.ኤ.አ በኢባንስተን /አሜሪካ/ 1954፣ በኒውደልሂ /ሕንድ/ 1961፣ በኡፕሳላ /ስዊድን/ 1968፣ በናይሮቢ /ኬንያ/ 1975፣ በባንኮር /ካናዳ/ 1983፣ በካምቤራ /አውስትራልያ/ 1991፣ በሐራሬ /ዝምባብዌ/ 1998፣ በፖርቶ አሌግሬ /ብራዚል/ 2006 ዓ.ም. የተካሄዱት ጉባኤያት ሲሆኑ ቅዱስነታቸው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ፕሬዚዳንት ሁነው የተመረጡት እንግዲህ በዚህ በ9ኛው ጉባኤ ነው። ምርጫው በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ የመጀመሪያው ስለሆነ ታሪካዊ ነው። ለዚህ ምርጫ የበቁትም እስከ አሁን በፈጸሙት ዓለም-አቀፍ ተልዕኮና ባላቸው ዓለም-አቀፍ ዕውቅና ስለሆነ ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ክብር ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን የድርጅቱ መሥራች አባል ብትሆንም እስከ አሁን ድረስ በቤተ ክርስቲያኒቱ መንበር ላይ ከተቀመጡት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች መካከል ለዚህ ኃላፊነት የተመረጠ አልነበረም። ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። ስለሆነም ምርጫው በቤተ ክርስቲያናችን የረጅም ዘመን ጉዞ አንድ አዲስ ታሪክ ለማስገንዘብ ያስቻለ ነው።

## ቅዱስነታቸው ለዚህ ምርጫ እንደበቁ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፡-

" ክብሩ የእኔ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያናችን ክብር ነው፣ የተገኘው ዓለም-አቀፋዊ ክብር ይህን የመሰለ ጥንታዊ የእምነት ታሪክና ክብር ላላት ሀገር በመሆኑ ደስታው የእኔ ወይም የቤተ ክርስቲያናችን ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያውያን የአፍሪካም ጭምር ነውና ለዓለም-አቀፍ ተልዕኮ መሳካት ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦና ትብብር ሊያደርግ ይገባዋል። ሀገራችንንም ሆነ ቤተ ክርስቲያናችንን ለዚህ ታሪካዊ ክብር ላበቃ ቸር አምላክ ምስጋናችንን እናቀርባለን"ሲሉ ተናግረዋል። በእርግጥም ደስታው የሁሉም ነው። ይህንም ከየአቅጣጫው ከጉረፈው የደስታ መግለጫ ማረጋገጥ ይቻላል። ከሀገር ውስጥም ሆነ ውጭ የጉረፈው የደስታ መግለጫ ብዙ ቢሆንም ለአብነት ያህል የሚከተለውን መጥቀስ ይቻላል።

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ ወቅዱስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት ሁነው በመመረጠዎ እንኳን ደስ አለዎ፤ ለረጅም ዓመታት እርስዎንም ሆነ በኢኩመኒካል እንቅስቃሴ ያለዎትን ልምድና ጽኑዕ አላማ ስለማውቅ ለኢኩመኒካል ጥንካሬና እድገት ዓይነተኛ ለውጥ እንደሚያስገኙ እርግጠኛ ነኝ፡፡ በዚህ የጋራ ኢኩመኒካል ትግል ምንጊዜም ከጎንዎ የማልለይ መሆኔን ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ፤ ለዚህ የኢኩመኒካል ተልዕኮ መሳካት ልዑል እግዚአብሔር የመንፈስና የአካል ጥንካሬ እንዲሰጥዎ ጸሎቴ ነው፡፡

## በክርስቶስ የእርስዎ አራም አንደኛ
## የሲሲሊያ /የኪልቅያ/ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት /ካቶሊኮስ/

ብፁዕ ወቅዱስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሁነው በመመረጠዎ እንኳን ደስ አለዎ ስል ታላቅ ደስታ ይሰማኛል፡፡ ከጠቅላላ ጉባኤው ዋና ተግባራት አንዱ በጉባኤው መካከል ባሉ ጊዜያት የሚያገለግሉ ስምንት ፕሬዚዳንቶችን መምረጥ ነው፡፡ በፖርቶ አሌግሬ ብራዚል ከፌብርዋሪ 14-23 ቀን 2006 ዓ.ም. የተካሄደው 9ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ከስምንቱ ፕሬዚዳንቶች አንዱ አድርጎ መርጦዎታል፡፡ እኔም በሚቀጥሉት 7-8 ዓመታት ማለት እስከ 10ኛው ጉባኤ ድረስ ባሉት ጊዜያት ከቅዱስነተዎ ጋር ለመሥራት በጉጉት እጠባበቃለሁ... ከላይ እንደተገለጠው ፕሬዚዳንት በመሆንዎ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልም ሁነዋል... በመሆኑም በድጋሚ እንኳን ደስ አለዎት እላለሁ፡፡

## የእርስዎ ሪበረንድ ዶ/ር ሳሙኤል ኮብያ
## የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዋና ጸሐፊ

አስቀድሞ እንደተገለጠው ይህ የደስታ መግለጫ መልእክት ለአብነት ያህል የቀረበ እንጂ ይህ ብቻ ነው ማለት አይደለም፡፡ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የተላከው የደስታ መግለጫ መልእክት እጅግ በርካታ ነው፡፡ ሁኖም በሌላ መጽሔት ራሱን ችሎ የወጣ ስለሆነ በዚህ አጭር ጽሑፍ ሁሉንም ማስፈሩ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርን የተልዕኮ እንቅስቃሴ ለማስፋፋትና ለማጠናከር ጠንካራ መሪዎች ያስፈልጉታል፡፡ ስለዚህ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የድርጅቱ ፕሬዚዳንት ሁኖ መመረጥ ይህን ምኞት ዕውን ለማድረግ የሚያስችል እንደሚሆን የሁሉም እምነት ነው፡፡

7.27 በ1998 ዓ.ም. በሐምሌ ወር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት በሞስኮ በተካሄደው የዓለም የሃይማኖት መሪዎች ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል፡፡ ቅዱስነታቸው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትን አስከትለው ሞስኮ ሲገቡ ደማቅ አቀባበል የተደረገላቸው ሲሆን በጉባኤው ላይ ንግግር አድርገዋል፡፡ በአደረጉትም ንግግር የዓለምን ሰላም ለማረጋገጥ ውይይትና መቻቻል፣ የሀብት ክፍፍልና የንግድ ነፃነት አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በጉባኤው ላይ የተገኙት የሃይማኖት መሪዎች በአወጡት የውሳኔ አሳብ የሰው ልጅ ክቡር ፍጥረት በመሆኑ ለሰው ልጅ ሕይወት ክትርፍና ከንብረት ክምችት በላይ ዋጋ ሊሰጠው እንደሚገባ፣ አክራሪነትና ጽንፈኝነት እንዲሁም በሃይማኖት ሽፋን የሚደረገው ማንኛውም ጥቃት ተቀባይነት የሌለው መሆኑንና እንዲሁም ሁሉም ሀገራትና ዜጐች ያላቸውን ሀብት በነፃነትና በእኩልነት የመጠቀም መብታቸውን እንዳይነፈጉ ለርእሳነ ብሔራትና ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብእ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ በሞስኮ በተካሄደው በዚህ ስብሰባ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት፣ የእስልምና፣ የቡዲዝምና የሌሎችም እምነት ተከታዮች መሪዎች ተገኝተዋል፡፡ በስብሰባው ወቅት ቅዱስነታቸው ከሩስያው ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ዳግማዊ አሌክሲ ጋር ተገናኝተው የተነጋገሩ ሲሆን የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በትምህርቱ ዘርፍ ለመርዳት ያላትን ፍላጐት ፓትርያርክ አሌክሲ ገልጸዋል፡፡

7.28 በ1998 ዓ.ም. በነሐሴ ወር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት በዋሽንግተን፣ በጀኔቭ፣ በአሲሲ ኢጣልያ በተካሄዱ ዓለም-አቀፍ ጉባኤያት ላይ ተገኝተው ተሳትፈዋል፡፡

ሀ. በዋሽንግተን የተካሄደውን ጉባኤ በሚመለከት ቅዱስነታቸው በዚህ ጉባኤ ላይ የተገኙት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤንና የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤን በመወከል ሲሆን በዚህ ጉባኤ ላይ 50 የአፍሪካ የሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎችና ታዋቂ ባለሀብቶች፣ ከአሜሪካ 50 ታዋቂ ሰዎች፣ የኮንግሬስ አባላት፣ የኮንግሬሱ ኮሚቴ፣ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣናትና የርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ተወካዮች የተገኙ ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የዓለም ባንክና ሌሎች የሚመለከታቸው ዓለም-አቀፍ ተቋማትና የረድኤት ድርጅቶች ተወካዮችም ስብሰባውን ተሳትፈዋል፡፡ ቅዱስነታቸው ስብሰባውን ተሳትፈው ከተመለሱ በኋላ በመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት በሰጡት መግለጫ አፍሪካ ለረጅም ጊዜ በቅኝ ግዛትና የእርስርስ ግጭቶች የተጐዳች በመሆንዋ ሀብታም ሀገሮችና ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች ለአፍሪካ የሚሰጡትን የልማት እርዳታ አጠናክረው እንዲቀጥሉ በጉባኤው ላይ ግልጽ መልእክት መተላለፉን፣ በአፍሪካ የእርስ በእርስ ግጭቱን የሚያባብሰው የጦር መሣሪያ ዝውውር መኖሩ ሲሆን የበለጸገው ዓለምና የአሜሪካ መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡ መተላለፉንና ጉዳዩን የሚከታተሉ ተወካዮችም መመረጣቸውን፣ በጤናውም ዘርፍ የአፍሪካ ሕዝቦች በኤች አይ ቪ ኤድስና በወባ እየተጠቁ መሆናቸውን ለዚህ ጥቃት የተጋለጡትም አፍሪካ ለዘመናት በደረሰባት አድልዎና መገለል ምክንያት መሆኑን በመግለጽ የአፍሪካውያን [illegible] ቡድን ድምፁን ማሰማቱን ገልጸዋል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

በመቀጠልም ቅዱስነታቸው በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ማነጋገራቸውንና ኢትዮጵያውያኑ ከመቸውም በበለጠ አንድነትንና ፍቅርን ተላብሰው ማየታቸውን ገልጸው ስለእነሱ የሚወራው ሁሉ አሉባልታ ሁኖ እንደአገኙት አስረድተዋል። ቅዱስነታቸው በጉባኤው ወቅት በአሜሪካ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያዎች በአፍሪካ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ላይ ያተኮረ ቃለ ምልልስ ማድረጋቸው ታውቋል።

ለ. የጀኔቩን ጉባኤ በሚመለከት ቅዱስነታቸው በሰጡት መግለጫ ጉባኤው የተካሄደው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ እንቅስቃሴን ለመመርመር፣ ለማሻሻልና ለማጠናከር መሆኑን ገልጸው ስለ ሰላም፣ ጦርነትና ችግር በአንድ ላይ ሁኖ መነጋገርና ስለመፍትሔው ተግባራዊነትም በጎብረት መንቀሳቀስ፣ ሰላም በሁሉም ሰው አእምሮ እንዲኖር በተለያየ ምክንያት የተጐዱ ወገኖችን መርዳት፣ አመለካከቶችንም በውይይት ማስታረቅ ወሳኝ መንገድ መሆኑን አስረድተዋል።

ሐ. በአሲሲ ኢጣልያ የተካሄደውን የዓለም የሃይማኖት መሪዎች ጉባኤን በሚመለከት ቅዱስነታቸው ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት የመሩ ሲሆን ጉባኤው ማንኛውንም ጽንፈኛ አመለካከት አውግዟል። በመቻቻልና በመመካከር የሰው ልጆች በሰላም እንዲኖሩ ማስቻል የሁሉም ሃይማኖት ሥነ ምግባር መሆኑንም አውስቷል።

7.29 በ1999 ዓ.ም. በመስከረም ወር ቅዱስነታቸው በናይሮቢ ኬንያ የሚገኘውን የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ጽ/ቤትን ጐብኝተዋል። በጉብኝታቸውም ወቅት በአደረጉት ንግግር "አሁን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ያገኘነውን የኃላፊነት ዕድል ተጠቅመን አህጉራችንን ከጉስቁልና ለማላቀቅ መሥራት አለብን ... አሁን አፍሪካውያን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ያገኙት ኃላፊነት በታሪክ ተገኝቶ እያውቅም። ስለዚህ ሁላችንም በመተባበር ፍሬያማ የሆነ ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል... የተገኘው ኃላፊነት ከባድ ነው፤ ካልሠራንበት ልንወቀስበት እንችላለን" በማለት አስገንዝበዋል። ቅዱስነታቸው ይህን ያሉት በአሁኑ ጊዜ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዋና ጸሐፊ አፍሪካዊ ከመሆናቸውም በላይ አርሳቸውም በአሁኑ ጊዜ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ፕሬዝዳንት ሁነው ስለተመረጡ አፍሪካውያን ያገኙትን ይህን የተደራረበ ኃላፊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ቅዱስነታቸው ጽ/ቤቱን በጐበኙበት ወቅት የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፕሬዝዳንት፣ ዋና ጸሐፊና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የተገኙ ሲሆን የተገኙት አባላት ቅዱስነታቸው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ፕሬዝዳንት ሁነው መመረጣቸው የአፍሪካውያን ኩራት መሆኑንና በሥራ ዘመናቸው አፍሪካን ለማሻሻል በሚያደርጉት ጥረት ሁሉ አብረዋቸው እንደሚሠሩ ገልጸው ጽ/ቤቱ ያዘጋጀውን ሽልማት አበርክተውላቸዋል።

በሌላ በኩል ቅዱስ ፓትርያርኩ በኬንያ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ምእመናን በአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ያስገነቡትን የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መርቀዋል። በመሐል ናይሮቢ የተገነባው ይህ ቤተ ክርስቲያን በሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በተገኙበት የተመረቀ ሲሆን ቅዱስነታቸው ለምእመናኑ ሰፊ ቃለ ምእዳን ሰጥተዋል።

በናይሮቢ የተገነባው ይህ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በሀገሪቱ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተገኘ ገንዘብና ቅዱስ ሲኖዶስ በአደረገው የ500ሺህ ብር ድጋፍ የታነጸ መሆኑ ታውቋል። በምርቃቱ ላይ የተገኙት በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ዲሳሳ ድርቢሳ የኢትዮጵያውያኑን ትብብር በማድነቅ ትብብሩ ቀጣይና የማይሸራረፍ እንዲሆን በማሳሰብ በየትኛውም ዓለም ሁነን በአንድነትና በጎብረት ስንሠራ ታላቅ የበለጸገች ሀገር ትኖረናለች በማለት ገልጸዋል።





# ክፍል 8

## የነፃ ትምህርት ዕድል /አስኮላርሽፕ/

በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚደረገው የውጭ ግንኙነት ከሚያስገኘው ጥቅም አንዱ የነፃ ትምህርት ዕድል /አስኮላርሽፕ/ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር በምታደርገው የውጭ ግንኙነት ለአያሌ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በርካታ የነፃ ትምህርት ዕድል በመገኘቱ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ተልከው ቤተ ክርስቲያናቸውንና ሀገራቸውን ለማገልገል የበቁ ምሁራን ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም፣ አሁንም በማገልገል ላይ ያሉ ብዙዎች ናቸው። የነፃ ትምህርት ዕድል ከተገኘባቸው የውጭ አህጉር መካከልም በግምባር ቀደም ሊጠቀሱ የሚገባቸው ግሪክና ራሺያ ሲሆኑ አሜሪካ፣ ሮማንያ ኢንግላድና ጀርመንም በተወሰነ ደረጃ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነፃ ትምህርት ዕድል ሰጭ ሀገሮች ሁነው ቆይተዋል። ቤተ ክርስቲያናችን ልጆቿን ወደ ውጭ ሀገር ለነፃ ትምህርት የምትልከው የራሳቸውን ጥለው የሌላውን አንጠልጥለው እንዲመለሱ አይደለም፣ የራሳቸውን ለሌላው እንዲያካፍሉ እነሱም የሌላውን እንዲያውቁ ለማድረግ ነው። ዓለም-አቀፍ ዕውቀት ያለው ሰው መሆን የሚቻለውም በዚህ መንገድ ነው። የሚላከው ግን በመጀመሪያ የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት ጠንቅቆ ያወቀ መሆን ይገባዋል። ይህ ካልሆነ በሌላ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ስለሚዋጥ ለራሱ ቤተ ክርስቲያን ታማኝ መምህር ሊሆን አይችልም። ይህ ሁኔታ ከተሟላ በዕውቀት ላይ ዕውቀትን ለመጨመር ከወላጅ አብያተ ክርስቲያናት በሚገኝ የነፃ ትምህርት ዕድል ወደ ውጭ ሄዶ መማር ጠቀሜታ ያለው ስለሆነ ወደፊትም መቀጠል ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ሺህ ዘመን ውስጥ ያደረገችው የውጭ ግንኙነት ይህ እስከአሁን የታተተው ብቻ እንደሆነ መገመት አይቻልም። በመሪዎችና በመልእክተኞች ደረጃ የተደረገው የውጭ ግንኙነት ከዚህም ሊሰፋ ይችላል። በዚህ ጽሑፍ የተካተተው በታሪክ ተመዝግቦ የተገኘውና የጐላው ብቻ ነው። ዓለም-አቀፋዊነት በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም በበለጠ እየሰፋና እያደገ የመጣ የክርስትናው ዓለም ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን ወደፊትም በሦስተኛው ሺህ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ የበለጠ የውጭ ግንኙነት ማድረግ ይጠበቅባታል። ሁኖም ይህን ተልዕኮ ለመፈጸም ዓለም-አቀፍ ዕውቀት ያለው የሰው ኃይል ያስፈልጋታል። ለዚህም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ደረጃ ማሳደግና ማጠናከር ግድ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያናችንን ከሁለተኛው ሺህ ወደ ሦስተኛው ሺህ ክፍለ ዘመን ለመሸጋገር ያበቃ አምላክ ሦስተኛውንም ሺህ ክፍለ ዘመን በሰላም አስጀምሮ በሰላም እንዲያስፈጽምልን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

ቅዱስነታቸው በግብፅ ካይሮ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳና ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሐራም ካሽሽያን ጋር ስለ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ውይይት ባደረጉበት ወቅት



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 13

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መንግሥት በየዘመናቱ

## ክፍል 1

### ከ1ኛው መቶ ዓመት እስከ 16ኛው መቶ ዓመት መነሻ ድረስ

ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና ከአበው፤ በሕገ ኦሪት ከመሣፍንቱ፤ ከነገሥታቱ፤ ከነቢያቱ፤ ከካህናቱ፤ በሕገ ወንጌል ከሐዋርያትና ከተከታዮቻቸው ጋር የእግዚአብሔር ቤተ ሰብእ ሁና በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ ዕጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ የኖረች፤ የምትኖር ሀገረ እግዚአብሔር ናት ፡፡

ሙሴ በኦሪት የጻፈለት፤ ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት፤ ሱባኤ የተቆጠረለት ጊዜው ደርሶ በጊዜው ጊዜ ሰውን ለማዳን ቃለ እግዚአብሔር ወልድ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኖ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በዳዊት ከተማ ቤተ ልሔም ምድረ ኤፍራታ በአምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመተ ፍዳ፤ ዓመተ ኵነኔው ፍጻሜ ተወለደ /ገላ 4 ቁ. 4-5 ሉቃ. 2 ቁ. 7/ ዓመተ ፍዳው፤ ዓመተ ኵነኔው አክትሞ፤ ልደተ ክርስቶስን መነሻ በማድረግ በዐለ ዕሥራ ምዕት ዓመተ ምሕረትን በማክበር ላይ እንገኛለን ፡፡

ይሁንና ሕገ ኦሪቱ ትንቢት፤ ሕገ ወንጌሉ የትንቢቱ ፍጻሜ በመሆኑ፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሕገ ወንጌልን የተቀበሉት ሕገ ኦሪትን መሠረት በማድረግ ነው፤ ከዚህ አንጻር ያለው ሁኔታ ሲታይ አንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አስተዳደርን የምታከናውነው በሕገ ወንጌሉ መሠረትነት ነው ፡፡

ኦሪት ዘፍጥረትና መጽሐፈ ኩፋሌ የሁሉንም ነገር አጀማመር የሚያስረዱን፤ በሃይማኖት ትምህርት የሚታየውና የማይታየው ሁሉ በእግዚአብሔር የሆነበት የሕገ ልቡናው ታሪክ መነሻ ሲሆን፤ ጊዜን መቁጠርና መቈጣጠር፤ የሥራ እንቅስቃሴንም ማድረግ የተጀመረውም ከዚያኑ ጊዜ ጀምሮ መሆኑ ግልፅ ነው ፡፡ በየዓመቱ መስከረም አንድ ቀንን በታላቅ መንፈሳዊ ስሜትና ስነ ሥርዓት የምናከብረው በቤተ ክርስቲያናችን ባሕረ ሐሳብ ዘመን አቈጣጠር ስሌት መሠረት ነው፡፡
የአቈጣጠሩም ሒደት የሚገለፀው፤

- በዐውደ ዕለት፤
- በዐውደ ወርኃ፤
- በዐውደ ዓመት፤
- በዐውደ አበቅቴ፤
- በዐውደ ዓቢይ ቀመር፤
- በዐውደ ማዕከላዊ ቀመር፤
- በዐውደ ንዑስ ቀመር ነው ፡፡

በእነዚህ በሰባቱ ዐዕዋዳት መስፈሪያና መቁጠሪያ፤ በሱባኤ፤ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት፤ ሕገ እግዚአብሔር የሚነገርበት፤ የበዐላቱ የአጽዋማቱ መደብ የሚታወቅበት፤ የዘመናቱ ሒደት ተተምሮ የሚታወጅበት ርእሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ ይባላል ፡፡ በዚህ ሒደት መሠረት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት መነሻ ሆኖ የየዘመናቱን የአቈጣጠር ስሌት በመከተል እስካሁን የተደረሰበት በግዕዙ ዘይቤ ፳፤ በተለመደው አባባል 2000 ዓመተ ምሕረት መሆኑ ነው ፡፡





‹‹እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አስቀድሞ ሐዋርያትን ሁለተኛም ነቢያትን ሦስተኛም አስተማሪዎችን፤ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ ርዳታንም አገዛዝንም አድርጓል›› ይላል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (1ኛ ቆሮ. 12:28)

በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ካህናቱን ሕዝበ ክርስቲያኑን በሕግና በሥርዓት ለመምራት፤ ለማስተዳደርና ለመርዳት የወጣውን ሕግና የአፈጻጸሙን ቅደም ተከተል ጠብቆ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማ ተግባራዊ ማድረግ ነው፤ በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው አንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት በመሆኗ አስተዳደሯን በተመለከተ ሕግንና ሥርዓትን ሠርቶላታል፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ሑሩ ወመሐሩ ኵሎ አሕዛበ ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሱ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ›› በማለት ለሐዋርያት ዝርዝር መመሪያን በመስጠት በየሀገረ ስብከታቸው መድቦአቸዋል፤ በዚሁ መነሻነት የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አጀማመርና አፈጻጸም ስፋትንና ጥልቀትን እያገኘ ሔዷል ፡፡

ቅዱሳን ሐዋርያት መነሻቸው ኢየሩሳሌም ጽርሐ ጽዮንን፤ መዳረሻቸው የዓለም ዳርቻን አድርገው፤ በዓለም ተሰማርተው ዓለሙን ሁሉ የክርስቶስ ቤተ ሰብእ፤ የክርስቶስ ተከታይ፤ የክርስቶስ ወገን ያደረጉት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ነው ፡፡

የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ፓትርያርክን፤ ሊቃነ ኤጲስ ቆጳሳትን ኤጲስ ቆጳሳትን ካህናትን፤ ዲያቆናትን ምእመናን ምእመናትን ያካተተ፤ የሚያካትት ነው ፡፡

እነዚህም በየሥራ መደባቸው በቤተ ክርስቲያን አመራር መንፈሳዊውንና ማኅበራዊውን አስተዳደር የሚፈጽሙ ናቸው ፡፡

አስተዳደር ማለት በወጣው፤ በሚወጣው ሕግና ስነ ሥርዓት መሠረት የአፈጻጸሙን መመሪያ ጠብቆ እቅዱ ግቡን እንዲመታ ተግባራዊ ማድረግ ነው ፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ የቤተ ክርስቲያኒቱም ታሪክ ፤ የሀገሪቱ ታሪክ መሆኑ ግልጥ ነው፤ እንደታሪክ ባለሙያ፤ በኢትዮጵያ የታሪክ ገጽታ ሁለቱን ነጣጥሎ ማስቀመጥ የማይቻል መሆኑ የተረጋገጠ ዕይታ አለው ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ነን ከሚሉት የምሥራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ቀደምትነት ያላት ለመሆኗ ታሪክ ይመሰክራል፡፡

ኢትዮጵያ የክርስትናውን እምነት የተቀበለችው በሠላሳ ዐራት ዓመተ ምሕረት በጃንደረባው ሐዋርያነት ሲሆን /የሐዋ. ሥራ. 8፡ 26-40/ የአበው ሐዋርያትን ፈለግ ተከትላ ስብከተ ወንጌልን በአኵስም ቤተ መንግሥትና በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ በማሰማት ቆይታ ከጊዜ በኋላም በዐራተኛው መቶ ዓመት ኤጲስ ቆጳስ ተሾሞላት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም ጀመረች ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያነት ሥራዋን መፈጸም የጀመረችው በቅዱስ ፍሬምናጦስ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ዘመነ ክህነት መሆኑ ግልጥ ነው ፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ከሐዋርያትና ከተከታዮቻቸው ያገኘቻቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት መመሪያዋ በማድረግ ትውልዱን በማስተማር ከዚህም ጋር የተቀደሰ ባህሏን ሥርዓቷንና ቀኖናዋን በመጠበቅ ተተኪውን ትውልድ በማስተማር ላይ ትገኛለች ፡፡

ከ34 ዓ.ም. እስከ 4ኛው መቶ ዓመት ድረስ በኢትዮጵያ የሐዋርያነት ሥራ የተካሔደው የቤተ መንግሥት ሐዋርያ በሆነው ኢትጵያዊው ጃንደረባ ነበር፤ ከጊዜ በኋላም በ4ኛው መቶ ዓመት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጳስ የቅዱስ ፍሬምናጦስ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን መገኘት ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም ወሳኝ ሁኖ ተገኝቷል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ዐራተኛው መቶ ዓመት በቅዱሳን ነገሥተ ኢትዮጵያ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት፣ በቅዱስ ፍሬምናጦስ ዘመነ ክህነት ስብከተ ወንጌል የሰፋበት፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር አምሮ፣ ሰምሮ የታየበት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ብሔራዊት የሆነችበት ጊዜ ነበር ፡፡

4ኛው መቶ ዓመት በቅዱስ ፍሬምናጦስ ሰላማ ክሳቴ ብርሃን የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም፣ የቅዳሴው አገልግሎት ዳብሮ የታየበት፣ ቅዳሳት መጻሕፍት ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከነገረ ዮናኒ ወደ ግዕዝ ቋንቋ የተተረጉመበት ጊዜ ነበር ፡፡ በኢትዮጵያ የክርስትናው ታሪክ ከቤተ መንግሥቱ ተነሥቶ ወደ ሕዝቡ የወረደው መነሻውን ቤተ መንግሥት በማድረጉ ወደሕዝቡ ለመድረስ ችግር አላጋጠመውም፡፡

ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያነት ሥራ ይፋ የሆነው በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት በቅዱስ ፍሬምናጦስ ሰላማ ክሳቴ ብርሃን ዘመነ ክህነት መሆኑ ግልጥ ነው ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያላ የኬልኬዶንን ጉባኤ ከማይቀበሉት አኃት አብያተ ክርስቲያናት አላዷ ናት ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረተውን፣ ሐዋርያት ያስተማሩትን፣ በሦስቱ ጉባኤያት የተወሰኑትን ማለት በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ 318 ቅዱሳን አበው በ325 ዓ.ም. በኒቅያን 150 ቅዱሳን አበው በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ፣ 200 ቅዱሳን አበው በ431 ዓ.ም. በኤፌሶንን ያስተማሩትንና የወሰኑትን እነዚህም ቅዱሳ ን አበው ትምህርትና ውሳኔ ጋር የሚተባበሩ በየጊዜው የተነሡ ቅዱሳን አበው የወሰኑትንና ያስተማሩትን የእነርሱንም የተቀደሰ ሥርዓታቸውን አምናና ተቀብላ የምታስተምር ናት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋር አንድ የምትሆን ክርስቶስን በተዋሕዶ አንድ አካል፤ አንድ ባህርይ ሆነ ብላ የምታምን የሀገሪቱን ሕልውና በታሪክ፣ በነፃነት፣ በባህል፣ በስነጽሑፍ፣ በትምህርት ወዘተ. ጠብቃ የኖረችና የምትኖር ጥንታዊት፣ ሐዋርያዊት፣ ብሔራዊት፣ ታሪካዊት፣ ሉአላዊት እናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት ፡፡

ከዚህ አንፃር እግዚአብሔር አምላካችን፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን፤ ቤተ ክርስቲያን እናታችን የማይል ኢትዮጵያዊ የለም ፡፡

ከዚህም ጋር ተሰአቱ ቅዱሳን በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን የተደረገው ጉባኤ ባስከተለው የምሥጢረ ሥጋዌ፣ ትምህርተ ሃይማኖት ልዩነት ምክንያት ከቢዛታይን ግዛት ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ የመጡና በዐራተኛው መቶ ዓመት በፍሬምናጦስ ሰላማ ክሳቴ ብርሃን እንደተደረገው ሁሉ በዚህም ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ከፅርዕና ከመሳሰሉት ጥንታውያን የሥልጣኔ ቋንቋዎች ወደ ግዕዙ ብሔራዊ ቋንቋ የተረጎሙበት፣ ገዳማዊ ሕይወት የመሠረተበት ጊዜ ነበር፡፡

ተሰዓቱ ቅዱሳን በስብከታቸው፤ በድርሰታቸው፤ በትርጓሜያቸው፤ በስነ ጽድቃቸው፣ በቅድስናቸው፣ በትምህርታቸው፣ በተአምራታቸው፣ በአመራራቸው፤ በሕዝበ ክርስቲያኑ ከመወደዳቸውም በላይ ገዳማዊ ሕይወትን መሥርተው አልፈዋል ፡፡ ከዚህም ጋር በስድስተኛው መቶ ዓመት የቤተ ክርስቲያናችን በአጠቃላይ የሀገራችን ኢትዮጵያ የውዳሴ የቅዳሴ፣ የዝማሬ ዜማ ስልቶች በግዕዝ፣ በአራራይና በዕዝል በፈቃደ እግዚአብሔር በኢትዮጵያዊው አባት በቅዱስ ያሬድ የተደረሱበት የዜማ ስልትና የስነ ጽሑፍ ውበት የታየበት ወቅት ነበር፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ በ7ኛው መቶ ዓመት ሰሜን አፍሪካና መካላለኛው ምሥራቅ በሰለሙ ዓረቦች በመወረሩና ይህም ሁኔታ ከጊዜ በኋላ በ8ኛው መቶ ዓመትና ከዚያም ወዲህ በቀይ ባሕር አካባቢ ቀይ ባሕርን ተከትሎ እየሰፋ በመምጣቱ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመካከለኛው ምሥራቅ የ ክርስትናው ዓለም ጋር የነበራቸው የአስተዳደር ግንኙነት ተቋረጠ ።



ይሁንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊት ከሆነችበት ከዐራተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥገኛ ሆና በመገኘቷ፤ በሕዝቡ ቋንቋ የሚናገር፣ የሚቀድስ፣ የሚያስተምር፣ ቀድሶ ቆርቦ የሚያቆርብ፣ የሚያስተዳድር ኤጲስቆጶስ ባለመገኘቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገትና አስተዳደር የታሰበውን ያህል ሊፋጠን አልቻለም፤

ከዐራተኛው እስከ ዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት ድረስ ከዚያም በይቀጥላል ከግብፅ በየጊዜው ከሚመጡ ኤጲስ ቆጶሳትና ከሕገ ኦሪቱ አስተዳደር ሲያያዝ በመጣው ልማድ መሠረት ሲቀ ካህናት እየተባለ በሚጠራው ኃላፊ አመራር ስጭነት ቤተ ክርስቲያን ስትተዳደር ቆይታለች፤ መተዳደሪያዋም ከነገሥታቱ፤ ከመሳፍንቱ፣ ከመኳንንቱና ከወይዛዝርቱ በሚገኝ ድጎማ ነበር እንጂ ሌላ መተዳደሪያ ገቢ እንዳልነበራት ከታሪክ ሠነዶች መረዳት ተችሏል፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት ከነጋሢው ከአፄ ይኩኖ አምላክ የተገኘ የሲሦ መንግሥት ሀብትና ንብረት እንደነበራት በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል ፡፡

በኢትዮጵያ ከዐራተኛው መቶ ዓመት እስከ ዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት በይቀጥላልም እስከ ዐሥራ አምስትኛው መቶ ዓመት በነበሩት ዘመናት በመካከሉ በየጊዜው ችግር ቢያጋጥምም ሁለንተናዊ የሆነ አርኪ የቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ አስተዳደር ከተፈጸመባቸው ዘመናት አንዱና የመጀመሪያው ክፍል ሲሆን፤ ከዘጠነኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ለዓርባ ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ የሆነ የፖለቲካ ቀናና ይዛ በተነሣችው የክርስትናው ታሪክ ተቃዋሚ

www.ethiopianorthodox.org

በዮዲት /በጉዲት/ ቤተ ክርስቲያናችንና ሀገራችን ብዙ ቅርሶችን አጥተዋል፤ የብዙ ሰዎችም ሕይወት ጠፍቷል፤ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ የሀገሪቱና የቤተ ክርስቲያኒቱም አስተዳደር ለስደት ተዳርጓል ።

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት የቀዳሹን ሲሦ መንግሥት ካገኘች ወዲህ አስተዳደርዋ እየሰፋና እያደገ መጥቷል፤ ካገኘችውም መተዳደሪያ በተጨማሪ በየጊዜው የተነሡ ቅዱሳን ነገሥታት፤ መሳፍንት፤ መኳንንትና ወይዛዝርት ለቤተ ክርስቲያን የሚሆን መተዳደሪያን በመመደብ አድባራትን ሲገድሙ፤ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ሲደብሩ ኑረዋል፤ ከዚህም ጋር ከሀብታሞችና ከድሆች ምእመናንና ምእመናት በስእለትና በስጦታ መልክ የምታገኘው ገቢም በቀላሉ የሚገመት አልነበረም፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነገሥተ ኢትዮጵያ ‹‹ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ፅገሌ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ›› እየተባሉ በብሔራዊቷ ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ ጸሎት መንገሥ የጀመሩት፤ ከዐራተኛው መቶ ዓመት ከአብርሃ ወአጽብሐ ነገሥተ ኢትዮጵያ ጀምሮ እስከ ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ መሆኑ ግልጥ ነው፡፡
ንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣኑን ሲቀበል ሕዝቡን በፍትሕና በርትዕ በፈሪሃ እግዚአብሔር እንደሚያስተዳድር ቃለ መሐላ ተቀብሎ ሥርዓተ ጸሎት የሚደርስለት መሆኑ ነው፤ የንጉሡ በሕዝቡ ላይ መንገሥ በፈቃደ እግዚአብሔር ይሁን እንጂ ፍላጎቱና ጥያቄው ከሕዝቡ የሚቀርብ መሆኑ ግልጥ ነው ። (1ኛ ሳሙኤል ም.10)

በዚሁ መሠረት ከዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የተሠራው የጥንቱ የኢትዮጵያ አስተዳደር ሥርዓት በ3ት ምድቦች የተቀመጠ ነው ።

## የግብር ስማቸውም፤

-የነጋሽ፤
-የአንጋሽ፤
-የቀዳሽ፤ ተብለው ይታወቃሉ ።

አንጋሽ፡- ሕዝብ ነው፤ ሥርዓቱን ወዶና ፈልጎ የተቀበለው ነውና፤
ነጋሽ፡- የተባለው የአስተዳደሩን ኃላፊነት በእግዚአብሔር ፈቃድ ከሕዝቡ የተቀበለ ስለሆነ ንጉሡ ሁሉንም በየወገኑ ያስተዳድራል፤

ቀዳሽ፡- የተባሉት ካህናት ናቸው፤ ለሀገሩ፣ ለሕዝቡ ደኅንነትና ሰላማዊ ሕይወት መገኘት በቅዳሴ በውዳሴ የሚተጉ ከመሆናቸውም በላይ በመንፈሳዊውና ማኅበራዊው ኑሮ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ነው፡፡

ቀደም ብሎ እንደተነገረው ይህ ዓይነቱ አሠራር ከዐሥራ ሦስተኛው እስከ ሃያኛው መቶ ዓመት ድረስ ጸንቶ ሲሠራበት የኖረ ነው ። በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ ከነበረው የአስተዳደር ግንኙነትና ቀረቤታ አንዱ ሌላውን የመጥቀሙ ሁኔታ መኖሩ ግልጥ ቢሆንም፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለቤተ መንግሥቱ የነበራትን ቀረቤታና ግንኙነት ያህል መጠቀም ባትችልም ተቀራርበውና ተገናኝተው፤ ተመካክረው መሥራታቸው ለሀገር፣ ለወገን፣ ለቤተ ክርስቲያን የበለጠ ጠቀሜታ ነበረው፡፡



ከዚህም ጋር ከ13ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ ማኅበራዊ አስተዳደር ይመራ የነበረው በዕጨጌዎቹ አማካይነት መሆኑ ግልጥ ነው ። ቀደም ሲል እንደተነገረው ቤተ ክርስቲያኒቱ በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ ክህነት ታገኝ የነበረው ገቢ፤

-አንደኛው ሲሦ ለነጋሽ፤

-ሁለተኛው ሲሦ ለአንጋሽ፤

-ሦስተኛው ሲሦ ለቀዳሽ፤

በሚል አሠራር የሀገሪቱና የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር በጥሩ ሁኔታ እንዲመራ ተደርጓል ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የቋሚ ንብረት ባለቤት በመሆን ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ብትላቀቅም ያላትን ሀብትና ንብረት የምታስተዳድርበት ወቅቱን የተከተለ የንብረት ይዞታ አስተዳደር ደንብ ስላልነበራት ከዚህ ጊዜ ፊትና ኋላም የራሷ የሆነ ሲኖዶስ ስላልነበረ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ችግር ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ዘግይቶ በዐሥራ አምስተኛው መቶ ዓመት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ወደ ሀገራችን ከገባው ከፍትሐ ነገሥት በቀር ሌላ ሕግና ደንብ ስላልነበረ ነው፡፡

ሲኖዶስ ማለት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለመወሰን የሚደረግ በፓትርያርክ ሰብሳቢነት የሊቃነ ኤጲስ ቆጳሳት፣ የኤጲስ ቆጳሳት ጉባኤ ነው ። ሲኖዶስ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ለመወሰን በሐዋርያት ጊዜ ተጀምሯል፤ ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ሊቃነ ኤጲስ ቆጳሳት፣ ኤጲስ ቆጳሳት ቤተ ክርስቲያንንና ዓለሙን ለማስተዳደር ሲኖዶስ በማድረግ ውሳኔን አስተላልፈዋል፤ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛሉ፤ እስከዓለም ፍጻሜም በዚሁ ሁኔታ ይቀጥላል ። (የሐዋ. ሥራ 15፡19-25)

- ከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን ሥልጣነ ክህነት ባለሥልጣን ቅዱስ ሲኖዶስ ነው፤ ሥልጣኑም በካህናት በዲያቆናት፣ በምእመናንና በምእመናት ሁሉ ላይ ይሠራል፤

- ካህናት የሚባሉትም ኤጲስ ቆጳሳትና፤ ቀሳውስት ናቸው፤ ዲያቆናትም ላእካነ ካህናት ይባላሉ፤ የሲኖዶስ አባላት የሚባሉትም ቅዱስ ፓትርያርኩ፤ ሊቃነ ኤጲስ ቆጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት ናቸው፤

- የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በቅዱስ ፓትርያርኩ ሰብሳቢነት ውሳኔን ሰጭዎች ሲሆኑ፤ ከኤጲስ ቆጳስነት ማዕርግ በላይ ያሉት ሁሉ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በመሆን ይሰበሰባሉ ።

- በኤጲስ ቆጳስነት ደረጃና ከዚያም በላይ ማዕርግ ያላቸው አባላት በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ናቸው፤

- በማንኛውም የክህነት ደረጃ ላይ የሚገኝ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል፣ ከትክክለኛው የቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ያፈነገጠ፤ በመናፍቅነትና በክህነት ጉድለት የወደቀ እንደሆነ፤ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የመለየትና የመወገዝ ውሳኔ ከተላለፈበት ከቅዱስ ሲኖደስ አባልነት ይወገዳል፤ የሚወገደውም በቅዱስ ሲኖዶስ ይፋ በሆነ ውሳኔ ነው ።

- ቅዱስ ሲኖዶስ ለመሠረተ እምነትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ እንደመሆኑ፤ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲወራረድ ጸንቶ የመጣውን የእምነት ሥርዓት ያለምንም ለውጥ ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት አለበት ።

- የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ይግባኝ የሌለበት የመጨረሻ ውሳኔ ነው፤

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰበሰበው በፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

በሌላም ዘይቤ ‹‹ሲኖዶስ›› የሚለው ቃል ‹‹ጉባኤ›› ወይም ስብሰባ ማለት ነው፤ በኢትዮጵያ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቅዱስ ሲኖዶስ ባይኖርም በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የተከበበ የተጠናከረ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር በሚመለከት ሲኖዶስን አህሉ የሚሠራ ‹‹የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር›› እየተባለ የሚጠራ አንድ የአስተዳደር ጉባኤ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው ። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ጊዜው እንደ አካባቢውና እንደ ሁኔታው በየጊዜው መመሪያዎችን እያወጣች ከመንግሥትም ጋር እየተመካከረች መመሪያንና ደንቦችን እየተቀበለች ስትተዳደርና ስታስተዳድር ቆይታለች፤ ይህም የሚያመለክተው ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ አንድ ሁነው ተባብረው ይሠሩ የነበር መሆኑን ነው፡፡

በሌላም መልኩ ከሐዋርያት ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና አመራር የተሰበሰቡ ሊቃውንትና የቤተ ክርስቲያን አበው ያስተላለፉአቸው የተለያዩ ውሳኔዎች በአንድነት ተጠቃለው ‹‹ሲኖዶስ›› በሚል ስያሜ ይጠራሉ ።

በፀሥራ አምስተኛው መቶ ዓመት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የቤተ መንግሥቱና የቤተ ክህነቱ የአስተዳደርንና የሥራ ግንኙነትን፣ ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን፣ የበዐላት አከባበርን፣ በኢየሩሌም ስለሚገኙት ገዳማተ ኢትዮጵያ፣ የወጣውን ሕግ በሚመለከት የተለያዩ መመሪያዎችና ደንቦች እየተዘጋጁ አገልግሎትን ይሰጡ ዘንድ በአዋጅ የተሰጡ መሆናቸውን የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በላይ የተነገረው እንዳለ ሁኖ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ነገሥታት የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ከመንግሥታቸው አመራር ለይተው አይመለከቱትም ነበር ብለናል፤ ምክንያቱም የመንግሥታቸው ጥንካሬ ወይም ድክመት የሚለካው ከቤተ ክርስቲያን ጋር በነበራቸው የቅርብ አሠራር ግንኙነት በመሆኑ ነው ።

# ክፍል 2

## ከ16ኛው መቶ ዓመት መነሻ እስከ 19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ

ይህ እስከአሁን የተነገረው እንዳለ ሁኖ 16ኛው መቶ ዓመት የግራኝ አሕመድን አነሣሥና አወዳደቅ የምንመለከትበት ጊዜ ይሆናል፤ የግራኝ አሕመድ አነሣስ የጊዜውን አመችነት ተከትሎ የግብፆችንና የቱርኮችን ወረራና መስፋፋት ተጠግቶ የመጣ አደገኛ እንቅስቃሴ ነበር፤ ይህም የኃይል ወረራ መካከለኛው ምሥራቅን፣ ደቡብ ምሥራቅ አውሮፓን የሜድትራንያን ባሕር ተከትሎ እስከ ምዕራቡ አውሮፓ የደረሰ ሰሜን አፍሪካን ያካተተ ነበር፤ ይህም አደገኛ አነሣስ የሁሉንም አህጉር አስተዳደር ያቃወሰ ነበር ።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን ግራኝ አህመድ ያደረሰው ጥፋትና እልቂት የ15 ዓመታት የመከሰተ ዘመን ቢሆንም በኢትዮጵያ ታሪክ በአጥፊነቱ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ዘመነ ሰማዕታት ነበር፤ በግራኝ አህመድ ወረራም ወቅት በርዳታ መልክ ከመጡት የፖርቱጋል ወታደሮች ጋር ተሰባጥረው ለፖርቹጋሎቹ ወታደሮች የንስሐ አባቶች ሁነው የመጡ የሱሳውያን እየተባሉ ይጠሩ የነበሩ መነኮሳትም እንደነበሩ ታሪክ ያስታውሰናል፤ በእነዚህም መነኮሳት ትምህርተ ሃይማኖት ምክንያት የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ጠፍቷል ።



በየጊዜው የኢትዮጵያን ገጽታ ለማጥፋትም ሆነ ኢትያጵያን ለመውረር የፈለጉና የሚፈልጉ ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ለአላማቸው መሳካት በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መደምሰስ ወይንም በተለያየ ምክንያት ማዳከም ነበር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጉዲት ብዙ ጥፋትና ጥቃት ከደረሰባት በኋላ የጠፋውን ሁሉንም ነገር እንደገና አድሳ ከከፍተኛ ደረጃ መድረሷ የታወቀ ሲሆን እንደገና በ16ኛው ክፍለ ዘመን በኦቶማን ኢምፖየር ድጋፍ ሰጭነት በሀገሩና በወገኑ ላይ ያመፀው የውስጥ ጠላት የሆነው ግራኝ አህመድ በቤተ ክርስቲያናችንና በሀገራችን ሕልውና ላይ ከባድ ጉዳትን ያደረሰበት ወቅት ነበር ብለናል ። 16ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ የጨለማው ዘመን በመባል የታወቀ ነው ። በዚያን ጊዜ ግራኝ አሕመድ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ተነሥቶ ወደ መሐል ኢትዮጵያ በመምጣት ከዚያም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ በማምራት በሀገሪቱ የነበረውን የክርስትና ታሪክ ደምስሶ የድጋፍ ሰጭውን የኦቶማን ኢምፖየርን አገዛዝ በኢትዮጵያ ለማስቀመጥ ከፍተኛ ጥረትን አድርጎ ነበር፤ ግን በጊዜው የነበረው ኢትዮጵያው ትውልድ በሃይማኖቱ የጸና፣ በስነ ምግባሩ የተዋበ፣ በሀገር ፍቅር የነደደ በመሆኑ ያን የውስጥ ጠላት ግራኝ አሕመድን ከነሠራዊቱ በእግዚአብሔር ኃይል በመደምሰስ የሀገሪቱንና የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር መልሶ ለማቋቋም በቅቷል።

የሚገርምና የሚያስገርም ነገር ቢኖር በግራኝ አሕመድ አነሣስ በሀገርና በወገን ላይ የደረሰው ጥፋትና እልቂት እንደ ተራማጅ ተቆጥሮለት በደርግ ሥር ነቀል ወታደራዊ አስተዳደር ዘመነ መንግሥት በ1969 ዓ.ም. አንድ ቀን ምሽት ተራማጅነቱ በሕዝብ መገናኛ ብዙኃን ተነግሮለት ነበር፤ ምክንያቱ ባይታወቅም በድጋሚ አልተነገረም ።

ለፀሥራ አምስት ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ከምሥራቅ እስከ መሐል ከዚያም በይቀጥላል እስከ ሰሜን ኢትዮጵያ ሀገርን ያጠፋ፣ ወገንን የጨረሰ፣ የፈጀ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት የሞከረ ጀግና ነው ተብሎ ከተጠራ ለጀግንነት ሙያ ቦታ አልተገኘለትም ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህም ጋር 17ኛውና 18ኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን የአውሮፓውያን ፍላጎት በኢትዮጵያ ላይ አይሎ የታየበት ጊዜ ነበር ። የሱሳውያን የተባሉ ካቶሊካውያን መነኮሳት ከ16ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ ትምህርተ ሃይማኖታቸውን በጎቡዕ ውስጥ ውስጡን ሲያቀጣጥሉ ቆይተው ውስጥ

ለውስጥ የተቀጣጠለው ትምህርተ ሃይማኖታቸው ይፋ የሆነው በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በ1626 ዓ.ም. ነበር ። የአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጥሩ ጊዜ አልነበረም፤ የዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ከ9ኛውና ከ16ኛው ክፍላተ ዘመን ማለት ከዮዲትና ከግራኝ አሕመድ ተያይዞ የመጣ ከነዚያ ተነጥሎ የማይታይ ዘመነ ሰማዕታት መሆኑ በኢትዮጵያ ታሪክ የተመዘገበ ነው ።

ዐፄ ሱስንዮስ የቫቲካኑ መንበረ እምነት ታዛዥና ተከታይ መሆናቸውን በይፋ አሳውቀው በ1626 ዓ.ም. መልእክታቸውን ወደ ቫቲካን-ሮም አስተላለፉ ። ከዚህ በኋላ በዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት፤

ኦርቶዶክሳውያን፣ ኦርቶዶክሳውያት እንደገና ተጠምቀው ካቶሊካውያን፣ ካቶሊካውያት
እንዲሆኑ፤ የካህናቱ ክህነትም እንዲከለስ፤
አብያተ ክርስቲያናቱም እንደገና እንዲባረኩ፤
በኦቶዶክሳውያን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተሣለው የቀለም ሥዕል ቀሪ ሁኖ በሮማውያን ባህል የተተረጐመ ምስል እንዲቆም፤ -የሮማውያን የቅዳሴ ሥርዓትና የቀን መቁጠሪያ የጎርጎርዮስ፣ ባሕረ ሀሳብ ዘመን በኢትዮጵያ እንዲሠራበት፤
ግርብና ረቡዕ መጾማቸው ቀርቶ ቅዳሜት እንዲጾም፤
የቅዳሜት ሰንበትነት እንዲሻር የሚል ሕግ ወጥቶ ታውጆ ነበር፤ ይህንም አዋጅ ያላከበረ የአካል [illegible] ወጥቶ ነበር፤

www.ethiopianorthodox.org

በዚህም ጊዜ ከላይ እንደተገለፀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማንያን ‹‹ሰማዕትነት አያምልጥህ›› እየተባባሉ በመጣደፍ ከየአቅጣጫው በመሰባሰብ በበለጠ በሰሜን ጐንደር ‹‹ደንቀዝ ጐመንጌ›› እየተባለ በሚጠራው በዐፄ ሱስንዮስ ቤተ መንግሥት አደባባይ ተገኝተው ሰማዕታት የሆኑ፤ ሰማዕትነትን የተቀበሉ ኦርቶዶክሳውያን ከ8,000 በላይ መሆናቸውንና በዚህም ምክንያት ለሰባት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ የሃይማኖት ጦርነት መደረጉን የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ያረጋግጣል ፡፡ ከዚህም ጋር የኦርቶዶክሳውያኑን አፅም ከወደቀበት እየሰበሰቡ ማቃጠላቸውን፤ ኦርቶዶክሳውያን ካህናት፣ ምእመናን፣ ምእመናት፣ ልጆች አዋቂዎች እየተመረመሩ አስቃቂ ስቃይ የተፈጸመባቸው መሆኑን ታሪክ ይነግረናል ፡፡ ዐፄ ሱስንዮስ በነገሡ በ27 ዓመታቸው ታመው አንደበታቸው ተዘግቶ የነበረ መሆኑም ይነገራል ፡፡

በዚያን ጊዜ ዐፄ ሱስንዮስ ‹‹ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ›› የሚል አዋጅ እንዲነገር የፈቀዱ መሆናቸውም ይነገራል፤ ኦርቶዶክሳውያኑም ይህን በመስማታቸው ተደሰቱ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትና አድባራትም የደስታ ደወል ድምፃቸውን አሰሙ፤ ከሞት የተረፉት ሸሽተው በየዋሻው፤ በየጥሻው ተጠግተው ይኖሩ የነበሩትም ሰባራ ስንጥራቸውን እየያዙ ወደየቤታቸው መመለሳቸው ይነገራል ፡፡ ዐፄ ሱስንዮስ መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለአቤቶ ፋሲል በማስረከብ በነገሡ በ28ኛው ዓመታቸው ሞቱ፤ ልጃቸው ፋሲል ነገሡ፡፡

ዐፄ ፋሲል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ በመሆናቸው የውጭ ሃይማኖትን ተጠግቶ የሚመጣን ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ሁነው የሚቋቋሙት፤ የአባታቸው የዐፄ ሱስንዮስ ወደባዕድ ሃይማኖት መግባት ሕዝቡን የከፋፈለ በመሆኑ፤ የአባታቸው ዐሠራር ለሀገር፣ ለወገን አደገኛም ስለነበር፤ ዐፄ ፋሲል ይህ ዓይነቱ የአባታቸው ዐሠራር እንዳይደገም ከፍተኛ ጥንቃቄን አድርገው ነበር፤ ዐፄ ፋሲል ሃይማኖታዊ፣ ወገናዊና ብሔራዊ ስሜታቸው የላቀ ነበር ፡፡

ዐፄ ፋሲል ሰላምን መመሥረትና ሀገራቸውን እንደገና ማጠናከር እንዳለባቸው በመገንዘብ ካቶሊኮችን አባረሩ፤ ከእስላሞችም ጋር ተስማምተው ሀገሪቱን በጥሩ ሁኔታ ማስተዳደር ጀመሩ፤

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መርዳት ጀመሩ፤ በ16ኛው መቶ ዓመት በግራኝ አህመድ ተቃጥሎ የነበረው የአዙስም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያንን እንደገና ዐሠሩ፤

ከዐፄ ፋሲል ሥራዎች የበለጠ ዕውቅናን ያገኘው የጐንደር መናገሻ ከተማቸውን መሥራታቸውና የቤተ መንግሥቱ ሕንፃዎች በልዩ ኪነጥበብ የተሠሩ መሆናቸው ጎልቶ ይታያል ነበር፤ ሕንፃዎቹም ከአውሮፓውያን ሕንፃዎች ጋር የሚወዳደሩ ሲሆኑ እስከ ዛሬም በመታየት ኢትዮጵያ በ17ኛው መቶ ዓመት የነበራትን ስነ ጥበብና ሥልጣኔ ያበስራሉ ፡፡

በ16ኛው መቶ ዓመት በግራኝ አህመድና በ17ኛው መቶ ዓመት በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት አስተዳደር የሱሳውያን እየተባሉ በሚጠሩ ካቶሊካውያን መነኮሳት ትምህርተ ሃይማኖት ምክንያት የጠፋው ጠፍቶ፤ የሞተው ሞቶ፤ ከሞት የተረፈውም ኢትዮጵያዊ በሞት አፋፍ ላይ እያለ ከ1768-1848 ዓ.ም. ድረስ በተራዘመው ዘመነ መሳፍንት፤ በመሳፍንት አገዛዝ ኢትዮጵያ የተከፋፈለችበት፤ የተዳከመችበት ጊዜ የነበረ፤ በዚህም አጋጣሚ እስላሞች ከ16ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ በይቀጥላል በነበረው አመች ጊዜ በመጠቀም የእስልምናውን ዜጋ ለማብዛት፤ ጠንክረው የተወራጨበት፤ መጤዎች የሃይማኖት ሰዎችም ኃይላቸውን አጠናክረው የታዩበት ወቅት ነበር፤ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ የጥፋት ድርጊትና የሃይማኖት ወረራ፤ ቅሰጣ በበለጠ ጎልቶ የታየው በምሥራቅና በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በሁሉም አቅጣጫ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

በዚህም ዘመነ መሳፍንት የካቶሊክ፣ የቅብአትና የጸጋ እምነት ተከታዮች ኢትዮጵያውያን፣ ከመጤዎቹ ረዳቶቻቸው ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮችን እስከ ማሳደድ የደረሱበት ጊዜ እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል ፡፡

ከዚህም ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብቷን፣ ንብረቷን፣ ቅርሷን ያጣችበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ ሕልውናዋም እንደ 16ኛው መቶ ዓመት በአስጊ ሁኔታ ላይ የነበረ መሆኑን ታሪካችን ይናገራል ፡፡

የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር በተለያየ ጊዜና ምክንያት የመውደቅና የመነሣት ታሪክ ያጋጠመው መሆኑ ግልጥ ሲሆን ለመረጃም ያህል፤ የውድቀቱ ዘመነ ታሪክ የሆነበት፤

- በዘጠነኛው መቶ ዓመት በዮዲት፤
- በ16ኛው መቶ ዓመት በግራኝ አህመድ፤
- በ17ኛው መቶ ዓመት በአፄ ሱስንዮስ፤
- በ19ኛው መቶ ዓመት በቱርኮችና በግብፆች፤
- በይቀጥላልም በ19ኛው መቶ ዓመት በ1880 ዓ.ም. የድርቡሾች የሃይማኖት ጦርነት፤
- በ20ኛው መቶ ዓመት በፋሽሽት ኢጣሊያ ከ1928 - 1933 ዓ.ም.፤
- አሁንም በ20ኛው መቶ ዓመት ማለት ከ1967-1983 ዓ.ም. የደርግ የ17 ዓመታት ድንገተኛና አደገኛ ሥር ነቀል ወታደራዊ አስተዳደር መሆኑ ግልጥ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጠው ከጊዜ በኋላ የመጣው ለሰማንያ ዓመታት ያህል የቆየው የከፋፍለህ ግዛው የመሳፍንቱ አገዛዝ በቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር ላይ ጥቁር አሻራን አስቀምጦ ያለፈ ነው፤ በዘመነ መሳፍንቱ የሆነው ጥፋትና እልቂቱ፤ መለያየቱ ቀጥሎ ከ1768 - 1848 ዓ.ም. ድረስ የነበረው ክፍለ ዘመን ዘመነ መሣፍንት በመባል የታወቀ ነበር ፡፡

ከላይ እንደተነገረው ኢትዮጵያ በመሣፍንት አገዛዝ በተከፋፈለች ጊዜ የምሥራቁ፣ የምዕራቡና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን፤ ወደ እስልምና ሃይማኖት በበለጠ የተለወጠው በዚያ አስከፊ በሆነ ዘመነ መሣፍንት ነበር፤ በዚያ የጨለማ ዘመን የኢትዮጵያ ኦቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታደርገውን አጥታ ተቸግራ በመከራ ላይ መከራ፤ እየጨመረ በመሔዱ

በማዕከለ ምድር ኢትዮጵያ ያለውንም ለመከፋፈል ካቶሊካውያን በመሯሯጥ ላይ ይገኙ ነበር፤ ቤተ ክርስቲያናችን በዘመነ መሣፍንት ብዙ ነገሮችን አጥታለች፤ በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ቀራንዮ ጎልጎታ ከነበሩን ብዙዎች ቅዱሳት መካናትን የተነጠቀችው በዚያው በዘመነ መሣፍንት የተመሰቃቀለ አስተዳደር ነበር ፡፡

ወደኢየሩሳሌም ይደረግ የነበረው ጉዞም የተቋረጠው በዚያው በዘመነ መሣፍንት ከፋፍለህ ግዛው ጊዜ ነበር፤ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ቀራንዮ ጎልጎታ ይኖሩ የነበሩት መነኮሳትም በሕመምና በችግር ምክንያት ያለቁበት ጊዜም ነበር፤

ከመነሻው ዘመነ መሣፍንት አንሥቶ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ጎልጎታ ቀራንዮ የነበረው ንብረታችን ይዞታችን፣ ሀብታችን ባለቤት እንደሌለው ጠፍ ቦታ ተቁጥሮ በአርመኖች፣ በግሪኮች፣ በኮፕቶችና በመሳሰሉት የተወሰደውም በዚያው ዘመን መሆኑ ግልጥ ነው

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል 3

## ከ19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ እስከ 20ኛው መቶ ዓመት 1967 ዓ.ም. መነሻ ድረስ

ይህ ዘመነ መሣፍንት በዚህ ዓይነት አስከፊ አስተዳደር ላይ እንዳለ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በድንገተኛው የዐፄ ቴዎድሮስ አነሣስ የኢትዮጵያ አንድነት ዳር ድንበር አስተዳደር ተጠብቆ ወደ ሚቀጥለው ዐረፍተ ዘመን ለመሸጋገር በቅቷል ፡፡

የካቲት 5 ቀን 1847 ዓ.ም. ደጃዝማች ካሳ በአቡነ ሰላም እጅ ተቀብተው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ ፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ መንግሥታቸውን ለማሳደግ የነበራቸው ጥበብ በጣም የላቀ ነበር፤ በውጭ አስተዳደራቸውም ኢትዮጵያ በዓለም እንድትታወቅ አድርገዋል ፡፡

በነገሡ በአምስት ዓመት በ1852 ዓ.ም. በጥቅምት ወር የእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ቄርሎስ 4ኛ ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ፤ ይህም የፓትርያርኩ ጉብኝት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያ ነበር፤ ፓትርያርኩ የመጡበትም ምክንያት፤

- ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ የሔዱት ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ኢትዮጵያን ያዩላቸው፤ ይባርኩላቸው ዘንድ ለምነዋቸው ስለነበር፤ ኢትዮጵያን ዓይተውና ባርከው ለመመለስ፤

- ዐፄ ቴዎድሮስ ከቱርኮች ጋር ተጣልተው ስለነበር ለማስታረቅ፤
- ካይሮ ያለውን የቅዱስ ማርቆስን ካቴራል ለማሳደስ አስበው ነበርና የገንዘብ ርዳታን ለመጠየቅ ነበር፤ ይባላል ፡፡

ፓትርያርኩ ኢትዮጵያ ሲደርሱ ታላቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል ፡፡ በውይይቱም ወቅት ዐፄ ቴዎድሮስ ሌላውን ጥያቄ ሁሉ በደስታ ሲቀበሉ ከቱርክ መንግሥት ጋር ዕርቅን ያድርጉ የሚለው የፓትርያርኩ ጥያቄ ዐፄ ቴዎድሮስን ስለአስቆጣቸው አልተቀበሉትም፤ እንዲያውም የሃይማኖት አባት ሁነው እንዴት ለቱርኮች አማላጅ ሆኑ በማለት ዐፄ ቴዎድሮስ በፓትርያርኩ ላይ ጥርጣሬ አደረባቸው፤ በዚህ ምክንያትም ፓትርያርኩን ወደ ዕሥር ቤት አስገቧቸው ግን የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ እንዳይጎድፍ መኳንንቱ፤ መሣፍንቱ፤ መክረው ዘክረው ለንጉሠ ነገሥቱ ሀሳብ በማቅረብ ዐፄ ቴዎድሮስ ፓትርያርኩን ከዕሥራት ፈትተው ለካቴድራሉ ማሠሪያ የሚሆን ብዙ ወርቅና የዝሆን ጥርስ ሰጥተው ወደ ሀገራቸው መለሷቸው ፡፡



በተለይ ዐፄ ቴዎድሮስ በበለጠ ያናደዳቸው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ጎልጎታ ቀራንዮ የኢትዮጵያ ይዞታ የነበሩትን ገዳማት የቱርክ መንግሥት ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አሳልፎ በመስጠቱ ተናደው በቱርኮች ላይ ለመዝመት ቁርጥ ሀሳብ አድርገው፤ ስለዚሁ ከእንግሊዝ መንግሥት የጠየቁትን የጦር መሣሪያ ማግኘት ባለመቻላቸው ከዚህ የተነሣ ዐፄ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ተጣሉ፤ ከኢትዮጵያ ታሪክ እንደምረዳውም ዐፄ ቴዎድሮስን ለሞት ያደረሳቸውም የዚሁ መነሻ መሆኑ ግልጥ ነው ፡፡

እንደቀድሞው አጠራር በጉንደር ጠቅላይ ግዛት የተወለኑ ካህናት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተገን አድርገው ዐፄ ቴዎድሮስን ሊያወናብዷቸው ቢሞክሩም ዐፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋሕዶ ሃይማኖት፤ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ ሃይማኖታዊና ሀገርን ወዳድ ኢትዮጵያዊ መሪ ስለነበሩ በወንበዴዎቹ ሙከራ ሊበረግጥ አልቻሉም ፡፡

የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዋና አላማ በመሣፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን በአንድ ንጉሠ ነገሥት ጥላ ሥር ለማስተዳደር ሲሆን አላማቸውም ተሳክቶላቸው ኢትዮጵያን አንድ አድርገው አስተዳድረዋል፤ ከእርሳቸው በኋላ የተነሡት ነገሥተ ኢትዮጵያም የእርሳቸውን አላማ በመከተል እስከ 1967 ዓ.ም. መነሻ ድረስ በተስተካከለ አስተዳደር ሕዝቡን አንድ አድርገው መርተዋል፤ ከዚህም በላይ ለማድረግ ዐፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ መንግሥት ሀሳብ አቅርበው ሳይደግፋቸው ቀርቶ ነው እንጂ ኢየሩሳሌምን የመያዝና የማስተዳደር ምኞት የነበራቸው መሆኑ ግልጥ ነው፤ ለዚህም መረጃ የሚሆነው፤

‹‹ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም፤ ዓርብ ዓርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም››
በማለት ገጣሚው የዘመረውም ከዚህ የተነሣ ነው ይባላል ፡፡

ከዚህም ጋር ዐፄ ቴዎድሮስ በዘመናቸው በኢትዮጵያ የነበሩትን ሚሲዮናውያን ሁሉ ሰብስበው ‹‹ኢትዮጵያ የራሷ የወንጌል መምህራን አሏት፤ ይልቁንስ እናንተ የሠለጠናችሁበትን፤ ለእኛም የሚያስፈልገንን የብረት ማቅለጡንና መቀጥቀጡን ቴክኖሎጂ አስተምሩን›› ብለዋቸው ነበር ይባላል፤ በጊዜው ንጉሠ ነገሥቱ የሚያስቡትን ያህል በዙሪያቸው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ሹማምንት ሁሉ ለእርሳቸው፤ የሀገር ግንባታ ዕድገት አላማ ሁሉም ተባባሪዎች ባለመሆናቸው ሀገሪቱን የማልማት ሀሳባቸው ሁሉ እንዳሰቡት ከግቡ ሳይደርስ ቀርቷል ይባላል ፡፡

ይሁንና ከዐራተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስከ ዐሥራ ሰባተኛው መቶ ዓመት ፍጻሜ ድረስ ማለት በእነአብርሀ-ወአጽብሐ፤ በእነዐፄ ካሌብ፤ በእነዐፄ ገብረ መስቀል፤ በእነ ቅዱስ ሐርቤ-ገብረ ማርያም፤ በእነቅዱስ ላሊበላና በሌሎቹም፤ በእነ ዐፄ ይኩኖ አምላክ፤ በእነ ቀዳማዊ ዐፄ ዳዊት፤ በእነዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ፤ በእነዐፄ ናኦድ፤ በእነዐፄ ገላውዴዎስ፤ በእነ ዐፄ ሠርፀ ድንግል፤ በእነ ዐፄ ፋሲልና በመሳሰሉት ዘመነ መንግሥት እንደነበረው ሁሉ፤ ከዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮም እስከ 20ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ በነበሩት ነገሥተ ኢትዮጵያ ማለት በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ፤ በዐፄ ዮሐንስ 4ኛ፤ በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ፤ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፤ በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፤ ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ በጎዘኑም፤ በደስታውም፤ በሞት በሕይወቱም አንድ ሁነው ያስተዳደሩበት፤ የሠሩበት ጥሩ ጊዜ የነበረ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል ፡፡ በእነዚህም ዘመናት የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያናችን የአስተዳደር ዕድገት በበለጠ ጎልቶ የታየበት ጊዜ ነበር፡፡

ያም ጊዜ ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ ሀገርን ለመውረር፤ ዳር ድንበርን ለማፍረስ፤ ነፃነትን ለመፈፍ በየጊዜው ከየትም የመጡትን ወራሪ ጠላቶችን፤ የሀገር ውስጥ ተፋላሚዎችንም ለመከላከል አንድ ሁነው የመከቱበት ጥሩ አጋጣሚ ጊዜ ነበር፡፡ ቤተክርስቲያናችን በዚህ ረጅም የታሪክ ዘመኗ በየጊዜው የመውደቅና የመነሳት ታሪክ ያጋጠማት መሆኑ ተደጋግሞ ተነግሯል፡፡

ቀደም ሲል እንደተነገረው ከአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ከቅዱስ ፍሬምናጦስ ሰላማ ሰሣቴ ብርሃን ዘመነ ክህነት በኋላ በ7ኛው መቶ ዓመት ሰሜን አፍሪካና መከላከለኛው ሥምራቅ በሰለሙ ዓረቦች በተወረረ ጊዜ የእስክንድርያው ኮብት ቅዱስ ሲኖዶስ በዓረቦቹ ተፅዕኖ ከእስክንድርያ መንበረ ማርቆስ ወደ ካይሮ ተዘዋውሮ ባካይሮ ባሮጌው ከተማ መአልቃ በተባለው ቦታ መሰብሰቢያውን አድርጎ «ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሣሙ ሊቀ እማዕምራኒሆሙ» «የኢትዮጵያ ሰዎች ከሊቃውንቶቻቸው መካከል ኤጲስቆጳስን አይሹሙ›› የሚል አንቀጽ በፍትሕ መንፈሳዊ ሥርዋፅ በማስገባት በ325 ዓ.ም. 318 ቅዱሳን አበው በኒቅያ ጉባኤ እንደወሰኑት በማስመሰል ጽፎ ያስገባል፤ ይህም ሥርዋፅ በሌሎቹ ጥንታውያን አብያተ [illegible] ውያን ፍትሕ መንፈሳዊ መጽሐፍ ብቻ የሚገኝ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያ ሀገራችን በመጽሐፍ መልክ ካሏት ጥንታውያን የሕግ መጻሕፍት መካከል አንዱ ታላቁና የታወቀው ፍትሐ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ነው፤ ይህም ፍትሐ ነገሥት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ቋንቋ የተተረጐመውና በሥራ ላይ የዋለው በ15ኛው መቶ ዓመት በአፄ ዘርዐያዕቆብ ዘመነ መንግሥት መሆኑን ቀደም ሲል ገልፀናል ፡፡

ፍትሐ ነገሥት የሚለው ቃል ‹‹ፍትሕና ነገሥት›› የተባሉት ሁለት ቃላት የተያያዙ ናቸው ፡፡ ትርጓሜያቸውም በፍርድ ውሳኔን በመስጠት ሕግንና ሥርዓትን ማስፈን ማለት ሲሆን ነገሥታቱ ክርስቲያኖች እንደመሆናቸው ሥጋዊውንና መንፈሳዊውን ፍትሕ ይመለከቱ ስለነበር፤ በነገሥታቱ ስም ‹‹ፍትሐ ነገሥት›› ተብሎ መሰየሙ ግልጥ ነው ፡፡ ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊና ፍትሕ ሥጋዊ ተብለው በሁለት ዓበይት ክፍላት የተከፈለ ነው ፡፡

በ1948 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ተረቆ በአዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኢትዮጵያ ይሠራበት የነበረው ሕግ ፍትሐ ነገሥት መሆኑ ግልጥ ሲሆን መንፈሳዊ ሕግነቱ አሁንም በሥራ ላይ ያለ ነው፤ ወደፊትም እስከዓለም ፍጻሜ የሚሠራ ነው ፡፡

«ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሚሙ ሊቀ ኢማዕምራኒሆሙ» የሚለው በ7ኛው መቶ ዓመት የገባው ሥርዋዕ ከዓረብኛ ወደ ግዕዙ ተተርጉሞ በመቅረቡ 318ቱ ቅዱሳን አበው የደነገጉት አንቀጽ ነው በሚል በደግነት ይሁን በየዋህነት ኢትዮጵያውያን ለ1600 ዘመናት ያህል ተቀብለውት ኖረናል፤ ከታሪካችን እንደምንረዳው ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ስሜት የነበረው በ11ኛው መቶ ዓመት የነገሠው ቅዱስ ሐርቤ ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ማርያም፣ የኢትዮጵያን ስፋት፣ የሕዝበ ክርስቲያኑን ብዛት በማየትና በመመልከት መላ ኢትዮጵያን ሾረው፣ ተዘዋውረው በሕዝቡ ቋንቋ የሚያስተምሩ፣ የሚባርኩ፣ የሚቀድሱ፣ የሚክኑ፣ የሚያስተዳድሩ ዐሥር ኢትዮጵያውያን ቆሞሳትን የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣነ ክህነት በመስጠት እንዲሾምለት በዘመኑ የነበረውን የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ዳግማዊ ገብርኤልን ጠይቆ ነበር፤ ይሁንና ከላይ የተጠቀሰውን በ7ኛው መቶ ዓመት የገባውን ሥርዋዕ ተገን በማድረግ የካይሮው ቅዱስ ሲኖዶስ ለንጉሥ ሐርቤ ተገቢውን መልስ ካለመስጠቱም በላይ ሚያዝያ ዐሥር ቀን በሚነበበው የስንክሳር መጽሐፋችን ‹‹ኢትዮጵያውያን የማይገባቸውን ኤጲስ ቆጶስነትን ስለተመኙና ስለፈለጉ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በሀገራቸው ላይ ሦስት ዓመታት ሙሉ ጠል ለመከር፤ ዝናም ለዘር ከልክሏቸው በድርቅ ቀጣቸው ›› በማለት ግብፃዊው ዳግማዊ ሊቀ ጳጳሳት ገብርኤል በታሪክ መዝገቦት ይገኛል፤ እኛም ይህን ስንክሳር እንደመልካም ነገር ሚያዝያ 10 ቀን እናነበዋለን ፡፡

ከጊዜ በኋላም በ19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ አፄ ዮሐንስ ነጉሠ ጽዮን፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን በስፋትና በጥልቀት በኢትዮጵያ ለማስተማር እንዲያመች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በራስዋ ልጆች እንድትመራ፣ እንድትባረክ፣ እንድትቀደስ በ11ኛው መቶ ዓመት በንጉሥ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት ተጠይቆ ሳይሳካ የቀረውን እንደገና በመቀስቀስ ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው እንዲሾሙላቸው በዘመኑ የነበሩትን የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ቁርሎስ አምስተኛን ጠይቀው ለጥያቄው እንዳለፈው ሁሉ ቀና መልስ ባለመገኘቱ አፄ ዮሐንስ ስለጉዳዩ ቀጠስጥንጥንያ ከሚገኘው ከአርመኑ ፓትርያርክ ጋር መጻጻፍ ጀምረው እንደነበር ታሪክ ይነግረናል ፡፡ ይህም አሠራር ማርቆስ አባታችን፣ እስክንድርያ እናታችን ከሚለው ኢትዮጵያዊው ትውፊት ርቆ መሔዱ ኢትዮጵያውያኑን ቅር የሚያሰኝ



መስሎ ስለታያቸው ከችግሩ አንባር አፄ ዮሐንስ በኢትዮጵያውያኑ ፈንታ ግብፃውያን ኤጲስ ቆጶሳት በብዛት እንዲሳኩላቸው የእስክንድርያውን ፓትርያርክ በድጋሜ ጠይቀው ዐራት ግብፃውያን ኤጲስ ቆጶሳትን የላኩላቸው መሆኑ ይታወቃል፤ ከነዚህም አንዱን ሊቀ ጳጳሳት ብለው በመቀሌ ሲመድቡ፤ ሌሎቹንም በአዲስ አበባ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በጐንደር በፋርጣ ጎሩይ ጊዮርጊስ ያስቀመጧቸው መሆኑ ታውቋል::

ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ዓይነት የታሪክ ሒደት እስከ 20ኛው መቶ ዓመት ድረስ ስትጓዝ ቆይታ «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር» ነውና በ1921ና በ1922 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ 4 በካይሮ፣ 1 በአዲስ አበባ፣ ድምር 5 ቆሞሳት ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው ተሾሙ ፡፡ ይህም በቤተ ክርስቲያናችን አዲስ የታሪክ ምዕራፍን ከፈተ ፡፡ የእነዚህም ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት ሊቀ ጳጳሳት ሁኖ የመጣው ግብፃዊው ሊቀ ጳጳሳት ቁርሎስ ነበር::

ዕውነቱን ለመናገር ከሆነ ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው ከእስክንድርያ-ግብፅ ሐዋርያት ተልከውላት ሳይሆን ቀደም ሲል እንደተገለፀው የክርስትናው ታሪክ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአንደኛው መቶ ዓመት በ34 ዓ.ም. በሐዋርያት ዘመን በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካይነት ነው ብለናል፤ ከዚህም ጋር አባ ፍሬምናጦስ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ ተልኮ ኤጲስ ቆጶስነትን የተሾመው በእስክንድርያ ክቅዱስ አትናቴስ ነው ፡፡ ኤጲስ ቆጶስነትን ከእስክንድርያ ማምጣትም የክርስትናውን ታሪክ ከግብፅ አለማምጣት መሆኑ ለሁላችንም ግልፅ ነው ፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ የታሪክ ሒደት ላይ እንዳለች በ1928 ዓ.ም. ፋሽስት ኢጣሊያ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ገብቶ ወረራውን እንደቀጠለ በጊዜው በአዲስ አበባ የነበሩት ግብፃዊው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ቁርሎስ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ብፁዕ አቡነ አብርሃምን ወክለው ወደሮም ሔዱ:: አቡነ ቁርሎስ በሮም እንዲሆንላቸው የጠየቁት ባለመሳካቱ መንጋውን ያለበቂ ጠባቂ በትነው ወደ ኢትዮጵያ የማይመለሱ መሆ ናቸውን ገልፀው ወደ ሀገራቸው ግብፅ ገብተው ቀሩ::

በ1921 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያናችን አዲስ የተከፈተው ምዕራፍ በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ኤጲስ ቆጶሳትን የመሾሙ ተግባር ሳያቋርጥ ቀጥሏል፤ የቀጠለውም የኤጲስቆጶስነቱ ሹመት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ሒደት ነበር ፡፡ ከ1928 እስከ 1933 ዓ.ም. ከላይ እንደተገለፀው እነዚህ አምስት ዓመታት የመከራ፣ የፈተና፣ የወረራ፣ የግድያ ጊዜያት ነበሩ:: በዚህም ጊዜ በግብፅና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ኃላፊች መካከል ከፍተኛ አለመግባባት የተፈጠረበት ጊዜ ነበር:: የአለመግባባቱ ምክንያትም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ቀዳማዊ በይቀጥላል ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ጊዜ ጀምሮ ኤጲስ ቆጶሳትን በይቀጥላል በመሾሟ ነበር፤ አለመግባባቱም ውግዘትን እስከማስከተል ደርሷል ፡፡

ከዚህ ጊዜ በኋላ ፋሽስት ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ተጠራርጎ ከወጣ ከ1933 ዓ.ም. ወዲህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤና በካይሮ ቅዱስ ሲኖዶስ መካከል በተፈጠረው ቅራኔ በየጊዜው ውይይት ለማድረግ የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት መልእክተኞችን ወደ ካይሮ በመላ ክ ከስምምነት ላይ በመድረሳቸው በ1940 ዓ.ም. አምስት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው ተሾሙ ፡፡ ቀደም ሲል የተጀመረው ውይይትም ቀጥሎ በ1943 ዓ.ም. የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ተገኘ:: ይህም ሲሆን የቻለው የግብፃዊው አቡነ ቁርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዕረፍት ከካይሮ በመሰማቱና በዚህ ወቅት ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳትን መሾም ስለታመነበት ነው ፡፡

ከዚህ በኋላ ከኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ተወጣጥቶ የተሰየመው ልዑክ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ ሥልጣን የሆነውን የፓትርያርክነት ሹመት ለማምጣት ውይይቱ ስላላቋረጠና መልካም ውጤትም ስላስገኘ በ1951 ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው በግብፃዊው ፓትርያርክ በቁርሎስ ፍኖ በካይሮ መንበረ ማርቆስ ተሾሙ:: በዚህም ሹመት ስነ ሥርዓት ላይ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ተገኝተዋል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የኤጲስ ቆጶስነትን፣ የሊቀ ጳጳስነውንና የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ለማግኘት የተደረገው ጥረትና ድካም የተከፈለውም መሥዋዕትነት ቀላል አልነበረም ፡፡ በዚሁ ክፍለ ዘመን ማለትም በዐሥራ ዘጠነኛውና በሃያኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያናችን የትምህርት ጉባኤያት በበለጠ የተስፋፋበት ጊዜ ነበር ፡፡

ለማስረጃም ያህል፡-

ሀ. የቅኔና የሰዋስው ዘይቤ ማዕከላት የሆኑ ትምህርት ቤቶችን፣

ለ. የትርጓሜ መጻሕፍት ጉባኤያትን፣

ሐ. የጸዋትወ ዜማ ትምህርት ቤቶችን፣

በማስፋፋትና በማጠናከር የቤተክርስቲያኒቱ እርምጃ ተጠናክሮ የቀጠለበት ጊዜ ነበር ከዚህም ጋር የመጤ እምነት ተከታዮች ለተወሰኑ ዓመታት ያህል የተለያዩ የእምነት ማስፋፊያ መገልገያቸውን ይዘው በተለያየ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ያልቻሉበት ጊዜ የነበረ ቢሆንም ቀደም ሲል የገቡት ጀስዊት መነኮሳትን በትምህርተ ሃይማኖታቸው ብዙ ሰዎችን ያቀረቡ በመሆኑ ችግሩ ሥር የሰደደ ነበር፡፡

በተለይ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነገሥተ ኢትዮጵያ የአውሮፓውያንን ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ከፍተኛ ጥረት ያደረጉበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሁንና የአውሮፓውያን ኃያላን መንግሥታት ኢትዮጵያ በሥልጣኔ እንዳታድግ በስውር ተስማምተውና ተባብረው በ19ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የኢጣሊያ ተስፋፊና ወራሪ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ እንዲዘምት ተደረገ፤ ተሸንፎም ተመለሰ፡፡ ይህም የአድዋ ጦርነት በኢትዮጵያዊያን ድል አድራጊነት መፈጸሙ ለአፍሪካውያንና ለዓለሙ ሁሉ በቂ ትምህርትን የሰጠ በመሆኑ የአድዋው ጦርነት ድል መነሻ ሆኖ ሁሉም ትግሉን ቀጥሎ አሁን ዓለሙ ሁሉ ከቅኝ ገዥዎች ነፃ ሆኖ ይታያል፡፡

እንደገና ከ40 ዘመናት ዝግጅት በኋላ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ፋሽሽት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ በፈለገ ጊዜ ለዓላማው መሳካት በኢትዮጵያ መጀመሪያ መደምሰስ ካለባቸው አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንደነበረች ታሪክ ያስረዳል፡፡ ይህም መጥፎ አመለካከት 1928 ዓ/ም እስከ 1933 ዓ/ም ድረስ በተደረገው ወረራ በተግባር የታየ ነው፡፡ ለዚህ በዓይን የሚታይ የቅርብ መረጃ የሚሆነን በማዕከለ ምድር በአዲስ አበባ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኘው የታላቁ ሰማዕት የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሰማዕት ሐውልት፣

በኢሉባቡር ጮሬ ከተማ መዳረሻ በጥይት ተደብድበው ያረፉት የሁለተኛው ሰማዕት የብፁዕ አቡነ ሚካኤል፣ በደብረ ሊባኖስና በሌሎችም ገዳማት በጥይት ተደብድበው ያለቁት መናንያን መነኮሳት፣ መነኮሳይያት፣ የተቃጠሉት ገዳማትና አድባራት በቂ መረጃዎች ናቸው፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ከ1921-1928 ዓ.ም. ድረስ የወሎ ሊቀ ኤጲስቆጶስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ‹‹ኢታርእየኒ መስናሃ ለኢትዮጵያ›› ‹የኢትዮጵያን ጥፋት አታሳየኝ› የሚለውን ዘይቤ መነሻ በማድረግ ‹‹ፋሽሽቶች የሀገራችንን አርበኞች፣ ሽፍቶች ቢሏቸው ዕውነት አይምሰላችሁ፤ ሽፍታ ማለት ያለሀገሩ መጥቶ የሰውን ሀገር የሚወር ይህ በመካከላችሁ የቆመው አረመኔው የኢጣሊያ ፋሽሽት ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፋሽሽቱ ኢጣሊያ እንዳይገዛ ውጉዝ ከመ አርዮስ፤ የኢትዮጵያም ምድር እንዳትቀበለው የተገዘተች ናት›› ብለው ምሥራቁን፣ ምዕራቡን፤ ሰሜኑንና ደቡቡን በመስቀላቸው ባርከው ቤተሰቦሰቦው ሕዝብ ፊት እንደቆሙ ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. በአዲስ አበባ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ አሁን ሐውልታቸው ቆሞ በሚታይበት ቦታ በፋሽሽቱ ኢጣሊያ በጥይት ተደብድበው የተገደሉ ‹‹ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳስ ሰማዕተ ጽድቅ ዘኢትዮጵያ›› ተብለው እንዲጠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል አስከሬናቸውንም ፋሽሽት ኢጣሊያ ገድሎ የጣለበት ወዴት እንደሆነ እስከዛሬ ድረስ ያልታወቀ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመጥቀስ እንወዳለን ፡፡

ከዚህም ጋር 20ኛው ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያናችን ከካይሮ ቅዱስ ሲኖዶስ የመንፈስ ተገዥነት ነፃ የወጣችበት በራሷ ቀኖና በተዳደር የጀመረችበት ጊዜነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፪ (2000) ዓ.ም

በ11ኛው መቶ ዓመት ቅዱስ ሐርቤ በዘመነ መንግሥታቸው የጠየቁት በኋላም በ19ኛው መቶ ዓመት ዐፄ ዮሐንስም ጀምረውት የነበረው ማለት ኢትዮጵያ የራሷን ልጆች ኤጲስቆጶሳት አድርጋ መሾም አለባት የሚለው፤ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት፤ በንጉሥ ተፈሪ አልጋወራሽነትና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በነበሩበት በ1921 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያውያን ኤጲስቆጶሳት መባረክ፤ የጀመረችበት ጊዜ መሆኑ ግልጥ ነው፤ ከላይ እንደተገለጠው ዐራት ኢትዮጵያውያን ቆሞሳት ወደካይሮ ሐዲው ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. በፓትርያርክ ዮሐንስ 19 ኛ ኤጲስቆጶሳት ሁነው መመለሳቸውን ታሪካችን ይናገራል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በ1928ና በ1929 ዓ.ም. በፋሽሽት ኢጣሊያ በጥይት ተደብድበው በሰማዕትነት ያረፉት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በ1921 ዓ.ም. ወደካይሮ ሐዲው ኤጲስ ቆጶሳት ከሆኑት ከዐራቱ መካከል ሁለቱ ናቸው ፡፡

በ19ኛውና በ20ኛው ክፍላተ ዘመን ሊቃውንቱ በቤተ መንግሥቱ አስተዳደር ዙሪያ ስላለው የሥራ አፈጻጸም ተሰሚነት ስለነበራቸው የቤተ ክርስቲያኒቱን ሁለንተናዊ ዕድገት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ሚናን ተጫውተዋል፤ በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደ ወቅቱ ሁኔታ የመንግሥት ሕግ አውጭዎችና ተርጓሚዎችም ስለነበሩ ባላቸው ሙያ ተጠቅመው፤

- ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፤
- ሥርዓተ ገዳማትን፤
- ሥርዓተ መነኮሳትንና የመሳሰሉትን የመተዳደሪያ ደንቦች በማውጣትና በማዘጋጀት ተግባር ተባባሪዎች በመሆን ይሠሩ እንደነበር ይታወቃል፤ በእነዚህም ሊቃውንት እየተዘጋጁ በየጊዜው ከወጡት ደንቦች መካከል በ1934 ዓ.ም. በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ የወጣው ደንብ ሁሉንም አጠቃሎ የያዘ የቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ በመሆኑ ለቤተ መንግሥቱ አስተዳደር ቀረቤታ ካላቸው መካከል ግንባር ቀደም አገልግሎትን የፈጸሙ ሊቃውንት ቁጥርም ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም፤

በየጊዜው የተነሡት ነገሥታት፣ መሳፍንትና መኳንንት ከቤተ ክህነቱ ጋር በመሆን ለቤተ ክርስቲያን ሕግንና ደንብን ከማውጣታቸውና ከማወጃቸው ጋር፤

- አብያተ ክርስቲያናትን ሲያሳንፁ፤
- ገዳም ሲገድሙ፤
- ደብር ሲደብሩ፤
- መተዳደሪያ ሀብትንና ንብረትን ሲመድቡ ኑረዋል ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካላትና ከሚኖራት ከባድ ኃላፊነት አንጻር የኅብረተ-ሰቡን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በበለጠ ማሟላት ያስችላት ዘንድ ተጨማሪ አስተዳደራዊ ሥልጣን እንዲኖራት ለማድረግ ታስቦ በፍትሐ ብሔር ሕግ በተወሰነው መሠረት በተሻሻለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 127 በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 398 እና 400 መሠረት አገልግሎቷን በበለጠ እንድታጠናክር ተደረገ ፡፡

ደጋግመን እንደተናገርነው ከጊዜ በኋላ ጊዜው ሲደርስ ‹‹ወስብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሚሙ ሊቀ ኤጲስቆጶሳኒሆሙ›› የሚለው በ7ኛው መቶ ዓመት የገባው አደገኛ ሥርዋፅ ተወግዶ ቤተ መንግሥቱ፣ ቤተ ክህነቱ ሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉንም አንድ ሁነው የመረጧቸው ብቃት ያላቸው ቆሞሳት ከ1921 ዓ.ም. ጀምሮ ኤጲስ ቆጶሳት ሁነው ተሠይመው ኤጲስ ቆጶስነቱን፣ ሊቀ ኤጲስ ቆጶስነቱን፣ ፓትርያርክነቱን በቅደም ተከተል ቤተ ክርስቲያናችን ተረክባ ከ1951 ዓ.ም. ጀምሮ ነፃ ቤተ ክርስቲያን ሁና በራሷ ቅዱስ ሲኖዶስ መተዳደር ጀመረች፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን የፓርያርክነቱን ሥልጣን ተረክባ አስተዳደሯን በስነ ሥርዓት በማከናወን ላይ ትገኛለች ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅር ከሃያኛው መቶ ዓመት አጋማሽ አንሥቶ ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ ሀገረ ስብከት መንበረ ሊቀ ኤጲስ ቆጶስ፣ መንበረ ኤጲስ ቆጶስ ከዚያ በተዋረድ እስከ ወረዳ ከዚያም እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚደርስ ሆኖ ተዋቅሮአል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕልዋናዋ ታውቆ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ከሆነበት ከ4ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የትምህርትና የስነ ጥበብ ባለቤት ሁና በእምነት ላይ በተመሠረተ ትምህርትና የአስተዳደር ዘይቤ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን አንድ አድርጋ በሁሉም አቅጣጫ ሁሉንም በዕኩልነት ደረጃ ስታስተዳድር፣ ስታገለግል የነበረች፣ ያለችና የምትኖር ጥንታዊት፣ ታሪካዊት፣ ብሔራዊት፣ ሐዋርያዊትና ሉአላዊት ቅድስት እናት ቤተ ክርስቲያን ናት ። ሀ ገ ራ ች ን ኢትዮጵያ የፓትርያርክነቱን መዐርገ ሥልጣን ከያዘችበት ከ1951 ዓ.ም. ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በተሟላ መልኩ ሲከናወን ቆይቷል፤ ከዚያም ወዲህ ባለማቋረጥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተልዕኮ እድገትን እየጨመረ በመምጣቱ የሥራው እንቅስቃሴ በመፋጠን ላይ ይገኛል ።

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በየዓመቱ መጀመሪያ ጥቅምት 12 ቀንና ትንሣኤ በዋለ በ25ኛው ቀን በርክበ ካህናት ከሚያደርገው መደበኛ ስብሰባ ሌላ በቤተ ክርስቲያን፣ ጊዜ የማይሰጥ ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም አስቸኳይ ስብሰባን በማድረግ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ደኅንነት እየመከረ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፍ መሆኑንም ቀደም ብለን ገልፀናል ።

የብፁዓን፣ ቅዱሳን ፓትርያርኮች ዘመነ ክህነት ቅደም ተከተል ሲታይ፤

1. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ከ1951 — 1963 ዓ.ም.፤
2. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ከ1963 — 1968 ዓ.ም.፤
3. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ከ1968 — 1980 ዓ.ም.፤
4. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ አሁን አባ ዘሊባኖስ ከ1980 — 1983 ዓ.ም.፤
5. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱን የአመራር ተግባር በከፍተኛ ደረጃ በማፋጠን ላይ ይገኛሉ ።

በእነዚህ አምስት ብፁዓን ቅዱሳን አበው ፓትርያርኮች አንብሮተ እድ የተሠየሙት ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳት ቁጥር፤

- በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ 17
- በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ 9
- በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት 28
- በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አሁን አባ ዘሊባኖስ 6
- በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ እስከአሁን 49

ጠቅላላ ድምር 109 ሲሆኑ ከእነዚህ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት መካከል በሞት የተለዩም ስላሉ ድምር ቁጥራቸው ከዚህ ያነሰ ይሆናል ።

በሕይወት ያሉ ብፁዓን አበው ሊቃነ ኤጲስቆጶሳት ወኤጲስቆጶሳት በየሀገረ ስብከታቸው የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር በሰመረ ሁኔታ በመምራት ላይ ይገኛሉ ።

## ቤተ ክርስቲያኒቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት የአስተዳደር ሥራ አመራር

ቤተ ክርስቲያኒቱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርን ከመሠረቱት አንዲና የመጀመሪያዋ ናት፣ የመላ አፍሪካ አብያተ ክርስቲናት መሥራች አባልም ናት ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከማንም ጥገኝነት ነፃ ሁና የሥልጣን ባለቤት ከሆነችበት ከ1951 ዓ.ም. አንሥቶ የአሁኑ አምስተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት እስከመሆን ደርሰው የአብያተ ክርስቲያናቱን አስተዳደር በሀገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በመምራት ላይ የሚገኙ ናቸው፤ በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ቀደም ሲል ከነበራት የአመራር ምዕራፍ ወደላቀ ደረጃ ለመሸጋገር እንድትብቃ አስችለዋታል።



ይህም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት መሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለ1600 ዘመናት ያህል የኮፕቶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ጥገኛ ሁና የኖረችበትን ዘመን ለማዘከር የሚረዳ ይሆናል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚመራው በቅዱስ ፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት ሲሆን ቅዱስ ፓትርያርኩ ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊውንና ማኅበራዊውን አገልግሎት በተሰጠፈ አሠራር ለማከናወን ትችል ዘንድ ዘመናዊ አስተዳደርና የሥራ አመራር እንዲኖራት ጥረትን በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።

## እስከአሁን ለተተረከውና ለሚተረከው የአስተዳደር ሥራ አፈጻጸም፤ በየጊዜው የነበረው የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ሀብት አመሠራረት

### ርስተ ጉልትን በተመለከተ

የቤተ ክርስቲያን ርስተ ጉልት ሲባል ዓይነቱ ብዙ ነው ።

- መንቀያና መትከያ የሚባል የአገልግሎት ርስት
- ሁዳድ የሚባል የአንድነት ገዳማት መተዳደሪያ ርስት
- ሪም ወይንም ቀላድ የሚባል የስሪት መተዳደሪያ ርስት
- የመስቀል መሬት

ይህ ሁሉ በአንድነት ተጠቃሎ የቤተ ክርስቲያን ርስተ ጉልት ይባል ነበር፤ ይህም በስፋት ሲተነተን እንደሚከተለው ይሆናል ።

1. መንቀያ፣ መትከያ የሚባለው የመሬት ስሪት የአድባራት አለቆች፣ የገዳማት መምህራን የገጠር መሪጌቶች መተዳደሪያ ነው።

የዚህም የመሬት ይዞታ ዓይነት በየጊዜው የሚሾሙት የቤተ ክርስቲያን አስተዳሪዎች በሹመቱ ላይ እስካሉ ድረስ ብቻ በአላባው እየተጠቀሙ ቆይተው ከሹመቱ ሲነሡ ወይም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በሹመታቸው የሚተካው አስተዳዳሪ ተረክቦ የሚተዳደርበት እንጂ የሚሸጥ የሚለወጥ፤ በውርስ በስጦታ ለሌላ ሰው የሚተላለፍ አይደለም ። ይህ ዓይነቱ የመሬት ስሪት ሁሉ በታቦቱ ስም ተመዝግቦ ሲገበርበት የኖረ ነው ።

2. ሁዳድ የሚባለው የመሬት ስሪት ዓይነት በአንድነት ገዳም ተወስነው የሚኖሩ ጥሪት ቁሪት የሌላቸው መነኮሳት እያረሱ የሚጠቀሙበት የአንድነት ገዳም ርስተ ጉልት ነው።

3. ሪም ወይንም ቀላድ የሚባለው በተራ ቁጥር 1 በተመለከተው ዓይነት የመሬት ስሪት ለካህናት መገልገያ ተብሎ ከመንግሥት በጠቅላላው ተሰጥቶ በየደብሩ አለቆች ኃላፊነት ለካህናት ተደልድሎ በርስትነት የሚገበርበት ወይም ርስትነቱ የታቦቱ ሆኖ ካህናቱ በአላባው እየተጠቀሙ በማደሪያ ያገልግሉበት ተብሎ የተሰጠ የቀላድ መሬት ነው ።

4. የመስቀል መሬት የሚባለው መኳንንትና ወይዛዝርት ሌሎችም ሁሉ ከገዛ ርስታቸው ቀንሰው ለቤተ ክርስቲያን መትከያ የሚሰጡት ርስተ ጉልት ነው ።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያናችን ቅድመ ሰበካ ጉባኤ ስትተዳደር የነበረው ከዚህ በላይ በየመልኩ ከተገለፁት የመሬት ዓይነቶች በሚገኘው የገቢ ምንጭ ነበር ።

ከላይ የተጠቀሰው የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ብዛት ጎልቶ ከመታየቱ በቀር ለካህናቱ መተዳደሪያ ይሆን ዘንድ የተፈቀደው ርስተ ጉልት የሚሰጠው ጥቅም የአገልጋዮች ካህናትን ችግር ከመሸፈን አኳያ በቂ አልነበረም ።

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበት ርስተ ጉልት መልክኝነትም ሁሉ ባለርስቶች ምድሩና ጉልቱ በእጃቸው ሆኖ ሳለ የለም መሬት፣ የጠፍ መሬትና የለም ጠፍ መሬት ግብር፣ መንግሥት በሚቆርጠው ግምት ልክ ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወሰን ነበር ፡፡

ለመጥቀስም ያህል በአንድ ጋሻ ለም የሰሞን መሬት
-ግብር ብር 15.00
-የትምህርት ታክስ ብር 15.00
-የጤና ታክስ ብር 15.00
-ዐሥራት ብር 35.00
ድምር ብር 80.00 ይከፈል እንደነበር ተረጋግጧል ፡፡

ከዚህ የመሬት ገቢ ሒሳብ የትምህርትና የጤና ታክስ እየተባለ የሚሰበሰበው ገቢ የትምህርትና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴሮች ከመቋቋማቸው በፊት በቤተ ክርስቲያኒቱ በኩል እየተሰበሰበ ይሠራበት የነበረ ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት የሕዝብ አገልግሎት መ/ቤቶች በይፋ ከተቋቋሙ በኋላ ግን የጤናውና የትምህርቱ ታክስ በቀጥታ ከላይ ወደተጠቀሱት ሚኒስቴር መ/ቤቶች እንዲገባ በመደረጉ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተቋርጧል ፡፡

ይሁንና ለቤተ ክርስቲያን መግባት የሚገባውን የግብር ገንዘብ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ባላባቶችና ወይዛዘርት በግብዝና፣ በአልቅና፣ በመሪጌትነት በድብትርና፣ በቅስና፣ በዲቁናና በልዩ ልዩ የክህነት ግብር ስም ርስት እየያዙ በግል እየተጠቀሙ በተወሰነ ክፍያ ወይንም በቶፍነት ካህናትን ያስገለግሉ ነበር ፡፡

ከዚህም ጋር ለቤተ ክርስቲያን በስዕለትና በርዳታ፣ በጸሎተ ፍትሐት አገልግሎትና በማናቸውም ይህን በመሳሰለው ሁሉ ከዕቃ ቤት የሚገባ ገንዘብ ሌላውም ቤተ ክርስቲያን በውርስ፣ በስጦታ፣ በግዥና በሌላም ምክንያት ባገኘችው መሬትና ቦታ ከሱቅም ከመኖሪያ ቦታም በኪራይና በሰብል የሚገኘው ገንዘብ ሁሉ በደብሩ አለቃ ኃላፊነት እየተጠራቀመ ወደ ቤተ ክርስቲያን ግምጃ ቤት እንዲገባ ተደርጎ ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ይሆን ነበር ፡፡

## የመተዳደሪያ ሀብት አመዳደብ፣

ይህን ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ሀብትና ንብረት የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ኃላፊች በመንፈሳዊ ጉባኤ አቅራቢነት በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ይሾሙ ነበር ፡፡

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው በቤተ ክርስቲያን ስም ይሰበሰብ የነበረው ገንዘብ ማለትም፣

-የርሻ ታክስ
-የፍሬ ግብር ታክስ
-የትምህርት ታክስ
-የጤና ታክስ

እንደየአካባቢው ሁኔታና እንደየሥራው ማዕረግ ለወር፣ ለመንፈቅና ለዓመት ቀለብ እየተባለ ለሠራተኞች፣ ለአገልጋይ ካህናትና መምህራን ይመደብ ነበር ፡፡ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶቿን የምታቋቋምበትና ለበጎ ሥራ ማስፋፊያ የሚሆናትን ሁሉ ከዚሁ ከተሰበሰበው ገንዘብ የሥራ ማስኬጃ በጀት በማሰመደብ እዴራት ቆይታለች ፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ለሀገራችን ኢትዮጵያ ባለውለታና ብሔራዊት እንደመሆኗ የራሷን አስተዳደር እንድትመራ የሚያስችላት የሥራ መመሪያና የበጀት አያያዥ ደንብ ተዘጋጅቶላት መመሪያዋም በመላ የኢትዮጵያ ንሠ ነገሥት መንግሥት አስተዳደር ተግባራዊ እንዲሆን የነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ታውጆላት ልዕልናዋም ተረጋግጦላት የሚጠበቅባትን ድርሻ ለጎብረተሰቡ እያበረከተች ኖራለች፡፡



ከዚህ ስነ ጽሑፍ አቀራረብ አኳያ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ጉዳይ ቢኖር የቤተ ክርስቲያኒቱንና የመተዳደሪያዋን ጥንተ አመሠራረት ታሪክ በአጭሩ ለማመልከት ያህል እንጂ ያለፈው ታሪኳ ሁሉ በዚህ ጠባብ አጌሌ ተጠቃሎ ቀርቧል ለማለት የሚያስደፍር ሆኖ አይደለም ፡፡

ከዚህም ግንዛቤ አንጻር መታየት ያለበት ሌላው ዓቢይ ጉዳይ ባለፈው የደርግ መንግሥት አስተዳደር የቤተ ክርስቲያኒቱ የመተዳደሪያ ሀብት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በአጭሩ መግለፅ ያስፈልጋል ፡፡

ከ1967 ዓ.ም ፊትና ኋላ፣

በበለጠ ከ1966 ዓ.ም ቀደም ሲል ጀምሮ «መሬት ላራሹ» በሚል ዘይቤ በተካሔደው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሁሉም የአላማው ደጋፊ በመሆኑ ተደርጎ በነበረው የዓመፅ ተግባር ቤተ ክርስቲያኒቱ በጸድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ ክህነት ከዚያም ወዲህ በየጊዜው በተነሡት ቅዱሳን ነገሥ ኢትዮጵያ አግኝታ የነበረውን የሲሶ መንግሥት መብት ሥልጣንና ጥቅሙን አጥታለች ፡፡

በዚህም የሥርዓተ መንግሥትና የአስተዳደር ለውጥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብታቸውንና ንብረታቸውን ከተወረሱት መብታቸውን ካጡት ጋር ተቆጥራ የሰው ሰውኛው ዘለፋ የደረሰባት ቢሆንም በጊዜው ፈተናውን በትዕግሥት ተቋቁማ አልፋዋለች፡፡

ከዐራተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስከ 1967 ዓ.ም. መነሻ ድረስ ብሔራዊ ሃይማኖት ሁኖ ቤተ መንግሥቱንና ቤተ ክህነቱን አቀራርቦ ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘመናት ያህል ሲሠራ የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በተለይም በ1948 ዓ.ም የወጣው ሕገ መንግሥት እንዳይሠራ በ1967 ዓ.ም. የወጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ማቋቋሚያ አዋጅና በ1980 ዓ.ም. የጸደቀው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ የነበረውን የቀረበ ግንኙነት በአዋጅ የሻረው በመሆኑ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሁለቱም ዘንድ የነበረው ይፋ የሆነ የሃይማኖትና የአስተዳደር ግንኙነት ሊቋረጥ የቻለ ቢሆንም የደርግ መንግሥት እስከ ወደቀበት ግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. ድረስ የጠቅላይ ቤተ ክህነቱን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከመሾም አልተገታም ነበር፤ ይሁንና በ1987 ዓ.ም. የጸደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 11 መንግሥትና ሃይማኖቶች የተለያዩ መሆናቸውን ሲደነግግ ሃይማኖት በመንግሥት መንግሥትም በሃይማኖት ጉዳይ እንዳይገባ ሕገ መንግሥቱ በግልጥ አስቀምጧል፡፡

ይህ የሃይማኖት እኩልነት አዋጅ በሁሉቸም የእምነት ድርጅቶች ላይ እንዲሠራ በመደረጉ ከደርግ ውድቀት በኋላም ተያይዞ በመጣው በተለመደው አሠራር ሲንቀሳቀስ የቆየው አስተዳዳሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እንደሌሎች መሰል የእምነት ድርጅቶች የራሷን አስተዳደር በራሷ ሥራ አስኪያጅ የመምራት ኃላፊነት እንዳለባት በመገንዘብ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአዲስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ባደረጉት ጥረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በጎ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያናችን ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ በራሷ ሥራ አስኪያጅ እንድትተዳደር ተፈቀደ ፡፡

ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት ጀምሮ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ አመዳደብ ሥርዓት በሕገ ቤተ ክርስቲያኑ ድንጋጌ ቦታ ተሰጥቶት በየሦስት ዓመቱ የሥራ አስኪያጅነት ምርጫ እየተካሔደ በአሁኑ ወቅት በአምስተኛው ሥራ አስኪያጅ አስተዳደሩ በመከናወን ላይ ይገኛል ፡፡

ከዐራተኛውና ከዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ የነበረው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የኢኮኖሚዋ አቋም ከላይ በተጠቀሰው መልክ በአጭሩ የተገለፀ ሲሆን ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ለዘመናት ታገኝ የነበረው ጥቅም ሁሉ በደርግ መንግሥት አዋጅ ከየካቲትና ከሐምሌ 1967 ዓ.ም. ጀምሮ ተቋርጧል ፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ በ1965 ዓ.ም. በነጋሪት ጋዜጣ በወጣው ቃለ ዓዋዲ የቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከሕዝበ ክርስቲያኑ በሚሰጥ አስተዋጽኦ ከስእለት፣ ከሙዳየ ምጽዋትና ከመንግሥት በሚገኝ የድጎማ ገንዘብ እንድትተዳደር ተደርጓል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያናችን ከመሬት ጋር ተያይዞ ከነበረው የአስተዳደር ሥርዓት ወደ ሌላው ከመሸጋገሯ አስቀድሞ የተለያየ ፈተና አጋጥሟት እንደነበር በላይኛው መሥመር መግለፃችን ሳይዘነጋ ካጋጠማትም ችግር እንደኛውን ነጥብ እንደማስረጃ ጠቅሰን እናልፋለን ፡፡

- ያልቀናውንና በረሀማውን መሬት እየሰጡ የለማውን መሬት መቀማት፣
- ለም የሆነውን መሬት በጠፍ መሬት መለወጥ፤
- የኩታ ገጠም አቀማመጥ ያለውን ርስት ወደ ግል ይዞታ ማስገባትና የመሳሰለው ፍትሐዊ ያልሆነ ተግባር ይፈጸምባት እንደነበር ከቀየው የታሪክ ማኅደር መረዳት ተችሏል ፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገት ከማሰብ ይልቅ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም የግል ሀብታቸውን የሚያካብቱና የራሳቸውን ሕይወት የሚገነቡ ከቀድሞ ጀምሮ አንዳንድ ግለሰቦች እንደነበሩ መገንዘብ ተችሏል ፡፡

ስለዚህ አገልጋዮች ካህናት ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር ጥቅማቸውን ለማስከበር የነበራቸው አቅም ውሱን በመሆኑ የበይ ተመልካቾች ሆነው ዘመናትን አሳልፈዋል ፡፡

## የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕንፃዎች በተመለከተ

ከዚህም ሌላ ቤተ ክርስቲናችን በዘመኑ በነበረው ሁናቴ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለማስገኘት በነበራት ዕቅድ መሠረት በመንበረ ፓትርያርኩ ዙሪያ ባለው ቦታ ቪላ ቤቶችንና መደዳ ቤቶችን በመሥራትና በማከራየት ከዚያ በሚገኘው የኪራይ ገንዘብ የመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ሥራዋን ስታካሒድ ቆይታለች ፡፡

የከተማው ዕድገት እየተሻሻለ በመምጣቱ ታላላቅ ሕንፃዎችን /ፎቆችን/ በፕላኑ መሠረት እየሠሩ ማከራየት የከተማው ማስተር ፕላን ሕጋዊ መመሪያ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያኒቱም ክቤቶች ኪራይ የሚገኘውን ገቢ በማሰባሰብና ከባንክም በመበደር ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ከበጎ አድራጊዎች ርዳታን በመጠየቅ ታላላቅ ሕንፃዎችን መሥራትና ማከራየት በመጀመር ላይ እያለች የከተማ ቦታና የትርፍ ቤት አዋጅ ምክንያት ታገኝ የነበረው ሁሉ ቀርቷል፡፡

ከጊዜ በኋላም የተደረገውን የአስተዳደር ለውጥ በማስመልከት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአዲስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ክፍተኛ ጥረት፣ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በጎ ፈቃድ በአዋጅ ከተወሰዱባት መካከል የተወሰኑ ሕንፃዎችና ቪላ ቤቶች እንዲመለሱ ቢደረግም፤ ሕንፃዎቹ የረዥም ዘመን አገልግሎት ሰጥተው ያረጁና የተጐሳቆሉ በመሆናቸው አጠቃላይ ጥገናና እድሳት ቢደረግላቸውም ከእነርሱ የሚገኘው ገቢ የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግር ሁሉ ያቃልላል ተብሎ አይገመትም ፡፡

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያኒቱ የመተዳደሪያ ሀብት ችግር ዘለቄታ ያለው መፍትሔ እንዲያገኝ አዲሱ የቃለ ዓዋዲ ንድፈ ሐሳብ ረቂቅ በሚያስረዳው ድንጋጌ መሠረት ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ የተዋቀረውን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በሚገባ ማደራጀትና ማጠናከር ወቅቱ የሚጠይቀው ዓቢይ ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ፣
- ሃይማኖትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፣
- ምእመናንን በመንፈሳዊና በማኅበራዊ አገልግሎት ለመመገብ፣
- ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለመጠበቅና ለማስፋፋት፣
- ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና ለማጠናከር፣
- ወጣቶች ከአበው የተቀበሉትን ሃይማኖትና ሥርዓት ጠብቀው በትምህርትና በሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ለማስቻል፣
- የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ለማጠናከርና ለማስፋፋት፣






- የሰው ዘር ሁሉ ከረሀብ፣ ከእርዛት፣ ከበሽታና ከድንቁርና ተላቆ በሰላም፣ በአንድነት፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖር የሚያደርግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅር ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ፡፡

## የዐሥራት አስተዋጽኦን በተመለከተ

ዐሥራት በዘመነ ብሉይና በዘመነ ሐዲስ አማንያን ሠርተው ከሚያገኙት ከድካማቸው ውጤት ለቤተ እግዚአብሔር የሚከፍሉት አስተዋጽኦ ነው ፡፡

የዐሥራት አስተዋጽኦ እንደ ምድራውያን /ዓለማውያን/ መንግሥታት ግብርና ቀረጥ እንደየጊዜው ሁኔታ ከፍና ዝቅ በማድረግ ከፋዩን የሚያስጨንቅ አይደለም ፡፡ እያንዳንዱ አማኝ አምልኮተ እግዚአብሔርን ለሚፈጽምበት ቤተ እግዚአብሔር መገልገያ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ከሰጠው ሀብትና በረከት ከዐሥር እጅ አንዱን አንሥቶ እንዲሰጥ የታዘዘ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው፡፡

የዐሥራት አስተዋጽኦ /ክፍያ/ በኦሪት ከተጻፈው ሕግና ትእዛዝ አስቀድሞ ከሕገ ልቡና ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው ፡፡

ቀደም ሲል ደጋግመን እንደገለፅነው አብርሃም ካገኘው ሀብት ሁሉ ከዐሥር አንድ አውጥቶ ለካህኑ መልከጼዴቅ አቅርቦአል፣ ካህኑ መልከጼዴቅም አብርሃምን ባርኮታል ፡፡ ይህ ሥርዓት የሚቀጥልና የማይለወጥ ሥርዓት ሆኖ እንደሚሠራበት ቅዱስ ጳውሎስም በጊዜው አስተምሮታል ፡፡ /ዘፍ. 14፡20፣ ዕብ. 7፡1-11/

በስደቱና በመከራው ጊዜ እግዚአብሔር ረዳቱ የሆነለት ያዕቆብ ፍርሀት፣ ሥጋትና ጭንቀት በተመላበት የብቸኛነት ጉዞ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን በሚያቋርጥበት ምሽት ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥቶ ድንጋይ ተንተርሶ ባደረባት ሥፍራ /በምድረ ሉዛ/ የገጠመውን ችግር እንዲህ ሲል ለእግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

‹‹እግዚአብሔር ከኔ ጋር ቢሆን
በምሔድባት በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ
የምበላውን እንጀራና የምለብሰውን ልብስ ቢሰጠኝ
ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ
እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል

ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል›› የሚል ትንቢት ተናገረ ። ድንጋዩንም ለቤተ እግዚአብሔር መሠረተ ሕንፃ አድርጎ አቆመው ። ዘይትም አፈሰሰበት፤ ቤተ እግዚአብሔር ሲሠራም የመገልገያ ሀብት እንደሚያስፈልግ በማስተዋል፤

‹‹ከሰጠኸኝ ሀብት ሁሉ ከዐሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ››
በማለት የዐሥራቱን አስተዋጽኦ መሠረት አኖረ ።

የቃል ኪዳኑንም ማረጋገጫ አቀረበ ። እግዚአብሔርም ያዕቆብን ወደደው ስጦታውን ተቀበለለት፤ ሕይወቱን ጠበቀ፤ ዘሩን አበዛ፤ ያለውን ሁሉ ባረከለት። /ዘፍ. 28:22/

የሰው ሁሉ ሕይወት በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር ነው ። የእግዚአብሔር ጥበቃ፣ ቸርነትና መጋቢነት የማያስፈልገው ፍጡር የለም ። ቸርነቱን፣ ጥበቃውንና በረከቱን ለማግኘት ሕጉን፣ ሥርዓቱን መጠበቅ ይገባል ።

ጌታ ባስተማረን ጸሎት ‹‹ወይኩን ፈቃድከ፣ ፈቃድህ ይሁን ብላችሁ ጸልዩ›› ተብሎ ተጽፎአል (ማቴ . 6:10) ። የኛ ፈቃድ እንዲፈጸምልን የሱን ፈቃድ የመፈጸም ግዴታ እንዳለብን መገንዘብ ያስፈልጋል ። እኛ ሕጉን ለመጠበቅ፣ ትእዛዙን ለመፈጸምና ለፈቃዱ የምንታዘዝ መሆናችንን ካረጋገጥን እሱ የኛን ፈቃድ ለመፈጸም የታመነ ጌታ ነው ።

ከምናገኘው ገቢ ሀብት ሁሉ ከዐሥሩ እጅ አንዱ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው፤ የሰማይና የምድር ባለቤት ለሆነውና ሥነ ፍጥረትን በቸርነቱ ለሚመግበው ኃያል ፈጣሪ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር የሚቀርብ ስጦታ ነው ።

ክብሩ፣ ጌትነቱ የሚነገርበት፣ ስሙ የሚመሰገንበት ቤተ እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ አገልግሎት ለተመደቡ ካህናት የኑሮ ድጋፍና ለቤተ መቅደስ እንዲሆን የተወሰነ ስጦታ ነው ። ይህም በፈቃድና በፍላጎት ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን አባልና ተከታይ የሆነ ሁሉ እንዲከፍል ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ ነው ። /ዘሌ. 27:26-34/

የዐሥራት በኩራት አስተዋጽኦ በገንዘብ ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ከዕህል ሰብልና ከእንጨት ፍሬ ሁሉ ሳይቀር ከምድር ከሚገኘው በረከት ሁሉ እንዲከፈል መታዘዙን ቅዱስ መጽሐፍ ዘርዝሮ ይገልፃል ።

«ለእግዚአብሔር ግን የሚቀርበውን የእንስሳ በኩራት ማንም ይቀድሰው ዘንድ አይቻለውም፤ በሬ ቢሆን ወይንም በግ ለእግዚአብሔር ነው ። ... የምድርም ዐሥራት ወይንም የምድር ዘር ወይንም የዛፍ ፍሬ ቢሆን የእግዚአብሔር ነው፤ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው፤ ሰውም ዐሥራቱን ሊቤዥ ቢወደ አምስተኛ ይጨምርበታል፤ ከበሬም ሁሉ ከዐሥር አንድ ከእረኛም በትር በታች ከሚያልፍ በግና ፍየል ሁሉ ከዐሥር አንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል» እግዚአብሔር ከሲና ተራራ ላይ ለእስራኤል ልጆች ሙሴን ያዘዘው ትእዛዛት እነዚህ ናቸው ። (ዘሌ.27:26-34)

ቀጥተኛውና ግልፅ የሆነው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይህ ነው። እኛ ግን የምንጠይቀው፤ የምንከፍለውም ከታዘዘው እጅግ በጣም ያነሰ ነው ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙና የሃይማኖቱን ሥርዓት የሚያከብሩ ጥቂት እጅግ በጣም ጥቂት ሰች ብቻ ያደርጉታል ። በዚህም ምክንያት ቤታቸው በበረከት የተመላ ሕይወታቸው የተቀደሰ ሆኖ ይኖራል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

ከእግዚአብሔር የታዘዘውን ሁሉ የሚፈጽሙ የእግዚአብሔር የሆነውን ገንዘብ /ስጦታ/ ሳይጠራጠሩ በመስጠት ሳይሳሱ በመለገስ ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ምእመናን የሚሹትን ሁሉ ያገኛሉ፤ የሚለምኑትን ይቀበላሉ፤ በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ለሚኖረው መመላለስ መንገዱ ግልፅ ነው ። ፊቱን በመስታወት እንደሚያይ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ይተያያሉ ። የሰው ልጅ የሕይወት ጉዞ ብዙ ውጣ ውረድ ያለበት፤ እንቅፋትና መሰናክል የበዛበት፤ ስለሆነ በችግር ወጥመድ በሚያዙበት ጊዜ ለያዕቆብ እንዳደረገው «እኔ ካንተ ጋር ነኝ፤ በምትሔድበት መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ አልተውህም አልለይህም» የሚል ድምፅ ያሰማቸዋል ።

«እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፤ ከፍሬህም ሁሉ በኩራት
ጎተራህም ዕህልን ይመላል፤ መጥመቂያህም በወይን ጠጅ
መልታ ትትረፈረፋለች» ይላል የእግዚአብሔር ቃል ። /ምሳ.3:9-10/

አምልኮተ እግዚአብሔር በሚፈጸምበት በቤተ እግዚአብሔር እንዲያገለግሉ የተመደቡ ካህናት የእግዚአብሔርን መንጋ በሃይማኖት እንዲመሩ፤ በስነ ምግባር እንዲጠብቁ ቃለ እግዚአብሔርን እንዲመግቡ የታዘዙ የቤተ እግዚአብሔር ጠባቂች ናቸው ።

ነጋ ለኪዳን መሸ ለቁርባን እያሉ እግዚአብሔን በምስጋና ያገለግላሉ፤ ሕዝቡን በጸሎት በመሥዋዕት ይጠብቃሉ ። ስለ ሀገር ሰላም፤ ስለሰው ልጆች ማኅበራዊ ደኅንነት ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ይማልዳሉ ።

የቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት የማይቋረጥ ነው ። እስከ ዓለም ፍጻሜ ይቀጥላል ። ይህን የዘወትር መንፈሳዊ ተግባር ለሚያከናውኑ ካህናት የኑሮ ድጋፍ ሆኖ የተሰጠው ከተገልጋዮች ምእመናን የሚገኘው የዐሥራት በኩራት አስተዋጽኦና ልዩ ልዩ የፈቃድ ስጦታ ነው ።

የቤተ እግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናት ከመንፈሳዊ አገልግሎት ሳይርቁ፤ ከቤተ መቅደስ ሳይለዩ እንዲያገለግሉ የማይለወጥ ርስት ሆኖ ተባርኮ የተፈቀደላቸው ዐሥራት በኩራት ነው ።

እግዚአብሔርም አሮንን ‹‹ በምድራቸው ርስት በመካከላቸው ድርሻ አይሆንልህም፣ በእሥራኤል ልጆች መካከል ድርሻህና ርስትህ እኔ ነኝ፣ ለሌዋም ልጆች እነሆ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎትን ስለሚሰጡ የእሥራኤልን ልጆች ዐሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቻለሁ ›› አለው (ዘኁ.18:20-23)

ዕህልን የሚያበራየውን በሬ አፉ እንዳይታሠር /አንዳይታፈን/ በቅዱስ መጽሐፍ ታዝዞአል። ይህም ማንም ሰው የድካሙን ዋጋ ከሚያገለግለው ክፍል መቀበል ያለበት መሆኑን ያመለክታል። የራሱን ቀለብ እየበላ ቤተ መንግሥትን የሚጠብቅ /ዘብ እንዲቆም/ የሚገደድ /የሚመረጥ/ ወታደር የለም ።

በግብርናውም ዓለም ወይን ተክሎ ፍሬውን፣ ስንዴ ዘርቶ እሸቱን የማይበላ ፣ መንጋ እያረባ ወተቱን ሰጭነት አንዳር የተገለፀ ቃለ ሐዋርያ አለ ። ነጋዴውም ሆነ አርሶ አደሩ የድካሙን ትርፍ የሚያገኘው ከምድር በረከት ነው ። ለምድር ባለቤት በምድር አካባቢ ዐራቱን ባሕርያተ ሥጋ አስማምቶ ለሚመግብ ፈጣሪ የታዘዘውን /ድርሻውን/ መክፈል ይገባል ።

መንፈሳዊውን አገልግሎት የሚሰጡ ካህናትም ለሚሰጡት አገልግሎት ዋጋቸውን እንዲያገኙ ከእግዚአብሔር ተፈቅዶላቸዋል፣ የእግዚአብሔር ትእዛዝና ውሳኔ ነው ። የእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት በሰዎች አስተያየትና ውሳኔ የሚሻሻል የሚለወጥና የሚሻር አይደለም ።

እምነቱ፣ ማስተዋሉና በጎ ፈቃደኛነቱ ካለ ሕገ እግዚአብሔር ለሁሉ የሚከብድ ሸክም አይደለም ። የሚበልጠውን ዘጠኙን እጅ ለራስ አስቀርቶ ከዐሥር አንዱን እጅ ለእግዚአብሔር ከመስጠት የሚቀል ትእዛዝ ሊኖር አይችልም ። /ዘዳ. 25:4፣ 1ቆሮ. 9:4-14/

www.ethiopianorthodox.org

## ዐሥራት ለማንና ለምን እንደሚከፈል

የዐሥራት በኩራት አስተዋጽኦ ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋዮችና በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ለሚፈጸመው አገልግሎት የሚውል ነው ። ሙሴ ሕዝበ እሥራኤልን ከግብፅ የባርነት አገዛዝ ነጻ እንዲያወጣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝና መልእክት በጊዜው ለነበረው ፈርዖን እንዲያደርስ ተጠርቶ በተላከ ጊዜ ‹‹እኔ አንደበተ ርቱዕ አይደለሁም ከንፈረ ቆላፍ ነኝ›› ብሎ ለተልእኮው መሟላትና መቃናት የሚረዳውን ለማግኘት ለእግዚአብሔር ባቀረበው ልመና ‹‹ወንድምህ አሮን አፍ ይሆንልሀል / ይተረጉምልሃል/ ያዘዝሁህንም ነገር ሁሉ አንተ ትነግረዋለህ .... የእሥራኤልን ልጆች ከአገሩ ይለቀቅ ዘንድ ከፈርዖን ጋር ይናገራል ›› ተብሎ ለብሉይ ካህን ለአሮን በተሰጠው አምላካዊ ቃል መሠረት እስከ ዓለም ፍጻሜ በቤተ እግዚአብሔር ተመድበው በጸሎታቸው ከእግዚአብሔር ጋር ለሚነጋገሩ፣ መሥዋዕትን ለሚያቀርቡ፣ ዕጣንን ለሚያሳርጉ፣ ኃጢአትን የማስተስረይ ሥልጣን ለተሰጣቸውና የነፍሳትን ነጻነት ለሚያሰጡ ካህናተ እግዚአብሔር የኑሮ ድጋፍ የሚሆን ነው ። /ዘፀ. 6፡12፣ ዘኁ.18፡21-24/

ዐሥራት እንዲያወጡ የታዘዙም ምእመናን ብቻ አይደሉም ። የቤተ እግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናትም በማናቸውም መንገድ ከሚያገኙት ሀብት የዐሥራት ዐሥራት እንዲያወጡ ታዛዥል ። ሁሉም ተዳምሮ ለቤተ እግዚአብሔር ጠቅላላ አገልግሎት ይውላል ። /ዘኁ. 18፡26፣ ነህ. 10፡35-39፣ 12፡44፣ ሚል. 3፡10-12/

በዚሁ መልኩ ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት በሃይማኖት እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉ ካህናትና ምእመናን ሕይወት ይገባል ተብሎ ከእግዚአብሔር የተፈቀደውንና የታዘዘውን በማስተዋል ዐሥራት በኩራቱን የማውጣት ግዴታ እንዳለብን ሁላችንም ልንረዳው ይገባል ።/ዘዳ. 12፡6-7 ፣ 14፡22-26፣ ምሳ. 3፡10-12/

ለሕይወታችን የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ሕይወታችንንም ጭምር ለሰጠን ልዑል አምላክ፤ እንድንሰጥ የታዘዘውን ሁሉ በምንሰጥበት ጊዜ አክብደንና ሕይወታችንን እያስጨነቅን ሳይሆን ደስ እያለን መሆን እንደሚገባው ነቢያተ እግዚአብሔርና ባለሟሎቹ ቅዱሳን በየአንቀጹ ያስተምሩናል ።

‹‹በፍጹም ሰውነትህ እግዚአብሔርን ፍራው
አገልጋዮች ካህናትንም አክብራቸው፣
በፍጹም ዕውቀትህ ፈጣሪህን ውደደው፣

ለሚያገለግሉ ካህናትም የሚገባቸውን ከመስጠት አትለያቸው እግዚአብሔርን ፈርተህ የሚያገለግለውን ካህን አክብረው የታዘዘለትንም ድርሻውን ስጠው ከገንዘብህ ሁሉ ቀድሞ ያገኘኸውን›› / ሲራ. 7፡29-33/

‹‹ደስ ብሎህ እግዚአብሔርን አመስግነው፣ ካመሰገንሁትም ብለህ ቀዳማያትንና ዐሥራቱን መስጠትህን አትተው፣ ፊትህን አብርተህ ደስ እያለህም የሰጠህን ሁሉ ስጠው ዳግመኛም የሰጠህን ደስ ብሎህ ለሁሉ ስጥ ደስ እያለህም ዐሥራቱን አውጣ፤ ክቡርም እንደመሆኑ እንደክብርህም መጠን ለእግዚአብሔር መባን አቅርብ በእጅህም ሠርተህ ካገኘኸው ገንዘብህ ደስ ብሎህ መባን አቅርብለት፣ እግዚአብሔር ዋጋህን ሰባት እጥፍ አድርጎ ይሰጥሀል ›› /ሲራ. 32፡10-15/

## ስጦታው የት መቅረብ እንዳለበት ፤

ዐሥራት በኩራት ወይም ማናቸውም በስእለት፣ በብፅአትና በተለያዩ መንገዶች ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ስጦታዎች ሁሉ የሚሰበሰቡት እግዚአብሔር በመረጠው ስሙ በሚመሰገንበትና መለኮታዊ ጌትነቱ በሚነገርበት በቤተ እግዚአብሔር ነው ። /ዘዳ. 14፡22-25፤ ነህ. 10፡37-39፣ 13፣12፣ ኢሳ. 56፡7፣ ኤር. 7፡11፣ ማቴ. 21፡13፣ ሉቃ2:49/

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፪ (2000) ዓ.ም

መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለመረዳት የሚከተለውን ጥቅስ መነሻ አድርገን እንመለከታለን ። ‹‹... ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን... እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል፣ ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም›› ይላል የእግዚአብሔር ቃል /ማቴ. 20፡ 26-28/

ይህን ቃል የተናገረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሥራች እንደመሆኑ ቤተ ክርስቲያን የእርሱን ፈለግ በመከተል አገልጋይ እንጂ ተገልጋይ እንዳትሆን በዚህ ቃል አስተምሯል ።

## ዐሥራት በሐዲስ ኪዳን

የዐሥራትን አስተዋጽኦ ተገቢነትና አስፈላጊነት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ ጠቅሶታል፣ አስተምሮታል፣ አጽድቆታል ። /ማቴ. 22፡21፣ 23:23፣ ሉቃ. 18፡11-12/

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም በየመልእክታቱ በስፋት አስተምሮታል። የአማንያን ሁሉ ግዴታ መሆኑን በአጽንኦት ገልጾታል። እንዲያውም ዐሥራት በኩራትን አለመክፈል፣ ለእግዚአብሔር የተወሰነውን ድርሻ አስቀርቶ ለራስ ጥቅም ማዋል ታላቅ በደልና ጥፋት መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ቅጣትና ጉዳት አስመልክቶ ነቢዩ ሚልክያስ የጻፈውን ግልፅ አድርጎ በመልእክቱ አስቀምጦታል ። /ሚል. 3፡8-10 ሮሜ. 2:22/

መምህራን ከሚያስተምሩት ወገን ቀለብ ማግኘት እንደሚገባቸው ሐዋርያው ያስተምራል። /ገላ. 6:6/ ይህ ትምህርትና መመሪያ የእግዚአብሔር ፈቃድና ውሳኔ መሆኑን ያመለክታል። እሱም እግዚአብሔር በሀብት፣ በጤንነት፣ በዕውቀትና በልጅነት ያከበራቸው ምእመናን ሁሉ በኃላፊ ሀብት ለስተው እንዳይጎዱ ሁሉን አትርፎ በሚሰጥ እግዚአብሔር በረከት እንዲከብሩ ካላቸው በመርዳትና በማክፈል ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እንዲሰበስቡ ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስ ጠንክሮ እንዲመክር እንዲያስተምር አደራ ሰጥቶታል ። /1ቆሮ. 9:7-14፣ 1ጢሞ. 6:17-18/

ካገኙት ሁሉ ከዐሥር አንድ /ዐሥራት/ በመስጠት ክኅህኑ መልከ ጼዴቅ በረከትን ያገኙት የአብርሃም ልጆች ለሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ለካህናተ ወንጌል ዘለዓለማዊ የክህነት አገልግሎት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት እንዳለባቸው ጽፎአል ። /ዕብ. 6:20፣ 7:1-11/

የአብርሃም አምላክ ብለን ቅዱስ ስሙን የምንጠራ፣ የአብርሃም ልጆች ነን የምንል ሁሉ አብርሃም በሕገ ልቡና ተመራምሮ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ሥራ በመሥራት ለካህኑ መልከ ጼዴቅ ዐሥራት እንደሰጠና በረከቱን እንደተቀበለ እኛም በሃይማኖት የደረሰንን ሕጉንና ሥርዓቱን ልንጠብቅ፣ ትእዛዙን ልንፈጽም ይገባናል ። አባትን በሥራ እንጂ በስም ብቻ መምሰል ውጤት ሊኖረው አይችልምና ። /ማቴ. 3:9፣ ሮሜ. 4:12/

## ዐሥራት በኩራትን በመክፈል የሚገኝ በረከት፤

ሕጉን በመጠበቅ፣ ትእዛዙን በመፈጸምና በሥርዓቱ በመመራት ከፈጣሪአችን ጋር የቀረበ ግንኙነት፣ የሰመረ ወዳጅነት እንዲኖረን፣ የሰማይ መስኮቶች ተከፍተው የምሕረት ዝናም እንዲዘንምልን፣ በረከትን አትረፍርፎ እንዲያፈስልን፣ ዋጉ፣ ተምቼ፣ አንበጣውና ኩብኩባው በእርሻችን ያለውን አዝመራችንን እንዳያጠፋው ውርጭና በረዶ የወይናችንን ፍሬ እንዳያረግፈው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አጥፊውን ነገር ሁሉ እንዲገስጽው ለፍጥረት ሁሉ የምድርን በረከት እንዲያበዛለት ነው ። /ሚል. 3:7-12፣ ምሳ. 3 :9-10/

በሙሴም ሕግ እንደተጻፈው የሚቀርበው ስጦታ ሁሉ፣ ለሕይወት፣ ለበረከት፣ ለቅድስና መሆኑ ይታወቃል ። አብርሃምም ለካህኑ መልከ ጼዴቅ ባቀረበው ዐሥራት ከካህኑ ያገኘው በረከትን ነው ።
(ዘፍ.14:20)

www.ethiopianorthodox.org

«የተቀደሰውን ነገር ከቤቴ ወስጄ ለሌዋዊው ለመጻተኛው ለድሀ አደጉም፣ ለመበለቲቱም እንዳዘዝኸኝ ሁሉ ሰጥቻለሁ፣ ትእዛዝህንም ምንም አላፈረስሁም፣ አልረሳሁም፣ በኀዘኔ ጊዜ እኔ ከእርሱ አልበላሁም፣ ... የአምላኬን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቼአለሁ ያዘዝኸኝንም ሁሉ አድርጌአለሁ ፤ ከቅዱስ ማደሪያህ ከሰማይ ኀብኝ ሕዝብህንም እስራኤልን ባርክ» /ዘዳ. 26፡13-15/

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሁሉ ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን ለተወጡትና በመጽሐፍ ቅዱስ የተደነገገውን ለሚፈጽሙ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን በርዋን ከፍታና የተቃና አስተዳደር መሥርታ የሚያስፈልገውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ ስታበረክት ኑራለች፤ አሁንም የማበርከቷ ሒደት እንደቀጠለ ይኖራል ፡፡

ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን የምታበረክተው ያላት አስተዳደር በሚነድፈው መርሐ ግብር እየተመራች ነው፡፡ የየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ቃለ ዓዋዲውን መሠረት አድርጎ በሚያወጣው የአገልግሎት መርሐ መሠረት ካህናትና ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ያከናውናሉ ፡፡

ከላይ ከመንበረ ፓትርያርክ ጀምሮ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ የአስተዳደር መዋቅር አለ ፡፡ የዚህ አስተዳደር መሠረታዊ ዓላማ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን የአገልግሎት ኃላፊነት በአግባቡ እንድትወጣ ማድረግ ነው ፡፡

በልዩ ልዩ የተልእኮ ዘርፍ ማለት በቅስና፣ በዲቁናና በመዘምርነት እግዚአብሔርን ማመስገን፣ ፈጣሪነቱን፣ ኃያልነቱንና ገናናነቱን በቅዳሴ በውዳሴ በዝማሬ መግለፅ፤

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም የእግዚአብሔርን ጸጋ ማሰጠት፣ በጸሎት፣ በአስተብቁዖት፣ በምሕላ የፈጣሪን ምሕረቱን፣ ሰላሙን፣ ፍቅሩን ማስገኘት፣ ከሁሉም በላይ የመንፈሳዊ ሕይወት ምንጭ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔር መስበክ ማለት ትምህርተ ወንጌልን ማስፋፋት ከየአንዳንዱ አገልጋይ የሚጠበቅ ተግባር ሲሆን፤

ይህንም አገልግሎት የጀመረው፣ ያስተማረውና ቤተ ክርስቲያን እንድትፈጽመው ያዘዘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፡፡

ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰቡ መካከል የምትገኝ፣ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት የቆመች የእግዚአብሔር መንግሥት እንደመሆኗ ለኅብረተሰቡ በትምህርት፣ በጤና፣ በምግባረ ሠናይና በልማት ዘርፎች ለምትሰጠው አገልግሎት ጀማሪውና ፈጻሚው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ «ሑሩ ወመሐሩ» «ሒዱና አስተምሩ» ብሎ ትምህርትን፣ በተለያየ በሽታ ተይዘው ይሠቃዩ የነበሩ ድውያንን በመፈወስ ጤና አጠባበቅን፣ ለተራቡ በማዘን አምስት እንጀራንና ሁለት አሣን አበርክቶ በማብላት ምግባረ ሠናይን ወዘተ. በተግባር በማሳየት ቤተ ክርስቲያን ኅብረተሰቡን እንድታገለግል እንድታስተዳድር አዝዟታል፣ አርአያነቱን አሳይቷታል ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ እነዚህን ታላላቅ አገልግሎቶች ስትፈጽም ኖራለች፣ በትምህርት ዘርፍ ብቻ የፈጸመችውን እንኳ ብንጠቅስ ፊደል ቀርፃ፣ ቀለም አሽታ፣ ብራና ፍቃ መጻሕፍትን አዘጋጅታ ከፊደል ቁጠራ እስከ ዳዊት ደገማ፣ ከዚያም እስከ ትምህርተ ሃይማኖት ያለውን ሁሉ በማስተማር ስፊ ማኅበራዊ አገልግሎትን ስታበረክት ኖራለች፣ አሁንም በማበርከት ላይ ትገኛለች ፡፡ በጤና ረገድም ሊቃውንቷ ከተለያዩ ዕፀዋት፣ መድኃኒቶችን በመቀመም በሽታን ሲከላከሉ ከመኖራቸው ጋራ በትምህርት፣ በተአምራትና በመሳሰሉ ሁሉ ሀብተ ፈውስ ስታሰጥ ኖራለች፡፡ በምግባረ ሠናይ በኩልም በሮቿን፣ ደጆሏሞቿን የድሆች፣ የችግረኞች መጠጊያ በማድረግ እስካሁን ስትሬዳ ትገኛለች፤ እየረዳችም ነው ፡፡

በአጠቃላይም ቤተ ክርስቲያናችን ለኅብረተሰቡ የምትሰጠው አገልግሎት ዘመኑ በሚፈቅደው መሠረት የተሟላና የተደራጀ ሆኖ ተገልጋዩ ሕዝብ በሚገኝበት በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ በሚከተሉት ዘርፎች ተገቢው አገልግሎት እየተሰጠ ነው ፡፡



ለማስረጃም ያህል፤

### ሀ/ በትምህርት ዘርፍ

- አፀደ ሕፃናት
- የ1ኛ ደረጃ ትምህርት
- የ2ኛ ደረጃ ትምህርት
- የሙያ ሥልጠና ትምህርት
- የ3ኛ ደረጃ ትምህርት /መንፈሳዊ ኮሌጅ ወዘተ/

### ለ/ በጤና ዘርፍ

- አነስተኛ ክሊኒክና ላቦራቶር
- ከፍተኛ ደረጃ ክሊኒክና ላቦራቶር
- የጤና ጣቢያ
- መለስተኛ ሆስፒታል
- መድኃኒት ቤት

### ሐ/ በምግባረ ሠናይ ዘርፍ

- ለድሆችና ለደካሞች መርጃ የሚሆን ርዳታ መስጫ ተቋም በማቋቋም
- እናት አባት ለሌላቸውና አሳዳጊ ላጡ ሕፃናት ማሳደጊያዎችን በመመሥረት፤

### መ/ በገጠር ልማት ዘርፍ

- አነስተኛ የእርሻ ልማት
- ከብት ርባታ
- የደን ልማትና የአካባቢ ጥበቃ
- የንብ ርባታ
- የንጹሕ ውሀ አቅርቦት

ከዚህ በላይ እንደተነገረው ቤተ ክርስቲያናችን በእነዚህ ዘርፎችና በመሳሰሉት መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን በመስጠት ላይ ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ በምሥራቅና በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ ከጥንቱ ከጧቱ ሠሪዋም፤ አስተዳዳሪዋም እግዚአብሔር ነው ፡፡

ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት ከእግዚአብሔር የተሰጠች ሀገረ እግዚአብሔር ናት፤ ሕዝቧም ሕዝበ እግዚአብሔር ነው ብለናል ፡፡

የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ቅርሶች ከሆኑት አንዱ ይህ በዘመን አቁጣጠር የተደረሰበት ፅሥራ ምዕት ወይንም ሁለት ሺህ ዓመተ ምሕረት የሆነውን ክብረ በዐልና በየዘመናቱ የነበረውን አስተዳደር ገጽታ በተገቢው ሁኔታ ማየቱና መመልከቱ ተገቢ ይሆናል ፡፡

ይሁንና ከነበረው ከታሪካችን ጉዞ የተረዳነው፤ የሀገራችንና የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር ያን ሁሉ ፈተና አልፎ አንድነቱ፣ ነፃነቱ፣ ጸርድንበሩ እንደተጠበቀ ከዚህ መድረሱን ነው፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደሯ ለበዙ ዘመናት ፊደሉን፣ ቋንቋውን፣ ስነ ጥበቡን፣ ኪነ ጥበቡን፣ ተዋሕዶ ሃይማኖቱን፣ ጠብቃ አስጠብቃ ያቆየች፣ አሁንም ጠብቃ በበለጠ፣ በማስተማር ላይ የምትገኝ ናት፤ ከዚህም ጋር ከልደተ ክርስቶስ በፊት የነበረውን ታሪክ ሳይጨምር ቤተ ክርስቲያናችን የ2,000 ዘመናት የአስተዳደር ልምድ ያላት በአፍሪካም ቀደምትና ብቸኛዋ የነፃነት ባለቤት መሆኗን ታሪክ ያረጋገጠው ነው ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

የዚህም አኩሪ ታሪክ ባለቤት የሆነው ሕዝቧም ለሀገሩ ህልውና ለነፃነቱና ለብአዊ ክብሩ አቻ የሌለው መሥዋዕትነትን ከፍሏል ። ሕልውናውን ከማረጋገጡ ባሻገር በእምነቱና በዕውቀቱ የታነፀ ማኅበራዊ ሥርዓትን በመገንባትና በማዳበር የሁለት ሺህ ዘመናትን የታሪክ ማዕበል በረጋ መንፈስ በሙሉ ልብ አሳልፎ ኅብረቱንና አንድነቱን ጠብቆ እነሆ አሁን ከምንገኝበት 2,000 ዓ.ም. መዳረሻና 3,000 ዓ.ም. መነሻ ለመድረስ በቅቷል ።

ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያውያት የኑሮ ሥርዓታቸው በሕገ እግዚአብሔር የተመሠረተ እግዚአብሔርን እምላኪች በአጠቃላይ በነበራቸው አስተዳደር ከነገሥተ ተርሴ ወዴያት ጋር ተወዳዳሪች የነበሩ መሆናቸውን ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙረ ዳዊቱ ይናገራል። (መዝ. 71:9-11)

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ያላት ሀገረ ስትሆን ያስተዳደሯ፣ የሕልውናዋ ታሪክ የታወቀውና የሚታወቀው ከአምልኮተ እግዚብሔር ጋር ባላት የሃይማኖት ታሪክ መሆኑ ግልጥ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማንም ሰው ዓይን መታየት ያለባት በጥንታዊነቷ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድ ለእግዚአብሔር መንግሥት ጽናት የራሷ የሆነ ጥንታዊ የክርስትና የአስተዳደር ታሪክ ማቆየቷ፣ ለሀገር አንድነትና ነፃነት ስላደረገችው መሥዋዕትነት ጭምር መሆን አለበት።

ከፍ ብሎ ከተነገረው መረዳት እንደተቻለው፣

-የቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ሀብት በነገሥታቱ በመኳንንቱ በመግፍጉቱ፣ በወይዛዝርቱ በአጠቃላይ በምእመናን በምእመናት ልግስና፣ ርዳታ ከጊዜ በኋላም በመሬትና ከመሬት በተገኘ አላባ ላይ የተመሠረተ እንደነበረና እንዲሁም ከቤቶች ኪራይ በሚገኝ መጠነኛ የኪራይ ገቢ ስትተዳደር መቆየቷ ተወስቶአል ።

-የመሬት ይዞታውን በተመለከተም በስም የሲሶ መንግሥት ባለቤት ናት እየተባለ የሚነገር ከመሆኑ በቀር ሲሶ መንግሥት ማግኘት ቀርቶ በራስዋ ይዞታ ሥር ከነበረው የሰሞን መሬትም እንኳ ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ እንዳልነበረች የታወቀ ነው ።

-ትጠቀምበት የነበረው የሰሞን መሬትና የኪራይ ቤት ገቢ ከ1967 ዓ.ም. የመሬት፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ዓዋጅ ወዲህ፣ የኪራይ ገቢ ታገኝባቸው ከነበሩት ሕንፃዎችና ቤቶች ጋር ተወርሶ ቆይቷል፣ የሰሞን መሬቱም መሬት ላራሹ በሚለው መፈክር የተወሰደ ነው ።

-የመሬትዋና የቤቶቿ መወረስም ቤተ ክርስቲያኒቱ ከጥንት ጀምሮ ትሠራበት ወደነበረው የዐሥራት በኩራት አስተዋጽኦ እንድታተኩር የግድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲቋቋምና ደረጃ በደረጃ እየተጠናከረ እንዲሔድ ተደርጎአል ።

-ቤተ ክርስቲያን በሰበካ ጉባኤ መደራጀቱን ቀደም ብላ የጀመረች መሆኑ ቢታወቅም የዐሥራት በኩራቱ አስተዋጽኦ ክፍያ በቅዱሳት መጻሕፍት በተገለፀውና ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን ኋላም በሐዲስ ኪዳን በዘመነ ሐዋርያት ይሠራበት በነበረው ዓይነትም የተሟላና የተስተካከለ አይደለም ።

-ሰበካ ጉባኤን በተጠናከረ መልኩ ለማደራጀት የሕዝበ ክርስቲያኑን መንፈሳዊ ግዴታ በአግባቡ ለማሳወቅና ለማስፈጸም ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ ብዙ ማስተማርና ማስተባበር ያስፈልጋል ።

-ከዚህም ጋር ይህች ጥንታዊት፣ ታሪካዊት፣ ብሔራዊት ሐዋርያዊትና ሉዓላዊት ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጠው ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሰፊ አገልግሎት ባሻገር እምነትዋን፣ ሥርዓትዋንና ትውፊትዋን የሚቀናቀኑ ልዩ ልዩ ድርጅቶችን መቋቋም እንድትችል የሰበካ ጉባኤን ገቢ በማጠናከር መንፈሳዊውንና ማኅበራዊውን አገልግሎት ማስፋፋትና ማጠናከር ይኖርባታል ።



በአጠቃላይም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት እየተጠናከረ፣ እያደገና እየሰፋ ከግቡ መድረስ የሚችለው መላው የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ካህናትና ተክታዮች ምእመናን ምእመናት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዓላማና ተልዕኮ መሟላት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው በተግባር ተሠልፈው ሲገኙ ብቻ ስለሆነ አፈጻጸሙ በበለጠ ሊተኮርበት የሚገባ ነው ።

- ይህ የካህናትና የምእመናን ኅብረት ለ3ኛ ጊዜ ተሻሽሎ በወጣው የቃለ ዓዋዲ ረቂቅ ደንብ መሠረት ከብዙ አቅጣጫ ታይቶና ተጠንቶ የቀረበውን የ20% /ሃያ ከመቶ/ ክፍያ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ እምነት ተጥሎበታል ።

- የ20% /ሃያ ከመቶ/ ክፍያ ተግባራዊ መሆን የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትንም ሆነ በየደረጃው የተዋቀሩትን የቤተ ክርስቲያኒቱን መዋቅሮች ያጠናክራል እንጂ የሚያስከትለው ጉዳት የለም፣ ይህም በጥናት የተረጋገጠ ነው ።

ምእመናንም በሃይማኖት መንፈሳዊ ግዴታቸው አምልኮተ እግዚአብሔርን ለሚፈጽሙባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲከፍሉ የሚጠየቁት አስተዋጽኦ በቅዱሳት መጻሕፍት እንዲከፍሉ ከታዘዘው ዐሥራት /ከዐሥር አንድ/ እጅግ አነሥተኛ ከመሆኑም ሌላ ከእግዚአብሔር ከሚያገኙት ልዩ ልዩ ሀብትና በረከት አንፃር ሲታይ የበለጠ በረከትን የሚያስገኝላቸው እንጂ የሚጎዳቸው አለመሆኑን ሁሉችም ሊገነዘቡት ያስፈልጋል ።

ቤተ ክርስቲያናችን ቅድመ ሰበካ ጉባኤ በመሬት አላባ ላይ በተመሠረተና በበጀት አያያዝ ረገድ ከመላ ጎደል በሆነ ሀብት ስትተዳደር መቆየቷ ቢታወቅም ያንን ይተካል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ሰበካ ጉባኤ የነበራትን ሀብት የሚተካ ሆኖ ባለመገኘቱ በየዓመቱ ከመንግሥት የተፈቀደውንና የሚፈቀደውን የድጋፍ በጀት እገዛ በማድረግ እስካሁን እያዘገመች መቆየቷ ግልፅ ነው ።

ይሁንና ይህ አሁን ያለንበት ወቅት የሁሉም እምነት የእኩልነት መብት እንዲጠበቅ የሚያደርግ ሥርዓተ ማኅበር የሰፈነበት ጊዜ ስለሆነ ከዚህ ግንዛቤ አንጻር እንደ ጊዜው ሁኔታ ራስን በራስ ለማስተዳደርና ነፃ ለመውጣት ጥረት ከማድረግ በቀር አማራጭ እንደሌለን በመገንዘብ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ያልተቆጠበ ጥረት በቅዱስ ሲኖዶስ ወሳኝነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በጎ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን ችላ እንድትተዳደር ተደርጓል፣ እየተደረገም ነው ።

እንግዲህ ያለፈውንና የጊዜውን ታሪካችንን መነሻ በማድረግ ወይንም ከአለፈውና ከአሁኑ ታሪካችን በመማር፣ የአሁኑንና የወደፊቱን የአስተዳደር ሒደታችንን መገንባት የሚቻለው በአሁኑና በሚቀጥለው ትውልድ ጥረት ስለሚሆን የአሁኑንና የሚቀጥለውን ትውልድ ለዚህ አላማ በትምህርት ማዘጋጀቱና ብቁ ማድረጉ አማራጭ የማይገኝለት የቤተ ክርስቲያናችን ተቀዳሚ ሥራ መሆኑ ታውቆ በተግባር መታየት ይኖርበታል ።

ስለዚህ ይህን ተልእኮ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ከመንበረ ፓትርያርኩ ቢሮ ጀምሮ የሥራ ኃላፊነት የተጣለብን ሠራተኞች የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ኤጲስቆጳሳት፣ ኤጲስቆጳሳትና የየሥራ ዘርፉ ኃላፊዎች ሁሉ የሚፈለግብንን ግዴታ በበለጠ መወጣት ይጠበቅብናል፣ የየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ ካህናትም ሁሉ ሊተባበሩ ይገባል ። ለዚህም መርሐ ግብር አፈጻጸም የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች የሆን ሁሉ በርትተን እንድንሠራ በቤተ ክርስቲያናችን ስም አደራ እላለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 14

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅርሶች

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ዕድገቱ የተገነባው የኢትዮጵያዊነት ክርስትና መሰዮ በሆነው "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች፡፡" በሚለው መሠረት ላይ ነው፡፡ (መዝ. 67፣37)

ታሪክ መስታወት ነው፡፡ የረቀቀውን አጉልቶ የተረሳውን መዝግቦ ያሳያል እንደሚባለው የአንድ አገር ሕዝብ ታሪኩ፣ ጀግንነቱ፣ ታላቅነቱ፣ ባህሉና አኗኗሩ በሚገባ ሊታወቅ የሚችለው በሥነ-ጽሑፍና በሥዕል ወይም በቅርጻቅርጽ ተስሎና ተቀርጾ ለትውልደ ትውልድ በሚተላለፈው ሥዕላዊ መግለጫ እንደሆነ ማንም ሰው የሚረዳው ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በሕገ ኦሪት፣ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ በሕገ ወንጌል ያመነች ጥንታዊት ሀገር ከመሆኗም በላይ በዚያው ዘመን ርዝመት መጠንም በሥነ-ጽሑፍ የታወቀችና የሕዝቧ ሥልጣኔ፣ ጥንታዊነቱ፣ ጀግንነቱ፣ እምነቱና ባህሉ ሌላውም ሁሉ እንዴት እንደሆነ ሊታወቅ የቻለው፡፡ መጀመሪያ በሐውሎቶች በጠፍጣፋ ድንጋዮችና በሸክላ ዕቃዎች ላይ በኋላም ብብራና ተጽፈውና ተሥለው ለትውልደ ትውልድ እየተላለፉ በመጡት የቅርጻቅርጽ፣ የጽሑፍና የሥዕል ቅርሶች ነው፡፡ ከታሪክ ማኅደር እንደምንረዳው በሀገራችን ሥነ-ጽሑፍ የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ለመሆኑ ብዙ መረጃዎች ይገኛሉ፡፡

ለምሳሌም ያህል በአክሱም ሐውልቶች ላይ በሳባውያን፣ በግሪክና በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ጽሑፎች የዓይን እማኞች /ምስክሮች/ ናቸው፡፡ ሆኖም የሥነ-ጽሑፍ መሠረት የሆነው ፊደልና የሥነ-ጽሑፍ ስልት በደንብ የታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት በኢትዮጵያ ከተጀመረበት ዘመን አንስቶ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ዓለም ገና በጨለማ ውስጥ በነበረበት የዕውቀት ብልጭታም ባልፈነጠቀበት ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊታውንት ከበግ፣ ከፍየልና ከልዩ ልዩ እንስሳት ቆዳ ብራና ፍቀው ልዩ ልዩ ቀለማ-ቀለማትን ቀምመው የሸምበቆ ብዕር ቀርጸው በጉልሕ ወይም በረቂቅ ለመጻፍ የሚያስችል ሁኔታ እያዘጋጀ ከፈደል በኋላ ከዘመናዊው የአሠራር /የአጠራረዝ/ ስልት በማያንስ ሁኔታ እየጠረዙና እየደጎሱ ለተጠቃሚው ሕዝብ በማቅረብ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ያደረገችው አስተዋጽኦ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

በመልክዓ ምድር አቀማመጧ ውብና ድንቅ የሆነችው አገራችን ኢትዮጵያ የሰው ልጅ የኖረባት ለመሆኗ አያሌ ማስረጃዎች አሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የብዙ ተመራማሪዎች ጥናት የሚካሄድባት የውጪ አገር ጎብኚዎችንም ትኩረት የምትስብ ሆናለች፡፡

የሰው ልጅ አጽም ተሟልቶ የተገኘባት ኢትዮጵያ በአስቸጋሪውና በቆላማው የአገራችን ክፍል አርኪዮሎጂስቶች ለረጅም ጊዜያት ተሰማርተው አመርቂ የምርምር ሥራዎቻቸውን ለዓለም በማቅረብ ላይ የሚገኙባት አገር ነች፡፡

ከዚህም አልፎ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ጀምሮ በተመራማሪዎች ዘንድ ብዙ ትኩረት ሲሰጥ የቆየው ጥንታዊ ሥልጣኔ ብዙ ጥናቶች የተደረጉበትና የምርምር ጽሑፎችም የቀረቡለት ነው፡፡

ካለው በርካታ የታሪክ ቅርስ አኳያ ሲታይ ግን ዕውብና ድንቅ የሆኑትን የታሪክ አሻራዎች መቼ፣ እንዴትና ለምን እንደተሰሩ ለመግለጽ የሚያስችሉ ማጠቃለያዎች ተሟልተው ገና አልቀረቡም፡፡ እስካሁን ባለው ሁኔታ መልሶችን ለመስጠት ከመሞከር ይልቅ ታሪካችንን ለሚመለከቱ ጥያቄዎችን በማንሳት መገረምና ማሰላሰል የበለጠ ቀላል ነው፡፡



የአያሌ ጥንታዊና አስገራሚ ታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት የሆነችው አገራችን በየዘመኑ ታሪኳ ከውልና ከውስጥ ይነሱ በነበሩት ጦርነቶች ምክንያት የጀመረችውን የሥልጣኔና የእድገት ፈለግ ከመቋረጡም በላይ የነበረውም ቢሆን ተበታትኖና ተበላሽቶ በአብዛኛው ለጥፋት ተዳርጓል፡፡ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ሲያባሩ የነበሩት አለመረጋጋቶች ያካበትናቸውን አያሌ የድንጋይና የብራና ጽሑፎች ተሰብስበው የታሪክ ሠነድ አሟልተን በያዝ ታሪካችንን በሚገባ ለመግለጽ ሳያስችሉን ቆይተዋል፡፡ የዚህ አኩሪ ቅርስ ባለቤት የሆነው ህዝብም ታሪኩን በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ብቻ በመግለጽ ከሚገኝበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

እስካሁን ምርምርና ጥናት የተካሄደበት የአገራችን ታሪክ በአብዛኛው በውጭ ምሁራን የተካሄደ በመሆኑ በራሳችን ቋንቋ በሚገባ ተተርጉሞና ተዘጋጅቶ ሕዝቡ በስፋት እንዲያውቀው ለማድረግ አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ለማንበብ ወይም ተዘዋውሮ አገሩን ለማወቅ አቅም ያለው ኢትዮጵያዊ ሳይቀር ታሪኩንና ያካቶቹን አኩሪ ቅርስ በጥልቀት ለማወቅ አላስቻለውም፡፡ ስለ ጥንታዊ ታሪካችን ጉዳይ ሲነሳ የኢትዮጵያ ጥንታዊትና ታሪካዊት አገር ለመሆኗ በብዙዎች ዓለም አቀፍና በታሪክ ዘንድ የሚታወቅ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያለው እውቀት ግን አነስተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ አክሱምን ከአንድ ሐውልትና አንድ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ሌላ ምንም የሌላት የሚመስላቸው ሰዎችም ብዙዎች ናቸው፡፡

ላሊበላን ከውቅር ቤተ ክርስቲያን በቀር ሌላ ምንም የሌላት አስመስለው የሚናገሩም አሉ፡፡በኢትዮጵያ ድንቅ የተባለ እነዚህም አብያተ መንግሥት፣ ሐውልቶች፣ መቃብሮች፣ ጥርብ የድንጋይ ቅርሶችና ሌሎች ከምድር በላይና በታች የሚገኙ የታሪክ ሥፍራዎች ናቸው፡፡

በአገራችን ውስጥ ያሉትንና ወደሌሎች አገሮች የተሸገሩትን ቅርሶች በተመለከተ በርካታ ጽሑፎች የወጡና በመውጣት ላይ ያሉ ቢሆንም ከጊዜው ርቀትና በመረጃዎች መውደም፣ መጥፋት ወይም ተቆፍረው ያለመውጣት የተነሣ በምርምር በተገለፁትና በአፈ-ታሪክ በሚነገሩት ታሪኮች መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ በቁፋሮዎች የሚገኙት ማስረጃዎች በምርምር ጥናት ለሚደረጉ ትንተናዎች መሠረት ሲሆን በአፈ-ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆዩት ታሪኮች ደግሞ ለዘመናዊ ምርምር አጋዥነት ቢኖራቸውም የማስታወስ ችሎታንና የተናጋሪዎቹን ስሜት ተከትለው የሚሄዱ ናቸው፡፡ በአገራችን ውስጥ ከ12ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በቀደምት ሊታውኑት የተጻፉ የብራና መጻሕፍትም ለዘመናዊው ታሪክ ምርምር ሥራ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ቀላል ባይሆንም ዓላማቸውና አጻጻፋቸው ሃይማኖታዊ እሴትን ለማጐልበርና በጸሐፊዎቹ የማስታወስ ችሎታ ላይ ተመርኩዘው የተጻፉ ናቸው፡፡ ስለዚህ የብራና መጻሕፍት በሃይማኖት መሪዎች ተከታት ከፍተኛ ክበራታ አላቸው፡፡

በዘመናዊ የታሪክ ምርምር የተሰማሩት የውጭና የሀገር ውስጥ ምሁራን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያወጧቸው ጽሑፎች ማስረጃዎችና ቀደም ሲል የውጭ አገር ተመራማሪዎች ያሳተሟቸውን መጻሕፍት ዋቢ አድርገው በመጥቀስ ነው፡፡ በአንዳንድ የተለየዩ ሁኔታዎችም ጥንታውያኑ የሀገር ውስጥ የብራና መጻሕፍት እንደማነባበሪያና እንደማሟያ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ስለዚህም ዘመናዊው የታሪክ ምርምር ውጤት ለባለታሪክ በሚገባ መንገድ ሊቀርብ ባልቻለበት ሁኔታ ውስጥ እየተረሳ ያለውን ፈአ-ታሪክ እንደያሁኔታው እየገደለበትና እየተጨመረበት ለመጠቀም የግድ ይሆናል፡፡ ይህም የታሪክ ትምህርት በሕብረተሰቡ ዘንድ ሊኖረው የሚችል ጥቅም እንዳይጎላ ከማድረጉም በላይ ሕዝቡ ታሪካዊ ቅርሶቹን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ብታት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡ ከዚህም በላይ አገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክና ነባትት ያላት ጥንታዊት ሀገር መሆኗን አበክር ለማወቅ የሚጣጣረው ዜጋዋ ራሱ አይቶና አንብቦ ለመረዳት የሚኖረው ዕድል ጠባብ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በቅርብ ጊዜ እየተደረጉ ያሉት ጥናቶችና ምርምሮች የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ጎልቶ እንደወጣ እያበረከቱት ያሉት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት የተጀመረው ዘመናዊ የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ እስካሁን የተራመደበት የዕድገት ሂደት በጣም አዝጋሚ መሆኑ ባይካድም በቅርብ ዓመታት የተካሄዱት ተከታታይ ጥናቶች ግን አበረታች ናቸው፡፡

ሌላው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ምን እንዳለና በቤተ ክርስቲያን ዙርያ ያሉት የታሪክ ቅርሶችን በሚመለከት ያለው እውቀት ለአካባቢው ነዋሪዎቹ ሳይቀር እውቀቱ አነስተኛ ነው፡፡ስለዚህ እውቀትና ግንዛቤ አለመዳበር በርካታ ምክንያቶች ሊቀርቡ የሚችሉ ቢሆንም ዋና የሚባሉትግን በጽሑፎችና በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት ታሪካችንንና ቅርሳችንን ለማስተዋወቅ የተደረገው ጥረት አምነት ነው፡፡የኢትዮጵያ ቅርስና ታሪክ፣ በውስጧ የያዘቻቸውን ቅርሶችና ሌሎች መስህቦች፣ ኢትዮጵያ በሰው ልጅ ታሪካዊ ዕድገት ሂደት ውስጥ በጥንታዊ የሕንፃ አሠራር፣ ሀብረተሰባዊ አደረጃጀት፣ በሥነ-ጽሑፍ በሥዕል የሃይማኖታዊ ትሩፋቶችና ሌሎች የሥልጣኔ አሻራዎች ያበረከተችው አስተዋጽኦ የሚገባውን ያህል እንዲታወቅ አልተደረገም፡፡አሁን ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብን አርሶ መበቀያ፣ በጥቁር አፍሪካ የመጀመሪያዋ ቤተ

www.ethiopianorthodox.org



በወርቅና በብር የተሰበጠ ወንጌል





የብራና ላይ የውስጥ ሥዕላት እና ሐረጎች





በብራና ተጽፈው በሐረጋት የተጌጡ መጻሕፍት

www.ethiopianorthodox.org

ጥንታዊ መየር መስቀሎች





የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም



ከብርና ከወርቅ የተሰሩ
የጥንት መጾር መስቀሎች





www.ethiopianorthodox.org

ከወርቅ ከብርና ከአንጨት የተሠሩ የእጅ መስቀሎች



ከወርቅ የተሠራ የወርቅ መጸር

ከብር የተሠሩ የእጅ መስቀሎች

www.ethiopianorthodox.org

በወርቅ ሙካሽ የተሠሩ ጥላዎች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

በወርቅ ሙካሽ የተሠሩ አልባሳት



www.ethiopianorthodox.org

በወርቅ ሙኃኒሽ የተሠሩ አልባሳት

የፓትርያርክ አስኬማ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

የወርቅ ዘውዶች

አርዋ ብርት

www.ethiopianorthodox.org

ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፍ

የጥንት ሳንቲሞች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም



አይሕኖች

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም



ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ገጽታ

www.ethiopianorthodox.org



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም



ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ገጽታ

www.ethiopianorthodox.org

ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ገጽታ



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም



የሳባ ቤተ መንግሥት ፍራሽ

www.ethiopianorthodox.org



ቤተ ማርያም



ሚካኤል አምባ /ትግራይ/

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም



ይምርሃነ ክርስቶስ



ቤተ አማኤል

www.ethiopianorthodox.org



ደብረ ብርሃን ሥላሴ /ጎንደር/

የጥምቀት በዓል /ጎንደር/

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም



ክብራን ገብርኤል

አክሱም ጽዮን

www.ethiopianorthodox.org



ደብረ ዐሐይ እንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን

ደብረ ኃይል እንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን



ታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም

www.ethiopianorthodox.org



መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል



ደብረ ሳሌም ቦሌ መድኃኔዓለም ካቴድራል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፤ (2000) ዓ.ም

## ዋቤ መጻሕፍት


1. ሉሌ መልአኩ "የቤተ ክርስቲያን ታሪክ" አዲስ አበባ
2. ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የሥራ አካሄድ የተሰጠ ጠቅላላ ደንብ 1946 ዓ.ም. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመ
3. ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ "ሠለስቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት" የ1951 ዓ.ም. አዲስ አበባ
4. ሊቀ ሊቀውንት መሐሪ ትርፌ "የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው" 1948 ዓ.ም. አዲስ አበባ
5. ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ "ገድለ ተክለ ሃይማኖት" አዲስ አበባ
6. ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ "ስንክሳር" አዲስ አበባ
7. ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ "መርሐ ልቡና" 1943 ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
8. ሊቀ ጎሩያን ዘገየ ገብረ ሥላሴ ዘደብረ መዊእ "500 የቅኔ ጎዳናዎች" /ያልታተመ/
9. "ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ትናንትናና ዛሬ" ህዳር 8 ቀን 1994 ዓ.ም.
10. "ሐመር መጽሔት" የተለያዩ ዕትሞች
11. መጽሐፍ ቅዱስ (ንባቡና ትርጓሜው)
12. "መዘክረ ምግባር መንፈሳዊ" ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የተጻፈ አዲስ አበባ
13. "መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ" 1917 ዓ.ም. /ትርጓሜ/ አዲስ አበባ
14. "መጽሐፈ ቅዳሴ" 1918 እና 1928 ዓ.ም. ትርጓሜ አዲስ አበባ
15. "መጻሕፍተ መነኮሳት" 1920 - 22 ዓ.ም. አዲስ አበባ
16. መምህር ሉሌ መላኩ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" 1997 ዓ.ም.
17. መምህር መንክር መኮንን "መጽሔተ ሊቃውንት" 1969 ዓ.ም.
18. መ.ጋቤ ብርሃናት ተስፋ ጥሩነህ "ማዕዶት መጽሔት" ጥር 11 ቀን 1977 ቁ.16
19. መምህር ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ "ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ" 1989 ዓ.ም.
20. መምህር ይኄይስ ወርቁ "ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት አዕማደ ምሥጢራት"
21. መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ "ዝክረ ሊቃውንት" አንደኛ መጽሐፍ ከ - ቀ እና ከበ-ፈ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1963 ዓ.ም. እና 1991 ዓ.ም.
22. ማኅበረ ቅዱሳን "የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር" 1996 ዓ.ም.
23. "ማዕዶት መጽሔት" ቁጥር 13/1979 ዓ.ም.
24. "ማዕዶት መጽሔት" ቁጥር 19/1978 ዓ.ም.
25. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ 1915 እና 1924 ዓ.ም.
26. ቆሞስ አባ ተክስተ ብርሃን ወ/ሳሙኤል "ባህታውያን ከዋልድባ ገዳም" አዲስ አበባ 1997
27. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ "የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ"
28. በረሁን ከበደ "የዋልድባ ገዳም ታሪክ " 1983 ዓ.ም.
29. በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን መምሪያ "ልማትና አስተዳደር አዲስ አበባ" 1978
30. ባላምባራስ ማህተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል "ዝክረ ነገር" 1942 ዓ.ም.
31. ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ "መዝሙረ ዳዊት" 1950 ዓ.ም. ትርጓሜ


www.ethiopianorthodox.org

32. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ "የኢትዮጵያ ብርሃን ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት" 1993 ዓ.ም.
33. ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ "የመጀመሪያው ኢትዮጵያ ፓትርያርክ" 1978 ዓ.ም.
34. ብላቴን ጌታ ኀሩይ ወልደ ሥላሴ "መጽሐፈ ቅኔ" 1918 ዓ.ም. አዲስ አበባ
35. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ "የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጌ" "ከዛጌ እስከ ዓፄ ይኩኖ አምላክ" "ከአፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል" "ከዓፄ ልብነ ድንግል እስከ ዓፄ ታዎድሮስ" "ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ" 1964፣ 1965፣ 1966 ዓ.ም. አዲስ አበባ
36. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ "ዓፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት" 1982 ዓ.ም.
37. "ትንቢተ ኢሳይያስ" ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1997 ዓ.ም.
38. "ትርጓሜ ኦሪት" ግእዝ በግእዝ የእጅ ጽሑፍ
39. "ትርጓሜ ዳንኤል" ግእዝ በግእዝ የእጅ ጽሑፍ
40. "ትርጓሜ መሐልይ" ግእዝ በግእዝ የእጅ ጽሑፍ
41. "ትርጓሜ ሕዝቅኤል" ግእዝ በግእዝ የእጅ ጽሑፍ
42. "ትርጓሜ ደቂቀ ነቢያት" ግእዝ በግእዝ የእጅ ጽሑፍ
43. "ትርጓሜ ሄኖክ" በግእዝና አማርኛ ያልታተመ
44. "ትርጓሜ አርባዕቱ ወንጌላት" በግእዝ ያልታተመ
45. "ትርጓሜ ራእይ ዘዮሐንስ" ግእዝ በግእዝ
46. "ትርጓሜ አምስቱ ብሔረ ኦሪት" በግእዝና አማርኛ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1999 ዓ.ም.
47. "ትርጓሜ ቁርሎስ" ያልታተመ
48. "ትንቢተ ዳንኤልና 12 ደቂቀ ነቢያት" ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት 1998 ዓ.ም.
49. "ትንሣኤ መጽሔት" የተለያዩ እትሞች
50. ነጋ ወልደ ሥላሴ "ባለታሪክ ኢትዮጵያ" አዲስ አበባ 1948
51. "ክብረ ነገሥት" የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ 1994 ዓ.ም.
52. አቶ አስረስ የኔ ሰው "ትቤ አክሱም መኑ አንተ"
53. አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ "ሀገረ መጻሕፍት" 1980 ዓ.ም.
54. አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት" አርቲስቱክ ማተሚያ ቤት 1948 ዓ.ም.
55. አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "መጽሐፈ ሕዝቅኤል" 1916 ዓ.ም.
56. አለቃ ይኩኖ አምላክ ገብረ ሥላሴ "የቀድሞ ቅኔዎች ከእነትርጓሜያቸው" 1959 ዓ.ም.
57. "አክሱም የሃይማኖትና የሥልጣኔ መሠረት" አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም.
58. አለቃ ታዬ ገ/ማርያም ምንኩሱ "መጽሐፈ ሰዋስው" 1889 ዓ.ም.
59. "ወንጌል ቅዱስ" ንባቡና ትርጓሜው 1916 ዓ.ም.
60. "ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት" 1978 ዓ.ም.
61. "ዜና መዋዕል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ" ሐምሌ 5 ቀን 1989 ዓ.ም.
62. "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ" ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ የተጻፈ.
63. "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት" ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ የተጻፈ.
64. "የአርባዕቱ ብሔረ ነገሥት አንድምታ" /ያልታተመ/







65. የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ድርሳንና ተግሣጽ" 1923
66. "የአርባዕቱ ብሉያት መጻሕፍት" ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅር 1998 ዓ.ም.
67. የኔታ ታለ ማዕነት "ዕርባ ትምርና አገባብ" /ያልታተመ/
68. "የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ" 1934 ዓ.ም. አዲስ አበባ
69. "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት 1987 ዓ.ም. አዲስ አበባ
70. "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት" 1987 ዓ.ም. አዲስ አበባ
71. "የግእዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ ንባብ ከነትርጓሜው" ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ መጽሐፍ 1980 ዓ.ም.፣ 1982 ዓ.ም.፣ 1995 ዓ.ም.
72. ዮሐንስ ወልደ ማርያም ዘብሔረ ተጉለት "የዓለም ታሪክ" አዲስ አበባ 1936 ዓ.ም.
73. ዮሐንስ አድማሱ "ስለ ሰምና ወርቅ ቅኔ ፅንሰ ሐሳብ" ለአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት 1959 ዓ.ም.
74. የቤተ ክህነት የተለያዩ የታሪክ ሠነዶች
75. ዶ/ር ሥርግው ሀብተ ሥላሴ "የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት" 1981 እና 1982 ዓ.ም.
76. ዶ/ር ሐዲስ የሻነው "ፍንጭ፣ ፍተሻ" 1998 ዓ.ም. አዲስ አበባ
77. "ግብረ ሕማማት" 1996 ዓ.ም.
78. ጳውሎስ ኞኞ "ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ" 1984
79. ጳውሎስ ኞኞ "ዳግማዊ ዓፄ ቴዎድሮስ" 1985
80. ጳውሎስ ኞኞ "የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት" 1980
81. "ፍትሐ ነገሥት" አዲስ አባ 1990 /ንባቡና ትርጓሜው/




www.ethiopianorthodox.org